ኬሚስትሪ

4ኛ ዕትም



t.me/OLDBOOKSPDF

ፓ ፒ ዮ

PAPILLON

ድርሰት

ሄንሪ ሻሪየ

ትርጉም

በ

ጌታቸው ገበሬ

የሽፋን ሥዕል፤ ሉቃስ አማረ

የኮምፒውተር ጽሑፍ፤ ራሔል ከበደ እና ልዋም ተ/ሃይማኖት

በመጀመሪያ በ1985 ዓም በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ታተመ

በድጋሚ በ2006 ዓም በአማይ ማተሚያ ቤት ታተመ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

©All Rights Reserved

t.me/OLDBOOKSPDF

መታሰቢያነቴ

የድርሰትን ጉዞ «ሀ» ብለህ ስትጀምር
ምጭትህ ተሳክቶ ማየት ስለነበር
ብዙ ዕቅድ አውጥተህ
ሌት ከቀን አስበህ
«ፓፒዮን» ተርጉመህ
ለህትመት አብቅተህ
አየሁ ተሳካልኝ ጮላልኝ ምጭቴ
«ባንኮን» መተርጎም ነው ቀጣይ ፍላጎቴ
አልከና ለህዝቡ አጥል ተሰፋ ሰጥተህ
ቃልህን ሳትፈፅም ሞት አደናቀፈህ
ይህ የራስህ ትርጉም ላንተው ማስታወሻ
ይሁንልህ በቃ እስከመጨረሻ

ወ/ሮ ዘሪያሽ ጀራ ለሜ
ባለቤቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምስጋና

ይህ አጓጊና መሳጪ የትርጉም መጽሐፍ በድጋሚ ታትሞ ለአንባቢዎች ይደርስ ዘንድ የተለያዩ አስተዋጽኦ ያደረጉትን በሙሉ የተርጓሚው ባለቤትና ልጆቻቸው ማመስገን ይፈልጋሉ::

በመጀመሪያ ፓፒዩ እንዲተረከና የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ በማድረግ ትንሳኤውን ላበሰረው እና የተርጓሚው ስራ እንደገና እንዲታወስ ከፍተኛውን ሚና ለተጫወተው ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እና ለመላው ሰራተኞቹ በተለይ ደግሞ በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የአፐሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስፈፃሚ ለሆኑት ለአቶ ብሩክ ከበደ ፣ ለጋዜጠኞች ዘካርያስ ብርሃኑ፣ ዮናስ አዘዘ እና ስዩም ፈቀደ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን::

በመቅጠልም ለአርቲስት ሽመልስ አበራ (ጆሮ) እና ባዩሽ አለማየሁ መፅሐፉን እንደሚገባ በመተረካቸው፣ ለጃፋር መጽሐፍት ቤት ባለቤት ለአቶ ጃፋር ቪፋ ድጋሚ መጽሐፉን አሳትሞ ለገበያ እንዲቀርብ በማድረጉ፣ በመጨረሻም ከመላው አገሪቱ ስልክ በመደወል አድናቆታቸውን ለገለጹልን እና ለድጋሚ ህትመት ላበረታቱን በሙሉ ከልብ የሆነ ምስጋና እናቅርባለን::

ወ/ሮ ዙሪያሽ ጃራ እና

ልጆቻቸው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመጀመሪያው የመጽሐፉ አሳታሚ

በሐምሌ ወር 1967 ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ በደረሰበት ዓመት፥ አንድ የስድሳ ዓመት አዛውንት በካራካስ ጋዜጦች ላይ በአልበርቲን ሳራዚን የተጻፈውን ባያኑቦ ኖሮ፥ ምናልባትም ይህ መጽሐፍ ፈጽሞ ሊጻፍ ባልተቻለ ነበር።

ብሩህ ገጽ ያላትና ሳቅ የማይለያት ይህች መንፈሰ ጠንካራ ጥቁር አልማዝ አሁን ሞታለች። በአንድ ዓመት ገደማ ብቻ ጽፋ በመላው ዓለም ዝናን ካተረፈችባቸው ሦስት መጻሕፍት መካከል ሁለቱ የሚተርኩት ስለ ራሷ ከወህኒ ቤት ማምለጥና ስለ ወህኒ ቤት ኑሮዋ ነበር።

አዛውንቱ ሰውዬ ፥ ሄንሪ ሽሪየ ሲሆን ፥ እዚያ ለመድረስ ረጅም መንገድ ተጉዟል - ከካየን የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት። እቅጩን ለመናገር ያህል በ1933 ወደዚያ ሥፍራ ተግዞ ነበር። ሕገወጥ መሆኑን መካድ ባይቻልም የኢድሚ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ግን ያልገደለውን ገድለሃል ተብሎ ነበር።

ሄንሪ ሽሪየ፣ በአራዳው ዓለም መጠሪያ ስሙ ፓፒዮ ፥ የተወለደው በ1906 ከአንድ የመምህራን ቤተሰብ አርዴቭ በምትባል ቦታ ነበር። ትውልዱ ፈረንሣዊ ሲሆን ፥ በኋላ ግን የቬኔዙዌላ ዜጋ ሆኗል። የቬኔዙዌላ ሕዝብ የሚያደንቀው በጨዋነቱ እንጂ ባለፈው የወንጀለኛነት ሪከርዱ አይደለም። ከአሳቃቂው የቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ለማምለጥ በትግሉ ያሳለፋቸው ዐሥራ ሦስት ዓመታትም ያለፈውን ታሪኩን ከማጨለም ይልቅ የወደፊት ዕድሉን ብሩህ አድርገውለታል።

በሐምሌ ወር በ1967 ሽሪየ ካራካስ ወደሚገኘው የፈረንሣይኛ መጻሕፍት መሸጫ መደብር ሔዶ ፥ "ለስትራጋል" የተባለ አንድ መጽሐፍ ገዛ፤ እስከዚያ ጊዜ ድረስ ስለራሱ አስደናቂ ታሪኮች እንዲት መስመር እንኳ ለመጻፍ ፍጹም አላሰበም። ታታሪና ኑሮን የሚወድ ሰው ነበር። ሰው አፍቃሪና ንቁ ፥ የሚማርክ ጎርናና ድምፅ የታደለ የደቡባዊ ፈረንሣይ ሰው ነበር። ታሪኮቹን የሚያቀርበው ልክ እንደ አንድ ዕውቅ ተራኪ ስለሆነ ያለአንዳች መሰልቸት ለብዙ ሰዓት ማዳመጥ ይቻላል። እንግዲህ ተአምሩን እነሆ - ሥነ ጽሑፋዊ ከሂሎትን ሳያከልበት (በጻፈልኝ ደብዳቤ ውስጥ "አስገራሚ ታሪኮቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንሁልህ ፤ ·ባለሞያ ይጻፍልኝ ·ብሎኛል።) የማዳም አልበርቲ ሳራዚንን አርአያ በመከተል።

ታዩታላችሁ፥ ትሰሙታላችሁ፥ ኑሮውን ትኖራላችሁ፥ ድንገት የአንድ ገጽ የመጨረሻ መስመር ላይ ስትደርሱ ÷ ወደ መጻዳጃ መሐዱን ሲነግራችሁ (በቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ÷ ያ በታ ·ብዙ ድርጊት የሚከናወንበት ነበርና) እንባችሁን መግታት አትችሉም። ምክንያቱም ወደዚያ የሚሄደው ሽሪየ ሳይሆን እናንተው እንደሆናችሁ ስለምታስቡ፥ ከመቅጽበት ገጹን ትገለብጣላችሁ።

"ስትራጋል"ን አንብቦ ከጨረሰ ከሦስት ቀን በኋላ ቁጭ ·ብሎ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ምዕራፎች በአንድ ጊዜ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ ጻፈ። ለእንደዚህ ዓይነቱ አንግዳ የሆነ አስደናቂ ታሪኩ አንዳንድ ምክሮች ለማግኘት ሲል ረዘም ላለ ጊዜ አቋርጦ ቆየ፡- ምናልባትም ታሪኩን ካማከራቸው ሌሎች ሰዎች ይልቅ ÷ ይበልጥ ያስደነቀው ራሱን ስለሆነ ÷ የቀሩትን ደግሞ በ1968 መግቢያ ላይ ሊያጠናቅቅ ተነሳ። ዐሥራ ሦስቱንም ማስታወሻዎች በሙሉ በሁለት ወር ውስጥ ጨረሰ።

ልክ እንደ ማዳም አልበርቲን ÷ የአርሱም ረቂቅ ጽሑፎች በመስከረም ወር በፖስታ ቤት በኩል ደረሱኝ። ከሦስት ሳምንት በኋላ ሽሪየም ፓሪስ መጣ። የአልበርቲንን ጽሑፎች ከዮሐንስ ጎርክ ፓውሼ ጋር አሳትሜላቸው ስለነበር ÷ በዚህ ምክንያት ሽሪየም እምነቱን በእኔ ላይ ጣለው።

መጽሐፉን ያጠናቀረው ከፍተኛ ትዝታ ባፈለቀበት ወቅት ሲሆን፥ የተተየበውም ስሜቱ በማረካቸውና ፈቃደኞች በሆኑ ÷ ግን እምብዛም የፈረንሣዊኛ ቋንቋ ችሎታ በሌላቸው ግለሰቦች ነበር። እንዲያም ሆኖ ምንም ዐይነት ለውጥ አላደረግሁበትም። አልፎ አልፎ ነጥቦችና ሰረዞችን አስተካክያለሁ፤ በጣም ግልጽ ያልሆኑና ትርጉማቸውም የሚያደናግር አንዳንድ ጊዜም የተዘበራረቁና ታሪኩን የሚያምታቱ ሐሳቦችን ካራካስ ውስጥ የተለመደ ግን ከዚያ ውጭ እንግዳ የሆኑ ቀበሌኛ አነጋገሮችንና ጥቂት የስፖኛ ቃላትን አሻሽያለሁ።

ለታሪኩ ዕውነተኛነት መተማመኛ ልሰጥበት እችላለሁ። ከሠላሳ ዓመታት በኋላ በመጠኑም ቢሆን፤ ዝርዝር ሐሳቦች መደብዘዛቸው ስለማይታበል በማስታወስ መስተካከላቸው ግልጽ ነው። ከሥረ መሠረቱ ሐቅ ለመሆኑና የቅኝ ግዛቱን አስቃቂ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወህኒ ቤት ኑሮ ወይም ለቆቃ ሽሪየ ፍጹም አንዳላጋነነው ለማረጋገጥ ካየን የተባለውን የፕሮፌሰር ዴቪን መጽሐፍ ማንበብ ብቻ ይበቃል። (የጆልያር ስበስብ መዛግብት፥ 1965)

በቅኝ ግዛት ወህኒ ቤቶች የቅጣት አስተዳደር ውስጥ የነበሩትን የእሥረኞች ፥ የዘበኞችና የወህኒ ቤት አዛውች ትከክለኛ ስሞች በሙሉ እኛ በመሰለን መንገድ ቀይረናቸዋል። የመጽሐፉ ዓላማ ግለሰቦችን ለመኰነን ሳይሆን በአንድ የተለየ ሕብረተሰብ ውስጥ የተለዩ ከፍሎችም እንዳሉ ለመግለጽ ያህል ነው። ከቱናት አቆጣጠር አኳያም ተመሳሳይ እርምጃ ወስደናል። አንዳንዶቹ አስተማማኝ ሲሆኑ ፥ ሌሎች ደግሞ በግምት ናቸው። ከዚህ ውጪ ሌላ እርምት አልተካሔደም።

የሽሪየ ፍላጎት ታሪክ ለመጻፍ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ በራሱ ተማምኖ፥ ምንም ነገር ሳይበግረው ሕይወቱን እንዴት እንዳሳለፈ ለመናገር ነው። የዚህም ውጤት፥ ራሱን ከወንጀለኞች በተገቢው መንገድ ለመጠበቅ ፍላጎት ባለው አንድ ሕብረተሰብና፥ ስብዕናን የሚያጎድፍ የጭቆና ሥርዓት በምትከተል አንዲት የሰለጠነች ሀገር መካከል የነበረው ቅራኔ አልዋጥልህ ብሎት የታገለ የአንድ ልዩ ግለሰብ መዘከር ለመሆን በቃ።

የሐንስ ፒየር ካስቴልናው

ይህን መግቢያ የጻፍኩት በግንቦት ወር 1969 ነበር። መጽሐፉ የታተመው በዚያው ዓመት በሰኔ ወር ፈረንሣይ ውስጥ ነበር። በሚያዚያ ወር 1970 አንድ ሚሊየን ቅጅ እዚያው ተሸጠ። አንድ ጸሐፊ ይህን ያህል መጻሕፍት ሊሸጥ የቻለውና ሚስተር ሻሪየንም በማሞገስ አውነተኛ ድርጊታቸውን ተማምኖበት ለማሳተም የተነሳሳው ምናልባት ምን ነገር ይሆ ይሆን የሚል ጥያቄ በአንዳንድ አካባቢ በዚያው ሰሞን አስነሥቶ ነበር። እንደነዚህ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሲባል፣ የላፎ አሳታሚ ድርጅትና ባለታሪኩ በተገኙበት መጋቢት ወር 1970 አንድ ጋዜጣዊ ጉባኤ ተደረገ። አንዳንድ ወቅቶችና ጥቃቅን አውነታዎች ከጊዜ መርዘም የተነሳ ተዘንግተው ቢሳሳቱም፣ ይህ መጽሐፍ ትክክልና በእርግጥም የራሳቸው ከንዋኔ መሆኑን ሚስተር ሽሪየ በድጋሚ ራሳቸው አረጋግጠዋል። ከዚያም ቦሶይ ራሳችሮ አንዳሉት፣ "እዚያ ገሃነም እሳት ውስጥ" የገቡት ታሪክ ለመጻፍ ብዕር እንግበው እንዳልሆነ ተችሮውበታል።

t.me/OLDBOOKSPDF

መግቢያ ከተርጓሚው

ዝናው በዓለም ያተደነቀውን "ፓፒዮ" የተሰኘ መጽሐፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች ሳበረከት ደስታ ይሰማኛል።

መጽሐፉ በቅጽል ስሙ «ፓፒዮ» (ቢራቢሮ) እየተባለ የሚጠራው ሄንሪ ሽሪየ ባልፈጸመው ወንጀል የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተፈርዶበት የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ወደነበረችው ፈረንሣይ ጊያና (በደቡብ አሜሪካ ሰሜናዊ ክፍል የምትገኝና አሁን ሲሪናም በሚል ሥያሜ የምትጠራ) አሰቃቂ ወህኒ ቤት ከተላከ በኋላ በተደጋጋሚ እያመለጠና እየተያዘ የተቀበለውን ፍዳና ያየውን የቁም ስቃይ፥ በወህኒ ቤቱም ሆነ በተለያዩ ሥፍራዎች ያጋጠሙትን የግለሰቦችና ማህበረሰቦች አኗኗር በሥፋት የሚገልጽ እውነተኛ ታሪክ ነው።

በውጪ ቋንቋ የተጻፈውን መጽሐፍ ምንም ሳይቀንስ ጋ'ኑም ሳይጨምር ቃኡ በቃል ወደ አማረኛ መተርጎም ከባድ ተግባር ነው። የአንድን ሕብረተሰብ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋና ዘይቤ ሳይዛቡ በትክክል ሰሌላው ሕብረተሰብ ለማንጸባረቅ ምን ያህል አታካች ሥራ እንደሚሆን አንባቢ ሊገነዘበው ይችላል።

ጽሑፉን ወደ አማርኛ ስመልሰው ተስማሚ ፍቺ ያላገኘሁላቸውን አንዳንድ ቃላት በግዕዝና በዘልማድ በሚነገረው ቋንቋ የተካሁ ስሆን፥ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ፥ ጣሊያንኛ ፥ ፈረንሣይኛና የስፓኝ ቃላትን እንዳሉ በመገልበጥ በመጨረሻው ገጽ ላይ መግለጫ ሰጥቻቸዋለሁ።

ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች እንግዳ ይሆናሉ ብዬ የገመትኳቸውን ገሮ፣ መቲው፣ ሴንት ገርሴፍ፣ ዲያብል፣ ወዘተ ... የመሳሰሉ የፈረንጅኛ አጠራሮችን ዮሐንስ፣ ማቴዎስ፣ ቅዱስ ዮሴፍ፣ ዲያቢሎስ ወዘተ ... በማለት ለውጫቸዋለሁ።

ዘመኑ የተገለጸው በአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው። ሰዓቱን ግን ለአንባቢያን በቀላሉ ለመከታተል እንዲያመች ከኢትዮጵያውያን ሰዓት አቆጣጠር ቀመር ጋር አስተካከየዋለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የሸሪየ ድርጊትና ትረካዎች በማያሻማ መንገድ ዕውነት ለመሆናቸውና አንባቢም ከጥርጣሬ ባሻገር እንዲሆን÷ መጽሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረንሣይኛ ሲታተም ያስተዋወቁት ጸሐፊ ዮሐንስ ፒየር ካስቴልኖው ያሰፈሩትን መግቢያና የላፎን አሳታሚ ድርጅት በአዘጋጀው ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ ራሳቸው ባለ ታሪኩ ተገኝተው የሰጡትን መተማመኛ ቃል በቃል ተርጉሜ ከዚህ በሚቀጥለው ገጽ አቅርቤያለሁ።

ሄንሪ ሸሪየ ከአሰቃቂው ወህኒ ቤት ነጻ ከወጡ በኋላ ያጋጠማቸውን የኑሮ ውጣ ውረድ ለማሳተም ያላቸውን ፍላጎት በፓፒዮ የመጨረሻ ገጽ ላይ በገቡት ቃል መሠረት "ባንኮ" የተባለ ሁለተኛ መጽሐፍ አዘጋጅተው የላፎን አሳታሚ ድርጅት በአዘጋጀው ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ ራሳቸው ባለ ታሪኩ አስመርቀዋል። ጊዜና ሁኔታ ከፈቀደ እኔም አንድ ቀን "ባንኮ"ን ተርጉሜ ለወገኖቼ ለማቅረብ ተስፋ አደርጋለሁ።

ጌታቸው ገብሬ

(ደሴ)

t.me/OLDBOOKSPDF

አንደኛ ማስታወሻ

ወደ ገሃነመ እሳት መውረድ

ችሎት

ሕሊና የሚያስት ትጣት ነበረ - ካረፈብኝ ከርን ከብደት የተነሣ ለሚቀጥሉት ዐሥራ አራት ዓመታት ከተዘረርኩበት መነሣቱ አልሆነልኝም። ያንን ያህል መዓት ላወረዱብኝም ሰዎች ቢሆን፤ አድራጎታቸው ሳይከብዳቸው አልቀረም።

ወኅቱ ኤ.አ. ጥቅምት 26 ቀን 1931 ነበር። ለአንድ ዓመት በጥበቃ ጣቢያው ቅይቼባት ከነበረችው ከፍል ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ አወጡኝ። ጺሜን ተላጭቼና በጥንቃቄ ለብሼ ነበር። ልብሴ በጥሩ ሰፊ የተዘጋጀ በመሆኑ አምሮብኛል። ነጭ ሸሚዜ፤ ዘንጠጥ ብሎ የመረደውና ደብዘዝ ያለው ሰማያዊው ክራቫቱ ማራኪነቴን ጨምረውልኛል።

ሐያ አምስት ዓመቴ ነበር፤ ግን የሐያ ዓመት ልጅ ነው የምመስለው። ፖሊሶቹ በጨዋ አቀራረቤ ይሉኝታ ተሰምቷቸው ስለነበር፤ በእከብሮት ይዘውኛል። የእጄን ካቴና እንኳ ሳይቀር አውልቀውልኝ ነበር። ስድስታችንም ገሙሉ፣ ማለት አምስቱ ፖሊሶችና እኔ ፓሪስ ከሚገኘው የሲያ ፍርድ ቤት ሕንፃ በአንድ ማረፊያ ክፍል ውስጥ በሁለት አግዳሚ ወንበሮች ላይ ተቀመጥን። በእኛ ትይዩ የሚገኙት መዝጊያዎች ወደ ችሎቱ ከፍል የሚያሳልፉ ነበሩ። ከውጭ በኩል እየሩ ጭፍግግ ብሏል።

በነፍስ ግድያ ወንጀል ፍርዴን ለመቀበል በመቃረብ ላይ ነበርኩ። ጠበቃዬ ሬይሞንድ ሂውበርት ሰላምታ ሊያቀርብልኝ ወደ እኔ መጣ። «ተጨባጭ ማስረጃ የላቸውም፤ እኛ በነጻ እንደምንለቀቅ እተማመናለሁ» አለ። በዚያች «እኛ» ባላት ቃል ፈገግ አልኩ። እርሱ ሳይሆን፤ እኔው ነበርኩ ለራሴው ጥበቅና የቆምኩት። አንድ ሰው ወህኒ ቤት ስለገባ ጠበቃውም አብሮ ይገባል ማለት አይደለም።

አንድ ዘበኛ መጥቶ ወደ ውስጥ አንድንገባ ቀሰቀሰን። ሁለቱ መዝጊያዎች ወለል ብለው ተከፈቱና በዳርና ዳር አራት ፖሊሶችና አንድ የሃምሳ አለቃ እንደተገተሩ ወደ ሰፈው አዳራሽ ገባሁ። የሚጠበቀኝን ውርጅቦች እንደሚጠቁመኝ ሁሉ የማየው በሙሉ፣ ፃንጣፎቹ፤ በትላልቆቹ መስኮቶች ላይ የተሰቀሉት መጋረጃዎች፣ በእኔ ላይ ፍርድ ሊሰጡ ተጣድፈው የተቀመጡት ዳኞች የለበሷቸው ካባዎች እንኳን ሳይቀሩ ቀይ ሆኑብኝ።

«ችሎት ተሠይሟል!»

ሰብሳቢው ዳኛ፣ ከዚያም አምስቱ ዳኞች ቆባቸውን እንዳደረጉ በስተቀኝ በኩል

t.me/OLDBOOKSPDF

ካለ አንድ መገረጊያ በቅደም ተከተል ገቡ። ሰብሳቢው ዳኛ ከመካከለኛው ወንበር ፊት ለፊት ሲቆም የግራና የቀኝ ዳኞች ደግሞ በጎንና ጎን ቦታቸውን ያዙ።

ከፍሉን ረጭ ያለ ጸጥታ ሞላው። ከእኔ ጀምሮ ሁሉም ሰው ቀጥ ብሎ ቆመ። ከዚያም ዳኞቹ ተቀመጡ። እኛም እነሱን አይተን ተቀመጥን።

ሰብሳቢው ዳኛ ፈዘዝ ዐይናቸውና ፍም የመሰለ ጉንጭ ያለው ወፍራም ሰው ነበር። ስሙ ቢቪን ይባላል። ቅንጣት ስሜት ሳይኖረው አትኩሮ ይመለከተኛል። ዘግየት ብሎም አድልዎ የሌለበት ብያኔውን በጥንቃቄ ይመራል። ከብዙ ጊዜ የዳኝነት ልምዱ የተነሣ በምስክሮችም ሆነ በፖሊሶች ላይ ያለው እምነት ጽኑ መሆኑን ሁኔታው በይፋ ይናገራል። ፍርዱን ብቻ ያነብንብ እንጂ በተከሳሽ ላይ ለሚሠነዘረው ጠጫ ኃላፊነትን አይወስድም።

ዓቃቤ ሕጉ ፕራደል ይባል ነበር። አንገት በማስቀንጠሉ ሆነ ሰውገር ውስጥና ለቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ሰዎችን በማቅረብ «በቁጥር አንድ» መጋቢነቱ የጭካኔ ዝናን አትርፏል።

ፕራደል ያለአንዳች ሰብዓዊ ርኅራሄ ወንጀለኛን ለመበቀል ሕዝቡን ወክሎ የቆመ አፈሊያላዊ ነበር። ሕግና ፍትሕን ይወክላል፣ በማጣመምና ማንኛውንም ነገር ወደ ራሱ ፍላጎት በመጠምዘዝ የልቡን ያደርሳል። የጆቢራ ዐይኖቹ ትኩር ብለው ቁልቁል ይመለከቱኛል። ቁልቁለት የሆነበትም ምክንያት ከእኔ በላይ በመቀመጡና ቁመቱም ረጅም በመሆኑ ነበር። ስድስት ጫማ በመርዘሙም ይጀነናል። ቀይ ካባውን እንደለበሰ ሲሆን፣ ኬፑን ግን ከፊት ለፊቱ አስቀምጦ መንሽ በመሰሉት ትላልቅ እጆቹ አካሉን ደባበሰ። ባለትዳር መሆኑን ለማመልከት የወርቅ ቀለበት አድርጓል። በትንሿ ጣቱ ላይ ደግሞ በሚገባ የተወለወለ የፈረስ ኮቴ ምልክት ያለበት ሌላ ቀለበት ነበረው።

ይበልጥ ሊጫነኝ በማሰብ ወደፊት ትንሽ ሰገግ በማለቱ እንዲህ የሚለኝ ይመስለኛል። «ስማ ቀልደኛው ጓደኛዬ፣ ከእኔ ማምለጥ እችላለሁ ብለህ ብታስብ በጣም ተሳስተሃል። አታውቃቸውም እንጅ እጆቼ ሊቦጫጭቁህ የተዘጋጁ የአውሬ ጥፍሮች ሆነዋል። ጠበቆች የሚፈሩኝ እጆቼ የገቡልኝን ተከሳሾች እንዲያመልጡ ዕድል ስለማልሰጣቸው ነው።

«ወንጀለኛም ሆንክ ወይንም ንፁሕ ሰው ለእኔ ጉዳዬ አይደለም። ተግባሬ ማንኛውንም ለአንተ ማንበርከኪያ የጋጠመኝን ዘዴ ሁሉ መጠቀም ነው። ቅጥ ያጣ የሞንትማርትር ኑሮህ፣ በፖሊሶች ተደጋጋሚ የተነበብህን መረጃ፣ ፖሊሶቹ ራሳቸው የመሰከሩብህና በመርማሪዎቹ ተቀናብሮ የቀረበብህን የግፍ አድራጎትህን አጣምሬ ፈጽሞ ተቀባይነትን በማሳጣት ተችዎች ከሕብረተሰቡ ውጭ ወርውረው እንዲጥሉህ ማድረግ እለብኝ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

በእውን እየተናገረኝ ነው ወይንስ በሕልሜ? ያም ሆነ ይህ በዚህ «ሰው በላ» ፍጡር በተመሰጠ ተማርኬ ነበር።

«ልትከራከር አትሞክር። ለማምለጥ አትሞክር። በምንም መንገድ ወደ ቅጣት ጎዳናህ አሽቀልቁዬ ልልክህ ነው። በተቺዎቹም በኩል እምነት እንደማይኖርህ አምናለሁ። ከዚያ አኳያ ግብዝ እንዳትሆን። እነርሱ ስለሕይወት ምንም ነገር አያውቁም።

«ተመልከታቸው ከፊት ለፊትህ ናቸው። እነዚያን ከሩቅ መንደር ወደ ፓሪስ የመጡ ዐሥራ ሁለት ደደቦች በግልጽ ለማየት ችለሃል? እንዳንዶቹ ጡረተኞች፣ ሌሎቹ እነስተኛ ነጋዴዎች የሆኑ ንፁህ ከበርቴዎች ናቸው። ስለእነርሱ መናገር ዋጋ የለውም። በሞንትማርትር ስላሳለፍከው ኑሮም ሆነ ዕድሜህ ገና ሐያ አምስት ዓመት መሆኑን ተረድተው ያዘኑልኛል ብለህ መጠበቅ አትችልም። ለእነርሱ ፒጋሌና ፕላስ ብላንሽ የመሳሰሉት የምሽት ክበቦች ራሳቸው ገሃነም እሳት ሲሆኑ፣ ማንም ግማሽ ሌሊት በዚያ የሚያሳልፍ ሰው ሁሉ የሕብረተሰብ ጠላት ነው። በመሆኑም በዚህ ዓይነቱ ኑሮ ላይ በተቺነት ማገልገሉን ከመውደድም ከመጠን በላይ ይኮራበታል። በተጨማሪም እነርሱም ቢሆኑ የሚፈጽሙት አንዳንድ መናኛ ተንኮል በዚህን ጊዜ ወለል ብሎ እንደሚታያቸው አረጋግጥልሃለሁ።

«ወጣትና መልከ መልካሙ ሏ የሞንትማርትሬው ዶን ጅዎን ክህ ብዬ ስገልጽልህ ምንም ነገር አንዳልደበቅሁ በእርግጥ ትገነዘባለህ? በቀጥታ ያንተ ጠላቶች እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ። ተሸቀርቅረሃል። ይህን ያህል ማሽብረቅ አይገባህም ነበር። አለማወቅህ እንጂ! ትልቁ ስሕተትህ እዚያ ላይ ነው። በልብሶችህ አንደሚቀኑ ታያይም? የእነርሱን የሚገዙት ከአውርዱልኝ መደብር ነው። በሕልማቸው እንኳ ወደ ልብስ ስፌት ቤት ሄደው አያውቁም።»

አሁን አራት ሰዓት ስለሆነ ጉዳያችንን ለመጀመር ተዘጋጅተን ነበር። ከፊት ለፊቴ ስድስት ዳኞች ሲኖሩ ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ያለውን የጭካኔ ሃይልና ብልህነት በሙሉ በመጠቀም እነዚህን ዐሥራ ሁለት ነጋዴዎች ወንጀለኛ መሆኔንና ለዚህም ተገቢው ቅጣቴ ወህኒ ቤት መውረድ ወይም ሞት መሆኑን ለማሳመን ታጥቆ የተነሳብኝ ዓቃቤ ሕጉ ነበር።

የተከሰስኩት ሞንትማርትር ውስጥ በሚዘዋወር አንድ አቃጣሪና እርግብ ሻጭ ሰው ግድያ ነበር። ማስረጃ አልነበረም፣ ግን ፖሊሶቹ በየጊዜው አንድ ወንጀለኛ ባቀረቡ ቁጥር የደረጃ እድገት ስለሚያገኙ እኔ ወንጀለኛ እንድሆን ይገፋፉ ነበር። ማስረጃ ከማጣታቸው የተነሳ ከጥርጣሬ ጥላ ሥር የሚጥል አንድ «ሚስጥራዊ» መረጃ አለን ይላሉ። በዋና ፖሊስ መምሪያ ፓሊየን በሚል ስም የሚጠራ እንደ ተንቀሳቃሽ ቴፕሪኮርደር የሚቆጠር ቀንደኛ ምስክር መልምለው ነበር። ለፍርድ ቤቱም ይበልጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተጨባጭ ማስረጃ ነው የሚባለው እርሱው ነው። ከአሁን ቀደም እንደማላውቀው ብረዳም ሰብሳቢው ዳኛ አድልዎ የሌለበት በሚመስል ድምፅ እንደዚህ አለኝ።

«ይህ ምስክር ይዋሻል ትላለህ። መልካም፣ ግን ለምን ይዋሻል?»

«ከቡር ሆይ፣ ከታሰርኩበት ጊዜ ጀምሮ ለሊቱን እንቅልፍ ሳይወስደኝ የቆየሁት ሮላንድ ጥቂን በመግደሌ ምክንያት ተጸጽቼ አልነበረም። አልገደልኩትም። ይህ ምስክር በተቻለ መጠን ለምን እኔን ለመጉዳት ቆርጦ እንደተነሳና እንደዚሁም ፍርድ ቤት ጠበቃዬ አዲስ የመከላከያ ነጥብ ባነሳ ቁጥር ለምን እንደሚያኮላሽበት ምክንያቱን ለመረዳት በመሞከር በሀሳብ በመናወዜ ነበር።

ከቡር ሆይ ምስክሩ ራሱ የሚያስጠይቀው አንድ ወንጀል በመፈጸም ላይ እንዳለ በፖሊስ መያዙንና በእኔ ላይ እንዲመሰክርም ድርድር ማድረጋቸውን አውቃለሁ። 'በፓፒዮ ላይ የምታቀርበውን የምስክርነት ቃል ከሌላ አቅጣጫም እንመለከተዋለን' ሲሉ ደልለውታል ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ።»

, በዚያን ጊዜ የቱን ያህል ወደ አውነቱ መቃረቤን አላወቅሁትም ነበረ። ፖሊሶን ራሱን ባለንጹሕ ሪኮርድና የተከበረ ሰው አድርጎ በችሎቱ ላይ ለማስገንዘብ ሞክሯል። ሆኖም ከጥቂት ዓመታት በኋላ አደገኛ ዕፅ ሲያዙበል በወንጀለኛነቱ ተይዞ ለመታሰር በቃ።

ጠበቃዬ ሂውበርት ሊንላነልልኝ ሞኮረ። ግን ከዓቃቤ ሕጉ ጋር መቋቋም አልሆነለትም። አንደኛው ምስክሬ ቡፍሬይ እንኳ በብስጭት ገንፍሎ የትንሽ ጊዜ ችግር ተፈጥሮበት ነበር። ብልጣ ብልጡ ፕራደልም ረቺ ለመሆን በቃ። ሌላው ቀርቶ ተችዎቹን ያለመጠን በማሞካሸት በዚህ አስገራሚ ጠባዩ እንደአቻና ተባባሪዎቹ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ ገፋፉቸው።

በዚያ ሌሊት አምስት ሰዓት ላይ ፍርድ ተሰማ። ያለማንገራገርም እጄን ሰጠሁ። ንጹሕ የነበርኩት ወንጀለኛ ሆኜ ተገኘሁ።

የፈረንሣይ ጎብረተሰብ ፕራደል በተባለ ዓቃቤ ሕጉ አማካይነት አንድን የሐያ አምስት ዓመት ወጣት በዕድሜ ይፍታህ እሥራት ለማስወገድ ተሣካለት። ይድነቃችሁ፣ ቅጣቱ የሚሻሻል አልነበረም! ይህ እንደ ጣፋጭ ምግብ በሣህን ሙሉ ተቆልሎ የቀረበልኝ ውሳኔ የተነገረኝ በለዛቢሱ የመሐል ዳኛ ቤቪን አንደበት ነበር።

«አሰረኛው እንዲቆም ይጠየቃል»።

ተነሣሁ። ሁሉም ሰው ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ስለያዘ ክፍሉ ጸጥ ብሏል። ልቤም የምቱን ፍጥነት ትንሽ ጨመረ። ተቺዎቹ ወደ እኔ ይመለከታሉ። አለበለዚያም ራሶቻቸውን ይቀረቅራሉ። ያፈሩ ይመስላል።

ከአንዱ በስተቀር ለሁሉም ጥያቄዎች ተችዎች፣ «በአምንታ» መልሰዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሱም በቂም በቀል ያልተፈጸመ ወንጀል መሆኑን ነው። ስለሆነም «የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶበሃል። የምትናገረው ጉዳይ አለህ?»

አልተነቃነቅኩም። የእስረኛ መቆሚያ ሣጥኑን አግዳሚ ብቻ ትንሽ ጠበቅ አድርጌ ያዝኩ። «ከቡር ሆይ፣ እዎ፣ በአንድ ፖሊስ ለተቀነባበረ ሻጥር ተዳረግኩ እንጂ፣ በሐቅ ንፁሕ ነኝ ማለት እፈልጋለሁ።»

በስተኋላ ካለው ወንበር በተለይ ተጋብዘው ከተቀመጡት ወይዛዝርት የሆነ ማጉረምረም ተነሣ። ድምፄን ከፍ ሳላደርግ እንዲህ አልኳቸው። «እርኩስ ስሜታችሁን ለማርካት ወደዚህ የመጣችሁ፣ በሱል የተሸቀረቀራችሁ እናንተ ሴቶች፣ ዝም በሉ። ድራማው አብቅቷል። በሕጋችሁና በፖሊሶቻችሁ አንድ የነፍስ ግድያ ወንጀል ተጣርቷል፣ ስለዚህ ልትደሰቱ ይገባል።»

«አባከህ ይህን አስረኛ ወዲያ ብታገልልን» አለ ሰብሳቢው ዳኛ። ወደ ውጭ ከመወሰዴ በፊት አንድ ጎላ ያለ ድምፅ ሰማሁ፣ «አትጨነቅ የእኔ ፍቅር፣ እዚያው ድረስ እከተልሃለሁ።» እውነተኛዋን መልካሚ የእኔዋ ኒኔቴ ፍቅሯን እያስተጋባችልኝ ነበር። በችሎቱ አዳራሽ የነበሩትም የአራዳ ጓደኞቼ አጨበጨቡልኝ። ስለዚህ ግድያ እውነቱን ያውቁ ስለነበርና እኔም ባለማልቀሴ ኩራት እንደ ተሰማቸው ለመግለጽ ነበር።

ከችሎቱ በፊት ወደነበርንበት አነስተኛ ከፍል ተመልሰን ሐዲን። እዚያም ፖሊሱ እጄ ውስጥ ካቴና አስገባና ቆለፈው። ከእነርሱም ውስጥ ከአንደኛው የግራ እጅ አንጓ ጋር የእኔን ቀኝ እጅ አንጓ አቆራኘ። ማንም ሰው አይናገርም። አንድ ሲጃራ ጠየቅኩ። ዘበኛው አወጣና አቀጣጥሎ ሰጠኝ። በየጊዜው ወደ አፌ በወሰድኩና ባወረድኩ ቁጥር ፖሊሱም የእኔን እንቅስቃሴ ለመከተል ከንዱን ማንሣት ወይም ማውረድ ነበረበት። የሲጃራውን ሦስት አራተኛ ጨረስኩ። አሁንም አንድ ቃል እንኳ አልተሰነዘረም። ግልጡ ሠረገላ እኛን እየጠበቀ ነበር። ሁላችንም መቀመጫው ላይ ቦታችንን ያዝን። «ጥበቃ ጣቢያ» አለ ሃምሳ አለቃው።

ጥበቃ ጣቢያ

የንግሥት ማሪ አንቷኔት የመጨረሻው ቪላ ስንደርስ፣ ፖሊሱ አንድ የመተማመኛ ደብዳቤ የጥበቃውን ኃላፊ አስፈረመና አስረከበኝ። ከፖሊሶቹ ጋር አንድም ቃል ሳንነጋገር ከመለያየታችን በፊት በካቴና የታሰረውን እጄን ሃምሳ አለቃው ጨበጠኝ።

«ምን ፈረዱብህ?» ሲል የጥበቃ አዛዡ ጠየቀኝ።

«ዕድሜ ልክ!»

«ማመን አልችልም» አለና እንደገና ፖሊሱን ትኩር ብሎ ሲመለከተው፣

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳልኩት መሆኑን አረጋገጠለት። ከዚያም ብዙ ነገሮችን ያየውና ስለእኔም ከስ በሚገባ የተረዳው ይህ ሃምሳ ዓመት ዕድሜ ያለው የወህኒ ዘበኛ እነዚህን የማጽናኛ ቃላቶች ጣለልኝ።

«እነዚያ ውሾች፣ ዕብዶች መሆን አለባቸው!»

የእጄን ካቴና በዝግታ አወለቀና በተለይ ሞት ለተፈረደባቸው፣ ለዕብዶች፣ በጣም አደገኞችና የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ለተፈረደባቸው ማሠሪያ እንዲሆን ወደተቀየሰው ድርብርብ ከፍል ይዞኝ ሔደ።

«በርታ ፓፒዮ» አለኝ በሩን በመዝጋት ላይ እንዳለ። «ጓዞችህንና ከአሁን በፊት በሌላው ከፍል ስታገኝ የነበረው ዓይነት ተመላሳይ ምግብ ይላክልሃል። አንገትከን አትድፋ» አለ።

«አመሰግናለሁ ጌታዬ። እመነኝ አንገቴን አልደፋም፣ እነርሱም ዕድሜ ልካቸውን እንደሚታፈኑ ተስፋ አደርጋለሁ።»

ከትንሽ ደቂቃ በኋላ በመዝጊያዬ ላይ አንድ የሚቧጥጥ ድምፅ ሰማሁ።

«ምንድነው?»

«ምንም አይደለም። እኔ ነኝ አንድ ምልክት እየሰቀልኩ ነው» የሚል አንድ ድምፅ መለሰ።

«ለምን? ምን ይሳል?»

«ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደበት፣ በዐይነ ቁራኛ ይጠበቅ» የሚል።

በእውነት እብዶች ናቸው ብዬ አሰብኩ። ያ የወረደብኝ የፍርድ በትር ራሴን እንድገድል ሊገፋፋኝ ይችላል ብለው በአርግጥ ያስባሉ እንዴ? አንገቴን አልደፋሁም፣ በዚያ ሁኔታም እጠበቀዋለሁ። ሁሉንም ልታገላቸው ነው፣ ከነገ ጀምሮ ተግባሬን አቀጥላለሁ።

በማግሥቱ ቡናዬን በመጠጣት ላይ እንዳለሁ፣ ይግባኝ መጠየቅ ይኖርብኝ ይሆን ስል ራሴን ጠየቅሁት። በሌላ ፍርድ ቤት የተሻለ ዕድል አገኝ ይሆን? ይህን ለማድረግ ምን ያህል ጊዜ ይወስድብኛል? ምናልባት አንድ ዓመት . . . ዐሥራ ስምንት ወራት፣ ግን ለምን? በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፋንታ ሐያ ዓመት ለማግኘት?

ማንኛውንም ዋጋ ከፍዬ ለማምለጥ እስከወሰንኩ ድረስ የዓመቶቹ ብዛት ፋይዳ የለውም። አንድ ሌላ አስረኛ ለሰብሳቢው ዳኛ አመልክቶ የነበረውን አቤቱታ አስታውሳለሁ።

«ከቡር ሆይ፣ ለመሆኑ በፈረንሣይ ውስጥ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ማከተሚያው እስከ መቼ ይሆን?»

በከፍሌ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እመላለሳለሁ። ብቻዋን ከዓለም ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

ለወንድሟ ልትከራከር ለምክረችው አሁንና ለሚሰቱ የማጽናኛ ሰልክ ደውያለሁ።

ያከተመ ነገር ነበር፣ መጋረጃው ተዘግቷል። ከእኔ ይበልጥ የሚሰቃዩት ቤተሰቦቹ ናቸው። ከከፍለ ሀገር ርቆ የሚኖረው ምስኪኑ አባቱም ይሆን ከባድ መሰቀል ለመሸከም ይሳነዋል።

ይሆን ማሰላሰል እንደጀመርኩ ከሐሳቤ ብንን አልኩ። በእርግጥ አንተ ንጹሕ ነበርክ። ግን ማን ያምንሃል ስል ራሴን ጠየቅሁት። ንጹሕነትህን በየቦታው እየዞርክ መወትወት አቁም። መሣቂያ ብቻ ነው የሚያደርግህ። ያወቃ ሌላ ሰው በፈጸመው። በአንድ አቃጣሪ ግድያ ምክንያት ዕድሜ ልክ መታሰር ከባድ ግፍ ነው። አፍሆን መዝጋት ይሻላል።

ያም ሆነ ይህ፣ በቅድሚያ መደረግ የሚገባው ጉዳይ ማምለጥ ከሚፈልግ አንድ ሌላ አስረኛ ጋር ግንኙነት መፍጠር ነበር።

ከማርሴይ የመጣ ዴጋ የተባለ አንድ ሰው አስታወስኩ። ምናልባት ጸጉር ማስተካከያ ቤት አገኘው ይሆናል። በየቀኑ ጺሙን ለመላጨት ይሔዳል። እኔም እንደዚሁ እዚያው ለመሔድ ጠየቅኩ። እዚያ በምደርስበት ወቅት ፊዞን ወደ ግድግዳው አዙሮ ቁም ነበር። ረዘም ላለ ጊዜ ተራውን እየጠበቀ ለመቆየት እንዲያመቸው አንድ ሌላ ሰው ቀድሞት እንዲሔድ ዕድል ሲሰጠው ተመለከትኩት። እኔም አንድ ሌላ ሰው ፈቀቅ እንዲልልኝ በጎይል ገፈተርኩና ልክ ከእርሱ ቀጥዬ አንድ ቦታ ያዝኩ። ድምጼን ዋጥ በማድረግ በለሆሳስ፣

«ታዲያስ ዴጋ ሁኔታዎች እንዴት ናቸው?» ስል አናገርኩት።

«ደህና ነኝ ፓፒ። ዐሥራ አምስት ዓመት ተፈረደብኝ። የአንተስ እንዴት ነው? ያለጥርጥር እንደ ቀለዱብህ ሰማሁ።»

«አዎ፣ ዕድሜ ልክ ተፈረደብኝ።»

«ይግባኝ ልትጠይቅ ነው?»

«ሐልጠይቅም፣ ጥሩ ምጣብ እየበላሁ እቋሜን አጠነክራለሁ። ጠንካራ መሆን ይኖርብሃል ዴጋ። አንድ ቀን ጠንካራ ጡንቻዎች ያስፈልጉን ይሆናል። ትንሽ ፕንዘብ አለህ?»

«አዎ፣ በፓውንድ ስተርሊንግ ዐሥር ሺ ፍራንክ አለኝ። አንተስ?»

«እንዲት ቢላ የለችኝም»

«ትንሽ ምክር ልስጥህ? ጥቂት ፕንዘብ ቆሎ ብለህ ፈላልግ። ጠበቃህ ሂውበርት ነበር እንዴ? እርሱ ጭራሽ አይረዳህም፣ ከንቱ ነው። ይልቅስ አንድ የፕንዘብ መደበቂያ ቱቦ ሚስትህን አሲዘህ ወደ ዳንቴ ላክት። ለዶሚኒክ ሪቼ አንድትሰጠው ንገራትና አርግጠኛ ነኝ ታገኛለህ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሽሽሽ፣ ዘበኛው ወደ እኛ እየተመለከተ ነው።»

«ታዲያስ፣ ትንሽ ጨዋታ ይዛችኋል?»

«ምን የሚያስደስት ነገር አለ?» ብሎ ዴጋ መለሰለትና በማከታተል፣

«አርሱ ሕመም ይሰማኛል ይላል» አለው።

«ምን እገኘው? የፍርድ ቤት ቁንጣን ነው?» ብሎ ቂሎ በሳቅ ፈነዳ።

እንግዲህ ይኸው ነው። እንዴ ከቅጣት ወጥመድ ገብቻለሁ። የፅድሜ ልክ ጽኑ እስራት በተፈረደበት አንድ የሐያ አምስት ዓመት ወጣት ላይ እየቀለደ እንደ ዕብድ ይንከትከት እንጂ።

የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዎን አገኘሁ። በመካከሏ ተከፋች የሆነች በጣም የምታንጸባርቅ አንዲት የአሉሚኒየም ቱቦ ነበረች። የአምስት ሺ ስድስት መቶ ፍራንክ አዲስ ኖቶች ታጭቀውባታል። እንዳገኘኋት ሳምኳት። አዎ ርዝመቷ ሁለት ኢንች ተኩል የሆነና አውራ ጣት የምታክለውን ያችን አንዲት ትንሽ ቱቦ ወደ ፊንጢጣዬ ከመግፋቴ በፊት እንደገና ሳምኳት። ፊንጢጣዬ እንዲሰፋልኝ ያለማቋረጥ ትንፋሼን ለረጅም ጊዜ ወደ ውስጥ ሳብኩ። ካዝናዬ መሆኑ ነበር። ልብስህን ሁሉ አውልቅ፣ እግሮችህን ለየብቻ አንፈራጥ፣ እንጢስ በል፣ ወይም ወደፊትና ወደ ኋላ አጎንብስ፣ እነሱን ደስ ባላቸው መንገድ ሁሉ ሊበረብሩኝ ይችላሉ። የገንዘብ መደበቂያዋ ቱቦ ወደ ውጭ አንጀቴ አሻቅባ ወጥታለች። የአካላቴ እንዴ ከፍል ሆናለች። ሕይወቴንና ነጻነቴን፣ የመበቀያዬንም ጎዳና መከፈቻ በውስጤ ተሸክሜያለሁ። በሐሳቤ ውስጥ የሚመላለሰው ይህ ነበር፣ ብቀላ። በእርግጥም ሐቁ ይኸው ብቻ ነበር።

ከውጭ ጨለማው ከብዷል። በክፍሌ ውስጥ ብቻዬን ነኝ። ከጣራው ላይ አንድ ኃይለኛ መብራት ስለሚበራ መገኪያው መካከል በምትገኝ አንዲት ቀዳዳ ዘበኛው ሊያየኝ ይችላል። ኃይለኛው ብርሃን ዐይኔን ወጋኝ። በቆሰለው ዐይኔ ላይ አንድ መሐረብ አጣጥፌ አስቀመጥኩበት። ትራስ በሌለው የብረት አልጋዬ ፍራሽ ላይ ተጋደምኩና ያንን አሰቃቂ ፍርድ እየደጋገምኩ ማብሰልሰል ጀመርኩ። ይህን ረጅም ታሪክ ሳይታጠፍ አንድትረዱትና እኔንም ከትግሌ ጋር ምን እንዳቆራኘኝ፣ በረጅሙ መተንተን ይኖርብኛል። ከእነዚያ በሕይወት ተቀብሬባቸው ከነበሩት ቀኖች በኋላ ምን እንደተደረገና በአዕምሮዬ መነጽር ያየሁትን ማንኛውንም ነገር በሙሉ ልነግራችሁም ይገባኛል።

ከአመለጥኩ በኋላ ምን ማድረግ ይኖርብኛል? አሁን የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ ስላለችኝ፣ ለጊዜው ምንም የሚያሳስበኝ ነገር ይኖራል ብየ ፍጹም አላሰብም።

እንግዲህ በተቻለ ፍጥነት ወደ ፓሪስ እመለሳለሁ። ከዚያም በመጀመሪያ የምገድለው ሰው ያን አዋሻኪ ፖሊየንን ይሆናል። ከዚያ በኋላ ሁለቱን ጆሮ ጠቢዎች።

t.me/OLDBOOKSPDF

ግን ሁለቱ ጆሮ ጠቢዎች በቂ አይሆኑም፤ ጆሮ ጠቢዎቹን በሙሉ መግደል አለብኝ። ወይም በብዛት የሚቻለውን ያህል። እንድ በርሜል ውስጥ የቻለውን ያህል ፈንጂ አሞላበታለሁ። ያ በትክክል ምን ያህል እንደሚይዝ አላውቅም። ሐያ፣ ሠላሳ፣ ዐርባ ፓውንድ? ለብዙ ሰዎች መግደያ የሚያስፈልገኝ ምን እንደሚሆን ለማሰላሰል ሞከርኩ። የማፈንጃው ከምሱር በከፍተኛ ጥንቃቄ ተጠምዶበት በፈንጂ የተወጠረውና ሲመለከቱት ግን አልባሌ ነገር የሚመስለው በርሜል ቁል ¨ ብሎ ሲታየኝ ለመከለያ በመሐረም ሸፍኛቸው የነበሩትን ዐይኖቹን ከውስጥ በ ¨ ጭፍን አደረግኩ። ቆይ በ36 የቪደ አርፈኛር ጎዳና ላይ ከሚ ¨ ኖሩ ዋናው ፖሊስ መምሪያ ሁለተኛ ፎቅ ስምሪት ክፍል ውስጥ፤ ልክ ከጠዋቱ አራት ሰዓት መፈንዳት አለበት። በዚያ ሰዓት የዕለቱን የሥራ ትዕዛዝ ለመቀበልና ሪፖርት ለመስማት ቢያንስ አንድ መቶ ሃምሳ ፖሊሶች በከፍሉ ውስጥ ይኖራሉ። ይህን ለመውጣት ስንት ደረጃዎች አሉ፤ በትክክል ማወቅ ይኖርብኛል።

ለመፈንዳት በሴኮንድ የሚቆጠር ጊዜ ሲቀረው በርሜሉን ከመንገዱ ወደ አድራሻው ለመውሰድ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅብኝ በትክክል መገመት አለብኝ። ለመሆኑ በርሜሉን የሚሸከመው ማነው? መልካም፤ ቆይ . . . በመግቢያው ፊት ለፊት ድንገት በአንድ ታክሲ እደርስና ሁለቱን ዘበኞች በባለሥልጣን ትዕዛዝ ድምፅ እንደዚህ ብዬ አነግራቸዋለሁ። «ይህን በርሜል ወደ ስምሪት ክፍል ውሰዱ። እኔም አዚያው እመጣለሁ። የላከኮት ዋናው ኢንስፔክተር ዱቧ መሆኔንና በትንሽ ደቂቃ ውስጥ እዚያው እንደምመጣ ለኮሚሽነር ዱፖ ንገሩት።»

ግን ይታዘዙኝ ይሆን? በሥራዊቱ ውስጥ ካሉት ከነዚያ ሁሉ ደደቦች መካከል የእኔ ዕድል ሁለት 'ነጭ ለባሾችን ብቻ መግደል ቢሆንስ፣ ከዚያም እኔም ቢጨርሱኝ። ሌላ የተሻለ ነገር ማሰብ አለብኝ። ስለሆነም ደጋግሜ አሰብኩ። ሚንኛውንም ነገር ሙቶ በመሮ አርግጠኛ ሆኜ ለመቀበል ፈጽሞ አልሆነልኝም።

ውሃ ለመጠጣት ተነሣሁ። ብዙ ማሰቤ ሁስ ምታት አሳድሮብኝ ነበር። ዐይኔን ሳልሸፍን እንደገና ተጋደምኩ። ጊዜው ተጉተጉኝ። ያ መብራት ደግሞ፤ ያ መናጢ መብራት ነበር! መሐረቤን አራስኩና እንደገና አስቀመጥኩበት። ችግታዚው በሚገባ ተሰማኝ። ከብደቱም ጨርቁ ዐይኔ ላይ ምርግ ብሎ እንዲቆይ አደረገው። ከዚያ ወዲያ ዘወትር እንደዚሁ አደርጋለሁ።

የወደፊት-ብቀላዬን አንድ ላይ እያቀነባበርኩ የማጠፋቸው ሰዓቶች እጅግ የላቁ ከመሆናቸው የተነሣ አቅዶቹ አሁን ልክ በተግባር ላይ የዋሉ ይመስሉኝ ጀመር። ዘወትር ለሊትና ቀኑንም በከፊል ማምለጫ በገሃድ እንደተሳካልኝ ሁሉ ፓሪስ ውስጥ አሠራለሁ። አመልጣለሁ፤ ፓሪስም አመለሳለሁ። ከዚያም እንደሚታወቀው በትድሚያ ብያኔዬን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለፖሊየን፣ ቀጥሎም ለጆሮ ጠቢዎቹ አቀርባለሁ። ግን ተቺዎቹስ? እነዚያ ውላጅኽ የሰላም ኑሮን እየገፉ ናቸው? እነዚያ ግብዞች ሥራቸውን በከፍተኛ ጥራት እንዳከናወኑ ሁሉ ደስ ብሏቸውና ፈንደቀው በኩራት እንደ ተወጠሩ በጎረቤቶቻቸው ፊት ታላቅ መስለው ለመታየትና ጸጉራቸውን ሳያበጥሩ ከሚጠበቋቸው ሚስቶቻቸው ጋር ሾርባ ለመጋት ወደቤታቸው ሐደው መሆን አለባቸው።

ተቺዎቹን ምን ማድረግ ይኖርብኛል? ምንም። መልሱ ይኸው ነበር። በእርግጥም ታላፊነት የጎደላቸው አሳዛኝ ጥርቅሞች ነበሩ። ዝም ብዬ አተዋቸዋለሁ።

እነዚህን ሐሳቦች በመጻፍ ላይ እንዳለሁ ከረጅም ዓመታት በፊት የነበሩ ሐሳቦች አሁን ከፉኛ በሚያስፈራ ሁኔታ እየተጋረጡ፣ ረጭ ባለ ጸጥታና በሙሉ ብቸኝነት አንዲት ከፍል ውስጥ ተዘግቶበኝ የሐሳብ ኑሮን መግፋቴ ስሜቴን ይከነክነዋል። በእርግጥ ሁለት ሕይወቶችን ኖሬያለሁ። ወደቤቴ፣ ወደ አባቴ ወደ እናቴ ወደቤተሰቦቼ፣ ወደ ሕፃንነቴና በየደረጃው ካንዱ ወደሌላው የሕይወት ዘመኔ በሐሳቤ እየበረርኩ የፈለግሁበት ቦታ ሁሉ ዞሬያለሁ።በሌላ በኩል ለጋው አእምሮዬ በፈለሰፋቸው በስፓኝ ውስጥ ባሉ ቤተ መንግሥቶች ውስጥ በመኖር ላይ እንደምገኝ አድርጌ ራሴን ለማሳመንም በቅቼ ነበር።

ሠላሳ ስድስት ዓመታት አልፈዋል፣ በዚያ የሕይወት ዘመኔ ያሳለፍኳቸውን ሁሉ አስታውሼ ለመጻፍ አእምሮዬ እምብዛም አይጨነቅም።

አላደርገውም! ተቺዎቹን አልጎዳቸውም። ግን የዓቃቤ ሕጉስ ጉዳይ? እርሱንማ . . .! አሱንስ አልምረውም! ከዚህም በላይ ለአሌክሳንደር ዱማስ ምስጋና ይግባውና በጣም ተስማሚውን ቅጣት በሚገባ አግኝቼለታለሁ። «የሞንቴ ኪሪስቶ መኳንንት» በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ያንን ምስኪን ከንቱ ሰው በአንድ ከምድር ሥር በተሠራ ከፍል ውስጥ ቆልፈውበት እንደገደሉት ዐይነት፣ ልክ እኔም እንደዚያው አደርጋለሁ።

በተቻለው መጠን የመጨረሻ አሰቃቂ ውድቀት እንዲገጥመኝ ማንኛውንም ነገር ሁሉ የፈጸመብኝ፣ በቀይ ካባ ውስጥ የተሸፈነው ያስ ጆቢራ አሞራ? አዎ በተለይ በእርሱ ላይ የማተኩረው፣ ከፖሊሶቹና ከፖሊየን በኋላ ይሆናል። ከሥሩ ከመቀመቅ የጠለቀ ምድር ቤት ወፍራም ግድግዳና ከባድ መዝጊያ ያለው አንድ ቪላ እከራያለሁ። መዝጊያው ወፍራም ካልሆነም ራሴው በኪሳና በጥጥ አለብደዋለሁ። አንድ ጊዜ ቪላውን ካገኘሁ በኋላ ጌታው ፕራደልን አፈልግና አፍኜ አወስደዋለሁ። ወዲያውኑ እንደደረስን በግድግዳው ካሉት ቀለበቶች ጋር በሰንሰለት አጠፍረዋለሁ። ከዚያም የእኔ ተራ ይጀምራል።

ከእርሱ ፊት ለፊት ነኝ። ከተከደኑት የዐይኖቹ ቆቦች ሥር በልዩ ሁኔታ ግልጽ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሆኖ አየዋለሁ። እርሱ በፍርድ ቤቱ እንደ ተመለከተኝ ዐይነት እኔም አመለከተዋለሁ። የትንፋሹ መውጣት በፊቴ ላይ ይሰማኛል።

በእርሱ ላይ ያነጣጠርኩት ኃይለኛ የብርሃን ጨረር የጆቢራ ዐይኖቹን ስላደናበራቸው በጭንቀት ተደናግጠዋል። ግዑዝ በሆነው ፊቱ ላይ ወፍራም የላብ ጠብታዎች ቁልቁል ይወርዳሉ። አዎ፤ የእርሱንም መልስ እያዳመጥኩ የእኔንም ጥያቄዎች አሰማለሁ። ጊዜውን በጋራ ስሜት አገፋዋለሁ።

«አንተ መናጢ ደደብ፤ ለመሆኑ ታስታውሰኛለህ? እኔ ፓፒዮ ነኝ! ወደ ዕድሜ ልክ ፅኑ አሥራት እንድገባ አንተ በደስታ የተስማማህብኝ ያ ፓፒዮ! በሮማውያን የሕግ አንቀጾች ላይ ያጠፋሃቸው እነዚያ ሁሉ ሌሊቶች፤ ግሪክና ላቲን ለማጥናት የወጣትነት ዘመንህን በመሠዋት ዕውቀትን ለማትረፍ ያሳለፍካቸው እነዚያ ሁሉ አድካሚ ዓመታት፤ አሁን ዋጋ አላቸው ብለህ ታስባለህ? የት ለመድረስ ነበር ያለምከው አንተ ከንቱ? የተሻለ የሕበረተሰብ ሕግ ለመፍጠር ነበር? ሰላም ለሸበር ፋጣሪዎች በዓለም ውስጥ ከፍተኛ ጠቃሚ ነገር መሆኗን ለማሳመን ነበር? አንድ ቤዛ የሆነ አዲስ ሃይማኖት ለመስበክ ነበር? ወይም ሌሎች ሰዎች በቀላሉ የተሻሉ የሚሆኑበትን አለበለዚያም ቢያንስ ከፉ መሆናቸውን እንዲያቆሙ ለመንገር ነበር? -

«ከዚህ ውስጥ ምንም ነገር አልፈጸምከም። የሚገፋፋህ አንድ ምኞት ብቻ ነው። ሞንጠላጠል፤ መንጠላጠል፤ በወራዳው ሙያህ መሰላል ላይ መንጠልጠል። ለአንተ ከብርህ ሰውን ለቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ዳረጎት አቅራቢነትና ይበልጥ ደግሞ ለምትና ለስቃይ ከፍተኛ ችሮታ ለጋሽ መሆን ነበር።

«ዲብለር፤ (በ1932 ዋና ገዳይ የነበረ) ቅንጣት ታህል ምስጋና ሊያቀርብልህ ቢፈልግ በየዓመቱ መጨረሻ ላይ አንድ ሠጥን ምርጥ ሻምፓኝ ይልክልሃል። በአንድ ዓመት ውስጥ አምስት ወይም ስድስት ተጨማሪ ጭንቅላቶች ለመቁረጥ መቻሉ ለአንተ ምስጋና አይደለም? አንተ ዓሣማ! ያም ሆነ ይህ አሁን በዞን ግድግዳ ላይ በሰንሰለት ጠፍሬሃለሁ።

«የፍርዱን ውጤት ስትሰማ የነበረህን ፈገግታና የፍንደቃ አስተያየት በሚገባ አስታውሳለሁ! አሁን ታድያ ወዳጄ፤ ያንን ሁሉ ልለውጠው ነው። ይሁንና እኔ ያላጋጠመኝ አንድ ዕድል አለሀ። እኔ ሚልቀስ አልቻልኩም፤ አንተ ግን ትችላለህ። ስለዚህ ቀጥል። ፍለግከውን ያህል አልቅስ፤ አልቅስ፤ የፈለግከውን ያህል ጩህ። ምን ባደርግህ ይሻለኛል? በረኃብ እንድትሞት ልተውህ? አይሆንም፤ በቂ አይሆንም። በቅድሚያ ዐይኖችህን አወልቃቸዋለሁ። ይህም አይሆንም። ያ በኋላ የሚመጣ ነው። በመጀመሪያ ያንን እንደ ጩቤ የተሳለ እንዲያውም ከጩቤ የበለጠ እንደ ምላጭ የሰላውን ያን መዓተኛ ምላስህን አቆርጠዋለሁ። ያንን ሃሳስ ለዝነኛው ሙያህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሸርሙጠህበታል!»

ጭንቅላቴ እስኪዞር ድረስ እየደጋገምኩ አራመዳለሁ፣ ግን ድንጉት መብራቱ ጠፍቶ በመንጋት ላይ ያለው የቀን ውጋጋን በከፍሌ መስኮት ፍርግርግ ብረቶች ውስጥ እስኪገባ ድረስ . . . ከርሱ ጋር ፊት ለፊት እንደ ሆንኩ ቆየሁ።

እንዴት ሊሆን ቻለ? በአንድ ጊዜ ነጋ ማለት ነበር? እነዚያ ሰዓቶች ምንኛ ቀንጃዎች ነበሩ! የረጅም ረጅም ሌሊት እንዴት ፈጥኖ ሔደ!

በአልጋዬ ላይ እንደ ተቀመጥኩ አዳምጣለሁ። ምንም ነገር የለም። ፍጹም ፀጥታ። አልፎ አልፎ በመዝጊያ በኩል አንድ ትንሽ ድምፅ «ቲክ» ትላለች። ዘበኛው ድምፅ የሌለው ነጠላ ጫማ አድርጎ አንዲት የተዘጋች ትንሽ ቀዳዳ እየገለጠ ዐይኑን በማጮለቅ እኔ ሳላየው እየተመለከተኝ ነበረ።

በፈረንሣይ ሪፑብሊክ የተወጠነው መሣሪያ አሁን ሁለተኛውን ደረጃ ይዞ ነበር። በሚያስደንቅ ሁኔታ ተግባራዊ ሆኗል። የመጀመሪያው ደረጃ የተበሳጨን ሰው አውድም ነበር። ግን ያ በቂ አልሆነም። ሰውየው በጣም ፈጥኖ መሞት አይኖርበትም፣ ወይም ራሱን በራሱ በመግደል ማምለጥ የለበትም። ይፈልጉታል። አስረኞች ባይኖሩ የቅጣት አስተዳደር ምን ሊያደርግ ኖሯል? የሌሎቹን ቢሮክራቶች ሀልውና ለማረጋገጥ አስረኛ መጠበቅና ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤቶች መሔድ ሊኖርበት ነው።

«ቲክ» የምትለውን እንደገና ስለሰማሁ ፈገግ አልኩ። ተዝናኑ፣ ጊዜያችሁን እያባከናችሁ ነው፣ ብየ በዝግታ ነገርኳቸው። እኔ አላመልጣችሁም - ያውም ራሱን በራሱ ይገድላል ብላችሁ እናንተ በምትሠጉበት መንገድ። አንድ ነገር ብቻ አጠይቃችኋለሁ። በተቻለ መጠን ጤነኛ እንደሆንኩ ቆይቼ ባስቸኳይ ወደ ፈረንሣይ ጊያና እንድሔድ።

ስማ የእኔ የጥንቱ የወህኒ ዘበኛ፣ ባልደረቦችህ ሕፃናት መዘምራን እንዳልሆኑ ዐውቃለሁ፣ ታዲያ በየጊዜው ያችን «ቲክ» የምትል ድምፅ የሚያሰማው ማነው። ከእነርሱ ጋር ስትነጻጸር አንተ ጥሩ አባት ነህ። ይህንንም ከረጅም ጊዜ በፊት ዐውቃለሁ። ምክንያቱም ሣልሳዊ ናፖሊዎን አሰቃቂ ወህኒ ቤቶችን ረቆረቁር። እነዚህን ወንበዴዎች ማነው የሚጠብቃቸው? ተብሎ ተጠይቆ ነበረ። የሰጠውም መልስ «የባሱ ወንበዴዎች» በማለት ነበር። ከጊዜ በኋላ የአሰቃቂ ወህኒ ቤቶቹ መሥራች አባት ውሸቱን እንዳልነበረ ሐቁን ለማረጋገጥ ችያለሁ።

ከላከ፣ ከላከ፣ አለችና በመዝጊያዬ መካከል ያለች ስምንት ኢንች ካሬ የሆነች አንዲት ቀዳዳ ተከፈተች። ቡናና ሁለት ፓውንድ የሚመዝን አንድ ቁራሽ ዳቦ አቀበሉኝ። አስረኛ እንደመሆኔ ሆቴል ውስጥ ገብቼ ለመመገብ ያለኝ እድል አከትሟል። ሆኖም ግንዛቤ አስካለኝ ድረስ ሲጋራ ለመጣዛትና ከአነስተኛ ሆቴል ምግብ ለማስመጣት

t.me/OLDBOOKSPDF

እችላለሁ። የቀረኝ ትንሽ ቀን ስለሆነ ምንም የሚያሳስበኝ ነገር አልነበረም። የጥበቃ ጣቢያው፣ አስረኞች ከሰው ተለይተው በግዞት ለጥቂት ቀናት የሚቆዩበት ከፍል ነበር። ሁለት ሲጋራ አንዱን በሰድስት ፍራንክ ከሰደሳ ሂሳብ ገዛሁ፣ አንዱን ላኪስትራይክ በደስታ አጨስ ጀመር። ለመልስ የሚሰጡ ሳንቲሞች በፍትህ ስም መወሰዳቸው ስለማይቀር ኩርፍራፊ ምንዛሬዎቹን አጠፋቸው ነበር።

በዳቦ ውስጥ አንዲት ትንሽ ማስታወሻ ተሸጉጣ አገኘሁ። የተላከችው ከዴጋ ሲሆን ወደ ተባይ ማራገፊያ ከፍል እንድሄድ ትጠቁማለች።

«በከብራት ሣጥን ሦስት ቅማሎች ልኬልሃለሁ። ፍልውሃ መታጠቢያ ከፍል መጥተህ እንድንገናኝ። «የከብራት እንጨቶቹን አውጥቼ ሳጥኗን ስፈትሽ ሦስት ወደል ቅማሎች አገኘሁ። ምን ማድረግ እንደሚኖርብኝ ገባኝ.:

ተባይ ጨረሰኝ ብዬ እነዚህን ቅማሎች ለዘበኛ ማሳየት አለብኝ። ጓዜን ጠቅለዬ ከነፍራሹ ነገ ጠዋት ወደ ፍልውሃ እንድሄድና እኔ ብቻ ሰቀር ተባዮቹን በሙሉ እንዳራግፍ ዘበኛው ይፈቅድልኛል። ዘዴያችን ሰመረና በማግስቱ ጠዋት ዴጋ ጋር መታጠቢያው ከፍል ተገናኘን። ወታደሮች የሉም ብቻችንን ነበርን።

«አመሰግናለሁ ዴጋ፣ ምስጋና ይድረስህና በገንዘብ መደበቂያ ቱቦ ያለውን ገንዘብ አገኘሁ።»

«ችግር ፈጠረብህ እንዴ?»

«ምንም አላስቸገረኝም።»

«መጸዳጃ ቤት በምትሔድበት ወቅት ወደ ፊንጢጣህ ውስጥ መልሰህ ከመክተትህ በፊት ቱቦውን በሚገባ እንድታጥባት።»

«እሺ፣ ቱቦዋ ተሰተካከለ ስለተዘጋጀች ኖቶቹ ገና አዲስ እንደሆኑ ናቸው። አልተበላሹም። ከያዝኳት ሰባት ቀን መሆኑ ነበር።»

«ሁኔታው በመሳካቱ ተደስቻለሁ።»

«ወደፊት ምን ለማድረግ ዕቅድ አለህ ዴጋ?»

«ዕቡድ በመምሰል ላጭበረብር ነው። ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መሄድ አልፈልግም። አዚሁ ፈረንሳይ ውስጥ ስምንት እና አሥር አመት መታሰር አመርጣለሁ። ግንኙነት አለኝ፣ አምስት ዓመት ለማስቀነስ እችላለሁ።»

«ዕድሜህ ምን ያህል ነው?»

«ወርባ ሁለት።»

«አበደሃል እንዴ! ታዲያ ዕሥር ወይም አሥራ አምስት ዓመት ወህኒ ቤት ውስጥ ቆይተህ ከወጣህ ሽማግሌ መሆንህ ነው እኮ! ጽኑ አሥራት ያስፈታሃል እንዴ?»

«አዎ፣ የዚያን የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ኑሮ አፈራለሁ ብል

t.me/OLDBOOKSPDF

አላፍርበትም። ታውቃለህ የጊያና ደሴት በጣም አሰቃቂ ነው። በየዓመቱ ከእሥረኞቹ ከመቶ ሰማንያውን ያጣሉ። ኮንቮይ በየጊዜው እየተካቸው ነው። አንዱ ሲሄድ ሌላው ይመጣል። እያንዳንዱ ኮንቮይ ከአንድ ሺህ ስምንት መቶ እስከ ሁለት ሺህ ሰዎች ያጓጉዛል።

«ዝምጥና ከሳተህ፣ ቢጫ ወባ ወይም የደም ተቅማጥ ወዲያውኑ ይቀስፍሃል፣ ሳንባ ነቀርሳና የወባ መረርሽኝም የዚያኑ ያህል ነው። ከነዚህ ሁሉ በሽታዎች ካመለጥክ ሌላው የሚጠብቅህ እድል በቆርቆሮ ቱቦ ለደበቅከው ገንዘብ ሲል ከሚገድልህ እጅ መውደቅ ወይም በአንዱ ረብሻ መሞት ይሆናል። አመነኝ ፓፒዮ፣ ይህን የምነግርህ አንተን ተስፋ ለማስቆረጥ እንዳይመስልህ። ግን የምናገረውን በትክክል ምን እንደሆነ አውቃለሁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ማለት፣ በአምስት እና በሰባት ዓመት እንኳ ወደ ፈረንሳይ የተመለሱ አሥረኞችን አውቃለሁ። የሰው ዝቃጭ ናቸው። ከዓመቱ ዘጠኙን ወር የሚያሳልፉት ሆስፒታል በመመላለስ ነው። ለማምለጥም ቢሆን አንተ እንደምትገምተው እንደዚህ ቀላል እንዳይመስልህ።»

«አምንሃለሁ ዴጋ፣ ግን በራሴ ስለምተማመን በዚያ በማይረባ ቦታ ብዙ ጊዜ ለመቆየት አልፈልግም። ጥሩ ጀልባ ቀጣሬ ነኝ። ባህሩንም አውቀዋለሁ። ስለዚህ ለማምለጥ ጊዜ አይፈጅብኝም። አሥር ዓመት ሙሉ ራስህን በማዞት ለማቆየት የሚቻል ይመስልሃል? አምስት ዓመት እንኳ ቢቀጣሉልህ፣ ለዚያውም ማድረጋቸው ገና እስተማማኝ አይደለም። ፈጽሞ አብደት ሳይገጥምህ ብቸኝነትን ሙሉ በሙሉ መቋቋም ይቻላል? እስኪ እኔን አሁን ተመልከት አንድ ከፍል ውስጥ ብቻዬን ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ! የምታነበው ነገር ናለህ፣ ወደ ውጪ መውጣት አይፈቀድ፣ የምታነጋግረው የለህ። ስልሳ ደቂቃ ሳይሆን እንደ ሰድስት መቶ ደቂቃዎች ይረዝምብሃል። ታሪኩ ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላ ብዙ ነገር አለ።»

«ሊሆን ይችላል፣ ግን አንተ ወጣት ነህ። እኔ ዐርባ ሁለት ዓመት ሆኖኛል።»

«ስማ ዴጋ፣ የሚያስፈራህ ነገር አለ እንዴ? አሰረኞቹ ናቸው?»

«ፓፒ እንግዲያውስ እውነቱን ከፈለግህ እዎ። እነርሱው ናቸው። ሚሊዮኔር እንደ ነበርኩ ማንም ያውቃል። በዚህ ምክንያት ቢያንስ ሃምሳ ወይም መቶ ሺ ፍራንክ ይይዛል ብለው ቢገድሉኝ ምን የሚያጣዳቸው ነገር አለ?»

«አዳምጥ፣ በእንድ ነገር መስማማት ትፈልጋለህ? ወደ ዕበዶች ሐኪም ቤት ሳለመግባት ቃል ግባልኝና እኔም ዘወትር ከሳንህ ሳልነጠል ልጠብቅህ ቃል እገባልሃለሁ። እርስ በርሳችን በሚገባ እንተባበራለን። ጠንካራና ፈጣን ነኝ። በጩቤ ትግልም ችሎታ አለኝ፣ ቀደም ሲልም የውጊያውን ስልት ተምሬአለሁ። ስለዚህ አታስብ። እርግጥ ሌሎች አሰረኞች ሊያከብሩን አይፈልጉም፣ ቢሆንም አይደፍሩንም። ለማምለጥ ሌላ አሰረኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

መጨመር አያስፈልገንም። ገንዘብ ከሆነ አንተም ሆንክ እኔ ይዘናል። ጀልባ መቅዘፍና ኮምፓስ እንዴት እንደሚስተካከል ዐውቃለሁ። ታዲያ ከዚህ ወዲያ ምን ትፈልጋለህ?»

ትኩር ብሎ ፊት ለፊት ተመለከተኝና . . . ሁለታችንም በስሜት ተቃቅፈን በሐሳብ መስማማታችንን አጸደቅን።

ከትንሽ ጊዜ በኋላ የፍልውሃ መታጠቢያ ከፍሉ መዝጊያ ተከፈተ። ሁለታችንም ተለያየንና መንገዳችንን ቀጠልን። ከፍላችን ብዙም የተራራቀ ስላልነበረ፣ በየጊዜው ወደ ጸጉር ማስተካከያ፣ ወደ ሐኪም ቤት፣ በሰንበት ቀን ደግሞ ግቢው ውስጥ ወደምትገኘው ጸሎት ቤት ስንሔድ እንገናኛለን።

ዴጋ የተያዘው መንግሥት ያሳተማቸውን የገንዘብ ሰነዶች በማጭበርበር ሲጠቀም ነበር። አንድ የሐሰት ሰነድ ደላሽ፣ ልክ እንደ አርጅናሉ ኖት አያስመስለ ቀይሯቸው ነበር። በማያስነቃ ዘዴ ባለ አምስት መቶውን ኖት ቁጥሩን ፍቆ፣ ወደ ዐሥር ሺ ኖት ይለውጠዋል። ሥራው በጣም ግሩም ነበር። ወረቀቱ ተመሳሳይ ስለነበረ ባንኮችም ያለመጠራጠር ይቀበሉታል። በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት ሲያጭበረብር ቆይቷል። የገንዘብ ሚኒስቴሩም ፍንጩን ለማግኘት ግራ ተጋብቶ ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ብሪውሌ የተባለ ሰው እጅ፣ ከፍንጅ ይያዛል። ይህ በዚህ እንዳለ ፣ ዴጋ ጉዳዩን ዳዋ ልበስ ብሎ ማርሴይ ውስጥ የሚገኘውን ሬስቶራንቱን ያለሥጋት ያስተናብር ነበር። በከተማው ከሚገኙት ዕውቅ የደቡብ ፈረንሣይ ጎሣዎችና ከየአህጉሩ ከሚመጡ ተዘዋዋሪ ወመኔዎች ጋ በየዕለቱ እየተገናኘ ሲገናኛ ያመሻል።

በ1929 ሚሊዮኔርነቱን አረጋገጠ። አንድ ቀን ማታ ሺክ ያለ ልብስ የለበሰች አንዲት ውብ ኮረዳ ወደ ሬስቶራንቱ ጎራ ብላ፣ አቶ ሉዊ ዴጋ ወዴት እንደሚገኝ ትጠይቃለች።

«እኔ ነኝ አመቤቴ፣ ምን ልርዳሽ? ወደሚቀጥለው ከፍል ገብተሽ ትጠብቂኝ?» ይላታል።

«የብሪውሌ ሚስት ነበርኩ። የተጭበረበረ የገንዘብ ኖት ሲጠቀም ተይዞ፣ ፓሪስ ውስጥ በእስር ላይ ይገኛል። በሳንቲ የእስረኛ ጎብኝዎች ማረፊያ ከፍል ውስጥ ተነጋግረን የእርስዎን ሬስቶራንት አድራሻ ሰጥቶኝ ነበር። ለጠበቃ ማቆሚያ የሚሆን ሐያ ሺ ፍራንክ እንዲሰጡኝ ንገሪ ብሎኝ ነው የመጣሁት» ትላለች።

ዴጋ ፈረንሣይ ውስጥ አሉ ከሚባሉት አራዳዎች ቀንደኛው ሆኖ ሳለ በወንጀሉ ውስጥ እርሱም እንዳለበት ሲተየዋ ማወቋ አደገኛ መሆኑን እየተረዳ፣ ይህን የማይገባ መልስ መስጠት የለበትም ነበር። ይሁንና፣

«አመቤቴ፣ ስለእንች ባል ምንም የማውቀው ነገር የለም። ገንዘብ የምትፈልጊ ከሆነ ጎዳና ወጥተሽ ተዘዋወሪ። በጣም ቆንጆ ስለሆንሽ ከምትፈልጊው በላይ ታገኛለሽ»

t.me/OLDBOOKSPDF

ይላታል።

ምስኪኗ ሴት ይህን ቃል መቋቋም ስለተሣናት እንባዋን ረጭታ ሮጣ ወጣች። ከዚያም በፍጥነት ወደ ፓሪስ ተመልሳ ሰባሏ ነገረችው። ብሪውሌም ከመጠን በላይ በጎነ። በማግሥቱ ለመርማሪው ዳኛ ምስጢሩን በሙሉ ዘከዘከ ተናገረ። የሐሰት ኖቱንም የሰጠው ዴጋ እንደነበረ በማጋለጥ ሕጋዊ ክስ መሠረተበት።

በፈረንሣይ ዕውቅ የሆኑ የፖሊስ ነጭ ለባሾች ዴጋን መከታተል ጀመሩ። በአንድ ሣምንት ውስጥ ዴጋ፣ ኖት ደላላቡ፣ አታሚውና ዐሥራ አንድ ግብረ አበሮች ጭምር ተይዘው በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ታሰሩ። ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ ለዐሥራ አራት ቀናት ያህል ችሎቱ ሲያጣራ ሰነበተ። ለእያንዳንዱ አስረኛ መንግሥት ከፍተኛ ጠበቃ አቁሞላቸው ነበር። ብሪውሌም ሽንጡን ገትሮ ተከራከረ። የመጨረሻውም ውጤት፣ በፈረንሣይ የታወቀው ምላጭ አራዳ፣ በማይረባ ሐያ ሺ ፍራንክና በተነፈሰው ጸያፍ አነጋገር የተነሣ ለዐሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ተዳረገ። እንደዚህ ከመሰለው ሰው ጋር ነበር የሞትና የሽረት ውል የፈራረምኩት።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . ጊዜ አራመድና ከዚያም እዞራለሁ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . አሁንም እዞራለሁ። ሰባዙ ሰዓቶች በመዝጊያውና በመስኮቱ መካከል በከፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ሰራመድ አቅያለሁ። ሲጃራ ስላጨስኩ ሞራሌ ከፍ ብሎ ለማንኛውም ነገር ተዘጋጅቻለሁ። ሰዢዉው ስለ ብቀላ ምንም ነገር እንዳላስብ ራሴን በራሴ ቃል አስገባሁት። ዓቃቤ ሕጉንም በሰንሰለት ከፊት ለፊቴ አስሬ እንደተውኩት ፍርዱን ይጠብቅ። ይሁን እንጂ፣ እንዴት አድርጌ እንደምገድለው ገና አልወሰንኩም።

በከፍሌ መዝጊያ በኩል ድንገት የሚያስደነግጥ አንድ የጣዕረሞት ጩኸት ሰርስሮ ገባ። ምን ይሆን ድምፁ? ያንድ የሚደበደብ ሰው አሪታ ይመስላል። ግን ይህ ቦታ ፖሊስ ጣቢያ አልነበረም። ምን እንደሆነ የማውቅበት መንገድ አጣሁ። በውድቅት ሌሊት የሚሰማው አሪታ መንፈሴን ረበሸው። ይህንን መርግ የሆነ መዝጊያ አልፎ እዚህ ከፍል ድረስ የሚሰማ ድምፅ ምን ዓይነት ኃይል ቢኖረው ነው! ያለጥርጥር አንድ ሰው አብዷል ማለት ነው። መቸም እዚህ ቦታ የማይደረግ ነገር የለም። ጮክ ብየ ራሴን ጠየቅኩት። «የፈለገው ነገር ቢሆን አንተ ምን ቸገረህ? ስለራስህ ብቻ፣ ስለራስህ ስለአዲሱ ኤጋርህ ስለ ዴጋ ብቻ አስብ።»

ጎንበስ ብየ ቀና አልኩና ወደ ኋላ ለጠጥ በማለት ደረቴን ደህና አድርጌ በአንድ ወፍራም ቡጢ አቀመስኩት። በእርግጥ የሚሰማ ምት ቢሆንም፣ ማንኛውም አቋሜ አስተማማኝ ነበር። የእጅቼ ጡንቻዎች ፈርጠም ብለው በጥሩ ቅርፅ ላይ ይገኛሉ።

የእግሮቼስ ሁኔታ? እንኳን ደስ አላችሁ ልላቸው ይገባል። በቀን ውስጥ ዐሥራ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስድስት ሰዓት እየተራመድኩባቸው ፍጹም የመዛል ስሜት አይታይባቸውም። በሞንቅላት ላይ ውሃ ማንጠባጠብን ቻይናውያን ፈለስፉ። ፈረንሣውያን ዝምታን ፈለሰፉ። ከማንኛውም የከፉ ቅስም ሰባሪ መጨቆኛ አገኙ። መጽሐፍ የለም፣ ጋዜጣ የለም፣ ኦርሳስ የለም፣ መስኩቱ ትንሽ ብርሃን የሚያስገቡ ቀዳዳዎች ይኑሩት እንጂ ከወፍራም ቋሚ ምሰሶዎች ጋር ሙሉ በሙሉ በጣውላ የተሸፈነ ነው።

የሚያሸብረው ጩኸት ፍጹም ሰላም ነሳኝ። ልከ በወጥመድ ውስጥ እንዳለ አውሬ የከፍሉን ዙሪያ አማተርኩ። በዕውን በሕይወቴ እንደተቀበርኩና ብቻየን የተጣልኩ መሆኔ ተሰማኝ። በእርግጥም ብቻየን ነበርኩ። ከለቅሶ በስተቀር ምንም ነገር ወደ እኔ የሚደርስ የለም።

መገዢያው ተከፈተ። አንድ አረጋዊ ቄስ ነበሩ። ሌላው ቢቀር ብቻህን አልሆንክም። በቀጥታ ከፊት ለፊትህ አንድ ቄስ ቆመውልሃል።

«እንደምን አመሸህ ልጄ ፈጠን ብዬ ባለመምጣቴ ይቅርታ አድርግልኝ። ግን በበዓሉ ምክንያት ነበር። እንደምን አለህ?» ያለምንም ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት ሩህሩህ አረጋዊ ወደ ከፍሉ ገቡና በታጣፊ አልጋዬ ላይ ተቀመጡ። «ምን አድርገህ ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ።

ንጹሕነቴን መደጋገሙ ፋይዳ ቢስ መሆኑን ስለ ተመለከትኩ፣ «ፖሊሶች አንድ ሰው ገድለሃል ይሉኛል፤ እንደዚያ ከሆነም ያሉት መሆን አለበት» በማለት ፈጠን ብየ መለስኩላቸው።

«ምን ዓይነት ሰው ኖሯል?»

«አንድ አታጣሪ።»

«ታዲያ ለአንድ ወራዳ ሰው ግድያ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፈረዱብህ? አልገባኝም። በቂም በቀል ኖሯል?»

«አይደለም»

«ማመን አልችልም፣ የእኔ ምስኪን ልጅ። ምን ላደርግልህ እችላለሁ? ከእኔ ጋር መጸለይ ትፈልጋለህ?»

«ይቅርታ አድርጉልኝ አባቴ፣ ፊጽሞ የምከተለው የሃይማኖት መመሪያ ስለሌለኝ እንዴት እንደሚጸለይ አላውቅም።»

«የእኔ ልጅ፣ ልዩነት የለውም። ራሴው እጸልይልሃለሁ። የተጠመቁትንም ሆነ ያልተጠመቁትን ልጆቹን ሁሉ ቸሩ እግዚአብሔር ይወዳቸዋል። እኔ የምናገራቸውን እያንዳንዳቸውን ታላት ደግመህ ለማለት ፈቃደኛ ነህ?»

ዐይኖቻቸው ረጋ ብለው ሰፈው ገጻቸው በርኅራኄ ብሩህ አመለካከት የተሞላ ስለነበር፣ የጠየቁኝን እምቢ ለማለት ኃፍረት ተሰማኝና በርከክ ሲሉ እኔም እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

አርሳቸው ተንበረከከሁ።

«አባታችን ሆይ፣ በሰማይ የምትኖር . . .»

በዐይኖቼ እንባዎች ተንቆረዘዙ። ርኅሩኑ አባት እንባዎቼን ሲመለከቱ አጫጭር ጣቶቻቸውን በጉንጮቼ ላይ አስቀመጡና አንድ ወፍራም እንባ ይዘው ወደ ከንፈራቸው በመውሰድ መጠጡ።

«የእኔ ልጅ እንባዎችህ አግዚአብሔር ለእኔ ሊሰጠኝ የቻላቸው ከፍተኛ በረከቶች ናቸው። አመሰግናለሁ» አሉና ብድግ ብለው ግንባሬን ሳሙኝ። እንደገና አልጋው ላይ ጎን ለጎን ተቀመጥን።

«ካሁን በፊት እንደዚህ ካለቀስክ ምን ያህል ጊዜ ሆኖሃል?»

«ወሥራ አራት ዓመት»

«ወሥራ አራት፣ ለምን?»

«እናቴ ሞታብኝ» እጄን ያዝ አደረጉና፣ «ለመሠቃየት ያደረሱህን በሙሉ ይቅርታ አድርግላቸው» ሲሉኝ፣ የማደርገውን ሳላውቅ እጆቼን አወናጨፍኩና ከተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋው ላይ አመር ብየ በከፍሉ መካከል ቆምኩ።

«አ፣ አላደርገውም! ያስ አይሆንም። ፍጹም ይቅርታ አላደርግም። አንድ ነገር እንድነግርዎት ይፈልጋሉ አባቴ? ሌሊቱንና ቀኑን በሙሉ፣ ማንኛዋንም ሰዓትና ደቂቃ የማሳልፈው ወደዚህ ያላኩኝን ሰዎች መቼና እንዴት እንደምገድል በማሰላሰል ነው።»

«የእኔ ልጅ፣ አሁን የምታስበውና የምትናገረው ይህንኑ ነው። ወጣት ነህ፣ በጣም ወጣት ነህ። እየሸመገልክ ስትሄድ ግን፣ የቅጣትንና የመበቀልን ሐሳብ ትተዋለህ።»

ከሦሳሳ አራት ዓመታት በኋላ ከአርሳቸው ሐሳብ ጋር ተስማምቻለሁ።

«ምን ላደርግልህ እችላለሁ?» አሉ ቄሱ በድጋሚ።

«ሕግ ያፍርሱ።»

«የምን ሕግ?» ወደ ቁጥር ሰላሳ ሰባት ከፍል ይሒዱና ለዴጋ ጠየ ቃህን ወደ ኪየን ወህኒ ቤት እንዲያስልክህ ጠይቀው ብለው ይንገሩልኝ። የእኔንም ፣ሬ እንዳልኩት ይንገሩት። ወደ ፈረንሣይ ጊየና ኮንቮይ የሚንቀሳቀሰው ከዚያ ወህኒ ቤት ስለሆነ፣ በተቻለ ፍጥነት ወደ እዚያ መሔድ አለብን። የመጀመሪያው ኮንቮይ ካመለጠን፣ ሌላ እስኪመጣ ድረስ ሁለት ተጨማሪ ዓመታት በግዞት መቆየታችን ነው። አባቴ፣ ከነገሩት በኋላ ወደዚሁ እንዲመለሱ»

«የማመካኝበት ምን ምክንያት ልጠቀም?»

«የዘወትር ጸሎት መጽሐፌን ረስቼ ነው ይበሉ። መልሱን አጠባበቃለሁ።»

«ወደ አስፈሪው የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ለመሔድ እንዴት እንደዚህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተጣደፍክ?

እኅህን ተዘዋዋሪ የእግዚአብሔር ቃል ወኪል አድም በመገምገም የማያጋልጡኝ መሆናቸውን ስለተማመንኩ፣ ብፍጥነት ማምለጥ እንድችል ነው አባቴ» አልኳቸው። «አምናለሁ፣ እግዚአብሔር ይረዳሃል የእኔ ልጅ። ኑሮህንም እንደገና እንደምታድስ ይሰማኛል። የጥሩ አስተዋይነትና የጨዋ መንፈስ አለህ። ወደ ቁጥር ሦላሳ ሰባት እሑድና መልሱን ይገቢልህ እመጣለሁ።»

ጊዜ ሳያባክኑ ተመለሱ፣ ዴጋም ተስማምቶ ነበር።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ከጧቱ አራት ሰዓት ላይ እኛ ሰባቶቻችን በጥበቃ ጣቢያው ከፍል መተላለፊያ በመስመር ተሰልፈን ነበር። ዘበኞችም ኃይላቸውን አጠናክረው እዘያው ነበሩ።

«አውልቁ!» ተባልን።

በዝግታ አወለቅን። ይቀዘቅዝ ነበር። አካላቴ ተጉረበረበ።

«ልብሶቻችሁን ከፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ፣ ቀኝ ኋላ ዙሩና አንድ እርምጃ ወደ ኋላ ተመለሱ» ከአያንዳንዳችን ፊት ለፊት አንድ ጥቅል አገኘን።

«ልበሱ!»

ከጥቂት ጊዜ በፊት ለብሸው የነበረ ካናቴና በሻካራና ግርር ባለ አንድ ነጭ ሸሚዝ፣ የሚያማምሩት ልብሶቼ፣ ሱሪዎቼና ጃኬቶቼ በከርዳዳ የጹቁት ከረጢት ጨርቅ ተተኩ። ጫማዎቼም ደብዛቸው ጠፍቶ በአንድ ጥንድ ነጠላ ጫማዎች ውስጥ እግሮቼን ደነቀርኳቸው። እስከዚያች ቀን ድረስ ሁኔታችን እንደማንኛውም ሰው ይመስል ነበር። ወደ ሌሎቹ ስድስቱ ሰዎች ተመለከትኩ። ምን ዐይነት ቀፋፊ ኖሯል! ልዩነታችን እከተመ። በሁለት ደቂቃ ውስጥ ወደ አሥረኛነት ተቀየርን።

«ወደ ቀኝ ዙር! በነጠላ ረድፍ፣ ተጠንቀቅ፣ ወደፊት ሒድ!»

ከሐያ አጃቢ ዘበኞዎቻችን ጋር ወጣንና እያንዳንዳችን በየተራ አንድ ጠባብ የፖሊስ ካሚዎን ውስጥ ታጎርን። ኪየን ወደሚገኘው (የቦሊያ) ወህኒ ቤት ጉዞ ቀጠልን።

የኪየን ወህኒ ቤት

ወዲያው እንደ ደረስን ወደ አዛዡ ቢሮ ተወሰድን። ከፍታው ሦስት ጫማ በሆነ ሰገነት ላይ በሚያስፈራ ግርማ ከአንድ ጠረጴዛ በስተኋላ በኩራት ተቀምጧል።

«ተጠንቀቁ ! አዛዡ አሁን ንግግር ያደርጉላችኋል።»

«አስረኞች፣ ይህ ቦታ ወደቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት እስከትሔዱ ድረስ የምታርፉበት የመሸጋገሪያ ጣቢያ ነው። ወህኒ ቤት ነው። በማንኛውም ወቅት ጸጥታ አስፈላጊ ነው። ጉበኛዎች እንዲጠይቋችሁ አይፈቀድም። ደብዳቤ የለም። አሜን

t.me/OLDBOOKSPDF

ብላችሁ ታዘዙ::»

«አለበለዚያ ትንከታከታላችሁ:: ለእናንተ የተዘጋጁ ሁለት መዝጊያዎች አሉ:: አንደኛው መልካም ሥነ ምግባር ካሳያችሁ ወደ ቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ወደ መቃበር ጉድጓድ ነው:: ለመጥፎ ሥነ ምግባር በጣም ኢምንት ቢሆንም እንኳን ቅጣቱ በውሃና በዳቦ ብቻ ለሰድሳ ቀናት በቀዝቃዛ ግንብ ውስጥ መቆየት ይሆናል:: እዚያ ሁለት ጊዜ በተከታታይ ከተቀጡት ውስጥ ማንም የተረፈ ሰው የለም:: ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷችኋል!»

ከስፓኝ ተባርሮ የነበረውን ፒየሮ ለፉን አነጋገረው::

«ሙያህ ምን ነበር?»

«እንደ ስፔን ወታደሮች ሁሉ የሠለጠንኩት ከኮርማዎች ጋር ፍልሚያ በመግጠም ነበር::»

አዛገፍ በመልሱ ተናደደና እንደዚህ ሲል አጓራ፣ «ይህን ሰው ወዲያ ውሰዱልኝ!»

ወዲያውኑ አራት ወይም አምስት ወታደሮች እየደበደቡ በወሳንሳ ተሸከመው ወሰዱት:: «እናንት ግማታሞች፣ አምስት ሆናችሁ ለአንድ ሰው ዱላ ትጠቀማላችሁ? እናንት ቆሻሻ ዲቃላዎች!» እያለ ሲጮህ መስማት ችለን ነበር:: ከዚያም ሊሞት እንደ ቆሰለ አውሬ «አህህ» ሲል ሰማን:: በኋላ ምንም ነገር የለም:: በሲሚንቶው ወለል ላይ የሚጎተት የአንድ ነገር ድምፅ ብቻ::

አጋጣሚ ዴጋ ከእኔ ከፍል ቀጥሎ ያለው ደረሰው:: በቅድሚያ ግን ቁመቱ ስድስት ጫማ ከአምስት ኢንች የሆነ፣ ቀይ ጸጉር ያለው አንድ ዓይናና ግዙፍ ሰው ጋር ተዋውቀን ነበር:: በቀኝ እጁ አንድ አዲስ የበሬ ጅራፍ ይዟል:: እስረኛ ቢሆንም በጠነኛ አሰቃይነቱ ዘበኞችን የሚያገለግል ባለሟል ነበር:: አርሱ እስካለ ድረስ ወታደሮች ማንኛውንም ሰው መደብደብ ከመቻላቸውም ሌላ በዚያው ሳቢያ አንድ ሰው ቢሞት ራሳቸውን ስለማያጋልጣቸው በእስተዳደሩ ዐይን ከወንጀሉ ነጻ ይሆናሉ::

በሕከምና ከፍሉ ለአጭር ጊዜ እንደ ሰነበትኩ ስለዚህ የሆው አውሬ ማወቅ ቻልኩ:: እንደዚህ የመሰለውን ተግባር የሚካሒድለት ምርጥ ነፍስ ገዳይ በመመልመሉ የወህኒ ቤቱ አዛዥ እንኳን ደስ አለህ መባል ይገባዋል:: የሥራ ልምዱ ድንጋይ ፈላጭነት ነበር:: አንድ ቀን መኖሪያው ከሆነችው አንዲት ሰሜናዊ አነስተኛ ከተማ፣ ራሱን በራሱ ለመግደልና ሚስቱንም ጭምር ለማጥፋት አንድ ሐሳብ ይመጣለታል:: ለዚህም አቅዱ የሚጠቀምበት አንድ ትልቅ ጉማጅ ፈንጅ ያዘጋጃል:: በእንቅልፍ ላይ ከነበረችው ሚስቱ አጠገብ ያጋድምና (በቤቱ ውስጥ ስድስት ቤተሰቦች ነበሩ) አንድ ሲጋራ ለኩሶ በግራ እጅ በኩል በሚስቱና በእርሱ ጭንቅላት መካከል ያለውን የፈንጅ ክር ያቀጣጥላል::

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚያሸብር ፍንዳታ አስተጋባ። ውጤቱም የሚስቱ አካላት አንድ በአንድ እየተለቀመ ሲሰበሰብ፣ የቤቱ ግማሽ ጎን ተደረመሰ። ከሦስት ልጆቹ ጋር አንዲት የሰባ ዓመት ባልቴትም ፍርስራሽ ተጭኗቸው ሞቱ። ሌሎቹ ደግሞ በየደረጃው የሞቁበል እጀታ ደርሶባቸዋል።

ራሱ ትሪኮላርም አንዲት ጣትና አውራ ጣቱ ሲቀሩ፣ በከፊል የግራ እጁን የግራ ዐይኑንና ጆሮውን አጣ። ሞንቅላቱም ላይ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገው ቁስል ደረሰበት። አሁን ግን መንጀለኝነቱ አንሶት፣ የወህኒ ቤቱ የሥነ ሥርዓት ኃላፊ ስለሆነ፣ ይህ ወራሌ ባለመታደል ከመጻፉ ውስጥ የገቡሰትን አስረኞች እየተከታተለ ደስ ያሰኘውን ድርጊት ይፈጽምባቸው ነበር።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት አምስት . . . እዞራለሁ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . እዞራለሁ። እንግዲህ በግድግዳውና በከፍሉ መዝጊያ መካከል የማያቋርጠው የመለስ ቀለስ አርምጃ ተጀመረ።

ቀን በከፍሉ ውስጥ መተኛት አይፈቀድልህም። ጧት ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ መብረቅ የመሰለ አንድ ፈሽካ ያባንንሃል። መነሣት አልጋህን ማንጠፍ፣ መታጠብ ወይም መቁም፣ አለበለዚያም ከግድግዳው ጋር ከተያያዘችው ዱካ ላይ መቀመጥ ነበረብህ። ለመጋደም አይፈቀድልህም! የቅጣት ሥርዓቱ ከፍተኛ የጠባይ ማረሚያ መሆኑ ነበር። አልጋው ወደ ግድግዳው ይታጠፍና በዚያው ይቀራል። በዚህ ዓይነት አስረኛው መጋደም ለለማይችል ይበልጥ በቀላሉ ሊጠበቅ ይችላል።

. . . አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . የዐሥራ አራት ሰዓት አርምጃ። ይህንን የማያቋርጥ እንቅስቃሴ በፍጥነት ለመለማመድ ቢያስፈልግ፣ ሚንቅላትህን አቀርቅረህ፣ እጆችህን በሰተጀርባህ አዙረህ፣ ስትራመድ በጣም ሳትፈጥን ወይም በጣም ሳተዘግይ፣ አርምጃህን በተመሳሳይ ርቀት መመጠን፣ እንዴ በግራ እግርህ በኩል በፍጥንት ከግድግዳው መጨረሻ ስትታጠፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሰተቀኝ በኩል መዞርን መማር ይኖርብሃል።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . ከጥበቃ ጣቢያዎች ይልቅ እነዚህ ክፍሎች ቀለል ያሉ ስለነበሩ፣ ከሥነ ሥርዓት ከፍሉም ሆነ ከውጭ በኩል ጩኸቶች መስማት ትችላለህ። በተጨማሪም እንደዚሁ በማዶ ካሉ ቀበሌዎችም ጭምር። በምሽት ወቅት ሠራተኞች ቢራ በመቀማመስ ደስ ብሏቸው እያቈጩና እየዘፈኑ ከሥራ ወደ ቤታቸው ሲጓዙ ደምፃቸውን መስማት ትችላለህ።

አንድ ስጦታ አግኝቼ ነበር። ይኸውም መስኮቴን በሸፈነው ጣውላ ቀዳዳ በኩል አንዳንድ ትላልቅ ዛፎችና በበረዶ የተሸፈነውን ቀበሌ፣ በሙሉዋ ጨረቃ አማካይነት ለማየት መቻል ነው። የሚመስለው ልክ አንደ አንድ የልደት በዓል ካርድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር። በነፋሱ ንቅናቄ ዛፎች የተሸከሙትን በረዶ ስላራገፉ በነጩ ላይ ጥቁር ጥላ ጥሎበታል። የጭና በዓል ነበር። በወሀኒ ቤቱ ውስጥ እንኳ በከፊል የልደት በዓል ተከብሯል። በሽግግር ላይ ላለነው አስረኞች አስተዳደሩ አንድ አስተያየት አድርጎ ነበር። ሁለት ቁራጭ ቸኮሌቶች ለመግዛት ተፈቀደልን። የምለው ሁለት ቁራጮች እንጅ፣ ሶስት ጉማጅች አንዳይመስላችሁ። በእነዚህ ሁለት የአውገርቤል ቁራጭ ቸኮሌቶች ነበር 1931 የዘመን መለወጫ ዋዜማየን ያከበርኩት።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . የሕጉ መጥበቅ ልክ እንደሰዓት ፔንዱለም አድርጎኝ ነበር። በከፍሉ ውስጥ የማደርገው የወደኋላና ወደፊት ምልልስ በአጠቃላይ ሁለመናየን አስተካክሎታል። የሚከናወነው በሒሳብ ስሌት ነበር። ምንም ነገር፣ በክፍሌ ውስጥ የሚቀረኝ ባጠቃላይ ምንም ነገር አልነበረም። አስረኛ መበሳጨት የለበትም። በመስኮቱ ቀዳዳ ሳጮልቅ ብያዝ ኖሮ ከባድ ቅጣት ይደርስብኝ ነበር። በእርግጥም ለእነርሱ እኔ አንድ የቁም ሬሣ ሰለሆንኩ ትከከል ናቸው። በየትኛው መብቱ ነው ተፈጥሮን በጨረፍታ በማየት የምደሰተው?

አንድ ጥቁር ቀጭን መስመር የተጋደመባት ወሃ ሰማያዊ ቢራቢሮ ውልብ ብላ ስታልፍ፣ አንዲት ንብ ደግሞ ከመስኮቱ ሳትርቅ ትጮሃለች። እነዚህ ጥቃቅን ነፍሳት ምን እየፈለጉ ኖሯል? ምናልባት ካልቀዘቀዛቸው በስተቀር በክረምቱ ፀሐይ ሰከረው ወደ ወሀኒ ቤት መግባት ፈልገው ነው። በክረምቱ የአንዲት ቢራቢሮ መታየት ልክ ከሞት በኋላ ሕይወት እንደዘራች የሚቆጠር ነው። ለምን አልሞተችም ነበር? ንቢቱስ ቀፎዋን ለምን ለቀቀች? ምን የመሰሉ የሞኝ ደፋሮች ቢሆኑ ነው ወደ እዚህ የመጡ!

ትሪቡላር የወጣለት አረመኔ ነበር። በመካከላችን አንድ የሆነ ነገር ይፈጠራል የሚል ስሜት አደረብኝ፣ ትከከል ነበርኩ። እነዚያ ማራኪ ነፍሳት በንበኙኝ ማግሥት ታመምኩ። ልቋቋመውም ጨርሶ ተሳነኝ። በብቸኝነት ታፍኜ ስለነበር ፣ ድምፅ ይሁን እንጂ የቁጣም ድምፅ ቢሆን እንኳ ለመስማትና አንድ ፊት ለማየት ፈለግኩ።

ራቱቴን እንደ ሆንኩ እንደ በረዶ በሚቀዘቅዘው መተላለፊያ አፍንጫዬን ለግድግዳው ትይዩ አድርጌ ዶክተሩን ለማየት በሰልፍ ተራቸውን ከሚጠባበቁት ስምንት ሰዎች ወስጥ ከመጨረሻ ሁለተኛ በመሆን ቆሜያለሁ። ሰው ለማየት መፈለጌ . . . ግሩም ሆኖ ተሣካልኝ። «ባለመዶሻው ሰው» ከተባለው ከጁሎ ጋር ድምፄን አጥፍቼ በምነጋገርበት ወቅት ባለሚሉ ደርሶበን ማጅራቴን በአንድ ቡጢ ሲወግረኝ፣ ሕሊናዬን ልስት ምንም አልቀረኝ ነበር። ሲመጣ አይቼው ስላልነበር በምወድቅበት ጊዜ አፍንጫዬ ከግድግዳው ጋር ተላተመ። ደሜ ፊን ብሎ ሲወጣ ብድግ አልኩና ግብግብ ለመግጠም ተንጎዳጎድኩ። ግዙፉም የሚፈልገው ይህንኑ ነበር። መልሶ ዘረረኝ። አንድ ጠንካራ ጡጫ ሆዴ ላይ አቀመሰኝና፣ ከዚያም በበሬ ጅራቱ ይሞሸልቀኝ ጀመር። ይህም ለጁሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

የማይቋቋመው ነገር ሆነበት። ዘልሎ ተከመረበትና የጠፈ ትግል ተጀመረ። የሚደበደበው ጁሎ እስከሆነ ድረስ ዘበኞቹ ምንም ላይነቃነቁ ቆሙ። ስለ እኔ ማንም ምንም ያስታወሰ አልነበረም። አንድ ዐይነት መሣሪያ ለመፈለግ አካባቢየን አማተርኩ። በኮሪደሩ የሚደረገውን ሁኔታ ለማየት ዶክተሩ በቢሮ ወንበሩ ላይ እንዳለ ወደፊት ሰገግ ሲል ድንገት አየሁት። ይህ በዚህ እንዳለ፣ ከሚፈላ ውሃ ላይ፣ አንድ ግጣም ከፍት ከድን ሲል ልብ አልኩና ተመለከትኩ። በከሰሉ ፈርኔሎ ላይ ትልቅ ብረት ድስት የተጣደው የዶክተሩን ከፍል ለማሞቅ ነበር በእንሱሎቱ ። የብረት ድስቱን ጀሮዎች ያዝኩና ቢያቃጥለኝም ሳልለቅ በፍጥነት አንሥቼ ከሚፈላው ውሃ ጋር ባለሚሊ ፊት ላይ አሳረፍኩበት። ከጁሎ ጋር በመታገል ላይ ስለነበር እኔን አላየኝም። አንድ የሥቃይ ዋይታ አስተጋባ። በሚገባ አግኝቼው ነበር። ሦስቱን የሱፍ ሹራቦቹን አወልቃለሁ ብሎ ሲታገል ወለሉ ላይ ተንከባለለ። ሦስተኛው ላይ ሲደርስ ቆዳው ከሹራቡ ጋር አብሮ ተነሣ። የሹራቡ አንገት ጠባብ ስለነበር በጭንቅላቱ በኩል አወልቃለሁ ብሎ ሲታገል የደረቱ፣ የጉንጩና በከፊል የአንገቱ ቆዳ ከሱፉ ጋር ተጣብቆ ተነሣ። ብቸኛዋ ዐይኑም ስለ ተቀቀለች ያለጥርጥር ታውሮ ነበር። በመጨረሻ በኃፍረት ተውጠ፤ በደም ተለውሶና አካላቱ ጥሬ ሥጋ መስሎ በእግሩ ሲቆም፣ ከፍርንትቱ ላይ አንድ ኢደገኛ ቡጢ ለመስጠት ጁሎ ዕድል ገጠመው። ተኮራመተና በእፉ አረፉ እየደፈቀ ያስታውከ ጀመረ። የሚገባውን አግኝቷል። እኛንም የሚጠበቁን ቅጣት ሩቅ አይሆንም። ትዕይንቱን ሲመለከቱ የነበሩት ሁለት ዘበኞች እኛን ለመደብደብ በጣም ፈርተዋል። ለእርዳታ ተጣሩ። ከየአቅጣጫው ተሰበሰቡና በላያችን ላይ ዱላ እንደ በረዶ አዘነመቡብን። በመጀመሪያው ድብደባ ሕሊናዬን ለመሳት ዕድለኛ ስለሆንኩ ምቶቹ አልተሰሙኝም።

ሕሊናዬን ሳውቅ ከምድር በታች ሁለት ወለል ገቦ ብሎ በውሃ በተጥለቀለቀ እንድ ጨለማ ግንብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ራቱቴን ተጋድሜያለሁ። ቀስ በቀስ ስሜቴን ሳውቅ ቁስሎቼም ይሰመኝ ጀመር። ያስታያሉ። ከጭንቅላቴ ላይ ቢያንስ ዐሥራ ሁለት አብጠቶች ነበሩ። ስንት ሰዓት ይሆን? ማወቅ አልቻልኩም። እዚህ ቦታ ቀንም ሆነ ሌሊት የሚባል የለም። በግድግዳው ላይ አንድ ቁርቁራ ሰማሁ። የመጣው ከሩቅ አካባቢ ነበር።

ድም፣ ድም . . . ኪል፣ ኪል፣ ኪል . . . ቁርቁራዎቹ «የስልክ» አደዋወል ይመስላሉ። በመስመር ላይ ነኝ ለማለት ከፈለግኩ ሁለት ጊዜ መቆርቆር ነበረብኝ። እሺ ልቆርቁር። ግን ለምን? በጨለማ ውስጥ አንድም ነገር ማየት አልቻልኩም። ድምፁ ልቆርቁር። ግን ለምን? በጨለማ ውስጥ አንድም ነገር ማየት አልቻልኩም። ድምፁ ማስተጋባት ስለማይችል ቡጢዎችም በቂ አልነበሩም። ትንሽ ብርሃን ስለነበረ፣ መዝጊያው መሆን አለበት ብዬ ወደ ገመትኩት አካባቢ ቀረብ አልኩ። ከፍርግርጉ ጭሚ መዝጊያው መሆን አለበት ብዬ ወደ ገመትኩት አካባቢ ቀረብ አልኩ። ከፍርግርጉ ጭሚ ጋር ተላተምኩ። በዳበሳ እንደ ደረስኩበት የጨለማው ግንብ መዝጊያ የሚገኘው ከዚያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሦስት ጫማ ባሻገር ስለ ነበር፣ ቋሚ ፍርግርጉ ወደ አዚያ ለመድረስ እንደ ከለከለኝ ገመትኩ። የዚህም ቀያሽ ዓላማ ወደ አንድ አደገኛ አስረኛ ከፍል ውስጥ አንድ ሰው ቢገባ፣ አስረኛው የሚገኘው በወጥመድ ውስጥ ስለሆነ ሰውየውን ማግኘት እንዳይችል ነበር። ምንም ጉዳት ሳያደርሰብህ ልትናገር፣ ውሃ ልትረጭበት ፣ ምግብ በላዩ ላይ ልትወረውርበትና ልትሰድበው ትችላለህ። በሌላው አንጻር ደግሞ ወደ እርሱ ለመጠጋት ቋሚ ፍርግርጉን መክፈት ስለሚኖርብህ፣ ራስህን ለአደጋ ሳታጋልጥ ልትመታው አትችልም።

ቁርቁራው ቀጠለ። ከእኔ ጋር ለመገናኘት የሚታገለው ማን ይሆን? ሰውየው በእርግጥ አንድ መልስ ይጠበቃል። ከፍተኛ ጥረት በማድረግም ላይ ነበር። በጨለማው ውስጥ በመዘዋወር ላይ እንዳለሁ፣ ከብና ጠንካራ የሆነ አንድ ነገር እግሬን እንሸራትቶኝ በፊቴ ተደፍቼ ወደቅኩ። አንዲት የእንጨት ማንኪያ ነበረች። ያዝኳትና ለመመለስ ተዘጋጀሁ። ጆሮዬን ከኘሩግሶው ላይ ...ኖረ አጠባበቃለሁ። ድም-ድም-ድም-ድም- ፓንግ። ቆመ። ድም-ድም አድርጌ አ...ኑ። አንቢህ ሁለት ቁርቁራዎች፣ «ቀጥል እየሰማሁ ነው» ለማለት ነበር። ቁርቁራው ተጀመረ። ድም-ድም-ድም የንግግሮቹ ፊደሎች በፍጥነት ይሸጎደጎዱ ጀመር። ከኤ ይጀምርና በፒ ፌዷል ያቆማል። አንድ ኃይለኛ ፓንግ ቆረቆርኩ። ይህም የፒ ፊደልን እንዲመዘግብ ልነግረው ነበር። ከዚያም አንድ ኤ፣ አንድ ፒ፣ አንድ አይ ወዘተ ...

«እንዴት ይዘሃል ፓፒ? በእርግጥ ቻልከው? እኔ እ...ደኛው ኒንዴ ተሰበሯል» ይለኝ ነበር። ለካ ጁሎ ኖሯል።

አደጋውን ዘንግተን ከሁለት ሰዓት በላይ በስልካችን አወራን። በተመስጦ ተውጠን ነበር። ጭንቅላቴ በሙት በአ...ከት ቢሸፈንም ቅሉ፣ በግልጽ እንዳልተፈነከትኩና ምንም እንዳልተሰበርኩ ገርኩት። እግሬን ይዘው ቁልቁል በደረጃው ሲያወርዱኝና ጭንቅላቴም ከእያነዳንዱ ደረጃ ላይ ሲነጥር ማየቱን ነገረኝ። እርሱ ፍጹም ሕሊናውን አልሳተም ነበር። ትሪቡላር ከፉኛ መቃጠሉና በአሥጊ ሁኔታ ላይ መሆኑ ሰጊዜውም ቢሆን በመጠኑ አሳስቦት ነበር።

ሦስት ፈጣን ቁርቁራዎች ችግር ሊፈጠር መቃረቡን አስጠነቀቁኝ። እኔም አቆምኩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መዝጊያው ተከፈተና አንድ ሰው ሲያጓራ ሰማሁ።

«ወደ ኋላ ተመለስ፣ አንተ ዲቃላ! ከከፍሉ ጥግ ሒድና በተጠንቀቅ ቁይ» አዲሱ ባለሟል ነበር።

«ስሜ ባቶን ነው። ስሜ ከሙያየ ጋር ይስማማል» አለና ጨለማው ግንብ ውስጥ እርቃነ ሥጋዬን እንደ ቆምኩ አንድ ትልቅ ፋኖስ በላዬ ላይ አበራብኝ።»

«የምትደርበው ነገር ያውልህ። ግን እንዳትንቀሳቀስ። ዳቦና ውሃም

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሽውልህ። ሁሉንም በአንድ ጊዜ እንዳትበላ፣ ለሚቀጥሉት ሐያ አራት ሰዓቶች የምታገኘው ይህንኑ ብቻ ነው።»

አንድ የመጓጎር ጩኸት አሰማና ከዚያም ፋኖሱን ወደ ራሱ ፊት ቀረብ አደረገው። ፈገግታ ያሳይ እንደነበር ተመለከትኩት። የክፉት አልነበረም። ከከንፈሮቹ ላይ እንደኛ ጣቱን አስቀመጠና ትቶልኝ ከነበሩት ዕቃዎች ላይ ዐይኑን ተከለ። በኮሪደሩ ውስጥ አንድ ዘበኛ ኖሮ ነው እንጂ፣ ጠላቴ አለመሆኑን እንዳውቅለት ሊገልጽልኝ ፈልጎ ነበር።

በእርግጥም ጠላቴ አልነበረም። በዳቦው ውስጥ አንድ ትልቅ ጉማጅ የተቀቀለ ሥጋና ከሱሪዎቹ ኪስ ደግሞ - ይገርማል፣ ትላልቅ ጓጎች! አንድ ፓኬት ሲጃራና አንድ ማቀጣጠያ አገኘሁ። እዚህ እነዚህን የመሰሉ ስጦታዎች ዋጋቸው በሚሊዮን ነበር። ሁለት ሸሚዞችና ቁርጭምጭሚቴ የሚደርስ ከሱፍ የተሠራ አንድ የውስጥ ፒጃማም ሰጠኝ። ባቶንን ፍጹም አልረሳውም። ይህን ያደረገው ትሪቡላርን ስላስወገድኩለት ወረታ ሊመልስልኝ ነበር። ከግጭቱ በፊት ረዳት ባለሟል ብቻ ነበር። አሁን ምስጋና ለእኔ ይድረሰኝና ሙሉውን ማዕረግ ይዟል።

«የሰልኩን» ቁርቆራ አድራጊ ለማግኘት ታላቅ ትዕግሥት ስለሚጠይቅና ዘበኞቹም በጣም ሰነፎች በመሆናቸው ሊደርስበት የሚችለው ባለሟሉ ብቻ ስለነበር፣ ጁሎና እኔ ልባችን ያሰኘውን ያህል እንደሰትበታለን። በሦስት ወይም በአራት ወራት ውስጥ ገዘ የምንጅምር መሆናችንን ከእርሱ ተረዳሁ።

ከሁለት ቀን በኋላ ከጨለማው ግንብ ወጣንና እያንዳንዳችን በሁለት ዘበኞች ታጅበን ወደ አዛገቦቹ ቢሮ ተወሰድን። ሦስት ሰዎች በመዝጊያው ትይዩ ከሚገኝ አንድ ጠረጴዛ ኋላ ተቀምጠዋል፣ አንድ ዐይነት ችሎት ይመስላል። አዛዙ ሰብሳቢ ዳኛ በመምሰል፣ በመካከል፣ ረዳት አዛገቦና የዘበኞቹ ኃላፊ እንደ ረዳት ዳኞች ሆነው ተሠይመዋል።

«አህሳ፣ ወዳጆቼ እንግዲህ ለዚህ በቃችሁ! ስለራሳችሁ የምታስረዱት አላቸሁ?»

ምናልባት የብርድ ሕመም ሳይዘው አልቀረም ይመስለኛል፣ ጁሎ ዐይኖቹ አብጠው ፊቱ በጣም ገርጥቶ ነበር። ከንዱን ከተሰበረ አሁን ሦስት ቀን ሆኖታል። በከፍተኛ ሥቃይ ላይ መሆን አለበት። በጣም ቀስ ብሎ፣

«ከንዴን ተሰብሬያለሁ» አለ።

«ምስህን ነው ያገኘኸው፣ ሰዎችን ላለመደብደብ ይህ ትምህርት ይሆንሃል። እዚህ ሲመጣ ዶክተሩ ያይልሃል። ይህም በሳምንት ውስጥ እንደሚደረግልህ ተስፋ አለኝ። ምናልባት ሥቃዩ አንዳንድ ነገር ስለሚያስተምርህ መቆየቱ ለአንተ ጥሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይሆናል። በተለይ እንደ አንተ የመሰለ ጠባይ ላለው አንድ ዶክተር ባስቸኳይ መቸም አትጠበቅም። ትጠብቃለህ እንዴ? ስለሆነም ጊዜ አግኝቶ እስኪመጣ ድረስ ጠብቅ፣ ከዚያም ያከምሃል። ይህንንም ስል ያለምንም ተጨማሪ መግለጫ ሁለታችሁንም ወደ ጨለማው ግንብ ከመላክ አያግደኝም።»

የጆሎ ዐይን ከእኔ ጋር ግጥምግም ሲል፣ «ይህ የተቀናጣ መኳንንት የሌሎችን ሰዎች ሕይወት ለማፈን አስደናቂ ዘዴ አለው» የሚል ይመስል ነበር።

ወደ አዛገቦ ዘወር አልኩና ትኩር ብየ ተመለከትኩት።

ለመናገር የፈለግኩ መስሎት፣ «አንተ ለብያኔዎቼ ደንታ የለህም? አትቀበላቸውም?» አለ።

«አይደለም ጌታዬ፣ የሚሰማኝ ድኑ ፍላጎት በቀጥታ እፊትህ ላይ መትፋት ነው። ግን አላደርገውም። ምክንያቱም ምራቄን ለማቆሸሽ አልፈልግም።»

ከመግረሙ የተነሣ ፊቱ አመድ መሰለና ምን እንደሚሠራ ግራ ገባው። ግን የወታደሮቹ ታላፊ ዐውቋል። ዘበኞቹን ጠራ።

«አንጠልጥላችሁ ውሰዱና ደሀና አድርጋችሁ ተንከባከቡት! በአንድ ሰዓት ውስጥ እየዳኸ ሲሔድ ለማየት እጠብቃለሁ።»

«አንክትክቱን እናወጣዋለን!»

ጫማዎቼን በሁለቱም በኩለ ማለት ከላይና ከውስጥ በምላሱ አስጠርገዋለሁ። የሥራውን ስጡት። ሁለመናው የእናንተው ነው።»

ሁለት ዘበኞች የግራ ክንዴን፣ ሌሎች ሁለት ደግሞ የቀኜን ጨመደዱኝ። ክንዶቼን በጀርባዬ አዙረው እጆቼ የትከሻዎቼን መጋጠሚያዎች እስኪነኩ ድረስ ጠመዘዙና ፊቴን ወደ መሬት ደፍተው አስተኙኝ። በእጅ ካቴና ታሰርኩና የግራ እጄ መካከለኛ ጣት ከቀኝ አውራ ጣቴ ጋር በመወጠሪያ ቪቴ አጣበቁቸው። ከዚያም የዘበኞቹ ታላፊ ልክ እንደ አንድ አውሬ ጸጉሬን ጨምድዶ ወደላይ ሳበኝ።

ወደ ተጨማሪ ሐተታ መግባት አያሻም። ማወቅ ያለባችሁ ብቻ ለዐሥራ አንድ ቀናት ካቴናዎቹን እንዳጠለቅኩ የፊጥኝ እንደ ታሠርኩ መቆየቴን ነው፣ ነፍሴን ለባቶን አደራ ሰጥቻለሁ። በየቀኑ የተለመደውን ቁራጭ ዳቦዎች ይወረውርልኛል። ግን በእጆቼ ስለማልጠቀም ልመገባቸው አልቻልኩም። በጭንቅላቴ ወደ ቋሚ ፍርግርጉ እየገፋሁ ባጋጫቸውም እንኳ አይሰበሩም። ግን ባቶን በሕይወት ለመቆየት የሚያስችሉኝ ተጨማሪ ቁርጥራጭ ዳቦዎች ይወረውርልኝ ነበር። በእግሮቼ ትናንሽ ቁልሎች አበጅና ከዚያም በሆዴ ተንጋልዬ ልክ እንደ ውሻ እበላቸዋለሁ። ቅንጣት ያህል እንኳ እንዳያመልጠኝ እያንዳንዷን ቁራጭ በሚገባ አኝካለሁ።

በዐሥራ ሁለተኛው ቀን የእጅ ካቴናዎቼን አወለቁልኝ። ብረቱ ሥጋዬን ሰርስሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገበቶ ስለነበር በሚሸት ሥጋ ተሸፍኗል። በተለይ ከሥቃዩ የተነሣ ተዳከምኩ። ይህም የዘበኞቹን ኃላፊ አስፈራው። መለስ ሲልልኝ ወደ ሕክምና ክፍል ተወሰድኩና በተፈላ ውሃ ታጠብኩ። የሕክምና ሠራተኛው የቲታነስ መከላከያ መርፌ እንዲሰጠኝ ደጋግሞ አሳሰበ። ከንዶቹ በድን ስለሆኑ ወደ ተለመደው አቅጣጫቸው መመለስ አልቻሉም። ለግማሽ ሰዓት በቅባት ከታሸሁ በኋላ ነበር በጎንና ጎን ቁልቁል ልዘረጋቸው የቻልኩት።

ወደ ክፍሉ እንደ ተመለስኩ፣ የዘበኞቹ ኃላፊ ዐሥራ አንዶቹን ቁራጭ ዳቦዎች ተመለከተና፣ «ግብግቦ ልታደርግ ነው እንዴ! የሚገርም ነው፣ ግን ከዐሥራ አንድ ቀን ጾም በኋላም በጣም የከሣህ አትመስልም . . .» አለ።

«በዙ ውሃ አጠጣለሁ ጌታዬ።»

«አሃ፣ ለዚህ ነዋ! ገባኝ። አሁን በብዛት መበላት ይገባሃል። ስለዚህ ጥንካሬህን መልሰህ ታገኛለህ» አለኝና ሔደ።

ሞኙ፣ ዐሥራ አንድ ቀን መሉ ምንም ነገሮ ስላልበላሁ፣ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ጠራርጌ በመብላት በቁንጣን እንድሞትለት አስቦ ነበር።

ወደ ምሽቱ አቅራቢያ ባቡን ጥቂት ትምባሆና የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀት ሸነጠልኝ። ደጋግሜ በማጤስ ጢሱን በአንድ ያማይሠራ የመቁት ማስተላለፊያ ቱቦ ውስጥ አቦንነው ጀመር። ቢያንስ ለአንድ ተግባር ተጠቀምኩበት ማለት ነው። ትንሽ እንደቆየሁ ጹሎን ጠራሁት። እንደዚሁ አርሱም ለዐሥራ አንድ ቀን ያልበላሁ መስሎት ረጋ እንድል መከረኝ። ይሁንና አንዳንድ አሳባቂዎች ሮልአክቱን ያጋልጣሉ በሚል ፍርሃት ዕውነቱን ልነግረው አልደፈርኩም። በቆርቆሮ ቱቦ የተደበቀውን ፕንዙብ በጥንቃቄ መያዜንም ጹሎ በየዋህነት ጠየቀኝ።

አዎ፣ ይኖት ነበር፣ ግን እንደዚያ በማድረግ ያሳለፍኩትን ሥቃይ መግለጽ አልፈለግሁም። ፊንጢጣዬ ቆስሎ አያሰቃየኝ ነበር።

ከሦስት ሳምንት በኋላ ከከፍላችን ወጣን። ጉዳዩ ለምን ኖሯል? በሣሙናና ሙቅ ውሃ ገላችንን ተዝናንተን ታጠብን። ወደ መኖር ዓለም እንደገና መመለሴ ለራሴው ተሰማኝ። ጹሎ እንደ ሕፃን ልጅ ፈነደቀ፣ ፒየሮ ለፋም ፊቱ በደስታ አንጸባረቀ።

ከጨለማው ግንብ ስንወጣ የመጀመሪያ ጊዜያችን ስለነበር፣ ይህ የሚካሔደው ጉዳይ ለምን እንደሆነ ለማወቅ መንገድ አጣን። ጸጉር አስተካካዩ እንዲገልጽልኝ ሹክ ብለው መልስ ሊሰጠኝ አልፈለገም።

አስቀያሚ ፊት ያለው አንድ የማላውቀው አስረኛ፣ «እንደሚመስለኝ ከጨለማው ግንብ መግላግላችን ነው። ተቆጣጣሪዎች ይመጡብናል ብለው ፈርተው ይሆናል። ዋናው ቁም ነገር በሕይወት መገኘታችን ነው» አለ።

አያንዳንዳችን ወደ ተለመደው ክፍላችን ተወሰድን። ከሰዓት በኋላ በዐርባ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሦስተኛው ቀን ከተሰጠኝ የመጀመሪያው ትኩስ ሾርባዬ ውስጥ አንድ ትንሽ ቁራጭ እንጨት አገኘሁ። ከሥሯ በኩል፣ «በስምንት ቀን ውስጥ ጉዞ እንጀምራለን፣ ነገ ከትባት ይሰጣል» የሚል አነበብኩ።

ይህን የላከው ማን ይሆን? ወሬውን እንዲነግረን የፈለገ አንድ ቅን አስረኛ መሆን አለበት። አንዳችን ካወቅን ሁሉም እንደሚያውቁ ጉበቶት ነበር። መልዕክቱ ወደ እኔ መምጣቱም በእርግጥ ጥሩ ዕድል ሆነ።

ለጂሎ ባስቸኳይ በስልክ አስታወቅኩ። «ዜናውን ለሌላው አስተላልፍ።»

ሌሊቱን ሙሉ ስልኩ ሲዘዋወር አስማለሁ። መልዕክቱን አንድ ጊዜ ከሰጠሁ በኋላ እኔ አቆምኩ። አልጋየ በጣም ተመችቶኝ ስለነበር፣ ጣጣ ውስጥ ለመግባት አልፈለግኩም። ሌላ ቢቀር በዚህች ቀን እንኳ ወደ ጨለማው ግንብ ከሚመለሱት ጋር ለመጓዝ ተካፋይ መሆን አልፈለግኩም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለተኛ ማስታወሻ

ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት በመንገድ ላይ፡-
ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ

ወደ ማታ ላይ፣ ባቶን ሦስት ሲጋራዎችና፣ «ፓፒዮ፣ ከእኔ የደስታ ትዝታዎች ጋር ከዚህ እንደምትሔድ ዐውቃለሁ። ባለሟል ተብዬ ይሆናል፣ ግን በአስረኞች ላይ በተቻለኝ ሁሉ አነስተኛ ጉዳት ለመፈጸም እሞክራለሁ። ሥራውን የተቀበልኩት ዘጠኝ ልጆች ስላሉኝ በፍጥነት ለመፈታት ስለቸኮልኩ ነው። በጣም የባሰ ጭካኔ ውስጥ ሳልገባ ምሕረት ለማግኘት እንድቻል እጥራለሁ። ደህና ሁን። መልካም ዕድል። ኮንቮዩ ከነገ ወዲያ ይነሣል» የምትል መልዕክት ያዘለች አንዲት ቁራጭ ማስታወሻ አሾለከልኝ።

በሚቀጥለው ቀን በሠላሳ ቡድን እየሆንን በሥነ ሥርዓት ከፍሉ ኮሪደር ውስጥ ተሰበሰብን። ለበሽታዎች መከላከያ ክትባት የሚያደርጉ የሕክምና ባለሙያዎች ከካዮን መጥተው ነበር። ለአያንዳንዳችን ሦስት ክትባቶችና ሁለት ሊትር ወተት ተሰጠን። ዴጋ እኔ አጠገብ ቆሟል። አንድ ጊዜ ከተከተብን በኋላ ተመልሰን ወደ ጨለማው ግንብ እንደማንገባ ስላወቅን የፀጥታ ማከበሩን ሕግ ጨርሶ ረሳነው። ዘበኞቹ እያዩን ድምፃችንን ዝቅ አድርገን ስናወራም፣ ከከተማ በመጡት የሕክምና ሰዎች ፊት ምንም ነገር ለማለት አልደፈሩም።

ዴጋ ሐሳብ ገብቶት ነበር። «ሁላችንንም በአንድ ጊዜ ለመውሰድ የሚበቃ ግልጥ ፉርጎዎች ያገኙ ይሆን? ሲል ጠየቀኝ።

«እንዴት እንደሚያደርጉ አላውቅም።»

«ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ በጣም ሩቅ ነው፣ ስለዚህ በቀን ስድሳ ሰዎች እንኳ ቢያጓጉዙ ዐሥር ቀን ይወስዳል። እዚህ ብቻ ስድስት ሙዶ ያህል እንሆናለን።»

«ዋናው ነገር መከተባችን ነው። ይህም ማለት በመዝገብ ላይ ስለገባን በፍጥነት ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት እንሔዳለን። ደስ ይበለን ዴጋ፣ በአዲስ ሽግግር ላይ ነን። በአንተ ስለምተማመን አንተም በእኔ መተማመን ትችላለህ።»

ትኩር ብሎ ተመለከተኝና ዐይኖቹ በደስታ በሩ። እጁን በከንፈሬ ላይ ጣል አደረገና፣ «ፓፒ፣ በሕይወትም በሞትም» አለ። በሽፍኑ ካሚወን ውስጥ ተጨናንቀን ከመታፈናችን በስተቀር ስለ ኮንቮዩ መዘርዘሩ ዋጋ የለውም። ትንሽ አየር ለማስገባትም ሆነ መዝጊያዎቹን እንኳ ገርበብ አድርጎ ለመከፈት ዘበኞቹ አሻፈረን አሉ። ላ-ሮሼል ሰንደርሰ ሁለት ሰዎች በአየር ማጣት ምክንያት ሞተው ነበር።

ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ፣ ደሴት ሰለ ነበረችና ባሕሩን ለማቋረጥ አንድ ጀልባ

t.me/OLDBOOKSPDF

መያዣ ስለሚኖርብን፣ በወደቡ ዳር የሚመላለሱት ሰዎች የምስኪኖቹን አስከሬን በማየት ታዛቢዎች ሆኑ። በከፋት አልተመለከቱንም። መጨረሻ ላይ ሲያስረክቡን የሞቱትንም ያሉትንም ጭምር ሰለ ነበር፣ ፖሊሶቹ አስከሬኖቹን ከእኛ ጋር በጀልባው ላይ ጫኗቸው።

መሻገሩም ረጅም ጊዜ አልወሰደም፣ ይሁንና ትንሽ ንውሕ አየር ለመሳብ ዕድል አጋጠመን። «ማምለጥ ማምለጥ ይለኛል» ብለው ዱጋ ፈገግ አለ። አጠገባችን የቆመው ጁሎም እንደዚህ አለ፦

«አዎ፣ በእርግጥም ይዳዳኛል። አብረን ለመሆን እንሞክር። በቅዱስ ማርቲን ዶ-ሬ ለእያንዳንዱ ክፍል ፀሥር አሥረኞችን በመደዳው እያስነሱ ይወስዳሉ።»

ጁሎ ተሳስቶ ነበር። በምንደርስበት ወቅት አርሱንና ሁለት ሌሎች ሰዎች ጠርተው ለብቻ አስቀመጧቸው። ሦስቱም ከቅኝ ግዛት አሲታቂ ወህኒ ቤት ቀደም ሲል ያመለጡ አስረኞች ስለሆኑ፣ ተይዘው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ፈረንሣይ ተመልሰው መላካቸው ነበር።

እኛ ከፍል ውስጥ ያለነው የፀሥር ሰዎች ቡድን የቆይታ ኑሮን ቀጠልን። ማውራትና ማጨስ ተፈቅዶልን ነበር፣ በጥሩ ሁኔታም ይመግቡናል። የምንፈራው ቢኖር በቆርቆሮ ቱቦ ለተደበቀው ገንዘብ ነበር። ያለ አንድ ምክንያት ድንገት አውልቅ ትባልና በጥበቅ ልትፈተሽ ትችላለህ። በመጀመሪያ እያንዳንዷ በስንዝር የምትለካ አካላትህ እስከ ውስጥ አግርህ ድረስ፣ ከዚያም ልብሶችህ፣ በመጨረሻም «ልበስ» ትባልና ወደ ክፍልህ ትመለሳለህ።

ኑሯችን እንደዚያ ነበር፣ መታሠሪያ ክፍሉ፣ የምግብ አዳራሹ፣ ለረጅም ሰዓት በሰልፍ እየሆንን የምናሳልፍበት መስክ። አንድ፣ ሁለት፣ አንድ፣ ሁለት፣ አንድ፣ ሁለት ... በአንድ መቶ ሃምሳ ቡድን እንሰለፋለን። ሰልፉ ረጅም ስለነበረ የአንጨት ጫማዎቻችን ይንኳኳሉ። ፀጥታ ግዴታ ነበር። ከዚያ «ሰልፉ ተበትኗል» ይባልና ሁሉም በየቢጤው በቡድን እየተከፋፈለ መሬት ላይ ይቀመጣል። በመጀመሪያ ከመላው ኮርሲካ፣ ማርሲይ፣ ቱሎስ፣ ብሪታኒ፣ ፓሪስ ወዘተ ... ዕውቅ የሆኑት አራዳዎች ይሰበሰባሉ። ከአርዴክም ቢሆን አንድ ሰው ነበር፣ አርሱም እኔ ነኝ። ለአርዴክ ተወከዬ መናገር ካስፈለገን፣ በዚያ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰዎች የሚገኙበት ኮንቮይ ውስጥ ያለነው ሚስቱን ገድሎ የነበረ አንድ ፖሊስና እኔ፣ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበርን። ለማጠቃለል ያህል፣ የአርዴክ ሰዎች ጥሩ ሰዎች ናቸው ማለት ነው። ከአራዳዎቹ አባሎች ይልቅ ሌሎቹ ቡድኖች ወደ ቅኝ ግዛት አሲታቂ ወህኒ ቤት ለመሔድ ይበልጥ ፈቃደኞች ነበሩ። እነዚያ የቆይታ ቀኖች «የጥናት ወቅቶች» እየተባሉ ይጠራሉ። በዕርግጥም ነበሩ፣ በጥበቅ እንጠበቃለን።

አንድ ጊዜ ከለዓት በኋላ ፀሐይ ለመሞቅ ተቀምጬ እንዳለሁ፣ አንድ ሰው ወደ እኔ መጣ። መነጽር ያደረገ፣ አጭርና ክሳሳ ነበር። ላስታውሰው ሞከርኩ፣ ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዩኒፎርማችን አንጻር ችግር ሆነብኝ።

«ፓፒዮ አንተ ነህ?»

«አዎ፣ እኔ ነኝ። ምን ትፈልጋለህ?»

«ወደ መጸዳጃ ቤት ና» አለኝና ሔደ።

«ይኸ ኮርሲካዊ መሳይ ነው፣ አንድ የተራራ ወንበዴ ይመስላል። ምን ይፈልጋል?» አለ ዴጋ።

«እኔም ለመረዳት የምፈልገው ይህንኑ ነው።» ከግቢው መካከል ወደሚገኘው መጸዳጃ ቤት ሔድኩና የምሽና መሰልኩ። ሰውየውም ከጎኔ ቆመና ወደ እኔ ሳይመለከት፣ «የፓስካል ማትራስ አማች ነኝ። ሊጎበኘኝ እንደመጣ፣ እርዳታ ካስፈለገኝ ወደ አንተ መጥቼ ስሙን እንዳነሣልህ ነግሮኛል» አለ።

«አዎ፣ ፓስካል ጓደኛዬ ነው። ምን ትፈልጋለህ?»

«ከአሁን ወዲያ የጎንዙብ መደበቂያ ቱቦዮን ለመያዝ አልቻልኩም። ተቅማጥ አሞኛል። ዘበኞቹ ያገኙብኛል፣ ወይም አንድ ሰው ይሰርቃታል ብዬ ፈርቻለሁ፣ ማንን እንደማምን አላወቅኩም፣ አባከህ ፓፒዮ፣ ለትንሽ ቀን አንተ ያዝልኝ» አለና ከእኔ የበለጠ አንድ ትልቅ የጎንዙብ መደበቂያ ቱቦ አሳየኝ። ይህን ብሎ የጠየቀኝ ለማውጣጣት ይሆናል ብዬ ፈርቼ ነበር። ሁለቱንም ለመያዝ አልችልም ብየ ብነግረው ደግሞ ሊያውቅብኝ ሆነ።

ስለዚህ ለስለስ ብዬ፣ «በውስጥ ምን ያህል አለባት?» አልኩት።

«ሐያ አምስት ሺ ፍራንክ።»

ሌላ ቃል ሳልናገር የጎንዙብ መደበቂያ ቱቦዋን ተቀበልኩ። በጣም ንፁሕ ስለነበረች አንድ ሰው ሁለት ለመያዝ ይቻል እንደሆነ እየደነቀኝ በቀጥታ ከእርሱ ፊት በፈጋራየ ወደላይ ገፋኋት። ምንም ሐሳብ አልነበረኝም። ጥነሣሁና ሱሪየን መልሼ አጠለቅኩ። አላስቸገረኝም።

ከመሐዱ በፊት «ሰሜ ኢኛስ ጋልጋኒ ነው። አመሰግናለሁ ፓፒዮ» አለ። ወደ ዴጋ ተመልሼ ሔድኩና ታሪኩን ነገርኩት።

«በጣም አይከብድም?»

«አይከብድም።»

«አሺ፣ እንግዲያውስ።»

ከተቻለ ከጁሎ ወይም ከጊቱ ጋር፣ አለበለዚያም ካሁን በፊት አምልጠው ከነበሩ ሰዎች ጋር ግንኙነት ልናደርግ ሞከርን። ያ ቦታ ምን ይመስላል? የአሥረኛ አያያዛቸው እንዴት ነው? የጎንዙብ መያዣ ቱቦህን እንዴት ትደብቃለህ? ወዘተ . . . ለሚለው ሁሉ መልስ ለማግኘት ጓጉተን ነበር። ዕድል የሚያመጣው የለም፣ አንድ በጣም

t.me/OLDBOOKSPDF

እንግዳ የሆነ ፍጡር ላይ ጣለን። አባቱ ዘበኛ ሲሆን፣ ከባለቤቱ ጋር በደሳሌያ ደሴቶች ኗሪ ነበር። የተወለደው ከሦስቱ አንዱ በሆነችው በሮያሌ ደሴት ውስጥ ሲሆን፣ ሌሎቹ ቅዱስ ዮሴፍና የዲያብል ደሴት ይባላሉ። ወይ ዕድል! ተመልሶ የሚሔደው እንደ ዘበኛ ልጅ ሳይሆን፣ እንደ እንድ እሥረኛ ሆኖ ነበር።

ቤት በመሰርሰር ዝርፊያ ዐሥራ ሁለት ዓመት ጽኑ እሥራት ተፈርዶበት ነበር። ዕድሜው ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ሲሆን፣ ግልጽ ፊትና ጥርት ያሉ ብሩህ ዐይኖች ነበሩት። በአጋጣሚ የፈጸመው ድርጊት መሆኑን ወዲያውኑ ለመገነዘብ ችለናል። ስለ እራዳው ዓለም የሚያውቀው በጣም የተወሰነ ቢሆንም፣ ከፊታችን ለሚጠብቀን ኑሮ መረጃዎችን ለመስጠት ይጠቅመናል። ለዐሥራ አራት ዓመት ስለ ቆየባቸው ደሴቶች ኑሮ ሁኔታ ነገረን። ለምሳሌ እርሱን በደሴቱ ውስጥ አሳድጎት የነበረው አንድ የታወቀ ወመኔ እሥረኛ ሲሆን፣ የተወነጀለውም በሳስክ ደ አር ውብ ዐይኖች መነሻ የጩቤ ፍልሚያ እድርጎ መሆኑን ተረዳን።

አንዳንድ ዋጋ ያላቸው ምስክሮችም ሰጠን። ማምለጫችንን ማቀድ የሚኖርብን ከግራንዴቴሬ መሆን እንዳለበት እንጅ፣ ከደሴቲቱ አለመቻሉን፣ ከዚያም እደገኞች ተበለን መመዝገብ እንደማይኖርብን፣ ምክንያቱም በዚህ ስም ከጎደፍን ወደ አድራሻችን ቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ ወዲያው ስንደርስ፣ የቱን ያህል አደገኞች ናቸው ብለው እነርሱ በገሙቱት መጠን ለዓመታት ወይም በዕድሜ ይፍታህ እዚያው ሊያሰሩን እንደሚችሉና በአጠቃላይ በደሴቶቹ ከመቶ ውስጥ ከአምስት በላይ እንደማይታሠሩ ነበር። ሌሎቹ በግራን ይቆያሉ። ደሴቶቹ ጤናማ ነበሩ፣ ግራንዴቴሬ ግን ቀደም ብሎ ዴጋ እንደነገረን ከሆነ አንድን አሰረኛ ቀስ በቀስ በዐፅሙ የሚያስቀር፣ ማንኛውም ዓይነት በሽታና ብዙ ዓይነት ድንገተኛ ሞት የሞላበት የታወቀ መዓተኛ ቦታ ነበር። በደሴቶቹ ላለመታሠር ተስፋ አደረግን። ግን በጉሮሮየ ላይ የሆነ ሸምቀቆ ተሰማኝ። አደኛ ተበዬ ተመዘገቢ ከሆነስ ምን ልሆን ነው? በወህኒ ቤቱ አዛኝና ትሪቡላር ላይ የፈጸምኳቸው ድርጊቶች ከዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፍርዴ ጋር በጥሩ አቋም ላይ አያስገኙኝም።

ቅዱስ ማርቲን ደራ ከዳር እስከዳር በእሥረኞች ተጨናንቃለች። ሁለት ዓይነት እሥረኞች ነበሩ፣ በሰምንት መዶና በአንድ ሺ መካከል የሚገመቱ ሌቦችና ዘጠኝ መዶ ከባድ ወንጀለኞች። ልማደኛ ወንጀለኛ ለመባል አንድ ከበድ ያለ ጥፋት መፈጸም፣ ወይም ቢያንስ አንድ ከባድ ጥፋት አድርጓል በመባል መከሰስ ይኖርብሃል። ቅጣቱ ከሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እስከ ዕድሜ ይፍታህ ይደርሳል። አንድ ወንጀለኛ በአመክሮ ከሞት ቅጣት ቢያመልጥ በቀጥታ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ያገኛሉ። የልማደኛ ሌቦቹ ግን ከዚያ የተለየ ነበር። አንድ ሰው ልማደኛ ሌባ የሚለው ከሦስት ወይም ከአምስት ወንጀሎች በኋላ ነው። የማይታረሙ ሌቦች ናቸውና ሕብረተሰቡም እንዴት ራሱን

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊጠበቅ እንደማይችል አንጃ። በሌላ አንጻር እንደዚህ የመሰለውን ተጨማሪ ዓይነት ቅጣት አንድ የሠለጠነ ሕዝብ በሥራ ላይ ማዋሉ ደግሞ አሳፋሪ ነበር። ልማደኞቹ ሌቦች ጊዜያዊ ናቸው። ዘወትር ሰለሚያዙ ፈዛዞች ነበሩ። በእኔ ጊዜ ልማደኛ ሌባ መሆንና የዕድሜ ይፍታህ እሥራት ተወራራሽ ነበሩ። ሕብረተሰቡን ያስቸግራሉ በሚል ምክንያት ብቻ እነርሱን ለማውደም የሚሯሯጥና ለመበቀል መብት ያለው ማንም ሀገር አይኖርም። እንደዚህ የመሰለው ከሰብአዊ ርኅራሄ ውጭ የሆነ ቅጣት ከሚጣልባቸው ይልቅ ቢታረሙ ይበጃል።

አሁን በቅዱስ ማርቲን ደ ሬ ወሥራ ሰባት ቀን ሆነን። ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት የምትወሰደን ጀልባ ስም «ላ-ማርቲኜ» መባሏን ተረዳን። አንድ ሺ ሰምንት መቶ አስረኞች ልትሸከም ነው። በአምባው ውስጥ ከሚገኘው መስክ ስምንት ወይም ዘጠኝ መቶ የምንሆን አሥረኞች ተሰብስበን ። በዐሥር ረድፍ ተሰልፈን ግቢውን እንደ ሞላን ለአንድ ሰዓት ያህል ስንጠባበቅ ቆየን። በሩ ተከፈተና እኛ እናውታቸው ከነበሩት ዘበኞች በጣም ልዩ የሆነ ልብስ የለበሱ በቡድን ሆነው ከውጭ በኩል መጡ። የለበሱት ውሃ ሰማያዊ የሚሊታሪ ቅድ ሆኖ አለባበሳቸውም ደስ ይላል። ፖሊሶችም አልነበሩም፣ ወታደሮችም አልነበሩም። ሁሉም ሰፊ ቀበቶዎች ታጥቀው በአነርሱ ላይ የሽጉጥ ማኅደሮች አንጠልጥለዋል። የሽጉጦቹንም እጀታዎች ማየት እንችላለን። ሰማንያ ይሆናሉ። አንዳንዶቹ በእድገዎቻቸው ላይ ጥበጣቦች ለጥፈዋል። ሁሉም ፊታቸው በፀሐይ የበለዘና በሠላሳ አምስትና በሃምሳ ዓመት መካከል ያሉ ይመስላሉ። ሸምገል ያሉት ርኅሩኖች ሲመስሉ፣ ወጣቶቹ ደግሞ በጭበጠነት ስሜት ደረታቸውን አሳብጠዋል። የቡድኑ አዛዥ መኮንን በቅዱስ ማርቲን ደሬ የፖሊስ ኮሎኔል፣ የቅኝ ግዛት ልብስ በለበሱ ሦስት ወይም አራት ዶክተሮችና ነጭ ካባ በለበሱ ሁለት ቄሶች ታጅቦ ነበር። የፖሊሱ ኮሎኔል አንድ የድምፅ ማጉሊያ ወደ አፉ ቀረብ አደረገ። «ተጠንቀቅ!» የሚል ትእዛዝ ስንጠባበቅ ነበር። ግን በትእዛዙ ምትክ «በጥንቃቄ አዳምጡ» አለ ኮሎኔሉ። ቀጠለናም፣

«ከእንግዲህ ወዲያ ዋና መሥሪያ ቤቱ ካየን ከተማ የሆነው በፍትሕ ሚኒስቴር የፊረንሣይ ጊያናን በሚወክለው የቅጣት አስተዳደር ባለሥልጣኖች ዳኝነት ሥር ናችሁ። የወህኒ አዛዡ ባሮ፣ እነኝህ የተሰለፉትንና ስማቸው መዝገብ ላይ የሰፈረውን ስምንት መቶ አስረኞች አስረክበዎታለሁ። ሁሉም መኖራቸውን አጣርተው በፊርማዎ ቢያረጋግጡልን?»

የስም ጥሪው ተጀመረ። «አከሌ አከሌ፣ አለሁ! አከሌ አከሌ፣ አለሁ! ወዘተ . . . » ሁለት ሰዓት ፈጀ። ሁሉም ነገር ተስተካከለ ነበር። ከዚያም በሁለቱ አስተዳደሮች የተደረገውን የፊርማ ልውውጥ ለሥነ ሥርዓቱ በተዘጋጀች እንዲት ትንሽ ጠረጴዛ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊከናወን ተመለከትን።

ወህኒ አዛዡ ባሮ፣ በብር ፋንታ የከር ጥልፍ ቢሆኑም፣ እርሱም እንደ ኮሎኔሉ ብዙ የማዕረግ ምልክቶች ነበሩት። እሱም በተራው የድምፅ ማጉሊያውን ያዘ። «ተጓጉች፣ ከአሁን ወዲያ የምትጠሩበት ስም ይሆናል። - «ተጓዥ እከሌ እከሌ» ወይም በተሰጣችሁ ማንኛውም መለያ ቁጥር መሠረት ቁጥር ይሆን ያህል» ይሆናል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ተገቢ ነው ብለው የማያምኑበትን ውሳኔ በሚያሳልፉ የውስጥ ፍርድ ቤቶችና በቅኝ ግዛት ወህኒ ቤቶች ልዩ ሕግና መመሪያ ሥር ናችሁ። በአሰቃቂው የቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ውስጥ በምትፈጽሙት ጥፋት መሠረት ራሱን ችሎ የሚሠራው ፍርድ ቤት፣ ከቀላል አሥራት አንሥቶ እስከ ሞት ቅጣት ድረስ በማንኛውም አኳያ ሊቀጣችሁ ይችላል። በአሥራትም ይሁን በግዞት እነዚህ የሥነ ሥርዓት ቅጣቶች የሚከናወኑት በአስተዳደሩ ሥር በሚገኙ ማናቸውም በታዎች ነው። ከፊታችሁ የምታዩዋቸው ፖሊሶች የሚጠሩት ዘበኞች አየተባሉ ነው። እናንተ ስትጠሯቸው ሌቶ ዘበኛ» እያላችሁ መሆን አለበት። ከእራት በኋላ ለቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ከሚሆን ልብሶቻችሁ ጋር እንድ ሻንጣ ይሰጣችኋል። ማንኛውንም ነገር ተረድታችኋል። ነገ «ላ - ማርቲኔ» ላይ ትሣፈራላችሁ። ጉዞውን የምናደርገው አብረን ነው። በፈረንሣይ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ጠባይ ማረሚያ ይልቅ የቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት የተሻለ ስለሆነ በመሐዳችሁ ሐዘን አይሰማችሁ። ማጤስ፣ መዝፈን፣ ካርታ መጫወትና መናገር ትችላላችሁ። መልካም ሥነ ምግባር እስካሳያችሁ ድረስ ሥቃይ ይደርስብናል ብላችሁ አትሥጉ። ማንኛውም ዓይነት የግል አለመግባባት ያላችሁ፣ ወደ ቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ደርሳችሁ አስከታቃልሉ ድረስ እንድትታገሡ እጠይቃለሁ። በጉዟችን ወቅት ሥነ ሥርዓት በጣም ጥብቅ መሆን አለበት፤ ይህም ለምን እንደሆነ እንደምትረዱ አምናለሁ። ከእናንተ ውስጥ ጉዞውን ለመቀጠል ሕመም የሚሰማችሁ ካላችሁ ወደ ሕክምና ከፍል ሒዱና ኮንቮዩን በሚያጅቡ የሕክምና ሻምበሎች ልትታከሙ ትችላላችሁ። «መልካም ጉዞ እመኝላችኋለሁ።» ሥነ ሥርዓቱ ተፈጸመ።

«እንግዲህ፤ ምን ታስባለህ ዴጋ?»

«ወዳጄ ፓፒዮ፣ ትልቁ እደጋ የሌሎቹ አስረኞች ነው ብዬ ስነግርህ እርግጠኛ ነበርክ። «ማንኛውም ዓይነት የግል አለመግባባት ያላችሁ ወደቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ደርሳችሁ አስከታቃልሉ ድረስ ታገሡ» ያላት ጉዳይ ብዙ ስንከላር ትናገራለች። መዓት ግድያዎች መኖር አለባቸው!»

«ስለዚህ ጉዳይ አትጨነቅ። እኔን ብቻ አመነኝ።»

ፍራንሷ ላፓሴን ፈለግኩና እንደዚህ ሰል ጠየቅኩት።

«ወንድምህ አሁንም የአሥረኛ ጤና ሬዳት እንደሆነ ነው?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ፤ ልማደኛ አሥረኛ ነው።»

«በተቻለ ፍጥነት ሒድና አንድ ጩቤ አንዲሰጥህ ጠይቀው። ፖንዙብ ከፈለገ ስንት እንደሆነ ንገረኝና አከፍለዋለሁ።»

ከሁለት ሰዓት በኋላ በጣም ጠንካራ የብረት እጀታ ያላት የአንዲት ጩቤ ባለቤት ሆንኩ። ጣንካዋ ትንሽ ረዘም ማለቷ ነው እንጂ የምታስደነግጥ መሣሪያ ነበረች።

በግቢው መካከል ከሚገኘው መጸደጃ ቤት አጠገብ ቁጭ አልኩና የጎንዙብ መደበቂያ ቱቦውን መልሼ መስጠት እንድችል ወደ ጋልጋኒ ላከሁ። ሆኖም ሰፈውን ግቢ ሞልተው ከሚርመሰመሱት ስምንት መቶ ሰዎች መካከል እርሱን ለማግኘት አስቸጋሪ ነው። ከመጣን ጀምሮ ሉጊቱን፣ ጁሎን ወይም ሳንቲኒን አላገኘናቸውም ነበር።

የማኅበራዊ ኑሮ ጥቅሙ አብረን መኖራችን፣ ማውራታችንና የአንድ አዲስ ማኅበረሰብ አባል መሆናችን ነበር። አንድ ማኅበረሰብ ይሁን ብላችሁ ከጠራችሁት በጣም ብዙ ለመናገር፣ ለመስማትና ለማድረግ ይቻላል። ለማሰብ ግን ጊዜ አልነበረም። ያለፈው የብቸኝነት ኑሮዬ የአሁኑን ኑሮየን ምንና አደብዝዞትና ጋርዶት ኖሯል? ወህኒ ቤት ከደረስኩ በኋላ ማን እንደነበርኩና ለምን እንደ መጣሁ ማሰቡን አርግፍ አድርጌ ትቼ ለማምለጥ ብቻ ማተኮር አልዳለብኝ ተገነዘብኩ።

ግን ተሳስቼ ነበር። ከሁሉም የበለጠ አንገብጋቢው ነገር በሕይወት መቆየት ነው። ለመሆኑ ፖሊሶቹ፣ ተችዎቹ፣ ፍርድ ቤቱ፣ ዳኞቹ፣ ሚስቴ፣ አባቴና ጓደኞቼ ወዴት ይሆኑ? ሕያው ሆነው ተመለሱብኝ። ሊያንዳንዳቸውም በልቤ ውስጥ ቦታ ነበራቸው፣ ግን ወደ አልታወቀው አካባቢ የማደርገው ከፍተኛ የጉዞ ሽግግር መሸበርና፣ ከአዲስ ጓደኞች ጋር ከመለማመድ የተነሣ እንደ ወትሮው ተመሳሳይ ዋጋ አልሰጣቸውም። ይሁን እንጂ፣ እንድ ጊዜ ፍላጎት ኖሮኝ ለሊያንዳንዳቸው መኖሪያ ያደረገሁትን የአእምሮዬን ጓዳ ስከፍት ሁሉም ቁልጭ ብለው ይታዩኛል።

ጋልጋኒን ወደ እኔ እየመሩ አመጡት። በባዶ ዐይኑ ቀርቶ በወፍራሙ መነጥሩ እንኳ ለማየት አይችልም። ጤንነቱ የተሻሻለ ይመስላል። ወደ እኔ ቀረብ አለና ምንም ሳይናገር እጅን ጭምድድ አደረገኝ።

«የፖንዙብ መደበቂያ ቱቦህን መልሸ ልሰጥህ እፈልጋለሁ» አልኩና በማከታተል፣ «አሁን ደህና ነህ፣ ራስህ መያዝ ትችላለህ። በጉዞው ወቅት ለእኔ ከባድ ኃላፊነት ነው፣ ደግሞስ እርስ በርሳችን የትም ቦታ ባንቀራረብ ወይም በቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ስንደርስ እንኳ ባንገናኝ፣ ምኑ ይታወቃል። ስለዚህ የሚሻለው ብትወስደው ነው።»

ጋልጋኒ የከፋው ይመስላል።

«እንግዲህ፣ ወደ መጸዳጃ ቤት ናና የፖንዙብ መደበቂያ ቱቦህን ልስጥህ።»

«ይቅር በኝ፣ አልፈልግም። አንተው ውሰደው፣ እንደ ገጸ በረከት ለአንተው

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰጥቸሃለሁ። ሁሉም የአንተው ይሁን።»

«ለምን እንደዚህ ትላለህ?»

«ለገንዘብ መደበቂያ ቱቦየ ስል መገደል አልፈልግም። በእርሱ ምክንያት ከምገደል ያለ ገንዘብ መኖርን እመርጣለሁ። ከዚህም ሌላ የእኔን ገንዘብ ለማስቀመጥ ስትል ሕይወትህን አደጋ ላይ መጣል ይሉኝታ ማጣት ስለሆነ፣ ለአንተው አሰጥሃለሁ። በዚህ መንገድ ሕይወትህን ለአደጋ ብታጋልጥ አንኳ ለገዛ ራስህ ጥቅም ይሆናል።»

«ፈርተሃል ጋልጋኒ። የሚያስፈራሩህ አሉ እንዴ?»

«አዎ፣ ሦስት ዓረቦች ሁልጊዜ ከኋላየ እንደ ጅራት ይከተሉኛል። ወደ አንተ ያልመጣሁበት ምክንያት በዚህ ነገር ሁለታችን እንደ ተመሳጠርን እነርሱ እንዲጠረጥሩ ስላልፈለግኩ ነው። ቀንም ሆነ ሌሊት በማንኛውም ጊዜ ወደ መጸዳጃ ቤት ስሔድ፣ ከእነዚያ ጥላቢሶች አንዱ ይመጣና አጠገቤ ይቆማል። ስለ ሁኔታው እምብዛም ሳላስተጋባ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እንደሌለኝ ግልጽ ለማድረግ ሞክርኩ። ግን ከመከታተል አልቦዘኑልኝም።

እርግጠኛ ነኝ አንድ ሰው እንደ ያዘልኝ ጠርጥረዋል። ማን እንደሆነ አላወቁም፣ ግን መልሼ ስቀበል ለማየት ዙሪያውን ያንጎራብቡብኛል።»

ጋልጋኒን ስመለከተው ተጨንቆ እንደነበር ተገነዘብኩ።

«የሚዘዋወሩት ከግቢው በየትኛው በኩል ነው?» ስል ጠየቅኩት።

«ከልብስ ማጠቢያውና ኩሽና ቤቱ አጠገብ።»

«መልካም፣ እንተ እዚህ ቆይና እኔ ወደዚያው አሔዳለሁ - ግን አይሆንም፣ አንተም ከእኔ ጋር ና።»

ጩቤየን ከኮፍያዬ አወጣሁና ስለቱን በቀኝ እጅጌዬ ውስጥ ወደላይ አስገብቼ እጀታዋን በእጄ ጨበጥኩ። ወዲያው ተመለከትናቸው። አራት ያህል ነበሩ። ሦስት ዓረቦችና ጅራንዶ የተባለ አንድ ኮርሲካዊ። ወዲያውኑ ነገሩ ገባኝ። ኮርሲካዊው በአራዳዎች ጓደኞቹ ገሸሽ ስለተደረገ ነበር ወደ ዓረቦቹ የተጠጋው። ጋልጋኒ የፓስካል ማትራስ አማች መሆኑንና እንደዚያም ከሆነ አንድ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እንደሚኖረው ዐውቆ መሆን አለበት።

«ታዲያስ ሞከሬን?»

«ደህና ነኝ ፓፒዮ። አንተስ እንዴት ነህ?»

«አለሁ . . . መቼስ! ወደእዚህ የመጣሁት ጋልጋኒ ጓደኛዬ መሆኑን ልነግራችሁ ነው። አንድ ነገር በእርሱ ላይ ቢደርስ፣ ጉዳዩ መጀመሪያ የሚመለከትህ አንተን ጅራንዶን ነው። የቀራችሁትንም ይከተሉችኋል። በፈለጋችሁት መንገድ ተርጉሙት።»

ሞከሬን ተነሣ። በግምት ቁመቱ ስድስት ጫማ የሚሆን፣ እንደ እኔው ረጅምና

t.me/OLDBOOKSPDF

አቋሙም የተደላደለ ነበር። 'ለመጣላት ተዘጋጅቶ ነበር፣ - ሁለመናዋ የሚያበለጨልጨውን አዲስ ጩቤ መዘዝኩ። በእጇ መዳፍ ውስጥ እንደያዝኩ፣ «በትንቀሳቀስ ልክ እንደ ውሻ አገድልሃለሁ» አልኩት።

መሣሪያ በመያዜ ምክንያት በግልጽ ከመገረሙም ሌላ ቁርጠኛ የመሆኔና የጩቤውም ርዝመት ሰላስደነገጠው፣

«የተነሣሁት እኮ ላናግርህ እንጂ ለጥል አይደለም» አለ።

ይህ ዕውነት እንዳልነበረ ዐውቄአለሁ፣ ግን በጓደኞቹ ፊት ከኃፍረት እንዲድን እርሱን መርዳት ፍላጎቱ እስከሆነ ድረስ ተዝናንቶ እንዲያልፍ ፈቀቅ አልኩለት።

«አሺ፣ የተነሣኸው ለመናገር እስከሆነ ድረስ»

«ጋልጋኒ የአንተ ጓደኛ መሆኑን አላወቅኩም። ወቅታዊ ትውውቅ መስሎኝ ነበር። እንዴት እንደሆነ ታውቃለህ ፓፒዮ፣ ለማምለጥ ገንዘብ ማግኘት ሰላለብህ እዚህ ማንኛውም ሰው ከአንተ ይሰርቃል» አለ።

«መልካም፣ ሊሆን ይችላል፣ ለኑሮህ ለመታገል ማንኛውም መብት አለህ ሞከሬን። ማስታወስ ያለብህ ብቻ ይህ የተከለከለ ቀበሌ መሆኑን ነው። ሌላ አካባቢ እስስ።»

እጁን ዘረጋና ጨበጥኩት። የክርስቶስ ያለህ፣ አልቆልኝ ነበር። ሰውየውን ገድየው ቢሆን የሚቀጥለው ቀን እርግጠኛ ነኝ ከጉዞየ ተጨናግፌ ነበር።

ጋልጋኒ ከእኔ ጋር ተመለሰ። «ስለዚህ ጉዳይ ለማንም ሰው እንዳትናገር። ከዴጋ ጋርም ለመቀያየም አልፈልግም» አልኩት። ጋልጋኒ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን እንዲወስድልኝ ለማሳመን ሞከርኩ።

«ከመሐዳችን በፊት ነገ» አለ። ግን በሚቀጥለው ቀን ራሱን ስለደበቀ፣ እነሆ ከሁለቱ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዎች ጋር ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ጉዞ መነሣት ነበረብኝ።

በዚያች ሌሊት እኛ ከፍል ውስጥ ማንም አልተናገረም። በፈረንሣይ አፈር ላይ ይህ የመጨረሻ ቀናችን መሆኑን ሁላችንም እያሰብን ነበር። ፈረንሣይን እስከ መጨረሻው ለቅቀን ወደ አልታወቀ መሬትና ወደ አልተላመድነው ኑሮ መሐዳችን አባብቶን ነበር። በቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ተወልዶ ከነበረው ወጣት ኮርሲካዊ በስተቀር በከፍላችን ውስጥ ከሚገኙት ዐሥራ አንድ ሰዎች ዐሥሩም ከታወቀው የአራዳ ዓለም የመጡ ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ሰዎች፣ በወቅቱ ከባድነትና ወሳኝነት ልባቸው ተንጠልጥሎ ነበር። የሲጃራው ጢስ ከከፍሉ ውስጥ እየተነነ ወደ ኮሪደሩ ሲወጣ፣ ዐይኖችሀን ለማዳን ከጢሱ ጉምበታች መቀመጥ ነበረብህ።

ያሳለፍኩት ኑሮ እንደ ተንቀሣቃሽ ፊልም ከፊት ለፊት ተተረተረ። ፍቅር

t.me/OLDBOOKSPDF

በተሞላበት ቤተሰብ ውስጥ ያሳለፍኩት የልጅነት ዘመኔ፣ ትምህርቴ፣ አስተዳደጌ፣ ጨዋነቴ፣ በመስኩ ላይ የነበሩት አበቦች፣ የፍራፍሬዎቹ ጣዕም፣ የአትክልት ቦታችን በብዙት የሚያፈራቸው ኮኮችና ፍራፍሬዎች፣ በየፀደዩ ከመዝጊያችን ፊት ሰፊት የሚፈካው ባለሽቱ መዓዛ አበባ፣ የቤታችን ውጭና ልዩ በሆነው የቤተሰቦቼ እንቅስቃሴ የተሞላው የቤታችን ውስጥ፣ ይህ ሁሉ በአእምሮየ ተመዝግቧል። ድምፅ ያለው አንድ ተንቀሳቃሽ ፊልም ነበር። በጣም የምትወደኝን የምስኪኗ እናቴን ድምፅ ሰማሁ። ከዚያም ሁልጊዜ የሚደባበሰኝንና የሚሳሳልኝን የአባቴን። ከአትክልቱ ቦታ ውጭ እንድንጫወት የሚጠራኝ የከላራን (የአባቴ አዳኝ ውሻ ነበረች) ጩኸት፣ በደስታ ቀኖች ያጫወትኳቸው ጉበሎችና ልጃገረዶች። ይህን ተንቀሳቃሽ ፊልም ለማየት አልጠየቅኩም ነበር። ወደ ማይታወቀው ቦታ ለመሻገር በዚህ የቆይታ ምሽት እንዳለሁ፣ ሕሊናዬ በሰመመን መልክ ያመጣልኝ የሆነ አስማታዊ የሩኖስ ብልጭታ ነበር።

ዕድሜዬ ሐያ ስድስት ዓመት ሆኖ የተሟላ ጤንነት ነበረኝ። በሆዴ ውስጥ የራሴን አምስት ሺ ስድስት መቶ ፍራንክና የጋልጋኒን ደግሞ ሐያ አምስት ሺ ፍራንክ ይገባለሁ። ከእኔ ቀጥሎ ያለው ዴጋም ዐሥር ሺ ነበረው። ጋልጋኒ ገንዘቡን እዚህ ተከላከሎ መያዝ ካልቻለ፣ በጀልባው ላይና ጊያና ውስጥ የበለጠ ችግር ሰለሚሆን፣ የዐርባ ሺህ ፍራንክ ኃላፊነት በእኔ ላይ ወድቋል ለማለት እችላለሁ። የገንዘብ መደበቂያውን ቱቦ ለመጠየቅ ያልመጣውም በዚሁ ምክንያት ነው። ስለዚህ የእርሱንም ሆነ የእኔን በግዴታ የማኖር ኃላፊነት ከእኔው ራስ ኢይወርድም።

እርሱም ገንዘቡ ነውና ጥቅሙን ማግኘት አለበት። በእርግጥ እኔም እንደዚሁ በተዘዋዋሪ መንገድ ጥቅም ቢኖረኝም ቅሉ፣ እርሱም ጥቅሙን እንዲያገኝ ማድረግ አለብኝ። ዐርባ ሺ ፍራንክ ብዙ ነው። ዘበኞችን፣ ያመለጡ ኦሥረኞችንና ለኦሥረኞች ማምለጥ ተባባሪ የሚሆኑትን ሁሉ ለመደለል መንገዱን ያቃልለዋል።

እንደ ደረስኩ ወዲያውኑ ከዴጋና ጋልጋኒ ጋር ማምለጥ ነው። የማተኩረው በዚሁ ይሆናል፣ በቃ በዚሁ ብቻ። ጩቤየን ስነካት ቀዝቃዛው ብረት ተሰማኝና ደስ አለኝ። እንደዚህ የመሰለች አንዲት ልብ የምትሞላ መሣሪያ በመያዜ በራስ መተማመን አደረብኝ። ጠቃሚነቷን ያረጋገጥኩት ቀደም ሲል ከወረቦቹ ጋር በፈጠርኩት ግጭት ነበር።

በግምት ከጧቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ከከፍላችን በስተውጭ በኩል በትልቁ ምልከቶች የተጻፉባቸው ጥቅጥቅ ያሉ ዐሥራ አንድ ጥቅሎች ተደርድረው አየሁ። ከእነርሱ እንደኛው፣ «ሲ-ፒየሮ ፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት፣ ቁመቱ አምስት ጫማ ከዘጠኝ ኢንች፣ የልብስ መጠን ዐርባ ሁለት፣ የጫማው ቁጥር ስምንት፣ የመለያ ቁጥር ነው» የሚል ይነበብበታል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ያ ሲ፡ ፒየሮ፣ ፓሪስ ውስጥ በነፍስ ግድያ ተወንጅሎ ሐያ ዓመት ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ከቦርዶው ቀበሌ የመጣው ፒየር ለፋ ነበረ። ጥሩ፣ ጎበዝ፣ ሞኖፖኛና የአራዳው ዓለም የሚመካበት መሆኑን በሚገባ ዐውቅ ነበር።

ፍርድ ቤቱን፣ ተቸዎቹን፣ ዓቃቢ ሕጉንና የቀሩትንም ምሥል በሙሉ እንዲያሳየኝ አእምሮየን ጠየቅኩት። ወዲያውኑ ተቃወመኝ። ያገኘሁት መልስ ድፍን ያለና የማይታይ ነበር። ነገሩ ገባኝ። ባለፈው ወቅት በበሊየ ጥበቃ ጣቢያ ብቻየን ሆኜ በጥሞና ሳሰላስላቸው ያለፉት ትዝታዎቼ ድቅን ይሉብኝ ነበር። እንዲመጡልኝ ካስፈለገ ብቻየን መሆን አለብኝ። ሙሉ በሙሉ ብቻየን። ይህንንም ማወቅ ሸከም ማታለል ነበር። የሚጠብቀኝ የማነበረሰብ ኑሮ አዲስ ፍላጎቶችን፣ አዲስ ሐሳቦችንና አዲስ ዕቅዶችን እንደሚፈጥር ተገንዝቤያለሁ።

ፒየሮ ለፋ ወደ ቋሚ ፍርግርፉ ቀረብ አለና፣ «እንዴት ይሠሃል ፓፒ?» ሲል ጠየቀኝ።

«ነንተስ ኒንዴት ነህ?»

«ታውቃለህ፣ እኔ ሁልጊዜ ምኞቴ ወደ አሜሪካ መሔድ ነው። ግን ቁማርተኛ በመሆኔ ለጉዞ የሚሆነኝ በቂ ገንዘብ ለማጠራቀም ፍጹም አልሆነልኝም። ፖሊሶቹ ጉዞውን ያለከፍያ ሊያበረከቱልኝ ተስማምተዋል። ነገሩ ጥሩ መሆኑ መቼም አጠያያቂ አይሆንም፣ ፓፒዮ፣ አ?» አለኝ።

የሚናገረው ፍጹም ወደ ኋላ ሳይል በራሱ በሚገባ ተማምኖ ነበር።

«ይህ ወደ አሜሪካ የነጻ ጉዞ ያለጥርጥር ጥቅም አለው። በፈረንሣይ የማዞት ወህኒ ቤት ውስጥ ዐሥራ አምስት ዓመት ከማጥፋት ይልቅ ወደቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መሔድን አመርጣለሁ።»

«ሁኔታዎች አስኪስተካከሉ ድረስ መታገል የሚኖርብን ይመስለኛል። እንደ ገመትኩት ከሆነ ካንተ ጋር አልማማለሁ። ተመልከት ፒየሮ፣ ያ የአንተ ምልክት ነው» አልኩት።

ሊያነብበው ጎንበስ አለና፣ «ይህን ልብስ ለመልበስ ጊዜ መውሰድ አልቻልኩም። አነዚያ ቀይ ጥብጣቦች ድንቆች አይደሉም? ፓኮውን ከፖቼ አሁኑኑ መልበስ አፈልጋለሁ። ማንም ሰው ፍጹም አይናገረኝም። ኮሮ ዞሮ የራሴው ናቸው» አለ።

«ይቅርብህ። አስኪነገረን ድረስ ቆይ። አሁን ሬብሻ የሚረግበት ወቅት አይደለም ፒየሮ። ሰላም አፈልጋለሁ» ስለው ገባውና ወደ ኋላ ገሰል አለ።

ዴጋ ወደ እኔ ተመለከተና፣ «ወጣቱ ባሲደረባዬ፣ እንግዲህ የመጨረሻው ሊሊታችን ነው። ነገ ወጪቱን ሀገራችንን እንለታለን» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«የእኛ ውብ ሀገር ውብ የሆነ ሕግ የላትም ዴጋ። ጥፋተኞችን በቸሸለ ሁኔታ የሚይዙ ምናልባት ግን፣ በጣም ውብ ያልሆኑ ሀገሮችን አናውቅ ይሆናል።» የቱን ያህል ወደ እውነቱ እንደተቀራረብኩ አላወቅኩም። ወደፊት የሚሆነው ያስተምረኛል።

ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መለቀቅ

የዐሥራ ሁለት ሰዓት ደወል ሲሰማ፣ አንዳንድ እሥረኞች ቡና አመጡልን። ከዚያም አራት ዘበኞች መጡ። አሁንም ሽጉጣቸውን በሽንጣቸው ላይ እንደ ገነደሩ ነጫጭ ለብሰዋል። የብረት ቅበ ያላቸው አዝራሮቻቸው ያንጸባርቃሉ። ከእነርሱ ወስጥ አንድ በግራ ክንዱ ክሣድ ላይ የv ምልክት ያላቸው ሦስት የወርቅ ጥበጣቦች ነበሩበት፣ ይሁንና በትከሻው ላይ ምንም ነገር የለውም።

«ተጓዦች፣ ጣምራ እየሆናችሁ ወደ መተላለፊያው ሒዱ፣ እያንዳንዳችሁ አንድ ጥቅል ታገኛላችሁ። - ስማችሁ በላዩ ላይ ተጽፎበታል። አንሥና ከፊት ለፊታችሁ ይዛችሁ በኮሪዶሩ ትይዩ ቁሙ።»

ይሆን ካደረግን በኋላ፣ «አውልቁ፣ ልብሶቻችሁን ሽከፉና ጃኬቶቻችሁ ውስጥ አስገቡታችሁ በእጅጌዎቹ እሰሯቸው። ጥሩ። አንተ እዚያ ያለኸው፣ ጥቅሎቹን አንሣና ወደ ክፍል አስገባቸው። አሁን አዲሶቹን ልብሶቻችሁን ልበሱ። የውስጥ ሱሪና ካናቴራችሁን፣ ባለጥብጣብ ሱሪያችሁን፣ ጫማውንና ካልሲውን። ሁሉም ሰው ተዘጋጀ?»

«አዎ ጌታዬ!»

«ጥሩ። ዝናም ወይም ቅዝቃዜ የመጣ እንደሆነ.ሹራቦቻችሁን ከጥቅሉ ውስጥ አውጥታችሁ ያዙ። ጥቅሎቻችሁን በግራ ትከሻችሁ! - በሁለት መስመር ተሰለፉና ተከተሉኝ።» የጥበጣብ መለከት ያለው ሰው ከፊት፣ ከጎንና ጎን አንዳንድ ዘበኛ፣ አራተኛ ከኋላ ተከትሎን፣ ትንሿ የሰልፈኛ ቡድን ወደ ግቢው ውስጥ አመራች። ሁለት ሰዓት ሳይሞላ ስምንት መቶ እሥረኞች አሠልፈው ነበር። ከዚያም ከእነርሱ ውስጥ እኔና ዴጋ፣ አምልጠው የተያዙት ሦስቱ፣ ማለት ጁሎ፣ ለጊቱና ሳንቲኒ የምንገኝበትን የወርባ ሰዎች ቡድን ጠሩና ለይተው አወጡን። በዐሥር ረድፍ ተሰልፈን ቆምን። በእያንዳንዱ ረድፍ ጎን አንዳንድ ዘበኛ ቆመ። እግር ብረት የለም፣ ካቴና የለም። ከፊት ለፊታችን ሦስት ያርድ ርቀት ላይ ዐሥር ፖሊሶች ነበሩ። ጠመንጃ እንደ ወደሩ ከፊት ለፊታችን በመሆንና አንዱ ፖሊስ ሊላውን በቀበቶው እየሳበ በመምራት መንገዳቸውን የቀጠሉት በኋሊየሽ አርምጃ ነበር።

የአምባው ግዙፍ መዝጊያዎች ተከፈቱና ሰልፉ በዝግታ ወደፊት ይጓዝ ጀመር። ከግቢው እንደወጣን፣ ከኮንቮዩ ጎን በመሆን አሰከሚቀጥለው መዳረሻችን ለማጀብ

t.me/OLDBOOKSPDF

አውቶማቲክ ጠመንጃ የወደሩ ፖሊሶች ተጨመሩ። እግረ መንገዳቸውንም በእኛ ጉዞ ተደንቀው የተሰበሰቡትን ሰዎች ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ ነበር። ግማሽ ጉዞ እንደ ሐድን እንድ ለስላሳ ፉጨት ሰማሁ። ቀና ስል፣ ኒኒታና አንቷን ዲ የተባለ እንድ የቅርብ ጓደኛዬ በአንድ ሕንባ መስኮት ብቅ ብሎ አየሁት። የዴጋ ሚስት ፓውላና ጓደኛው አንቷን ጀሊቲ በሕንባው ሌላ መስኮት በኩል ብቅ ብለው ነበር። ዴጋም አይቷቸዋል። በመስኮቶቹ ላይ ዐይናችንን እንደ ተከልን እስከ መጨረሻው ድረስ በመራመድ አለፍናቸው። ከዚያ ወዲያ ሚስቴንም ሆነ የማርሴይ ወደብ በቦምብ ስትደበደብ የሞተውን ወዳጄን አንቷንን አይቻቸው አላወቅም። ማንም ሰው አይናገርም። ፀጥታው ሙሉ በሙሉ ነበር። ይህን አሳዛኝ ወቅት ሕዝቡ፣ ኢሥረኞቹም ሆኑ ዘበኞቹና ፖሊሶቹም ጭምር በአርምሞ ይመለከቱ ነበር። እነዚህ ሰምንት ሙቶ ሰዎች ከተላመዱት ኑሮ ለመጨረሻው ተሰይተው መሐዳቸውን ማንኛውም ሰው ተረድቶታል።

ወደ መርከቡ ተሣፈርን። የመጀመሪያዎቹ ዐርባ ሰዎች በመርከቡ ምድር ቤት ዙሪያውን በብረት ምሰሶ ከተከበበ ወጥመድ ውስጥ ተወስደን ታሠርን። «ከፍል ቁጥር ፣ በልዩ ደረጃ የሚገኙ 40 ሰዎች፣ ጥብቅ ቁጥጥር» የሚል፣ አንድ ጽሑፍ ተሰቅሏል። ለእያንዳንዳችን ተንጠልጣይ አልጋ ታደለን። ለአርሱ መስቀያ የሚሆኑ ቀለበቶች በብዛት ተንጠልጥለዋል።

አንድ ሰው ድንገት ጎንተል አደረገኝ። ጆሎ ነበር። በዚህ ሁኔታ ከዐሥር ዓመት በፊት ተገዝ ስለነበር ገመዶቹን ያውቃቸዋል።

«ፈጠን በል፣ ወደዚህ ና። ጓዝህን፣ ተንጠልጣይ አልጋህን ከምትዘረጋበት ጋንች ጋር አብረህ አስቀምጠው። ከሁለቱ መካፈቻዎች አቅራቢያ እዚህ ብንሆን ይሻላል። አሁን ተዘግተዋል። ወደ ባሕሩ ስንዘልቅ ግን ይከፈታሉ። ከማንኛውም ቦታ የተሻለ ቀዝቃዛ አየር እናገኛለን» አለ።

ከዴጋ ጋር አስተዋወቅኩት። በማውራት ላይ እንዳለን ከመካከላችን አንድ ሰው ጣልቃ ገባ። ጆሎ ሰውየውን ለመምታት ከንዴን መከተ። «ወደቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ከነነፍስህ ለመድረስ ከፈለግህ ወደዚያ ራቅ ብትል ይሻልሃል። ገባህ?

«አዎ!» አለ ያ ሰው።

«ለምን እንደሆነ ዐውቀሃል?»

«አዎ!»

«አሺ፣ በል ጥፋ ከዚህ» ብሎት ሰውየው ገለል አለ።

በዚህ የኃይል ትዕይንት ዴጋ ተደስቶ ነበር። «ከእናንተ ከሁለታችሁ ጋር እንቅልፍ መተኛት አችላለሁ» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከእኛ ጋር በመሆንህ በባሕር ትይዩ መስኮቱ በተከፈተ አንድ ቪላ ቤት ውስጥ ከመኖር የተሻለ ሰላም አለህ።»

ዐሥራ ስምንት ቀናት በወሰደው ጉዞ ውስጥ ቁምነገር ነው ተብሎ የሚገለጽ አንድ ድርጊት ብቻ ነበር። አንድ ሌሊት አንድ አጥንት የሚሰብር ኡኡታ አባነነን። በትከሻው መካከል ጩቤ የሰጠመበት አንድ ሰው ሞቶ ተገኘ። ያ የሚያስፈራው መሣሪያ ርዝመት ከሰምነት ኢንች የበለጠ ስለነበር፣ ተንጠልጣይ አልጋውን ዘልቆ ነበር።

በድንገት ሐያ አምስት ወይም ሠላሳ ዘበኞች ጠመንጃቸውን ወደ እኛ ደግነው፣ «ሁላችሁም ልብሳችሁን አውልቁ፣ ፍጥነት ይኑራችሁ!» ብለው ጮሁብን።

ሁላችንም እወለቅን። የምንፈተሽ መሆኑን ገምቻለሁ። ጩቤዎን በቀኝ ባድ አግሬ ሥር ረገጥኩትና ከብድቴን ወደ ግራዬ አጋደልኩ። ስለቱ ወደ ውስጥ ይቆርጠኛል። ግን መሣሪያው በሚገባ ተደብቆ ነበር። አራት ዘበኞች ወደ ወጥመዱ ከፍል ገቡና ልብሶቻችንና ጫማዎቻችንን ይበረብሩ ጀመር። ከመግባታቸው በፊት መሣሪያዎቻቸውን ከውጭ በኩል ትተው የወጥመዱን መዝጊያ ከኋላቸው ሸንሩት። ይሁንና ከወጥመዱ ከፍል ውጭ የቀሩት ዘበኞች ጠመንጃዎቻቸውን በእኛ ላይ ወድረዋል። «በመጀመሪያ እንቀሳቀሳለሁ የሚለው ሰው ሚች ነው» አለ ዋናው አዛዥ።

የፍተሻው ውጤት ሦስት ጩቤዎች፣ ሁለት የተሣሉ ምስማሮች፣ አንድ የቆርኪ መክፈቻና አንድ የገንዘብ መደበቂያ ዋወርቅ ቱቦ ኃሰገኘ። ስድስት ሰዎች እንደዘይው ራቁታቸውን እንዳሉ ወደ መርከቡ ወለል ተጠሩ። የካንቮዩ መሪ አዛዥ ባሮ ከሁለት ዶክተሮችና የመርከቡ ካፒቴን ጋር ደረሰ። ዘበኞቹ ከወጥመዱ ከፍል እንደወጡ ማንኛውም ሰው ትእዛዝ ሳይጠብቅ እንደገና ለበሰ። እኔም ጩቤዎን አዳንኩ።

ዘበኞቹ ከመርከቡ ወለል በስተኋላ አፈገፈጉ። አዛዙ ባሮ ከመካከል፣ ሌሎቹ ከደረጃዎቹ አጠገብ ነበሩ። ከእነርሱ ትይዩ በቀጥታ መስመር ራቁታቸውን የሆኑት ስድስት ሰዎች በተጠንቀቅ ቆመዋል። ሲፈትሽ የነበረ አንድ ዘበኛ፣ «የዚህ ዕቃ ባለቤት እርሱ ነው» አለ።

«ትከከል ነው። የራሴ ነው።»

«መልካም» አለና አዛዡ ባሮ በማከታተል፣ «በሞተሩ ከፍል ውስጥ እንደሆነ ጉዞውን ይፈጽማል» አለ።

የመሣሪያዎቹ ባለቤቶች፣ የምስማሮቹ፣ የቆርኪ መክፈቻውና የጩቤዎቹ ታወቁና እያንዳንዳቸው ባለቤትነታቸውን አመኑ። ስለሆነም ራቁታቸውን እንደሆኑ በዘበኞች ታጅበው በደረጃው ወደ ላይ ወጡ። ሁለት ነገሮች ቀሩ አንድ ጩቤና ከወርቅ የተሠራች የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ። ግን ያለው አንድ ሰው ብቻ ነበር። ዕድሜው በግምት ሐያ አራት ዓመት የሚሆነው ሰውነቱ በሚገባ የተገነባ፣ ቁመቱ ስድስት ጫማ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሆነና ሰማያዊ ዐይኖችና የስፖርተኛ አካል ያለው አንድ ወጣት ነበር።

«ይህ የአንተ ነው። አይደለም እንዴ?» አለ ዘበኛው ከወርቅ ወደ ተሰራችው የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እያመለከተ።

«አዎ፣ የራሴ ነው።»

«በውስጧ ምን ያህል አለባት?» ሲል አዛዡ ባሮ ከወለሉ ላይ እያነሣት ጠየቀው።

«ሦስት መቶ የእንግሊዙ ፓውንድ፣ ሁለት መቶ ዶላርና ሁለት ባሉ አምስት ካራት አልማዞች።»

«ደህና፣ አስኪ እንመልከተው።» ከፈታት። እኛ ምንም ነገር አላየንም። ግን፣ «ትከከል ነው። ማነው ስምህ?» ሲል ሰማነው።

«ሳልቫዲያ ሮሚዎ»

«ኢጣሊያዊ ነህ?»

«አዎ ጌታዬ»

«ለገንዘብ መደበቂያው የወርቅ ቱቦ አትቀጣም፣ ለጩቤው ግን አዎ።»

«ይቅርታ አድርግልኝ ጌታየ፣ ጩቤው ግን የእኔ አይደለም።»

«እንደዚህ ብለህ አትመልስልኝ። ስማ፣ ያገኘሁት በሚማህ ውስጥ ነው» አለ ዘበኛው።

«እደግመዋለሁ፣ ጩቤው የእኔ አይደለም።»

«ታዲያ እኔ ውሸታም ነኝ?»

«አልወጣኝም፣ ተሳስተሃል።»

«መልካም፣ ታዲያ የማን ጩቤ ነው?»

«የእኔ አይደለም፣ የማውቀው ይሆንኑ ብቻ ነው።»

«የተጣደ ድስት ውስጥ መቀቀል ካልፈለግህ የጩቤው ባለቤት ማን እንደሆነ ንገረን።»

«አላውቅም።»

«ልታሾፍብኝ አትሞክር። በሚማህ ውስጥ አንድ ጩቤ አግኝተን ባለቤቱ ማን እንደሆነ አታውቅም? ሞኝ ነው ብለህ ታስባለህ? ወይ የአንተ ነው አለበለዚያም እዚያ ያስቀመጠው ማን እንደሆነ ታውቃለህ።»

«የእኔ አይደለም፣ የማን እንደሆነ ለመናገር ደግሞ የእኔ ጉዳይ አይደለም። አዋሻኪ አይደለሁም። ከእንደ እናንተ ዓይነት ጥርቃሚዎች አንዱ መሰልኩህ እንዴ?»

«ዘበኛው በካቴና አሰረው። ለዚህ ብልግናህ ዋጋህን ታገኛለህ፣»

ሁለቱ መኮንኖች ቃላት ተለዋወጡ። የመርከቡ ካፒቴን ለአንድ የበታች

t.me/OLDBOOKSPDF

መኮንን እንድ ትዕዛዝ ሰጠና ከዚያ ሔደ።

ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ፣ የጨው ውሃ የተሞላበት አንድ የእንጨት ባልዲና ውፍረቱ ከንድ የሚያክል ገመድ የያዘ እንድ ግዙፍ መርከበኛ ብቅ አለ። ሮሚዮ እስክ መጨረሻው ድረስ በማነነበስ ተንበርክኮ ታስሯል። መርከበኛው ገመዱን ባልዲው ውስጥ ነክረና ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም ምስኪኑን ሰው ከመቀመጫው እስክ ጀርባው ዝማ እያለ አግድም ይገርፈው ጀመር። ከከንፈሩ አንድ ድምፅ አይወጣም፣ ግን ደሙ በመቀመጫው መውረድ ጀመረ። እንደ መቃበር ቦታ ረጭ ባለው ፀጥታ ውስጥ አንዲት የተታውሞ ጩኸት ከአኛ ከፍል በኩል «አናንተ ውሻዎች!» ስትል አስተጋባች።

እኛም ለሰበብ እንዲመቸን የፈለግነው ይህንኑ ስለነበር፣ «ነፍሰ ገዳዮች!» የውሻ ልጆች! ብስብሶች!» አልናቸው። አነርሱ ዛቻቸውን በጨመሩ መጠን እኛም ጩኸታችንን ጨመርን። ከዚያም አዛዡ ድንጥት እንደዚህ ሲል ጮኸ።

«የሞተሩን እንፋሎት ልቀቁባቸው!» ሽከርከሪዎቹ ተከፍተው የእንፋሎቱ ግፊት እየፈነዳ በደረቶቻችን ላይ ሲያርፍ ኃይሉ በወለሉ ላይ ይወረውረን ጀመር። ተሸበርን። የተቁቀሉት ሰዎች መጮህ አልቻሉም። የቆየው ከአንድ ደቂቃ ያነሰ ነበር፣ ግን ማንኛውም ሰው ድንጋጤ ዋጠው።

«አናንተ ችግር ፈጣሪዎች፣ የሚገባችሁን እንዳገኛችሁ ተስፋ አለኝ። ምንም ነገር ይሁን እንፋሎቱን አስፍተዋለሁ። ግልጽ ነው? አሁን ተነሡ!»

ከባድ ቃጠሎ የደረሰባቸው ሦስት ሰዎች ወደ ሕክመና ከፍል ተወሰዱ። ሲገርፉት የነበረውንም ልጅ ወደ እኛ ከፍል መለሱት። ከስድስት ዓመታት በኋላ ከእኔ ጋር በማምለጥ ላይ እንዳለ ለመሞት በቃ።

በዐሥራ ስምንት ቀን ውስጥ፣ ስለ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት መረጃዎች ለመቅሰም ሰፊ ጊዜ አግኝቷን ነበር። ጁሎ ከተነበየው ምንም ነገር የተለወጠ አልነበረም። እንዲያውም በተሻለ ሁኔታ አብራርቶታል።

ለምሳሌ፣ ከባሕር በግምት ሰባ አምስት ማይል ርቀት ላይ ማሮኒ ከተባለ እንድ ወንዝ ቅዱስ ላውረን ደ ማሮኒ የተባለው መንደር እንደሚገኝ ገልጾልናል። ጠባይ ማረሚያው የሚገኘው እዚሁ መንደር ውስጥ ነው። የቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤቶች ዋና መሥሪያ ቤት ነው። በየደረጃቸን የሚከፋፍሉንም ከዚያ ቦታ ነው። ልማደኞች አሥረኞች በቀጥታ የሚሔዱት ከዚያ ዘጠና አምስት ማይል ርቀ ከሚገኝ ቅዱስ ዮሐንስ ከተባለ ጠባይ ማረሚያ ነው። የቀሩት በሦስት ቡድን ይከፈላሉ። በጣም አደገኛ የሆኑት ወዲያው እንደ ደረሰን ይጠራሉ። ወደ ደሳሊዩ ደሴቶች አሰኪዛወሩ ድረስ ሥነ ሥርዓት ከፍል ውስጥ ተቀምጠው ይጠባበቃሉ። የቅጣታቸውን ዘመን አስኪጨርሱ የሚታሠሩት እዚያው ነው። ደሴቶቹ ከቅዱስ ላውረን ሦስት መቶ ማይልና ከካየን ደግሞ ስድሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማይል ርቀት ላይ ነበሩ። አሥረኞች በብዛት ወደ ዲያብሎስ ደሴት አይሔዱም፤ እዚያ የሚሔዱት የፖለቲካ እሥረኞች ናቸው።

«ሁለተኛው የአደገኛ እሥረኞች ቡድን የአትክልት ቦታዎችና፣ የእርሻ ሥራዎች ላይ ለመመደብ በቅዱስ ላውረን ይቆያሉ፤ አስፈላጊም ከሆነ በጣም መጥፎ ወደሆኑት ፎሬስትሴር፣ ሻርቪኝ፣ ካስኪድ፣ ከሪከ ሩገርና «ወርባ ሁለት ኪሎ ሜትር» የሞት ካምፕ፣ ተበለው ወደ ሚጠሩ ሠፈሮች ይላካሉ።

«ከዚያም የተለመዱ ከፍልፍሎች አሉ። የሚያገለግሉት በአስተዳደሩ ውስጥ ሲሆን፣ በኩሽና ቤቶች፣ መንደሩን ወይም ካምፑን በማጽዳት፣ ወይም እንደ አናጢነት፣ ቀለም ቀቢነት፣ ብረታ ብረት ሠራተኛነት፣ የኤሌክትሪክ ሠራተኛነት፣ ፍራሽና፣ ልብስ ሰፊነት፣ ልብስ አጣቢነት ወዘተ . . . ይሠራሉ።

«ለማንኛውም ዕውነቱ የሚታወቀው እዚያው በምንደርስበት ሰዓት ነው። ከተጠራችሁና ወደ አንድ ከፍል ከተወሰዳችሁ፣ ወደ ደሴቶቹ ሐዳችሁ ልትታሠሩ ነው ማለት ነው። ይህም ከሆነ ለማምለጥ ያላችሁን ምኞት ሙሉ በሙሉ አርግፍ አድርጋችሁ መተው ይኖርባችኋል ማለት ነው። ከዚህ ለመዳን ብቸኛው መንገድ በፍጥነት ጉልበትህን ወይም ሆድህን ወግተህ ሰትቆስል ነው፣ ከዚያም ወደ ሆስፒታል ይልኩሃል። ከዚያ ማምለጥ ትችላለህ። ግን የፈለገው ነገር ቢሆን ወደ ደሴቶቹ አንዳትሔድ። ሌላው ተስፋ ደግሞ ወደ ደሴቶቹ የሚጓዘው ጀልባ ለመነሣት ካልቸኮለ፣ በሕክምና ከፍል ለሚሠራ አንድ የወህኒ ቤት ጤና ረዳት ገንዘብ ትሰጥና አንድ የተርፔንታይን መርፌ ይወጋሃል። ወይም በሽንት የተነከረ የጸጉር ዘለላ ከቆዳህ ወስጥ አንዲኪትልህና አካላትህን በቁስል አንዲነፈርቅ ማስደረግ ነው፣ ወይም ትንሽ ከብረ ሰማይ በአፍህ እንድትስብ ይሰጥህና ከዚያም ትኩሳትህ አንድ ሙቶ አራት ዲግሪ ሆኗል ብሎ ለዶክተሩ ይነግርልሃል። እዚህ በምትቆይባቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ እንደ ምንም ብለህ ሆስፒታል ለመግባት ተጣጣር።

«እንድትሔድ ካልተጠራህና፣ በዚህ ካምፕ ምሽግ ወደ ኋላ ከቀረህ፣ አንድ ነገር ለማድረግ ጊዜ ይኖርሃል። ያም ቢሆን ግን፣ በካምፑ ውስጥ ሥራ ላለመያዝ ሞክር። ለአሠሪው ጉቦ ብትሰጠው በመንደሩ ውስጥ የሠገራ ጽዳት ሠራተኛ፣ ወይም መንገድ ጠራጊ፣ አለበለዚያም ቦርጌሶች ከሚያካሔዱት አንድ የእንጨት መሰንጠቂያ ሞተር ቤት ውስጥ መሥራት ትችላለህ። እግረ መንገድህን ሲሠራ በምትመላለስበት ወቅት በመንደሩ ውስጥ ነጻ ወጥተው ከሚኖሩ እሥረኞች ወይም ቻይናውያን ጋር ለመገናኘት ዕድሉ ይኖርሃል፤ ስለሆነም የምታመልጥበትን ዘዴ ለማመቻቸት ዝግጅት ሊጀምሩልህ ይችላሉ። በመንደሩ አካባቢ ከሚገኙት ካምፖች እንዳትጠጋ። እዚያ ማንኛውም ሰው ይችላሉ። በመንደሩ አካባቢ ከሚገኙት ካምፖች እንዳትጠጋ። እዚያ ማንኛውም ሰው ቶሎ ይሞታል። ማንም ሰው ሦስት ወር የማይቆይባቸው ካምፖች አሉ። በቀን ሩብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀላድ ስፋት ያለው አንጨት በጫካው መካከል ያስቆርጡሃል።»

በመላው ጉዟችን ውስጥ ጆሎ አነዚህን የመሳሰሉ ውድ መረጃዎች ሲያስኮመኩመን ቆየ። ራሱም ተዘጋጅቶ ነበር። ተይዞ የተመለሰ አምላጭ እንደመሆኑ መጠን፣ በቀጥታ ወደ ጨለማ ማንብ እንደሚሔድ ዐውቆታል። እንደዚሁም በጣም ትንሽ ሆና ታይለኛ ሰለት ያላትና ከማነሷም ብዛት በጠንዙብ መደበቂያ ጉቡው ውስጥ ያስቀመጣት አንዲት ሴንጢ ነበረችው። አንደ ወረድን ጉልበቱን ለመቁረጥ አቅዷል። ከዚያም ጀልባውን በመልቀቅ ላይ እንዳለ በሰው ሁሉ ፊት ከመረማመጃው ላይ ሲወድቅ ነበር። ከመሸጋገሪያው ድልድይ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል እንደሚወስዱት ተስፋ አድርጓል። እንዳለውም ሆኖለት ነበር።

ቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ

አንዳንድ ዘበኞች በዕረፍት ላይ ስለነበሩ ልብሶቻቸውን ለመቀየር ቻሉ። በመለዮአቸው ሩንታ የቅኝ ግዛት ኬፓቸውንና ኮሜጭ ዩኒፎርም ለብሰው ተመለሱ። «ወዲያው መቃረባችን ነው» አለ ጆሎ። የሞተር ማናፈሻውን ሰለዘጉት፣ መቅዘፉ በጣም ከፍተኛ ነበረ። በዚያው ውስጥ ጫካ ለማየት ቻልን። እንግዲህ ማሮኒ ደረሰን። ድንግሉ መሬት በደማቅ አረንጓዴ ተከሎች የተሸፈነ፣ ጭቃማ ውሃ ነበረው። በመርከቡ ጡሩምባ አሞራዎች ሰለ ተረበሹ ሸሹ። አሁን የምንሔደው በጣም ዝግ ብለን ስለነበር፣ ረጅም ሆኖ ጥቅጠቅ ያለውን በአረንጓዴ ልምላሜ የተሸፈነ አካባቢ ጥርት አድርገን ለመመልከት ሰፊ ጊዜ አገኘን። ከዚያም በቆርቆሮ ጣሪያና በእንጨት የተሠሩትን የመጀመሪያዎቹን ቤቶች አየን። ከመዝጊያዎቻቸው ፊትለፊት ጥቁር ወንዶችና ሴቶች ቆመው መርከቡ ሲያልፍ ይመለከታሉ። በየጊዜው ሰው አየጫነ በመምጣት ሲቆምና ሲያራግፍ ማየት ለምደዋል። ለመቆም መቃረባችንን የነገሩን መርከቡ ያምባረቃቸው ሦስት ጡሩምባዎችና የሚፈታቱት ቡለኖች ቅጭልጭልታ ነበር። ከዚያም ማንኛውም ድምፅ ጸጥ አለ። ከጸጥታው መስፈን የተነሣ የአንዲት ዝንብ ከንፎች ሲርገበገቡ እንኳ ለመስማት ይቻል ነበር።

ማንም አይናገርም። ጆሎ ሱሪውን ከጉልበቱ ላይ ቀደደና ጫፉን ወደ ላይ ጠቀለለው። ሰውነቱን የሚቆርጠው ወደ መሸጋገሪያ ድልድዩ ሲደርስ ብቻ ነው። ስለሆነም የደም ነጠብጣብ ምልክት እንዳይታይ ይረዳዋል። ዘበኞቹ መዝጊያውን ከፈቱና በሦስት ረድፍ አሠለፉን። ዴጋና እኔ፣ ጆሎ ከመካከል እንደሆነ አራተኛው መስመር ላይ ነበርን። እስከ ድልድዩ ድረስ ወጣን። ወቅቱ ከሰዓት በኃላ ስምንት ሰዓት ስለነበር፣ እንደአሳት የምትፋጀው ፀሐይ ዐይኔንና የተላጨ ጭንቅላቴን አንጫረረችኝ። በመርከቡ ወለል ላይ ተሰለፍንና ከዚያም ወደ መሸጋገሪያው ድልድይ አመራን።

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጀመሪያው ሰው የመሸጋገሪያውን ድልድይ እንደነካ በጠቅላላው ጥድፊያ ሆነ። ጓዙን እኔ ያዝኩለትና ጁሎ የጉልበቱን ቆዳዎች በሁለት እጁ ይዞ ጩቤውን ወደ ውስጥ በመሰግሰግ ሦስት ወይም አራት ኢንች ሥጋ ቆርጦ አወጣ። ከዚያም ጩቤውን አቀበለኝና ጥቅሉን ተሸከመ። የመሸጋገሪያውን ድልድይ እንደ ረገጥን ቁልቁል ተንከባለለና ወደቀ። እንሥቱው ሲያዩት ተንድቶ ስለነበረ ሁለት ቃሬዛ ተሸካሚዎች ጠሩ። የድራማው ጨዋታ ልክ እንደ ታቀደው ተከናውኖ ነበር።

እኛን ለመመልከት ልዩ ልዩ ቀለም ያለው ሕዝብ ተሰብስቧል። ጮቤሮች፣ ከልሶች፣ ሕንዳውያን፣ ቻይናውያን፣ በዐፅማቸው የቀሩ ነጮች፣ (ምናልባት ነፃ የወጡ አሥረኞች ይሆናሉ) ወደ መሬት ወርደን ከሌሎቹ ጋር ስንሰለፍ አያንዳንዳችንን ይመለከቱናል። ከዘበኞቹ በስተጀርባ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሲቪሎች፣ የበጋ ቀሚስ የለበሱ ሴቶችና የቅኝ ግዛቸ ኬፕ የደፉ ልጆች ቆመዋል። እነርሱም የሚመለከቱት እንደዚሁ አዲሱን መጤ ነበር። ሁለት መቶ ስንሞላ ወደፊት በሰ፡ፍ እንጓዛለን። ዐሥር ደቂቃ ያህል እንደ ተጓዝን አንድ ሕንፃ ፊትለፊት ደረስን። በግ፡ ፉ የእንጨት መዝጊያው ላይ «የቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ ጠባይ ማረሚያ - ለ3000 ሰዎች የተሠመነ» የሚል ተጽፎበት ነበር። በሩ ተከፈተና በዐሥር ረድፍ እንደ ተሰለፍን ገባን። «አንድ ሁለት፣ አንድ ሁለት፣ ተሰለፍ!» የእኛን መድረስ በዛ ያሉ አስረኞች ይመለከታሉ። በድንጋይ ላይ ቆመው እየተንጠራሩ ያዩን ነበር።

ከግቢው መካከል ስንደርስ አንድ ዘበኛ፣ «ቁሙ! ጥቅሎቻችሁን ከፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ! አንተ እዚያ ያለኸው ባርኔጣዎቹን አስተላልፍ!» ብሎ ጮኸ። ለእያንዳንዳችን አንድ የሰሌን ባርኔጣ ተሰጠን። ግሩም ነው እንፈልገዋለን። ከፀሐዩ ቃጠሎ የተነሣ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ሕሊናቸውን ስተው ነበር። የጥበጣበ ማዕረግ ምልክት የለጠፈ አንድ ዘበኛ በእጁ አንድ የሰም ዝርዝር ሊሰት ይዞ ነበር። ዴጋና እኔ እርስ በእርሳችን ተያየን። ጁሎ ምን ተናግሮ እንደነበር ትውስ አለን። ላ ጊቱን ጠሩና፣ «በዚህ በኩል!» ብለው ሁለት ዘበኞች አጅበው ወሰዱት። ሳንቲኒን፣ ጅራሶሎንና ሌሎቹንም በዚሁ ዓይነት ወሰዷቸው።

«ጁልስ ፒኛርድ!»

ጁልስ ፒኛርድ ቆስዷል። ሆስፒታል ውስጥ ነው» ተባለ።

«እሺ፣ አሁን በጥንቃቄ አዳምጡ። ስማችሁን ስጠራ ጥቅሎቻችሁን በትከሻችሁ እንደያዛችሁ ከሰልፉ በመለየት ወደ ቢጫው ግንብ ፊት ፊት ሔዳቸሁ ትቆማላችሁ። ቁጥር አንድ ነው» አለ።

አከሌ አከሌ፣ አቤት ወዙተ . . . ዴጋ፣ ካሪየና እኔ ከግንቡ ፊትለፊት ከተሰለፉት መካከል ነበርን። መዝጊያው ተከፈተና ርዝመቱ ሰባ ጫማ ከሆነ እንድ አዳራሽ ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገባን። በመካከሉ ሰባት ጫማ ስፋት ያለው መተላለፊያና በግራና በቀኝ በአዳራሹ ርዝመት በተርታ የቆሙ የብረት ምሰሶዎች ነበሩ። ከአግዳሚዎቹ ወደ ግድግዳዎቹ የሸራ ተንጠልጣይ አልጋዎች ተዘርግተው እያንዳንዱ አልጋ ላይ አንድ ብርድ ልብስ ነበረበት። ወደ መረጥከው መሔድ ትችላለህ። ዴጋ ፒየሮ ለፉ፣ ሳንቶሪ፣ ግራንዴና እኔ ተርታውን አከታትለን ያዝንና፣ ወዲያውኑ ጓዛችንን ማሰናዳት ጀመርን። እስከ አዳራሹ መጨረሻ ሔድኩ። መታጠቢያ በስተቀኝ፣ መጸዳጃ ቤት በስተግራ አለው። የቧንቧ ውሃ የለም። በመስኮቶቹ ቋሚ ፍርግርጎች ጥግ ተለጠፍንና የሚቀጥለውን የአሥረኞች መድረስ እንመለከት ጀመር። ከጭንቀታችን ተገላግለናል። ለመታሰር-አንደማንሔድ ግልጽ ሆኖ ነበር። ምክንያቱም እዚህ አዳራሽ ውስጥ አብረን ሆነናል። ብንታሠር ኖሮ ጁሎ ነግሮን እንደነበረው ቀደም ብለን ወደ ልዩ ክፍሎች ውስጥ እንገባ ነበር።

በምድር ወገብ ሲመሽም ሆነ ሲነጋ ቅፅበታዊ ነው። ዓመቱን በሙሉ ከቀን ወደ ሌሊት የምትሸጋገረው በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ ወቅት ነው። በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ከመቅፅበት ጨለማ ይሆናል። ስለሆነም በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል፣ ሁለት ሽማግሌ እሥረኞች ሁለት የጋዝ ፋኖሶች አመጡና በጣራው ከሚሾኝ አንድ ሜንጦ ላይ አንጠለጠሉ። የሚሰጡት ብርሃን በጣም ደብዘዝ ያለ ነበር። የምሽጉ ሦስት አራተኛ ሙሉ በሙሉ በጨለማ ተዳፈነ። ሦስት ሰዓት ላይ ማንኛውም ሰው ተኛ። የጉዞአችን ዜና አለፈና በሙቀት ተዋጥን። ሲሞትንፈስ አየር አልነበረም። ማንኛውም ሰው በካናቴራው ብቻ ቀረ። እኔ ከዴጋና ፒየሮ ለፉ መካከል ነበርኩ። ለትንሽ ጊዜ ተንሸካሸከንና ከዚያም እንቅልፍ ወሰደን።

በሚቀጥለው ቀን ለቆጠራ የሰዓት ደወል ሲጮህ ገና ጨለማ ነበር። ሁሉም ሰው ተነሣና ፊቱን ታጥቦ ልብሱን ለበሰ። ቡናና አንድ ቁራጭ ዳቦ ተሰጥቶን ነበር። ከግድግዳው ጋር የተያያዘ አንድ ጣውላ ለመመገቢያ ገበታና ለጓዞቻችን መደርደሪያ አገለገለን። ሦስት ሰዓት ላይ ሁለት ዘበኞችና ማዕረግ የሌለው ነጭ ልብስ ብቻ የለበሰ አንድ ወጣት እሥረኛ ተያይዘው ገቡ። ሁለቱ ዘበኞች ኮርሲካውያን ስለነበሩ፣ ከሀገሮቻቸው ሰዎች ጋር በኮርሲካውያን ቋንቋ ይነጋገራሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ የሕክምና ከፍሉ የአሥረኛ ጤና ሪዳት አዳራሹን መዘር ጀመረ። እኔ አጠገብ ሲደርስ፣ «እንደምን አለህ ፓፒ? አታስታውሰኝም እንዴ?» አለ።

«አላስታውስህም።»

«ሲየራ ነኝ። አልጀሪያዊው። በፓሪስ ዳንቴ ውስጥ ዐውቅሃለሁ።»

«አሃ፣ አዎ፣ አሁን አስታወስኩህ። ግን የመጣኸው ከ1929 በፊት ነበር። አሁን 1933 ነው። አሰካሁን እዚሁ ነህ?»

«አዎ፣ ከዚህ ቦታ ለመውጣት እንደዚህ ቀላል አይደለም። ለምን አምኖል

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለህ አታመለክትምን? እርሱስ እንዴት ነው? ማን ነው?»

«ዴጋ። የእኔ ጓደኛ ነው።»

«እርሱንም እንዲመረመር አመዘግበዋለሁ። አንተ ፓፒ ተቅማጥ አለብኝ በል። አንተ ሽማግሌው ሰው ደግሞ በአሰም በሽታ ተለከፈያለሁ በል። በአምስት ሰዓት አያችኋለሁ። ላነጋግራችሁ እፈልጋለሁ።» በጣም እየፈሽ ዙረቱን ቀጠለ። «ሕዚህ የታመመ ሰው አለ?» አንድ ሰው ጣቱን ከቀሠረ፣ ወደ እዚያው ሔዶ ሊስት ውስጥ ይመዘግበዋል። ተመልሶ በእኛ በኩል ሲያልፍ በጣም የገረጀፈና በጸሐይ የበለዘ አንድ ሽማግሌ ዘበኛ አጅቦት ነበር።

«ፓፒዮ፣ የሕከምና ከፍሉ ዘበኛ አለቃዮን ባርቲሎኒን ላስተዋውቅህ እፈልጋሁ። አቶ ባርቲሎኒ፣ ይኸ ሰውና ያ እዚያ ማዶ ያለው፣ ሁኔታቸውን የነገርኩዎት ጓደኞቼ ናቸው።»

«እሺ ሲየራ፣ በጉብኝቱ ወቅት እናመቻችላቸዋለን። በእኔ ላይ ጣለው።»

በአምስት ሰዓት እኛ ዘንድ መጡ። ዘጠኝ ነበርን። በግንባቹ መካከል ካምፑን አቋረጥንና አንድ የቀይ መስቀል ምልክት ያለበት አዲስ ነጭ ቀለም ከተቀባ ሕንፃ ደረስን። ወደ ውስጥ ገባንና በግምት ሰድሳ የሚሆኑ ሌሎች ሰዎች ከሚገኙበት አንድ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ተገኘን። በአያንዳንዱ ጥግ ዘበኞች ቆመዋል። ነጥብ የሌለበት ነጭ ሽርጥ ለብሶ ሲየራ ብቅ አለ። «አንተ፣ አንተና አንተ ወደ ውስጥ ሒዱ» አለ። የዶክተር መመርመሪያ ከሚመስለው ከፍል ውስጥ ገባን። ሲየራ ከሦስት ሽማግሌ ሰዎች ጋር በስፓኝ ቋንቋ ተነጋገረ። ከሰፓኞቹ መካከል አንደኛውን ያኔው አስታወስኩት። ፓሪስ ውስጥ በካፌ ዴ ማድሪድ መጠጥ ቤት ሦስት አርጀንቲናውያን ገድሎ የነበረ ፊርናንዴዝ የሚባል ሰው ነበረ። ትንሽ ቃላት ተለዋወጡና ወደ ዋናው አዳራሽ ወደሚከፈት አንድ ገላ መታጠቢያ ክፍል ሲየራ ይዞት ገባ። ከዚያም ወደ እኔ ተመልሶ መጣና፣ ፓፒዮ በጣም ደስ ስላለኝ ልቀፍህ። ለአንተና ለጓደኛህ አንድ ነገር ማድረግ ችያለሁ። አናንተ ሁለታችሁም አሥረኞች ናችሁ። ቆይ፣ ልናገር! አንተ ፓፒ፣ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራትና አንተ ዴጋ ደግሞ አምስት ዓመት ነው። ትንሽ ገንዘብ አላችሁ?»

«አዎ!»

«አያንዳንዳችሁ አምስት መቶ ፍራንክ ስጡኝና አንተ ፓፒ፣ ነገ ጧት ሆስፒታል እንድትገባ አደርጋለሁ። አንተ ዴጋ ደግሞ መዝጊያ ቁርቁርና፣ አለበለዚያም ከሁለት አንዳቸሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፣ ዘበኛውን ጥሩና ዴጋ በአየር ታፍኗል ብላችሁ ጤና ረዳቱን እንዲጠራላችሁ አመልክቱ። ለሌላው እኔ አስብበታለሁ። አንድ ነገረ ብቻ አጠይቅሃለሁ ፓፒዮ። ለማምለጥ ከፈለግክ ቀደም ብለህ አስጠንቅቀኝና እኔ እዚያው እገኛለሁ። ለአያንዳንዳችሁ አንድ መቶ ፍራንክ በማስከፈል በሆስፒታሉ ውስጥ አንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳምንት ያቆዩዋቸኋል። ስለዚህ ፈጠን ብላችሁ መንቀሳቀስ ይኖርባቸኋል። ፌርናንዴዝ ከመታጠቢያ ክፍል ወጣና አምስት መቶ ፍራንክ ለሲየራ ሰጠው። እኔም ወደ ውስጥ ገባሁና ስመለስ እንድ ሺህ ፍራንክ ሳይሆን አንድ ሺህ አምስት መቶ ፍራንክ ሰጠሁት። ተጨማሪውን አምስት መቶ አልቀበልም አለ። እኔም አልገፋፋሁትም። «ለንዘቡ» ለዘበኞቹ ነው። ለራሴ ምንም ነገር አልፈልግም፣ ጓደኞች ነን። አይደለንም እንዴ?» አለ።

በሚቀጥለው ቀን ዴጋ ፈርናንዴዝና እኔ ሆስፒታሉ ውስጥ አንድ ሰፊ ክፍል ተገናኘን። ዴጋ ሆስፒታል የገባው አኩለ ሌሊት ላይ ነበር። የሕክምና ክፍል ጤና ረዳቱ ስሙ ቻታል የተባለ የሠላሳ አምስት ዓመት ሰው ነበር። በእኛ በኩል ስላለው ሁኔታ ሲየራ ምስጢሩን በሙሉ አስረድቶታል። ለዶክተሩ ሲያቀርበን፣ እኔን አሜባ የበጣጠሰኝ በማስመሰል አንድ የሠገራ ምርመራ ውጤት ሊያሳየው ነበር። በዴጋ በኩልም ዶክተር ከመምጣቱ በፊር ደቂቃ ቀደም ብሎ ትንሽ ከብረ ሰማይ አቃጥሎ ፎጣ ጭንቅላቱ ላይ ጣል በማድረግ ጢሱን ወደ ውስጥ እንዲሰበው ነበር። የፈርናንዴዝ ጉንጮች ቅትት ብለው አብጠዋል። ያለማቋረጥ ለአንድ ሰዓት ከወጭና ከውስጥ በጣም በመርፌ ስለ ጠቀጠቃቸው፣ ዕብጠቱ ዐይኖቹን ሳይቀር ሸፍኖት ነበር። ከፍሉ የሚገኘው ከሆስፒታሉ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ሲሆን፣ ብዙዎቹ በደም ተቅማጥ የተያዙ፣ ሰባ ያህል ሕመማን ይገኙበታል። ጁሉ የት እንዳለ ጤና ረዳቱን ጠየቅኩት። «ከመንገዱ ባሻገር ካለው ሕንፃ ውስጥ ነው፤ መልዕክት ወደ አርሱ እንዳደርስልህ ትፈልጋለህ?» አለ።

«ሉም ፓፒዮና ዴጋ እዚህ ናቸውና በመስኮት በኩል ብቅ ብለህ እንተያይ፣ ብለህ ንገረው።»

ጤና ረዳቱ እንደ ፈለገ መውጣትና መግባት ይችላል። መዝጊያውን ሲቆረቁር አንድ ዐረብ ከፈተለት። ዐረቡ አስረኛ ቢሆንም በቁልፍ ያዥነት እያገለገለ ዘበኞቹን ይረዳል። ከመዝጊያው ጎንና ጎን ጠመንጃዎቸውን ከጭኖታቸው ላይ አጋድመው ሦስት ዘበኞች ተቀምጠዋል። መስኮቶቹ ቋሚ ብረቶች ስለነበሩ፣ እንዴት አድርገን እንደምንቆርጣቸው ጨንቆኛል። በእኛና በጁሉ ሕንፃ መካከል በውብ አበቦች ያሸበረቀ አንድ የአትክልት ቦታ ነበር። ጁሉ «ጎበዞች» ብሎ በቾክ የጻፈባት አንዲት ጠፍጣፋ ድንጋይ በእጁ እንደያዘ በመስኮቱ በኩል ብቅ አለ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ደግሞ ጤና ረዳቱ አንድ ደብዳቤ ከአርሱ አመጣልኝ።

«ወደ እናንተ ከፍል ለመምጣት እየሞከርኩ ነው። ይህም ካልሠራ እናንተ ወደ እኔ ለመምጣት ሞክሩ። በክፍላችን ውስጥ ጠላቶች አሉን በሉ። ታዲያስ፣ ሆስፒታል ገባችሁ? በርቱ፣ በቀላሉ እናታልላቸዋለን።»

በቦሊየ አሥር ቤት ፈንድቶ በነበረው ግርግር አብረን ያሳለፍነው መከራ

t.me/OLDBOOKSPDF

በመካከላችን አንድ ከፍተኛ መተሳሰር መሥርቷል። ጁሎ በእንጨት መዶሻ የተካነ ነበር። ስለዚህም ነበር፣ «ብለ መዶሻው ሰው» የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው። አንዴ ምርጥ የሆኑ ጌጣጌጦች ለትዕይንት በመደብር መስኮት ላይ እንዳሉ አውቶሞቢሉን እያሽከረከረ በጠራራ ፀሐይ ወደ ጌጣጌጡ መደብር ያመራል። አንድ ግብረ አበሩ መኪና ውስጥ ይቀመጥና ሞተሩን እያሠራ ይጠብቃል። ከትልቁ መዶሻው ጋረ ጁሎ ይወጣና፣ በእንድ ምት መስኮቱን አነካክቶ ለማፈስ የቻለውን ያህል የጌጣጌጥ ሣጥኖች ጋፍፎ ወደ መኪናው ዘልሎ ይገባና፣ በከፍተኛ ፍጥነት ተፈትልኮ ይበርራል። በሊሐቫር፣ በቱር፣ በእንገርስና በሊዮን ይህ ድርጊቱ ተሳክቶለት ነበር። ከዚያም፣ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን፣ በፓሪስ የታወቀ አንድ ጌጣጌጥ መደብር ወስጥ ይገባና አንድ ሚሊዮን ፍራንክ የሚገመት ዋጋ ያላቸው ጌጦች ይዞ ይነጉዳል። እንዴት ወይም በምን እንደተነቃበት ግን ፍጹም አልነገረኝም። ሐያ ዓመት ተፈርዶበት ነበር። በአራተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ አመለጠ።

ሆስፒታል ውስጥ ከገባን አሁን አንድ ሳምንት ሆኖን ነበር። ለሌላው ሳምንት ከፍያ ትላንት አንድ ሺ ፍራንክ ለቻታል ሰጠሁ። ጓደኛ ለማፍራት ለሁሉም ሰው ትምባሆ እንጋብዛለን። የማርሲይ ተወላጅ የሆነ ካሮራ የተባለ አንድ የስድሳ ዓመት ሽማግሌ አሥረኛ፣ ከዴጋ ጋር ጓደኝነት አበጀ። እንደ አማካሪው አድርጎት ነበር። ብዙ ገንዘብ ካለህና በመንደሩ የሚገኙ ሰዎች ይህንን ካወቁ፣ (ለፈረንሣይኛ ጋዜጦች ምስጋና ይግባቸውና ማንኛውም ሰው ዜና ያገኘ ስለነበር) ነጻ የወጡት አሥረኞች ለገንዘብ መደበቂያ ቱቦህ ሲሉ ስለሚገድሉህ፣ አመልጣለሁ ብለህ ባትሞክር ይሻላል» እያለ ይመክረው ነበር። ከካሮራ ጋር የሚያደርገውን ውይይት ዴጋ ለእኔ ደበቀኝ። ሽማግሌው ሰው ሐያ ዓመት እዚሁ ተቸክሎ ጊዜውን ያጠፋ ከንቱ መሆኑ ግልጽ እስከሆነ ድረስ ዴጋ ማመን እንደማይኖርበት ብነግረውም ሊሰማኝ አልፈለገም። ሽማግሌው በሚያነበንብለት ወሬ ዴጋ ተሰብኮ ስለነበር፣ ሐሳቡን ለማስለወጥ አስቸጋሪ ወቅት ገጠመኝ።

ጋልጋኒን ወደ እኔ እንዲልከልኝ አንድ ማስታወሻ ለሲያራ ላከሁ። ብዙ ጊዜ አልወሰደም። በሚቀጥለው ቀን ጋልጋኒ ከሆስፒታሉ ሌላ ክፍል ውስጥ ገባ። እንዴት አድርጌ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን መልሼ ልስጠው? ለማምለጥ ዕቅድ ቢኖረው ነው ብሎ እንዲገምት ቻታልን ለማሳመን ለመጨረሻ ጊዜ ጋልጋኒን ማነጋገር እንደፈለግኩ ነገርኩት። ዘበኞቹ ተረኝነት በሚለዋወጡበት ወቅት ልክ ለስድስት ሰዓት አምስት ገዳይ ወደ እኔ ሊያመጣውና ሊያገናኘን ያሰበው ያለምንም ከፍያ ነበር። ጋልጋኒ ስድስት ሰዓት ላይ በመስኮቱ በኩል ብቅ ሲል፣ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን በቀጥታ እጁ ላይ አስቀመጥኩለት። አዚያው እንደቆመ አለቀሰ። ከሁለት ቀን በኋላ ባለ አምስት ሺ ፍራንክ ኖቶች የተጠቀለሉበት አንድ መጽሔትና «አመሰግናለሁ» የምትል አንዲት ቃል

t.me/OLDBOOKSPDF

ላከልኝ።

መጽሐፉን ያመጣልኝ ቻታል ፕንዘቡን አይቷል። ምንም ነገር አላለም፣ ግን ትንሽ ላበረከትለት ሞከርኩ። አልቀበልም አለ።

«ፈናመልጥ ፈልገናል፣ እኛ ጋር መምጣት ትፈቅዳለህ?»

«አልፈልግም ፓፒየ። ከሌሎች ጋር ተነጋግሬአለሁ። ጓደኛየ ነጻ እስኪሆን ድረስ ከእሁን ጀምሮ ለአምስት ወራት ያህል ማምለጥ ልሞክር አልፈልግም። የእኛ ምርጫ በተጠናከረ ሁኔታ የሚዘጋጅና አርግጠኛ የሆነ ነው። አናንተ ለምን እንደ ቸኮላችሁ ገበቶኛል። የሆስፒታል ሕመማኖች ናችሁ። ሆኖም እነዚህ ቋሚ ፍርግርግ ብረቶች በጣም አስቸጋሪ ሊሆኑባችሁ ነው። ስለምፈራ ልረዳችሁ አልቻልኩም። ራሴን አደጋ ላይ መጣል አልፈልግም። ጓደኛዬ አስኪዘጋጅ ድረስ እዚሁ ጸጥ ብዬ ለመጠበቅ ፈልጌያለሁ።»

«በጣም ጥሩ ነው ቻታል። እንደዚህ በመሰለው ወቅት አርስ በርሳችን ግልጽ መሆን አለብን። ዳግመኛ አላነሣብህም።»

«ግን ያም ቢሆን መልዕክቶችህን አደርሳለሁ፣ ምስጢርም አላከሃለሁ።»

«አመሰግናለሁ ቻታል።»

«በዚያ ሌሊት የአውቶማቲክ ጠመንጃ ሩምታ ተኩስ ሰማን። በሚቀጥለው ቀን ጧት ጁሎ አመልጦ መሐዱን ተረዳን። አግዚአብሔር ይከተለው። ግሩም ጓደኛዬ ነበር። አንድ ከፍት ቦታ አይቶ የተቻለውን ተጠቅሞበት መሆን አለበት።

ከዐሥራ አምስት ዓመት በኋላ፣ በ1948 ወደ ሐይቲ ሔጄ ነበር። የሔድኩትም ከአንድ ቬአዙዌላዊ ሚሊዮኔር ጋር ሕጋዊ ቁማር ማጫወቻ፣ ጠረጴዛዎቹን ለመከራየት ከድርጅቱ ፕሬዚዳንት ጋር ኮንትራት ለመፈራረም ነበር። አንድ ቀን ምሽት፣ ሻምፓኝ ሰንጠጣ ከነበረበት የግታ ከበብ በመውጣት ላይ እንዳለን፣ ከእኛ ጋር ከነበሩት ኮረዳዎች ውስጥ እንደ ከሰል የጠቆረችና ደግሞ እንደ ማንኛውም ጥሩ የፈረንሣዊ ቤተሰብ የጠለቀ ዕውቀት ያላት ወጣት «አያቴ አንድ የታወቀች ጠንቋይ መነኩሲት ናት። የምትኖረው ከአንድ ሽማግሌ ፈረንሣዊ ጋር ነው። ያመለጠው ከካዮን ሲሆን፣ ከአርሷ ጋር በጣም ረጅም ጊዜ ኖሯል። ሁልጊዜ እንደ ሰከረ ነው። ስሙ ጁልስ ማርቶው ይባላል» አለችኝ።

ወዲያውኑ ጥርጣሬ ያዘኝ። «አሁኑኑ አያትሽን አሳይኝ።»

የታከሲ ሾፌሩን በሐይቲ ቋንቋ እናገረችውና በከፍተኛ ፍጥነት ሸመጠጥን። ቦግ ያለ ሙበራት ያለው አንድ የግታ ከበብ ስናልፍ፣ «አቁም!» አልኩና ወደ መጠጥ ቤቱ ሔጄ፣ አንድ ጠርሙስ ፔርኖ፣ ሁለት ጠርሙስ ሻምፓኝ፣ ሁለት ጠርሙስ የሀገር ውስጥ ራም ገዛሁ። «እንሒድ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀይ ለስላሳ የጡብ ክዳን ያላት አንዲት የምትሞቅ ትንሽ ጎጆ ፊት ለፊት ከባሕሩ ጠርዝ ላይ ቆምን። ባሕሩ እስከ ደረጃዋ ድረስ ያጥባት ነበር። ልጃገረዷ ስትቆረቁረ ሽበት የወረራቸው አንዲት ግዙፍ ጥቁር ሴት መዝጊያውን ከፈቱላት። ቁርጭምጭሚታቸው የሚደርስ አንድ የተንቧለለ ቀሚስ ለብሰው ነበር። ሁለቱ ሴቶች በሀገራቸው ቋንቋ ተነጋገሩ። ከዚያም እሮጊቷ፣ «ግቡ፣ ቤቱ የእናንተው ነው» አሉ።

አንድ የናፍታ ፋኖስ፣ ያችን የጸዳች ጎጆ ብርሃን ሰጥቷታል።

«ጁሎን ለማየት ትፈልጋለህ? ቆይ፣ እየመጣ ነው። ጁልስ! ጁልስ! አንተን ለማየት አንድ ሰው አለ።»

የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ዩኒፎርማችንን ያስታወሰኝን ሰማያዊ ጥብጣብ ያለበት ፒጃማ የለበሰና ባዶ እግሩን የሆነ አንድ ሽማግሌ ብቅ አለ።

«በዚህ ውድቅት ሌሊት እኔን ሊያየኝ የሚፈልገው ማንነው ቡል ዶኒጅ? ፓፒዮ! ሊሆን አይችልም!»

አቀፈኝና፣ «ፋኖሱን ቀረብ አድርጊው ቡል ዶኒጅ፣ የጥንቱ ጓደኛዬን ፊት ማየት አፈልጋለሁ። አዎ፣ አንተው ነህ፣ አንተ አሮጌ! በእርግጥም አንተው ነህ! እንኳን ደህና መጣህ። ቤቴ፣ ያለችኝ ትንሽ ገንዘብ፣ የሚስቴ የልጅ ልጅ፣ ሁሉም ያንተው ናቸው። የምትፈልገውን ለማዘዝ ትችላለህ።»

ፔርኖውን፣ ሻምፓኙንና፣ ሩሙን ጠጣን። አልፎ አልፎ ጁሎ ይዘፋፍናል።

«ሕሀ፣ እንዴት የመሰሉ ጊዜዎች አብረን አሳለፍን ባልንጀራ? ጀብዱን የመሰለ ምንም ነገር የለምኮ! ኮሎምቢያን፣ ፓናማን፣ ኮስታሪካንና ጃማይካን አዳረስኩ። ከዚያ በኋላ መቼውንም ወንድ ከማያገኛት ግሩም ሴት ከቡል ዶ ኒጅ ጋር እዚህ ተቀመጥኩ። መች ትሐዳለህ? እዚህ ብዙ ትቆያለህ እንዴ!»

«አልቆይም። አንድ ሳምንት ብቻ።»

«እዚህ ምን ልትሠራ ነው?»

«የቁማር ጠረጴዛዎቹን በኮንትራት እንዲሰጠኝ፣ ከካሲኖው ፕሬዚዳንት ጋር ለመዋዋል እየሞከርኩ።»

«እስከ ዕድሜ ልክህ እንተን እዚህ አካባቢ ከማቆየት የበለጠ ሌላ ምንም ነገር አልወድም ባልንጀራ። ግን ከዚያ የውሻ ልጅ ጋር ምንም ነገር አትሥራ። ጥሩ ንግድ ማንቀሳቀስህን ሲያይ በደቂቃ ያስገድልሃል።»

«በአንቺ በኩል ደግሞ ቡል ዶ ኒጅ፣ ለቱሪስቶች የሚቀርበውን ሳይሆን ትክክለኛውን የአስማት ትርዒትሽን እዘጋጂ። ለጓደኛየ ዕውነተኛውን ነገር እንድትነግሪው አፈልጋለሁ።»

ጁሎ እንዲያ አመለጠ፣ ግን ዴጋ ፈርናንዴዝና እኔ ገና በመጠባበቅ ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበርን። አልፎ አልፎ በመሰኮቱ ላይ ያሉትን ቋሚ የብረት ፍርግርጎች አፈትሻቸዋለሁ። ዕውነተኞቹ የባቡር ሐዲድ ብረቶች ስለነበሩ በዚያ በኩል ምንም ማድረግ አልቀቻለም። እንዲያውም ገና መዘጊያው አለ አይደል። ሌት ከቀን ሦስት ዘበኞች እዚያው ተመድበዋል። ጁሎ ካመለጠ ጀምሮ ቁጥጥሩ ጠብቋል። የዘበኞቹ መቀያየር ወዲያው ወዲያው ሆኗል። ዶክተሩም የቀድሞው ተግባቢነቱን አቀዝቅዟል። ቻታል ወደ ከፍል የሚመጣው መርፌ ለመውጋትና ሙቀት ለመለካት በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር። ሁለተኛ ሰምንት አለፈና እንደገና ሁለት መቶ ፍራንክ ከፈልኩ።

ዴጋ ከማምለጥ በስተቀር ስለ ማንኛውም ነገር ያወራ ነበር። ትላንት ጨቤዮን አየና፤ «ሕሁንም ይዘሃታል? ለምን?» አለ።

«የእኔንና የእንተንም ነፍስ የማተርፍ መስሎኝ» አልኩና በቁጣ መለስኩለት።

ፈሬናንዴዝ የስፓኝ ዜጋ ሳይሆን አርጀንቲናዊ ነበር። በተፈተነ አስቸጋሪ ጉዟ የሠለጠነ፣ ደህና ሰው ነበር። ግን አርሱም እንደዚሁ በሽማግሌው ካሮራ ፍሬ ቢስ ወሬ ተሰብኮ ነበር። አንድ ቀን ለዴጋ እንደዚህ ብሎ ሲያወራው ሰማሁት።

«እንደዚህ ሳይሆን ደሴቶቹ በጣም ጤናማ ቦታዎች ናቸው ይባላል። መቀታቸውም አስከዚህ አይደለም። እዚህ ወደ መጸዳጃ ቤት በመሔድ ብቻ በጀርሞች ትበከልና የደም ተቅማጥ ይይዝሃል።»

እኛ ከፍል ከሚገኙት ሰባ ሰዎች አንድ ወይም ሁለት በየቀኑ በደም ተቅማጥ ይሞታሉ። የሚያስገርመው ደግሞ ሁሉም የሚሞቱት ማዕበሉ ጋብ በሚልበት ወቅት ከሰዓት በኋላ ወይም ሲመሽ ነበር። ጧት ምንጊዜም የሚሞት ሰው የለም። ለምን ይሆን? የተፈጥሮ ምስጢር?

በዚያው ሌሊት ከዴጋና ከፈርናንዴዝ ጋር መመካከር ነበረብኝ። ቁልፍ ያገኘ ዓረብ ሌሊት ሲሆን፤ እንዳንድ ጊዜ ወደ ከፍል ወስጥ እየገባ፤ አንሶላ ወደ ኋላ በመግፈፍ በጣም የጠናበትን በሽተኛ ይመረምራል ብየ ነገርኳቸው። አርሱን መምታትና ዩኒፎርሙን መልበስ፡ (እኛ ሁላችንም የለበስነው ፒጃማና ነጠላ ጫማ ብቻ ነበር) ቀላል ይሆናል። አንድ ጊዜ ከለበስኩ በኋላ ወደ ውጭ አወጣና ከአንደኛው ዘበኛ ጠመንጃውን በመንጠቅ በአነርሱ ላይ ወድሬ ወደ ከፍሉ ውስጥ እንዲገቡ በማስገደድ መዝጊያውን መሸጎር ነው። ከዚያም በሆስፒታሉ ግንብ ላይ ወደ ወንዙ ዳር ዘልለን፣ ውሃው ውስጥ መግባትና በማዕበሉ እየተገፋን ማምለጥ። ከዚያ ወዲያ ደግሞ የሚሆነውን እናያለን። ገንዘብ አሰካለን ድረስ አንድ ጀልባና ምግብ ገዝተን ወደ ባሕር ለመውጣት እንችላለን። ዕቅዱን ሁለቱም በየበኩላቸው ውድቅ አደረጉት። ችላ ማለታቸው ስለ ተሰማኝ በጣም ተከፋ ቆርጪ ነበር። ስለሆነም ቀኖቹ አለፉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አሁንም በሆስፒታሉ ሦስት ሳምንት ሊሆነን የቀረው ሁለት ቀን ነው። ማምለጥ ለመሞከር የቀረን ጊዜ ቢበዛ ከዐሥር እሰከ ዐሥራ አምስት ቀን ብቻ ነበር። ዛሬ አንድ የሚታሰብ ቀን ነው። ኅዳር 21/1933 ዮሐንስ ከሎሲዎ ወደ ከፍሉ ውስጥ መጣ። በቅዱስ ማርቲን ጸጉር ማስተካከያ ቤት አንድ ሰው ሊገድለው ሞክሮ ነበር። ለመታወር ተቃርቧል። ዐይኖቹ ምርግ ብለው ተዘግተው በመግል ተሞልተው ነበር። ወዲያው ቻታል እንደ ወጣልኝ እርሱ ዘንድ ሔድኩ። ሌሎቹ እሥረኞች ከሁለት ሳምንት በፊት ወደ ደሴቶቹ ሔደዋል። እርሱ ግን ወደ ኋላ ለመቅረት እንደ ተሳካለት ነገረኝ። እነርሱ ለመሔድ ሦስት ቀን ሲቀራቸው አንድ ባለሥልጣን አስጠነቀቀኝ አለ። የጉሎ ዘይት ፍሬ ዐይኖቹ ውስጥ አስገባና፣ በሚያብጡበት ጊዜ በቁስሉ ምክንያት ወደ ሆስፒታል ለመግባት ቻለ። ለማንኛውም ነገር ወደ ኋላ የማይልና የማምለጥ ፍላጎት ያሳበደው ከመሆኑ የተነሣ ከተሳካለት ገድሎ እንኳ ለማምለጥ ወደኋላ አይልም። ሦስት ሺ ፍራንክ ነበረው። ዐይኖቹ በሙቅ ውሃ ከታጠቡ ወዲያው ጥርት አድርጎ ለማየት ይችላል። የማምለጥ ዕቅዴን ገለጽኩለት። ወደደልኝ፣ ግን ዘበኞቹን በድንገት የምናጠቃ ከሆነ እኛ ሦስት መሆን ይኖርብናል አለ። የአልጋዎቹን አግሮች አውልቀን አያንዳንዳችን አንድ አግር ከያዝን፣ ሁሉንም በአንድ ጊዜ መምታት እንችላለን። እርሱ እንደሚለው፣ ጠመንጃቸውን ብንነጥቃቸው እንኳ ቆርጠን እንደምንተኩሰባቸው ስለማያምኑ፣ ቢያንስ ሐያ ያርድ ከማይርቀው ጁሎ ካመለጠበት ሕንጻ የሚገኙትን ዘበኞች ሊያስጠነቅቁ ይችላሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሦስተኛ ማስታወሻ

የመጀመሪያው ማምለጥ
ከሆስፒታሉ ማምለጥ

ዛሬ ማታ ዴጋን፣ ቀጥሎ ፈርናንዴዝን በነገር ወጥሬ ያዝኳቸው። ዴጋ «በዕቅዱ ዕምነት የለኝም። ግን ወደ ሆስፒታል በሕመምተኛነት የተመዘገብኩበት እንዲሰረዝልኝ የሚያስፈልገውን ገንዘብ አከፍላለሁ» አለ። ይህን አርሱ ያቀደውን ሐሳብ ማሳካት የሚቻል እንደሆነ ለሲየራ ማስታወሻ ጽፌ እንድነግርለት ጠየቀኝ። በዚያው ቀን ቻታል መልሱን ይዞ መጣ። ማስታወሻዋ፣ «ሕመምተኞች መሆናችሁን ለማሰረዝ ለማንም ሰው ገንዘብ እንዳትከፍሉ። ትእዛዙ የሚመጣው ከፈረንሣይ ስለሆነ፣ ማንም ቢሆን፣ ሊላው ቀርቶ የጠባይ ማረሚያው አዛዥ እንኳ ለመፍቀድ አይችልም። ቁርጠኛ ከሆንክ ለማምለጥ መሞከር ትችላለህ፣ ግን «ማና» የተባለችው መርከብ ወደ ደሴቶቹ ከሐኢች ከአንድ ቀን በኋላ ብቻ መሆን ይኖርበታል» ትላለች።

ወደ ደሴቶቹ ከመሔዳችን በፊት ስምንት ቀን ቀርቶን ስለነበር፣ ከሆስፒታሉ ከፍላችን ይልቅ ከዚያ ማምለጡ ይበልጥ የተሻለ መሆኑን ማሰብ ጀመርኩ። የምፈልግ ከሆነ ከእኔ ጋር የሚነጋገርና አንድ ጀልባ ከሆስፒታሉ በስተጀርባ የሚያዘጋጅልኝ ነጻ የወጣ አንድ አሥረኛ እንደሚልክልኝ በዚያችው ማስታወሻ ሲየራ ገልጾልኝ ነበር። ከሁለት ዓመት ቀደም ሲል የዶክተር በግራትን ማምለጥ ያቀነባበረ ስሙ ኢዮአስ የተባለ አንድ የቱሎስ ቀበሌ ተወላጅ ነበር። እርሱን ለማነጋገር ስል ራጅ እነሣለሁ በማለት ወደ ሴላ ሕንፃ መሔድ ነበረብኝ። ያ ከፍል የተሠራው ከሆስፒታሉ ሕንፃ ግድግዳ ጋር ተያይዞ ስለነበር፣ ነጻ ለወጡ አሥረኞች መገናኛ የምስጢር መሿለኪያ ነበረው። ከሣንባዬ በታች ከተነሣሁ፣ ዶክተሩ ሊታየው ስለሚችል ራጅ ከመነሣቴ በፊት የገነዘብ መደበቂያ ቱቦየን ማውጣት እንዳለብኝ አስጠነቀቀኝ። ኢዮአስን ወደ ራጅ ከፍል እንዲልከልኝና እኔም ከቻታል ጋር አብሬ ወደ እዚያ እንድላክ ለሲየራ አንድ ማስታወሻ አስተላለፍኩ። ከነገ ወዲያ በሦስት ሰዓት እንደሚሆን በዚያው ሴሊት ሲየራ ነገረኝ።

በሚቀጥለው ቀን ዴጋና ፈርናንዴዝ ከሆስፒታል ለመውጣት አመለከቱ። «ማና» በዚያን ዕለት ጧት ሐዲ ነበር። ካምፕ ከሚገኙት ከፍሎቻቸው ለማምለጥ ምኞት አላቸው። መልካም ዕድል እመኝላቸዋለሁ። የእኔ ዕቅዶች ግን አልተለወጡም።

ኢዮአስን አገኘሁት። ሁለት አስቀያሚ ጠባሳዎች በበለዘው ፊቱ ላይ አግድም የተሰመረበትና እንደ ተለበለበ ዓሣ ድርቅ ያለ፣ ነጻ የወጣ ሽማግሌ አሥረኛ ነበር። ሁልጊዜ አንድ ዐይኑ ያለቅሣል። አስቀያሚ ፊትና ዛላ ነበረው። ዕምነት አላሳደረብኝም፣

t.me/OLDBOOKSPDF

የዚህም እውን መሆን ወሮፈት ሊፈጥጥ ነው። በጥድፊያ ተነጋገርን።

«ለእራት ወሮም ቢበዛ ለአምስት ሰዎች የምትሆን እንዲት ጀልባ ላዘጋጅልህ እችላለሁ። እንድ በረዶል ውሃ፣ ምግብ፣ ቡናና ትምባሆ፣ ሶስት መቅዘፊያዎች፣ ባዶ ዩጴቱት ከረጢቶች፣ ሻናውን የነፋስ ሽራና የአቅጣጫ ማስተካከያውን ሽራ የምትሰፋበት ክርና መርፌ፣ አንድ ኮምፓስ፣ አንድ ቆንጨራ፣ አንድ ጩቤና አምስት ሊትር ሩም፣ ይሆን ሁሉ በሁለት ሺ አምስት መቶ ፍራንክ። በዚህ ሶስት ቀን ውስጥ ጨረቃ አይኖርም። ከአራትኛው ጀምሬ፣ የምትስማማ ከሆነ ለስምንት ተከታታይ ቀናት ከሊሊቱ አምስት ሰዓት አስከ ንጋቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጀልባ ውስጥ ሆኜ ልጠብቅህ። አንድ ጊዜ ጨረቃ ከታየች ከመጀመሪያው ሳምንት በኋላ መጠበቁን አቆማለሁ። ጀልባዋ ልክ ከሆስፒታሉ ግንብ በስተጀርባ ትሆናለች። ከስድስት ጫማ ርቀት ላይ ሆነህ እንኳ ልታያት ስለማትችል፣ ግንቡን እየዳሰስክ ራስህን ምራ አለ።

እሙንኩትም፣ ግን ያም ሆኖ እሺ አልኩ።

«ፖፐንዘበት ጉዳይ እንዴት ነው?» አለ ኢዮአስ።

«በሲያራ በኩል አልከልሃለሁ።»

ሳንጨባበጥ ተለያየን። ጥሩ ጅምር አልነበረም።

በዘጠኝ ሰዓት ቻታል ፖንዘቡን ለሲያራ ለመስጠት ወደ ካምፕ ሔደ። ሁለት ሺህ አምስት መቶ ፍራንክ ነበር። አደገኛ እንደሆነ ቢታየኝም ሊጋልጋኔ ምስጋና ይግባውና ይሆን ፖንዘብ ቁማር እንደተጫወትኩበት አቆጥረዋለሁ። ብቻ አሱስ ቢሆን ሁሉንም ፖንዘብ በሩም ባይጨርሰው አይደል?

ከለሲዎ ከመጠን በላይ ፈንድቶ ነበር። በራሱ፣ በእኔና በዕቅዱ ሙሉ በሙሉ ተማምኗል። እንድ ነገር ብቻ አሳስቦታል። ዐረቡ በምሽት አይመጣም፣ በሚመጣበት ጊዜ ግን አዘውትሮ ቀደም እያለ ነበር። አንድ ተጨማሪ ሦስተኛ ሰው ማን ይሆን የሚለውም ሌላው ችግር ነበር። ከኒስ ቀበሌ የመጣ ቢያጂ ፖተባለ አንድ ኮርሲካዊ ነበር። ከ1929 ጀምሮ በቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ቢሆን፣ እውንም እንድ ሰው ገድለሃል በሚል ጥርጣሬ በከፍተኛ ጥበቃ ሥር ይገኛል። ከለሲዎና እኔ እርሱን ማነጋገር ነበረብን። መቸ እናነጋግረው በማለት በመወያየት ላይ እንዳለን፣ በግምት ዐሥራ ስምንት ዓመት የሚሆነው እንድ ልጅ ወደ እኛ መጣ። ልክ እገደ ልጃገረድ ቆንጆ ነበር። ስሙ ማቹሬ ይባላል። በእንድ የታክሲ ሾፌር ግድያ የተነሣ የሞት ቅጣት ከተፈረደበት በኋላ፣ በዕድሜው ምክንያት (በዚያን ጊዜ ዐሥራ ሰባት ዓመቱ ነበር።) ወደ ዕድሜ ይፍታህ ተሻሽሎለት ነበር። የተከሰሱት የዐሥራ ስድስትና የዐሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሁለት ልጆች ነበሩ። ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እያንዳንዳቸው የታክሲውን ሾፌር መግደላቸውን በማመን ቃላቸውን ሰጡ። ግን ሾፌሩ የተመታው

t.me/OLDBOOKSPDF

በአንድ ጥይት ብቻ ነበር። በፍርድ ቤት ያሳዩት ሥነ ምግባር እሥረኛቹን በሙሉ ስሜታቸውን በሐዘን መስጠታል።

ማቹሬ ወደ እኛ ቀረብ አለና የልጃገረድ ድምፅ በመሰለ አነጋገር የሲጃራ ማቀጣጠያ ጠየቀን። እራት ሲጃራዎችና አንድ ዛጥን ከብራት በስጠታ መልክ ወረወርኩለት። ከመሽኮርመም ፈገግታ ጋር አመሰገነኝ። እኛም አሰናበትነው።

ከሎሲዎ በድንገት፣ «ፓፒ ድነናል። ያን ዐረብ እኛ እንደ ፈለግን አዘውትሮ ወደዚህ መምጣት የሚችልበትን ዘዴ ዐወቅኩ፣ እጃችን ውስጥ ገብቷል» አሰ።

«እንዴት አስብከ?»

«ቀላል ነው። ማቹሬና ዐረቡ የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው አያጠራጥርም። ልጁ ማድረግ ያለበት እንዳልታይ አፈራለሁ አያለ ልከ እኛ በምንፈልግበት ሰዓት ዐረቡ እንዲመጣ ማመቻቸት ብቻ ነው።»

«አስኪ እንሞከረው።»

ማቹሬ ዘንድ ስሐድ እንደገና በሌላ የመሽኮርመም ፈገግታ ተቀበለኝ። የመጀመሪያው ፈገግታ ስሜቴን ቀስቅሶታል ብሎ ገምቷል። በቀጥታ እንደዚህ አልኩት። «አንድ ጊዜ ላነጋግርህ አፈልጋለሁ። ወደ መጸዳጃ ቤት እንድትመጣ» ተያይዘን እንደሔድን እንዲህ አልኩት። «አሁን የምነግርህን አንዷን ቃል ለሌላ ሰው ብትተነፍስ ሟች ሰው ነህ። እንደዚህ ነው . . . » ስል ዕቅዳችንን በዝርዝር ነገርኩትና ምን ያህል ገንዘብ እንደሚጠይቅ፣ ወይም ከእኛ ጋር ማምለጥ የሚፈልግ ከሆነ ጠየቅኩት።

«ከአናንተ ጋር ማምለጥ አፈልጋለሁ።»

ተስማማን። ለዚህም እጅ ለእጅ ተጨባበጥን። ለመተኛት ሔደ፣ ከሎሲዎ ጋር ትንሽ ቃላት ከተለዋወጥን በኋላ እኔም ተኛሁ። በሚቀጥለው ሌሊት በሰምንት ሰዓት ማቹሬ ከመስኮቱ አጠገብ ተቀመጠ። ዓረቡ መጠራት አላስፈለገውም። በገዛ ራሱ መጣና ድምፃቸውን ዝቅ በማድረግ አወሩ። በዐሥር ሰዓት ማቹሬ ወደ አልጋው ሔደ። እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ አንድ ዐይናችንን እንዳጮለቅን በአልጋችን ውስጥ ቆየን። ዓረቡ ወደ ከፍል ገብቶ ሁለት ጊዜ ሲፈትሽ፣ አንድ ሰው ሞቶ አገኘ። መዝጊያውን ቆረቆረና ወዲያውኑ ሁለት ቃሬዛ ተሸካሚዎች መጥተው አስከሬኑን ወሰዱ። አስከሬኖች ጠቃሚነታቸው ከሌሊቱ በማንኛውም ሰዓተ ዓረቡ እንደልቡ ወጣ ገባ እንዲል ማስቻላቸው ነው። የእኛን ምክር በመከተል ማቹሬ በሚቀጥለው ሌሊት በአምስት ሰዓት አንድ ቀጠሮ ሰጠው። ቁልፍ ያገቦም ዓረብ በቀጠሮው ሰዓት ከተፍ አለና በልጁ አልጋ በኩል ሲያልፍ ሊቀሰቅሰው አማሮቹን ሳብ አድርጎ አለፈ። ማቹሬ ተከተለው። ከዐሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ቁልፍ ያገቦ ተመለሰና በቀጥታ ወደ መዝጊያው ሔዶ ወጣ። በዚያው ወቅት ማቹሬም ምንም ሳይናገር ወደ አልጋው ተመልሶ ሔደ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በሚተኙለው ምሽት እንደዚሁ ሆነ። ግን ውድቅት ሌሊት ላይ ነበር። ማንኛውም ነገር የሚከናወነው ልክ እንደ ሕልም ይመስል ነበር። በማንኛውም ጊዜ ልጁ ከጠየቀው ዓረቡ ይመጣል።

ነሳር 27/1933 ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት ላይ ሁለቱን የአልጋ እግሮች ለመፈንከት አዘጋጅቼ፣ ከሲየራ የሚደርሰኝን ቃል አጠባበቅ ጀመር። ጤና ረዳቱ ቻታል መጣ። ግን እንድም ማስታወሻ አልያዘም። ያለው፣ «ኢዮአስ በተጠቀሰው ቦታ እየጠበቃችሁ ነው። መልካም ዕድል ብዬ እንድነግራችሁ ፍራንሷ ሲየራ ልኮኛል» ብቻ ነበር። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ማቹሬ ለዐረቡ «ከግማሽ ሌሊት በኋላ እንድትመጣ» አለው።

ዐረቡም እንደተባለው አደርጋለሁ አለ። ልክ ግማሽ ሌሊት ሲሆን ተዘጋጅተን ነበር። ዐረቡ ስድስት ሰዓት ከሩብ ላይ መጣ። ማቹሬም ተከተለው። የአልጋየን እግር ላወልቅ በሚወድቅበት ወቅት እንድ ድምፅ አሰማብኝ። ከሎሲዎ ግን ምንም ድምፅ አልነበረውም። እኔ መዝጊያውን ተከልዬ ልቅምና ከሎሲዎ ደግሞ የዐረቡን ስሜት ለመሳብ በተጥታ ወደ እርሱ ሲሔድ ነበር። ከሐያ ደቂቃ ቆይታ በኋላ ማንኛውም ነገር በጣም እየተቀላጠፈ ሔደ። ዐረቡ ከመጸዳጃ ቤት ሲወጣ ከሎሲዎን በማየቱ ደነቀውና፣ «በዚያ ሴሊት በከፍሉ መካከል ምን እየደረግክ ነው? ወደ አልጋህ ተመለስ» አለው።

ከዚያም ጭንቅላቱ ላይ አፈጋህበትና ምንም ድምፅ ሳያሰማ ተፈነገለ። ቶሎ ብየ ጫማዎቹንና ልብሶቹን አጠለቅኩ። ወደ አልጋ ሥር ጎተትነውና ሙሉ በሙሉ ወደ ውስጥ ከመግፋታችን በፊት ማጅራቱ ላይ አንድ ሌላ ምት ደገምኩት። አሁን ያለጥርጥር ሕሊናውን ስቷል።

በከፍሉ ውስጥ ካሉት ሰዎች ማንም የተንቀሳቀሰ የለም። ማቹሬና ከሎሲዎ የሆስፒታል ፒጃማቸውን እንደለበሱ ተከትለውኝ በቀጥታ ወደ መዝጊያው አመራሁ። ሰቀረቁር ዘበኛው ከፈተ። የአልጋውን ብረት አምዘገዘግኩና በቀጥታ ጭንቅላቱን ነረትኩት። ከእኛ ፊት ለፊት ያለው ሌላ ዘበኛ ካርባይኑን ጣለው። ተኝቶ መሆን አለበት። እንቅስቃሴ ከማድረጉ በፊት እርሱንም ነረትኩት። ከእኔዎቹ ማንም ድምፅ ያሰማ የለም። የከሎሲዎ ግን በወለሉ ላይ ከመዘርጋቱ በፊት «አህ» አለ። የእኔ ሁለቱ ዘበኞች ገና በወንበሮቻቸው ላይ ሲሆኑ፣ ሦስተኛው ግርር እንዳለ ተዘርግቶ ነበር። ትንፋሻቸንን ዋጥ አድርገን ይዘናል። በእኛ ግምት «አህ» የምትለዋ የዘበኛው የመጨረሻ ድምፅ በመላው ዓለም ተሰምታብናለች። በእርግጥ በቂ ጩኸት ነበር። ይሁንና ማንም አልተንቀሳቀሰም። መጀመሪያ ከሎሲዎ፣ በመካከል ልጁ፣ እኔ ከኋላ ሆነን የሦስቱንም ካርባይኖች አነሣንና እንደተጋደሙ ትተናቸው ሔድን። የደበዘዘ መብራት ባለበት ደረጃ ቁልቁል ሸመጠጥን። ከሎሲዎ የአልጋውን እግር ወደ ኋላ ጥሎት ነበር። የእኔን ጠመንጃ

t.me/OLDBOOKSPDF

በቀኜ፣ የአልጋውን አግር በግራ እጁ ይዤዋለሁ። ከደረጃው በታች ምንም ነገር የለም። አካባቢዎችን በሌሊቱ ድቅድቅ ጨለማ የተዋጠ ነበር። ከወንዙ ቀጥሎ ያለውን ግንብ ለማግኘት አተኩረን መመልከት ነበረብን። የቻልነውን ያህል በከፍተኛ ፍጥነት እንራመዳለን። አንድ ጊዜ ወደ ግንቡ ከደረስኩ በኋላ በእጆቼ በመደገፍ የቁም ዕረፍት አደረግኩ። ከሎሲዎ ወደ ላይ ተንጠለጠለና በግንቡ ላይ ተንፈራጥጦ ማቹሬን፣ ከዚያም እኔን ጎትቶ አወጣን። በሌላው በኩል ተንሸራትተን ወረድን። ከሎሲዎ አንድ ጉድጓድ ውስጥ ስለገባ እግሩን ተሰበረ። ማቹሬና እኔ ያለችግር ዘለልን። ከመዝለላችን በፊት ጠመንጃዎቹን ጥለናቸው ስለነበር፣ ያለችግር በእግራችን ቆምን። ከሎሲዎ ግን እቆማለሁ ብሎ ቢሞክር አልቻለም። ጉልበቱን ተሰብሬአለሁ አለን። ማቹሬን ከከሎሲዎ ጋር ተውኩና በእጄ እየዳበስኩ ወደ ግንቡ ማዕዘን አቅጣጫ መሮጥ ያዝኩ። በጣም ጨለማ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ግንቡ መጨረሻ መድረሴን ስላላወቅኩ፣ በፊቴ ጥ ብዬ ወደቅኩ። ከወንዙ በታች አንድ ድምፅ ሰማሁ።

«አንተ ነህ?»

«አዎ፣ ኢዮአስ ነህ?»

«አዎ»

አንድ ከብሪት ለኮሰ። ወንዙ ውስጥ ገባሁና እያንቦጫረቅኩ እርሱ ወደሚገኝበት አመራሁ። ሁለት ሰዎች ነበሩ።

«መጀመሪያ አንተ ግባ፣ ማንኛው ነህ?»

«ፓፒዮን»

«አሸ»

«ኢዮአስ፣ ወደ ላይ ተመልሰን መሔድ ሊኖርብን ነው። ከግንቡ ላይ እዘላለሁ ሲል ጓደኛየ ቅልጥሙን ተሰብሯል።»

«አንግዲህ ይህን መቅዘፊያ ውሰድና ቅዘፍ።» ሦስቱንም መቅዘፊያዎች ወደ ውሃው አጠለቅንና በመቅዘፍ በእኛና በጓደኞቹ መካከል ያለውን የአንድ መቶ ያርድ ርቀት ጀልባዋ በፍጥነት አጠናቀቀች። ምንም ነገር ካለማየታችን የተነሣ እናገኛቸዋለን ብየ ከገመትኩበት አካባቢ ስደርስ

«ከሎሲዎ!» ብዬ ተጣራሁ።

«ሰለ ከርስቶስ አትናገር። ሌንፍሌ፣ የሲጃራ ማቀጣጠያህን ተጠቀም» አለ ኢዮአስ። ትንሽ ብልጭታ ቦግ ሲል እነ ከሎሲዎ አዩን። ከሎሲዎ በጥርሶቹ መካከል አንድ ፉጨት አሰማ። ልክ እንደ አባባ ፉጨት ጥርት ብሎ የሚሰማ የሊዮን ቀበሌ ፉጨት ነበረ። አሰከምንቀራረብ ድረስ ማፏጨቱን ቀጠለ። ሌንፍሌ ወጣና የከሎሊዎን ከንድ ደግፎ ወደ ጀልባው አመጣው። ከዚያም ማቹሬ ተንጠለጠለ፣ በመጨረሻ ሌንፍሌ

t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣ። አምስት ነበርን፣ ስለሆነም ውሃው ወደ ጀልባዋ አፍ ጠርዝ ሊደርስ የቀረው ጥቂት ነበር።

«ያለ አንድ ማስጠንቀቂያ ማንም ሰው እንዳይነቃነቅ። ፓፒዮ መቅዘፍህን አቁም። መቅዘፊያውን በጉልበቶችህ እግድም አስቀምጥ። እንሒድ ሌንፍሌ» አለ ኢዮአስ።

በማዕበሉ እየተረዳች ጀልባዋ ወደ ጨለማው ውስጥ ጠለቀች። የአንድ ማይል ሲሶ በወንዙ ቁልቁል እንደወረድን የጠባይ ማረሚያውን ከልል አለፍን። ወደ ወንዙ መካከል እንደገባን፣ ማዕበሉ በማይታመን ፍጥነት ተሸከሞን ነንደ። ሌንፍሌ መቅዘፊያውን አቁሞ ነበር። ኢዮአስ ደግሞ፣ መቅዘፍ ሳይሆን የመቅዘፊያውን እጀታ ከሞኑ ጋር ጥብቅ አድርጎ በመያዝ የጀልባዋን አቅጣጫ ለመቆጣጠር ይጥራል።

ከዚያም ኢዮአስ እንደዚህ አለ። «አሁን ሲጋራ ማጨስ እንችላለን። እንደማስበው ሁሉም ነገር የተሳካ ይመስለኛል። እርግጠኞች ናችሁ ምንም ሰው አልገደላችሁም?»

«አይመስለኝም።»

«እግዚአብሔር ይይልህ ኢዮአስ! ያታለልከኝ አንተ ነህ!» አለ ሌንፍሌ። «አንተ ያልከው ሁላል ማምለጥ ነበር። አሁን እንዳየሁት ግን የሕመማን ሩጫ ነው።»

«ትክክል ነው፣ ሕመማን አሥረኞች ናቸው። አልነገርከህም ሌንፍሌ፣ ምክንያቱም እትረዳኝም ነበር፣ አኔም አንድ ሌላ ሰው ማግኘት ነበረብኝ። ተዝናና። ከተያዝን ኃላፊነቱን በሙሉ እኔ እወስዳለሁ።»

«እንዳልከው ይሁን ኢዮአስ። አንድ መቶ ፍራንክ ከፍለሽኛል ብየ አንድ ሰው ቢገደል ወይም ቢቆሰል እንኑቴን ለአደጋ ልሰጥ አልፈልግም።»

«ሌንፍሌ፣ ለሁለታችሁም አንድ ሺ ፍራንክ በተጨማሪ አበረክትላችኋለሁ» አልኩ።

«እንግዲያስ ደህና ነው ጓዴ። ማሰብህም ተገቢ ነው። እናመሰግናለን። መንደሩ ውስጥ በረኃብ መሞታችን ነው። ወህኒ ቤት ከመሆን ይልቅ የሚበሰው ነጻ መውጣቱ ነው። በወህኒ ቤት ውስጥ ሌላው ቢቀር በየቀኑ ምግብና ልብስ ታገኛለህ።»

«ብዙ ተጎድተሃል እንዴ ጓዴ?» ሲል ኢዮአስ ከሎሲዎን ጠየቀው።

«አስከዚህ ከባድ አይደለም። ግን በሰባራው ቅልጥሜ እንዴት አድርጌ ልሑድ ነው ፓፒዮ?» አለ ከሎሲዎ።

«አስኪ እናያለን። ወዴት ነው የምንሔደው ኢዮአስ?»

«ለወንዙ ሩቅ ዐሥራ ሁለት ማይል ሲቀረን፣ ከምትነጠል አንዲት ጠባብ ጅረት ውስጥ እሸሸጋችኋለሁ። ዘበኞቹና ሰው አዳኞቹ ፍለጋቸውን ተስፋ ቆርጠው

t.me/OLDBOOKSPDF

አሰኪተውት ድረስ እዚያ ስምንት ቀን ያህል ትቆያላችሁ። በዛሬው ሴሊት በማሮኒ ወንዝ ወርዳችሁ ወደ ባህር ዘልቃችኋል ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። አዳኞቹ የሚጠቀሙባቸው ጀልባዎች ሞተር አልባ ናቸው። ምናልባት በአካባቢው ስለሚቀርቡ እሳት ማንደድ፣ መነጋገርና መሳል አደገኛ ይሆናል። ዘበኞቹ የሚጠቀሙበት ባለሞተር ጀልባ ግን በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ጅረቷ ዘልቆ መቃናት ስለማይችል የሚሯሯጡት በመሬት ነው።»

ሴሊቱም ወገግ አለ። ከረጅም ፍለጋ በኋላ በመጨረሻ ኢዮአስ ብቻ ከሚያውቃት የመሸሸጊያ ሥፍራ ስንደርስ፣ ከጧቱ አንድ ሰዓት ሊሆን ተቃርቦ ነበር። ሙሉ በሙሉ ጫካ ውስጥ ነበርን። አጫጭር የሆኑትን ቁጥቋጦዎች ጀልባዋ እያስተኛቻቸው ካለፍን በኋላ፣ እንደገና ቀጥ ብለው ይቆሙና አንድ ወፍራም መጋረጃ ይሆናሉ። አንድ ጀልባ የሚያንሳፍፍ በቂ ውሃ አዚህ አለ ብሎ ለማወቅ ጠንቋይ መሆንን ይጠይቃል። ወደ በሸሎዋ ገባን። ከዚያም መንገዳችንን የዘጉብንን ቅርንጫፎች በመመንጠር ወደ ጫካዎቹ ውስጥ ሰርገን ለመግባት ከአንድ ሰዓት በላይ አጠፋን። ድንጉት አንድ ቦይ የመሰለ ቦታ ውስጥ ገባንና ቆምን። የበሸሎው ዳር ንጹሕና አረንጓዴ ሆኖ የዛፎቹ ቅጠሎች በጣም ሰፋፊ ስለሆኑ፣ ከውፍረታቸውም የተነሣ የፀሐይዋን ብርሃን አያስተላልፉም ነበር። በዚህ ማራኪ አረንጓዴ አጎበር ሥር ፍጹም ሰምተናቸው የማናውቅ በሺህ የሚቆጠሩ አራዊት ይኖራሉ። «ስምንት ቀን የምትቆዩት እዚህ ነው። በሰባተኛው ቀን ተመልሼ ስንቃችሁን አመጣላችኋለሁ» አለ ኢዮአስ። ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ ገላለጠና ስድስት ጫማ ርዝመት ያላት አንዲት ትንሽ ጀልባ ከሁለት መቅዘፊያዎች ጋር ጎትቶ አወጣ። ማዕበል ሲነሣ ወደ ቅዱስ ላውረን መልሳ የሚወስደው ጀልባ ይህች ነበረች።

ጅረቷ ዳር ተዘርግቶ ለነበረው ከሎሲዎ አንድ ነገር ማድረግ የሚቻለው አሁን ነበር። የለበሰውም ፒጃማውን ብቻ ስለሆነ ባቶቹ ራቁታቸውን ናቸው። ሰማይን የሚያገለግሉን ደረቅ ቅርንጫፎች በቆንጨራችን ቆረጥንና ሰነጣጠቅን። ሌንሮ ፡ እግሩን ሲሰብለት ከሎሲዎ በከባድ ላብ ተዘፈቀ። ድንገት ከሎሲዎ፣ «አቁሞ አሁን ሰሚያመኝ በመጠኑ ነው። አጥንቱ ከቦታው መግባት አለበት» አለ። ስንጥሮቹን አሰናዳንና ጀልባው ውስጥ ባገኘነው አዲስ የታሜ ገመድ አሠርናቸው፣ ሥቃዩ በረደለት። ቀደም ሲል ኢዮአስ ለእኛ ያዘጋጃቸው አራት ሸሚዞች፣ አራት ሱሪዎችና አራት የስፍ ሹራቦች ይዘ ነበር። ማቹሬና ከሎሲዎ ለበሷቸው። እኔ የሣረቡን ልብሶች እንደ ለበስኩ ቆየሁ። ትንሽ ሩም ጠጣን። ከተነሣን ጀምሮ ሁለተኛው ጠርሙስ መሆኑ ነበር። ሞቅ አደረገን። ከፉኛ በቢንቢዎች በመነደፋችን እንድ ፓኪት ትምባሆ ለመሥዋት ተገደድን። ውሃ ከሞላ ጠርሙስ ወስጥ ዘፈዘፍንና ፊታችንን፣ እጆቻችንና እግሮቻችንን ለቀለቅናቸው። ሰርሥሮ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚገባው እርጥበት የሰጡ ሹራቦቹ መሞት ጠበቁን።

«መሐዳችን ነውኮ። ቃል የገባህልንን እንድ ሺ ፍራንክ አታመጣም?» አለ ሌንፍሌ።

ለትንሽ ጊዜ ገለል አልኩና አንድ ባለ አንድ ሺ ፍራንክ አዲስ ኖት ይዤ ተመለስኩ።

«ደህና ሁኑ። ለስምንት ቀን ከዚህ እንዳትንቀሳቀሱ፣ በሰባተኛው እንመለሳለን። በስምንተኛው ወደ ባሕር ትወጣላችሁ። በምትቆዩበት ጊዜ የነፋስ ሸራችሁን፣ የአቅጣጫ ማስተካከያ መሣሪያችሁን በመጠገን ጀልባዋን አዘጋጁ። ከበስተኋላ ያለውን የጀልባዋን መሪ አስተካክላችሁ፣ ማንኛውንም ነገር በቦታው አስቀምጡ። ከዐሥር ቀን በኋላ ካልመጣን ታስረናል ማለት ነው። እነዚያን ዘበኞች ማጥቃታችሁ ብዙ ችግር ማስከተሉ አይቀርም።»

ከዚያም ከሎሲዎ ካርባይኑን በግንቡ ሥር እንዳልተወው ነገረን። ከግንቡ ላይ ሆኖ ሲወረውረው ወንዙ ቅርብ መሆኑን በዚያ ወቅት ባለማስተዋሉ ነው እንጂ ወደ ውሃው ውስጥ መውደቅ አለበት። አዳኞቹ መሣሪያ ታጥቀናል ብለው ስለሚያስቡ አለመገኘቱ ጥሩ ነው አለ ኢዮአስ። አሁን ትንሽ መዝናናት እንችላለን። የሚይዙት ሽጉጥና ገጀራ ብቻ ስለሆነ፣ እኛም መሣሪያ እንዳለን ከጠረጠሩ እኛን ለማደን መንገዳቸውን አሳብረው አይወጡም። ይሁንና በአጋጣሚ ከተገኘን ጀልባዋን ትተን ደረቅ መሬት አስከናነኝ ድረስ ጅረቷን ተከትለን ሽቅብ መውጣት ይኖርብናል። ከዚያም የሰሜንን አቅጣጫ እየጠበቅን በኮምፓስ በመመራት መሔድ አለብን። ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በኋላ ቫርቪን ተበላ ከምትጠራው ካምፕ ለመድረስ ጥሩ ሪድል ይኖረናል። አንድ ጊዜ እዚያ ከደረስን ለአንድ ሰው ጉርሻ ሰጥተን የት እንዳለን ለኢዮአስ እንዲነግርልን ማድረግ ነው።

ሁለቱ ሽማግሌ ተባባሪዎቻችን ሔዱ። ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ጀልባቸው ተሠወረች። ምንም ነገር ማየትና መስማት አልቻልንም። የቀኑ ብርሃን ጫካውን ሰርጎ የሚገባው በጣም ልዩ በሆነ መንገድ ነበር። በላዩ ላይ ዐሐይ የምታርፍበትና ጨረሯ ግን ተጣርቶ የማይወርድበት አንድ ጃንጥላ ውስጥ ያለን ይመስል ነበር። መሞቅ ጀመረ። ማቹሬ፣ ከሎሲዎና እኔ ብቻችንን ቀረን። እየተያየንም እንሣሣቅ ጀመረ። ጥቂት ቅሬታ ቢኖረን በከሎሲዎ ቅልጥም መሰበር ነበር። ግን ዙሪያውን በታሠረለት እንጨት ምክንያት ደህና ነኝ አለ። ቡና ብናፈላለት የሚሻለው መሆኑን ነገረን። ወዲያው አዘጋጀንለት። እሳት አነደድንና እያንዳንዳችን በወየበ ስኳር የጣፈጠ ጥቁር ቡና ጠጣን። የሚያረካ ነበር። ካለፈው ሌሊት ጀምሮ ኃይላችንን በብዛት አባክነን ስለነበር፣ ጓዛችንን ለመመርመርም ሆነ ጀልባዋን ለመፈተሽ አቅም አላገኘሁም። ያ በኋላ ሊደርስ ይችላል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቁም ካሬ ነፃ፣ ነፃ፣ ነፃ መሆናችን ነበር። ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት የደረስነው ልክ ከሠላሳ ሰባት ቀን በፊት ነበር። ማምለጡ ከተሳካ የዕድሜ ልክ እሥራት ቅጣት ርጥም ረጅም ላይሆን ነው፣ «ከቡር ፕሬዚዳንት፣ ፈረንሣይ ውስጥ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ማከተሚያው እስከ መቼ ይሆን?» አልኩና በሣቅ ፈነዳሁ። እንደኔ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ማቹሬም እንደዚሁ ቀጠለ። «አሁን አትንጫጩ። ኮሎምቢያ ገና ሩቅ ስለሆነ ይህች ጀልባ እስክዚህም ለባሕር ጉዞ ዋጋ ያላት አትመስለኝም» አለ ከሎሲዎ።

አልመለስኩለትም፣ ምክንያቱም ይህች ጀልባ ወደ አሰቱማማጉ ግባችን እንደምታደርሰን እስክ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ እምኔ ስለነበር ነው። ተሳስቼ እንደነበር ሰረዳ ግን፣ ጓደኞቼን አሸብራለሁ በሚል ሥጋት ምንም ነገር ለማለት አልደፈርኩም። እንደዚሁም ኢዮአስ በሚገባ የተስተካከለች ናት ብሎ እሰካሰበና በተለይም ለማምለጥ የሚጠቀሙባቸው ጀልባዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ እኔም እሰካላወቅኩ ድረስ የምፈልገውን ዓይነት እንዲሠራልኝ መመሪያ ለመስጠት አልችልም ነበር።

የመጀመሪያውን ቀን ያጠፋነው በማውራትና ከዚህ ምኑም የማይታወቅ ጫካ ጋር በመለማመድ ነበር። ዝንጀሮዎችና ትናንሽ የሸኮኮ ዝርያዎች ከጭንቅላታችን በላይ ትንግርታዊ አክሮባት ይሠራሉ። አንድ የዱር አሳማዎች መንጋ ወደ ጅረቱ ለመታጠብና ለመጠጣት መጣ። ቢያንስ ሁለት ሺህ መሆን አለባቸው። ከዚያም ወደ ውሃው ውስጥ በመግባት የተንጠለጠሉትን ሐረጎች እየበጣጠሱ ይዋኙ ጀመር። ከወዴት እንደ መጣች አግዚአብሐር ይወቅላትና አንዲት አዞ ኩቱፍ ብላ ከእነርሱ ውስጥ የአንዷን እግር ያዘቻ። ዓሣማዋ፣ ሌሎቹ ዓሣማዎች በአዞዋ ላይ እየተንጠላጠሉ ግዙፍ የሆነ አፏን ዳርና ዳር በመንከስ ይታገሏት ጀመር። አዞዋ በየጊዜው ጅራቷን ባወናጨፈች ቁጥር አንድ ዓሣማ አየር ላይ ይሽቀነጠራል። ከእነርሱ ውስጥ አንዷ ሞተችና ሆዷን ወደ ሰማይ ገልብጣ ተንሳፈፈች። ወዲያውኑ ጓደኞቿ አርሷን ለመብላት ተሰበሰቡ። ጅረቱን ደም አጥለቅልቆት ነበር። አዞዋ ወደ ውሃው ጠልቃ እስክትጠፋ ድረስ ትዕይንቱ ሐያ ደቂቃ ፈጀ። ዳግመኛ ፊጽሞ አላየናትም።

ጭልጥ ያለ አንቅልፍ ወስዶን አደርን። ጧት ቡና አፍልተን ከጠጣን በኋላ ሹራቤን አውልቄ ጀልባው ውስጥ ባገኘሁት አንድ ትልቅ የማርሲይ ሳሙና አጠብኩ። ማቹሬ በራሴው ጩቤ ጉንጩን እየቆራረጠ ጺሜን ላጨኝ። ቀጥሎ ከሎሲዎንን ላጨው። ማቹሬ ራሱ ግን ጺም አልነበረውም። ሹራቤን ለመልበስ ብድግ ሳደርግ፣ የጥቁር ሐምራዊ የሆነ አንድ ግዙፍ ሽረራት ከላዩ ላይ ዱብ አለ። ጫፎቻቸው ትናንሽ የፐላቲነየም ኳሶች በመሰሉ ቀጫጭንና በጣም ረጅም ጸጉሮች የተሸፈነ ነበር። ቢያንስ አንድ ታውንድ የሚመዝን መሆን አለበት። ቀፈፈኝና ጨፈለኩት። የውሃውን በርሜል

t.me/OLDBOOKSPDF

ጨምሮ ማንኛውንም ነገር ከጀልባው ውስጥ አራግፉን። ውሃው ዳወይን ጠጅ መስሎ ነበር። እንዳይበላሽ በማለት ኢዮአስ ብዙ ፐርማንጋኔት ጨምሮበት መሆን አለበት። የከብራት እንጨቶችና አንድ መጫሪያ ጥብቅ ብለው በተዘጉ ጠርሙሶች ውስጥ አገኘን። ኮምፓሱ ከልጅ መጫወቻ አሻንጉሊት የማይሻል ነበር። የጀልባው ምሰሶ ከፍታ ሁለት ያርድ ተኩል በቻ እስከሆነ ድረስ፣ የዳቱት ከረጢቶቹን በአግድመት አቅጣጫ በማድረግ ለማጠናከር ያህል የከፈሱን ዙሪያ በገመድ ሰፋነው። ሦስት ማዕዘን የሆነች አንዲት ትንሽ የአቅጣጫ ማስተካከያ ቢጤ መሣሪያ ሠራሁ። የነፋስ አቅጣጫ ለመከተል ትረዳናለች።

ምሰሶውን ለመትከል በምንዘጋጅበት ወቅት የጀልባው ሥር ጠንካራ አለመሆኑንም ተመለከትኩ። የምነሱው መትከያ ጉድጓድ በጠቅላላው ተበልቶ ነበር። መሪውን ይደግፈው በነበረው እርፍ ውስጥ ቪቱዎቹን ለማሰር ሳስገባ እንጨቱ አንደቅቤ የቦከቦከ ስለነበር በቀጥታ ወደ ውስጥ ጠለቀ። ጀልባዋ የበሰለበሰች ነበረች። ያ የውሻ ልጅ ኢዮአስ ወደ ሞታችን ልኮናል። ይሆን ከእነርሱ ለመሸሸግ ሙበት ስለማይኖረኝ፣ ሌሎቹም እንዲመለከቱት አደረግሁ። ምን ማድረግ ይሻለናል? ኢዮአስ ሲመለስ እንድ የተሻለች ጀልባ እንዲፈልግ እንጠይቃለን። መሣሪያውን እንግፈፈውና፣ ከዚያም አዲ ገጀራና ጩቤ ታጥቄ ሌላ ጀልባ ለመፈለግ ከእርሱ ጋር ወደ መንደሩ እንሔዳለን። ራሴን ለትልቅ አደጋ ማጋለጥ መሆኑ ይሰማኛል። ያም ሆኖ በዚያች የሬሣ ሣጥን ውስጥ ወደባሕር ከመግባት የከፋ አይሆንም። በቂ ምግብ የሚሆነን ማለት እንድ ትልቅ ጠርሙስ ዘይትና፣ አንድ ሣጥን ዱቄት ነበረን። በዚህም ረጅም ጉዞ ለመሸፈን እንችላለን። በተረፈ ግን፣ በዛፊው ጧት አንድ አንግዳ ትርዒት ተመለከትን። ማራጫ ፊት ያላቸው የዝንጅሮ መንጋዎች ጸጉራማ ከሆኑ ጥቁር ፊት ካላቸው ዝንጅሮዎች ጋር ጦርነት ገጠሙ። ጦርነቱ በመፋፋም ላይ እንዳለ ማቹፊ ጭንቅላቱን አንድ ዝንጣይ ቅርንጫፍ ስለመታው የትልቅ ፍሬ ያህል አብጦ ነበር።

አዚህ ከመጣን አምስት ቀንና አራት ሌሊት ሆነን። ዛሬ ማታ ድፍ የሆነ ዝናም ጣለ። በጫካ የመገ ቅጠሎች አንድ መጠለያ ሠራን። እንደ ቫርኒሽ በሚያሙለጨልጩት ቅጠሎች ላይ ውሃው ወዲያው እየተንኳለለ ስለሚወርድ ከአግሮቻችን በስተቀር ደረቅ ነበርን። ጧት ቡናየን በመጠጣት ላይ እንዳለሁ፣ ኢዮአስ ምን ዓይነት ተንኮለኛ እንደነበር አሰብኩ። ይህችን የበሰበሰች ጀልባ በመስጠት በሞኝነታችን ተጠቀመበን! ለአምስተ መዶ ወይም ለአንድ ሺ ፍራንክ ሲል ሦስት ሰዎችን ወደ ዕውነተኛ ሞት ይልካል። ሌላ ጀልባ እንዲሰጠን ካደረግን በኋላ እርሱን ካልገደልኩ መቸውንም ይገርመኛል።

ትንሿን ዓለማችንን የአሞራዎች ጩኸት አሸበራት። እንደዚህ ለመሰለው የሚሰቀጥጥና ደም የሚያረጋ ጩኸት መነሥዒው ምን እንደሆነ ማቹፊ ገጀራ ይዘ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዲፈልግ ነገርኩት። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ተመለሰና አንድከተሰው ጠራኝ። በግምት አንድ መቶ ሃምሳ ያርድ ርቀት ላይ ካለ ቦታ ስንደርስ፣ ከአንድ ትልቅ አውራ ዶሮ በአጥፍ የሚበልጥ ኻርግራ ወይም ዳክዬ የሚመስል በአየር ላይ ተንጠልጥሎ አየሁኝ። በገመድ ሸምቀቆ ቢያዝም፣ ጥፍሮቹ አንድ ቅርንጫፍ ላይ የመጥኝ ብለው ነበር። ትዕግሥት አስጨራሽ ጩኸቱን ለማቆም በአንድ የገጀራ ውዝግዝግ አንገቱን ቀላሁት። ከብደቱ ቢያንስ ዐሥራ አራት ፓውንድ እንደሚሆን ገመትኩ። ልንበላው ወሰን። ግን ወጥመዱ እዚያ የተቀመጠው በአንድ ሰው መሆኑ ስለማይቀር ከአርሱ ሌላ ተጨማሪ ሕይወት መኖር እንዳለበት ገመትን። ዙሪያውን ለመቃኘት ሔድንና አንድ አስደናቂ ነገር ተመለከትን። ከቅጠሎችና ከሐረጎች የተተበተበ ዐሥራ ሁለት ኢንች ከፍታ ያለው አንድ ወጥመድ አግድም ተዘርግቶ ነበር። አለፍ አለፍ እያሉ በሮች ሲኖሩት፣ በእነርሱም ላይ ማለሳቻ ጭራሮዎች ተረብርበባቸው ከመዳብ ሽቦ የተሠሩ ሸምቀቆዎች ተቀምጠባቸው ነበር። እንደ ገመትኩት ከሆነ አውሬው ወደ ወጥመዱ ውስጥ ሮጦ ከገባ በኋላ መሸሸኪያ ለመፈለግ በዚያ ላይ እንዲራመድ ነበር። በሩን ሲያገኝና ወደ ውስጥ ለመግባት ሲጀምረ ሸምቀቆው እግሮቹን ስለሚይዙት አዳኙ መጥቶ እስኪያገኘው ድረስ ወጥመድ ውስጥ የገባው እንስሳም ሆነ ወፍ በአየር ላይ ይንጠለጠላል።

ይህ እንግዲህ ሰላምን የሚያሳጣ ግኝት ነበረ። ወጥመዱ በሚገባ የተሠራና ፍጹም አዲስ ስለሚመስል፣ የመጋለጥ አደጋ ላይ እንደሆንን ተሰማኝ። እሳት ማንደድ የለብንም። ወጥመዶቹን የሚጠብቅ አንድ ዘበኛ ለማቆም ወሰንን። ጀልባዋን በዛፍ ቅርንጫፎቹ ሥር ደበቅንና ስንቃችንንም በጫካው ውስጥ ሸሸግን።

በሚቀጥለው ቀን አራት ሰዓት ላይ በጥበቃ ተረኝነት ላይ ነበርኩ። ጅግራም ሆነ ሌላ ነገር፣ ያን አሞራ ባለፈው ሌሊት በልተነዋል። መረቁ ግሩም ነበር፤ ሥጋውም ይጥማል። አያንዳንዳችን ሁለት ሣህን ሙሉ በላን። እዚህ በጥበቃ ላይ እንደነበርኩ አያንዳንዳቸው ትላልቅ ቁራጭ ቅጠሎች ወደ አንድ ግዙፍ ኩይሳ የሚያመላልሱ ግዙፍና ጥቋቁር ጉንዳኖች አጋጠሙኝና በአድናቆት ተዋጥኩ። ጉንዳኖቹ ቁመታቸው ከግማሽ ኢንች በላይ ሲሆን፣ የሚቆሙትም በቅልጥሞቻቸው በጣም ቀጥ ብለው ነበር። ቅጠሎቻቸውን ወደሚቆርጡበት አትክልት ተክተልኳቸውና አንድ ሰፊ ድርጅት ይመስል በሥራ ላይ እንዳሉ ተመለከትኩ። በመጀመሪያ ቁራጮቹ ብቅ ይላሉ። መቀረጣጠፍ ካልሆነ በስተቀር ምንም ነገር አይሠሩም። ከእነዚያ የመዝ ከባዎች የመሰሉ ሰፋፊ ቅጠሎች ውስጥ እየገቡ በከፍተኛ ፍጥነት በመከርተፍ በሚያስገርም ጥበብ እኩል በሆነ መጠን ይቆራርጡና ወደ መሬት ይጥሏቸዋል። በአጠቃላይ ዘራቸው ተመሳሳይ ሆኖ ግን ትንሽ ለየት ያሉ የጉንዳን ሰልፈኞች ከሥር በኩል ነበሩ። በአገጫቻቸው ጎንና ጎን ቁልቁል የወረደ አንድ ግራጫ መስመር ነበረባቸው። እነዚህ ጉንዳኖች ግማሽ ክብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠርተው ተሸካሚዎቹን ይቆጣጠሩ ነበር። ተሸካሚዎቹ በሰልፍ ሆነው ከቀኝ በኩል ይመጡና ከዚያም ወደ ኩይሳቸው አቅጣጫ በስተግራ በኩል ያመራሉ። መጀመሪያ ከዚያ ይሸከሙና በኋላ በሰልፍ ይገባሉ። ግን አልፎ አልፎ ጭነታቸውን ተሸክመው ወደ ሰልፉ ለመመለስ ከሚያደርጉት ጥድፊያ የተነሣ የትራፊክ መጨናነቅ ነበር። ሆኖም ሠራተኞቹ ጉንዳኖች የተወሰነ ቦታቸውን እንዲይዙ ‹የፖሊስ ጉንዳኖች› እየገፉ ተርታ ያስገቧቸዋል። ምን ዐይነት ከባድ ጥፋት ፈጽሞ እንደነበረ ግልጽ ባይሆንልኝም ከሠራተኞቹ ጉንዳኖች አንደኛውን፣ ሁለት የፖሊስ ጉንዳኖች ከሰልፉ ውስጥ ጎትተው አወጡና አንደኛው ጭንቅላቱን በጥሶ ሲጥለው፣ ሌላው ደግሞ ከወገቡ ላይ ሰውነቱን ለሁለት ቆረጠው። ከዚያም ፖሊሶቹ ሁለት ሠራተኛ ጉንዳኖች አቆሙና ቁርጥራጭ ቅጠሎቻቸውን አውርደው በአግሮቻቸው ጉድጓድ አስቆፈሯቸው። በመጨረሻም የተገደለው ጉንዳን ሦስት ከፍሎች፣ ማለት ጭንቅላት፣ ደረትና የቀረውም ተጨማምሮ ተቀበረና አፈር ለበሰ።

ይህችን ትንሽ ዓለም ተመልከቼ ፖሊሶቹ ቁጥጥራቸውን የሚያከናውኑት እስከ ኩይሳው መጨረሻ ድረስ ይሆናል በማለት በጠቅላላው በኢድናቆት ተመስጬ በመከታተል ላይ እያለሁ ነበር አንድ ድምፅ፣ «እንዳትንቀሳቀስ አለበለዚያ ትሞታለህ። ቀኝ ኋላ ዙር» ሲል የሰማሁት። ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ካኪ ቁምጣ ሱሪ የለበሰና ቀይ ቆዳ ቦት ጫማ ያደረገ፣ ረዘ ጠመንጃ የያዘ አንድ ሰው ቆሞ ነበር። የዐይኖቹ ዙሪያና አፍንጫው ደማቅ ሰማያዊ በሆኑ ውቅራዮች የተቦርነረነረ፣ በጣም ወፍራም ሆኖ ቁመቱ መጠነኛ፣ ፀሐይ ያበለዘው ራሰ በራ ነበር። ግንባሩ መካካል አንድ የትኋን ምሥል ተወቅሯል።

«መሣሪያ ታጥቀሃል?»

«የለኝም።»

«በቃህን ነህ?»

«አይደለሁም።»

«ስንት ናችሁ?»

«ሦስት።»

«ወደ ጓደኞችህ ውሰደኝ።»

«አልችልም፣ ምክንያቱም ከእነርሱ አንደኛው ካርባይን ስላለው አስተሳስበህን ከማወቁ በፊት እንድትገደል አልፈልግም።»

«አሃ! እንግዲያውማ ሳትንቀሳቀስ ዝማ ብለህ አውራኝ። ሦስቱ ከሆስፒታል ያመለጣችሁት ናችሁ?»

«አዎ»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ፓሊዮ የሚባለው የትኛው ነው?»

«እኔ ነኝ::»

«መልካም የእናንተ ማምለጥ በመንደሩ ውስጥ ለብጥብጥ ምክንያት ሆኗል! ነፃ ከወጡት እስረኞች ከፊሎቹ አንደገና ወህኒ ቤት ውስጥ ናቸው::» ቀረብ አለና የጠመንጃውን አፈ ሙዝ ወደ መሬት ዘቅዝቆ እጁን እየዘረጋ «ባለወቅራታሙ ባሪቶን እኔ ነኝ:: ስለ እኔ ሰምተሃል?» አለ::

«አልሰማሁም:: ግን ከአዳኞቹ ወገን እንዳልሆንክ ገብቶኛል::»

«ልክ ነህ:: አሞራዎች ለመያዝ አዚህ ወጥመድ አስቀምጣለሁ:: እናንተ ካልሆናችሁ ድመት አውርዶ በልቶት መሆን አለበት::»

«እኛ ነበርን::»

«ትንሽ ቡና ትፈልጋለህ?» አለና በጀርባው ከተሸከመው ጥቅል አንድ ፔርሞስ አወጣና አንድ ጉንጭ ሰጥቶኝ ለራሱም ትንሽ ጠጣ::

«ናና ጓደኞቼን ላግናኝህ» አልኩት

ተከትሎኝ መጣና ከእኛ ጋር ተቀመጠ:: ካርባይን በመያዛችን ለቅቄበት ስለነበረው ፍርሃት ሣቀ:: «ካርባይን ይዛችሁ ማምለጣችሁን አዳኞቹ ከዐወቁ ስለማይከታተሏችሁ ነው ያመንኳችሁ» አለ::

ጊያና ውስጥ ለሐያ ዓመታት እንደኖረና ከአምስት ዓመታት በፊት ከአሥር ቤት መለቀቁን ተረከልን:: ዕድሜው ዐርባ አምስት ዓመት ነበር:: በሞኝነት ፊቱን በውቅራት አቫኮንጉሮት ስለነበር ወደ ፈረንሣይ አመለሳለሁ የሚለውን ሐሳብ እርግፍ አድርጎ ለመተው ተገድዷል:: የጫካውን ኑሮ በመውደዱም ውሎው በዚሁ አካባቢ ነበር:: የአባቡና፣ የአቦ ሸማኔ ቆዳዎች፣ ቢራቢሮዎች መሰብሰብና ከዚያም ይበልጥ እኛ በልተነው የነበረውን ዓይነት አሞራ የመሰሉ ከነነፍሳቸው ይይዝ ነበር:: ከሁለት መቶ እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ፍራንክ ይሸጣቸዋል:: ልከፈለው ብየ ሰጠሁት፣ ግን በቁጣ አልቀበልም አለ:: ከዚያም ስለ አሞራው ሁኔታ ነገረን:: «ይህ የዱር አሞራ ወይም የዶሮ ዘር ሰው ፍጹም አይቶ እንደማያውቅ ግልጽ ነው:: ይሁንና አንዱን በምይዝበት ጊዜ ወደ መንደር እወሰድና የዶሮ ርቢ ላለው ሰው እሸጠዋለሁ:: የእርሱ ዓይነት አሞሮች በጣም ተፈላጊዎች ናቸው:: እየወለህ፣ ከንፉን አትሰብርም:: ምንም ነገር አታደርገውም:: ቀኑ እንደመሸ ብቻ ዶሮዎች ቤት ወስደህ አስቀምጠው:: በሚቀጥለው ቀን ጧት መዝጊያውን ከፍተህ ሲካካዎቹና አውራ ዶሮዎቹ ሲወጡ ዶሮዎቹን የሚቆጥር በመምሰል ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ታየዋለህ:: ከእነርሱ ጋር አብሮ በመልቀም በአካባቢው ጫካ ላይና ታች እያለ ለመጠበቅ ይከተላቸዋል:: እንደ አንድ ጥሩ የውሻ ዘበኛ ማለት ነው:: ምሽት ሲመጣ በዶሮዎቹ ቤት መዝጊያ ይቆምና ይቆጣጠራል:: ምናልባት አንድ ወይም ሁለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ዶሮዎች ቢጎድሉ እንዴት እንደሚያውቅ ራሱን የቻለ ምስጢር ነው፣ ፍለጋ ይሔዳል። እንዳጎደቸውም፣ ሲካካም ትሁን አውራ ዶሮ ወደ በት የመመለሻ ሰዓት መሆኑን ለማስተማር ሲል በሹል ከምቢው እየጠቀጠቀ ወደ ማደሪያቸው ያሰማራቸዋል። አይጦችን፣ እባቦችን፣ አይጠመኔዎችን፣ ሽረራዎችን ትላትሎችን ይገድላል። እንደዚሁም እንዲት ጭልፊት ሰማይ ላይ ከነዮች፣ በዚያው ወቅት እሱ ጭልፊቷን ወደ ሰማይ እንጋፀ እየተመለከተ ዶሮዎቹ እንዲደበቁ ያጣድፋቸዋል። ከዚህም በላይ ፍጹም አይኮበልልም።»

ልክ እንደ ማንኛውም ተራ አውራ ዶሮ ነበረ ይህን ታሪክኛ አሞራ የበላነው።

አያአስ፤ ሊንፍሌና ሠላሳ ያህል ነፃ አሥረኞች በቅዱስ ላውረን ፖሊስ ጣቢያ አሥር በት ውስጥ ጉበተው ስለእኛ ማምለጥ እየተመረመሩ መሆናቸውን ብሪቶኑ ነገረን። ዓረበም እንደዚሁ ተባባሪ ይሆናል በሚል ጥርጣሬ አንድ ከፍል ወስጥ ተዘግቶበት ነበር። ያደነዘዙት ሁለት ምሶች ለጉዳት አላደረሱትም፣ ግን ዘበኛቹ ጭንቅላታቸው በመጠኑ አብጦ ነበር። «እኔ አስረኞችን ለማስመለጥ ተባባሪ እንደማልሆን ሁሉም ሰው ስለሚያውቅ ማንም አያስቸግረኝም» አለና፣ አያአስ ግን መናጢ መሆኑን ነገረን። በበኩሉም ስለ ጀልባዋ ሁኔታ ሳጣራው ሊያያት ይችል እንደሆነ ጠየቀኝ።

ሲመለከታት፣ «ያ የውሻ ልጅ! የላካችሁ ወደ ሞት ነበር! ይህች ጀልባ በባሕር ላይ አንድ ሰዓት አትቆይም። የመጀመሪያው ትልቅ ማዕበል ለሁለት ይከፍላታል። ምንም ነገር ይሁን በዚህች ተልካሻ ጀልባ እንዳትሐዱ። ራስን በራስ መግደል ይሆናል» ብሎ ጮኸ።

«ታዲያ ምን እናድርግ?»

«ፐንዙበ አላችሁ?»

«አዎ»

«ምን እንደምታደርጉ እነግራችኋለሁ፤ እንዲያውም አረዳችኋለሁ ማለቱ ይመረጣል። በእርግጥም መረዳት ይገባችኋል። የሚደርገውም ያለ ምንም ከፍያ ነው፤ ምክንያቱም እንተና ጓደኞችህ ሲሳካላችሁ ለማየት እፈልጋለሁ። ከሁሉ በፊት፣ የፈለገው ነገር ይሁን ወደ መንደሯ አትሒዱ። አንድ ጥሩ ጀልባ ለማግኘት ወደ ፒዝን ደሴት ማምራት ይኖርባችኋል። በደሴቷ ውስጥ ሁለት መዶ ያህል ቆማጦች ይኖራሉ። ሐኪምም ሆነ ሌላ ማንም ጤነኛ ሰው ምንጊዜም ወደዚያ አካባቢ አይሔድም፤ ዘበኞች የሉም። በየጊዜው ጧት በሁለት ሰዓት ለሐያ አራት ሰዓታት የሚበቃ የምግብ ራሽን አንድ ጀልባ ያመጣላቸዋል። የሆስፒታሉ ጤና ረዳትም አንድ ሣጥን መድኃኒት ለሌሎች ሁለት ጤና ረዳቶቹ ያስረክባል። እነርሱም እንደዚሁ ቆማጦች ናቸው። የደሴቷን

t.me/OLDBOOKSPDF

ነዋሪዎች የሚያከሙት እነርሱ ብቻ ናቸው። ምን ጊዜም ወደ ደሴቷ የሚሔድ ዘበኛ የለም፣ ሰው አዳኝ የለም፣ ቂስ የለም፣ ማንም ሰው ወደዚያ ዝር አይልም። ቆማጡቹ የሚኖሩት ራሳቸው በሠሯቸው ትናንሽ የሣር ጎጆዎች ውስጥ ሲሆን፣ በሕብረት የሚሰበሰቡበት አንድ የጋራ አዳራሽ አላቸው። የዘወትር ምግባቸውን ለማግኘት ዶሮዎችና ዝዮች ያረባሉ። ከደሴቷ ውጭ ምንም ነገር በግልጽ አይሸጡም። ግን ከቅዱስ ላውረን፣ ከቅዱስ ዮሐንስና በዳች ጊያና አልቢና ውስጥ ከሚገኙ ቻይናውያን ጋ የኮንትሮባንድ ንግድ ያካሒዳሉ። ሁሉም ነፍሰ ገዳዮች ናቸው። ብዙውን ጊዜ እርስ በርሳቸው አይገዳደሉም። ይሁንና ከደሴቷ ውጭ ሲሔዱ ብዙ ወንጀሎች ይፈጽሙና ከዚያ በኋላ ለመሰወር ይመለሳሉ። ለዚህ ተልዕኳቸው ከጎረቤት መንደር የሰረቋቸው ጥቂት ጀልባዎች አሏቸው። አስከፊ ወንጀል የሚፈጽሙት ደግሞ ጀልባ ለማግኘት ነው። ከፒኮን ደሴት በሚመጣው ወይም በሚሔደው በማንኛውም ነገር ላይ ዘበኞቹ ይተኩሳሉ። ቆማጡቹም ጀልባዎቻቸው እንዳይታዩ ድንጋይ በመሙላት ማስቀመጥና እንደገና ሲያስፈልጓቸው ጠልቀው በመውረድ ቋጥኞቹን ገልብጠው ጀልባዎቹ ወደ ላይ እንዲንሳፈፉ ማድረግ ነው። ከየትኛውም የፈረንሣይ ክፍልና ከማንኛውም ዓይነት ጎሣ የተውጣጡ ሕዝቦች በደሴቷ ውስጥ ይገኛሉ። ይህች የእናንተ ጀልባ ጥሩነቷ ለማሮኒ ወንዝ ብቻ ያውም ጭነት ሳታበዛ ሲሆን ወደ ባሕር ለመውጣት ግን፣ አንድ ሌላ ሻል ያለ መፈለግ አለባችሁ። ለዚህም የሚመረጠው ቦታ የፒኮን ደሴት ነው።»

«ለዚያ እንዴት እንደርሳለን?»

«እንደዚህ ነው - ወንዙን ወጥተን ደሴቷን ለማየት እስከምንችል ድረስ ከእናንተ ጋር አብሬ እሔዳለሁ። ብቻችሁን ፍጹም ልታገኟት አትችሉም፣ ወይም ልትሳሳቱ ትችሉ ይሆናል። ከወንዙ አፍ ስድሳ ማይል ስለሚሆን ወደ ኋላ መመለስ ይኖርባችኋል። ከቅዱስ ላውረን ባሻገር ሐያ ማይል ይሆናል። ጀልባየን ከእናንተ ጋር እናቆራኛታለን። በተቻለ መጠን እስከትቃረቡ አሸኛችሁና ከዚያ በኋላ በራሴ ጀልባ ሆኜ ወደ ኋላ እመለሳለሁ። ከዚያም ወደ ደሴቷ ታመራላችሁ።»

«ለምን ከእኛ ጋር ወደ ደሴቷ መምጣት አትችልም?»

«ሕ፣ የእግዚአብሔር ያለህ፣ ወደ ፒኮን ደሴት ከምትመለሰው የአስተዳደሩ ጀልባ የመሸጋገሪያ ድልድይ እግሬን ለማሣረፍ ሞከሬ ነበር። ጠራራ ቀን ስለነበር በዚያ ጊዜ ያየሁት ይሰቀጥጠኛል። ስለዚህ ይቅርታ አድርግልኝና ፓፒዮ፣ በዚያች ደሴት ላይ ዳግመኛ ፍጹም እግሬን አላሣርፍም። ምን እንደሚሰማኝ መሸሸግ ስለማልችል ከምጠቅማቸሁ ይልቅ ይበልጥ ጉዳት አደርስባችኋለሁ።»

«መቼ እንሔዳለን?»

«ሊመሽ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን ስንት ሰዓት ነው?»

«ዘጠኝ ሰዓት።»

«አሺ። ለትንሽ ጊዜ አተኛለሁ»

«ኢይሆንም። አትተኛ። ጀልባዋን መጫን ይኖርብሃል።»

«ኢይሆንም። የምሔደው ጀልባዋ ባዶ እንደሆነች ነው። ከዚያ በኋላ እዚህ ቆይቶ ጓዞችንን ወደሚጠብቀው ከሎሲዎ ተመልሼ እመጣለሁ።»

«ኢይቻልም። ይህን ቦታ በጠራራ ቀን እንኳ ቢሆን እንደገና በሞራሽ አታገኘውም። በተጨማሪ፣ ምንጊዜም ቢሆን በቀን ወንዙ ላይ እንዳትታይ። አሁንም ገና እየፈለጓችሁ ነው። ወንዙ አሁንም ገና በጣም አደገኛ ነው።»

ምሽት መጣ። ጀልባውን ለመፈለግ ሔደና ከእኛ ጋር አቆራኘናት። ከሎሲዎ መሪውን ከያዘው ብራቶን ቀጥሎ፣ ማቹሬ በመካከል፣ እኔ ደግሞ ከፊት በኩል ተቀመጥኩ። ጅረቷን ለመውጣት ችግር ስለነበረብን፣ ወደ ወንዙ አፍ በምንደርስበት ወቅት ጨለማ ጋረደ። የቀይ በሩማ የሆነች ግዙፍ ፀሐይ ከባሕሩ ባሻገር ትንቀለቀል ነበር። ግርማ ሞገስ ያለው ወንዝ ሐምራዊና ብር የሚመስሉ ጨረሮችን እያፈናጠቀ ባሕሩን ለመገናኘት ሲገሠግሥ ከፊት ሰፊት እስከ ዐሥራ ሁለት ማይል ርቀት ግልጽ ሆኖ ማየት ቻልን።

«ማዕበሉ በርዷል። በአንድ ሰዓት ውስጥ ግን እያየለ ስለሚመጣ ወደማሮኒ ለመውጫ እንጠቀምበታለን። በዚህ ዘዴ ያለበዙ ድካም ወደ ደሴቷ እንደርሳለን» «ወደፊት ግፉ፣ ወደ ወንዙ መካከል እንድንገባ በኃይል ቅዘፉ። ሲጃራ ማጨስ የለም።» አለ ብራቶኑ። ወዲያው ጨለመ።

ውሃውን በመቅዘፊያዎቹ እየሰነጣጠቅን ከማዕበሉ ጋር ተፈተለከን። ብራቶኑና እኔ በተመሳሳይ ቅኝት ስንሰብ ማቹሬም የተቻለውን ይሞክራል። ወደወንዙ መካከል እየገፉን በገባን መጠን የሚነሣው ማዕበልም እየጨመረ መሔዱ ተሰማን። አሁን በፍጥነት እንንሣፈፍ ጀመር። ማዕበሉ እየጠነከረ በሔደ መጠን እኛንም በፍጥነት ይገፋን ነበር። ከስድስት ሰዓት በኋላ ወደ ደሴቷ በጣም ስለተቃረብን፣ በቀጥታ ወደ እርሷ አመራን። ደሴቲቱ ከሞላ ጎደል በወንዙ መካከል፣ ትንሽ ወደ ቀኝ ሲል የምትገኝ አንዲት ጥቁር ነጥብ ትመስላለች። ዝግ ባለ ድምፅ ብራቶኑ፣ «ያች ናት» አለ። በጣም ጨለማ ሊሊት ባይሆንም እንኳ ከውሃው በላይ ባለው ጭጋግ ምክንያት ከፍቅ ሆኖ እኛን ለማየት አስቸጋሪ ነበር። እየተጠጋን መጣን። የቋጥኞቹ ገመገም ግልጽ ሲሆን፣ ብራቶኑ ወደ ጀልባው ተዛወረና በፍጥነት ፊትዮ፣ «መልካም ዕድል ልጆች!» ሲል ሹክ አለን።

«አናመሰግናለን።»

«ምንም አይደል።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ብራቶኑ መሪው ላይ ስለሌለ ጀልባዋ እንዳጋደለች ወደ ደሴቷ አመራች። እንድትዞር ለማድረግ ሞከርኩ፣ ግን አልቻልኩም። ወደ ውሃው ቁልቁል የተንጠለጠሉ ቅጠላቅጠሎች ጥግ እየገፋ ማዕበል ወሰደን። ከድንጋጤ የተነሣ ወደ ኋላ ስቀዝፍ፣ በዚያ ፍጥነት በቅጠሎችና በቅርንጫፎች ፈንታ ከቋጥኞች ላይ ዐርፈን ቢሆን ኖሮ፣ እንከትክታችን ወጥቶ ማንኛውም ነገር ባበቃልን ነበር። ማቹሬ ወደ ውሃው ውስጥ ዘለለና ጀልባዋን ጎትቶ ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ሥር አበታት። አንድ ኩባያ ሩም ተከፋፈልንና ሁለቱን ጓደኞቼን ጀልባው ላይ ትቼ፣ ብቻዮን እሻቅቤ በውሃው ዳር ተቃናሁ። ጫካዎቹን ወደ ኋላ እየመነጠርኩና መንገድ ላይ ባሉት ቅርንጫፎች ላይ የዱቄት ከረጢት ጨርቅ ትልታዮች በማሰር ኮምፓስ እንደያዝኩ መራመዴን ቀጠልሁ። ከፊት ለፊቴ አንዲት ስልምልም ያለች መብራት ከማየቴ ወዲያው ድምፅ ሰማሁ፣ ከዚያም ሦስት የሣር ጎጆዎች ብቅ አሉ። እንዴት መቅረብ እንዳለብኝ እስካላወቅኩ ድረስ ወደፊት እየተንቀሳቀስኩ እነርሱው እንዲያገኙኝ ወሰንኩ። አንድ ሲጋራ አቀጣጠልኩ። መብራቱ በልጭ እንዳለ አንዲት ትንሽ ውሻ ወደ እኔ እየጮኸች መጣችና ባቴ ላይ ቦጨቀችኝ። ብቻ ቆማጣ እንዳትሆን ብዬ አሰብኩ። ታዲያ ደደብነቴ እንጂ ውሾችን ለካስ ቁምጥና አይዛቸውም ኖሯል!

«ማነው? . . . ማነህ ማርሴል ነህ እንዴ?

«ያመለጥኩ አስረኛ ነኝ።»

«እዚህ ምን ታደርጋለህ? ልትዘርፈን ነው? ከበርቴዎች መሰልንህ እንዴ?»

«አይደለም። እርዳታ እፈልጋለሁ።»

«በነፃ ነው ወይስ በከፍያ?»

«እንዴ ዝም በል እንጅ ላሹዌት!»

ከጎጆዋ ውስጥ አራት ጥላዎች ብቅ አሉ።

«ረጋ አያልክ ተጠጋ ወዳጄ። እርግጠኛ ነኝ ባለካርባይኑ ሰው ነህ። ይዘኸው ከሆነ ከመሬት ላይ አስቀምጠው፣ እኛን የምትፈራበት ምንም ነገር የለም።»

«አዎ፣ እኔ ነኝ። ግን ካርባይኑን አውን አልያዝኩትም» በመጠኑ ቀረብ አልኩ። አውን ተጠግቼ ነበር፤ ግን ጨለማ ስለሆነ አቋማቸውን ማጣራት አልቻልኩም። በየዋህነት እጄን ዘረጋሁ። ማንም አልተቀበለኝም። እንደዚህ የመሰለ ሰላምታ እዚህ እንደማይደረግ በጣም ዘግየት ብሎ ገባኝ። ሊበከሉኝ አልፈለጉም።

«ወደ ጎጆዋ እንግባ» አለ ላሹዌት።

ጠረጴዛ ላይ በተቀመጠ አንድ ዘይት ፋኖስ ትንሿ ከፍል ታበራለች።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ተቀመጥ።»

በአንዲት ዱካ ላይ ተቀመጥኩ። ላሹዌት ሦስት ተጨማሪ ፋኖሶች አቀጣጠለና አንደኛውን በቀጥታ እኔ ፊት ለፊት ከሚገኘው አንድ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው። የኮከነት ዘይቱ ጢስ የሚያንገሸግሽ ሽታ ነበረው። አምስቱም ቆመው ስለነበር መልካቸውን መለየት አልቻልኩም። እኔ ግን እነርሱ በፈለጉት ሁኔታ ከፋኖሱ ፊት ለፊት ነበረ የተቀመጥኩት።

ላሹዌትን ዝም በል ብሎ ተናግሮ የነበረው ድምፅ፤ «ለአንቲዊ፤ ወደ ዋናው አዳራሽ ሒድና፤ እዚያ እንድናመጣው ይፈልጉ እንደሆን አሰቀቻችንን ጠይቅ። መልሱን ወዲያው ይዘህ ተመለስ። በተለይም ቶሲያ ፈቃደኛ መሆኑን እንድታረጋግጥ። ዕንቁላሎች እንድትውጥ ከማድረግ በስተቀር እዚህ ምንም የምትጠጣው ነገር ልንሰጥህ አንችልም» አሰና፤ ዕንቁላል የተሞላበት አንድ ቅርጫት ከፊት ለፊቴ አስቀመጠ።

«ይቅር ብኝ። አመሰግናለሁ።»

ከዚያም ከእነርሱ ውሰጥ አንደኛው ወደ አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠ። በዚህም የመጀመሪያውን ቆማጣ መመልከቴ ነበር። በጣም ያሰቅቃል። ዘወር ላለማለት ወይም ስሜቴን ላለማሳየት ጥረት ማድረግ ነበረብኝ። ሥጋውን አጥንቱም ሳይቀር ሙሉ በሙሉ አፍንጫው ተቦጭቆ ሒዷል። ከፊቱ መካከል አንድ ቀዳዳ ብቻ አለው። ለማለት የፈለግሁት፤ ሁለት ቀዳዳዎች ሳይሆኑ፤ ያለው ጠባራ ብር የሚያክል አንድ ሰፊ ቀዳዳ ነው። በተጨማሪ ከቀኝ በኩል ያለው የታችኛው ከንፈሩ ተቦጭቆ ስለሔደ፤ ከላይኛው አገጩ ቁልቁል የወረዱ ሦስት ረጃጅም ቢጫ ጥርሶች ገጥጠዋል። በፋሻ የተጠቀለለ እጁን ጠረጴዛው ላይ አጋድሞታል። የቀኝ እጁ ነበር። ከግራ እጁ ውስጥ በተረፉት ሁለት ጣቶቹ አንድ ወፍራምና ረጅም ሲጃራ ይዟል። ቁለሙ አረንጓዴ ስለነበር የጠቀለለው በከፊል ከበሰለ የትምባሆ ቅጠል ሳይሆን አይቀርም። የግራ ዐይኑ ብቻ የዐይን ቆብ ነበረው። የቀኝ ዐይኑ ቆብ ከቦታው ጠፍቶ አንድ የተጠረመሰ ጠባሳ ከዐይኑ ጀምሮ በግንባሩ ላይ በመጋደም ወደ ተቆጣጠረው ግራጫ ጸጉሩ ውስጥ አልፎ ጐኒጒኗል።

«እንረዳሃለን። እዚህ አካባቢ ቆይተህ እንደ እኔ እንድትሆን አልፈልግም» አለ በተነፋነፈ ድምፅ።

«አመሰግናለሁ።»

«ሰሚ የሐንስ ፐር ነው። ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መጀመሪያ ስመጣ ከአንተም ቆንጆ፤ ጤነኛና ጠንካራ ሰው ነበርኩ። ዐሥር ዓመታት እንዴት እንዳደረገኝ ተመልከት።»

«ማንም የሚያከምህ ሰው የለም?»

«አዎ። የቬዋልሙግራ ዘይት መርፌ ራሴን በራሴ መውጋት ከጀመርኩ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንሥቶ በጣም ተሸሎኛል። ተመልከተው።» ጭንቅላቱን አዞረና በግራው በኩል አሳየኝ። «ሕዚህ ላይ እየደረቀ ነው።»

ለዚህ ሰው ከፍተኛ ሐዘን ተሰምቶኝ የጓደኝነት ምልክት ለማሳየት ጉንጩን ልነካ ስንቀሳቀስ፣ ወደ ኋላ አፈገፈገና፣ «ለመንካት ስላልተጠየፍከኝ እመሰግናለሁ፣ ግን ቆማጣን ፍጹም መንካት ወይም በእርሱ ሣህን መብላትና መጠጣት የለብህም» አለ። ይህ ሰው እንድመለከተው ኢደፋፍሮኝ ስለነበር ከቆማጣዎቹ ሁሉ የማስታውሰው የእርሱን ፊት ነው።

«እንግዳው የታል?» ሲል፣ ከድንክ ብዙም የማይሻል አንድ በጣም አጭር ሰው በበሩ ተመለከትኩ። «ቶሲያንና ሌሎቹም ሲያዩት ይፈልጋሉ። ወደ ማዕከሉ እምጠት።»

ዮሐንስ ፐር ብድግ አለና፣ «ተከተለኝ» አለ። ሁላችንም በጨለማው ውስጥ ጉዞ ጀመርን። አራት ወይም አምስት የሚሆኑት ከፊት ለፊት፣ እኔ ከየሐንስ ፐር ቀጥዬ፣ ሌሎች ተጨማሪዎች ሰዎች ከኋላ ነበሩ። ከሦስት ደቂቃ በኋላ የደበዘዘች ጨረቃ ብርሃን ወደምትታይበት ገላጣ ቦታ ደረስን። የደሴቷ ከፍተኛው ደልዳላ ቦታ ነበር። በመካከሉ አንድ ቤት አለ። ከሁለቱ መስኮቶች በኩል ብርሃን ይታያል። ሐያ የሚሆኑ ሰዎች የእኛን መምጣት ይጠባበቃሉ። መዘጊያው አጠገብ እንደ ደረስን እኛን ወደ ውስጥ ለማሳለፍ ወደ ኋላ አፈግፍገው ቆሙ። ምድጃ ከሚመስል ቦታ ተመሳሳይ ቁመት ባላቸው አራት ትላልቅ ድንጋዮች ተከብቦ እንጨት ይነድበት ከነበረና ርዝመቱ ሠላሳ ጫማና ስፋቱ ዓሥራ ሁለት ጫማ ከሆነ አንድ ከፍል ውስጥ ነበር የገባሁት። አዳራሹ ብርሃን የሚያገኘው ከሁለት ትላልቅ ፋኖሶች ነበር። ከነጭ ፊቱ ላይ ጥቁቁር ዐይኖች ያፈጠጡበት ዕድሜው የማያስታውቅ አንድ ሰው ከድንጋይ ዱካዎቹ በአንደኛው ላይ ተቀምጧል። ከእርሱ በስተጀርባ አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ደግሞ ሌሎች አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ነበሩ።

«ቶስያን ኮርሲካዊው ነኝ፣ ፓፒዮ መሆን አለብህ።»

«ነኝ።»

«ልክ እንደእናንተ ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ወሬውም ፈጥኖ ይጓዛል። ካርባይንህ ወዴት አለ?»

«ወደ ወንዙ ወርውረነዋል።»

«የት?»

«እኛ ከዘለልንበት ከሆስፒታሉ ግንብ ትይዩ።»

«እንግዲያ መልሶ ለማግኘት ይቻላላ?»

«እንደዚያ ይመስለኛል። እዚያ ውሃው በጣም ጥልቅ አይደለም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዴት ዐወቅከው?»

«የኛሰለውን ጓደኛየን ወደ ጀልባ ለመሸከም በውስጡ ሔደንበት ነበር::»

«ምን አጋጥሞት ነው?»

«ቅልጦመን ተሰብሮ»

«ምን አድርገህለታል?»

«ቅርንጫፎች ሰነጣጥቄ አሥሬለታለሁ::»

«ሥቃይ አየተሰማው ነዋ?»

«አዎ::»

«ወዴት ነው?»

«ጀልባ ውስጥ::»

«የመጣሁት ለእርዳታ ነው ብለሃል፤ ዕርዳታው ምን ዐይነት ነው?»

«የተሻለች ጀልባ::»

«አኛ ጀልባ አንድንስጥህ ትፈልጋለህ እንዴ?»

«ናምጣበት ገንዘብ አለኝ::»

«ጥሩ፤ እንግዲያው የእኔን አሸጥልሃለሁ:: አዲስ የሆነች ከፍተኛ ጀልባ ናት:: ባለፈው ሳምንት ከአልበና ሰርቂያት ነው:: ጀልባ ሳትሆን ውቅያኖስ አቋራጭ መርከብ ናት:: የሚጎድላት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ወለል:: ግን በሁለት ሰዓት ውስጥ ጥሩ ዓይነት እንገጥምላታለን:: ሊያስፈልግህ የማችለውን ማንኛውንም ነገር ታሟላለች:: አንድ መሪ፣ ከጠንካራ እንጨት የተሠራ አንድ ባለዐሥራ ሦስት ጫማ ተራዳና አንድ አዲስ ከባድ የነፋስ ሸራ አላት:: ለዚህች ምን ትከፍለኛለህ?»

«አንተ ምን ያህል እንደምትፈልግ ንገረኝ:: እዚህ የዕቃዎች ዋጋ ሰንት እንደሚያወጣ አላውቅም::»

«ካለህ ሦስት ሺ ፍራንክ:: ከሌለህ ነገ ሌሊት ሔደህ ካርባይኑን ፈልግና በለውጡ ጀልባዋን አሰጥሃለሁ::»

«አልፈልግም:: መክፈሉን አመርጣለሁ::»

«እሺ:: በሺያጩ ተስማምተናል:: ቡና አምጡልን ላፑስ!»

እኔን ለመውሰድ መጥቶ የነበረው ከድንክ የማይሻለው ላፑስ፣ ከምድጃው በላይ ከሚገኘው ግድግዳ ላይ ወደ ተሠራ አንድ ቁምሣጥን ሔደና አዲስ በሚያንጸባርቅ ንውስ ጎድጓዳ ሣህን ላይ ጠርሙስ ውስጥ የተቀመጠ ቡና ቀድቶ ምድጃው ላይ ጣደ:: ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሣህኑን አነሣና በኩባያዎቹ ቀዳ:: ቶሲያን ከኋላው ወደ ተቀመጡት ሰዎች ሰገግ ብሎ ኩባያዎቹን አደለ:: «አትሥጋ፤ ይህ ሣህን ለእንግዶች ብቻ ነው:: በእርሱ የሚጠጡ ቆማጦች የሉም» በማለት ላፑስ ጎድጓዳ ሣህኑን አቀበለኝ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ሣህኑን ተቀበልኩና ጠጣሁ። ከዚያም ጉልበቴ ላይ አሣረፍኩት። በዚያው ወቅት እንዲት ጣት በሣህኑ ላይ መጣበቋን ተመለከትኩ። ይህን በማይበት ጊዜ ነበር ላጥስ፣ «ወይ መከራ፣ ደግሞ እንድ ሌላ ጣት ጣልኩ። ወዴት አባቷ ሔደች?» ያለው።

«ይህችውና» አልኩና ሣህኑን አሳየሁት።

መንጭቆ አነሣና አሳዙ ውስጥ ወረወራት። «መጠጣት ትችላለህ። የያዝኝ ደረቅ ቁምጥና ነው። የማልቀው አየተቆራረጥኩ ነው፣ ግን አልሸትም፣ አስተላላፊም አይደለሁ» አለ። የሚጠበስ ሥጋ ጠረን አወደኝ። የአርሱው ጣት መሆን አለባት።

«ዝቅተኛ ማዕበል እስከሆነ ድረስ ቀኑን ሙሉ እዚሁ መዋል አለብህ። ሒድና ለጓደኞችህ ንገራቸው። የተሰበረውን ጓደኛህን ከጎጆዎቹ ወደ አንደኛዋ አምጣው። ያላችሁን ማንኛውንም ነገር ከጀልባ ውስጥ አውጡና አስቀምጡት። እዚህ ሊረዳችሁ የሚችል ማንም ሰው የለም። ለምን እንደሆነም ይገባሃል» አለ ቶሲያን።

ወደ ባልደረቦቹ ተመለስኩና ከሎሲዎን ተሸከመን ወደጎጆዋ አመጣነው። ከአንድ ሰዓት በኋላ ማንኛውም ነገር ከጀልባዋ ወጥቶ በጥንቃቄ ተቀመጠ። ጀልባዋንና በተጨማሪ እንድ መቅዘፊያ በስጦታ እንድናበረክትለት ላጥስ ጠየቀኝ። ሰጠሁትና እርሱ ከሚያውቀው አንድ ልዩ ቦታ ሊደብቃት ወሰዳት። ሌሊቱ በፍጥነት ሔደ። ሦስታችንም ቶሲያን በላክልን አዲስ ብርድ ልብሶች ተጠቅልለን ጎጆዋ ውስጥ ተኛን። ብርድ ልብሶቹ ከፋብሪካ ሲወጡ በተጠቀለሉበት ወፍራም ወረቀት ውስጥ እንዳሉ ነበር። እንደዚያ እንደተጋደምን ወደ ደሴቷ ከመጣን ጀምሮ ምን እንዳደረግኩና ከቶሲያን ጋር የቀናኝን የሸያጭ ሰምምነት ለከሎሲዎና ለማቹሬ በዝርዝር አወራሁላቸው።

«አንግዲህ ለማምለጥ በእርግጥ ሰድስት ሺ ፍራንክ ሊያስወጣን ነው። ግማሹን እኔ እከፍላለሁ ፓፒዮ፣ ወይም ያለኝን ሦስት ሺ» አለ ከሎሲዎ አፉ እንዳመጣለት።

«ሕዚህ ያለነው ስለገንዘብ ለመጨቃጨቅ አይደለም። ገንዘብ እስካለኝ ድረስ እኔ እከፍላለሁ። ከዚያ ደግሞ እናያለን።»

ሌሊት ብቻችንን ነበርን። ሲነጋ ቶሲያን ወደእኛ መጣ። «እንደምን አደራችሁ። ወደ ውጭ ለመውጣት አትፍሩ። እዚህ ማንም የሚያስቸግራችሁ ሰው የለም። በወንዙ ላይ ስለሚንቀሳቀሱት የፖሊስ ጀልባዎች በደሴቷ አናት ከሚኖኝ እንድ የካካዎ ዛፍ ላይ ሆኖ የሚጠባበቅ ሰው አለ። እስካሁን ምንም አላየንም። እንድ ነገር ሲያይ ወደ ታች ይመጣና ይነግረናል። ካስፈለጋችሁ ፓፓያ ራሳችሁ ቁረጡ።

«የወለሉ ጉዳይ ከምን ደረሰ ቶሲያን?» አልኩት።

«የሕከምና ከፍሉን መገዢያ ነቅለን እንገጥምለታለን። የተሠራው ከወፍራምና ጠንካራ እንጨት ነው። ወለሉ ሁለት ጣውላዎች ይፈልጋል። ማታውኑ ጀልባዋን ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ አውጥተናታል። መጥተህ ተመልከታት።»

ሐድን። ርዝመቷ ዐሥራ አምስት ሜማ የሆነ፣ አንድ የተራዳ መትከያ ጉድጓድና ሁለት አግዳሚ መቀመጫዎች ያሏት አዲስና ድንቅ የሆነች ጀልባ ነበረች። ከባድ ስለነበረች ማቹሬና እኔ ሆነን ለመግልበጥ አቅቶን ነበር። እንደዚሁም የነፋስ ሸራውና ገመዶቹም አዲስ ነበሩ። ለበርሜል ውሃ መስቀያ የሚሆኑ ቁለበቶች ከጎን ይገኛሉ። መሥራት ጀመርን። በረጅም ቪቴዎችና በአራት የብረት ማገሮች በጥበቅ የተሠራ አንድ ጠንካራ ወለል ከፊት እስከ ኋላ ድረስ ከሰዓት በኋላ ተገጠመላት።

ቆማጦቹ ዙሪያችንን ከብ ሠርተው በፀጥታ ይመለከታሉ። ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ቶሲያን ይመራናል። እኛም እንታዘዛለን። በቶሲያን ፊት ላይ ምንም የቁስል ምልክት የለበትም። በእርግጥም እንደማንኛችንም እንከን የሌለበት ይመስላል። ግን ሲናገር በአንድ በኩል ያለው ፊቱ፣ ማለት የግራው ብቻ የሚንቀሳቀስ መሆኑን ተገነዘብኩ። የእርሱም እንደዚሁ ደረቅ ቁምጥና መሆኑን ነገረኝ። ከቀኝ እጁ ጀምሮ ግማሽ አካላቱ በድን እንደሆነና የቀኝ ባቱም በቅርብ ተቆርጦ እንደሚወድቅ ይጠበቃል። የቀኝ ዐይኑ ልክ እንደ ጠርሙስ አንድ ቦታ የተተከለ ነበር። ሊያይበት ይችላል፣ ግን ሊያነቃንቀው አይችልም።

ማንም ሰው ይህን አሳዛኝ ዕድላቸውን ባያየው ምኞቴ ነው።

በመሥራት ላይ እያለሁ ከቶሲያን ጋር አወራ ነበር። ሌላ ማንም የሚናገር ሰው የለም። ሆኖም ከብረት ማዕዘኖች አንዱን ለማንሣት ስል ከመካከላቸው አንዱ፤ «አትንካቸው። አንደኛውን ብረት እነቅላለሁ ስል ራሴን ቆርጨ ሰለነበር ደሙን ለመጥረግ ብሞክርም አልተቻለኝም» አለ።

ሌላው ቆማጣ በላዩ ላይ ሩም አፈሰሰበትና በእሳት አቃጠለው። ከዚያም እየደጋገመ እንደዚሁ አደረገ። «አሁን ልትጠቀምበት ትችላለህ» አለ ሰውየው በመሥራት ላይ እንዳለ። ቶሲያን ከሰዎቹ ለአንደኛው እንደዚህ አለው። «አንተ ብዙ ጊዜ ከደሴቷ ውጪ ተመላልሰሃል። ፓፒዮና ጓዶቹ ግን እንግዶች ናቸው። ታዲያ እንዴት እንደሚያደርጉ አሰኪ ምከራቸው።»

ሠዓሬ ማዕበሉ ፀጥ እንዳለ ይቆይና በዘጠኝ ሰዓት ላይ እየገፉ መሐድ ይጀምራል። በዐሥራ ሁለት አካባቢ እስከ ወንዙ አፍ ድረስ ያለውን ስድሳ ማይል በሦስት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለመሸፈን የሚረዳችሁ ኃይለኛ ማዕበል ይነሣል። ከዚያም ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ጀልባችሁን ከአንድ ጠንካራ ዛፍ ጋር ደህና አድርጋችሁ በማሠር ከለሊቱ ስድስት ሰዓት የሚነሣውን ማዕበል መጠበቅ ይኖርባችኋል። ይህም ማዕበል እስከ ንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ይቀጥላል። ግን በዚያ ወቅት አትንቀሳቀሱ፣ ማዕበሉ ፍጥነት የሚጨምረው ቀስ በቀስ ነው። በዐሥር ሰዓት ተኩል ወደ ወንዙ መካከል

t.me/OLDBOOKSPDF

ግቡ። የሠላሳ ማይል ጉዟችሁን ለመፈጸም ከመንጋቱ በፊት አንድ ሰዓት ተኩል ይኖራችኋል። የመጨረሻ ዕድላችሁ ይህ ነው። ፀሐይ በበሥራ ሁለት ሰዓት ብቅ ስትል ከባሕሩ ደርሳችሁ ጉዞ ትቀጥላላችሁ። ዘበኞቹ እንኳ ቢያዩዋችሁ፣ ሊይዟችሁ አይችሉም። ምክንያቱም በባሕሩና ወንዙ መገናኛ ላይ የሚደርሱት ማዕበሉ ሲመለስ ስለሆነ የአሸዋ ከምር ያማጸቸዋል። ሊያልፉት ስለማይችሉ እናንተ ይሰካላችኋል፣ ህልውናችሁን የሚወስነው ይህን ግማሽ ማይል ቀድማችሁ መገኘት ነው። ይህች ጀልባ አንድ የነፋስ ሸራ ብቻ አላት። የእናንተስ ጀልባ ምን አላት?»

«አንድ ዋና የነፋስ ሸራና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራ።»

«ይህች ከባድ ጀልባ ናት። ከፊት ጀምሮ እስከ ምሰሶው የሚዘረጋ አንድ ባለ ሦስት ማዕዘን ሸራና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራ፣ እንዲሁም ሁለት ተጨማሪ ሸራዎች አሏት። ሸራዎቻችሁን በሙሉ ወጥራችሁ በቀጥታ ወደ ማዕበሎቹ ውስጥ ግቡ። ከወንዙና ከባሕሩ መገናኛ ላይ ሞገዱ ሁልጊዜ ከባድ ስለሚሆን፣ ጀልባዋን ለማርጋት ጓደኞችህን ከጀልባዋ ሥር ለጥ ብለው እንዲጋደሙ አድርግና አንተ መሪውን ጥምም አደርገህ በእጅህ ጨብጥ። ዣሙዴን ከባትህ ላይ እንዳታስር። ግን በቀለበቱ ውስጥ አሳልፍና አንድ ጊዜ በአጅህ ላይ ጠምጥመህ ያዘው። የነፋሱ ኃይልና የማዕበሉ መጠን ተጨማምሮ የሚገለብጣችሁ መስሎ ቢታይህ ብዙም አትጨነቅ። ጀልባዋ በገዛ ራሷ ወዲያውኑ ሚዛኗን ትጠብቃለች። አትቁም። ዋናውን የነፋስ ሸራ ወደ ነፋስ አቅጣጫ አድርግና የሦስት ማዕዘኑንና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራውን ሳታወርድ መጓዝህን ቀጥል። ባሕሩ ፀጥ ሲል የነፋስ ሸራውን ለማውረድ ጊዜ ይኖርሃል። ከዚያም እንደገና ከሰቀልከው በኋላ መንቀሳቀስ ቀጥል። ለመሆኑ የጉዞህን አቅጣጫ ታውቀዋለህ?»

«አላውቀውም። የማውቀው ቢኖር ቬኔዙዌላና ኮሎምቢያ በስተሰሜን ምዕራብ በኩል መሆናቸውን ብቻ ነው።»

«ልክ ነህ። ግን ወደ ጠረፍ እንዳትመለስ ተጠንቀቅ። ከኛ ትይዩ ያለችው የዳች ጊያና አስረኞችን ሁሉ መልሳ ለፈረንሣይ ታስረክባለች። የእንግሊዝ ጊያናም እንደዚሁ ታደርጋለች። ትሪኒዳድ ግን አትመልሳችሁም። ሆኖም ከዚያ መቆየት የሚቻለው ሁለት ሳምንት ብቻ ነው። ቬኔዙዌላ ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመት በመንገድ ሥራ ብርጌድ ውስጥ ካሠረቻችሁ በኋላ ትመልሳችኋለች።

በጥሞና አዳመጥኩት። በየጊዜው ከደሴቷ መውጣቱን ነገረኝ። ቆማጣ ስለሆነም በአጭር ትእዛዝ ዘወትር እየተባረረ ይመለስ ነበር። ከእንግሊዝ ጊያናዋ ጀርድ ታውን ግን ፍጹም ርቆ እንዳልሔደ ተናገረ። በባዶ እግሩ ስለነበር ለማየት እንደቻልኩት ጣቶቹን በማጣቱ ነው እንጅ በግልጽ ቆማጣ የሚባል አልነበረም። የነረኝን መመሪያዎች እንድደግማቸው ቶሲያን ጠየቀኝና አንድ ስሕተት ሳላደርግ ቃል በቃል

t.me/OLDBOOKSPDF

መለስኩለት። በዚህ ነጥብ ላይ እንዳለን የሐንስ ፐር፣ «በተንጣለለው ባሕር ላይ ምን ያህል ጊዜ ማጥፋት ይኖርበታል?» አለው።

በቀጥታ ራሴ መለስኩለት። «ሦስት ቀናት ያህል ወደ ሰሜን ምሥራቅ እጓዛለሁ፣ ማለትም ወደ ሰሜን አቅጣጫ ከሚሔደው የውሃ አዙሪት ጋር። በአራተኛው ቀን ግን ወደ ሰሜን ምዕራብ አመራለሁ።»

«ሳበዝ» አለ ቆማጣው። «ባለፈው ጊዜ እኔም እንደዚሁ ነበር ያደረግኩት። ወደ ሰሜን ምሥራቅ ለመሔድ ሁለት ቀን ብቻ አጠፋሁና አንግሊዝ ጊያና ደረስኩ። ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሦስት ቀን ከተጓዝክ፣ ሰሜናዊ ትሪኒዳድን ወይም ባርባዶስን ታልፍና ቬኔዙዌላን እያካለልክ ሳታውቀው ኮሎምቢያ ወይም ኩራሶ ትደርሳለህ» አለ።

«ጀራባህን ምን ያህል ሠው የሸጥካት ቶሲያን?» ሲል የሐንስ ፐር ጠየቀው።

«ሦስት ቪ። በጣም ብዙ ነው እንዴ?»

«አይደለም። ለዚህ አይደለም የጠየቅኩህ። ለማወቅ ብቻ ፈልጌ ነው። ገንዘቡን ታገኛለህ ፓፒዮ?»

«አዎ።»

«የሚተርፍ ይኖርሃል?»

«የለኝም፣ ያለን ይሸው የጓደኛየ የክሎሲዎ ሦስት ቪ ጉራንከ ብቻ ነው።»

«ሽጉጤን ትገዛኛለህ ቶሲያን?» አለና የሐንስ ፐር በማከታተል፣ «አንዚህን ጓዶች ለመርዳት እፈልጋለሁ። ምን ያህል ትከፍለኛለህ?» አለ።

«አንድ ቪ ፍራንከ» አለና ቶሲያንም፣ «አኔም እንደዚሁ ልረዳቸው፣ እፈልጋለሁ ሲል ሐሳቡን ገለጸ።

«ለማንኛውም ዕርዳታችሁ እናመሰግናለን» አለ ማቹሬ ወደ የሐንስ ፐር እየተመለከተ።

«እናመሰግናለን» አለ ክሎሲዎም።

እኔ ግን፣ በውስጤ ታፍረት ስለ ተሰማኝ፣ «አይሆንም፣ መቀበል አልችልም። በምንም ምክንያት» አልኩ።

የሐንስ ትኩር ብሎ ወደ እኔ ተመለከተና፤

«በዕርግጥ ምክንያት አለ እንጂ። ሦስት ቪ ፍራንከ ብዙ ገንዘብ መሆኑን ዐውቃለሁ። ያም ሆኖ ይህች ጀልባ ከፍተኛ ስለሆነች፣ ቶሲያን ለእናንተ በዚህ ዋጋ የሸጠላችሁ ቢያንስ ሁለት ቪ ፍራንከ ከስሮ ነው። ስለዚህ እኔም እንደዚሁ አንድ ውለታ ልውልላቸሁ የማልችልበት ምክንያት የለም» አለ።

ከዚያም አንድ በጣም ስሜት የሚነካ ጉዳይ ተከናወነ። ላሹዊት አንድ ባርኔጣ ከመሬት ላይ አነሥመጠና ቆማጠቹ ሁሉ እየመጡ ብሮችና ሳንቲሞች ይወረውሩ ጀመር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከየአቅጣጫው በመምጣት የመጨረሻው ዝቅተኛ ሰው ሳይቀር አንድ ነገር ያስቀምጣል። አሁን በዕርግጥ አፍሬ ነበር። ትንሽ የተረፈ ገንዘብ እንዳለኝ አሁን እንዴት አድርጌ ልነግራቸው እችላለሁ? ወይ አግዚአብሔር፣ ምን አጋጣሚ ነው! በዚህ በጎ አድራጎት መካከል ጉሀን መናገሩ ደግሞ ውርደት ነበር። ከዚያም፣ ቅንጣት ጣት ያልነበረውና እጆቹ ተጎንድሸው የተጎሳመደ አንድ ጥቁር የቲምበከቱ ተወላጅ እንደዚህ አለ። «ገንዘብ ለእኛ ኑሮ አይረዳንም። ለመቀበል ታፍረት አይሰማችሁ። ሁሉንም የምንጠቀምበት ለቁማር መጫወቻ፣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ከአልቢና ወደ እዚህ የሚመጡ የቅማጣ ኮረዳዎችን ለመደለያ ብቻ ነው።» ይህ አነጋገር ታፍረቴን ስላሰወገደልኝ ገንዘብ አለኝ ማለቴን አርግፍ አድርጌ ተውኩት።

ቆማጦቹ የቀይ መስቀል ምልክት ባለበት አንድ ቅርጫት ውስጥ ሁለት መቶ የተቀቀሉ እንቁላሎች ሞልተው ሰጡን። በዚያን ቀን ጧት ከዕለቱ የመድኃኒት ራሽን ጋር መጥቶላቸው የነበረው ያው ቅርጫት ነበር። በተጨማሪ ቢያንስ አያንዳንዳቸው ስድሳ ፓውንድ የሚመዝኑ ሁለት ኤሊዎች ከነነፍሳቸው፣ የትምባሆ ቅጠሎች፣ ሁለት ፓኮ ከብሪትና አንድ መጫሪያ፣ መቶ ፓውንድ የሚመዝን አንድ ከረጢት ሩዝ፣ ሁለት ኪሻ ከሰል፣ ከሕከምና ከፍል የተወሰደች እንዲት ፔርሙዝና አንድ ደምበኛን ነዳጅ ሰጡን። በዚህ ጎስቋላ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው በእኛ አሥጊ ሁኔታ ስሜቱ ተነክቶ ሊረዳን ፈለገ። የእኛ ማምለጥ ለእነርሱ እንደሆነላቸው ይመስሉ ነበር። ጀልባዋ በመጀመሪያ እኛ ወርፈንበት ወደ ነበረው አካባቢ ተጎተተች። በባርኔጣው ውስጥ ያለውን ገንዘብ ሲቆጥሩት ስምንት መቶ ዐሥር ፍራንክ ሆነ። የቶሲያን ያለብኝ ዕዳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ፍራንክ ብቻ ነበር። የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን ከሎሲዎ ሰጠኝና በሁሉም ሰው ፊት ከፈትኳት። አንድ ባለ አንድ ሺ ፍራንክ ኖትና አያንዳንዳቸው ባለ አምስት መቶ ፍራንክ አራት ኖቶች ይዛለች። ለቶሲያን አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ ሰጠሁትና ሦስት መቶ ፍራንክ መልስ በመስጠት ላይ እንዳለ፣ ያውልህ፣ ሸጥጡንም ወሰድ። ስጦታ ነው። ብቸኛ ዕድልህ ይህ ነው። በመሣሪያ ዕጦት ምክንያት በመጨረሻ ጊዜ ዕድልህ እንዲከላሽ አልፈልግም። ግን ለከፋት እንደማትጠቀምበት ተስፋ አደርጋለሁ» አለ።

በቅድሚያ አርሱን፣ ከዚያም ሌሎቹን በሙሉ እንዴት አድርጌ እንደማመሰግናቸው አታውቅ። ጤና ሪዳቱ በአንድ ትንሽ ሣጥን ውስጥ ጥጥ፣ አልኮል፣ አስፐሪን፣ ፋሻ፣ አየዲን፣ መቀስና ማጣበቂያ አዘጋጀልን። አንድ ቆማጣ ደግሞ፣ ሁለት ትንንሽ የተላጉ የስብራት ማሰሪያ ጣውላዎችና ከፋብሪካቸው ታሽገው እንደወጡ የሚገኙ ሁለት የፋሻ ጥቅሎችን በማምጣት የከሎሲዎን ማሰሪያ እንድንለውጥ ረዳን።

ዐሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ዝናም መጣል ጀመረ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ዕድል አጋጠማችሁ። ዝናቡ አዳኞቻችሁ እናንተን ከማየት ይገታቸዋል። በግማሽ ሰዓት ቀድማችሁ የመነሣት ዕድል ይኖራችኋል ማለት ነው። ቅድሚያ ስለሚሰጣችሁ አሁን መሔድ ትችላላችሁ። ጧት ላይ ወደ ወንዙ አፍ ቶሎ እንድትቃረቡ ያደርጋችኋል» አለ የሐንስ ፐር።

«ሰዓቱን እንዴት ዐወቀዋለሁ?»

«ማዕበሉ በሚነሣበት ወይም በሚበርድበት ወቅት ነው።»

ጀልባዋ ተንሣፈፈች። ከቀድሞዋ በጣም የተለየች ነበረች። ይህች ጀልባ የእኛን ጭነት ሁሉ ተሸክማ ከውሃው መስመር በላይ ያዐሥራ ስድስት ኢንች ከፍታ ነበራት። ከወንዙ አሰካልወጣን ድረስ ስለማንጠቀምበት ምሰሶው በነፋስ ሸራው ተጠቅለሎ ከጀልባዋ ሥር ተቀመጠ። መሪውንና መቅዘፊያውን ከግዘጋጀታችንም በላይ ለእኔም የምቀመጥበት አንድ የሣር ትራስ አገኘሁ። ከጀልባዋ ሥር፣ በእኔና በውሃው በርሜል መካከል ለከሎሲዎ ብርድ ልብሶች ደለደልንለት። ማቹሬም ከሥር በኩል ከፊት ለፊት ተቀመጠ። በዚያችኛዋ ጀልባ ፍጹም ያልነበረኝ መተማመን አሁን ከመቅዕበት በዘህችኛዋ አደረብኝ።

አሁንም ገና አየዘነመ ነበር። ስለሆነም በወንዙ መካከል ቁልቁል መውረድ ይኖርብኛል። ሆኖም ወደ ዳች ጊያና አቅጣጫ ትንሽ ወደ ሳ ,ነማድላት ነበረብኝ። «ደህና ሁኑ። ተንቀሳቀሱ!» አለ የሐንስ ፐር።

«መልካም ዕድል» አለና ቶሲያን ጀልባዋን አንድ ጊዜ በኃይል በእግሩ ገፋት።

«አመሰግናለሁ ቶሲያን፤ አመሰግናለሁ የሐንስ፤ ሁላችሁንም ፣ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ!»

ተመላሽ ማዕበል ፍጥነት ከጀመረ ከሁለት ሰዓት ተኩል በፊት በመሆኑና አሁንም የሚንቀሳቀሰው በኃይል ስለነበረ፣ ወዲያው ከመነሣታችን ርቀት ተጓዝን።

ዝናሙ ስለጨመረ ከፊት ለፊታችን ሠላሳ ጫማ ርቀት እንኳን ማየት አልቻልንም። ከበታቻችን ሁለት ትንንሽ ደሴቶች ስለነበሩ፤ ማቹሬ ከጀልባዋ ፊት ሰገግ በማለት በአካባቢው የቋጥኝ ምልክቶች መኖራቸውን በዐይኖቹ ይቃኛል። ምሽት መጣ። አንድ ትልቅ ዛፍ በዝግታ ጉዞ ከእኛ ጋር በወንዙ ቁልቁል ይወርዳል። ለተወሰነ ጊዜ በቅርንጫፎቹ መሰናከልነት ችግር ገጥሞን ነበር። ግን በፍጥነት ራሳችንን አላቀቅንና የቸኮላ ፍጥነታችንን ቀጠልን። ሲጃራ አጨስንና ትንሽ ሩም ጠጣን። ሩም የተሞላባቸው በሰሌን የተሸፈኑ ስድስት የኪያንቲ ጠርሙሶች ቆማጦቹ ሰጥተውናል። ዝም ብለን ጠጣን እንጂ፣ የቆማጦቹን አሰታቱ አካለጎዶሎነት ከእኛ ውስጥ ማንም ያነሣ አልነበረም። የምናወራው ቢኖር ስለ ርኅሩኅነታቸው፤ ችሮታቸውና፤ ጨዋነታቸው፤ እንደዚሁም ከውቅራታሙ ብሪቶን ጋር ለመገናኘት ስላቢታን ዕድል ነበር። ዝናሙ እየከበደ ሔደ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እስክ እጥንቱ ድረስ በስብሼ ነበር። ሆኖም የሱፍ ሹራቦቻችን ጥሩ ከመሆናቸው የተነሣ በጣም ብንርስም ሙቀት አልተለየንም። በቅዝቃዜ የተኮማተረው በመሪው ላይ ያለው እጄ ብቻ ነበር።

«አሁን በስዓት ከሐያ አምስት ማይል የበለጠ እየተጓዝን ነው» አለ ማቹሬ።

«ምን ያህል ርቀት ተጉዘናል ብለህ ትገምታለህ?»

«በደቂቃ ውስጥ እነግርሃለሁ» አለና ከሎሲዎ፣ «አንድ ጊዜ ቆይ ሦስት ሰዓትና ዐሥራ አምስት ደቂቃ» አለ።

«አየቀለድክ ነው። እንዴት ዐወቅከው?»

«ከተነሣን ጀምሮ ያለማቋረጥ ሦስት ሦስት ሴኮንዶች ለየብቻ አቆጥር ነበር። በአያንዳንዱ ሦስት መቶ መጨረሻ አንድ ቁራጭ ካርቶን እቀዳለሁ። እስከ አሁንም ሠላሳ ዘጠኝ ቁራጮች ቀድጃለሁ። አያንዳንዳቸው ሦስት መቶ ሴኮንዶች አምስት ደቂቃ እሰከሆኑ ድረስ ከተነሣን ጀመሮ ሦስት ሰዓት ከሩብ ይሆናል ማለት ነው። ካልተሳሳትኩ በስተቀር በሚቀጥለው ዐሥራ አምስት ወይም ሐያ ደቂቃ ቁልቁል መውረዳችን ቀርቶ ወደ መጣንበት ተመልሰን መውጣት ይኖርብናል።»

ወንዙን አያካፈልኩ ለማቋረጥና ወደ ዳች ጊያና ጠረፍ ለመጠጋት መሪውን ወደ ቀኝ ገፋሁ። ልክ ከቁጥቋጦ ጋር ልንላተም ስንል ማዕበሉ ቆመ። ወደላይም ሆነ ወደፊት አልተንቀሳቀስንም። አሁንም ገና እየዘነመ ነበር። መነጋገር አቆምን፣ ማጨስ አቆምን። «አንድ መቅዘፊያ ግፉ» ብዬ ሹክ አልኩ። መሪውን በቀኝ ጭኔ ሥር በመያዝ እኔም እቀዝፋለሁ። ቁጥቋጦውን መንጥረን ቅርንጫፎች ሳብንና ከሥሩ ተጠለልን። የደኑ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጨለማ ነበር። ወንዙም ደፍርሶ በከባድ ጭጋግ ተሸፍኗል። በማዕበሉ ዳግመኛ መቀስቀስ ምልክት ካልሆነ የወንዙ መጨረሻና የባሕሩ መጀመሪያ የት እንደሆነ መናገር አይቻልም።

ታላቁ አስቸጋሪ ጉዞ

ማዕበሉ አንዴ ከተነሣ የሚቆየው ለስድስት ሰዓት ያህል ነበር። እሰኪነሣ ድረስ ደግሞ አንድ ሰዓት ተኩል መጠበቅ ሊኖርብን ነው። ይህም ማለት እንቅልፍ ከወሰደኝ የሰባት ሰዓት የመኝታ ጊዜ ነበረኝ። አሁን ካልተኛሁ በባሕር ላይ ምን ጊዜ እተኛለሁ?

በበርሜሉና በአግዳሚው መቀመጫ መካከል እንደ ድንኳን አድርጎ ማቹሬ አንድ ብርድ ልበስ ዘረጋልኝና፣ በግራም ሁኔታ ተከልየ ለጥ አልኩ። ሕልም የለም። ዝናም ወይም የእኔ አለመመቻቸት፣ ምንም አልረበሸኝም። ማቹሬ ቀስቅሶ እንዲህ እሰከሚለኝ ድረስ ተኛሁ።

«ጊዜው የተቃረበ ይመስለኛል ፓፒ። ማዕበሉ መመለስ ከጀመረ ረጅም ጊዜ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው።»

ጀልባዋ በወንዙ ቁልቁል አፈተለከች። የማዕበሉ እንቅስቃሴ ጣቶቼን ይሰማኛል። የሚንቀሳቀሰው በጣም ፈጥኖ ነበር። ዝናሙ አቆመ። ከወንዙ ፊትለፊት በሦስት መቶ ጫማ ላይ የሚንሳፈፉትን የሣር ማብሰቢያች፣ ዛፎችና የማይለዩ ጥቁር ቅርፆች የሩብ ጨረቃ ብርሃን ግልጽ አድርጋ አሳየችኝ። በወንዙና በባሕሩ መካከል ያለውን ከልል ለመለየት ሞከርኩ። አኛ በነበርንበት አካባቢ ነፋስ የለም። በወንዙ መካከል ይኖር ይሆን? ጠንካራ ይሆን? የወንዙን መጨረሻና የባሕሩን መጀመሪያ መለየት የምችለው ወደ ሰማይ በመመልከት ብቻ ነበር። ከአሰብነው በላይ በጣም ርቀን ቁልቁል መጥተን ስለነበር እንደሚመስለኝ ቢበዛ የምንርቀው ከወንዙ አፍ ከስድስት ማይል በላይ አይሆንም። እንዳንድ ሙሉ ጉጭ ራም ከለበስን። ምዕሶው ወዴት መቅም እንዳለበት ለማረጋገጥ የጀልባዋን ዙሪያ ቃኘሁ። አነሣነውና በአግዳሚው ወንበር ከሚገኘው ቋቱ ውስጥ አስገብተን ገጠምነው። የነፋስ ሽራውን ሰቀልኩ፣ ግን ከተራዳው ላይ እንደ ተጠቀለለ ተውኩት። ባለ ሦስት ማዕዘን የአቅጣጫ ማስተካከያውን ሽራም በምንፈልግበት ወቅት እንዲወጥራቸው ለማቹሬ አዘጋጅቼለት ነበር። የነፋስ ሽራውን ለመዘርጋት ማድረግ ያለብኝ ከምሰሶው ጋር የተጠቀለለበትን ገመድ መተርተር ብቻ ነበር። ይህንንም ከተቀመጥኩበት ሳልነሣ ማድረግ እችላለሁ። ማቹሬ ከፊት በኩል አንድ መቅዘፊያ፣ እኔ ከኋላ ሌላ ይዣለሁ።

ከወንዙ ዳር ስድሳ ጫማ እንደ ራቅን ማዕበሉ የሦስት መቶ ያርድ ያህል ቁልቁል ወሰደን። ወዲያውኑ ነፋስ ገፋና ወደ ወንዙ መካከል አደረሰን።

«የነፋስ ማስተካከያ ሽራዎቹን አንሣና ሁለቱም በሚገባ ጠበቀው መታሠራቸውን አረጋግጥ!»

ነፋስ ሞላቸውና ጀልባዋ ልክ እንደ ፈረስ ወደፊት ተፈተለከች። ወንዙ ድንገት በፀሐይ ብርሃን የተጥለቀለቀው ገምተነው ከነበረበት ጊዜ ዘግይቶ ነበር። የፈረንሣይ ጠረፍ በግምት አንድ ማይል ከሩብ በስተቀኞችን፣ የዳችን ጠረፍ በግምት ግማሽ ማይል በስተግራችን በቀላሉ መለየት እንችላለን። እየተነሣ የሚወድቀው ነጭ አረፋ ከፊት ለፊታችን በጣም ግልጽ ሆኖ ይታየን ነበር።

«የክርስቶስ ያለህ! ስለ ሰዓቱ ተሳስተን ነበርኮ» አለ ከሎሲዎ።

«ልናስተካክለው እንችላለን ብለህ ታስባለህ?»

«አላውቅም።»

«ማዕበሉ እንዴት ከፍተኛ እንደሆነ ተመልከት! ሞገዱ ተመልሶ ነበር እንዴ?»

«ሊሆን አይችልም። ቁልቁል የሚንሳፈፍ ነገር አያለሁ።»

«የምንወጣው አይደለም። ጊዜ የለንም» አለ ማቹሬ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ዝም በልና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሽራዎቹን አጥብቀህ ያዝ። አንተም ከሎሲዎ እንደዚሁ ዝም በል።»

ድው . . . ድው . . . ተኩስ ተከፈተብን። ተኩሱ ከየት እንደመጣ በሁለተኛው ዙር መመልከት ቻልኩ። ዘበኞቹ አልነበሩም። ተኩሱ የመጣው ከዳኞች ጠረፍ በኩል ነበር። ዋናውን የነፋስ ሽራ ስሰቅለው በፍጥነት ነፋስ ሞላና በጣም በመወጠሩ የእጄን እንጓ ገንጥሎ ሊወስደው ተቃርቦ ነበር። ጀልባዋ ዐርባ አምስ ዲግሪ ከአፍንጫዋ ቀና ብላ ተነሣች። በጣም ቀላል ስለነበር የቻልኩትን ያህል የነፋሱን ኃይል ለመቆጣጠር ሞከርኩ። ድው . . . ድው . . . አለና ከዚያ ጸጥ አለ። ወደ ፈረንሣይ ጠረፍ አቅራቢያ አዘንብለን ናፖል። ተኩሱም ያቆመው ለዚሁ ናፖል። ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነ ፍጥነት ወደ ፊት ተገፋን። ላይቆም ከፈረንሣይ ጠረፍ አካባቢ ከሚገኘው የባሕሩና የወንዙ መገናኛ አፍ ተደንቅረን ዐረፍነው። ሰዎች ወደዚያው አቅጣጫ ሲሯሯጡ አየን። ገመዱን በተቻለኝ መጠን በዝግታ ትተትኩ። ዋናው የነፋስ ሽራ አሁን ከፊት ለፊቱ ቁጥ ብሏል። የነፋስ አቅጣጫ ማስተካከያ ሽራው በገዘ ራሱ ተስተካከለ፣ ባለ ሦስት ማዕዘን ሽራውም እንደዚያው። ጀልባዋ ሦስት አራተኛ ዙራ ተሸከረከረች። የነፋስ ሽራውን ዘረጋሁና ከነፋሱ ቀድመን እየሮጥን የወንዙንና የባሕሩን መጋጠሚያ ለቀቅን። ከርስቶስ! ተሣክቶልን ነበር! ከፀሥር ደቂቃ በኋላ የመጀመሪያው የባሕር ማዕበል ቢጋረጥብንም በቀላሉ በላዩ ላይ ተንሳፈን አለፍን። በወንዙም ላይ ሽው ስትል ትበር የነበረችው ጀልባችን አሁን በሞገዱ ላይ ብቅ ጥልቅ ትል ጀመረ። በከፍተኛዎቹ ማዕበሎች ላይ የምንንጠሳጠለው ልክ ጢብ ጢብ እንደሚጫወት ልጅ በቅልጥፍና ነበር። ንዝረት የለም፤ የመሰበር ድምፅ ሊሰማም፣ ብቻ ጀልባዋ በማዕበሉ ትነሣና እንደገና ትወርዳለች። አንድ ማዕበል ካለፈች በኋላ ባሕሩን ስትመታ የምታሰማው ዘጭ የሚል ድምፅ ብቻ ነበር።

«ይኸው! ይኸው፣ ተሳካልን!» አለ ከሎሲዎ ሳንባዎቹ እስኪሰነጠቁ ድረስ በመጮኽ።

በአስቸጋሪዎቹ ፈተናዎች ላይ የተጎናጸፍነውን ድል እንድናከብር ቸሩ ፈጣሪ ግሩም የፀሐይ ጮራ ፈነጠቀልን። ማዕበሎቹ ተመሳሳይ ንቅናቄአቸውን ቀጠሉ። አየራችን በሐሩን መጠን የጀልባዋ መንጠር እየቀነሰ ሔደ። ውሃው በጣም ጭቃማ ነበር። ከፊት ለፊታችን በሰሜን በኩል ባሕሩ ጠቁሯል፣ ዘግይቶም ወደ ስማያዊነት ይለወጣል። ኮምፓስ መመልከት አላስፈለገኝም። ፀሐይዋ በቀኝ ትከሻየ በኩል ነበረች። የነፋሱ ሽራውን ዘርግቸው በከፊል ስለሞላ፣ አሁን ጀልባዋ ቀና ማለቷን ቀንሳ በቀጥታ መሥመር ከነፋሱ ፊት እየሮጠች ነበር። ታላቁ አስቸጋሪ ጉዟችን በመካሔድ ላይ ይገኛል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሎሲዎ ቀና አለና ተቀመጠ። የሚካሔደው ምን እንደነበር ማየት ፈልጓል። ጀርባውን በበርሜሉ ትይዩ አድርጎ ከእኔ ፊትለፊት አንዲቀመጥ ማቹሬ ደገፈው። አንድ ሲጃራ ጠቀለለና አቃጥሎ አቀበለኝ፤ ከዚያ ሦስታችንም አጨስናት።

«ዙሪያውን ሩም ቅዳ፣ ለድላችን እንጠጣ» አለ ከሎሲዎ። ማቹሬ በሦስት የብረት ኩባያዎች ለቀቅ አድርጎ ቀዳና ለድላችን! ሰጤናችን! ተባባልን። ማቹሬ ከእኔ በግራ በኩል ተቀምጦ ስለነበር ሁላችንም እንተያያለን። ፊቶቻቸው በደስታ በርተዋል። የእኔም እንደዚያው መሆን አለበት።

«ወዴት ነው የምትጓዘው ካፕቴን?» ሲል ከሎሲዎ ጠየቀኝ።

«ሕግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን፣ ወደ ኮሎምቢያ።»

«ሕግዚአብሔርማ ረዳር ነውና ፈቃደኛ ይሆናል!» አለ ከሎሲዎ። ፀሐይዋ በፍጥነት ወጣች። ልብሳችንም ጊዜ ሳይፈጅ ደረቀ። የሆስፒታል ፒጃማችንን ወደ ዐረቦች ዐይነት ጥምጣም ቀየርናቸው። በሚረጥቡበት ወቅት ቀዝቃዛ ስለሚሆኑና ጭንቅላት ላይ ስለሚጣበቁ የፀሐዩን ሐሩር ይከላከሉልን ነበር። ባሕሩ የሚያንጸባርቅ፣ ሰማያዊ፣ ማዕበሎቹም ሰፊና ረጅም ሆነው ለጀልባ ጉዞ ይመቻሉ። ነፋሱ ኃይሉን እንደጨመረ ስለሆነ ከጠረፉ በከፍተኛ ፍጥነት ራቅን። ከአረንጓዴው ገመገም በራቅን መጠን ምሥጢርነቱ እየነላ ከእድማሱ ላይ ደበዘዘ። ዛሬ ይህንኑ ስመለከት ነበረ አንድ ማዕበል ከተፍ ብሎ ታላፊነቴን ያስገነዘበኝ።

«ትንሽ ሩዝ ልቀቅል ነው» አለ ማቹሬ።

«አንተ ብረት ድስቱን ስትይዝ፣ እኔ ምድጃውን አይዛለሁ» አለ ከሎሲዎ። የነዳጁ ደምበኛን ማንም ሰው እንዲያጨስ ከማይፈቀድበት ቦታ ተሰትሮ ነበር። ሩዙን በዘይት ሲቀቅለው ሽታው ግሩም ነበር። ከሁለት ጣሳ ሠርዲኖች ጋር አደባልቀን ትኩሱን በላነው። በዚያ ላይ ጥሩ ቡና ጨመርንበት። «አንድ አንድ ጉንጭ ሩም?» አሉ ሁለቱም። አይሆንም አልኩ። በጣም መቀት ነበር። ከሎኒዎ ለእኔ ሲጃራ መጠቅለሉንና ማቃጠሉን ቀጠለ። ከፀሐይዋ አቅጣጫ በግምት ከጧቱ አራት ሰዓት እንደሚሆን ገመትን። በባሕር ላይ የቆየነው አምስት ሰዓት ብቻ ነበር። ከሥራችን ያለው ውሃ በጣም ጥልቅ መሆኑ ያስታውቃል። ማዕበሎቹ ለጥ ያሉ ስለነበሩ የምንሰነጣጥቃቸው ያለ አንድ ድምፅ ነበር። ደስ የሚል ቀን ሆነ።

በቀን ኮምፓስ እንደማያስፈልገን ተግኑብኑ። አልፎ አልፎ ግን ከኮምፓሱ መርፌ ጋር የፀሐይዋን አቅጣጫ እያዛመድኩ በዚያ ሁኔታ እመራለሁ። ግን የፀሐይዋ ነጸብራቅ ዐይኔን ጎዳኝ። አንድ ጥቁር መነጽር ለማግኘት ባለመሞከሬ አዘንኩ።

«ሰውየ፣ ካንሁ ጋር ሆስፒታል በመገናኘቴ ዕድለኛ ነኝ» አለ ከሎሲዎ ድንገት።

«አንተ ብቻ አይደለህም። እኔም አንተን በማግኘቴ ዕድለኛ ነኝ።» ስለእነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዴጋ፣ ፈርናንዴዝ ... እስታወስኩ። እሺ ብያቸው ቢሆን ኖሮ፣ እነርሱም በዚህ ጊዜ ከእኛ ጋር እዚሁ ይሆኑ ነበር።

«እኔ ብቻ አይደለሁም» አለ ክሎሲዎ፣ «ማቹሬ ባይኖር ኖሮ በምትፈልገው ጊዜ ዐረቡን ወደ ከፍሉ ውስጥ ማምጣት ችግር ይሆንብህ ነበር።»

«አዎ፣ በእርግጥም ማቹሬ ጠቃሚ ነበርክ። ጎበዝና ብልህ ልጅ ስለሆንክ ከእኛ ጋር በመምጣትህ ደስ ብሎኛል።»

«አመሰግናለሁ» አለና ማቹሬ «ካለኝ አቋምና ከዕድሜየ አንጻር ሁለታችሁም በእኔ ላይ እምነት ሰለጣላችሁብኝ አመሰግናለሁ። አስከወዲያኛው በዚሁ ለመጽናት እሞክራለሁ» አለ።

«ፍራንሷ ሲየራም ከእኛ ጋር መሆን በቻለ ነበር። ጋልጋኒም» አልኩ።

«ነገሮች በመለዋወጣቸው፣ ይህ ሊሆን አልቻለም ፓፒዮ። ኢዮአስ ቀና ሆኖ ጥሩ ጀልባ ቢሰጠን ኖሮ ከተሸሸግንበት ቦታ ሆነን ልንጠብቃቸው በቻልን ነበር። ለማምለጡ ኢዮአስ ሊረዳቸው በቻለና ሌላውን እኛ ማድረግ በቻልን ነበር። ሌላው ቢቀር አንተን ስለሚያውቁህ፣ ያልሞከርከው አቅዶህ መሆኑን ይገነዘቡታል።»

«ጨዋታችንን ሳንለቅ፣ ከሆስፒታል ከፍተኛ ጥበቃ ከፍል እንዴት ልትገባ ቻልክ ማቹሬ?»

«ሆስፒታሉ እንዴት እንደገባሁ እኔም አላወቅኩም። ወደ ዶክተሩ የሔድኩበት ምክንያት ጉሮሮዬ ስለ ቆሰለና በተጨማሪ አካባቢውን ሰመቃኘት ነበር። ዶክተሩ ሲያየኝ፣ ካርድህ ሆስፒታል መግባት አለበት ይላል አለኝ። «ለምን? ዶክተር?። ሆስፒታል ይግባ ማለት ምን ማለት ነው?» ስል ጠየቅሁት። ግድየለም፣ ወደ ሆስፒቲል ሒድ» ተባልኩ። በዚሁ የተነሣ ሆስፒታል ውስጥ ተቀመጥኩ።»

«ውለታ አድርጎልህ ነበራ?» አለ ክሎሲዎ።

«እንደዚህ ስትል ስሜቱን ገምተህ ነው? ይህን ጊዜ ያ መልክ መልካምና የዋህ የሚመስለው ልጅ ለካስ እንደዚህ የዋዛ አልነበረም። አምልጦ ለመሔድ ወኔ ነበረው፣ በማለት ራሱን በራሱ መውቀሱ አይቀርም» ብዙ የማይረቡ ወሬዎች አወራን። «ማን ያውቃል ጁሎን እናገኘው ይሆናል። አሁንም ገና በጫካው ውስጥ ካልተሸሸገ በስተቀር በጣም ርቆ መሔድ አለበት» አልኩ።

«በምለቅበት ወቅት፣ የምገኝበትን አድራሻ አልገለጽኩም ስል ከትራሴ ሥር እንዲት ማስታወሻ አስቀምጫለሁ» አለ ክሎሲዎ። ሁላችንም በሣቅ ፈነዳን።

ለአምስት ቀናት ያለ ችግር ተጓዝን። ቀን ሲሆን አቅጣጫችንን በፀሐይ እናስተካከላለን፣ ሌሊት በኮምፓስ እንጠቀማለን። በስድስተኛው ቀን ፍንትው ያለች ፀሐይ ወጣችና ሰላምታ አቀረበችልን። ባሕሩም ድንገት በረደና በራሪ ዓሣዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

በአጠገባችን ይመላለሱ ጀመር። ደከሞኝ ነበር። በዚያ ሌሊት በአንቅልፍ እነዳልወድቅ ለመጠባበቅ የጨው ውሃ በተነከረ ጨርቅ ማቹሬ ፊቴን ያረጥብልኝ ነበረ። ግን ወዲያው እንቅልፍ ይጥለኛል። ከዚያም ከሎስዮ፣ አሁን ማዕበሉ እረጭ በማለቱ በአርግጥ መተኛት እንደምችል ነገረኝ። ባለ ሦስት ማዕዘኑን ሸራ ብቻ እንደ ተሰቀለ ትተን፣ የነፋስ ሸራውንና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራውን አወረድን። ከፀሐይ ለመከላከል ከበላይ ያለውን ሸራ ተከለልኩና ከጀልባዋ ሥር ልከ እንደ ግንድ ተጋደምሁ። ማቹሬ ነቅንቆ ቀሰቀሰኝ። «ገና ወደ ቀትር አካባቢ ነው፣ ግን የቀሰቀስኩህ ነፋሱ በመነሣት ላይ ስለሆነ ነው። ከአድማሱም በኩል ማንኛውም ነገር እየጠቆረ በመምጣት ላይ ይገኛል» አለኝ። በድግ አልኩና መሪውን ጨበጥኩ። ብቸኛው ባለ ሦስት ማዕዘን ሸራ ለጥ ባለው ባሕር በፍጥነት አስፈተለከን። ከበስተጀርባዬ በስተምሥራቅ አቅጣጫ ሰማዩ ጠቁሮ ነበር፣ የነፋሱም ኃይል እየጨመረ ሔደ። ፍጥነት ለመጠበቅ ያህል ሁለቱ የነፋስ ማስተካከያዎች በቂ ናቸው። የነፋስ ሸራውን በምሰሶው ዙሪያ ጠቀለልኩ።

ሕጥበቃችሁ ያዙ። ሞገድ እየመጣ ነው።»

ትላልቅ የነፋስም ነጠብጣቦች መውረድ ጀመሩ። አንድ አስቀያሚ ቁልል ደመና ወደ እኛ አቅጣ ያስገመግም ነበር። ዐሥራ አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ እኛ ዘንድ ደረሰ። ቁጠኛ ነፋስ ገፈተረን። አንዳች ልከፍት የያዛቸው ይመስል ማዕበሎቹም አረፋቸውን ይደፍቁ ጀመር። አንድም ነገር ማየት አለቻልንም። ዶፍ ይጥላል፣ ፀሐይዋም ተሰወረች። ማዕበሉ ጀልባዋን ሲመታት የሚቆጠቁጠው የውሃ ዐረፋ እየተፈናጠረ ፊቴን እኮማተረው። ነጎድጓዱን፣ መብረቁን፣ ዝናውን፣ ማዕበሎቹንና በአካባቢያችን የሚወርደውን ነፋስ፣ ተፈጥሮ ባላት ኃይል ሁሉንም ፈትታ የለቀቀችበን ሞገድ ነበር። አውነተኛው ዓውሎ ነፋስ ነበር የተነሣው። ልከ አንድ ቁራጭ ላባ መስላ ጀልባዋ ከከፍተኛ ቦታ ጥልቅ ወደ ሆነ አዘቅት፣ ከጥልቁም የተነሣ ፍጹም ተመልሰን እንወጣለን ብየ ወደማላስብበት ታሽቆለቁላለች። ያም ሆኖ ከሚያስገርመው ማሽቆልቆል ውስጥ በእያነዳንዱ አዲስ የማዕበል ጫፍ ተመልሰን ወደ ሶይ እንንናለን። መሪውን በሁሉም አጆቼ ጨመደድኩና ሊሰብራት የተቃረበውን ትልቅ የማዕበል አብጠት መቋቋም መቻል አለብኝ በማለት በላዩ ላይ ሰንጥቄ ለማለፍ ጀልባዋን አዘጋጀኋት። ምናልባት በጣም በፍጥነት መሪውን በማዞር ይሆናል፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ወደ ጀልባዋ ውስጥ ገባና በውሃ ተጥለቀለቀች። ሠላሳ ኢንች ያህል ዐኗ ታች ሳንሰምጥ አንቀርም። ትዕግሥቴ አለቀና ምን እነደማደርግ ሳላውቅ የሚቀጥለውንም ማዕበል በጎን በኩል ለማለፍ ራሴን ለጥፋት ጋበዝኩ። ያም ሆነና ጀልባዋ በጎኗ እንደ መተኛት ብላ ማዕበሉን ለታልፍ ገብቶ የነበረው ብዛት ያለው ውሃ ፈሰሰ።

«ሳበዝ» አለና ከሎሲዎ፣ «ብትከከል ገመዶቹን ማዘዝ ይውቅህበታል ፓፒዮ!

t.me/OLDBOOKSPDF

ጀልባዋን ባዶ ለማድረግ በአቋራጭ ዘዴ ተጠቀምክ» አለ።

«እትጠራጠር» ብየ መለስኩለት። ግን በእኔ ልምድ ማጣት የተነሣ ልንበምጥ ተቃርበን እንደነበር ተረድቶ ይሆን!» የሚል ሃሳብ ጫረብኝ።

ከማዕበሎቹ ጋር መታገሌን ወይም አቅጣጫ ማስተካከሌን ለማቆም ወሰንኩ። ጀልባዋ በተቻለ መጠን ረጋ እንድትል በማድረጉ ላይ አተኮርኩ። ማዕበሎቹን ወደ ጎን በማሳለፍ ቁልቁል እየወረደች ወደላይ እንድትወጣ አደረግኋት። ከአንድ ጠቃሚ ግኝት መድረሴንና አደጋውም ከሙቶ ዘጠና አጅ መቃለሉን ወዲያውኑ ተገነዘብኩ።

ምንም እንኳ ነፋሱ እንደ ቀጠለ ቢሆንም፣ ገናና ስላቆመ አሁን ወደፊትና ወደ ኋላ በግልጽ ለማየት ችያለሁ። ከኋላችን ፈካ ብሎ ከፊታችን ደግሞ የጠቆረ፣ ሁለት ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ የአየር ጠባይ መካከል ነበር ያለነው።

በዐሥራ አንድ ሰዓት ሁሉም ነገር አለፈ። ማዕበሉም በረደ፣ ነፋሱም እንደ ተለመደው ረጋ፣ ፀሐይዋም እንደገና ወጣች። ሸራውን ሰቀልኩና በዕድላችን በጣም እየተደሰትን እንደገና ጉዟ ጀመርን። ጀልባው ውስጥ ቀርቶ የነበረውን ውሃ በባረት ድስታችን እየቀዳን አፈሰስነው። ብርድ ልብሶቻችንንም ምሰሶው ላይ ሰቅልንና ነፋሱ ወዲያውኑ አደረቃቸው። ከዚያም የሩዝና የዱቄት ምሳ በዘይት አዘጋጀን። በወፍራም ቡናና በእንዳንድ ደህና ጉንጭ ሩም አሳረግን። ፀሐይዋ ለመጥለቅ ተቃርባ በሰማያዊው ባሕር ላይ እሳት የመሰለ ብርሃኗን ረጨችበት። በጣም ያምር ነበር፡- የቀይ ቡናማው ሰማይ፣ ስከፊል ወደ ባሕሩ ጠልቃ በትልቁ ቢጫ ምላሷ ሰማዩን የምትልስ የምትመስለው ፀሐይ፣ መጠነኛዎቹ ነጫጭ ደመናዎችና ራሱ ባሕሩ ውብ ትርዒቶች ነበሩ። ማዕበሎቹ ከሥር በኩል ሰማያዊ ቢሆኑም እንደሚያርፋብቸው የፀሐይ ጨረሮች አረፋዎቻቸው አረንጓዴና ቀይ፣ ሐምራዊ ወይም ቢጫ ይሆናሉ።

አንድ የማይናቅ ሰላም ተሰማኝ። ከዚህም ሰላም ጋር በራስ መተማመን አደረብኝ። ሁኔታዎችን በሚገባ ለመቆጣጠር ቻልኩ። የአጭሩ ጊዜ ሞገድ ብዙ አስተምሮኛል። ኃይለኛ ባሕር ውስጥ እንዴት መገለባበጥ እንደሚቻል በገዛ ራሴው ለምጃለሁ። ሌሊቱንም በጸጋ እንኳን ደህና መጣህ ለማለት ችያለሁ።

«ታዲያስ፣ ከሎሲዎ፣ ከጀልባዋ ውሃ ያፈሰስኩበትን ዘዴ ወደደከው?»

«ጓደኛዬ፣ ይህን ባታደርግና ኑናችንን አንድ አዲስ ማዕበል ቢመታን ኖሮ አልቆልን ነበር። ሻምፒዎን ነህ።»

«ይህን የተማርከው ባሕር ኃይል ውስጥ ነበር?» አለ ማቹሬ።

«አዎ፣ ሌላው ቢቀር ለአንዳንድ ነገሮች ባሕር ኃይል ጥሩ ነው» አልኩት። መለመራችንን አሳስተን ርቀን መሆን አለብን። በዚያ ነፋስና እነዚያ ማዕበሎች ውስጥ ከአራት ሰዓት ቆይታ በኋላ ይህ ቢፈጸም የሚያስደንቅ ነገር አይሆንም። ወደ ሰሜን

t.me/OLDBOOKSPDF

ምዕራብ ለመሐድ መሪውን ማስተካከል ነበረብኝ። ለመስነባበቻ ያህል ፀሐይዋ ሐምራዊ ጨረሯን ለመጨረሻ ጊዜ ፈንጥቃ ስትጠልቅ፣ ጨለማው ወረረን።

ያለምንም ችግር ሌላ ተጨማሪ ስድስት ቀኖች ተጓዝን። በአንዳንድ አነስተኛ የነፋስ ግፊትና ዝናም ከሦስት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ ከመነብነታችን በስተቀር ከመጀመሪያው ሞገድ ደረጃ የሚመጣጠን ፈተና ፊጽሞ አላጋጠመንም።

አሁን ከጧቱ አራት ሰዓት ነበር። አንድም የነፋስ ሽውታ የለም። ባሕሩ መስታወት መስሏል። አራት ሰዓት ያህል ተኛሁ። በምነቃበት ጊዜ ፊቴ እየተሰበሰበ ነበር። ከከንፈሮቼና ከአፍንጫየ ቆዳዬ ተነሥቷል። የቀኝ እጄም ተገሸልጧል። የማቹሬና የከሎሲዎም እንደዚሁ ሆኖ ነበር። ፊቶቻችንንና እጆቻችንን በቀን ሁለት ጊዜ ዘይት እንቀባቸዋለን፣ ግን ይህ በቂ አልሆነም። የምድር ወጥ ፀሐይ ወዲያውኑ ታደርቀዋለች።

ከፀሐይዋ አቅጣጫ እንደ ተረዳሁት፣ አሁን ከሰዓት በኋላ ስምንት ሰዓት ነበር። ምግብ ብጤ ቀማመስኩና ከዚያም ባሕሩ ረጋ ባለበት ወቅት ጥላ እንዲሆነን በማለት የነፋስ ሸራውን አስተካከልን። ማቹሬ ሣህኖቹን ያጥበበት ከነበረው አካባቢ ዓሣዎች ተሰበሰቡ። ገጀራችንን እነሣሁና ትንሽ የሩዝ ፍሬዎች እንዲበትንላቸው ለማቹሬ ነገርኩት። ሩዙ በሞገድ ወቅት ረጥቦ ስለነበር በቆልት መሆን ጀምሯል። ሩዙ በተበተነበት አካባቢ ዓሣዎች ተሰበሰቡና ከእነርሱ አንደኛው ሚንቅላቱን ከውሃው በላይ ሲያወጣ ደህና አድርጌ በገጀራው ቀላሁት። ወዲያው ሆዱን በአየር ሳይ ገለበጠ። ያ ዓሣ ሐያ አምስት ፓውንድ መመዘን አለበት። በጨው ውሃ አጥበን ቀቅልንና ከታፒዋካ ዱቄት ጋር በዚያኑ ምሽት በላነው።

አሁን በባሕር ላይ ፀሥራ አንድ ቀን ሆኖን ነበረ። በጠቅላላው በዚህ ጊዜ ውስጥ አንድ ጀልባ ብቻ ከአድማሱ በጣም ራቅ ብሎ አይተናል። የትኛው ቦታ እንሆን አያልኩ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። በዓለም አቀፍ ባሕሮች ላይ መሆናችን ግልጽ ነበር። ግን ከትሪኒዳድ ወይም ከሌሎቹ የእንግሊዝ ደሴቶች ጋር ያለን መቀራረብ የቱን ያህል ይሆን? ያንንስ የሰይጣን ጀሮ አይሰማው በቀጥታ ከፊት ለፊታችን እያደር እያደገ የሚሔድ አንድ ጥቁር ነጥብ ነበር። ትልቅ መርከብ ይሆን ወይስ አነስተኛ ጀልባ? ጀልባ ነበር፣ ግን የሚመጣው ወደ እኛ አቅጣጫ አልነበረም። ከእኛ መስመር ባሻገር ሲንቀሳቀስ አሁን ግልጽ ሆኖ ማየት ቻልን። ሆኖም እየቀረበ መጣ፣ ግን በማዕዘን በኩል ነበር። የጉዞ መስመሩ ሊያቀርበው አይችልም። ነፋስ ካለመኖሩና የነፋስ ሸራዎቹም ስለተመለሱ የሚያዩን አይመስልም። ከዚያ ድንገት አንድ የጡሩምባ ድምፅ ተምባረቀና ሌሎች ሦስት ያህሞ ተከታተሉ። ጀልባው መስመሩን አሳብሮ በቀጥታ ወደ እኛ ገሠገሠ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አስካልተጋጨን ድረስ» አለ ከሎሲዎ።

«አደጋ አይኖርም። ባሕሩ እንደ መስታወት የለሰለሰ ነው።»

አንድ ነዳጅ ጫኝ መርከብ ነበር። እየቀረበ ሲመጣ በመተላለፊያው ላይ የተሰበሰቡትን ሰዎች ማየት ቻልን።በዚህች ያወቅ ጎጆዋቸው ውስጥ ሆነው እነዚህ ሦስት ዕበዶች በውቅያኖስ መካከል ምን እያደረጉ ይሆን ብለው መገረም አለባቸው። በጥንቃቄ እየቀረቡን ሲመጡ፣ የመርከቡን መኮንኖች፣ አንዳንድ የመርከቡን ሠራተኞች፣ ዝጉርጉር ቀሚስ የለበሱ ሴቶችንና ባለቀለም ሸሚዝ የለበሱ ወንዶችን ወደ መተላለፊያው ሲሰባሰቡ ለማየት ቻልን። በግልጽ እንደሚታየው መንገደኞች ናቸው። በዘይት ጫኝ መርከብ ላይ መንገደኞች ማየት ያልተለመደ ነገር ይመስላል። አሁን መርከቡ በጣም ቀርቦ ስለነበር ካፕቴኑ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተጣራ።

«ከወዴት ናችሁ?»

«ፈረንሣይ ጊያና»

«ፈረንሣይኛ ትናገራላችሁ?» አሉት እንዴት ሴት።

«አዎ አመቤቴ።»

«ምን እያደረጋችሁ ነው?»

«አግዚአብሔር ይወቅ . . .»

ሴትየዋ ከካፒቴኑ ጋር ተነጋገሪችና እንደዚህ አሉት። «ካፒቴኑ ወደ መርከቡ መጥታችሁ እንድትሣፈሩ ይጋብዛችኋል። ጀልባችሁንም ወደ ወለሉ ላይ ስቦ ያወጣላችኋል።»

«አናመሰግናለን ብለሽ ንገሪው፣ ግን በጣም ተመችቶናል።»

«ሕርዳታ አትፈልጉምን?»

«ያመለጥን አሥረኞች ስለሆንን፣ በእናንተ አቅጣጫ እንሔድም።»

«ወዴት ነው የምትሔዱት?»

«ማርቲኒክና ከዚያ ባሻገር። የት እንዳለን አላወቅነውም። ወደ አንቲይ ደሴቶች የሚወስደን የትኛው አቅጣጫ እንደሆነ ልትነግሩን ትችላላችሁ?

«የእንግሊዝኛ የባሕር መስመር ካርታ ማንበብ ትችላለህ?»

«አዎ።»

ከትንሽ ጊዜ በኋላ አንድ የእንግሊዝኛ ካርታ፣ አንድ ካርቶን ሲጃራ፣ ዳቦና አንድ የበግ አሮስቶ ሰደዱልን።

«ካርታውን ተመልከተው» ካርታውን ተመለከትኩና ከዚያም፣ «ወደ እንግሊዝ አንቲይስ ለመጓዝ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አንድ ሩብ መዞር ይኖርብኛል። ልክ ነው?» አልኩ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ።»

«ምን ያህል ማይል ይሆናል?»

«በሁለት ቀን ውስጥ መድረስ ትችላለህ» አለ ካፒቴኑ።

«ለማንኛውም እናመሰግናለን፣ ደህና ሁኑ።»

«ስለባሕር ተጓዥነት ወኔያችሁ ካፒቴኑ እንኳን ደስ አላችሁ ይላችኋል»

«በድጋሚ እናመሰግናችኋለን። ደህና ሁኑ» ከዚያም መርከቡ ሊታከክን ተቃርቦ በዝግታ አሰፈን። እንዳይገለብጠን በማለት የቻልኩትን ያህል ለመራቅ ጠመዘዝኩ። ልክ በዚያ ወቅት አንድ መርከበኛ ከወለሉ ላይ ሆኖ መለዮውን ሲወረውራት በቀጥታ በጀልባዋ መካከል ወደቀች። ከሁለት ቀን በኋላ ትሪንዳድ ስንደርስ ይህችን በወርቅ የተጠለፈችና መልሕቅ ያላት መለዮ ደፍቼ ነበር።

ትሪንዳድ

ጠረፏን ለማየት ከመቻላችን በጣም ቀደም ብሎ መሬት መድረሳችንን አንድ የአሞራዎች በረራ አበሠረን። በላያችን እያንጎበጎበ ሲመጣ ከጪቱ አንድ ሰዓት ተኩል ይሆን ነበር። « ተሳክቶልናል! ተሳክቶልናል ጓደኞቼ! የመጀመሪያው የማምለጥ ምዕራፍ ማከተሙ ነው። ያውም ከባዱ ክፍል። ረጅም ዕድሜ ለ!ዊ!ታችን!» ኪደስታችን ብዛት እንደ ሕፃናቶች ሆንን። ዐሐይ ያቃጠለው ፊታችንን ለማለሰለስ የመርከቡ ሰዎች ሰጥተውን የነበረውን የኮኮሰ ቅባት ለደፍነው። ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ መሬት አየን። በእርጋታ በሚንከባለለው ባሕር የሚጓዘው ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ ወደዚያው አቅጣጫ በፍጥነት አሰጠጋን። ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት ላይ ነበር ወደ መሬት በመጠጋታችን የአገሩን አቀማመጥ አስተካከለን ለማየት የቻልነው። በረጅሙ ደሴት ባሕር ጠርዝ ላይ በመቀራረብ ተደርድረው የሚታዩት ኮሚጭ ቤቶችና የኮከናት ዛፎች ቁንጮዎች ለጠረፉ ጉልላት ሆነውታል። አቤቶቹ ውስጥ ሰው ይኑርባቸው አይኑርባቸው ወይም ሥፍራዋ በትክክል ደሴት ትሁን ወይም ልሣነ ምድር ገና መለየት አልቻልንም። እኛ ወደምናመራበት የባሕር ዳር አቅጣጫ የሚሯሯጡትን ሰዎች ከመለየታችን በፊት ሌላ አንድ ሰዓት ሆነ። ሐያ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሕዝብ ተሰበሰበ። የትንሿ መንደር ነዋሪ ሁሉ እኛን ለመቀበል ወደ ባሕሩ ዳር ግልብጥ ብሎ ወጣ። በኋላ አንደ ተረዳነው የቦታዋ ስም ሳንፈርናንዶ ነው።

ከባሕሩ ዳር ሦስት መቶ ያርድ ርቀት ላይ መልህቅ ጥዬ ወዲያው ቀነጠልኝ። ይህን ያደረግኩት በአንድ በኩል የሰዎቹን እዝማሚያ ለመመልከት በሌላ በኩል የባሕሩ ወለል ኮራል ከሆነ ጀልባዋን ለአደጋ ከማጋለጥ ለማዳን ስል ነበር። የነፋስ ሽራዎቹን አወረድንና ጠበቅን። አንዲት ትንሽ ጀልባ ወደ እኛ አቅጣጫ መጣች።

t.me/OLDBOOKSPDF

በውስጧ ሁለት የሚቀዝፉ ጥቁሮችና የቅኝ ግዛት መለያ ያደረገ አንድ ነጭ ነበር።

« ወደ ትሪኒዳድ እንኳን ደህና መጣችሁ» አለ ነጩ ጥርት ባለ ፈረንሣይኛ።

« እመለማናለሁ ጌታዬ እዚህ ከባሕሩ ሥር ኮራል ነው ወይስ አሸዋ?»

« አሸዋ ነው። ያለምንም አደጋ እስከ ባሕሩ ዳር ድረስ መሔድ ትችላላችሁ።»

መልህቁን ወደ ላይ ሳብንና ማዕበሎቹን በዝግታ ወደ ዳር ገፋን። ዐሥር ሰዎች ወደ ውሃው ውስጥ እየተሯሯጡ ጀልባዋን በአንድ ግፊት ወደ መሬት ያወጧት ገና አፈር ላንነካ ነበር። መላው ሁኔታችንን ተመለከቱ፣ ተንከባከቡን፣ ጥቁር ሴቶች፣ ቻይናውያንና ሕንዶች የአክብሮት አቀባበል አደረጉልን። ከእነርሱ ጋር አንድንቆይ ማንኛውም ሰው መፈለጉን ነጩ ገለጸለን። ማቹሬ በእፍኙ ሙሉ አሸዋውን ዘገነና እንደ መሳም አለ። ይህም ተመልካቾቻችንን አስደነቀ። ስለ ክሎሲዎ ሁኔታ ለነጩ ሰው ገለጽኩለትና በባሕሩ ዳር ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ አሸከሞ አስወሰደው። እሰኪነጋ ማንኛውንም ነገር ጀልባዋ ውስጥ መተው እንደምንችልና ማንም ሰው ምንም ነገር እንደማይነካ ገለጸልን። ሁሉም ሰው፣ «ካፒቴን» እያለ ስለ ጠራኝ ይህ አዲስ የወጣልኝ የክርስትና ስም አሣቀኝ። በእንግሊዝኛም ቋንቋ በትንሽ ጀልባ ረጅም ጉዞ ያደረገን ሰው፣ «ጎበዝ ካፒቴን?» ይላሉ።

ምሽት መጣ። ለጥበቃ ያህል ጀልባችንን ትንሽ ራቅ አድርገን በመግፋት ከአንድ ከፍ ካለ ጀልባ ጋር ማቆራኘት ይቻል እንደሆነ ጠየኩ። ከዚያም እንግሊዛዊውን ተከተልኩና ወደ ቤቱ አመራሁ። ትንሽ ደረጃዎችና ባለወንፊት መዝጊያ ያለው በእንግሊዝ ሀገር በየቦታው የሚታዩትን ቪላዎች ይመስላል። ማቹሬ ከእኔ ኋላ፣ እኔ እንግሊዛዊውን ተከትየ ገባን። ወደ ውስጥ እንደገባሁ፣ ከሎሲዎ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ተቀምጦ እግሮቹን አንፈራጦ ሁለት ሴቶች እያሟሟቁ ይንከባከቡት እንደነበረ አየሁ።

እንግሊዛዊው፣ «ሚስቴና ልጄ» አለና አስተዋወቀን። «እንግሊዝ ሀገር በትምህርት ላይ የሚገኝ አንድ ወንድ ልጅም አለኝ።»

«ወደ ቤታችን እንኳን ደህና መጣችሁ» አለች ሚስቱ በፈረንሣይኛ።

«እባካችሁ ተቀመጡ» አሉች ልጅቱ ሁለት ከቀርከሃ የተሠሩ ወንበሮች እያቀረበች።

«እናመሰግናለን፣ እባካችሁ ለእኛ ብላችሁ አትቸገሩ።»

«ለምን? ከየት እንደመጣችሁ ስለምናውቅ አትሥጉ፣ እደግመዋለሁ፣ ወደ ቤታችን እንኳን ደኅና መጣችሁ።»

ሰውየው ጠበቃ ሲሆን፣ ስሙ ቦውን ይባላል። መሥሪያ ቤቱ በግምት ሐያ አምስት ማይል ከምትርቅ ፖርት ኦፍ ስፔይን ከተባለች የትሪኒዳድ ዋና ከተማ ውስጥ ነበር። በሻይ፣ በወተት፣ በኬክ፣ በቅቤና በማርማላታ አስተናገዱን። እንደ ነገ ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

የሆንባት የመጀመሪያዋ ምሽት ስለነበረች ፈጽሞ አልረሳትም። ገዛው እንዴት እንዳለፈና ስንት ቀን እንደ ፈጀብን፣ እዚህ መድረሳችንን ለፖሊስ የምናሳውቅ ነገ ይሁን ወይስ በሌላ ቀን፣ ክሎሲዎ ሥቃይ የሚሰማው እንደሆነ፣ ደብዳቤ የምንጽፍላቸው ቤተሰቦች፣ ሚስቶች ወይም ልጆች እንዳሉን ብቻ ካለሆነ በቀር፣ ሌላ ዓይነት ወይም ስላለፈው ታሪካችን አንድም ጥያቄ አላቀረበልንም። ልንጽፍላቸው ከፈለግን ደብዳቤዎቹን እነርሱ እንደሚልኩልን ገለጹልን። እንዴት አድርጌ ልናገረው። እነዚህ እንግሊዛውያን ቤተሰቦችና ከሕሩ ጠረፍ ያጋጠሙን ሰዎች፣ ሁሉም እንደኛ ላሉ ለሦስት ተባራሪዎች ያደረጉልን መስተንግዶ ልዩ ነበር። ሚስተር ቦውን ወደ አንድ ዶክተር ስልክ ደወለና በሚቀጥለው ቀን ክሎሲዎን ወደ ከሊኒኩ አምጥቶ ራጅ እንደሚያስነሣውና ምን እንደሚያስፈልገው እንዲመረምረው ነገረው። ከዚያም ሚስተር ቦውን ፖርት ኦፍ ስፔይን ወደሚገኘው የወታደራዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ኃላፊ ወደ ነበረው ካፒቴን ስልክ ደወለ። ካፒቴኑም በበጎ አድራጎት የአንሣዶች ማረፊያ አንድ ከፍል እንደሚያዘጋጁና በሚያስፈልገን ጊዜ ጠምጣት እንደምንችል፣ ጀልባችንም ጥሩ ከሆነች ለመሐድ ስንዘጋጅ ስለምታስፈልገን ማሽቀመጥ እንዳለብን ገለጸለት። ከባድ ወንጀለኞች ወይም ልማደኛ ሌቦች መሆናችንን ጠየቀንና ከባድ ወንጀለኞች መሆናችንን ሰንመልስለት ጠበቃው ደስ ያሰው መሰለን።

«ገላህን መታጠብና ጺምህን መላጨት ትፈልጋለህ?» ስትል ልጃገረዷ ጠየቀችኝና፣ «ሕባክህ አምቢ እንዳትል፣ ምንም ችግር የለውም። ቁታጠቢያ ቤቱ ውስጥ የሚያስፈልጉህን ማናቸውንም ነገሮች እንደምታገኝ ተስፋ አደርጋለሠ» አለች።

ወደ መታጠቢያ ቤት ገባሁና ገላየን ታጥቤ ጺሜን ከተላጨሁ በኋላ የቴኒስ ጫማ፣ ነጭ ካልሲ፣ ነጭ ሽሚዝና ቡላ ሱሪ ለብሼ ብቅ አልኩ።

አንድ የሕንድ ዜጋ መዝገያ ቆረቆረ። ለማቹሬ አንድ የሆነ ጥቅል አምጥቶ ነበር። ዶክተሩ የእርሱም መጠን በእኔ ልክ ይሆናል ብሎ በመገመት ሊሆን ይችላል ልብስ ልኮለት ነበረ። ግን ትሳሳው ማቹሬ እንዳይለብሰው ችግር ሆነበት። ምክንያቱም ጠበቃው ቤት ውስጥ ካለነው ከሦስታችን አንደ አርሱ ቀጫጫ አልነበረም። ሰውዬው ሕንዶች እንደሚያደርጉት እጅ ነሣና ሐደ። እንደዚህ የመሰለ ርኅራኄ ሲገጥመን ምን ለማለት እንችላለን? በልቤ ውስጥ የታመቀውን ስሜት ለመግለጽ አልቸልም። ክሎሲዎ ቀደም ብሎ ተኛ። ከዚያም የቀረነው አምስታችን በለዩ ልዩ ርዕሶች ላይ ብዙ ሐሳቦች ተለዋወጥን። እነኛን የደስ ደስ ያላቸውን ሁለት ወይዛዝርት ያስገረመው ኑሯችንን እንደገና ለማታገት እንዴት እንዳቀድን እየነገርናቸው ነው። የወደፊቱንና የወትቱን ብቻ ካለሆነ ስላለፈው ምንም ወሬ አልተነሣም። ትሪኒዳድ ያመለጡ እስረኞችን ለማቆየት ባለመጥቀዷ ሚስተር ቦውን አዘነ። እንዳፈቀድልን ቀደም ሲል ጠይቆ እንደነበርና ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍጹም እንዳልቻለ ነገረን። ልጅቷ ልከ እንደ አባቷ በጣም የተጣራ ፈረንሣይኛ ትናገራለች። ስትናገርም ሊቋን ያገ አያደርገውም ነበር። ዕድሜዋ በዐሥራ ሰባትና በሐያ መካከል ሆኖ ፊቷ በብጉር የተሸፈነ ጸጉረ ወርቃማ ወጣት ነበረች።

«ገና ወጣት ስለሆንክ ዕድልህ ወደፊት ነው። ለመታሠር የበቃኸው ምን አድርገህ እንደሆነ አላውቅም፣ ለማወቅም አልፈልግም። ግን በዚህች አነስተኛ ጀልባ ባሕር ለማቋረጥ ያለህ ቆራጥነትና ይሆን የመሰለ ረጅምና አደገኛ ጉዞ ማድረግህ፣ ነፃ ለመውጣት ከፍተኛ ወኔ እንዳለህ ያሳያል። ይህም እንደማስበው ከሆነ ዕውቦ ድንቅ የሚያሰኝ ነው» አለችኝ።

በሚቀጥለው ጧት እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ተኛን። ገበታው ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶአል። ሚስተር ቦውን ወደ ፖርት ኦፍ ስፔይን መሔዱንና የእኛን የወደፊት ዕድል በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ እስኪሰበስብ ድረስ እስከ ሰዓት በኋላ እንደማይመለስ ወይዘሪቱ ነገሩን።

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ሰው ሦስት ያመሰጡ ወንጀለኞች እቤቱ ትቶ ወደ ውጭ ሊሔድ መቻሉ ለእኛ ትልቅ ዋጋ ያለው ትምህርት ነበር። «እንደ ማንኛውም ትከከለኛ ሰው ተመልከቻችኋለሁ። ከተዋወቅን ዐሥራ ሁለት ሰዓቶች ብቻ ቢያልፉም፣ ከልጄና ከባለቤቴ ጋር እቤት እንድተዋችሁ በቂ እምነት አድሮብኛል። ከዚህ በኋላ በቤቴ ውስጥ መጥፎ ምግባር ለመፈጸም ትችላላችሁ ብዬ አላምንም። ስለሆነም ልከ እንደ ቀድሞ ጓደኞቼ እዚሁ ትቻችኋለሁ» የሚል ይመስላል። ይህ ዕምነቱ በከፍተኛ ደረጃ ስሜታችንን ነካው።

ገና አዲስ ሕይወት ባልጀምርም ወደዚያው እያዘገምኩ ነበር። አዲስ ክብር መላበሴ፣ ንፁሕ ሆኜ መቆጠሬ፣ ተዘፍቄበት ከነበረው ቆሻሻ በአንድ ሌሊት የተላቀቅሁ አንድ ልዩ ሰው ስለመሆኔ ማረጋገጫ ሆነኝ። በእግር ብረቶች ማቃጨል የበታችነት ስሜት የሚያድርበት አሥረኛ፣ ነፃ ሆኖ እንኳ በዐይነ ቁራኛ እጠበቃለሁ ብሎ የሚከበው ጭጋግ፣ ያየሁት ያለፍኩበት፣ የተሠቃየሁበትና ማንኛውም አኔነቴን የበከለው፣ ያበሰበሰኝና አደገኛ ያደረገኝ፣ ላይ ላዩን ታዛዥ ብመስልም በውስጤ የታመቀው አሥጊው አደገኛነቴ ሁሉ በተአምር እልም ብሎ ጠፋ። በጥብቅ የሚያገለግለውን አቶ ቦውን፣ አመሰግነዋለሁ። በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ አንድ አዲስ ሰዉ ስላደረገኝ አመሰግነዋለሁ።

ዐይናቿ ልከ በአካባቢያችን እንዳለው ባሕር ሰማያዊ የሆኑት ባለወርቃማ ጸጉር ኮረዳ፣ አባቷ ቤት ሳን ከሚገኘው የከከነት ዘንባባ ሥር አብራኝ ተቀምጣ ነበረ። ቀይ ፣ ቢጫና ሐመራዊ የሆኑት በወቅታቸው የፈኩ አበቦች፣ የአትክልት ቦታውን የማራኪ ሥነ ግጥም ማመንጫ አድርገውት ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሚስተር ሐንሪ» ብላ ጠራችኝ! አንድ ሰው ሚስተር ብሎ ከጠራኝ ምን ያህል ረጅም ጊዜ ሆኖኝ ነበር! «ትሳንት ኤባባ እንደ ነገረህ በእንግሊዛውያን ባለሥልጣኖች ይደብትና የማይረባ አመለካከት፣ ያሳዝነናል፣ እናንተ እዚህ ለመቆየት አልቻላችሁም። ለማረፍ ያህል ብቻ ሁለት ሳምንት ይሰጣችሁና ከዚያም እንደገና ወደ ባሕር መሐድ ሊኖርባችሁ ነው። ጀልባችሁን እንዳየኋት ከፊታችሁ ለሚጠብቃችሁ ረጅም ጉዞ በጣም ትንሽና በጣም ቀላል እንደሆነች ለመገንዘብ በቅቻለሁ። ከእኛ ይበልጥ እንግዳ ተቀባዮችና ተግባቢዎች ወደሚገኙበት አገር እንድትደርሱ እመኛለን። ሁሉም የእንግሊዝ ደሴቶች ከዚህችኛዋ ደሴት ተመሳሳይ ናቸው። የምለምናችሁ፣ የሚቀጥለው ጉዟችሁ አንድ ሥቃይ ቢያስከፍላችሁ፣ በእነዚህ ደሴቶች ሕዝቦች ላይ ቅሬታ እንዳትይዙባቸው ነው። ኃላፊዎቹ አነርሱ አይደሉም። ትእዛዙ የሚመጣው ከእንግሊዝ አገር ነው፣ እናንተን ከማያውቋችሁ ሰዎች ነው። የአባቴ አድራሻ 101 ኩዊን ስትሪት፣ ፖርት አፍ ስፔይን፣ ትሪኒዳድ ነውና እባካችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ትንሽ ቃላት ጻፉልንና ስለ ደህንነታችሁ እንወቅ።»

እንደገና ስሜቱ ተነካና ምን እንደምናገር ተደናገረች። ማዳም ቦውንም ወደ እኛ መጣች። አረንጓዴ ዐይኖችና ቡና ቀለም ጸጉር ያላት፣ ዐርባ ዓመት አካባቢ የሚሆናት በጣም ውብ ሴት ነበረች። ፈካ ያለ አረንጓዴ ነጠላ ጫማ አድርጋ፣ ሳሳ ባለው ነጭ ቀሚሷ ላይ አንድ ነጭ መታጠቂያ ሸብ አድርጋ ነበር።

«ባለቤቴ እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት አይመለስም። ያለ አንድ አጃቢ ፖሊስ ወደ ቁና ከተማዋ እንድትሔዱ ፈቃድ ሊያወጣላችሁ እየሞከረ ነው። በተጨማሪ የመጀመሪያ ሌሊታችሁን በፖርት አፍ ስፔን ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንዳታሳልፉ ለመከላከል ይፈልጋል። ቅልጥሙን የተሰበረው ጓደኛችሁ የእኛ ወዳጅ ወደሆነ አንድ ዶክተር ከሊኒክ በቁጥታ ይሔዳል። እናንተ ሁለታችሁ ደግሞ ወደ በጎ አድራጎት የእንግዶች ማረፊያ ልትሔዱ ነው።»

አትከልቱ ቦታ ማቹሬም ተቀላቀለን። ጀልባዋን ለመመልከት ሔዶ እንደነበርና በሚያደንቋት የመንደሩ ኗሪዎች የመከበቧንም ዜና ጨምሮ ነገረን። ምንም የተነካ ነገር አልነበረም። ግን በሚያተኩሩበት ወቅት ኗሪዎቹ ከመሪው ሥር አንዲት ጥይት አይተው ኖሮ፣ ከአነርሱ ውስጥ አንደኛው መታሰቢያ ሊያደርጋት መውሰድ ይችል እንደሆነ ጠይቆ፣ ማቹሬ፣ «ካፒቴን፣ ካፒቴን» ብሎት ነበር። ማቹሬ የካፒቴኑን ፈቃድ መጠየቅ ይኖርብኛል ማለቱ እንደነበረ ኗሪዎቹ ጉበታቸዋል። በተጨማሪ ኤሊዎቹን ለምን እንደማንለቅቃቸው ጠይቀውታል።

«ኤሊዎች አሏችሁ እንዴ?» ብላ ልሻገረዷ ጠየቀችኝና፣ «አስኪ ሔደን እንያቸው!» አለች።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ጀልባዋ ሔድን። በመንገድ ላይ እንዳለን በዓለም ላይ ሁሉ የተለመደ ነገር ይመስል አንዲት ሕፃን ሕንጻዊ ልጃገረድ እጇን ልትጨብጥ አቅሙችኝና በእንግሊዝኛ፣ «እንደምን ዋላችሁ» አለች። በጠቅላላው የተሰበሰበው መንደርተኛም «እንደምን ዋላችሁ» አለ። ሁለቱን ኤሊዎች አወጣሁና፣ «ምን እናድርጋቸው? ወደ ባሕሩ መልሰን እንልቀቃቸው ወይስ በአትክልትሽ ቦታ ልታሰቀምጪያቸው ትፈልጊያለሽ?» አልኳት ልጃገረዷን።

«ከቤታችን ጀርባ አንዲት ትንሽ ኩሬ አለች። ስለዚህ እዚያ ኩሬ ውስጥ እንከተታቸውና ለእናንተ ጉብኝት መታሰቢያ ይሁኑን» አለች።

«መልካም፣ እንግዲያው የምናደርገው ይህንኑ ነው።» ኮምፓሱን፣ ትንሽ ትንባሆ፣ የውሃውን በርሜል፣ ጩቤዬን፣ ገጀራውን፣ ቆንጨራውን፣ ብርድ ልብሱንና ቶሎ ብዬ በብርድ ልብስ ውስጥ የደበቅኩትንና ማንም ሰው ያላየውን ሽጉጤን ብቻ በማስቀረት ማንኛውንም ጀልባዋ ውስጥ ማግኘት የቻልኩትን ነገር በሙሉ ለሰዎቹ አከፋፈልኩ።

ሚስተር ቦውን በዐሥራ አንድ ሰዓት ደረሰ። «ከቡራን፣ ማንኛውም ነገር ተሳክቷል። ወደዋናው ከተማ ራሴ አደርሳችኋለሁ። መጀመሪያ ሚስተር ከሎሲዎን እናወርድና ከዚያም ወደ አንግዶች ማረፊያ እንሔዳለን።»

ከሎሲዎን ከአውቶሞቢሏ የኋላ ወንበር አስቀመጥነው። ልጃገረዷን ደህና ሁኝ ስል ነበር እናቷ አንድ ሻንጣ ተሸክማ በመምጣት፣ «አባካችሁ እነዚህን የባልተቤቴን ስጦታዎች ውሰዱ። መልካም ምኞታችንን ያስታውሳሉ» ያለችን።

«አናመሰግናለን፣ በጣም አናመሰግናችኋለን» አውቶሞቢሏ ተንቀሳቀሰች።

ሰዐሥራ ሁለት ሩብ ጉይ ከክሊኒኩ ደረስን። የተሠየመው በ«ቅዱስ ጊዮርጊስ» ስም ነበር። ጤና ረዳቶች ከሎሲዎን እነሡና ቃሬዛ ላይ በማድረግ አንድ የሕንድ ዜጋ አልጋ ላይ ሆኖ ይጠባበቀው ከነበረበት ከፍል ውስጥ አስገቡት። ዶክተሩ ወደ ውስጥ መጣና መጀመሪያ ቦውንን፣ ከዚያም ሌሎቻችንን ጨበጠን። ፈረንሣይኛ አይናገርም፣ ግን ለከሎሲዎ ጥሩ ሕክምና እንደሚደረግለትና እኛም ዘወትር በፈለግንበት ወቅት እየመጣን ልናየው መቻላችንን በአንድ አስተርጓሚ አማካይነት ገለጸልን። ወደ ቦውን አውቶሞቢል ተመለስንና ከተማውን አቋረጥን። በመብራቶቹ፣ በመኪናዎቹ በብስክሌቶቹ ተደነቅን። የዘህችን የአንጨት ቤቶች ከተማ አውራ መንገዶች፣ ነጮች ጥቁሮች፣ ሕንዶችና ቻይናውያን አጣብበውታል። የበጎ አድራጎት እንግዶች ማረፊያ የሚገኘው ደጋማ መብራት ካለው አደባባይ «የዓሣ ገበያ» የሚል ጽሑፍ ከሠረረበት አንድ መደብር አጠገብ ነበር። የሕንፃው ምድር ቤት ከድንጋይ የተሠራ ሆኖ፣ የተቀረው ከጣውላ ነበር። የበጎ አድራጎቱ ድርጅት ካፒቴንና መላው አባሎቹ ወንድም ሆነ ሴቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳይቀር ተቀበሉን። በመጠኑ ፈረንሣይኛ ይናገራሉ። ግን ማንኛውም ሰው የሚያነጋግረን እኛ በማይገባን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነበር። ፊጣ ከሚለው ፈታቸውና ሰላምታ ከማይለያቸው ወይኖቻቸው አኳያ ርኅሩኅ ቃላት እንደሚያፈልቁ ገብቶናል።

ሦስተኛው ፎቅ ላይ ወደሚገኘና ሦስት አልጋዎች ወዳሉት አንድ ከፍል ወሰዱን። ከእኛ ጋር የሚመጣ ከሆነ ሦስተኛው አልጋ ለክለሲዎ መሆኑ ነበር። ከክፍሉ ጋር አብሮ የተያያዘ አንድ የገላ መታጠቢያ ቤት ከሣሙናና ፎጣዎች ጋር ነበር። ካፒቴኑ ከፍላችንን ካሳየን በኋላ፣ «ከአሁን በኋላ ግማሽ ሰዓት ያህል ቆይተን አንድ ሰዓት ሲሆን፣ ሁላችንም አብረን እራት እንበላለን» አለ።

«እናመሰግናለን፣ ግን አልራበንም።»

«በከተማው መዘዋወር ከፈለጋችሁ ሁለት የአንቲይ ዶላር ይኸውላችሁ። ስለዚህ ቡና፣ ወይም ሻይ ወይም ጀለቲ መግዛት ትችላላችሁ። ግን መንገዱ እንዳይጠፋችሁ። ወደ ቤት ለመመለስ ስትዘጋጁ የሚያስፈልጋችሁን ታክሲ አስቁማችሁ ‹አባከህ ወደ በጎ አድራጎት ድርጅት› ማለት ብቻ ነው።»

ከዐሥር ደቂቃ በኋላ ወደ አውራ ጎዳናው ወጣን። ማንም ሰው ሳያተኩርብን፣ ማንም ሰው ጉዳይ ሳይለን፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር እየተጋፋን በእግር መንገዶቹ ላይ መጓዝ ጀመርን። በአንድ ከተማ ውስጥ የመጀመሪያዎቹን ነፃ እርምጃዎቻችንን በማድረጋችን ተደንቀን በሰፈው ተነፈስን። የማይናቅ ሰፋት ባለት አንዲት ከተማ ውስጥ በነፃ እንድንራመድ ስለተፈቀደልን ይበልጥ ደስታችንን ኢደነደነው።ታዲያ በተጨማሪ በእኛ ላይ የጣሉብንን እምነታቸውን ፍጹም ሳለመጣስ ሐቀኝነትም እደረብን። ማቹሬና እኔ ዝማ እያልን በሕገቡ መካከል እንጓዛለን። ከሰዎች ጋር ለመጠጋት፣ ለመነካካትና ከእነርሱ እንደ አንዱ ነዋሪ ለመሆን እምሮናል። አንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ገባንና ሁለት ቢራዎች ጠየቅን። እንደዚያ ለማለት ብዙ የሚያዳግት አይመስልም። «ሁለት ቢራ እባክሽ።» አፍንጫዋ ላይ የወርቅ ጌጥ ያደረገች አንዲት የሕንድ ኮረዳ ካመጣችልን በኋላ፣ «ግማሽ ዶላር ጌቶች» ማለቷ አሰደነቀን። ፊጣ ስትል ሉል የሚመስሉ ጥርሶቿ፣ ቦግ ያሉት የጥቁር ሐምራዊ ትላልቅ ወይኖቿ፣ በትከሻዋ የተንዘፋለለው ጥቁሩ ጸጉሯ፣ የጡቶቿን ውበት ለማሳየት በከፊል የተገለጠው ደረቷ፣ ለሌላው ሰው የተለመዱ ተራ ነገሮች ቢመስሉም ለእኛ ግን ትንግርታዊና አስማታዊ መሰሉን። አትቸኩል ጋፒ! እየቀለድክም መሆን አለበት፣ ዕውነት አይደለማ በቅርቡ በቱምህ የተቀበርህ ወንጀለኛ፣ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደብህ እሥረኛ ነበርክ፣ አሁን ደግሞ አንድ ነፃ ሰው በመሆን ላይ ትገኛለህ፤

ማቹሬ ከፈለ። የዶላር ግማሽ ብቻ ተርፎት ነበር። ቢራው አርኪና ቀዝቃዛ ነበር። «ሌላ እንጨምር ይሆን?» ሲል ጠየቀኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለተኛ ዙር ማዘዝ ብልሀነት አልመሰለኝም። «ስማ፣ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነፃ ሆንህና ልትሰከር ትፈልጋለህ እንዴ?»

«ተው አንጂ ፓፒ፣ አታጋንነው! ሁለት ቢራዎች መውሰድኮ መሰከር አይባልም።»

«ላይሆን ይችላል፣ ግን ደስታን በአንድ ጊዜ ተሰንብግበን መጨረስ ትከከል ነው ብዬ አልገምትም። በየጊዜው አንድ አንድ እያልን እየቆጠብን መቅመስ አለብን እንጂ መስገብገብ አይኖርብንም። በተጨማሪ ገንዘቡ የእኛ አይደለም።»

«እሺ ልክ ነህ። መጠቀም የሚኖርብን በቁጠባ ይሁን፣ ተገቢ ነው።»

መጠጥ ቤቱን ተውንና ከአንዱ የከተማው ዳር እስከ ሌላው በተዘረጋው የዋተርስ አውራ ጎዳና ቁልቁል ወረድን። በከተማዎቹ ታክሲዎች፣ በበቅሎዎች በሚሳቡ ትናንሽ ጋሪዎች፣ በካሚዎኖች፣ በሲኒማ ቤቶች በሚንቦገቦጉት የመብራት ምልክቶችና የማታ ክበቦች፣ በሕንዶችና በጥቁር ኮረዳዎች ዐይኖች ከመጠን በላይ አየተደነቅን ድንጉት ሳናውቀው በወደቡ አካባቢ ደረስን። ከፊትለፊታችን መብራት ያላቸው ጀልባዎች፣ እንደ ፓናማ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ቦስተን፣ ኩዊቢክ፣ የመሳሰሉ የዘነጋ ወደቦችን ስም የያዙ የመንገደኞች መርከቦችና፣ ከሐምቡርግ፣ ከአምስተርዳም፣ ከለንደን የመጡ ዕቃ ጫኝ መርከቦች ተገተግጠዋል። ወደቡ ከዳር እስከዳር በመጠጥ ቤቶች፣ በሰተኛ አዳሪዎችና በሆቴል ቤቶች ተጨናንቋል። በወጭጣቸው ወንዶችና ሴቶች ጥቅጥቅ ብለው ሲጠጡ፣ ሲዘፍኑና እየተጫጫሁ ሲጨፈጨፉ በድንጉት እኔንም ከእነዚህ ሰዎች ጋር ተቀላቀል የሚል የማልቋቋመው ከፍተኛ ፍላጎት አደረብኝ። ስድነት ሲመስል ይችል ይሆናል፣ ግን ስሜትን በጣም ፈንቅሎ የሚማርክ ነበር። ከመጠጥ ቤቶቹ በአንደኛው ደጃፍ ላይ በበረዶ የታጀሉ የኦይስተሮች፣ ሽሪምፖች፣ የክላሞች . . . አለ የተባለ የባሕር ውስጥ ምግብ በያይነቱ ተላላፊውን ለማስጎምጀት ለትዕይንት ተደርድሮ ነበር። ቀይና ነጭ ጨርቅ የለበሱት ገበታዎች ብዙ ሰዎችን እንዲማያስተናግዱ እኛም እንድንቀመጥ ይጋብዛሉ። ጠያይምና ደስ የሚል መልክ ያላቸው ኮረዳዎች ባለደማቅ ቀለምና ሰውነት የሚያሳዩ ስስ ቀሚሶቻቸውን ለብሰው ይበልጥ አንድንደሰት ይገፋፉናል። ከአነርሱ መካከል ወደ አንዷ ሔድኩና፣ «የፈረንሣይ ገንዘብ ተቀባይነት አለው?» ብየ የአንድ ሺ ፍራንክ ኖት ሰጠኋት። «አዎ አመነዝርልሃለሁ። እሺ።» ኖቱን ተቀበለችና ወደ ሚጪጪኸው ከፍል ወስጥ ገበታ ቆየች። ከዚያም ተመልሳ «ወደዚህ ና» አለችና ገንዘብ ተቀባዩ ዘንድ ወሰደችኝ። ቻይናዊ ነበር።

«ፈረንሣዊ ነህ?»

«አዎ»

«አንድ ሺ ፍራንክ ለመመንዘረ ነው?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ»

«ሁሉንም በአንቲይ ዶላር ነው?»

«አዎ»

«ፓስፖርት?»

«የለኝም»

«የመርከበኛ መታወቂያ ካርድ?»

«የለኝም»

«የይለፍ ወረቀት?»

«የለኝም»

«እሺ::» ከኮረዳዋ ጋር አንድ ሁለት ቃላት ተነጋገረ:: የከፍሉን ዙሪያ ቃኘች:: የወርቅ ጥልፍና መልህቅ ያለው የእጄን የመሰለች ኪፕ የደፋ አንድ መርከበኛ መሳይ ሰው ዘንድ ሒደችና ወደ ግንዙበ ተቀባዩ ይዛው መጣች::

«መታወቂያ ካርድህን?» አለው ቻይናዊው::

«ይኸው::»

ቻይናዊው ኮስተር ብሎ በእርሱ ስም አንድ የምንዛሪ ፋክቱር አዘጋጀና አስፈረመው:: ከዚያም ኮረዳዋ ከንዱን ይዛ እየመራች ወደ መቀመጫው መልሳ ወሰደችው:: ምን መደረግ አንዳለበት ቀደም ብሎ የለመደ ኖሯል:: ባለ ሃምሳ ዶላር አንድ ኖትና የሁለት ዶላር ኖቶች፣ በጠቅላላው ሁለት መቶ ሃምሳ የአነቲይ ዶላር ተቀበልኩ:: ለኮረዳዋ አንድ ዶላር ጉርሻ ሰጠሁ:: ወደ ውጭ ወጥተን ከጠረጴዛዎቹ በአንደኛው ላይ ተቀመጥንና የጎመገሶትን የባሕር ምግብ ከተመገብን በኋላ፣ በደረቅ ነጭ የወይን ጠጅ አወራረድነው::

t.me/OLDBOOKSPDF

አራተኛ ማስታወሻ

የመጀመሪያው ማምለጥ (ይቅጥላል)

ትሪኒዳድ

በእንግሊዞች ከተማ ያሳለፍኳትን ያችን የመጀመሪያ የነፃነት ሌሊት ልክ ትላንት እንደሆነች ሳስታውሳት አኖራለሁ። በልባችን ብርሃንና ሙቀት ተሞልተን ከሚደሰተውና ከሚስቀው ሕዝብ ጋር በየቦታው ዞርን። መጠጥ ቤቶቹ በመርከበኞችና አነርሱን ለማጥመድ አሰፍስፈው በሚጠባበቁ ኮረዳዎች ተሞልተው ነበር። እነዚህ ግን በፓሪስ በሊ ሐቭር ወይም በማርሴይ እንዳሉት ሞጋኝች ዐይኖቻቸው በጉጉትና በጮሌነት የፈጠጡ አራዳዎች አልነበሩም። የትሪኒዳድ ኮረዳዎች የተለያዩ መልኮች ነበራቸው። ወደ ብጫነት የሚያደሉ ቻይናውያን ጠቆር ያሉ አፍሪቃውያን እንደዚሁም የሸንኮራ አገዳና የኮከነት ተከል ለማልማት ዘሮቻቸው ቀደም ብለው ተግዘው የነበሩ የሕንድ ጠያይምና ባለ ሐር ጸጉር ሴቶች የቻይናውያንና የሕንድ ድብልቅና በአፍንጫዎቻቸው ላይ የወርቅ ቀለበቶች የሚያንጠለጥሉ ጭምር ነበሩ። ከዚያም በሮማውያን ገጽታቸው ላይ የሚንበገበጉ ትላልቅ ጥቁር ዐይኖችና እንደ መዳብ የሚያበሩ ፊቶች ያሏቸውና « እንዴት እንደ ተስተካከሉ አስኪ ተመልከቷቸው» የሚሉ የሚመስሉ ወደፊት የተወጠሩ ጡቶች የሚያስመዘግቡ የላቲን ዝርያዎችም አሉ። እነዚህ ሁሉ ጸጉሮቻቸውን በልዩ ልዩ ቀለማት አበባዎች የሚያስጌጡ ኮረዳዎች ስሜታቸው የሚቀሰቅሰው ለወራዳ ተግባር ወይም ለንግድ አልነበረም። በአርግጥ የሚደሰቱበት ሞያ እንዳልነበረና ገንዘብም በኑሯቸው ውስጥ ዓቢይ ነገር እንዳልሆነ ሁኔታቸው ይነግራል።

ማቹሬና እኔ ልክ ከሙበራት ጋር የሚጋጩ ጥንድ የአሳት አራት ቢራቢሮዎች መሰለን ከመጠጥ ቤት ወደ መጠጥ ቤት ስንናውዝ ቆየን። ደማቅ መብራቶች ከሚፕፑባት አንዲት ትንሽ አደባባይ ብቅ ስንል አንድ ቢተከርስቲያን ላይ ሰዓት አየሁ። ከሌሊቱ ሰምንት ሰዓት ሆኗል። መመለስ ነበረብን። ፈርለቀቅን። ወደ እንግዶች ማረፊያ በሁለት ዶላር የሚወስደን አንድ ታክሲ ጠራሁ። በጣም ኃፍረት እየተሰማን ስንገባ፣ ዕድሜዋ በሐያ አምስትና በሠላሳ መካከል የሆነ ቡናማ ጸጉር ያላት የበጎ አድራጎቱ ድርጅት አባል የሆነች ሴት በሰላምታ ተቀበለችን። እንኳን ደህና መጣችሁ አለችና ለስሚት በሚጥሙ ታላት በእንግሊዝ ቋንቋ ጥቂት አውርታን ከዚያም የከፍላችንን ቁልፍ ሰትሰጠን መልካም ሌሊት ተመኝትልን። ወደ አልጋችን ውስጥ ገባን። ከሻንጣየ ውስጥ አንድ ፒጃማ አገኘሁ። መብራቱን ላጠፋ ስል ነበር ማቹሬ እንደዚህ ሲለኝ የሰማሁት። « እንደዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ሁሉ የሰጠንን አምላክ ማመስገን

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚኖርብን አይመስልህም? ምን ታስባለህ ፓፒ?»

« አንተው የራስህን ኣምላክ አመሰግንልኝ:: ታላቅ ወዳጅ ነው:: ለእኛ በጣም ግሩም እንደሆነልን ሐቅ ነው:: ደህና አደር::» ከዚያም መበራቱን አጠፋው::

ይህ ትንሣኤ ይህ ከተቀበርኩበት መቃብር ያመለጥኩበትና ከዓለም ሕዝቦች ጋር የተቀላቀልኩበት አጋጣሚ በጣም አስፈንድቆኝ ስለነበር መተኛት አልቻልኩም:: በዐይኖቹ ላይ እንደ ሕልም ቦግ አልም የሚሉ ድብልቅልቅ ስሜቶች ድቅን አሉብኝ:- ችሎቱ፣ ማረፊያ ጣቢያው፣ ቆማጦቹ፣ ቅዱስ ማርቲን ደ ሬ ፣ ትሪቡላር፣ ኢዮአስ፣ ሞገዱ - ባለፉት ዓመታት አልፈ፞ባቸው የነበሩት አገሮች በመሉ ልክ እንደ ባሌ ዳንስ ተጫዋኞች እየተከታተሉ ወደ አእምሮዬ ለመግባት ይታገሉ ነበር:: ትዝታዎቼን ለመርሳት ሞክርኩ:: ግን ልረሳቸው አልቻልኩም:: እንግዳ የሆነብኝ ሌላው ነገር ደግሞ እነዚህ ትዝታዎች ከዱር ዓሣማዎቹ ጩኸት ከአሞራዎቹ ጫጫታ ከነፋሱና ከማዕበሎቹ ውሽንፍር ትተናቸው ከመጣነው መጠጥ ቤቶች ውስጥ ከሰማኋቸው የሕንዶች ቫዮሊን የሙዚቃ ድምፆች ጋር መቀላቀላቸው ነበር::

በማግሥቱ እስከ ረፋዱ ተኛሁ:: በአራት ሰዓት መዝጊያው ተቆረቆረ ሚስተር ቦውን ነበር:: ፊገግ እያለ « እንደ ምን አደራችሁ:: ገና አልጋ ላይ ናችሁ እንዴ? ዘግይታችሁ መሆን አለበት:: ጥሩ ጊዜ አሳለፋችሁ?» አለ::

« እንደምን አደሩ:: አዎ አምሽተን ነው የመጣነው እባክዎ ይቅርታ ያድርጉልን::»

« በምን የተነሣ? ካሳለፋችሁት ሕይወት አኳያ አድራጎታችሁ በትክክል ተገቢ ነው:: እንደ ነፃ ሰዎች የሆናችሁበትን የመጀመሪያዋን ምሽታችሁን መጠቀም ነበረባችሁ:: የመጣሁት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይዣችሁ ልሔድ ነው:: ወደ ሀገሪቱ ያለሕጋዊ ፈቃድ መግባታችሁን በግንባር ቃል ለመስጠት እዚያ መሔድ አለባችሁ:: ያ ፎርማሊቲ ከተጠናቀቀ በኋላ ጓደኞችሁን ለማየት እንሔዳለን:: ቀደም ብለው ዛሬ ጧት ራጅ አንሥተውታል:: ውጤቱን በጥሞት እናውቃለን::»

ልብሳችንን ሰበሰንና ሚስተር ቦውንና ካፒቴኑ ከሚቆዩበት የምድር ቤት ወረድን::

«እንደምን አደራችሁ ጓደኞቼ» አለ ባልተስተካከለ ፈረንሣይኛው::

«ሁላችሁም እንደምን አደራችሁ:: ደህና ናችሁ?» ስትል አንዲት የበነ አድራጎቱ የሴት መኮንን ተናገረችና፤ «ፖርት አፍ ስፔይን ተወዳጅ ሆና አገኛችኋት?» ብላ ጠየቀችን::

«አዎ፣ እንዴ! በጣም ግሩም ጊዜ አሳለፍን»

ቡና ጠጣንና ከአንግዶች ማረፊያው አስከ ፖሊስ ጣቢያው ሁለት መቶ ያርድ

t.me/OLDBOOKSPDF

የነበረውን ርቀት በእግራችን ተጓዝን። ያለምንም ልዩ አመለካከት ፖሊሱ ሰላምታ አቀረበልን። ካኪ ዩኒፎርም የለበሱ ሁለት ጥቁር ዘበኞች መህል አለፍንና ከፍተኛ ግርማ ያለው አንድ ቢሮ ውስጥ ገባን። ካኪ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ የለበሰ፣ በሚዳሎች የተንቆጠቆጠ፣ ዕድሜው በግምት ሐምሳ ዓመት የሚጠጋው አንድ መኮንን ብድግ ብሎ በፈረንሣይኛ ቋንቋ አነጋገረን። «እንደምን አደራችሁ። አባካችሁ ተቀመጡ። ኦፊሺያል የሆነውን ቃላችሁን ከመቀበላችን በፊት ትንሽ ጥያቄዎች ላቀርብላችሁ አፈልጋለሁ።»

«ዕደሜያችሁ ስንት ነው?»

«ሐያ ስድስትና ዐሥራ ዘጠኝ።»

«ምን ነበር ወንጀላችሁ?»

«ነፍስ መግደል።»

«ምን ያህል ተፈረደባችሁ?»

«የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት።»

«እንግዲያስ በአንደኛ ደረጃ ነፍስ መግደል ነበራ?»

«አይደለም ጌታዬ፣ የእኔ ሁለተኛ ደረጃ ነበር።»

«የእኔ አንደኛ ደረጃ ነበር» አለና ማቹሬ በማከታተል፣ «ዕድሜዬ ግን ዐሥራ ሰባት ዓመት ብቻ ነበር» አለ።

«በዐሥራ ሰባት ምን እንደምታደርግ ታውቃለህ» አለና መኮንኑ በማከታተል፣ «እንግሊዝ ውስጥ ቢሆን ኖሮ ትሰቀል ነበር። ይሁንና የፈረንሣውያንን ሕግ እንግሊዛውያን ባለሥልጣኖች ሊተቹበት አይገባም። ወንጀለኞቻቸውን ወደ ፈረንሣይ ጊያና መላካቸውን ግን አንስማማበትም። ፈረንሣይን ለመሰለ አንድ ሥልጡን ሀገር ይህ ድርጊት ኢሰብአዊና ከብርን የሚያቃልል ነው። ግን አናዝናለን። በትሪኒዳድም ሆነ በማናቸውም የእንግሊዝ ደሴቶች ውስጥ ለመቆየት አትችሉም። የሚሰጣችሁን የጊዜ ገደብ ለማስረዘም በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት ሰበብ ለመፈለግ እንዳትሞክሩ። ከእኛ ጋር አንድንተማመን መጠየቅ ይኖርብኛል። ለዐሥራ ስምንት ቀናት ፖርት አፍ ስፔን ውስጥ ለመቆየት ነፃ ናችሁ። እንደሚታወቀው አንዲት ጥሩ ጀልባ አላችሁ። ጥገና ቢያስፈልጋት የእንግሊዝ ባሕር ኃይል ሠራተኞች ይሠሩላችኋል። ለጉዟችሁ የሚያስፈልጋችሁ ማንኛውም ምግብና ከዚህም ሌላ አንድ ጥሩ ኮምፓስና አንድ የባሕር መስመር ካርታ ይሰጣችኋል። እንዳንድ የደቡብ አሜሪካ ሐገሮች እንደሚቀበሏችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ለፈረንሣይ ባለሥልጣኖች ሊልኳችሁ እስከሚወስኑበት ጊዜ ድረስ ታሥራችሁ በመንገድ ሥራ ብርጌድ ውስጥ ስለምትመደቡ ወደ ቬኔዙዌላ እንዳትሔዱ። ወንጀላችሁ ከባድ ሊሆን ይችላል፣ ግን ይህ ደግሞ ሕይወታችሁ እስከዘለዓለም ተበላሸ ማለት አይደለም። ወጣትና ጤነኛ ከመሆናችሁም ሌላ ጨዋ ልጆች ትመስላላችሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሆነም ካለፉችሁበት ሁኔታ አንባር ቋሚ ሽንፈት ለመቀበል እንደማትፈልጉ ተስፋ አደርጋለሁ። ራሱ አዚህ ድረስ መምጣታችሁም አለመፈለጋችሁን ይመሰክራል። ታላፊነት የሚሰማው የሕብረተሰብ አባል እንድትሆኑ ለመርዳት እጀን ስዘረጋ ደስ ይለኛል። መልካም ዕድል! ማንኛውም ችግር ቢገጥማችሁ በፈረንሣይኛ ልታነጋግሩት የምትችሉት አንድ ሰው ስለሚኖር በዚህ ስልክ ቁጥር ደውሉ።

ደመል አንቃጨለና አንድ ሲቪል ሰው ወደ እኛ መጣ። ብዙ ፖሊሶችና ሲቪሎች ታይፕ ከሚመቱበት አንድ ክፍል ውስጥ ተወስድንና ከመካከላቸው አንዱ ታላችንን ተቀበለ።

«ወደ ትሪኒዳድ ለምን መጣችሁ?»

«አግረመንገዳችንን ለማረፍ ነበር።»

«ከወዴት ነው የመጣችሁት?»

«ከፈረንሣይ ጊያና።»

«በምታመልጡበት ወቅት፣ የፈጸማችሁት ወንጀል ነበረ? ጉዳት የደረሰበት ወይንም የሚደላችሁት ሰው ቢኖር?»

«ከባድ ጉዳት የደረሰበት ሰው አልነበረም።»

«አንዴት ዐወቃችሁ?»

«ከመልቀቃችን በፊት ዐውቀነዋል።»

ዕድሚያችንን፣ በፈረንሣይ ሕግ የቅጣታችንን ደረጃ፣ ሌለ ሌላውንም በሙሉ አስረዳነው። ከዚያም ታል ተቀባዩ እንደዚህ አለ። «አስከ ዐሥራ ስምንት ቀናት ድረስ አዚህ ለመቆየት ትችላላችሁ። በዚያ ወቅት ማንኛውንም የምትፈልጉትን ለማድረግ ነፃነት አላችሁ። ማረፊያችሁን ከቀየራችሁ አስታውቁን። የሃምሳ አለቃ ዊሊ አባላለሁ። አድራሻዬ ከሁለት ስልክ ቁጥሮች ጋር ይሽመላችሁ። እንደኛው የታወቀው የፖሊስ ባልደረባነቴ ቁጥር፣ ሌላው የግል ቁጥሬ ነው። አንድ ነገር አጋጥሟችሁ ዕርዳታ ቢያስፈልጋችሁ ወዲያውኑ ደውሉልኝ። ለዕምነታችን ዋጋ እንደምትሰጡት እርግጠኞች ነን። መልካም ሥነ ምግባር እንደምታሳዩ አምናለሁ።»

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሚስተር ቦውን ወደ ከሊኒኩ ይዞን ሔደ። ከሎሲዎ እኛን በማየቱ ደስ ብሎት ነበር። በከተማ ስላሣለፍነው ምሽት ምንም ነገር አልተናገርንም። የነገርነው ቢኖር አንደፈለግን ለመውጣትና ለመግባት ነፃ መሆናችንን ብቻ ነበር። ይህም አስደነቀውና፣ «ያለ ምንም አጃቢ?» አለ።

«አዎ፣ ያለ ምንም አጃቢ»

«አነዚህ አንግሊዞች ቀልደኛ ሰዎች ናቸው ጃል።»

ቦውን ዶከተሩን ለመፈለግ ሄዶ ስለነበር አሁን ከአርሱ ጋር ተመለሰ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ስብራቱን የጠገነው ማነው?» ሲል ከሎሲዎን ጠየቀው።

«እኔና እዚህ የሌለ አንድ ሌላ ሰው» አልኩ።

«ጥሩ ስለጠገናማችሁት እንደገና ማስተካከል እያስፈልገንም፣ የተሰበረው እጥንት ከቦታው ጉብቷል። አንድ የብረት ምርኩዝ እንሠራልሀና በመጠኑ እየተራመድክ ለመዘዋወር ትችላለህ። እዚህ መቆየት ትፈልጋለህ፣ ወይስ ከጓደኞችህ ጋር ለመሔድ?»

«ከእነርሱ ጋር ለመሔድ።»

«መልካም ነው። ነገ ጧት መሔድ ትችላለህ። »

በእጅጉ አመሰገንነው። ዶክተሩና ሚስተር ቦውን በየፊናቸው ሔዱ። እኛም የቀረውን ጧትና ከቀትር በኋላ በከፊል ከከሎሲዎ ጋር አሳለፍን። የማቀዝቀዣ መሣሪያ አየሩን በሚያናፍስበትና መስኮቱ ወለል ብሎ በተከፈተ የአንግዳ ማረፊያ ክፍላችን ወስጥ እንደገና በማግሥቱ ስንሰባሰብ ደግሞ ከመጠን በላይ ደስታችን ጋለ። በአዲሶቹ ልብሶቻችን ውበትና ሙሉ ጤነኞች በመሆናችን ራሳችንን የምሥራች አልነው። ግን ውይይቱ ወደ አለፈው ታሪካችን ሊያዘነብል ሲል እንደዚህ አልኩ።

«ስለ ወደፊቱና ስለአሁኑ ብቻ ማሰብ አንጂ፣ ያለፈውን መርሳት አለብን። ለምሳሌ፣ ወዴት መሔድ ይኖርብናል - ወደ ኮሎምቢያ? ፓናማ? ኮስታሪካ? ይበልጥ ሊቀበሉን የሚችሉት የትኞቹ ሀገሮች እንደሆኑ ቦውንን መጠየቅ ይገባናል።»

ወደ ቦውን ቢሮ ስልክ ደወልኩ፣ አዚያ አልነበረም። ሳን ፊርናንዶ ወደሚገኘው ቤቱ ደወልኩ፣ ልጁ መለሰች። ለትንሽ ጊዜ እንደተነጋገርን፣ «ሚስተር ሔንሪ፣ ልክ ከእናንተ ማረፊያ አጠገብ ከሚገኘው ከፈረንሣውያን ገበያ ተነሥተው ሳንፈርናንዶ የሚመላለሱ አውቶብሶች አሉ። ለምን መጥታችሁ ከሰዓት በኋላ እዚህ አትቆዩም። አባካቸሁ እንደዚያ አድርጉ። አጠብቃችኋለሁ» አለች።

ስለሆነም ከሎሲዎ በመጠኑ ሚሊታሪ የሚያስመስለውን አዲሱን ቡናማ ቀለም ልብስ እንደለበሰ ሽክ ብሎ፣ ሥስታችንም በሙሉ ወደ ሳን ፊርናንዶ ተነሣን።

ያን የመሰለ የሞቀ መስተንግዶ ተሰጥቶን ወደ ነበረበት ቤት እንደገና ስንመለስ መንፈላችንን ደስታ ሞላው። ሁለቱ ሴቶች ስሚታችንን ተረድተውት መሆን አለበት፣ «ውድ ወዳጆቻችን፣ ወደ ራሳችሁ ቤት ተመለሣችሁ» አሉን። ስለሆነም አሁን የሚጠሩን በመጀመሪያ ስሞቻችን፣ እንደመሆኑ «ሔንሪ፣ ስኳር ላድርግልህ?» ወይም «አንድሬ፣ (የማቹሬ ስም ነበር) ተጨማሪ ነገር ትፈልጋለህ?» በማለት ነበር።

«የተወደዳችሁ ማዳም ቦውንና ሚስስ ቦውን፣ እግዚአብሔር ለጋስነታችሁንና ሩኅሩኅነታችሁን ተገንዝቦ፣ ከዚያች ቀን ጀምሮ በደስታ እንድትኖሩ፣ ውለታችሁን ሁሉ መልሶላችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።»

በጠረጴዛው ላይ አንድ ካርታ ዘረጋንና ዕቅዶቻችንን ነደፍን። መንገዶቹ ረጅም

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበሩ። ሳንታ ማርታ ወደ ተባለችው የመጀመሪያዋ የኮሎምቢያ ወደብ ሰባት መቶ ሐያ ማይል፣ ወደ ፓናማ አንድ ሺ ሁለት መቶ ማይል፣ ወደ ኮስታሪካ አንድ ሺ አምስት መቶ ማይል።

ቦውን ተመሰሰ። «ቆንሲሎቹ ዘንድ በሙሉ ስልክ ደውዬ መልካም ዜና ሰምቻለሁ» አለን፣ «ለማረፍ ያህል በኮራሶ ለትንሽ ቀናት መቆየት ትችላላችሁ። ኮለምቢያ ስለአመሰጡ ወንጀለኞች መመሪያ አላወጣችም። ቆንሲሉ እስከሚያውቀው ድረስ እስካሁን ኮሎምቢያም ሆነ ፓናማ ውስጥ ወይም የትኛውም ቦታ በባሕር የደረሰ ወንጀለኛ ከቶውንም የለም።»

«አንድ ሐሳብ አለኝ» አሉች የሚስተር ቦውን ልጅ ማርጋሬት። «ግን በጣም ሩቅ ነው ቢያንስ አንድ ሺ ስምንት መቶ ማይል።»

«ቦታው ወዴት ነው?» ሲል አባቷ ጠየቃት።

«እንግሊዝ ሆንዱራስ። አገረገርው የክርስትና አባቴ ስለሆነ ምናልባት እዚያ እርዳታ ታገኙ ይሆናል።»

ወደ ጓደኞቼ ተመለከትኩና፣ «ጉዞ ወደ እንግሊዝ ሆንዱራስ» አልኩ። በምዕራብና በደቡብ፣ ጓቴማላ፣ በሰሜን፣ ሚክሲኮ የሚያዋዶናት የእንግሊዝ ይዞታ ነች።

በማርጋሬትና በአናቷ አርዳታ ካርታ ላይ መስመራችንን እየነደፍን የከሰዓት በኋላውን ጊዜ አሳለፍን። የመጀመሪያ ማረፊያ ሰድስት መቶ ማይል ላይ በኮራሶ። ሁለተኛ ማረፊያ - ከኮራሶ መንገዳችን ላይ ከሚያጋጥመን ማንኛውም ደሴት ላይ። ሦስተኛ ማረፊያ - እንግሊዝ ሆንዱራስ።

በባህር ላይ ምን እንደሚያጋጥመን ፍጹም ማወቅ ስለማይቻል የጣሳ ምግቦች ሣጥን መያዝ እንዳለብን ተወሰነ። ሥጋ፣ አትክልቶች፣ ማርማላታ፣ ዓሣ ወዘተ . . . ይህም ከቆንሲሎቹ የተሰጡንን ስንቆች ማጠናከሪያ እንዲሆን ነበር።

የሳልቫዶሬ ሁለገብ መደብር ስንቃችንን በስጦታ መልክ ለማበርከት ደስተኛ እንደሚሆን ማርጋሬት አንድ ሐሳብ አቀረበችና፣ «ግን ፣ እነርሱ ካልፈለጉም እማማና እኔ እንገዛላችኋለን» አሉች።

«አይሆንም፣ በምንም ምክንያት» አልኩ።

«ዝም በል ሔንሪ»

«አይሆንም፤ አልፈቅድልሽም። የራሳችን ገንዘብ አለን። ለዕቃዎቹ ራሳችን በቀላሉ መክፈል እየቻልን የእናንተን ሩኅሩኅነት ለማሟጠጥ መሞከር ለእኛ ነውር ይሆንብናል።»

ከታላቁ ጉዟችን በፊት አንድ የመጨረሻ ጉበኝት ለማድረግ ቃል ገብተን ተለያየን።

t.me/OLDBOOKSPDF

በየምሽቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ ወደ ከተማ እንወጣለን። በጣም እንቅስቃሴ ባለበት አደባባይ አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ከሎሲዎን እናስቀምጥና አንዳችን በከተማ ስንዘዋወር፣ ሌላው ከእርሱ ጋር ለመሆን ማቹራና እኔ ተራ እንለዋወጣለን። እዚህ ከመጣን አሁን ዐሥር ቀን ሆነን። ለዚያ ሰብረት ምርኩዝ ምስጋና ይግባውና ከሎሲዎ ያለ ችግር በመጠኑ ይራመዳል። በከተማ ታክሲዎች ወደ ወደብ መሐል በብዙዎቹ መጠጥ ቤቶች ዘንድ እንደ ደንበኞች ታይተን ነበር። ፖሊሶቹም ሰላምታ ያቀርቡልናል። ምን እንደነበርንና ከወዴት እንደመጣን ማንኛውም ሰው ዐውቋል። ይሁንና አንድም ሰው ስለዚህ አይገልጽም። የተለማመድናቸው መጠጥ ቤቶች ለምግብና ለመጠጥ ከመርከበኞቹ ይልቅ ለእኛ የሚያስከፍሉን በቅናሽ ዋጋ ነበር። ኮረዳዎቹም እንደዚሁ ያደርጋሉ።

አብዛኛውን ጊዜ ኮረዳዎቹ ከመርከበኞች፣ ከመኮንኖችና ከቱሪስቶች ጋር ሲቀመጡ ሣያስልሉ ይጠጣሉ፣ በተቻለ መጠን ብዙ እንዲሰክሩም ያደርጓቸዋል። በመጠጥ ቤቱ ዳንስ በሚኖርበት ወቅት በመጀመሪያ ብዙ መጠጥ ካልገዛላቸው በስተቀር ፍጹም ከአንድ ሰው ጋር አይደንሱም። ከእኛ ጋር ግን የተለየ ነበር። ከእኛ ጋር ረጅም ጊዜ ይቀመጣሉ፣ ካልገፋፉናቸው በስተቀር መጠጥ አይወስዱም። ያንንም ሲቀበሉ ዝነኛውን የአነርሱን መጠጥ ሳይሆን አንድ ቢራ ወይም ፅውኑተኛውን ውስኪ በለዳ ነበር። ሁኔታችንን አንዳወቁና እንዳዘኑልን የሚገልፁበት መንገድ በመሆኑ ይህም አስደሰተን።

ጀልባዋ ፖርት ኦፍ ስፔይን ከሚገኘው የአንግሊዝ ባሕር ኃይል ሰፈር ጉብታለች። ወለሏ ተጠናክሮና በጠርዟ ላይ ሌላ ሰድሰት ኢንች ተጨምሮላት ታድሳ ነበር። በጥሩ ቅርፅ የምትገኝ ትመስላለች። ምሰሶውን በቀላልና በከፍተኛ ዓይነት ሌላ ምሰሶ ተክተው፣ ለአቅጣጫ ማስተካከያ እንጠቀምባቸው የነበሩትንም የዱቄት ከረጢቶች በጠንካራና ቀለም በተነከሩ የነፋስ ሸራዎች ለውጠውልናል። አንድ ቦሳሕር ሐይል መኮንን የተስተካከለች እንዲት ኮምፓስ አበረከተልኝና በካርታ ላይ አቅጣጫችንን እንዴት እንደምንቀይስ አሳየኝ። የኮራሶ መስመራችን በሰሜን ሆኖ አንድ ነጥብ ወደ ምዕራብ ሲል ይሆናል።

ካፒቴኑ «ታርፖን» ከምትባል አንድ የማሠልጠኛ መርከብ አዛዥ ከሆነ የባሕር ኃይል መኮንን ጋር አስተዋወቀኝ። በሚቀጥለው ቀን ጧት በሁለት ሰዓት ከወደቡ ለልምምድ ልገኝ እችል እንደሆነ ፈቃደኝነቴን ጠየቀኝ። ነገሩ ግራ ገብቶኝ ነበር፣ ግን ተስማማሁ። በሚቀጥለው ቀን ጧት ማቹራና እኔ ወደ ባሕር ኃይል ሠፈር ሔድን። አንድ መርከበኛ አጀበንና ጥሩ ነፋስ አግኝተን ወደ ባሕር ወጣን። ለሁለት ሰዓት እንደተለማመድን ድንገት አንድ የጦር መርከብ ብቅ አለ። ሙሉ ማዕረግ ልብሳቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደለበሱ ሠራተኞቹና መኮንኖቹ ሁሉ በመርከቡ ወለል ላይ ተሰልፈው ነበር። እኛን በማሳለፍ ላይ እንዳለ «ሁ ራ» ብለው ጮሁና መለየሞቻቸውን ሁለት ጊዜ አወረዱ። አንድ ዐይነት የክብር ሰላምታ ኖሯል፣ እኔ ግን ምን ማለት እንደሆነ ቅንጣት ታክል ግንዛቤ አልነበረኝም። የወር መርከቡ ቆሞ ወደነበረበት ሠፈር ተመለስን። የእኛንም እንደዚሁ አቆምንና መርከበኛው እንድንከተለው አንድ ምልክት አሳየን። ወደ ጦር መርከቡ ስገመጣ አዛዡ ከድልድዩ ላይ ተቀበለን። ከመድረሳችን አንድ የፈሸክ ድምፅ አስተጋባና ከመኮንኖቹ ጋር ከተሞወቅን በኋላ፣ በተጠንቀቅ ቆመው የነበሩ አጩ መኮንኖች በፊት ለፊታችን በሰልፍ አለፉ። አዛዡ በእንግሊዝኛ ቃላት ገለጻ ካደረገ በኋላ ሰልፉ ተበተነ። አዛዡ ለተማሪዎቹ ሲገልጽላቸው የነበረውና ከእነርሱም የክብር ሰላምታ ያገኘነው ይህችን በመሰለች ትንሽ ጀልባ ያን ያህል ረጅም ጉዞ ማድረጋችንና አሁንም ገና ይበልጥ አደገኛና ረጅም ጉዞ ለማድረግ በመነሣት ላይ መሆናችን እንደነበር አንድ ወጣት መኮንን አስረዳን። ለተደረገልን ክብር መኮንኑን አመሰገንን። ሦስት የመርከበኛ ጃኬቶች አበረከቱልን። ጥቁር ሆነው ጠንካራ ዚፕና የራስ ቆብ ያላቸው ነበሩ። ደሴቲቷን ለመልቀቅ ሁለት ቀናት ሲቀረን፣ ከሳምንት በፊት የታሠሩ ሦስት ልማደኛ ሌቦችን አንድንወሰድለት የፖሊስ አዛዥ ትቡብር የጠየቀ መሆኑን ሮ ስተር ቦውን አጫወተን። ደሴቷ ላይ ሊቀሩ የቻሉት ወደ ቬኔዙዌላ ወይም ሌላ ሀገር የሔዱ ጓደኞቻችን ትተውን ነው ይላሉ። ሐሳቡን አልወደድኩትም፣ ግን እምቢ ለማለት ደግሞ ከሚገባው በላይ እንከብካቤ ተደርጎልናል። የመጨረሻ መልስ ከመስጠቴ በፊት ከእነዚህ ሦስት አሥረኞች ጋር ለመገናኘት ጠየቅኩ። አንድ የፖሊስ መኪና መጣልኝና ከአዛዡ ጋር ለመወያየት ሔድኩ። እርሱም መጀመሪያ በደረሰንበት ወቅት ጠይቆን የነበረው መኮንን ነበር። ሃምሳ አለቃ ዊሊ አንደ አስተርጓሚ ሆነ።

« አንድ ውለታ ብታደርጉልን ደስ ባለን ነበር።»

« የሚቻል ከሆነ፣ በደስታ»

« እዚህ አሥር ቤት ውስጥ ሦስት ፈረንሣውያን ልማደኛ ሌቦች አሉን። ጓደኞቻችን እዚህ ትተውን ሔዱ ይላሉ። ጀልባቸውን ራሳቸው ያሰመጡ መስሎናል፣ እነርሱ ግን መቅዘፍ እንኳ አናውቅም ይላሉ። እኛ ሁኔታው ተማታብን፣ አንድ አዲስ ጀልባ እንድንሰጣቸው እየጣሩ መስሎናል። መሔድ ይገባቸዋል፣ ግን እዚህ ለሚመጣው የመጀመሪያ የፈረንሣይ መርከብ መልሽ ላስረከባቸው አለፈለግኩም።»

« ጌታዬ ፣ እኔ እመሰዳቸዋለሁ። ግን መጀመሪያ ከእነርሱ ጋር መነጋገር አፈልጋለሁ። ሦስት እንግዶችን አጠቃለሎ መውሰድ አደገኛ መሆኑን እርስዎም መገንዘብ አለብዎት።»

« ጉበቶኛል። ዊሊ፣ ሦስቱን ፈረንሣውያን ወደ አሥር በቱ ግቢ

t.me/OLDBOOKSPDF

አውጪቸው::» ብቻየን ላነጋግራቸው ስለፈለግኩ ሃምሳ አለቃ ዊሊ ገለል እንዲልልኝ ጠየቅኩት::

«ልማደኛ ሌቦች ናችሁ?»

«አይደለንም፣ ከባድ ወንጀለኞች ነን::»

«ታዲያ ለምን ልማደኛ ሌቦች ነን አላችሁ?»

«ከአንድ ትልቅ ወንጀል ይልቅ ብዙ ትንሽ ወንጀሎች የሥራን መሆናችንን ከዐወቁ የተሻለ አንከብካቤ አናገኛለን ብለን ተስፋ በማድረግ ነበር:: ግን ስሕተተኞች ነን:: አንተስ ምንድን ነህ?»

«ከባድ ወንጀለኛ»

«አላወቅህም?»

«በመጨረሻው ኮንቮይ ነው የመጣሁት:: ስሙ፣ ሥስታችሁን በእኛ ጀልባ እንድንወሰዳችሁ የምትፈልጉ ከሆነ እንድጠይቃችሁ የፖሊሱ አዛዥ ነግሮኛል:: እኛም ሥስት ነን:: እርሱ የሚለው፣ እኔ ካልወሰድኳችሁ በስተቀር በዚያ በሚያልፈው የመጀመሪያው የፈረንሣይ ጀልባ አሣፍራቸዋለሁ ነው:: ምን ይመስላችኋል?»

«ወደ ባሕር ዳግመኛ ለመውጣት ያልፈለግንበት ምክንያቶች አሉን::»

«ከእናንተ ጋር የሔድን እንመስልና፣ ከዚያም ከደሴቷ መጨረሻ ትታችሁን እናንተ መንገዳችሁን አትቀጥሉም እንዴ?»

«አይሆንም፣ እንደዚያስ ማድረግ አልችልም::»

«ለምን አይሆንም?»

«ምክንያቱም ሩኅሩኀነታቸውን በዚህ መልኩ መልሶ አጸፋ መክፈል አስነዋሪ መንገድ ነው::»

«ለእንግሊዛውያን ከማሰብህ በፊት ለእኛ ማሰብ ይኖርብሃል::»

«ለምን?»

«ምክንያቱም አንተም ራስህ እሥረኛ ነሃ?»

«ያ ሊሆን ይችላል፣ ግን ብዙ ዓይነት የተለያዩ እሥረኞች አሉ:: ምናልባትም ከእኔና ከእንግሊዛውያኑ ይልቅ፣ በአንተና በእኔ መካከል የበለጠ ልዩነት ይኖራል:: ወሳኙ የአመለካከት ሁኔታ ነው::»

«ታዲያ ለፈረንሣውያን ባለሥልጣኖች እንዲያስረከቡን ልትነግራቸው ነዋ?»

«አይደለም:: ግን ኮራሶ ከመድረሳችን በፊት እንደማላወርዳችሁ ነው::»

«አንደገና ጉዞ መቋቋም አልችልም» አለ ከእነርሱ ውስጥ አንዱ::

«ስማ፣ በመጀመሪያ የእኛን ጀልባ ተመልከታት:: ምናልባት የቀድሞዋ ጀልባችሁ አሮጌ ትመስለኛለች»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሺ፣ እስኪ እንሞክራ»

«መልካም፣ ጀልባዋን ለመመልከት እንዲፈቅድላችሁ አዛዡን እጠይቀዋለሁ።»

ከሃምሳ አለቃ ዊሊ ጋር አብረን ወደ ወደቡ ሔድን። አንድ ጊዜ ጀልባዋን ከተመለከቱ በኋላ ሦስቱ ጓደኞች እምነት ያደረባቸው መሰሉ።

አዲስ ጉዞ

እኛ ሦስታችንና ሦስቱ እንግዶች ከሁለት ቀን በኋላ ጉዞ ጀመርን። ወሬው እንዴት እንደ ነፈሰላቸው አላውቅም፣ ከቦውን ቤተሰቦችና ከወታደራዊው በጎ አድራጎቱ ኃላፊ ጋር የመጠጥ ቤቶቹ አሥራ ሁለት ያህል ኮረዳዎች እኛን ለመሸኘት መጡ። ከኮረዳዎቹ አንዷ ለመሸነባበቻ አንድ ጊዜ ስትስመኝ፣ ማርጋሬት አየሣቀች፣ «ሔንሪ፣ ለካ ቀልጣፋ ወንድ ኖረሃል!» አለች።

«ሁላችሁም ደህና ሁኑ። ዳግመኛ ባናያችሁም በልባችን ውስጥ አንድ ትልቅ ቦታ እንዳላችሁ አስታውሱ። ፍጹም አንረሳችሁም።»

ከሰዓት በኋላ በዐሥር ሰዓት ተንቀሳቀስን። ጊዜ ሳንፈጅ ከወደቡ ወጣንና እኛን ለመሸኘት መጥተው የነበሩትን ቡድኖች ለመጨረሻ ጊዜ ለመመልከት ቆምን። አሁንም ነጭ መሐረቦች እያውለበለቡልን ነበር። የኦሎስ ሽራዎቻችንን ነፋስ ሞላቸው፣ በመነሻችንና በመድረሻችን መካከል ከሚያጋጥሙ በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ማዕበሎች ውጪ የመጀመሪያውን በድፍረት ተጋፈጥነው።

ጀልባችን ወስጥ የእኔና የማቹሬ ሁለት ጩቤዎች ነበሩ። ቆንጨራው ከከሎሲዎ አጠገብ ነበር ያለው፣ ገጀራውም እንደዚያው ነበር። ከእነርሱ መካከል ግን ማንም እንዳልታጠቀ አርግጠኞች ነበርን፣ ለማንኛውም ቢሆን ነገሮችን ለመቆጣጠር ቢያንስ ሁለታችን ዘወትር መንቃት ይኖርብናል። ፀሐይ ልትጠልቅ አቅራቢያ የማሠልጠኛው መርከብ መጣና ለግማሽ ሰዓት ሲያጅገን ቆየ። ከዚያም ሰላምታ ሰጥቶን ሔደ።

« ማነው ስምህ?»

« ሴሩው»

« ስንተኛ ኮንቮይ?»

« ሐያ ሰባተኛው።»

« ቅጣትህ?»

« ሐያ ዓመት»

« የአንተስ ማን ይባላል?»

« ካርጉሬ ሐያ ዘጠነኛው ኮንቮይ። ብሪቶን ነኝ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

« ብራቮን ሆነህ ጀልባ መቅዘፍ እንዴት አታውቅም?»

« ስሜ ዳዶልስ ነው። ከአንገር ቀበሌ ነኝ። በቮልት ላይ አንድ ጸያፍ ካር በመኖሩ ምክንያት ዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተፈረደብኝ። ያ ባይሆን ኖሮ ቢበዛ ሀያ ዓመት በተፈረደብኝ ነበር። በሐያ ዘጠነኛው ኮንቮይ ነበርኩ።»

« የተናገርከው ምን ብለህ ነበር?»

« ያማ እንደዚህ ነበር። ሚስቱን በካውያ ገደልኳት። ለፍርድ በቀረብኩበት ወቅት ከተችዎቼ አንደኛው ለምን በካውያ እንደ መታኋት ጠየቀኝ። ለምን እንደሆነ እኔም አላውቅም፤ ግን ልብስ በሚገባ መተኮስ ባለመቻሏ በካውያው ገደልኳት አልኩት። ከባድ ቅጣት ሊያስከትልብኝ የቻለው ያ አስቀያሚ ንግግር መሆኑን ጠበቃዬ ገለጸልኝ።»

« ያመለጥከው ከየት ነበር?»

« ከካስኬድ፡- ከትዳስ ላውረን በግምት ሃምሳ ማይል የምትርቅ የጫካ ካምፕ ነች። ከዚያ ለማምለጥ ቀላል ነበር፤ ምክንያቱም ብዙ ነጻነት ነበረን። የነበርነው አምስታችን ስለሆን ቀላል ነበር።»

« አምስት ስትል ምን ማለትህ ነው? ሁለቱ ወዴት ሐዱ?»

የታፍረት ዝምታ ረጭ አለ።

በመጨረሻም ከሎሲዎ « ስሙ ጓደኞቹ ሁላችንንም የሚያገቡን ጉዳይ ይሆናል። ለማወቅም መብት አለን» አለ።

« እኔ እነግራችኋለሁ» ብሎ ብሪቶኑ ጀመረ። « አርሱ እንዳለው ሁሉ ስንነሣ አምስት ሆነን ነበር። ግን ሁለቱ የጎደሉት የካኒስ ቀበሌ ሰዎች ስለነበሩ ዓላ አጥማጆች ነን ብለው ነገሩን። ለማምለጡ ዝግጅት ምንም ነገር አልከፈሉም ግን ጀልባ በመቅዘፍ እየረዱን አናካስላችኋለን አሉን። ታዲያ ወደ መንገድ ስንገባ ከአነርሱ ውስጥ አንዳቸውም ስለጀልባ ቀዘፋ ምንም ነገር አያውቁም። ሐያ ጊዜ ልንሰጥም ተቃርበን ነበር። ወደ ጠረፍ ተጠጋን መጀመሪያ ዳኾ ጊያና ከዚያም እንግሊዝ ጊያና በመጨረሻም ትሪኒዳድ። በጅርጅታውንና በትሪኒዳድ መካከል ጀልባ መቅዘፍ እችላለሁ ያለውን አንደኛውን ገደልኩት። ድርሻውን ስላልከፈለና ጥሩ ጀልባ ቀዛፊ ነኝ ብሎ ስለዋሸ ሰውየው የሚገባውን አግኝቷል። ሲላው ደግሞ ገና ለገና እገደላለሁ ብሎ ስለፈራ በአንድ ሞገድ መካከል የጀልባውን እርፍ ስፋትና ወደ ባሕር ዘለለ። የምንችለውን ሁሉ ጥረት አደረግን ብዙ ጀልባዋ ልትሰምጥ ተቃረበች። በመጨረሻም ከአንድ ቋጥኝ ጋር ተጋጨንና ዕድለኞች ሆነን ከዚያ ውስጥ ለመትረፍ ቻልን። እምላለሁ ዕውነቱ ይኸው ነው ሲላ ምንም ነገር የለም ሐቅ ነው።»

« ልክ ነው» አሉ ሊሎቹ ሁለቱ። « ይኸታው ይኸው ነው። ሰውየው መገደል

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደሚገባው እኛ ሁላችንም ተስማምተናል። አንተስ ምን ይመስልሃል ፓፒዮን?»

« እኔ ፍርድ ለመስጠት አልተዘጋጀሁም።»

« ግን አንተ በትሆን ምን ታደርገው ነበር?» ሲል ብሪቶኑ አጥብቆ ጠየቀኝ።

« ስለሁኔታው አስብበታለሁ። እርግጡን ለማወቅ ራስህ የታሪኩ ተካፋይ መሆን ይኖርብሃል። አለበለዚያ የትኛው ልክ እንደሆነ ለመናገር አትችልም።»

« እኔ ብሆን አገድለው ነበር። በርሱ ውሸት የተነሣ የሁሉም ሕይወት ሊጠፋ ነበርኮ» አለ ከሎሲዎ።

« እሺ ዳግመኛ ስለዚህ ጉዳይ አናውራ። ግን አሁንም ገና በመፍራት ላይ መሆናችሁ ተሰምቶኛል። ወደ ባሕር የተመለሳችሁት እነርሱ ሒዱ ብለው ስላስገደዷችሁ ብቻ ነው ልክ ነው?

« ልክ ነው» ሲሉ ሁሉም በአንድነት መለሱ።

« እንግዲያው እሺ። ግን የፈለገው ነገር ቢሆን ማንም ሰው መርበትበት የለበትም። ሌላው ቢቀር መፍራታችሁን አታስታውቁ። ፍርሃት ቢገባችሁም እንኳን አትፍሩ ይህች ጥሩ ጀልባ ነች ማንነቷን በሚገባ አስመስክራለች። ከበድ ያለ ጭነት አለን። ግን ከፈሩ የስድስት ኢንች ከፍታ ስለአለው የተጨመረውን ጭነት በሚገባ ይችላል።»

ትንሽ ቡና ቀማመስንና ሲጃራ አጨስን። በምንነሣበት ወቅት ጥሩ ምግብ በልተን ስለነበር እስከሚቀጥለው ቀን ላለመብላት ወስነናል። ከቅዱስ ላውረን ሆስፒታል ከፍላችን ለማምለጥ ከተነሣንበት ጊዜ ጀምሮ እኩሌን ዐርባ ሁለት ቀናት መሆኑን ልማደኛው መዘክር መዝጋቢያችን ከሎሲዎ ገለናል። ከዚያ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሦስት ውድ ዕቃዎች ባለንብረት ሆኜአለሁ። ትሪኒዳድ የገዛሁት ውሃ የማያበላሸው አንድ የእጅ ሰዓት ጥንድ ማንዣ ያለው አንድ በጣም አስተማማኝ ኮምፓስ ባለፕላስቲክ መስታወትና አንድ ጥቁር መነጽር። ከሎሲዎና ማቹሬም እያንዳንዳቸው የማርከበኛ መለዮ ነበራቸው። ከዶልፊን መንጋዎች ጋር ሁለት ጊዜ ያህል ከመገናኘታችን በስተቀር የመጀመሪያዎቹን ሦስት ቀናት ምንም ችግር አልገጠመንም። በቁጥር ስምንት የሆኑ መንጋዎች በጀልባዋ ሊጫወቱባት ተነሡ። ሁላችንም ላብ አጠመቀን። በቅድሚያ ውስጥ ለውስጥ እየታከኳት ከፊቷ ወደ ላይ ብቅ አሉና እንደገና ከጀልባዋ ሥር በጎኗ በኩል አግድም አለፉ። በሌላው ጨዋታ ደግሞ ሦስት ዶልፊኖች ሦስት መዓዘን በመሥራት አንዱ ከፊት ሁለቱ ከኋላ በመሆን በትክክል ሰልፍ ገቡ። በሚያስፈራ ፍጥነት ወደ እኛ ይሸመጥጡና አላያችን ላይ ሊወጡብን ሲቃረቡ ወደ ጀልባዋ ሥር በመጥለቅ በሌላ አቅጣጫ ብቅ ይላሉ። ኃይለኛ ነፋስ ስላጋጠመን ሰነጣጥቀናቸው ቀድመን ለማለፍ በሙሉ ኃይል ቀዘፍን። ግን እነርሱም ይበልጥ ፍጥነት ጨመሩ። ጨዋታው ብዙ ሰዓት ወሰደ፣ እኛም ፈገዘን ቀረን። ሦስቱ አዲስ መጤዎች ምንም

t.me/OLDBOOKSPDF

አልተነፈሱም። ሆኖም ገጸቸውን ሳየው በጣም ተቀያይሮ ነበረ።

በአራተኛው ሌሊት እጋማሽ ላይ ግዙፍ በሆነ ሞገድ ተመታን። የሚያስደነግጥ ነበር። አንዳንዶቹ ጥልቅ ሌሎቹ አጫጭር ከሆኑ መስመሮቻቸው ጋር እየተላተሙ ማዕበሎቹ በሁሉም አቅጣጫዎች ይሮጣሉ። አልፎ አልፎ ብቻ ከሰዓዎ « በርታና ጣፋ ጓደኛ! ሌሎቹን እንዳለፍክቸው ይኼንንም እንደዚሁ አሰፈውሃ» ወይም « ከኋላ ተመልከት!» እያለ ይጮህ ነበር። ጫፎቻቸው በረፋዎችን የሚያፈናጥቁ ማዕበሎች በሶስት አቅጣጫ ሲመጡብን በጥንቃቄ አጠባበቃለሁ። ከዚያም ከወዴት እንደመጣ ያላወቅነው አንድ ማዕበል ወደ ላይ ቀጥ ብሎ በመቆም ከኋላችን አጣፈረን። ብዙ ጊዜ ማዕበሎች ከትከሻዬ በላይ እየለተሙኝ ጀልባዋን ያጥለቀልቋታል። አምስቱም ሰዎች መቀቀያ ብረት ድስቶችና ባዶ ጣሳዎች በመያዝ ልከ እንደ ዕብድ ሆነው ውሃውን እየቀዱ ያፈስሳሉ። ግን ያ የተንጣለለባት ውሃ ከፍታ ጀልባዋን ከሩብ የበለጠ ያልሞላት ስለነበር በማያወላውል ሁኔታ ከመስመጥ አደጋ ድነናል። ይህ የሰርከስ ትዕይንት ግማሽ ሌሊት ሙሉ ለሰባት ሰዓት ያህል ቆየ። በዝናሙ ምክንያት አንድም ነገር ማየት አልቻልንም። ፀሐይዋም እስከ ጧት ሁለት ሰዓት ድረስ ብቅም አላለችም።

አዲሱን ቀን ከደስታ ጋር መጀመር፣ የፀሐይዋን መመለስና የሞገዱን ማብቃት በሰላምታ ተቀበልነው። ይሆንንም ለማክበር ቡና መውሰድ ይገባናል! በቆርቆሮ የታሸገ ወተት በቡና አፈላንና እንደ ብረት የጠነከረውን ብስኩት ቡና ውስጥ እያራስን በላን። ምንም እንኳ ነፋሱ ኃይለኛ ማዕበሎቹም ከፍተኛና የማይሰገሩ ቢሆኑም ከሞገዱ ጋር የተጋፈጥኩበት የሌሊቱ ትግል እድከሞኝ ስለነበር መሪውን ማቹሬ እንዲይዝልኝ ጠየቅኩት። መተኛት ይኖርብኛል። ከጎን በኩል አንድ ማዕበል ሲገባና የጀልባዋ ሦስት አራተኛ በውሃ ሲጥለቀለቅ እኔ ለፀሥር ደቂቃ እንኳ ያህል ጋደም አላልኩም ነበር። የቆርቆሮ ጣሣዎቹ ምድኛው ብርድ ልብሶቹ . . . ማንኛውም ነገር ተንሣፈፈ። እስከ ሆዴ ድረስ ውሃ ሲወጣ ባነንኩና ልከ ሌላ ማዕበል በላያችን ላይ ከመምጣቱ በፊት መሪውን ጨመደድኩ። በእንድ ኃይለኛ ጥምዘዛ ጀልባችንን ወደ ማዕበሉ አቅጣጫ አዞርኩ ውጤቱም በሠላሳ ጫማ ርቀት ወደፊት አፈናጠረን።

ማንኛውም ሰው ዕቃ ሊወረውር ተነሣ። ማቹሬ አራት ጋሎን የሚይዘውን ቅልቱን ብረት ድስት ወረወረው።

ማንም ሰው ምንም ነገር ሊያስቀር አልተመኘም። ያለን አንድ ነሐሳብ ብቻ- መወርወር። በተቻለ ፍጥነት መወርወር ምክንያቱም ከፍተኛው የጀልባዋ ከበደት ማዕበሎቹን ለመቋቋም አስቸጋሪ ሆነባት። አዲሶቹም መጤዎች የተቻላቸውን ያህል መልክም ምግባር ማሳየታቸውን ማመን ይኖርብኛል። ብራዶኑ ሽንጣው መወርወሩን ሊመለከት በተጨማሪ ጀልባዋን ለማቃለል ከጎን በኩል ሰቅሎት የነበረውን የመጠጥ ውሃ

t.me/OLDBOOKSPDF

በርሜል ወደ ባሕሩ ወረወረ። ከሁለት ሰዓት በኋላ ደረቀልን። ግን ብርድ ልብሶቻችንን፣ የፔርመገዝ ምድጃውን፣ ከሰላችንን፣ ነዳጅንና የመጠጡን ውሃ በገዘ እጃችን ወርውረናቸዋል። ሻንጣዬ እና እንደዚሁም ሦስቱ የመርከበኛ ጃኬቶቻችን አብረው መሐዳቸውን የተገነዘብኩት ከሰዓት በኋላ ሱሪየን አቀይራለሁ ሰል ነበር። ትምባኋችንም ጨርሶ ጠፍቶ ወይም ረጥቦ ነበር። የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀቶቹም ውሃ እንዳያስገቡ ከታሸጉበት የአሉሚኒየም ሣጥን ጋር አብረው ሰጥመዋል። ግን ከጀልባዋ ወለል ላይ ሁለት ጠርሙስ ሩም አገኘን።

« ጓደኞቼ!» አልኩ። « በቅድሚያ አንዳንድ ደህና ጉንጭ ሩም እንጎንጭና፣ ከዚያም የመጠባበቂያ ሣጥናችንን ከፍተን የተረፈንን እንመልከት። የፍራፍሬ ጭማቂ ነበር። ጥሩ። እንከፋፈለዋለን። በብረት ሣጥኖች የታሸጉ ደረቅ ብስኩቶች አገኘን። አንዱን እናጋባና ራሱን ምድጃ እንሠራዋለን። የጣሳ ምግቦቹን ከጀልባዋ ውስጥ እናስቀምጥና የእንጨት ሣጥኑን ሰማግዶ እንጠቀምበታለን። ሁላችንም በጣም ፈርተን ነበር። ግን አሁን አደጋው አልፏል። ራሳችንን አንድ ላይ በማስተባበር ወደ ፊት ለሚጠብቀን ሁሉ መዘጋጀት ይኖርብናል። ከአሁን በኋላ ማንም ሰው ‹ጠምቶኛል› ማለት፣ ‹ማንም ሰው ረቦኛል› ማለት፣ ‹ማንም ሰው ‹ምነው እንድ የማጨሰው ሲጃራ ባገኘሁ› ማለት የለበትም። እሺ?»

« እሺ።»

ማንኛውም ሰው ተግባብቷል ምሕረት ወረደና ነፋሱ የሥጋ ሾርባ ለመቀቅል አስቻለን። አንድ ሙሉ ሣሆን ሾርባ ከደረቅ ብስኩት ጋር ጠጣንና፣ አስከሚቀጥለው ቀን ድረስ በቂ የሆነ ጥሩ የረኃብ ማስታገሻ እደረግነው። ከዚያም እያንዳንዳችን ትንሽ ጠብታ ሻይ ቀማመስን። አንዳጋጣሚም ሰምንት ሲጃራዎች የሚይዙ ሐያ አራት ነጠላ ፓኪቶችን የያዘ አንድ ካርቶን ካልረጠበው ሣጥን ውስጥ ተገኘ። ማጨስ የሚገባኝ እኔ ብቻ እንድሆን አምስቱ ባልደረቦቼ ወሰኑ። ምክንያቱም ነቅቼ ለመቆየት እንዲረዳኝ ተብሎ ነበር። ስለሆነም ሌሎቹን እያስቀናም። ከሰሲዎ ሲጃራዎቼን ማቀጣጠል አቆመ። ለብልሃቱ ላመሰግነው ይገባኛል። አንድም ያልተግባባንበት ወቅት አልነበረም።

ጉዞ ከጀመርን ስድስት ቀናት ሆኖናል፣ ግን ገና በሚገባ አልተኛሁም ነበር። በዚሁ ምሽት ባሕሩ ረግቶ ስለነበር ተኛሁ። ለአምስት ሰዓት ያህል ልከ እንደሞተ ሆኜ ተዘረርኩ። በምነቃበት ወቅት ከምሽቱ አራት ሰዓት ሆኖ ነበር። ባሕሩ መስታወት መስሏል። ሌሎቹ ቀደም ሲል ተመግበው ነበር። እንድ የቆርቆሮ ግንፎ አገኘሁና ከተለበለበ ቋሊማ ጋር በላሁት። ይጥም ነበር፣ ሻዩም ከሞላ ጎደል ቀዝቅዟል። ሲጃራ አጨስኩና ነፋስ አጠብቅ ጀመር። ሰማዩ በኮከቦች ይንቦገቦግ ነበር። የሰሜን ኮከብ ያለ የሌለ ድምቀቱን ረጭቶ ይንቀለቀላል። የደቡብ መስቀል ብቻ ይበልጠዋል። ትልቁና

t.me/OLDBOOKSPDF

ትንሹ ድቦች (የኮከቦች ስሞች ናቸው) ጥርት ብለው ይታያሉ። ዳመና አልነበረም። ሙሉዋ ጨረቃም ሰማዩ ላይ ከፍ ብላ ትታያለች። ጃኬቱ ተወርውሮበት በጉርድ ሸሚዝ ብቻ የነበረው ብራዞኑ በአሳዛኝ ሁኔታ ላይ ይገኛል። የመርከበኛ ጃኬቴን አዋስኩት። ወደ ሰባተኛ ቀን ተላለፍን።

« እንግዲህ አሁን ከኮራሶ መራቅ አንችልም። ምናልባት ወደ ሰሜን በጣም ርቀን ሔደን ይሆናል። ከእንግዲህ ወዲያ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አመራለሁ። ስለዚህ የዳች አንቲይስን አንስታትም። አለበለዚያ ችግር ላይ እንወድቃለን።»

« አንተ የተሻለ ነው ብለህ ያሰብከውን አድርግ» አለ ብራዞኑ። ያንን ሌሊት በሙሉ ነፋስ ስንጠብቅ ቆየን። በመጨረሻም ከጧቱ አንድ ሰዓት ላይ ቀኑ እየረፈደ ሲሔድ ኃይሉን እየጨመረ የመጣ አንድ ጥሩ የነፋስ ሽውታ ያዟሟ ጀመረ። ለሦላሳ ስድስት ሰዓቶች በጥሩ እንቅስቃሴ ያለማቋረጥ ሲገፋን ቆየ፣ ማዕበሉም ፀጥ ከማለቱ ጎተነሣ መንገዱን የተጓዝነው ያላንዳች ድካም ነበር።

ኩራሶ

ጋልሶ የባሕር አሞራዎች፣ ጨለማ ስለነበር መጀመሪያ ጩኸታቸውን ብቻ ሰማን። ከዚያም አሞራዎቹ በጀልባዋ ላይ አንጎበጡ። አንድ አሞራ በምሰሶው ላይ ወርፋ፣ በረረችና እንደገና ተመልሳ መጣች። የፀሐይ ብርሃን አስኪታይ ድረስ በዘህ ሁኔታ ከሦስት ሰዓት በላይ ቆየን። ከአድማስ በኩል የመሬት ምልክት የሚያሳይ ምንም ነገር የለም። ታዲያ አሞራዎቹ ከወዴት መጥተው ይሆን? ሙሉ ቀን ስንመለከት ዋልን። የመሬት ምልክት የለም። በጣም ሞታት ከመሆኗ የተነሣ ዐይኖቹን ያሳመመችኝ ፀሐይ ስትጠልቅ፣ እንዲት ሙሉ ጨረቃ ብቅ አለች። ጥቁር መነጽሬን ጥየው ነበር። ወደ ጀልባዋ በገባው የማዕበል ውሃ ከመከላከያ ኪሶቻችን ጋር አብረው ተጠራርገው ሔደዋል። ከዚያም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አካባቢ በጨረቃዋ ብርሃን አማካይነት ከአድማሱ ባሻገር አንድ ቁጥር መስመር ለማየት ቻልን።

« መሬት መሆን አለበት!» አልኩ።

በእርግጥ አንድ ጥቁር መስመር እነደ ነበረና ያም መሬት መሆን እንዳለበት አጠቃላይ ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር። የተረፈውን ሌሊት ወደዚያው አቅጣጫ መጓዝ ቀጠልኩ። እየቀረብን ስንሔድ ቅርፁም ቀስ በቀስ ሾጣጣ እየሆነ መጣ። አሁን አንድ ኃይለኛ ነፋስ ከኋላ ስላገኘን በቀላሉ ገሥግሠን በፍጥነት ቀረብን። ገደሎች ይሁኑ ቋጥኞች ወይም አሸዋማ ጠረፍ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ጥቁር ቁልል ከውሃው ላይ ተከምሯል። ጨረቃዋ ከመሬቱ ወዲያ ራቅ ብላ በመጥለቅ ላይ ስለነበረች ለመለየት ችግር ፈጠረብኝ። ከዚያም እየቀረብን ስንሔድ በውሃው ዳር አልፎ አልፎ መብራቶች

t.me/OLDBOOKSPDF

አየሁ። እየቀረበን፣ አሁንም ከዚያ እየቀረበን መጣንና በማምት ከባሕሩ ዳር ግማሽ ማይል ሲቀረን መልህቅ ጣልኩ። ነፋሱ በጣም ቁጡ ከመሆኑ የተነሣ ማዕበሎቹ በሚያልፉበት ወቅት ጀልባዋን በማንባሯ ሊተክሏት እየተቃረቡ ትሽከረከር ነበር። የማያቋርጠው ንቅናቄ ትዕግሥት አስጨራሽ ሆነ። ምንም እንኳ የማይስማማ አቅጣጫ ቢሆንም፣ ምናልባት አስኪነጋ ድረስ እዚህ በሰላም እንቆይ በማለት የነፋስ ሽራዎቹን አውርደን ጠቀለልናቸው። ግን መልህቁ ከቆነጠጠበት ለቀቀ። ጀልባዋን እንደ ሁኔታው አቅጣጫ ለማስያዝ መንቀሳቀስ ነበረብን። የአቅጣጫ ማስተካከያውንና ባለሦስት ማዕዘኑን ሸራ ስንሰቅል ድንገት መልህቁም ቆነጠጠ። ጓደኞቹ ገመዱን ሲሰቡ ግን መልህቁ አመለጠን። የምችለውን ሁሉ አደረግኩ ግን ማዕበሎቹ ወደ ቋጥኞቹ በጣም ስላስጠጉን ዋናውን የነፋስ ሸራ ለመስቀልና ወደዚያው ለመሔድ ቆረጥኩ። ያደረግኩት መገለባበጥ በመልካም ሁኔታ በመሳካቱ ጀልባዋ በጠቅላላው ከጥቅም ውጭ ብትሆንም እኛ ከሁለት ቋጥኞች መካከል ተሠነቀርን። የሚቀጥለው ማዕበል ሲንከባለል ወደ ውሃው ውስጥ ተወርውረን ገባንና ብንቆስልም ሕይወታችንን አትርፈን እየተንከባለልን ወደ ዳር ወጣን። ከሎሲዎ ብቻ ከጀሶው ጋር ከባድ መቁሰል ደረሰበት። ከንዶቹ ፊቱና እጆቹ ቆሳስለው በደም ተሸፈኑ። የቀረነውም እንደዚሁ በጎልበቶቻችን በእጆቻችንና በቁርጭምጭሚቶቻችን ላይ ትንሽ መጋጋጥ ደረሰብን። ከአንድ ቋጥኝ ጋር ተላትሜ እኔም እንደኛው ጀሮዬ ደማ።

ዋናው ቁም ነገር ማዕበሉ ሳይደርስብን መሬት ረግጠን በሕይወት መገኘታችን ነበር። ፀሐይ ስትወጣ አንዱን የመርከበኛ ጃኬት ሲንሳፈፍ አገኘነው። እኔም መሰባበር ወደ ጀመረችው ጀልባ ተመለስኩ። ኮምፓሱ ከኋላ መቀመጫ ሥር ወድቆ ነበርና አነሣሁት። በየትም አካባቢ የሕይወት ምልክት አይታይም። መብራቶች አይተንበት የነበረውን ቦታ ፈልገን እንደ ተረዳነው። ያ አካባቢ አደገኛ መሆኑን ለዓሣ አጥማጆች ለማሰጠንቀቅ ነበር። በየብስ ጉዞ ቀጠልን። ምንም ነገር የለም። ትላልቅ ቁልቋሎችና አሀዮች ብቻ። ወደ አንድ የውሃ ጉድጓድ ደረስን። እጆቻችንን እንደ መቀመጫ አቆላልፈን ከሎሲዎን ለሁለት ለሁለት በተራ ስንሸከም ስለነበር ደክሞናል። የአሀዮችና የፍየሎች አጥንት በጉድጓድ አካባቢ ተበታትኖ ወድቋል። ጉድጓዱ ደርቆ ስለነበረ ቀደም ሲል ውሃ ለማውጫ ያገለግል የነበረው የነፋስ ሽክርክሪት (ዊንድ ሚል) አሁን በዘፈቀደ አየር እየቀዘፈ ብቻውን ይዞራል።

የተከፈተችው መዝጊያዋ ግቡልኝ እያለች የምትጋብዝ ከምትመስል እንዲት ትንሽ ጎጆ እስከንደርስ ድረስ ጉዞ ቀጠልን። « ቤቶች» ብለን ተጣራን። መልስ የለም። ከምድጃው አካባቢ አንዲት የጨርቅ ከረጢት በገመድ ተንጠልጥላለች። አወረድኩና አፏ የተሸበበበትን ገመድ ስበጥስ ሙሉዋን የዳች ፎሎሪን (ፖንዘብ) ታጭቆባት አገኘሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀኒየር፣ ኩራሶ፣ ወይስ እሩባ እንሆን? የያዘችውን አንድም ሳንነካ ከረጢቷን ወደ ቦታዋ መለስን። ውሃ አገኘንና ሁሉም ሰው በየተራ በአንድ ጭልፋ ጠጣን። አንድም ሰው እቤት የለም ማንም ሰው ከውጭ የለም፤ በከሎሲዎ ምክንያት ዝግ እያልን እንደገና ጉዞ ጀመርን። አንዲት አሮጌ ፎርድ መኪና በመንገዳችን ላይ ድንገት ድቅን አለችብን። መሪውን የያዘው አንድ ግዙፍ ሰው ነበር።

« ምንድን ናችሁ? ፈረንሣውያን ናችሁ?»

« አዎ ጌታዬ፣ ነን።»

« ተሣፈሩ።»

ከሎሲዎን ከኋላ መቀመጫ ሦስቱ ሰዎች ጭን ላይ አጋደምንና እኔ ከሾፌሩ ጎን ማቹሬ ከእኔ ቀጥሎ ተቀመጥን።

« ጀልባ የተሰባበረባችሁ ናችሁ?»

« አዎ።»

« ማንም የሰመጠ የለም?»

« የለም።»

« የመጣችሁት ከወዴት ነው?»

« ከትሪኒዳድ»

« ከዚያስ በፊት?»

« ከፈረንሣይ ጊያና።»

« ከባድ ወንጀለኞች ወይስ ልማደኛ ሌቦች?»

« ከባድ ወንጀለኞች።»

« ስሜ ዶክተር ናል ይባላል። የዚህች ሾጣጣ መሬት ባለቤት ነኝ። ከኩራሶ አሞጥሙጣ የወጣች ልሣነ ምድር ናት። የምትጠራው የአህያ ደሴት በመባል ነው። አህዮችና ፍየሎች የሚበሉት ቁልቋሉን ነው። በጣም ረጃጅም አሾሆች አሏቸው። እዚህ የሚኖሩት ሰዎች እሾሆቹን ‹የኩራሶ ኮረዳዎች› እያሉ ይጠሯቸዋል።

« እውነተኛዎቹን የኩራሶ ኮረዳዎች የሚያስደስት ቁልምጫ አይመስለኝም» አልኩ።

ሰውየው አፉ እስኪሰነጠቅ ሣቀ። ከዚያም ፎርዷ መኪና አስም እንዳለበት ሰው ተኩረፍርፋ በጉዞ ላይ እንዳለች ቀጥ አለች፤ ወደ ተከማቹት የአህያ መንጋዎች እያመለከትኩ « መኪናዋ እምቢ ብላ ከሆነ እነርሱን ልንጎትትባቸው እንችላለን» አልኩት።

« ኮፈኑ ውስጥ ገመድ አለኝ ግን ችግሩ እነርሱን ይዞ መለጎሙ ላይ ነው። እንደዚህ ቀላል አይደለም። ወፍራሙ ዶክተር የመኪናዋን ኮፈን ሲከፍት በታይለኛ ንቅናቄ የተበጠሰ አንድ ሽቦ አገኘ። የተለያየውን ሽቦ አገናኝና ወደ መኪናው ከመግባቱ በፊት

t.me/OLDBOOKSPDF

አካባቢውን በምሬት ተመለከተ። እንደገና ጉሠ ቀጠልንና ወጣ ገባ የሆኑ ብዙ መንገዶች ካለፍን በኋላ አንድ ኪላ አጠገብ ደረስን። ከኪላው ጎን እንዲት ትንሽ ነጭ ቤት አለች። እየደጋገመ « እቪ ጌታዬ ፣እቪ ጌታዬ» ማለት የማያቋርጥና በጣም ንጹሕ ልብስ የለበሰ ቆዳው ፈካ ያለ አንድ ጥቁር ሰው ጋር ዶከተሩ በሆላንድ ቋንቋ አወራ። ዶከተሩ ወደ እኛ ዘወር አለና « የሚጠጣ ነገር እንዲሰጣችሁና እኔ እስከመለስ አብሯችሁ እንዲቆይ ለዚህ ሰው ትእዛዝ ሰጥቸላችኋለሁ። ከመኪናው ለመውረድ ፈቃዳችሁ ቢሆን» አለ። ጥላ ሥር ካለ ሣር ላይ ተቀመጥን። ፎርዲም አንኮራፋችና መንገዲን ቀጠለች። ዶከተሩ ሃምላ ያርድ ያህል አልራቀም ነበር። ጥቁሩ ሰው በፓፒአሜንቶ ቋንቋ (እንግሊዝኛ፣ ሆላንድኛ፣ ፈረንሣዊኛና ስፓኝ የተቀላቀለበት የዳች አንቲይስ ቋንቋ ነበር።) ጌታው ዶክተር ናል እኛን ስለፈራ ወደፓሊስ ጣቢያ መሔዱንና እኛም ያመለጥን ሌቦች ስለሆንን ጠንቀቅ ብለህ ጠብቅ ብሎ ያስጠነቀቀው መሆኑን ነገረን። እንዲሁም ምስኪኑ ሰው ከዚህ የበለጠ እርዳታ ሊያደርግልን አልቻለም። ቀጠንጠን ያለ ቡና አፈላልን። ግን በጣም ማሩም ጣዕም ነበረው። ከአንድ ሰዓት በላይ ስንጠባበቅ እንደቆየን የጀርመን ዩኒፎርም መሳይ የለበሱ ስድስት ፖሊሶች በአንድ ትልቅ መኪናና በአንዲት ግልጽ አውቶሞቢል ዶክተር ናልና ሁለት ሰዎች ከኋላ ተቀምጠው ደረሱ።

ከአውቶሞቢሉ ወጡና ከሦስቱም መካከል ቦጣም አጭሩና ጸጉሩን በአጭሩ የተቆረጠ « የኩራሶ ደሴት የፀጥታ ክፍል ሹም ነኝ። የመጣሁትም እናንተን ሰማሠር ነው። ከደረሳችሁ ጀምሮ የፈጸማችሁት ወንጀል አለ? ከሆነስ ምን ነበር? የፈጸመውስ ከእናንተ ውስጥ የትኛው ነው?» አለ።

« ጌታዬ እኛ ያመለጥን እሥረኞች ነን። የመጣነውም ከትሪኒዳድ ሲሆን፣ በቋጥኞች ላይ ጀልባችን የተከሰከሰችው ከትንሽ ሰዓት በፊት ነበር። የዚህች ትንሽ ቡድን ኃላፊ በመሆኔ አንዳችንም ብንሆን ቅንጣት ታክል ወንጀል አለመፈጸማችንን ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ።»

የፖሊሲ መኮንን ወደ ወፍራሙ ዶክተር ዘወር አለና በሆላንድ ቋንቋ አነጋገረው። በመነጋገር ላይ እያሉ አንድ ሌላ ሰው ብስክሌት እየጋለበ ደረሰ። መጀመሪያ ለዶክተር ናል ከዚያም ለመኮንኑ እየሮጠና እየቸኮለ ተናገረ።

« ዶክተር ናል ሌቦች ናቸው ብለህ ለዚህ ሰው ለምን ነገርከብን?» ስል ጠየቅኩት።

« ምክንያቱም እናንተን ከማግኘቴ በፊት አሽከሬ እንደዚህ ብሎ ነግሮኛል። አንድ ቁልቋል ጀርባ ቆሞ ወደ ቤቱ ስትገቡ ተመልክቷችኋል። የእኔ አረኛ ስለሆነ አህዮቹን ይጠብቃል።»

« ወደ ቤቱ ውስጥ ስለገባን ሌቦች ነን? እንደዚህ ማለት ነውር ነው ጌታዬ። እቤቱ ትንሽ ውሃ ጠጥተናል። ይህ ዘረፋ ነው?»

t.me/OLDBOOKSPDF

« የከረጢቱ ፍለጋናችስ?»

« ከረጢቱን በእርግጥ ከፍቻለሁ። ስከፍተው እንኳ ሽምቀቅውን በጥሸዋለሁ። ግን ያደረግሁት ቢናር የገባንበት ሀገር ማን እንደሆነ ለማወቅ ያህል ገንዘቡን ብቻ ተመልከቼ ነበር። ከዚያም ከረጢቱን መልሼ አግኝቸበት ከነበረበት ቦታ ምድሯው በላይ ስቅያለሁ።»

መኮንኑ ዐይኔን ትኩር ብሎ ተመለከተና በብስከሌት ወደ መጣው ሰው ቶሎ ዘወር በማለት ፍርጥም ብሎ አናገረው። ዶክተር ናል መናገር እንደ ጀመረ መኮንኑ ድርቅ ባለ ጀርመናዊ አስተያየት በዚህ ነገር ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደማይኖርበት አስታወቀው። በተጨማሪም ባለብስከሌቱ ሰው ወደ መኪና ውስጥ ገቡቶ ሾፌሩ ጎን እንዲቀመጥ አደረገና ከሁለት ፖሊሶች ጋር ራሱም ገብቶ ሔዱ። ናልና ሦስተኛው ሰው ከእኛ ጋር ቆዩ።

« ለማስረዳት ይፈቀድልኛል?» አለ ናል። « ገንዘቡ የተሰረቀበት መሆኑን የነገረኝ አሽከሬ ነው። መኮንኑ እናንተን ከመበርበሩ በፊት እርሱን የመረመረው ምናልባት ውሸቱን ይሆናል በሚል ጥርጣሬ ይሆናል። ንጹሕ ከሆናችሁ በእውነት አዝናለሁ ግን የእኔ ስሕተት አልነበረም።

ዐሥራ አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መኪናዋ ተመለሰችና መኮንኑ እንደዚህ አለ። « አንተ የተናገርከው እውነት ነበር። ሰውየው ውሸታም ነው። ለዚህም ዋጋውን ያገኛል።» ምስኪኑ ቅሌታም! በግልጹ ካሚዎን ላይ ተጫነና ሌሎቹ አምስት ከኋላ ገብተው እኔም ልከተላቸው ስል ነበር መኮንኑ ከኋላዬ ይዞ « እኔ መኪና ውስጥ ግባና ከሾፌሩ ጎን ተቀመጥ» ያለኝ። የፖሊሶቹን መኪና ቀድመን አለፍነውና ወዲያው ከአይታችን ጠፋ። በጥሩ ሁኔታ በተነጠፉ መንገዶች ላይ ስንጓዝ ቆይተን በመጨረሻ ወደ ከተማ ደረስን። ቤቶቹ የተሠሩት እንደ ሆላንዶች ቤት አሠራር ነው። ማንኛውም ነገር በጣም ጽዳት ያለውና፣ ሰውም ከሞላ ጉደል በቢስከሌት ነበር የሚጓዘው። በየአካባቢው በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ይጋልባሉ። ወደ ፖሊስ ጣቢያው አመራን። ከዚያም ነጫጭ ልብስ የለበሱ ብዙ ፖሊሶች የተቀመጡበትን አንድ ሰፊ ከፍል አቋርጠን፣ የአየር ማቀዝቀዣ መሣሪያ ካለበት አንድ ቢሮ ውስጥ ገባን። በጣም ይቀዘቅዝ ነበር። ዕድሜው ዐርባ ዓመት የሚጠጋ ግዙፍና ፍርጥም ያለ፣ ለስላሳ ጸጉር ያለው አንድ ሰው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ተቀምጧል። እንዳየንም ብድግ አለና ከመኮንኑ ጋር በሆላንድ ቋንቋ ተነጋገሩ።

ውይይታቸው ሲያበቃ መኮንኑ ለእኔ በፈረንሣዊኛ « የኮራሶን ዋና ፖሊስ አዛዥ ላስተዋውቅህ?» አለና ከዚያም ወደ ፖሊሱ አዛዥ ዘወር ብሎ « ጌታዬ ይህ ሰው ፈረንሣዊ ሲሆን፣ አሁን ያሰርናቸው የስድስቱ ሰዎች ተጠሪ ነው» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

« በእኛ ግዛት ጅልባ የተሰባበረባችሁ ሰዎች እንደ መሆናችሁ ሁሉ ወደ ኩራሶ አንኳን ደህና መጣችሁ። ማን ነው ስምህ?»

« ሔንሪ» ነው። ግን ብዙውን ጊዜ ሰው ፓፒዮ ኢያለ ነው የሚጠራኝ»

« ሔንሪ የከረጢቷ ገንዘብ ጉዳይ ከአወዛጋቢ ችግር ውስጥ ከቶህ እንደነበረ እሙን ነው ፣ ግን ሐቀኛ መሆንህ ጨዋነትህን አስመስክሮልሃል። ማረፍ እንድትችል አንድ ከፍል ከአንዲት ድንክ አልጋ ጋር አሰጥሃለሁ። ጉዳይህ ወደ አገረ ገርው ይቀርብና ምን መደረግ እንዳለበት ራሳቸው ይወስናሉ። ይህ መኮንንና እኔ ሆነን ስለአንተ እንነጋገርልሃለን።»

እጁን ዘረጋልኝና ተጨባበጠን ወጣሁ። በግቢው ውስጥ ዶክተር ናል ይቅርታ ጠይቆን ስለ እኛ ጉዳይ የሚተባበረን መሆኑንም ቃል ገባልን። ከሁለት ሰዓት በኋላ ደርዘን የሚሆኑ አልጋዎችና በመካከሉ አንድ የእንጨት ጠረጴዛና ከሳንና ጎኑ አግዳሚ ወንበሮች የሚገኙበት አንድ ሰፊ ከፍል ውስጥ ተቆለፈ።

በመስኮቱ ቋሚ ፍርግርግ አንድ ፖሊስ በትሪኒዳድ ዶላራችን ትምባሆ የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀቶችና ከበሪት እንዲገዛልን ጠየቅነው፤ ሊገባን ያልቻለ፤ የሆነ ሐሳብ በመሰንዘር ገንዘቡን አልተቀበለንም።

የረጅም ጊዜ ቅይታ ነበር። « ያ የመጨረሻ አፈ ጮያሚ ሰው ምንም እርዳታ አያደርግልንም»? አለ ከሎሲዎ። « የት አለ ትምባሆችን?»

መገጊያውን መቆርቆር ሰጀምር ወዲያው ተከፈተ። ማንኑቱ እንዲያላስት በደረቱ ላይ መለያ ቁጥር የተጻፈበት የአሥረኛ ቡላ ዩኒፎርም የለበሰ አንድ ኩሊ ከፊት ለፊት ቆሞ ነበር። « ገንዘብ፤ ሲጃራ» አለ።

« አይደለም ትምባሆ፤ የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀትና ከብሪት።» በትንሽ ደቂቃ ውስጥ ከእኛ መልዕክት ጋር በተጨማሪ አንድ ትልቅ ማንቆርቆሪያ ካካዎ ከነእንፋሎቱ ይዘልን መጣ።

ከሰዓት በኋላ ወደ ዋናው ፖሊስ አዛዥ ቢሮ እንደገና ተጠርቼ ነበር።

« በወህኒ ቤቱ ግቢ ውስጥ መዘዋወር እንዲፈቀድላችሁ አገረ ገርው ትእዛዝ ሰጥተዋል፤ ጓደኞችህ እናመልጣለን ብለው እንዳይሞክሩ ንገራቸው። አለበለዚያ መዘዙ ለሁላችሁም ከባድ ይሆናል። የቡድኑ መሪ እንደ መሆንህ በየጊዜው ሺት ከሁለት ሰዓት አስከ ሰድስት ሰዓት ከሰዓት በኋላ ደግሞ ከዘጠኝ ሰዓት አስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት ወደ ከተማ መሔድ ትችላለህ። ገንዘብ አለህ?»

« አዎ የእንግሊዝና የፈረንሣይ።»

« ለመሔድ በምትፈልግበት የትኛውም ቦታ አንድ የፖሊስ ኑጭ ለባሽ ያጅብሃል።»

t.me/OLDBOOKSPDF

« ስለ እኛ ጉዳይ ምን ልታደርጉ ነው?»

« እንደሚመስለኝ በልዩ ልዩ ሀገሮች ነዳጅ ጫኝ መርከቦች ላይ ለያይተን ልናሣፍራችሁ እንሞክራለን። ኩራሶ ከቬኔዙዌላ ድፍድፍ ዘይት እያመጣች የምታጣራበት በዓለም ከታወቁት የነዳጅ ማጣሪያዎች እንደኛዋ ናት። በዓመቱ ውስጥ በቀን ከሐያ እስከ ሐያ አምስት ነጃጅ ጫኝ መርከቦች ሲገቡና ሲወጡ ይውላሉ። ያላችሁ አማራጭ ይኸው ይሆናል፣ ስለሆነም ያለ አንድ ችግር ወደ ማንኛውም ሀገር ልትገቡ ትችላላችሁ።»

« ወዴት ማለትዎ ነው? ላቲን አሜሪካ? ሰሜን አሜሪካ? በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር ወደሚገኙ ሀገሮች?»

« አይደለም። እነርሱ ከጥያቄ ውጭ ናቸው። አውሮፓም እንደዚሁ አይቻልም። ግን አትሥጉ። እመኑን። ወደ አንድ አዲስ ኑሮ እንድትንጠላጠሉ መርዳት እንፈልጋለን።»

« አመሰግናለሁ ጌታዬ!»

ይህን በሙሉ ለጓደኞቼ በትክክል አሰረዳሁ።

ከቡድናችን ውስጥ ተጠራጣሪው ከሎሲዎ « የእንተስ አስተሳሰብ ምንድን ነው ፓፒዮ?» አለ።

« ገና አላወቅኩም። ማምለጥ እንዳንሞክር እኛን ለመግታት ማለዘቢያ የሚሆን ማታለያ ዘዴ ነው ብየ ፈርቻለሁ።»

« ልክ ነህ እኔም ፈርቻለሁ።»

ይሁንና ብሪቶኑ ዕትዱ የሚደነቅ መሆኑን ገመተ።

« ከእንግዲህ ጀልባ የለም፣ ከእንግዲህ አስቸጋሪ ጉዞ የለም። እያንዳንዳችን በአንድ ነዳጅ ጫኝ መርከብ ሆነን አንዱ ሀገር ወይም ሌላው እንደርስና በግልጽ ሙበት አግኝተን ወደ አንዱ ገጠር ውስጥ መጥፋት ነው» ሲል ለሩ ስምምነቱን ገለጸ።

« አንተስ ምን ይመስልሃል ማቹሬ?»

ይህ የዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ወጣት፣ ይህ ከአንዲት ሴት ይበልጥ ፊቱ የለሰለሰና ሳያስበው ወደ አሥረኛነት የተለወጠ ጉብል በለዘበ ድምፁ « እነዚያ ዓሣማዎች የሐሰት የመታወቂያ ካርድ ያዘጋጁልናል ብለህ በዕርግጥ ታስባለህ? እኔ አላስብም። እንዲያውም ወደ አንድ ነዳጅ ጫኝ መርከብ ላይ ስንወጣላቸው ሐሳባቸውን ይለውጡ ይሆናል። ለዚህ ብቻ ብለው ነው። ይህን የሚያደርጉበት ብቸኛው ምክንያት ከእኛ ለመገላገል ነው። ቢያንስ የምገምተው ይህን ነው አላምናቸውም» አለ።

አንዳንድ ጊዜ ጧት ምስጢራዊ መልዕክቶችን ለማከናወን በጣም ለተወሰነ ወቅት አወጣለሁ። አሁን እዚህ አንድ ሳምንት ሆነን። ግን ምንም ነገር

t.me/OLDBOOKSPDF

አልተደረገልንም። እንበሳጭ ጀመር። አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ቄሶች በፖሊሶቹ ታጅበው ከከፍል ወደ ከፍል ሲዘዋወሩ ተመለከትን። በማስገደድ ዝሙት የፈጸመ አንድ ጥቁር ሰው ከታሠረበት አቅራቢያ የሚገኝ ከፍል ውስጥ ረጅም ጊዜ አጠፉ። በሚቀጥለው ወደኛ ይመጣሉ ብለን በመገመት ወደ ክፍላችን ገባንና በአልጋዎቻችን ላይ ተቀመጥን። ዕውነትም ሦስቱም፣ ማለት ዶክተር ናል፣ የፖሊሱ አዛዥና የባሕር ኃይል መኮንን የመሰለ በነጭና በወርቅ የተጠለፈ ዩኒፎርም ከለበሰ አንድ ሰው ጋር አብረው መጡ።

« በዕውነትዎ፡ እነዚህ ናቸው ፈረንሣውያኖቹ» አለና የፖሊሱ አዛዥ በማከታተል « ጠባያቸው ለሌሎች አርአያ መሆን የሚችል ነው» አለ።

« የምሥራች አላችኋለሁ ልጆቼ፣ በጠረጴዛው ዙሪያ እንቀመጥ፣ በዚህ ዓይነት ለመነጋገር ይመቸናል» አሉ።

ማንኛውም ሰው፣ ከአቡኑ ጋር የመጡትም ሰዎች ጭምር፣ በአግዳሚ ወንበሮቹ ላይ ተቀመጡ። አንድ ሰው አንዲት ዱካ ከውጭ ይዞ መጣና ጸጸሉ ሁሉንም ሰው ለማየት ከሚችሉበት ከጠረጴዛው አካባቢ አስቀመጠላቸው።

« አብዛኞቹ ፈረንሣውያን ካቶሊኮች ናቸው። ከእናንተ ውስጥ ካቶሊክ ያልሆነ አለ?» ሲሉ ማንም አጯን አላነሳም። ከዚህ ቀደም በጥበቃ ጣቢያ በሚያገለግል አንድ ቄስ እንደ ተጠመቅኩ አስታወስኩና አውንም ያው ካቶሊክ መሆኔን ለማብሠር አሰብኩ።

« ወዳጆቼ፣ እኔም የፈረንሣይ ተወላጅ ነኝ።ስሜ ኢሬኔ ደ ብሩያን ይባላል። ዝርያዎቹ የሁጌኖትስ ቤተሰቦች ሲሆኑ የካተሪን ዲሜዲቼ መንግስት ሕዝብን በሚጨፈጭፍበት ጊዜ ወደ ሆላንድ የተሰደዱ ነበሩ። ስለዚህ የፈረንሣውያን ደም አለኝ። ከካቶሊኮች ይልቅ ፕሮቴስታንቶች ይበልጥ የሚኖሩባት ግን ካቶሊኮቹ ዕምነታቸውን የሚያጠብቁባት ከተማ የኩራሶ አቡን ነኝ። እስኪ ሁኔታችሁን ንገሩኝ።»

« በነዳጅ ጫኝ መርከቦች ልንሣፈር እየተጠባበቅን ነው።»

« በዚህ ሁኔታ እናንተን የመሰሉ ስንት ሰዎች ከዚህ ሔደዋል?»

« ገና ማንም የለ።»

« አህ! ለዚህ ምን ትላለህ አዛዥ? ቋንቋውን አጣርተህ ስለምትናገር እባክህ በፈረንሣይኛ መልስልን።»

« በዕውነትዎ፣ አገረ ገርው በትክክል አምነውበት እነዚህን ሰዎች ረድተዋቸው ነበር። ግን ሐዘን መናገር ያለብኝ እስከሆነ ድረስ በተለይ ፓስፖርት ስለሌላቸው የማንኛውም መርከብ ካፒቴን አንድም አሥረኛ ለመውሰድ ፈቃደኛ አልሆነም።»

« እንግዲያ መጀመር የሚገባን ከዚያው ይሆናል። አገረ ገርው ልዩ ፓስፖርት ማውጣት አይችልም?»

t.me/OLDBOOKSPDF

« አላወቅኩም። ይህን ገና አልተወያየንም።»

ለትንሽ ጊዜ ፀጥታ ሆነ። ከዚያም አቡት « ከነገ ወዲያ ለእናንተ ፀሎት አደርግላችኋለሁ። ነገ ከሰዓት በኋላ ልትናዘዙ ትመጣላችሁ። ኑዛዜዎቻችሁን ራሴን በግል አሰማና አግዚአብሔር ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ አማፀንላችኋለሁ» አሉ። ወደ ፖሊሱ አዛዥ ዘወር ብለው « በዘጠኝ ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲያመጧቸው ትፈቅድላቸዋለህ?» አሉት።

« አዎ።»

« በግል መኪና ወይም በታክሲ እንዲያመጧቸው አፈልጋለሁ።»

« እኔ ራሴ አመጣቸዋለሁ፣ ብፁዕ አባታችን» አለ ዶክተር ናል፡

« አመሰግናለሁ የእኔ ልጅ። ልጆቼ ተስፋ ልሰጣችሁ የምችለው ምንም ነገር የለም። ከዚህች ወቅት ጀምሮ እናንተን ለመርዳት የተቻለኝን ጥረት ሁሉ አደርጋለሁ።» ዶክተር ናል ቃለበታቸውን ሲሰምና ብሪቶኑም እንደዚያው ሲያደርግ በማየት፣ እኛም እያንዳንዳችን ከንፈሮቻችንን ቀለበቷ ላይ አሳረፍንና በግቢው ውስጥ ቆማ ከነበረችው አውቶሞቢላቸው ድረስ ሸኘናቸው።

በሚቀጥለው ቀን ሁሉም ኃጢአቱን ለአቡት ተናዘዘ። እኔ የመጨረሻው ነበርኩ።

« የእኔ ልጅ ከፍተኛ ኃጢአትህ ምን ነበር?»

« አባቴ መጀመሪያውንም አልተጠመቅኩም ነበር። ግን ፈረንሣይ ውስጥ ወህኒ ቤት ሳለሁ፣ ተጠመቅክም አልተጠመቅክም ሁላችንም የአግዚአብሔር ልጆች ነን ብለው አንድ ቄስ ነግረውኛል።»

« ትክክል ነው። መልካም! ቀጥል።»

የሕይወት ታሪኬን በዝርዝር ገለጽኩ። እኅህ የቤተ ክርስቲያን አባት በዕርጋታ ለረጅም ጊዜ አዳመጡኝ። እጆቼን በእጆቻቸው ይዘው ጥልቅ በሆነ አስተያየት ተመለከቱኝ። ለመናዘዝ ከበድ ወደሚሉት ከፍሎች ስደርስ ቀላል ለማስመሰል ያህል ኢንገታቸውን ያቀረቅራሉ።

የእኅህ ዕድሜያቸው ስድሳ ዓመት የሆነ አረጋዊ ቄስ ዐይኖች ጥልቀትና ጥራት ሕፃን ልጅ አስመስለዋቸዋል። ወደር የሌለው ደግነታቸው ግርማ ሞገስ ከተጎናጸፈው አቋማቸውና ስልምልም ከሚሉት ግራጫ ዐይኖቻቸው አየመነጨ ልክ ቁስል እንደሚፈውስ ቅባት አራሰኝ። የሚናገሩን ረጋ ብለው ፣በጣም ረጋ ብለውና እጆቼን በእጃቸው ውስጥ አድርገው ነበር። « አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከልጆቹ ውስጥ አንዱን የሰዎች ሞካኒ እንዲፈታተነው ፈቃዱ ይሆናል። ይኸም ከመቼውም ለበለጠ ጠንካራና ጨዋ ሰውነት ለማብቃት ነው። ይታይህ የእኔ ልጅ ይህን የቀራንዮ ፈተና

t.me/OLDBOOKSPDF

ባትመጣ ራስሀን ከፍ በማድረግ እንደዚህ ወደ አግዚአብሔር በፍጹም ፅውነተኝነት ትቀርባለህ? በሌላ አጣለጽ ላስቀምጠውና፡- ሰምቼ፣ ሥርዓቱ፣ አንተን የፈጨህ ሞተርና ወንጅለው ያስቃዩህ አርከሰ ሰዎች ታላቅ አስተዋጽኦ በማድረግ ረድተውሃል። ከበፊቱ የላቀ አንድ አዲስ ሰው አድርገውሃል እና ዛሬ የከበርን፣ የደግነትን፣ የበጎ አድራጊነትን ምንነት ተረድተህ ችግርን ለመወጣት ምን ያህል ታይል እንደሚያስፈልግህና ከፍተኛ ፍላጐር መሆንህን ከተገነዘብክ ጠላቶችህ ባሰወለታህ ናቸው። ከተፈጸመብህ ግፍ አንጻር አነርሱን በብቀላ ለመቅጣት ያለህ ፈላጎ ከአሁት ሰብፅናህ ጋር አይጣጣምም። የተፈጸመብህ ግፍ ትክክል ነው ብለህ ብታምንም፣ ሰዎችን የምታተርፍ መሆን አለብህ እንጂ ከፋትን ለመፈጸም አትተር። አግዚአብሔር ለአንተ ቸር ነበር። ራስሀን አርዳና እኔም ረዳሃለሁ ብሎ ነግሮሃል። በብዙ መንገዶችም ረድቶሃል። ሌሎችን ሰዎች እንድታተርፍና ወደ ነፃነት አንድትመራቸው እንኳ አርሱ ፊቅዶልሃል። ግን ዋናው ቁም ነገር ጋጠአቶቹ ብዙ ናቸው ብለህ አታጋንናቸው። ከዚህ ይበልጥ የከፉ ወንጀለኞች ሆነው በዚፍተኛ ሥልጣን ላይ የተቀመጡ ብዙ ሰዎች ሞልተዋል። የሰውን ልጅ የፍትሕ አስተሳሰብ ከብደት ለመስጠት ስላሉታይሉ፣ አንተ አንዳደረግከው ሁኔ ከአርሷ በላይ ለመሆን የነበራቸው ፅድል አምልጧቸዋል።»

« አመሰግናለሁ አባቴ። ፈጽሞ የማልረሳው በጣም ቁም ነገር ያዘለ ምክር አካፍለውኛል» አልኩና እጃቸውን ሳምኩ።

« የእኔ ልጅ በቅርቡ ልትሐድ ስለሆነ አዲስ አደጋ ያጋጥምህ ይሆናል። ከመሐዴህ በፊት ላጠምቅህ አፈልጋለሁ። ምን ይመስልሃል?»

« አባቴ፣ ለአሁት እንደዚህ አንደ ሆንኩ ይተዉኝ። ወላጅ አባቴ ያለ ሃይማኖት አሳድጎኛል። ንጹሕ ልብ ነበረው። አናቴ ስትሞት፣ በሕይወቴ ውስጥ የእርሷን ቦታ ለመተካት አዲስ ታላትና አዲስ አስተሳሰቦች አስተዋወቀኝ። አሁን በራሴ ፈቃደኛነት ልጠመቅ ብል መከዳት ይሆናል። የተደላደለ ኑሮ ለመጀመር መ·ሉ በሙሉ ነፃ አስከሆን ድረስ ጊዜ ይስጠኝና፣ ከዚያም የአባቴን ፍልሰፍና በመተው ራሴው መጠመቅ አችል እንደሆን ፈታድኝነቱን በደብዳቤ አጠይቀዋለሁ።»

« ገባኝ የእኔ ልጅ፣ አርግጠኛ ነኝ፣ አግዚአብሔርም እንደዚሁ ያደርግልሃል። ባርከሃለሁ· አግዚአብሔር እንዲጠበቅህ አማፀንልሃለሁ።»

« አንግዲህ አሁን ምንድን ነው የምናደርገው?» ስል ዶክተር ናልን ጠየቅኩት።

« በሚቀጥለው ረቡረታ ከሚወጡት የኮንትሮባንዲስቶች ጀልባዎች የመጀመሪያ ምርጫ እንዲሰጠኝ አገረ ግርው ለገምሩክ እንዲነግሩልኝ ልጠይቃቸው ነው። ጥሩ ናት ብለኛቸው የምትፈልጓትን ለመምረጥ ከእኔ ጋር ትሔዳላችሁ። በተረፈ ተሪው የምጣባችሁና የስንቃችሁ ጉዳይ በጣም ቀላል ይሆናል።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ከአቡኑ ቃሰ-ቡራኬ በኋላ ብዙ ትብኒዎች ነበሩን። ማንኛውም ሰው እኛን ለማወቅ ፈለገ። አዘውትረው የሚመጡት ዐሥራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ሲሆን፣ የሚመለሱትም ምንም አስተያየት ሳይሰጡ አልጋዎቻችን ላይ ስጦታዎች ጥለውልን ነበር። ከሰዓት በኋላ ስምንት ሰዓት አካባቢ ፈትል ሲስተርስ አፍ ዙፍርኡ የተባሉ ደናግሎች ጥሩ ፊረንሚይኛ የምትናገረዋን አመምኔታቸውን እጅበው ይነበኑናል። አነርሱው የሚያበስሉትን ሁሉ በቅርጫት እየሞሉ ዘወትር ያመጡልናል። እናት መነኩሴዋ ወጣት ነበረች። ከዐርባ ዓመት በታች ትሆናለች አላለሁ። ጸጉሯ በነጭ ቆቡ ቢሸፈንም፣ ዐይኖቿ ሰማያዊና ሽፋሽፍቶቿም ለስላሳ ነበሩ። ዶክተር ናል እንደ ነገረን ትውልዷ ከታወቁ የሆላንድ ቤተሰቦች ሲሆን፣ እንደገና ወደ ባሕር ከሚሰድዱን ይልቅ ነፃ የምትሆንበት ሌላ አማራጭ ዘዴ ካለ አንድ መፍትሔ እንዲፈለግልን ወደ ሆላንድ ደብዳቤ ጽፋ ኖሯል። ጥሩ ጊዜ አንድ ላይ አሳልፈናል። የማምለጡን ታሪክ ሳወራላት መስማት ትወዳለች። አንድ ነገር ከረሳሁ ወይም አንድ ታሪክ ከዘለልኩ፣ ረጋ ብላ ወደ ርእሱ ትመልሰኛለች። « አትፍጠን እንጅ ሔንሪ፣ የአሞራውን ታሪክ ዘለልከውኮ፣ ዛሬ ጉንዳኖቹን ለምን ረሳሃቸው? ጉንዳኖቹ በጣም ጠቃሚ ናቸውኮ! ምክንያቱም አነርሱ ባይኖሩ በወቅራታሙ ብራቡን አትያዝም ነበር!»

እነዚህ ካሁን በፊት ከነበሩት ይበልጥ አስደናቂ ወቅቶች ሙሉ በሙሉ የተለዩ ነበሩና በፍጥነት እየደበዘዘ በሚሔደው ያለፈ ታሪካችን ላይ አንድ አዲስና ልዩ የሆነ ግለት ይጥሉበታል።

ጀልባዋን አየኋት። ግሩም ነበረች። ርዝመቷ ሐያ አምስት ጫማና አንድ ጥሩ ወለል፣ በጣም ረጅም ምሰሶና ሰፋፊ የነፋስ ሸራዎች አሏት። የጉምሩኩን ማኅተም ብዙት መዘርዘሩ አያሻም እንጅ በተረፈ በሚገባ የተሟላች ነበረች። ጨረታውን አንድ ሰው ስድስት ሺ ፍሎሪን (በአማካይ ግምት አንድ ሺ ዶላር) ከፈተ።

ዶክተር ናል፣ ወደ ሰውየው ጆሮ ትንሽ ቃላት ሹክ አለውና እኛ በስድስት ሺ አንድ ፍሎሪን ወሰድናት።

ከአምስት ቀን በኋላ ተዘጋጀን። ጀልባችን አዲስ ቀለም ተቀብታና የደለበ ስንቅ በጥንቃቄ ኣሟልታ፣ ለንጉሥ የምትገባ ሆናለች። ለእያንዳንዳችን አዲስ ልብሶች እንደያዙ ውሃ በማያረጥበው ጨርቅ ተጠቅልለው በዕቃ ማስቀመጫው ከፍል ስድስት ሻንጣዎች ተደርድረዋል።

የሪዮ ሐቻ ወህኒ ቤት

እንደነጋ ጉዞ ጀመርን። ዶክተሩና ደናግሎቹ ሸኙን። ወዲያው ነፋስ አጋጠመንና ከወደቡ በፍጥነት ተንቀሳቅሰን ራቅን። ፀሐይ ደማቅ ብርሃኗን ፈነጠቀችና

t.me/OLDBOOKSPDF

ምንም አዲስ ነገር ያልታየበት ቀን ቀጠለ። ለያዝናቸው የነፋስ ሽራዎች በቂ የሆነ የጀልባ ሚዛን መቆጣጠሪያ እንዳልነበረን ያኔውኑ አስታወስኩና ጥንቃቄ ለማድረግ ወሰንኩ። ጀልባዋ በሚገባ የተገራችና በጣም ፈጣን ነበረች። ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አመራሁ። ሦስቱን አዲስ ባልደረቦቻችንን ኮሎምቢያ ጠረፍ ልናወርዳቸው አሰበን ነበር። የረጅም ጉዞ ተካፋይ ሊሆኑን አልፈለጉም። በእኔ ላይ እምነት ነበራቸው። ግን የአየሩ ጠባይ አላስተማመነንም አሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ አውሎ ነፋስ ያለበት መጥፎ የአየር ጠባይ በጉዞ ላይ እንደሚገጥመን ከጋዜጦች ተረድተን ነበር።

ላጓጅራ ከምትባል ሰው ከማይኖርባት ብቸኛ ልሣነምድር አነርሱን ማውረድ አንዳለብን ሰምምነት ላይ ተደረሰ። ከዚያም እኛ ወደ አንግሊዝ ሆንዱራስ እንቀጥላለን። የአየሩ ጠባይ አስደሳች የሆነውን ቀን ተከትሎ የመጣው ኮከባዊ ሌሊት፣ በእንዲት ደማቅ ግማሽ ጨረቃ ደምቆ ነበር። በቀጥታ ወደ ኮሎምቢያ ጠረፍ አመራንና መልህቁን ጥለን አነርሱን ለማውረድና ሰላም መሆኑን ለማጣራት ዱካ አናዳምጥ ጀመር። ሆኖም ውሃው በጣም ጥልቅ ስለነበረ፣ ከአምስት ጫማ ከፍታ በላይ ያልሆነ ሌላ የውሃ አካባቢ ለመፈለግ አደገኛ ወደሆነው የቋጥኝ ጠረፍ በጥንቃቄ መቅረብ ነበረብን። እጆቻችንን ተጨባበጥንና አያንዳንዳቸው በሳን በኩል እየዘለሉ አግሮቻቸው መሬት እንደነኩ ሻንጣዎቻቸውን በራሳቸው ተሸክመው ወደ ደረቅ መሬት አያንበጫረቁ ሔዱ። አካሔዳቸውን በተመለከተና በመጠነኛ ትካዜ ስንመለከት ቆየን። ጓደኞቻችን መልካም ሥነ ምግባር አሳይተዋል ማንኛውንም መክራ ለመጋፈጥ ጥረዋል። መለየታቸው ያሳዝናል። ከዚያም በኋላ አነርሱ ወደ መሬት እንደተቃረቡ ነፋሱ በድንገት ፀጥ አለ። አርጉም ! ብቻ የፖሊስ ኃይል ካለባት የመጀመሪያዋ ወደብ ሪዮ ሐቻ አቅራቢያ አሰካለሆነ ድረስ ግድ የለም። በካርታው ላይ የሚታየውን ትንሽ የአደጋ ማስጠንቀቂያ መብራት አልፌ ስለነበር፣ በዚያ ማምት የፖሊስ ጣቢያውንም አለፈነው መጥተን ይሆናል ብየ አሰብኩ።

ጠበቅን፣ አሁንም ጠበቅን አሻቸውን አውለብልበው ደህና ሁኑ ካሉን በኋላ፣ ሦስቱም ሰዎች ለዐይን ጠፍተውናል። የነፋስ ያለህ! ሰለ እግዚአብሔር ብለህ ንፈስ! መውጫው ከማይታወቅበት የኮለምቢያ ጠረፍ ለማምለጥ ነፋስ አስፈልጎናል። ያመለጡ እሥረኞች ምን እንደሚደረጉ የምናውቀው ነገር አልነበረም። በመጨረሻ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ነፋስ ተነሣ። የነፋስ ሽራዎቹን በሙሉ ሰቀልኩና ፍጥነት ጨምሬ ሁለት ሰዓት ያህል በጥሩ ሁኔታ ቀዘፍን። ከዚያም ድንገት በአንድ የሞተር ጀልባ የታጨቁ ሰዎች አኛን ለማቆም በላያችን ላይ እየተከሱ ወደ እኛ አቅጣጫ በቁጥታ መጡ። ከውሃ ወሰን ከለላቸው ባሻገር ዓለም አቀፍ ባሕር ለመድረስ በመሞከር እንዳልሰማሁ መስዬ ጀልባዋን አሮጥኩ። ዕድል ከዳን። ኃይለኛው ባለሞተር ጀልባ ደረሰብንና ዐሥር ሰዎች

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠመንጃቸውን ሲወድሩብን እጃችንን ሰጠን።

ወታደሮች ይሁኑ ፖሊሶች የማያስታውቅ በጣም ልዩ የሆነ ዩኒፎርም ለብሰው ነበር። ሱሪዎቻቸው የቁሸቱና ፍዱም ታጥበው የማያውቁ በየቦታው የተነዳደሉ የሱፍ ሹራቦች ያጠለቁ ነበሩ። ንጽሕናው በመጠኑ ሻል ያለ ልብስ ከለበሰው « አዛኖቹው» በስተቀር በባዶ እግራቸው ነበሩ። ልብሶቻቸው ጎስቋላ ቢያስመስሏቸውም አስከ አፍንጫቸው ታጥቀዋል። እያንዳንዳቸው ጥይት የሞላበት ዝናርና ትልቅ ሆንጃ ሰገባ ውስጥ ይዘው ነበር። « አዛኖቹው» ከልስ ብጤና ጨካኝ ነፍሰ ገዳይ ይመስላል። ጥይት ከሞላበት ዝናሩ ላይ አንድ ሽጥ አንጠልጥሏል። የሚነጋገሩት በስፓኝ ቋንቋ እስከሆነ ድረስ ምን እንደሚሉ አይገባንም። ግን አገላለጻቸው፣ አስተያየታቸውና ድምፃቸው የጥላቻ ነበር።

ከወደቡ ወደ ወህኒ ቤቱ የተወሰድነው አውነትም ሪዮ ሐቾ በተባለችው መንደር ውስጥ አቋርጠን ነበር። ስድስቱ ነፍሰ ጉዳዮች ከጎንና ጎናችን፣ ሊሎች ሦስት ተጨማሪ ከኋላ ጠመንጃዎቻቸውን በቀጥታ እኛ ላይ እንዳነጣጠሩብን ነበር።

በአጭር የግንብ አጥር ከተከበበ አንድ ወህኒ ቤት ግቢ ደረስን። ሐያ የሚሆኑ ነጽሕና የጎደላቸውና ጺማቸውን ያጎፈሩ እሥረኞች ቆመው ወይም ዙሪያውን ተቀምጠው በአንድ ዓይነት የጥላቻ ስሜት ይመለከቱናል። « ቮሞስ ቮሞስ» ነበር ዘበኞቻቸው የሚሉት። « ፈጠን ብላችሁ ሒዱ» ማለታቸው እንደሆነ ገባን። ይሁንና ምንም እንኳ ከሎሲዎ በማጠም ላይ ቢሆንም፣ ገና ከነጀሶው ስላለ እንደዚህ ቀላል አልሆነለትም። ዘግይቶ የነበረው « አሳሾር»። ኮምፓሳችንንና የመርከበኛ ጃኬታችንን በከንዱ ይዞ፣ ከኋላችን ተከትሎ መጣ ብስኩቶችንንና ቸኮላታችንን ይበላ ስለነበር፣ ሰንታችንን በሙሉ መጥጥ እንዳደረገው ወዲያውኑ ተገነዘብን። አልተሳሳትንም ነበር። በከባድ የብረት ፍርግርግ የተጋረደ አንድ መስኮት ካለው ቆሻሻ ክፍል ውስጥ ቆለፈብን። በወለሉ ላይ አልጋዎች ተበለው ጣውላዎችና የአንጨት ትራሶች ነበሩ። ወዲያው ፖሊሶቹ እንደሐዱ በመስኮታችን በኩል አንድ እሥረኛ « ፈረንሣዮች፣ ፈረንሣዮች» አለ።

« ምን ትፈልጋለህ?»

« ፈረንሣዮች፣ ጥሩ አይደለም፣ ጥሩ አይደለም!»

« ምኑ ነው ጥሩ ያልሆነው?»

« ፖሊስ።»

« ፖሊስ?»

« አዎ ፖሊስ ጥሩ አይደለም።» ከዚያም ጥሎ ሐደ። ምሽት መጣ። ከፍተ ብርሃን የሚያገኘው ከአንዲት አነስተኛ አምፑል ብቻ ነበር። ቢንቢዎች በጆሯችን

t.me/OLDBOOKSPDF

በእፍንጫችን አካባቢ ይሮሃሉ።

« የሚገርም ነው! እነዚያን ሰዎች ጠረፍ እናወርዳለን ብለን ፍዳችንን ልንከፍል ነው።»

« እንዴት እንወቅ! ምክንያቱም ነፋስ አልነበረም።»

« በጣም ወደ ዳር ዘልቀህ ገብተህ ነበር» አለ ከሎሲዎ።

« በቃ እንግዲህ። እኛንም ሆነ ማንንም ሰው የምንወቅሰበት ወቅቱ አሁን አይደለም። ከዚህ በፊት ፍጹም ካደረግነው ይበልጥ አንዱ ላይ ተረባርበን አርስ በርሳችን በመረዳዳት ችግሩን መወጣት አለብን።»

« አዝናለሁ ፓፒ፣ ልክ ነህ። የማንም ሰው ስሕተት አልነበረም።»

እህ ያን ያህል በከፍተኛ ደረጃ ታግለን፣ በመጨረሻ ማምለጣችን በዚህ ሁኔታ ሊያከትም በጣም ያሳዝናል። ሆኖም አልበረበሩንም ነበር። የገንዘብ መደበቂያ ቱቦየ በኪሴ ውስጥ ስለነበረች፣ ወደ ታቢው ቦታዋ ለማስቀመጥ ጊዜ አላባከንኩም። ከሎሲዎም እንደዚሁ አደረገ። እነርሱን በመያዛችን አሁንም ዕድለኞች ነን። በእኔ ሰዓት አቆጣጠር ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆነ። በጨው ውሃ ተበከተው የተጋገሩ ሦስት ዓይነት የሩዝ ቂጣዎችና ቡጢ የሚያካክሉ የጥቁር ስኳር ጭበጠዎች አመጡልን። « ቦናስ ናቼስ» ሲለ « ደህና እደሩ» ማለት መሆን አለበት አለ ማቹሬ። በሚቀጥለው ቀን ጧት በግቢው ውስጥ ግሩም የሆነ ቡና በእንጨት ኩባያ ሰጡን። ሁለት ሰዓት አካባቢ የፖሊሱ አዛዥ መጣ። ጓዞችንን ለመሰብሰብ ወደ ጀልባዋ መሐድ አችል እንደሆነ ጠየቅኩት። ወይ አልተረዳኝም፤ አለበለዚያ ያልሰማ ለማስመሰል ፈልጓል። አስቀያሚ ፊቱን ባስተዋልኩ መጠን አርሱን መውደዴም እየቀነሰ መጣ። በግራ ሽንጡ በኩል በአንድ ቆዳ ቦርሳ ውስጥ የተቀመጠች አንዲት ትንሽ ጠርሙስ አንጠልጥሏል። አውጥቶ ቡሿን በመክፈት አንድ ጊዜ ተንነጨና ጨቅ ብሎ ጠርሙሷን ወደ እኔ አቀበለኝ። ይህም የመጀመሪያው የወዳጅነት አከብሮት መግለጫ በመሆኑ ተቀበልኩና ጠጣሁ። ነገሯ ጥሩ ነበረች ግን ብዙ አልጠጣሁላትም። ምላስ የሚያቃጥል የአንጨት አልኮል ጣዕም ነበረው። ቶሎ ጭልጥ ሳደርገው ማንጠስ ጀመርኩ። ይህም ከልሱን ሕንዳዊ አስኪፈነዳ አሳቀው።

አራት ሰዓት ላይ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሲቪሎች በቡድን ሆነው መጡ። ስድስት ወይም ሰባት ያህል ነበሩ። የወህኒ ቤቱ የአስተዳደር ሕንፃ ወደሚመስለው አቅጣጫ አመሩና ተጠራን። በብዙ ሲሻኞች ከተሸቆጠቆጠ አንድ መኮንን ፎቶግራፍ በታች ግማሽ ክብ ሠርተው ተቀምጠዋል። ፎቶግራፉ የኮሎምቢያው ፕሬዚዳንት የአለፎንሶ ሎፔዝ ነበረ። ከመኳንንቶቹ አንደኛው ከሎሲዎን እንዲቀመጥ ነገረው። ሌሎቻችን እንደ ቁምነ ቁየን። ከመካከል የተቀመጠው ቀጭን ሰው መነጽሩን የጭሉሌ

t.me/OLDBOOKSPDF

መንቆር በመሰለው አፍንጫው ላይ አስቀምጦ ጥያቄውን ጀመረ።

ትሩጁማኑ በማስተርጎም ፋንታ እንደዚህ አለ።

« እኝህ አሁን የሚናገሩትና ምርመራውንም የሚያካሒዱት ሰው የሪዮ ሐቻ ከተማ ዳኛ ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ የታወቁ የከተማው ነዋሪዎችና ጓደኞቻቸው ናቸው። እኔ ዜግነቴ ሔይቲያዊ ሆኖ፣ ለዚህ መሥሪያ ቤት የኤሌክትሪክ ሥራዎች ኃላፊ ነኝ። እንደ አስተርጓሚም አገለግላለሁ። ከእነዚህ ሰዎች አንዳንዶቹ በመጠኑ ፈረንሣይኛ ይገባቸዋል። ምናልባት ዳኛውም ጭምር። ግን እንዲታወቅባቸው አይፈልጉም።»

ይህ የማስታወቂያ መግቢያ ዳኛውን ጤና ነሣው። በመካከል አቋረጠውና ሔይቲያዊው እየተረሳመ ጥያቄውን ቀጠለ።

« ፈረንሣውያን ናችሁ?»

« አዎ!»

« ከወዴት ነው የመጣችሁት?»

« ከኩራሶ።»

« ከዚያስ በፊት?»

« ትሪኒዳድ።»

« ከዚያስ በፊት?»

« ማርቲኒክ።»

« ይኸ ውሸት ነው። ኩራሶ ያለው ቆንሲላችን ከአንድ ሳምንት በፊት ከፈረንሣይ ጠባይ ማረሚያ ያመለጡ ስድስት እሥረኞች በእኛ ሀገር መሬት ላይ ለማረፍ ይሞክራሉ ብሎ አስጠንቅቆናል።»

« እሺ እንግዲያው ከጠባይ ማረ ያው ያመለጥን ነን።»

« ከሀገር ሀገር ተዘዋዋሪ ናችኋ!»

« አዎ።»

« ፈረንሣይን የመሰለች አንዲት ጨዋ ሀገር ወደዚህ ሩቅ ቦታ ልካ ይህን የመሰለ ያልተመጣጠነ ቅጣት እንዲፈጸምባቸው ተገቢ ሆኖ ያገኘችበት ምክንያት በጣም አደገኛ ወንበዴዎች ብትሆኑ ነው።»

« ምናልባት።»

« ሌቦች ናችሁ ነፍሰ ገዳዮች?»

« ነፍሰ ገዳዮች።»

« ያው ነው። ስለዚህ ቀንደኛ ወንጀለኞች ናችኋ? ሌሎቹ ሦስቱስ ወዴት ናቸው?»

« ኩራሶ ቀርተዋል።»

t.me/OLDBOOKSPDF

« ይኸ ደግሞ ሌላ ውሸት ነው። ከዚህ ሠላሳ አምስት ማይል የምትሆን ካስቲሌቴ ከተባለች ቦታ አውርዳችኋቸዋል። ምን ይሆናል! እነርሱም ስለተያዙ በትንሽ ሰዓት ውስጥ እዚህ ይደርሳሉ። ጀልባችሁን ሰርቃችኋት ነው?»

« አይደለም። ሰጠታ ነች - ከኩራሶ አቡን።»

« በጣም ጥሩ። ስለ እናንተ ምን ማድረግ እንደሚቻል አገረ ገዢው እስኪወስኑ ድረስ እንደ እሥረኛ ሆናችሁ እዚሁ ትቆያላችሁ። ሦስታችሁ ግብረ አበሮች ኮሎምቢያ ማዛት በማረፍ ለፈጸማችሁት ጥፋትና ከዚያም በባሕር ለማምለጥ ላደረጋችሁት ሙከራ፣ አንተን የጀልባዋን ካፕቴን በሦስት ወር እሥራት ሌሎቹን ሁለቱን ደግሞ በአንድ ወር ቀጥቻለሁ። ፖሊሶቻችን እዳይገርፏችሁ ከፈለጋችሁ ጥሩ ሥነ ምግባር ብታሳዩ ይሻላል። ከባድ ሰዎች ናቸው። የምትናገሩት ሐሳብ አላችሁ?»

« የለም። የምፈልገው ቢኖር በጀልባዋ ውስጥ የተውነውን ስንቃችንና ሀብታችን እንዲሰጠኝ ብቻ ነው።»

« ለአያንዳንዳችሁ ሱሪ፣ ሸሚዝ፣ ጃኬትና ጫማ ሲቀር ማንኛውም ነገር በጉምሩክ ተወርሷል። ቁርጡ ይኸው ነው። ስለ ሁኔታው ምንጥ የምታደርጉት ነገር የለም። ሕግ ነው።»

ወደ ወህኒ ቤቱ ግቢ ተመለሰን። ጎስቋላዎቹ እሥረኞች ዳኛውን በመከበብ አስፍሰፈው « ዶክተር! ዶክተር!» ሲሉ በትልቅነት ስሜት ተውጥሮ አንድም ቃል ሳያናግራቸው እንደ ተሰበሰቡ ሸምጥጦ ሔደ። ነጫጭ የለበሱትም መኳንንቶች ከወህኒ ቤቱ ወጡና ተሰወሩ።

ሰባት ወይም ስምንት መሣሪያ ከታጠቁ ሰዎች ጋር ቦአንድ ካሚዮን ተጭነው የቀሩት ሦስቱ ጓደኞቻችን ሰባት ሰዓት ላይ ደረሱ። ሻንጣዎቻቸውን በራሳቸው ተሸከመው ኃፍረት እየተሰማቸው ወረዱ። ወደ ክፍላችን ተከትለናቸው ገባን።

« አድርግልን ስንል ያስገደድንህ ነገር በዕውነት የደደብ አድራጎት ነበር» አለ ብሪቶኑ። « በአርግጥ እናዝናለን ፓፒዮ። ከፈለግህ ልትገድለኝ ትችላለህ። ራሴን ልከላከል አልሞከርም። የሰው ልጅ ሥነ ምግባር አላሳየንም። ታዲያ፣ ከኮሎምቢያና ኮሎምቢያውያን አንጻር፣ የባሕሩ አደጋ ቀልድ ነበር። የያዟችሁ ነፋሱ በመጥፋቱ ምክንያት ነበር?»

« አዎ፣ ግን እኔ ማንንም ሰው የምገድል አይደለሁም። እዚህ ነገር ውስጥ የገባነው አብረን ነበር። እናንተን ለማውረድ እምቢ ልል እችል ነበር። እንደዚያም ቢሆን ኖሮ አንዱም ችግር ባልተፈጠረ።»

« በጣም ሲበዛ ግሩም ሰው ነህ ፓፒ!»

« አይደለም፣ ሐቁን ለማስገንዘብ እየሞከርኩ ነው።» ስለ ተካሔደብንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ምርመራ ነገርኳቸው። « ምናልባት አገረገርው በነፃ ይለቀን ይሆናል።»

« ደህና፣ እስኪ ለማንኛውም ተስፋ አናደርጋለን። 'ሕይወት ካለ ምኞት አለ' ተብሎ የለ!»

በዚህ አካባቢ የሚገኙት ባለሥልጣኖች የእኛን ጉዳይ ለመወሰን እንደማይችሉ አንድ ስሜት አድሮብኝ ነበር። ኮሎምቢያ ቆየን፣ ወደ ፈረንሣይም ተመለስን፣ ወይም ጀልባችንን መልሰው ሰጥተውን መንገዳችን መቀጠል ቻልን፣ ወሳኞቹ ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ይሆናሉ። እነዚህ ምንም ያላደረግናቸው ሰዎች በገዛ ራሳቸው ውሳኔ ማሳለፋቸው ከመጠን በላይ አሳፋሪ ይሆናል። ሌላው ቀርቶ ግዛታቸው ውስጥ ምንም ዓይነት ወንጀል አልፈጸምን።

አሁን እዚህ አንድ ሳምንት ሆነን። አንድ ሙቶ ሐያ ማይል ከምትርቅ ሣንታ ማርታ ወደ ተባለች ከፍተኛ ከተማ እንዛወር ይሆናል ከሚለው ወሬ በስተቀር ምንም አዲስ ነገር የለም። ዘበኞቻችን፣ ከአስቀያሚው የባሕር ወንበዴ ገጽታቸው እንደምንረዳው፣ ስለ እኛ ያላቸው አመለካከት አልተሻሻለም። ትላንት ገላ መታጠቢያው ከፍል ውስጥ የራሴን ሣሙና እንዲሰጠኝ፣ ከእነርሱ አንዱን ብጠይቀው ፣ በጠመንጃው ሰደፍ መታኝ ! ምንም እናኳ ማቹሬና ብሪቶኑ ከፍላችንን በየቀኑ ስለሚያጥቡት በመጠኑ የጸዳ ቢሆንም፣ አሁንም ገና በቢንቢ እንደ ተወረረ ነበር። ተስፋ በመቁረጥ በራስ መተማመኔም ይከዳኝ ጀመር። በራስ መተማመኔን ኮሎምቢያውያኑ ከላይ ከላዩ እየቆነጠሩብኝ ነበር። ከአሥረኞቻቸው አንዱ በሣንታ ማርታ የሚታተም አንድ አሮጌ ጋዜጣ አዋሰኝ። በመጀመሪያው ገፅ የስድስታችን ፎቶግራፍና ከታች በኩል ከግዙፉ ዘርፋፋ ባርኔጣውና ሲጃራው ጋር የፖሊሱ አዛዥ ከዚያም መሣሪያ የታጠቁ የደርዘን ፖሊሶች ፎቶግራፍ ነበር። የእኛን መያዝ እንደ ዓቢይ ጉዳይ እንደ ወሰዱት ግልጽ ነበር። የተጫወቱት ሚና ተጋንኖላቸዋል። የእኛ መታሠር መላው ኮሎምቢያን ከአስፈሪ ጥፋት እንዳተረፉት አስመስለውታል። ግን ለመናገር የምፈልገው የእኛ ወንበዴዎች የተባልነው ሰዎች ፎቶግራፍ ከፖሊሶቹ ፎቶግራፍ ይልቅ ይበልጥ የተሻለ ነበር። « ወንበዴዎቹ» የጨዋ ሰዎች አቋም ሲኖራቸው፣ የፖሊሶቹ ግን ይቅርታ አድርጉልኝና ከአዛኞቻቸው ጀምሮ ምን ልበላችሁ - ምናልባት ሐሜት ያስመስልብኝ ይሆናል . . .።

ምን ማድረግ ይኖርብናል? በስፓኝ ቋንቋ መጠነኛ ቃላት መረዳት ጀምሬ ነበር። ማምለጥ - « ፋ ጋር»፣ እሥረኛ - « ፕሬሶ»፣ መግደል - « ማታር»፣ ሰንሰለት - « ካዲና»፣ እግርብረት - « ኤስፓሳስ»፣ ሰው - « አምብሬ»፣ ሌት - « ሙገር»።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሪዮ ሐቻ ማምለጥ

ዘወትር በእጅ ካቴና የሚጠፈር አንድ ሰው በግቢው ውስጥ ነበረ። ከእርሱ ጋር ጓደኝነት መሠረትኩ። አንድ ሲጃራ ለሁለት እየተጋራን እናጨስ ነበር። ሲጃራው ረጅምና ቀጭን ሆኖ በጣም ጠንካራ ቢሆንም አጨሰዋለሁ። ከቬኔዙዌላና አሩባ ደሴት መካከል የኮንትሮባንድ ንግድ ሲያካሒድ እንደነበር ተረዳሁ። በጠረፉ ያሉ ጥቂት ዘበኞችን በመማደል ተከስሶ ፍርዱን እየተጠባበቀ ነበር። አንዳንድ ቀን በጣም የረጋ፤ በለላ ጊዜ ደግሞ ቁጡና ቅበጥብጥ ይሆናል። ዝምተኛ የሚሆነው አንድ የሚንበኘው ሰው ሲኖርና የሚያመጣለትን ቅጠሎች ሲያኝክ መሆኑን መገንዘብ ጀመርኩ። አንድ ቀን ግማሽ ቅጠል ሰጠኝና ጉዳዩን ተረዳሁ። ምላሴ፣ ትናጋዬና ከንፈሮቹ ደነዘዙ። ቅጠሎች ኮካ የተባሉ ነበሩ። ዕድሜው ሠላሳ አምስት ሆኖ ከንዶቹና ደረቱ በለስላሳና ጥቁር ጸጉሮች የተሸፈኑ፣ ፍርጥም ያለ ጠንካራ ነበር። እግሮቹ ከመቆርፈዳቸው የተነሳ ምንም ነገር ሳይሰማው በአንድ ጠርሙስ ወይም ምስማር ላይ ለመራመድ ይችላል።

« አንተና እኔ ሆነን 'ፋጋ' አልኩት አንድ ቀን ማታ (በሒይቲያዊው ጉብኝቶች በአንደኛው ወቅት የስፓኝና ፈረንሣይ መዝገበ ቃላት ጠይቄው አምጥቶልኝ ነበር።) ጓደኛዬ ገባውና ማምለጥ መፈለጉን በጥቅሻ አመለከተኝ። ግን የእጅ ካቴናዎቹን እንዴት እናደርጋለን? ለጠፍጣፋ መከረቻ ተስማሚ ቀዳዳ ያለው የአሜሪካውያን ካቴና ነበር። ከአንደኛው ጫፉ ጠፍጣፋ የሆነ ቆላፋ የብረት ሺቦ ብሪቶኑ ሠራልኝ። ከትንሽ ጊዜ ሙከራ በኋላ የጓደኛየን የእጅ ካቴና በምፈልግበት በማንኛውም ጊዜ ለመክፈት ቻልኩ። ሌሊት ሲሆን በጣም ወፍራም የሆነ የብረት ቋሚ ካለው አንድ ጨለማ ግንብ ቤት ውስጥ ይገባ ነበር። እኛ ከፍል ያሉት ብረቶች ቀጫጭን ስለነበሩ በቀላሉ እንደምቆለምማቸው እርግጠኛ ሆኛለሁ። ሆኖም በመጋዝ መቆረጥ የሚያስፈልገው አንድ ቋሚ ብቻ ይኖራል። - አንቶኒዎ (ስሙ « አንቶኒዎ ኮሎምቢያዊው» ነበር) « አንድ መጋዝ እንዴት እናገኛለን?»

« ገንዘብ።»

« ምን ያህል?»

« አንድ መቶ ፔሶ።»

« በዶላር ምንዛሬ ስንት ይሆናል?»

« ዐሥር።»

ስለዚህ በሰጠሁት አሥር ዶላር ሁለት የብረት መጋዞች ገዛ። በየጊዜው በትንሹ እየተገዘገዘ የብረቱን ጥቅሩቂ ከሩዛችን ትራፊዎች ጋር እንዲለውሰውና የተቆረጠውን ቦታ እንዲሞላው ግቢው ውስጥ ባለው አቧራ መሬት ላይ ምልክት እየሣልኩ አስረዳሁት። ልክ ተመልሰን ልንገባ ስንል የእጁን ካቴና ፈታሁለት። የሚፈተሽ ከሆነ ቁልፉ በገዛ ራሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚዘጋ ማድረግ ያለበት እርስ በርሳቸው ጫን ማለት ብቻ ነበር። ቋሚውን ብረት እስከ መጨረሻው ድረስ ለመቁረጥ ሦስት ሌሊት ወሰደበት። የተረፈችውን ለመቁረጥ ከአንድ ደቂቃ የበለጠ እንደማይፈጅበትና ቋሚውንም በእጅቹ ለማንበጥ እንደሚችል ነገረኝ። ከጨለማው ማንበ ሲወጣ ወደ እኔ ሊመጣ ነበር።

ሁልጊዜ ስለሚዘንም፣ የሚወጣው በመጀመሪያው የዝናም ሌሊት መሆኑን ንገረኝ። ጓዶቹ ምን አቅጂ እንደነበር ዐውቀዋል። ግን አንዳቸውም ከእኔ ጋር ለመሔድ አልፈለጉም። በጣም ሩቅ ወደሆነ ቦታ እንደምሔድ ንቢቷቸዋል። ለመድረስ የፈለግኩት ከቬኔዙዌላ ድንበር ቀጥላ ከምትገኝ የኮሎምቢያ ልሣነ ምድር የሆነች አንዲት ነጥብ ነበር። በካርታችን ላይ ይህች ቀበሌ ጓጅራ ተብላ ስትጠራ፣ ኮሎምቢያና ቬኔዙዌላ በይገባኛል ይከራከሩባታል። ኮሎምቢያዊው ጓደኛዬ የቀይ ሕንዳውያን መሬት ነች አለ። አንዳንድ ኮንትሮባንዲስቶች ብቻ ያውቋታል እንጅ የኮሎምቢያም ሆነ የቬኔዙዌላ ፖሊሶች አልነበሩባትም። አደገኛ ነበር። ምክንያቱም የጓጅራ ቀይ ሕንዳውያን ማንም የሠለጠነ ሰው በቀበሌያቸው ውስጥ እንዲኖር አይፈልጉም። ወደ መሐል ሀገር ሰርገህ ስትገባ አደገኛነቱም የዚያኑ ያህል ይጨምራል። ከካስቲሌቱ መንደርና ላቬላ ከምትባል አንዲት ትንሽ መንደር መካከል እያቋረጡ የሚያሸጋግሩ ጓላ ቀር የቀይ ሕንዳውያን ዓሣ አጥማጆች በጠረፉ አካባቢ ይገኛሉ። አንቶኒም ወደዚያ መሔድ አልፈለገም። በጀልባ ሙሉ የተጫነ የኮንትሮባንድ ዕቃቸውን ወደ ሕንዳዊያኑ ጠረፍ ለማድረስ ሲሞክሩ እርሱ ወይም ባልደረቦቹ ከእነዚህ ህንዶች እንዱን ለመግደል ሳይገደዱ አይቀሩም። እንቶኒም እስከ ጓጅራ አቅራቢያ እንደሚሸኘኝና ከዚያ ወዲያ ግን የምሔደው ብቻየን እንደሚሆን ተስማማን። የሚጠቀምባቸው ቃላት በጣም ብዙዎቹ በመዝገበ ቃላት መፍቻው ውስጥ ስላልነበሩ፤ መግባባት የቱን ያህል አድካሚ እንደነበር መገመት አይሳናችሁም።

ስለሆነም በዚያ ሌሊት ዶፍ የሆነ ዝናም ጣለ። በመስኮቱ ጥግ ተሰጥዬ ቆሜያለሁ። ቋሚዎቹን ለማሰፋት እንዲረዳን ከከፍሉ መለያ አንድ ጣውላ ገንጥለን ጥለናል። ከሁለት ሌሊት በፊት ምከረናቸው ቋሚዎቹ በቀላሉ የሚታጠፉ ሆነው አግኝተናቸዋል።

« ሊሰሩ፣ (ተዘጋጅቻለሁ)።»

በቋሚ ብረቶች መካከል የአንቶኒዎ ፊት ብቅ አለ። ከማቹሬና ብራቦኑ እርዳታ ጋር ቋሚዎቹን ለማንበጥ ብቻ ሳይሆን ነቅለን ለመጣል አንድ ጉተታ በቂ ሆነ። ከውስጥ በኩል ወደ ላይ ተሸክመው ሲገፉኝ ከመሔዴ በፊት ለመሰነባበቻ አንድ ጊዜ ከኋላዬ በጭጋ አቀመሱኝ። አሁን ግቢው ውስጥ አንገኛለን። ዶፍ ዝናም በቆርቆሮዎቹ ጣሪያ ላይ ሲወርድ ጩኸቱ እንደ ጉድ ነበር። አንቶኒዎ እጁን ያዘና ወደ ግንቡ መራኝ። ከጉታው ሰድስት ጫማ ብቻ ስለነበር፣ በዚያ ላይ መዝለል የልጅ ጨዋታ ነበር። በጫፉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ የተተከሉት ጠርሙሶች እጇን ቆረጡኝ። ግን ምንም አይደል። ምንም እንኳ ከፊት ለፊታቸን በዐሥር ጫማ ርቀት ለማየት ቢያዳግተንም፣ አስደናቂው ኮሎምቢያዊ የመሿለኪያ መንገዷን ለማግኘት ቻለ። በጫካውና በውሃው ዳር መካከል ያለውን መንገድ አስከናኝ ድረስ ከገፋው የተነሣ በቀጥታ በመንደሩ ውስጥ አቋርጠን ለማለፍ ቻልን። ዘግየት ብሎ አንድ መብራት አየንና ረጅም መንገድ በማሳበር ወደ ጫካው ውስጥ ገባን። ሆኖም ከዳር በኩል ገላጣ ነበር። ከዚያም መንገዳችንን እንደገና ያዝንና አስኪነጋ ድረስ ዝናም እየወረደብን ተጓዝን። በምንነሣበት ወቅት አንቶኒዎ አንድ የኮካ ቅጠል ሰጥቶኝ ስለነበር፣ በወሀኒ ቤቱ ሲያደርግ አይቸው እንደነበረው ዓይነት እኔም እኝከው ነበር። ሲነጋ ገና አልደከመኝም ነበር። ቅጠሉ ይሆን? እርግጠኛ ኖኝ እርሱ መሆን አለበት። እሁን ቀን ቢሆንም መጓዛችንን ቀጠልን። አንቶኒዎ አልፎ አልፎ ይጋደምና ጀርመን ውሃ ባረጠበው መሬት ላይ ይለጥፋል፣ ከዚያም እንደገና መገሥገሥ ይጀምራል።

አንድ አስደናቂ የአረማመድ ዘዴ ነበረው። መራመድም አይባል፣ መሮጥም አይባል። አንድ ዓይነት ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ተከታታይ አጫጭር ዝላዮች ሆነው፣ ከንዶቹን እየር የሚቀዝፍ በመምሰል ይጠቀምባቸዋል። በእንድ አጋጣሚ አንድ ነገር ሰምቶ ይመስለኛል ወደ ጫካ ውስጥ ጎተተኝ። ታዲያ ዕውነት ነበር፣ ጩጣ ገባውን መንገድ ለማስተካከል መዳመጫ የሚሰብ አንድ ትራክተር መጣ።

አሁን ከጧቱ አራት ሰዓት ተኩል ነበር። ዝናሙ አቆመና ፀሐይ ወጣች። በግምት ሲሶ ማይል በሣር ላይ ከተጓዝን በኋላ፣ እሾህ ከሞላበት ጥቅጥቅ ባለአንድ ጫካ ውስጥ ተጋደምን። ከአደጋ ርቀናል ብዬ አሰብ ነበር፣ አንቶኒዎ ግን ሲጃራ ለማጨስም ሆነ በሹክሹክታ ለመናገር እንኳ አልፈቀደልኝም። የቅጠሎቹን ጭማቂ መዋጡን አለሟረጠም፣ እኔም እንደርሱ አደርጋለሁ። ይሁንና በበኩሌ ብዛቱን በጣም ቀንሼ ነበር። ከሐያ የበለጡ ቅጠሎች ያለባትን ቦርሣውን አሳየኝና ደስ የሚሉ ጥርሶቹን በደብዛዛው ብርሃን ፈገግ አድርጎ በጸጥታ ሣቀ። ቢምቢዎቹን ለመከላከል አንድ ሲጃራ እንከና ፊቶቻችንን በምራቁ ለቀለቅናቸው። ይህም በጥሩ ሁኔታ ተከላከለልን።

አሁን ከምሽቱ አንድ ሰዓት ነበር። ጨለማ ቢሆንም የጨረቃዋ ብርሃን በጣም ደማቅ ስለነበር መንገዳችንን ቀጠልን። አንቶኒዮ ወደ ሰዓቱ እየጠቆመ የሦስት ሰዓት ምልክት በማሳየት « ዝናም» አለ። በሦስት ይዘንባል ማለቱ እንደሆነ ተረዳሁ። በዕርግጥም ሦስት ሰዓት ከሐያ መዘነም ጀመረ፣ እኛም ገሠገሥን። ከእርሱ ጋር አኩል ለመጓዝ የአዘላለሉን ዘዴ ቀሰምኩና አየሩን በከንዶቼ እቀዝፍ ጀመር። ለማድረግ አዳጋች አልነበረም። በሊሊቱ ጉዟችን ወቅት በጫካው ውስጥ ሦስት ጊዜ ተሸሸገናል። አንድ ጊዜ አንድ መኪና፣ አንድ ጊዜ አንድ ካሚዮንና ሌላ ጊዜ ደግሞ በእሆች የሚሳብ አንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠረገላ ለማሳለፍ። ለቅጠሎቹ ምሥጋና ይግባቸውና ሴኔጋም አልደከምኩም። ዝናሙ በሁለት ሰዓት አቆመና ከዚያም ወደ ጫካው ውስጥ ለመሸሸግ ከመግባታችን በፊት በሣሩ ላይ በጥንቃቄ እየተራመድን እንደ በፊቱ ከግማሽ ማይል በላይ ተጓዝን። ስለ ቅጠሎቹ አንድ ያልወደድኩላቸው ነገር ቢኖር ሙትኛት አያስችሉም። ከጀመርን አንሥቶ ወይናችንን እንኳ አልጨፈንም ነበር። የአንቶኒዎ ወይኖች በእንባ ከመሸፈናቸው የተነሳ ብሌኖቹ ጨርሰው አይታዩም ነበር። የእኔም እንደዚያው መሆን ነበረበት።

አሁን ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ስለሆነ ዝናሙም ተመልሶ መዝነብ ጀምሯል። ዝናሙ ሁልጊዜ ሶስት ሰዓት መድረሱን የሚጠብቅ ይመስላል። በኋላ እንደ ተረዳሁት በምድር ወገብ አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ በማንኛውም ሰዓት ዝናም መጣል ከጀመረ በዚያች የሩብ ጨረቃ ሰሞን የሚጀምረውና የሚያቆመው ከሞላ ጎደል በዚያው ተመሳሳይ ሰዓት ይሆናል። የሌሊቱን ጉዞ እንደጀመርን ድምፆች ሰማን፤ ከዚያም መብራት አየን። « ካስቲሌቴ» አለ አንቶኒዎ። ይህ ልዩ የሆነ ሰው እጁን ሜጫምድ ኤድርን በጫካው አየሰበ ከሁለት ሰዓት አድካሚ ጉዞ በኋላ እንደገና ወደ መንገዱ ተመለስን። ቀሪውን ሌሊትና የሚቀጥለውንም ቀን ያለማቋረጥ ሰንሪመድ ወይም ሰንዘል ማለቱ ይሻላል ዋልን።

ልብሶቻችንን ፀሐይዋ አደረቀችልን። ሦስት ቀን ሙሉ እንደ ረጠብን፤ ሦስት ቀን ሙሉ የበላነው ጥቁር ስኳር ብቻ ሲሆን፤ ለዚያውም በመጀመሪያው ቀን ነበር። ከአደጋ ውጭ መሆናችንን እንቶኒዎ አሁን እምነት ያደረበት መሰለ። የሚራመደው ያለሥጋት ሲሆን፤ ለመጨረሻ ጀሮውን በመሬት ለጥፎ ከአዳመጠ ብዙ ሰዓቶች አልፈዋል። መንገዱ የባሕሩን ዳር የተከተለ ስለነበር ከትንሽ ጊዜ በኋላ አንቶኒዎ አንድ ዘንግ ብጤ እንጨት ዘንጥፎ ያዘና አሸዋው በረጠበበት ላይ መራመድ ጀመርን። ከባሕሩ አስከ ደረቁ መሬቱ በማምት ሐያ ኢንች የራቀ አንድ የተደለደለ አሸዋ ሊፈትሽ ቆመ። በመጨረሻም ከብ ሆኖ አስከሚያቆምበት ድረስ አሸዋውን ተከተልን። አንቶኒዎ እንጨቱን በከቡ አሸዋ ውስጥ ቁልቁል ከተሞው። ወደ ላይ ሲመዘዝ ጫፉ የእንቁላል አሰኳል በመሰለ ቢጫ ፈሳሽ ተለውሶ ወጣ። ግምቴ ልከ ሆነ። በእጆቻች አንድ ጉድጓድ ሰንቆፍር ወዲያውኑ አንድ የእንቁላል ከምችት አገኘን። ምናልባት ሦስት መቶና አራት መቶ ያህል ነበሩ። በቅርፊት ፋንታ በቆዳ የተሸፈኑ የባሕር ኤሊ እንቁላሎች ነበሩ። የአንቶኒዎ ሸሚዝ አስከ ቻለልን ድረስ አንድ መቶ ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ሞላንና የባሕሩን ዳር ትተን መንገዱን በማሳበር ወደ ቁጥቋጦው ውስጥ ገባን። አንድ ጊዜ ያለ ሥጋት ከተደበቅን በኋላ እስከምንጠግብ ሙበላት ጀመርን። የአንቶኒዎን መመሪያ በመከታተል እስኳሉን ብቻ እውጣለሁ። ቆዳውን አንድ ጊዜ በጥርሱ ይበሳና መጀመሪያ ነጩን በማፍሰስ እስኳሉን ይመጥጣል። አንድ ለእርሱ፣ አንድ ለእኔ፣ እንደዘህ እያለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጠለ። እስክንፈነዳ ጠብንና ጃኬቶቻችንን እንደ ትራስ በማድረግ መሬት ላይ ተዘረጋን። እንቶኒዎ በስታኘ ቋንቋ፤ « ነገ ለተጨማሪ ሁለት ቀናት ብቻህን ትቀጥላለህ። ከነገ በኋላ ፖሊስ የሚባል አይኖርም» አለ።

በዐሥራ ሁለት ሰዓት ወደ መጨረሻዋ የጠረፍ ጣቢያ ደረስን። መድረሳችንንም ያወቅነው ከእንዲት ትንሽ ቤት ውስጥ በሚወጣው ውጋጋንና በውሻዎቹ ጩኸት ነበር። እንቶኒዎ ለብልሀቱ ምሥጋና ይድረሰውና መንገዳችንን ለማሳበር ተሳክቶልን ቀሪውን ሴሲት ምንም ሥጋት ሳይኖርብን ተጓዝን። መንገዱ ጠባብ ቢትሆንም፣ ሣር ስላልበቀለበት ዘወትር የሚጠቀሙባት መሆኗ ያስታውቃል። ሐያ ኢንች ስፋትና ከእኛ በታች እስከ ባሕሩ ጠርዝ ድረስ ስድስት ጫማ ስፋት ያለው የጫካ ጠርዝ ነበራት። አልፎ አልፎ የፈረሶችና የበቅሎዎች ኮቴ ምልክት እናያለን። እንቶኒዎ እንድ ጉዮ ላይ ተቀመጠና እኔም እንደዚያው እንዳደርግ ጠቀሰኝ። ፀሐይ ቁልቁል ትለበልበን ጀመር። ሰዓቴ አምስት ትላለች፤ ግን እንድ ትንሽ እንጨት ወደ መሬት ሲተከል ጥላ አልነበረውም። ሰለዚህ ቀትር መሆን አለበት። ሰዓቴን አስተካከልኩ። እንቶኒዎ ቦርሣውን ሲያራግፍ ሰባት ቅጠሎች ቀርተውታል። አራቱን ሰጠኝና ሦስቱን ለራሱ አስቀረ። ወደ ጫካው ውስጥ ገለል ብየ ከእንድ ሙቶ ሃምሳ የትሪኒዳድ ዶላርና ስድሳ ፍሎሪን ጋር ተመልሼ ወጣሁ። ገርሞት ነበር። ወደ ኖኖቹ እጁን ልከ ሲነካቸው እንዴት በጣም አዲስ ሲሆኑ እንደቻሉና ለምን አንዳልረጠቡ ሊገባው አልቻለም። በኢጆቹ አንደ ያዛቸው አመሰገነኝና ለረጅም ጊዜ ከአሰበ በኋላ እያንዳንዳቸው ባለ አምስት ፍሎሪን የሆኑ ስድስት ኖቶችን ብቻ ወስዶ ቀሪውን መልሶ ሰጠኝ። እንዲቀበል አባበልኩት። ግን ከዚህ በላይ አልወስድም አለ። በዚያ ወቅት ይመስላል ሐሳቡን የቀየረው። ቀደም ሲል መንገዳችንን ለያይተን መሐድ እንዳለብን ወስኖ ነበር፤ አሁን አንድ ሴላ ተጨማሪ ቀን ከእኔ ጋር ለመቀጠል የፈለገ ይመስላል። ከዚያም ግማሽ መንገድ ወደ ኋላ ተመልሶ ብቻውን ሊጓዝ ነበር፤ መልካም። እንቁላሎች ዋጥን። ጭበጥ ሙሉ ደረቅ ጭራሮዎችና ሁለት ድንጋዮች በማፋጨት እሳት ለማግኘት ስንል ለማማሽ ሰዓት ያህል ከታገልን በኋላ አንድ ሲጃራ ለኮስን። ከዚያም ጉዞ ቀጠልን።

ሦስት ሰዓት ከተጓዝን በኋላ ነበር አንድ ሰው በፈረስ ሆኖ በቀጥታ ወደ እኛ ሲመጣ ያየነው። አንድ ትልቅ የሰሌን ባርኔጣ፣ ረጅም ጫማ፣ በሱሪ ፋንታ ረጅምና ዘርፋፋ ቡዳ፣ አንድ አረንጓዴ ሸሚዝና ቀለሙ የደበዘዘ አረንጓዴ ጃኬት ለብሶ ነበር። አንድ ጥሩ ካርባይን አንግቶ ዝናሩ ላይ ደግሞ አንድ ትልቅ ሽጉጥ ተንጠልጥሏል።

« ካራምባ! የእኔ ልጅ፤ እንቶኒዎ!» አለ። እንቶኒዎ ፈረሰኛውን ከፍ ብ ዐውቆት ነበር። ሙልኩ መዳብ የሚመስለው ግዙፍ ፈረሰኛ፣ ከፈረሱ ጹበ አለና ሁለት ሰዎች ትከሻዎቻቸውን በኃይል ተመታቱ። ይህም የቀበሌው ባህላዊ የሰላምታ መግለጫ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠሆኑን በኋላ ተረዳሁ።

« ይኸ ማነው?»

« አብሮኝ ያመለጠ ጓደኛየ ነው፣ ፈረንሣዊ ነው።»

« ወዴት ነው የምትሔዱት?»

« ከቀይ ሕንዳውያን ዓሣ አጥማጆች ጋር እስከምንገናኝ ድረስ ነው። እርሱ በሕንዶች ቀበሌ አቋርጦ ወደ ቬኔዙዌላ ለመግባትና ከዚያም አሩባ ወይም ኩራሶ ሊመለስ ይፈልጋል።

« የጓሹራ ሕንዶች በጣም መጥፎ ሰዎች ናቸው» አለና ሰውየው በማከታተል፤ « መሣሪያ አልታጠከም። ይሆን ውሰድ» ብሎ የተወለወለ የቀንድ እጀታ ያላት ስገባ ውስጥ የተቀመጠች ጩቤ ሰጠኝ። በመንገዱ ዳር ተቀመጥን። ጫማዎቼን ሳወልቃቸው በደም ተለውሰው ነበር። አንቶኒዎና ፈረሰኛው በችኮላ ሲነጋገሩ የእኔን አቋርጦ የመሔድ ዕቅድ እንዳልደገፉት ልገነዘብ ቻልኩ። በፈረሱ ላይ መውጣት እንዳለብኝና የደሙት እግሮቼ እንዲደርቁልኝ ጫማዎቼን በትከሻየ ላይ ማንገት እንደሚኖርብኝ እንቶኒዎ ገፋፉኝ። ፈረሰኛው ተመልሶ ወደ ፈረሱ ወጣና እኔም ከኋላ ተፈናጠጥኩ። ምን እንደማደርግ ግራ ገበቶኝ ነበር። ያን ዕለት ሙሉውን ቀንና እስከሚቀጥለው ሌሊት ድረስ ስንጋልብ ቆየን። አልፎ አልፎ ቆም እያልን አንድ ጠርሙስ አንቹ አረቄ ያቀበለኝና አንድ ጉንጭ እንኳጫለሁ። ፀሐይ ስትወጣ ቆምን። እንደ ድንጋይ የጠነከረ አንድ ቁራጭ አይብ፣ ሁለት ብስኩቶችና ስድስት የኮካ ቅጠሎች ሰጠኝ። ለእነርሱ መያዣ የሚሆነኝ ውሃ የማያረጥባት አንዲት ከረጢት አበረከተልኝና ከቀበቶዬ ጋር አቆራኝኋት። እጆቼን በዙሩያየ ጠመጠመና እንቶኒዎን እንዳደረገው ዓይነት ትከሻየን ጠበጠበኝ። ከዚያም ፈረሱ ላይ ተመልሶ ወጣና እየጋለበ ሔደ።

ሕንዶች

ከቀትር በኋላ እስከሰባት ድረስ ስጓዝ ቆየሁ። ጫካው ሲያበቃ ለዓይን የሚታይ አንድም ዛፍ አልነበረም። ከምታነደው ፀሐይ በታች ባሕሩ እንደ ብር ያብረቀርቃል። ጫማዎቼን በግራ ትከሻየ አንጠልጥዬ በባዶ እግሬ አራመዳለሁ። ብጋደም ይሻለኝ ይሆን እያልኩ በማቅማማት ላይ እንዳለሁ አምስት ወይ ስድስት ዛፎች ወይም ቋጥኝ ይሆናሉ ከባሕሩ ባሸገር በሩቁ ተመለከትኩ። ርቀቱን ለመገመት ሞከርኩ፤ ስድስት ማይል ወይም ወደዚያው ይጠጋል። አንድ ሰፊ ቅጠል አወጣሁና ከአኘኩ በኋላ እንደገና ጉዞ ቀጠልኩ። ከአንድ ሰዓት በኋላ አምስት ወይም ስድስት የነበሩትን ቅርፆች መለየት ቻልኩ። ጣሪያቸው በሣር ወይም በአንድ ዐይነት የወየበ ቅጠሎች የተከደኑ ጎጆዎች ነበሩ። ከእነርሱ በአንዱ ውስጥ ጢስ ይወጣ ነበር። ከዚያም ሰዎቹ አየሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እነርሱም አይተውኛል። ድምፃቸውን መሰማት ከመቻሌም ሌላ ወደ ቤሕሩ ዳር መጡና ወሥር የሚሆኑ ሰዎች ወደ ውጭ ሲወጡ አየሁ። ሁሉም ሰው ከጎጆዎቹ ፊትለፊት ቆሞ ወደ እኔ አቅጣጫ ይመለከታል። ከትንሽ ሜርቆ በስተቀር ወንዶቹም ሆኑ ሴቶቹ ራቁታቸውን ነበሩ። ዝማ አያልኩ ተጠጋሁ። ከሰዎቹ ውስጥ ሦስቱ ፍላፃዎቻቸውን በእጆቻቸው ይዘው ከቀስቶቻቸው ጋር ተንበርክከው ነበር። የጥላቻም ሆነ የመልካም አቀባበል እንቅስቃሴ አያሳዩም። አንድ ውሻ እየጮኸ በቁጣ ገሥግሦ ወደ እኔ መጣ። ቡቴን ነክሰኝና ከሱሪዬም ትንሽ ጨርቅ ቦጨቀ። እንደገና ሊነክሰኝ ሲል፣ ከወዴት እንደ መጣች ያላወቅኳት አንድ ትንሽ ፍላፃ ከኋላው ቀነጠበችው። ከባለ ቱቦ ቀስት ውስት የተተኮሰች እንደ ነበረች በኋላ ተረዳሁ። ውሻው አያለዘነ ሮጠና አንድ ጎጆ ውስጥ ገብቶ ጠፋ። አንድ ጋይለኛ ንክሻ አቅምሶኝ ሰለነበር ማንከስ ጀመርኩ። አሁን ከቡድኑ ምናልባት ሠላሳ ሚሶሳ ብርቅ ነበር። ከእነርሱ ውስጥ አንድም የሚነጋገር ወይም የሚንቀሳቀስ አልነበረም። ሊጎዟም ከእናቶቻቸው ኋላ ተሸሽገዋል። አከላቶቻቸው የሚያስደንቁ ነበሩ። መዳብ የመሰሉና ፍርጥም ያሉ ጡንቻዎች፣ ሴቶቹ ትላልቅ ጫፎች ያሏቸው ጠማርና ቀጥ ያሉ ጡቶች ነበሯቸው። የወደቀ ጡት ያላት አንዲት ሴት ብቻ ነበረች።

በአቋሙ የተለየ ግርማ ያለው አንድ ሰው ነበር። ፊቱ መልከ መልካም ስለነበር ከሌሎቹ ሁሉ የላቀ መሆኑ ያስታውታል። በቀጥታ ወደ እርሱ አመራሁ። ቀስት አልያዘም ነበር። የቁመቱ መርዘም እንደ እኔ ሆኖ ጸጉሩን በግራም ሁኔታ ተከርክሞታል። በጣም ከመጥቆሩ የተነሣ ሐምራዊ የሆነና ከፊቱ በኩል ቅንድቡ ድረስ ወርዶ ከጎንና ከጎኑ ደግሞ እስከ ጆሮው የደረሰ ነበር። ዐይኖቹ እንደ ብረት ግራጫ ናቸው። በአካላቱ ላይ ጸጉር የለውም። መዳብ የመሰሉት ታቱዎቹ በጠንካራ ጡንቻዎች የተሸበቡ፣ ባቶቹም ደስ የሚሉና የተመጣጠኑ ነበሩ። በባዶ እግሩ ነበር። ከእርሱ ፊት ለፊት ዐሥር ጫማ እንደ ተራመድኩ ቆምኩ። ዐይኖቹን በሞኖታ ከእኔዎቹ ላይ እንደ ተከለ እርሱም ሁለት እርምጃ ወደፊት ቀረብ አለ። መተያየት ሁለት ደቂቃ ፈጀ። የማይንቀሳቀሰው ፊቱ ከፈጠጡት ዐይኖቹ ጋር ልክ የመዳብ ሐውልት አስመስሎታል።

ከዚያም ፈገግ አለና ትከሻዎን ነካኝ። ይህም ምልክት ኖሯል። ሁሉም ሰው እየቀረበ ነካኝና አንዲት ሕንዳዊት ኮረዳ እጇን ይዛ እየመራች ከጎጆዎቹ ወደ አንደኛዋ ጥላ ሥር ወሰደችኝ፤ ሊሉኝም በሙሉ ተከተሉና ዙሪያውን ከበው ተቀመጡ። ከሰዎቹ ውስጥ አንዱ አንድ የተቀጣጠለ ሲጃራ ሰጠኝና ተቀበዬ አጤስ ጀመር። በእነርሱ ዘንድ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የተቃጠለውን ጫፍ የሚይዙት በአፋቸው ውስጥ ሰለነበር ፣ በእጣጢያሴ ሁሉም ሣቁብኝ። ኮረዳዋ ሱሪየን ወደ ጭኔ ሰቀሰቀች። የተነከስኩበት ቦታ መድማቱን አቁሟል። ግን ሩብ ኪሎ የሚመዝን እንድ ሙዳ ሥጋ ከላዬ ላይ ተንሥቶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር። ጸጉሮቹን በመሉ ነቀለችና እስከ መጨረሻው ድረስ ቆዳውን ካለሰለሰች በኋላ፣ እንዲት ሌላ ሕንዳዊት ኮረዳ ባመጣችው የባሕር ውሃ ቁስሉን አጠበችልኝ። ከዚያም ቁስሉ እንዴደማ አፍረጠረጠችው። አሁንም ገና ስላላረካት እያንዳንዱን የደም ሥር በእንድ ሹል ብረት ታነቃቂው ጀመር። ሁሉም ሰው አተኩሮ ይመለከት ስለነበር እመመኝ ብዬ ወደ ኋላ ላለማፈግፈግ ጥረት አደረግኩ። አንዲት ሌላ ሕንዳዊት ኮረዳ ልትረዳት ፊልጋ ቀረብ ስትል ወደ ጎን ገፈተረቻት። በአንድ የሆነ ምክንያት ሁሉም ሰው ሣቀ። ቁስሌን ታከመኝ የነበረችው ኮረዳ ለሌላዋ ግልጽ ለማድረግ የፈለገችው፣ እኔ የግሏ ንብረት አንደ ነበርኩ መሆኑ ገባኝ። እነርሱንም አስቂቸው የነበረው ይኸው ነበር። ከዚያም ሱሪየን ከጉልበቴ በላይ ቆረጠችና በአንድ ድንጋይ ላይ የባሕር አሬሙቻ ቀጥቅጣ ከቀደደችው ሱሪ ጨርቅ በመተልተል በቁስሉ ላይ አሰቀመጠችበት። በመጨረሻም በሥራዋ ስትረካ አንድቁም ጠቀሰችኝ።

ተነሣሁና ጄኬቴን አወለኩ። በዚያ ወቅት ነበረ አንገቴ ሥር የተወቀርኩትን ቢራቢሮ ትኩር ብላ የተመለከተችው። ከዚያ ቀረብ ብላ ስትመለከት ተጨማሪ ውቅራቶች ስላየች የቀሩትን ለመመልከት ሸሚዜንም አወለቀች። ሁሉም ሰው ዙሪያውን ተሰበሰበ። ከደረቴ በስተግራ አንድ የካልቪ ዘበኛ፣ በስተቀኝ የአንዲት ሴት ጭንቅላት፣ ከሸንጨ በላይ የአንድ ኑብር ጭንቅላት፤ በአከርካሪየ ላይ አንድ የተሰቀለ መርከበኛና በኩላሊቴ አካባቢ በአዳኞች የሚባረር አንድ ኑብርና የዘምባባ ዛፍ ዝሆኖችና ነብሮች ነበሩ። ወንዶቹ አጣርተው ለማየት ሴቶቹን ወደ ጸር በማግለል እያንዳንዷ ውቅራት ምንም ሳትቀር እየመረመሩ ዳሰሱኝ። አለቃው የራሱን አስተያየት ሲሰነዝር ሌላውም ሰው የየበኩሉን ሰጠ። ከዚያች ጊዜ አንሥት ነበር በወንዶቹ በኩል ተቀባይነትን እንዳገኘሁ ግልጽ የሆነልኝ። ሴቶቹ የተቀበሉኝ አለቃው ፈገግ ብሎ ትከሻየን በነካ በደቂቃ ውስጥ ነበር።

ከጎጆዎቹ በጣም ትልቅ ወደሆነው ውስጥ ሰንገቡ፣ በጠቅላላው ከሰው ሁሉ ኋላ ያለሁት እኔ ነበርኩ። ጎጆው የተሠራው ከቀይ አፈር ጭቃ ነበር። ከብ ሆኖ ስምንት መገባያዎች ሲኖሩት፣ በአንድ ጥግ በኩል ከደማቅ ቀለም ሱፍ የተሠሩ ተንጠልጣይ የብርድልብስ አልጋዎች ተሰቅለዋል። በጎጆው መካከል በጣም የለሰለሰ፣ ጠፍጣፋ፣ ከብ ድንጋዮች ነበሩ። ብዙት ድጥኝና፣ ዙሪያውን ደግሞ ለመቀመጫ የሚሆን አነስተኛ ከብ ድንጋዮች ነበሩ። ብዙት ያላቸው ባለሁለት አፈሙዝ ጠመንጃዎች አንድ ጎራዴና ልዩ ልዩ ዐይነት ቀስቶች ግድግዳው ላይ በብዛት ተሰቅለዋል። በተጨማሪ ከተልቅነቱ የተነሣ አንድ ሰው ማስተኛት የሚችል አንድ የኤሊ ልባስና ያለሲሚንቶ ከጥርብ ድንጋይ የተገነባ አንደ የጠለ መውጫ ነበር። ሁለት ወይም ሦስት ጭበጥ ያህል ሉሎች የያዘ አንድ ጉርድ ቅል በአንድ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጧል። የፍራፍሬ ጭማቂ በአንድ የእንጨት ዋንጫ ተሰጠኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም ግሩም የሆነ የመራራ ጣፋጭ ጣዕም ነበረው። ከዚያም ከብደቱ እምስት ፓውንድ የሚመዝን በከሰል ላይ የተጠበሰ ዓሣ በመጣ ኮባ ተሸፍኖ ቀረበልኝ። በገማታ በላሁ። እርኪውን ዓሣ እንደ ጨረስኩ ሕንዳዊቷ ኮረዳ እጇን ይዛ ወደ ባሕሩ ዳር ወሰደችኝና እጆቼንና እፈን በባሕር ውሃ ለመታጠብ ቻልኩ። ሰንመለስ ሁላችንም ዙሪያ ከብ ሆነን ተቀመጥንና፣ ወጣቷ ሕንዳዊት ኮረዳ እጆቿን ከጭኔ ላይ ጣል አድርጋ ከኔ በመሆን በታላችና በመጠቃቀስ እርስ በርሳችን ለመተዋወቅ መሞከር ጀመርን።

አለቃው ድንገት ብድግ ብሎ ወደ ጎጆው ጓላ ሔደና አንድ ነጭ ድንጋይ ይዞ በመመለስ ጠረጴዛው ላይ ሥዕል መሥራት ጀመረ። መጀመሪያ ራቁታቸውን የሆኑ ሕንዶች ሣለ። ከዚያም መንደሩን፣ ከዚያ ባሕሩን ከሕንዶቹ መንደር በስተቀኝ፣ መስኮት ያላቸው ቤቶችና ልብስ የለበሱ ወንዶችና ሴቶች ሣለ። ወንዶቹ ጠመንጃ ወይም በትር ይዘዋል። በስተግራ በኩል ሌላ መንደርና ጠመንጃ የያዙ፣ ባርኔጣ የደፉና ዐልከ ጥቅ ወንዶች እንደዚሁም ሴቶቻቸው ልብስ እንደ ለበሱ ሣለ። ሥዕሎቹን በጥንቃቄ ተመለከትኳቸው። አለቃው እንድ ነገር መሠርጋቱን አስታወሰና ከሕንዶቹ መንደር በስተቀኝ በኩል ላለው መንደር፣ እንድ የእግር መንገድ በስተግራ ላለው ሌላ መንደር ፣ እንድ ሌላ የእግር መንገድ ጨመረ። ከራሱ መንደር ጋር በማዛመድ የእነርሱን አቅጣጫ ለማመልከት ከቬንቱዌላ ጎን በስተቀኝ በኩል ጨረሯን በሁሉም አቅጣጫ የበተነች አንዲት ከብ ፀሐይ አስቀምጦ በመከከሏ ወጣ ገባ የሆነ አንድ መስመር አጋደመበት። አስተሳሰቡ ግልጽ ነበር። ፀሐይ በአንድ በኩል ወጥታ በሌላ በኩል ትጠልቃለች። አለቃው ሥዕሎቹን በኩራት ሲመለከት ሁሉም ሰው በየተራ ይመለከት ጀመር። እኔም የገባኝ መሆኑን ሲመለከት፣ የራሱን እንዳለ ትቶ ሌሎቹን ሁለት መንደሮች በመስመር ሸፈናቸው። በሁለቱ መንደሮች ውስጥ ያሉት ሰዎች ከፉዎች እንደ ነበሩና የእርሱ መንደር ብቻ ጥሩ መሆኑን ሊነግረኝ እንደ ነበር ተገነዘብኩ። እርሱ ሊነግረኝ እንደ ፈለገው ከሆነ!

አንድ እርጥብ ጨርቅ አነሣና ጠረጴዛውን ጠረገ። ሲደርቅ የእኔ ተራ መሆኑን ለማመልከት ድንጋዩን በእጄ ላይ አስቀመጠልኝ። የእኔ አሣሣል ከእርሱ ይበልጥ ውስብስብ ነበር። እጆቹን የታሠረ አንድ ሰው መሣሪያ የታጠቁ ሁለት ሰዎች ከጎንና ጎኑ ሆነው እርሱን ሲጠብቁ፣ ከዚያም ያው ሰውየ ሲሸሽና ሁለቱ ሰዎች ጠመንጃቸውን ወድረው ከኋላው ሲሮጡ። ይህንኑ ሥዕል ሦስት ጊዜ በመደጋገም በእያንዳንዱ ወቅት በእኔና በሚያባርሩኝ መካከል ተጨማሪ ቦታ በማራራቅ ሣልኩለት። መጨረሻ ላይ ሥሊሶቹ ቀመው እኔ ብቻዬን ወደ እነርሱ መንደር ስሮጥና ይህንንም ለማመልከት ሕንዶቹን፣ ውሻውን፣ አለቃው ከንዶቹን ዘርግቶ እንኳን ደህና መጣህ የሚል በማሰመሰል እኔ ከሁሉም ሰው ፊት ለፊት እንደ ቆምኩ ሣልኩለት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሥዕሎቹ በጣም ግላጭ መሆን ይኖርባቸዋል። ምክንያቱም ከሰዎቹ ጋር ረጅም ውይይት ካደረገ በኋላ፣ ልክ የእኔን ሥዕል አስመስሎ አለቃው ከንዶቹን ፈጋቸው። ጉበቷቸው ነበር።

የዚያኑ ዕለት ማታ፣ ሕንዳዊቷ ኮረዳ ሰድስት ሴቶችና አራት ወንዶች ይኖሩበት ወደነበረ አንድ ጎጆ ወሰደችኝ። ከስፋቱ የተነሣ ሁለት ሰዎችን በአግድመት አመቻችቶ የሚያስተኛና ከባለ ቀለም ሱፍ የተሠራ ግሩም የሆነ አንድ የብርድ ልብስ ተንጠልጣይ አልጋ ዘረጋችኝ። እኔ በቁመቱ ስተኛ እርሷ ደግሞ በግርጌ በኩል በሌላ አቅጣጫ እግድም ተኛች። በኋላ አቅጣጫየን ለወጥኩና በአግድመት ስተኛ እርሷም ወደ አጠገቤ መጥታ ተኛች። ሰውነቴን፣ ጀሮዎቼን፣ ዐይኖቼን፣ አፌን ሁሉ ዳሰሰችኝ። ጣቶቿ ረዣዥሞችና የሚያማምሩ ቢሆኑም፣ አይስተሮች ሰሞነኛውን ስትዋኝ ልባሶቻቸው ስለሚቆርጢት በትንንሽ ጭረጭች የተሸፈኑና በጣም ሻካራ ነበሩ። እኔ ደግሞ በተራዬ ፊቷን ሳሻሸት የእጆቼን ለስላሳነት በመመልከት አድናቆት ያዛት። ቡተንጠልጣዩ የብርድልብስ አልጋ ላይ እንድ ሰዓት ያህል አንደቆየን ተኮሣንና ወደ አለቃው ጎጆ ሔድን። ከትዱስ ኢትየን ያመጧቸውን ባለ ዐሥራ ሁለትና ባለ ዐሥራ ስድስት ጎራሽ ጠመንጃዎች ፈተሽኩላቸው። በተጨማሪ ሰድስት ሣጥን ጥይቶች ነበሩ።

ሕንዳዊቷ ኮረዳ ቁመቷ መካከለኛ፣ ዐይኖቿ እንደ አለቃው ግራጫ የሆኑና ጸጉሯ ተጎንጉኖ ዳሌዋ ድረስ የወረደ ውብ መልክ ያላት ነበረች። ጡቶቿም ቀጥ ያሉና የሚያማምሩ ነበሩ። ጫፎቻቸው መዳብ ከመሰለው ሰውነቷ ለየት ብለው የጠቆሩና በጣም ረዣዥሞች ናቸው። አሳሳሟ ንክሻ ነበር። የአኛ ዓይነት አሳሳም እንዴት እንደሆነ አታውቅም። ወዲያውኑ አስተማርኳት። ከኋላየ ካልሆነ ጎን ለጎን አብራኝ አትሔድም። ስለዚህ ጉዳይ ምንም ማድረግ አልቻልኩም። ከጎጆዎቹ አንደኛዋ ሰው የማይኖርባትና የፈራረሰች ነበረች። ከሌሎች ሴቶች ጋር በመረዳዳት ጣራዋን በዘምባባ ቅጠል ጠጋገነችና ግድግዳዋን በቀይ አፈር ጭቃ ለሰነቻት። በጣም ከጥቶኛ ብዛት ያለው ልዩ ልዩ የመቆራረጫ መሣሪያዎች አሏቸው። ጩቤዎች፣ ጉዶዎች፣ ጎጆራዎች፣ ቆንጮራዎች፣ መኮትኮቻዎችና የብረት ጣት ያላቸው መንሾች። በተጨማሪ ከአሉሚኒየምና ከነሐስ የተሠሩ መቀቀያ ብረት ድስቶች፣ የውሃ መቅጃ ጣሳዎች፣ መጥበሻዎች፣ የድንጋይ ወፍጮዎች፣ ምድጃ ከአንጨትና ከብረት የተሠሩ በርሜሎች ነበሯቸው። የብርድ ልብስ ተንጠልጣይ አልጋዎቻቸው ንጹሕ ሱፍ ሆነው፣ ከፈፎቻቸው በግሩም ሁኔታና በደማቅ ቀይ፣ ሰማያዊ፣ ቢጫና በሚያብረቀርቅ ጥቁር ቀለማት የተጠለፉ ነበሩ። ጎጆዋ በአስቸኳይ ተዘጋጅቶና ከሌሎች ሴቶች በተውጣጡ ቁሳቁሶች መመላት ጀመረች። ለአሳት ምድጃ የሚሆን ሦስት እግሮች ያሉት አንድ የብረት ፈርኔሎ፣ ከስፋቱ ብዛት አራት ሰዎችን የሚያስተኛ አንድ ተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ፣ ብርጭቆዎች፣

t.me/OLDBOOKSPDF

የበረት በራዶች፣ መጥበሻዎች፣ የአህያ ልጓም እንኳ አልቀረም።

ሁለት ሳምንት ያህል አፍ ያለ ፍቅር ይዞን ነበር። ግን ከዚያ በኋላ ፈጽሞ መቀጠል አሰፈራት። ምንም እንኳ የጀመረችው እርሷ ብትሆን፣ እኔን ጨንቆኝ ነበር። ወቅቱ ሲደርስ ትተወው ይሆናል። ከሽንቅጡ ዳሌዋ በታች በእንዲት ቀጭን ገመድ ከታጠቀቻት ትንሽ ሜርቆ በስተቀረ ፈጽሞ ምንም አልለበሰችም። ከኋላዋም እርቃኗን ነበረች። ያለ አንድ ሥርዓት ከብ በሆነችው ትንሽ ጎጆ ውስጥ በገዛ ራሳችን ትዳር መሠረትን። ሦስት በሮች ነበሯት። አንድ ዋና በርና እርስ በርሳቸው ትይዩ የሆኑ ሌሎች ሁለት በሮች። ሦስቱም በሮች ሦስት ማዕዘኖች ላይ ሆነው በእነርሱ ለመጠቀም የጠበቀ ሕግ ነበራቸው። እኔ ሁልጊዜ መግባትና መውጣት የምችለው በሰሜኑ በር ሲሆን፣ እርሷ ደግሞ በደቡቡ ነበር። እኔ በእርሷ ለመጠቀም ወይም እርሷ በእኔ ለመጠቀም ፍጹም አይፈቀድም። በመካከል ያለው ትልቁ በር ሰእንግዶች ሲሆን፣ ከእንግዶች ጋር ካልሆነ በስተቀር እርሷም ሆነች እኔ አንጠቀምበትም።

እንዳቅፋት የምትፈቅድልኝ አቢት ውስጥ ስንሆን ብቻ ነበር። ወደ ሰፊ ሐተታ ሳልገባ፣ ብልህና አስተዋይ የሆነች ጥልቅ ስሜት ያላት እመቤት ነበረች። የምታቅፈኝ እንደ ወይን ሐረግ ጥምጥም አድርጋ ነበር። ብቻችንን ስንሆን ጸጉሯን አበጥርና አጎንጉላታለሁ። ይህን ሳደርግላት ስለምትወደኝ ከደስታዋ የተነሣ ፊቷ ይግላል። በዚህ መካከል ደግሞ ፍረሃት ነበር። ፍርሃቱም አንድ ሰው ያየን ይሆናል የሚል ሲሆን፣ ምክንያቱንም ስትገልጽልኝ፣ አንድ ባል የሚስቱን ጸጉር ማበጠር፣ ወይም እጅጅን በሻካራ ድንጋይ መፈግፈግና አቧንም ሆነ ጡቶቿን በተለያዩ መንገዶች መሣል እንደሌለበት ነበር።

ታዲያ ላሊ፣ (ስሟ መሆኑ ነው) እና እኔ ራሳችንን ጎጇችን ውስጥ አደራጀን። ምን ቢደረግ በብረት ወይም በአሉሚኒየም ድስቶች አትጠቀምም፣ ፈጽሞ በብርጭቆ አትጠጣም። ማንኛውንም ነገር የምትቀቅለው ሕንዶቹ ራሳቸው በሚሠሯቸው የሸክላ ድስቶች ነበር። ገላችንን የምንታጠበው በተነደሉ የውሃ ገንዳዎች ሥር በመሆን ወይም ወደ ባሕሩ በመሔድ ነበር።

አይስተሮችን በመፈልቀቅ ረዳለሁ። በጠቅላላው ይህ ሥራ የሚከናወነው ከሴቶቹ ሁሉ በጣም አሮጊት በሆነችው ነበር። እያንዳንዷ ሉል አዳኝ ወጣት፣ የራሷ ከረጢት አላት። የሚያገኟቸውን ሉሎች ይከፋፈሉ ነበር፣ አንድ እጅ ሕብረተሰቡን ለሚወክለው አለታ ይሰጣል። እንደኛው ደግሞ ለዓሣ አጥማጅ፣ ግማሹ ከፍያ አይስተሮቹን ለምትፈለፍለው አሮጊትና አንድ ዕጣ ከግማሽ ለሉል አዳኟ። ሉል አዳኟ ከቤተሰቧ ጋር የምትኖር ከሆነ፣ ሉሎቿን የምትሰጠው ለአባቷ ወንድም ማለት ለአጎቷ ነበር። አሳት የሚጫወተው ሚና ፍጹም አልገባኝም። በተጨማሪ፣ ለጋብቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሚተመጣጠኑ ተጠያያቂዎች ቤት ለመግባትም የመጀመሪያው ሰው እርሱ ነበር። ሴቷ እጇን በወንዱ ወገብ ዙሪያ አንድትጠመጥም ያደርግና፣ የወንዱን ቀኝ እጅ በሴቲ ወገብ አዙሮ ለመልካች ጣቱን በአምብርቷ ላይ ያደርጋል። አንድ ጊዜ ይህንን ካደረገ በኋላ ወጥቶ ይሐዳል።

ታዲያ አይስተሮችን በመፈልፈል ሪዳለሁ። ጀልባ ላይ እንደወጣ ገና ስላልተጋበገዙ አይስተሮች አላጠምድም። አይስተሮች የሚጠመዱት ከባሕሩ ዳር ሩብ ማይል ያህል ወጣ ብሎ በመራቅ ነበር። እንዳንድ ቀን ላሊ ታሩዎቹና የሽንጢ አካባቢ በኮራሎች (ድንጋይ መሰል የባሕር ውስጥ ተክሎች) ተሞንሚጭረው ትመለሳለች። አልፎ አልፎ የተሚጨረችው ሲደማባት የባሕር አራሙቻ ትጨምቅና ቁስሎቹ ላይ ትፈገፍጋቸዋለች። ከለተጋበዝኩ ምንም ነገር አልሠራም። አንድ ሰው እጇን ይዞ ካልወሰደኝ በስተቀር ወደ አለቃው ቤት ፈጽሞ አልገባም። ብቻችንን ስንሆን ምን እንደምናደርግ ለማየት ወይም ለመስማት፣ በበራችን አጠገብ ከሚገኘው ሣር ውስጥ የሚተኙ ሦስት ወጣት ሕንዳዊ ኮረዳዎች መኖራቸውን ላሊ ጠርጥራለች። ከጠረፍ ጣቢያው ባሻገር አንድ ማይል ላይ በምትገኝ የመጀመሪያዋ የክሎምቢያ መንደርና በእኛ መንደር መካከል ደላላ ሆኖ ከሚሠራ አንድ ሕንዳዊ ጋር ትላንት ተዋወቅኩ። የመንደሯ ስም ላቪላ ይባል ነበር። ሕንዳዊው ሁለት አህዮችና አንድ ዊንቸስተር አውቶማቲክ ጠመንጃ ነበረው። እንደመጠናቸው ለያይቶ በአንድ የክብሪት ሣጥን ውስጥ ሉሎች ይዟል። ልከ እንደ ማንኛውም ሰው እርሱም ሜርቆ ብቻ ታጥቂል። ኮሰስ ያለና ደቃቅ ነበር። ከግራ ደረቱ ሥር አንሥቶ እስከ ቀኝ ትከሻው ድረስ በአካላቱ ዙሪያ የተጋደመ አንድ አስቀያሚ ጠባሳ ነበረበት። እንደ ጣት ጉብ ያለ ሰምበር ይመስላል።

አለቃው ንቅሳት አንድወቅረው ጠይቆኝ ስለነበረ በመዝገበ ቃላት እየተረዳሁ አንድ ዝርዝር አዘጋጀሁ። የሚያስፈልጉን መርፌዎች፣ ጥቁርና ቀይ ቀለም እንዲሁም ከር ነበሩ። ደላላው ሕንዳዊ ግን አንዲት የስፓኝ ቃል እንኳ አሰካልተናገረ ድረስ ሥራውን እንዴት ማከናወን እንደሚችል ገርሞኛል።

ሕንዳዊው ለመሔድ ሲነሣ አንድ ጊዜ ከአርሱ ጋር አብሬ እንድሔድ አለቃው ፈቃድ ሰጠኝ። መመለሴን ለማረጋገጥም አንድ ጠመንጃ ከስድስት ጥይቶች ጋር አዋሰኝ። እንደሚታወቀው የእኔ ያልሆነ ማንኛውንም ነገር ፈጽሞ እስኪማልወስድ ድረስ ለመመለስ የምገደድ መሆኔ ተሰምቶታል። ሕንዳዊው በአንደኛው አህያ፣ እኔም በሌላዋ ላይ ወጣሁ። ወደ መንደሩ መጥቸበት በነበረው የአግር መንገድ ሙሉ ቀን ስንጓዝ ዋልን። ከዚያም ጠረፍ ጣቢያ ለመድረስ በግምት ሁለት ማይል ሲቀረን ከባሕሩ ራቅ ብለን በመዞር ወደ መሐል ሀገር አመራን።

ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ አምስት የሕንድ ጎጆዎች ከሚገኙበት አንድ ወንዝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዳር ደረስን። ሁሉም ሰው እየመጣ እኔን ይመለከታል። እንድ ቁፋሮ የሆነ ሰው እስኪመጣ ድረስ ሕንዶቹ እርስ በርሳቸው እየደጋገሙ ሲያወሩ ቆዩ። ከቀለሙ በስተቀር ወይኖቹ፣ ጸጉሩ፣ አፍንጫውና ሁሉንተናው የሚመስለው ሕንዳዊ ነበር። ቆዳው ግን በጣም ነጭ ሆኖ እንደ ፈረንጆች ቀያይ ወይኖች ነበሩት። ኳኪ ሱሪ ታጥፎል። ከዚያ በኋላ ነበር የእኛ ደሳላ ከዚህ ቦታ ፍጹም ርቆ እንደማይሔድ የተረዳሁት።

ነጩ ሕንዳዊ በስፓኝኛ ቋንቋ ፣ «ሰላም፣ ከእንቶኒዎ ጋር አምልጠህ የነበርከው ነፍሰ ገዳይ አንተ ነህ፣ አንቶኒዎ የእኔ ዘመድ ነው። በደግኾን የቃል ኪዳን ዝምድና ተሣሥረናል» አለ። «በዝምድና ለመተሳሰር» ሁለት ሰዎች እያንዳንዳቸው ክንዶቻቸውን በጩቤዎቻቸው ይቆርጠሩና ሁለቱም የቆረጠትን ቁስላቸውን አንድ ላይ ያፈጋፍጉታል። ከዚያም እጆቻቸውን በደም ይለቀልቁና ይሰሏቸዋል። «ምን ትፈልጋለህ» አለ።

«መርፌዎች፣ ቀይና ጥቁር ቀለም፣ ከር። ይሆንኑ ብቻ ነው።»

«በሚቆጥለው ሩብ ጨረቃ መውጫ ላይ ይደርሱኛል።» የስፓኝ ቋንቋ ችሎታው ከእኔ የተሻለ ስለነበር፣ ወገኖቹን የሚጠቅምበት ትርፍ እንዴት ለማግኘት እንደሚቻል ማወቁ ልዩ ስሜት አሳድሮብኛል። በምንለያይበት ወቅት በጣም ነጭ በሆነ ብር የተንከረ ከኮምቢያ ማንቲሞች የተሠራ አንድ የአንገት ሐብል ሰጠኝ። ሰላሊ ነው አለ።

«እንደገና መጥተህ እንድታየኝ» አለና መመለሴን ለማስተማመን አንድ ቀስት ሰጠኝ።

ብቻየን የመልሱን ጉዞ ጀመርኩ። ግን ከግማሽ መንገድ ይበልጥ አልሔድኩም ነበር፣ ዕድሜዋ ዐሥራ ሁለት ወይም ዐሥራ ሦስት ዓመት ከሚሆናት አንደኛዋ እህቷ ጋረ ሆና ላሊ ብቅ ስትል። ላሊ ራሷም ብትሆን በዐሥራ ሰድስትና ዐሥራ ሰምንት መካከል መሆን ነበረባት። ልከ እንዳበደች ሴት ሆና ዘልላ ደረቴን በጥፍሯ ስትቧጭረኝ፣ ፊቴን እከላከላለሁ ስል አንገቴን ነከሰችኝ። ያለኝን ኃይል በሙሉ ተጠቅሜ የቻልኩትን ያህል ልቀጣጠራት ብቻ ነበር የሞከርኩት። ከዚያም ወዲያውኑ በረደች። ጨቅላዋን ልጃገረድ አህያዋ ላይ አወጣሁና ላሊና እኔ ክንዶቻችንን እርስ በርሳችን በማቆላለፍ ተቃቅፈን በዝግታ ከኋላ እንጸዝ ጀመር። በመንገድ ላይ እንዲት ጉጉት ገደልኩ። የተኮስኩባት ምን እንደሆነች ሳላውቅ ነበር የተኮስኩት፣ ሁለት ወይኖች ሲበለጨለጩ ቡማየቴ ብቻ ነበር። ላሊ ልትወስዳት ፈልጋ ስለነበር በኮርቻው ላይ እንጠለጠለቻት። ጀምበር ልትጠልቅ ስትቃረብ ደረስን። ደከሞኝ ስለነበር መታጠብ ፈለኩ። ላሊ አጠበችኝ። ከዚያም በቶጥታ ከፊት ለፊቴ የአህቷን ሚርቦ አውልቃ አጠበቻትና በመጨረሻ ራሷ ታጠበች።

አቢት እንደተመለስን፣ የለሚ ጭማቂ ለመሥራት ውሃ እስኪፈላልኝ ድረስ እየጠበቅኩ ነበር። ከዚያ በኋላ በጣም ዘግይቼ የተረዳሁት አንድ ድርጊት ተከናወነ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ላሊ እህቷን ገፋ አድርጋ ወደ ጭኖቹ መካከል በማስገባት ከንዶቹን አንሥታ በልጓሙ ወንበ ላይ ጠመጠመቻቸው። ለላሊ ሰጥቻት የነበረውን የአንገት ሐብል አንገቷ ላ ማድረጓንና ሚርቆሞንም አለመታጠቋን ተመለከትኩ። ይህ የሚደረገው በትክክል ለም እንደነበረ አላወቅኩም። በዝግታ ከጭኖቹ መካከል አወጣሁና ከንዷን ይዤ ከተንጠልጣዩ የብርድ ልብስ አልጋ ላይ አጋደምኳት። የአንገት ሐብሉንም አወለቅኩና ለላሊ መልሼ አጠለቅኩላት። ከዚያ ላሊ ከአርሷ ቀጥሳ ተኛች፣ እኔም ከላሊ ጎን ተኛው። ከረጅም ጊዜ በኋላ እንደተረዳሁት፣ እኔ ለመሐድ ጥያቄ የማነሣበት ምክንያት በአርሷ ስላልተደሰትኩ ይሆናልና ምናልባት እህቷ ተንከባከባኝ መያዝ ትችላለች በሚል ምኞት ነበር። ወይኖቼን የላሊ እጆች እንደሸፈኗቸው ከእንቅልፌ ነቃሁ። በጣም ረፍዶ ከሚቱ አምስት ሰዓት ይሆን ነበር። ትንሽ እህቷ ተነሥታ ሔዳለች። የላሊ ትላልቅ ግራጫ ወይኖች በፍቅር ተሞልተው ትኩር ብላ ተመለከተቸኝና፣ የአፌን ጠርዝ በዝግታ ነከሰችኝ። ትቻት አለመሔዴ የቱን ያህል እንዳስደሰታት እንዳውቅላት ፈልጋለች።

ዘወትር ለላሊ ጀልባዋን የሚቀዝፍላት ሕንዳዊ ከቤቴ ፊት ለፊት ተቀምጦ እርሷን ይጠብቅ ነበር። በሚሰብ አስተያየት ወደ እኔ ፈገግ አለና ላሊ አሁንም ገና እንቅልፍ ላይ መሆኗን እንዳወቀ ለማመልከት ወይኖቹን ጭፍን አደረጋቸው። አጠገቡ እንደተቀመጥኩ ያው ሊገባኝ የማይችለውን መቀባጠሩን ቀጠለ። ወጣት ሆኖ እንደ ስፖርተኛ የተገነባ ጠንካራ ጡንቻ ነበረው። ሰረጅም ጊዜ ውቅራቱቹን በስሜት ሲመለከት፣ እርሱም እንደዚሁ ሊወቀር መፈለጉን ተገነዘብኩ። በመስማማት ራሴን አወዛወዝኩ፤ ግን ችሎታ ያለኝ መሆኑን የተጠራጠረ ይመስላል። ላሊ ብቅ አለች። አካላቷን ዘይት ተለቅልቃ ነበር። እንደማልወድላት ታውቃለች። ግን አየሩ ደመናማ በሚሆንበት ወቅት ውሃው በጣም ቀዝቃዛ እንደሚሆን ገለጸችልኝ። ይህም በክፈል ማቅና በክፈል መሽኮርመም የተደገፈ ድርጊታዊ ገለጻዋ በጣም ይማርከ ስለነበር፣ ያልገባኝ በማስመሰል ደጋግማ እንደዚያው እንድታደርግልኝ ስጠይቃት፣ ከንፈሯን ንክስ ታደርግና፣ «ወይ አንተ ደደብ ነህ፣ አለበለዚያም እኔ በትክክል ለማስረዳት አልቻልኩም» የምትል ትመስል ነበር።

አለቃው ከሁለት ሕንዳዊ ሴቶች ጋር በአጠገባችን አለፈ። ቢያንስ ወሥራ ሁለት ፓውንድ የሚመዘን አንድ አረንጓዴ እንሽላሊት ተሸክመው ነበር። የያዘው በቀስታ ፍላጻ ወግቶ ሲሆን፣ ወደ ኋላ መጥቼ በመበላት እንድተባበረው ጋበዘኝ። ላሊ አነጋገራችውና ከዚያም ትከሻየን ነካ በማድረግ ወደ ባሕሩ አመለከተኝ። የምትፈልግ ከሆነ አሁን ከላሊ ጋር መሐድ ትችላለህ ማለቱ እንደሆነ ተገነዘብኩ። ሦስታችንም ማለት ላሊ፣ የዘወትር የጀልባ ረዳቷና እኔ ሆነን ሔድን። ጀልባዋ የተሠራችው ከቡሽ ስለሆነ በጣም ቀላል ነበረች። በትከሻቸው ተሸከሚትና ወደ ባሕሩ ወስጥ እየተራመዱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገቡ። ሕንዳዊው አንድ ትልቅ መቅዘፊያ ይዞ ከኋላ በኩል ተቀመጠ። ላሊ እስከደረቷ ድረስ ውሃው ወስጥ ሆና ጀልባዋ እንድትረጋና ወደ ባሕሩ ዳር እንዳትመለስ ለመከላከል ደግፋለች። ጀልባዋ ላይ ወጣሁና በመካከል ተቀመጥኩ። ከዚያም ላሊ በአንድ እመርታ ጀልባዋ ላይ ዐረፈችና፣ ሕንዳዊው በመቅዘፊያው አንድ ኃይለኛ ግፊት ሰጣት። እየራቅን በሔድን መጠን ማዕበሎቹ እየተንከባለሉና በየጊዜው እያደጉ መጡ። ከባሕሩ ዳር ፫አንድ ሺህ አምስት መቶ ጫማ ርቀት መተላለፊያ ከሚመስል አንድ ቦታ ሁለት ጀልባዎች ዓሣ እያጠመዱ ነበር። ላሊ ጸጉሯን በቀይ ቆዳ ጠፍሮች ጠቅልላው ነበር። ሕንዳዊው እንደ መልህቅ የሚጠቀምበትን አንድ ገመጫ በረት ቁልቁል ሲሰድ፣ ላሊም አንድ ትልቅ ጡቡ በእጇ, እንደ ጨበጠች ገመዱን ተከትላ ወደ ውሃው አሽቀልቁላ ወረደች። ጀልባዋ በጣም ከልፋታ ስለነበረች በእያንዳንዱ ማዕበል ላይ ከፍ ዝቅ ትል ጀመር።

ከሦስት ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ላሊ ብቅ ጥልቅ፣ ብቅ ጥልቅ ስትል ቆየች። በእጠቃላይ ጥልቀቱ ሃምሳ ጫማ መሆኑ ይኖርበታል። ምክንያቱም ሥሩን ማየት አይቻልም። በየጊዜው አይስተሮች ይዛ በወጣች ቁጥር ከረጢቷን ሕንዳዊው ወደ ጀልባው ይገለብጥላታል። ሦስት ሰዓት መሉ ላሊ አንድ ጊዜ እንኳ ጀልባዋ ላይ አልወጣችም። ብቸኛው ዕረፍቷ ለአምስት ወይም ሰዐሥር ደቂቃ በጎን መንጠላጠል ነበረ። ቦታችንን ሁለት ጊዜ ቀየርን። በሁለተኛው ቦታ አይስተሮቹ ትላልቆችና ይበልጥ ብዛት ያላቸው ነበሩ። ከዚያም ወደ ባሕሩ ዳር ለመመለስ ላሊ ጀልባው ላይ ወጣችና ማዕበሉ እየገፋ አደረሰን። አንዲት ሕንዳዊት ባልቴት ትጠብቀን ነበር። እርሷና የላሊ የጀልባ ሪዳት አይስተሮቹን ተሸከመው ወደ አሸዋው ዳር አሻገሯቸው። አይስተሮቹ በሙሉ እዚያ ከተከማቹ በኋላ ላሊ አሮጊቷን ወደ ጎን አገለለችና ራሷ መፈልቀቅ ጀመረች። አንድ ሉል ከማግኘቷ ብፊት በጩቤዋ ጫፍ በመጠቀም ሠላሳ ያህል አይስተሮችን ፈለቀቀች። በዚያ ወቅት እኔ ቢያንስ ሁለት ደርዘን የሚሆኑትን በልቼ ነበር። የምትፈለቅቃቸው ረጋ ብላ በማተኮር ሲሆንና መጠናቸው ሸምበራ የሚያካክል ትላልቅ ዘሮች ነበሩ። አቤት ሲያብለጨልጩ! ተፈጥሮ ልዩ ልዩ ዓይነት ቀለማትን አድላቸዋለች። ላሊ አንድ ሉል አነሣችና አፏ ውስጥ አስገብታ በማስቀመጥ ትንሽ ጊዜ አዚያው አቆየችና ከዚያም በማውጣት አፌ ውስጥ ከተተችው። በመጨረሻም፣ በጥርሶቼ መካከል ፈረካከሼ እንድውጠው ስለ ፈለገች፣ አገጯን በማንቀሳቀስ እንደዚያው እንዳደርግ አመለከተችኝ። አምቢ አልኩ፣ ይሁንና ስትማፀን በጣም ማራኪ ከመሆኗ የተነሣ መጨረሻ ላይ የጠየቀችኝን ፈጸምኩ። አራት ወይም አምስት አይስተሮች ፈለቀቀችና አንድውጣቸው ሰጠችኝ። የተፈረካከሱትን ሉሎች ቁልቁል እንዲወርዱ ያደርጓቸዋል። ከዚያም ልከ እንደ ሕፃን ልጅ አፌን ከፈተችና ሽርፍራፊዎቹ በጥርሶቼ

t.me/OLDBOOKSPDF

መካከል ቀርተው እንደሆነ ፈተሸች። በመጨረሻ ሥራውን ለቀሩት ሁለቱ ትተንላቸው እኛ ሔድን።

እዚህ ከመጣሁ አሁን አንድ ወር ሆኖኛ። ያወቅኩበትም ምክንያት እያንዳንዱን ቀንና የዕለቱን ስም በአንድ ቁራጭ ወረቀት ምልክት እደርግ ነበር። ቀደም ሲል መርፌዎቼና ቀለሞቼ መጥተውልኝ ነበር። ዛሬ፣ አለቃው፣ ሦስት ምላጫች ነበሩት። ቀይ ሕንዶች ጸም ሰለሌላቸው ለመላጫ አልተጠቀመባቸውም፣ ግን ጸጉሩን ይከረከምባቸው ነበር። ላሊ ሰውነቱ ላይ ያለውን ጸጉር በሙሉ ነቅላዋለች። አንድ ሰዓት፣ ቶሎ ብላ ትነቅላትና ከመድ ጋር በተደባለቀ የባሕር ቅጠል ጭማቂ ትፈገፍገኛለች። ይህም ዕድገቱን ለመግታት መስለኛል። ባለ ብዙ ቀለም ላባዎች አክሊል የደፉ የአንድ ሕንዳዊ ምስል በአለቃው ክንድ ላይ ወቀርኩላት። በጣም ከመደሰቱ የተነሣ ከዚህ የበለጠ አንድ ትልቅ የነብር ጭንቅላት በደረቱ ላይ ሳልወቅርለት ማንንም ሰው እንዳልወቅር ሲያስረዳኝ ፈለገ። ከግዙፉ ጥርሱ ጋር የእኔን ነበር ይፈልጋል። ሆኖም ይህን አስደናቂ ጭንቅላት አስቱካክሎ ለመቅረፅ ቸሎታ ስለሌለኝ አማቀኝ።

የጓጅራ ቀይ ሕንዶች የሚኖሩት ከጠረፉ እሰከ ተራራዎቹ ሥር በሚኘ ሜዳ ላይ ነበር። በተራራዎቹ ደግሞ ሞቲለንስ የተባሉ ሌሎች ማኅበረሰቦች ይኖራሉ። ከዓመታት በኋላ ከአነርሱ ጋር የንግድ ግንኙነት ለመመሥረት በቅቼ ነበር። ቀደም ብየ እንደ ገለጽኩት፣ የጓጅራ ሕንዶች ከሠለጠነው ሕዝብ ጋር የሚገበያዩት ዕቃን በዕቃ ልውውጥ አማካይነት ብቻ ነበር። የጠረፎቹ ሕንዶች ሱሎቻቸውንና ከነነፍሳቸው ያሉ ኤሊዎችን ለነጮቹ ሕንዶች ያቀርባሉ። አንዳንዶች ኤሊዎች እሰከ አራት መቶ ፓውንድ ይመዝናሉ። በኦሪኖኮ ወይም በማሮኒ የሚገኙትን ከብደትና መጠን ግን ፍጹም አይደርሱባቸውም። እነዚያኞቹ አንዳንድ ጊዜ ከብደታቸው አንድ ሺ ፓውንድ ሆኖ የመሸፈኛ ልብሳቸው ርዝመት ስድስትና ሰባት ጫማ፣ ስፋቱም ከሦስት ጫማ በላይ ይሆናል። ኤሊዎች አንድ ጊዜ በጀርባቸው ከተንጋለሉ አይገለበጡም። ምግብም ሆነ መጠጥ ሳያገኙ ሦስት ሳምንት ሙሉ በጀርባቸው ተገልብጠው በሕይወት እንደቆዩ አ፫ቻለሁ። ትላልቆቹ አረንጓዴ አንሽላሊቶች ለሙበል በጣም ጥሩዎች ነበሩ። ሥጋቸው በጣም የለሰለሰ ሆኖ እንቁላሎቻቸውም በፀሐይ መሞቅ አሸዋ ውስጥ ሲቀቀሉ ልዩ የሆነ ጣፋጭ ጣዕም ነበራቸው። ሃለመብላት የሚቀፉት መልካቸውን ሲያዩዋቸው ብቻ ነበር።

ላሊ በየጊዜው እይስተር ለማጥመድ በሐይች ቁጥር የምትካፈላቸውን ሉሎች ለእኔ ወደ ቤት ታመጣልኛለች። ሁሉንም በአንድ የአንጨት ቆሬ ውስጥ አስቀምጣቸዋለሁ። አንድ ባዶ የከብሪት ሣጥን ውስጥ ለብቻ ለይቼ ያስቀመጥኳቸው ሁለት ሐምራዊ፣ ሦስት ጥቁሮችና ሰባት በጣም ልዩና ቆንጆ የሆኑ የብረት ግራጫ ቀለም

t.me/OLDBOOKSPDF

ያላቸው ሱሰኞች ነበሩ። በተጨማሪ ቅርፀም ሆነ መጠኑ እደንጓሬ የሚመስል አንድ ልዩ የሆነ ሉል ነበር። አንዳቸው በሌሎቹ ላይ የተደራረቡበት ሦስት ዓይነት ቀለማት ያንጸባርቃል። እንደ አየሩ ጠባይ ገር የሆነው ቀለም ጥቁር፣ ወይም የተወለወለ ንጹሕ ብረት፣ አለበለዚያም ብርማ ሐምራዊ ይሆናል። እነዚህን ለመሰሉ ሱሰኞችና አልፎ አልፎ ለሚይዟቸው ኤሊዎች ምስጋና ይድረሳቸውና ጎሣዎቹ ምንም የሚጎድላቸው ነገር የለም። አንዳንድ የማይጠቅሙ ነገሮች አንዳሏቸውም ግልጽ ነበር፣ ግን ሊጠቅሟቸው የሚችሉ ደግሞ ይጎድላቸዋል። ለምሳሌ በመንደሩ ውስጥ አንድም የፊት መስታወት አልነበረም። በማምት ዐሥራ አምስት ኢንች ተኩል ካሬ ስፋት ያላት በኒኬል የተለበደች አንዲት መስተዋት ከመርከብ ስብርባሪ ውስጥ አግኝቼ ሰለነበር፣ ጺሜን ለመላጨት ወይም ራሴን ለማየት ልጠቀምባት ችያለሁ።

ራሴን ለወዳጆቹ የማሳየው በጣም ዝቅ በማድረግ ነበር። የአለቃውንም ሆነ ሌላው ቀርቶ ከአርሱ ሥልጣን እንኳ ዝቅ ያሉትን ከመንደሩ ሦስት ማይል ወደ መሐሉ ገባ ብለው በአባቦች፣ በሁለት ፍየሎች፣ በአንድ ደርዘን በጎችና በሐያ ዶሮዎች ተከብበው ብቻቸውን የሚኖሩትን ሽማግሌ ሕንዳዊ ከብር የሚያንኳስስ ምንም ነገር ፍጹም አልሠራም። በጓጅራ ለሚገኙት መላው መንደሮች ጠንቋይ ነበሩ። በዚህም የተነሣ ስለ እኔ ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው አደረግኩ። በሁለተኛው ወር መባቻ ላይ በማንኛውም ሰው ዘንድ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነትን አግኝቼ ነበር።

በማውቃቸው ሁለት መንደሮች ውስጥ ፍየሎች ሆኑ ዶሮዎችና በጎች አላየሁም። የቤት እንስሳዎች አርቢ ለመሆን መብት ያላቸው ጠንቋዩ ብቻ ይመስላሉ። አያንዳንዷ ሕንዳዊት ሴት ወዲያው የተያዙ ዓሣዎችን፣ በጋለ ድንጋይ ላይ ጋግራ ከትኩስ የበቆሎ ቂጣዎች ጋር በቅርጫት አድርጋ በጭንቅላቷ በመሸከም በየቀኑ ጧት ወደ ቤታቸው ብቅ ትላለች። ዘወትር ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ ዕርጎና እንቁላሎች ሰጥተዋት ትመለሳለች። ጠንቋዩ መጥቼ እንዳያቸው ስለፈለጉ፣ ሦስት እንቁላሎችና አንዲት የተወለወለች የአንጨት ቢላዋ ላኩልኝ። ላሊ ግማሽ መንገድ ድረስ ሸኝቸኝና፣ ከዚያም አንድ ትልቅ ቁልቋል ጥላ ሥር ልትጠብቀኝ ቀረች። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጠንቋዩ ቤት ስጠራ፣ የእንጨቱን ቢላዋ እጄ ላይ አስቀመጠችና፣ መከተል የሚኖርብኝን አቅጣጫ በከንፈ አሳየችኝ።

ሕንዳዊው አዛውንት የሚኖሩት ጸጉሩ ከውስጥ በኩል ደሆነ በጣም የሚያስጠይቁ ቆሻሻ የሞላበት ከከብት ቆዳ በተሠራ ድንኳን ውስጥ ነበር። ዘወትር እሳት የሚነድበት፣ ሦስት ጉልቻዎች ዙሪያውን የተቀመጡበት አንድ ምድጃ አለ። የሚተኙት በተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ ላይ ሳይሆን ከመሬት በላይ ሦስት ጫማ ከፍታ ባለው ከባላዎች በተሠራ አልጋ ላይ ነበር። ድንኳኑ በጣም ሰፊ ቢሆንም ከነፋሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

አቅጣጫ በትንሽ ቅርንጫፎች ከመከለሉ በስተቀር ምንም ማድግዳ አልነበረውም። ያን ጊዜም እባቦቹን አየኋቸው። አንደኛው ቁመቱ ዐሥር ሜማ ሆኖ ውፍረቱ አንድ ከንድ የሚመጥን ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ርዝመቱ ሦስት ሜማ ሆኖ በጭንቅላቱ ላይ አንድ ቢጫ ባሳ ምልክት ነበረበት። «ዶሮዎቹንና እንቁላሎቹን እነዚህ እባቦች እንዴት አልጨረሷቸውም!» አልኩ ራሴን በራሴ። ፍየሎች፣ ዶሮዎች፣ በጎችና አንድ አህያ፣ሁሉም አበረው አንድ ድንኳን ውስጥ እንዴት መኖር እንደቻሉ ለመመራመር ከአቅም በላይ ሆኖብኝ ነበር። ሽማግሌው ሕንዳዊ ደጋግመው ተመለከቱኝና ከዚያም ላሊ ወደ ቁምጣ ሱሪ ለውጣልኝ የነበረውን ሙታንታየን አንዳወልቅ ጠቀሱኝ። ራቁቴን ወደ መሆን ደረጃ እንደ ተቃረብኩ፣ ከድንጋይ ጉልቻዎቹ በአንዱ ላይ እንድቀመጥ አመለከቱኝ። እሳቱ ላይ አንድ አረንጓዴ ቅጠል ሲጨምሩበት እንደ ሜንታ የሚሸት ወፍራም ጪስ ተንቧለቀ። የሚቀጥሉትን ዐሥር ደቂቃዎች በአየር መታረፌ መስሎኝ ተፈጨነኩ። ከዚያም ቁምጣ ሱሪዬን አታጠሱና አንድ ከበግ፣ ሌላው ከአጅ ጓንቲ ከለሰለሰ የአባብ ቆዳ የተሠራ ሁለት የሕንዳውያን ሽርጦች ሰጡኝ። ከፍየል፣ ከበግና፣ ከአባብ ቆዳ አብረው በተጎነጎኑ ጠፍሮች የተሠራ አንድ አምባር ደግሞ በክንዴ ዙሪያ አሠሩልኝ። ሰዓቱ አራት ኢንች ሆኖ ማሠሪያው ባስፈለገ ጊዜ ለመፍታትና ለማሠር የሚመች አንድ አምባር ነበር። በጠንቋዩ የግራ ታፋ ላይ መጠኑ አንድ ጠገራ ብር የሚያክል ቁስል በገንቦች ተሸፍኖ እየሁ። በየጊዜው ያለማቋረጥ አሽ! አሽ! እያሉ ያባርሯቸውና፣ በጣም ሲያስቸግሯቸው ደግሞ በቁስሉ ላይ አመድ ይነሰንሰብታል። ሕጋዊ የሆነው የሳሳ አባልነቴ ሥርዓት ተፈጸመና ለመሔድ በመነሣት ላይ እንዳለሁ፣ ሌላ የእንጨት ብላዋ አበረከቱልኝ። ይህችኛዋ ሊያዩኝ ሲፈልጉ ከምጠራበት ከሌላዋ የእንጨት ቢላዋ አነስ ያለች ነበረች። ላሊ በኋላ እንደገለፀችልኝ እኔ ላያቸው ስፈልግ የምልክላቸው እነስተኛዋን ቢላዋ ነበር። እርሳቸው ሊያዩኝ ፈቃደኛ ከሆኑ የሚልኩልኝ ትልቋን ነበር። ከሽማግሌው ሕንዳዊ በምለያይበት ወቅት ነበረ ፊታቸውና አንገታቸው እንዴት እንደተጨማደደ የተመለከትኩት። በጎደንዱት ጉንጮቻቸው ውስጥ የቀሯቸው አምስት ጥርሶች ብቻ ሲሆኑ ሦስቱ ከታችኛው አገጫቸው፣ ሁለቱ ደግሞ ከላይኛው በኩል ከፊት ለፊት ነበሩ። የዐይኖቻቸው ቀለሞች እንደማንኛውም ሕንዳዊ ግራጫ ቢሆንም ቆቦቻቸው ከመክበዳቸው የተነሳ ሲከድኗቸው ልክ ሁለት ዱቡልቡል ኳሶች ይመስሉ ነበር። የቅንድብ ጸጉርም ሆነ የዐይን ሽፋል የላቸውም። ጥቁሩ ጸጉራቸው ግን በትክክል ተከርክሞ ወደ ትክሻቸው ቀጥ ብሎ የወረደ ነበር። ከፊት ለፊታቸው እንደማንኛውም ሕንዳዊ ቅንድባቸው ሥር ሲደርስ በትክክል ተከርክሟል። ነፋስ የሚነፍሙ መቀመጫዬ ጤና እየነሳኝ ወደ ቤት ጉዞ ጀመርኩ። እንደ ቂል መሆኔም ተሰማኝ። ግን ይህንን ሁሉ የማደርገው ለማምለጥ ስል ነበር፣ አይደለም እንዴ? ስለዚህ በሕንዶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማፌገዝ የለብኝም። ከትንሽ ጊዜ ምቾት ማጣት ይልቅ ነጻ መሆን ይበልጥ ዋጋ አለው። ላሊ ሜርቆምቼን ስትመለከት ከባሕር እንደምታወጣቸው ሉሎች የነጡት ጥርሶቿን ገለጥ አደረገችና ሣቁች። የቆዳ አምባሬና ከአባብ ቆዳ የተሰራውን ሜርቆዬን እየመረመረች በጢሱ ፈተና ውስጥ ማለፌን ለማረጋገጥ ጠረኔን አነፈነፈች። ቀይ ሕንዶች በጣም ከፍተኛ ደረጃ የሆነ የማሽተት ተሰጥኦ እንዳላቸው መግለጽ ይገባኛል።

ከዚህ ኑሮ ጋር እየተላመድኩ ስለነበር ምናልባት ብዙ ጊዜ ከቆየሁ ለመሄድ ያለኝን ምኞት ችላ እለው ይሆናል ብዬ ተጠራጠርኩ። ከማህበረሰቡ አኗኗር ጋር ይበልጥ ንቁ ተሳትፎ ያሳያል በሚል ተሰፋ ላሊ አዘውትራ ትከታተለኛለች። ለምሳሌ ዓሣ ለማጥመድ በሔድኩበት ወቅት ጀልባዋን እንደ'ት እንደምቀዝፉትና እንዴት አድርጌ በዘዴ እንደምቆጣጠራት ተመልከታለች። ከዚህ በመነሳት የሉል ማደኛ ጀልባዋን ይይዝልኛል ወደ ሚለው ሐሳብ ተሸጋገረች። እኔ ግን ማድረግ አልፈልግም። በመንደሩ ከሚገኙት ኮረዳዎች ላሊ የታወቀች ዋናተኛ ነበረች። ምክንያቱም ወደ ጥልቅ ባሕር እየወረደች በብዛት ሆነ በመጠን ከሌሎች የተሻሉ አይስተሮች ይዛ ትመለሳለች። ይሁንና የጀልባዋ ረዳት ወጣት ሕንዳዊም የአለቃው ወንድም ነበር። እኔ ላሊን ወደ ባሕር ብወስዳት እንድ መጥፎ ድርጊት ፈፀምኩበት ማለት ሰለሆነ፣ ማድረግ አይኖርብኝም።

ላሊ ምንጊዜም ቢሆን በአንድ ሐሳብ ተመስጪ ካየችኝ አህጉን ልትፈልግ ሮጣ ትሄዳለች። አፍለኛዋ ልጃገረድም እየፈነደቀች ትመጣና በእኔ በር በኩል ትገባለች። ይህም አንድ አብይ ምክንያት ነበረው። በባሕሩ ትይዩ ከሚገኙ እስከ ትልቁ በር ድረስ አብረው ይመጡና ከዚያም ተለያይተው፣ ላሊ በራሷ በር ዞራ ስትገባ ዞራይማ በእኔ በኩል ትገባለች። የዞራይማ ጡቶች ከመንደሪን ብዙም አይበልጡም ነበር። ጸጉሯም ገና አጭር ስለሆነ፣ ቁመቱ አገጯ ሥር የቀረና ከፊት ለፊቷም ወደ ዐይኖቿ ቆበች ሊቃረብ ሲል ተስተካከሎ የተከረከመ ነበር። በየጊዜው አህጉ ጠርታት ወደ ቤት ስትገባ ሁለቱም ሜርቋቸውን አውልቀው በተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ ላይ ,ጋሰቅሉና ገላቸውን ይታጠባሉ። ትንቧን ስለማላቅፋት በዚሁ የተነሳ ተሰፋ እየቆረጠች ዘወትር ወደ ውጭ ትሄዳለች። አንድ ቀን ላሊን በመከከል አድርጎን ሦስታችን ተኝተን እንዳለን፣ ራቁቷን ከሆነችው ዞራይማ ጋር አንድተቃቀፍ አኔን ትታ ላሊ ብድግ አለችና በሴላ በኩል ተኛች።

አንድ ቀን የላሊ ጀልባ ቀዛፊ ጉልበቱ ላይ በጣም ከባድ መቆረጥ ደረሰበት። ወደ ጠንቋዩ ተሸከመው ወሰዱትና ነጭ አፈር ተነስንሶለት መጣ። በዚህ የተነሳ እኔ ከላሊ ጋር ጀልባ ቀዛፊ ሆኜ ሄድኩ። ጀልባዋን በግሩም ሁኔታ አሰገርኳት ግን ከተለመደው ቦታ ትንሽ ራቅ አድርጌ ወሰድኳት እኔን ጀልባው ውስጥ ከእርሷ ጋር በማግኘቷ ፈንድቃ ነበር። ከመዝለሷ በፊት ቅባት ተለቀለቀች። ከሥር በኩል በጣም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሞቱር ስለሆነ ያለጥርጥር ባሕሩ ቀዘቃዛ ነበር። የሦስት ዓሣ ነባሪ ጅራቶች ሽው ብሉ በአጠገቧን ሲያልፉ አሳየኋት፣ ግን ለእርሷ ስሜት አልሰጣትም። ከረጢቷን በግራ ጎንዷ ዙሪያ አንደጠመጠመች፣ በሰገባ ውስጥ ያለች ጩቤዋን መታጠቂያዋ ላይ አጥብቃ ነጀልባዋ ተፈናጠረችና በሚያስደንቅ ፍጥነት ወደ ጥቁሩ ውሃ ጠልቃ ጠፋች። የመጀመሪያው ዘላይዋ ለፍተኛ ብቻ ስለነበር ተመልሳ የመጣችው በጣም መጠነኛ ከሆኑ አይስተሮች ጋር ነበር። ከዚያም አንድ ሐሳብ ተከሠተልኝ። በጀልባዋ ውስጥ የተጠቀለለ አንድ ትልቅ የቆዳ ጠፍር ነበር። ወደ ታች ስትወርድ አንደኛውን ጫፉን ከከረጢቷ ጋር ቋጠርኩና ይዛው ወረደች። ሐሳቡ ገብቷት ስለነበር ረጅም ጊዜ እዚያው ቆየችና እንደኛ ወደ ላይ ስትመጣ ከረጢቱን አልያዘችውም። ከረጅም ጊዜ ዋና የተነሳ ደክሟት ስለነበር፣ በጀልባዋ ጎን ተንጠልጥላ ከረጢቱን እንድስበው አመለከተችኝ። እየደጋገሙ በመሳብ ላይ እንዳለሁ ምናልባት ከአንድ ኮራል ጋር ተጠላልፎ ይሆናል ድንት ቁጥ አለ። ወደ ታች ዘለለችና አለቀቀችው። በከፊል የሞላውን ከረጢት ጀልባው ውስጥ ገለበጥኩ። ግማሽ ቀን ሲሆን ሲል እያንዳንዳቸው ሃምሳ ጫማ ጥልቀት ያላቸው ስምንት ዋናዎች ካደረገች በኋላ ጀልባዋን ልንሞላት ተቃረብን።

በመጨረሻ አሷ ወደ ጀልባዋ ስትወጣ፣ በጠርዙ ላይ ውሃ ሊሰርግ ምንም አልቀረውም ነበር። መልህቁን ወደ ላይ ስትሰብ ወደ ታች ልንዘፈቅ ተቃረብን። እስክንዞር ድረስ ተንሳፍፋ እንድትቆይ ለማድረግ የመልህቁን ገመድ ከጀልባዋ ላይ ፈትተን በመቅዘፊያው ላይ ማሰር ነበረብን።

አሮጊቷና የላሲ ጀልባ ቀዛፊ አይስተሮችን ለመፈልቀቅ በአሸዋው ላይ እየጠበቁን ነበር። በአንታተታችን ተደንቀ ነበር። በከረጢቱ ላይ እንዴት ጠፍሩ አንደተቋጠረና ወደ ላይ ለመውጣት ፍጥነት እንዴት እንደጨመረላት ያደረግነውን ላሲ ገለፀችለት። ስለዚህም ነበር ተጨማሪ አይስተሮች ለመሰብሰብ የቻለችው። ከረጢቱን እንዴት አድርጌ እንደቋጠርኩትና በተለይም የቆርኪሣውን አስተጣሠር በጥንቃቄ መረመረ። ቁጥሩን ፈታና በመጀመሪያ ሙጫው አርሱን እንደዚያው ማድረግ ቻለ። በራሱ ኩራት ተሰማው።

አሮጊቷ ከአይስተሮቹ ውስጥ አሰራ ሦስት ሉሎች አገኘች። ላሊ አልፎ አልፎ የምትቀየው ይህንን ለመስለው የራሯ ከፍል አንጂ፣ የእርሷን ድርሻ ዘወትር ወደ ቤት የሚያመጡላት እነርሱው ነበሩ። በአሁኑ ወቅት ግን የመጨረሻዋ አይስተር እስክትፈለቀቅ ድረስ ቆየች። እኔ ሦስት ደርዘን ያህል መዋጥ አለብኝ እላለሁ። የላሲም አምስት ወይም ስድስት ይሆናል። አጣዎቹን አሮጊቷ ከፋፈለች። ሌሎቹም ሁሉም ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ትልቅ አተር የሚያካክሉ ነበሩ። ላሲ የእኔን ድርሻ ሦስቱን አነሳችና እጇ ላይ አደረጉትልኝ። እኔም ለቆበለው የጀልባ ረዳቷ ሰጠኋቸው። መጀመሪያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሊቀበል አልፈለገም፣ ግን እጁን በማስገደድ ፈለቀቅኩና ጣቶቹን በላያቸው ላይ ሸፈንኳቸው። ከዚያ ተቀበለ። ሚስቱና ሴት ልጁ ድርጊቱን በሩቅ ሆነው ይመለከቱ ነበር። በፊት ፀጥ ብለው የነበረው አሁን በሣቅ እየተንከተከቱ እኛ ዘንድ መጡ። እስከ ሳጅው ድረስ ደግፌ ለማድረስ ረዳሁት።

ይሆንን ሥራ ለሁለት ሳምንት ደጋገምን። በየጊዜውም ጉሎቹን ለቁስለኛው ሕንዳዊ አሰጣለሁ። አንድ ጊዜ አንድ አስቀረሁና፣ ወደ ቤት ስመለስ ላለ አንድትበላው ሰጠኋት። በጣም ደስ ብሏት ከሰዓት በኋላ ስትዘፍን ዋለች።

አልፎ አልፎ ነጩን ሕንዳዊ አጎበኘለሁ። ዞሪሎ ብዙ እንድጠራው ነገረኝ። ይህም በስፓኝ ቋንቋ « ትንሽ ቀበሮ» ማለት ነበር። የኑብሩን ሜንቅላት በደረቱ ላይ ለምን አንዳልወቀርከሳት አለቃው ጠይቆት እንደነበር ገለፀልኝ። በቂ ችሎታ ያለኝ ሰዓሊ አለመሆኔን አስረዳሁት። በመዘገበ ቃላቱ በመጠቀም፣ መጠኑ በእኔ ደረት ስፋት የሆነ አንድ የፊት መስታወት፣ የስዕል ወረቀት፣ ለስላሳ የስዕል ቡርሽ፣ አንድ ብልቃጥ ቀለም፣ ካርቦንና ያንንም ማሞኛት ካልቻለ አንድ ለስላሳ እርሳስ እንዲፈልግልኝ ጠየቅኩት። እርሱ ዘንድ የማስቀምጣቸው አንዳንድ ልብሶችና ተጨማሪ ሥስት ካኪ ሸሚዞች እንዲዘልኝ ጠየቅኩት። ስለ እንቶኒዎና ስለ እኔ ፖሊሶች ጠይቀውት እንደነበር ነገረኝ። አንቶኒዎ በእባብ ተነድፎ መሞቱንና፣ እኔም በተራራው ተሻግሬ ወደ ቬኔዚዌላ ውስጥ መግባቴን ነግሯቸዋል። ሴሎቹ ፈረንሣውያን አሥረኞችም ሣንታ ማርታ ወህኒ ቤት ውስጥ መሆናቸውን ወውቅ ነበር።

የዞሪሎም ቤት እንደ አለቃው ኣይነት ተመሳሳይ የሆኑ የጎሳዎቹ የባህል ቁሳቁሶች ነበሩበት። በሕንዳውያኑ ምርጥ ዲዛይኖቹ የተሸለመለሙ የሸክላ ድስቶች፣ በቀለም፣ በቅርጽም ሆነ በዲዛይን ብርቅ የሆኑ የሚያማምሩ ሰሂዎች፣ የእባቦች፣ የእንሽላሊቶች፣ የጎሽ ለስላሳ ቆዳዎች፣ ከጭ ወይም ከባለ ቀለም ሀረግ የተሰሩ ቅርጫቶች ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ የተሠሩት የራሱ ጎሳዎች በሆኑት ሕንዳውያን ነው። ይሁንና እነዚህ ሰዎች የሚኖሩት ከዚህ የሃያ አምስት ቀን ጉዞ የሚፈጅ አንድ ጫካ መካከል ነው። እርሱ የሰጠኝ የኮካ ቅጠሎችም የሚመጡት ከዚያው ነበር። የሚጫጫን ስሜት ሰይዘኝ አንዷን ማኘክ ነበረብኝ። ከዞሪሎ ጋር ልለያይ ስል ከሴሎቹ ጥያቄዎች በተጨማሪ በመዘገበ ቃላት የተረዳሁት በሁለት ወር ውስጥ ብዙ ቃላት አጥንቼ ስለነበር፣ አንዳንድ የስፓኝ ጋዜጦችና መጽሔቶችን ሊያመጣልኝ የሚችል እንደሆነም ጠየቅኩት። ስለ እንቶኒዎ ምንም ወሬ አልተሰማም ነበር። በጠረፍ ዘበኞችና በኮንትሮባንዲስቶች መካከል አዲስ ግጭት እንደነበረ ብቻ አውቋል። አምስት ዘበኞችና አንድ ኮንትሮባንዲስት ተገድለዋል፣ ጀልባዋ ግን አምልጣ ነበር።

ከፍሬ የሚጠመቅ አንድ እንግዳ መጠጥ በስተቀር በመንደሩ ውስጥ አንዲት

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠበታ እንኳን አልኮል ፍጹም አላየሁም። ዞሬሎ ዘንድ አንድ ጠርሙስ አረቄ ስመለከት መውሰድ የምችል እንደሆነ ጠየቅኩት። እይሆንም አለ። ከፈለግሁ እዚያው መጠጣት እንደምችል፣ አለበለዚያ መውሰድ እንደማልችል ነገረኝ። እስከዚህ ቂል አልነበረም።

በሚቀጥለው ቀን በገዛ ራሷ አርሱ ዘንድ ተመልሳ የምትመጣ መሆኗን በተማመነባት አንዲት የተውሶ አህያ ከዞሬሎ ተሰየሁ። ስድሳ ፓኮ ሲጃራዎችና በአንድ ትልቅ ሣጥን ባለቀለም ከረሜላዎች ይዣለሁ። ሳሊ ከመንደሩ ሁለት ማይል ወጣ ብላ ከአህቷ ጋር ሆና የእኔን መምጣት ትጠባበቃለች። በአሁኑ ወቅት የተለየ ሁኔታ አላሳየችም። እጆቻችንን በወገባቸን ዙሪያ አቅላልፈን ተመለስን። አሁንም አሁንም እየደጋገመች ቀም ትልና ከንፈሬን ሣም ታደርገኛለች። ወደ መንደሩ ስንደርስ አለቃው ቤት ሄድኩና ከረሜላዎችና ሲጃራዎቹን አበረከትኩለት። በባሕሩ ትይዩ ከሚገኘው በሩ ፊት ለፊት ተቀመጥን። በሽክላ ዋንጫ ሆኖ የቀዘቀዘ የፍራፍሬ ጭማቂ ቀረበልን። ሳሊ እጅጅን በጭኔ ዙሪያ ጠምጥማ ከኮኜ በኩል ስትቀመጥ፣ አህቷም እንደዚያው አደረገች። የከረሜላውም ፓኮ እፊታችን ተከፈተና ሴቶችና ሕፃናቱም እየተሽኮረመሙ ራሳቸውን ይጋበዙ ጀመር። አለቃው የዘራይማን ራስ ወደ እኔ አቅጣጫ ገፉ በማድረግ እርስዋም እንደ ላሊ ባል እንድሆናት መፈለግዋን ሊያስረዳን ሞከረ። ምናልባት ያልወደድኳት የዘራይማ ጡቶች አነስተኞች ስለሆኑ ይሆናል ብላ ለማመልከት ላሊ ጡቶቿን በእጆቿ ያዘቻቸው። በእምንታ አንገቴን ሳነቃንቅ ሁሉም ሰው ሣቀ። ዘራይማ ሐዘን ተሰምቷት እንደነበረ ግልጽ ነበር። ስለዚህ እጆቼን በአንገቷ ዙሪያ ጠመጠምኩና ጡቶቿን አሻሸሁላት። ይህም ደስ አሰኛት። ጥቂት ሲጃራዎች አጨስኩ። ሕንዶቹም በመጠኑ ሞከሩ ፣ ግን ለራሳቸው ትምባሆ ምርጫ በመስጠት ይኸኛውን ናቁት። የላሊን ከንድ ደግፌ እነሣሁና ሔድን። ላሊ ከእኔ ኋላ ዘራይማ ከአርሷ ቀጥላ ሆነን እንራመዳለን። አሳት ላይ ትላልቅ ዓሣዎች ጠበስን፣ እኔ በዚያ ላይ አምሰት ፓውንድ የሚመዝን አንድ ሎብስተር ጨመርኩበት። የፋሲካ ግብር ሆኖ ነበር።

የፊት መስታወቱና የሥዕል ወረቀቱ፣ ቅርፅ የማነሣበት መንደሬያ ወረቀትነ ጠይቄው ያልነበረ ቢሆንም በኋላ የጠቀመኝ አንድ ብልቃጥ ሙጫ፣ ብዙ ለስላሳ እርሳሶች፣ ቀለሞችና የሥዕል ቡርሾች መጡ። የፊት መስታወቱን በአንድ ሲባን አንጠልጥዬ በምቀመጥበት አቅጣጫ ልክ በደረቴ ትክክል አድርጌው ነበር። በዚያ የፊት መስታወት ውስጥ የተነቀስኩት የነበር ጭንቅላት ከነሙሉ ግርማው ቁልጭ አለ። ላሊና ዘራይማ በከፍተኛ አድናቆት ተውጠው ይመለከቱኛል። በመስታወቱ ያሉትን መስመሮች በቡርሹ እከተላለሁ። ግን ቀለሙ አቅጣጫ ሊስትብኝ ሲል መጫወት አስታወስኩ። ስለሆነም ቀለሙና መጫወት ቀላቀልኩና ማንኛውም ነገር ተስተካከለ። ከሦስት ሙከራ የአንድ ሰዓት ሥራ በኋላ ትከከለኛውን የነበር ጭንቅላት ቅርፅ በመስታወቱ ላይ ቀበቼ

t.me/OLDBOOKSPDF

ላሊ አሰታውን ፍለጋ ሄደች። ዞራይማ አጆቹን አነሳችና በጡቶቿ ላይ አስተመጠቻቸው። በጣም የከፉት ትመስላለች፣ ዐይኖቿ ግን በከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ተሞልተው ስለነበር በቀጥታ እዚያው ከወለሉ ላይ በጎጆዋ መካከል የፍቅር ጭውውት ጀመረግን። ተጠመጠመችብኝና ለመሐድ አልፈቅድልህም አለችኝ። ራሴን በዝግታ አላቀቅኩና በጎጆዋ ወለል ላይ ባለው አቧራ ተለውሼ ስለነበር ገላዬን ለመታሸብ ወደ ባሕሩ ወረድኩ። አርሷም ተከተሉችኝና አብረን ታጠብን። ጀርባዋን ስፈገፍግላት አርሷም ከንዶቹንና ባቶቹን አሻሸችልኝና ከዚያ በኋላ ወደ ቤት ተመልሰን ሐድን። ላሊን ልከ እኛ ተጋድመንባት ከነበረችው ቦታ ላይ ተቀምጣ አገኘናት። ንብቷታል። ብድግ አለችና እጆቿን በእንገቴ ዙሪያ ጠምጥማ ለሰለስ አድርጋ ሳመችኝ። ከዚያም የእህቷን ከንድ ያዘችና በእኔ በር በኩል እየመራች አውጥታ እንደገና ተመልሳ በራስዋ በኩል ወጣች። ወዲያውኑ ከቤት ውጭ አንድ ድምፅ ተሰማኝ። ነገሩ ምን እንደሆነ ለማየት ስወጣ፣ በእንድ ጉማጅ ብረት አንድ ቁዳዳ ለመክፈት ላሊ፣ ዞራይማና ሴሎች ሁለት ሴቶች ሆነው ሲታገሉ አገኘኋቸው። አራተኛ በር ሊከፍቱ መሆኑ ገባኝ። ግድግዳው እንዳይሰነጠቅ በጣሳ ውሃ እያረጠቡት ነበር። በሩ ወዲያውኑ ተሰርቶ አለቀና የረጋፈውን አፈር ዞራይማ ወደ ውስጥ ገፉችው። ከዚያ በኋላ የምትጠቀመውም በዚያ በር ሆነ ዳግመኛም ጥፀም የአኔን በር አልተጠቀመችበትም።

አለቃው በቆሰለው ወንድሙና በሌሎች ሦስት ሰዎች ታጅቦ መጣ። የወንድሙ ጉልበት ወደ መዳኑ ተታርቧል። በመስታወቱ ላይ ያለውን ሥዕል ተመለከተና የራሱንም ተመለከተ። ነበሩም በግሩም ሁኔታ "መሣሌና እንዲሁም የራሱን ፊት በመስታወቱ ውስጥ ማየቱ አስገረመው ግን ምን እንዳሰብሁ የተረዳው ነገር የለም። አሁን ሥዕሉ ስለደረቀ ፤በጠረጴዛ ላይ አስቀመጥኩትና፣ በላዩ ላይ መንደፊያ ወረቀት በማልበስ መስመሮቹን መሳል ጀመርኩ። በፍጥነት ተከናውኖ ነበር። ማንኛውንም መስመር ለስላሳው አርሳስ በትክክል ተከተለ። ሁሉም ሰው በመገረም አፍጥጦ እየተመለከተ ግማሽ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ እንደመጀመሪያው ግሩም የሆነ ንድፍ አነሳሁ። አያንዳንዳቸው በየተራ ንድፉን አያነሱ በደረቴ ላይ ካለው ነበር ጋር በማመሳከር መረመሩ። ላሊን በጠረጴዛው ላይ እንድትተኛ አድርጊያት ነበር። በእንድ እርጥብ ጨርቅ ላይ ሆዷን ጠርጊ በላዩ ላዩ አንድ የመንደፊያ ወረቀትና ቀደም ሲል ሥየው የነበረውን ሥዕል አደረግኩ። ትንሽ መስመሮች እንደነደፍኩ፣ ከሥዕሉ በጥቂቱ በላለ. ሆድ ላይ ዘልቆ መውጣቱ ሁሉንም ሰው በአድናቆት ዋጠው ከዚያ በኋላ ብቻ ነበር አለቃው ይህ ሁሉ ድካም ለእሱ መሆኑን የተረዳው።

እነዚህ በግብዝነት ለተሞላው የዘመኑ « ሥልጣኔ» ያልተጋለጡ ሰዎች ነገሮችን

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚመለከታቸው በዚያው በላዕላይ ገጽታቸው ነው። ደስተኞችም ሆኑ ሐዘንተኞች፣ ሣቂታዎችም ሆኑ አኩራፊዎች፣ ተግባቢዎችም ሆኑ ገለልተኞች፣ ስሜታቸውን የሚያንፀባርቁት አዚያውና ወዲያው ነው። የአነዚህ የጓጅራ ንጹህ ሕንዶች ምጥቀት የሚማርክ ነበር። በማንኛውም ነገር እኛን ይቀድሙናል። አንድ ሰው ከወደዱ፣ ያላቸው ማንኛውም ነገር የእርሱ ንብረት ነው። ማንም ሰው በቸልተኝነት ከተመለከታቸው ደግሞ እንጀታቸው ቁርጥ ይላል።

በመጀመሪያው ሥራዬ ከሥዕሉ ዳር ያለውን መስመር በአንድ ምላጭ ቀፍፌ ለማውጣት ወሰንኩ። ስለዚህ የውቅራቱ ዋና መስመር ወዲያውኑ ሊታይ ይችላል። በኋላ አንድ አሞር በትር ላይ በተሰኩ ሦስት መርፌዎች ውቅራቱን አደርጃለሁ። በሚቀጥለው ቀን የንቅሳቱን ሥራ ጀመርኩ።

ዛፉ ጠረጴዛው ላይ ተጋደመ። በመንደፊያ መረቀት ላይ ያለውን ሥዕል ወፈር ወዳለ ነጭ ወረቀት አስተላለፍኩና በአንድ ጠንካራ አርሳስ ቆዳው ላይ መቅረጽ ጀመርኩ። ቀደም ሲል የነጮ አፈር ጭታ ለቅልቁ እንዲደርቅ አድርጌያለሁ። ቅርጹ በሚገባ እስኪደርቅ ተውኩት። አሰቃው ሥዕሉን አበላሽ ይሆናል በሚሉ ፍርሃት ቃጥ ያለ የህዲድ ብረት መስሎ ጠረጴዛ ላይ በመዘርጋት፣ መፈራገጥ ቀርቶ ቅስቅስ እንኳ አይልም ነበር። እያንዳንዱን መስመር በምላጭ አሰነብጣለሁ። ደሙ ትንሽ ኩልል ሲል በየጊዜው አብሳለሁ። በጥቁር አርሳስ የነደፍኳቸው መስመሮች በሙሉ በቀጫጭን ቀያይ መስመሮች ከተከኋቸው በኋላ፣ በጠቅላላ ደረቱን ሰማያዊ የሕንድ ቀለም ቀባሁት። አንዳንድ ጠለቅ ብዬ ከሰነበጥኳቸው ቦታዎች ላይ ደሙ አጠበው እንጂ ቀለሙን ሁሉም ቦታ ተቀበለ። ሥዕሉ ደንቅ ሆኖ ተቀመጠ። ከስምንት ቀን በኋላ ዛፉ የተመኘው ትልቁ የነብሩ ጭንቅላት ከትልቁ መንጋጭላው ውስጥ ከሚታየው ሐምራዊ ምላሱና፣ ነጭ ጥርሱ፣ ጥቁር አፍንጫ፣ ጺምና ወይኖቹ ጋር በኩራት ታየ። እኔም በውጤቱ በጣም ተደስቼ ነበር። ቀለማ ቀለሞቹም ከእኔ ይበልጥ ደማቅ ነበሩ። የደረቀው ቁስል እንደተቀረፈ አንዳንድ ቦታዎችን እንደገና መጠቅጠቅ ይኖርብኛል። ዛፉ በጣም ተደስቶ ስለነበር፣ ለራሱ ሁለት ጎጆዎችና ለሌሎች አራት ጎጆዎችን በጠቅላላ ስድስት የሬት መስታወቶች እንዲያመጣልን ሦሬሎን ጠየቀው።

ቀኖቹ አለፉ፣ ከዚያም ሳምንቱ፣ ከዚያም ወራቱ፣ ሚያዝያ ሲገባ፣ ወደዚህ ከመጣሁ አራት ወር ሆነኝ። በጣሩም ሁኔታ ጤነኛና ጠንካራ ነበርኩ። በባዶ አግሬ መሐድ ከመልመዴ የተነሣ ትላልቅ እንሽላሊቶችን ለመፈለግ በማይል የሚቆጠር ርቀት ሳልደክም መጓዝ እችላለሁ። ያለ ሚስት የምታይበት ቀን አልነበረም። ላሊ ወደ አይስተር ኢደን ስትሔድ፣ ዞራይማ ከጎኔ ትገኛለች። ዞራይማ ወደ ውኋ ዋና ከሔደችም ላሊ አጠገቤ ትቀያለች።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመጀመሪያው የጠንቋዩ ጉበኑቱ በኋላ ዞሬሎ እንዲያመጣልኝ ጠይቂው የነበሩትን ሃይድሮጅን ፐር አክሳይድ፣ ጥጥ፣ ፋሻ፣ እንክብሎችና መጠነኛ ስቶቫርሶል፣ ቀደም ብዬ ሳልገልፅ ቀርቻለሁ። ሆስፒታል ውስጥ ሳለሁ አንድ ከባድ ወንጀለኛ ልክ የጠንቋዮን የሚያክል አንድ ቁስል ነበረበት። ጤና ረዳቱ ቻታል የስቶቫርሶል እንክብሎች ደቁሶ በቁስሉ ላይ ሲነሰንስበት ተመልከቼ ነበር። ዞሬሎ በራሱ ወጭ ከገዛው አንድ ተጨማሪ ቅባት ጋር መድሃኒቶቹ ደረሱኝ። ከዚያም ትንሽዋን የእንጨት ቢላዋ ወደ ጠንቋዩ ቤት ላከውና እርሳቸው የራሳቸውን ትልቁን በመላክ መለሱልኝ። መታከም እንዳለባቸው ለማሳመን ብዙ ከደከምኩ በኋላ፣ በትንሽ ቀናት ውስጥ ቁስሉ ከቀድሞው መጠን በግማሽ ሲቀንስላቸው፣ ህክምናውን በራሳቸው ፈቃደኝነት ለመቀጠል ተስማሙ። ሙሉ በሙሉ መዳናቸውን ለማየት እንድችል ትልቁን የእንጨት ቢላዋቸውን ላኩልኝ። ይሆን ግን እንዳደረገላቸው እስከ መጨረሻው ሰማንም ሰው አላወቀም።

አንድ ወንድ ልጅ ለዘጭ ተመለደለት። ሚስቱ ምዮ እንደጀመሪት ወደ ባሕሩ ዳር ወረደችና ከአንድ ትልቅ ቋጥኝ በስተጀርባ ለዋራ ቦታ ውስጥ ተደበቀች። ሌሎቹ የዛኩ ሚስቶች ቂጣ፣ የመጠጥ ውሃ፣ አምስት ፓውንድ የሚመዝን ግርድፍ ጥቁር ስኳር፣ በአንድ ትልቅ ቅርጫት ሞልተው ወሰዱላት። የተገላገለችው ከሰዓት በኋላ በዐሥር ሰዓት መሆን አለበት። ምክንያቷም ወደ መንደሩ መመለስ የጀመረችው ፀሀይ ከጠለቀች በኋላ ህፃኑ ወደ አየር ከፍ አድርጋ በመያዝ በደስታ አየጮኸች ነበር። ስለዚህ አርሷ ከመድረሷ በፊት ወንድ ልጅ መሆኑን ዛቱ ዐውቋል። ሴት ልጅ ብትሆን ኖሮ ወደ መንደሩ የምትመለሰው ነፃንሞን በብብትዋ ሥር በማቀፍ ድምጽዋን አጥፍታ ነበር። እንዴት እንደሚደረግ ሳሊ ነግራኝ ነው እንደዚህ መሆኑን ያወቅኩት። ህፃኑን ከፍ አድርጋ ሚስቱ ወደ ዛቱ ቀረበች። ዛቱ ግን ካለበት ምንም ሳይንቀሳቀስ እጆቹን ብቻ ዘርግቶ ይጮኽ ነበር። ወደ ፊት ትንሽ ተራመደችና ህፃኑን አነሳች። እንደነና ጮኸችና መልሳ ቆመች። ዛቱም እጆቹን እንደዘረጋ እየደጋገመ ጮኸ። በመካከላቸው ባለው የአንድ መቶ ሜጣ ርቀት መካከል አምስት ወይም ሰድስት ጊዜ የዚሁ ዓይነት የድምፅ ምልልስ አሰሙ። ዛቱ ከጎጆው በራፍ ፍፁም አልተነቃነቀም። መንደሩ ውስጥ በሚገኙት ሕንጻውያን በሙሉ እንደታጀበ ከዋናው ቤት ፊት ለፊት ቆሚል። እናትየዋ እንደነና ቆመች። አሁን ከአራት ወይም ከአምስት አርምጃ አትርቅም ነበር። ህፃኑን ወደ ፊት አነሳችና ለመጨረሻ ጊዜ ጮኸች። ከዚያም ዛቱ ወደፊት ተንቀሳቀሰና ህፃኑን ከብብቱ ሥር ይዞ ወደ ላይ አነሳው። ወደ ምሥራቅ ዘረና ደጋግሞ ህፃኑን አያጓነ ሦስት ጊዜ ጮኸ። ከዚያም ከቀኝ ከንዱ ወደ ደረቱ አጋድሞ ጭንቅላቱን በብብቱ ሥር በግራ ከንዱ በመሸፈን ታቀፈና ህፃኑን ይዞ ተቀመጠ። ወደ ጉልቱ በር ተመልሶ ወደ ኋላ ዞር ሳይል ጎጆው ውስጥ ገባ። ሁሉም

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰው ተከተለው፤ እናትየዋ በመጨረሻ ገባች። ከዚያም በቤቱ ውስጥ ያለውን የተጠመቀ የፍራፍሬ መጠጥ በሙሉ ተጋበዝን።

በሚቀጥለው ሳምንት ጧትና ማታ በዛፉ ጎጆ ፈትለፈት ያለውን መሬት ሕንዶቹ በውሃ እያራሱ በእግሮቻቸው ተረከዞች ሲደመድሙ ሰነበቱ። ያንን ሲያበቁ፣ አንድ ትልቅ የቀይ አፈር አውድማ ሰሩ። በሚቀጥለው ቀን ደግሞ አንድ ትልቅ የከብት ቆዳ ድንኳን ሲተክሉ ግብግ ሊደረግ መሆኑን ገመትኩ። የድንጋይ ጉልቻዎች በየቦታው እየተስተካከሉ ይቀመጣሉ፤ እያንዳንዱ ቀን ባለፈ ቁጥር የሚያድጉ የአርጥበና የደረቅ የሁለቱም እይነት እንጨቶች ይከመራል። አብዛኛው እንጨት ደረቅ፣ ነጭ፣ በጣም ለስላሳና የከረመ፣ ማዕበል የተፋው ነበር። ከምን ያህል ጊዜ በፊት እንደሆነ እማዚአብሔር ይወቀው፣ ከባህር የተሰፋ ሦስት ግዙፍ ግንዶች ነበሩ።

ለብልት መጥበሻ የሚያገለግሉ ተመጣጣኝ ቁመት ያላቸው ሁለት የእንጨት መንሾች ተዘጋጅተው በቦታው ተቀምጠዋል። አራት የተንጋለሉ ኤሊዎች፣ ሁለት በጎችና፣ ከሥላሳ በላይ ከነነፍሳቸው ያሉ ትላልቅ እንሽላሊቶች እንዳያመልጡ ጥፍሮቻቸው ታስረው ለአርድ ይጠባበቃሉ። ቢያንስ ሁለት ሺህ የኤሊ እንቁላሎችና፣ በሃያ ጋኖች የተጠመቁ አራት የሕንዶቹ ተወዳጅ የባህል መጠጦችም አሉ።

አንድ ቀን ጠዋት አስራ አምስት ሕንዳውያን በፊረስ ሆነው መጡ። እያንዳንዳቸው በእንቧታቸው ዘለበት አጥልቀዋል። ትላልቅ የሰሌን ባርኔጣ ደፍተው ጭኖቻቸውን፣ ባቶቻቸውን፣ እግሮቻቸውንና፣ መቀመጫቸውን ባዶ ያስቀሪችውን የሜርቆ ሽርጥ እንደታጠቁ እጅጌ የሌለው አንድ የበግ ቆዳ ጃኬት ለብሰዋል። እያንዳንዱ ሰው በመታጠቂያው ላይ የስካው ትልቅ ጩቤ ሲኖረው፣ ከእነርሱ ውስጥ ሁለት ብቻ ባለ ሁለት ኢፈሙዝ የአደን ጠመንጃ ይዘዋል። አለቃቸው ከሣዱ በጥቁር ቆዳ የተከፈፈ ግሩም ጃኬት ለብሶ፣ አንድ አውቶማቲክ ጠመንጃና ጥይት የታጨቀበት ዝናር ታጥቋል። ፈረሶቻቸው የማደነቁ ነበሩ። ትንንሾች፣ በጣም ቁልጣፎችና የማራጫ ጠቃጠቆ ሆነው ከእያንዳንዳቸው ኮርቻ በስተኋላ ሣር ቀርቅበዋል። ገና በርቀት እንዳሉ መምጣታቸውን ለማሳወቅ የጠመንጃ ሩምታ አሾነደነዱ። ከዚያም ሽምጥ በመጋለብ ወዲያው እኛ ዘንድ ከተጉ አሉ። አለቃቸው ትንሽ ኤድሜው ጠና ከማለቱ በስተቀር ከዛፉና ከወንድሙ ጋር በጣም አሳሳች የሆነ ተመሳሳይነት ነበረው። ከፈረሱ ወረደና ወደ ዛፉ ሔዶ እንዱ የሌላውን ትከሻ ነካ። ከዚያም ጎብኘው ዛፉን ከኋላው አስከትሎ ወደ ቤት ገባና ህፃኑን በእጅ ታቅፎ ወደ ውጭ ብቅ አለ። ሁሉም እንዲያየው ከፍ አድርጎ ያዘውና ዙሪ አድርጎት እንደነበረው በተመሳሳይ እንቅስቃሴ፤ ፀሀይ በምትወጣበት አቅጣጫ አነሳና ከብብቱ ሥር በግራ ከንዱ ደብቆ ወደ ቤት ተመልሶ ገባ። ፈረሰኞቹ ሁሉም ፈረሶቻቸውን አሰሩና የመመገቢያ ከረጢቶቻቸውን ፈትተው ሣር ሞሉላቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሚስቶቻቸው በአራት ፈረሶች በሚሳብ አንድ ትልቅ ሰረገላ ሆነው ዞራሎ እየነዳ ከሰዓት በኋላ ደረሱ። ቢያንስ ሃያ ሕንዳውያን ኮረዶችና ሰባት ወይም ስምንት ኮበሌዎች ነበሩ።

ዞራሎ ከመምጣቱ በፊት ከአለቃቸው ጭምር ከእንግዶቹ ጋር በሙሉ ተዋውቄ ነበር። ዛቶ የግራ እግሩ ትንሽ ጣት ተጠምዝዛ በሚቀጥለው ጣቱ ላይ መደረቧን አሳየኝ። የወንድሙና አሁን የመጣው አለቃ በትከከል ተመሳሳይ መሆናቸውንም ገለፀልኝ። ከዚያም በእያንዳንዳቸው አንድ ከንዳቸው ሥር ተመሳሳይ ማርያም የሳመቻቸው ምልክት አንዳለባቸው አሳየኝ። እንግዳውም እንደዚሁ ወንድሙ መሆን አለበት ብዬ ገመትኩ። የዛቶ ንቅሳት በተለይ የነበሩ ሞንቅላት ተደንቆለት ነበር። ሕንዳውያኑ ሴቶች በፊቶቻቸውና በእከላቶቻቸው ላይ በደማቅ ቀለም የተሸበረቀሩ ዲዛይኖች ነበሩባቸው። ላሊ ሰእንዳንዶቹ ከኮራል የተሰራ የአንገት ጌጥ፣ ለሌሎቹ ደማሞ የዛጎል የአንገት ጌጥ አደረጉላቸው። ከሁሉም በላይ ረጅም አቋም ያላትና ፅንቁ የምትመስል አንዲት ልዩ የሆነች ውብ ሴት አየሁ። ጸጉሯ የጥቁር ቡናማ ሆኖ ትላልቆቹ ወይኖቿ እውነተኛውን አረንጓዴ ፅንቁ የመሰሉና በጣም ረጃጅም በሆኑ ሽፋኖች የተከበቡ ነበሩ። ጡቶቿ በልዩ ጥበባዊ ቅርጽ ጉች ጉች ብለዋል።

ላሊ ከአርሷ ጋር አስተዋወቁኝ። ከዞራይማ፣ ዋንጫዎችና የሥዕል መቀቢያ የመሰሉ ብሩሾች ከያዙት አንዲት ሕንዳዊት ልጃገረድ ጋር ሆነን ወደ እኛ ቤት ሄድን። እንግዳዋ የመጣችው እኔ መንደር ውስጥ ያሉትን ሀንዳውያን በቀለም ለማስዜጥ ነበር። ውቢቱ ሕንዳዊት ላሊንና ዞራይማን ስታሸበርቁራቸው መመልከት ጀመርኩ። ብሩሾቹ ስንጥር እንጨቶችና ከጫፋቸው ላይ ትንሽ ቁራጭ ሱፎች የተጠቀለሉባቸው ሆኖ በተለያዩ ቀለሞች ውስጥ ትነክራቸው ነበር። እኔም ብሩሼን አወጣሁና ከላሊ እምብርት በመጀመር፣ ሁለቱ ቅርንጫፎቹ ከጡቶቿ ሥር የቀረ አንድ አተከልት ሳልኩኝ። ሐምራዊ አበባዎች ጨመርኩበትና የጡቶቿን ጫፎች ቢጫ ቀለም በመቀባት እንቡጦቻቸው ተገልጠው በከፊል በከፊል የፈኩ አበባዎች አስመሰልኳት። ሌሎቹ ሦስቱም በእነርሱ ላይ የዚያው ተመሳሳይ ዲዛይን እንዲሰራላቸው ተማፀኑኝ። ግን የዞራሎን ፈቃድ መጠየቅ ነበረብኝ። እነርሱ አስከተስማሙ ድረስ የፈለግከውን ማድረግ ትችላለህ አሉኝ። ራሴን ምን ጉድ ውስጥ ከተትኩ፣ እኛን ሊጎበኙ የመጡ ሕንዳውያን ኮረዳዎች ጡቶች፣ የራሳቸንንም ጭምር በሙሉ ከሁለት ሰዓት በላይ ስቀባ ቆየሁ። የእርስዋንም ልክ ለላሊ እንደሰራሁት አይነት እንዳደርግ ዞራይማ አስጠነቀቀችኝ። ይህ በዚህ እንዳለ ወንዶቹ በጎቹን መጥበሻው ላይ አያገላበጡ ሁለቱ ኤሊዎች በቅድሚያ ሥጋቸውን በትንሹ ቆራርጠው ከሰሉ ላይ ይጠበሰሉ። የኤሊዎቹ ሥጋ ደስ የሚልና እንደ ጥጃ ሥጋ ቀይ ነበር።

ድንኳኑ ውስጥ ከንብኒው አለቃና ከዛቶ ቀጥዬ እኔ ተቀመጥኩ። እኛን ቆመው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሚያስተናግዱት በስተቀር በሙሉ ወንዶች በአንድ ወገን፣ ሴቶች በሌላ ወገን ተቀመጡ። በዓሉ እስከ ሌሊቱ ማብቂያ ድረስ በአንድ የአንጨት ዋሽንትና በሁለት የበግ ቆዳ ከበሮቻቸው ሲጨፈር ቆይቶ ተፈፀመ። ሴቱም ሆነ ወንዱ ብዙዎቹ ሰክረው ነበር። እንደዚያም ሆኖ ረብሻ አይታይባቸውም። ጠንቋዩ አህያቸው ላይ ሆነው መጡ። ስር የሰደደው ቁስላቸው ከነበረበት ቦታ ላይ የቀረውን ሐምራዊ ጠባሳ ሁሉም ሰው በየተራ ይመለከት ጀመር። የተለመደው ቁሰል መዳኑ አስገርሟቸው ነበር። እንዴት ሊሆን እንደቻለ የምናውቀው ግን ዞራሎና እኔ ብቻ ነበርን።

የጎብኚዎቹ ጎሳዎች አለቃም የዛቱ አባት መሆኑን ዞራሎ ገለፀልኝ። ስሙ ጁስቶ ይባላል። ትርጉሙም « ሐቀኛ» ማለት ነበር። ለመላው የጓጅራ ጎሳ ፍርድ የሚያየው እርሱ ነበር። ከኢያፐስ፣ (አብረው ያሉ ሌሎች የቀይ ሕንዶች ጎሳዎች ናቸው) ጋር አለመግባባት ሲኖር፣ ጦርነት መግጠም እንዳለባቸው ወይም ነገሩን በሰላም ለማብረድ የሚቻል እንደሆነ ለመወያየት ይሰበሰባሉ። አንድ ሕንዳዊ ከሌላው ጎሳ አንዱን ከገደለው፣ ጦርነት እንዳያስከትል ሲባል ገዳዩ ለሟች ወገን ጉማ መክፈል ይገባዋል። ከተራራው ላይ የሚገኙት ጎሳዎች ብዙ የቀንድ ከብቶች ስላሏቸው አንዳንድ ጊዜ እስከ ሁለት መቶ የቀንድ ከብቶች ለመክፈል ይገደዳሉ። ግን መክላከያ ስለማይኩቡ ከከብቶቹ አብዛኞቹን ወረርሽኝ ይጠራርጋቸዋል። ሆኖም ዞራሎ እንደሚለው ይህም አንድ የራሱ ጠቃሚነት ነበረው። ያለ እነዚህ አልቂቶች ከአቅም በላይ ይረቡባቸዋል። በሽታ ያስራጫሉ በሚል ፍርሃት በኮሎምቢያም ሆነ በቬኔዙዌላ ውስጥ ከብቶቻቸው እንዲሸጡ አይፈቀድላቸውም። ቢሆንም በደጋማው ክፈል የተፋፋመ ኮንትሮባንድ ሽያጭ ስላለ ዞሮ ዞሮ ያው መሸጣቸው አይቀርም።

ጁስቶ በዞራሎ አማካይነት ወደ መንደሩ መጥቼ እንድነበኘው ጠየቀኝ። ከአንድ መቶ ጎጆዎች በላይ ሰላለው፣ ለላሊ፣ ለዞራይማ ና ለእኔ የግላችን ሊሰጠን፣ የሚያስፈልገንን ማንኛውንም ነገር ሊያዘጋጅልንም አስቧል። ለዚህም ጁስቶን ለመውቀር መያዝ የሚኖርብኝ የመውቀሪያ ቁሳቁሶችን ብቻ ይሆናል። በእጁ አንጓ ላይ ያሰረውን የቆዳ አምባር አውልቆ ሰጠኝ። ዞራሎ እንደሚለው ይህ አከበሮት ከፍተኛ ቁምነገር አዘሏል። ይኸውም ከእንግዲህ የምፈልገውን ትንሽዋን ነገር እንኳ ለመፈፀም እምቢ ለማለት ሃይል የለውም የሚል ነበር። ፈረስ ያስፈልገኝ እንደሆነ ጁስቶ ጠየቀኝ። ሣር ለማግኘት ትንሽ ችግር ስለሚገጥመኝ ቢያስፈልገኝም እንኳ በመቀበል ደረጃ ላይ አይደለሁም አልኩት። ምንጊዜም ሣር ሲያስፈልገን ላሊና ዞራይማ በፈረስ የግማሽ ቀን መንገድ ሔደው ማምጣት ብቻ ነው አለኝ። ረጅምና ጥሩ ሣር መሆኑንና ወዴት እንደሚገኝም ገለጸልኝ። ስለዚህ ፈረሱን ለመቀበል ተስማማሁና ባስቸኳይ አልከለሃለሁ አልኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከዘሪሎ ጋር ያደረግሁት ይህ ረጅም ጉብኝት ወደ ኮሎምቢያ ወይም ቬኔዙዌላ ለመሔድ ያለኝን አቅድ ለማንም ሰው እንደማይነግርብኝ በማሰብ ልገልጽለት አጋጣሚ ሆነኝ። ኮንትሮባንዲስቶቹ እንደሚሉት ከኮሎምቢያ ይልቅ በቬኔዙዌላ በኩል ያለው አዋላኝ ይበልጥ አደገኛ እንደሚሆን አዋየኝ። ቀደም ሲል መንገዱን አንድ ጊዜ ተጉዣበት ስለነበረና የተሻለ ምልከትም ስላለው፣ ወደ ኮሎምቢያ ገባ በማለት እስከ ሣንታ ማርታ አቅራቢያ ድረስ ራሱ አብሮኝ ለመሔድ ተስማማ። አንድ ሌላ መዘገበ ቃላት ወይም ከዚያ የተሻለ የተለመዱትን የስፓኝ ቋንቋ ዐረፍተ ነገሮች ገላጭ መጽሐፍ መግዛት እንደሚኖርብኝ መከረኝ። አነጋገሬን መቆራረጥ ጥሩ ዘዴ መሆኑንም ሐሳብ አቀረበልኝ። ምክንያቱም፣ የጀመርኩትን ንግግር እስከምጨርስ ድረስ ሰዎቹ ትዕግስታቸው ስለሚያልቅ ዐረፍተ ነገሩ ራሳቸው ይጨርሱልኛል፣ በዚህ መንገድ የቋንቋ ችሎታዬ ዝቅተኝነት አይታወቅብኝም። ስለዚህ መጻሕፍቱንና ሊያገኝ የቻለውን ጥሩ ካርታ እንደሚያመጣልኝና የኮሎምቢያ ገንዘብ ካስፈለገኝ የሉሎቹ ሽያጭ በእርሱ አማካይነት እንደሚፈፅም ወሰንን። የፊለግከው ይህንኑ እስከሆነ ድረስ ከአለቃው ጀምሮ እታች እሰካሉት ሕንዶች ውሳኔህን በሙሉ ይደግፉታል አለኝ። መሔዴን ሲያውቁ መቼም ያዝናሉ፣ ግን ወደ ራሴ ወገኖች ለመመለስ ያለኝን ምኞት ደግሞ እንደሚረዱልኝ እርግጠኛ ነኝ። ዋናው ችግር የላሊና የዘራይማ ነው። ከሁለቱ አንዱ፣ በተለይ ላሊ እንደምለያት ካወቁኝ ባንድ ጥይት ተኩሳ ልትገለኝ እንደምትችል ነበር የዘሪሎ ፍርሃት። ከዚያም ዘሪሎ አንድ ሌላ ነገር ገለጸልኝ። ዘራይማ አርግዛ ነበር። አንድም ነገር ልብ ብዬ ስላልነበር ከው አልኩ።

በመጨረሻም በዓሉ አበቃና ሁሉም ሰው ተበታተነ፣ ድንኳኑም ተነቀለ፣ ነገሮችም ወደ ነበሩበት ተመለሱ ወይም እንደቀድሞው መሰሉ። መልኩ ደስ የሚል የግራጫ ጠቃጠቆና ጭራው መሬት ሊነካ የተቃረበ፣ ጋማው የሚያስደንቅ ኮርማ መልክ ያለው ፈረሴ መጣልኝ። በሁኔታው ላሊና ዘራይማ ብዙም አልተደሰቱበትም ነበር። ላሊና ዘራይማ ፈረሱን ለመግደል የጠርሙስ ስብርባሪ ብናበላው ምን ይደርስበናል ብለው መጠየቃቸውን ሊነግሩኝ ጠንቋዩ ጠሩኝ። እንዳያደርጉ ነግረዋቸዋል። ይህን ካደረጉ፣ በሚጠበቀኝ ሕንዳዊ መልአክ ቁጣ የተሰባበረው ጠርሙስ እነርሱው ሆድ ውስጥ ገብቶ እንደሚጨርሳቸው አስፈራርተውልኝ ነበር። አሁን ፈረሱ ከአደጋ እንደተረፈ አውቀዋል። ግን መጠንቀቅ እንዳለብኝ መከሩኝ። ለመሔድ ስሰናዳ ካዩኝ በተለይ ላሊ በጠመንጃ ትገድለኛለች። እመለሳለሁ በሚል ተስፋ ለመሔድ እንዲለቁኝ ማድረግ እችላለሁ? አይሆንም። ምኞቴን ይፋ አላወጣሁም።

ዘሪሎ መጥቶ እንደ አስተርጓሚ በመሆን እንዲረዳን በመጠየቃቸው ጠንቋዩና እኔ በብዙ ነጥቦች ላይ ተወያየን። የዘሪሎ ማጠቃለያ፣ ሁኔታው በጣም አስጊ ስለሆነ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማንኛውንም ጥንቃቄ መውሰድ እንዳለብን ነበር። ወደ ቤት ሔድኩ። ዞሬሎ መጥቶ የተመለሰው በአንዲት ልዩ የምስጢር መንገድ ነበር። ጠንቋዩ ሁለታችንንም አንድ ላይ መጥራታቸውን ከመንደሩ ውስጥ ማንም ሰው አላወቀም።

እሁን እዚህ ስድስት ወር ስለሆነኝ፣ ጉዞዬን ለመቀጠል ተቻኩየ ነበር። አንድ ቀን ወደ ቤት ስመጣ፣ ላሊና ዞራይማ በካርታው ላይ አቀርቅረው አገኘኋቸው። እንግዳ የሆኑትን ምልክቶችና በተለይም ስሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ፣ የሚያሳዩትን አራት በሮች ምን እንደሆኑ ለመረዳት እየሞከሩ ነበር። ይህች ቁራጭ ወረቀት ከህይወታችን ጋር የተያያዘ አንድ ከፍተኛ ምስጢር ይኖራታል ብለው ጠርጥረዋል።

የዞራይማ ሆድ እየገፋ ይሔድ ጀመር። ይህም ላሊን ስላስቀናት የትኛውም ቦታ ብንሆን ምንም ደንታ ሳይኖራት፣ ቀንና ሌሊት በማንኛውም ሰዓት ከእርሷ ጋር የፍቅር ጭውውት እንዳደርግ ታስቸግረኝ ጀመር። ዞራይማም እንደዚሁ ጥያቄ ታቀርብባለች፣ ደግነቱ ግን ምን ይሆናል የምንፈጽመው ሌሊት ሲሆን ብቻ ነበር።

የዛቱን አባት ጆስቱን ለመጎብኘት ሔድኩኝ ላሊና ዞራይማ አብረውኝ መጡ። በእጋጣሚ የነብሩን ምስል አስቀምጬው ስለነበር ለእርሱ መወቀሪያ ልጠቀምበት ቻልኩ። ከውሃ ጋር አቀላቅሎ የኖራ ጭቃ ሰርቶ ነበርና የመጀመሪያው የቁስሉ ቅርፊት ቀደም ብሎ ስለ ረገፈለት፣ በስድስት ቀን ውስጥ ተነቅሶ አበቃ። ጆስቶ ከደስታው ብዛት ፊቱን በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ በመስታወት ይመለከተው ነበር። እኔ እዚያ በቆየሁበት ወቅት ዞሬሎ መጣ። አንድ ልዩ ፈረስ ስለ ፈለግኩ፣ ያለኝን ዕቅድ ለጆስቶ እንዲገልጽለት ፈቃድ ሰጠሁት። የጓጅራ ፈረሶች ኮሎምቢያ ውስጥ ዓይነታቸው የማይገኝና ሁሉም የግራጫ ጠቃጠቆ በመሆናቸው ሊያጋልጡ ይችላሉ። ጆስቶ ሦስት የኮሎምቢያ መጋልግ ፈረሶች ነበሩት። በሚገባ የተገራውን አንዱን መረጥኩና ራሱ ኩርቻውን ጭኖ፣ እርካቡን አስተካከለ፣ በብረት ልጓም ለጎመልኝ። ሕንዳውያኖቹ በሙሉ የሚጋልቡት ከአጥንት በተሰራ ልጓም ሌጣውን ነበር። ትክክለኛው የኮሎምቢያውያን አጫጫን ተሟላልኝና ፈረሱ ላይ ወጣሁ። ጆስቶ የጠፍሩን ዘብ አቀበለኝ። ከዚያም እያንዳንዳቸው የአንድ መቶ ፒሶ ዋጋ ያላቸው ሠላሳ ዘጠኝ የወርቅ መሐለቆች እኔ ፊት ቆጥሮ ለዞሬሎ ሰጠው። ለመሔድ እስክዘጋጅ ድረስ ዞሬሎ እንዲያስቀምጥልኝ ነበር። በተጨማሪም የራሱን አንድ አውቶማቲክ ዊንቼስተር ጠመንጃ ሊሰጠኝ ፈለገ ፤ ግን እምቢ አልኩት። እንዲያውም መሣሪያ እንደ ታጠቁ ኮሎምቢያ ውስጥ መግባት አንደማይፈቀድ ዞሬሎ ነገረኝ። ስለዚህ ጆስቶ ቁመታቸው ጣት የሚያክክል ሁለት ትናንሽ ፍላጻዎች በሱፍ እንደ ተጠቀለሉ ለእነርሱ ማስቀመጫ ከምትሆን አንዲት ትንሽ የቆዳ ቦርሳ ጋር ሰጠኝ። መርዛማ ፍላጻዎች እንደሆኑና መርዛቸውም ቅፅበታዊ ጉዳት የሚያደርስና እንደ ልብ የማይገኙ መሆናቸውን ዞሬሎ ነገረኝ። ዞሬሎ ራሱም እንድም

t.me/OLDBOOKSPDF

መርዛማ ፍላፃም አይቶ ወይም አማኝቶ አያውቅም። እነዚህንም አስከሄድ ድረስ እርሱ ሊያስቀምጥልኝ ነበር።

ለጹሁፉ ልባዊ ችሮታዎች ምሥጋናዬን እንዴት አድርጌ መግለፅ እችላለሁ? በዞሪሎ አማካይነት ስለ እኔ ሁኔታ አንዳንድ ነገሮች መረዳቱን ቢነግረኝም፣ በሁኔታዬ ብዙ ችግር ያሳለፍኩ ሰው ስለምመስል፣ ስለእኔ ያላወቃቸው አያሌ ጉዳዮች መኖራቸውን ገለፀልኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ያወቀው ነጭ ሰው እኔ ስሆን፣ ሁሉንም ነፍሶች የሚገምታቸው እንደ ጠላቶቹ አድርጎ ነበር። ግን ከእንግዲህ ወዲያ በሙሉ እንደሚወዳቸውና እኔን የመሰለ አንድ ሌላም እንደሚፈልግ ነበር።

« አዘህ በሚወዱህ ሰዎች ነው የተከበብከው። እናም ብዙ ጠላቶች ወደምታፈራበት ሀገር ከመሄድህ በፊት ጠለቅ አድርገህ ማሰብ ይኖርብሃል።» አለ።

ላሊና ዞራይማን ግን እርሱና ዛቶ እንደሚንከባከቧቸውና የዞራይማ ልጅ ወንድ ከሆነም ያው እንደተለመደው በሳሣው ውስጥ አንድ ከፍተኛ የክብር ቦታ ምንጊዜም እንደሚያገኝ ነገረኝ። « የአንተን መሐሪ አልፈልግም፣ የምትኖር ከሆነ በበዓሉ ሰሞን ያየሃትን ውብ ሕንዳዊት ኮረዳ አሰጥሃለሁ። በጣም የምትደነቅ ልጃገረድ ከመሆንዋም ሌላ እርሷም ትወድሃለች። እዘሁ ከእኔ ጋር መሆን ትችላለህ። ከአንድ ትልቅ ጎጆ ጋር የፈለግከውን ያህል ላሞችና ከብቶች አሰጥኃለሁ» አለ።

ከዚህ ድንቅ ሰው ተለይቼ ወደ መንደሬ ተመለስኩ። በጠቅላላው ጉዟችን ውስጥ ላሊ ጭጭ ብላ ነበር። ከመጋላው ፈረስ ከኋላው በኩል ኮርቻው እየፈገፈጋት ከእኔ ጋር ተፈናጥጣለች። ዞራይማም እንደዚሁ ከአንዱ ሕንዳዊ ጋር እየጋለበች ነበር። ዞሪሎ በሌላ መንገድ ወደ መንደሩ ሔደ። ምሽቱ ሲቃረብ ይቀዘቅዝ ጀመር። ስለሆነም ጹሁፉ ሰጥቶኝ የነበረውን የበግ ቆዳ ጃኬት ለላሊ አቀበልኳት። አንድም ቃል ሳትናገር እንዳለብሰት ብቻ አመለከተችኝ። ጃኬቱን ለበሰች፣ ግን ከዚያ ምንም አልተናገረችም። ፈረሱ ሶምሶማ መጋለብ ሲጀምር እንኳ እኔን ማቀፍ አልፈለገችም። ወዲያው ወደ መንደሩ እንደተመለስኩ የአከብሮት ሰላምታዬን ለማቅረብ ዛቶ ዘንድ ሔድኩ። ላሊ ፈረሱን ወደ ጎጆው ወስዳ አሰረችና ኮርቻውንም ሆነ ልጓሙን ሳታወልቅለት ዛር ፊቱ አስቀመጠችለት።

ሕንዶች ሲያኮርፉ በተለይ ሴቶቻቸው ፊታቸው በድን ይሆናል። አንዲት ንቅናቄ እንኳ አያሳይም። ምናልባት ዐይኖቻቸው በሐዘን ይዋኝ ይሆናል፣ ግን ፈጽሞ አያለቅሱም። አንዳንድ ጊዜ ይታትቱ ይሆናል፤ በቃ ይኸው ብቻ ነው። በዚያ ሌሊት በእንቅልፍ ላይ እንዳለሁ ስንቀሳቀስ ዞራይማን ሆዷ ላይ ጎሸምኳት መሰለኝ ሕመም ተሰማትና ጮኸች። ዳግመኛ እንደዚህ እንዳላደርግ፣ ተነሣሁና በለላ ተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ ላይ ተኛሁ። የተዘረጋው ገሞ ብሎ ስለነበር፣ በመውጣት ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳለሁ አንድ ሰው ውልብ ያለ መሰለኝ። እንቅልፍ እንደወሰደኝ መስያለሁ። ላሊ አንድ ጉቶ ላይ ተቀምጣ ምንም ሳትንቀሳቀስ ትጠብቀኛለች። ከትንሽ ጊዜ በኋላ የዞራይማን ከእህቷ ጋር አብራ መኖር ጠረኗ ነገረኝ። የብርቱካን አበባዎች በመጭመቅ ገላዋን መቀባት እንደለመደችና እነዚህንም የምትገዛው በትንሽ ከረጢቶች እየያዘች አልፎ አልፎ በመንደሩ ውስጥ ከምታልፍ አንዲት ሕንዳዊት ሴት ነበር። ብንን ስል ሁለቱም ኮረዳዎች አሁንም ከዚያው ሳይነቃነቁ ነበሩ። ፀሐይዋ ከፍ ስላለች ሁለት ሰዓት ሊሆን ተቃርቧል። ወደ ባሕሩ ዳር ይዣቸው ሔድኩና በአሸዋው ላይ ተጋደምኩ። ላሊ እንደ ተቀመጠች ቀረች። ዞራይማም እንደዚያው አደረገች። የላሊን ጡቶችና ሆዷን ባሻሸላትም እንደ እብነበረድ ረግታ ዝም አለች። ወደ አጠገቤ ሳብ አደረግኩና ልስማት ብሞክር ከንፈሮቿን ግጥም አድርጋ ዘጋቻቸው። ዘግየት ብሎ የጀልባ ረዳቷ ወደ ላሊ መጣ። የእንድ ጊዜ ግርማሜዋ ብቻ በቂው ነበር። ቀኝ ኋላ ዞረና ሔደ። በጣም ከባድ ችግር ላይ ወደቅኩ። የምወዳቸው መሆኔን ለማሳየት እነርሱን ከመሳምና ከማሻሸት በስተቀር ምን እንደማደርግ ማወቅ አዳገተኝ። ፀጥ እንዳሉ ቀሩ። ያለ እኔ ልንኖር ነው ብለው በማሰብ ይህን የመሰለ ሐዘን ሊሰማቸው መቻሉ አበሳጨኝ። ከዚያም ላሊ ተስፋ በቆረጠ ስሜት ሁለመናዋን ገላለጠችና እኔንም እንደርቧው ራቁቴን አስቀረችኝ። ለምን ይሆን? አድራጎቷ ከበስተጀርባው ምን ጉዳይ ይዟል? አንድ ነገር ብቻ ሊሆን ይችላል። እርሷንም እንዳስረግዛት ትፈልጋለች።

በዚያች ዕለት ጧት በላሊና ዞራይማ መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የመቀናናት ፍንጭ አየሁባቸው። በባሕር ዳር አንድ ሠዋራ ጉድባ ውስጥ ተኝተን ነበር። የዞራይማን ሆድና ጡቶች እያሻሸሁ፤ እርሷም ጀሮዎቼን ትነክሰኛለች። ላሊ ደረሰችና የእህቷን ክንድ ይዛ በማንሣት አጇን ወደ አበጠው የእህቷ ሆድ አሳልፋ አስነካችና ከዚያም በራሷ የተሸለገ ሽንቅጥ ሆድ ላይ አደረገችው። ዞራይማም፤ «ልከ ነሽ» በሚል አስተሳሰብ ብድግ ብላ ቦታውን ለእህቷ ለቀቀች።

በየቀኑ ሚስቶቼ ምግቤን ያዘጋጁልኛል፤ እነርሱ ግን ምንም ነገር አይቀምሱም። ለሦስት ቀን አልበሉም ነበር። ፊረሴን ጫንኩና በመጠኑ ከበድ ያለ አንድ ስሕተት ፈጸምኩ። ይህም ከአምስት ወር በላይ ስቆይ የመጀመሪያየ ጥፋት መሆኑ ነበር። በቅድሚያ እንደ ወትሮው ፈቃድ ሳልጠይቅ ወደ ጠንቋዩ ቤት ሔድኩ። ግማሽ መንገድ እንደተጓዝኩ በጉዳዩ አስብኩበትና በቱጥታ ርሳቸው ዘንድ ሳልቀርብ በሁለት መቶ ያርድ ርቀት ላይ ከድንኳናቸው ፊት ለፊት ወደ ኋላና ወደፊት እመላለስ ጀመር። በመጨረሻ አዩኝና እንድመጣ አንድ ምልክት አሳዩኝ። ላሊና ዞራይማ መበላት ማቆማቸውን በተቻለኝ ሁሉ ለመግለጽ ሞከርኩ። ከምንጠጣው ውሃ ውስጥ የምጨምረው ፍሬ የመሰለ አንድ ነገር ሰጡኝ። ወደ ቤት ሔድኩና ትልቁ የሸክላ እንስራ ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጨመርኩት። ብዙ ጊዜ ከውሃው ቢጠጡም፤ አውንም ገና አልበሉም። ላሊም አይስተር ማጥመጃን በተጨማሪ ተወችው። በመጨረሻው ከአራት ቀን ጾም በኋላ በደመነፍሲ እየዋኘች ሁለት መቶ ያርድ ያህል ከባሕሩ ዳር ርቃ ወጣችና እኔ የምበላችው ሠላሳ አይስተሮች ብቻ ይዛ ተመለሰች። የአነርሱ በኩርፊያ መኮራመት እኔንም ሰላም ስለነሣኝ እኔም እንደዚሁ መብላት ወደ ማቆሙ ተቃረብኩ። በዚህ ሁኔታ ሰድስት ቀን አለፈ። ከዚያም ላሊን ትኩሳት አመማትና አልጋ ላይ ወደቀች። በስድስት ቀናት ውስጥ የመጠጠችው ጥቂት ሎሚዎች ነበር። በቃ ይኸው ብቻ።

ዞራይማ ከቃትር በኋላ በቀን አንድ ጊዜ ትበላለች። ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝ። ላሊ አጠገብ ተቀመጥኩ። እንደ ፍራሽ እንዲሆንላት ሁለቱን ተንጠልጣይ የበርድ ልብስ አልጋዎች አጣጥፌላት ሰለነበር፣ በዚያ ላይ ተዘርግታ ጣሪያ ጣሪያውን ትኩር ብላ ትመለከታለች። አርሷን ተመለከትኩና የዞራይማንም የገፋ ሆድ ቃኘሁ። ከዚያም በትክክል ምን እንደሆነ ሳላውቅ ማልቀስ ጀመርኩ። ለራሴ ይሁን፣ ለአነርሱ፣ ማን ያውቃል? ያለማቋረጥ እንባዬ በጉንጮቼ ቁልቁል አሰኪጎርፉ ድረስ አለቀስኩ። ዞራይማ አይታ ማታለት ስትጀምር፤ ላሊ ዘወር አለችና አርሷም እንባዬን አየች። አመር ብላ በመነሣት በለዘብታ አየታለተች ከጭኖቼ መካከል ጉብታ ተቀመጠች። ሳመችኝና አቀፈችኝ። ዞራይማ እጇን በትከሻዬ ዙሪያ እንዳስቀመጠች ላሊ መናገር ጀመረች። ታታስታለች፣ ትናገራለች፣ ዞራይማም መልስ ትሰጣለች። በአንድ ነገር ምክንያት ላሊን የምትወቅሳት ይመስላል። ላሊ መጠኑ የእጇን ጭብጥ የሚያክል አንድ ጥቁር ስኳር በውሃ በጠበጠችና በሁለት ትንፋሿ ጨለጠችው። ከዚያም ከዞራይማ ጋር ወደ ውጭ ወጥተው ፈረሱን ሲሰቡ ለመስማት ቻልኩ። ወደ ውጭ ብቅ ስል ፈረሱ ኮርቻው ተጭኖና ተለጉሞ አገኘሁት። ዞራይማ የበግ ቆዳ ጃኬቴን ሰትሰጠኝ፣ ላሊም አንድ ተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ አጣጥፋ በኮርቻው ላይ አስቀመጠችልኝ። ዞራይማ በቅድሚያ ወጣችና ወደ ፈረሱ ጋማ ተጠግታ ከፊት ለፊት በሩቁ ተቀመጠች። ላሊ ከኋላ፣ እኔ በመካከል ተቀመጥኩ። እንድም ሰው ደህና ሁኑ ብዬ ሳልሰናበት፣ ከአለቃው አንካ ጋር ሳልነጋገር መሐዴ መስሎኝ በጣም ተደናግጬ ነበር።

ምናልባት ወደ ጠንቋዩ ዘንድ የምንሔድ መስሎኝ ሣመራ፤ ላሊ ልጓሙን ወደኋላ መለሰችብኝ። ግን አልነበረም፣ ልጓሙን አውንም እንደገና ላበችና «ዞሬሎ» አለች። ሰሰሆነም የምንሔደው ወደ ዞሬሎ ነበር። በመንገዶችን ላይ ወገቤን እቅፍ አያደረገች ብዙ ጊዜ ማጅራቴን ትስመኛለች። በግራ እጇ ልጓሙን ይዛ በቀኜ ዞራይማን አሻሻለሁ። ዞሬሎ ከባድ ጭነት ከተጫነ አንድ ፈረስና ሦስት አህዮች ጋር ከኮሎምቢያ ሲመለስ እኛም ከመንደሩ ደረስን። ወደቤት ገባን። መጀመሪያ ላሊ ተናገረች። ከዚያም ዞራይማ ቀጠለች።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዞሪሎ እንደሚለው ታሪካቸው እንዲህ ነበር። አልቅሼ እስክ ነበረበት ጊዜ ድረስ፣ እኔ ነጭ ሰው (ፈረንጅ) በመሆኔ ብቻ ስለ እርሷ ምንም የማላስብ መስሏት ነበረ። አንድ ቀን እንደምሔድ ዐውቃለች፣ ግን ለእርሷ ባለመንገሬ እንደ አታላይ ተቆጥሬ ነበር። እንደምትለው በጣም ጥልቅ የሆነ ቅሬታ ተሰምቷታል። ምክንያቱም፣ አንድን ሰው ለማስደሰት ችሎታ አለኝ ብላ ትገምት ነበር። ደስተኛ ሰው ደግሞ ቤቴን ትቼ ልሒድ አይልምና ይህን የመሰለ መከራ የሚሻበት ምንም ምክንያት የለም አለች። ዞራይማ ከሞላ ጎደል ያለችው እንዲሁ ነበር። ግን በተጨማሪ የፈራችው ልጇም ልክ እንደ አባቱ፣ ዝምተኛና ሕይወታቸውን ለእርሱ ለመስጠት አንኳ የሚዘጋጁትን ሚስቶችን የሚያስጨንቅ ውሽታም እንዳይሆን ነው። በደረስኩበት ቀን ነክሳኝ የነበረችውን ውሻ ለማምለጥ እንደ ሞከርኩት ሁሉ አሁን ደግሞ ከእርሷ የምሸሸው ለምን ይሆን?

እኔም ምላሽ ሰጠሁ፣ «አባትሽ ታመው ቢሆን ኖሮ ምን ታደርጊ ነበር ላሊ?»

«እርሱን ለማዳን ስል ቆንጥር ለቆንጥር እዞራለሁ።»

«እንደ ውሻ ብትታደኝና ከዚያም ብቀላሽን የምትወጭበት አንድ ዕድል ቢያጋጥምሽ ምን ታደርጊያለሽ?»

«በየትኛውም ቦታ ጠላቴን አፈልግና ሳገኘው፣ መላወስ እንኳ የማይችልበት ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ እቀብረዋለሁ።»

«ይህን ከፈጸምሽ በኋላ አንችን የሚጠብቁ ሁለት ግሩም ሚስቶች ቢኖሩሽ ምን ታደርጊያለሽ?»

«በፈረስ እመለሳለሁ።»

«እኔም የማደርገው እንደዚያ ነው።»

«ስትመለስ እኔ አሮጊትና አስቀያሚ ከሆንኩስ?»

«አሮጊትና አስቀያሚ ከመሆንሽ በፊት በጣም ቀደም ብዬ እመለሳለሁ።»

«አዎ፣ እንባዎች ከዐይኖችህ ጎርፈዋልና ያለ አንድ ምክንያት እንደዚያ ልትሆን አልቻልክም። በፈለግክበት ጊዜ መሔድ ትችላለህ፣ ግን በሁሉም ሰው ፊት በጠራራ ጸሐይ እንጅ እንደ ሌባ ተደብቀህ እንዳይሆን። ልብሶችህን አጥልቀህ ከቀትር በኋላ እንደ መጣህ ሁሉ ልክ እንደዚያው ሆነህ በዚያው ሰዓት መሔድ አለብህ። በተጨማሪም ቀንም ሆነ ሌሊት እኛን ማን እንደሚጠብቀን መናገር አለብህ። ዛቶ አለቃችን ነው፣ ግን እኛን የሚጠብቅ ሌላ ሰው ያስፈልገናል። ቤቱም የአንተው ቤት ሆኖ እንዲቆይና ዞራይማ ሆድ ውስጥ ያለው ወንድ ከሆነ፣ ከልጅህ በስተቀር አንድም ሰው ምንጊዜም ወደቤትህ እንዳይገባበት በግልጽ መንገር አለብህ። አንተ በምትሔድበት ቀን ዞሪሎ መምጣት አለበት። የምትለውን ነገር እንዲተረጉምልን ያስፈልጋል። »

ሌሊቱን ከዞሪሎ ጋር አሳለፍን። ሞቅ ያለና የሚያቀራርብ ወቅት ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

እነዚህ ንጹሕ ሴቶች የሚወጣው የሐዘን ድምፅ ከፍተኛ ፍቅር የተሞላበት ስለሆነ በሚቴን ከመጠን በላይ ይነካው ነበር። በፈረሱ ወደ ቤታችን ተመለስን፤ ግን ለዞራይማ ያድ ስንል ዝማ እያልን ነበር የምንሔደው። አዲስ ጨረቃ ከወጣች ከስምንት ቀን በኋላ ይሆናል። በዚያን ጊዜ ላሊ ማርገዟን ታውቅ ይሆናል። በመጨረሻው የጨረቃ ሰሞን የወር አበባ አላየችም። በዚህች ጨረቃ አሁንም የወር አበባ ማየት አለማየቷን ልታረጋግጥ ትፈልጋለች። ከዚያም ያረገዘች መሆኗን ታውቃለች። ልብሶቼን ዞሬሎ ሊወስድ ነው። ከዚያም «በጓጅራ ልማድ»፤ ራቁቴን ማለት ነው፤ የመሰነባበቻ ንግግር ካደረግሁ በኋላ አርሱ ቤት እለብሳለሁ። ለመጨረሻም በሩን ከፍቼ ወይም ዘግቼው መሔድ እንዳለብኝ ለማወቅ እንደነገ ልሔድ ዛሬ ማታ ሦስታችንም ወደ ጠንቋዩ ዘንድ ሔድን። ስንመለስ ለዞራይማ ሆድ ስንል የምንራመደው ዝማ እያልንና ያለምንም ትካዜ ነበር። በመንደሩ ወይን ብቻቸውን የተተው ዕቃዎች ተበለው መዘባበቻ ከሚሆኑ ይልቅ የአኔን መሔድ እንዲያውቁት መደረጉ ለእነርሱ የተሻለ ይሆናል። ዞራይማ ከወለደች በኋላ ከአንድ የጀልባ ረዳት ጋር ሆና ወደ ባሕር በመውጣት ብዙ ሱሎች ታስቀምጥልኛለች፤ ላሊም ሥራ ላለመፍታት ዓሣ በማጥመድ ረጅም ጊዜ ታሳልፋለች። ከዐሥራ ሁለት ቃላት በላይ የጓጅራ ቋንቋ አለማወቁ አሳዝኖኛል። በአስተርጓሚ ሊነገሩ የማይችሉ በጣም ብዙ ነገር ልገልጽላቸው በቻልኩ ነበር።

ወደቤት ደረስን። በመጀመሪያ ማድረግ ያለብኝ ዛዮን ማየትና መሔዴን በቅድሚያ ለአርሱ ባለመንገሬ የቱን ያህል እንዳዘንኩ ለመግለጽ ነበር። ዛዮም ልክ እንደ አባቱ ጨዋ ነበር። ልናገር አፌን ከመክፈቴ በፊት እጁን በአንጉቴ ላይ አስቀመጠና፣ «ኡዊሎ (ዝም በል)» አለኝ በቋንቋው። በሚቀጥሉት ዐሥራ ሁለት ቀናት አዲስ ጨረቃ ትጠበቅ ነበር። ከዚያ በኋላ ከምቆይበት ሳምንት ጋር ከመሔዴ በፊት ሐያ ቀን ይኖረኛል ማለት ነው። አንደገና ካርታውን እየተመለከትኩ የማልፍባቸውን ብዛት ያላቸው መንደሮች በማጥናት ላይ እንዳለሁ አስምሮዬ ጹሰቶ ተናግሮት ወደ ነበረው ቃል ተመለሰ። ወዴትስ ሔጄ ይበልጥ ደስተኛ እሆናለሁ? እዚህ በሁሉም ሰው ዘንድ ተወዳጅ ነበርኩ። ወደ ሰለጠነው ዓለም በመመለስ ችግርን መማፀኔ አልነበረም? ለማንኛውም ወደፊት ይነያ..።

የሚቀጥሉት ሦስት ሳምንቶች ውቦች ነበሩ። በላሊ እርግዝና እርግጠኞች ሆን፣ የአኔን መመለስ ሁለት ወይም ሶስት ሕፃናት ይጠባበቃሉ ማለት ነው። ለምን ሶስት ይሆናሉ? እናቷ ሁለት ጊዜ መንታ እንደ ወለዱ ራሷ ነግራኛለች። ወደ ጠንቋዩ ዘንድ ሔድን። አይሆንም በሩን መዘጋት የ..ቢንም፣ እንደ ተከፈተ ትተን አንድ ቅርንጫፍ ማጋደም ብቻ ነበረብን። ሦስታችን ስንተኛበት የነበረውም ተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ በጎጆዋ ጣሪያ አግድም መዘርጋት አለበት። ከአሁን ጀምሮ እንደ ተዋሐዱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሚቆጠሩ፣ ላሊና ዞራይማ አብረው መተኛት አለባቸው። በምድጃው አጠገብ ተቀመጡ ተባልን። ትንሽ አረንጓዴ ቅጠሎች በተኑና ለዐሥር ደቂቃ ያህል በጢስ ውስጥ ተዉን። ከዚያም ዞሪሎን ለመጠባበቅ ወደ ቤታችን ተመለስን። በዚያው ዕለት ምሽት ደረሰ። በጎጆዬ ፊትለፊት የሚንቀለቀለውን እሳት ዙሪያውን ከበን ሌሊቱን ሙሉ ከሕንጻውያኑ ጋር ስናወራ አደርን። ዞሪሎ እንደ አስተርጓሚ ሆኖ፣ ለእያንዳንዳቸው አንዳንድ የወዳጅነት ቀልዶች ሳወራቸው፣ እነርሱም እፀፋውን መለሱልኝ። ፀሐይ ብቅ እንዳለች ከላሊና ዞራይማ ጋር ሆነን ዕረፍት ወሰድን። ቀኑን ሙሉ በፍቅር ጭውውት አሳለፍነው።

የጉዞዬ መነሻ ከሰዓት በኋላ ነበር። እኔ እናገራለሁ፣ ዞሪሎ ይተረጉማል።

«በዙ ነገሮች የሰጠሽኝና በጋለ ስሜት የተቀበልከኝ የዚህ ጎሣ ታላቅ አለቃ ዛቶ፣ ለብዙ ቀናትና ሊሊቶች ልለይህ ስለሆነ ፈቃድህን እጠይቃለሁ።»

«ከጓደኞችህ ለመለየት ለምን ትመኛለህ?»

«ምክንያቱም ልክ እንደ እንዕሳ ሲያድኑኝ የነበሩትን ሰዎች መበቀል አለብኝ። በመንደራችሁ ውስጥ መጠጊያ አግኝቻለሁ። በሚገባ በልቻለሁ፤ ጨዋ የሆኑ ጓደኞችና ደስታ ያጎናጸፉኝ ሚስቶች ነበሩኝ። ግን ይህ ሁኔታ አንድ ጊዜ የተመቻቸ መጠጊያ ካገኘ በኋላ ችግር ይገጥመኝ ይሆናል በሚል ፍርሃት ቀሪ ዕድሜውን በሙሉ አዚያው ቦታ ተወሽቆ እንደሚያሳልፍ አንስሳ ደረጃ እንዲለውጠኝ ፈቃደኛ ሆኜ መገኘት የለብኝም። የምሐደው ጠላቶቼን ለመፋለምና ወደሚናፍቀኝ አባቴ ለመመለስ ነው። መንፈሴን በሚስቶቼ በላሊ፣ በዞራይማና በሕብረት በምናፈራቸው ፍሬዎች ውስጥ እዚሁ አተዋለሁ። ጎጆዬ የእነርሱና በቅርብ የሚወለዱት ሕፃናት ንብረት ትሆናለች። ማንም ሰው ይህን ቢዘነጋ ዛቶ ራስህ እንደምታስታውሰው ተስፋ አደርጋለሁ። በተጨማሪ እንተ ከምታደርግላቸው የግል ክብካቤ ሌላ ኡስሊ የተባለው ሰው ቤተሰቦቼን ቀንና ሌሊት እንዲጠብቅልኝ አጠይቃለሁ። ሁላችሁንም በጠቅላላው ምን ጊዜም እወዳችኋለሁ። በፍጥነት ለመመለስ የቻልኩትን ማንኛውንም ነገር አደርጋለሁ። ከሞትኩም ነፍሴ ወደ ላሊ፣ ዞራይማ፣ ልጆቼና ቤተሰቦቼ ወደ ሆናችሁት ወደ እናንተ የጓድራ ሕንዶች ትበራለች። ላሊና ዞራይማ እንደ ተከተሉኝ ወደ ጎጆዬ ገባሁና ካኪ ሸሚዜንና ሱሪዬ ለብሼ፣ ካልሲና ጫማዬን አደረግኩ።

ከስድስት ወር በላይ ቆይቼባት የነበረችውን ጸጋ የተጎናጸፈች መንደር ለረጅም ሰዓት ቁጭ ብዬ ስመለከታት ቆየሁ። እነዚህ የጓድራ ጎሣዎች በሌሎች ጎሣዎችም ሆነ በነጮች ዘንድ የተፈሩትን ያህል በሰዎች ጭካኔ ለተባረርኩ እኔን ለመሰለ ተወዳዳሪ የማይገኝልኝ ስደተኛ መጠጊያ በመስጠታቸው እፎይ ለማለት ችያለሁ። እዚህ ፍቅር፣ ሰላም፣ ፀጥታና የመንፈስ ጨዋነትን አግኝቻለሁ። ደህና ሁኑ ጓድራዎች! ሰፈዎቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሬቶቻችሁ ከዘመኑ ሥልጣኔ ነፃ በመሆናቸው አመሰግኗቸው። የአኗኗር ዘይቤያችሁ ለወደፊት ከፍተኛ ቁም ነገሮችን አስተምሮኛል። ከሙሉ ከብሩ ጋር አንድ ዳኛ ከመሆን ይልቅ አንድ ዘላን ሕንዳዊ መሆን ይመረጣል።

ሳላስበው ያገኘኋችሁ፣ ከተፈጥሮ ጋር የተዛመዳችሁት ተወዳዳሪ የማይገኝላችሁ ሚስዮቼ ላሊና ዞራይማ ደህና ሁኑ። ያለ ጥርጥር ተመልሼ እመጣለሁ። መቼ? እንዴት? ይህን አላውቅም፤ ግን ራሴን ቃል ኪዳን አስገባለሁ፤ እመለሳለሁ።

የቀትሩ ሰዓት ገፋ እንዳለ ዞሬሎ ፈረሱ ላይ ወጣና ወደ ኮሎምቢያ ጉዞ ጀመርን። የሰሌን ባርኔጣ እንደ ደፋሁ የፈረሴን ዛብ ይዤ በእግሬ አራመዳለሁ። እያንዳንዱ ሕንዳዊ በግራ እጆቹ ፊቱን ሸፍኖ ቀኙን ወደ ፊት ዘረጋ። ይህንንም ያደረጉት መሐዴን እንዳልፈለጉና ሁኔታው እንዳሳዘናቸው ሲገልጹልኝ ነበር። ላሊና ዞራይማ በግምት አንድ መቶ ያርድ ያህል ከእኔ ጋር አብረው ተራመዱ። የሚሰሙኝ መስሎኝ ስዘጋጅ፣ በድንገት ዘወር ብለው ወደ ኋላ ሳይመለከቱ እንባቸውን እየረጩ ወደ ጎጆዋ አቅጣጫ ሮጡ።

t.me/OLDBOOKSPDF

አምስተኛ ማስታወሻ

ወደሥልጣኔ ዓለም መመለስ፣ የሣንታ ማርታ ወህኒ ቤት

ከጓጅራ ለመውጣት ቀላል ነበር። ድንበሩን በላ ቪላ በኩል ያለ ምንም ችግር ተሻገርን። ከአንቶኒዎ ጋር ያን ያህል ረጅም ጊዜ ወስዶብኝ የነበረውን፣ አሁን በፈረስ ጀርባ ሆነን በሁለት ቀን ውስጥ መጨረስ ቻልን። ግን አደገኞች የሚባሉት ወሰን ጠባቂ ዘበኞች ብቻ አልነበሩም። ከጠረፉ አንሥቶ እኔ አስካመለጥኩበት የሪዮ ሐቻ መንደር ድረስ የሚገኘውም የስድሳ ማይል አካባቢ እንደዚያው ነበር።

ዞሪሎ አጠገቤ እንደቆመ በአንዲት ትንሽ የገጠረ ሆቴል ቤት ውስጥ የመጀመሪያዋን ንግግሬን ከአንድ ኮሎምቢያዊ ጋር አደረግኩ። እስከዚህም ቋንቋውን በዙ አላበላሸሁም ነበር። ዞሪሎ አንዳለው ሁሉ መንተባተቤ የአነጋገር ቅላጼዬን ለመሸሸግ በጣም ረዳኝ።

ወደ ሣንታ ማርታ አቅጣጫ እንደገና ጉዞ ቀጠልን። ዞሪሎ ግማሽ መንገድ ድረስ ሸኘቶኝ ጧት ላይ ወደ ቤቱ ሊመለስ ነበር።

አሁን ዞሪሎ ሔዷል። ፈረሱ ከእርሱ ጋር መመለስ እንዳለበት ወስነናል። ፈረስ መያዝ ማለት፣ ቤት ንብረት አለህ፣ የአንድ የተወሰነ ቀበሌ አባል ነህ ማለት ሲሆን፣ ፈረስ አለመያዜ እንደ «አከሌና አከሌን ታውቃለህ? የከንቲባው ስም ማን ይባላል?» «ወይዘሮ እከሊት ምን እያደረጉ ነው?» ከመሳሰሉት ልመልስ በማልችላቸው ጥያቄዎች ከመዋከብ ያድነኛል።

ለእኔ የሚሻለኝ በእግር መቀጠልና በካሚዎን ወይም በአውቶቡስ ተጉዤ ከሣንታ ማርታ መድረስ፣ በኋላ ደግሞ በባቡር መሣፈር ነው። ምን እየሠራሁ እንደምኖር ወይም ከወዴት እንደመጣሁ ማንም ሰው ስለማያውቅ ከእንግዲህ በየቦታው ባይተዋር መሆኔ ነው።

ለሥስቱ የወርቅ መሐለቆች ምንዛሬ ዞሪሎ የሰጠኝን አንድ ሺ ፔሶ ይዣለሁ። አንድ ጥሩ ሠራተኛ በቀን ከስምንት እስከ አሥር ፔሶ ቢያገኝ ነው፣ ስለዚህ ለረጅም ጊዜ የሚያቆየኝ ገንዘብ አለኝ። ዞሪሎ ትቶኝ ከሔደበት ባሻገር በግምት ሰማንያ ማይል ከሚርቅና የማይናቅ ስፋት ያለው ወደብ ከሚገኝበት ሣንታ ማርታ አጠገብ የሚሔድ አንድ ካሚዎን አሣፈረኝ። ካሚዎኑ የሚሔደው ፍየሎች ለመጫን ነበር።

በየአምስቱ ማይል ወይም አንድ መጠጥ ቤት በደረስን ቁጥር፣ በየመጠጥ ቤቱ እንቆምና ሾፌሩ ወጥቶ ከእርሱ ጋር አብሬ እንድገባ ይጋብዘኛል። እርሱ ይጋበዛል፣ እኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

አከፍላለሁ። በየጊዜው አምስት ወይም ስድስት መለኪያ የሀገር ባህል አልኮል ሲጠጣ እኔም አንድ የምጠጣ አስመስላለሁ። በግምት ሠላሳ አምስት ማይል ያህል እንደ ሔድን ጥምብዝ ብሎ ሰክሮ ነበር። በጣም ከመስከሩ የተነሣ መስመሩን ለቅቆ ወደ ጭቃማ መንገድ ገባና ካሚዎኑ ማጥ ውስጥ ተሰነቀረ። ይህም ኮሎምቢያዊውን ምንም አላስጨነቀውም። ወደ ጋቢና ውስጥ ገብቼ እንድተኛ ነግሮኝ እርሱ በስተኋላ መጥቶ ተጋደመ። ምን ነገር እንደማደርግ ግራ ገባኝ። ሣንታ ማርታ ለመድረስ ገና ሰላሣ ማይል ይቀረናል። አንድ ሰው ቢያገኝኝ እንኳ ከእርሱ ጋር እሰከ ሆንኩ አያሠጋኝም። ብዙ ጊዜ መቆማችን ነው እንጅ በእግር ከመሔድ የተሻለ ፍጥነት ነበረው።

ትንሽ እንቅልፍ ለመተኛት ወሰንኩ፤ ግን ወዲያው ነግቶ ነበር። ፀሐይ ወጥታ አንድ ሰዓት ሊሆን ተቃርቧል። ድንገት በሁለት ፈረሶች የሚሳብ አንድ ሠረገላ መጣ። ካሚዎኑን አልፎ ሊሔድ አልቻለም። ጋቢና ወስጥ ስለነበርኩ እኔ የካሚዎኑ ሾፌር መስያቸዋለሁ። ስለሆነም እኔም ከእንቅልፌ የባነንኩ በመምሰል እየተንተባተብኩ ማደናገር ያዝኩ።

ከዚያም ዕውነተኛው ሾፌር ነቃና ከሰረገላ ነጅው ጋር መወያየት ጀመሩ። ከብዙ መከራ በኋላ እንኳ ካሚዎኑን ከማጡ ውስጥ ማውጣት አልቻሉም። ጭቃው እሰከ ተሻጋሪ ብረቱ ድረስ ወጥቷል። ሠረገላው ውስጥ ጥቁር ልብስ ለብሰው ነጫጭ ቆብ የደፉ ሁለት ደናግሎችና ሦስት ትናንሽ ልጃገረዶች ነበሩ። ከብዙ ውይይት በኋላ ሁለቱ ሰዎች የጫካውን ከፍል መመንጠር እንዳለብንና አንድ ሌላ መተላለፊያ አውጥተን፣ አንዱ ሽከርከሪት በመንገዱ ላይ ሌላውን በተመነጠረው ጫካ ላይ በማድረግ ሰረገላውን ለማሳለፍ ተሰማሙ። ገጀራቸውን አወጡና ቁጥቋጦውን በመመንጠር ሰረገላውም ጭቃ ውስጥ እንዳይሰምጥና ደረቱ ከመሬት ጉበታ ጋር እንዳይገናኝ ለመቀነስ የተመነጠረውን ቁጥቋጦ በመንገዱ ላይ ረበረቡት። ከሁለት ሰዓት ሥራ በኋላ መተላለፊያ ተጠረገ። ደናግሎቹ አመሰገኑና ወዴት እንደምሔድ ጠየቁኝ።

«ሣንታ ማርታ» አልኩ።

«ግን መንገዱን» ተሳስተሃልኮ። ተመልሰህ ከእኛ ጋር መምጣት አለብህ። ለሣንታ ማርታ አምስት ማይል እሰከሚቀርህ ድረስ እኛ እንወስድሃለን» አሉ።

አምቢ ማለት አልቻልኩም። ለሰሚውም ግራ ይሆናል። በሌላ በኩል ደግሞ አዚሁ ቆይቼ የካሚዎኑን ሾፌር ለመርዳት እፈልጋለሁ ለማለት ፈለግኩ። ግን ይህን ሁሉ አቀነባብሮ መናገሩ ሰለ ከበደኝ በዚያ ፋንታ «ግራሲያስ፣ ግራሲያስ ሉመሰግናለሁ፤ አመሰግናሰሁ» ለማለት ተገደድኩ።

ስለዚህ ከሰረገላው በስተኋላ ከሦስቱ ትናንሽ ልጃገረዶች ጋር ተቀመጥኩ። ሁለቱ ሩጎሩጎ ደናግሎች ከፊት በኩል ከሠረገላ ነጅው ጋር ተቀመጡ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በካሚዎኑ ·በሰሀተት መጥተነው የነበረውን ሦስት ወይም አራት· ማይል በፍጥነት አስተካከልንና በአንድ አፍታ ወደ ትከከለኛው መንገድ ከደረስን በኋላ ጥሩ ጉዞ አደረግን። ሰዓት እንደ ደረሰ ምሳ ለመብላት አንዲት ትንሽ የገጠር ሆቴል ቤት ቆምን። ሦስቱ ትናንሽ ልጃገረዶች ከሰረገላ ነጅው ጋር በአንድ ጠረጴዛ፣ እኔ ከደናግሎቹ ጋር በሌላው ተቀመጥን። ደናግሎቹ በሃያ አምስትና በሠላሳ ዓመት መካከል የሚገኙ ወጣቶች ነበሩ። አንዷ የስፓኝ ዜጋ ስትሆን፣ ሌላዋ ደግሞ የአየርላንድ ተወላጅ ናት።

የአየርላንዷ ድንግል ቀስ ብላ፣ «እንደሚመስለኝ እዚህ አካባቢ ነዋሪ አይደለህም?» አለች።

«አ፣ አዎ፣ ከባራንኳላ ነኝ።»

«አይደለም፣ ኮሎምቢያዊ ልትሆን አትችልም። ጸጉርህ ጥቁር ካለመሆኑም፣ ቆዳህም የጠቆረው በፀሐዩ የተነሣ ነው። ከወዴትነው የመጣኸው?»

«ከሪዮ ሐቻ»

«እዚያ ምን ትሠራ ነበር?»

«የኤሌክትሪክ ቴክኒሺያን»

«አሃ በኤሌክትሪክ ኩባንያው አንድ ጓደኛ አለኝ። ስሙ ፔሬዝ ይባላል። የስፓኝ ዜጋ ነው።»

ምሳ ካበቃ በኃላ እጃቸውን ሊታጠቡ ተነሡ። የአየርላንዷ ድንግል በቻዋን ተመለሰች። ትኩር ብላ እየቸኝና ከዚያም በፈረንሣይኛ፣

«እሣልፌ አልሰጥህም፣ ሳን ጓደኛዬ ፎቶግራፍህን በጋዜጣ ላይ አይቼዋለሁ ብላለች። ከሪዮ ሐቻ ወህኒ ቤተ ያመለጥከው ፈረንሣዊ ነህ፣ አይደለህም?» አለች።

ብከድ ነገሮችን የበልጥ ማባባስ ሊሆንብኝ ሆነ።

«አዎ፣ እሀት። እባክሽ ሊጋልጠሽ እንዳታስገርኝ። እነርሱ እንደሚሉት መጥፎ ሰው አይደለሁም። እግዚአብሔርን የማከብርና የምወድ ነኝ።

የስፓኟ ድንግል ስትደርስባት፣ «አሺ» አለችና አንድ ልይዘው ያልቻልኩት ነገር ጨምራ ፈጠን በማለት ተናገረች። ለትንሽ ጊዜ በሁኔታው ያሰቡበት መሰሉና አንደገና ብ·ግ ብለው ወደ መታጠቢያው ክፍል ተመለሱ። እነርሱ በሌሉበት የአምስት ደቂቃ ·ቢ ውስጥ በፍጥነት አሰብኩ። ከመመለሳቸው በፊት ልሒድ፣ ወይስ ልቆይ? አሳልፈው ቢሰጡኝ ወሰነው ከሆነ ብሔድም ብቀርም ልዩነት አያመጣም። ወዲያው ሊያገኙኝ ይችላሉ። ይህ አካባቢ ጫካም ሆነ ቁጥቋጦ ፈጽሞ ስለማይገኝበት እስከ ኩተማው መዳረሻ በሙሉ ግልጥልጥ ያለ ነበር። አላደርገውም። በዚህ ፈንታ ወደፊት የዕድሌን መጠበቁ ይሻለኛል። መቸም እስካሁን አልጨከነችብኝም።

ፈገግ እያሉ ተመለሱ። የአየርላንዷ ድንግል ስሜን ጠየቀችኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሐኒሪ»

«መልካም፣ ሐኒሪ፣ ወደ ገዳሙ ከእኛ ጋር ትሔዳለህ። በሰረገላው ውስጥ እኛ እያለን ምንም የምትሠጋበት ነገር የለም። ብቻ አትናገር። ማንኛውም ሰው የሚገመተው በገዳሙ ሠራተኛ ነህ ብሎ ነው።»

የምግባችንን ሒሳብ ደናግሎቹ ከፈሉ። አንድ ፖኪት ሲጃራና አንድ ከብሪት ገዛሁ። ከዚያም ተነሣን። በጠቅላላው ጉዟችን ላይ ደናግሎቹ ምንም አልተናገሩኝም፣ ለዚህም ባለውለታዎቼ ነበሩ። በዚህ ዓይነት ሠረገላ ነጅው ቋንቋውን ዩቡን ያህል ስቡበሬ እንደምናገር ሊያወቅብኝ አልቻለም። ከሰዓት በኋላ መግቢያጃው ላይ አንድ ትልቅ የገጠር ሆቴል ቤት ቆምን። ከፊት ለፊቱ፣ «ሪዮ ሐቻ ሣንታ ማርታ» የሚል ጽሑፍ የተሰቀለበት አንድ አውቶቡስ ቆሟል። ልሣፈር ፈለግኩና ወደ አየርላንዱ ድንግል ጠጋ ብዬ ሐሳቤን አማከርኳት።

«ይህን ማድረግ አደገኛ ነው» አለች። አውቶቡሱ ሣንታ ማርታ ከመድረሱ በፊት ማንኛውም ተሳፋሪ የመታወቂያ ካርድ የሚጠየቅበት ቢያንስ ሁለት ፖሊስ ጣቢያዎች ይቆማል። ለሠረገላ ተሳፋሪዎች ግን ይህን አያደርጉም።

ሞቅ ያለ ምስጋና አቀረብኩላት። እንዲያውም ምን መሆኔን ካወቁበኝ ጀምሮ ይሰማኝ የነበረው ሥጋት አሁን በጠቅላላው ጠፋልኝ። በተቃራኒው ወደ እነዚህ ደናግሎች እያሮጠ ያመጣኝ ያልታሰበ ዕድል የማይታመን ሆነብኝ። እንደመሸ ወደ መጀመሪያው የፖሊስ ጣቢያ ደረስን። ከሣንታ ማርታ ወደ ሪዮ ሐቻ የሚሔድ አንድ አውቶቡስ በፖሊሶች እየተፈተሸ ነበረ። የሰሌን ባርኔጣየን ፊቴ ላይ ጣል አድርጌ፣ አንቅልፍ የወሰደኝ በመምሰል ሠረገላው ውስጥ በጀርባዬ ተጋደምኩ። ከልጃገረዶቹ ውስጥ አንደኛዋ (ስምንት ዓመት ያህናታል) ራሷን ከትከሻየ ላይ እንዳሰገደፈች ዕውነተኛው አንቅልፍ ወስዷታል። ሠረገላው በመሐል ሰንጥቆ አልፎ ከጣቢያው አጠገብ ቆመ።

«እንዴት ይዟችኋል» ስትል የስፓኟ ድንግል ጠየቀች።

«በጣም ደህና ነን እናት»

«ጎሽ። እንሒድ ልጆች»

አራት ሰዓት ላይ በጣም ደማቅ መብራት ያለበት ሌላ ጣቢያ ደረሰን። በእኛ በስተግራና በስተቀኝ ደግሞ የማንኛውም ሞዴል መኪናዎች በሁለት መስመር በዚያው ዓይነት ተደርድረው ነበር።

ፖሊሶቹ የመኪናዎቹን የዕቃ ማስቀመጫዎች በሙሉ እየከፋፈቱ ነበር። አንዲት ሴት ከመኪናዋ ወርዳ ሻንጣዋን ታተረማምስ ነበር። ከዚያም ወደ ጣቢያ አንዲት ሴት ከመኪናዋ ወርዳ ሻንጣዋን ታተረማምስ ነበር። ከዚያም ወደ ጣቢያ ተወሰደች። ምናልባት የመታወቂያ ካርድ አልነበራትም ይሆናል። እርግጠኛ ነኝ እኔም

t.me/OLDBOOKSPDF

አብቅቶልኝ ነበር። ከፊት ለፊታችን መንገደኞች የተጠቀጠቁባት አንዲት በጣም ትንሽ አውቶቡስ ነበረች። መጫኛዋ ላይ ሻንጣዎችና ትላልቅ ጥቅሎች፣ ከኋላ ደግሞ ተጨማሪ ቋጠሮዎች የያዘ አንድ መረብ የመሰለ ነገር ነበረባት። አራት ፖሊሶች ተሣፋሪዎቹን ውረዱ እያሉ ያስገድዷቸዋል። ሴቶቹ ሕፃኖቻቸውን በእቅፎቻቸው እንደያዙ ከሰዎቹ ጋር የሚወርዱባት ከፊት በኩል አንድ መዝጊያ ብቻ አላት። ከዚያም አንድ በአንድ ወደ ውስጥ ተመልሰው ገቡ።

እያንዳንዱ ሰው ፎቶግራፉ ያለበት የመታወቂያ ደብተር ይዟል። ስለዚህ ጉዳይ ዞሬሎ ፍጹም አልነገረኝም ነበር። ዐውቄ ቢሆን ኖሮ አንድ የተጭበረበረም ቢሆን፣ መታወቂያ ለራሴ ማግኘት በቻልኩ ነበር። አንድ ጊዜ ከዚህ ፍተሻ ቦታ ባለፍኩ፣ ወደ ባራንኳላ ከመሔዴ በፊት ማንኛውንም የጠየቀኝን ዋጋ ከፍዬ አንድ ካርድ መያዝ ይኖርብኛል።

ወይ አግዚአብሔር፣ ግን በዚያች አውቶቡስ ጊዜያቸውን አጠፉኮ! የአየርላንዷ ድንግል ወደ እኔ ዘወር አለችና፣ «አትሥጋ ሐንሪ» አለች። እኔን በማናገሯ በቁጣ አፈጠጥኩባት። ሠረገላ ነጂው በዕርግጥ መስማት ነበረበት።

ዐይን ሊያጠፉ ወደሚደርሰው መብራት ለመቅረብ የእኛ ተራ ነበር። ተነሥቼ ለመቀመጥ ወሰንኩ። ከተጋደምኩ የተደበቅኩ ይመስላል። የሠረገላውን የኋላ በር በመደገፍ ከደናግሎቹ ጀርባ ትይዩ በመሆን ተቀመጥኩ። የሚያዩት ሰውነቴን ብቻ ሲሆን፣ ባርኔጣዬን በፊቴ ላይ ጣል አድርጌያለሁ። ግን በጣም አላበዛሁትም።

«እንዴት ናችሁ» አለች የስፓኟ ድንግል በድጋሚ።

«በጣም ደህና ነን እህት። ለምን እንደዚህ ዘግይታችሁ ትጓዛላችሁ?

«ድንጉኖኛ ችግር አጋጥሞን ነው፣ ስለዚህ እባካችሁን አታስጠብቁን፣ ከመጠን በላይ ቸኩለናል።»

«አግዚአብሔር ከናንተ ጋር ይሁን እህቶች።»

«አመሰግናለሁ፣ ልጆቼ አግዚአብሔር ይጠብቃችሁ።»

ስለሆነም ማንም ሰው ምንም ነገር ሳይጠይቀን በሰላም አለፍን። ግን የእነዚያ ደቂቃዎች ጭንቀት የደናግሎቹን ሆድ ሳያገለባብጠው አልቀረም፣ ከፍተሻው ጣቢያ አንድ መቶ ያርድ አለፍ እንዳልን ሠረገላውን አስቆሙና ወደ ቁጥቋጦ ውስጥ ገቡ። ይህም በጣም ስሜቴን ስለነካው የአየርላንዷ ድንግል ወደ ሠረገላው ተመልሳ ስትወጣ፣

«አመሰግናለሁ እህት» አልኳት።

«ተቀብያለሁ። ግን በጣም ከመጨነቃችን የተነሣ ሆዳችንን ተጠናውቶናል ብዬ ፈርቻለሁ።

ግማሽ ሌሊት አካባቢ ወደ ገዳሙ ደረሰን። ረጅም የግንብ አጥርና ሰፊ

t.me/OLDBOOKSPDF

መዝጊያ ነበረው። ሰረገላ ነጅው ፈረሶቹን ፈታና ሠረገላውን ከሦስቱ ትናንሽ ልጃገረዶች ጋር ወደ ውስጥ ጎተተ። ወደ ግቢው ከሚያስገባው ደረጃ ላይ ስንደርስ ባመጡኝ ደናግሎችና በሩን በምትጠብቅ አንዲት መነኩሲት መካከል አንድ የጋለ ንትርክ ተነሣ። ሌሊቱን እኔ እዚህ እንዳሣልፍ የእናት መነኩሴዋን ፈቃድ ለመጠየቅ መቀስቀስ ያልፈለገች መሆኑን የአየርላንዷ ድንግል ነገረችኝ። እዚህ ላይ ነበር ለውድቀት ያበቃኝን ታላቅ ስሕተት የፈጸምኩት። አጋጣሚውን በመጠቀም አምስት ማይል ብቻ መራቋን ከማውቀው ሣንታ ማራታ መሐድ በቻልኩ ነበር። ያ ስሕተት በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ለሰባት ተጨማሪ ዓመታት እንድማቅቅ አድርጎኛል።

በመጨረሻም እናት መነኩሴዋን ቀሰቀሱና ሦስተኛው ፎቅ ላይ አንድ ክፍል ተሰጠኝ። በመስኮቱ በኩል የከተማውን መብራቶች ማየት እችላለሁ። የእደጋ ማስጠንቀቂያ መብራትና ትላልቅ ጀልባዎች ከወደቡ ሲወጡና ሲገቡም ይታዩኛል።

እንቅልፍ እንደወሰደኝ፣ በመዝጊያዬ ላይ አንድ ቁርቆራ አባነነኝ። አሰቃቂ የሆነ ሕልም እያየሁ ነበር። ላሊ ሆኗን ሸረካከታ ከፊት ለፊቴ የልጃችን ቁርጥራጭ ተዘርግቷል።

ወዲያው ታጠበኩና ጺሜን ተላጨሁ። ቁልቁል እንደ ወረድኩ፣ ደረጃዎቹ መጨረሻ ላይ የአየርላንዷ ድንግል ቆማ ከንፈሮቿን በከፊል ገለጥ በማድረግ ፈገግ አለች።

«እንደ ምን አደርክ ሐንሪ፣ ደህና ተኛህ?

«አዎ እህት።»

«ወደ እናታችን ቢሮ ና እባክህ እንሒድ። ሊያዩህ ይፈልጋሉ።»

ወደ ወስጥ ገባን። ከጠረጴዛው ኋላ የተቀመጠችው ሴት ዕድሜዋ በግምት ሃምሳ ዓመት ይሆናል። በጣም ቁጡ አስተያየትና የሚያሸሹ ጥቁር ዐይኖች ነበሯት።

«የስፓኝ ቋንቋ ትናገራለህ?»

«በጣም መጠነኛ»

«ደህና፣ ድንግሏ እንደ አስተርጓሚ ታገለግላለች። ፈረንሣዊ መሆንህ ተነግሮኛል።»

«አዎ እናቴ»

«ያመለጥከው ከሪዮ ሐቻ ወህኒ ቤት ነው?»

«አዎ፣ እናቴ።»

«መቼ?»

«ከሰባት ወር በፊት ይሆናል።»

«ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ምን እያደረግክ ነበር?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከሕንዳውያን ጋር እኖር ነበር።»

«ምን? አንተ፣ ከጓጅራዎች ጋር? ይህ የማይታመን ነው። እነዚያ አውሬዎች ቀበሌያቸው ውስጥ ማንም ሰው እንዲኖር አይፈቅዱም፤ ሚሲዮናዊ እንኳ ቢሆን። አምኜ አልቀበልህም። በዕርግጥ የት ነበርክ? እውነቱን ንገረኝ።»

«እናቴ፣ ከሕንዳውያኑ ጋር ነበርኩ፣ ይህንንም ላረጋግጥልዎ እችላለሁ።»

«እንዴት?»

«በያዝኳቸው ሉሎች» ከጃኬቴ ኋላ ሰፍቼው የነበረውን ከረጢት ፈትቼ በእጇ ሰጠኋት። ከፈተችና አንድ እፍኝ ሙሉ ሉሎች አወጣች። «ስንት ናቸው?»

«አ፤ አላውቅም። ምናልባት አምስት ወይም ሰድስት ሙዩ።»

ይህ መተማመኛ አይሆንም። ከሌላ አካባቢ ሰርቀሃቸው ሊሆን ይችላል።»

«እናቴ፣ ህሊናዎን ለማረጋጋት ያህል፣ ከማንኛውም ቦታ የተሰረቁ ሉሎች ካለ እስኪያጣሩ ድረስ እቆያለሁ። ገንዘብ አለኝ። ለምግቤና ለመኝታዬ መክፈል እችላለሁ። ያለ እርስዎ ፈቃድ ከክፍሌ ውስጥ ንቅንቅ ላለማለት ቃል እገባለሁ።»

ትከ ብላ ተመለከተችኝ። ድንገት ቢያመልጥስ? ብላ ታሰላስል እንደነበረ ዐወቅኩ። ከወህኒ ቤት ያመለጠ፣ ከዚህማ በጣም ቀላል ይሆናል።

«የከረጢት ሉሎቼን ለእርስዎ አተዋቸዋለሁ። ያሉኝም ሀብቶቼ እነርሱ ናቸው፣ ግን እርስዎ ዘንድ በመቀመጣቸው እንደማይጠፉብኝ አተማመናለሁ።»

«መልካም፣ ተስማምተናል። ግን በክፍልህ ውስጥ ተዘግተህ መቆየትም አያስፈልግም። ልጆቼ ጸሎት ቤት በሚሆኑበት ወቅት ጧትና ከሰዓት በኋላ በአትክልት ቦታው ውስጥ ለመዘዋወር ትችላለህ። ከረዳቷ ጋር ኩሽና ቤት ውስጥ ትመገባለህ።»

ምልልሱ ያስተማመነኝ በከፊል ብቻ ነበር። የአየርላንዷ ድንግል ወደ ኩሽና ቤቱ ወሰደችኝ፤ ትኩስ ዳቦና ቅቤ ተዘጋጅቶልኛል። ድንግሏም ምንም ሳትናገር ግራ የተጋባች መስላ ዝም ብላ እዚያው ቆመች። «ላደረግሽልኝ ማንኛውም ነገር አመሰግናለሁ፣ እህት» አልኳት።

«ይበልጥ ልረዳህ በቻልኩ ምኞቴ ነበር። ግን የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ ሔንሪ።» ይህን አለችና ከኩሽና ቤቱ ወጣች።

በመስኮቱ አጠገብ ተቀምጬ ባሕሩን፣ ወደቡን፣ ከተማውን አመለከታለሁ። ገጠሩ በሚገባ ታርሶ ነበር። ግን በአደጋ ላይ እንደሆንኩ የሚሰማኝ ስሜት ከራሴ ውስጥ ማውጣት አልቻልኩም። ወጣም ወረደ በሚቀጥለው ሌሊት ለመጥፋት ወሰንኩ። ሉሎቹም ገሃነም ይግቡ። ለገዳሙ ወይም ለራሷ ልትጠቀምባቸው ትችላለች። ሚርተኛ አሮጊት። በምንም ዓይነት አላመንኳትም። በተጨማሪም፣ ይህች የካታላን ተወላጅ፣ የአንድ ገዳም እናት መነኩሴና ከፍተኛ ምሁር ነች ተብላ የምትገመት፣ እንዴት

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈረንሳይኛ አትናገርም? እንግዳ ነገር ነበር። በዛሬዋ ሌሊት አሐዳለሁ። ከሰዓት በኋላ አጥር በመታኘት ከግንቡ ላይ ለመንጠላጠል ተስማሚውን ቦታ አጠናለሁ። ሰባት ሰዓት አካባቢ መዝጊያየ ተቆረቆረ።

«ወደታች ወርደህ እህል አትቀምስም ሔንሪ?»

«እሺ፤ አመሰግናለሁ። መጣሁ።»

ሽጉጥ በእጁ የያዘ መኮንንና ነጫጭ ዩኒፎርም ለብሰው ጠመንጃ ያነገቱ አራት ፖሊሶች መዝጊያውን ከፍተው ከፊት ለፊቴ ድቅን ያሉት፣ ኩሺና ቤቱ ጠረጴዛ ላይ ተቀምጬ ትንሽ ሥጋና የተቀቀሉ ድንችች ለመብላት ስሰናዳ ነበር።

«እንዳትንቀሳቀስ፤ አለበለዚያ እተኩሳለሁ» አለ አዛዡ። የእጅ ካቴና አስገቡብኝ። የአየርላንዷ ድንግል አንድ ጊዜ ጮሽችና ሕሊናዋን ሳተች። ሁለት የኩሽናው ቤት ረዳቶች አነሷት።

«እንሒድ» አለ አዛዡ። ወደ ከፍሌ ይዘውኝ ሔዱ። አዚያም ንብረቶቼን ሲበረብሩ፤ ቀርተውኝ የነበሩትን ሠላሳ ሰድስት የወርቅ መሐለቆች ወዲያው አገኟቸው። ግን ሁለቱን መርዘማ ፍላፃዎች የያዘችዋን ቦርሳ ተመልከተው አለፉት። እርሳሶች መስለዋቸው መሆን አለበት። መኮንኑ የወርቅ መሐለቆቹን ወደ ኪሱ ውስጥ ሲከትት በሆዱ ደስ አያለው ነበር። ከዚያም ተያይዘን ወጣን፣ አንድ መኪና - ወጉ አይቀርምና ያም መኪና ይባል ይሆናል - ግቢው ውስጥ ይጠብቀናል።

አምስቱ ፖሊሶችና እኔ በወላለቀው ከርካሳ መኪና ውስጥ ተጨናንቀን ባለ በሌለ ፍጥነቱ በረርን። ቮሬራችን የለበሰው የፖሊስ ዩኒፎርም ሆኖ ጥቁረቱ ከሰል የመሰለ ነበር። ተጨብጫለሁ፤ ከብሬን ለመጠበቅ ስል ለመጋፋት አልሞከርኩም። ይቅርታ ወይም ርኅራኄ የሚል ጥያቄዎችም ቦታ አልነበራቸውም። ራሴን ብቻ ወንድ ሁን፤ ተሰፋ አትቁረጥ አልኩት። ይህም በሚገባ ሠመረልኝና ከመኪናዋ እንደ ወረድኩ የተገናኘኝ መኮንን መጀመሪያ የተናገረው «ይህ ፈረንሣዊ ደስተኛ ይመስላል ጃል፣ ተያዘም አልተያዘም ደንታ ያለው አይመስልም» የሚል ነበር። ወደ ቢሮው ባርኔጣዬን አውልቄ ጓዜን በእግሮቼ መካከል በማድረግ፣ ሳልጋበዝ ተቀመጥኩ።

«የስፓኝ ቋንቋ መነጋገር ትችላለህ?»

«አልችልም።»

«ጫማ ሰፊውን ጥሩ።»

ጫማ ሰፊው ማርቴሎ በእጁ የያዘና ሰማያዊ ሸርጥ የለበሰ አንድ አጭር ሰው ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወደ ውስጥ ገባ።

«ከአንድ ዓመት በፊት ከሪዮ ሐቻ ያመለጥከው ፈረንሣዊ አንተ ነህ?»

«አይደለሁም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ውሸትክን ነው።»

«ውሸቴን አይደለም። ከአንድ ዓመት በፊት ከሪዮ ሐቻ ያመለጥኩት ፈረንሣዊ አይደለሁም።

«የእጅ ካቴናውን አውጡለት። ጃኬትና ሸሚዝህን አውልቅ።»

አንድ ወረቀት አነሣ መረመረ። የንቅሳቶቹ ዓይነት በሙሉ በዚያ ላይ ተመዝግቦ ነበረ።

«የግራ እጅህ አውራ ጣት ጎድሏል? አዎ፣ ታዲያ አንተ ነሃ?»

«አይደለሁም፣ እኔ አይደለሁም፣ ምክንያቱም ከአንድ ዓመት በፊት አላመለጥኩም። ያመለጥኩት ከሰባት ወር በፊት ነው።»

«ያው ነውኮ!»

«ለአንተ አዎ። ለእኔ አይደለም።»

«አሁን ገባኝ፣ ዕውነተኛው ነፍሰ ገዳይ ነህ ለካ፣ አይደለህም እንዴ? ፈረንሣውያንም ሆናችሁ ኮሎምቢያውያን ነፍሰ ገዳዮች ስትባሉ በሙሉ ያው ናችሁ። የሰው አውሬዎች። እኔ የዚህ ወህኒ ቤት ረዳት አዛዥ ነኝ የበላዮቼ ምን እንደሚያደርጉህ የማውቀው ጉዳይ የለም። ግን ለጊዜው ከጓደኞችህ ጋር ወስጄ አደባልቅሃለሁ።»

«የምን ጓደኞች?»

«አንተ ወደ ኮሎምቢያ ያመጣሃቸው ፈረንሣውያን።»

ከግቢው ባሻገር ወደሚታይ አንድ ክፍል ወስጥ ተወሰድኩ። እዚያም አምስቱን ጓደኞቼን አገኘኋቸው። ተቃቀፍን። «አስከ መጨረሻው ሰላም አግኝተሃል ብለን ገምተን ነበር አንተ ሽማግሌ» ሲል ክሎሲዎ፣ ማቹሬ ደግሞ ልክ እንደ ሕፃንነቱ ጊዜ አለቀሰ። የቀሩት ሦስቱም እንደዚሁ ተቆጭተው ነበር። እነርሱን እንደገና በማየቴ ሞራሌ ታደሰ።

«ምን እንደሆንክ አስኪ ንገረን» አሉ።

የኔን በኋላ እነግራችኋለሁ «የእናንተስ እንዴት ነው?» አልኳቸው።

«እዚህ ሦስት ወራችን ነው።»

«እንዴት ተቀበሏችሁ»

«እንደ ነገሩ፣ ለፈረንሣውያን ባለሥልጣኖች እንመልሳችኋለን ወደሚሉበት ወደ ባራንኳላ ለመዛወር እየተጠባበቅን ነው።»

«ምን ዓይነቶቹ የማትረቡ ናችሁ። እንዴት ለማምለጥ ሙከራ አላደረጋችሁም?»

«ራስህ እዚሁ ተመልሰህ መጥተህ፣ እንደገና ደግሞ ስለ ማምለጥ ታስባለህ!»

«ለምን አላስብም? እንደዚህ በቀላሉ ተስፋ ይቆርጣል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

t.me/OLDBOOKSPDF

በእናንተ ላይ የቁጥጥሩ መጥበቅ እንዴት ነው?»

«ቀን ሲሆን፣ እሰከዚህ አይደለም፤ ሌሊት ግን አንድ ልዩ ተከታታይ ቡድን አለ።»

«በቡድኑ ውስጥ ያሉት ስንት ናቸው?»

«ሦስት።»

«ቅልጥምህ እንዴት ነው?»

«ደህና ነኝ። አያስነክሰኝም።»

«ከፍል ውስጥ ሁጊዜ ይቆለፍባችኋል እንዴ?»

«አይቆለፍበንም። ጧት ሁለት ሰዓት፣ ከሰዓት በኋላ ሦስት ሰዓት በግቢው ውስጥ እንዘዋወራለን።»

«ሌሎቹስ ኮሎምቢያውያን እስረኞች ምን ይመስላሉ?»

«ከዚህ አንዳንድ እውነተኛ አይበገሬዎች አሉ፤ ሌቦቹም እንደ ነፍሰ ገዳዮቹ ጨካኞች ናቸው ብለው የሚያምኑ።»

ከሰዓት በኋላ በግቢው ውስጥ ከከሎሲዎ ጋር አንድ የቆይታ ውይይት በማድረግ ላይ እንዳለሁ ተጠራሁ። በዚያ ጧት ወደነበርኩበት ቢሮ ውስጥ ፖሊሱን ተከትየ ገባሁ። ቀደም ሲል ጠይቆኝ ከነበረው ሰው ጋር የወህኒ ቤቱ አዛዥም አብሮት ነበረ። የከበር መቀመጫው የተያዘው ጥልማኮስ በሚመስል ሰው ነበር። ቀለሙ ከሕንዳዊ ይልቅ ይበልጥ ወደ ጥቁርነት ያደላል። በተጨማሪ አጭርና ቁርንድድ የሆነ ጥቁር ጸጉር ነበረው። ዕድሜው ሃምሳ ዓመት የሚጠጋ ፈዛዛ ጥቁር ዐይኖች፣ ወፍራም ከንፈሮችና አጭር ሪዝ ነበረው። ሸሚዙ ከአንገቱ በኩል ገለጥ ብሎ በግራ በኩል ነጭና አረንጓዴ የማዕረግ ምልክቶች ቢጤ ለጥፏል። ጫማ ሰፊውም እዚያው ነበር።

«ፈረንሣዊው፣ ከሰባት ወራት በፊት አምልጠሃል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምን ትሠራ ነበር?»

«ጓጅራዎች ጋር እኖር ነበር።»

«እንደዚህ ያለ ውሸት አትንገረኝ፣ አለበለዚያ አሣርህን ነው የማሣይህ።»

«እውነቴን ነው።»

«ምንጊዜም ከሕንዶች ጋር ማንም ሰው አይኖርም። በዚህ ዓመት ብቻ ከሐያ አምስት በላይ የሚሆኑትን የእኛን ዘበኞች ገድለዋል።»

«አይደለም። ዘበኞቹ የተገደሉት በኮንትሮባንዲስቶች ነው።»

«እንዴት ዐወቅከ?»

«ለሰባት ወር ያህል ከእነርሱ ጋር ኖሬያለሁ። ከቀበሌያቸውጪጽሞ አልወጡም ነበር።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሺ። ምናልባት ልክ ትሆናለህ። እነዚህን ሠላሳ ስድስት የወርቅ መሐለቆች ከየት ሰረቅካቸው?»

«የራሴ ናቸው። ጁስቶ ሰጥቶኝ ነው። የተራራው ጎሣዎች አሉቃ።»

«አንድ ሕንዳዊ ይህን ያህል ሀብት እንዴት ሊኖረው ችሎ፣ ለአንተስ ይሠጥሃል?»

«አሺ ጌታዬ፣ ባለፉት ሰባት ወራት የተሰረቁ የወርቅ መሐለቆች ነበሩ?»

«የለም፣ ልክ ነህ። ስለዚህ ጉዳይ በሪፖርታችን ምንም ነገር የለም። ግን ይህ ደግሞ ሁኔታውን ከመከታተል አያግደንም።»

«አባክህ ተከታተል። አንድ ውለታ እንደሠራህልኝ ነው የምቆጥረው።»

«ከሪዮ ሐቻ ወህኒ ቤት ስታመልጥ ከባድ ወንጀል ፈጽመሃል፣ ከዚያ የባሰው ደግሞ አንቶኒዎ አንዲያመልጥ መርዳትህ ነበር። ብዙ የጠረፍ ዘበኞች በመግደሉ ሊረሽን ነበር። በፈረንሣይ ባለሥልጣኖች እንደምትፈለግና የፅድሜ ልክ እሥራት እንደ ተፈረደብህ እናውቃለን። ነፍሰ ገዳይ ነህ። አንተን ከሌሎቹ ጓደኞችህ ጋር በማስቀመጥ ከዚህ ደግሞ አምልጠህ አደጋ እንድታስከትል አላደርግም። ወደ ባራንኳያ አስከትሐደ ድረስ ጨለማ ማንብ ውስጥ ትቀመጣለህ። ያልሰረቅካቸው መሆኑን ስናጣራ የወርቅ መሐለቆችህ ይመለሱልሃል።»

እንጦሮጦስ የመውረድ ያህል በአነኛ ደረጃዎች ቁልቁል አመራሁ። በግምት ሐያ አምስት ደረጃዎች አንደ ወረድን፣ በግራና በቀኝ ካሉት ትናንሽ ከፍሎች አንዱን ከፈቱና ወደ ውስጥ ገፈተሩኝ። መዝጊያውን ሲዘጉት ከአሮንቋው ወለል የተነሣው ሽታ በሙሉ ኃይሉ አወደኝ።

በሌሎቹ ከፍሎች ውስጥ አንደኔው ተዘግቶባቸው የነበሩት እስረኞች፣ «ፈረንሣዊው! ፈረንሣዊው! ምን አድርገሃል? ለምን እዚህ መጣህ? እነዚህ ጨለማ ማንቦች የሞት ወጥመድ መሆናቸውን ታውቃለህ?» እያሉ በስፖኝ ቋንቋ ለፈለፉብኝ።

«ዝም በሉ! እስኪ አርሱ ይናገር፤» የሚል አንድ ድምፅ ጮኸ።

«እዚህ የመጣሁበት ምክንያት፣ ከሪዮ ሐቻ ወህኒ ቤት አምልጬ ነው።» የተዘበራረቀውን የስፓኝ ቋንቋ ንግግሬን በሚገባ የተረዱት ይመስላሉ።

«ስማ ፈረንሣዊው፤ ሐቁን ማወቅ ትፈልጋለህ?» ከከፍልህ ጥግ አንድ ጣውላ አለ። ያም መተኛ ነው። በስተቀኝ በኩል ውሃ ያለበት አንድ ጣሣ አለ። በጣም ፈጥነህ እንዳትጠጣ። ጧት ጧት በትንሹ ይሰጥሃል፤ ከዚያ ሌላ ምንም ልትጠይቅ አትችልም። በሰተግራ በኩል፣ የምትጸዳዳበት አንድ ባልዲ አለ። በጃኬትህ ሸፍነው። አዚህ ጃኬት አያስፈልግህም። ምን ጊዜም ከፍተኛ ሙቀት አለ። ባልዲውን ሸፍንበት፤ ስለዚህ በጣም መጥፎ ጠረን አይሸትህም። ሁላችንም የምናደርገው እንደዚያ ነው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ፊቶቻቸውን ለማየት ወደ ቋሚዎቹ ብረቶች ቀረብ አልኩ። ልለያቸው የቻልኩት ከፊት ለፊት ያሉትን ሁለት ሰዎች ብቻ ሲሆን፣ እግሮቻቸውን በውጭ በኩል ቸከለው ቋሚ ብረቶቹ ላይ ተለጥፈዋል። አንዱ የስፓኝ ሕንዳዊ መልክ ሲኖረው በሪዮ ሐቻ አሥሮኝ የነበረውን ፖሊስ ይመስላል። ሌላው ደግሞ ቆዳው ፈካ ያለ ጥቁር ሆኖ ወጣትና መልከ መልካም ነበር። በየጊዜው ማዕበል በመጣ ቁጥር በከፍሎቹ ውስጥ ውሃ እንደሚሞላ ጥቁሩ አስጠነቀቀኝ። «ከሆድህ በላይ ፈጽሞ ሰለማይሞላ መፍራት የለብህም። በላዩ ላይ የሚፏለሉትንም አይጦች ጭንቅላታቸው ላይ አንድ ጡጫ አቅምሰቸው እንጅ ለመያዝ አትሞክር። እይዛቸዋለሁ ብለህ ብትሞክር ይነክሱሃል።»

«እዚህ ጉድጓድ ውስጥ ስንት ጊዜ ሆኖሃል?» ብየ ጠየቅኩት።

«ሁለት ወር።»

«ሌሎቹስ ምን ያህል ይሆናቸዋል?»

«ሦስት ወር የሚበልጠው ማንም ሰው የለም። ከሦስት ወር በፊት ካልወጣህ እዚህ የመጣኸው እንድትሞት ነው ማለት ነው።»

«ረጅም ጊዜ እዚህ የቆየ ማን ነው?»

«አንድ ሰው ሰምንት ወር ሆኖታል፤ ግን አሁን ወደ ማብቃቱ ገደማ ነው። ለአንድ ወር ያህል መቆም አልሆንለት ብሏል። በሚቀጥለው ጊዜ አንድ ኃይለኛ ማዕበል ከመጣብን ያለጥርጥር ይሰምጣል።»

«የእዚህ ሀገር ሰዎች የአረመኔ ጥርቃሚዎች ናችሁ ልበል እንዴ?»

«እኔም ሠልጥነናል የሚል ቃል ፍጹም አልወጣኝምኮ! የአንተም ቢሆኑ እስከዚህ ሠልጥነዋል የሚባሉ አይደሉም። ዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፈርደውበሃል። እዚህ ኮሎምቢያ ውስጥ የመጨረሻው ቅጣት ሐያ ዓመት እሥራት፣ አለበለዚያም ሞት ነው። የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የሚባል ፈጽሞ የለም።»

«ስማ፣ ሁሉም ዘንድ ያው ነው።»

«በዙ ሰዎች ጨርሰሃል እንዴ?!

«የለም፣ አንድ ብቻ ነው።»

«ሕይመስለኝም። በአንድ ሰው ብቻ ይህንን ዓይነት ረጅም ቅጣት ሊፈርዱብህ አይችሉም።»

«እንደዚያ አደረጉልሃ!»

«ታዲያ የአንተም አገር እንደ እኔው አልሠለጠኑችማ?»

«ሕሺ፣ እንግዲህ ስለየአገሮቻችን መነታረኩን እንተወው። አንተ ልክ ነህ። የትም ቢሆን ፖሊሶች ያው ናቸው። አንተስ ምን አድርገህ ነው?»

«አንድ ሰው ከልጁና ከሚስቱ ጋር ገድየ!»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምን?»

«ጪቅላውን ወንድሜን ለአንዲት እንስት ዓሣማ ስለአስበላብኝ::»

«ምን! ይህን አላምንም::»

«ትንሹ ወንድሜ በአነርሱ ልጅ ላይ ዘወትር ድንጋይ እየወረወረ ሁለት ጊዜ ጭንቅላቱን ፈንክቶታል::»

«ይህም ቢሆን በቂ ምክንያት አይደለም::»

«አኔም ብሆን ያልኩት እንደዚሁ ነበር::»

«አንዴት ልትደርስበት ቻልክ?»

«ትንሹ ወንድሜ ሦስት ቀን ሙሉ ጠፋ:: ስፈልገው ቆየሁና በመጨረሻም አንድ የተከመረ ፍግ ውስጥ ነጠላ ጫማዎቹን አገኘኋቸው:: ዓሣማዋ ከነበረችበት ጉረኖ የተዛቀ ፍግ ነበር:: አካባቢውን ስቃኝ አንድ በደም የተጨማለቀ ካልሲ አገኘሁ:: ከዚያም ገባኝ:: ሳልገድላት በፊት ኦናትዬዋ ተናዘዘች:: ጸሎታቸውን እንዲያደርሱ ፈቀድኩላቸውና ከዚያም ተኮሰኩባቸው:: የመጀመሪያው ተኩስ የአባትየውን ጭን በታተነው::

«መማደልህ ትከከል ነበር:: ለዚህ ምን ይፈርዱብሃል?»

«ቢበዛ ሐያ ዓመት::»

«ሕዚህ ጨለማ ግንብ ውስጥ ያስገባህ ምንድን ነው?»

«የአነርሱ ቤተሰብ የሆነ አንድ ፖሊስ ደብድቤ:: እዚህ ወህኒ ቤት ነበር:: ግን ከእንግዲህ ዳግመኛ አይኖርም:: ወዲያ ስላባረሩት እፎይ ብያለሁ::»

የመተላለፊያው መዝጊያ ተከፈተ:: በሁለት ኦግዳሚ እንጨቶች ላይ የተንጠለጠለ አንድ በርሜል ከተሸከሙ ሁለት አስረኞች ጋር አንድ ዘበኛ መጣ:: ከአነርሱ ኋላ ደግሞ ጠመንጃ የያዙ ሁለት ዘበኞች አሉ:: ከከፍል ወደ ከፍል እየተዘዋወሩ እንደ መጸዳጃ የምንገለገልባቸውን ባልዲዎች በማውጣት ወደ በርሜሉ ወስጥ ያራግፏቸዋል:: የሠገራና የሽንት ከርፋት አፈነን:: ማንም ሰው አልተናገረም:: ወደ እኔ ሲደርሱ፣ አስረኛው ባልዲየን ወሰደና ወለሉ ላይ አንዲት ትንሽ ጥቅል ጣለ:: አነርሱ ከሔዱልን በኋላ ጥቅሏን ስከፍታት፣ ሁለት ፓኬት ሲጃራዎች፣ አንድ ከብሪትና በፈረንሣይኛ የተጻፈች አንዲት ማስታወሻ አገኘሁ:: ሁለት ሲጃራዎች አቀጣጠልኩና ከእኔ ባሻገር ላሉት ሁለት ሰዎች ወረወርኩላቸው:: ከዚያም ጎረቤቴን ጠራሁና ለሌሎቹ እሥረኞች ሲጃራዎቹን እንዲያስተላልፍ ነገርኩት:: ለራሴም አንድ አቀጣጠልኩና ኮሪደሩ ላይ ባለው መብራ ወረቀቷን ለማንበብ ሞከርኩ:: አልነበብ አለኝ፣ ስለዚህ ጥቅሉ ታሽጎበት የነበረውን ወረቀት ጥበት አድርጌ ሸመለልኩና ከብዙ መከራዎች በኋላ በአሳት ለማቀጣጠል ቻልኩ:: በችኮላ አነበብኳት::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ነታ በል ፓፒዮ። በአኛ መመካት ትችላለህ። እርሳስና ወረቀት ነገ ስለምንልክልህ ልትጽፍልን ትችላለህ። እሰከ ዕለተ ሞታችን ካንተ ጋር ነን።»

ልቤን አሞቀኝ። ለካስ ብቻዬን አልነበርኩም። በጓደኞቼ መመካት እችላለሁ። ማንም ሰው አያወራም። ሁሉም አያጨስ ነበር። በዚህ የሞት ወጥመድ ውስጥ ያለነው ፀሥራ ዘጠኝ መሆናችንን የሲጃራው ከፍፍል አመልክቷል። እንግዲህ በእርግጥ ለቅጣት ወደ መሀኒ ቤት ተመልሼ ገባሁ! እነዚያ ኮስማና የአግዚአብሔር አገልጋዮች በእርግጥ የዲያብሎስ አሁቶች ኖረዋል። አሳልፈው የሰጡኝ የሰፓኟ ወይም የአየርላንዷ መነኩሲት እንዳልሆኑ እርግጠኛ ነበርኩ። ግን ሁሉም ያው ናቸው። ያመንኳቸው ምን ዓይነት የለየልኝ ሞኝ ብሆን ነበር! የለም. . . አይሆንም። ያስያዙኝ እነርሱ አይደሉም። ሠረገላውን የሚነዳው ሰውስ? ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ፊረንሣይኛ ተነጋግረን ነበር። ሰምቶን ይሆን? ወይ ፈጣሪ፣ ምን ልዩነት አለው! ንቡተህበታል፣ አንድ ጊዜ ያለጥርጥር ንበተህበታል ፓፒዮ። ደናግሎች፣ ሠረገላ ነጅ፣ ወይም እናት መነኩሲቷን ብትጠረጥር ቅንጣት ያህል ሩይዳ የለውም።

በቀን ሁለት ጊዜ ጎርፍ ከሚያጥለቀልቀው የጣሳ ጉድጓድ ውስጥ ቆየሁ። መቀቱ በጣም ስለሚያፍን ሽሚዜን አወለቅኩ፣ ከዚያም ሱሪዬን፣ ከዚያም ጫማዬን አወለቅኩና ሁሉንም አግዳሚው ብረት ላይ አንጠለጠልኳቸው።

እንደገና ተመልሼ ከወህኒ ቤት ለመግባት አንድ ሺ አምስት መቶ ማይል ልጓዝ! እግዚአብሔር ለእኔ ደግ ሆኖልኝ ነበር። አሁን ግን ችላ ብሎ የተወኝ ይመስላል። ምናልባት ተቆጥቶ ይሆናል፣ ምክንያቱም ቀደም ሲል ማድረግ የሚችለውን ጥሩ ነገር ሁሉ አድርጎልኝ ነበር። ነጻነት ሰጥቶኝ ነበር፣ እውነተኛ ነጻነትና ሙሉ በሙሉ የተቀበለኝ አንድ ማኅበረሰብ። አንድ ሳይሆን ሁለት አስደናቂ ሚስቶችም ሰጥቶኝ ነበር። ጸሐይዋንና ባሕሩንም። ጌታና አባወራ የነበርኩባት አንድ ጎጆ። ምናልባት አኗኗራቸው ኋላቀር ቢሆንም በጣም የረጋ፣ በጣም ሰላም የሞላበትና ኪተፈጥሮ ጋር የተዛመደ ኑሮ፣ ያለ ፖሊሶች፣ ያለ ዳኞች፣ ያለ ምቀኛ፣ ልዩ የሆነ የነጻነት ገጸ በረከት ሰጥቶኝ ነበር። እኔ ግን ጥጋብ ተሰማኝ።

የባሕሩ ሰማያዊነት፣ አረንጓዴ ወይም ጥቁር በማይሆንበት ወቅት፣ እነዚያ የፀሐይ መውጫያና መጥለቂያ ወቅቶች የሚያመጡት ፍጹም የሆነ ሰላም። ያለ ገንዘብ እየኖርኩ የሚያስፈልገኝ አንድም ነገር ሳይጎድለኝ። ያን ሁሉ አሸቀንጥሬዋለሁ። ለማን ብዬ ጥሯል? እኔን ለመርዳት ፍላጎት ለሌለው አንድ ሕብረተሰብ። እኔ ዋጋ ቢኖረኝ እንኳ ለማዳን ደንታ ለሌላቸው ሰዎች። ከተስፋ ጭላንጭል ባሻገር ይህን ከመሰለ ጉድጓድ ውስጥ ሊወረውሩኝና ምንም ይሁን ምን በአእምሯቸው ውስጥ የሚጉላላው እኔን ቶሎ ገድሎ ለመቅበር ለሚመኙ ሰዎች የእኔ መያዝ ዜና ይፋ ሲወጣ፣ በትችት ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

የነበሩት እነዚያ ዐሥራ ሁለት ደደቦች፣ አይጥ ብጤው ፖሊሶን፣ ፖሊሶቹና ሕግ አስከባሪው ተንከትክተው ይሆናል። ዜናውን ወደ ፈረንሣይ የሚያስተላልፍ አንድ ጋዜጠኛ መመደብ አለበት።

የራሴው ሰዎችስ እንዴት ይሆኑ? ማምለጤን ፖሊሶች ሲለፍፉ፣ ልጃቸው ከፈራጆቹ እጅ ማፈትለኩን በማወቃቸው በጣም ደስ ብሏቸው መሆን አለበት! ዳግመኛ ተያዘ ማለትን ሲሰሙ ደግሞ እንደገና መልሰው ይሰቃያሉ።

ጎሣዎቼን መካዴ ስሕተተኛ ነበርኩ። አዎ «ጎሣዎቼ» ለማለት ሙሉ መብት አለኝ። ከልብ ተቀብለውኛልና ነው። ጥፋተኛ ነበርኩ። ስለሆነም ዕጣው ይገባኛል። ይሁንና ቀድሞውንም ከወሀኒ ያመለጥኩት . . . የደቡብ አሜሪካ ቀይ ሕንዳውያንን የሕዝብ ብዛት ለመጨመር አልነበረም። ውድ አምላኬ ሆይ፣ ከሠለጠነው ዓለም ሕዝብ መካከል መኖር እንዳለብኝና የኑሯቸው ተካፋይ መሆን እንደምችል እንጂ ለእነርሱ ችግር ፈጣሪ አለመሆኔን ተገንዘብልኝ። ከእንተ ዕርዳታ ጋር ሆነም አልሆነም፣ ተጨባጩ ዓላማዬ ይህ ነው። ብቁ ሰው እንደ ሆንኩና ለመሆን መቻሌን ማስመስከር አለብኝ። ምናልባት ከብዙዎቹ ባልሻልም፣ በእርግጥ ከእነርሱ የባስኩ አልሆንም። ሲጃራ አጨስኩ። ውሃው ከፍ እያለ መሔድ ጀመረ። ወደ ቁርጭምጭምቱ አካባቢ ደርሶ ነበር።

«ሔይ፣ ጥቁሩ ሰው! በክፍሉ ውስጥ ውሃው ለስንት ጊዜ ይቆያል?» ብዬ ተጣራሁ።

«እንደ ማዕበሉ ሁኔታ ይወሰናል። አንድ ሰዓት፣ ቢበዛ ሁለት ሰዓት።»

«እየመጣ ነው!» እያሉ ብዙዎቹ እሥረኞች ሲጯጯሁ ሰማሁ። ዝማ እያለ ውሃው ተነሣ። ከልሉና ጥቁሩ እግሮቻቸውን በመተላለፊያው ውጭ ዘርግተው በቋሚ ብረቶቹ ላይ ተንጠልጥለዋል። ውሃው ውስጥ አንድ ነገር ሰማሁ። ድመት የምታክል ከቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቦ የወጣች አንዲት አይጥ ዙሪያውን ትንቦራጨቅ ነበር። ፍርግርጉ ላይ ልትንጠላጠል ትሞክራለች። ወደ አጠገቤ ቀረብ ስትል አንዱን ጫማዬን አነሣሁና ጭንቅላቷ ላይ አሳረፍኩባት። እየተንሳጠጠች በመተላለፊያው በኩል ወረደች።

«ፈረንሣዊው፣ ሁሉንም መግደል እችላለሁ ብትል ራስህ ይዞራል። ፍርግርጉ ላይ ተንጠላጠልና አግዳሚ ብረቶቹን ጨብጠህ ጊዜውን ማሳለፍ ነው» አለ ጥቁሩ።

ምክሩን ተከተልኩ፣ ግን አግዳሚ ብረቱ ስለ ቆረቆረኝ፣ ለረጅም ጊዜ በዚያ አቀማመጥ መቆየት አልቻልኩም። ከመጸዳጃ ባልዲው ላይ ጃኬቴን አንሣሁና በአግዳሚ ብረቱ ላይ አስሬ ቁጢጥ አልኩ። እንደ መቀመጫ ስለሆነልኝ አሁን ተሰማማኝ። በትናንሽ ሽርጣኖች፣ በሙቶ እግር ትሎችና በአይጦች የተወረረው ውሃ ሙላት ምንጊዜም

t.me/OLDBOOKSPDF

የማልለምደው በጣም የሚቀፍ ነገር ሆነብኝ። ከአንድ ሰዓት በኋላ ውሃው ወደኋላ ሊመለስ፣ የማሽ ኢንች ውፍረት ባለው ደለል ወለሉ ተሸፍኖ ነበር። እግሮቼን ከደለሉ ለመጠበቅ ጫማዬን አደረግኩ። ጥቁሩ ሰው ቁመቱ ስድስት ኢንች የሆነ አንድ ቁራጭ እንጨት ወረወረልኝና ከምተኛበት ጣውላ ጀምሮ ሜቃውን ወደ ኮሪደሩ እንድገፋው ነገረኝ። ይህም የማሽ ሰዓት ጊዜ ስለወሰደብኝ ምንም ነገር ከማሰብ እንድታቀብ ረዳኝ። እስከሚቀጥለው ማዕበል ድረስ ከውሃ ነጻ እሆናለሁ። ይህም ለዐሥራ አንድ ሰዓቶች መሆኑ ነበር። ስድስት ሰዓት ማዕበሉ ወደ ውጭ ሲሔድ፣ አምስት ሰዓት ወደኋላ ሲመጣ፣ አንድ አስቂኝ አስተሳሰብ ወደ አእምሮዬ ጎረ አለ።

ፓፒዮ ከማዕበሎች ጋር ለመኖር የተፈጠርክ ነህ። ወይድከም ጠላህም በሕይወትህ ውስጥ ጨረቃ ዓቢይ ሚና ትጫወታለች። ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ስታመልጥ፣ ከግሮኒ ለመውጣት የቻልከው ምስጋና ይግባቸውና በማዕበሎቹ ነበር። ትሪኒዳድንና ኩራሶንም ስትለቅ ከማዕበሎቹ ጋር ብዙ ሚና ተጫውተህ ነው። ወደ ውጭ ሊያወጣህ ማዕበሉ ጋይል በማጣቱ በሪዮ ሐቻ ታሥረህ ነበር። እዚህ ደግሞ እሰከ መጨረሻ በእርሱ እጅ ወድቀሃል። አንዳንዶቹ፣ «ይበለው፣ ይገባዋል፣-በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ቆይቶ ቢሆን ኖሮ ይህ ሁሉ ፍጹም ባልደረሰበት» ይላሉ። ግን አንድ ነገር ልንገራችሁ፣ ተስፋ አልቆርጥም። በምንም ዓይነት፣ አንድ ሌላ ነገር ደግሞ ልንገራችሁ፣ በቅድሚያ ልላከበት ከነበረው ዱ ሳልዩ ደሴቶች ወህኒ ቤት ይልቅ በዚህ አስፓኞች ለፍርድ ማጣሪያ ብለው ባሳነፁት የኮሎምቢያውያን እሮጌ እምባ ጨለማ ግንብ ውስጥ መቆየት ይሻለኛል። ከጨለማው ግንብ ውስጥ ከማምለጥ አኳያ ገና ብዙ የምለው አለኝ። እዚህ የጣሣ ጉድጓድ ውስጥ ብሆንም፣ ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት በአንድ ሺ አምስት መቶ ማይል ርቄ አገኛለሁ። እኔን ወደ እዚያ ለመመለስ፣ አንድ ጥሩ ዘዴ ማውጠንጠን ይኖርባቸዋል! ሕንዳውያኑን አሰብኩና ኢምንት ታህል ወንጀል ባልፈጸመባቸው ሰው ላይ ይህን ዓይነት ቅጣት ሊያወርዱበት ቀርቶ፣ ከቶውንም አንደማያልሙት ተሰማኝ።

ሌሎቹ ሊያዩኝ ሰለማይችሉ ከከፍሌ በስተኋላ ባለው ጣውላ ላይ ተጋደምኩና ሁለት ሲጃራዎች አጨሰኩ። ቁራጩን እንጨት ከአንድ የተለከሰ ሲጋራ ጋር አያይዤ ለጥቁሩ ሰው ወረወርኩለት። በሚያጨስበት ወቅት እርሱም ልክ እንደኔ ተደበቀ። እነዚህን የመሰሉት ሐተታዎች ቁም ነገር ያላቸው አይመስሉ ይሆናል፤ ለእኔ ግን እጅግ የላቁ ናቸው። ምንም እንኳ የተገለልን ፍጡሮች ብንመስልም አንዳንድ በጎ ጠባዮችና ልምዶች አሁንም ገና እንዳልተለዩን ያረጋግጣሉ።

ገዳሙ ውስጥ መሆኔን ለፖሊሶች የነገረው ማን ይሆን? መቼውንም ካገኘሁት ያ ሰው ዋጋውን ያገኛል! ከዚያም ራሴን መልሼ እንደዚህ አልኩት፤ «ጨርሰህ ሞኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

እትሁን ፓፒዮ! ፈረንሣይ ውስጥ የምታከናውነው የበቀል ሥራ አለህኮ? የባሰ ችግር ውስጥ ለመግባት አይደለም ወደዚህ አጸያፊ ሀገር የመጣኸው። ማንም ሰው ቢሆን ለበደሉ ዋጋውን ያገኛልና፣ እንተ ግን ተመልሰህ ብትወጣ እንኳ ለላሊና ለሥራይጣ፣ ምናልባትም አነርሱ ለሚወልዱልህ ልጆች ደስታን ለመስጠት አንጅ ለብቀላ መሆን የለበትም። በማንኛውም ጊዜ ከዚህ ጉድጓድ ስትወጣ፣ ከብር ለሰጡህ ለጓጅራዎች ውለታ መመለስ ይሆናል። አውንም ገና በቅጣት ጎዳና ላይ ትገኛለህ፤ ግን እዚህ ከውሃ ሥር ባለ ጨለማ ግንብ ውስጥ እንኳ ሆነህ፣ ወደዱም ጠሉም ወደ ነጻነት ጎዳና እያዘገምከ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው።»

ወረቀቴንና እርሳሴን ከሁለት ፓኬት ሲጃራዎች ጋር አገኘሁ። እዚህ ከገባሁ ሦስት ቀን ሆነኝ፤ ወይም ዘወትር እዚህ ውስጥ ሌሊት ስለነበረ ሦስት ሌሊት ማለት ይኖርብኛል። አንድ ሲጃራ በማቀጣጠል ላይ እያለሁ አሥረኞቹም እርስ በርሳቸው የሚያሳዩትን የተለየ መሥዋዕትነት ከማድነቅ ልቆጠብ አልቻልኩም። ጥቅሎቹን አምጥቶልኝ የነበረው ኮለምቢያዊ ለአንድ ከባድ አደጋ ራሱን አጋልጧል፣ ቢያዝ ኖሮ ያለጥርጥር ወደ ተመሳሳይ ጨለማ ግንብ ውስጥ ይጣል ነበር ማለት ነው። ምናልባትም ይህ የሚከተለው መሆኑን በማገባ እየተገነዘበ ጣጣ ውስጥ ገቡቶ አኔን መርዳቱ፤ ታይቶ የማይታወቅ የቆራጥነትና የጨዋነት ተግባር ነበር። በምትቃጠለው ወረቀት ብርሃን፣ «ፓፒዮ፣ በሚገባ ጠንክረህ መቋቋምህን ሰምተናል። ጎበዝ! አንዳንድ ወሬዎች ላክልን። እዚህ ምንም አዲስ ነገር የለም። ፈረንሣይኛ የምትናገር አንዲት ድንግል እንተን ልትጠይቅ መጥታ ነበር። ከእኛ ጋር እንድትነጋገር አልፈቀዱላትም። ግን እንድ ኮሎምቢያዊ ፈረንሣዩ በሞት ግንብ ውስጥ ይገኛል ብሎ ለእርሷ ለመንገር ጊዜ አግኝቶ እንደነበረ ሪፖርት አቅርቦልናል። እርሷም፣ ሕመለሳለሁ› ብላለች። ይኸው ብቻ ነው። «ፍቅራችንን ልከንልሃል። ያንተው ጓደኞች» የሚል አነበብኩ። መልስ መስጠቱ ቀላል አልነበረም፣ ሆኖም ለመጻፍ ተሳካልኝ።

«ለማንኛውም ነገር አመሰግናለሁ። አየተቋቋምኩት ነው። ለፈረንሣይ ቆንሲል አመልክቱ። የሚሆነው ፍጹም አይታወቅም። ሁሉንም መልዕክት የሚላላከው ያው ሰው ይሁን። ለለዚህ ቢያዝ እንኳ የሚቀጣው አንድ አሱ ብቻ ይሆናል። የፍላፃዎቹን ጫፎች ለማንም ሰው እንዳታስነኩ፣ ረጅም ዕድሜ ለብጤያችን!»

ከሣንታ ማርታ ማምለጥ

ለቢልጅግ ቆንሲል ምስጋና ይድረሰውና ስሙ ከላውሰን በተባለ አንድ ሰው አማካይነት ከዚያ የበሰበሰ ጉድጓድ ውስጥ ከሐያ ሰምንት ቀናት በኋላ መውጣት ችዩ ነበር። ፖላሲዎስ ይባል የነበረው ጥፋር ሰው እኔ ከደረስኩ ከሦስት ሳምንት በኋላ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲወጣ ተደርጎ ስለነበር፣ ጨለማው ግንብ ውስጥ እንድ ቢልጅጋዊ ይኖኛል ብሎ አናቱ ለቆንሲሉ ከላውሰን እንድትነግር ለማድረግ እንድ ብሩህ ሀሳብ ተከስቶለት ነበር። ይህ ሃሳብ የመጣለት እንድ እሁድ ቀን ቆንሲሉ እንድ ቢጅልጋዊ አሥረኛ በሚነበጉበት ወቅት ብር ።

ስለሆነም እንድ ቀን ወደ ዋናው የወህኒ አዛዥ ቢሮ ተወሰድኩ።

«አንተ ፈረንሣዊ ነህ። ለምንድነው ለቢልጅግ ቆንሲል የምታመለከተው?» ሲል ጠየቀኝ።

ከእርሱ ጋር በቢሮው ውስጥ ወደ ነጭነት ያደላ ለስላሳ ጸጉርና ቀላ ያለ ድቡልቡል ፊት ያለው ዕድሜው ወደ ሃምሳ ዓመት የሚጠጋ አንድ ሰው ነበር። አንድ የቆዳ ቦርሳ በጭኑ ላይ ጣል አድርጎ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ተቀምጧል። ሁኔታው ወዲያው ገባኝ።

«ፈረንሣዊ ነህ ያልኸኝ ራስህ ነህ። ከፈረንሣይ ፍርድ ማምለጡ የማይካድ ነው። ግን እንደ አውነቱ ከሆነ ቢልጅጋዊ ነኝ።»

«መጀመሪያ ለምን እንደዚህ አላልክም ነበር?»

«ለአናንተ ምንም ዓይነት ለዩነት ያመጣል ብየ አልገመትኩም። ማንኛውም አሥረኛ ለማደረግ እንደሚሞክረው ሁሉ፣ ከማምለጥ በስተቀር ሀገራችሁ ውስጥ የፈጸምኩት ወንጀል አልነበረም።»

«በጣም ጥሩ፣ ከዛደኞችህ ጋር እንድትደባለቅ አደርጋለሁ። ግን ሲኞር ቆንሲል፣ የማስጠንቅቅዎ፣ ለማምለጥ ምንም ዓይነት ሙከራ ቢደርግ በቀጥታ ወደ መጣበት ቦታ መልሼ ነው የምልክው። ጸጉር ማስተካከያው ዘንድ ውሰደውና ከዚያም ከባልደረቦቹ ጋር ቀላቅለው» አለ አዛዡ።

«አመሰግናለሁ ቆንሲል። ለእኔ ብለው እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ በመግባትዎ አመሰግናለሁ።»

«የእግዚአብሔር ያለህ፣ እዚያ የሚዘጥንን ቦታ ውስጥ ተሠቃይተህ መሆን አለበት! አሁን ቶሎ በል፣ መንገድህን ቀጥል። ያ ጨካኝ ሐሳቡን እንዳለውጥ ጊዜ አትሰጠው። እንደገና ልጠይቅህ አመጣለሁ። ደህና ሁን።»

ጸጉር አስተካካዩ እዚያ ስላልነበረ፣ በቀጥታ ወደ ጓደኞቼ ወሰዱኝ፣ በጣም የተለዋወጥኩ መሆን አለብኝ፣ ምክንያቱም፣ «አንተ ልትሆን አትችልም! የማይሆን ነው! እነዚያ ውላጆች እንደዚህ እንድትመስል ምን አዞሩብህ? ተናገር። አንድ ነገር በል። ታውረሃል እንዴ? ዐይኖችህን ምን አግኝቷቸዋል? ሁልጊዜ ለምን ብልጭ ድርግም ታደርጋቸዋለህ» እያሉ ይወተውቱ ነበር።

«ከመቧራቱ ጋር መለማመድ አልቻልኩም። እዚህ በጣም ብረሃን ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዐይኖቼ የለመዱት ጨለማውን ነው። ብርሃን ሲያርፍባቸው ሕመም ይሰማቸዋል» ጀርባየን ለሙበራቱ ሰጥቼ ተቀመጥኩ። «ይሽ ይሻላል።»

«ትሸታለህሳ?»።

ልብሶቼን አወለቅኩና መዝጊያው አጠገብ አስቀመጥኳቸው።

ከማዕበሉ ጋር በሚመጡት ትናንሽ ሽርጣኖችና ቁንጫ በመላሰሉት ነፍሳት ከሻ ከንዶቼ፣ ጀርባዬ ጭኖቼና ባቶቼ ቀልተው ነበር። እንዴት እንደማስደነግጥ ለማወቅ ሪፈት መስታወት መመልከት አላስፈለገኝም። እነዚህ አምስት አሥረኞች ከዚያም የበለጠ አይተው ነበር፣ ሆኖም በሁኔታዬ ተደናግጠው ምንም ሊናገሩ አልቻሉም። ከሎሲዎ ኣንድ ዘበኛ ጠራና ጸጉር አስተካካዩ እንኳ ባይኖር ቢያንስ ግቢው ውስጥ ውሃ አለኮ አሉው። ዘበኛው ወደ ውጭ ለመውጣት ሰዓት እስኪደርስ ጠበቁ አለ።

ራቁቴን ወጣሁ። ልለብሰው የነበረውን አዲስ ልብስ ከሎሲዎ ያዘልኝ። ማቹሬ እየረዳኝ በሀገር ውስጥ ጥቁር ሣሙና ደጋግሜ ታጠብኩ። መታጠቤን በጨመርኩ መጠን እድፉም እየተጥመለመለ ይወጣ ነበር። በመጨረሻ፣ በብዙ በሣሙና ከመታሸትና መለቃለቅ በኋላ እንደጸዳሁ ተሰማኝ። በፀሐይ ላይ አምስት ደቂቃ ስቆይ ወዲያው ደረቅኩ፤ ልብሶቼን እንዳጠለቅኩ ጸጉር አስተካካዩ ብቅ አለ። እንደ በግ ሊሸልተኝ ፈለገ። ግን «አይደለም። በተገቢው መንገድ አስተካከለህ ጺሜንም ላጪኝ። እከፍልሃለሁ» አልኩት።

«ስንት?»

«አንድ ፔሶ»

«አሣምረህ አስተካከለውና» አለ ከሎሲዎ። «እኔ ሁለት ፔሶ እከፍልሃለሁ።»

«ወሃው ምን ያህል ከፍታ ይወጣል? የኢይጡቹስ ጉዳይ እንዴት ነበር? የመቶ አግር ትሎቹስ? ጭቃውስ? ሽርጣኖቹና ሰገራውስ እንዴት ኖሯል? የሚሞቱት ሰዎች ሁኔታስ እንዴት ነበር? አሟሟታቸው ሥፈጥሯዊ ነው ወይስ ራሳቸውን በራሳቸው ይሰቅላሉ? ወይስ ራሳቸውን በራሳቸው እንዲገድሉ ዘበኞቹ ይገፋፏቸዋል?»

ጥያቄው ሳያቋርጥ ይኸንደጎዳል፣ በጣም ብዙ መናገሩም አስጠማኝ። በግቢው ውስጥ ቡና የሚሸጥ አንድ ሰው ነበር። በዚያ በቆየንበት የሦስት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ቢያንስ በጥቁር ሰኳር የጣፈጠ ዐሥር ስኒ ቡና ጠጥቼ መሆን አለብኝ። በጣዕሙ በዓለም ላይ ካሉት መጠጦች ሁሉ ከፍተኛውን ሥፍራ የያዘ ሆኖ ነበር ያገኘሁት። በጨለማው ግንብ የነበረው ጥቁሩ ጓደኛዬ ሰላም ሊለኝ መጣ። እናቱና የቤልጅጉ ቆነሲል ያከናወኑትን ድርጊት ደምፁን አጥፍቶ ገለጸልኝ። እጁን ጨበጥኩት። አኔን ከጨለማው ግንብ እንድወጣ ስለረዳኝ በጣም ኩራትና ደስታ ተሰምቶት ነበር፤ በሚሔድበት ወቅት፣ «ከ እናወራለን። ለዛሬ ይብቃን» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የጓደኞቹ ከፍል ለእኔ ልክ እንደ አንድ ቤተመንግሥት መሰለኝ። ከሎሲዎ በራሱ ገንዘብ የገዛው አንድ ተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ ስለ ነበረው በዚያ ላይ እንድተኛበት ጋበዘኝ። በመሰቀልያ ቅርፅ ተዘርሬ ተኛሁ። በተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ ላይ ለመተኛት ትከክለኛው መንገድ ይህ መሆኑን ስገልጽለት ተገረመ።

እንበላለን፣ እንጠጣለን፣ እንተኛለን፣ ዳማ እንጫወታለን፣ ካርታ እንጫወታለን፣ ቋንቋውን ለመማር እርስ በርሳችን፣ ከኮሎምቢያውያኑም ዘበኞችና ከአሥረኞች ጋር በስፓኝ እናወራለን።

በሦስት ሰዓት መተኛት ቢኖርብንም፣ እንቅልፍ ግን በዐይኔ አልዞረም ነበረ። በመሆኑም ቅዱስ ላውረን ከሚገኘው ሆስፒታል እስከ ሣንታ ማርታ ያሉት የማምለጫ መንገዶች፣ ተራቸውን እየጠበቁ በዐይኖቼ ፊት ለፊት ይደቀናሉ። ፊልሙ እዚያ ላይ አያቆምም፣ መቀጠል አለበት። ይቀጥላል ጓዶች! ብቻ ኃይሌን መልሼ እስካገኝ ድረስ ጊዜ ስጡኝና ሌላም የማወራችሁ ታሪክ ይኖራል። ፈጽሞ አታስቡ! ትንንሾቹን መርዘማ ፍላፃዎችና ሁለቱን የኮካ ቅጠሎች፣ አንደኛው ሙሉ በሙሉ ደርቆ ሌላው አሁንም ትንሽ ረጠብ እንዳሉ አገኘኋቸው። እርጥቡን አኘክሁት። ሁሉም ሰው በአድናቆት ተመለከተኝ። ኮኬይን የሚሠራው ከእነዚህ ቅጠሎችመሆኑን ገለጽኩላቸው።

«እየቀለድክ ነው!»

«ቅመሰው።»

«እዚህ ይሸጣሉ እንዴ?»

«አላውቅም። ስማ ከሎሲዎ፣ እንዴት ብዙ ሀብት ማግኘት ቻልክ?»

«ከሪዮ ሐቻ ጀምሮ የተለወጥኩ ሰው ነኝ። ማንኛውም ሰው ቢሆን እኔን ሀብታም እንደሆንኩ አድርጎ ነው የሚገምተው።»

«የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ የያዘብኝ ሠላሳ ሰድስት የወርቅ መሐለቆች አሉኝ። አያኑዳንዱ መሐለቅ የሦስት መቶ ፔሶ ዋጋ አለው። ከዕለታት አንዱን ቀን መልሼ አገኛቸዋለሁ።»

«ከእርሱ ጋር አደራድርሃለሁ። ሰዎቹ በረኃብ እየተጠቁ ናቸው እለዋለሁ»

«ይህም አንድ መላ ነው።»

አሉድ ከቤልጅጋዊው ቆንሲልና ከቤልጅጋዊው አሥረኛ ጋር ተነጋገርኩ። አሥረኛው ጸተጋዘው ከአንድ የአሜሪካ የሙዝ ኩባንያ ጋር የኮንትራት ውል በማፍረሱ ነበር። ቆንሲሉ እኛን፣ ሁለታችንንም ሊረዳን ቃል ገባልን። በብሩሴልስ የሚኖሩ ቤልጂጋዊ ቤተሰቦች እንደ ነበሩኝ በመግለጽ አንድ ቅፅ ሞላልኝ። ስለ ደናግሎቹና ሌሎቹ ነገርኩት። ፕሮቴስታንት ስለሆነ ደናግሎቹን ባያውቃቸውም፣ አቡኑን ግን በመጠኑ ያውቃቸዋል። ገንዘቡን አሁን መጠየቅ እንደሌለብኝ መከረኝ። በጣም አደገኛ ይሆናል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከሐያ አራት ሰዓት በፊት የእኛ ወደባራንኳስ ጉዞ ይነገረዋል። ሐኔ ባለሁበት ገንዘቡን ጠይቅ፣ እንደ ተረዳሁት ምስከሮችም ነበሩ» አለ።

«ልክ ነው።»

«ግን አሁን፣ ምንም ነገር አታድርግ። ወደ እነዚያ አሰቃቂ ጨለማ ግንቦች በቅጥታ መልሰው ሊያስገቡህ ወይም ሊገድሉህ እንኳ ችሎታ አላቸው። እነዚያ የወርቅ መሐለቆች አንድ መጠነኛ ቅርስ ናቸው። ሰይጣን እንዲፈታኑንን ማድረግ የለብንም። ሉሎችም እንደዚሁ ጠቃሚ ናቸው። ስለ እነርሱም ቢሆን ላስብበት ይገባል።»

ከእኔ ጋር ማምለጥ ከፈለገና ስለ ሁኔታውም የሚያውቀው ዕቅድ ካለ ጥቁሩን ጠየቅኩት። ገና ከውጥኑ ቆዳው ገረጣ።

«ሰውዬ፣ ስለ ሁኔታው ትንሽ እንኳ አታስብም። ከተሳሳትን አዝጋሚ ሞት ማለት ነውኮ። ራስህም ቀምሰኸው ነበር። ባራንኳሳን ወደ መሰለ ሌላ ቦታ እስከትደርስ ድረስ ታገሥ። እዚህ መሞከር ራስን በራስ መግደል ነው። ለመሞት ትፈልጋህ? እሺ፣ እንግዲያው ረጋ በል። እኛ የነበርንበትን የመሰለ ጨለማ ግንብ በመላው ኮሎምቢያ ውስጥ የለም። ታዲያ ለምን ለዚህ አደጋ ትጋለጣለህ?»

«አዎ፣ ግን እዚህ ግድግዳው አጭር ነው። በላዩ ላይ ለመንጠላጠል በጣም ቀላል ይሆናል።»

«ሰውዬ፣ ቀላልም ሆነ አልሆነ በእኔ አትተማመን። አልሐድም፣ አልረዳህም። ስለዚህ ጉዳይ መነጋገር እንኳ አልፈልግም።» ከዚያም ዐይኖቹ በሚጮቅት እንደ ተሞሉ በተጨማሪ፣ «ጤነኛ አይደለህም። በሞንታ ማርታ እንደዚህ የመሰለ ነገር ማሰብህ አብደህ ነው» አለ። ይህን ተናገረና ጥሎኝ ሔደ።

ዘወትር ጧትና ከሰዓት በኋላ ወህኒ ቤቱ ውስጥ በከባድ ወንጀል እሥርላይ የሚገኙ ኮሎምቢያውያንን መከታተል ጀመርኩ። በሁሉም ላይ የነፍስ ገዳይ ፊት ይታይባቸዋል፤ ሆኖም ለአንድ ነገር ተርበትባቾች ይመስላሉ። የእነዚያን ጨለማ ግንቦች ሰቆቃ በማሰብ ደንዝዘው ነበር። ከአራት ወይም ከአምስት ቀን በፊት ከእነርሱ ውስጥ አንድ የሰው ዱራሳን የመሰለ መልምዬ ወጣሁ። ገና ከዚያ ከጨለማ ግንብ መለቀቁ ነበረ። የቁመቱ መርዘም ከእኔ በጣም የሚያስከነዳና ካይማን በመባል የሚጠራ ነበር። በጣም አደገኛ ሰው ለመሆኑ ዝነኛ ነበር። አነጋገርኩትና ሦስት ወይም አራት እርምጃዎች ያህል አብረን ከተጓዝን በኋላ በስፓኝኛ ቋንቋ

«ከእኔ ጋራ ማምለጥ ትፈልጋለህ?» ስል ጠየቅኩት።

ራሴ አንድ ሰይጣን መሰልኩትና ትኩር ብሎ ከተመለከተኝ በኋላ፣ «ወደ መጣሁበት ተመልሼ እዚያው የመጨረሻዬ እንዲሆን ነውን አልፈልግም። እመሰግናለሁ። እዚያ ተመልሼ ከምወርድ ይልቅ እናቴን መግደል እመርጣለሁ» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የመጨረሻው ሙከራዬ ይኸው ሆነ። ዳግመኛ ከማንም ሰው ጋር ስለማምለጥ ፈጽሞ አልወያይም። በዚያው ዕለት ከሰዓት በኋላ የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ በአጠገቤ ሲያልፍ፣ ቆም ብሎ ተመለከተኝና፣ «እንደምን ነህ?» አለ።

«ደህና ነኝ፣ ግን ይበልጥ ደህና የምሆነው ደግሞ የወርቅ መሐለቆቼን ባገኝ ነበር።»

«ለምን?»

«ምክንያቱም፣ አንድ ጠበቃ ልገዛበት እችላለሁ።»

«ከእኔ ጋር ና»

ወደ ቢሮው ወሰደኝ። ብቻችንን ነበርን። አንድ ሲጃራ አውጥቶ፣ በጣም መናኛ የሚባል አይደለም፣ አቀበለኝና አቃጠለልኝ። ነገሮች ቀስ በቀስ እየተሻሻሉ መጡ።

«ከእኔ ጋር ለመነጋገር በቂ የስታኝ ቋንቋ ትችላለህ? በጣም ዝግ እያልን እንነጋገራለን።»

«አሺ»

«መልካም፣ የምትለው ሐያ ስድስት የወርቅ መሐለቆችህን ለመሸጥ እፈልጋሁ ነው?»

«አይደለም፣ ሠላሳ ስድስቱን መሐለቆቼን።»

«አህ፣ አዎ፣ አዎ! እና ጠበቃ ልትገዛበት ነዋ? ግን እነዚህ መሐለቆች እንዳሉህ የምናውቀው እኛ ሁለታችን ብቻ ነን እኮ!»

«አይደለንም፤ እኔን አስረውኝ የነበሩት ሃምሳ አለቃውና አምስቱ ሰዎች፣ ለእንተ ከመሰጠቱ በፊት ከእኔ የወሰዳቸው ረዳት የወህኒ ቤቱ አዛዥ ጭምር ያውቃሉ። ከዚያም በላይ የራሴም ቆንሲል አለ።»

«መልካም፤ ብዙ ሰዎች ቢያውቁት ይሻላል። ስለሆነም ማንኛውም ነገር ግልጽ ሆኖ ይወጣል። ከፍተኛ ውለታ እንዳደረግኩልህ ታውቃለህ። አንዲት ቃል ትንፍሽ አላልኩም። አንተ ባለፍከባቸው ቦታዎች የወርቅ መሐለቅ ስርቆት ተካሒዶ እንደሆነ እንኳ ለመከታተል አልሞከርኩም።»

«ግን፣ ማድረግ ነበረብህ።»

«አይሆንም፤ ለአንተ ስል አለማድረጌ የተሻለ ይሆናል።»

«አመሰግናለሁ ጌታዬ።»

«እነርሱን እንድሸጥልህ ትፈልጋለህ?»

«ምን ያህል!»

«አ፤ ለእያንዳንዱ ሦስት መቶ ፔሶ። አንተ ለሦስቱ ከፈሉኝ ያልከው ይኸንኑ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዋጋ ነበር። ላደረግኩልህ ውለታ ከአያንዳንዱ መሐለቅ አንድ መቶ ፔሶ ትሰጠኛለህ። ምን ይመስልሃል?»

«አይሆንም በየጊዜው ዐሥራን መሐለቆች መልስልኝ። እኔም ለአያንዳንዱ መሐለቅ በመቶ ፋንታ ሁለት መቶ ፔሶ እሰጥሃለሁ። ላደረግክልኝ ሁሉ ይኸ መልሶ የሚከስህ መሆን አለበት።»

«ፈረንሣዊው፣ አንተ በጣም ሲበዛ ብልጥ ነህ። እኔ አንድ ምስኪን ኮሎምቢያዊ መኪንን ነኝ። ሞኝና ሰውን በጣም የማምን ነኝ። አንተ ጮሌ ነህ፤ ቀደም ብዬ እንዳልኩት በጣም ብልጥ ነህ።»

«አሺ፤ እንግዲያው አንተ የተመጣጠነ ዋጋ አቅርበልኛ።»

«ነገ ገበርውን እዚሁ ቢሮዬ ድረስ እንዲመጣ አደርገዋለሁ። መሐለቆቹን ይመለከታል፤ ዋጋ ይቆርጣል፤ ከዚያ አኩል በኩል እንካፈላለን። ይኸው ብቻ እንጂ ምንም ምርጫ አይኖርህም። ከወርቅ መሐለቆችህ ጋር ወደ ባራንኳላ ወዲያውኑ እልክሃለሁ፤ አለበለዚያም መሐለቆችህን ለምርመራ እዚሁ አቅያቸዋለሁ።»

«አይሆንም። አሁን የምነግርህ የመጨረሻዬ አማራጭ ይሆናል። ሰውዬው እዚህ ይመጣል፤ መሐለቆቹን ይመለከታል፤ ከሶስት መቶ ሃምሳ ፔሶ በላይ ያለው ማንኛውም ገንዘብ በሙሉ ለአንተ ይሆናል።»

«ደህና፤ ይበቃል። በዚህ ቃል እገባልሃለሁ፤ ግን ይህን ሁሉ ገንዘብ ወዴት ልታስቀምጠው ነው?»

«ወዲያው ገንዘቡን ስትቀበል የቤልጅጉ ቆንሲል እዚህ እንዲመጣ ታደርግልኛለህ። ለጠበቃየ እንዲከፍልልኝ ለአርሱ አሰጠዋለሁ።»

«አይሆንም። ምስክሮች በፍጹም አልፈልግም።»

«ይህ አንሶን አደጋ ላይ የሚጥል አይሆንምኮ። ሰላሳ ስድስት መሐለቆቼን ሰጠኸኝ ብዬ አንድ መስመር ወረቀት ላይ አፈርማለሁ። ስምምነቱን መቀበሉ ይሻልሃል። ከእኔ ጋር ግልጽ ከሆንክ አሁንም ገና ሌላ ውለታ አደርግልሃለሁ።»

«ምንድን ነው?»

«አመነኝ። ያም እንደ አሁኑ ሁሉ ጥሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እንዲያውም በዚያ ጊዜ እኩል በኩል እንካፈላለን።»

«ምንድን ነው? እስኪ ንገረኝ።»

«አይሆንም። አሁን አይደለም። ነገ ብቻ አንተ የተቻለህን አድርግና በዐሥራ አንድ ሰዓት ገንዘቤ በሰላም ቆንሲሉ እጅ ሲገባ፣ ስለ ሁኔታው እነግርሃለሁ።»

ምልልሳችን ረጅም ነበር። በጣም ተደስቼ ወደ ግቢው ስመለስ፣ ጓደኞቼ ቀደም ብለው ወደ ክፍላቸው ገብተዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ታዲያስ፣ ምንድን እያደረክ ነበር?»

ውይይቱን በሙሉ ደገምኩ። ብቸኞች ከመሆናችን አንጻር ልክ እንደ ዕብድ ሆነን ሣቅን።

«ያ ሰውዬ ምን ዐይነት ቀበሮ ነው!» ግን አጉተ ረትተኸዋል። በዚሁ ይጸናል ብለህ ታስባለህ?»

«እንደሚጸና እናንተ በአንድ መቶ፣ እኔ በሁለት መቶ ፔሶ እንወራረድ። የሚፈልግ አለ?»

«የለም፣ የሚጸና ይመስለኛል።»

ሌሊቱን ሙሉ በሀሳብ ተውጬ አደርኩ። የመጀመሪያው ሰምምነት ተስተካክሎ ነበር። ሁለተኛውም፣ ስለ ሉሎቹ በሚያውቅበት ወቅት በጣም ስለሚደሰት እንደዚሁ ጥሩ ይሆናል። ሦስተኛውስ እንዴት ይሆን? መልካም፣ ከወደቡ አንድ ጀልባ እንድሰርቅ ቢፈቅድልኝ፣ ያሰኘን ማንኛውንም ነገር መልሼ አበረክትለታለሁ። በገንዘብ መደበቂያ ቱቦዬ ውስጥ ባለኝ ገንዘብ ጀልባ መግዛት እችላለሁ። ይህን ፈተና እንዴት እንደምቋቋመው እስኪ እናያለን። ያለቅጥ ድፍረት አበዛሁ ይሆን? ግሃነም ይግባ፣ ከመጀመሪያዎቹ ሁለት ስምምነቶች በኋላ ሊቀጣኝ እንኳ አይችልም። ብቻ እስኪ እናያለን። እስከ ባራንኳላ ድረስ ልጠበቅ አችላለሁ። ግን ለምን? ትልቅ ከተማ፣ ስለሆነም ትልቅ ወህኒ ቤት፣ ስለሆነም ተጨማሪ ዘበኞችና ከፍተኛ የግንብ አጥሮች ይኖሩታል ማለት ነው። ተመልሼ ሔጄ ላሊና ዞራይማ ጋር መቀመጥ አለብኝ። ቶሎ አምልጬ ከሕንዶቹ ጋር ለትንሽ ዓመታት አቀመጥና ከዚያም በተራራው ላይ ከብቶች እያረቡ ወደሚኖሩት ጎሣዎች ሔጄ ከሺኔዙዌላውያን ጋር ግንኙነት ማድረግ አለብኝ። በማንኛውም ዘዴ. ይህ የማምለጥ ዕቅዴ መሣካት አለበት። ሦስተኛውን ሰምምነት በማሰላሰል ሌሊቱን ሙሉ አሳለፍኩ።

በሚቀጥለው ቀን ነገሮች ተቀላጥፈው ተከናወኑ። በሦስት ሰዓት የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ ቢሮ አንድ ሰው ይፈልግሃል ብለው እኔን ሊጠሩኝ መጡ። ፖሊሱ ከቢሮ ውጭ ቆየ። ግራጫ ልብስና ግራጫ ከራቫት ያሠረ ዕድሜው ስድሳ ዓመት ከሚቃረብ አንድ ሰው ፊት ቆምኩ። በላ ቀለም ያለው የአሜሪካን ከብት አረኞች የሚያደርጉት ብጤ የሰፍ ባርኔጣ ጠረጴዛው ላይ ነበር። የብር ግራጫ ሰማያዊ ቀለም ያለው አንድ ትልቅ ሉል፣ ልክ በጌጣጌጥ ሣጥን ውስጥ ያስቀመጠ ይመስል ከራቫቱ ላይ ሰክቷል። ቁጭንና ድርቅ ያለ ቢሆንም፣ ሰውየው ሽክ ያለ ነበር።

«እንደምን አደርክ።»

«ፊረንሣይኛ ትናገራለህ?»

«አዎ፣ ቀደም ሲል በሊባኖስ ነበርኩ። የአንድ መቶ ፔሶ ምንዛሪ መጠን

t.me/OLDBOOKSPDF

ያላቸው የወርቅ መሐለቆች እንዳሉህ ሰምቻለሁ። እፈልጋቸዋለሁ። ለኢያንዳንዱ አምስት መዶ ትወስዳለህ?»

«አይሆንም፤ ስድስት መዶ ሃምሳ።»

«አሳስተው አውርተውሃል፤ ጌታዬ! ለአንድ መሐለቅ ከፍተኛው ዋጋ አምስት መዶ ሃምሳ ነው።»

«ስማ፤ ሁሉንም ጨርሰህ ከወሰድካቸው፤ ለአንተ ስል በስድስት መዶ እሸጥልሃለሁ»

«አይሆንም። አምስት መዶ ሃምሣ።»

ለማሳጠር ያህል በአምስት መዶ ሰማንያ ተስማማን። ሽያጩ ተከናወነ።

የወህኒ አዛዡ በስታኝ ቋንቋ «ምን ተባባላችሁ? በስንት ተስማማችሁ?» ሲል ጠየቀኝ።

«ጌታዬ፤ በአምስት መዶ ሰማንያ ነው የተስማማነው። ሺያጩ ከሰዓት በኋላ ሊከናወን ነው።»

ሰውዬው ሔደ።

የወህኒ አዛዡ ብድግ አለና «ጥሩ። የእኔስ ድርሻ ሰንት ነው?» አለ።

«ከአንዱ መሐለቅ ሁለት መዶ ሃምሳ። አየህ፤ አንተ ከጠየቅከው ሁለት ተኩል እጥፍ እኔ ልሰጥህ ነው።»

ፈገግ አለና፤ «ሴላውስ ነገር እንዴት ነው?» አለ።

«በቅድሚያ ለገንዘቡ ቆንሲሉ መምጣት አለበት። እርሱ ሲሔድ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ስለሁለተኛው ስምምነት እነግርሃለሁ።»

«ሁለተኛ ስምምነት ስትል በእርግጥ ከምርህ ነው?»

«ቃል አገባልሃለሁ።»

«እንደርሱ ይሻላል።»

በሰምንት ሰዓት ቆንሲሉና ሊባኖሳዊው አዚያው መጡ። ሊባኖሳዊው 20.880 ፔሶ ሰጠኝ። ለወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ 8,280 እና ለቆንሲሉ 12,600 ሰጠሁ። ሠላሳ ስድስቱን የወርቅ መሐለቆች መልሶ እንደሰጠኝ በመግለጽ በእንድ ደረሰኝ ላይ ለአዛዡ ፈረምኩለት። እነርሱ እንደሔዱ፤ ከገዳሙ እመምኔት ጋር ስላደረግኩት ግንኙነት ለአዛዡ ገለጽኩለት።

«ሰንት ሉሎች አሉህ?»

«በአምስትና በስድስት መዶ መካከል።»

«ያች ሴት ሌባ ነች። ለአንተ መመለስ ይገባት ነበር፤ ወይም እዚህ መላክ፤ አለበለዚያም ለፖሊስ ማስረከብ ነበረባት። አጋልጣታለሁ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አይሆንም። በፈረንሣይኛ ከእኔ የተጻፈ አንድ ደብዳቤ ይዘህላት ሒድና ጠይቃት። ግን ስለ ደብዳቤው ከመግለጽህ በፊት የአየርላንዷን ድንግል በመካከላችሁ እንድትገኝ ጠይቃት።»

«ገባኝ። የፈረንሣይኛውን ደብዳቤ የአየርላንዷ ድንግል እያነበበች ለእናት መነኩሴዋ እንድትተረጉምላት ነው። በጣም ጥሩ፣ መሐይሮ ነው»

«እንዴ! ደብዳቤውን አስካዘጋጅ ቆይ እንጅ!»

«ልክ ነህ። ዮሴፍ፣ መኪና አዘጋጅ። ሁለት ፖሊሶችም አፈልጋለሁ» ብሎ ገርበብ ባለው መዝጊያ ጮኸ።

ከወህኒ አዛዡ ጠረጴዛ ተቀመጥኩና በወህኒ ቤቱ የጽሕፈት መሣሪያ የሚኩለውን ደብዳቤ ጻፍኩ።

«አግዚአብሔር ወደ ቤትዎ ሲመራኝ፣ በክርስቲያኖች ሕግ መሠረት ለስደተኛ ሰው ሁሉ ዕርዳታ ይሰጣሉ ብዬ በመገመትና የማላመልጥ መሆኔን ለማረጋገጥ የራሴው የሆነ አንድ ከረጢት ሉል በመያዣ ስም ሰጥቼዎት ነበረ። አንድ ከንቱ ፍጡር የራሱን ግዴታ የተወጣ መስሎት ለፖሊስ ባደረገው ጥቆማ ወዲያውኑ በግቢዎ ውስጥ በፖሊሶች ተይዤ ለመታሠር በቃሁ። ይህን ጭካኔ ያፈለቀችው የተኮነነች ነፍስ በእርስዎ ቤት ከአሉት የአግዚአብሔር ልጆች አንዷ እንደማትሆን ተስፋ አደርጋለሁ። ይህችን ጭካኔ የሞላባት ነፍስ ይቅርታ አድርጌላታለሁ ብዬ ብነግርዎ መዋሸት ይሆናል። በተቃራኒው ይህን የመሰለ አሰቃቂ ወንጀል ለመሥራት የበቃው ፍጡር እንዲቀጣ ወደ አግዚአብሔር አጸልያለሁ። እርስዎ ዘንድ በዕምነት ያስቀመጥኳቸውን የከረጢት ሉሎች ለወህኒ አዛዡ ቸዛሪዎ እንዲሰጡልኝ አጠይቅዎታለሁ። በታማኝነት ወደ እኔ እንደሚያመጣልኝ ዐውቃለሁ። ይህ ደብዳቤ እንደደረሰኝ ያገለግላል፣ የእርስዎ ታማኝ - ወዘተ»

የገዳሙ ርቀት ከሣንታ ማርታ አምስት ማይል ስለነበር፣ መኪናው በአንድ ሰዓት ተኩል ተመለሰ። የወህኒ አዛዡ እኔ ዘንድ ላከ።

«አኘሁልህ። ቁጠራቸው። አንድ የጎደለ ካለ አጣራ»

«ሁሉም እዚሁ ያሉ ይመስለኛል።»

«አርግጠኛ ነህ። ምንም የጎደለ የለም?»

«አርግጠኛ ነኝ። እንዴት እንዳደረግከ አስኪ ንገረኝ?»

«ወደ ገዳሙ ስደርስ እናት መነኩሲቷ በግቢው ውስጥ ነበረች። ሁለቱ ፖሊሶች ከጎኔ እንዳሉ እንደዚህ አልኳት። 'እዚህ ያመጣኝን ከባድ ጉዳይ ምናልባት ሊገሙቱ ይችላሉ። እርስዎ ባሉበት ከአየርላንዷ ድንግል ጋር መነጋገር ፈልጌ ነበር'።»

«ከዚያስ ምን ሆነ?»

«ደብዳቤህን ለእናት መነኩሲቷ በምታነብበት ወቅት ድንግሏ ተንዘፈዘፈች።

t.me/OLDBOOKSPDF

እናት መነኩሲቷ ምንም አላለች። አቀርቅራ እየተመለከተች የጠረጴዛዋን መሣቢያ ከፈተችና፣ «ሉሎቹ ምንም አልተነኩ፣ ከነከረጢቱ ይኸው። ይህን የመሰለ አሰቃቂ ወንጀል የፈጸመውን ሰው እግዚአብሔር ይቅር ይበለው። ለሐጎሪ እንደምንጸልይለት ነገረው አለች። ስለዚህ ሁኔታው ይኸው ብቻ ነበር» አለና የአዛውንት ፊት በፈገግታ በረቱ።

«ሉሎቹን መች እንሸጣቸው?»

«ነገ። ከወዴት እንደመጡ ልጠይቅህ አልፈልግም። ነፍሰ ገዳይ መሆንህንም ዐውቃለሁ፤ ግን በተጨማሪ ቃልህን የምታከብር ሰው እንደሆንክ ደግሞ ተገንዝቤአለሁ። ያውልህ፤ ይህን የዓሣማ ሥጋ፣ አንድ ጠርሙስ ወይን ጠጅና የፈረንሣይ ዳቦ ውሰድ። ከጓደኞችህ ጋር ይህችን የትዝታ ቀን እንድታከብር አፈልጋለሁ።»

ባለሁለት ሊትር አንድ ጠርሙስ ኪያንቲ፣ አራት ፓውንድ የሚመዝን የዓሣማ ሥጋና አራት ረጃጅም የፈረንሣይ ዳቦዎች ይዤ ወደ ከፍላችን ተመለስኩ።

«አንድ ጠበቃ ብንገዛ ሊረዳን የሚችል ይመስልሃል?»

በሣቅ ፈነዳሁ። ምስኪን ደደቦች። ስለ ጠበቃ ጉዳይ ሳይቀር ሐሳብ ላይ ወድቀው ኖሯል።

«አላውቅም። ለማንም ሰው አንድ ገንዘብ ከመስጠታችን በፊት አንዳንድ ምክር ማግኘትና ሁኔታውን ማጥናት ይኖርብናል።»

«ያሚሻለው ጠበቃው ሲያስፈታን ብቻ ብንከፍለው ይሆናል» አለ ከሎሲዎ።

«ጥሩ ሐሳብ ነው። በዚህ የሚስማማ አንድ ጠበቃ እንፈልጋለን» ከማለት በስተቀር ሌላ አላልኩም። ትንሽ ታፍረት ያዘኝ።

በሚቀጥለው ቀን ሊባኖሳዊው ተመልሶ መጣ። «በጣም የተዘበራረቀ ነው» አለ። «በመጀመሪያ ሉሎቹን እንደ መጠናቸው፣ ቀለማቸውና ቅርጻቸው ከብም ሆኑ አራት ማዕዘን መመደብ አለብን።» ሊባኖሳዊው ከእርሱ ጋርአንድ የተሻለ ልምድ ያለው ሌላ ገዢ ማምጣት ይኖርብኛል አለ። አራት ቀን ፈጀብን። ሠላሳ ሺ ፔሶ ከፈለ። ለቤልጅጉ ቆንሲል ሚስት የምስጣቸው ሁለት ጥቁሮችና አንድ ሐምራዊ ሉል መጨረሻ ላይ መልሼ ወሰድኩ። እነዚያ ሦስት ሉሎች ብቻ ቢያንስ የአምስት ሺ ፔሶ ዋጋ እንደነበራቸው ነገሩኝ። ግን እንዴ ወስጃቸዋለሁ። የቤልጅጉ ቆንሲል መቀበል ከባድ ሽከም ሆነበት፤ ግን ዐሥራ አምስቱን ሺ ፔሶ ሊያስቀምጥልኝ ተስማማ። ስለዚህ አሁን ከሐያ ሰባት ሺ ፔሶ በላይ በእኔ ይዞታ ይገኛል። ማድረግ የቀረኝ ሦስተኛውን ስምምነት መጀመር ብቻ ነበር።

«አዛኸር፣ አሁን ከምታገኘው የበለጠ የሚያተርፍህ አንድ የንግድ ድርጅት ለመግዛት ምን ያህል ገንዘብ ያስፈልግሃል?»

«አንድ ጥሩ ንግድ በዐርባ አምስትና በስድሳ ሺ ፔሶ መካከል የሚገኝ ዋጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

.ይጠይቀኛል::»

«ታዲያ ለምን ንግድ አትጀምርም?»

«ለግማሹ እንኳ በቂ ካፒታል የለኝማ::»

«ስማ አዛዥ፣ ሦስተኛው ስምምነቴ ይህ ነው::»

«በእኔ ላይ ቁማር ልትጫወት አይደለም?»

«አልጫወትም፣ አመነኝ:: ሐያ ሰባት ሺ ፔሶዎቼን ትፈልጋለህ? በምትጠይቅበት ጊዜ የአንተው ናቸው::»

«እንዴት ተብሎ?»

«ማምለጥ የምችልበትን አመቻችልኝ::»

«ስማ ፈረንሣዊው፣ እንደማታምነኝ ዐውቃለሁ:: እርግጥ በፊት ልክ ነበርክ:. ግን ከድህነት እንድላቀቅ ረድተኸኛል፤ ቤት ለመግዛት ችያለሁ፤ ልጆቼን ወደ ግል ትምህርት ቤት ልኬያለሁ:: አሁን ጓደኛህ ነኝ:: እኔ ልዘርፍህ ወይም ስትገደል ላይህ አልፈልግም:: ስለዚህ በቀጥታ ዕድሉን ለአንተው አሰጥሃለሁ:: ያለ የሌለ ሀብት ብታሸከመኝ እንኳን ከዚህ ወዲያ የማደርግልህ ምንም ነገር አይኖርም:: ታመልጣለህ ብዬ ተስፋ ስለማላደርግ ልረዳህ አልችልም::»

«ስህተተኛ መሆንህን ባረጋግጥልህስ?»

«አሱን ያኔ እናያለን:: ግን ስለሁኔታው መጀመሪያ አስብበት::»

«አዛዥ፣ የምታውቃቸው አሣ አጥማጆች አሉ?»

«አዎ::»

«ታዲያ፣ ጀልባውን ሸጠልኝ ወደ ባሕር የሚያወጣኝ ከአነርሱ አንድ ሰው ጋር ልታገናኘኝ ትችላለህ?»

«አላውቅም::»

«ያንድ ጀልባ ዋጋ ስንት ይሆናል?»

«ሁለት ሺ ፔሶ::»

«ለአንተ ሐያ ሺ እና ለዓሣ አጥማጁ ሰባት ሺ ብሰጣችሁ ምን ይመነልሃል?»

«ፈረንሣዊው፣ ለእኔ ዐሥሩ ሺ በቂዬ ነው:: አንድ ነገር ለራስህ አስቀር::»

«ዝግጅቱን ልትጀምርልኝ ነው?»

«የምትሐደው ብቻህን ነው?»

«አይደለም::»

«ታዲያ ስንት ናችሁ?»

«ጓደኞቼ ጋር ልነጋገር::»

የአስተሳሰቡ መለዋወጥ ደንቆኝ ነበር:: ከጨፈገገው ፊቱ በስተጀርባ ልቡ ሥር

t.me/OLDBOOKSPDF

የተደበቁ ቅን አስተሳሰቦች ነበሩ።»

ግቢው ውስጥ ከክሎሲዎና ማቹሬ ጋር ተወያየሁ። ምንም ነገር ልወስን ብቻ ከእኔ ጋር እንሔዳለን አሉ። ሕይወታቸውን በእኔ እጅ ላይ ይመጣላቸው ጥልቅ የሆነ ደስታ ሰጠኝ። የእነርሱን እምነት በግል ጥቅሜ ለመለወጥ ፍጹም አልሞከረውም። ከፍተኛ ታላፊነት ስለሆነ በጥንቃቄ መመራት አለብኝ። ግን ለቀሩትም የእኛ ባልደረቦች መንገር ነበረብን። አንድ የዶሚኖ ጨዋታ ጉከከር ስንጨርስ ሦስት ሰዓት አካባቢ ሆኗል።

«ቡና!» ብዬ ተጣራሁና ስድስት ትኩስ ቡና መጣልን።

«የማነጋግራችሁ ጉዳይ አለኝ። ሁኔታዎች የሚገፉት በዚህ ደረጃ ላይ ነው። እንደምገምተው፣ ጠፍቼ ለማምለጥ ሳይሳካልኝ አይቀርም። ግን አዝናለሁ ለመሔድ የምንችለው እኛ ሦስታችን ብቻ ነን። በእኔ በኩል የማይቀረው ነገር ያው ከክሎሲዎና ማቹሬ ጋር መሔድ ነው፣ ምክንያቱም ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤትም አብረን አምልጠናል። ከእናንተ ውስጥ ይህን የማይወድ ካለ ተናገሩ፤ አሰማችኋለሁ።»

«የለም» አለ ብራዮኒ። «በእኔ በኩል ተገቢ ይመስለኛል። ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት አብራችሁ አምልጣችኋል። በተጨማሪ እኛ ኮሎምቢያ ውስጥ እንድንወርድ ባንጠይቅ ኖሮ ይህ ዕድል ባልገጠማችሁም ነበር። ግን ሐሳባችንን ስለጠየቃችሁን ሁላችሁንም እናመሰግናለን። እንዲሳካላችሁ በአማዚአቢሔር ተስፉ አደርጋለሁ። ከተያዛችሁ ግን ያለ ጥርጥር ሞት ነው።»

«እናውቃለን» ሲሉ ክሎሲዎና ማቹሬ በአንድ ድምፅ ተስማሙ።

በሌላ ጊዜ ከሰዓት በኋላ አዛገቦ አነጋገረኝ። አንድ ሰው አግኝቶ ነበር። በጀልባው ውስጥ ምን ዓይነት ስንቆች እንደምንይዝ ለማወቅ ይሻል።

«ወሥራ ሁለት ጋሎን የመጠጥ ውሃ የሚይዝ አንድ በርሜል፣ ሃምሳ ፓውንድ የበቆሎ ዱቄትና ስድስት ሊትር ዘይት። ይኸው ነው።»

«የቸሩ ፈጣሪ ያለህ!» አለና አዛገቦ ጮኸ። «በዚህ ብቻ ወደ ባሕር ልትዘልቁ አትችሉም!»

«አርግጠኛ ነኝ ኮርተን እንችላለን»

«ጎበዝ ሰው ነህ፣ ፈረንሣዊው።»

በዚሁ ደመደምን። ከዚያም ለሰለስ በማለት እንደዚህ አለ። «በታምንም ባታምንም ይህን የማደርገው ለሁለታችሁም፣ ማለት ለልጅቼና ለአንተ ብዬ ነው። የሚገባህ ነው፣ ምክንያቱም ጠንካራ መንፈስ አለህ።»

አመሰገንኩት።

«ታዲያ እኔ እዚህ ውስጥ እንደሌለሁበት ማንም ሰው ሳያውቅ እንዴት

t.me/OLDBOOKSPDF

ማቀነባበር እንችላለን?»

«አንተ አትገባበትም። ረዳትህ ተረኛ በሚሆንበት ሌሊት አሐዳለሁ።»

«ዕቅድህ ምንድን ነው?»

«ነገ ከፖሊሶቹ ውስጥ አንደኛውን ከሌሊት ተረኝነቱ ዕረፍት እንድትሰጠው እፈልጋለሁ። ከዚያም በሦስተኛው ቀን ሌላውን አንዱን ዕረፍት ሰጠው። አንድ ብቻ ሲቀር ከከፍላችን መዝጊያ ትይዩ አንዲት የዙብ መቆሚያ ሣጥን እሠራ። በመጀመሪያው ዝናባማ ሌሊት ዘበኛው ሊጠለል ወደ ዙብ ሳጥኗ ሲገባ እኛ በኋላ መስኮት በኩል እንወጣለን። ሌላው የምታደርገው ቁም ነገር በግቡ አጥሩ ላይ ያሉትን መብራቶች ገመድ ማገናኘት ነው። ይህንንም ለማድረግ ዘዴው ከዳርና ዳር ድንጋዮች የተያያዙበት አንድ ያርድ የመዳብ ሽቦ የግቡን መብራቶችና ዋናውን መስመር በሚያገናኘው ምሰሶ ሁለት ሽቦዎች ላይ መወርወር ነው። በዓሣ አጥማጁ በኩል ደግሞ፣ ጀልባዋን በአንድ ሰንሰለት እንዲያብታትና ቁልፉንም ራሱ መከፈት እንደሚኖርበት አስጠንቅቀው። ስለዚህ ያን በመሥራት ጊዜያን አላባክንም። በተጨማሪ የነፋስ ሽራዎቹን ለመስቀል መሰናዳትና ወደ ገላጣው ባሕር የሚያወጡት ሦስት መቅዘፊያዎች መኖር አለባቸው።»

«ግን ጀልባዋኮ አንድ ትንሽ ሞተር አላት»

«አሃ፣ ይኼማ በጣም የተሻለ ነው። ዶሚያሞቅ መስሎ ሞተሩን እያሠራ ይተወዉና፣ ከዚያም አቅራቢያው ወደሚገኝ ቡና ቤት ይሔድ። እኛን ሲያይ አንድ ጥቁር የመርከበኛ ጃኬት ለብሶ ከጀልባዋ በስተኋላ ይቁም።»

«የገንዘቡስ ጉዳይ እንዴት ነው?»

«የአንተን ድርሻ ለሁለት እከፍለዋለሁ። የዓሣ አጥማጁን ሰባት ሺ በቅድሚያ እከፍላለሁ። የአንተን ግማሽ ከፍያ ከጊዜው ቀደም እድርጌ አሰጥሀና ሌላውን ግማሽ እዚህ ከሚቀሩን ፈረንሣዮች ውስጥ በአንደኛው አማካይነት ይሰጥሃል። የትኛው እንደሚሆን እነግርሃለሁ።»

«እንደማታምነኝ ተረዳሁ። ይህ ጥሩ አይሆንም።»

«አይደለም፣ አላምንህም ለማለት ሳይሆን፣ ግን ኤሌክትሪኩን ምናልባት በትከከል ኮንታክት አታደርገው ይሆናል። እንደዚያ ከሆነ ደግሞ አልከፍልህም። ምክንያቱም ኮንታክት ካላደረገ መውጣት አንችልም።»

«እሺ።»

ማንኛውም ነገር ተዘጋጅቶ ነበር። በወሀኒ አዛዡ አማካይነት ሰባት ሺውን ፔሶ ለዓሣ አጥማጁ ከፈልኩና ለአምስት ቀናት የተመደበው አንድ ዘበኛ ብቻ ሲሆን፣ የዙብ ሣጥኑም ተሠርቷል። የምንጠበቀው ዝናሙን ብቻ ነበር። ግን ሊመጣ አልቻለም። ቋሚ ብረቶቹ ከአዛዡ በተበረከተልን የብረት መጋዝ ተቆርጠው ነበር። የተቆረጠው

t.me/OLDBOOKSPDF

በሚገባ ተሸፍኗል፤ በተጨማሪም «ቆሻሻ» ማሉት አጥንታ የነበረች አንዲት በቅቅ በምትኖርበት ጎጆ ተከልሎ ነበር። በለቀቀን ላይ ሆነን በየሴሊቱ አንጠባበቃለን፤ ግን ዝናብ የለም። የዝናቡ በዚህ ወቅት መጥፋት የማይታመን ነበር። ከመስኮታችን ማዶ ያለችው ትንሽ ደመና በተስፋ ትሞላንና፤ አልም ትላለች። ዕብድ ወደ መሆን ደረጃ የሚያደርስ ነበር። ልባችን በጉሮሯችን እንደ ተወተፈ ዐሥራ ስድስት ቀንና አሥራ ስድስት ሌሊት ሙሉ አቆብቁበን ጠበቅን። አሑድ ሧት ግቢው ውስጥ እንዳለሁ የወህኒ አዛዡ እኔ ዘንድ መጣና ወደ ቢሮው ይዞኝ ሔደ። ባለ ግማሽ ኖቶች አንድ ጥቅልና ሦስት ሺ ሙሉ ፔሶ ሰጠኝ።

«ምንድን ነው የሚደረገው?»

«ፈረንሣዊው ጓደኛዬ የመጨረሻው ዕድልህ ዛሬ ሌሊት ነው። ካ ጧት በዐሥራ ሁለት ሰዓት ወደ ባራንኳላ ትሔዳለህ። ከአሣ አጥማጁ የተመለስልህ ሦስት ሺ ፔሶ ብቻ ነው። ምክንያቱም የቀረውን አጥፍቶታል። ዛሬ ሌሊት ለማዝነም እግዚአብሔር ፊቃዱ ከሆነ፣ አሣ አጥማጁ ይጠብቅሃል፣ ጀልባውን ስትወስድ ቀሪ ገንዘቡን ልትሰጠው ትችላለህ። አምንሃለሁ።»

ከባራንኳላ ማምለጥ

ከጧቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን፣ በስምንት ወታደሮችና ሁለት ዐሥር አለቆች የታጀበ አንድ መቶ አለቃ በካቴና አሠረንና በአንድ የወታደር ካሚዎን ወደ ባራንኳላ ጉዞ ቀጠልን። አንድ መቶ ዐሥሩን ማይል በሦስት ሰዓት ተኩል ጨረስነው። በአራት ሰዓት፤ «80»ው ካሌ ሚዶሊን ከተባለ ባራንኳላ ውስጥ ከሚገኘው ወህኒ ቤት ገባን። ባራንኳላ ከመሐድ ለመዳን ያን ሁሉ ጥረት እንዳላደረግን ሁሉ አዚሁ መጣን! ወደ መሐል ሀገር ገባ ብሎ በማግዳሌና ወንዝ አፍ ላይ የተቆረቆረ የኮሎምቢያ ትልቁ ወደብና እንቅስቃሴ ያለው ከተማ ነበር። ወህኒ ቤቱም እንደዚሁ አራት መቶ አሥረኞችና አንድ መቶ ዘበኞች ያህል ያሉት በጣም ትልቅ ከርቸሌ ነበር። ልክ እንደ አውሮፓውያን ወህኒ ቤቶች ቁመቱ ከሐያ አምስት ጫማ በላይ በሆነ ድርብርብ ግንብ የታጠረ ነበር።

በወህኒ ቤቱ ሠራተኞችና በዲሬክተሩ በዶን ግሪጎሪዮ አቀባበል ተደረገልን። ወህኒ ቤቱ አራት ግቢዎች ሲኖሩት፣ ሁለቱ በአንድ ጎን፣ ሁለቱ በሌላ ጎን ሆነው መካከሉ ለቅዳሴና ለጎብኝዎች በሚያገለግል አንድ ረጅም የጸሎት ቤት የተከፈለ ነበር። በጣም አደገኛ ለሆኑ አሥረኞች ከተከለለው ግቢ ውስጥ ገባን። ሲበረብሩን የእኔን ሐያ ሦስት ሺህ ፔሶና ፍላፃዎቹን አገኟቸው። መርዛማ መሆናቸውን ለዲሬክተሩ ማስጠንቀቅ የእኔ ተግባር ነው ብዬ ገመትኩ። ግን ሙግሳን ለማትረፍ አልረዳንም።

t.me/OLDBOOKSPDF

«እነዚህ ፈረንሣዮች መርዛማ ፍላፃ ሳይቀር አላቸው!» ተባልን።

በእስቸጋሪው ጉዟችን ውስጥ በጣም ከፍተኛውን የአደጋ መድረክ የያዘው ባራንኳላ ነበር። ሰፈረንሣይ ባለሥልጣኖች የምንመለሰውም ከዚሁ ነበር። አዎ፣ ባራንኳላ በጣም ወሳኝ ነበር። የፈለገውን ዋጋ ቢጠይቀንም ከዚህ ማምለጥ ነበረብን። ይኸው ብቻ እንጂ ሌላ ምንም አማራጭ የለም።

ከፍላችን በግቢው መካከል ነበር። ከፍል ሳይሆን፣ አንድ ወጥመድ ነበር። በወፍራም የብረት አግዳሚዎች ላይ በሲሚንቶ የተከደነ ጣሪያ ኖሮት መጸዳጃውና የቱም መታጠቢያው ከአንድ ጥግ በኩል ይገኛል። ሌሎች አንድ መቶ የሚሆኑ እሥረኞች ደግሞ ፍርግርፍ በሮቻቸው ወደግቢው ተከፋች ሆነው፣ ስፋታቸው ስድሳ በአንድ መቶ ሐያ ጫማ በሆኑ ከአራቱም ግንቦች ጋር በተያያዙ ክፍሎች ውስጥ ይገኛሉ። ከአያንዳንዱ ፍርግርግ በላይ ዝናም ወደ ክፍሎቹ እንዳይገባ መከላከያ የሚሆን እንደ ቆርቆሮ የመሰለ አሸንዳ ተንጠልጥሎበታል። የመካከሉን ወጥመድ የያዝነው እኛ ስድስት ፈረንሣውያን ብቻ ስንሆን፤ ለዘበኞችም ሆነ ለአስረኞች ቀንና ሌሊት ተጋልጠን የምንታየውም እኛው ነበርን። ከጧት ዐሥራ ሁለት ሰዓት አስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ቀኑን ሙሉ የምናሳልፈው በግቢው ውስጥ ነበር። ምንጊዜም በፈለግንበት ወቅት ወደ ወጥመድ መግባትና መውጣት እንችላለን። ማውራት፣ መዘዋወርና በግቢው ውስጥ መብላት ሳይቀር እንችላለን።

አዚህ ከደረስን ከሁለት ቀናት በኋላ፣ ወደ ጸሎት ቤቱ ተወሰድንና፣ ከሰባት ወይም ስምንት የጋዜጣ ሪፖርተሮችና ፎቶግራፍ አንሺዎች፣ ፖሊሶችና ከዲፊክተሩ ፊት ቀረብን።

«በፈረንሣይ ጊያና ከሚገኘው የቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ያመለጣችሁ እስረኞች ናችሁ?»

«አይደለንም አላልንም»

«ወንጀሎቻችሁ ምን ነበሩ?»

«ይኸ ቁም ነገር የለውም። ቁም ነገሩ ኮሎምቢያ ግዛት ውስጥ ምንም ወንጀል አልፈጸምንም። ግን ሀገራችሁ አዲስ ሕይወት እንዳንጀምር ከመቃወሚም በላይ ለፈረንሣይ መንግሥት የአዳኝ ውሻ ሚና መጫወቷ የሚያሳዝን ነው።»

«ኮሎምቢያም በግዛቷ ውስጥ አትፈልጋችሁም።»

«እኛም ለመቅረት አንፈልግም። የተያዝነው በዓለም አቀፍ ባሕር ላይ ነበር። አዚህ ለመምጣት አልሞከርንም። እንደ እውነቱ ደግሞ በተቻለ መጠን ከዚህ ርቀን ለመሔድ ማንኛውንም ጥረት አድርገን ነበር።»

ከአንድ የካቶሊክ ጋዜጣ የመጣ ሪፖርተር። «ፈረንሣውያን ልክ እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ኮሎምቢያውያን ከሞላ ጎደል ካቶሊኮች ናቸው» አለ።

«በካቶሊክነት ተጠምቃችሁ ይሆናል፤ ግን የምትፈጽሙት አድራጎት ክርስቲያን ሊያስብላችሁ ያዳግታል» አልኩ።

«ከእኛ ጋር ምን ቅራኔ አለህ?»

«ማንቁርታችንን ሊያንቁ ከተነሡብን ባለሥልጣኖች ጋር ተባብራችኋል። የአነርሱን ሥራ እናንተ ታከናውኑላቸዋላችሁ። ከማንኛውም ንብረቶቻችን ጋር ጀልባችንንም ወረሳችሁብን፤ ልጨምር የምፈልገው ጀልባዋ ከኩራሶ ካቶሊካውያን በጨዋው አቡናቸው በኢሬኒ ደብሩዬን በኩል የተሰጠችን ገጸ በረከት መሆኗን ነው። ራሳችንን እናርም ብለን ብንሞክርም ልትፈቅዱልን ፍላጎት የላችሁም፤ ከዚህ የባሰው ደግሞ ሊቀበለን ፈቃደኛ ወደሆነ የትኛውም ሀገር ከመሔድ አገዳችሁን።»

«ይህን በእኛ በኮሎምቢያውያን ላይ ትፈርዳላችሁ እንዴ?»

«በኮሎምቢያውያን ሕገቦች ሳይሆን በፖሊሶቻችሁና ፍርድ ሥርዓታችሁ ነው።»

«ይህን ስትል ምን ማለትህ ነው?»

«የምለውማ ፈቃደኝነት ካለ ስሕተቶቹ ሁሉ መታረም ይችላሉ። ወደ ሌላ ሀገር ለመሔድ አንድ ዕድል ስጡን ነው።»

«እንሞክራለን።»

ወደ ግቢው ከተመለስን በኋላ ማቹሬ እንደዚህ አለ። «ይገርማል! ይገርማል! ነገሩ ሁሉ ግልጽ ሆነላችሁ አይደለም? ከእንግዲህ ጭበዝነት እንዳያጠቃን። ያለጥርጥር ማጥ ውስጥ ገብተናል፤ ለመውጣት ደግሞ እንደዚህ ቀላል አይሆንም።»

«መልካም ጓዶች፤ በሕበረት ለመጋፈጥ ጠንካራ ነን ወይም አይደለንም፤ አላውቅም። ግን አስታውሱ፣ የተሻለ ነው ብላችሁ ራሳችሁ የምታስቡትን ለማድረግ ሁላችሁም ነፃ ናችሁ። በእኔ በኩል ግን ከዚህ መውጣት እንዳለብኝ ነው፤ ያው ነው፤ ያው ነው።»

ሽክ ያለ ልብስ የለበሰና ዕድሜው ዐርባ አምስት ዓመት የሚሆነው አንድ ሰው ወደ ነበረበት የንብኝዎች ክፍል ሐሙስ ቀን ተጠርቼ ነበር። ትኩር ብዬ ተመለከትኩት። ከሉዊ ዴጋ ጋር የሚያሳስት ተመሳሳይነት ነበረው።

«ፓፒዮ አንተ ነህ?»

«አዎ»

«የሉዊ ዴጋ ወንድም ዮሴፍ ነኝ። ምን ሆናችሁ እንደነበር በጋዜጣ ላይ አነበብኩ።»

«አመሰግናለሁ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ወንድሜን እዚያ አይተኸዋል? ታውቀዋለህ እንዴ?»

ከሆስፒታል እስከ ተለያየንበት ጊዜ ድረስ ያለውን የዲጋን የጉዞ መዘክር በዝርዝር ተነተንኩለት። ከዚያም ወንድሙ በዴላልዩ ደሴቶች መኖሩን በማርሲይ በኩል ዐውቆ እንደነበረ አርሱም አወሳ። ከሚስቶቻቸው ጋር የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ ባራንኳላ የመጡ ጥቂት ፈረንሣውያን እንደሚኖሩም በተጨማሪ ነገረኝ። ሁሉም አቃጣሪዎች ነበሩ። በከተማው አንድ ልዩ ሠፈር ሃያ የሚሆኑ ወይዛዝርት ፈረንሣውያን የታወቁበትን የሽርሙጥና ሙያ ያካሔዳሉ። ከካይሮ እስከ ሊባኖስ፣ ከእንግሊዝ እስከ አውስትራሊያ፣ ከቦይነስ አይረስ እስከ ካራካስ፣ ከሲይሻን እስከ ብራዛቪል፣ ተመሳሳይ ወንዶችና ሴቶች የሠለጠኑበትን ሥራ ሲያካሒዱ ይገኛሉ። ይኼ በዚሁ ይቆይ።

ከዚህም በላይ የባራንኳላ አቃጣሪዎች በጭንቅ ላይ መሆናቸውን ጠቆመኝ። የእኛ መምጣት ሰላማቸውን የሚያናጋባቸውና የተሟሟቀ ንግዳቸውን አደጋ ላይ የሚጥልባቸው መስሏቸው ሠግተው ነበር። አንዳችን ወይም ሁላችንም ብናመልጥ፣ በምንም መንገድ ባይተባበሩን እንኳ ወዲያውኑ ፖሊሶች እንደሚከታተሏቸው ግልጽ ነው። በዚህ ሒደት ደግሞ እንደ ሐሰት ሰነዶች፣ ዋጋ የሌላቸው ወይም ጊዜ ያለፈባቸው የጎብኝዎች ፈቃዶችና ብዙ ነገሮች ፖሊሶቹ ሊያጋልጡ ይችላሉ። ከተገኙባቸው ከባድ ችግር ላይ የሚወድቁት ጥቂቶች አይሆኑም።

ማንኛውንም ዓይነት መረጃ ገለጸልኝ፣ ከዚያም ሌላ አእምሮዬ ውስጥ ለሚጉላላው ለማንኛውም ችግር ከጎኔ እንደሚቆምና ዘወትር ሐሙስ እና እሑድ በጸሎት ቤቱ ሊጠይቀኝ እንደሚመጣ ነገረኝ። በቃሉ የጸና ሰው መሆኑን በተደጋጋሚ በማስመስከሩ ይህን ጠንካራ ጓደኛ አመሰግነዋለሁ።

ከጋዜጦቹ አባባል ፈረንሣይ እኛን ለመረከብ ፈቃድ አግኝታ እንደነበር ጨምሮ ነገረኝ።

ወደ ክፍል ሰመለስ ወሬውን አበሠርኳቸው። « ከቡራን፣ ግብዝነት እንዳያጠቃን። ለፈረንሣይ ሊያስረክቡን ወስነዋል። እኛን መልሶ የሚወስድ አንድ ልዩ ጀልባ ከፈረንሣይ ጊያና እየመጣ ነው። በተጨማሪ፣ እዚህ ከተማ የሞቀ ንግድ ባላቸው ፈረንሣውያን አቃጣሪዎች ዘንድ የእኛ እዚህ መገኘት የፈጠንቱት ምክንያት የሆነ ይመስላል። እኔን ለማየት የመጣውን ሰው አይመለከተውም። ስለእነርሱም ሰሜት የለውም። ባልደረቦቹ ግን ከእኛ አንዳችን ብናመልጥ አንኳ ሁሉም ችግር ላይ እንደሚወድቁ ፈርተዋል።»

ሁሉም ሣቁ፣ የምቀልድ መስሏቸው ነበር። «ውድ አቶ አቃጣሪ ለማምለጥ ፈቃድዎን ማግኘት እችላለሁ?» ሲል ከሎሲዎ አሽሟጠጠ።

«ይኸ ፈጽ አይደለም። ከአቃጣሪዎቹ ግንም እኛን ለማየት ቢመጣ ወዲያው

t.me/OLDBOOKSPDF

ማባረር አለብን። እሺ?»

«እሺ»

ቀደም ሲል እንደ ገለጽኩት እኛ ግቢ ውስጥ አንድ መቶ ያህል ኮሎምቢያውያን አሥረኞች ይገኛሉ። ከየዋህነት የራቁ ነበሩ። እሳት የላሱ ሌቦች፤ የታወቁ ሰነድ ደላዦች፣ ጨካኞችና የማይራሩ ወመኔዎች፤ አደጋ በመጣልና በዘረፉ የተካኑ፤ የኢንዝቨር ዕፅ ኮንትሮባንዲስቶችና በተለይ ቁጥራቸው ባይበዛም ለነፍሰ ገዳይነት የሠለጠኑም ነበሩ። በዚህኛው ከፍለ ዓለም እነዚህ ነፍሰ ገዳዮች ለከበርቴዎች፣ ለፖለቲከኞችና ለተዋጣላቸው ጀብደኞች አስፈላጊዎች ነበሩ።

በቆዳቸውም ቀለም እንደዚሁ ከፍተኛ ልዩነት ነበራቸው። ከሴኔጋላዊው ጥቁር እንሥቶ የሻይ ቀለም እስካለው የማርቲኒክ ከልሰ፣ እንደ ጡብ ቀይ ከሆነውና ቁጥ ያለ ሐምራዊ ጸጉር ካለው ሕንዳዊ እስከ ጠራው ነጭ ይገኙባቸዋል። ከእነርሱ መካከል አንዳንድ ግንኙነት አደረግኩና ለማምለጥ ያላቸውን ምኞትና ችሎታ ለመገምገም ሞከርኩ። ብዙዎቹ የእኔው ተመሳሳዮች ነበሩ። ፍርዳቸውን የሚጠባበቁ ወይም ቀደም ሲል ረጅም ፍርድ የተቀበሉ ስለሆኑ ምን ጊዜም ለማምለጥ ዝግጁ ነበሩ። የእኛን ግቢ ከከበቡት አራት ግንቦች በላይ አንድ ትንሽ ማማ ኖሮት ሌሊት ሲሆን በደማቅ መብራቶች ይጠበቃል። ስለሆነም ቀንና ሌሊት አራት ዘበኞች በጥበቃ ላይ ነበሩ። እንደዚሁም በጸሎት ቤት መዝጊያ አንድ ሌላ ተጨማሪ ዘበኛ ይመደባል። ይህ ዘበኛ መሣሪያ አይታጠቅም።

ምግቡ በቂ ስለሆነ፣ ብዙዎቹ አሥረኞች ከውጭ የሚመጣላቸውን ምግብ፣ ቡና፣ ወይም ብርቱካን፣ አናናስ፣ ፓፓዬ ወዘተ . . . የመሳሰሉ የፍራፍሬ ጭማቂዎች ይሸጣሉ። በየጊዜውም የዱብዳ ደደጋ ጭዳዎች ነበሩ።

ከአደጋው ፈጣንነት የተነሣ ጩኸት እንዳያሰሙ ፊታቸው ላይ የሚታሠረውን ትልቅ ጨርቅና ላመል ታህል ቢነቃነቁ በአንገታቸው ወይም በጀርባቸው የሚጠልቀውን ጩቤ ለመመልከት አንኳ አይችሉም። የመታቸውን ሳያውቁት ገና ድሮ ተበርብረዋል።

ከዚያም አንድ ፈጣን ጡጫ ማጅራታቸው ላይ ይቀምሱና ፎጣው ይገለጥላቸዋል። ይህም መደምደሚያው ይሆናል። ማንም ሰው ዳግመኛ ስለዚህ አያነሣም። አንዳንድ ጊዜ ያ ኪሱን የተራቆተው ሰው ልክ ሱቁን እንደ ተዘረፈ ነጋዴ ባላንጣውን ፍለጋ ይሔዳል። ካገኘውም የጩቤ ጦርነት ምንጊዜም የማይቀር ነበር።

ሁለት ኮሎምቢያውያን ሌቦች አንድ ሐሳብ ይዘው ወደ እኔ ቀረቡና በጥንቃቄ አዳመጥኳቸው። አንዳንዶቹ ፖሊሶች እንደ ሌቦችም ሆነው በመጣመር የሚሠሩ ይመስላል። በከተማ ውስጥ ጥበቃ ላይ ሲመደቡ ግብረ አበሮቻቸውን እንደልብ ወደሥራቸው እንዲሰማሩ ይጠቁሟቸዋል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉበኟዎች እነዚህን በሙሉ ስለሚያውቋቸው፣ በሚመጣው ሳምንት ከእነዚህ ፖሊሶች አንዱ በጸሎት ቤት በር ላይ መመደቡ በሚገባ አስተማማኝ መሆኑን ገለጹልኝ። በአሥረኛ ጉበኟዎች መጠየቂያ ሰዓት አንድ ሽጉጥ በእጇ ሊገባ ነው። ወደ አንዲት ትንሽ የዘበኞች ቤት የሚከፈተውን የጸሎት ቤቱን የኋላ መዝጊያ የፖሊስ ሌባው እንዲቆረቁር በቀላሉ ማሳመን ይቻላል። በውስጧ ከስድስት ሰዎች የበለጡ ፊጽሞ አይኖሩም። እጇ ላይ ሽጉጥ ቢያዩ ድንጋጤ ስለሚይዛቸው፣ ወደ ጎዳናው ከመገለቅ አይገቱንም። ከዚያ በኋላ ትርምሱ ውስጥ ገብቶ ለመጥፋት ቀላል ይሆናል።

ዕቅዱን አምበዛም አልወደድኩትም። ለእኔ አንድ ሽጉጥ ማቀበሉ በጣም ቀላል ይሆናል፤ ከዚህ ይበልጥ ከባዱ ዘበኞችን ማስፈራራቱ ላይ ነበር። ወይም ከእነርሱ አንዱ የተሳሳተ እንቅስቃሴ ያሳይና ለመግደል አገደድ ይሆናል። ስለዚህ አይሆንም አልኩ።

ለአንድ ድርጊት ተፈጻሚነት በምኞት የምንገበገበው እኔ ብቻ ሳልሆን ጓደኞቼም እንደዚያው ነበሩ። የጀልባዋን መድረስ በጉጉት የሚጠባበቁ አየመሰሉ ቀን ይገፉሉ። ከዚያ ወዲያ ሁሉንም ነገር አርግፍ አድርጎ ተስፋ ወደ መቁረጡ መቃረብ ጊዜ የማይወስድ ጉዳይ ይሆናል። ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ስንደርስ ምን ዓይነት ፍርድ እንደሚበየንብንና ምን ዓይነት አቀባበል እንደሚጠብቀን እንኳ ካሁኑ ይወያዩ ነበር።

«እንደዚህ የመሰለውን ወሬ መስማት ጭራሽ አልፈልግም። ያን ለማውራት ከፈለጋችሁ በሌላ አካባቢ አድርጉት። እኔ ልሰማችሁ በማልችልበት አንድ ጥግ ይዛችሁ አውሩ። ወኔአችሁን ምን ሰለበው? ወንዶች አይደላችሁም? የነካችሁ ነገር ካለ እባካችሁ ንገሩኝ፤ እናንት ጓደኞቼ አንድ ነገር አንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ። ስለማምለጥ በማስብበት ወቅት አቅዱን የማዘጋቸው ለሁላችንም ነው። ማምለጥ እንዴት እንደሚቻል ዕቅድ በማውጣት አንጎሌ የሚጨነቀው ለሁላችንም ስል ነው። ሌላ አንድ ነገር ደግሞ ልንገራችሁ። ጊዜያችን መቃረቡንና እኛም ጣና ያላመለጥን መሆናችንን ከተረዳሁ፣ ተጨማሪ ጊዜ ለማግኘት ስል አንድ ኮሎምቢያዊ ፖሊስ እገድላለሁ። ከእነርሱ አንዱን ከገደልኩ፣ ለፈረንሣውያኖቹ ሊያስረከቡኝም። ይህም ተጨማሪ ጊዜ ያስገኝልኛል። ከዚያ በኋላ ብቻዬን አመልጣለሁ። እስከዚህ ድረስ ቀላል ነው።»

ኮሎምቢያውያኑ በተግባር ላይ የሚውል አንድ ሌላ ዕቅድ አወጡ። ይሽኛው ጥሩ ነበር። አሉድ ጧት ጸሎት ቤት ዘወትር በጉበኟዎችና በአሥረኞች ይሞላ ነበር። በቅድሚያ ቅዳሴ ይደረግና ፎ ካበቃ በኋላ አሥረኞቹ ከጎብኟዎቹ ጋር በጸሎት ቤት ውስጥ ይቆያሉ። የሚቀጥለው አሉድ ወደ ቅዳሴ ሔጂ ነገሮቹ እንዴት እንደሆኑ እንዳይና፣ በተከታዩ አሉድ ለምንወስደው አርምጃ ቅንብር ማድረግ እንድንችል ነበር። ዓመፁ ውስጥ ኮሎምቢያውያኑ ጠየቁኝ። የዓመፁ መሪ እኔ እንድሆንም ሐሳብ አቀረቡ። ዓመፁ ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

የዘጡትን ሰዎች ስለማላውቃቸው ሹመቱን ውድቅ አደረግኩት።

ለእኛ ለአራቱ ፈረንሣውያን ግን ተስማማሁ። ብሪቶኑና ጓደኛው በዚህ ውስጥ ሊካፈሉ አልፈለጉም። ለዚህ ችግር አይኖርም። እነርሱ ወደ ጸሎት ቤቱ እንሒድም አሉ። እኛ ሒድን። ጸሎት ቤት አፊት ማዕዘን ከፍል ነበር። ጎላ ቤተመቅደሱ ሲገኝ ወደ ውስጥ የሚከፈቱ ሁለት መዝጊያዎች ከጎንና ጎን ነበሩት። ዋናው በር የሚከፈተው በዘበኞቹ ቤት በኩል ሆኖ፣ ከጎላ በኩል በብረት ፍርግርግ ተሸፍኖ ሐያ ዘበኞች ቆመዋል። ከእነርሱ ጎላ ወደ ጎዳና የሚያስወጣ መዝጊያ ነበረው። በቅዳሴ ጊዜ ጸሎት ቤት ስለሚሞላ፣ ዘበኞች ፍርግርጉን መዝጊያ ከፍተው ይተዉና በተርታ ተጠጋግተው ይቆማሉ። ከጎብኚዎቹ መካከል ሁለት ወንዶችና ጥንዶቻቸው መካከል መሣሪያ የሚይዙ ሁለት ሚስቶቻቸው ይኖራሉ። ወዲያው ጸሎት ቤት እንደሞላ ባለ .38 ወይም .45 ካሊበር ሁለት ሽጉጦች ለወንዶቹ ያቀብሏቸዋል። ለዓመፁ መሪ አንድ ከባድ ካሊበር ሽጉጥ አንዲት ሌላ ሴት ትሰጠውና ወዲያው ትወጣለች። የጸሎት ቤቱ ብላቴና ለሁለተኛ ጊዜ ደወል ሲያሰማ ሁላችንም በአንድ ጊዜ ልናጠቃ ነበር። እኔም አንድ ትልቅ ጩቤ በዲፊክተሩ ጉሮሮ ላይ አጋድሜ፣ ሐእንዲያሳልፉን ትእዛዝ ስጥ፣ አለበለዚያ እገድልሃለሁ› ልለው ነበር። አንድ ሌላ ሰው ልክ ተመሰሳይ ድርጊት በቁሱ ላይ ሊፈጽም ነበር። በሦስት ልዩ ልዩ ማዕዘን የቆሙት ሌሎቹ ሦስት ደግሞ በዋናው መግቢያ ፍርግርግ ወደ ቆሙት ፖሊሶች ጠመንጃዎቻቸውን ሊወድሩ ነበር። መሣሪያውን ለመጣል የሚያንገራግረውን የመጀመሪያ ዘበኛ ለመግደል ተወሰኗል። በመጀመሪያ መሣሪያ ያልታጠቁት ቀድመው ይወጣሉ። ቁሱና ዲፊክተሩ በመጨረሻ ለሚወጡት እንደ ሽፋን ሆነው ያገለግላሉ። ማንኛውም ነገር እንደ ታሰመው ከሠመረ፣ ፖሊሶቹ በሙሉ ጠመንጃዎቻቸውን ያስቀምጣሉ። ከዚያም ሽጉጥ የያዙት ሰዎች ወዴ ጸሎት ቤቱ ውስጥ እንዲገቡ ያስገድዷቸዋል። በመጀመሪያ ፍርግርጉን ከዚያም የአንጨቱ መዝጊያ እንዘጋባቸውና እንሔዳለን። የዘበኞቹ ቤት ባዶ ይሆናል። ምክንያቱም ቅዳሴ ላይ ለመገኘት ግዴታ ይኖርባቸዋል። ከውጭ በኩል በሃምሳ ያርድ ርቀት ላይ፣ ፈጠን ብለን ለመንጠልጠል እንዲረዳን አንድ ትንሽ መሰላል ከጎላው ያስደገፈ አንድ ካሚዎን ይጠብቀናል። ካሚዎኑ መንቀሳቀስ የሚጀምረው መሪያችን ከገባ በኋላ ብቻ ነው። ጸሎት ቤቱን ለመልቀቅ የመጨረሻው እርሱ ይሆናል።

የቅዳሴውን ሒደት ተከታተልሁና በዕቅዱ ተስማማሁ።

ዮሴፍ ዴጋ አሐዱ አልተገኘም። አንዲት አሳሳች ታከሲ እያዘጋጀልን ስለነበረ፣ በካሚዎኑ በመሐድ ፋንታ አሳቻ ቦታ ልንከለል ነው። ሳምንቱን ሙሉ በሐሳብ ተወጥሬ ነበር። ድርጊቱ እስኪጀመረ ድረስ መጠበቅ አቃተኝ። መሪያችን ፈርናንዶ፣ የአንድ ኮሎምቢያዊ ሲቪል ዘበኛ ንብረት የሆነ አንድ አስደንጋጭ .45 ሽጉጥ ለማግኘት

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሳከቶለት ነበር። ሐሙስ ከዮሴፍ ዴጋ ወይዛዝርት አንዷ ልትጠይቀኝ መጣች። በጣም ሽጋ ነበረች። ታከሲው ቢጫ ስለሚሆን ሊያሳስተን እንደማይችል ነገረችኝ።

«መልካም ዕድል» አሰችና ሁለቱንም ጉንጮቼን በዝግታ ሳመችኝ። ስሜቷ ከመጠኑ በላይ የተነካ ይመስላል።

«ግቡ፤ ግቡ። ይህች ጸሎት ቤት ትሙላ፤ የእግዚአብሔር ቃል እንሰማ ዘንድ» አሉ ቄሱ።

ረጋ ብዬ በመራመድ ቦታዬን ያዝኩ። ከሉሲዎም ከአንድ በኩል ወደ እኔ ጠጋ ብሎ ቆመ። ማቹሬም ዐይኖቹን እያቁለጨለጨ በሌላ በኩል ሆነ። ዲሬክተሩ ዶን ግሪጎሪዮ በቀጥታ ከፊት ለፊት ከአንዲት ሴት ቀጥሎ ተቀምጧል። ወደ ጎዳና ከወጣን ብለን ሁላችንም የለበስነው በማያስነቃ ሁኔታ ነበር። ጩቤዬን ከቀኝ ከንዴ ሥር ሰጥፌ በአንድ ወፍራም የላስቲክ ማሰሪያ ይገጥለሁ። በእጄ እንጓ ላይ አዝራሩን አጥብቄ በቆለፍኩት ካኪ ሸሚዝ እጅጌ ተሸፍና ነበር። አሁን ቡራኬ ለመቀበል የመነሻው ጊዜ ደረሰ። መሬት ላይ አንድ ነገር የሚመለከቱ መስለው ሰዎቹ ሁሉ ጭንቅላቶቻቸውን አቀረቀሩ። የጸሎት ቤት ብሳቴና ደውሉን በፍጥነት አወዛወዘና ከዚያም ሦስት ጥርት ያሉ ድምጾች ተንቃጨሉ። ሁለተኛው የእኛ ምልክት ነበር። አያንዳንዳችን ምን እንደምናደርግ ዐውቀናል።

አንደኛ ደወል፣ በሁለተኛው ደወል ... ዶን ግሪጎሪዮ ላጋ፦ተመረወርኩና ጩቤዬን በተሸበሸበው ወፍራም እንጉቱ ላይ ደቀንከብት። «እግዚአብሔር ዘበአረትህን አውርድልኝ፤ አትግደለኝ» ብለው ቄሱ ተማፀኑ። ሌሎቹን ማየት አልፌ ፡ኩም፣ ግን ጠመንጃዎቻቸውን እንዲጥሉ ዘበኞቹን ሲያስገድዷቸው አሰማቸዋለሁ። ማንኛውም ነገር በትክክል ሰምሮ ነበር። ዶን ግሪጎሪዮን በልብሱ ኮሌታ እየጎተትኩ፣ ወተከተለኝ፣ አይዞህ አትፍራ፣ አልጎዳህም» አልኩት።

ቄሱም በጉሮሯቸው ላይ አንድ ስለት ተጋድሞባቸው ነበር።

«ፈረንሣዊው አይዞህ፤ ወደ መዝጊያው እናምራ» አለኝ ፈርናንዶ። ሁለት ተኩሶች ተከታትለው የሰማሁት፣ ድል አድራጊነት ተሰምቶኝ ምርኮኞቹን ወደ ጎዳናው በሚያወጣው በር አቅጣጫ በመግፋት ላይ እንዳለሁ ነበር። ፈርናንዶና ከታጠቁት አስረኞች አንዱ መሬት ላይ ወደቁ። ሌላ ሦስት ጫማ ወደፊት ተንቀሳቀስኩ። ግን አሁን ዘበኞቹ ራሳቸውን አደራጅተው ኖሮ መተላለፊያውን በማገድ ላይ ነበሩ። የዕድል ጉዳይ ሆኖ አንዳንድ ሲቶች በመካከላችን ስለቆሙ መተኮስ አልተመቻቸውም። የጠመንጃው ተኩስ ቀጠለ። ሦስተኛው ባልደረባችን ዓላማ የለሽ ተኩስ ተኩሶ አንዲት ትንሽ ልጃገረድ ካቆሰለ በኋላ ተመትቶ ወደቀ። ዶን ግሪጎሪዮ እንደሞተ ሰው አመድ መስሎ «ይህን ጩቤ ስጠኝ» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በአጁ ላይ አስቀመጥኩለት። ጦርኑን መቀጠሉ ዋጋ የለውም። ሠላሳ ሴኮንድ ባልሞላ ጊዜ ሁኔታው የተገላቢጦሽ ሆነ። ዓመፁ የከሸፈው፣ ከጸሎት ቤቱ ውጭ ሆኖ ይመለከት በነበረ አንድ አስረኛ ምክንያት መሆኑን ከአንድ ሳምንት በኋላ ተረዳሁ። የመጀመሪያው እርምጃ ከተወሰደ ሴኮንድ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በሰገነቱ ላይ ያሉትን ዘበኞች አስጠንቅቋቸው ኖሯል። ሐያውን ጫማ ወደ ግቢው ዘለሉና፣ ከጸሎት ቤቱ ጎንና ጎን ቦታ በመያዝ በመዝጊያዎቹ ዳር ባለው ቋሚ መካከል ፖሊሶቹን እያስፈራሩ ከአንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ቁመው በነበሩት ሁለት ሰዎች ላይ ተኮሱባቸው። ሦስተኛውም ሰው የተገደለው ከትንሽ ሴኮንድ በኋላ ሂላማቸው ራሱ መጥቶ ሲገባላቸው ነበር። ከዚያ በኋላ የተከተለው ድንቅ የሆነ «የወይፈን ውጊያ ትርዒት» ነበር። እየጮኸ ትእዛዝ ያስተላልፍ ከነበረው ከዲሬክተሩ ጎን ጠጋ ብዬ ቆየሁ። እኛን ፈረንሣውያንን ጨምሮ ዐሥራ ስድስታችንም በዳቦና ውሃ ብቻ በአንድ ጨለማ ግንብ ውስጥ ታጎርን።

የሴፍ ዴጋ ዶን ግሪጎሪዮን ጎበኘው። ወደ ውስጥ ጠራኝና የሴፍ ዴጋን ለማስደሰት ሲል እኔንና ጓደኞቼን ወደ ግቢው መልሶ የሚያወጣን መሆኑን ገለጸልኝ። ስለዚህ ለዴጋ ምስጋና ይድረሰውና ዓመፁ ከተካሔደ ከዐሥር ቀን በኋላ በግቢው ውስጥ ወደሚገኘው ወጥመዶቻን እንደገና ተመለስን። ሁላችንም አንድ ላይ ስንገናኝ በዓመፁ ላይ ለሞቱት ለፈርናንዶና ለሁለቱ ጓደኞቹ የትንሽ ደቂቃ ፀሎት ጠየቅኩ። ዶን ግሪጎሪዮን ጨምሮ አቃጣሪዎቹ የእርዳታ እጃቸውን እንዲዘረጉ አስተባብሮ እምስት ቪ ፔሶ እንኤ የሳበ ከጉበኝቶቹ በአንደኛው ወቅት ሮሴፍ ነገረኝ። አቃጣሪዎቹ ከፍተኛ ግምት የምንሳጣቸው ሆኑ።

ግን አሁን ምን ማድረግ ይሻላል? ምን አዲስ ዕቅድ ማለም እንችላለን? ሽንፈትን ለመቀበልና እጄን አጣጥፌ በመቀመጥ ያን ጀልባ ለመጠበቅ ምኞት አይኖረኝም፣ የእነርሱን ትኩረት ሳልማርክ በግንቡ ላይ ያሉትን ዘበኞች ማጥናት እንድችል ከምትጠብሰው ፀሐይ ፊቀቅ በማለት ከመታጠቢያው ከፍል ሥር አጋደማለሁ። ሌሊት ሲሆን ዘበኞቹ በየዐሥር ደቂቃው፣ «ዘበኞች፣ ተጠንቀቁ!» እያሉ በየተራ ይጮሃሉ። ይህ የሚደረገው፣ ከአራቱ ውስጥ ማንም ሰው አለመተኛቱን የዘበኞቹ ኃላፊ እንዲያረጋግጥ ነበር። ከእነርሱ እንደኛው መልስ ለመስጠት ካልቻለ አንድ ምላሽ አሰኪያገኝ ድረስ ዘበኛው ጩኸቱን ይቀጥላል።

በዚህ ሐይት እንዳለሁ አንድ ዓቢይ ድክመት ያገኘሁ መሆኔን ተገነዘብኩ። በእያንዳንዱ ግንብ አራት ማዕዘኖች ላይ ከዘብ ሣጥኑ አጠገብ አንዲት ጣሳ በገመድ ተንጠልጥላለች። ዘበኛው ቡና ሲፈልግ « ቡና» ብሎ ይጣራና አንድ ሰው ከጣሣው ውስጥ ይቀዳለታል። ከዚያም ዘበኛው በገመዱ ወደ ላይ ስቦ ይወስዳታል። ታዲያ በስተቀኝ በኩል ራቅ ብሎ የሚገኘው የዘብ ሣጥን ወደ ግቢው ገባ ብሎ ከተንጠለጠለ

t.me/OLDBOOKSPDF

ማማ ላይ ነበር። አንድ ወፍራም ሜንጦ ለመሥራት ከቻልኩ፣ ጠንካራ ሆኖ ከተፈተለ ገመድ ጋር አቆራኝና ማማውን በማስቆንጠጥ በትንሽ ሴኮንዶች ውስጥ በግንቡ ላይ ተንጠላጥየ ወደ ጎዳናው ለመግባት እችላለሁ። ብቸኛው ችግር ዘበኛውን እንዴት ማፍዘዝ እንደሚቻል ነበር። በግንቡ ላይ ትንሽ እርምጃዎች አግድም ሐዲ ቆም ሲል አየሁት። በሙቀቱ የተሠቃየ ይመስላል፣ ነቅቶ ለመቆየት እየታገለ ነበር። ይኸማ ይፈለጋል! እንዲተኛ መደረግ አለበት! በመጀመሪያ ገመዱን ፈትዬ ከዚያም አንድ አስተማማኝና ጠንካራ ሜንጦ ሳገኝ፣ እንቅልፍ እንዲተኛ አደርገውና ዕድሌን እሞክራለሁ። በተለይ ካኪ የሆኑና እጅቼ ሊገቡልኝ የቻሉትን ጠንካራ የጥጥ ሸሚዞች በመጠቀም ሰባት ያርድ የሚሆን ገመድ በሁለት ቀን ውስጥ ፈትዬ ነበር። ሜንጡውንም ማግኘት ቀላል ሆነ። ከፍሎቹን ከዝናም ለመከላከል ከተንጠለጠሉት አሸንዳዎች ላይ የአንዱን ማስደገፊያ መነተፍኩ። የሴፍ ዴጋ አንድ ኃይለኛ የእንቅልፍ መድኃኒት የያዘ ብልቃጥ አመጣልኝ። መግለጫው በአንድ ጊዜ ከዐሥር ጠብታዎች የበለጠ አይወሰድም ይላል። ብልቃጡ በግምት ስድስት ትልቅ ማንኪያዎች ይይዛል። እንደ ተላላኪ አድርጎ እንዲቀበለኝ ዘበኛውን አግባባሁት። ጣዣዋን ቁልቁል ይልከለኛል፣ በአንድ ጊዜ ሰባት ስኒ እየሞላሁ ወደ ላይ አመልስለታለሁ። ኮሎምቢያኖች ሲባሉ አልኮል አስከሚያፈቅሩ ድረስ የእንቅልፍ መድኃኒቱም በመጠኑ የአንቺ (አንስላል) ታና ስለነበረው፣ አንድ ጠርሙስ አረቄ ያዝኩ።

«የፈረንሣዮችን ዓይነት ቡና አሠራር እንዴት ትወደዋለህ?» ስል ዘበኛውን ጠየኩት።

«ምን ምን ይላል?»

«አውስጡ አረቄ ይጨመርበታል»

«እስኪ ልቅመሰው።»

ብዙዎቹ ዘበኞች የእኔን ቡና በአረቄ ይቀምሱልኝ ነበር። አሁን ቡናዎቻቸውን ስሰጣቸው ዘወትር፣ «የፈረንሣዩን ዐይነት» ይላሉ።

ስለዚህ አረቄውን ጠብ አደርጋለሁ።

ጊዜው ደረሰ። አንድ አሁድ ቀትር ላይ ነበር። ወበቁ የማይቋቋሙት ሆኗል። የጊዜ እጥረት ስለሚኖር፣ ሁለት ሰዎች በአንድ ጊዜ ማምለጥ እንደማይችሉ ጓደኞቼ ተገንዝበዋል። ግን ዓሊ በሚል ስም የሚጠራ አንድ ኮሎምቢያዊ ከእኔ ቀጥሎ አንጠላጠላለሁ አለ። እሺ አልኩ። በዚህ አይነት ከፈረንሣውያኑ ውስጥ ማንም ግብረ አበር አይጠየቅም።

በተጨማሪ ለዘበኛው ቡናውን በማፁበልበት ወቅት ገመዱና ጋንቾውን ለመሸሸግ ስለማይመቸኝ፣ ዓሊ ገመዱን ይሸከምልኛል። መድኃኒቱ በአምስት ደቂቃ

t.me/OLDBOOKSPDF

ውስጥ ድብን አድርጎ እንደሚዘርረው ተማምነናል።

አሁን፣ አምስት ጉዳይ ነበር።

«እንዴት ይሆሃል?» ሰል ወደ ዘበኛው ተጣራሁ።

«ደህና ነኝ።»

«ትንሽ በና ትፈልጋለህ እንዴ?»

«አዎ፣ የፈረንሣይ ዓይነት።»

«ዮይ፣ አመጣልሃለሁ።»

ወደ በና አሳላፊው ሐድኩና፣ «ሁለት በና» አልኩ፣ በብልቃጥ ውስጥ ያለውን የእንቅልፍ መድኃኒት በሙሉ ቀደም ሲል ጣሳዋ ውስጥ ከትቻለሁ። ይኼ የማይዘርረው ከሆነ ደግሞ፣ ከማማው ሥር እንደሆንኩ ሰው ሁሉ እንዲመለከተኝ በማጋነን አረፋውን ጨመርኩበት።

«ጠንከር እንዲልልህ ትፈልጋለህ እንዴ?»

«አዎ»

አሁንም ትንሽ ጠበታ ጨመርኩለትና ወደ ላይ ሳባት። አምስት ደቂቃ አለፈ፤ ከዚያ ዐሥር፣ ዐሥራ አምስት፣ ሐያ። እርሱ ግን ገና አልተኛም ነበር። ከመቀመጥ ፋንታ እንዲያውም ይባስ ብሎ ጠመንጃውን በእጁ እንደያዘ፣ ወደ ኋላና ወደ ፊት ይንሳፈፍ ጀመር። ጣሣዋን በሙሉ ጨልጧታልኮ! ቀያሪው ዘበኛ የሚመጣው በሰባት ሰዓት ነው። እንቅስቃሴዎቹን ተሰፋ በቆረጠ ሰሜት አከታተላለሁ። መድኃኒት የመቅመስ ምልክት አይታይበትም። አህ! አለና ትንሽ ተንገዳገደ። ከዚያም ራሱን ወደ ትከሻው ዘንበል በማድረግ ጠበንጃውን በጭኑ መካከል እንደያዘ፣ ከዘብ መቆሚያ ሣጥኗ ፊት ለፊት ተቀመጠ። ሁላችንም ልክ እንደ ጭልፊቶች ሆነን እንቅስቃሴውን እንከታተላለን። «አሰኪ ወደዚያው ሒድ» አልኩት ኮሎምቢያዊውን። «አሁን ገመዱን አዘጋጅ።»

ሲወረውር ሲዘጋጅ ነበር፣ ዘበኛው ቁም ሲል፣ ጠመንጃው ወደ መሬት ወድቆበት አለበት ቦታ የሚሮጥ መስሎ የተንደረደረው። ኮሎምቢያዊው ቶሎ አቆመ። ዘበኛ እስኪቀያየር ድረስ አሥራ ስምንት ደቂቃዎች አሉ። በሆዴ የእግዚአብሔርን እርዳታ ተማፀንኩ። «ለአንድ የመጨረሻ ጊዜ ብቻ አምላኬ! ፈጥኜ ተግፅኜሃለሁ፤ አሁን አትጣለኝ!» አንዳንድ ጊዜ የምሄድባቸው መንገዶች በጣም ሚስጢራዊ ናቸውና በተለይ የእኔ አይነቱ ከሃዲ ይህን የከርስቲያን አምላክ መጥራት ዋጋ አልነበረውም።

«ይህን እንዴት ታየዋለህ!» አለ ከሎሲዎ ወደ እኔ እየመጣ።

«ያ የውሻ ልጅ ለምን እንቅልፍ አይወስደውም?»

ዘበኛው ጠመንጃውን ማንሳት ሲጀምር ወደ ታች ጎንበስ እንዳለ፣ ልክ በመብረቅ የተመታ መስሎ ተዘረጋ። ኮሎምቢያዊው ገመዱን ወረወረ፤ ግን ሜንጦው

t.me/OLDBOOKSPDF

መቆንጠጥ ስላልቻለ ገመዱ ወደ ታች ወደቀ። ለሁለተኛ ጊዜ ሲወረውረው ጨምድዶ ያዘ። የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ጎተተው። እኔም በድጋሜ ፈተሸኩና እግሬን ግንቡ ላይ ሳሳርፍ ነበር ከሎሲዎ «ተሸንፋችኋል! ተቀያሪው ዘበኛ እዚህ ነው!» ያለው።

እርሱ ከሚያየኝ በፊት ለመደበቅ ጊዜ ነበረኝ። ራሴን ለማዳን ባለኝ ተፈጥሮአዊ ፀጋና በአሥረኞቹ መካከል የሚታየው መተሳሰር አሥራ ሁለት የሚሆኑ ኮሎምቢያውያን ቶሎ ከብበው ከመካከላቸው አስገቡኝ።

ገመዱ እንደተንጠለጠለ ትተን በግንቡ ሥር አግድም ሄድን። ሜንጦውንና የተዘረረውን ዘበኛ ሁለቱን አንድ ጊዜ ቀያሪው ዘበኛ አገኛቸው። ማምለጥ ተካሒዶ መሆን አለበት ብሎ ስለተጠራጠረ ትንሽ ያርድ ሮጠና የኢደጋ ማስጠንቀቂያ ደወል ተጫነ።

ዕንቅልፍ ለወሰደው ዘበኛ አንድ ቃሬዛ አመጡለት። ከሐያ የበለጡ ፖሊሶች በግንቡ ላይ ቆሙ። ዶን ግሪጎሪዮም እዚያው ላይ ስለወጣ፣ ገመዱን ወደ ላይ ሳበው። ሜንጦውን በእጁ ይዘት ነበር። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ጠመንጃ የወደሩ ፖሊሶች በግቢው ውስጥ ይፏልሉ ጀመር። ስም መጥራት ያዙ። ከእያንዳንዱ ስም በኋላ ተጠሪው ወደ ከፍሉ ይላክ ነበር። ይገርማል! አንድም የጎደለ አልነበረም።

ሁለተኛው ፍተሻ ከከፍል ወደ ከፍል ነበር። የጎደለ አልተገኘም። በዘጠኝ ሰዓት ወደ ግቢው አንድንወጣ ተፈቀደልን። ዘበኛው አሁንም ገና በድን መሆኑንና ምንም ነገር እንዳላነቃው ተረዳን። እንደ እኔው ኮሎምቢያዊው ተባባሪየም ልቡ በሐዘን ተሰበረ። እንደሚሳካልን በጣም ተማምኖ ነበር። የዕንቅልፍ መድኃኒቱ ከአሜሪካን ፋብሪካ የወጣ ስለነበር፣ የአሜሪካ የሆኑትን ነገሮች በሙሉ ተሳደበ።

«እንግዲህ የምናደርገው ምንድን ነው?»

«ለምን እንደገና አንጀምርም ሰውዬ!» ማሰብ የቻልከት ይህንኑ ብቻ ነበር። በእርሱ ቤት ሌላ ዘበኛ እንቅልፍ እናስተኛ ማለቴ መስሎታል። «ከእንግዲህ የፈረንሣዩ ዓይነት ቡና ብትላቸው ዳግመኛ የሚጠጡልህ፣ እነዚህ ዘበኞች ሞኞች ናቸው ብለህ ታስባለህ እንዴ?» አለ።

የምንገኝበት ሁኔታ አሳዛኝ ቢሆንም መሣቅ ነበረብኝ። «ጓዶቼ፣ ለእኔ ይህ አያስደንቀኝም!»

ዘበኞችን ሦስት ቀንና አራት ሌሊት ተኛ። በመጨረሻው ሲነቃ፣ እኔ እንቅልፍ እንዲወስደው ያስደረግኩት ያው በፈረንሣይ ዓይነቱ ቡናዬ መሆኑን ገለፀ። ዶን ግሪጎሪዮ ጠራኝና ዘበኛውና እኔ ፊት ለፊት ተፋጠጥን። የዘበኛው ኃላፊ ሊመታኝ ጎራዴውን አምዘገዘገ። ሸወድኩትና ወደ አንድ ጥግ ፈግፈግ አልኩ። ጎራዴው በአየር ላይ እንዳለ ዶን ግሪጎሪዮ ሊገላግል በመካከላችን ሲገባ ትከሻውን አገኘውና መሬት ላይ ወደቀ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በመውደቁ የትከሻው ቀጭን ስንጥር ተሰበረ። ከፉኛ ከመጓጉ የተነሣ የዘበኛው ኃላፊ ሙሉ ትኩረቱን ወደ እርሱ አዙሮ ነበር። ዶን ግሪጎሪዮ ለአርዳታ በመጮህ ላይ እንዳለ እርሱ አነሣው። በአቅራቢያው ከሚገኙት ቢሮዎች ሲቪል ሠራተኞች እየተሯሯጡ መጡ። የዘበኛው ኃላፊ፣ ሌሎች ሁለት ፖሊሶችና፣ መድኃኒት አጠጥቼው የነበረው ዘበኛ፣ ዲሬክተራቸውን መበቀል ከሚፈልጉት አስረኞች ጋር የተጋጋፈ ጦርነት ጀመሩ። ብዙዎቹ በመጠኑ ቆስለው ነበር። አንድም ሳልሞር ያመለጥኩት እኔ ብቻ ነበርኩ። በዲሬክተሩና በዘበኛው ኃላፊ መካከል የተጫረው ጠብ ብቻ እንጂ የእኔ ጉዳይ ከቁጥር አልገባም።

ዲሬክተሩ ወደ ሆስፒታል ተወስዶ ስለነበር፣ የእርሱ ተወካይ ወደ ግቢዬ ይዞኝ ሲመለስ «የእንተን ጉዳይ በኋላ እናያለን ፈረንሣዊው» አለ።

በሚቀጥለው ቀን ዲሬክተሩ ትከሻው ላይ ጀሶ ታስሮለት ተመለሰ። ዘበኛውን በመቃወም በጽሁፍ ቃሌን እንድሰጥ ጠየቀኝ። የጠየቀኝን ማንኛውንም ነገር በደስታ ፈጸምኩ። የእንቅልፍ መድኃኒቱም ጉዳይ ሙሉ በሙሉ ተዘንግቶ ነበር። ዕድለኛ በመሆኔ እንጂ፣ ችላ የሚባል አልነበረም።

ከትንሽ ቀናት በኋላ ከውጭ በኩል አንድ ነገር አቀነባብሬ እንድሞክር ዮሴፍ ዴጋ ሐሳብ አቀረበ። ከግንቦቹ ላይ ባሉት መብራቶች ምክንያት በሌሊት ማምለጥ የማይቻል መሆኑን ገልጨለት ስለነበር፣ ኮረንቲውን ማቋረጥ የሚቻልበትን ዘዴ አመጣ። በአንድ የኤሌክትሪክ ቴክኒሺያን ተባባሪነት ከወህኒ ቤቱ ውጭ በአንድ ትራንስፎርመር ማብሪያና ማጥፊያውን መቆጣጠር የሚቻል ሆኖ አግኝቶታል። በጸሎት ቤቱ መዝጊያ፣ በግቢው ውስጥና በመንገዱ ዳር የሚገኙትን ዘበኞች በመደለል መማዘት ነበረብኝ። ከጠበቅኩት በላይ የተወሳሰበ ሆነብኝ። በቅድሚያ በዮሴፍ አማካኝነት ለቤተሰቦቼ ነው በሚል ሰበብ ዶን ግሪጎሪዮ አሥር ሺ ፔሶ መልሶ እንዲሰጠኝና ለዚህም «ግግባቢያ» ለሚሰቱ አንድ ስጦታ እንዲገዛበት በሚል ሽፋን ሁለት ሺ ፔሶ እንዲቀበለኝ ግፊት አደርጋለሁ። ከዚያም በግንቡ ሠገነት ላይ የሚዘዋወሩትና የሚቀያይረው ዘበኛ የትኛው እንደሆነ ፈልጌ መደለል ነበረብኝ። የሚከፈል ሦስት ሺ ፔሶ ሲሆን፣ ግን ከሌሎቹ ሁለት ዘበኞች ጋር በማደርገው ስምምነት ውስጥ ተካፋይ አይሆንም። እነርሱም መፈለጉና ከእነርሱ ጋር መስማማቱ የእኔ ጉዳይ ይሆናል። ስማቸውን እሰጠውና፣ ከዚያም በእኔ መመሪያ መሠረት የጥበቃ ተረኝነት ምድባቸውን ያስተካከላል።

ይህ የማምለጥ ዝግጅት ከወር በላይ ፈጀ። በመጨረሻም ማንኛውም ሁኔታ በቅደም ተከተል ተቀነባበረ። በግቢው ውስጥ ያለው ዘበኛ እስከማያሠጋን ድረስ፣ ቋሚ ብረቶችንም በብረት መጋዝ ቆረጥናቸው። ሦስት ጠርዞች ነበሩት። ሜንጦውን ለሚሠራው ኮሎምቢያዊ መመሪያ ተሰጥቶታል። ቋሚ ብረቱን የሚቆርጠው እያረፈ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር። ለመሥራት በሚያቅድበት ሴሊት፣ በአንድ ወቅት አብድ ሆኖለሁ ብሎ የሚያታልል ጓደኛውን አንድ ቁራጭ ቆርቆሮ እየደበደበ ድምፁን ከጣሪያ በላይ አድርጎ እንዲዘፍን አድርጎታል። ዘበኛው እንዲያመልጡ ቆርጦ የተስማማው ለሁለት ፈረንጣውያን ብቻ መሆኑን ኮሎምቢያዊው ዐውቋል። አንድ ሦስተኛ ሰው ካለ እንደሚተኩሰበት ነበር። ግን ያም ሆኖ ለመሞከር ስለፈለገ፣ ሦስታችንም አንድ ላይ ተጠጋግተን ጥብቅ ካልን፣ ሦስት ወይም ሁለት መሆናችን በጨለማ ውስጥ መለየት እንደማይሆንለት አሰበ። ከእኔ ጋር ግን እንደሚሄድ ከሎሲዎና ማቼሬ ፅጣ ተጣጣሉ። ከሎሲዎ ወጣለት።

የመጀመሪያው ጨረቃ አልባ ሴሊት መጣ። ሃምሳ አለቃውና ሁለቱ ፖሊሶች ግማሽ ከፍያ ፕንዘባቸውን ወስደዋል። ባሁኑ ጊዜ ኖቶቹን መመንዘር አላስፈለጎንም። ቀደም ሲል ተመንዝረው ነበር። ፖሊሶቹ ቀሪውን ግማሽ የዮሲፍ ዴጋ ሚስት ከምትሠራበት ከቻይና መጠጥ ቤት ሊወስዱ ነበር።

መብራቱ ጠፋ። በቋሚ ብረቱ ሥራ ተጠመድን። ዐሥር ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ። ጥቁር ሱሪና ሸሚዞች እንደለበሰን ከከፍሎቹ ውስጥ ተንጠላጠልን። ኮሎምቢያዊውም ከአንድ ጥቁር ካናቴራ በስተቀር ራቁቱን እንደሆነ መተላለፊያው መንገድ ላይ ተገናኘን። የመዝጊያችንን ቋሚ ብረቶች ረገጥኩና ወደ ማማው አቅጣጫ በመንጠላጠል፣ ሦስት ያርድ ርዝመት ካለው ገመድ ጋር ሜንጦውን ወረወርኩት። ሦስት ደቂቃ ሳይሞላ በግንቡ ላይ ነበርኩ። አንድ ድምፅ አላሰማውም። በሆዴ ለጥ ብዬ ከሎሲዎን አጠብቃለሁ። ጨለማው የጥቁር ጥቁር ነበር። ወደ ላይ እየደረሰ እንደገና የሚወርድ አንድ እጅ በድንገት አየሁ ወይም እንዳየሁ ገመትኩ። ሲጢጥ የሚል አንድ ጩኸት ነበር። ከሎሲዎ በግንቡና በማማው መካከል ተንጠልጥሎ እንዳለ፣ የቀበቶውን ዘለበት አንድ ቆርቆሮ ይዞበት ኖሯል። መጎተቱን አቆምኩ። ጩኸቱም አቆመ። ከሎሲዎ አላቅቆ ይሆናል ብዬ በመገመት እንደገና ጎተትኩ። ግን የቆርቆሮው ሲጢጥታ ቀጠለ። እስኪላቀቅ ድረስ አወዛወዝኩና ከዚያም መንጭቄ ወደ ላይ አወጣሁት።

ከሌሎች የጥበቃ ቦታዎች ተኩሶች ተንጣጡ። በተኩሱ ሳንሸበር በግንቡ አሳቻ አቅጣጫ በኩል ወደ ውጭ ዘለልን። ወደ ቀኝ ራቅ ብንል ኖሮ ከዘለልን በኋላ የምናርፍበት ቦታ ከአሥራ አምስት ጫማ የማይርቅ ሲሆን፣ እዚህ ለካስ ከሐያ አምስት ጫማ በታች የወረደ ኖሯል። በዚህም ምክንያት ከሎሲዎ የቀኝ ቅልጥሙን እንደገና ተሰበረ፣ እኔም እንደዚሁ መቆም አልቻልኩም። የሁለቱንም እግሮቼን መጋጠሚያዎች ተሰበረ፣ እኔም እንደዚሁ መቆም አልቻልኩም። የሁለቱንም እግሮቼን መጋጠሚያዎች ተሰብሬ ነበር። ኮሎምቢያዊውም ጉልበቱ ከቦታው ተለያየ። የጠመንጃው ተኩስ ተሰብሬ ነበር። ኮሎምቢያዊውም ጉልበቱ ከቦታው ተለያየ። የጠመንጃው ተኩስ ዘበኞቹን ወደ መንገዱ ዳር አወጣቸው። በአንድ ትልቅ የኤሌክትሪክ ፋኖስ ተለቀምንና ዘበኞቹን ወደ መንገዱ ዳር አወጣቸው። በአንድ ትልቅ የኤሌክትሪክ ፋኖስ ተለቀምንና ጠመንጃ ተደገነብን። በንዴት አለቀስኩ። ከዚህም በላይ ቆሜ መሐድ አለመቻሌንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘበኞቹ ሊረዱልኝ አልቻሉም ነበር። ወደ ወህኒ ቤቱ የተመለስኩት፣ በጠመንጃ ሰደፍ እየተገሸምኩና በጉልበቴ እየዳሁ ነበር። ከሎሲዎና ኮሎምቢያዊው በአንዳንድ እግራቸው እንጣጥ ይላሉ። በአንድ የጠመንጃ ሰደፍ ምት ከጭንቅላቴ ደም እየጎረፈ ነበር። በአጋጣሚ በዚያ ሌሊት ዶን ግሪጎሪዮ የጥበቃ ተረኛ ስለነበር፣ ቢሮው ውስጥ ተኝቶ እንዳለ፣ የጠመንጃው ተኩስ አባነነው። እርሱ ባይኖር ኖሮ ዘበኞቹ ጨርሰውን ነበር። ከፉኛ ሲደበድበኝ የነበረው ሁለቱን ተባባሪዎቻችንን እንዲመድበልኝ ደልየው የነበረው ሃምሳ አለቃ ነበር። ዶን ግሪጎሪዮ ድብደባው እንዲቆም አዘዘ። ከፍተኛ ጉዳት ካደረሱብን ለፍርድ እንደሚያቀርባቸው ዛተባቸው። ይህ አስማታዊ ቃል ግንኙውንም ሰው ጋብ አደረገው።

በሚቀጥለው ቀን የከሎሲዎ ቅልጥም ሆስፒታል ውስጥ በጀሶ ተጠነሰች። የኮሎምቢያዊውም የጉልበት ውልቃት በአንድ እሥረኛ ገባለትና በፋሻ ታሠረለት። ሌሊቱን እግሮቼ ልከ ጭንቅላቴን አክለው አበጡና ከተቋጠረው ደም የተነሣ ቀለማቸው ወየበ። ዶከተሩ እግሮቼን በጨው ውሃ እየዘፈዘፈ በቀን ሦስት ጊዜ በዋገምት ይመጥልኛል። ደም ሲሞላባቸው ዋገምቶቹ ይነቀሉና ኮምጣጤ ውስጥ ይዘፈዘፋል። ኮምጣጤ ያደርግባቸዋል። የጭንቅላቴን ቁስሎች ለመድፈን ስድስት ቦታ ተሰፋሁ።

ይህን መነሻ በማድረግ አንድ ጋዜጠኛ ስለ እኔ አንድ ሐተታ ጻፈ። የጸሎት ቤት ዓመፅ መሪ እንደ ነበርኩ፣ አንድ ዘበኛ እንደ መረዝኩና ከዚህም በላይ ለማጋነን ያህል፣ ከውጭ ካሉ ተባባሪዎች ጋር በመረዳዳት በትራንስፎርመሩ አማካይነት ኤሌክትሪክ እንዲቋረጥና የጅምላ ማምለጥ እንዲደረግ አነሣሥቷል ሲል ገለጸ።

በማጠቃለያውም፣ «በቁጥር አንድ ከሆነው ከዚህ የሕዝብ ጠላት ፈረንሣይ በተቻለ ፍጥነት እንደምትገላግለን ተስፋ እናደርጋለን» አለ።

ዮሴፍ ዴጋ ከሚሰቱ ከአን ጋር ሆኖ ጎበኘኝ። ሊላወጓ ግማሽ ገንዘባቸውን ሊጠይቁ ሃምሳ አለቃውና ዘበኞቹ በየተራ መጥተው ነበር። ምን ማድረግ እንደሚኖርባት አን ማወቅ ስለፈለገች፣ በቃላቸው እስከረጉ ድረስ መከፈል አለባቸው አልኳት። ያልተሳካልን በእነርሱ ስህተት አልነበረም።

አሁን ለአንድ ሳምንት ያህል በግቢው ዙሪያ የምገፋው፣ እንደአልጋ ሆኖ የሚያገለግል አንድ የብረት ጋሪ ነበር። ከጋሪው እጀታዎች ጋር ቀጥ ብለው በተያያዙ ሁለት እንጨቶች መካከል በተጋደመ ነገር ላይ እግሮቼን አስደግፌያለሁ። እፎይታ ማግኘት የምችልበት መንገድ ይኸው ብቻ ነበር። እግሮቼ አሁንም አብጠው ስለነበር፣ ተጋድሜ እንኳ ጥቂት ማንቀሳቀስ አልቻልኩም። ከዐሥራ አምስት ቀን በኋላ አብጠቱ በማሽ ስለወረደ፣ ራጅ ለመታየት ተወሰድኩ። ከዚያ በኋላ ነበር፣ ሁለቱም ቁርጭምጭሚቶቼ መውለቃቸውን የተረዳሁት። ከዚያ ጊዜ ጀምሮም እስከ መጨረሻው

t.me/OLDBOOKSPDF

. ሰፊድ እግር ሆንኩ።

«ማና» በፈረንሣውያን ፖሊሶች ታጅባ በወሩ መጨረሻ ወደ እኛ እንደምትመጣ የዛሬው ጋዜጣ አበሠረ። ዛሬ ጥቅምት ዐሥራ ሁለት ሲሆን፣ ዐሥራ ሥምንት ቀን ቀርቶናል። የመጨረሻዋን ዕድላችን መሞከር አለብን፣ ግን በነዚያ በተሰበሩት ቁርጭምጭሚቶቼ ምን ለማድረግ እንችላለን?

ዮሴፍ ተስፋ ወደ መቁረጥ ላይ ሆነ። ያን ያህል ለነጻነቴ ታግዬ በትንሽ ቀናት ውስጥ በፈረንሣውያን እጅ እንደምወድቅ በማሰብ በቻይና መጠጥ ቤት የሚገኙት ፈረንሣውያን ወንዶችና ሴቶች ማዘናቸውን ነገረኝ። በጣም ብዙ ደጋፊዎች ከጎኔ አሉኝ ከሚለው ሐቅ በመነሣት እርካታ አገኘሁ።

አንድ ኮሎምቢያዊ ፖሊስ እገድላለሁ የሚለውን ሃሳብ እርግፍ አድርጌ ተውኩት። ምንም ነገር ያላደረገኝን አንድ ሰው ለመግደል ራሴን መገፋፋት አልችልም። ምናልባት እናትና አባቱን የሚረዳ ይሆናል፣ ምናልባት ሚስትና ልጆች ይኖሩታል። ቤተሰብ የሌለው፣ አንድ ክፉ ፖሊስ አፈልጋለሁ በሚለው አስተሳሰቤ ፈገግ አልኩ። እንዴት ብዬ ጥያቄ ላቀርብለት እችላለሁ? «በገድልህ የአንተን እርዳታ የሚፈልግ ምንም ሰው ስላለመኖሩ እርግጠኛ ነህ?» ልለው? በዐሥራ ሦስተኛው ቀን ጧት የማደርገው ጠፋብኝ። ቢጨንቀኝ ጉበት በሽታ እንዲይዘኝ ስል ለመብላት የምመኘው ፒዜሪክ አሲድ ላይ አተኮርኩ። ሆስፒታል ከገባሁ ምናልባት ዮሴፍ በሚዋዋልልኝ ሰዎች እርዳታ ለማምለጥ እችል ይሆናል።

ዐሥራ አራተኛ ቀን፣ የበሰለ ሎሚ መሰልኩ። ዶን ግሪጎሪዮ በግቢው ውስጥ እንዳለሁ ሲያየኝ መጣ። እግሮቼን በአየር ላይ ዘርግቼ ጋሪዬ ላይ አንድ ጥላ ሥር እንደ ተጋደምኩ ነበርኩ።

ያለምንም ማመንታት ፊት ለፊት አፈረጥኩለት። «ሆስፒታል ልታስገባኝ ከቻልክ ዐሥሩ ሺ ፔሶ ላንተ ይሆናል።»

«አምክራለሁ ፈረንሣዊው። ዐሥር ሺ ፔሶ ለአኔ አስከዚህ ቁም ነገሬ አይደለም፤ ግን ያን ያህል ከባድ ትግል አድርገህ ሊቀናህ አለመቻሉ ያሳዝነኛል። ችግሩ ጋዜጣ ላይ የወጣው ያ ታሪክህ እያለ ሆስፒታሉ ውስጥ አንድትቆይ ይፈቅዱልሃል ብዬ አልገምትም። ይፈራሉ።»

ከአንድ ሰዓት በኋላ ዶክተሩ ወደ ሆስፒታል ልኮኝ ነበር። የምወጣውም ሆነ የምገባው ምንም ይሁን ምንም ያው በሽክም ብቻ ነበር። በአምቡላንሱ ቃሬዛ ላይ ተዘርሬ ከረጅም ምርመራና የሽንት ምርመራ በኋላ ሁለት ሰዓት ያህል ቆይቼ ወደ ወህኒ ቤቱ ተመለስኩ።

ዛሬ ዐሥራ ዘጠነኛው ቀን ሲሆን፣ ዕለቱም ሐሙስ ነው። የዮሴፍ ሚስት አን፣

t.me/OLDBOOKSPDF

ከአንድ ኮርሲካዊ ሚስት ጋር ልትጠይቀኝ መጣች። የእነርሱ የወዳጅነት ጉብኝት ያንን ቀፋፊ ቀን ወደ ጠራ የፀሐይ ብርሃን ቀየረው። የእነዚህ የባራንካላ የአራዳው ዓለም ሰዎች ድጋፍ ለእኔ ከባድ ውለታ ነበረ። በተለይም እንዳመልጥ ለመርዳት ሲል ሥራውንና የራሱን ነጻነት ለአደጋ ያጋለጠው ዮሴፍ ዴጋ የቱን ያህል ውለታ እንደዋለልኝ ቅጹም ማስረዳት አልችልም።

አን፣ በወሬያችን ጣልቃ አስገብታ አንድ ሐሳብ ያፈለቀልኝ አስተያየት ሰነዘረች።

«ውድ ፓፒዮ» አለች። «ነጻነትህን እንደገና ለማግኘት ስትል ለሰው ልጅ የምችለውን ማንኛውንም ነገር አድርገሃል። ዕድል አንተ ላይ ጨካኝ ሆነች። የቀረህ ነገር ቢኖር ወህኒ ቤቱን ማፈንዳት ብቻ ነው!»

«ታድያ እንዴት ነው! ይህን አሮጌ ወህኒ ቤት ለምን አላፈነዳውም? ለኮሎምቢያውያኖችም አንድ ከፍተኛ አገልግሎት አደርግላቸዋለሁ። ካፈነዳሁት ምናልባት አንድ አዲስና ንጹህ ግንብ ያንጹ ይሆናል።»

ውቦቹን ወይዛዝርት ደህና ሁኑ ብዬ ለመጨረሻ ጊዜ ስስም እንዲህ አልኩ። «ኢሑድ መጥቶ እንዲያየኝ ለዮሴፍ ንገሩልኝ።»

በሐያ ሁለተኛው ቀን ኢሑድ፣ ዮሴፍ መጣ።

«ሰማ፣ አንድ የፈንጅ ጉማጅ፣ አንድ ማቀጣጠያና የቢከፎርድ ገመድ ሐሙስ ልታመጣልኝ ሞክር። ለጡቡ አንድ መሰርሰሪያ ለማግኘት ራሴው አፈልጋለሁ።»

«ምን ልታደርግ ነው?»

«የዚህን ወህኒ ቤት ግድግዳ የቻልኩትን ያህል ላፈነዳው ነው። የማደርገውም በጠራራ ፀሐይ ነው። ለዚያ ባለ ቢጫ ታክሲ አምስት ሺ ፔሶ ቃል ግባለት። ከጧቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ ካሌሜደሊን በስተጀርባ ካለው መንገድ መቆየት አለበት። ምንም ነገር ካልሆነ በየቀኑ አምስት መቶ ፔሶ ያገኛል፣ ከተሣካ ደግሞ አምስት ሺውን። እስከ ታክሲው ድረስ በሚያዝለኝ አንድ ጠንካራ ኮሎምቢያዊ ጀርባ ሆኜ በተነደለው ግንብ በኩል አመልጣለሁ። የታክሲው ሾፌር ፈቃደኛ ከሆነ ፈንጅውን ላክልኝ። እምቢ ካለ ግን ይህ የመጨረሻ ሙከራዬ ይሆናል። እርግጡ አድርጌ አተዋለሁ።»

«አመነኝ ግዴለም» አለ ዮሴፍ።

ብቻዬን ሆኜ መጸለይ እፈልጋለሁ ብዬ በማስወራት አምስት ሰዓት ላይ ወደ ጸሎት ቤቱ አዝለው እንዲወስዱኝ አደረግኩ። ዶን ግሪጎሪዮም መጥቶ እንዲያየኝ ንገሩልኝ አልኩ። መጣ።

«ለመሐድ የቀረህ ስምንት ቀን ብቻ ነው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«የፈለግኩህም ለዚሁ ነበር። የራሴ የሆነ ዐሥራ አምስት ሺ ፔሶ አንተ ጋ አለኝ። ከመሐድ በፊት ለጓደኛዬ መስጠት አፈልጋለሁ፣ ገንዘቡን ሰቤተሰቦቼ ሊልከልኝ ይችላል። ከዘበኛቹ ስለ ተከላከልክልኝ የምስጋና መግለጫ እንዲሆነኝ ሦስቱን ሺ ፔሶ አንተ እንድትወስደው አፈልጋለሁ። በሚቀጥለው ሐሙስ ለጓደኛዬ አዘጋጅቼ እንዲጠብቅ፣ ከአንድ ማጣበቂያ ሙጫ ጋር ገንዘቡን ዛሬውኑ ልታገኝልኝ ከቻልክ፣ ከፍተኛ ውለታ እንዳደረግክልኝ አቆጥረዋለሁ።»

« እንደዚያው አደርጋለሁ።»

ሦስቱን ሺ ለራሱ አስቀረ፣ ዐሥራ ሁለቱን ሺ ፔሶ እንደለ አስረከበኝ።

ወደ ጋሪዬ ተመለስኩና፣ ወደ አንድ ፀጥ ያለ ጥግ ሔጄ ኮሎምቢያዊው ጓደኛዬን ጠራሁት። ዕቅዴን አስረዳሁትና አስከ ታክሲው ድረስ ያለውን ሐያ ወይም ሠላሳ ያርድ በጀርባው ሊሸከመኝ ይችል እንደሆነ ጠየቅኩት። እንደሚያደርግ ቃል ገባልኝ። ስለዚህ በዚህ በኩል ያለው ጉዳይ ተስተካከለ ነበር። ዕቅዴቼን የማያይዘው የሴፍ ቀንዶት ይመለስ ይሆናል በሚል ግምት ነበር። ሰኞ ጧት ማለድ ብዬ በመታጠቢያ ቤቱ አንድ ጥግ ያገኘሁና፣ ጋሪዬን «በመሸፈር» ከከሎሲዎ ጋር የሚተጋገዘውን ማቹሬን ሦስት ሺ ፔሶ ሰጥቼው የነበረውንና ያን በመሰለ አረመኔያዊ ድብደባ አፀፋውን የከፈለኝን ሃምሳ አለቃ እንዲፈልገው አደረግኩ።

«ሃምሳ አለቃ ሎፔዝ ላነጋግርህ እፈልግሃለሁ።»

«ምን ትፈልጋለህ?»

«የሦስተኛ ደረጃ ፍጥነት ያለው አንድ ጠንካራ መሠርሠሪያና ለጡብ መስበሪያ የሚሆን ስድስት መሮዎች በሁለት ሺ ፔሶ እንድታመጣልኝ እፈልጋለሁ። ሁለቱ የአንድ ኢንች አንድ ዐሥረኛ፣ ሁለቱ አራት ዐሥረኛና ሁለቱ ግማሽ ኢንች ውፍረት ያላቸው ይሁኑ።»

«እኔ ገንዘብ የለኝም።»

«አምስት መቶ ፔሶ ይሽውልህ።»

«ዘበኛው ሲቀየር ነገ በሰባት ሰዓት ይደርሱሃል። ሁለቱን ሺ ፔሶ አንድታዘጋጅ።»

በሚቀጥለው ቀን ሰባት ሰዓት ላይ ዘበኞቹ ሲቀያየሩ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት ውስጥ መሣሪያዎቹ ደረሱኝ። የእኔው ጠንካራ ጎበዝ ኮሎምቢያዊ ጳውሎስ ቀብ አደረገና ሸሸጋቸው።

ሐሙስ የሴፍ የውሃ ሽታ ሆኖ ዋለ። በመጨረሻው የጉብኝት ሰዓት ማብቂያ ገደማ ተጠራሁ። የሴፍ በአርሱ ምትክ፣ አንድ ጨምዳዳ ፊረንሣዊ ሽማግሌ ልኮ ነበር።

«የምትጠብቃቸው ነገሮች እዚህ ቁራጭ ዳቦ ውስጥ አሉልህ።» አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለታክሲው ሁለት ሺ ፔሶ ይኸውልህ። በየቂኑ አምስት መቶ ስጠው።»

«የታክሲው ሾፌር ግልፍተኛ የሆነ ሽማግሌ ቺሩያዊ ነው። ከእርሱ ጋር ንትርክ ውስጥ እንዳትገባ።»

ዳቦውን ያስቀመጡት በአንድ ትልቅ የወረቀት ኪስ ውስጥ ሲሆን፦ ሲጃራዎች፣ ከብራቶች፣ የተጠበሱ ቋሊማዎች፣ አንድ ቁራጭ ቅቤና አንድ ጠርሙስ ጥቁር የወይራ ዘይት ጋር አብሮ ነበር። እቦሩ ላይ ዘበኛው የወረቀት ከረጢቱን በመበረቃቅስ ላይ እንዳለ፣ አንድ ፓኬት ሲጃራ፣ ጥቂት ከብራቶችና ሁለት ቋሊማዎች ሰጠሁት። «ለዚህ ማባያ የሚሆነኝ አንድ ቁራጭ ዳቦስ እንዴት ነው?» አለ።

እኔም ከሁሉ የምፈልገው ያን ጥያቄ ነበር!

«አይሆንም፣ ራስህ ዳቦውን ግዛ። አምስት ፔሶ ያውልህ። እንዲያውም ለስድስታችን ይኼ በቂ አይሆንም።»

ኢየሱስ፣ አበቅቶልኝ ነበር! ቋሊማ ለሰውየው እንዲሰጥ ምን ሰይጣን ቦታወተኝ! ግን በተቻለ ፍጥነት ተሠወርኩት። ለዳቦው ቅሌት እምብዛም ያልተዘጋጀሁበት ከመሆኔ የተነሣ በላብ ተዘፍቄ ነበር።

«ነገ ርችቱ ይተኮሳል። ሁሉም ነገር ተዘጋጀ። ጳውሎስ፣ ሽንቁሩን ማበጀት ያለብህ ልክ ከረጅሙ ሠገነት ሥር መሆን አለበት። ስለሆነም እላይ ያለው ዘበኛ ሊያይህ አይችልም።»

«ግን ይሰማኛልኮ።»

«ስለዚያም አስቤበታለሁ። ጧት በአራት ሰዓት በዚያ በኩል ያለው ግቢ ጥላማ ይሆናል። በግንቡ ትይዩ አጠገብ ፀሐይ ላይ ሆኖ አንድ ነገር እንዲቆረቁር ከብረታ ብረት ሠራተኞቹ ውስጥ አንዱን እንመድባለን። እንዲያውም ሁለት ሰዎች ቢሆኑ ይሻላል። ለእያንዳንዳቸው አምስት መቶ ፔሶ አሰጣቸዋለሁ። ተጣጥረህ ሁለት ሰዎች ፈልግ።»

አገኛቸው።

«አስከሚፈልግበት ጊዜ ድረስ እዚያው እየቀጠቀጡ ለመቆየት የራሴው የሆኑ ሁለት ጓደኞቼ ተስማምተዋል። ስርሰራውን ዘበኛው ፍጹም ሊሰማ አይችልም። አንተም ከማማው ትንሽ ፈቀቅ ብለህ በጋሪህ ላይ ተቀመጥና ከፈረንሣውያኑ ጋር አንድ ውይይት ከፈት። በዚህ መንገድ ከግንቡ ሌላ ማዕዘን በኩል ያለውን ዘበኛው ትከልለኛለህ።»

ፋካው በአንድ ሰዓት ውስጥ ተሰርስሮ አበቃ። በመሰርሰሪያው ላይ ባለው ዘይትና በቅጥቀጣው ምክንያት ዘበኛው ምንም ነገር አልጠረጠረም። በተሰረሰረው ፋካ ውስጥ ፈንጅው ተጠመደና ማፈንጃው ስምንት ኢንች ከሆነ አንድ ገመድ ጋር ተያያዘ። ከዚያ አከባቢ ራቅን። ማንኛውም ነገር ተስተካክሎ ከተካሄደ፣ ፍንዳታው አንድ ትልቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀዳዳ በርግዶ ይከፍትና ዘበኛውም ከዙበ መቆሚያ ሣጥኑ ጋር አብሮ ይደረመሳል፣ እኔም በጳውሎስ ጀርባ ሆኜ በቀዳዳው ውስጥ ወደ ታከሲው አፈተልካለሁ። ሌሎቹ ራሳቸው ይወጣሉ። ምንም እንኳ እኔ የመጀመሪየው ብሆን፣ ከሎሲዎና ማቹሬ ምናልባት ከእኔ በፊት ታከሲ ውስጥ ቀድመው ይገቡ ይሆናል።

ከማቆጣጠላችን ቀደም ሲል ለአንድ የኮሎምቢያውያን ቡድን ጳውሎስ አሸጠነቀቀ። «ማምለጥ የምትፈልጉ ከሆነ ከትንሽ ደቂቃ በኋላ አንድ ሰፊ ቀዳዳ በግድግዳው በኩል ይከፈትላችኋል።»

ይህም ጥሩ እንደሚሆን ገመትኩ። ፖሊሶች የሚያተኩሩት መጨረሻ ላይ በሚሾልኩት ይሆናል።

ለኮስን። አንድ አስደንጋጭ ፍንዳታ አካባቢውን በሙሉ አነቃነቀው። ማማው ወደቀ። ግን አንድ ሰው ማሾለክ የሚችል ሰፊ ፋካ አይኑር እንጂ፣ በስተውጭ ያለውን መንገድ ለማየት የሚያስችሉ ቀዳዳዎች ግንቡ ተበዳድሶ ነበረ።

ሁሉም ነገር ዋጋ ቢስ መሆኑን መጨረሻ ላይ ለማመን ተገደድኩ። ወደ ካየን የመመለስ ዕድሌ በግልጽ ተወስኖ ነበር።

ፍንዳታው ያስከተለውን ትርምስ መዘርዘሩ ያዳግታል። ከሃምሳ የበለጡ ፖሊሶች ግቢውን አጥለቀለቁት። ተጠያቂው ማን እንደነበረ ዶን ግሪጎሪዮ በማያሻማ መንገድ አውቆታል።

«መልካም፣ ፈረንሣዊው፣ እንደሚመስለኝ የመጨረሻው ሙከራ ይኸው ነው።»

ከብስጭቱ የተነሣ የዘበኞቹ ሐላፊ እንደአውሬ ሆኖ ነበር። ጋሪ ላይ የተጋደመ አንድ አካለ ስንኩል ምታ ብሎ አንዱን ሰው ለማዘዝ ደግሞ ችግር ሆነበት። ለሌሎቹ ልከላከል ስለፈለግኩ፣ ማንኛውንም ነገር የፈጸምኩት እኔ መሆኔን ድምጼን ከፍ በማድረግ ለፈፍኩ። ስድስት ዘበኞች ከግንቡ ፊት ለፊት፣ ሌሎች ስድስት በወህኒ ቤቱ ግቢና ስድስት ከውጭ በኩል በመንገዱ ላይ እንዲቆሙ ተመድበው አንድ ግምበኛ የፈረሰውን አስኪጠግን ድረስ ጠበቁ። ደግነቱ ከማማው ጋር የወደቀው ዘበኛ አልተጎዳም ነበር።

ወደቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መመለስ

ከሦስት ቀን በኋላ ጥቀምት 30 ቀን ከጧቱ አምስት ሰዓት ላይ ነጫጭ ዩኒፎርም የለበሱ ዐሥራ ሁለት ዘበኞች እኛን ለመረከብ ከቅኝ ግዛቱ አሰቃቂ ወህኒ ቤት ደረሱ። ከመሐዲችን በፊት አንድ አጠር ያለ ሥነ ሥርዓት ተደረገ። የአያንዳንዳችን ማንነት መረጋገጥ ነበረበት። የሕይወት ታሪካችንን፣ ፎቶግራፋችንን፣ የጣት

t.me/OLDBOOKSPDF

አቫራዎቻችንንና አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ይዘው ነበር። በመረጃዎቻችን ለመጨረሻ ጊዜ ከተማመኑ በኋላ የፈረንሣዩ ቆንሲልና እኛም ለፈረንሣይ መልሶ ለማስረከብ ተወከለው የአውራጃው ዳኛ አንድ ሠነድ ሊፈራረሙ ብድግ አሉ። ዘበኞቹ በሚያሳዩን የጓደኝነት ስሜት ሁላችንም ተደንቀን ነበር። ጥላቻ የለም፣ የቁጣ ትዕዛዝ የለም። ለረጅም ጊዜ የቆዩት በእኛ ቡድን ያሉት ሦስቱ፣ ብዙዎቹን የቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህን ቤት ዘበኞች ስለሚያውቋቸው ልከ እንደ ቅርብ ጓደኛ ይቀላለዳሉ። የአጃቢዎቹ ኃላፊ ቦርሣል፣ ስለእኔ ሁኔታ ሠግቶ ነበር። እግሮቼን ተመለከተና «ብመርከቡ ላይ ምርመራ ይደረግልሃል» አለኝ። መርከቡ ውስጥ ጥሩ ጤና ረዳት ነበር።

አሮጌ ገላ መታጠቢያ በሚመስለው የምድር ቤት ውስጥ ታሸግን። ግን ከሁሉም የሚበሰው መታፈኑ፣ ወበቁና ሰንሰለቶቻችን የሚቆራኙባቸው «የፍርድ ምሰሶዎች» የሚባሉት ነበሩ። በጉዞው ውስጥ አንድ አሥቂኝ ጉዳይ ብቻ ተከናውኗል። ጀልባው ከትሪኒዳድ ከሰል ይጭን ነበር። ወደቡ ውስጥ እንደገባን፣ አንድ የእንግሊዝ ባሕር ኃይል መኮንን ሰንሰለቶቻችን እንዲፈቱልን ጠየቁ። መርከብ ላይ ያለን ሰው ማሠር የእንግሊዝን ሕግ መፃረር ነበር። በዚህ ውዝግብ መካከል ያን የእንግሊዝ ባሕር ኃይል መኮንን ፊቱን በጥፊ ለማቃጠል አጋጣሚ አገኘሁ። ታስሬ ወደ የብስ እንዲያወጡኝ ለመሞከር ነበር። ግን መኮንኑ፣ «አሁን ለፈፀምከው ላስቀጣህ አልፈልግም። የምትሔድበት ቦታ አሰከሚቢቃ ቅጣት ታገኛለህ» አለኝ።

ወደ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ለመመለስ በግልጽ የታጨሁ ነበርኩ። በጣም ያሣዝናል። አሥራ አንድ ወር በሙሉ ለማምለጥ ያደረግኩት ያ ሁሉ ትግል ያለምንም ዋጋ ቀረ። ቢሆንም የእኔ ወደ አስቃቂው ወህኒ ቤት መመለስ ያሳለፍኳቸውን አስደሳች ጊዜዎች እዚያ የሚያጋጥመኝ፣ የፈለገው ነገር ቢሆን፣ ፈጽሞ ሊፍቃቸው አይችልም።

እንኮን የማይወጣላቸው የበውን ቢተሰቦች ትዝታ የተቀሰቀሰብኝ ትሪኒዳድን ለቅቀን ስንወጣ ሲሆን፣ ከዚያም ታላቁ ሰው ኢሬኒ ደ ብሩየን በጸጸስነት ከሚያገለግሉበት በኩራሶ አጠገብ ስናልፍ አርሳቸውንም አስታወስኩ። በኢጋጣሚ የፍቅርን ንጹህነት ያወቅኩበት የጓጅራ ሕንዳውያንንም ቀበሌ እንደዚሁ ጠረፉን እየነካን አልፈን መሆን አለበት። እነዚያ ሕንዶች ነገሮችን የሚመለከቱት እንደ ሕጻን ግልጽ ባለ መንገድ ሲሆን፣ የሰውን ልጅ ችግር በመረዳትና በፍቅር የበለጸጉ ነበሩ።

ከዚያም የፒኮን ደሴት ቆማጦች፣ ከአሰቃቂው መከራቸው ጋር እነዚያ ጎስቋላ እሥረኞች፣ እኛን ለመርዳት አሳይተውት የነበረው ምግባረ ሠናይ በቀላሉ የሚዘነጋ አልነበረም።

በመጨረሻም ወደር የማይገኝለት የቢልጅጉ ቆንሲል ደግነትና ምግም

t.me/OLDBOOKSPDF

ያወቀኝ ለእኔ ብሎ ሳያስልስ ለማንኛውም ነገር ራሱን ለአደጋ ያጋለጠው የሴፍ ዴጋ፤ ለማምለጥ በማደርገው መከራ የእነዚህ ሰዎች ርዳታ እንድ ጠቃሚ ቁም ነገር አስገብይቶኛል። ምንም እንኳ ባይሳካልኝም፤ እነዚህ ልዩ ሰዎች ሕይወቴ ተሐድሶ ስላገናጸፉኝ፣ መከራዬ እንደ አንድ ድል ይቆጠር ነበር። በማንኛውም ደረጃ ቁጭት አይሰማኝም። አላደርገውም።

አሁን ወደ ማሮኒ ወንዝ ድፍርስ ውሃ ደርሰን ከጧቱ ሦስት ሰዓት ሲሆን፤ በ«ግና» መለል ላይ ቆመን ነበር። የምድር ወገብ ፀሐይ መሬቱን ታቃጥለዋለች። እንደዚያ በችኮላ ሔጄበት የነበረውን ወንዝ ዝግ አያልን ሽቅብ ተንሣፈፍንበት። ጓዶቹና እኔ ፀጥ ብለን ነበር። ዘበኞቹ በመመለሳቸው ደስ ብሏቸዋል። በጉዞው ወቅት ባሕሩ አስቸጋሪ ስለነበር፤ ከረጋ ውሃ ላይ መድረሳቸውም አስደስቷቸዋል።

ሕዳር 16, 1934

መሬት በምንደርሰበት ወቅት ድብልቅልቅ ያለ ትርምስ ነበር። እንደዚህ የመሰለውን ረጅም ጉዞ ለማድረግ ያልፈሩትን ሰዎች ለመመልከት ይመስላል ሰው ሁሉ አድናቆት የያዘው። በተጨማሪ አሑድ ስለነበረ ስለሁኔታው ያላወቁትንም ሰዎች እንደመስህብ ማርኳቸው ነበር። አንዳንድ ሰዎች «ያ መራመድ የማይችለው ፓፒዮ ነው። ያኛው ደግሞ ከሎሲም ነው፤ ያ ማቹሬ ነው» ሲሉ መስማት ችያለሁ። በዚሁ ሁኔታ ቀጠሉ።

ጠባይ ማረሚያው ሠፈር ውስጥ ከማንቡ ፊት ለፊት፤ ስድስት መቶ ሰዎች በሰልፍ ተደርድረዋል። ከአያንኳንዱ ጎን ዘበኞች ቆመዋል። በመጀመሪያ ያስታወስኩት ፍርኃት ሲየራን ነበር። በሕክምና ክፍሉ መስኮት በኩል ብቅ ብሎ በቀጥታ ወደ እኔ ይመለከታል። ራሱን መቆጣጠር ተስኖት ያለቅሳል። ሐዘኑ ከምር መሆኑ ግልጽ ነበር። ከካምፑ መካከል ስንደርስ ቁም ተባልን። የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ እንድ የድምፅ ማጉሊያ ብድግ አደረገ።

«ለእሥረኞች በሙሉ! እመልጣለሁ ብሎ ለሚሞክር ይህ ማረጋገጫ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። የማያስራችሁና ወደ ፈረንሣይ የማይመልሳችኁ ሀገር የለም። ማንም ቢሆን እንደ እናንተ ዐይነቱን ሰው አይፈልግም። ስለዚህ እዚሁ በፀጥታና በመልካም ጠባይ መቆየቱ ይሻላል። እነዚህ ሰዎች የሚጠብቃቸው ዕድል ምንድን ነው? በቅዱስ ዮሴፍ አንድ ከባድ የግዞት ፍርድና ከዚያም በዱላቢዩ ደሴቶች የዕድሜ ልክ ጽኑ አሥራት ነው ማምለጣቸው ያስገኘላቸው ትርፍ ይኸው ነው። ሐሣቤን እንደተረዳችሁ አተማመናለሁ። ዘበኞች! እነዚህን ሰዎች ወደ ሥነ ሥርዓት ሠፈር ውሰዱ።»

ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ከፍተኛ ቁጥር ወደሚደረግበት ጣቢያ አንድ ልዩ ክፍል ተወሰድን። እንደ ደረስን፤ ያበጡትን እግሮቼን እንዲመለከቱኝ ጠየቅኩ። ከሎሲዎም

t.me/OLDBOOKSPDF

በቅልጥሙ ላይ ያለውን የፕላስቲክ ጂሶ አመለከተ። አንድ ሴላ ሙከራ ማድረግ በቻልን። ዳግመኛ ወደ ሆስፒታል እንደሚልኩን ሁሉ ፍራንሷ ሲየራ ከዘበኛው ጋር መጣ።

« ይኸውና የጤና ረዳቱ» አለ ዘበኛው።

« እንዴት ይዞሃል ፓፒ?»

« አሞኛል። ወደ ሆስፒታል መሔድ አፈልጋለሁ።»

« ላሰገባህ እሞክራለሁ፣ ግን እዚያ ከፈፀምከው ድርጊት አንፃር በቀላሉ የሚቻል አይመስለኝም። ለከሎሲዎም ያው ነው። «አግሮቼን እየፈተገ በቅባት አሻሸና የከሎሲዎንም ጂሶ መርምሮ መንገዱን ቀጠለ። በዘበኛው ምክንያት ልናወራ አልቻልንም፣ ግን ዐይኖቹ ከሐዘን ከመሞላታቸው የተነሣ ስሜቴ ተነክቶ ነበር።»

«አልሆነም፣ ምንም ነገር ማድረግ አልተቻለም» በማለት በሚቀጥለው ቀን አግሮቼን እንደገና ሊያሽ ሲመጣ ነገረኝ። «አስረኞች በሕብረት ወዳሉበት ክፍል እንድወስድህ ትፈልጋለህ? ሌሊት አግሮቻችሁን ያስሯችኋል እንዴ?»

«አዎ።»

«እንግዲያማ አሥረኞች በሕብረት ወደሚገኙበት ክፍል መሔድ ነው የሚሻለው። ይህን የመሰለው ብቸኝነት ለአንተ ሥቃይ መሆን አለበት።»

በዕርግጥም ነበር። ከመቼውም የበለጠ ብቸኝነትን መቋቋም ከባድ ነበር። በከፍተኛ ሐዘን ከመዋጤ የተነሣ፣ ሲለአሁንም ሆነ ስለአለፈው ለማሰብ፣ ዐይኖቼን መጨፈን እንኳ አላስፈለገኝም። መራመድ አለመቻሌ ደግሞ በስጭቴን የዚያኑ ያህል አባባሰው።

እንግዲህ በቀጥታ ተመልሼ ከዚህ የቅጣት ጎዳና ውስጥ ገባሁ። ግን በአንድ ወቅት ደግሞ ለማምለጥ በቅቼ፣ በነጻነት ዋኝቼ፣ እንደገና ሰው መሆን በመቻሌ ተደስቼ፣ ከዚያም ወደ ብቀላ አቅዴ ለማምራት ችዬ አልነበረም እንዴ ሀሳቤ? ይሁንና ለፓሊየን፣ ለእነዚያ ዓሣማ ፖሊሶችና ለአቃቤ ሕጉ፣ ብድራቸውን መክፈል እንደሚኖርብኝ መርሳት የለብኝም። ሻንጣዬን ከዋናው መምሪያ መግቢያ ለሚገኙ ፖሊስ ማስረከቡ አስፈላጊ አይሆንም። እንደ ዋገን ሊትስ ኩክ ፋብሪካ ወዛደር ለብሼና የኩባንያውን የመለለ ኬፕ በራሴ ላይ ደፍቼ ራሴው አደርስዋለሁ። በላዩም ላይ፣ «ለኮሚሽነር ቢኖይ፣ 36 ኪይ አርፌቭር፣ ፖሊስ (ሴየን)» የሚል አንድ ትልቅ አድራሻ ይጻፍበታል። እኔ አስከመለስ ድረስ ማስጠንቀቂያው እንዳይጮኽ አሰተካክልና ሪፖርት ማቅረብያው ከፍል ድረስ ራሴው እሸከመዋለሁ። ሊከሽፍ አይችልም።

ይህን መፍትሔ ማግኘቴ - አእምሮዬን ከከባድ ሸክም ገላገለው። የአቃቤ ሕጉንም ምላስ በተመለከተ፤ ስለዚያ የማደርገውን የማዘጋጅበት በቂ ጊዜ አለኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዲያውም እንዳደረግኩት ፡ የሚቆጠር ነበር። ተልትዬ ወደ ቅንጥብጣቢኮት፡ አለውጣቸዋለሁ። የማደርገው ይህንኑ ነው።

ለጊዜው አግሮቼን ማዳን አለብኝ፤ በተቻለ ፍጥነት ለመራመድ እንድችል ለሦስት ወር ያህል ወደ ልዩ ፍርድ ቤት ሰለማልቀርብ፣ በሦስት ወር ውስጥ ብዙ ማድረግ ይቻላል። አንድ ወር መልሶ መራመጃ፤ አንድ ወር ዝግጅት ማድረጊያ፤ ከዚያም መልካም ሌሊት ከቡራን፤ አቅጣጫ እንግሊዝ ሆንዱራስ። ግን በዚህ ጊዜ ማንም ሰው እጅቹን በእኔ ላይ አያሳርፍም።

አዚህ ከመጣን ከሦስት ቀን በኋላ ትላንት፣ እሥረኞች በሕብረት ወደሚኖሩበት ክፍል ተሸከመው ወሰዱኝ። ዕድላቸውን የሚጠባበቁ ፀርባ ሰዎች አዚያው ይገኛሉ። ከወንጀሎቻቸው መካከል፣ ሌብነት፣ ዘረፋ፣ በመርገ መግደል፤ የመግደል ሙከራ፤ የማምለጥ ሙከራ፣ ማምለጥና ሰው መብላት እንኳ ሳይቀር ይገኝባቸዋል። ሃምሳ ርዝመት ጪማ ካለው አንድ የብረት አግዳሚ ጋር ሁላችንም ተቆራኝተን ሐያ ሰዎች በአንድ ጎን፣ ሐያ ሰዎች በሌላ ጎን ነበርን። ከምሽቱ ወሥራ ሁለት ሰዓት ላይ የአያንዳንዱ ሰው የግራ እግር ከአግዳሚው ብረት ጋር በሰንሰለት ይታሠራል። ጧት በወሥራ ሁለት ሰዓት፤ እግር ብረቶቹ ይፈቱልንና ቀኑን ሙሉ ስንቀመጥ፤ ስንዘዋወር፣ ዳማ ስንጫወትና ስፋቱ ሰድስት ጫማ ሆኖ ከፍሉን ዳር እስከ ዳር በሚያቋርጥ መተላለፊያ «የትርዒት መድረክ» ብለን በምንጠራው አግዳሚ ላይ ተቀምጠን ስናወራ እንውላለን። ቀን ቀን ለመስለቸት እንኳ ጊዜ አልነበረም። የማምለጥ ታሪኬን መስማት በሚፈልጉ ሰዎች ተከብቤ አውል ነበር። ላሊን፤ ዞራይማንና የጓድራ ጉሣዎቼን በራሴው ፍላጎት አንደ ተውኩ ስነግራቸው፣ አእምሯቸው ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል።

«ምን ሌላ ነገር ፈልገህ ነው ሰውዬ?» ሲል ከፓሪስ የመጣ አንድ እሥረኛ ጥያቄ አቀረበልኝ። «በመሬት ውስጥ የሚጓዙ ባቡሮች? አሳንሰሮች? ሲኒማዎች? ኤሌክትሪክ? ለኤሌክትሪክ ወንበር መሥሪያ የሚሆኑ ከፍተኛ ስበት ያላቸው ሽቦዎች? ወይስ በፕላስ ፒጋሌ ፏታቱ ገለህን ልትታጠብ ፈለግክ? ወዳጄ፤ ዕብድ ነህ?» ሰውዬው በመቀጠል፤ «የሚያማምሩ ሁለት ኮረዳዎች ነበሩህ። እንደፈለግክ አራቱትህን ሆነህ ብቻህን በጫካ ውስጥ ሆነህ ስትፈነጥዝ ትውላለህ። ትበላለህ፤ ትጠጣለህ፤ ታድናለህ፤ ባሕሩ፤ ፀሐይዋ፤ የሚምቅ አሸዋ ያንተው ነበሩ። ኢይስተሮችን፣ ሉሎችን እንኳ በነጻ አግኝተሃቸው ነበር። ይሁንና እነዚህን ሁሉ አሻፈረኝ ብለህ ከሙተው የተሻለ ሌላ ምንም ካር ማሰብ አልቻልክም። ለምኑ ብለህ ነው? አሰኪ ንገረኝ። በየትዳናው በአውቶሞቢል ሰመባረር? ለልበሰ ሰፊ፤ ለኤሌክትሪክ፤ ለስልክ መከፈል ፈልገህ? ወይስ እንዲት ከርክሳ አውቶሞቢል ለማግኘት? ልትሰርቅ ወይም በረታብ ለአንዱ ሰው ልክ እንደውሻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልታገለግል? አልገባኝም! ገነት ውስጥ ነበርከ፤ ራስህ በፈቃደኝነት ወደ ገሀነመ እሳት ተመለስከ። እነዚህን ሁሉ ፖሊሶች ከአጠገብህ እንዲርቁ ማድረግ ሊኖርብህ ነው። በዚያ የፈረንሣውያን ትኩስ ደም አሁንም ገና እንደ ተሞላህ መሆንህ ሐቅ ነው፤ ስለሆነም አንተትከን ለመዘንጋት ጊዜ አልነበረህም ማለት ነው። በአሰቃቂው ወህኒ ቤት ውስጥ ወሥር ዓመት አለኝ፤ ግን የአንተን አስተሳሰብ ልገነዘብ አልችልም። የሆነ ሆኖ እንኳን ወደዚህ በደህና መጣህ፤ እንደገና ለማምለጥ ዘዴ እንደምትፈልግ ይገባኛልና ልንተባበርህ ዝግጁ ነን። ሐቅ ነው፤ አይደለም እንዴ ጓዶች?»

ጓደኞቹ ተስማሙ፤ እኔም ሁሉንም አመሰገንኩ።

እነዚህ ሰዎች ልተዋወቃቸው የሚገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ቻልኩ። ከመተፋፈጋችን የተነሣ፤ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እንዳለኝ ሐቁን ለመሸሸግ አዳጋች ነበር። ሌሊት ሁላችንም የምንቆራኘው በዚያው አግዳሚ ብረት ላይ ስለሆነ አንድ ሰው መገደል በጣም ቀላል ነበር። ለቁልፍ ያገቡ አርብ ቀን ላይ አንድ ትንሽ ጉርሻ መሸንጥ ነው። ማታ እግር ብረትህን ሙሉ በሙሉ አይቆልፍብህም። ከዚያም ሲጨልም ገዳይ የሚፈልገውን ያርድና ወደ ቦታው ተመልሶ እግር ብረቱን በመቆለፍ ጭጭ ብሎ ይጋደማል። በተዘዋዋሪም መንገድ አረቡም ተባባሪ ስለሆነ አፉን ዘግቶ ጭጭ ይላል።

ከተመለስኩ አሁን ሦስት ሳምንት ሆነኝ። ጊዜውም በጣም እየተፋጠነ ሔዶ ነበር። መደዳውን በተዘረገቱ አልጋዎች መካከል ባለው መተላለፊያ ላይ የሚገኘውን አግዳሚ ብረት እየያዝኩ ቀስ በቀስ መራመድ ጀመርኩ። ባለፈው ሳምንት ለጥያቄ በቀረብንበት ወቅት እነዚያ ደብድበን መሣሪያዎቻቸውን ነጥቀናቸው የነበሩትን ሦስት የሆስፒታል ዘበኞችን አየኋቸው። ተመልሰን በማየታቸው በግልጽ ተደስተው ሁላችንም በአንድ ሰዋራ ቦታ ታምቀን ሲያገኙን ብድራቸውን ለመመለስ በጋለ ምኞት ይጠባበቃሉ። ከእኛ ማምለጥ በኋላ ከባድ ቅጣት ደርሶባቸው ነበር። ከአንድ ዓመት የቅኝ ግዛት መደንገጫ አበል ጋር፤ በፈረንሣይ የሚያሳልፉት የስድስት ወር የመዝናኛ ዕረፍት ተሠርዘባቸዋል። እንደገና መገናኘታችን የተሟላ ወዳጅነት እንደማይኖረው ልትገምቱ ትችላላችሁ። ለመርማሪዎቻችን ይህን ማመልከቱ ብልህነት እንደሆነ አሰብንበት።

አረቡ የተሻለ ጠባይ ነበረው። ምንም ሳያጋንን ዕውነቱን ብቻ ይናገርና ማቹሬ የተጫወተውን ሚና ዘልሎ ያልፋል። ጀልባ ማን ሰጥቶን እንደነበር ለማወጣጣት መርማሪው ዳኛ ጥረት ማድረጉን ቀጠለ። ራሳችን ጀልባ ሠርተን ነው በማለት አስመሰለ ታሪክ በመጥጠር ሐቁን ለመሸፈን ተገደድን።

ዳኛው በዘበኞቹ ላይ አደጋ በመጣላችን ምክንያት፤ እኔና ከለሚዶን በአምስት ዓመትና ማቹሬን በሦስት ዓመት ለማስቀጣት የተቻለኝን ሁሉ እሞክራለሁ አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ስምህ ፓፒዮ(ቢራቢሮ) እስከሆነ ድረስ፣ እንደሚመስለኝ ከንፎችህን መቀንጠስ ያስፈልጋል፤ ስለሆነም በቅርቡ እንደገና ለመብረር አትችልም።»

ወደ ልዩ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ሁለት ወር ብቻ ቀረኝ። ትናንሾቹን መርዛማ ፍላጻዎች በገንዘብ መደበቂያ ቱቦዬ ውስጥ ባለማስቀመጤ ተናደድኩ። ምናልባት እነርሱ ኖረውኝ ቢሆን ከሠፈሩ ውስጥ ማምለጥ በቻልኩ። ለማንኛውም በመጠኑ አየተራመድኩ በየቀኑ ማሻሻል አደርግ ነበር። ፍራንሷ ሲየራ እግሮቼን በቅባት ሊያሸልኝ ጧትና ማታ መጎብኘቱን ፍፁም አቋርጦ አያውቅም። ለእግሮቼም ሆነ ለሞራሌ፣ ለሁለቱም አንድ ከፍተኛ እርዳታ ነበር። እግዚአብሔር ዕውነተኛ ጓደኞችን በመፍጠርህ ምስጋና ይግባህ!

ረጅሙ የማምለጥ ጅብዳችን በአስረኞች ጓዶቻችን መካከል ከፍተኛ ከብርን አጎናጽፎን እንደነበር ቀደም ብዬ ገልጫለሁ። ለገንዘባችን ሲባል የሚያጋጥመን የመገደል ዕድል አነስተኛ መሆኑንና ሰላም ማግኘታችንን ዕርግጠኛ ነበርኩ። አብዛኞቹ ሰዎች እንደማይደፍሩን ነው፣ አንድ ሰው እሞክራለሁ ካለም ያለጥርጥር በቀጥታ እንደሚገደል ነው። ያለምንም ልዩነት ማንኛውም ሰው ያከብረናል። እንዲያውም ዕውነተኛ አድናቆት ይሰማቸዋል። ዘበኞችን መዘረር አስካልፈራን ድረስ ማንኛውንም ነገር እንደምናደርግ ገምተዋል። ሰላም ማግኘት ደስ የሚል የመንፈስ እርካታ ነው። በየቀኑ እርምጃዬን በመጠኑ አራዝማለሁ፣ ሲየራ አንዲት ትንሽ ጠርሙስ ቅባት ትቶልኝ ስለነበር፣ ብዙ ጊዜ ካለመንቀሳቀሳቸው የተነሣ የገረሩትን የባቶቼን ጡንቻዎች፣ ጓደኞቼ ሊያሹልኝ ችለዋል።

ከሜሪቆቼ ማምለጥ

«ባለ እንጨት እግሩን በሉትኮ!» «ባለ እንጨት እግር ወጥ እባከህ!» ከዚያም የሴት ድምጽ በማስመሰል፣ «እባክህ በርበሬ ያልገባበት ከሽን ያለ የሰው ሥጋ!» ይላሉ።

ከእነዚህ ያልተለመዱ ሐረጎች ውስጥ አንዷ ሳትናገርና የምሽቱን ፀጥታ ሳታደባልቀው ያለፈበት ሌሊት በቁጥር ነበር። ይህ ሁሉ በምን ምክንያት እንደሆነ ከሎሲዎንና እኔን ደነቀን።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ፣ በነገሩ ውስጥ ከነበሩት አንደኛው ታሪኩን ሲያብራራልኝ የምስጥሩን ቁልፍ አገኘሁ። ስሙ ማሪየስ ደ ሲዎታት የተባለ (እንደ እኔ) መከራ የማያጣው ነበር። ለእኔ ሊገልጽልኝ የወሰነው ቲቲን የተባለ አባቱን እንደማውቀው ከተረዳ በኋላ ነበር።

ስለማምለጫ አንድ ታሪክ አወራሁለትና እንደዘበት፣ «የአንተስ እንዴት ነው?» ሰል ጠየቅኩት።

«እኔ ሰውየው፣ ያለጥርጥር ከባድ ችግር ውስጥ ገብቻለሁ። ለአንድ ቀላል

t.me/OLDBOOKSPDF

የማምለጥ ሙከራ፣ አምስት ዓመት ይፈረድብኝ ይሆናል ብዬ ፈርቻለሁ። እነርሱ ደግሞ ማምለጥ እያሉ ከሚጠሩት የማምለጥ ሙከራ ውስጥ ነበርኩበት። ሌሊት የምትሰማው ያ ሁሉ ሁካታ ስለግራቪይ ወንድማማቾች ነው።

«ከሶ ሜትር ዐርባ ሁለት ከሚባለው ቦታ ያመለጥነው ስድስታችን ነበርን። በቡድኑም ውስጥ ዴዴና ዮሐንስ ግራቪይ የተባሉ ዕድሜያቸው በሠላሳዎቹ ዐመታት የሚገመት ከሊዮን የመጡ ሁለት ወንድማማቾች፣ ከማርሴይ አንድ ኢጣሊያዊና ከሲዎታት የመጣሁት እኔ፣ ከእንገርስ የመጣ የእንጨት አግር ያለው አንድ ሰውና አንድ የሐያ ሦስት ዓመት ልጅ ነበሩ። ከማሮኒ በሰላም ወጥተን ነበር። ግን አንድ ጊዜ ወደ ባሕሩ ከደረሰን በኋላ ፍጹም መቀጠል አልቻልንም። ጀልባችን ተጋጨና በትንሽ ሰዓቶች ውስጥ ወደ ዳች ጊያና ጠረፍ ተመለስን።

«ከስብርባሪው ውስጥ ምግብም ሆነ ምንም ነገር ማዳን አልቻልንም። ወደ ጫካ ገባን። አካባቢው የአሸዋ ጠረፍ ስላልነበረ ባሕሩ በቀጥታ እስከ ጫካ ውስጥ ይገባል። ባሕሩ ከሥር እየገነደሰ የጣላቸው ዛፎች በሙሉ አንድ ት የተቆላለፉ በመሆናቸው ምክንያት የማይጣስ አንድ ጥቅጥቅ ያለ ደን ነበር።

«ወደ ደረቅ መሬት ከመድረሳችን በፊት ሙሉ ቀን ተጓዝን። ከዚያም በሦስት ቡድን ተከፋፈልን። የግራቪይ ወንድማማቾች፣ እኔና ጁሴፔ፣ ባለ እንጨት እግሩ ከልጅየው ጋር፣ አያንዳንዳችን በልዩ ልዩ አቅጣጫ ሐድን። ረጅሙን ታሪክ ለማሳጠር ያህል፣ ከዐሥራ ሁለት ቀናት በኋላ፣ ከግራቪይ ወንድማማቾች ጋር ልክ መጀመሪያ ተለያይተንበት ከነበረው ቦታ ተገናኘን። ቦታው በሙሉ በአሸዋ የተዋጠ ስለነበር፣ የምንወጣበት መንገድ ማግኘት አልቻልንም። ከሥሮችና የቅጠል አምቡጦች በስተቀር ምንም ነገር ሳንበላ ዐሥራ ሦስት ቀን አሳለፍን። በረሃብና በድካም ልንሞት ተቃረብን። የተስፋችን ገመድ ሊበጠስ ደረሰ። ጁሴፔና እኔ ባለን ኃይል ወደ ጠረፉ በመመለስ፣ አንድ ሸሚዝ በአንድ ዛፍ ላይ የቻልነውን ያህል ከፍ አድርገን ሰቅለን በአጠገባችን ለሚያልፈው ለመጀመሪያው የዳች ጠረፍ ዘበኛ እጃችንን ለመስጠት ወሰንን ነበር። ሁለቱ ወንድማማቾች ደግሞ ትንሽ ሰዓት አርፈው፣ ከዚያ በኋላ የሌሎቹን የሁለቱን ዱካ ለመከታተል ሊሐዱ ነበር።

«ነገሮችን ለማቃለል ያህል፣ አያንዳንዱ ቡድን ወዴት እንደሐደ ለማመልከት በመንገዱ ላይ የሚገኙትን ቅርንጫፎችን እንዲቆርጥ በምንለያይበት ወቅት ተመካከርን።

«ከተለያየን ትንሽ ሰዓት በኋላ፤ ባለ እንጨት እግሩ ብቻውን ወደ እነርሱ አቅጣጫ ሲመጣ አየት።

«ልጁ ወዴት አለ?»

«ወደ ኋላ ቀርቷል። ፍጹም መራመድ አቃተው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«በቻውን እዚያ በመተውህ የውሻ ልጅ ነህ።»

«ይህ በዚህ እንዳለ፣ ሰውዬው የልጁን ጫማ በጤነኛው እግሩ ላይ መደንቀሩን ይዴ ልብ አድርጎ ተመለከተ።

«ያም ሆነ ይህ እርሱን በባዶ እግሩ ትተህ፣ አንተ እንዴት ጫማውን ልታደርግ ቻልክ? ደግሞም ሰውነትህ እንደ ቀረነው አይደለም፤ አቋምህ ጥሩ ይመስላል። እስክትጠግብ የምትመገብ መሆን አለብህ።»

«አዎ፣ አንድ ትልቅ የቆሰለ ዝንጀሮ አግኝቼ ነው»

«ዕድለኛ ነሃ» ብሎ ዴዴ በዚያው ወቅት ጩቤውን በእጅ እንደጨበጠ ብድግ አለ። የባለ እንጨት እግሩ ኮረጆ የተወጠረ ይመስላል፣ ስለሆነም ዴዴ ምስጢሩ አየገባው ይሔድ ጀመር።

«ኮርጆህን ከፈት፣ በውስጡ ምን ይዘህበታል?»

«ከረጢቱን ሲከፍት ዴዴ ቁርጥራጭ ሥጋ አየ።»

«ይኸ ምንድን ነው?»

«የዝንጀሮው ሥጋ ነው።»

«አንተ ውላጅ፣ ያንን ልጅ ገድለህ በላኸው!»

«አይደለም፣ ዴዴ፣ አምላለሁ አላደረግኩም። በድካም ምክንያት ሲሞት ትንሽ ቁራጭ ብቻ ነው የበላሁት። አትፍረድብኝ ...»

«ንግግሩን ለመጨረስ ጊዜ ሳያገኝ፣ የዴዴ ጩቤ ሆዱ ውስጥ ገብቶ ነበር።

ከዚያም ሰውነቱን ሲበረብረው የከብሪት እንጨቶች ከነመጫሪያው የያዘ አንድ የቆዳ ቦርሳ አገኘ።

መጀመሪያ ሲለያዩ ሰውዬው ከብሪቱን እንኳ አለማካፈሉ ቆጨውና ዴዴ በንዴት እንደ አውሬ ሆነ፣ ከረሃቡ ጋር ይህ ሲጨመርበት ... በአጭሩ ታሪኩን ለመቋረጥ ያህል፣ እሳት አነደዱና ሰውዬውን ጠበሰው ይበሉት ጀመር።

«በግብዣው መካከል ጁሴፔ ደረሰ። እንዲሳተፍ ጋበዙት፣ ግን እምቢ አለ። ከባሕሩ ዳር አካባቢ ጥቂት ሽርጣኖችና ጥሬ ዓሣዎች በልቶ ነበር። ስለዚህ እሳቱ እየነደደ እንዲቆይ ወንድማማቾቹ በሚቹ የእንጨት እግር እየቆሰቆሱ በእሳቱ ላይ ተጨማሪ ቁርጥራጭ ሥጋ ሲጥሉ እርሱ ተካፋይ ሳይሆን ታዝቧል። በዚያ ዕለትና በሚቀጥለውም ሙምር፣ ወንድማማቾቹ ሰውዬውን ሲበሉና ሌላው ቀርቶ የትኛውን የአካላት ክፍሉን በቅደም ተከተል እንደበሉ፣ መሐል አገዳውን፣ ታሩውንና ቂጡን ተራ በተራ መጥበሳቸውን ጁሴፔ አይቷል።

«ጁሴፔ ወደ እኔ ሲመጣ አውንም ገና ከባሕሩ ሆኜ እጠብቅ ነበር። በእንድ ባርኔጣ ትናንሽ ዓሣዎችና ሽርጣኖች ሞላንና እነግራቪይ ባነደዱት እሳት ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠበስናቸው። ሬሣውን እኔ አላየሁም። ወደ አንድ አካባቢ ጎትተው ጥለውት መሆን አለበት። ግን ብዙ ቁርጥራጭ ሥጋዎች አመዱ አካባቢ መንጠባጠባቸውን አጣርቼ አይቻለሁ።

«ከሦስት ቀን በኋላ፣ አንድ የጠረፍ ዘበኛ በጀልባው አንሥቶን ቅዱስ ላውረን ለሚገኘው ጠባይ ማረሚያ መለሰን።

«ጁሴፔ አፉን መዝጋት አልቻለም። እዚህ ከፍል ያለ ሰው ሁሉ፣ ዘበኞቹ እንኳ ሳይቀሩ ታሪኩን ያውቁታል። ስለዚህ ነው እነዚያን ድምፆች በምሽቱ የምትሰማቸውና እኔም የነገርኩህ። የተወነጀልነው ለማምለጥ ሙከራ በማድረጋችንና ሰው በመበላታችን ነው። ከፋቱ ደግሞ ራሴን ለማዳን ሌሎቹን ማጋለጥ ስለሚኖርብኝ እንዲያ ለማድረግ አልፈልግም። በምርመራው ወቅት ማንኛውም ሰው፣ ጁሴፔም ሳይቀር ይክዳሉ። ሌሎች የሚሉት ወደ ጫካ ገብተው ጠፉ ነው። እንግዲህ የእኔ ሁኔታ በዚህ ላይ ነው ፓፒዮ።»

ስለ እንተ አዝናለሁ። ይሁን እንጂ፣ የእንተ ዓይነተኛው መከላከያህ ሌሎቹን መክሰስ ነው» አልኩት።

ከአንድ ወር በኋላ ግማሽ ሌሊት አካባቢ በጁሴፔ ልብ ላይ አንድ ያልታወቀ ሰው ጩቤ ተከለበት። ማን እንዳደረገው ግምት ውስጥ ልንገባ አልፈለግንም።

ዛሬ ማታ ቦታ ቀየርኩ። ማንኛውንም ሰው ፈቀቅ እንዲል ጠየቅኩና አንድ የለቀቀ ሰው ተክቼ ከከሎሲዎ ጎን ሆንኩ።

አሁን ከመረጥኩበት ሥፍራ እንደ ተቀመጠኩ የግራ እግሬ ከአግዳሚው ብረት ጋር እንደ ተቆራኘ ቢሆንም እንኳ ግቢው ውስጥ ምን እንደሚካሔድ ለማየት ችያለሁ።

ቁጥጥሩ በጣም ከመጥበቁ የተነሣ፣ ጥበቃው ፋታ አይሰጥም። ፍጹም አይቆሙም፤ ዘበኞች የሚቀያየሩት በማንኛውም ሰዓት ነበር።

አሁን አግሮቼ ከብደቴን በሚገባ ሲሸከሙልኝ፣ ሲዘንም ብቻ ሕመሙ ይሰማኛል። አዲስ ነገር ባገኝ ብዬ እመራመር ነበር። ግን እንዴት? በስፋት እስከ ጣሪያው ድረስ ከተዘረጋው የብረት ፍርግርግ በስተቀር ከፍሉ መስኮቶች አልነበሩትም። በሩ ከፊት ለፊት ስለሆነ፣ ከሰሜን ምሥራቅ ለሚመጣው ነፋስ የተጋለጠ ነበር። ከአንድ ሳምንት ጥበቅ ከትትል በኋላ፣ ሊምንት ቀዳዳ ገና ላገኝ አልቻልኩም። ስለሆነም በቅዱስ ዮሴፍ ግዙት ወህኒ ቤት የሚቆለፍብኝ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ማመኑ ተቃረብኩ።

ማንም ሰው አሰቃቂ ቦታ ነው ይለዋል። «ሰው በላ» በማለት ይጠሩታል። ሌላው ነገር ደግሞ፣ ከተመሠረተበት ሰማንያ ዓመት ጀምሮ አንድም ሰው ከዚያ ያመለጠ አለመኖሩ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይህ ሽንፈተን በከፊል ያመጣኩበት ሁኔታ፣ የወደፊቱን እንዳበላሽ አደረኝ። ዕድሜዬ ሐያ ሰምንት ነበር፣ ዳኛውም በግዛት መሀኒ ቤት አምስት ዓመት ይፈርድብኛ ይሆናል። ስለዚህ በምወጣበት ወቅት ሠላሳ ሦስት ዓመት ይሆነኛል። በጉንዘብ መደበቂያ ቱቦዬ ውስጥ አውንም ብዙ ፕንዘብ አለ። ስለዚህ ካላመለጥኩ፣ የሚሆንልኝም አልመሰለኝ፣ ሊላው ቢቀር ማድረግ የምችለው ራሴን በመሬካም ጤንነት ማጽዳት ነበር። ወደ ዕብድነት ደረጃ ሳይደርስ አምስት ዓመት ሙሉ ብቸኝነትን መቋቋም የማይቻል ነው። ፍርዴን ከምቀበልበት የመጀመሪያው ቀን አንሥቼ በጥንቃቄ በታቀደና በተሰያየ ፕሮግራም አእምሮዬ እንዲመራ ሥነ ሥርዓት አስይዘዋለሁ። በስታኝ ስላሎት ቤተ መንግሥቶችና በተለይም በጠቅላላው ስለብዛላ ምሥጢ የማልመውን በተቻለ መጠን አስወግዳለሁ። ከዚያች ወቅት ጀምሮ ከፊት ለፊቴ የሚጠብቀኝን አሰቃቂ ቅጣት ለመቋቋም እዘጋጃለሁ። አዎ፣ ጊዜያቸውን ማባከናቸውን እንዲገነዘቡ አደርጋቸዋለሁ። በሞራልና በአእምሮ ብቃት ጠንካራ ሆኜ ከግዞት መሀኒ ቤት አወጣ ዬ።

የምመራበትን ሕግ በማርቀቂና ወደፊት የሚጠብሥን በጸጋ ለመቀበል ቁርጠኛ በመሆኔ የተሻለ ሰሚት አደረብኝ።

ከፍሉን ሰንጥቅ የሚባው የመጀመሪያው ለስላሳ ነፋስ የሚሰማኝ እኔ ነበርኩ። ለማውራት በማልፈልግበት ወቅት ከሶሲዎ ስለሚያውቅ ወደ ማጪሉ ዘወር ይሳል። ጥቂት ኮከቦች ወጥተው ነበር። «አለህበት ሆነህ ኮከቦቹን ማየት ትችላለህ ከሶሲዎ?» ስል ጠየኩት።

ትንሽ ወደፊት ሰገግ አለና፣ «አዎ፣ ግን ላያቸው አልፈልግም። ስለማምለጣችን ከፉኛ ያስታውሱኛል» አለ።

«አስከዚህ በጣም ከባድ ዕዳ አድርገህ አትውሰደው። በሚቀጥለው ሙከራችን የአነርሱን ዓይነት በሺ የሚቆጠሩ ታይ ይሆናል።»

«መች? ከአምስት ዓመታት በኋላ?»

«ያሳለፍነው ዓመት፣ አሰቸጋሪው ጉዟችንና መተዋወቅ የቻልናቸው ሰዎች፣ ከአምስት ዓመት ግዞት የበለጠ ዋጋ እንዳላቸው አታስብም ከሶሲዎ? ያን ሁሉ ጊዜ ደሴቶቹ ውስጥ ብትሆን ትመርጣለህ? ከፊታችን የሚጠብቀን ምን እንደሆነ ስለማውቅ፣ በጣም ከባድ እንደሆነ አልጠራጠርም፣ ይልቁኑ ስለማምለጣችን በትክክል ምን ይሰማሃል? ዕውነቱን ንገረኝ። ይፀፅትሃል ወይስ አይፀፅትህም?»

«ፓፒ፣ እኔ ያላገኘሁት አንድ ነገር አንተን እንዳጋጠመህ ረስተኸዋል። ከሕንዳውያኑ ጋር ባሳለፍካቸው ሰባት ወሮች፣ ከአንተ ጋር ብሆን በአባልህ በተሰማማሁ፣ ግን ያኔ እኔ ወህኒ ቤት ውስጥ ነበርኩ።»

«አዝናለሁ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ምንም አይደል። እርግጥ በማምለጥ ሙከራችን ተደስቻለሁ። ምክንያቱም ጥሩ ጊዜ አሳልፈያለሁ። ትንሽ ያሠጋኝ አዚህ ሰው በሌ እሥር ቤት ውስጥ ምን እንደሚጠብቀኝ ብቻ ነው። የሚቀጥሉትን አምስት ዓመታት እንዴት እንደማሳልፍ አይገባኝም።»

ዕቅዴን አስረዳሁትና የሚያምንበት መሰለ። ወኔው ሲቀስቀስ በማየቴ ደስ አለኝ። በዐሥራ አምስት ቀን ውስጥ ወደ ልዩ ፍርድ ቤት ልንቀርብ ነበር። ሰብሳቢው መኮንን ከባድ፣ ሆኖም የማያዳላ መሆኑ ይወራል። ለአስተዳደሩ ሽፍጦች ተጨማሪ ድጋፍ የሚሰጥ አይደለም፤ ይህም ጥሩ ዜና ነበር።

እንደ ጠበቃ በሚቆምልን አንድ ዘበኛ ለመጠቀም፣ ከሎሲዎና እኔ ተቃወምን። ለሥነታችንም እኔ መከራከር እንዳለብኝና መከላከያችንንም ራሴው እንደማቀርብ ወሰንን።

ለፍርድ መቅረብ

ጸጉሬን ተስተካከዬ፣ ጺሜን ተላጭቼና ቀይ ጥብጣብ ያለው አዲስ ቱታ ለብሼ ነበር። ጫማ እንኳ ሳይቀር አድርጊያለሁ። ወደ ልዩ ፍርድ ቤት ለመቅረብ በግቢው ውስጥ እንጠባበቃለን። ከሎሲዎም ጀሶው ከተፈታለት አነሆ አሁን ሁለት ሳምንቱ ስለሆነ፣ የማንከሰ ምልከት ሳይታይበት እንደ ጤነኛ ሰው ይራመዳል።

ልዩ ፍርድ ቤቱ ችሎት የጀመረው ሰኞ ነበር። አሁን ቅዳሜ ጧት ነው። የመጀመሪያዎቹ አምስት ቀኖች ያለፉት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ነበር። የግራቪይ ወንድማማቾም ማስረጃ በመጥፋቱ አራት ዓመት ብቻ ተፈረደባቸው። ሌሎቹም የነፍስ ግድያ ክሶች አራት ወይም አምስት ዓመት ተፈረደባቸው። በአጠቃላይ የታዩት የዐሥራ አራት ክሶች ቅጣቶቹ ሁሉም ከብደት አላቸው፤ ግን ከወንጀሎቹ ጋር ተመጣጣኝ ነበሩ።

የልዩ ፍርድ ቤቱ ችሎት አንድ ሰዓት ተኩል ላይ ተጀመረ። እንደ ረዳት ዳኞች በሚያገለግሉ አንድ መቶ አለቃና አንድ ሻማሌ የእግረኛ ሻምበል የታጀበና ዩኒፎርም የለበሰ አንድ መኮንን ወደ ውስጥ ሲገባ፣ በክፍሉ ውስጥ ያለነው ቆምን።

«የሻሪየ፣ የከሎሲዎና የማቹሬ ክስ።»

ከሰብሳቢው ዳኛ በግምት ዐሥራ ሁለት ጫማ ርቀት ላይ እንኾናለን። የመኮንኑን ፊት በትክክል ማየት ችያለሁ። በበረሃው ምክንያት ፊቱ በልዞ፣ ጉንጩ አካባቢ ጸጉሩ ብርማ ሆኗል። ሰርሰረው የሚገቡና የሚንቀለቀሉ ጥቁር ዐይኖች ችፍግ ካሉ ቅንድቦች ጋር ያሉት፤ ዕድሜው በግምት ከዐርባ ዓመት ትንሽ ከፍ የሚል ነበር። ዕውነትም ለወታደርነት ተስማሚ ሰው፣ ግን ክፋት አይታይበትም። በመመልከት ብቻ ገመገመን። ዐይኖቹ ከእርሱ ጋር ግጥምጥም አሉና ሆን ብዬ እንቴን ቁልቁል ሰበር

t.me/OLDBOOKSPDF

አደረግኩ።

አስተዳደሩን የሚወክለው ሻምበል ክሱንና ምን ጥፋት እንዳስከተልን አጋንኖ አቀረበ። ዘበኞቹን መምታታችንን እንደ መግደል ሙከራ አስመዘገበና እኛ በሙከራችን አረቡ አለመሞቱ እንደ ተአምር የሚቆጠር መሆኑን አመለከተ። ሌላው መጥፎ ነጥብ ደግሞ በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ታሪክ ከማንኛውም አሥረኞች የበለጠ ለፈረንሣይ ውርደትን ያስከተልን እኛ መሆናችን መግለጹ ነበር። «ክቡር ፕሬዚዳንት! እነዚህ ሰዎች አንድ ሺ አምስት መቶ ማይል ተጉዘዋል! ትሪኒዳድ፣ ኩራሶ፣ ኮሎምቢያ፣ እነዚህ ሁሉ ሐገሮች ስለፈረንሣይ የቅጣት አሰተዳደር የሚሰብኩዋቸውንና የሚዋሹላቸውን ሰምተዋል! ለሻሪየና ክሎሲዎ ሎተከታታይ በጠቅላላው ስምንት ዓመት የሚቀጡበት ሁለት ፍርዶች ግለትም አምስቱን ዓመት ለመግደል ሙከራ በማድረጋቸው፣ ሦስቱን በማምለጣቸው እንዲበየንባቸው እጠይቃለሁ። ምስከሮቹ እንዳረጋገጡት፣ ማቹሬ በመግደል ሙከራው ውስጥ ስላልተካፈለ፣ በማምለጥ መከራው ሦስት ዓመት ብቻ እንዲቀጣ እጠይቃለሁ።

ፕሬዚዳንቱ ተናገረ። «ስለ ጉዟችሁ አንድ አጠር ያለ መግለጫ ለመሰማት ፍርድ ቤቱ ፈቃደኛ ነው።»

ስለዚህ በማሮኒ ወንዝ ላይ ቀዝፈን የትሪኒዳድ ጉዟችንን ገለጽኩና፣ ስለቦውን ቤተሰቦች ርኅራኄት ዘረዘርኩላቸው። በትሪኒዳድ ውስጥ የፖሊሱ አዛዥ የተናገረውንም «በፈረንሣውያን ሕግ በአርማጥ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች አያገባቸውም። እኛ የማንደግፈው አሥረኞቻቸውን እንዴት ወደ ፈረንሣይ ጉያና እንደሚልኩ ነው። ፈረንሣይን የመሰለ አንድ የሠለጠነ ሀገር፣ ይህን መሳይ ቅጣት መወሰን ከሰብዓዊ ርኅራኄ ውጭና ከብርን ዝቅ የሚያደርግ ነው።» በማለት ጠቀስኩ። ከዚያም ስለ ኩራሶ ጳጳስ አቡነ ኢሬኔ ደብሩን፣ በከረጢቷ ፍሎሪን መነሻ ስለደረሰብን ውጣ ውረድና ከዚያም ኮሎምቢያ ለምንና እንዴት እንደደረስን ነገርኳቸው። በመጨረሻም በሕንዶቹ መካከል ስላሳለፍኩት ኑሮ ፊጠን ያለ ማብራሪያ ሰጠኋቸው። በከፍተኛ ደረጃ ያስደነቀውን የሕንዶቹን ታሪክ በተመለከተ አንዳንድ ተጨማሪ ማብራሪያ ከመጠየቁ በስተቀር፣ በመግለጫዬ ወቅት ፕሬዚዳንቱ ያለ አንድ ማቋረጥ አዳመጠኝ። በአጠቃላይ ስለ ኮሎምቢያ መህኒ ቤቶችና በተናጠል ደግሞ በሣንታ ማርታ ስለሚገኘው ከውሃ ሥር ያለ ጨለማ ግንብ ነገርኩት።

«አመሰግናለሁ። ትርጓሜ አዘል መግለጫህን ችሎቱ የተበራራና የሚያስደንቅ ሆኖ አግኝቶታል። አሁን የዐሥራ አምስት ደቂቃ ቆይታ ይኖረናል። ጠበቆቻችሁ ወዴት ናቸው፣ የመከላከያ ጠበቆቻችሁስ አላያቸውምሳ?»

«ምንም የለንም። ለእኛ መከላከያ ራሴው ለማቅረብ እንዲፈቅዱልኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

አጠይቃለሁ::»

«ትችላለህ፣ ሕጉም ይደግፍሃል::»

«አመሰግናለሁ::»

ከዐሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ስብሰባው ቀጠለ::

«ሻሪየ፣ ለጓደኞችህና ለራስህ መከላከያ አንድታቀርብ ፍርድ ቤቱ መብት ሰጥቶሃል:: ግን አስተዳደሩን የማዋረድ አዝማሚያ ብታሳይ፣ ለመናገር የሰጠንህን መብት ለመሠረዝ እንደምንችል ልናስጠነቅቅህ እንወዳለን:: መከላከያህን ለማቅረብ ነጻነት አለህ፣ ግን በተገቢው መንገድ ማድረግ አለብህ፣ መጀመር ትችላለህ» አለ ፕሬዚዳንቱ::

«ፍርድ ቤቱ በመግደል ሙከራ የሚለውን ብቻ ሰይቶ እንዲያነሣልኝ እጠይቃለሁ:: እኛን የሚመለከት አይደለም፣ ለዚህም ላረጋግጥ እችላለሁ:: ባለፈው ዓመት እኔ ሐያ ሰባት፣ ከሎሲዎ ሰላሳ ዓመት ነበርን:: ከፊረንዛይ ወዲያው ስለደረሰን፣ በጣም የተሟላ አቋም ላይ እንገኝ ነበር:: ሁለታችንም ጨዋ ሰዎች ነበርን:: ዐረቡንና ዘበኞቹን የመታናቸው በአልጋዎቻችን የብረት እግሮች ነበር:: ከአራቱ እንዳቸውም ከባድ ጉዳት አልደረሰባቸውም:: ከባድ ጉዳት እንዳናደርስባቸው የተቻለንን ሁሉ ጥረት አድርገን፣ ይህም ተሳክቶልናል:: ለዚሁ ስንል የብረት እግሮቹን በጨርቅ መጠቅለላችንን ዓቃቤ ሕጉ ከመናገር ዘንግቷል፣ ወይም አላወቀም:: እናንተ በፍርድ ላይ ያላችሁ ሰዎች ረጅም ልምድ ያላችሁ መኮንኖች ስለሆናችሁ፣ በጠመንጃ ሰደፍ፣ አንድ ጠንካራ ሰው ሌላውን ቢመታው ምን ጉዳት ሊያደርስበት እንደሚችል ትገነዘባላችሁ:: ስለዚህ ለማድረግ ፈልገን ቢሆን ኖሮ፣ በእነዚያ የአልጋ እግሮች ምን ማድረስ እንችል እንደነበር መገመት ትችላላችሁ:: ለፍርድ ቤቱ ማስታወስ የምፈልገው፣ ከመታናቸው አራት ሰዎች እንዱም ወደ ሆስፒታል አለመወሰዱን ነው::

«ለሁለተኛው ክስ ደግሞ፣ እኛ ሁላችንም የዕድሜ ልክ እሥራት የተፈረደብን እስከሆነ ድረስ፣ የማምለጡ ወንጀል ቀላል ፍርድ ከተፈረደበት አንድ ሰው ጥፋት ጋር ሲነጻጸር ያነሰ ሆኖ መታየት እንደሚኖርበት አምናለሁ:: ወደ ተደላደለ ኑሮ ፍጹም አልመለስም የሚለውን ሐሳብ ለመቀበል፣ በእኛ ዕድሜ በጣም አስቸጋሪ ነው:: ስለዚህ ፍርድ ቤቱ አመክሮ እንዲያደርግልን አለምናለሁ::»

ፕሬዚዳንቱ ከሁለቱ ረዳቶቹ ጋር ተንሾካሾከና፣ ከዚያም በትንሽ እንጨት ጠረጴዛውን ቆረቆረ::

«ተከሳሾች፣ አስቲ ቆም በሉ::»

የሐዲድ ብረት መስለን ግትር በማለት ቆመን ጠበቅን::

«የመግደል ሙከራ የሚለውን ክስ ፍርድ ቤቱ ትቶታል:: በማምለጥ ጥፋትም ወንጀለኛ ሁናችሁ ያገኘናችሁ በሁለተኛ ደረጃ ነው:: በሁለት ዓመት እሥራት

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድትቀጡ ችሎቱ ወስኖባችኋል» አሰ ፕሬዚዳንቱ፡፡

«አናመሰግናለን ጌታየ» አልንና፣ እኔ በማከታተል፣ «ፍርድ ቤቱን አመሰግናለሁ» አልኩ፡፡

ፍርዱን ይመለከቱ የነበሩት ዘበኞች የሰሙትን ማመን አቃታቸው፡፡ ወደ ጓደኞቻችን ስንመለስ በእኛ ዜና ሁሉም ሰው ተደስቶ ነበር፡፡ እነዚያ ዕድል ያልገጠማቸው እንኳ ‹እንኳን ደስ አላችሁ አሉን፣ ማንም ቅናት ያደረበት አይመስልም፡፡ ፍራንሷ ሲየራ መጥቶ ተጠመጠመብኝ፡፡ በደስታ ሰከሮ ነበር፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰድስተኛ ማስታወሻ

ከዱሳሊዩ ደሴቶች

መድረሰ

በሚቀጥለው ቀን ወደ ደሴቶቹ ልንጓዝ ነው። ከዚያ ሁሉ ረጅም ትግል በኋላ፣ የሁለት ዓመት ጉዞ ምዕራፌን በቅዱስ ዮሴፍ ደሴት ለመጀመርና የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ለመግፋት በጥቂት ሰዓቶች ውስጥ መሐዴ ነው። «ሰው በላ» የሚለው ቅፅል ስም የወጣለት ያለምክንያት ቢሆን አመኛለሁ።

ተረትቻለሁ፣ ግን ሽንፈት አልተሰማኝም። ከአንድ እሥር ቤት ወደዚህ እሥር ቤት ለሁለት ዓመት ብቻ በቅጣት በመላኬ ዕድለኛ ነኝ ማለት እችላለሁ። ራሴን ቀደም ሲል ቃል አስገብቼው እንደነበረ ሁሉ፣ ብቸኝነት በሚያደርስብኝ ተጽዕኖ ለአዕምሮ መዋለል ፍጹም ቦታ አልሰጠውም።

ለዚህም ጥሩ መፍትሔ አገኘሁ። በደሴቶቹ ውስጥ በአካልም ሆነ በአእምሮ ጤነኛና ነጻ የሆንኩ አንድ እሥረኛ አድርጌ ራሴን አቆጥራለሁ። በምወጣበትም ጊዜ ዕድሜዬ ሠላሳ ዓመት ብቻ ነው የሚሆነው።

ከደሴቶቹ ለማምለጥ የሚደረገው ሙከራ አልፎ አልፎ መሆኑን ዐውቄአለሁ። ግን ጥቂት ሰዎች ብቻ ነጠላ በመሆን ሊሳካላቸው የቻሉ ነበሩ። ሽለሆነም እኔም ያው አመልጣለሁ። በሁለት ዓመት ውስጥ እንደማመልጥ ሰከሎሲዎ ነገርኩት።

«አንተን የሚያግድህ ምንም ነገር የለም ፓፒዮ። ይኖራል እንዴ? የምታደርገው መሆንህን እኔም ዕምነት ስላለኝ በተስፋ አጠባበቃለሁ። አስካሁን ድረስ አንድ ዓመት ያህል ለማምለጥ ስትሞክር ቆይተህ አሁንም በቃኝ ብለህ ገና አልተውከም። አንዱ ሲከሽፍብህና ሌላውን ስትጀምር ሰው አይቀድምህም። ከዚህ ግን፣ አንድ ጊዜ እንኳ ለማምለጥ አለመሞከርህ ገርሞኛል።»

«ጓደኛዬ፣ እዚህ ያለው አንድ መንገድ ብቻ ነው። ዓመፅ መቀስቀስ ብቻ። ከዚህ ደግሞ እነዚህን ሁሉ ምናምንቴዎች ለማስተባበር ጊዜ አላገኘሁም። የአንድ ጊዜ ሙከራዬ ሊያስበላኝ ነበር። እዚህ ያሉት ዐርባ ሰዎች የበሰበሱ እሥረኞች ናቸው። በሥርዓቱ ተጠምደው ተይዘዋል፣ እኛ እንደምናደርገው አይንቀሳቀሱም። ለምሳሌ እነዚያን ጭራቆችና ጠላቱን አጎዳለሁ ብሎ ሰባት ንጹሕ ሰዎችን ሾርባ ውስጥ መርዝ በመከተት የገደለውን ሰው ውሰድ። እነርሱ እንደ እኛ ዐይነቶች አይደሉም።»

«ግን ከደሴቶቹ የደረሰ ሁሉም ሰው እንደዚያው ይሆናል።»

«ጥርጥር የለውም፤ ግን ለማምለጥ ማንንም ሰው አልፈልግም። ብቻዬን

t.me/OLDBOOKSPDF

አወጣዋለሁ ወይም ቢበዛ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር:: ምን ያስቅሃል?»

«መረታትህን አሜን ብለህ አለመቀበልህ፣ ሊሆን አይችልም ብለህ በማመን ፋንታ ወደ ፓሪስ ተመልሰህ ከጠላቶችህ ጋር ለመፋጠጥ እንደዚህ በሐሳብ መብገንገንህ ነው::»

«መልካም ሌሊት ከሎሲዎ፣ ነገ እንገናኛለን:: የሆነ ሆኖ ጁሳሊዩ ደሲዮችን ልናይ መሔዳችን ይመስለኛል:: ግን ለማወቅ የፈለግኩት እነዚህ የተረገሙ ደሴቶች ለምን የመድኃን ደሴቶች እየተባሉ እንደሚጠሩ ነው::»

«ከከሎሲዎ ፈቀቅ ብዬ የሴሊቱን ለስላሳ ነፋስ ለማግኘት ወደ ውጭ እንጥቼን ሰገግ አደረግሁ::

በሚቀጥለው ጧት ማለዳ ወደ ደሴቶች ጉዞ ጀመርን:: በካየንና በቅዱስ ላውረን ደሴቶች መካከል በሚመላለስ ዐርባ ቶን ከብደት ባለው፣ «ታኖን» በተባለ አንድ የጠረፍ ጀልባ ሐያ ስድስት የምንሆን አሥረኞች ተሳፍረን ነበር:: ጥንድ እየሆን እግሮቻችንን በሰንሰለት ተቀራኝተን በአጅ ካቴናም ታሥረን ነበር:: አራት ዘበኞች ጠመንጃዎቻቸውን በተጠንቀቅ የደገኑባቸው ሰምንት ሰዎች የሚገኙባቸው ሁለት ቡድኖች በጀልባው ግንባር ገቡ:: ከሁለት የአጃቢዎቹ መሪዎችና ከስድስት ዘበኞች ጋር ዐሥር ሰዎች ያሉት ሌላ ቡድን ደግሞ ከጀልባው ኋላ በኩል መጣ:: ከአየሩ መጥፎነት የተነሣ መርከቡ ሊሰምጥ ቃጣው:: በጉዞው ወቅት ላለመጨነቅ ወስኜ ስለነበር፣ አንድ ዓይነት ማረሳሻ ለማግኘት በዙሪያዬ አማተርኩ:: ለማብሸቅ ያህል አጠገቤ የቆመውን አንድ ገደል ፊት ዘበኛ፣ «ጀልባው ቢሰምጥ በእነዚህ ሰንሰለቶች እንደተጠፈርን ፀሎት ማድረስ አይቻለንም:: እንጨቱ ክመቦክቦኩ የተነሣ መርከቡ ከዚህ ዕጣ የሚያመልጥ አይመስልም» አልኩት::

ዘበኛው እንደ መባነን አለና፣ «ስመጣ፣ ደንታ የለንም፣ እንድናስራችሁ ትእዛዝ ተሰጥቶናል፣ ይኸው ብቻ ነው:: ኃላፊነቱ ትእዛዙን በሰጡት ሰዎች ላይ ነው:: እኛ ንጹሕ ነን» አለ

«በዕርግጥ ልክ ነህ ጌታዬ:: ከሰንሰለት ጋር ሆነም አልሆነም ይህ የሬሣ ሣጥን የመሰለ መርከብ ለሁለት ቢገመስ፣ ወደታች የምንወርደው ሁላችንም አብረን ነው»

«አ፣ ይህ ጀልባ ይህን የመሰለ ጉዞ ሲያደርግ ረጅም ጊዜ ስላለው ምንም ነገር እንሆንም» አለ ቂላ ቂሉ ዘበኛ::

«ልክ ኅህ:: በጣም ለረጅም ጊዜ ከመቆየቱ የተነሳ ወደፊት ሆነ ወይም በቅርቡ አንድ ነገር ያጋጥመዋል::» የምፈልገውን ግብ መታሁ፣ አእምሮ የሚበጠበጠው ጸጥታ ተወገደ:: ሊሎች ዘበኞችና አሥረኞች በውይይቱ ወዲያው ተካፈሉ:: ከአሥረኞቹ አንደኛው እንደዚህ አለ:: «ይህ ጀልባ አደገኛ ነው፣ ከዚህም በላይ እኛ በሰንሰለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቆራኝተናል። ያለ ሰንሰለት ብንሆን እንኳ ቢያንስ የመትረፍ ዕድል ይኖረን ነበር።»

«እኛም ከእናንተ የተሻልን አይደለንም። ዩኒፎርሞቻችን፣ ሚግጋቻችንና ጠመንጃዎቻችን አሉ። እነዚህ ሁሉ ቀላል ከብደት አይደሉም» በማለት ዘበኞቹ መለሱ።

«ጠመንጃዎቹን አትቁጠሯቸው። የጀልባ አደጋ ቢያጋጥም ወዲያው ልትጥሏቸው ትችላላችሁ።»

ሚላማ መምታቴን ከተመለከትኩ በኋላ፣ ሁለተኛውን ለመቆስቆስ ሞከርኩ። «የአደጋ መትረፊያ ጀልባዎቹ ወዴት ናቸው? ማየት የቻልኩት አንዲት ብቻ ናት፣ እርሷም ቢበዛ የምትይዘው ሰምንት ሰዎች ነው። አዛዡና መርከበኞቹ ወዲያውኑ ይሞሏታል። ሌሎቹን ማን ጉዳይ ይላቸዋል?»

በጣም ርቀናል፣ በፍጥነት እየገሠገሥን ነበር።

«ትከከል ነህ። ምንም ነገር የለም። ለእነዚህ የአረመኔ መንጋዎች ተብሎ የበዙ ቤተሰብ ኃላፊዎች የሆኑትን ሕይወት ለአደጋ ማጋለጥ ኃላፊነትን አንደ መዘንጋት የሚቆጠር ነው።»

ከሁለቱ የኮንቮዩ መሪዎች ጋር ከጀልባው በስተኋላ ካለው ቡድን መካከል ነበርኩ።

ከእነርሱ አንደኛው ትኩር ብሎ ተመለከተኝና፣ «ከኮሎምቢያ ተመልሰህ የመጣኸው ፓፒዮ የተባልከው አንተ ነህ አንዴ?» አለ።

«አዎ።»

«ያን ያህል ርቀህ መሔድህ እስከዚህ አያስደንቀኝም። ስለ ባሕር ብዙ ልምድ ያለህ ትመስላለህ» አለ።

ደረቴን ወደ ፊት ነፋሁና፣ «አዎ፣ በሚገባ ብዙ ዐውቃለሁ» አልኩት። ይህም ቀዝቀዝ አደረገው። ይህ በዚህ አንዳለ፣ ካፒቴኑ መሪውን ለቀቀና እኔን ሊገናኝ መጣ። ማሮኒ ወንዝ ላይ ከነበርንበት ወቅት ጀምሮ ከመሪው አልተለየም ነበር።

በጉዟችን ላይ በጣም አደገኛው ከፍል ያ ነበር። ማን አሁን አልፈነው ስለነበር፣ አንድ ሰው እንዲይዝለት አድርጓል። ታዲያ ያ ትንሽ ወፍራም ጥቁር ሰው፣ በአንዲት የአንጨት ጉማጅ ላይ ሆነው ኮሎምቢያ ድረስ ያለውን መንገድ የተጓዙትን ቀልደኞች ለመገናኘት ጠየቀ።

የኮንቮዩ መሪ፣ «ይኸ፣ ያኛውና አንዱ ደግሞ እዚያ ወዲያ ያለው ነው» አለው።

«ካፒቴኑ ማንኛው ነበር?» ሲል ጠየቀ።

«አኔ ነበርኩ ጌታዬ!»

«ታዲያስ ልጅ፣ እንኳን ደስ አለህ ልልህ እፈልጋለሁ። አንተ ቀላል ሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

አይደለህም። ያውልህ» እጁን ከጃኬቱ ኪስ ውስጥ አስገባና፣ «ይህን ፓኬት ትንባሆና የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀቶች ውሰድ። አንግዳዬ ሁን» አለ።

«አመሰግናለሁ ጌታዬ። ይህን የሬሳ ሣጥን ለመቅበዝ ወኔ በማግኘትህ እኔም እንኳን ደስ አለህ አልሃለሁ» ስለው፣ በሣቅ ጢ ብሎ ፈነዳ። ይህም ለዘበኞቹ ከሚቋቋሙት በላይ ሆኖባቸው ነበር።

«በዚህ በኩል ልክ ነህ! ይህ የእንጨት በርሜል ቀደም ብሎ ወደ መቃብር ቦታው መላክ በተገባው ነበር፤ ግን ኩባንያው መድኀኒኑን ለመሰብሰብ ስለሚፈልግ እስኪሰምጥ ድረስ እየጠበቀ ነው።»

አንድ የመጨረሻ ግፊት ደግሞ ጨመርኩ። «አንተና ሠራተኞቹ የአደጋ መትረፊያ ጀልባ በማግኘታችሁ ዕድለኞች አይደላችሁም እንዴ?» ከአፉ አመለጠውና፣ «አዎ፤ አይገባም እንዴ?» አያለ ወደ ደረጃዎቹ ሔደ።

ባሕሩ ረጭ ብሎ የረጋ ቢሆንም፣ ነፍሱ ግን ከፊት ለፊታችን እየተጋረጠ ነበር። በምንሔደው ወደ ሰሜን ምሥራቅ ማለትም ወደ ነፋሱና ማዕበሎቹ አቅጣጫ በመሆኑ ጀልባው ይዋዥቃል። ብዙ ዘርኞችና አሥረኞች ታመሙ። ከእኔ ጋር ተቆራኝቶ የታሰረው ሰው ጥሩ መርከበኛ ነበር። ከፓሪስ የመጣ አልም ያለ ወመኔ ቢጤ ነበር። ወደ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት የተላከው በ1927 እንደ መሆኑ በደሴቶቹ ሰባት ዓመት ቆይቷል። እድሜው ሠላሳ ስምንት ይሆናል። ግን ወጣት ይመስላል። «ቲቲ ላ ቤሎቲ ተበዬ አጠራለሁ፣ እንደዚህ ስልም የምን ጊዜውም ፍላንቱ ቤሎቲ የተባለ ካርታ መጫወት ነው። በደሴቶቹ ላይ የምኖረው ለዚሁ ሰል ነው። ሌሊቱን ሙሉ በሁለት ፍራንክ እየተወራረድሁ ለመጫወት» አለ።

«ደሴቶቹ ውስጥ እስከዚህ ገንዘብ አለ?»

«ብትፈልግ እንወራረድ፤ ደሴቶቹ ሊፈነዱ በደረሱ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዎች ተጨናንቀዋል። አንዳንዶቹ ገንዘባቸውን ራሳቸው ይይዛሉ፡ ሌሎቹ ደግሞ ግማሹን እንደ ደላላ ለሚያገለግልዋቸው ዘበኞች በመስጠት ይጠቀማሉ። ጓደኛዬ አዲስ ነህ ልበል? ምንም ነገር የምታውቅ አትመስልም።»

«አላውቅም። ስለ ደሴቶቹ ብዙ አላውቅም። የማውቀው ቢኖር ለማምለጥ ከባድ መሆኑን ብቻ ነው።»

«ማምለጥ» አለ ቲቲ። «እርሱንስ አርሳው። በደሴቶቹ ውስጥ ሰባት ዓመት ሆኖኛል፡ በዚህ ወቅት ሁለት ማምለጦች ተደርገዋል። በውጤቱም ሦስቱ ሞቱ፡ ሁለቱ ተያዙ። ማንም ያመለጠ የለም። በዚህ ምክንያት ነው ይህን እድል ለመሞከር ፈቃደኛ የሆኑ ብዙ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የማይኖሩት።»

« ወደ ግራንዴቴሬ የሄድከው ለምን ነበር?»

t.me/OLDBOOKSPDF

« የሐድኩት የአንጀት ቁስል እንዳለብኝ ለማወቅ ራጅ ለመነሣት ነበር።»

«ታድያ ከሆስፒታል ለማምለጥ አልሞከርከም?»

«ስማ! ማንኛውንም ነገር ያበላሸኸው አንዱ አንተው ነህ። ይባስ ብሎ እኔ የታሰርኩት አንተ ካመለጥክበት ከፍል ውስጥ ነበር፡ ጥበቃውን አይተኸው ቢሆን ኖሮ፣ አየር ለመተንፈስ እንኳ ወደ መስኮቱ ራመድ ስል፣ አንድ ሰው ከኋላዬ ይንትተኛል። ለምን ብዬ ስጠይቅ፣ ምናልባት ልከ እንደ ፓፒዮ ልትሆን ትሞክር ይሆናል ይለኛል።»

«እስኪ ንገረኝ ቲቲ፣ ከኮንቩዩ መሪ ቭጥሎ የተቀመጠው ያ ግዙፍ ሰው ምንድን ነው? ነገር አዋሻኪ ይሆን እንዴ?»

«ለብደሃል? ያ ሰው ጨዋ ነው። የማንም ቲፎዞ ላይሆን ይችላል፣ ግን ራሱን እንዴት እንደሚጠብቅ ያውቃል። በዘበኞቹ አካባቢ እየተሹለከለከም ውለታ እንዲሠሩለትም አይጠይቅም። እንደ እሥረኛ ቢሆንም ስለ ክብሩ በጣም ይጠነቀቃል። ጥሩ ምክር ይሰጣል። ጥሩ ጓደኛ ነው። ከፖሊሶች ራሱን ያርቃል። ቁሱና ዶክተሩ እንኳ ሊቀርቡት አይደፍሩም። አሳባቂ ሊመስል ይችል ይሆናል፣ ሐቁ ግን የሉዊ ዐሥራ አምስተኛ የልጅ ልጅ መሆኑ ነው። ትከክል ነው ጓዴ። መኳንንት ነው። እርግጠኛ መኳንንትና የሚጠራውም የሸን ደቤራክ መስፍን ተብሎ ነው። ከመጣ በኋላ ከሰዎች ጋር መግባባት ለመጀመር ረጅም ጊዜ ፈጅቶበታል፣ ምክንያቱም ወደዚህ ሊያመጣው የቻለው ድርጊት በጣም የሚዘገንን ነበር።»

«ምንድን ነው ያደረገው?»

«ልጁን ከአንድ ድልድይ ላይ ወደ ወንዝ አሽቀነጠረው። ልጁ ግን ጥልቅ ያልሆነ ቦታ ላይ ዐረፈ። ስለሆነም ወደ ወንዙ ወረደና አንደገና አንሥቶ ውሃው ይበልጥ ጥልቅ ወደሆነበት ወረወረው።»

«በክርስቶስ! ይኸማ ልጁን ሁለት ጊዜ እንደመግደል ይቆጠራል!»

«ጓደኛዬ የሆነ አንድ ታማኝ ሰው ፋይሉን ኢይቶ እንዳለው፡ ይህን ወንጀል የፈጸመው ለመኳንንትነት ደሙ በመጨነቁ ነበር። የሕፃኑ እናት በቤታቸው ውስጥ አገልጋይ ስለነበረች፡ በተለይ በእናቱ ዘንድ እንደ ውሻ ነበር የምትታየው። መስፍኑም በእናቱ ተጽዕኖ የተነሣ አርቆ ባለማሰብ ወደ በጎ አድራጎት እንደሚወስደው አስመስሎ ሕፃኑን ከወንዝ ውስጥ ወረወረው።»

«የፈረዱበት ምን ነበር?»

«ዐሥር ዓመት ብቻ። ነገርከህኮ ፓፒዮ፤ እርሱ እንደ ሌሎቻችን ዐይነት ሰው አይደለም። የቤተሰቦቹን ክብር ለመጠበቅ የሚታገል አንድ መኳንንት የአገልጋዩን ልጅ ቢገድል እስከዚህ ከባድ ጥፋት ነው አይባልም ብላ እናቱ ለዳኛው አመለከተች።»

«ታዲያስ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ታዲያማ፡ እኔ ከፓሪስ የመጣሁ አንድ ዘዋሪ ፀረብ ነኝ፤ ግን አስተያየቴ ይሽውልህ። በመሠረቱ፤ ገርን ደ ቤራክ ከአስተዳደጉ ከብርን ብቻ እንደ ቁምነገር አንዲቀስም የተገደደ ገሪባ ነው። ምናልባትም አሽከሮቻቸውን በጨሰኝነት ብቻም ሳይሆን ከዚያም ግምት በታች ይመለከታቸው ነበር። አስፈሪ አውሬ የሆነችው እናቱ ደግሞ እርሱን እየጨቆነችና እያስፈራራች፤ ከአሽከሮቿ እንደ አንዱ ወደሚሆንበት ደረጃ አድርሳዋለች። በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ብቻ ነው ይህ ሰው ሰብአዊ መብቱን ተቀዳጅቶ ትክክለኛና ጨዋ ሰው ለመሆን የበቃው። ለሰሚ ግራ ይሆን ይሆናል፣ ግን በእርግጥ እሱ የቤራክ መስፍን የሆነው አሁን ብቻ ነው።»

በትንሽ ደቂቃ ውስጥ ዱሳሊዮ ደሴቶች የማይታወቁ ሀገሮች መሆናቸው ያከትማል። አሁን ያወቅኩት ነገር ቢኖር ከዚያ ለማምለጥ ከባድ መሆኑን እንጂ አለመቻሉን አይደለም። የባሕሩ ለስላሳ ነፋስ በሰፊው እየተመገብኩ፤ ይህ ከፊቴ የሚነፍሰው ንፋስ ከበስተኋላዬ ዞሮ ወደ ነጻነት ተሸክሞ የሚወስደኝ መቼ ይሆን ብዬ አሰብኩ።

ደረሰን። የሮያሊና የቅዱስ ዮሴፍ ደሴቶች ከሥር፣ ከዲያብሎስ ደሴት በላይ በኩል ሆነው ሦስት ማዕዘን ሠርተዋል። ፀሐይዋ ቀደም ሲል ብታሽቀለቁልም ሁለት በምድር ወገብ ብቻ የሚገኘው ያ ኃይለኛ ብርሃን ቁልቁሉ አድርጎ ያሳያቸው ነበር። ሮያሌ ለጥ ያለ ጠረፍ ኖሯት፣ ከዚያም በስድስት መቶ ጫማ ከፍታ ላይ አንድ ደልዳላ መሬት አላት። ጠርዙ ዙሪያውን ተቁርጦ ባሕር ላይ የተንሳፈፈ አንድ የሚከሲካውያን ባርኔጣ ትመስላለች። በየቦታው በጣም አረንጓዴ የኮከነት ዘምባባዎች ነበሩ። ቁይ ጣሪያ ያላቸው ትናንሽ ቤቶች፣ ለደሴቷ ልዩ የሆነ መስህብ ስሳንና ፀጥታ፣ ውስጧ ምን እንደሆነች ላላወቀ የቀረው ዕድሜውን እዚያው ለመጨረስ ታጓጓዋለች። በተጨማሪም ሞርከቦች ከጭጮኝ ጋር እንዳይጋጩ የሚረዳ አንድ የኢይጋ ማስጠንቀቂያ መብራት ከጠረፉ ዳር አለ። አሁን እየተቃረብን ስለሆነ አምስት ትላልቅና ረጃጅም ህንፃዎች መለየት ቻልኩ። ከእነርሱ ውስጥ ሁለቱ አራት መቶ እሥረኞች የሚኖሩባቸው ሰፊ አዳራሾች መሆናቸውን ቲቲ ነገረኝ። ከዚያም በከፍተኛ ፀጥታ የሚጠበቀው ሰፈር ከእሥር ቤቶችና ከፀሐይ ጉሮኖው ጋር በረጅም ነጭ የግንብ አጥር ዙሪያውን ተከብቦ ይገኛል። አራተኛው ህንፃ የእሥረኞቹ ሆስፒታልና አምስተኛው ደግሞ አብዛኞቹ ዘበኞች የሚኖሩበት ሲሆን፣ ቀሪዎቹ የሚኖሩት በሸንተረሮች ላይ ተበታትነው በሚገኙት ባለቀይ ጡብ ጣሪያ ትናንሽ ቤቶች ውስጥ ነበር። ራቅ ብላ ከሮያሌ ጫፍ ጋር በጣም በመጠጋት ያለችው ደግሞ ቅዱስ ዮሴፍ ደሴት ነበረች። ለምላሜዋ እስከዘሀ ባይሆንም ትንሽ የዘንባባ ዛፎችና ከበላይዋ አንድ ትልቅ ህንፃ ይገኙባታል። የግዙት ወህኒ ቤቱ መሆን እንዳለበት ገመትኩ፤ ቲቲም አረጋገጠልኝ። ጊዜያዊ ቅጣት ያለባቸው እሥረኞች የሚኖሩበት በውሃው ዳር ያሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ህንፃዎችንም አመለከተኝ። የጥበቃ ሰንሶችና የግንብ ምሽጎቹ ቁልጭ ብለው ይታያሉ። ሌሎች ንጹሀኖችና ትናንሽ ቤቶች ከቀይ ጣሪያዎቻቸው ጋር ነበሩባት።

ጀልባው ከደቡብ አቅጣጫ ወደ ሮያሌ ደሴት ስላሳበረ፤ የዲያብሎስ ደሴት ራቀችን። ከአለሁበት ሆኜ ማየት እንደቻልኩት፤ በኮከነት ዘንባባዎች የተሸፈነችና ምንም ዐይነት ህንፃ የሌለባት አንድ ትልቅ ቋጥኝ ነበረች። ቢጫ ቀለም የተቀቡና ግራጫ ጣሪያ ያላቸው ትናንሽ ቤቶች ብቻ በውሃው ዳር ይታያሉ። በኋላ እንደተረዳሁት የፖሊሳ ኢሥረኞች የሚኖሩት እዚህ ቦታ ነበር።

አሁን ቀጥ ብለው በተሰሩት ትላልቅ የሲሚንቶ ብሎኬቶች ወደ ተከለለው የሮያሌ ወደብ እየተጠጋን ነበር። ያንን ለማነፅ የብዙ ኢሥረኛ ሕይወት ተከፍሎበት መሆን አለበት!

በትላላቅ ኮረብቶችና በሲሚንቶ ጥበቅ ሆኖ ከታነፀ ዐሥር ጫማ ከፍታ ካለው አንድ ረጅም የጀልባ መቆሚያ ድልድይ ለመድረስ በማምት ሁለት መቶ ሃምሳ ያርድ ሲቀረው፡ «ታኖን» ጡሩንባውን ሦስት ጊዜ አምባረቀና መልህቅ ጣለ። በእኛ ትይዩ፡ በጥቁር ቀለም «የዘበኞች ጣቢያ»፣ «የባሕር መጓጓዣ አገልግሎት»፣ «ዳቦ ቤት»፡ «የወደብ አስተዳደር» የሚሉ ጽሑፎች የተጻፉባቸው ነጫጭ ህንፃዎች መደዳውን ይታያሉ።

ጀልባው ሲመጣ የሚመለከቱትን ኢሥረኞች ማየት ቻልን። የለበሱት ባለመስመሩን ቱታ ሳይሆን ሱሪና ነጭ ጃኬት መሳይ ልብስ ነበር። ገንዘብ ካለህ ደሴቶቹ ውስጥ ልብስ ሰፊ ቀጥረህ በራስህ ልክ ማሰፋት ትችላለህ ሲል ቲቲ ላ ቤሎቲ ነገረኝ። አንደጣቃ የሚጠቀሙት የዱቄት ከረጢቶቹን ምልክቶች በማጥፋት ሲሆን፡ ተስማሚ የሆኑ ልብሶችን፡ ፋሽን እንኳ ሳይቀር እየተከተሉ ይሰፋሉ። የኢሥረኞቹን ዩኒፎርም የሚለብሰው ሰው እምብዛም ነው።

አንዲት ባለሞተር ጎታች ጀልባ ወደ «ታኖን» ቀረበች። አንድ ዘበኛ በመሪው ላይ ሆኖ፤ ካርባይን የታጠቁ ሁለት ዘበኞች ከጎንና ጎኑ፤ ከኋላው ደግሞ ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን የሆኑ ስድስት ኢሥረኞች ቆመው ይቀዝፉ ነበር። በቅልጥፍና ተሻገሩ። ከጀልባው ኋላ አንድ ትልቅ ከአደጋ መትረፊያ ባዶ ጀልባ በገመድ ታስሮባት ነበር። ጎታች ጀልባው በፍጥነት ከታሰረች በኋላ ሁለቱ የኮንቮዩ መሪዎች ወጡና ከኋላ በኩል ቦታቸውን ያዙ። ወደ ጀልባዋ ፊት የሐዲዱ መሣሪያ የያዙ ሁለት ዘበኞች ተከተሏቸው። እጆቻችን አሁንም በካቴና እንደታሰሩ ይሁኑ እንጂ የአግሮቻችን ሰንሰለቶች ተፈትተውልን፡ በመጀመሪያ የእኔ ቡድን ዐሥሩ፣ ከዚያም ከፊት በኩል የነበሩ ሰምንቱ እየተጣመርን ወደ ጀልባው ውስጥ ገባን። ኢሥረኞቹ ወደ ፊት መቅዘፍ ጀመሩ። ለቀሩት ቡድኖች እንደገና ሊመለሱ ነበር። ከወደቡ ዳር አውርደው ተዉን

t.me/OLDBOOKSPDF

«የወደብ አስተዳደር» የሚል ጽሑፍ ካለበት ሕንፃ ፊት ለፊት በሰልፍ ሆነን እንጠባበቅ ጀመር። ጓዝ አልነበረንም። ምንም እንኳ አምስት ወይም ስድስት ጫማ ለጥንቃቄ ያህል ራቅ ቢሉም፣ እዚያ የቆሙት ኦሥረኞች ለዘበኞቹ ፍጹም ደንታ ሳይኖራቸው ያምፆቻቸውን ከፍ በማድረግ ከእኛ ጋር ያወሩ ነበር። አብዛኛዎቹ በእኔ ኮንቮይ የመጡ ስለነበሩ፣ የጓደኝነት ሰላምታ ሰጡኝ። በቅዱስ ማርቲን አውቃቸው የነበሩ ሲዛር እና ኤዛሪ የተባሉ ሁለት ኮርሲካዊ ወንበዴዎች የባሕር መጓጓዣ አገልግሎት ቀዛፊዎች መሆናቸውን ነገሩኝ። ከዚያም ከመታሰሬ በፊት ፈረንሣይ ውስጥ አውቀው የነበረውን ቻፓር ብቅ አለ። ለዘበኞቹ ምን ደንታ ሳይኖረው፣ «ፓፒዮ ፍፁም እንዳትሰጋ! በጓደኞችህ መተማመን ትችላለህ። በግዞት ወህኒ ቤት ምንም ነገር የሚጎድልብህ አይኖርም። ምን ፈረዱብህ?» አለ።

«ሁለት ዓመት።»

«መጥፎ አይደለም። ጊዜው ፈጥኖ ያልቅልህና ትመለሳለህ። ቆይ ታያለህ። እዚህ ኑሮ ከባድ አይደለም።»

«አመሰግናለሁ ቻፓር። ዴጋ ወዴት አለ?»

«በኮረብታው ላይ ጸሐፊ ነው። እንዴት እዚህ እንዳልተገኘ እኔም ገርሞኛል። መቼም ያላገኘህ እንደሆነ ያዝናል።»

ይህ በዚህ እንዳለ ጋልጋኒ ወደ እኔ መጣ። አንድ ዘበኛ ሊከለክለው ፈለገ ግን «ወንድሜን ሰላም ለማለት አትከለክለኝም» በማለት ወደ ጎን አገለለውና ትከሻዬን አቅፎ፣ «በአኔ ተማመን» አለ።

«አዚህ ምን እየሰራህ ነው?»

«ፖስታ አገልግሎት ውስጥ ነኝ።»

«ኑሮ እንዴት ነው?»

«መጥፎ አይደለም።»

የመጨረሻዎቹ ቡድኖች መጥተው ተቀላቀሉን። የእጆቻችን ካቴናዎች ተፈቱልን። ሰቲቲ ላ ቪሎቲ፣ ለቬራኩና ለሌሎችም አንድ ዘበኛ «እንሂድ፣ ወደ ካምፕ ቮፑ» አላቸው። ከቀኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት የያዟቸውን ጥቅሎች ተሸክመው ነበር። ትከሻዎቻቸው ላይ አነገቡና ወደ ደሴቷ አናት የምትወስደውን ቀጭን መንገድ ተከትለው ተቃኑ። የወህኒ ቤቱ አዛዥ ከሲድስት ዘበኞች ጋር መጣ። ስም መጥራት ጀመረ። ሁሉም ሰው ተገኝቶ ነበር። የእኛ እጃቢዎች ለብቻ ተለዩ።

«ጸሐፊው ወዴት አለ?» ሲል የወህኒ አዛዡ ጠየቀ።

«በመንገድ ላይ ነው ጌታዬ!»

ዴጋ ከባለአገራር ጃኬቱ ጋር በነጫጭ ልብሶቹ ተውቦ ሲመጣ አየሁት።

t.me/OLDBOOKSPDF

እርሱና አብሮት ያለው ዘበኛ እያንዳንዳቸው አንድ ትልቅ መዝገብ ይዘዋል። ከሰልፍ በየተራ እየወጣን አዲስ መለያ ተሰጠን።

«ግዞት ወህኒ ውስጥ የምትገባ እገሌ፣ እገሌ የተጻሸ መታወቂያ ቁጥር ... የነበርከው አሁን በግዞት ወህኒ ቤት ቁጥር ..... ተለውጦልሃል።»

የእኔ ተራ ሲደርስ፣ ዴጋ ወደፊት ራመድ አለና ትከሻዬን እቀፈኝ።

«ፓፒዮ የተባለው ይኸ ነው?» ጨል የወህኒ አዛዡ ጠየቀ።

«አዎ ጌታዬ» ሲል ዴጋ መለሰ።

«ግዞት ወህኒ ቤት መልካም እድል ይግጠምህ። ሁለት ዓመት ቶሎ ያልፋል።»

ግዞት

ጀልባው ተዘጋጅቷል። ከዐሥራ ዘጠኞቻችን ውስጥ አስሩ በመጀመሪያው ዕጣ ሊሄዱ ነበር። እኔም ተጠራሁ። «አይሆንም፣ በመጨረሻው ጉዞ ይሄዳል» አለ ዴጋ ፍርጥም ብሎ። ከከባድ እሥረኞቹ የአነጋገር ፈሊጥ ተደንቄ ነበር። ምንም ሥነ ሥርዓት ያላቸው አይመስሉም። ዘበኞቹን ከመጤፍ አይቆጥሯቸውም። ዴጋ ወደ እኔ ቀረበና ማውራት ጀመርን። ስለማምለጫ በጠቅላላው አውቋል። በቅዱስ ላውረን የማውቃቸው አንዳንድ ሰዎች ወደ ደሴቶቹ ሲመጡ ነግረውት ነበር። አዝናለሁ አላለኝም። ይህ ከእርሱ ግምት በታች ነው። ያለው ቢኖር፣ «ይሳካልህ በተግባ ነበር፣ የእኔ ልጅ። ግን በሚቀጥለው ጊዜ ይሆንልሃል!» ነበር። በርታም አላለኝም። አሁን እንደማያስፈልገኝ ያውቃል።

«ዋና ጸሐፊው ስለሆንኩ፣ ከወህኒ አዛዡ ጋር አግባብ አለኝ። በግዞት ወህኒ ቤት ራስህ ጠንቀቅ በል እንጂ ትንባሆና ምግብ እልክልሃለሁ። የሚያስፈልግህን ማንኛውንም ነገር ታገኛለህ» አለ።

«አንሂድ ፓፒዮ!» የእኔ ተራ ደረሰ።

«ሁላችሁም ደህና ሁኑ። ለርኅሩኅ ቃሎቻችሁ አመሰግናለሁ።»

ከሐያ ደቂቃ በኋላ ቅዱስ ዮሴፍ ደረስን። ለስድስት ቀዛፊዎችና ዐሥር ግዞተኞች በጀልባው ውስጥ ለጥበቃ የተመደቡት ሦስት መሣሪያ የታጠቁ ዘበኞች ብቻ መሆናቸውን ልብ ብዬ ተመለከትኩ። ጀልባውን ለመንጠቅ አንድ ጥሩ አጋጣሚ በሆነ ነበር። በደሴቷ የሚገኙ ጠባይ ማረሚያ አዛዥና በግዞት ወህኒ ቤቱ አዛዥ የሚመራ አንድ እንግዳ ተቀባይ ኮሚቴ ቅዱስ ዮሴፍ ስንደርስ አቀባበል አደረገልን። በላዩ ላይ «የሥነ ሥርዓት ግዞት ቤት» የሚል የተጻፈበት አንድ ትልቅ የብረት መዝጊያ አለፈን ስንገባ፣ ይህ ወህኒ ቤት የሚቀለድበት አለመሆኑን ተገነዘብኩ። «የአስተዳደር መምሪያ» የሚል በላዩ ላይ የተጻፈበት አንድ ትንሽ ሕንፃና ሦስት ሌሎች ሀ ለ ሐ ሕንፃዎች አለፈን

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ውስጥ አመራን። ቅዝቃዜም ነበረው።

በሁለት ረድፍ እንደተሰለፍን አዛዡ፣

«ጣዞተኞች፣ እንደምታውቁት ይህ ወህኒ ቤት ቀደም ሲል ወደቅኝ ግዛት አስቆቂ ወህኒ ቤት ተፈርዶባቸው ከመጡ በኋላ ተጨማሪ ጥፋት ለሚፈጽሙ ሰዎች ማቆያ ነው። እዚህ ርኅራኄ ልናሳይ እንሞከርም። ዋጋ እንደሌለው እናውቃለን። ልናርማችሁ እንሞክራለን። አንድ ሕግ ብቻ አለን። አፋችሁን መዝጋት ይኖርባችኋል። ፍጹም ጸጥታ። በ 'ሰልክ' መልእክት ለመለዋወጥ እንሞክራለን ስትሉ ብትያዙ፣ ከበድ ያለ ቅጣት ያስከትልባችኋል። ከባድ ሕመም ካልያዛችሁ ወደ ሕክምና ቦታ ለመሄድ አትጠይቁ። አግባብ ላልሆነ የሕክምና ጥሪ ትቀጣላችሁ። ማለት ያለብኝ ይህንኑ ብቻ ነው። አሃ! አንድ ተጨማሪ ነገር ቀርቷል ማጨስ በጥብቅ የተከለከለ ነው። እሺ ዘበኞች፣ መንገድ ቁጥሉ። በጥብቅ ፈትሹና ከዚያም እያንዳንዳቸውን አንድ ከፍል ውስጥ አስገቧቸው። ቫሪየን፣ ከሎሲዎንና ማቹሬን ከአንድ ሕንፃ ውስጥ አንዳታስገቧቸው። ሚስተር ሳንቶሪ፣ እባክህ ይህን ሁኔታ እንድትከታተል» አለ።

ከዐሥር ደቂቃ በኋላ፣ በሕንፃ - ሀ ቁጥር 234 ከፍሌ ውስጥ ተቆለፈብኝ። ከሎሲዎ - ለ - ማቹሬ - ሐ - ውስጥ ገቡ። በጥቅሻ ደህና ሁኑ ተባባልን። ምንጊዜም ከዚህ ቦታ በሕይወት ለመውጣት ከፈለግን፣ ጨካኝ ሕጋቸውን መቀበል እንደሚኖርብን እያንዳንዳችን ተረድተናል። አብረን ለተጋፈጥናቸው ነገሮች ፍጹም ቅር የማይላቸውና ፍጹም የማያማርሩት እነዚያ ኩሩና ጀግና አጋሮቼ ሲለዩኝ በአንከሮ ተመለከትኳቸው። የዐሥራ አራት ወራት የነጻነት ትግላችን በመካከላችን የማይበጠስ መተሳሰር መስርቶልን ነበር። ልቤ በሐዘን ተወጋ።

የከፍሌን ዙሪያ ተመለከትኩ። ሀገሬን ፈረንሣይን የመሰለች የነጻነት ቋንጮ፣ ይባስ ብላ በፈረንሣይ ጊያና ግዛቷ፣ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ውስጥ የምትገኝ አንዲት ኢምንት ደሴት ውስጥ የቅዱስ ዮሴፍ ግዞት ቤትን ዐይነት አረመኔያዊ መጨቆኛ ተቋም መመሥረቷን ለማመን አስቸጋሪ ነው። እያንዳንዳቸው አንዲት ትንሽ ብረት መዝጊያና ወፍራም የግንብ ግድግዳዎች ያሏቸው አንድ መቶ ሃምሳ ከፍሎችን አስኪ ገምቱ። ከእያንዳንዱ መዝጊያ በላይ «ያለ ልዩ ፈቃድ ይህን መዝጊያ አትክፈት» የሚል ማስጠንቀቂያ ነበር። ልክ አንደ ቦሊየ፣ አንድ የጣውላ አልጋና አንድ የጣውላ ትራስ በስተግራ በኩል አለ። አልጋው ወደኋላ ተመልሶ ግድግዳው ላይ ይለጠፋል። አንድ ብርድ ልብስ፣ በጥግ በኩል ለመቀመጫ የሚሆን አንድ የሲሚንቶ ብሎኬት፣ አንድ መጥረጊያ፣ አንድ ኩባያ፣ አንድ የአንጨት ማንኪያ ከከፍሉ አውጥቶ ለማራገፍና መጠቀም ሲያስፈልግ ደግሞ ወደ ውስጥ ለመጎተት በሚያስችል ዘዴ ባለ ረጅም ሰንሰለት አንድ ባልዲ ይገኛል። የከፍሉ ከፍታ ዘጠኝ ሜማ ነው፣ ኮርኒሱ የተሠራው

t.me/OLDBOOKSPDF

ውፍረታቸው የአውቶሞቢል ሻሲ በሚያካክል አግዳሚ ብረቶች ሲሆን፣ በጣም ከመጠጋጋታቸው የተነሣ አነስተኛ መጠን ያለው ኧንኳ በውስጣቸው አይሾልከም። ከዚያ በላይ ከመሬት በግምት በሐያ ሁለት ጫማ ከፍታ ላይ የራሱ የሕንፃው ጣሪያ ይገኛል። ሁለት ዘበኞች ሲገናኙ እየቆሙና እርምጃዎቻቸውን በማስተካከል ወደኋላ እየተመለሱ፣ ከአንዱ ዳር ወደሌላው ዳር ወደፊትና ወደኋላ የሚዘዋወሩበት ስፋቱ እንድ ያርድ የሆነና የብረት አግዳሚ ያለው መረማመጃ ሰገነት ከጣሪያው በላይ ተዘርግቷል። ከላይ በኩል አንድ ትንሽ መብራት አለ። በጣሪያው ሥር ግን፣ በጠራራ ፀሐይ እንኳ ማየት አይቻልም። አልጋችንን የምናወርድበትን የፊሽካ ትዕዛዝ በመጠባበቅ ወዲያ ወዲህ ማለት ጀመርኩ። አነስተኛዋን የኮሽታ ድምፅ ለማስወገድ ሲባል ዘበኞቹም ሆኑ እሥረኞቹ የሚያደርጉት ነጠላ ጫማ ነበር። ራሴን እንደዚህ አልኩት። «ሻርዬ ያለኸው እዚህ ቁጥር 234 ውስጥ ነው። ወደ ማበድ ደረጃ ሳትደርስ ሁለቱን ዓመታት ለማለፍ ሞክር። ይህም ሰባት መቶ ሠላሳ ቀን መሆኑ ነው። ለዚያ ወህኒ ቤት 'ሰው በላ' የሚል ተቀጽላ መሰጠቱ ውሸት ላለመሆኑ ራስህ ድረስበት።»

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት እዞራለሁ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት እዞራለሁ። ዘበኛው ልክ ከአኔ ጣሪያ በላይ አለፈ። ሲመጣ አልሰማሁትም። ድንገት ነበር በዚያ የመጣው። መብራት በራ። ግን የተንጠለጠለው ከጣሪያ በላይ በሐያ ጫማ ከፍ ብሎ ነበር። መረማመጃው ሰገነትም በርቶ ነበር፣ ከፍሎቹ ግን እንደጨለመ ቀሩ። እራመዳለሁ። እናንተ ወደዚህ ቦታ እንድመጣ የፈረዳችሁበኝ ቡድኖች በሰላም ተኙ፣ በእርግጥ ያደረጋችሁትን አውቃችሁት ቢሆን ኖሮ ጎትታችሁ ትመልሱኝ እንደነበረ ያለጥርጥር ስለማውቅ በሰላም ተኙ። በሐሳቤ ለመበረር እንኳ ችግር አየገጠመኝ ነበር። እንዲያውም አልቻልኩም። ለማፈን ከመሞከር ይልቀ እምብዛም በማይደብሩ ነገሮች ማተኮሩን መረጥኩ።

አልጋዎቻችንን መዘርጋት እንደምንችል አንድ የፊሽካ ጭርርታ አበሰረን። ሰከለስ ያለ ሌላ ድምፅ፣ «ለእዲሱቹ ሰዎች - ካስፈለጋችሁ አሁኑኑ አልጋችሁን እውርዳችሁ ለመተኛት ትችላላችሁ» አለ።

« ... ካስፈለጋችሁ» ብሏል። ስለዚህ መራመዴን ቀጠልኩ፣ ላለመተኛት ጥንቃቄ ማድረግ ነበረብኝ። ከዚህ ወጥመድ ጋር መለማመድ ይኖርብኛል። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት ወዲያው የሰዓት ደውሉን ቅኝት ተለማመድኩት። ራሴን አቀርቅሬ፣ እጅቼን ከጀርባዬ ኋላ አቆላልፌ፣ የእርምጃዎቼን ርዝመት ትከከል በመመጠን ያለማዛባት ወደኋላና ወደፊት እንጎራደዳለሁ። ልክ በእንቅልፍ ልብ እንደ መራመድ ያህል ነበር። መጨረሻ ወይም መጀመሪያ በሌለው በዚህ ማራቶን ውስጥ በየአምስቶቹ እርምጃዎች መጨረሻ ስታጠፍ ከመታከክ በስተቀር ግድግዳውን እንኳ አላየውም ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

በእርግጥም ነው ፓፒ፡ ይህ እስር ቤት «ሰው በላ» የተባለው ቀልድ አይደለም።

የዘበኛው ጥላ በግድዳው ላይ ሲያርፍ መመልከት ራሱ እንግዳ ስሜት ያላድርብሃል። እርሱን ለመመልከት ራስሆን ቀና ካደረግክ ደግሞ ከዚያ የባሰ ነበር። ልክ አዳኙ ይዞት በጉድጓዱ ውስጥ እንደሚጠብቀው ግሥላ ዓይነት ስሜት ይሰማሃል። ያን አስከፊ ስሜት ለመለማመድ ብዙ ወራቶች ፈጅቶብኛል።

እንድ ዓመት ሦስት መቶ ስድሳ አምስት ቀኖች ይሆናሉ፣ ሁለት ዓመት ደግሞ ጸጉሜ አንድ ቀን ካልተጨመረች፣ ሰባት መቶ ሠላሳ ቀኖች ይሆናሉ። በአስተሳሰቤ ፈገግ አልኩ። አንድ ቀን ቢጨመር አስከዘሀ ቁም ነገር አልነበረም። ባይሆንም ገሃነም ይግባ! አንድ ቀን መጨመር፣ ሐያ አራት ሰዓት መጨመር ነው። ሐያ አራት ሰዓት ደግሞ ረጅም ጊዜ ነው። ሰባት መቶ ሠላሳ ቀኖች እያንዳንዱ ቀን በሐያ አራት ሰዓት ሲበዛ አንድ መዓት ቁልል ይሆናል። እነዚህስ ሰንት ሰዓቶች ይሆናሉ? በጭንቅላቴ ላሰላቸው እችላለሁ? አይሆንም። አልችልም። የማይሞከር ነው። ለምን? እንዴታ! ይቻላል አንጂ። እስኪ እናስበው። አንድ መቶ ቀኖች፣ ሁለት ሺ አራት መቶ ሰዓቶች መሆናቸው ነው። በስባት ሲባዛ ደግሞ በጣም ቀላል ነው፡ ዐሥራ ስድስት ሺ ስምንት መቶ ሰዓቶች ይሆናሉ፣ በተጨማሪ የቀሩት ሠላሳ ቀኖች ደግሞ በሐያ አራት ሲባዙ፣ ሰባት መቶ ሐያ ሰዓቶች ይሆናሉ። በጠቅላላው ዐሥራ ስድስት ሺ ስምንት መቶ፡ ሲደመር ሰባት መቶ ሐያ፡ ባልሳሳት፡ ዐሥራ ሰባት ሺ አምስት መቶ ሐያ ሰዓቶች ይሆናሉ። ወዳጄ ሚስተር ፓፒዮ፣ በተለይ ለአውሬዎች በተቀየሰው በዚህ የግንብ ወጥመድ ውስጥ የምታጡዋቸው ዐሥራ ሰባት ሺ አምስት መቶ ሐያ ሰዓቶች ይጠበቁሃል። ለመሆኑ ደቂቃዎቹስ ሰንት ይሆናሉ? ምን አስጨነቀኝ! የሰዓቶቹ አንድ ነገር ነው ደቂቃዎቹ ግን? ደቂቃዎቹስ ገሃነም ይግቡ። ለምን ሴኮንዶቹ አይሆኑም? ምን ያስቸግራሉ? የሚያስቸግሩኝማ፡ ... ከኋላዬ፡ ከግራና ከቀኜ ያሉት እነማን እንደሆኑ ደንቆኛል። እነዚያ ከፍሎችም የተያዙ ከሆነ፣ እነርሱ ውስጥ ያሉት ሰዎች በቁጥር 234 ውስጥ የገባው ማን ይሆን ብለው መደነቅ አለባቸው።

አንድ ድምፅ የሌለው ነገር ወደ ከፍሌ ውስጥ ሲወድቅ ሰማሁ። ምን መሆን ይችላል? ጎረቤቴ ቀልጣፋ ሆኖ በፍርግርጉ በኩል አንድ ነገር መወርወር ይችላል? ምን እንደሆነ ለማወቅ ሞከርኩ። ረጅምና ቀጭን የሆነ አንድ ነገር መለየት ቻልኩ። ከዚያም ሰማንሳት በመዘጋጀት ላይ እንዳለሁ፣ ነገሩ ወደ ግድግዳው አቅጣጫ መንቀሳቀስ ጀመረ። ወደ ኋላ ዘለልኩ። ወደ ግድግዳው ደርሶ ወደ ላይ ለመንጠላጠል ሲሞክር ወደ መሬት ተመልሶ ወደቀ። ግድግዳው በጣም ከመለስለሱ የተነሣ ሊቆነጥጥ አልቻለም። ሦስት ጊዜ ሲሞክር ጠበቅኩትና በአራተኛው ሙከራ ሲወድቅ፡ በእግሬ ጨፈለቅኩት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ይለሰልስ ነበር። ምን ሊሆን ይችላል? የቻልኩትን ያህል አጣርቼ ለማየት በጉልበቴ በርከክ ስል፣ ርዝመቱ ከሰምንት ኢንች በላይ፡ ስፋቱ ከሁለት ወፍራም ጣቶች የበለጣ አንድ ግዙፍ ባለ መቶ እግር ትል መሆኑን ለማወቅ ቻልኩ። በጣም ቁፋፌ ስለነበር፡ እንሥቼ ወደ ባልዲው ለመወርወር ራሴን ማስጠጋት አቃተኝ። ነገ በቀን ብርሃን ስለ ሁኔታው አንድ ነገር እደርጋለሁ። ብዛት ያላቸው ባለ መቶ እግር ትሎች ልመለክት ነው። ከላይኛው ጣሪያ ይወድቃሉ። በምተኛበት ጊዜ ራቁቴን እንደሆንኩ በሰውነቴ ላይ ሲረማመዱ፣ ሳልረብሻቸው መቆየቱን ተለማመድኩት። ብሳሳት ምን እደጋ እንደሚያስከትልብኝ ተምሬያለሁ። በቀፋፊው ትል አንድ ጊዜ መነደፍ ለሰድስት ሰዓት የሥቃይ ቃጠሎና ለዐሥራ ሁለት ሰዓት ኃይለኛ ትኩሳትን ማትረፍ ነበር።

ይሁንና አንድ የሐሳብ መከፊያ ሆነኝ። በምነቃበት ወቅት አንድ መቶ እግር ትል ከወደቀ፣ በመጥረጊያ አሰቃየዋለሁ፣ ወይም ከአኔ እንዲደበቅ አፈቅድለትና ከተሸሸገ በኋላ እገባበት ጉብቼ አገኘዋለሁ።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት ... ረጭ ያለ ፀጥታ! እዚህ ማንም ሰው አያንኮራፋም? ማንም ሰው አይሰልም? መቅቱ የሚያፍን ነበር። ቀንማ ገሃነመ እሳት መሆን አለበት! ከባለ መቶ እግር ትሎች ጋር ለመኖር የታደልኩ ይመስላል። በሣንታ ማርታ ጨለማ ማንብ ውስጥ ውሃው ሲነሣ በጣም ብዙ ሆነው ይመጣሉ። ግን ትናንሾች ነበሩ። ይሁንና ተመሳሳይ ዝርያዎች ናቸው። በሣንታ ማርታ በየቀኑ ሳርፍ ይመጣብናል። ሆኖም ሊለው ቢቀር ማውራት እንችላለን፣ መርዝህ፣ ማቀንቀን፣ ወይም ዕብድ ለመሆን የተታረበት ሲያላገኙ ይሰማል። ተመሳሳይ አልነበረም። መምረጥ ቢቻል ሣንታ ማርታን በመረጥኩ። አብደሃል እንዴ ፓፒዮ። እዚያ አንድ ሰው ለመቆየት የሚችለው ስድስት ወር መሆኑን ሁሉም በአንድ ድምፅ የተስማማበት ሐሳብ ነበር። እዚህ አራትና አምስት ዓመት እንዲያውም የበለጠ የሚቆዩ ብዙ ናቸው። ቅጣቱን በአንድ ሰው ለይ መፍረድ አንድ ነገር ነው፣ ቅጣቱን መቀበል ደግሞ ፍጹም ሌላ ነገር ነው። ሰንቶቹ ናቸው ራሳቸውን የገደሉት? እንደዚህ ማድረግ እንኳ በምንም መንገድ አይታየኝም። እሺ፡ ላድርገው። ቀላል ላይሆን ይችላል፣ ሆኖም ከሱሪህ ቀድደህ እንድ ገመድ መፍተልና አንዱን ጫፍ ከመጥረጊያው ላይ መቋጠር ነው። ከዚያም አልጋህ ላይ በመቆም ከጣሪያው አግዳሚ ብረት በአንደኛው ውስጥ ገመዱን ማሹለክ ትችላለህ። ግድግዳው ጋር ልጥፍ ካደረግው ዘበኛው ገመዱን ላያየው ይችላል። ከዚያም ቶሎ እርሱ አልፍ እንዳለ ራስህን ማሰናበት ነው። ተመልሶ ወደዚያ አካባቢ ሲመጣ ሞተሃል። ከዚህም ሌላ ከተሰቀልክበት ለማውረድ ወደ ከፍልህ መምጣት ብዙም የሚያስቸኩለው አይደለም። የከፍሉን መዝጊያ እንዴት አድርጎ መክፈት ይችላል? አይችልም። መዝጊያው ላይ፣ «ልዩ ፈቃድ ሳታገኝ ይህን መዝጊያ አትክፈት» ይላል። ስለዚህ ምንም የሚያሰብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር የለም። ራሱን ለመግደል የሚፈልግ ማንም ሰው፣ «ልዩ ፈቃድ» የሚለው ግዳጅ አስከሚነሣ ሰፊ ጊዜ አለው።

ግር ግር ለማለውዱ ሰዎች ይህ ብዙ ላይጥማቸው ይችል ይሆናል። ከሰለቻችሁ፣ እነዚህን ገጾች ልትዘሏቸው ትችላላችሁ። ይሁን እንጂ በአዲሷ ከፍሌ የመጀመሪያውን ስሜቴንና እነዚያን የተቀበርኩባቸውን የመጀመሪያዎቹን ሰዓቶች ትዝታ በተቻለ መጠን በታማኝነት ለመግለጽ ሕሊናዬ ያስገድደኛል።

ለረጅም ጊዜ እየተራመደኩ ነበር። ወደ ሌሊቱ አጋማሽ ጆሮዎቼ አንድ ጉርምርምታ ሰማጡ። የዘበኛ መቀያየሪያ ወቅት ነበር። የመጀመሪያው ዘበኛ ረጅምና አጥንቱ የገጠጠ ሲሆን፣ አዲሱ ደግሞ አጭርና ወፍራም ነበር። ነጠላ ጫማዎቹን አጠለቀ። ከእኔ ፊት ለፊት ባሉት በሁለቱ ከፍሎችና ከኋላ ባሉት ሁለቱ ከፍሎች መሀል ሲራመድ መስማት ችያለሁ። እንደ ባልደረባው ዝምተኛ አልነበረም። መራመዴን ቀጠልኩ። ጊዜው ገፍቶ መሆን ይኖርበታል። ስንት ሰዓት ይሆን? ገረሞኛል። በስሜት የምረዳበት አንድ ዓይነት ሰዓት ነገ ይኖረኛል። አንድ አማካይ ማምት ለማግኘት፣ በመጓጊያየ መካከል ያለችውን ቁዳዳ በቀን አራት ጊዜ እከፍታለሁ። ሌሊት ደግሞ የመጀመሪያው ዘበኛ ለጥበቃ የሚመጣበትን ወውቅና፣ በሚቆይበት የጥበቃ ሰዓት ርዝመት ሁለተኛው ሲመጣ ጊዜው ምን ያህል እንደሆን መገመት እችላለሁ፣ ከዚያም ምስተኛና እንደዚያው አያለ ይቀጥላል።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት ... መጨረሻ የሌለውን አርምጃዬን ወዲያው ቀጠልኩና፣ ድካም ሰለተሰማኝ በትዝታ መብረር ያዝኩ፣ የከፍሌን ጨለማ ሰመቋቋም፣ በጣ ያለ የቀን ብርሃን ባለበት ባሕር ዳር አሸዋ ላይ ከጓጅራ ጎሣዎቼ ጋር ተቀመጥኩ። ከባሕሩ ዳር በግምት ሁለት መቶ ያርድ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ፣ ላሊ በምታጠምድባት ጀልባ ላይ ደፋ ቀና ትላለች። እግሮቼን በአሸዋው ውስጥ ቀበርኳቸው። ዞራይማ በከሰል ላይ የተጠበሰ አንድ ትልቅ ዓሣ፣ ትኩሰነቱ እንዳይበርድ በሙዝ ቅጠል ጠቅልላ አምጥታልኛለች። በጣቶቼ እያነሳሁ ስበላ፣ ዞራይማ ባቶቿን አቆላልፋ ከፊት ለፊቴ በመቀመጥ ትመለከተኛለች። ትላልቆቹ ጉርማጅሮ በጥራት ከዓሣው አጥንት ሲለያዩና ጣዕሙ የቱን ያህል እንዳረካኝ በፊቴ ላይ ስታነብ በጣም ደስ ይላት ነበር።

ከከፍሌ በጣም ርቄያለሁ። ስለ ግዞት ወህኒ ቤት፣ ወይም ቅዱስ የሴፍ ወይም ሌሎቹ ደሴቶች አይሰማኝም። ወደ ባሕሩ ጠርዝ ተንከባለልኩና በጣም ከመለሰለሱ የተነሣ ዳቄት በሚመስለው የኮራል-አሸዋ እጆቼን በመፈግፈግ አጸዳሁ። ከዚያም የተነሣ ዳቄት በሚመስለው የኮራል-አሸዋ እጆቼን በመፈግፈግ አጸዳሁ። ከዚያም በግራም ሁኔታ ንጹሕ በሆነው የጨው ውሃ አፌን ለመጉመጥመጥ ወደ ባሕሩ ገባሁ። ውሃውን በእጆቼ አፍስ አደረኩና በፊቴ ላይ ረጨሁት። አንጉቴን በምፈገፍግበት ወቅት

t.me/OLDBOOKSPDF

ጸጉሬ በጣም ረጅም ሆኖ እንዳደገ ተረዳሁ። ላሊ ስትመለስ እንድትቆርጥልኝ እነግራታለሁ። ሙሉውን ሌሊት ከጎሰዎቹ ጋር አሳለፍኩ። የዞራይማን የሚርቁ ሽርጥ አወለቅኩና በጠራራ ቀን የባሕሩ ለስላሳ እየር እየነፈሰብን፣ እዚያው አሸዋው ላይ ተጋናኝታት። ልዩ የሆነ ደስታ ሲሰማት፣ ዘወትር እንደምታደርገው ሁሉ በፍቅር፣ ተመስጣ አቃሰተች። ምናልባት ይሆን የፍቅር ሙዚቃ ነፋስ ተሸክሞ ለላሊ አድርሶላት ይሆናል። ምናልባትም በፍቅር ጨዋታ ላይ መሆናችንን ዐውቃ ይሆናል። አዎ፣ አይታን መሆን አለበት፣ ምክንያቱም ጀልባዋ ወደ ባሕሩ ዳር እየተመለሰች ነበር። ፈገግታ አያሳየች ወረደች። የረጠበ ጸጉሯን ፈታችና ከወዲያ ወዲህ አያወናጨፈች፣ በደማቁ ፀሐይ ለማድረቅ አለንጋ በመሰሉ ጣቶቿ ታፍታታቸው ጀመር። አርሷ ወዳለችበት ሔድኩ። ቀኝ እጇን በወገቤ ዙሪያ ጠመጠመችና ከባሕሩ ዳር ወደ ጎጇችን እቅጣጫ እየሳበች ወሰደችኝ። በምንራመድበት ወቅት ምን እንደምታሰላስል ግልጽ ነበር። «ለኔስ ለምን ይቅርብኝ?» ነው። አቤት ውስጥ በታጠፈው ተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋ ላይ፣ ተቃቅፈን ተኛን። የፍቅር ጭውውታችንን እንደ ጨረስን ዞራይማ መጣች። ራቁታችንን አልጋው ላይ ተጋድመናል። ከጎናችን ቁጭ አለችና የአህቷን ጉንጭ በጣቷቿ በሙነንተል፣ «ስማብማቢ» እንደማለት መሆን አለበት፣ አንድ ቃል ደጋግማ ታነበንባለች። ከዚያም ትሕትና በተመላበት አክብሮት የአኔንና የላሊን ሜርቀዎች አስተካከለችልን። ለእንቅልፍ አንድ ጊዜም ወይኔን ሳልጨፍን ሌሊቱን በጓጅራ ውስጥ አሳለፍኩት። ጋደም እንኳ አላልኩም። ከሰድስት ወር በፊት ኖሬበት ከነበረው ወደ አንደኛው ጣፋጭ ቀን ራሴን አጓጉዤ፣ በድን በመሆን አርምጃዬን ቀጠልኩ። መበራቱ ጠፉና አካባቢዬ የነበረውን ጭጋግ አያባረረ፣ የማለዳ ብርሃን ሲፈነጥቅ ለማየት ቻልኩ። ከዚያም የፊሽካው ድምፅና የጣውላ አልጋዎች ከግድግዳው ጋር መላተም ቀጠለ። ጎረቤቴ እንኳ ሜንጠውን ከቀለበቱ ጋር ሲያቆላልፍ ሰማሁት። ሳለና ከዚያም የውሃ ድምፅ ሰማሁ። እዚህ ቦታ እንዴት ትታጠባለህ?

«ዘበኛ፣ እባክህ እዚህ ቦታ እንዴት ነው የምንታጠበው?»

«አዲስ ስለሆንክ ይቅርታ አድርጌልሃለሁ። ግን አስታውስ፣ ከዘበኛ ጋር መነጋገር ያስቀጣሃል። ለመታጠብ ከባልዲው በላይ ቁምና በእንድ እጅህ ከማንቆርቆሪያው ውሃ እየቀዳህ በሌላው ታጠብ። ብርድ ልብስህን አልዘረጋህም እንዴ?»

«አልዘረጋሁም።»

«በውስጡ አንድ ፎጣ ታገኛለህ»

ምን ማለት ነው! ከዘበኛ ጋር እንኳ መነጋገር አትችልም፣ በሕመም ላይ ብትሆን እንኳ፣ ትን ቢልህ፣ የልብ ድካም ወይም ትርፍ አንጀት ቢኖርህ፣ ወይም አስም

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢያፍንህ፣ የሞት ሽረት ትግል ቢደርስብህ እንኳ ለእርዳታ መጥራት አትችልም ማለት ነው? የማይታመን ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እስከዚህ የማይታመን አይደለም። ለመቋቋም አቅቶህ መጨረሻ ነጥብ ላይ ስትደርስ፣ እንድ ማበሳጫ መፍጠሩ በጥም ቀላል ይሆናል። «ወደፊት ግፋበትና ታፍነህ ሙት፣ ግን ዝም በል» የሚል እንኳ ቢሆን እንድ ሰው አይጠፋም፣ ግን እዚህ ካሉት ሁለት መቶ ሃምሳ ምስኪን ምናምንቴዎች ውስጥ ሊቋቋመው ያልቻለውን ኃይለኛ ግፊት ለማስተንፈስ እንድ ሰው እንደሚነሣሣ እርግጠኛ ነበርኩ።

እነዚህን ወጥመዶች የዘረጋው የሥነ አእምሮ ሊቅ አይሆንም፣ ራሱን እስከዚህ የሚያቃልል ዶክተርም አይኖርም። በእርግጥም ለሕጎቹ በኃላፊነት የሚጠየቅ ዶክተር የለም። ተጠያቂዎቹ ይህን ቦታ የቀየሱት፣ የቅጣቱን ደንብ ያረቀቁት፣ በማሰቃየት ሱስ የተጠመዱት፣ በጭካኔ የተሞሉትና ከፍተኛ የኢሥረኛ ጥላቻ የተጠናወታቸው አረመኔዎች፣ ሁለቱ ማለት መሐንዲሱና ቢሮክራቱ መሆን አለባቸው።

ጥልቅ ከሆኑት፣ በቦሲየና በካየን ጨለማ ግንቦች ውስጥ በኢሥረኞች ላይ የሚፈጸሙት ሰቆቃዎችና መከራዎች፣ እንደ ገደል ማሚቶ እያስተጋቡ ወደ ሕዝብ ጆሮ የሚደርሱበት ዕድል ይኖር ይሆናል። ለዚህም ማረጋገጫው የእጆቹን ካቴናዎችና የጣት ማጣበቂያዎች ሲፈቱልኝ፣ ዘበኞች ፊቶች ላይ የሚነበበው እውነተኛ የፍርሃት ስሜት ነው።

እዚህ ወህኒ ቤት ግን፣ ምን እንደሚካሔድ የሚያውቁት የአስተዳደሩ ባለሥልጣኖች ብቻ ናቸውና ሰላም አላቸው።

ሲጥ፣ ሲጥ፣ ሲጢጥ አሉና የየከፍሉ ራካዎች በሙሉ ተከፈቱ። እኔም ወደ ራሴዋ ቀረብ አልኩና ለማጮለቅ ደፈርኩ፣ ከዚያም ግንባሬን ትንሽ ብቅ አደረግኩና በመጨረሻም ጭንቅላቴን በሙሉ ወደ ውጭ አዘለቅኩት። በግራና በቀኜ በጣም ቁጣቸው የበዛ ጭንቅላቶች ነበሩ። ቀዳዳዋ ወዲያው እንደተከፈተች ልክ እኔ እንዳደረግኩት ሁሉም ሰው ማድረጉ ግልጽ ነበር። በስተቀኜ በኩል ያለው አንደኛው መልዕክት አልባ በሆነ የቀዘዘ አስተያየት ይመለከተኛል። ድፍን ያለው አስቀያሚ ፊቱ ዝሎ በላብ ፣ዘፍቋል። በስተቀኝ ያለው ሌላው ደግሞ በችኮላ፣ «ምን ያህል?» ሲል ጠየቀኝ።

«ሁለት ዓመት»

«የእኔ አራት ነው። እንዱን ጨርሻለሁ። ስምህ ማነው?»

«ፓፒዮ»

«የእኔ ጆርጅ ነው። ሉውቬርኛው ጆርጅ የት ቦታ ነው ያገኙህ?»

«ፓሪስ። እንተንስ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

መልስ ለመስጠት ጊዜ አላገኘም። ቡናና ዳቦ የተሸከሙት ዘበኞች ከእኔ በሁለት ከፍሎች ርቀት ላይ ነበሩ። ጭንቅላቱን ወደ ውስጥ መለሰ። እኔም እንደዚያው አደረግኩ። ኩባያየን ብቅ አድርጌ ያዝኩና ቡና ሞሉልኝ፣ ከዚያም ዳቦውን ሰጡኝ። ግን በጣም ፈጠን ባለማለቴ ቀዳዳዋን በመዝጋት ላይ እንዳሉ ዳቦው ወለሉ ላይ ተንከባለለብኝ። ዐሥራ አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ፀጥታው ተመለሰ። ቀትር ሲሆን ከእንዲት ቁራጭ ሥጋ ጋር ሾርባ ተሰጠን። ማታ ደግሞ አንድ ሣህን ምሥር መጣ። ለሁለት ዓመት ምግቡ የሚለዋወጠው ማታ ብቻ ነበር። ምሥር፣ ፎሶሊያ፣ የአተር ክክ፣ ሽምብራ፣ እደንጋሬ፣ ሩዝ በቅባት የቀትሩ የዘወትር ምግቦች ነበሩ።

በየሁለት ሣምንቱ ጭንቅላቶቻችንን ወደ ውጭ ብቅ አናደርግና አንድ አሥረኛ ቡንዶስ ጺማችንን ይሸልትልናል።

እዚህ ከመጣሁ ሦስት ቀን ሆነኝ። መጨነቅ ጀመርኩ። ምግብና ትምባሆ እንደሚልኩልኝ ጓደኞቼ ሮያሌ እንዳለሁ ነግረውኝ ነበር። ነና ምንም ነገር አልደረሰኝም፣ ከዚህም በላይ እንደዚህ የመሰለው ተአምር እንዴት ሊሆን እንደሚችልም አልታየኝም። ምንም ነገር ለምን አልደረሰኝም ብዬ አልደነቅም። ሲጃራዎቹ እስከዚህ አላሳቢ አይደሉም። ማጨስም አደገኛ ይሆናል፣ ከዚህም በተጨማሪ የቅንጦት ዕቃዎች ናቸው። ምግቡ ግን አስፈላጊ ነበር። የቀትሩ ሾርባ፣ ሁለት ወይም ሦስት ጎመኖች ላይ ላዩን የሚንሣፈፉበትና ምናልባት አራት አውንስ የሚመዝኑ ትናንሽ ቁራጭ ሥጋዎች ያሉበት ሙቅ ውሃ ነው። ማታ ደግሞ ትንሽ የአተር ክኮች ወይም ባቄላዎች የሚዋኙበት አንድ ጭልፋ ሙሉ ውሀ ይሰጠናል። ምግቡን አያዘጋጁ የሚያከፋፍሉትን እሥረኞች እንጂ አስተዳደሩ ተገቢውን ራሽን አልሰጠንም ብዬ አስከዚህም አልጠረጠርኩም። ይህ ሊገለጽልኝ የቻለበት ምክንያት አንድ ሰሞን ማታ ከማርሲይ የመጣ አንድ ደቃቃ ሰው፣ ጎመኖቹን እየገላለጠ ጭልፋውን ወደ ብረት ድስቱ ሥር በቀጥታ በመስደድ ከውሃ ይልቅ ባቄላዎች የበዙበት ሾርባ ስለጨለፈልኝ ነበር። ሌሎቹ ልክ ተቃራኒውን ያደርጋሉ። ትንሽ ያማስሉና ከዚያም ከላይ በኩል ውሃውን ጨልፈው ያወጣሉ። መዓት ውሃ ትንሽ ባቄላዎች። ይህ ያልተመጣጠነ ምግብ በጣም አደገኛ ነበር። ሞራልህን ለመጠበቅ በተወሰነ ደረጃ የአካል ጥንካሬ አስፈላጊ ነው።

መተላለፊያውን በመጥረግ ላይ ነበሩ፣ ከእኔ ከፍል ውጭ ለረጅም ጊዜ ሲጠርጉ የቆዩ መሰለኝ። መጥረጊያው ከመገጊያየ ጋር መፋተጉን ቀጠለ። ትኩር ብዬ ስመለከት አንዲት ነጭ ወረቀት ወደ ውስጥ ስትገፋ አየሁ። አንድ ሰው በመገጊያው ሥር አንድ ነገር ሊያቀብለኝ እየሞከረ ከዚያ ይበልጥ አርቆ ለመግፋት አቅቶታል። ከመሐሉ በፊት አስካነሣት ድረስ እየጠበቀኝ ነበር። ወደ አርሷ ጎንበስ አልኩና በፎሰፈረሰንት ቀለም የተጻፈች አንዲት ማስታወሻ ገለጥኩ። ዘበኛው አግድም

t.me/OLDBOOKSPDF

አስኪያልፍልኝ ጠበቁ አነበብኳት።

«ፓፒ፣ ከነገ ጀምሮ አምስት ሲኝራዎችና አንድ ኮከንት በየቀኑ ባልዲው ውስጥ ታገኛለህ። ለመርካት ከፈለግክ ኮከኑን በሚገባ አኝከው፣ ከዚያም ጭማቂውን ዋጠው። ጧት ባልዲዎቹን በሚያራግፉበት ጊዜ ወይም በቀጥታ ከቱትር በኋላና ማታ በአራት ጊዜ አጭስ፣ ግን ከጧት ቡና በኋላ ፍጹም እንዳይሆን። አንድ እርሳስና ቁራጭ ወረቀት እዚህ አበሮ አለልህ። ምኞዚም አንድ ነገር ካስፈለገህ፣ ጻፍና ሲውዬው ከከፍልህ ውጭ ስጠርግ በጣቶችህ መዝጊያውን ቧጥጥ። መልሶ ከቧጠጠ ወረቀቷን አሹልከለት። መልሶ ከመቧጠጡ አስቀድመኒ ምንጊዜም ወረቀቷን እንዳትሰጥ። ወረቀቷን ከጀርህ ኋላ ደብቃት፣ ስለሆነም በገንዘብ መደበቂያ ቱቦህ መጠቀም አያሻህም፣ እርሳሱንም ከግድግዳው ሥር አንድ ቦታ አስቀምጠው። በርታ ፍቅሬችንን ልከንልሃል። ኢኖስና ሱዊ።

መልዕክቱ ከጋልጋኒና ዴጋ ነበር። አንድ አስደሳች ስሜት በጉሮሮዬ እየዳኸ አሸቅቦ ወጣ። እንደዚህ የመሰሉ ታማኝና ራሳቸውን የሚሠዉ ጓደኞች ማግኘት በጣም የሚያምቅ ነገር ነበር። ከዚህ መቃበር ቦታ በሕይወት እወጣለሁ የሚል ቁርጠኝነትና ታላቅ እምነት ስላደረብኝ እርምጃዬን በደስታና በንቃት መንፈስ ቀጠልኩ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ... በመራመድ ላይ እንዳለሁ፣ እነዚያ ሁለት ሰዎች የቱን ያህል የሚደንቁ እንደሆኑ አሰብኩ። ምናልባትም ሥራቸውን ከማጣት በላይ አደጋ ላይ የሚጥል፣ ይህ ነው የሚባል ፈተና ሊገጥማቸው ይችላል። ምን ዓይነት የሚያስገርም የአከብሮት መግለጫ ነበር። የቱን ያህል ውድ እንደነበረ መዘርዘሩ አያሻም። በሮያሌና በእኔ ከፍል መካከል የደለቧቸው ሰዎች ብዛት!

ደረቅ ኮከነት ብዙ ዘይት ያለበት መሆኑን ማስረዳት ይኖርብኛል፣ ስድስት ኮከኑቸ ፍጭና ጭማቂውን ለብ ባለ ውሃ ዘፍዝፈው፣ በሚቀጥለው ቀን ከላዩ ላይ ሩቡን ጨልፈህ መጠቀም ትችላለህ። ይህ ዘይት በምግባችን ውስጥ ያጠረውን የቅባት ፍላጎት ከማሟላት ሌላ ቫይታሚኖችም ሞልተውታል። በቀን አንድ ኮከነት ለጥሩ ጤንነት ዋስትና ከመሆኑም በላይ፣ በሆድ ድርቀትና በረታብ ምክንያት ከሚመጣ ሞት ይከላከላል።

ከሁለት ወር በላይ ምግብና ሲኝራ ያለማቋረጥ ደረሰኝ። በማጨስበት ወቅት ጢሱን ወደ ውስጥ በጥልቀት እየሳብኩ ከዚያም ቀስ በቀስ በትንሹ ወደ ውጭ በማውጣትና, በቀኝ እጄ ወዲያና ወዲህ በማራገብ ማናቸውንም ዐይነት ጥንቃቄ እወስዳለሁ።

አንድ ቀን አንድ አስቂኝ ነገር ተፈጸመ። ተግቢውን ነገር መሥራት ወይም አለመሥራቴን አላውቅም። ከመዘዋወሪያ ሰንኑቱ በላይ የነበረ አንድ ዘበኛ በአማዳሚው

t.me/OLDBOOKSPDF

ብረት ላይ ሰጥ አለና ቂጄ እኔ ከፍል አሙለቀ። እንድ ሲጃራ አቀጣጥሎ ሁለት ጊዜ ከሳበ በኋላ ወደ ከፍሌ ውስጥ እንድትወድቅ ላከት። በዚያም አርምጃውን ተጠለ። ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ጠበቅኩና ሲጃራዋን በእግሬ ስጨፈላልቃት እንዲያየኝ አደረግኩ። እኔን ለመመልከት ቆም አለና በዚያም እንቅስቃሴውን ቀጠለ። ለእኔ ሐዘን ተሰምቶት ይሆን? ወይስ ማጥመጃ ኖሯል? ስላላወቅኩ አስጨነቀኝ። በመከራ ላይ ስትሆን ለማንኛውም ነገር ከመጠን በላይ ስሜት ይኖርሃል። ይህ ዘበኛ ርኅራኄ ለማሳየት ከሆነ አድራጎቱን በንቀት በመመልከት ላስቀይመው ፈልጌ አልነበረም።

እንዳልኩት ሁሉ እዚህ ከሁለት ወር በላይ ሆኖኛል። ከግቦት ወህኒ ቤቱ ማምለጥ እንደማይቻል ግልጽ ሆኖልኝ ነበር። መደለል፣ መሰባጠር የሚባል ከጥያቄ ውጭ ነበር። ስለዚህ ራሴን ሁለት ቦታ በመከፋፈል ሙሉ በሙሉ አስተማማኝ የሆነ አንድ ዘዴ ፈጠርኩ። በኩስቦች መካከል በመሆርና በሕይወት ዘመኔ ያሳለፍኳቸውን የተለያዩ ሁኔታዎች በማስታወስ ወይም በሚያስደንቅ ሁኔታ ገሃድ የሚመስሉ፣ የሕፃኝ ቤተ መንግሥቶችን በመገንባት በቅድሚያ ራሴን ማድከም ነበረብኝ። ሰሰ አንድም የተለየ ነገር ሳላስብ፣ ምንም ሳልቀመጥና ፍጹም ሳላቋርጥ ሰብዙ ሰዓቶች አራመጻለሁ። አንድ ጊዜ ድቅቅ ብዬ ከደከምኩ በኋላ፣ ብርድ ልብሴን በራሴ ላይ ጠምጥሜ በጣውላ አልጋዬ ላይ እዘረጋለሁ። በዚህ ሁኔታ እንዳለሁ በከፍሌ ውስጥ የነበረው መጠነኛ አየር ጨርሶ ተቋረጠ። ሳንባዬ ታፈነና ጭንቅላቴ መንደድ ጀመረ። በአየር እጥረትና በወበቅ እንደታፈንኩ ድንገት አከንፍ ጀመር። አሀ ምን ዓይነት ሊገልጹት የማይችሉት ስሜት ነበር! ከገሃድ በጣም የላቀ የቁጭር ሊሊት አሰሰፍኩ። አነሆ ከሞላች ወሥራ ሰባት ዓመት ከሆናት እናቴ ጋር ተቀምፀሀ ልሸነረድ እንድመለለላት በረጅሙ ያሳደገችልኝን የተጠቀለለ ጸጉሬን ስትደባብሰኝ፣ እኔ ደግሞ በቀሚሷ እየተሜውትሁ እንደ ሐር የለሰለሰ ገላዋንና አለንጋ የመሰሉ ጣቶቿን እሻሸለሁ። አንድ ቀን በንንሽራሽር ትላልቆቹ ልጆች ሲያደርጉ እንዳየሁት እኔም ወደ ወንዝ ዘልየ ለመዋኘት ባለኝ የየዋህነት ምኞት የሣቀችብኝ፣ ረጋ ያሉት ቃላቶቿ፣ ከብሩህ ወይኖቿ የሚፈልቀው ፍቅሯ፣ ጸጉሯን እንኳ እንዴት እንደምትጠቀልል ወለል ብሎ ታየኝ። «የእኔ ቅልብልብ ወፍ፣ ጥሩ መሆን አለብህ፣ በጣም ጥሩ ልጅ መሆን አለብህ፣ እናትህ ይበልጥ እንድትወድህ። በኋላ ትንሽ ከፍ በምትልበት ጊዜ እንተም እንደነሱ ወደ ወንዝ አየዘለልክ መዋኘት ትችላለህ። አሁን በጣም ትንሽ ነህ የእኔ አለኝታ። ትልቅ ልጅ የምትሆንበት ቀኑ ፈጥኖ ይደርሳል፣ ቶሎ ይደርሳል» ስትለኝ ይሰማኛል።

አጅ ለአጅ እንደተያያዝን ወንዙን ተከትለን ወደ ቤታችን አመራን። የልጅነት ዘመን በቤቱ ውስጥ ገባሁ። አጆቼን በእናቴ ዐይኖች ላይ አድርጊያቸዋለሁ ስለዚህ የመዚታውን ኖታ ሳትመለከት ቺያኖ ትጫወት ነበር ከቺያኖው ኩርሲ ኋላ ባለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ወንበር ላይ ቆሚ ማየት አንዳትችል በትላልቁቹ ዐይኖቿ ላይ ትንንሽ እጆቹን ማጣበቂ እውን አንጂ ሀልም አይመስልም። «ደስተኛዋ ጋለሞታ» የሚለውን የሙዚቃ ቅኝት እስከ መጨረሻው ተጫውታ እስከትጨርስ ቀልጣፋዎቹ ጣቶቿ በፒያኖው ላይ መራወጣቸውን ቀጠሉ።

አንተ ጨካኝ ዓታቢ ሕግ፣ አናንተ ወራዳ ፖሊሶች፣ በሐሰት ነጻነትህን የገዘከው አንተ ችጋራም ፖሊዮን፣ በወንጀለኞነቴ ያመናችሁ አናንተ ዐሥራ ሁለት ደደብ ሥዎች፣ የ«ሰው በላው» ወህኒ ቤት ቀንደኛ ቃፊሮች የሆናችሁት የዚህ ግዞት ቤት ዘበኞች፣ በአካልም ሆነ በአእምሮ በምንም አኳኋን፣ በጽጌረዳማ ቀለም ካሸበረቀው አስደሰች ሕልሜ ዙረቶች ልትገቱኝ አትችሉም።

ቀደም ሲል ምን ያህል ጊዜ በብቸኝነት አጠፋለሁ ብዬ በማሰላበት ወቅት በለዓቦች ብቻ መወሰኔ ስሕተተኛ ነበርኩ። በደቂቃዎችም ለመለካት የምችልባቸው ዘዴዎች ነበሩኝ። ለምሳሌ ባልዲዎቹ የሚራገፉት የጧቱ ቡና ከታደለ በማምት ከአንድ ሰዓት በኋላ ነበር። ኮከኑት፣ አምስት ሲጃራዎችና አንዳንድ ጊዜ ማስታወሻዎቹ የሚደርሱኝ፣ የተራገፈው ባልዲ በሚመለስበት ወቅት ነበር። በየጊዜው ሳይሆን አልፎ አልፎ ጊዜውን በደቂቃ አሰላለሁ። ከባድ አልነበረም። አርምጃዎቼን በሴኮንድ አስተካክዬ ስለነበርና ሰውነቴንም ልክ አንደ ሰዓት ስለማሠራ፣ በየአምስቱ አርምጃዎቹ መጨረሻ በአእምሮዬ «አንድ» ብዬ አመዘግባለሁ። ዐሥራ ሁለት ሲደርስ አንድ ደቂቃ አልፏል። ግን የምጨነቅው ስለምጣብ ይሆናል ብላችሁ እንዳታስቡ፣ ሕልውናዬን በኮከኑት አጠብቃለሁ። አያንዳንዷን ሲጃራ ለሁለት ስለምከፍላት በየሐያ አራት ሰዓት ዐሥር ጊዜ አጨሳለሁ። የቡና ጊዜ ሊደርስ ሲል ዘወትር በፍርሃት የምጨበጠው፣ እኔን ለመርዳት ሲሉ ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው የሚገኙት ሰዎች ላይ አንድ ነገር ይደርስ ይሆን በማለት ነበር። አፎይታ ማግኘት የምችለው ኮከኑን በማይበት ጊዜ ብቻ ነበር። ያን ጊዜም ሁሉም ሰላም መሆናቸውን አረጋግጣለሁ።

በዝግታ፣ በጣም በዝግታ፣ ሰዓቶቹም፣ ቀኖቹም፣ ሣምንቶቹም፣ ወሮቹም እያለፉ ሔዱ። እዚህ ከገባሁ አንድ ዓመት ሊሆነኝ ነው። ልክ ዐሥራ አንድ ወር ከሐያ ቀን ድረስ፣ ከዐርባ ሴኮንድ ላልበለጠ ጊዜ፣ ያውም ከመናገር ይልቅ ወደ ማጉመትመት ባዘነበለ ሁኔታ ድምፄን ከማሰማቱ በስተቀር ከማንም ሰው ጋር አልተነጋገርኩም። የብርድ ሕመም ያዘኝና በጣም ያስለኝ ጀመር። የሕክምና ቦታውን ለመጎብኘት ያበቃኛል ብዬ በመገመት መታመሜን አመለከትኩ።

ዶክተሩ መጣ። ቀዳዳዋ ተከፈተችና አንድ ጭንቅላት ብቅ አለ።

«ምን ሆኖለሁ ነው የምትለው? የብርድ ሕመም? ወደ ኋላ ዙርና ሣል።»

ቀልድ ኖሯል? አይደለም፤ ዕውነት ነበር፤ ያለጥርጥር ዕውነት ነበር። ከአንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

አካባቢ አንድ ዶክተር በመመለስ ላይ አንዳለ፣ ከቀዳዳው በሦስት ጫማ ርቀት ላይ ሆኖ ጆሮውን ወደከፍቱ በማስጠጋት ደረቱን እያዳመጠ ሊመረምረን ነበር የመጣው። ከዚያም፣ ሕንድሀን ጥብቅ አድርግና ያዝ› ሲለኝ፣ አደርጋለሁ ብዬ ልጀምር ስዘጋጅ ነበር ከበሬን ለመጠበቅ እንድ ድንገተኛ ስሜት የጫጫኝና፣ «አመሰግናለሁ ዶክተርዬ፣ ብዙ አትቸገር። ይቺ ምንም ዋጋ የለውም» ያልኩት። ሌላው ቢቀር ምርመራውን በጥሞና እንዳልተቀበልኩለት ይወቀው።

«የራስህ ጉዳይ» በምንቸገረኝ አነጋገር መለስልኝና ሔደ። በንዴት ጢ ብዬ አለመፈንዳቴም ዕድለኛ በመሆኔ ነው።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ከዚያም አሥራለሁ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ እንደገና አሥራለሁ። ያለማቋረጥ አራመዳለሁ፣ ባቶቼን ገታትሬ በቁጣ አራመዳለሁ። አንደዚያ የመሰለ ነገር ከደረሰብኝ በኋላ የሆነ ነገር ለመረምረም ፈለግኩ። ምን ይሆናል! ከአግሮቼ ሥር ያለው ሲሚንቶ ብቻ ነበር። ግን የሚረመረሙ ገና ብዙ ነገሮች ነበሩ። ያንን ደነዝ ዶክተር ረመረምኩት። የሴሎች ሥቃይና ጭንቀት የሚያስደስታቸውን ደንታ ቢስ ሰዎች ረመረምኳቸው። በየሁለት ዓመት ከቅዳሰ ማርቲን የሚጓዘው የሰዎች ፉርጎ ወዴት እንደሚሔድና በምንስ ሁኔታ እንደሚገኝ ለማወቅ ደንታ ቢስ የሆኑትንና ምንም ያልተረዱትን የፈረንሣይ ሕዝቦች ረመረምኳቸው። የአንድን ሰው ስም በየጋዜጣው የመጀመሪያው ገጽ ላይ አሰራጭተው፣ ከትንሽ ወራት በኋላ መፈጠሩንም የሚረሱትን ወሬኞች ረመረምኳቸው። በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት የሚፈጸመውን ድርጊት ተናዝዘውላቸውና ሰምተው ምንም ነገር ያላሉትን የካቶሊክ ቄሶች ረመረምኳቸው። በከሳሽና ተከሳሽ መካከል የአነጋገር ሰልትን ከማጣመር በስተቀር ለምንም ነገር የማይጠቅመውን የፍርድ መዋቀራቸንን ረመረምኩት። የሰብአዊ ሙበት አክባሪ ማኅበር፣ «የአንተት መቀንጠሻችሁን አስወግዱ፤ ሰዎችን በጅምላ በማሰቃየት መደሰታችሁን ግቱ! በግለት ድምፁን ባለማንሣቱ ረመረምኩት። በየሁለት ዓመቱ ከሕዝቦቹ ሰማንያ ከመቶው በቅጣት ጎዳና እየወረደ ሲጠፉ አነዚያን ለሥርዓቱ ታላፊ የሆኑትን ያልጠየቀውን ሁሉ ረመረምኩት። ራስን በራስ በመግደል፣ በሕመም፣ በምጣብ ዕጥረት፣ በአቅርሣ፣ በዕብደት፣ በመገርጀፍ ሞት የሚሉትን ዶክተሮች ረመረምኳቸው። በሴሎች በምን፣ በምን ነገሮች ላይ እንደ ረመረምኩ ዝርዝሩን አላውቅም። ከዚህ ድርጊት በኋላ በተለመደው ዓይነት መራመድ አቃተኝ። በእያንዳንዱ እርምጃዬ አንድ ነገር አረመርማለሁ።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት ... የሰዓቶቹ ዝግታ ንዴቴን ቀስ በቀስ አስከነልኝ።

ከዐሥር ቀን በኋላ የግዞት ወህኒ ቤት ቅጣቴን ላጋምስ ነው። የሆድ ቁርጠት

t.me/OLDBOOKSPDF

ሕመሜን ወደ ጎን ትቼ፣ በጥሩ ጤንነት ላይ ስለምገኝ፣ ዋጋ ያለው የክብር ቀን ነበር። አላበድኩም ወይም ወደዚያው አዝማሚያ የሚያደርስ ሁኔታ አይታይብኝም። በሚቀጥለው ዓመት መጨረሻ ላይ በአካልም ሆነ በአእምሮ እንደ ተሟላሁ በሕይወት መውጣቴን እንኳ መኖ በመኖ እርግጠኛ ነበርኩ።

በታፈኑ ድምፆች ጩኸት ተቀሰቀስኩ። «ሚስተር ዱራን፣ እንደ አጥንት ደርቋል፣ እንዴት ላታየው ቻልክ?»

«አላወቅኩም ጌታዬ! የተሰቀለው ከመዘዋወሪያ ሰዓት ሥር በጥግ በኩል ነበር። ፊጽሞ አላየሁትም።»

«ዋጋ የለውም፣ ግን አላየሁትም ማለት ቀልድ ስለሚመስል፣ ማመን አለብህ።»

በስተግራ ያለው ጎቤቴ ራሱን በራሱ አጠፋ። ወደ ውጭ ተሸከመው አወጡት። መዘጊያው ተዘጋ። መዘጊያው የተከፈተውም ሆነ የተዘጋው «ከፍተኛው ባለሥልጣን» በተገኘበት እስከሆነ ድረስ በሕጉ መሠረት ተከናውኗል። /ድምፁን ስለማስታውሰው፣ ዋና የግዞት ወህኒ ቤት አዛዥ ነበር የመጣው።/ በዐሥር ወር ውስጥ በአካባቢዬ ካሉት ሰዎች አምስተኛው ማሽለቡ ነበር።

የዓመት በዓሌን በማክብርበት ቀን በባልዲዬ ውስጥ «ኔሰል» የሚል የንግድ ምልክት ያለበት አንድ ቆርቆሮ ፈሳሽ ወተት አገኘሁ። ውድነቱና እኔ ዘንድ ለመድረስ የተጓዘበት ጎዳና ሲገመገም በጓደኞቼ ዘንድ ዕውነተኛ ኪዛራ ነበር። የመከራን ዘመን ድል ነሥቼ የምደሰትባት ቀን ነበረች። በተጨማሪ፣ እንደተለመደው ሳደርገው የቆየሁትን በረራዬን ለመተው ራሴን ቃል አሰገባሁ። በአካልም ሆነ በአእምሮ በግዞት ወህኒ ቤቱ ውስጥ እቆያለሁ። ከመጣሁ ጀምሮ አንድ ዓመት አልፏል፣ ዕድል ከቀናኝ ለማምለጥ ካ አንደምችል ዓይነት ሆኖ ተሰማኝ። ያለጥርጥር የሚያስተማምን ስለሆነ የምኮራበት ነበር።

ብዙ ጊዜ ያልተለመደ ነገር ነው። ዛሬ ከሰዓት በኋላው ቤት ጠራጊው ከጓደኞቼ የተላከች አንዲት ማስታወሻ ሰጠኝ፣ «በርታ። አንድ ተጨማሪ ዓመት ብቻ። በጥሩ ጤንነት ላይ መሆንህን ዐውቀናል። እኛም እንደዚሁ ደህና ነን። ፍቅራችንን ልከንልሃል። የምትችል ከሆነ፣ ይህን በሰጠህ ሰውዬ አማካይነት አንድ ቃል ላክልን። ሊዊና ኢቫስ።»

ከማስታወሻዋ ጋር በተያያዘችው ትንሽ ቁራጭ ወረቀት፣

«ለማንኛውም ነገር አመሰግናለሁ። ጥንካሬ ይሰማኛል፣ ለእናንተ ምስጋና ይድረሳችሁ፣ ከእሁን ወዲያ ያለው አንድ ዓመት የዚሁ ተመሳሳይ እንደሚሆንልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለከሎሲዎና ማቹሬ ምን የሰማችሁት ወሬ አለ?» ቤት ጠራጊው ተመልሰና

t.me/OLDBOOKSPDF

መዝጊያየን ቧጠጠ። ቁራጯን ወረቀት አሸለኩለትና ወዲያው ተሰወረች። አዘውትሬ እፈጽመዋለሁ በማለት ራሴን ቃል ባስገባሁት መሠረት፣ ሙሉ ቀንና ሌሊቱንም በከፈል በዕውነተኛው ዓለም ውስጥ ቆየሁ። ከአንድ ተጨማሪ ዓመት በኋላ ከደሴቶቹ በአንደኛዋ ላይ እቀመጣለሁ። የትኛው ይሻላል? ሮያሌ ወይስ ቅዱስ ዮሴፍ? ብቻዬን በማውራት፣ በማጨስና የሚቀጥለውን ማምለጤን በማቀድ ሰከርኩ። የሚቀሩኝን ሦስት መዶ ስድላ አምስት ቀናት በሚቀጥለው ቀን በሙሉ ልብ ጀመርኩና፣ ለሚቀጥሉት ስምንት ወሮች ሁሉም በሰላም ተካሔደ። በዘጠነኛው ወር ግን ችግር ተፈጥሮ ነበር። አንድ ቀን ጧት ባልዲዬ በመራገፍ ላይ እንዳለ፣ ኮከነቱንና አምስትን ሲጃራዎች ልከ ወደ ከፍሌ ውስጥ ሲገፋልኝ ሲል ሰውዬው እጅ ከፍንጅ ተያዘ።

ሁኔታው በጣም ከባድ ከመሆኑ የተነሣ በምስኪኑ ሰው ላይ የሚያወርዱበት ድብደባ ግልፅ ነው። በጣዕረ ሞት ላይ እንደሚገኝ ሰው አላዘነ። የመዝጊያየ ቀዳዳ ተከፈተችና ፊቱ ፍም የመሰለ አንድ ዘበኛ፣ «አንተ የውሻ ልጅ፣ አንተም ታገኛታለህ!» ሲል አጓራበኝ።

በምስኪኑ ሰው የፈጸሙበት ሁኔታ አብሽቆኝ ስለነበር፣

«አስኪ አንድ ነገር ሞክር፣ አንተ እበት!» ብዬ እኔም መልሼ ጮህኩበት።

ይህ ሁሉ የተደረገው አንድ ሰዓት ነበር። በግዞት ወህኒ ቤቱ ምክትል አዛዥ የሚመራ አንድ ቡድን እስኪነበኝኝ ድረስ አምስት ሰዓት ፈጀ። ለሐያ ወራት ተዘግቶ የነበረው መዝጊያ ተከፈተ። ኩባያየን በእጄ ጨብጬ ለመደባደብ ተዘጋጀሁና ከከፍሏ ጥግ ሆንኩ። የቻልኩትን ያህል ደህና አድርጌ አቅምሼ፣ እኔም በተቻለ ፍጥነት እንደዘረር ፈልጌያለሁ። ሌላ ዕድል የለም።

«ወደ ውጭ ውጣ!»

«ከፈለጋችሁኝ መጥታችሁ ያዙኝ። ከየአቅጣጫው ተከብቤ ለመደብደብ ወደዚያ አልወጣም። እዚህ የሚነካኝን የመጀመሪያ ሰው ደህና ቡጢ ለማቅመስ ይመቸኛል።»

«ልንመታህ አይደለምኮ ሻሪየ።»

«ምን ዋስትና አለኝ?»

«የእኔ፣ የረዳት አዛዡ ቃልኪዳን»

«የአንተ ዋስትና ምን ፋይዳ አለው?»

«አትሰደበኝ። ይኸ ዋጋ የለውም። የክብር ቃሌን አሰጥሃለሁ፣ አትነካም። በል አሁን ና ውጣ።»

ኩባያየን እንደያዝኩ ነበር።

«ልታስቀምጠው ትችላለህ። የሚያስፈልግህ አይደለም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሺ» ወደ ውጭ ወጣሁና በረዳት የግዙት ቤት አዛጉና በስድስት ዘበኞች ተከብቤ በመተላለፊያው አግድም አቋረጥኩ። ሰማይ መሬቱ ሥራበኝና ከብርሃኑ ማንጸባረቅ የተነሣ ዐይኖቼን ጨፈንኩ። መጀመሪያ ስንመጣ ጉበተንበት ወደነበረው ትንሽ ሕንፃ እንደምንም ብዬ ደረስኩ። «አስተዳደር» የሚል ጽሑፍ ወዳለበት አንድ ክፍል ተመራሁ። አሥራ ሁለት የሚሆኑ ዘበኞች ቆመዋል። በደም የተለወሰ አንድ ሰው በወለሉ ላይ እያቃሰተ ነበር። ግድግዳው ላይ ያለው ሰዓት አምስት ይላል። ስለዚህ ምስኪኑን አራት ሰዓት ሙሉ ሲያሰቃዩት እንደነበር ተገነዘብኩ። ዋናው አዛዥ ምክትሉን በሹ አድርጎ ከጠረጴዛው ኋላ ተቀምጧል።

«ሻሪየ፣ ምግበና ሲጃራ ስታገኝ የነበረው ለምን ያህል ጊዜ ነበር?

«ሰውዬው ቀደም ብሎ አልነገራችሁም እንዴ?»

«የምጠይቅህ እኔ ነኝ።»

«የአለምሮ ሕመም አለብኝ። አላስታውስም።»

«የምን ጉድ እያወራህ ነው?»

«አታውቅም ማለት ነው? ከማጎሪያ ውስጥ ሳይያዝልኝ መቅረቱ ገርሞኛል። የአለምሮ ሕመሙ የያዘኝ ጭንቅላቱ ላይ በደረሰብኝ ድብደባ ነበር።»

ለምሰጠው መልስ መሉ በመሉ ሳልዘጋጅ፣ አዛጉ ወደ አንደኛው ዘበኛ ዘወር አለና፣ «ስለዚህ ጉዳይ አንድ መረጃ እንዳላቸው ወደ ሮያሌ ደውለህ ጠይቅ» አለው።

ስልኩን በመደወል ላይ እንዳለ እንደገና ቀጠለ። «ለምህ ሻሪየ መሆኑንስ በሚገባ ታስታውሳለህ?»

«ይህንንስ አዎ» አልኩና፣ ከዚያም በጣም ፈጠን በማለት ይበልጥ ላምታታው እየተጣደፍኩ «ስሜ ሻሪየ ነው፣ የተወለድኩት በ1906 በአርዲክ ቀበሌ። ቢፓሪስ፣ ሲየን ውስጥ የዕድሜ ልክ አሥራት ተፈርዶብኝ ነበር» አልኩ። ዐይኖቹ እንደ ብይ ፍጥጥ ብለው እንዳሣመንኩት አረጋገጥኩ።

«ዛሬ ጧት በናና ዳቦህን አግኝተህ ነበር?»

«አዎ።»

«ባለፈው ምሽት ምን ዐይነት አትክልት ነበር የተሰጠህ?»

«አላውቀውም።»

«ስለዚህ ብናምንህ ኖሮ በጠቅላላው ማስታወስ አይሆንልኝም ልትል ነበራ?»

«ማናቸውንም ድርጊት አላስታውስም፣ መልክ ግን አለያለሁ። ለምሳሌ እዚህ አንድ ጊዜ የተቀበልከኝ አንተ እንደነበርክ አውቃለሁ። ግን መቼ ብትለኝ አላስታውሰውም።»

«አንግዲያው ቅጣትህን ለመጨረስ ምን ያህል ጊዜ እንደቀረህ ታውቅም

t.me/OLDBOOKSPDF

ማለት ነዋ?»

«የዕድሜ ልክ እሥራቴ? እስከሞት ድረስ ነው ብዬ እገምታለሁ።»

«ሒይደለም፣ አይደለም። የግዞት ቅጣትህን»

«የግዞት ቅጣት አለብኝ እንዴ? ለምን?»

«አሁንስ በጣም በዛ! በማምለጥ ሁለት ዓመት የተቀጣህ መሆንህን አላስታውስም ብለህ ልትነግረኝ እየሞከርክ ነው እንዴ? ይህን አላምንም።»

እዚህ ላይ በእርግጥ የልኩን ነገርኩት «ማምለጥ? እኔ? ሞኝ አይደለሁም። ኃላፊነቴን በትክክል ማከናወን የምችልና ዐዋቂ ሰው ነኝ፣ አምልጩ ከሆነ ወደ ከፍሌ መጥተህ ተመልከት።»

አንድ ዘበኛ አቋረጠንና፣ «ሮያሌ በመስመር ላይ ነው አዛዥ» አለ። ስልኩን አነሣ። «ምንም ነገር የለም? የሚገርም ነው። እርሱ የአእምሮ ሕመም ይዞኛል ይላል ... እንዴት? ጭንቅላቱ ላይ አንድ ጊዜ ተደብድቦ ... ገባኝ። አጭበርባሪ ነዋ። መልካም፣ ስለሁኔታው እናያለን ... አቪ። አዝናለሁ አዛዥ፣ አጣራለሁ። ደህና ሁን። እም በተከታታይ እገልፅልሃለሁ።»

ታዲያስ አጭበርባሪው፣ አስኪ ጭንቅላትህን እንመልከተው። እም፣ በእርግጥም ረጅም የሆነ አንድ ጠባሳ አለ። በምትመታበት ወቅት የማስታወስ ስሜትህን ስታጣ ትዝ ይልሃል? ይህንን መልስልኝ!»

«መግለጽ አልችልም። የማስታውሰው መመታቴን ብቻ ነው፣ ስሜ ሻሪየ መሆኑንና ሌሎችም ጥቃቅን ነገሮች ዐውቃለሁ።»

«ሌላስ?»

«ስለምንነጋገርበት ጉዳይ ነዋ። ምግብና ሲጃራዎች ለምን ያህል ጊዜ ሲላክልኝ እንደቆየ ጠየቅኸኝ። መልሴም ይኸው ነው። የመጀመሪያ ይሁን ወይም አንድ ሺኛው አላውቅም። በአእምሮዬ ሕመም ምክንያት ልነግርህ አልቻልኩም። ስለዚህ ጉዳይ በቃ፣ ይኸው ብቻ ነው። የፈለግከውን ማድረግ ትችላለህ።»

«ምን እንደምፈልግማ አሁን ታያለህ። ለረጅም ጊዜ ከመጠን በላይ ስትበላ ኖረሃል። አሁን ትንሽ ከብደት መቀነስ ሊኖርብህ ነው። እስከ ቅጣትህ ፍጻሜ ድረስ አራት የሚባል ዳግመኛ አይኖርህም።»

በዚያው ዕለት በሁለተኛው ጠረጋ ወቅት አንዲት ማስታወሻ ደረሰችኝ። ያሳዝናል፣ የተጻፈችው በፎስፈረሰንት ካለመሆኑ የተነሣ ላነብባት አልቻልኩም። ከፍተሻ አምልጣ የነበረች አንዲት ሲጃራ ሌሊት ለኮስኩ። በምስባት ጊዜ በቂ ብርሃን ስለሰጠኝ ለማንበብ ቻልኩ። «ሰውየው አጋልጦ አልሰጠንም። ለአንተ ምግብ ሲሰጥ ሁለቴ ጊዜው ብቻ እንደነበረና ይህንንም ያደረገበት ምክንያት ፈረንሣይ ውስጥ ስለሚያውቅህ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑን ተናግሯል። በሮያሌ ማንንም ሰው አላሠጋም። በርታ።»

ስለዚህ፣ አሁን ከኮከነቱ፣ ከሲጃራዎቼና በሮያሌ ከሚጥሉት ጓደኞቼ ዜና ጋር ተቆራረጥኩ። ከዚያም ሴላ አራቴን ከልከለውኝ ነበር። ረኃብን ተለማመድኩ፣ የሲጃራ ሱሱን ተቋቋምኩት። በእኔ የተነሣ ይደበድቡት ስለነበረው ምስኪን ሰው ሥጋት ይዞኝ ነበር። በተጨማሪ እንዳይደበድቡት እማዚአብሔርን ተማፀንኩ።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት እዞራለሁ ... አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት እዞራለሁ። በተመጠነ ራቪን መቋቋም ቀላል አልነበረም። የምመገበው እንደዚህ በጣም ትንሽ ከሆነ፣ ዘዴየን መለወጥ እንደሚገባኝ አሰብኩ። ሰምሳሌ ተኝቼ ብቆይ ኃይሌን ማከማቸት አችላለሁ። አንቅስቃሴዬ ዝቅተኛ ከሆነ የማቃጥለው ካሎሪም አነስተኛ ይሆናል። ቀን ዝም ብዬ እቀመጣለሁ። በጠቅላላው አዲስ የአናኗር ስልት መልመድ አለብኝ። አራት ወር፣ አንድ መቶ ሐያ ቀን ነው። በአሥሚ የምግብ ዕጥረት ሕመም ከመያዜ በፊት ምን ያህል ጊዜ አቆይ ይሆን? ቢያንስ ሁለት ወር ነው። ስለዚህ በሁለት አደገኛ ወሮች ውስጥ ጠኔ ይጥለኛል ማለት ነው። አንድ ጊዜ በጣም ከደከምኩ ለማንኛውም የበሽታ ዐይነቶች መራቢያ መሬት መሆኔ ነው። ከምሽቱ ዐሥራ ሁለት እስከ ንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ቋጭ ብዬ ለመቆየት ወሰንኩ። የምሬመደው ከቡና አደላው በኋላ አነርሱ ባልዲ አንስተው እስከሚያበቁ ወይም በማምት ለሁለት ሰዓቶች ይሆናል። በቀትር ደግሞ ከቮርባ በኋላ ሴላ ሁለት ሰዓቶች። በጠቅላላው የአራት ሰዓት እርምጃዎች። የቀረውን ጊዜ እቀመጣለሁ ወይም እተኛለሁ። መቼም ካልደከምኩ በስተቀር በረራየን ለመተው አስቸጋሪ ነበር።

በአዲሱ የረሃብ ኑሮዬ ዐሥር ቀናት አሳለፍኩ። ቋሚ ረኃብተኛ ሆኛለሁ። ልክ ሥር አንደ ሰደድ በሽታ አንድ የማያቋርጥ ድካም ቀስፎ ይዞኝ ነበር። የሲጃራ እጦት አስከዚህ አልነበረም፣ ኮከነቱን ማጣቴ ከፉኛ በደለኝ። ወደ አልጋዬ በጣም ቀደም ብየ ተጋደምኩና ባስቸኳይ ከከፍሌ በሐሳብ ሾለከሁ። ትላንት ፓሪስ፣ በራት ሞርት ሦቴል ውስጥ ከአንዳንዶቹ ጓደኞቼ ጋር ሻምፓኝ እየጠጣሁ ነበር። ከአነርሱም ውስጥ ትውልዱ ከባሌአሪክ ደሴቶች ሆኖ ፈረንሣይኛ ሲናገር ልክ እንደ አንድ የፓሪስ ከተመኛ፣ እንግሊዝኛ ሲናገር ልክ እንደ ዕውነተኛ እንግሊዛዊ የነበረው የሎንዶኑ እንቶኒዎ ይገኝበታል። በሚቀጥለው ቀን ደግሞ ይኸው ሰው ማሮኒየ ውስጥ በከሊሼ አውራ ጎዳና ላይ ከጓደኞቹ አንደኛውን በሽጉጥ ይገድላል። በአራዳው ዓለም እንደዚህ የመሰሉ በጓደኛ ሕይወት አስከ መጨከን የሚያደረሱ ድርጊቶች ይፈጸማሉ። አዎ፣ ትላንት የኮርሲካና የማርሴይን ደምበኞቿን ከምታስተናግደው፣ በቅዱስ አን ጎና ከምትገኘው ፔቲ ኻርዲን ውስጥ በተደረገው የዳንስ ምሽት ላይ በአንድ የአኮርዲዎን ሙዚቃ እየታጀብኩና ከአነዚያ ሰዎች ጋር እየደነስኩ ፓሪስ ውስጥ ነበርኩ። በዚህ ልዩ ጉዞዬ ላይ እንደዚህ

t.me/OLDBOOKSPDF

የመሰሉትን አስደሣች ጊዜዎች ባሣለፍኩባቸው ብዙ ቦታዎች ሁሉ የእኔ መገኘት እውን ሆኖ ይታየኝ ነበር።

የዐይነ ሕሊናዬ ሥዕሎች ጊዜዬን ነጻ ሆኜ እንዳሳልፍ አስተዋጽኦ አድርገውልኛል።

አንድ ወር ቀረኝ። ለሦስት ወር አንዲት ቁራሽ ዳቦና አንድ ቁራጭ ሥጋ ያለበት ትኩስ መረቅ ብቻ ቀትር ላይ ይሰጠኝ ነበር። በዚህ ያለሰለሰ ረሀቤ ምክንያት፤ ሥጋው ወዲያው ሲሰጠኝ ዘወትር እንደሚያደርጉት አንጆ አለመሆኑን እየመረመርኩ አረጋግጣለሁ።

ዛሬ ጧት ቡናዬን ከጠጣሁ በኋላ በጣም በሽቴ ነበር። ካሁን በፊት ፍጹም አድርጌው የማላውቀውን ግማሹን ዳቦዬን በአንድ ጊዜ በላሁት። ዘወትር ሳደርግ የነበረው፤ በአማካይ ግምት አኩል እቆርሰና አንዱን በአሥራ ሁለት ሰዓት፤ እንዱን በቀትር፤ አንዱን ሲመሽና እንደኛውን ሌሊት ላይ አበላ ነበር። ራሴን ወቀስኩ። «ከሁለት ሰዓት እርምጃ በኋላ ከሲሚንቶ ዱካዬ ላይ ተቀመጥኩ። ከሠላሳ ቀኖች ወይም ሰባት መቶ ሐያ ሰዓቶች በኋላ መዝጊያው ይከፈትና አንድ ሰው፤ «ሻሪየ ውጣ። በወህኒ ቤት ውስጥ የሁለት ዓመት ቆይታህ አብቅቷል» ይለኛል። እኔስ የምመልሰው ምንድን ነው? የቀራንዮው አቀበት ፈተናዬ አበቃ» ይሆናል፤ ኦ! አይሆንም! እስምሮ ሕመምተኛነት ሸውጀው ከነበረው አዛቦር፤ እንደዚህ ከማለት መቆጠብ ይኖርብኛል። ለስለስ በማለት፤ «ምን? ምህረት ተደረገልኝ? ወደ ፊረንሣይ ሊሔድ ነው? ቅጣቴ አበቃ እንዴ?» እላለሁ። ያለአግባብ በጾም እንድቀጣ የፈረደበኝ ፀፅቶት «የእግዚአብሔር ያለህ» ይል እንደሆነ ለመስማት እጓጓለሁ። ምንቸግሮት፤ ትክክል ሠራ ወይም አልሠራ፤ መሳሳቱ ወይም አለመሳሳቱ ምንም ስሜት ሊሰጠው አይችልም። የዚያ ዓይነት ሰው ምን ሊፈይድ ይችላል? በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ያሉ መኮንኖች ጤነኛ ሰዎች አይደሉም። ሰው ነኝ ብሎ የሚያስብ ማንም ሰው እንደዚያ ያለው ሙያ ላይ አይሠማራም። በተጨማሪ፤ እዚህ ሥራ ውስጥ የሚገባ፤ የወጣለት ጉረኛ መሆንን እንኳ ይለመዳል። አንድ እግሩን ወደ መቃብር ውስጥ ሲያስገባ ያውም ሃይማኖተኛ ከሆነ ምናልባትኔ እግዚአብሔርን በመፍራት ይናዘዝ ይሆናል። ለዚያውም ላለፈው ድርጊቱ በእርግጥ ተፀፅቶ ሳይሆን በምዕዓት ቀን ቅጣቱን ለማግኘት የእርሱም ተራ ስለሚደርስ ያን በመፍራት ነው።

ከዚህ ቦታ በምወጣበት ጊዜ፤ በሚወስዱኝ የትኛውም ቦታ ቢሆን ከእንደነዚህ መሰሎች ጋር መጎዳኘት አይኖርብኝም። ሰዎችን አንድ መጋረጃ በሁለት ቡድን ይከፍላቸዋል። በአንደኛው ወገን ፍጹም ሕይወት የሌላቸው በድንና የማይንቀሳቀሱ የቢሮክራሲን ሥልጣን በመጨበጣቸው ሰውን ለማሰቃየት በሙሉ ፍላጎት የተጠመቁ ይኖራሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፤ እኔንና እኔን የመሳሰሉ ምናልባት ወንጀል ፈጽማችኋል

t.me/OLDBOOKSPDF

ተብለው ግን በቅጣታቸው መነሻ በሚደርስባቸው ሥቃይ፣ ሐዘንን፣ ርህራሄን፣ መሥዋዕትነትን፣ ጨዋነትንና ልቡ ሙሉነትን የመሰሉ ምግባሮችን የሚማሩ ሰዎች ይኖራሉ።

እውነቱን ለመናገር፣ የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ባለሥልጣን ከምሆን ይልቅ እንድ እሥረኛ መሆንን እመርጣለሁ።

ሐያ ተጨማሪ ቀኖች ቀሩኝ። በጣም ተዳከሜ ነበር። የዳቦ ራሽኔም እያነሰች የሔደች መሰለችኝ። እንደዚህ በመሰለው ስውር ተንኮል ተሰውቼ ይሆን? ለብዙ ቀኖች ሾርባ እየተባለ የሚሰጠኝ፣ አንድ አጥንት የተጣለበት ሙቅ ውሃ ነበር። አታመማለሁ ብዬ ሠጋሁ። መከራ ነበር። በጣም ከመዳከሜ የተነሣ ዐይኔ ፍጥጥ እንዳለ ሕልም ይታየኛል። ይህ ከፍተኛ ድካምና ከእርሱ ጋር የመጣው ፈዛዛነት በሚያስደነግጥ ሁኔታ አሳሰበኝ። አቋቋማለሁ ብዬ ሞከርኩ፤ ግን የእያንዳንዱን ቀን ሐያ አራት ሰዓቶች ማለፉ ከባድ ነበር። በመዝጊያዬ ላይ አንድ ቧጨራ ሰማሁ። ማስታወሻዋን ቶሎ ብዬ መነጨቅኳት። ከዶጋና ጋልጋኒ በርስፈረሰንት የተጻፈች ነበረች። «አንድ ቃል ላክብን። ስለጤንነትህ ጉዳይ ሠግተናል። ዐሥራ ዘጠኝ ቀኖች ቀሩ። በርታ፣ ሉዊ» ትላለች።

አንድ ቁራጭ ወረቀትና ቁራጭ እርሳስ ነበረኝ። ጻፍኩላቸው።

«እየተፍጨረጨርኩ ነው፣ ግን በጣም ተዳከሜያለሁ። አመሰግናለሁ ፓፒ።»

መጥረጊያው እንደገና መዝጊያየን ሲፈነቅፍ፣ ማስታወሻዋን ከሥር በኩል ገፋኋት። ከሲጃራዎቹም፣ ከኩከነቱም፣ ከሁሉም የሚበልጠብኝ እነዚያ ቃላት ነበሩ። የምፈልገው ይህን የመሰለውን ጓደኝነትና ታማኝነት ነበር። እዚያ ማዶ ስለእኔ ሁኔታ የሚያውቅልኝ ሰው አለኝ። ሕመም ቢሰማኝ እንኳ አንድ ዶክተር እንዲመረምረኝ ጓደኞቼ ያለጥርጥር ይከታተላሉ ማለት ነበር። ይህን አሰልቺ የሆነ ከሞትና ከዕብደት ጋር ለእሽቅድድም እየተቃረብኩ ነበር። አይሆንም፤ መታመም አይኖርብኝም። ካሎሪ ለመቆጠብ በተቻለ መጠን ሣልንቀሣቀስ ፀጥ ብዬ እቆያለሁ። የጧትና የሰዓት በኋላ የሁለት ሰዓት እርምጃዎቼንም አቋርጫለሁ። ለመቋቋም ያለው ብቸኛ መንገድ ይኸው ነበር። ሌሊት ሰዐሥራ ሁለት ሰዓቶች ተኝቼ እቆያለሁ፤ ሌላውን ዐሥራ ሁለት ደግሞ ምንም ሳልንቀሳቀስ በድንጋይ ጹካዬ ላይ እቀመጣለሁ። አለፍ አለፍ እያልኩ ከንዶቼን አንጠራራና ከዚያም እንደገና እቀመጣለሁ። ዐሥር ቀን ቀረኝ። በአንድ አስደንጋጭ ጩኸት ወደ ዕውነተኛው ሕሊናየ ከመመለሴ በፊት፣ በጃፓናውያን የቫዮሊን መዚቃ መንፈሴን እያደስኩ ትሪኒዳድ ውስጥ በመንሸራሸር ላይ ነበርኩ። ጩኸቱ የመጣው ከበስተጀርባዬ በጣም ቀረብ ብሎ ከሚገኝ አንድ ከፍል ነበር።

«አንተ ምናምንቴ! እዚህ ወደእኔ ከፍል አሽኪ ና ውረድ። እዚያ ላይ ሆነህ እኔን መመልከቱ አይሰለችህም? በዚህ ጉድጓድ ውስጥ ያለው ብርሃን በጣም አነስተኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

ከመሆኑ የተነሣ ብዙ እንደሚያመልጥህ አትገነዘብም?»

«ዝም በል! አለበለዚያ አስኪበቃህ ትቀምሳለህ?» ብሎ ዘበኛው ቁልቁል ጮኸ።

«ሉ፣ አታስቀኝ አንተ አበት። ከዚህ ዝምታ የባሰ ምን ይመጣል? ደስ ያለህን ያህል ቅጣኝ፤ አንገት ቆራጩ! ደስ የሚያሰኝህ ከሆነ ግረፈኝ፣ ከዚህ የበለጠ ምንም ነገር ልታደርገኝ አትችልም። ዕውነቴን ነው የምልህ፣ አልቻልከም። ሳልነጋገር፣ ከእንግዲህ መቀጠል አልችልም! እናንት የውሻ ልጆች፣ ድራሻችሁ ይጥፋ! አቀጣለሁ በሚል ፑርሃት ሠላሳ ስድስት ወራት መቆየቴ በጣም እንከፍ ኖሬያለሁ! እናንተ አስጠሊታዎች!»

ከትንሽ ጊዜ በኋላ መዝጊያው ተከፈተና፣ አንድ ድምፅ፣ «በዚህ ሁኔታ አይደለም። አካላቱን ገለባብጡት፣ እንዲያ ይሻለዋል።» ሲል ሰማሁ። ከዚያም ያ ምስኪን ጮኸ።

«የቅጣት ካባዬን ደስ ባላችሁ መንገድ አከናንቡኝ፣ እናንት ብስብሶች! ደስ ካሰኛችሁ ቆዳዬን ገለባብጡት፣ ወጥሩት፣ ማሠሪያዎቹን በጉልበቶቻችሁ ሳቡ። እናንት የቬርሙጣ ልጆች! እናንተ የአበት ጥርቃሚዎች ናችሁ ከማለት አትገቱኝም!»

አፍነውት መሆን አለበት፣ ከዚያ ወዲያ ምንም ነገር አልሰማሁም። መዝጊያው እንደገና ተዘጋ። ትኢይንቱ ወጣቱን ዘበኛ ትዕግሥት ያሳጣው መሆኑ ግልጽ ነበር። ምክንያቱም ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ከእኔ ከፍል ውጭ ቆም አለና፣ «ሉብዶ መሆን አለበት» አለ።

«አንደዚያ አሰብክ? ግን የተናገራቸው ማናቸውም ነገሮች በሙሉ ስሜት ይነካሉ እኮ» አልኩት። ይህም እንዳበሳጨው ገምቻለሁ፣ ምክንያቱም በሚሔድበት ወቅት፣ «የምትቀጥለው አንተ ትሆናለህ?» አለኝ።

ውዝግቡ፣ ከደሴቷና ከጥሩ ሕዝቦቿ፣ ከቫዮሊኑ ሙዚቃ በፓርት አፍ ስቼን ወደብ ከሚገኙት የሕንድ ኮረዳ ጡቶች አርቆኝ፣ ወደ ዕውነተኛው የሐዘን ግዞት ቤት ውስጥ መልሶ አስገባኝ።

ዐሥር ቀኖች ቀሩ። ሁለት መቶ ዐርበ ሰዓቶች። ምናልባት ይህን ተዐምር የሠራው ያለመንቀሳቀስ ዘዴዬ፣ ወይስ ከጓደኞቼ የምትመጣልኝ ማስታወሻ አጽናንታኝ? ምንም ነገር ይሁን፣ ብቻ ጥንካሬ እየተሰማኝ ነበር፣ በእኔና በነፃነቴ መካከል ያሉትን ሁለት መቶ ዐርባ ሰዓቶች አቀራርቤ በአሸናፊነት እንደምወጣ ተሰምቶኝ ነበር። ከእኔ በሁለት ያርድ የሚርቀው ሰው ወደ ዕብደት ደረጃ ገባ። ለረጅም ጊዜ የሚቆይ አይመስለኝም፣ ምክንያቱም አመፀኝነቱ በሣይንሳዊ ዘዴ አሰቃይተው ለመግደል ይበልጥ አመቺ መንገድ ከፍቶላቸው ነበር። ለእኔም ስሜቴን እንድቆጣጠር አስተማረኝ።

የግዞተኝነቴ ማከተሚያ ስለተቃረበ፣ በጤናና በሞራል በስድስት ወር ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

የማያለው ሆኜ፣ ለማምለጥ እንደምዘጋጅ ሙሉ በሙሉ አረጋገጥኩለሁ። የመጀመሪያው አፈታሪክ ይሆናል፣ በቅኝ ግዛት አስቃዩ መሀኒ ቤት ግንቦች ላይ ይተረጎሉ። ለዚህ ፍጹም አልጠራጠርም። በስድስት ወር ውስጥ እንደምሔድ ዕርግጠኛ ነበርኩ።

በግዙት መሀኒ ቤት የመጨረሻ ሌሊት ነበር። ቁጥር 234 ከፍል ውስጥ ከጣሁ ወራ ሰባት ሺ አምስት መቶ ስምንት ሰዓቶች ሆኖኛል። ወደ አዛው ዘንድ ቅርቢ ቃጣሪን ለመቀበል ስሔድ ለእንደ ጊዜ ብቻ መዘገያዬ ተከፍቶ ነበር። በየቀኑ ከጎረቤቱ ጋር ለትንሽ ሲኦንዶች የምለዋወጣቸው መጠነኛ ቃላት ሳይቆጠሩ፣ አራት ጊዜ ያህል ተንጋራያለሁ። በፈሽክ ድምፅ አልጋየን ማውረድ እንደሚገሰኝ በመጀመሪያው ቀን ሲነገረኝ፣ ሁለተኛው ደቂቀሩ «ዙርና ግል» ሲለኝ። ከአዛው ጋር ያደረግኩት ረዘም ያለ ንግግር ምስተኛው ነበር። አራተኛው ድግሞ በሚተኮለው ከፍል ስሳለው ያበደ ሰው ከዘበኛ ጋር የተለዋወጥኳቸው ጥቂት ቃላት ነበሩ። ይህም ቢሆን ሀሳብን እንደ ተራለገው የሚከፍል አልነበረምገ ነገ ደህ መዘገያ ለመጨረሻ ጊዜ ይከፈታል። ነገ፣ ፀሐይዋን አያለሁ። ወደ ሮያሌም ክላኩኝ የሚሉን ተዝቃዛ አየር መተንፈስ እችላለሁ። ነገ ነፃ አሆናለሁ። ሳላወቀው በሳት ፈነዳሁ። «ምን ማለትህ ነው ነፃ እንደ ተለመደው ወደ የዕድሜ ልክ ጽኑ አሥራትህ ትመለሣለህ። ደህን ነው ነገ ብለህ የምትጠራው? አውቃለሁ፣ አውቃለሁ» በማለት ከራሴው ጋር መግት ገጠምኩ። ከሥሴዎ፣ ማቹሬ እንዴት ሆነው እንደማገኛቸው ገርሞኛል።

በዐሥራ ሁለት ሰዓት በፍና ጸበዬ መጣልኝ። «እንዴ! የምፈታው ዛሬ አይደለም እንዴ? እንድ ስሕተት መኖር አለበት» ለማለት ታጣኝ። ታዲያ ወሥያው ትዝ ቢለኝ፣ የአእምሮ ሕመምተኛ ናሬያለሁ። ተናግሬ ቢሆን ኖሮ አዛውን በማጭበርበሬ ወደ ጨለማ ግንብ ውስጥ ለሰላሳ ቀን ሊያሰገባኝ ይችል ነበር። ደንቡም ያገዛል። ዛሬ ከቅዱስ የሴፍ ግዙት ወህኒ ቤት ልፈታ ነው።

ሁለት ሰዓት ሆኗል። ጸበዬን ጨርሼ በላሁ። መዘገያው ተከፈተ። ረዳት አዛውና ሁለት ዘበኞች አዚያው መጡ። «ሻሪየ ቅጣትህን ፈጽመሃል። ተከተለኝ።» ወደ ውጭ ወጣሁ፣ ፀሐይዋ ገርራ ስለነበር አደናበረችኝ። ድካም ተሰማኝ። ባቶቹ እንደጎማ አጥፍጥፍ ማለት ይከጅላቸዋል። ከአይኖቹ ፊት ለፊት ጥቁር ነጠብጣቦች ይደንሱብኛል። የተራመድኩት አንድ መቶ ሃምሳ ጫማ ብቻ ነበር።

ወደ አስተዳደሩ ሕንፃ ስቃረብ ማቹሬንና ከሎሲዎን አየኋቸው። ማቹሬ ጉንጮቹ ጎደጉደው፣ ዐይኖቹ ሰምጠው፣ አዕም መስሏል፣ ከሎሲዎ በአንድ ቃሬዛ ላይ ነበር። አመድ መስሎ የሞት ጠረን ይሸታል። የቅርብ ጓደኞቹ ያሉት አቋም ገመትኩ። እኔም እንደዚያ መስያለሁ? ራሴን በመስተዋት ውስጥ ለማየት ጓጉቼ ነበር።

«ታዲያስ እንዴት አሳለፋችሁት?» ስል ጠየቅኳቸው።

t.me/OLDBOOKSPDF

መልስ የለም።

በድጋሚ፣ «እንዴት አሳለፋችሁት?» አልኳቸው።

«ደህና» አለ ማቹሬ በለሆሳስ ድምፅ።

የግዙት ወህኒ ቤት ቅጣታችንን ስለጨረስን አሁን መነጋገር እንችላለን ልላቸው ፈልጌ ነበር። ከሎሲዎን ጉንጩን ሳምኩት። ዐይኖቹን ፍጥጥ አድርጎ ወደ እኔ ተመለከተና ፈገግ አለ።

«ደህና ሁን ፓፒዮ።»

«ምን ማለትህ ነው፣ የምን ደህና ሁን!»

«ተይገርለሁ፣ የእኔ ነገር አብቅቷል።»

ከትንሽ ቀን በኋላ ሮያሌ ሆስፒታል ውስጥ ሞተ። ዕድሜው ሠላሳ ሁለት ዓመት ሲሆን፣ ባልሰረቃት አንዲት ቢሰከሌት የሌብነት ወንጀል ተከስሶ ሐያ ዓመት ተፈርዶበት ነበር።

የወህኒ ቤቱ አዛዥ መጣ። ... «ወደ ውስጥ አስገቢቸው። ማቹሬና ከሎሲዎ፣ እናንተ ጥሩ ጠባይ አሳይታችኋል። በሪፖርታችሁ ላይ ይሆንኑ መዝግቤላችኋለሁ። አንተ ግን ሻሪየ፣ አንድ ከባድ ጥፋት ፈጽመሃል። ለዚህም ይሆንኑ ጠቅሼ መዝግቤልሃለሁ» አለ።

«ይቅርታ አድርግልኝ፣ ጥፋቴ ምን ነበር?»

«ሲጃራዎችና ኮከነት ልታስገባ ስትል እንደ ተጋለጥህ አታስታውስም?»

«አላስታውስም፣ በጭራሽ አላስታውስም።»

«እርሱን ተወው። ያለፉትን አራት ወሮች እንዴት አሳለፍክ»

«ምን ማለትህ ነው? ምን እየበላህ ነበር ነው የምትለኝ? ከደረሰኩ ጀምሮ ያው የምበላው ተመሳሳይ ነው።»

«ባለፈው ምሽት ምን በላህ?»

«የሰጡኝን አላውቅም። አላስታውስም። ባቄላ ወይም ሩዝ፣ ወይም እትክልት ይሆናል።»

«ስለዚህ ባለፈው ምሽት በልተሃላ?»

«የእግዚአብሔር ያለህ፣ ታዲያ ምግቤን እወረውራለሁ ብለህ ትገምታለህ እንዴ?»

«አይደለም፣ እርሱን ማለቴ አልነበረም። ትቸዋለሁ። እሺ፣ መጥፎ ጠባይ ያልኩብህን እፍቀዋለሁ። ሌላ መሸኛ ወረቀት አዘጋጁ... ‹ጥሩ ጠባይ› ብዬ ልጽፍልህ ነው፣ ደስ አለህ?»

«እንደሱ ይሻላል እንጂ። የሚገባኝም ይኸው ነው።»በዚህ ዓይነት ከቢሮው

t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣን።

እኛን ለማስወጣት ትልቁ የግዙት ወህኒ ቤት በር ተከፈተ። ወደ ካምፕ የምታመራውን የእግር መንገድ ተከትለን በአንድ ዘበኛ ታጅበን በዝግታ እየተራመድን ወረድን። ባሕሩ ከሥራችን እያንጸባረቀ ተንጣልሏል። አልፎ አልፎ የቀይ ጡብ ጣሪያዎች የሚፍለቀለቁባትና ደማቅ ልምላሜ ያላት ሮያሌ ባሻገር ትታያለች። የዲያብሎስ ደሴትም ምድረ በዳ መስላ በስተግዶ ትገኛለች። ለትንሽ ደቂቃዎች መቀመጥ አችል እንደሆነ ዘበኛውን ጠየቅኩት። ማቹሬና እኔ ከከሎሲዎ ጎንና ጎን ተቀመጥንና እጆቻችንን አጨባበጥናቸው። መነካካታችን አንድ የስሜት ትዝታ ፈጠረልንና ተቃቀፍን።

«ጎበዝ ተነሡ እንጂ፣ መሐድ አለብን አኮ» አለ ዘበኛው። በዝግታ በጣም በዝግታ ወደ ካምፑ ቁልቁል ወረድን። ማቹሬና እኔ እጆቻችንን እንደ ተጨባበጥን ሰንጓዝ የጓደኞችንን ቃሬዛ ሁለት ተሸካሚዎች ይዘው ከኋላችን እየተከተሉን ነበር።

ኑሮ በሮያሌ

ወዲያው ካምፑ እንደ ደረሰን «እንኳን ደህና መጣችሁ» የሚሉ ኢሥረኞች አሰፍስፈው ተቀበሉን። ፔየሮ ለፉ፣ ዮሐንስ ሣርትሮ፣ ኮሎንዲኒ፣ ቺዜሊያ፣ ሁሉም እዚያው ነበሩ። ወደ ሕክምና ቦታ መሐድ እንደሚኖርብን ዘበኛው ነግሮን ግቢውን ስንሻገር ሐያ የሚሆኑ ሰዎች አጅበውን ነበር። በአጭር ጊዜ ውስጥ ማቹሬና እኔ አንድ ደርዘን ሲጃራዎች፣ ትምባሆ፣ ትኩስ ቡና በወተትና ትኩስ ካካዎ ገጸ በረከቶች ተቀበልን። ሁሉም ሰው አንድ ነገር ሊሰጠን ፈለገ። ጤና ረዳቱ ለከሎሲዎ አንድ የካምፎር ዘይት መርፌ ወጋውና ለልብ ሕመሙ አድሬናሊን ሰጠው። በሽታ ያመነመነው አንድ ጥቁር፣ «ጤና ረዳት፣ የእኔን ቪታሚኖች ስጠው። ከእኔ ይበልጥ ለእርሱ ያስፈልጉታል» አለ። ፒዬር ደ ቦርዲላይ፣ «ገንዘብ ያስፈልጋችኋል? ወደ ሮያሌ ከመሐዳችሁ በፊት ትንሽ አርዳታ ለመሰብሰብ ጊዜ አገኛለሁ» አለ።

«ግዴለም፤ አመሰግናለሁ። ትንሽ አለኝ። ግን ወደ ሮያሌ መሐዴን በምን ዐወቅክ?»

«ጸሐፊው ነግሮኛል። በሙሉ ሥስታቺሁንም ነው። እንደሚመስለኝ ሁላችሁም እዚያ ባለው ሆስፒታል ልትገቡ ነው።»

ጤና ረዳቱ ዜግነቱ ኮርሲካዊ የሆነ አንድ ወንበዴ ነበር። ስሙ ኢዛሪ ይባላል። ደህና አድርጌ የማውቀው ስለሆነ ወደፊት ታሪኩን እነግራችኋለሁ። በጣም የሚያስገርም ነው። በሕክምና ቦታው የቆየንባቸው ሁለት ሰዓቶች ልክ እንደ ብልጭታ አለፉ። እስክ ፈለግን ድረስ በልተንና ጠጥተን፣ ከዚያም ሆዳችን ሲሞላ በደስታ ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሮያሌ ተነሣን። አጠገቡ ቀረብ ብዬ እጇን በግንባሩ ላይ ሳስቀምጥበት ካልሆነ በስተቀር፣ የከሎሲዎ ዐይኖች እንደ ተከደኑ ይቆያሉ። ከዚያም ገለጥ ያደርጋቸውና «ፓፒ፣ ዕውነትኛ ጓደኞች ነን እኮ! አይደለንም እንዴ?» ይለኛል።

«ከዚያም የበለጠ እንጂ! ወንድማማቾች ነን።»

ከነዚያው ከዘበኞች ጋር በመሆን ከሎሲዎ በቃሬዛ ላይ፣ ማቹሬና እኔ ከጎንና ጎኑ ሆነን በኮረብታው ቁልቁል መውረድ ጀመርን። በካምፑ መግቢያ ላይ ኢሥረኞቹ በሙሉ ደህና ሁኑ በማለት መልካም ምኞታቸውን ገለጹልን። ትምባሆና ሲጃራዎች፣ የወተት ቆርቆሮዎች የተመላበት አንዲት ከረጢት ፒየሮ ለፉ በአንገቴ ላይ አነገተልኝ። ለማቹሬም እንደዚሁ አንድ ሌላ ሰው ሰጠው። ከእኛ ጋር ወደ ወደቡ የወረዱት ጤና ረዳቱ ፌርናንዴዝና ዘበኛው ብቻ ነበሩ። በሮያሌ ለሚገኘው ሆስፒታል ለኢያንዳንዳችን አንድ ደብዳቤ ተጽፏል። ወደ ሆስፒታል እንድንገባ ለማድረግ ኃላፊነቱን የወሰዱት ሁለቱ ጤና ረዳቶች ኢዛሪና ፌርናንዴዝ መሆናቸውንና ሌላ ያማከሩት ዶክተር ኦነሪልነበረ ለመገንዘብ ቻልኩ። ጀልባው ደረሰ። ከጀልባው ኋላ ሰድስት ቀዛፊዎችና መሣሪያ የታጠቁ ሁለት ዘበኞች፣ ከፊት ደግሞ አነደዚሁ ሌሎች ሁለት ነበሩ። ከቀዛፊዎቹ አንዱ ቻፓር ነበር። ጉዞ ጀመርን። መቅዘፊያዎቹን ወደ ውሃው ሰድደው፣ በመቅዘፍ ላይ እንዳሉ፣ ቻፓር፣ «እንዴት ነህ ፓፒ? ኮከነቶቹን አገኘህ?» አለ።

«ላለፉት አራት ወራት ምንም አላገኘሁም።»

«ዐውቃለሁ። አንድ ችግር ተፈጥሮ ነበር። ሰውየው በጣም ጨዋ ስለነበር አንድም ነገር አልተነፈሰም።»

«ሐርሱንስ እንዴት አደረጉት?

«ሞቷል።»

«አይደረግም! እንዴት?»

«አንድ ሰው ሲደበድበው ጉበቱ ላይ ረግጦት ኖሮ በዚሁ ጦስ መሞቱን ጤና ረዳቱ ተናግሯል።»

ከሦስቱ ደሴቶች ውስጥ ትልቅ በሆነችው በሮያሌ ወደብ ዐረፍን። በዳቦ መጋገሪያ ቤት ግድግዳ ላይ ያለው ሰዓት ዘጠኝ ይላል። የቀትር በኋላዋ ፀሐይ ከመጠን አልፋ ግላ ነበር። ዘበኛው ቃሬዛ ተሸካሚዎች እንዲመጡለት ጠየቀ። ነጫጭ ንጹሕ ልብስ የለበሱ ሁለት ወጠምሻ ኢሥረኞች፣ ከሎሲዎን ልከ እንደ ላባ አንጠልጥለውት፣ እኔና ማቹሬ ከኋላ ተከተልን። ደብዳቤዎቹን የያዘ አንድ ዘበኛ ከኛ ጋር አብሮ ይጓዛል።

የመንገዱ ሰፋት ከዐሥራ ሁለት ጫማ በላይ ሆኖ ኮረት የተነጠፈበት ነበር። በላዩ ላይ መሪመድ ሥቃይ ሆነብን። ደግነቱ ቃሬዛውን የተሸከሙት ኢሥረኞች አልፎ አልፎ እያረፉ እኛን ይጠብቁ ነበር። ከቃሬዛው አጠገብ ከሎሲዎ ራስጌ እቀመጥና እጇን

t.me/OLDBOOKSPDF

በዘግታ በመዘርጋት ግንባሩንና ራሱን አዳስሳለሁ። በየጊዜው ፈገግ እያለ ወይኖቹን በመግለጥ፣ «አየ፣ የጥንቱ ጓደ ጋኘ» ይላል። ግቹራም እጁን ጨብጦታል።

እኛን አጠገቡ በማየቱ ደስ ያለው ይመስላል። ወደ መግቢያው በር አጠገብ ስንደርስ፣ ወደ ሥራ ከሚሰማሩ ሰዎች ጋር ተገናኘን። ከሞላ ጎደል ሁሉም እሥረኞች፣ የእኔ ኮንቮይ በድኖች ነበሩ። እያንዳንዶቸው ሲያልፉ የወዳጅነት ቃል ይጥሉልናል። ወደ ያልዳላው መሬት ስንደርስ፣ አራት ማዕዘን ከሆነ አንድ ነጭ ሕንፃ ጥላ ሥር የደሴቷ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ተሰምጠው የእኛን መምጣት ይጠባበቃሉ። ወደ እነርሱ አቅጣጫ አመራን።

አሆኾ ባሮ ከተሰመጠበት ብድግ ሳይል፣ «ለካስ የግዞት ቤት ኑሮ እስከዚህ ከባድ አልነበረም? እዚያ ታሪዛ ላይ ያለው ሰው ማነው አርሱ?»

«ከሎሲዎ ነው።»

ተመለከተውና፣ «ሁሉንም ወደ ሆስፒታል ውሰዷቸው። ሰመውጣት በሚዘጋጁበት ጊዜ እኔ እንዳውቀው። ወደ ካምፕ ከመሔዳቸው በፊት ላነጋግራቸው እፈልጋለሁ» አለ።

በሆስፒታሉ ውስጥ ወለል ያለ መበራት ያለበት አንድ ሰፊ ክፍል ውስጥ ንጹሕ አልጋዎች ከአንሶላና ትራስ ጋር ተሰጡን። በመጀመሪያ ያየሁት ሰው፣ በቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ በከፍተኛ ደረጃ ይጠበቅ በነበረው መታከሚያ ክፍል ጤና ረዳት የነበረውን ቻታልን ነበር። ወዲያው ከሎሲዎን መመርመር ጀመረና ዶክተር እንዲጠራለት አንድ ዘበኛ አዘዘ። ዶክተሩ ዐሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ደረሰ። ከረጅምና ጥበቅ ምርመራ በኋላ ደስ በማይል ሁኔታ ራሱን ነቅንቆ አንዳንድ ትእዛዞች ጻፈ። ከዚያም እኔን ለመመርመር ወደ አጠገቤ ቀረብ አለ።

«እኔና ጋፒዮ ጥሩ ወዳጆች አይደለንም እኮ» አለው ለቻታል።

«ገርሞኛል። ጥሩ ሰው ነው እኮ ዶክተር።»

«ሊሆን ይችላል፤ ግን ለእኔ ችግር ፈጥሮብኛል።»

«መቼ?»

«በግዞት ወህኒ ቤት ስመረምረው።»

«ዶክተር፣ ያንን ምርመራ ብለህ ትጠራዋለህ?» አልኩና በማከታተል፣ «ለአንዲት ቀዳዳ ብቅ ብሎ ደረቴን ማዳመጥ።»

«የአስተዳደሩ ሕግ ስለሆነ፣ የእንዱን እሥረኛ መዝጊያ መክፈት አንችልም።»

«ምናልባት ያ ሊሆን ይችላል ዶክተር፣ ግን ራስህ እስኪ ፍረድ፣ አንተ የአስተዳደሩ ጊዜያዊ ሠራተኛ ብቻ እንጂ አባል አይደለህም እኮ»

«ይሆን በሉላ ጊዜ እንወያያለን። አሁን አንተን ለማከም እየታገልኩ ነው፤

t.me/OLDBOOKSPDF

እንተንና ጓደኛህን። ያ ሰው ግን ጊዜ አልፎበታልና ያሠጋኛል።»

ለማምለጥ በመዘጋጀቱ ተጠርጥሮ ወደ ደሴቶቹ መላኩን ቻታል ነገረኝ። ከዚህም ሌላ ላመልጥ ሸንቶኝ የነበረው ኢዮአስም በእንድ ቆማጣ መገደሉን ተረዳሁ። ቻታል የቆማጣውን ስም አላወቀም፣ ምናልባት እኛ ከረዱን ውስጥ አንዱ ከሆነ ገርሞኝ እያበታም።

በዱላሊዩ ደሴቶች የአሥረኞች ኑሮ እናንተ ይሆናል ብላችሁ ከምትገምቱት ፍጹም ልዩ ነበር። ብዙዎቹ ሰዎች «አደገኛ» ከሚባሉት መደብ ውስጥ ነበሩ። አልኮል፣ ሲጃራ፣ ቡና፣ ቸኮላት፣ ስኳር፣ ሥጋ፣ ትኩስ አትክልት፣ ዐሣ፣ ኮከናት ... ወዘተ በሕገወጥ ንግድ ስለሚያገኙ በሚገባ ይባላሉ። ከዚህም የተነሣ ማንኛውም ሰው ጤነኛ ነበር። የአየሩም ጠባይ አስተዋጽኦ ነበረው። የአጭር ጊዜ ቅጣት ያላቸው አሥረኞች ብቻ ነፃ እንሆናለን የሚል ተስፋ ሲኖራቸው፣ የዕድሜ ልክ አሥራት የተፈረደባቸው ሰዎች ምንም የሚያስቡት ነገር አልነበረም። ዘበኞችም ሆኑ አሥረኞች ማንኛውም ሰው በየቀኑ በሚካሔደው ሕገ ወጥ ንግድ ተሳታፊ ነበር። በአጠቃላይ ሁኔታው የተደበላለቀ ነበር። የዘበኞቹ ሚስቶች በቤታቸው አካባቢ እንዲያገለግሏቸው አንዳንድ ወጣት አሥረኞችን ይመለምላሉ። አዘውትረው የሚይዟቸው ግን በውሽምነት ነበር። የሚጠሩት «የቤት ልጆች» በመባል ሲሆን፣ አንዳንዶቹ እንደ አትክልተኛ፣ ሎሎቹ ደግሞ እንደ ወጥ ቤት ሠራተኛ ያገለግላሉ። በካምፑና በዘበኞቹ ቤት መካከል የሚላላኩት አቀባባዮችም እነርሱ ናቸው። የቤት ልጆቹን በክፉ ዐይን ሊያሚመለከት አይኖርም፤ ምክንያቱም ሕገ ወጥ ቅብብል የሚካሔደው በእነርሱ አማካይነት ስለነበረ ነው። እኛ ግን እንደ «ንጹሕ» የአራዳው ዓለም ሰዎች አንገምታቸውም። ከነጠሩት አራዳዎች ማንም ሰው ቢሆን እንደዚህ ለመሰለው ሥራ፣ ወይም ቁልፍ ያገርነት፣ ወይም በዘበኞች ምግብ ቤት አገልጋይ ለመሆን አያጎበድድም። እንዲያውም ከዘበኞች ጋር የማያገናኘውን ሥራ ለማግኘት ሲል ገንዘብ ይከፍላል። ለምሳሌ፤ እንደ ሠገራ ጉድጓድ ማጽዳት፣ ቅጠል መጥረግ፣ ኩበት መጠበቅ፣ ጤና ረዳትነት፣ አትክልተኛ፣ ልኳንዳ ሠራተኛ፣ ዳቦ ጋጋሪ፣ ጀልባ ቀዛፊ፣ ፖስተኛ፣ የአደጋ ማስጠንቀቂያ መብራት ማንብ ጠባቂ፣ ወዘተ ... ለመሆን። እነዚህ ሥራዎች የሚከናወኑት በዕውቆቹ አይበገሬ አሥረኞች ነበር። በተጨማሪም ቁንኖቹ አሥረኞች፣ የወህኒ ቤቱን ግንቦች፣ ሞንጎዶች፣ ደረጃዎች ከሚጠግኑት ወይ የኮከነት ዛፎች ከሚተክሉት የሠራተኛ ቡድኖች ጋር ፈጽሞ አይሠሩም። እነዚህ ቡድኖች የሚሠሩት በጠራራ ፀሐይ በዘበኞች ቁጥጥር ሥር ሆነው ነበር። የሥራ ሰዓታቸው ከአንድ ሰዓት እስከ ቀትር፣ ከስምንት ሰዓት እስከ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ነበር። በዚህች ትንሽ መንደር ውስጥ የሚኖረው ማንኛውም ሰው ሌላውን ሰው የሚከታተል፣ እያንዳንዱ ሰው ሌላውን የሚታዘብና በአካባቢው የሚያካሔደውን ኑሮ የሚያጠና

t.me/OLDBOOKSPDF

ውጥንቅጡ የወጣ የተሰየ ሕዝብ ነበር።

ዴጋና ጋልጋኒ አሑድን ከእኔ ጋር ለማሳለፍ ሆስፒታል ምጡ። ዓሣ ጥብስ፣ የዓሣ ሾርባ፣ አይብ፣ ቡናና ነጭ የወይን ጠጅ ነበረን። ዴጋ፣ ጋልጋኒ፣ ማቹፊ፣ ግራንዴና እኔ ሆነን በቻታል ከፍል ውስጥ ምሳችንን በላን። እስከ መጨረሻዋ ነጥብ ድረስ የማምለጥ መዘክሬን እንድነግራቸው ጠየቁኝ። ዴጋ ማምለጥ ላለመሞከር ወስኗል። አምስት ዓመት እንደሚቀነሰለት በተስፋ ላይ ነበር። ሦስቱን ዓመት ፈረንሣይ ውስጥ በመጨረሱና እዚህ ደግሞ ሦስት ዓመት ስለሞላው፣ አሁን የቀረው አራት ዓመት ብቻ በመሆኑ እነርሱንም ለመጨረስ ቆርጧል። ጋልጋኒም፣ አንድ ኮርሲካዊ የምከር ቤት አባል ጉዳዩን እንደሚከታተሉለት ተናገረ።

ከዚያም የእኔ ተራ ሆነ። ለማምለጥ የተሻሉ ቦታዎች በዚህ አካባቢ የትኞቹ እንደሆኑ ጠየቅኳቸው። ከፍተኛ ኡኡታ ተፈጠረ። ጥያቄው ለዴጋ ፍጹም እንግዳ ነበር። እርግጠኛ ነኝ ለጋልጋኒም እንደዚሁ። ጀልባ ለመሥራት የአትክልት ቦታው አመቺ መሆኑን ቻታል ገምቷል። ግራንዴም በእጅ ሥራ ከፍል ውስጥ የብረታ ብረት ሠራተኛ እንደነበረ ገለጸልኝ። ብዛት ያላቸው የተለያዩ ሠራተኞች ያሉበት ወርክ ሾፕ መኖሩንም ዘረዘረ። ቀለም ቀቢዎች፣ አናጢዎች፣ ብረታ ብረት ሠራተኞች፣ ግንበኞች፣ ቧንቧ ሠራተኞች - አንድ መቶ ሐያ የሚሆኑ ሰዎች ይገኙበታል። በአስተዳደሩ ሕንፃዎች ላይ የጥገና ሥራ ያከናውናሉ። ዋና ጸሐፊ የነበረው ዴጋ፣ የምፈልገውን ማንኛውንም ሥራ እንደሚከታተልልኝ ነገረኝ። ግራንዲም የቁማር አሜዋችነቱን ሥራ ለእኔ እንደሚያጋራኝና በገንዘብ መደበቂያ ቱቦዬ ያለኝን ገንዘብ ከማጥፋት ይልቅ፣ ከተጫዋቾቹ በማገኘው ገቢ መኖር እንደምችል ሐሳብ አቀረበ። በኋላ እንደ ተረዳሁት ሥራው የሚጥም ቢሆንም፣ ይበልጥ አደገኛ ነበር።

ያ አሑድ ዕለት ልክ እንደ ብልጭታ ከመቅዕበት አለፈ። «ወሥራ አንድ ሰዓት ሆነ» አለ ዴጋ ደሰ የምትል ሰዓቱን ተመለከተና። «ወደ ካምፕ መመለሻ ጊዜያችን ነው።» በምንለያይበት ወቅት ካርታ የምትጫወትበት ይሁንህ ብሎ አምስት መቶ ፍራንክ ሰጠኝ። እንደተለመደው በእኛ ከፍል ውስጥ አንዳንዴ ከፍተኛ ጨዋታዎች ነበሩ። ራሱ የሠራትን አንዲት ግሩም የሆነች ጩቤ ግራንዴ ሰጠኝ። የምታስቀና መሣሪያ ነበረች።

«ቀን ከሌሊት መሣሪያ መያዝ ይኖርብሃል።»

«አይፈትሹም እንዴ?»

አብዛኛውን ጊዜ የሚፈትሹህ ዘበኞች፣ ቁልፍ ያገር ዐረቦች ናቸው። አንድ ሰው አደገኛ መስሎ ኮታያቸው፣ ቢያዩም ፍጹም አይተንበታል አይሉም በእጃቸው ቢነኩትም እንኳ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ካምፕ እንገናኛለን» አለ ግራንዴ።

ከመሐዱ በፊት አንድ ከፍት ቦታ ለእኔ ማሰናዳቱንና በጉርብትና አብረን እንደምንሆን ጋልጋኒ ነገረኝ። በጉርብትና የሚኖሩ ደባሎች የሚመገቡት በሕብረት፣ ገንዘባቸውም በሙሉ የጋራ ነበር። ዴጋ የሚተኛው ካምፕ ሳይሆን፣ በአስተዳደሩ ሕንፃ አንድ ከፍል ውስጥ ነበር።

ሆስፒታል ከገባን ሦስት ቀን ቢሆነንም፣ ሌሊቱን የማሳልፈው ከክሎሲዎ ጋር በመሆኑ፣ በከፍሉ ውስጥ የሚካሔደውን አጣርቼ አላወቅኩም ነበር። ከሎሲዎ በአሥጊ ሁኔታ ላይ ስለነበረ፣ ከሌላ ሰው ጋር አንድ ልዩ ከፍል ውስጥ አስገቡት። ቻታል በሞርፊን እየሞላ መርፌ ይጠቀጥቀዋል። በሌሊት ግን ያሠጋዋል ብሎ ስለሚፈራ አይጠጋውም ነበር።

በከፍሉ ውስጥ ሠላሳ አልጋዎች ሲኖሩ፣ አብዛኞቹ የተያያዙ ሆነው፣ በመካከሉ ዐሥራ ሁለት ጫማ ስፋት ያለው አንድ መተላለፊያ ይገኛል። ሁለት የጋዝ ፋኖሶች ይበሩበት ነበር።

«ሕዚያ ካርታ እየተጫወቱ ነው» አለ ማቹሬ። ወደዚያው ሔድኩ። አራት ተጫዋቾች ነበሩ።

«አምስተኛ መግቦት አችላለሁ?»

«አንዴታ፣ ተቀመጥ። መደቡ መቶ ፍራንክ ነው። ለመጫወት ሦስት እጥፍ መደብ ማስያዝ ይኖርብሃል፤ በሌላ መጌጌድ ሦስት መቶ ፍራንክ መሆኑ ነው። ሦስት መቶ ፍራንክ ዋጋ ያላቸው ካርዶች እኝሁልህ።»

ለከፋም ለደጉም መጠባበቂያ ሁለት መቶውን ለማቹሬ ሰጠሁ።

«በእንግሊዞች ሕግ ነው የምንጫወተው። ጆከር የለም። እንዴት እንደሆነ ታውቃለህ?» አለ ዱፖን የተባለ አንድ የፓሪስ ከተመኛ።

«በሚገባ።»

«እሺ፣ የአንተ ተራ ነው።»

እነዚህ ሰዎች ሲጫወቱ አፈጣጠናቸው የሚያስገርም ነበር። ልከ እንደ መብረቅ ፈጥነህ መውረድ አለብህ፤ አለበለዚያ ካርታ ሰጭው፣ «በጣም ዘገየህ» ይልና አንድ ዙር ጨዋታ ያመልጥሃል።

እነዚህ ቁማርተኞች፣ ራሳቸውን የቻሉ አንድ ልዩ የአሥረኛ መደብ ነበሩ። የሚኖሩት ለቁማርና በቁማር ነበር። ምንም የሚያስደስታቸው ሌላ ነገር የለም። ማንኛውንም ነገር ረስተዋል። ምን እንደነበሩ፣ ቅጣታቸውን፣ ኑሯቸውን ለመለወጥ ምን ማድረግ እደሚችሉ ሁሉ ተዘንግቷቸዋል። ዋናው አሳሳቢያቸው ጉዳይ ቁማር ነበር።

ሳንድዊች ብጤ ለመቅመስ ወረፍ ከምንል በስተቀር ሌሊቱን በሙሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተጫወትን። ሦስት ሺ ሦስት መቶ ፍራንክ በላሁ። ወደ አልጋ በማምራት ላይ እንዳለሁ ነበር፣ ስሙ ጳውሎስ የተባለ ከተጫዋቾቹ አንዱ ወደ እኔ መጥቶ ሁለት መቶ ፍራንክ ለበድረው ከቻልኩ ትርፍ የእኩል የሚጫወትልኝ መሆኑን የጠየቀኝ። የሚያስፈልገው ሦስት መቶ ፍራንክ ሲሆን፣ አርሱ ግን አንድ መቶ ብቻ ነበረው።

«ያውልህ፤ ሦስት መቶውን ውሰድና ትርፍ የኩል አናደርገዋለን።»

«አመሰግናለሁ ፓፒዮ፣ ሌሎች እንደሚሉህ በእርግጥም ጥሩ ሰው ነህ። ወደፊት ጓደኞች እንደምንሆን ይታየኛል»። እጁን ሲዘረጋልኝ፣ ጨበጥኩትና ደስ እያለው ሔደ።

ከሎሲዎ ዛሬ ጧት ሞተ። ባለፈው ሌሊት ነፍሱን እንደ ማወቅ ብሎ ስለነበር፣ ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ተጨማሪ ሞርፊን እንዳይወጋው ለቻታል ነግሮታል። «ጓደኛቼ በዙሪያ ሆነው አልጋየ ላይ እንዳለሁ መሞት እፈልጋለሁ» አለ።

ወደ ሕሙማን ማግለያ ከፍል ለመግባት በጥብቅ የተከለከለ ነበር፣ ግን ቻታል ኃላፊነቱን ወሰደና ከሎሲዎ በጓደኞቹ መካከል ለመሞት በቃ። ዐይኖቹን እኔ እገጣጠምኳቸው። ማቹሬ በሐዘን ተኮራምቶ ነበር።

«የአስቸጋሪው ጉዟችን ባልደረባ ተሰናበተ። አስከሬኑም ለዓሣነባሪዎች ተወረወረ።»

«ለዓሣነባሪዎች ተወረወረ» ያሏቸውን ቃላት ሰሰማ ክች ብዬ ቀረሁ። ዕውነትም ነበር። ለእሥረኞች የመቃብር ቦታ አልነበረም። አንድ እሥረኛ ሲሞት፣ በቅዱስ ዮሴፍና በሮያሌ መካከል ከሚኖኝ ዓሣነባሪዎች የሚርመሰመሱበት ባሕር ውስጥ ፀሐይ ስትጠልቅ ይወረወራል።

ከጓደኛዬ ሞት አንጻር ሆስፒታል ውስጥ ለመቆየት መቋቋም አቃተኝ። በሁለት ቀን ውስጥ መውጣት እንደምፈልግ አንድ መልዕክት ወደ ዴጋ ላከሁ። «ከካምፕ ውስጥ ለሁለት ሳምንት የሐኪም አረፍት እንዲሰጥህ ቻታልን ጠይቀው። በዚህ መንገድ ምን ዓይነት ሥራ እንደምትፈልግ ለመምረጥ ጊዜ ይኖርሃል» የምትል አጉዲት ማስታወሻ ላከልኝ። ማቹሬ ትንሽ ረዘም ላለ ጊዜ ሊቆይ ነው። የሕክምና ከፍል ረዳትነት ሥራ እንዲያገኝ ቻታል እየሞከረለት ነበር።

ከሆስፒታል በቀጥታ ወደ አስተዳደር ሕንፃ ተወሰድኩና በእሥረኞች ዘንድ «ኮክ ሲክ» በሚባል የቅፅል ስም ወደሚታወቀው የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ ባሮ ፊት ቀረብኩ።

«ፓፒዮ፣ ወደ ካምፕ እንድትሔድ ከምፈቅድልህ በፊት፣ አንዳንድ ነገሮች ከአንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ። የእኔ ዋና ጸሐፊ የሆነ ሉዊ ዴጋ የተባለ አንድ ኃይለኛ አጋር አለህ። ስለአንተ ከፈረንሣይ የደረሰኝ መረጃ እውነት እንዳልሆነና ወንጀሉን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንዳልፈጸምከው፣ ከደሙ ንጹህ መሆንህንም ይነግረኛል። ግን ማወቅ የምፈልገው፣ በአሁኑ ወቅት የአእምሮህ ሁኔታ እንዴት ነው?»

«ጌታዬ፣ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ለአንተ መልስ ለመስጠት ማጎደሬ ምን እንደሚል ማወቅ ይኖርብኛል።»

«ተመልከተው» ብሎ አንድ አረንጓዴ ካርድ አቀበለኝና የሚከተሉትን አነበብኩ።

«ሔንሪ ቫሪየ፣ ፓፒዮ በሚል ስም የሚጠራ፣ የተወለደበት በ1906 በአርዴከ፣ በአንደኛ ደረጃ ነፍስ መግደል ሲየን በተሠየመው ችሎት የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተፈርዶበታል። ከመጠን በላይ አደገኛ፣ በዐይነ ቁራኛ የሚጠበቅ፣ ምንም እንከብካቢ የማይደረግለት።

«የኪየን ማዕከላዊ ማረፊያ ቤት፣ የማይታረም፣ ማበጣበጥና ዓመፅ የመቀስቀስ ዝንባሌ ያለው በዐይነ ቁራኛ የሚጠበቅ።

«ቅዱስ ማርቲን፡- የሥነ ሥርዓት ተገዢ እንዲሆን ጥብቅ ቁጥጥር የሚያስፈልገው፣ በጓደኞቹ መካከል ተደማጭነት ያለው፣ ዘወትር ለማምለጥ የሚሞክር።

«ቅዱስ ላውረን ዲማሮኒ፣ ከሆስፒታል ሲያመልጥ በሦስት ዘበኞችና በአንድ ቁልፍ ያዥ ላይ የጭካኔ ድርጊት የፈጸመ። ኮሎምቢያ የተመለሰ፣ አዚያ እሥር ቤት በነበረበት ወቅት ጥሩ ጠባይ ያሳየ፣ ከወህኒ በማምለጡም የሁለት ዓመት ጽኑ እሥራት የተፈረደበት።

«በቅዱስ ዮሴፍ የግዞት ወህኒ ቤት፡- ጥሩ ጠባይ።»

ማጎደሬን ለአዛዡ በማቀበል ላይ እንዳለሁ «የእኔ ወዳጅ ፓፒዮ፣ ሁኔታው አንተነትህን በትክክል የሚያሳምንልህ አይደለም። ከእኔ ጋር አንድ ስምምነት ማድረግ ትፈልጋለህ?» አለ።

«ምናልባት፣ እንደ ስምምነቱ አቀራረብ ይወሰናል።»

«ከደሴቶቹ ለማምለጥ የምትችልበትን ማንኛውንም ነገር እንደምታደርግ ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ የለኝም። ምናልባትም ሊሳካልህ ይችላል። እኔ እዚህ በአዛዥነት ለመቆየት የቀሩኝ አምስት ወሮች ብቻ ናቸው። አንድ የተሳካ የማምለጥ ሙከራ ቢካሔድ ለወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ ምን እንደሚያስከትልበት ታውቃለህ? - የአንድ ዓመት ደመወዝ - የቅኝ ግዛት አበል በሙሉ ማጣትና በተጨማሪ የስድስት ወር ፈቃዴ ተሠርዞ ወደ ሦስት ወር መቀነስ። ከዚህም ሌላ ከትትል ተደርጎ ጥፋቱ በአዛዡ ንዝህላልነት መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ምናልባት ከደረጃም ዝቅ ሊያስደርግ ይችላል። እንዴት ጥብቅ መሆኑን ተረዳኸው? ታዲያ ሥራዬን በብቃት ለመወጣት ብዬ እንዳታመልጥ አንድ ከፍል ውስጥ አስሬ ላቆይህ መብት የለኝም። እርግጥ አንዳንድ ቅጣቶች ሊኖሩኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይችላሉ፣ ግን ያንን ለማድረግ አልፈልግም። ስለዚህ ከደሴቶቹ እስክምሔድ ድረስ ለማምለጥ እንደማትሞክር ቃልህን እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ።»

«አዛዥ፤ ስድስት ወር ካላሰፈህ በስተቀር እንኑ እዚህ ባለህበት ጊዜ እንደማላመልጥ የክብር ቃሌን እሰጥሃለሁ።»

«የምሔደው እንዲያውም ከአምስት ወር ትንሽ ቀደም ብዬ ነው። ጥርጥር የለውም።»

«ጥሩ፣ ቃል አክባሪ ስለመሆኔ ካሰፈለገ ዴጋን ልትጠይቀው ትችላለህ።»

«እኔም አምንሃለሁ።»

«ግን አንድ የማቀርበው ጥያቄ ይኖረኛል።»

«ምንድን ነው?»

«በምቆይባቸው አምስት ወሮች ውስጥ፣ ለወደፊቱ ጠቃሚ የሚሆኑ አንዳንድ ነገሮችን ለመሥራትና ደሴቶችም መለወጥ እንድችል ነው።»

«መልካም። እስማማለሁ። ግን ጉዳዩ በመካከላችን በጥበቅ ይያዝ።»

«እሺ ጌታዬ!»

«ጓደኞቼ በሙሉ በእደገኞቹ የአሥረኞች ሕንፃ ውስጥ የሚኖሩ አራዳዎች እንጂ እንድም ጥሩ ሰው እንደሌለባቸው ዴጋ አሳምኖታል። የአሥረኛ ዩኒፎርም ያለበት አንድ ጥቅልና አዛዡም የጨመረልኝ ነጫጭ ጃኬቶችና ሱሪዎች ተሰጡኝ።

ስለሆነም፣ ሁለት ጥንድ ነጫጭ አዲስ ሱሪዎች፣ ሦስት ጀርሲዎችና አንድ ባርኔጣ ይገዙ በአንድ ዘበኛ እንደታጀብኩ ወደ ማዕከላዊ ካምፕ መንገድ ጀመርኩ። ከእስተዳደሩ ሕንፃ ወደ ካምፑ ለመድረስ በጠቅላላው ተረተሩን መዞር ይኖራል። ጠባይ ማረሚያውን የከበበውንና ዐሥራ ስድስት ጫማ ከፍታ ያለውን ግንብ ዞርንና በዘበኞቹ ሆስፒታል ፊት ለፊት አልፈን፣ በአንድ ግዙፍ አራት ማዕዘን ሕንፃ ታጥፈን ወደ ዋናው መግቢያ በር ደረስን። «የደሴቶች ጠባይ ማረሚያ፡- የሮያሌ መምሪያ» ይላል። ከፍታው ቢያንስ ዐሥራ ስምንት ጫማ መሆን ያለበት አንድ ትልቅ የእንጨት መዝጊያ ወለል አለና ተከፈተ። እያንዳንዳቸው አራት ዘበኞች የሚገኑባቸው ሁለት ቡድኖች በጥበቃ ላይ ነበሩ። አንድ መኮንን ፊንጠር ብሎ ወንበር ላይ ተቀምጧል። ካርባይኖች አልያዙም። ሁሉም ሰው የታጠቀው ሽጉጥ ነበር። በተጨማሪ አራት ወይም አምስት ያህል ቁልፍ ያሻቸ ዓረቦች ነበሩ።

ወደ በሩ ስደርስ፣ ዘበኞቹ በሙሉ ወደፊት መጡ። ሃላፊያቸው አንድ ኮርሲካዊ ነበር። «እንግዳ ነው፣ ቀላል ሰው እንዳይመስላችሁ!» አለ። ቁልፍ ያገኙቹ ሊበረብሩኝ አሰፍስፈው ነበር። ግን እርሱ አቆማቸው። «ጓዙን መዘከዘክ አይኖርበትም። ገዘም በልና ሒድ ፓፒዮ። እዚያ ውስጥ የሚጠበቁህ ብዙ ጓደኞች

t.me/OLDBOOKSPDF

አሉህ። ስሜ ሶፍራኒ ይባላል። መልካም ዕድል! አለ።

«አመሰግናለሁ ጌታዬ» በሦስት ትላልቅ ሕንፃዎች ከተከበበ ከአንድ ግቢ ውስጥ ደረስኩ። ዘበኛው ከሦስቱ ወደ አንዱ መራኝ። ከመዝጊያው በላይ «የልዩ ቡድን ሕንፃ» የሚል አነበብኩ። ወለል ብሎ በተከፈተው መዝጊያ በኩል «ዘበኛ!» ብሎ ተጣራና አንድ ሽማግሌ አሥረኛ ብቅ አለ። «ይኸውልህ አዲስ ሰው» ብሎት ዘበኛው መንገዱን ቀጠለ።

የአንድ መቶ ሐያ ሰዎች መኖሪያ ወደ ሆነው አንድ ግዙፍ አራት ማዕዘን አዳራሽ ውስጥ ገባሁ። እንደ ቅዱስ ላውረን ምሽግ ስፋትና ርዝመት ያላቸው ሁለት አግዳሚ ብረቶች ተዘርግተውበት በመዝጊያዎች ብቻ ተከፋፍሏል። ማታ ማታ የሚዘጋ አንድ የብረት ፍርግርግ ነበር። በግድግዳውና በአግዳሚ ብረቶቹ መካከል ተወጥረው የተዘረጉ እንደ መኝታ የሚያገለግሉ ተንጠልጣይ ሸራ አልጋዎች አሉት።

ከዚህ በፊት የማውቃቸው ዓይነት አልጋዎች ሳይሆኑ ንጹሕና ምቾት ያላቸው ነበሩ። ከእያንዳንዱ በላይ ሁለት መደርደሪያዎች ሲኖሩ አንዱ ለልብስ፣ ሌላው ደግሞ ለምግብ፣ ለሣህኖች ወዘተ... ማስቀመጫ ነበረ። በአልጋዎቹ መካከል ስፋቱ ሦስት ያርድ የሚሆን «መንሸራሸሪያ» ተብሎ የሚጠራ አንድ ኮሪደር ይገኛል። ሰዎቹ «ጎረቤት» እየተባባሉ በመጠራራት መለስተኛ ማኅበረሰብ መሥርተዋል። አንዳንዶቹ ከፍሎች ከሁለት ሰው የማይበልጡ ሲኖሩባቸው በሌሎቹ እስከ ዐሥር ይደርሳሉ።

ወደ ከፍሉ ገና ሙሉ በሙሉ ሳልገባ ነበረ ኑሜጭ ዩኒፎርም የለበሱ ከባድ አሥረኞች ከሁሉም አካባቢ ወደ እኔ መጥተው፣ «ፓፒ ና ወደዚህ» ወይም «አይሆንም ወደ እኛ ና» ሲሉኝ፣ ግራንዴ ጓዜን ተቀበለና፣ «የእኔ ጎረቤት ነው የሚሆነው» አለ። ተከተልኩት። ተንጠልጣይ አልጋዬ በሚገባ ተወጥሮና ጠበቅ ተሰቅሎልኝ ነበር። «ጓዴ፣ ለእንተ የተዘጋጀ የላባ ትራስ ያውልህ» አለ ግራንዴ። ብዙዎቹ የቅርብ ጓደኞቼ እዚሁ ነበሩ፣ ከኮርሲካና ከማርሴይ የመጡ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ከፓሪስ። ሁሉንም በፈረንሣይ ወይም በሳንቲ፣ አለበለዚያም በማረፊያ ጣቢያው ወይም በኮንቮዩ ውስጥ የማውቃቸው ነበሩ። «እንዴት ሁላችሁም እዚህ ሆናችሁ?» ብዬ ጠየቅኩ። «ለምን ወደ ሥራ አትወጡም?»

ሁሉም ሣቁ። «እዚህ ማንም ሰው በቀን ከአንድ ሰዓት በላይ የሚሠራ የለም። ከዚያም ወደየሠፈራችን መመለስ ነው።»

ግሩም መስተንግዶ ተደረገልኝ። ግን ለአራት ቀናት ብቆይም፣ አሁንም ኾ ከሕብረተሰቡ ተደባልቄ እንዴት እንደምኖር መልመድ ነበረብኝ።

ይግረምህ ብሎ፣ ነጭ ልብስ የለበሰ አንድ ሰው በነጭ ጨርቅ የተሸፈነ አንድ ጎድጓዳ ሣህን ተሸክሞ፣ «ሥጋ፣ ሥጋ፣ ማነው ሥጋ የሚፈልግ?» እያለ መጣ። ቀስ በቀስ

t.me/OLDBOOKSPDF

መንጌን ወደ እኛ አምርቶ ቆመና፣ ሲገልጠው ንዴህ ሥጋ ተከምሯል። ግራንዴ የዘወትር ደንበኛ መሆኑ ግልጽ ነበር። የሚፈልግ መሆን አለመሆኑን ሳይጠይቅ፣

«አምስት» አለ።

«ጭቅና ነው ሻኛ?»

«ጭቅና። ምን ያህል ነው ያለብኝ? ሒሳብህን ብታዘጋጅልኝ ይሻላል፣ ምክንያቱም አሁን አንድ ተጨማሪ ሰው አለን።» ሥጋ ሻጩ አንድ ማስታወሻ ደብተር አወጣና መደመር ጀመረ።

«በጠቅላላ አንድ መቶ ሠላሳ አምስት ፍራንክ።»

ያው ገንዘብህ አሁን እንደገና መመዝገብ ትችላለህ።»

ሰውዬው ከሔደ በኋላ ግራንዴ፣ «አዚህ ገንዘብ ከሌለህ በረሀብ ትሞታለህ። ግን አንድ ዘዴ አለን፤ ስለዚህ ፍጹም ባዶ ኪሣችንን አንሆንም። ድርድር እያልን አንጠራዋለን» አለ።

በጽኑ አሥራት ካምፖቹ ውስጥ ድርድር ማለት እያንዳንዱ ሰው ገንዘብ ለማግኘት የሚችልበት ዘዴ መፍጠር ነበር። የካምፑ ወጥ ቀቃይ ለእሥረኞች የሚቀርበውን ሥጋ ይሸጣል። ሥጋው ወደ ወጥ ቤት ሲደርስ፣ ግማሽ ያህሉን ያስቀራል። ካስቀረው ከፊሉን ወደ ዘበኞች ዘንድ ይወስድና ግብርውን ሚስቶቻቸው ያከናውናሉ። ከፊሉን ደግሞ መግዛት ለሚችሉ እሥረኞች ያመጣል። ወጥ ቀቃዩ ከሚያተርፈው ለወጥ ቤት ዘበኛ ማካፈሉ የማይካድ ነው። ሥጋውን ተሸክሞ ሁልጊዜ የሚመጣው የመጀመሪያው ሕንፃ ወደሆነው ወደእኛው «ልዩ ሕንፃ-ሀ» ነበር።

ስለዚህ ድርድር የተባለበት ምክንያት፣ ወጥ ቀቃዩ ሥጋና ቅቤውን ይሸጣል፣ ዳቦ ጋጋሪው ለዘበኞች የተባሉትን ትናንሽና ረግቾም ዳቦዎች ይሸጣል፣ ልኳንዳ ሠራተኛውም እንደዚሁ ሥጋውን ይሸጣል፣ ጤና ረዳት መርፌውን ይሸጣል፣ ጸሐፊው ጥሩ ሥራ እንዲሰጥህ፣ ወይም ወደቀን ሠራተኝነት እንዲቀይርህ መደለያ ገንዘብ ይቀበላል፣ አትክልተኛው ለጋ አትክልትና ፍራፍሬዎችን ይሸጣል፣ በላቦራቶሪ ውስጥ የሚሠሩት እሥረኞች መድኃኒቶችን በመሸጥና ነቀርሳ፣ ቁምጥና፣ የደም ተቅማጥ፣ ወዘተ ... የሚል የሐሰት ምስክር ወረቀት በመስጠት መጠቀም ይችሉ ነበር። ከዘበኞቹ ቤት አካባቢ ዶሮዎች በመጥለፍ፣ እንቁላልና ሣሙና በመዝረፍ የሠለጠኑም ነበሩ። «የቤት ልጆቹ» ከአሠሪዎቻቸው ቤት እንደቅቤ፣ የቆርቆሮ ፈሣሽ ወተት፣ የዱቄት ወተት፣ ቶኖ፣ ሰርዲን፣ አይብ፣ ወይን ጠጅና የአልኮል መጠጥ በስውር እያጋዙ ያቀርባሉ። /የእኛ ቡድን አንድ ጠርሙስ «ሪካርድ»ና የእንግሊዝ ወይም የአሜሪካ ሲጃራዎች ፍጹም ተለይቶት አያውቅም።/

ግን ጠቃሚ ሆኖ በጣም አደገኛው ድርድር የቁማር ዳኛ መሆን ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ማንኛውም ሕንፃ ሊኖረው የሚችለው ከአምስት ቋማር አጫዋቾች በላይ መሆን እንደሌለበት በሕግ የተደነገገ ነበር። ከእነርሱ አንዱ ለመሆን ከወሰንክ የምሽቱ ጨዋታ ሲጀምር፣ ራስህን ታቀርብና፣ «የቋማር አጫዋች መሆን እፈልጋለሁ።» ትላለህ። ተጫዋቾቹ «እንፈልግም» ይላሉ፣

«ሁላችሁም ናችሁ እንፈልግህም ያላችሁት?!»

«አዎን ሁላችንም ነን»

«መልካም፣ እንግዲያው የአገሌ አገሬን ቦታ ለመተካተ እፈልጋለሁ።» ይልና ወደ ክፍሉ መካከል በመሔድ፣ ከተጠቆሙት ሰዎች ጋር ጨቤ ትገል ይገጥማል። ያሸንፈዳኛ ይሆናል። የቋማር ዳኞች በእያንዳንዱ አርታታ አምስት ከመቶ ያገኛሉ።

ቋማሩ በተጨማሪ ለሌሎች አነስተኛ ድርድሮች ይረዳል። የምንጫወትበትን ተወጥሮ የተዘረጋ ብርድ ልብስ የሚያዘጋጅልን ሰው ይኖራል። እንዲሁም በወለሉ ላይ አግሮቻቸውን አጣጥፈው መቀመጥ ለማይችሉ ተጫዋቾች ትንንሽ መቀመጫዎች የሚያከራይ አንድ ሰው ይኖራል። የፈረንሣይ፣ የአሜሪካ፣ የእንግሊዝና በእጅ የተጠቀለሉ ሲጃራዎችን እንኳ ሳይቀሩ በብርድ ልብስ ላይ, በየፓኬቶቻቸው ደርድረው የሚያስቀምጡ ሲጃራ ሻጮችም ነበሩ። እያንዳንዱ ሲጃራ የራሱ ዋጋ ስለነበረበት፣ ተጫዋቹ አንዱን ሲወስድ፣ የተተመነውን ትክክለኛ ሒሳብ ፓኮው ውስጥ ያስገባል። በተጨማሪም የሚያጨሱትን ለመመልከት የጋዝ መብራቶች /ኩራዞች/ አዘጋጅቶ የሚጠባበቅ ሰውም ነበር። መብራቶቹ የተሠሩት ከወተት መያዣ ጣሳዎች ሆነው በሲባጎ ተንጠልጥለዋል።

አነስተኛ የዕደጥበብ ቁሣቁሶች የሚሠሩም ነበሩ። የኪነ ጥበብ ይዘት ያለው ድርድርም ነበር። አንዳንዶቹ ዓሣ አጥማጆች ከሚይዟቸው የባሕር ኤሊ ልባሶች አንዳንድ ጌጦችን ይቀርፃሉ። ዐሥራ ሦስት ቆሬዎች ያሉት አንድ የኤሊ ልባስ እስከ አራት ፓውንድ ተኩል ሊመዝን ይችላል። የእጅ አምባሮች፣ ጉትቻዎች፣ ሐብሎች፣ የሲጃራ መያዣዎች፣ ማበጠሪያዎች፣ የብሩሽ እጀታዎች ይሠሩባቸዋል። በጣም የምታምር ከግራጫ የኤሊ ልባስ የተሠራች አንዲት ትንሽ ሣጥን አይቻለሁ። ሌሎች የእጅ ባለሙያዎች ደግሞ በደሴቶች ከሚገኙ ኮክኑቶች፣ ከኩበቶችና ከሸክ ቀንዶች፣ ከተለያዩ እንጨቶች ጌጣጌጦች ይሠራሉ። በአንድ ሚስማር እንኳ ሳይጠቀሙ፣ በማስካካት ብቻ በጣም ምርጥ የሆኑ ቁምሣጥን መሰል ቁሳቁሶች ይፈጥራሉ። ከሁሉም በላይ የላቁት ደግሞ የነሐስ ቅርፃ ቅርፆች የሚሠሩት ናቸው። ሠዓሊዎችም ነበሩ። አንድ ዕቃ ለማምረት አንዳንድ ጊዜ የብዙ ሙያተኞችን የቅንጅት ጥረት የሚጠይቅ ነበር። ለምሳሌ ዓሣ አጥማጁ አንድ አጣነባሪ ገደሎ ጥርሱን ወልውሎና አፉን ወጥሮ ያዘጋጃል። ከዚያም የአንጨት ሥራ ባለሙያው በጣም ከለሰለሰው አንዲት እንጨት ለሥዕል

t.me/OLDBOOKSPDF

መቅረጫ በቂ ቦታ ከመካከሏ ላይ በመተው የትንሽ መልህቅ ቅርፅ ይሠራል። መልህቋ ከዓሣ ነባሪው መንጋጋ ላይ ትንጠለጠልና፣ ሠዓሊው ደግሞ በመልህቋ ከፍት ቦታ ላይ ጆሊዩ ደሴቶች በባሕር እንደ ተከበቡ የሚያሣይ ምሥል ይስላል። ከሚወደዱት ውስጥ እንዱ በሮያሌ ደሴት ጫፍና በቅዱስ ዮሲፍ መካከል ባለው የባሕር ወሽመጥ ላይ ፀሐይ በምትጠልቅበት ወቅት ሐይለኛ ጨረሯን ፈንጥቃበት መቅዘፊያዎቻቸውን ያጋጠሙ ስድስት አሥረኞች ራቁታቸውን እንደሆኑ የሚገኙበት አንድ ጀልባና ከእነርሱ ኋላ ደግሞ አውቶማቲክ ጠመንጃ የያዙ ሦስት ዘበኞች ያሉበት ምሥል ሆኖ፣ ከጀልባው ፊት ለፊት ሁለት ሰዎች ከፍ አድርገው ከያዙት ሣጥን ውስጥ አንድ በዱቄት ከረጢት የተጠቀለለ የአሥረኛ አስከሬን ከባሕሩ ውስጥ ሲወድቅ፣ ሬሣውን የሚጠባበቁ ዓሣነባሪዎች እፋቸውን እንደ ከፈቱ ዙሪያውን ሲዋኙ ጭምር ያሳያል። ከሥዕሉ ወረድ ብሎ በስተቀኝ ከጥግ በኩል፣ «የሮያሌ መቃብር» የሚል ጽሑፍ ይነበብበታል።

አነስተኛ ዕደ ጥበቦች የሚሸጡት በዘበኞቹ ቤቶች ነበር። ምርጥ የሆኑት ቅርፆች ብዙ ጊዜ በቅድሚያ ይገዛሉ ወይም በትዕዛዝ ይሠራሉ። ሌላው የሚሸጠው በደሴቶቹ መካከል ሰሚመላለሱ ጀልባዎች ሲሆን፣ ንግዱም በብዛት የተያዘው በነርሱ ነበር። ጽሑፎችን በቁሳቁሶች ላይ የሚቀርፀውም ነበሩ። አንድ ሰው በተሠረጓጎደ አንድ አሮጌ ኩባያ ላይ «የዚህ ኩባያ ባለቤት የዱሳሊዩ ደሴቶች ዝነኛው አሥረኛ ድሬይፈስ ነው፤» ብሎ ቀንና ዓመተምሕረቱን ጭምር ይቀረፅበታል። በማንኪያዎችና የምግብ ሣህኖች ላይም እንዲሁ ያደርጋሉ። የብሪቶን መርከበኞች «ሲዝኒክ» የሚል ስም በላዩ ላይ ለተቀረፀበት ማንኛውም ነገር ልባቸው ወከክ ይላል።

ይህ ንግድ ወደ ደሴቶቹ ብዙ ገንዘብ እንዲጎርፍ ምክንያት በመሆኑ ዘበኞቹ ጣልቃ ለመግባት ፍላጎት አልነበራቸውም። በተጨማሪም ለአሥረኞቹም እያያዝ ቀላል ስለሚሆንና በሥራ ከተጠመዱ የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤቱን ኑሮ በጥሩ ሁኔታ ይለማመዱታል የሚል እምነት ነበረ።

ከእነዚህ ሁሉ ሰዎች ውስጥ የማምለጥ ወሬ ሲነሳ ከመቶው ሦስቱ እጅ እንኳ ደስተኞች አልነበሩም። የዕድሜ ልክ ጽኑ አሥራት የተፈረደባቸውም እንኳ ሳይቀሩ። ብዙኛው መንገድ ወደ ግራንዴ ቴራ፣ ቅዱስ ላውረን፣ ኮሮው፣ ወይም ካየን መላክ ነበር። ይህ የሚደረገው ደግሞ እጭር ቅጣት ላላቸው ብቻ ነበር። የዕድሜ ልክ የተፈረደበት ከሆነ አንድ ግድያ መፈጸም ይኖርበታል። ስለዚህ ልዩ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ወደ ቅዱስ ላውረን ይላካል። ግን ለመሐድም ቢሆን ጥፋተኛ መሆኑን በቅድሚያ ማመን ስለሚኖርበት፣ በግዞት አምስት ዓመት አሥራት የመቀጣት ዕድል ይጠብቀዋል። ከዚህም ሌላ ለማምለጥ መቻሉም አጠራጣሪ ነበር።

በተጨማሪ፣ በሕክምና ሰበብ እንዲላክ መሞከርም ይችላል። የነቀርሳ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሕመምተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ ከቅዱስ ላውረን በግምት ሃምሳ ማይል ከምትሆን ኑቮ ካምፕ ጎብላ ከምትጠራ የነቀርሳ ሕመምተኞች ካምፕ ይላካል።

እንደዚሁም፣ ቁምጥናና የደም ተቅማጥም አለ። እነዚህን በማጭበርበር ለመለከፍ በጣም ቀላል ነበር፣ ግን በዕውነተኛው በሽታ የተያዘ ለሁለት ዓመት ልዩ ከፍል ተገልሎ የመኖር አሰቃቂ አደጋ ይከተለዋል። ጤነኛው ሰው በቀላሉ በእነኚህ በሽታዎች እንደሚለከፍ ቢታወቅም፣ ብዙዎቹ የሚመርጡት አቋራጭ መፍትሔ ይኸው ነበር። የደም ተቅማጥ ደግሞ ከሁሉም ይበልጥ በንክኪ የሚተላለፍ ነው።

አሁን ከእንድ መቶ ሃያ ጓዶቼ ጋር በሕንፃ ቁጥር «ሀ» ውስጥ ኑሮን መሥርቻለሁ። ከዚህ ማነበረሰብ ጋር እንዴት መኖር እንደሚቻል መለማመዱ አስቸጋሪ ነበር። በቅድሚያ አደገኛ መሆንን ግልፅ ማድረግ ይኖርብሃል። አንድ ጊዜ ከፈሩህ በኋላ ደግሞ ከዘበኞች ጋር ባለህ የአቀራረብ ሁኔታ አከብሮታቸውንም እንደምታገኝ ማሰብ አለብህ። እንዳንድ ሥራዎችን ፍጹም መታዘዝ የለብህም፣ ከቀን ሠራተኞች ጋር ለመሥራት መቃወም አለብህ የቁልፍ ያገሮቹን ሥልጣን ፍጹም አሜን ብለህ መቀበል የለብህም፣ ከዘበኛ ጋር ዱላ የሚያማዝዝ እንኳ ቢሆን። ሌሊቱን ሙሉ ቁማር ስትጫወት ካደርክ፣ ስም ሲጠራ መቅረት ትችላለህ። የሣጥናችን (ሕንፃዎቹ ሣጥን እየተባሉ ነበር የሚጠሩት) ታማኝ «አሞት ተኝቷል» ብሎ ይነግርልሃል። በሌሎቹ ሁሉ ሣጥኖች ግን ብዙውን ጊዜ ዘበኞቹ «የታመመውን» ሰው ስም ጠሪ ያደረጉታል። ይህ በእኛ ዘንድ ፍጹም አይሞከርም። ከላይ ጀምሮ እስከታች ያለው የማንኛውም ሰው ጽኑ ፍላጎት፣ ሰላም የሰፈነበት ወህኒ ቤት እንዲሆንለት መሆኑ ግልጽ ነበር።

ደባሌ ግራንዴ፣ ዕድሜው ሠላሳ አምስት የሆነ የማርሴይ ተወላጅ ነበር። እንደ ሐዲድ ብረት ቅጥን ብሎ በጣም ረጅምና ብርቱ ነበር። ጓደኝነታችን ፈረንሣይ ውስጥ ሳለን እንደመሆኑ በተደጋጋሚ በቱሎን፣ በማርሴይና ፓሪስ አዛባቢ ስንገናኝ ቆይተናል። የታወቀ ቁልፍ ሰባሪ ቢሆንም ጥሩ ሰው ነው። ምናልባት በመጠኑም ቢሆን አደገኛ ሊሆን ይችላል።

ዛሬ በሰፈው ከፍል ውስጥ ከምላ ጎደል ብቻየን ያለሁት እኔ ነበርኩ። የሣጥኖች ተጠሪ የሆነው ሰው የሲሚንቶውን ወለል በመጥረግና በመወልወል ላይ ነበር። አንድ ሌላ ሰው ደግሞ ከግራ ዐይኑ ላይ እንዲት መነጥር አጣብቆ ሰዓት ሲገጣጥም ተመለከትኩ። ከተንጠልጣይ አልጋው በላይ ቢያንስ ሠላሳ ሰዓቶች የተንገረገጉበት እንድ መደርደሪያ ነበረው። የሠላሳ ዓመት ሰው ይመስላል፣ ጸጉሩ ግን በጠቅላላው ነጭ ነበር። ወደ አርሱ ቀረብ አልኩና የሚሠራውን እየተመለከትኩ ውይይት ለመከፈት ሞከረኩ። ቀና ብሎ እንኳ አልተመለከተኝም። ይህም ትንሽ በስጨት አደረገኝና ትቸው ገላ መታጠቢያው ቤት አካባቢ ልቀመጥ ወጣሁ። ቲቲ ላ ቤሎቲን ከርታ ጨዋታ ይህ

t.me/OLDBOOKSPDF

እዚያው አገኘሁት። ቀልጣፋ ጣቶቹ ሠላሳ ሁለቱን ካርታዎች በማይታመን ፍጥነት ይሸከሸኳቸዋል። የምትሐተኛ አጀቹን እንቅስቃሴ ሳያቋርጥ፣ «እንዴት ይዞሃል ጓድ፣ ሮያሌን ወደድከው?» አለ።

«በሚገባ፣ ግን ዛሬ በሽቄያለሁ። ከካምፕ አንድወጣ አንድ ትንሽ ድርጊት ልፈጽም መሰለኝ። ከዚያ ሰዓት ከሚያድሰው ሰው ጋር ለመነጋገር ፈልጌ እርሱ ግን ዘጋኝ። »

«ይህን ደጋግመህ ማለት ትችላለህ ፓፒ። ያ ሰው ለማንም ቢሆን ደንታ የሌለው፣ ማንኛውንም ነገር እርግፍ አድርጎ የተወ ነው። ግን ከተፈጸመበት ድርጊት አኳያ ደግሞ እንደዚህ ኮስታራ ቢሆንም አይፈረድበትም። ታውቃለህ፣ የአንድ ዘበኛ ሚስት በማስገደድ ደፍረሃል በሚል ጥርጣሬ በዚህ ልጅ ላይ፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት አይሞላም፣ የሞት ቅጣት ፈረዱበት። ቁልጭ ያለ ሐሰት ነበር። በእርግጥ ሴትየዋን ለረጅም ጊዜ ሲዳራት ቆይቷል። የአንድ ብራቦን ዘበኛ ሚስት ነበረች። እነርሱ ቤት እንደ ቤት ልጅ ሆኖ ሲሠራ፣ ልብስ እንዲያጥብም ሆነ እንዲተኩስ አታደርገውም ነበር። የምትሠራው ራሷ ነበረች፣ ግን የወጣላት ሰነፍ መሆኗን ባል ያውቅ ነበር። ይሁንና ግንኙነታቸውን ምንም ማረጋገጥ ስላልቻለ፣ እጅ ከፍንጅ በመያዝ አጋልጦ ሁለቱንም የሚገድልበትን አንድ ወጥመድ አዘጋጀ። አንድ ቀን ወደ ሥራው ከሔደ ከሁለት ሰዓት በኋላ ጥበቃውን ይተውና አንድ ሌላ ዘበኛ በመጥራት «ከሀገሬ የመጣልኝ ትኩስ የዓሣማ ሥጋ ልጋብዝህ እፈልጋለሁ» በማለት ወደቤት እንዲሔዱ ይጠይቀዋል። መዝጊያውን ከፍቶ እንደገባ የራሱ ተናጋሪ ወፍ፣ ምንጊዜም ዘበኛው ወደቤት ሲመጣ እንደምታደርገው ሁሉ፣ «ጌቶች መጡ!» ብላ ጮኸች። ከመቅፅበት ሚስቲቱ ኡኡታዋን አቀለጠችው። «እርዱኝ! እርዱኝ! እየተደፈርኩ ነው!» ሴትየዋ የአሥረኛውን ከንዶች ራሷ አንቃ እንዳለች ሁለቱ ዘበኞች ወደ ከፍሉ ውስጥ ገቡ። አሥረኛው በመስኮት በኩል ሲዘልል፣ ባልየው ተኮሰበትና ትከሻውን አቆሰለው። ወደቀ፣ ግን ብራቦኑ ሊጨርሰው በመዘጋጀት ላይ እንዳለ ሌላው ዘበኛ መሣሪያውን ነጠቀው። ይህ ልጅ ኮርሲካዊ ነው፣ የተወነጀለውም በሀሰት ነው። ግን ለብራቦኑ ይህን ግልጽ አድርጎ በሚያስረዳበት ደረጃ ላይ ስላልነበረ፣ በማስገደድ የደፈረ በመምሰል ራሱን አጋልጦ አመነ። በሞት እንዲቀጣ ተፈርዶበት ነበር። እንግዳ ነገር አይደለም። የሚገርመው ከዚያ በኋላ የተፈጸመበት ነው።

«በሮያሌ፣ ልዩ ቅጣት የተፈረደባቸው እሥረኞች የሚታሠሩት፣ ከእንገት መቀንጠሻው መሣሪያ ጋር ነበር። በየሳምንቱ፣ ሰያፈውና ረዳቶቹ ይገቡና መሣሪያውን እየገጣጠሙ፣ በጥሩ ሁኔታ መሥራቱን ያረጋገጥ ያህል አንድ ሁለት የሙዝ ግንዶች ይከረታትፋሉ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሰዓት አዳሹም የሞት ፍርድ ለተፈረደባቸው እሥረኞች በተወሰነው ክፍል ውስጥ ከሦስት አረቦችና አንድ የሲሲሊ ተወላጅ ጋር ነበር። አምስቱም በሙሉ ያመለከቱትን የይግባኝ መልስ እየተጠባበቁ ነበር።

«አንድ ቀን ጧት፣ መሣሪያውን ገጣጠሙና የሰዓት አዳሹን መዝጊያ ብርግዳ አድርገው ከፈቱ። ሰያፈዎቹ በላዩ ላይ ዘለሉና እጆቹን ጠፍረው ገመዱን በእግሮቹ ዙሪያ በመጥለፍ ተበተቡት። ከዚያም ኮሌታዎቹን ቀፍፈው አነሡና ወደ ማለዳ ላይ እየጎተቱ አወጡት። ከስለቱ ሥር እንጉቱን በማስተካከል ላይ እንዳለ ነበር፣ የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ ኮኮ ሲክ በማንኛውም ግድያ ሥነ ሥርዓት ላይ መገኘት አለበት በሚለው ሕግ መሠረት ከተፍ ያለው። አንድ ትልቅ ፋኖስ ይዞ ስለነበር፣ ድርጊቱ ወደሚከናወንበት አቅጣጫ ሲያነጣጥር፣ ዘበኞች የሰዓት አዳሹን አንገት ሊቆርጡ ነበር።

«አቁሙ! አቁሙ!» እያለ ባሮ ጮኸ።

«ጠጣም ከመደንገጡ የተነሣ መናገር የቻለው ይሆንኑ ብቻ ነበር። ፋኖሱን ወዲያ ጣለና ዘበኞቹንና ሰያፈዎቹን ገፈታትሮ በማለፍ ሰውየውን ራሱ ፈታው። ከዚያ በኋላ ነበር፣ ጤና ረዳት ጠርቶ ሁኔታውን እየተከታተልክ አብረኸው እንድትቆይ፣ ትንሽ ሩም ስጠው። ደግሞ እናንተ፣ ደደቦች፣ ሒዱና ሬንካሶን አምጡት። ዛሬ እንድትሰይፉ የታዘዛችሁት እርሱን ነበር» የሚል ትዕዛዝ አሰተላለፈ።

«በሚቀጥለው ቀን የሰዓት አዳሹ ፀጉር፣ ልኪ ዛሬ እንደሚታየው ነጭ ሆነ። ጠበቃ የቅመለት ከካልቪ ቀበሌ የመጣ አንድ ዘበኛ፣ የተፈጸመበትን ድርጊት በዝርዝር ጠቅሶ ለፍርድ ሚኒስቴር አመለከተለት። ሰውዬው ከሞት ተረፈና ቅጣቱ ወደ ዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተለወጠለት። ከዚያ ጀምሮ ጊዜውን የሚያሳልፈው የዘበኞቹን ሰዓት በማደስ ነው። ሰሰ ሆኖበታል ለምን ትንሽ ለየት ያለ ሰው እንደሆነ ገባህ?»

በየቀኑ ስለ አዲሱ ኑሮዬ በመጠኑ እማራለሁ። በሣጥን «ሀ» ውስጥ ባለፈው ጊዜ በፈጸሟቸው ድርጊቶችም ሆነ፣ አሁንም በካምፑ አካባቢ ከሚሠሯቸው አንዳንድ ነገሮች አንጻር፣ ማንም ሊቋቋማቸው የማይቻሉ ሰዎች የተከማቹበት ነበር።

አንድ ቀን ጧት፣ በኮከነት አትክልት ሥራ ላይ እንዲሰማራ፣ የዮሐንስ ካስቴሊ ስም ከሠራተኞቹ ሊስት ውስጥ ተጠራ። ከሰልፉ ፈንጠር ብሎ ወጣና «ምንድን ነው? ሥራ ላይ ልትመድቡኝ ነው እንዴ?» አለ።

«አዎ» አለ የሠራተኞቹ ኃላፊ የሆነው ዘበኛ። «ያውልህ፣ ይህን ደማ ተሸከም።» ካስቴሊ ቅዝዝ ብሎ ተመለከተው። «ዕብድ መሆን አለብህ፣ እኔ ከማርሴይ የመጣሁ ኮርሲካዊ ነኝ። በኮርሲካ፣ እንዲህ ያሉ መሣሪያዎችን ባሕር ውስጥ ነው የምንወረውረው፣ ማርሴይ ደግሞ መኖራቸውን እንኳ አናውቅም። ስለዚህ ደማህን ይዘህ ወደምትሔድበት ብትሔድ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ወጣቱ ዘበኛ ስለ እኛ ቡድን ግና አላወቀም፣ የዶማውን እጀታ ጨብጦ በካስቴሊ ጭንቅላት ላይ ሊሰነዝር ሞከረ። አንድ መዶ ሐያ ሰዎች በአንድ ድምፅ፣ «በስብሰ፣ ንካውና አንቲም ሟች ነህ» ብለን ጮህንበት።

«ከሰልፍ ተበተኑ!» አለና ግራንዴ፣ ለማጥቃት ጥግ ይዘው የነበሩትን ዘበኞች ከምንም ሣንቆጥር ጥለናቸው ወደ ሣጥናችን ተመልሰን ሔድን።

ሣጥን «ለ» ወደ ሥራ ለመሔድ ሲሰለፍ፣ ሣጥን «ሐ»ም ተከተለ። ጥቂት ዘበኞች ወደ እኛ ሣጥን መጡና የፍርግርጉን በር ዘጉት። ከአንድ ሰዓት በኋላ አውቶማቲክ ጠመንጃ በእጃቸው የወደሩ ዐርባ ዘበኞች ከበሩ ዳርና ዳር ቆሙ። ለሥራ ቁጥጥር ጉበኝት ወደ ዲያብሎስ ደሴት በዐሥራ ሁለት ሰዓት ሒዶ ከነበረው ዋና አዛዥ በስተቀር ረዳት የወህኒ አዛዡ፣ የዘበኞቹ ኃላፊ፣ ዘበኞቹ፣ ሁሉም አዚያው ነበሩ።

«ዳቼሊ! ሰዎቹን አንድ በአንድ ጥራልኝ» አለ የወህኒ ቤቱ ምክትል አዛዥ።

«ግራንዴ?»

«አለሁ።»

«ወደዚህ ውጣ።»

ወጣና ከዐርባዎቹ ዘበኞች መካከል ገባ።

«ወደ ሥራ ሒድ» አለው ዳቼሊ።

«አልችልም።»

«አምቢ አልከ?»

«አይደለም እምቢ ማለቴ ሳይሆን ታምሚያለሁ።»

«ከመቼ ጀምሮ? በስም ጥሪ ወቅት አላመለከትከም።»

«ዛሬ ጧት አላመመኝም ነበር። አሁን ግን አምኛል።»

በመጀመሪያ የተጠሩት ስድሳዎቹ በሙሉ ልክ እንደዚህ አሉ። አንድ ሰው ብቻ ምንም ሰበብ ሳያቀርብ አሻፈረኝ አለ። ምናልባት ወደ ቅጹስ ላውረን ሒዶ ልዩ ፍርድ ቤት ለመቅረብ ተመኝቶ ይሆናል። «አምቢ አልከ?» ተብሎ በሚጠየቅበት ወቅት፣ «አዎ፣ አምቢ» ሲል መለሰ።

«ለምን?»

«ምክንያቱም እናንተን ስመለከት ያስታውከኛል። እናንተን ለመስላችሁ አበቦች በጠቅላላው መሥራት አልፈልግም።»

ጠቡ እየተካረረ ሔደ። ዘበኞቹ፣ በተለይ ወጣት ዘበኞቹ በእሥረኞች መዋረዳቸውን መቋቋም አቃታቸው። የሚጠባበቁት፣ በጠመንጃዎቻቸው እርምጃ ለመውሰድ የሚያበቃቸው አንድ የትእዛዝ ምልክት እስኪሰጣቸው ነበር።

«ሰማችሁን የተጠራችሁት በሙሉ ልብሶቻችሁን አውልቁ! ከዚያም ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ፈላችሁ ሒዱ።» ልብሶቻችን ወደ መሬት ሲወድቁ፣ አልፎ አልፎ የጩቤ ኳኳታ መስማት ይቻላል። ከዚያም ወዲያው ዶክተሩ መጣ።

«እሺ ቁሙ። ዶክተር፣ እባክህ እነዚህን ሰዎች መርምር። በእርግጥ ያልታመሙት ወደ ጨለማ ቤት ይላካሉ። ሌሎቹ ሣጥናቸው ውስጥ ይቆያሉ።»

«ስድሳውም የታመሙ ናቸው?»

«አዎ ዶክተር፣ ለመሥራት እሻፈረኝ ብሎ እዚያ ወዲያ ካለው ሌላ።»

ከሰልፉ በመጀመሪያ የነበረውን፣ «ግራንዴ፣ አንተ ደግሞ ምንህን አሞህ ነው?» አለው ዶክተሩ።

«የሆድ ቁርጠት አሞኛል ዶክተር። ሆዴን የሚያሳምሙኝም ዘበኞቹ ናቸው። እዚህ ያለነው በሙሉ ረጅም ቅጣት ያለብን፣ ብዙዎቻችን ዕድሜ ልክ የተፈረደብን ነን። የማምለጥ ተስፋ የለንም፣ እንዳንድ ማካካሻ ካልተደረገልን በስተቀር ሌላ የምንቋቋምበት መንገድ የለንም። ዛሬ ጧት አንድ ዘበኛ ጓደኛችንን በዶማ እጅታ ሲመታው ተጋበዘበት። ራስን ለመከላከል የሚቀርብ አቤቱታ እንዳይመስል እንጂ ሥረኛው አንድ ጣቱንም አላነሣበትም። የተናገረው ቢኖር በዶማ መጠቀም አለመቻሉን ብቻ ነበር። እንግዲህ ለዚህ የሆድ ቁርጠት ወረርሽኝ ምክንያቱ ይኸው ነው። አሰኪ ራስህ ፍርድ።»

ዶክተሩ ወደ መሬት አቀርቅሮ ለአንድ ደቂቃ ያህል ካሰበ በኋላ፣ «ጤና ረዳት፣ የሚከተለውን ጻፍ፣ በተላላፊ የሆድ ቁርጠት መበከል ምክንያት ዛሬ ጧት አምናል ብለው ላመለከቱት በሙሉ፣ ለተቅማጥ የሚሆን ሐያ ግራም ሰልፌት ሶዳ እንዲሰጣቸው የሕክምና ቤፍሉን ዘበኛ አዝዣለሁ። እምቢተኛውን በሆስፒታል ውስጥ በቅርብ ክትትል እንዲመረመር ውሰደው። ለመሥራት እምቢተኝነቱን የገለጸው የተሟላ ሕሊና ይዞ መሆን አለመሆኑን ልንደርስበት እንችላለን» አለ።

ከዚያም ቀኝ ኋላ ዞረና መንገዱን ቀጠለ።

«ሁሉም ሰው ወደ ውስጥ!» ብሎ ምክትል አዛዡ ጮኸ።

«ልብሶቻችሁን አንሱ። ጩቤዎቻችሁን እንዳትረሱ።» ቀሪውን ቀን በሙሉ ሁሉም ሰው በሣጥኑ ውስጥ አረፈ። ማንኛውም ሰው፣ ዳቦአችንን የሚሸጥልን እንኳ ሳይቀር ወደ ውጭ መውጣት ተከለከለ። ወደ ቀትር ላይ፣ በሾርባ ፋንታ ከአፍ እስከ ገደፉ በተቅማጥ መድኃኒት የተሞላ አንድ የእንጨት ባልዲ ሁለት ጤና ረዳቶችና የሕክምና ከፍሉ ዘበኛ ወደ አካባቢው አመጡ። መድኃኒቱን ሦስት ሰዎች ብቻ ወሰዱ። አራተኛው ያለጥርጥር የሚጥል በሽታ የያዘው በማስመሰል ተንገዳግዶ ባልዲው ላይ ሲወድቅበት፣ የተቅማጥ መድኃኒቱን የያዘው ባልዲ በአየር ላይ ተገለባብጦ መድኃኒቱ ወለሉን አለበሰው። ዘበኞች የፈሰሰውን ጠራረጉና ውዝግቡም በዚሁ ተዘጋ።

የሐንስ ካስቴሊ ከእኛ ጋር ምሳ ለመብላት መጥቶ፣ ከለዓት በኋላ ከእርሱ ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

ሳወራ ቆየሁ። ውድ ቆዳዎችን በመሥረቅ ከተወነጀለ ሉዊ ግራቮን ከተባለ አንድ የቱሉን ተወላጅ ጋር ነበር በጉርብትና የሚኖሩት። ስለማምለጥ አንዳንድ ነገሮችን በማነሣበት ወቅት ዐይኖቹ ተጉረጠረጡ።

«ባለፈው ዓመት ለማምለጥ ምንም አልቀረኝም ነበር። ግን ከሸፈብኝ። ያለጥርጥር አንተ እዚህ ቦታ የምትቆይ ነህ ብዬ አላስብም። ግን እዚህ ስለማምለጥ ብታወራ የአብራይስጥ ቋንቋ እንደ መናገር ይቆጠራል። በደሴቶቹ ያሉትን አሥረኞች ገና የተረዳሃቸው አይመስለኝም። እዚህ ከመቶ ዘጠናዎቹ በማያሻማ ሁኔታ ደስተኞች ናቸው። ከዚህም ሌላ ምንም ነገር ማድረግ ብትፈልግ አንድም ሰው አያጋልጥህም። ሰው አንካ ብትገድል፣ አንድም ምስክር አይገኝም። አንድ ሰው ምንም ነገር ያድርግ፣ ሁሉም ሰው ተረባርቦ ከአደጋ ያድነዋል። የደሴቶቹ አሥረኞች ፍርሃታቸው አንድ ነገር ብቻ ነው። ይህም አሥረኛ ካመለጠ ሊደርስ የሚችለው ችግር ነው። በዚህም ምክንያት የማያቋርጥ ፍተሻ ይኖራል፣ ካርታ የሚባል ነገር አይኖርም። በፍተሻ ጊዜ መሣሪያዎቹን ስለሚያወድሟቸው፣ ሙዚቃ፣ ዳማም ሆነ ቼዝ፣ መጻሕፍት አይኖሩም፣ ምንም ነገር አይኖርም። አነስተኛ ዕደ ጥበቦችን መሥራት አንካ አይቻልም። ማንኛውም ነገር ቁጥ ይላል። በየጊዜው ይፈተሻሉ። ስኳር፣ ዘይት፣ ሥጋ፣ ቅቦ ይቼ ሁሉ ይጠፋል። በየጊዜው ከደሴቶቹ ማምለጥ ቢካሔድም፣ ሰዎቹ ግን ገና ግራንዴቴሬ ሲደርሱ ይያዛሉ። ሆኖም በአስተዳደሩ አመለካከት ማምለጡ እንደተሳካ ይቆጠራል። ሰዎቹ አመለጡ፣ አላመለጡ፣ በዘበኞቹ ላይ የገሃነም ፈተና ይደርስባቸዋል። እነርሱ በተራቸው ደግሞ በእኛ ይወጡታል» አለ።

በጥንቃቄ ካዳመጥኩ በኋላ ዳግመኛ ስለ ጉዳዩ ምንም አላነሣሁም። እንደዚህ ይሆናል ብዬ ፍጹም አላሰብኩም ነበር።

«በአጭሩ» አለ ካስቴሊ «ለማምለጥ ዝግጅት አደርጋለሁ በምትልበት ቀን ተጠንቀቅ። የቅርብ ጓደኛህ ካልሆነ በስተቀር ከማንም ሰው ጋር ከመወያየትህ በፊት ደጋግመህ አስብ።»

ዮሐንስ ካስቴሊ በዘረፋ ሙያ የበሰለ ልዩ ወኔ ያለው ጎበዝና ብልህ ነበር። ረብሻ አይወድም። የቅፅል ስሙ «ጥንታዊው» ነበር። የሚታጠበው በማርሴይ ሣሙና ብቻ ሲሆን፣ እኔ በፓልሞሊቭ ከታጠብኩ፣ «ሰማ፣ ልክ እንደ ሌላ ነገር ትሸትታለህሳ! በሸርሙጣች ሣሙና ታጠብክ እንዴ!» ይለኝ ነበር። ምን ይሆናል ዕድሜው ሃምሳ ሁለት ሆኗል። ግን እንደ ብረት የጠነከረ ስሜቱን ማየት ራሱ ደስታ ይሰጥ ነበር። እንድ ቀን እንደዚህ ሲል ገለጸልኝ። «ፓፒዮ፣ ልክ እንደ ልጄ ነው የማይህ። የደሴቶቹ ኑሮ ለአንተ አይሆንም። አቋምህን ለመጠበቅ ጥሩ እድርገህ ተመግብ፣ ግን የደሴቱን ኑሮ ተቀበለህ እዚሁ መርጋት ፍጹም አይኖርብህም። ከእነዚህ ሁሉ አሥረኞች መካከል አንተን

t.me/OLDBOOKSPDF

የመሰሉ ስድስት አይሞሉም። ከእነርሱ ውስጥ ብዙዎቹ ወደ ግራንዴቴሬ ለመሔድ አንዲችሉና ከዚያም እንዲያመልጡ ያላቸውን ሀብት ለመከስከስ ፈቃደኞች ናቸው። ግን ከዚህ ለማምለጥ ማንም ሰው በሐሳቡ እንኳ አይከሰትለትም።»

አዘውንቱ ካስቴሊ አንዳንድ ጥሩ ምክሮችን ለገሠኘ። «በተቻለ መጠን እንግሊዝኛ ተማር፣ በስፓኝ ቋንቋም ከስፓኞች ጋር የቻልከውን ያህል አዘውትረህ ተነጋገር» አለኝ። ከፈረንሣይኛ ወደ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት መፍቻና በሐያ አራት ምዕራፍ የተከፈለ የስፓኝ ቋንቋ መማሪያ አንድ መጽሐፍ አዋሰኝ። ስለ ማምለጥ ብዙ ድርሳናት የሚያወጡና አድሚጋ ወደ ሃምሳ አመት የሚጠጋ ጋርዴ የተባለ ከማርሴይ የመጣ አንድ ጥሩ ጓደኛ ነበረው። እንዴ ከፖርቱጋሎች አሰታቂ ወህኒ ቤት፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ ከግራንዴቴሬ ሰሁለት ጊዜ አምልጧል። በጉዳዩ ላይ አንድ አስተያየት አመጣ፣ ዮሐንስ ካስቴለም ሌላ አመጣ፣ አሁንም ግራቮን ሌላ አመጣ፣ የሁሉም የተለያየ ሆነ። ከዚያን ቀን ጀምሮ በራሴ ጠንቅ መወሰን እንጂ ስለ ሁኔታው ማውራት አቆምኩ።

የተስማማሁበት ብቸኛው ነገር ቢኖር፣ ሩምገር ጨዋታ፣ ገንዘብ በማስገኘት ረገድ ከማስደሰቱ በስተቀር በጣም አደገኛ መሆኑ ነበር። ከመጀመሪያው ረብሻ ቆስቋሽ ጋር የጨቢ ጦርነት ለመግጠም በማንኛውም ወቅት ትገኛለህ።

ባለፈው ምሽት ከተመለከትኳቸው ነገሮች የተነሳ ለሣጥኔ ሰዎች አንድ ትዕይንት አቀረብኩ። ከቶሎስ ቀበሌ የመጣ አንድ ደቃቃ ሰው፣ ከኒምስ የመጣ አንድ ሌላ ሰው ሲደበድብ ይጋበዝ ነበር። የኮሳሳው ሰው ቅፅል ስም ሣርዲን ሲሆን፣ ከኒምስ ቀበሌ የመጣው ሰዮ ደግሞ መሶን ይባላል። መሶን ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ጨቢውን በእጁ እንደጨበጠ መተላለፊያው መኒከል ተገትሯል።

«ለአንድ ሰዓት ሃያ አምስት ፍራንክ ክፈለኝ፣ አለዚያ አትጫወትም።»

«ካርታ ለመጫወት ማንም ሰው ምን ጊዜም ቢሆን ከፍሎ አያውቅም። ለምን ቦአኑ ይጀመራል? ሄደህ ሐብታሞቹን ታገል።»

«አስፈላጊ ግድ የለም። ክፈል፣ አለበለዚያ አትጫወትም፣ ወይም ይዋጣልን።»

«ጥሩ አሰሻም»

«ሣጨት ነሃ»

«ሂም፣ ማምለጥ ምን እንደሆነ ፍጹም በማያውቅ አንተን በመሰለ ሰው ተጨናግፎብኛል አደጋ ላይ መውደቅ አልፈልግም። እኔ ማምለጥ የምፈልግ ሰው ነኝ። እዚህ የለህት ለመግደል ወይም ለመገደል አይደለም።»

ምን እንደሚከሰስ ለማየት ሁላችንም እየተጠባበቅን ነበር። «ኮሳሳው ሰው ውኔ አለው» አለ ግራንያ። «በጣም ፀጥፎ ነው የሚሆነው፣ ጣልቃ መግባት አልችልም።» ጨቢዬን አዘጋጀሁና ከጭኔ ስር አስቀመጥኩ። የተፋጠጥኩት ከግራንዴ

t.me/OLDBOOKSPDF

አልጋ ላይ ነበር።

«አሺ ማሬጩት፣» ከአምስት ቀበሌ የመጣው ሰው ቀጠለ፣ «ታዲያ ምን ትላለህ?» አለና አንድ አርምኛ ወደ ሣርዲን ተረብ አለ።

«ዝም በል ሙቶን፤ ሰውዬውን ለቀቅ አድርገው!» አልኩ።

«አበደሃል እንዴ ጋኒየ?» አለ ግራንዴ።

አሁንም ጩቤዬን በግራ ባቴ ስር አድርጌ እጅታውን እንደጨበጥኩ ተቀምጬ፣ «እይደለም፣ አብድ አይደለሁም» አልኩና ከዚያም ከፍ ባለ ድምጽ «አዳምጥ ሙቶን! ከመጣላታችን በፊት በልቤ ውስጥ የሚጉላላ አንድ ነገር እንዲወጣልኝ አፈልጋለሁ። በጣም ድንቅ፣ በጣም ውድ የሆነው ዕውነተኛውና ብቸኛው ነገር ከዚህ ግምለጥ ሆኖ ሳለ እዚህ ሣጥን ውስጥ ግን፣ ከብር እንደሌለው ለመገንዘብ ችያለሁ። ለግምለጥ ሲል ሕይወቱን ለእሩጋ ለማጋለጥ ወኔ ያለውና አምላኬ መሆኑን ያስመሰከረ ማንኛውም ሰው መከበር የሚገባው ይመስለኛል። በዚህ የሚይስማማ እዚህ አለ? ፀጥታ ሠፈነ። «በዙ ሕጎች አሏችሁ፣ ግን ብጣም ተፈላጊው ይጎድላችኋል። የማከበር ግዴታ ብቻ ሳይሆን፣ የሚያመልጥን ሰው የመርዳትና የመገፋፋትም ኃላፊነት ጭምር መኖር ይኖርበታል። ከመካከላችሁ ብዙዎቻችሁ ኑሯችሁን እዚሁ ለመግፋት መወሰናችሁን ዐውቃለሁ። ሆኖም አዲስ ኑሮ ለመጀመር ቆራጥነት ባይኖራችሁም፣ ቢያንስ ይህን ለሚያደርጉት ትንሽ አክብሮት ይኑራችሁ። ይህን ሕግ በሚዘነጋ ማንም ሰው ላይ አስከፊ መዘገ እንደሚከተልበን ላረጋግጥ እቸላለሁ። እሺ በል ሙቶን። አንቀጥል!»

ጩቤዬን እንደጨበጥኩ ወደ መተላለፊያው ዘለልኩ። ግን ሙቶን ጩቤውን ጣለና፣ «ልክ ነህ ጋኒዮ፣ ግን ጩቤ መሰንዘር አልፈልግም። ማሬጩት አለመሆኔን ለማስመስከር ያህል ግን በቡጢ ልግጠምህ» አለ።

ጩቤዬን ለግራንዴ ሰጠሁና፣ ለሐያ ደቂቃ ያህል ልክ እንደ አበዱ ውሾች ስንራኮት ቆየን። ጭንቅላቱ ላይ ባቀመስኩት አንድ ጥሩ ቡጢ ላሸንፈው ቻልኩ። ፊት መታጠቢያው ላይ ጎነ ለጎን ቆመን በደም የተጨማለቁ ፊቶቻችንን በመታጠብ ሶድ እንጸሰን ነበር ሙቶን፤ «ሐቅ ነው፣ በእነዚህ ደሴቶች ተቆራምደን እናልቃለን። እዚህ ዐሥራ አምስት ዓመት ኖኖናል፣ ግን በሺህ የሚቆጠረውን ፍራንኬን ለእንድ ጊዜ አንኳ ሰማምለጫ አላጠፋሁትም። ይህም ጥሩ አልነበረም» ያለው።

ወደ ሣጥኔ ስመለስ ግራንዴና ጋልጋኒ ተጠመጠሙብኝ። «ሰውን ሁሉ እንደዚያ አድርገህ የምትሳደበው አብደሃል እንዴ? አንድ ሰው አንገትህን ለመቁረጥ ወደ መተላለፊያው ሳይዘል መቅረቱም ተአምር ነበር» አሉ።

«ተአምር አልነበረም። ትክክል መሆንህን ነገሩት የእኛ ቡድን ሰዎች ሁልጊዜ በሐሳብህ ይሰማማሉ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«እንደዚያ ሊሆን ይችላል» አለ ግራንዴ፤ «ግን በዚህ አሳተ ገሞራ በመሰለ አካባቢ ራሴን መቆጣጠር ይኖርብኛል» ምሽቱን ሁሉ ኦሥረኞች ሊያነጋግሩኝ ጎራ ይላሉ። በኢጋጣሚ የመጡ በመምሰል ዘው ይሉና፣ የባጡን የቆጡን አውርተው ሲሔዱ ሲሉ «ፓፒ ልክ ነበርክ እኮ» ይላሉ። ከዚህ ግጭት በኋላ፣ ሰዎች ስለ እኔ ያላቸው ግምት ከፍተኛ ሆነ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ከታወቁት ጎበዞች እንደ አንዱ ብገመትም፣ በቅድሚያ ሳልገመግምና ከኦሥረኞቹ ወይም ከደጋፊዎቻቸው ጋር ሳልወያይ ምንም ነገር እንደማልቀበል ጓደኞቼ ተገነዘቡ። የቁማር ዳኛ ስሆን፣ አነስተኛ ረብሻዎች መኖራቸውንና አንድ ትእዛዝ በማስተላልፍበትም ወቅት ቶሎ እንደሚቀበሉኝ ለማስተዋል ቻልኩ።

ከሠላሳ የበለጡ ተጫዋቾች ከብበውት ግራንዴ ጨዋታ እያካሔደ ነበር። እኔም አጠገቡ ከአንድ ሰው ጋር እያወራሁ ነበር። ጩኸትና ትርምስ ጨዋታውን አቋረጠው። ነገሩ ምን እንደሆነ ለመጠየቅ ሁሉም ሰው ብድግ አለ። ካርሊኖ የተባለ አንድ ኢጣሊያዊ ተገድሎ ነበር። ዘበኞችን መጥራት ይገባው እንደሆነ የሣጥናችን ተጠሪ ጥያቄ አቀረበ። አልሆነም። ካርሊኖ አንዴ ሞቷል፣ ምንም የሚደረግ ነገር የለም። ጧት በስም ጥሪ ወቅት ዘበኞችን መጥራት እንደሚችል ተነገረው።

«ማንም ሰው ምንም ነገር አልሰማም። ጧት የሰዓት ደወል ሲመታ ሞቷል ብለህ አመልክት» አለው ግራንዴ። ሁሉም ወደ ጨዋታው ተመለሰ።

ግድያ መፈጸሙን ዘበኞች በሚያውቁበት ወቅት ምን እንደሚሆን ለማየት ጓጉቼ ነበር። የመጀመሪያው ደወል በዐሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ተደወለ። በዐሥራ ሁለት ሰዓት ሁለተኛው ተደወለና ቡና መጣልን። በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ሦስተኛው ከተደወለ በኋላ ዘወትር እንደምናደርገው ሰስም ጥሪ ወደ ውጭ መውጣት ነበረብን። በሁለተኛው ደወል ቡናችንን ላመጣልን ዘበኛ፣ የከፍላችን ተጠሪ «ጌታዬ፣ አንድ ሰው ተገድሏል» አለው።

«ማነው?»

«ካርሊኖ»

«አሺ።»

ከዐሥር ደቂቃ በኋላ ከአንድ ቃሬዛ ጋር ስድስት ዘበኞች ብቅ አሉ።

«የሞተው ሰውዬ የት ነው?»

«ሕዚያ ማዶ።»

ጩቤው ተንጠልጣይ የብርድልብስ አልጋውን አልፎ በካርሊኖ ጀርባ ውስጥ ሰምጧል። መዘዙና ወደውጭ አወጡት።

«አናንተ ሁለታችሁ ወደ ውጭ ውሰዱት።» ሁለት ዘበኞች አነሱት። ሦስተኛው ደወል ተደወለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በደም የተበከለውን ጩቤ አሁንም በእጁ እንደያዘ የዘበኞቹ ኃላፊ፣ ሁሉም ሰው ለስም ጥሪ ወደ ውጭ ታምጣለህ ብሎ ማመካኘት ዛሬ አይቻልም» አለ። ሰው በሙሉ ወደ ውጭ ወጣ። የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥና የዘበኞቹ ኃላፊዎች የስም ጥሪውን አከሉዱ። ካርሊኖ ስም ጋ ሲደርሱ የከፍላችን ተጠሪ፣ «ሊሊት ሞቶ፣ ወደ ሬሣ ማረፊያ ቤት ተወስዷል» አለ።

«እሺ» አለ የስም ጥሪውን የያዘው ዘበኛ።

ሁሉም ሰው ተፈትሾ ሲያበቃ፣ የዘበኞቹ ኃላፊ ጩቤዋን አነሣና «ይሀን ጩቤ የሚያውቅ ሰው አለ?» ሲል ጠየቀ። መልስ የለም። «ገዳዩን ያየ ሰው አለ?» ረጭ ያለ ጸጥታ።

«ስለዚህ እንደ ተለመደው ገዳዩን የሚያውቅ ማንም ሰው የለም። እጆቻችሁን ከኪሶቻችሁ አውጥታችሁ በእኔ ፊት አለፉና ከዚያ ወደየሥራችሁ ተሠማሩ፣ ዘወትር እንደዚሁ ነው ጌታዬ፣ ማን እንዳደረገው የሚታወቅበት መንገድ የለም» አለ ጠያቂው።

«መልካም፣ ፋይል አድርገው» አለና አዛዡ፣ «ማን ጩቤውን ካርሊኖ የተገደለበት መሣሪያ መሆኑን የሚያመለክት ጽሑፍ በላዩ ላይ ጽፈህ አስቀምጥ» አለ።

በታ፣ ይቺው ነበር። ሌሊቱን ሙሉ ፍጥጥ ብዬ በማደሬ ወደ ሣጥኔ ተመለስኩና ተኛሁ። በማሸለብም ላይ እያለሁ፣ «አንድ ኢሥረኛ ምንድነው? ቢገደል እንኳ የገደለው ማን መሆኑን ለማወቅ ችግር ውስጥ የሚገባ ማንም ሰው የለም። እስተዳደሩም ቅንጣት ያህል አልተጨነቀም። ከአጋድ ውሻ ያልተሻለ አንድ ተራ ኢሥረኛ ነው ...» እያልኩ አሰላስል ነበር።

ሰኞ የፅዳት ሠራተኛ ሆኜ ሥራየን ለመቀጠል ወሰንኩ። ጧት በአንድ ሰዓት ተኩል፣ ከአንድ ሊላ ሰው ጋር በመሆን ከሕንፃችን ውስጥ ባልዲዎቹን አወጣሁ። ሕጉ የሚያዘው ወደ ባሕሩ ውስጥ እንድናራግፉቸው ነበረ። ግን ከኮረብታው ጫፍ ወደ ውሃው ቁልቁል የሚወርድ በሲሚንቶ የተሠራ አንድ ገንዳ አጠገብ እንዲቆየን ጎሾች ለሚያግድ አንድ እረኛ ገንዘብ ከፈልን። ሐያ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ባልዲዎቹን ገንዳው ውስጥ አራግፈናቸው ነበር። ቆሻሻውን ቁልቁል ለማውረድ ከአንድ ትልቅ በርሜል የጪው ውሃ እየቀዳን በማፍሰስ በአንድ ጠንካራ መጥረጊያ ገፋነው። እረኛው ጥቁር የማርቲኒክ ተወላጅ፣ የልብ የሚያደርስ ሰው ስለነበር፣ ለውሃው በቀን ሐያ ፍራንክ ሳንከፍለው ነበር። በመጀመሪያው የሥራ ቀኔ እነዚያን ባልዲዎች መሸከሙ እጅግ በጣም ያሳምም ነበር። ግን ወዳያውኑ ተለማመድኩት።

አዲሱ ጓደኛየ አደገኛ እንደነበረ ጋልጋኒ ቢያስጠነቅቀኝም፣ ሰውየው በጣም ተግባቢ ነበር። በደሴቶቹ ሰባት ሰዎች ገድሏል ይባላል። «ንግዱ» ቆሻሻ መሸጥ ሲሆን፣ እያንዳንዱ አትክልተኛ የራሱን ማዳበሪያ ያጠራቅም ነበር። አንድ ቦይ ይቆፍርና ደረቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቅጠልና ሣር በመያልደል፣ አንድ ሁለት ባልዲ ቆሻሻ ያፈስስለታል። ለብቻ ሆኖ ማድረግ እንደማይቻል ግልጽ ነበር፤ ስለዚህ እኔ አረዳዋለሁ። አትክልቶቹን በመበከል የደም ተቅማጥ ማስተላለፉን አውቃለሁና አሠራሩ ስሕተት ነበር። አንድ ጊዜ በሚገባ ከተዋወቅኩት በኋላ ይሆን አድርጎት ላስተዋው ወሰንኩ። ከዚህ ሥራ ያጣውን ትርፍ እኔው ልከፍለው አሰብኩ። ስለ ዓሣ ማጥመድ ሥራ ጠየቅኩት፤ ግን ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር አላውቅም አለ። በወደቡ ከሚገኘው ቻፓር ወይም አንድ ከሆነ ሰው እርዳታ ማግኘት ይኖርብኛል።

ሥራዬን በምጨርስበት ወቅት ሙልጭ አድርጌ ሰውነቴን እታጠብና ቁምጣ ሱሪየን ለብሼ ደስ ባለኝ ወቅት ዓሣ ለማጥመድ እሔዳለሁ። አንድ ግዴታ ብቻ አለ። ቀትር ሲሆን ወደ ካምፕ መመለስ ነበረብኝ። ቻፓር መንጠቆና በትር አዘጋጀልኝ። የያዝኳቸውን ዓሣዎች በአንድ ሽቦ ለክቼ ስመለስ፣ ከአንድ ዘበኛ ሚስት ሰላምታ ሳላገኝ የቀረሁበት ቀን እምብዛም ነበር። ሁሉም በስማ ያውቁኛል። «ፓፒዮ፣ እስኪ አራት ፓውንድ ዓሣ ሸጥልኝ?»

«ታምመሻል?»

«አልታመምኩም።»

«የታመመ ልጅ አለሽ?»

«የለኝም።»

«እንግዲያውስ ከዓሣዎቹ አንዱንም ልሸጥልሽ አልችልም።» ብዙ ጊዜ በካምፕ ውስጥ ለሚገኙ ጓደኞቼም ጭምር የሚበቃኝን ያህል አይዛለሁ። ዳቦ፣ አትክልትና ፍራፍሬም አለውጥባቸዋለሁ። ደባሎቼና እኔ ቢያንስ በቀን አንድ ጊዜ ዓሣ እንበላለን። አንድ ጊዜ በርካታ የተለያዩ የዓሣ ዘሮች ይገቼ በአዛዡ ባሮ ቤት በማልፍበት ወቅት፣ አንዲት ወፍራም ሴት ወደ ውጭ ብቅ ብላ፤ «ግሩም ይዘሃል ፓፒዮ። ባሕሩ በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ፣ ማንም ሰው አንዳንተ አልተሳካለትም። ዓሣ የሚባል ካገኘሁ ሁለት ሳምንት ሆነኝ። አንተ ደግሞ መሸጥ ነውር ነው ትል ይሆናል። ከዘበኞቹ ሚስቶች ለአንዷም ዓሣዎችህን እንደማትሸጥላቸው ባሌ ይነግረኛል» አለች።

«ትክክል ነው እሜቴ። ግን ለእርስዎ የተለየ አስተያየት ማድረግ ይኖርብኛል።»

«ለምን?»

«ምክንያቱም ከክብደት በላይ ስለሆኑ ሥጋ መብላት የለብዎትም።»

«ዐውቃለሁ። ዶክተሩ እንድበላ የነገረኝ እትክልትና የተቀቀለ ዓሣ ብቻ ነበር። ግን ከየት ላግኝ።»

«ያውልዎት እሜቴ፤ እነዚህን ይውሰዱ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

አራት ፓውንድ የሚሆን ዓሣ ሰጠኋት።

ከዚያ ቀን በኋላ በየጊዜው ማጥመድ ሲቀናኝ የምላብ ፍላትኟን ለማግለት አረዳታለሁ። ነገር ግን መከፈል እንደሚኖርባት በትረዳም አመሰግናለሁ ትለኛለች እንጂ ፍጹም ምንም ነገር አበርክታልኝ አታውቅም። ልክ ነበረች፤ የእርሷን ገንዘብ እንደማልፈልግ ዐውቃለች። በዚህ ፋንታ አንድ ብርጭቆ ኑዋ ወይን ጠጅ፣ ወይም አንድ ፓስቲስ፣ አለበለዚያም ከኮርሲካ የሚላክላትን ትንሽ ፈንቴሲ ዘወትር ትጋብዘኛለች። ስላለፈው ታሪክ ማዳም ባሮ ፈጽሞ አትጠይቀኝም። አንድ ጊዜ ስሰቅኝ ግዙት አሰቃቂ ወሂኒ ቤት ስንወያይ፣ አንድ አስተያየት ጨረፍ አደረገችልኝ።

«ከደሴቶቹ ማምለጥ እንደማትችል እርግጥ ነው፤ ግን ልክ እንደ ኩበት በግራንዴቴሬ ከመበስበስ ይልቅ፣ እዚህ ጤናማ አየር የሚኖንበት ይመረጣል።»

የደሴቶቹንም የጥንት መነሻ ስም ያወቅኩት ከእርሷ ነበር። የበጫ ወባ ወረርሽኝ በካዮን ገብቶ ሳለ፣ እዚያ በጉዳም ውስጥ የነበሩ የወንድና የሴት መነኩሴዎች ወደ ደሴቶቹ ተሰደው በመምጣት ሕይወታቸውን ለማዳን በቅተው ነበር። ስለዚህም ዴላሊዩ «የሰላም ደሴቶች» ተበለው ተሰየሙ።

ዓሣ ማጥመዴ በየትኛውም ቦታ ያዘዋውረናል። በመፀዳጃ ቤት ጠራጊነት ሦስት ወር ስለሆነኝ፣ ማናቸውንም የደሴቷን ጥጋጥጎች ዐወቅኩ። ዓሣዎቼን በአትክልቶችና ፍራፍሬዎች አለውጣለሁ በሚል ሰበብ የአትክልት ቦታዎቹን ፈተሸኳቸው። የክፍላችን አባል የሆነው ማቴዎስ ካርቡኔሪ ከዘበኞቹ መታበር ቦታ ቀጥሎ የአትክልት መደብ ያለማል። የሚያለማው ብቻውን ስለሆነ፣ ጊዜው ሲደርስ አንዲት ጀልባ ገጣጥመን በአትክልት ቦታው ውስጥ መቅበር እንችል ይሆናል የሚል ሐሳብ መጣልኝ። ከሁለት ተጨማሪ ወሮች በኋላ የወህኒ አዛዡ መሔዱ ነው። ከዚያም የማምለጥ ዕቅዴን ለመጀመር ነጻ እሆናለሁ።

ሥራዎቼን አቀነባበርኩ። ናርክና ኬነር ተብለው ከሚጠሩ አምቻዎች ጋር የጓደኝነት መግቢያ ንግግር ከፈትኩ። የሚጠሩት «የጋሪ ወንድማማቾች» እየተባሉ ሲሆን፣ የተከሰሱትም ገድለውት የነበረውን የአንድ ከበርቴ አስከሬን በሲሚንቶ አሽጋችኋል ተብለው ነበር። የሲሚንቶ ብሎኬት በአንድ የእጅ ጋሪ ላይ ጭነው፣ ማርን ይሁን ሲየን የትኛው መሆኑን ከማላስታውሰው ወንዝ አስከሬኑን ሲቀብሩ ማየቱን አንድ ሰው ያመለክታል። እንደ ወሬው ባለጉዘቡ ያበደራቸውን እንዲመልሱለት ለመጠየቅ ወደእነርሱ ከሔደ በኋላ ዳግመኛ እንዳልታየ ነው። እርሱን መግደላቸውን ሁለቱም ሰዎች ከደዋል። በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ከገቡም በኋላ ከደሙ ንጹህ መሆናቸውን ከመከራከር አላቋረጡም። ግን ምንም እንኳ አስከሬኑ ጨርሶ ባይገኝም፣ በአንድ ትልቅ መሐረብ እንደተጠቀለለ ጭንቅላቱ ተገኝቶ ነበር። ስለሆነም አምቻዎቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድሩም ማጉም ወዘተ ... ተመሳሳይ የሆኑ መሐረሞች እንደ ነበሯቸው፤ «መርማሪዎቹ» ቢያስታውቁም በሺህ ያርድ የሚገመት ተመሳሳይ ጨርቅ እንደሚሠራ ጠበቃቸው ለማሳመን ቻለ። ማንኛውም ሰው ሊኖረው ይችላል። ያም ሆኖ አምቻዎቹ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተከናነቡ።

ከእነርሱ ጋር ጓደኝነት አበጀሁ። ግንበኞች እንደመሆናቸው ከወርክሾፕ ለመውጣትና ለመግባት ነፃነት ነበራቸው። ምናልባት እየቆራረጡ ጥቂት በጥቂት አንድ ጀልባ መሥሪያ የሚሆን እንጨት ሊሰጡኝ ይችላሉ። የቀረኝ ነገር ቢኖር እነርሱን ማሳመን ነበር።

ትላንት ዶክተሩን አግኝሁት። ክብደቱ ቢያንስ ሃምሳ ፓውንድ የሚመዝን፣ ለምግብ በጣም ተስማሚ የሆነና ባስ የተባለ ግዙፍ ዓሣ ተሸከሜ ነበር። አስከ ደልዳላው መሬት አብረን ተጓዝን። ግማሽ መንገድ ስንደርስ በአንድ አጭር ግንብ ላይ ተቀመጥን። የዓሣዬ ጭንቅላት ግሩም መረቅ እንደሚወጣው ሲነግረኝ ከትንሽ ሥጋ ጭምር አበረከትኩለት።

አከብሮቴ ገረመውና። «ምንም ቂም አትይዝም እንዴ ፓፒዮ?» አለኝ።

«አልይዝም ዶክተር፣ ለጓደኛዬ ለከሎሲዎ ያደረግከለት ውለታ አለብኝ።»

ሌሎችም ነገሮች አወራንና ከዚያም እንደዚህ አለኝ። «ለማምለጥ ትፈልጋለህ? አትፈልግም እንዴ? አንተ ወንጀለኛ አይደለህም፣ ልዩ ሰው መሆንህን ስሜቴ ነግሮኛል።»

«በሚገባ ትከከል ነህ ዶክተር። እዚህ ኗሪ ለመሆን አልፈልግም። በጉብኝት ላይ እንዳለሁ አድርጌ ነው ራሴን የምቆጥረው።»

መሣቅ ሲጀምር፣ ቀጠልኩ፣ «ዶክተር፣ አንድ ሰው ራሱን እንደገና ማስተካከል መቻሉን ታምናለህ?»

«አዎ፣ በሚገባ።»

«የሕብረተሰብ አንዴ አባል መሆን የምችል እንጂ ችግር ፈጣሪ አይደለሁም የሚለውን እምነቴን ትቀበለኛለህ? አንድ ጨዋ ዜጋ ለመሆን አልችልም?»

«ከልብ አምንበታለሁ።»

«ታዲያ፣ ይህን በተግባር እንዳውለው ትረዳኛለህ?»

«እንዴት?»

«የሳምባ ነቀርሳ በሽተኛ እንድሆን ፍቀድልኝ።»

«ይህን ማድረግ አልችልም፤ አንተም እንዳትሞክር እመክርሃለሁ። በጣም ሲበዛ አደገኛ ነው። አስተዳደሩ በሕመም ምክንያት አንድን ሰው የሚልከው፣ በተለይ የእርሱ ዓይነት ሕመምተኞች ባሉበት ከፍል ውስጥ አንድ ወር ያህል ካቆየው በኋላ ነው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምን?»

«ማንም ሰው በማጭበርበር ለመታመም ቢሞክር፣ በክፍሉ ውስጥ ካሉት ሌሎቹ ጋር ስለሚነካካ፣ ራሱን ለአደጋ ያጋልጣል። ስለዚህ ይህን ማድረግ አልፈልግም።»

ከዚያ ቀን ወዲህ ዶክተሩና እኔ ወዳጆች ሆንን። ይህም ጓደኛዬን ካርቡኔሪን ሊገድለው እስከ ተቃረበበት ቀን ድረስ ነበር። ከእኔ ጋር በጉዳዩ ከተወያየንበት በኋላ አትክልተኛው ጓደኛዬ ለዘበኞቹ ወጥ ቀቃይነት ተመደበ። ይህን ያደረገው የወይን ጠጅ፣ የዘይትና የሆምጣጤ ሦስት በርሜሎች ለመስረቅ ሲሆን፣ ሦስቱንም በአንድ ላይ በማሰር ወደ ባሕር ሰመንሳፈፍ ነበር። ያም ቢሆን ባሮ ከሐዲ በኋላ ብቻ ነው። በቅድሚያ በርሜሎቹን መስረቅ ይኖርብናል፣ ሳንሰማ ወይም ሳንታይ ወደ ባሕሩ ዳር መድረስና ከዚያም አንድ ላይ በካቦ ጠፍረን በማሰር በዚያው ሌሊት ማምለጥ ነበር። ይህም ሊሠራ የሚችለው ሽፋን አንዲሆነን ዝናብና ነፋስ በሚኖርበት አንድ የሞገድ ወቅት ብቻ ይሆናል። በዚሁ አንጻር ደግሞ ጀልባዋን ለማንቀሳቀስ ችግሩም የዚያኑ ያህል ከባድ ነው፤ ምክንያቱም ባሕሩ ብዙውን ጊዜ በጣም ቁጡ ነበር።

የሚቀጥለው ቀን ዕለቱ ኡሉድ ስለነበር ሦስት ጥንቸሎች ለምሳ እንዲያዘጋጅ የወጥ ቤቱ ኃላፊ ሰጠው። ካርቡኔሪም ቆዳቸውን ከገፈፈ በኋላ አንዷን ጥንቸል በወደቡ ለሚገኘው ወንድሙ፣ ሁለቱን ለእኛ ላከ። ከዚያም ሦስት ወደል ድመቶች ገደለና ከሽን ያለ ወጥ አዘጋጀ።

የሚያሳዝነው ዶክተሩም ለምሳ ተጋብዞ ነበር። ጥንቸሏን ቀመሰና ለወጥ ቤት ኃላፊው፣ «ሚስተር ፊሊዶሪ፣ በምግብ ዝግጅት ችሎታህ እንኳን ደስ አለህ አልሃለሁ። ድመቷ እጅ የምታስቆረጥም ጣፋጭ ናት» አለው።

«ትቀልዳለህ ዶክተር። ሦስት ግሩም ጥንቸሎች ናቸው» አለ።

«ይቅርታ እንድታደርግልኝ አለምናለሁ» አለና ዶክተሩ። «ድመቶች ናቸው፣ ይህን ፍርምባ ታያለህ? ጠፍጣፋ ነው። የጥንቸል ከብ ነው፣ እርግጠኛ ነኝ፣ ድመት እየተመገብን ነው» አለው።

«ወይ አምላኬ!» በማለት ፊሊዶሪ ደነፋና፣ «በሆዴ ውስጥ ድመት ይገባለኃ!» ብሎ እየተንደረደረ ወደ ወጥ ቤት ውስጥ ገባ። ሽጉጡን በማቴዎስ አፍንጫ ሥር በማስደገፍ፣ «ልገድልህ ነው። ድመት አበላኸኝ» ብሎ ጮኸበት።

የፈሰሰ ውሃ አይታፈስም፤ ካርቡኔሪ ዐይኖቹ በድንጋጤ እየተጉረጠረጡ «አንተው የሰጠኸኝን ጥንቸሎች ድመቶች ብለህ ከጠራህ የእኔ ስሕተት አይደለም» አለው።

«የሰጠሁህማ ጥንቸሎች ናቸው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ታዲያ እኔም የቀተልኩት እነሱኑ ነዋ! ተመልከት፣ ቆዳዎቹንና ጭንቅላቶቹን።»

በተምታታ ሁኔታ የወጥ ቤቱ ኃላፊ የጥንቸሎቹን ቆዳዎችና ጭንቅላቶች ተመለከተ። «እንግሊያ፣ ዶከተሩ ምን እንደሚናገር እያወቅህ ማለት ነው እ?»

«ይህን የነገረህ ዶከተሩ ነው?» አለ ካርቡኔሪ ትንሩሹ ተመልሶለት። እያፈዘብህ ኖሯል። ግን ይህ ጉዳይ ቀልድ አለመሆኑን ንገረው።» በሐሳቡ ተማመነና ፈሊዶሪ ወደ ምግብ ክፍሉ ተመልሶ ዶከተሩን፣ «የፈለግከውን ማለት ትችላለህ ዶከተር፣ የወይን ጠጁ ወደ ጭንቅላትህ የወጣ መስሎኛል። ፍርምባዎቹ ጠፍጣፋ ወይም ክብ ቢሆኑ ጉዳዬ አይደለም፤ የማውቀው ጥንቸል መብላቴን ነው። ቆዳቸውን አይቻለሁ» ሲል አረጋገጠለት።

ዝግጅቱን ለመጀመር የምችልበት ቀን በፍጥነት እየተቃረበ ነበር። የቀሩት ጥቂት ሰምንቶች ብቻ ናቸው፤ ከዚያም ባሮ ይሐዳል። ትላንት ሚስቱን ለማየት ሔድኩና መልካሚ ወይዘሮ ወደ ቤት እንድገባ ጋበዘቸኝ። ልትሰጠን ያዘጋጀችው አንድ ብልቃጥ እንከብሎች ነበሯት። ጓዝ በመጠፈር ላይ ስለነበረች የሣሉን ከፍሉ በትላልቅ ባልጃዎች ተጨናንቋል። «ፓፒዮ፣ ባለፉት ጥቂት ወራት ላደረግክልኝ ሁሉ እንዴት አድርጌ እንደማመሰግንህ አላውቅም። ዓሣ ማጥመድ በማይቀናህ ጊዜ እንኳ ማንኛውንም የዮዝከውን ሁሉ ለእኔ እንደምትሰጠኝ ዐውቃለሁ። የሚበቃ ምስጋና ላገኘልህ አልችልም። በአንተ ምክንያት ከሠላሳ ፓውንድ በላይ ተንሻለሁ፤ በጣም የተሻለ ጤንነት ይሰማኛል። ምስጋናየን ለመግለጽ ያህል የማደርግልህ ምን ነገር ይኖራል?»

«አንድ ነገር አለ፤ ግን ምናልባት ችግር ይፈጥር እንደሁ ብየ ፈርቻለሁ። አንድ ጥሩ ኮምፓስ ሊያገኙልኝ ይችላሉ? በጣም ትንሽም ብትሆን። ግን ፍጹም የተስተካከለች መሆን አለባት።»

«ይቪ በጣም ቀላል ነበር ፓፒዮ፣ ግን በሦስት ሳምንት ውስጥ ለመፈጸም አመቺ ላይሆን ይችላል።»

የጠየቃትን ነገር ልታገኝልኝ ባለመቻሏ ተበሳጭታ፤ ከመሔዷ በፊት ስምንት ቀን ሲቀራት ወደ ካየን በሚመላለሰው ጀልባ ተሳፈረች። ከአራት ቀን በኋላ ግራም የሆነና ማግኔት የማይስበው አንድ ኮምፓስ ይዛ ተመለሰች።

የወህኒ ቤት አዛዡና ማዳም ባሮ ዛሬ ጧት ሔዱ። ፕሩሌ ለተባለ አንድ ቱኒዚያዊ መኮንን ትላንት ሥልጣኑን አስረክቧል።

መልካም ዜና ነበር። ለማንኛውም ሰው ሆነ በተለይ ለእኔ ከፍተኛ ጠቃሚነት የነበረው፣ አዲሱም የወህኒ ቤት አዛዥ ዴጋ ዋና ጸሐፊነቱን እንደያዘ አንዲቶይ ማድረጉ ነው። በተጨማሪ፣ በግቢው ውስጥ ተሰብስበው ለነበሩት አሥረኞች «አዲሱ የወህኒ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዛኝ እኔ ነኝ። አኔ የተካሁት አዛኙ የአሥራር ዘዴዎች አጥጋቢ ሆነው ስላረኩኝ፣ የምለውጥበት ምክንያት አይታየኝም። የአናንተው ጠባይ ካላስገደደኝ በስተቀር የአኗኗር ልምዳችሁንም መቀየር አስፈላጊ ሆኖ አላገኘሁትም» ብሏል።

ምንም እንኳ አምስቱ የግዴታ ቆይታ ወሮች በሚያስገርም ፍጥነት ቢያልፉም ቅሉ፣ የወህኒ አዛዡና ሚስቱ በመጨረሻ ሲሔዱ መሸኘቴ የደስታና ከመላላገል ጋር የተቀላቀለ መሆኑ ግልጽ ነበር።

እኛ እሥረኞች የምንደሰትበት የውሸት ነፃነት፣ ጨዋታዎቻችን፣ ዓሣ ማጥመዱ፣ ውይይቱ፣ አዲስ ጓደኞች ማበጀቱ፣ ከርከሮቹ፣ ድብድቦቹ ሁሉ ታይለኛ ማዘናጊያዎች ስለሆኑ፣ እምብዛም አንሰለችም ነበር።

ለእኔ ሁሉም ያው ነው። በኑሮው ብዙም አልተሳብኩበትም። በየጊዜው አዲስ ጓደኛ ባበጀሁ ቁጥር ፈተና አሰጠዋለሁ። «ለማምለጥ አጩ ሊሆን፣ አብሮኝ ለመሔድ የማይፈልግ ቢሆን እንኳን በዝግጅት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል?» የሚሉ ጥያቄዎች አነሳለሁ።

ለዚያ ስል ብቻ አኖራለሁ። ማምለጥ ቁርጥ ያለው ሐሳቤ ነበር። ዮሐንስ ካስቴሊ እንደ ነገረኝ ስለዚህ ጉዳይ ለማንም አላወራም። ግን ከማሰብ አልቦዝንም። በውሳኔዬ እንዳላወላውል ቆርጫለሁ፤ ማምለጥ የሚለውን ሐሳብ ፈጽሞ አልተውም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰባተኛ ማስታወሻ

የድሳሊዩ ደሴቶች (ይቀጥላል)

በመቃብር ውስጥ አንድ ጀልባ

በአምስት ወር ውስጥ የደሴቷን ማንኛውንም ቦታ አንድ በአንድ ለማወቅ ችያለሁ። ጓደኛየ ካርቡኔሪ ወጥ ቤት ከመሆኑ በፊት ዓላማው ከመቃበር ቦታ አጠገብ የሚገኘውን የአትክልት ቦታ ለጀልባ መገጣጠሚያ ለመጠቀም ነበር። እንደገና በአትክልተኝነት ተመድቦ ወደዚያው ሔዶ እንዲያለማ ጠየቅኩት። ፈቃደኛ ሆኖ ነበር። ለዴጋ ምስጋና ይድረሰውና ሥራውንም መልሶ አገኘ።

ዛሬ ጧት ያጠመድኳቸውን ዓሣዎች ይዤ አዲስ በመጣው የወህኒ አዛዥ ቤት በኩል ሳልፍ፣ አጠገቡ ቆማ ለነበረችው አንዲት ወጣት እንደ ቤት ልጅ የሚያገለግለው አንድ እሥረኛ እንደዚህ ሲላት ሰማሁ። «ይኸ ነው አሜቴ፤ ለማዳም ባሮ ዘወትር ዓሣ የሚያመጣላቸው» ከዚያም፣ ነሐስ የመሰለ ቆዳና ጥቁር ጸጉር ያላት አልጀሪያዊት የምትመስል ውብ ሴት፣ «ለካ ፓፒዮ አሱ ነው?» አለችው። ከዚያም እኔኑ አነጋገረችኝ።

«ማዳም ባሮ አንተ የያዝካቸው ናቸው ብላ ትንሽ ዓሣዎች ሰጠችኝ። ወደ ውስጥ አትገባም እንዴ? አንድ ብርጭቆ ወይን ጠጅ ጠጣ፣ ከፈረንሣይ የመጣልኝን የፍየል አይብ እንድትቀምስልኝም እፈልጋለሁ» አለች።

«አልፈልግም። አመሰግናለሁ። አሜቴ፤ አልችልም።»

«ለምን አትችልም? ማዳም ባሮ እዚህ በነበረች ጊዜ ታደርግ አልነበረም እንዴ?»

«ያ የሆነበት ምክንያት ወደ ቤቱ እንድገባ ባላቸው ስለፈቀደልኝ ነበር።»

«ፓፒዮ፣ የባሌ ኃላፊነት ለካምፑ ነው። እኔ ደግሞ ለቤቴ ኃላፊ ነኝ። ወደ ውስጥ ለመግባት አትፍራ።»

ይህች ቆንጆ ሴት ጠቃሚ እንደምትሆን ሰሜት አድሮብኝ ነበር፣ ግን አደገኛነቷም የዚያኑ ያህል ይሆናል። ወደ ውስጥ ገባሁ። በምግብ ከፍል ጠረጴዛው ላይ የዓሣማ ሥጋና አይብ በአንድ ሣህን አቀረበችልኝና በግድየለሽነት ከፊት ለፊቴ መጥታ ተቀመጠች። የወይን ጠጅ ሰጠችኝና ከዚያም አርኪ የሆነ የጀግይካ ሩም የገባበት ቡና ተከተለ።

በመቅዳት ላይ እንዳለች፣ «ማዳም ባሮ በምትሔድበት ወቅት፣ በዚያ የጥድፊያ ወቅት ስለአንተ ልትነግረኝ ጊዜዋን መሥዋዕት አድርጋ ነበር። በደሴቱ ውስጥ ዓሣ የምትሰጣት ብቸኛ ሴት እርስዋ እንደነበረች አውቃለሁ። ለእኔም ተመሳሳይ ውለታ እንደምታደርግልኝ ተስፋ አለኝ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለእርሳቸው የሰጠሁበት ምክንያት ጤነኛ ስላልነበሩ ነው። እንደማየው ከሆነ አንቺ በግሩም ጤንነት ላይ ትገኛለሽ» አልኳት።

«ለአንተ መዋሸት አልፈልግም ፓፒዮ። በጥሩ ጤንነት ላይ ነኝ። ሆኖም ያደግኩት በወደብ አካባቢ ስለሆነ ዓሣ እወዳለሁ። የመጣሁት ከአራ ነው። ግን ያበሳጨኝ አንተ አሣዎችህን እንደማትሸጥ ማወቄ ነው።»

ታዲያ፣ ወጣም ወረደም ዓሣ ላመጣላት ተስማማሁ።

ሰባት ፓውንድ የሚመዝኑ የተለያዩ ዓሣዎች ሰጥቻት፣ ወዲያው አንደ ሲጃራ በማጤስ ላይ እንዳለሁ ነበር የወህኒ ቤቱ አዛዥ ወደ ውስጥ የገባው።

ተመለከተኝና «ዠፎልየት፣ ከቤት ልጅ በስተቀር እንድም እሥረኛ ወደ ቤት ውስጥ እንዳይገባ አልነገርኩሽም?»

ለመነሳት ስጀምር እርሷ «አትነሳም። ማዳም ባሮ ከመሐዲ በፊት አደራ ያለችኝ ይህን ሰው ነው። ስለዚህ የአንተ ጉዳይ አይሆንም። ለእርሱ ካልሆነ እዚህ ቤት ውስጥ ማንም ሰው እንዲገባ አልፈቅድም። በተጨማሪ በሚያስፈልጠኝ ጊዜ ዓሣ ሊያመጣልኝ ነው» አለች።

«አቪ እንግዲያው» አለና አዛገቦ «ማነው ስምህ?» አለ። መልስ ለመስጠት በመነሳት ላይ እንዳለሁ ዠፎልየት እጁን ከትከሻዬ ላይ ጥላ ተቀምጠው እንድቆይ አደረገችኝ። «ይህ የእኔ ቤት ነው። እዚህ አዛገቦ ባሌ ሚስተር ፕሩሌ ሳይሆን እኔ ነኝ» አለች።

«አመሰግናለሁ እመቤቴ። ስሜ ፓፒዮ ነው» አልኩ።

«አሃ! ከሦስት ዓመት በፊት ከቅዱስ ላውረን ሆስፒታል ስለማምለጥህ ሰምቻለሁ። ከመታሣቸው ዘበኞች አንደኛው እንደዚህ የምትንከባከብህ የአጎት ልጅ ነበር» አለ።

በዚህም ዠፎልየት ደስታ በተመላበት አሣሣቅ ተንከተከተችና፣ «ለካ ጋስቶንን መትተከው የነበርከው አንተ ነህ! ይኸ ወዳጅነታችንን ቅንጣት ታክል አይለውጠውም» አለች።

አሁንም ገና እንደቆመ የነበረው ወህኒ አዛገቦ፣ «በየዓመቱ በደሴቶቹ ውስጥ የሚፈፀመው የግድያዎች ቁጥር የማይታመን ነው። ከግራንዴ ቴሬ በብዙ ቁጥር ይጨምራል። ለዚህ ምክንያቱ ምን እንደሆነ ትገልጽልኛለህ ፓፒዮ?» አለ።

«ጌታዬ፣ እዚህ ሰዎቹ የማምለጥ ተስፋ ስለሌላቸው ይበሳጫሉ። በተለይ ለዓመታት እንዱ ከሌላው ጋር የጠበቀ-ጓደኝነት ወይንም የከረረ ጥላቻ ይመሠርታል። በተጨማሪ ከገዳዩች ውስጥ ከመቶ አምስት እንኳን የሚሆነው ስለማይጋለጥ፣ እያዛለሁ ብሎ የሚፈራ ማንም ሰው የለም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ይህ አሳማኝ ይመስላል። ዓሣ በማጥመድ ምን ያህል ጊዜ ሆናሃል? ዓሣ የማጥመድ መብት ያገኘኸው ምን ሌላ ሥራ በማከናወንህ ነው?» አለ።

«የመፀዳጃ ቤቱን ጠረጋ አካሂዳለሁ። ሥራዬ የሚያቢቃው ጧት በዐሥራ ሁለት ሰዓት ነው። ከዚያም ዓሣ አጠምዳለሁ።»

«የቀረውን ቀን በሙሉ?» ብላ ዠልየት ጠየቀች።

«አይደለም፤ በቁትር ወደ ካምፕ መመለስ አለብኝ፤ ግን እንደገና በዘጠኝ ሰዓት አሄድና እስከ ዐሥራ ሁለት ሰዓት እቆያለሁ። ታዲያ፣ ማዕበሉ ስለሚለዋወጥ አንዳንድ ጊዜ ተስማሚው የማጥመጃ ወቅት ያመልጠኛል።»

«ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶሃል፤ አይደለም እንዴ ፍቅርዬ?» አሉች ዠልየት ወደ ባሏ ዘወር ብላ። «ከጧቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት እስከ ምሽቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት፣ ስለዚህ ቢሚፈልግበት ጊዜ ማጥመድ ይችላል።»

«መልካም» አለ አዘገቡ።

ነገሮችን ለማመቻቸት በመቻሌ ራሴን እንኳን ደስ አለህ አያልኩ ከቤት ወጣሁ። እነዚያ ከቁትር ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ያሉ ሦስት ሰዓቶች በጣም ውድ ዋጋ ነበራቸው። የዕረፍት ሰዓታቸው ስለሆነ ከሞላ ጎደል ሁሉም ዘበኞች በዚያ ወቅት ይተኛሉ።

ዠልየት እኔን ብቻ ሣይሆን ዓሣዎቼንም በቁጥጥሯ ሥር አደረገች። ነጩን የተረዳሁት ወጣቱን የቤት ልጇን እየላከች የያዝኳቸውን ዓሣዎች መጠን ስታስጠይቀኝ ነበር። «አሜቴ እንግዳ ሳይመጣባቸው ስለማይቀርና ቡላቢስ ማዘጋጀት ስለሚፈልጉ፣ የያዝከውን ማናቸውንም ዓይነት ዓሣ ይፈልጋሉ» ይላል። ከዚያ የያዝኳቸውን በሙሉ መውሰድ ብቻ ሳይሆን የተሰዩ ዓሣዎችን እንድፈልግ ትልከኝ ጀመር። ለደባሉቼ እንደወትሮ የምግብ አቅርቦቱ ቀነሰ። በሌላ መልኩ ግን እንዴት ያለ እንክብካቤ አገኘሁ። ለትንሹም ለትልቁም ዠልየት ታስብልኝ ነበር።

«ፓፒዮ፣ በሰባት ሰዓት ከፍተኛ ማዕበል አይሆንም?»

«አዎ አሜቴ»

«ታዲያ ወደ ካምፕ ተመልሰህ ከመሐድ ለምን እዚሁ አትበላም?» እንደ ማዳም ባሮ ይሉኝታ አልነበራትም። አንዳንድ ጊዜ ስላለፈው ታሪኬ ልትጠይቀኝ ትሞክራለች። በጣም የሚያስደንቃትን የሞንትማትር ኑሮዬን እየዘለልኩ ስለሕፃንነቴና የወጣትነት ዘመኔ አወራላታለሁ። ይህ የሚሆነው አዘገቡ በከፍሉ ውስጥ ተኝቶ እንዳለ ነበር።

አንድ ጊዜ ማለዳ ላይ ታላቅ እድል ገጠመኝና ስድሳ የሚሆኑ ልዩ ዓሣዎች ያዝኩ። ከቤቷ አጠገብ ስቆም በማምት አራት ሰዓት ነበር። ጸጉሯን ትሠራት ከነበረች

t.me/OLDBOOKSPDF

አንዲት ሌላ ወጣት ጋር ነጭ ፒጃማ እንደለበሰች አገኘኋት። እንደምን አደራችሁ አልኩና አንድ ደርዘን የሚሆን ሰጠኋት።

«አይሆንም፣ ሁሉንም አፈልጋቸዋለሁ። ስንት ናቸው?» አለች።

«ስድሳ ይሆናሉ።»

«ግሩም ነው። አንተና ጓደኞችህ ምን ያህል ያስፈልጋችኋል?»

«ስምንት።»

«እንግዲያው አንተ ስምንቱን ውሰድና የቀሩትን ሰልጅ ቡጣቸው፣ በበረዶ ውስጥ ያስቀምጣቸዋል።»

«በመሐድ ላይ አያለሁ ነበር፤ መቸኮልህ ለምንድን ነው? ተቀመጥና አንድ ፖስቲስ ውሰድ። ሞቅህ ሞሆን አለበት» አለችኝ።

ከዚህች ግራኒ ቤት ጋር ወቀመጡ ጤና ኑሩኝ። ፖስቲሴን በዝግታ ጠጣሁና አንድ ሲጃራ እያጨስኩ የገቦልየትን ጸጉር ወጣትዋ ስታበጥርላት እመለከታለሁ። አልፎ አልፎ ኩረዳዋ ሰረቅ እያደረገች ወይኗን ስትመረውርብኝ፣ የመሀረ አዛዥ ሚስት በመስታወቱ ውስጥ አየቻቸው። «ሲሞን ፍቅረኛዬ አይደለም እንዴ? ሁላቸውም እኔ በያዝኩት ትቀናናችሁ» አሰቻትና ሁሉቱ ሲሳሳቁ እኔ ወዴት እንደምመለከት ጠላ ትጡ ጠፋብኝ።

በለዘብታ አንጋገር፣ «ፍቅረኛ፣ አንቺ እንደምትይው ይሆን ያህል ችግር ፈጣሪ አይደለም። እንደርሱ ያለ ሰውም የማንም ፍቅረኛ ሊሆን አይችልም» አልኳት።

«ያም ሆኖ በእኔ ፍቅር አልወደቅኩም ብለህ እንዳትናገር፡ አንተን ለመግራት የቻልኩ የመጀመሪያዋ ሰው እኔ ነኝ። ስለዚህ አንተ ላይ ደስ ያሰኘኝን ማንኛውንም ነገር ማድረግ አችላለሁ። ትከከል አይደለሁም እንዴ ሲሞን?» አለቻት።

«ስለዚያ አላውቅም» ብላ ቢሞን መለሰችና፣ «ማውቀው ፓፒዮ፣ ከአዛዡ ሚስት በስተቀር ለማንኛውም ሰው ጨካኝ መሆንህ ነው። ባለፈው ረምንት የዘበኞቹ ኃላፊ ሚስት እንደነገረችኝ፣ ከዐርባ ፓውንድ የበለጠ ዓሣዎች ይዘህ ለአርሰዋ ሮን ሁለት ኮሳሳ ዓሣዎች እንኳ ልትሸጥላት አልፈለግክም። ሥጋ ስላልነበራት በጣም ፈልጋቸው ነበር። 'ትሰሚኛለሽ?' ብላ ወሬዋን በመቀጠል፣ «በሌላ ቀን ማዳም ሊብሎንድን ምን እንዳላት? እንዲሁ የተለያዩ ዓሣዎች ተሸክሞ ሲያልፍ ታየዋለች። 'ፓፒዮ' እባክህ ያንን ትልቁን ዓሣ ወይም ሥጋሹን እንኳ ሽጥልኝ። በተለይ እኛ በራሳችውያን ልዩ ምግባችን ነው ትለዋለች። ዒመቤቴ፡ ዓሣውን የሚያደንቁት በራሶናውያን አይደሉም። ብዙ ሰዎች፡ አርዴኮችም ከሮማውያን ዘመን ጀምሮ ምርጥ ምግብ መሆኑን ያውቁታል'" አለና አንድም ነገር ሳይሸጥላት መንገድን ቀጠለ።

ሁለቱም ከጣራ በላይ ሣዕ፡፡ እየተናደድኩ ወደ ካምፕ ተመለስኩና በዚያ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዕለት ምሽት ለደባሎቹ አሜወትኳቸው።

«ይህ ከባድ ጉዳይ ነው» አለ ካርቡኔሪ፡ «ያቺ ሴት መከራ ውስጥ ትከትሃለች። በተቻለህ መጠን ወደዚያ አልፎ አልፎ መሔድ፣ ያም ቢሆን የወህኒ አዛዥ ቤት ውስጥ መሆኑን ስታረጋግጥ ብቻ መሆን እንዳለበት አመክርሃለሁ።» ሁሉም ሰው በዚህ ተስማማ እኔም እንደዚሁ ለማድረግ ወሰንኩ።

ከተወለድኩባት ቀበሌ ብዙ ከማትርቅ ስፍራ ከቫሌንስ የመጣ አንድ አናጢ አገኘሁ። አንድ ዘበኛ ገድሎ ነበር። የቁማር ሱስ የተጠናወተው ስለነበር፣ ዘወትር ከቢድር አይወጣም። ቀኑን ሙሉ የእደ ጥበብ ሥራዎች በጥድፊያ ሲያከናውን ይውልና፡ ያተረፈውን ሌሊት ያወድመዋል። ብዙ ጊዜ አታዎቹን የሚሠራው የአበዳሪዎችን እዳ ለመክፈል ሲሆን፡ ከእርሱ ላይ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማግኘት የሚፈልጉ፡ ሦስት መቶ ፍራንክ ዋጋ ሊኖረው ለሚችል ለአንድ በምርጥ እንጨት ለተሰራ ሣጥን፣ አንድ መቶ ሃምሳ ወይም ሁለት መቶ ፍራንክ ብቻ ይከፍሉታል። እርሱን ለመከታተል ወሰንኩ።

አንድ ቀን መታጠቢያ ቤት ውስጥ አብረን እንደነበር

«ዛሬ ማታ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ። መፀዳጃ ቤት እንድንገናኝ። ስዓቱ መቼ እንደሚሆን እነግርሃለሁ» አልኩት።

በዚያው ሌሊት ብቻችንን በማውራት ላይ እንዳለን፣ «ቦርሴ፣ ከአንድ ዛፍ የወጣን ሁለት ቅርንጫፎች መሆናችንን ታውቃለህ?» አልኩት።

«እንዴት?» አለ።

«ከቫሌንስ አይደለህም እንዴ?»

«አዎ።»

«ታድያ እኔም ከእርዴክ ነኛ። ስለዚህ ጎረቤቶች ነን።»

«ታድያ፣ ምን ይሁን?»

«የዕቃዎችህን ግማሽ ዋጋ ብቻ እያገኘህ፣ ሌላው ሲጠቀምበሀና አንተ ዕዳ ውስጥ ስትዘፈቅ እንዳይህ አልፈልግም። ወደ እኔ አምጣቸው፣ ሙሉ ዋጋቸውን እከፍልሃለሁ። ይሽው ነው»

«አመሰግናለሁ» አለ ቦርሴ።

አበዳሪዎቹ ከፈላ ውሃ ውስጥ እንደገባች ዶሮ ሲሞሸልቁት ኖረዋል። ስለሆነም ከዚያ እንዲወጣ ሳላሰልስ እረዳው ጀመር። ከጥሩዎቹ ጓደኞቼ አንድ ከሆነው ቪሲዎሌ ከተባለ አንድ ኮርሲካዊ ጋር አስከተጋጨበት ዕለት ድረስ። ላቢደረው ሰባት መቶ ፍራንክ ቪሲዎሊ የሚከታተለው መሆኑን ቦርሴ ነገረኝ። ልታልቅ የተቃረበች አንዲት ትንሽ ጠረጴዛ እንዳለችውም አወሳኝ። ግን የሚሰራት በምስጢር ስለሆነ መቸ እንደሚጨርሳት እርግጠኛ አልነበረም። ትላልቅ ዕቃ መሥራት አይፈቅድላቸውም ነበር፤ ምክንያቱም

t.me/OLDBOOKSPDF

በጣም ብዙ እንጨት ይጨርሳል። ምን ማድረግ እንደሚቻል አሰብበታለሁ ብዬ ነገርኩት። በቪሲዎሊ ፈቃደኝነት አንድ አርምጃ ለመውሰድ ፈቀድኩ። ቪሲዎሊ ቦርሴን እንዲጨፋጭቀው፣ እንዲያውም እንዲዝትበት ማድረግ ከዚያም እኔ የቦርሴ ደጋፊ በመሆን ጣልቃ እንድገባ ነበር።

ያው በትክክል እንደታቀደው ሆነ። ከዚያ በኋላ ቦርሴ የእኔ ሰው ሆነና ያለማመላወል እምነቱን ጣሉብኝ። እሥረኛ ከሆነ እንስቶ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰላም እየር መተንፈስ ቻለ። ስለዚህ እኔም ጥቅሜን ለማስከበር አንድ ዕድል አገኘሁ።

አንድ ቀን ማታ እንደዚህ አልኩት። «የምጠይቅህን ብታደርግልኝ፣ ሁለት ሺ ፍራንክ አሰጥሃለሁ። ለሁለት ሰዎች የምትበቃ ተከፋፍላ የምትገጣጠም እንዲት ጀልባ እፈልጋለሁ።»

«ስማ ፓፒዮ፣ ለማንም ሰው ቢሆን ይህን አላደርግም ለአንተ ግን የሁለት ዓመት የግዞት ቅጣት ሊደጋ ቢያስከትልብኝም እንኳ ግድ የለኝም። ዋናው ነገር ትላልቅቹን ቁራጮች ከወርከ ሾፑ ለማውጣት አለመቻሌ ነው» አለ።

«ያንን የሚያደርግ ሌላ ሰው አለኝ።»

«ማን ነው?»

«የጋሪ ወንድማማቶቹ ፍሪከና ኪነሪ። ጀልባዋን ለመሥራት ዕቅድህ እንዴት ነው?»

«በቅድሚያ አንድ ሥዕል በስኬል እሠራለሁ፣ ከዚያም ቁራጮቹ እንዲሰካኩ ጥርስ ስለማወጣላቸው፣ ሁሉም ጥብቅ ብለው ይገጣጠማሉ። በደሴቱ ያለው እንጨት በሙሉ ከባድ ነው፣ ስለዚህ የሚንሳፈፍ እንጨት ለማግኘት ትንሽ ችግር ያጋጥመኝ ይሆናል።»

«መሥራት መቻልህን እስከመቼ ትወስናለህ?»

«በሦስት ቀን ውስጥ።»

«ከእኔ ጋር አብረን ለመጥፋት ትፈልጋለህ?»

«አልፈልግም።»

«ለምን?»

«ዓሣ ነባሪዎቹን አፈራለሁ፤ መስጠምም አልፈልግም።»

«እስከሚያልቅ ድረስ ልትጠነቀቅ ቃል ትገባልኛለህ?»

«እምልልሃለሁ። ብቻ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስድብኛ።»

«ለእዚያ ግድየለም። አሁን በጥንቃቄ አዳምጥ። በአንድ የማስታወሻ ቁራጭ ወረቀት ላይ የጀልባዋን ዲዛይን አቀጻና ከሥር በኩል፣ 'ቦርሴ፣ ልከ ይህን ሥዕል አስመስለህ አንድ ጀልባ ሥራ፤ አለበለዚያ ትሞታለህ' ብዬ አጽፍበታለሁ። አንድ ችግር

t.me/OLDBOOKSPDF

ቢመጣ ይህ ለአንተ ማምለጫ ይሆንሃል። እያንዳንዷ ቁራጭ እንዴት እንደምትሠራ ከዚያ በኋላ እየጻፍኩ ትእዛዝ እሰጥሃለሁ። በየጊዜው አንዱን ስትጨርስ የት እንደምትተውልኝ እኔ እነግርሃለሁ። ከዚያም ወደ ሌላ ቦታ ይወሰዳል። መቼ እንደሚወሰድ ለማወቅ አትሞክር።» ይህም ስሜቱን ያረጋጋው መሰለ። «ብትያዝ እንኳ የሚደርስብህን አደጋ በዚህ ዘዴ እንከላከላለን፤ በጣም ቢበዛ የሚፈረድብህም ስድስት ወር ይሆናል» አልኩት።

«የምትያዘው አንተ ብትሆንስ?» አለ።

«ያማ የተገላቢጦሽ ይሆናል ማለት ነዋ! የማስታወሻዎቹ ደራሲ እኔ መሆኔን እምናለሁ። አንተ ታዛቨርነትህን ትገልጻለህ። እሺ?»

«እሺ።»

«አትፈራም?»

«አልፈራም። እንዲያውም አንተን ለመርዳት ዕድል በማግኘቴ ደስ ብሎኛል።»

አንድም ቃል ለማንም ሰው አልተነፈስኩም። የቦርሴን መልስ እየጠበቅኩ ነበር። እንደገና ብቻችን ከቤተ መጻሕፍት ከመነጋገራችን በፊት ማለቅያ የሌለው አንድ ሳምንት አለፈ። ቦርሴ በመጨረሻው በልቤ ውስጥ የፀሐይ ጮራ ፈነጠቀልኝ።

«አሰቸጋሪው ሥራ ቀላልና ደረቅ እንጨት ማግኘቱ ነበር። ደረቅ ኮከኑቶች ሰብስቤ አንድ ዓይነት ዲዛይን በማውጣት ችግሩን አቃለልኩት። ከማንኛውም የቀለሱና ጭጋም ውሃ የሚያስገቡ ናቸው። ለጀልባዋ መለዋወጫ መፈለጉ የአንተ ፋንታ ይሆናል። የመጀመሪያውን ቁራጭ ነገ እጀምራለሁ። ሦስት ያህል ቀናት ሊወስድብኝ ይችላል። ከሐሙስ በኋላ በተቻለህ መጠን ከአምቻዎቹ አንዱ ፈጥኖ እንዲያነሳው አስደርግ። ያለቀው ቁራጭ ከወርክ ሾፑ ከመነሳቱ በፊት አዲስ ቁራጭ አልጀምርም። ዲዛይኔ ይኸውልህ። ገልብጥና ያን ያልከውን ቃል ጻፍበት። ከወንድማማቾቹ ጋር ተነጋግረሃል?» አለ።

«አልተነጋገርኩም፤ ገና ነኝ። የአንተን መልስ እየጠበቅኩ ነበር።»

«ታዲያ የኔንማ አግኝተኸዋል። እሺ ብያለሁ።»

«አመሰግናለሁ ቦርሴ። በዕውነት እንዴት አድርጌ እንደማመሰግንህ አላውቅም። ይኸውልህ፤ ይህን አምስት መዶ ፍራንክ ውሰድ።»

ትኩር ብሎ ዐይን ዐይኔን ተመለከተኝና፤ «አይሆንም፤ ገንዘቡን ያዘው። ግራንዴቴራ መድረስ ከቻልክ፤ ከዚያ የሚቀጥለውን የማምለጥህን ዕድል ማቀነባበር ያስፈልግሃል። ከዛሬ ጀምሮ አንተ እስክ ምትሔድ ድረስ ካርታ መጫወቴን አቆማለሁ። እዚህ የምሠራቸው ነገሮች ለሲጃራና ለሥጋ መግዣ ይበቁኛል።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ለምን መውሰድ አልፈለግክም?»

«ምክንያቱም ዐሥር ሺ ፍራንክ እንኳን ቢሆንም ይህን አላደርገውም። እንደዚህ የመሰሉትን ጥንቃቄዎች ሁሉ ወስደንም የሚያስከትለው አደጋ በጣም ከፍተኛ ነው። ማድረግ የምችለው በነገ ነው። ረድተኸኛል፤ ልትረዳኝ እጅህን ያነሣህልኝ አንተ ብቻ ነህ። ያስፈራኛል፣ ሆኖም ለመሥራት ደስ ብሎኛል።»

ዲዘይኑን በመገልበጥ ላይ እያለሁ ወንጀለኛነቱ ይሰማኝ ጀመር። የራሴን ፍላጎት ለማሟላት ስል የረዳሁት መሆኔን፣ የቦርሴ የቁህ አእምሮ ፍጹም አልጠረጠረም። በራሴው ዐይን ደግ የሠራሁ መስየ ለራሴው መንገር ነበረብኝ። የፈጸምኩትን ወራዳ ምግባር የማምለጥ ዕድል ተሳክቶ ያካከስልኝ ይሆናል።

ሌሊት ሲሆን ከናሪክ ጋር ተነጋገርኩና ለአማቹም ቃሉን እንዲያስተላልፍ ላከሁት።

እርሱም ወዲያውኑ እንደዚህ አለ። «ቁራጮቹን ከወርክሾፑ ለማውጣት ከሆነ በእኔ ላይ ጣለው። ብቻ ከመጠን በላይ መቸኮል የለብህም። ለግንብ ሥራ የሚሆን አንድ ትልቅ ዕቃ በሚወጣበት ጊዜ ብቻ ነው ልናንቀሳቅሳቸው የምንችለው። ዕድሉ እንዲያመልጠን አናደርግም፤ ስለዚህም ቃል እገባልሃለሁ» አለ።

ቀጥሎ መነጋገር ያለብኝ ከማቴዎስ ካርቡኔሪ ነበር። ምክንያቱም እርሱም አብሮኝ እንዲሔድ አፈልጋለሁ። መቶ በመቶ ተስማሚዬም እርሱ ነበር።

«ማቴዎስ፣ ጀልባ የሚሠራ አንድ ሰው አግኝቻለሁ፤ ቁርጥራጮቹንም ከወርክሾፑ የሚያወጡልኝ ሌሎች ሰዎች አግኝቻለሁ። አሁን ጀልባዋን ለመቅበር የምንችልበት አንድ ቦታ መፈለጉ የአንተ ፋንታ ይሆናል።»

«አይሆንም። የአትክልት ቦታው ጥሩ አይደለም። ዘበኞቹ አትክልት ሊሰርቁ ሌሊት ስለሚመጡ፣ ማየት ይችሉ ይሆናል። ከግንቡ ጥግ አንድ ትልቅ ድንጋይ አፈነቅልና ከኋላ በኩል ሰፊ ስፍራ በመቆፈር አንድ የመደበቂያ ጉድጓድ አዘጋጃለሁ። በዚህ ዘዴ ቁራጩን በማጎንበት ጊዜ ቋጥኙን እየፈነቀልኩ ቁራጩን አውስጥ ካስገባሁ በኋላ መልሼ መከደን ነው» አለ።

«ቁርጥራጮችን በቀጥታ ወደ አንተ አትክልት ቦታ መውሰድ አለብኝ?»

«አይሆንም። ይህ በጣም አደገኛ ነው። አምቻዎቹ ወደዚያ ለመሔድ ምንም አጥጋቢ ምክንያት አይኖራቸውም። የሚሻለው ቁራጮቹን በኦዳዲስ ቦታ በየጊዜው ቢያስቀምጧቸው ይሆናል።

« ትከክል ነው።»

ማንኛውም ነገር የሠመረ ይመስላል። የቀሩ ነገሮች ቢኖሩ ኮከኑቹ ብቻ ነበሩ። ምንም ሳይነታበኝ የሚበቃኝን ያህል ለማጠራቀም እንዴት እንደምሞከር

t.me/OLDBOOKSPDF

ማጥናት አለብኝ።

ወደሕያውነት መመለሴ ለራሴው ተሰማኝ። የቀረው ብቸኛ ነገር ከግራንዴና ጋልጋኒ ጋር መወያየት ነበር። በእንድ አጋጣሚ ተባባሪ ናችሁ ተበለው ሊወነጀሉ ስለሚችሉ፤ ምስጢሩን ደብቁ መቆየት አይኖርብኝም። ይሀን ለመከላከል ደባሎቹን ትቼ ብቻዬን ለመኖር ወሰንኩ፡ ግን እቅዶቹን ስነግራቸው ምርር ብለው ወቀሱኝ።

«በተቻለ ፍጥነት እንተ አምልጠህ ሒድ! እኛ አንደባለቅም። ግን እስካለህ ድረስ ከእኛ ጋር ቆይ። ካሁን በፊት እኛ ብዙ ሙከራ አድርገናል» አሉ።

አሁን የማምለጥ ዝግጅቱ ከአንድ ወር በላይ ሆኖት ነበር። እስካሁን ሰባት ቁርጥራጮች ከእነርሱም ውስጥ ሁለት በጣም ትልልቆች ደርሰውኛል። ማቴዎስ ለመደበቂያ ብሎ ቆፍሮት የነበረውን ጉድጓድ ለመመልከት ሒድኩ። ዙሪያውን በድንጋይ ሽበት በማጣበቅ ጥንቃቄ ወስዶ ስለነበር፤ ቋጥኙ ምን ጊዜም ከቦታው የተነቃነቀ አይመስልም። ቦታው ተስማሚ ነበር። ሆኖም በጠቅላላው ጀልባውን ለመያዝ በጣም ጠባብ ይመስላል። ለጊዜው ግን በቂ ቦታ ነበር።

የማምለጡን ሥራ ማከናወኔ ለሞራሌም ማሩም ሆኖልኛል። ከመቼውም የበለጠ እበላለሁ፤ ከዚያም በላይ ዓሣ ማጥመዱ ጥሩ የአካል ብቃት ሰጥቶኛል። ከዚያ በተጨማሪ ዘወትር ጧት ከሁለት ሰዓት በላይ የሰውነት እንቅስቃሴ አደርጋለሁ። ያተኮርኩት በባቶቼ ላይ ነበር። ከጎድጉን ዓሣ ማጥመድ ራሱ ያጠናከራቸዋል። ለባቶቹም አንድ ጥሩ መላ አገኘሁ።ምዕበሎቹ ከታሩዎቼ ጋር ወደሚጋጩበት ቦታ ወጣ ብዬ ባጠምድ፤ እንዳልወድቅ ሚዛኔን ለመጠበቅ ስለምታገል ለጡንቻዎቼ በጣም ጥሩ ልምምድ ይሆናል።

የወህኒ ቤት አዛዥ ሚስት ገቦልየት ለእኔ በጣም ደግ ሆናለች፤ ግን ወደ ቤት የምግባው ባሷ እዚያ በሚሆንበት ወቅት ብቻ መሆኑን ተረዳች። አንድ ቀን እኔን ለማዝናናት ያህል ከፊት ለፊት ቀርባ ጸጉሯን በምትሰራበት ቀን የተናገረችው ለቀልድ እንደነበር ገለጸችልኝ። ጸጉሯን ስትሰራት የነበረችው ወጣት፤ ዓሣ አጥምጇ ስመለስ ዘወትር በመንገዴ ላይ እየጠበቀች ስላምታ በመስጠት፡ ስለኑሮዬ ለመጠየቅ ወዘተ . . . ታቆመኝ ነበር። ስለዚህ በዚያ አካባቢ ያለውን ማንኛውም ነገር የተስተካከለ ሆኗል።

ቦርሳ ጊዜ ከማባከን ፈጽሞ ተቆጥቦ ነበር። ከጀመርን እስከአሁን አንድ ወር ተኩል ሲሆን፤ እንዳየሁት ከሆነ የመደበቂያው ቦታም ሞልቶ ነበር። የሚጎድሉን ሁለት ቁራጮች ሲሆን፤ እነዚህ ግን ስድስት ጫማ ተኩልና አምስት ጫማ ቁመት ያላቸው በጣም ረጅሞቹ ነበሩ። ከዚያ ቁዳዳ ውስጥ ፍጹም መግባት አይችሉም።

በመቃብሩ አካባቢ ስታኝ፤ አንድ የጠፋለገ አስቀያሚ የአበባ ጉንጉን የተቀመጠበት ትኩስ መቃብር ተመለከትኩ። ምናልባት ከሳምንት በፊት ሞታ የነበረች

t.me/OLDBOOKSPDF

የአንድ ዘበኛ ሚስት መቃብር ይሆናል። የመቃብር ቦታው ጠባቂ ፓፓ በሚል ቅጽል ስም የሚጠራ አንድ ዐይኑ የጨረጨሰ አስረኛ፣ አብዛኛውን ጊዜውን የሚያጠፋው በሩቅ ከሚገኝ ከአንድ የኮከነት ዘንባባ ጥላ ስር ነበር። እዚያ ሆኖ መቃብሩንም ሆነ ወደ አቅራቢያው የሚመጣውን ማንኛውንም ሰው ለማየት አይችልም። ከተገጣጠሙች በኋላ ለጀልባዋ መቃብሩን ብጠቀምበትና የቻልኩትን ያህል ብዙ ኮከኑቹ ባከማችበት ምን አለበት? ግን የሚይዘው ኮከነት እኔ ከምፈልገው በጣም ያነሰ ሠላሳ አምስት ያህል ብቻ ቢሆን ነው። ስለዚህ ከሃምሳ በላይ የሆኑትን በተለያዩ ቦታዎች በታተንኳቸው። በዋልየት አትክልት ቦታ ብቻ አንድ ደርዘን ያህል ነበሩኝ። እዚያ የተውኳቸውን አንድ ቀን ዘይት ሊጨምቃቸው ይሆናል ብሎ የቤት ልጁ ገምቷል።

የሚቺ ሴት ባል ወደ ግራንዴቴሪ መሔዱን ስረዳ፣ የመቃብሩን አፈር ቆፍሬ ለማውጣት ወሰንኩ።

ማቴዎስ በግቢው ላይ ተቀመጠና እንደ ታፈር ሆነ። አራት ቦታ ላይ የተቋጠረ አንድ መሐረም በጭንቅላቱ ላይ አደረገ። በእጠገቡ ደግሞ እንደዚሁ አራት ቦታ ላይ የተቋጠረ አንድ ቀይ መሐረም አሰቀምጧል። አደጋ እስካልነበረ ድረስ ነጩን መሐረም እንዳደረገ ይቆያል። አንድ ሰው በእርሱ ትይዩ ከመጣ ቀዩን ያደርጋል።

ይህ አደገኛ ሥራ ግማሽ ቀንና አንድ ሌሊት ወሰደብኝ። አፈሩን የሬሣ ሣጥኑ እስካለበት ድረስ ወርጄ አልዛቅኩም፣ ምክንያቱም ጉድጓዱን ለጀልባዋ የሚበቃውን ያህል ወደ ጎን ለማሰፋትና አራት ጫማ ስፋት ለማንቀሳቀስ እንዲያመቸኝ፣ ሌላም ዕቃ ለመደበቂያ አንድ ትንሽ ከፍል መቆፈር ስለነበረብኝ ነው። በማቴዎስ ጭንቅላት ያለው ቀይ መሐረብም ብዙ ጊዜ ቁፋሮዬን ለማቆም አስገደደኝ። በመጨረሻም ነጋና እኔም ጨረስኩ። ጉድጓዱ በተንነጎኑ የዘንባባ ቅጠሎች ተሸፍኖ ጠንካራ መድረክ ሆነ። ከዚያ በላይ ትንሽ አፈር ደለደልኩበት። ምንም ሊታይ አይችልም። ይሆን በማከናውንበት ወቅት ነፍሴ ፍትልክ ብላ ለመውጣት ተቃርባ ነበር።

የማምለጡ ዝግጅት ሲካሔድ አሁን ሦስት ወር መሆኑ ነው። ምልክት የተደረገባቸው ቁርጥራጮች ከየተደበቁበት ቦታ ተወሰዱና በላያቸው ላይ ርብራብ ተጋድሞባቸው በአፈር በተሸፈነው የምስኪኗ ሴት ሬሣ ሣጥን ላይ ተቀመጡ። ውስጥም ሦስት ከረጢት ዱቄት፣ ለነፋስ ሽራ የሚሆን ሰባት ጫማ ርዝመት ያለው አንድ ገመድ፣ አንድ ትልቅ ፓኮ ከብሪት፣ አንድ የመሣሪያ ሣጥንና አንድ ደረዘን የቆርቆሮ ወተት አከማቸን።

ቦርሲ እያደር ስሜቱ እየተቀሰቀሰ መጣ። የሚሠራው ለራሱ ማምለጫ ነው ብላችሁ ታስቡ ይሆናል። በሁለት ፋንታ ለሦስት ሰዎች የምትበቃ ጀልባ መሥራት በቻለ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

የዝናሙ ወራት ጀመረ። በየቀኑ ስለሚዘንም የመቃብሩን ጉድጓድ ለመጎብኘት ቀላል ሆነልኝ። የጎደሉን በጎንና ጎን ከፈፍ የሚሆኑት ሁለት ቁራጮች ብቻ ነበሩ። ኮከቦቹን ቀስ በቀስ ወደ አትከልት ቦታ ወሰድኳቸው። ጓደኞቼ ፈጽሞ አይጠይቁኝም። አለፍ አለፍ እያሉ ብቻ እንደዘበት «ከምን ደረሰ?» ሲሉኝ «ደህና ነው» እላለሁ። «ረጅም ጊዜ ሊወስድብህ ነው፤ አይደለም እንዴ? ትልቅ አደጋ ላይ እንዳትወድቅ መቻኮል የለብህም።» ይሽው ብቻ ነበር።

ከዚያም በግቢዋ ውስጥ አጠራቅሚያቸው የነበሩትን ኮከቦች ሳጓጉዝ ገቦልየት አየችኝ። «ንገረኝ እስኪ ፓፒዮ የኮከብ ዘይትህን መች ልትጨምቅ ነው? እዚህ ግቢ ውስጥ ለምን እንደማትሰራ አይታየኝም። የምትፈረካከስበት አንድ መደሻ አለልህ፣ ለዱቄቱም አንድ ትልቅ ብረት ድስት ላውስህ አችላለሁ።»

«በካምፑ ውስጥ ባደርገው ይሻለኛል።»

«የሚገርም ነው። ካምፑ አይመችም» አለችና አረፍ በማለት፣ «ምን እንዳሰብክ እንድነግርህ ትፈልጋለህ?» አንተ በጭራሽ የኮከብ ዘይት ትጨምቃለህ ብዬ አላስብም» ስትለኝ ደነዘዝኩ። ቀጠል አደረገችና «መጠቀም የምትችልበትን ያህል የወይራ ዘይት በሙሉ ልሰጥህ ስችል፣ ለምን ይህን ያህል ለመቸገር ፈለግህ? ኮከቦቹ ለአንድ ነገር የታቀዱ ናቸው። አይደሉም እንዴ?» ስትለኝ ወፍራም የላብ ጠብታዎች በፊቴ ላይ ኩልል እያሉ ይወርዱ ጀመር። ማምለጥ የሚለውን ቃል አስከሰማ ነበር የምጠብቀው። እንደልብ መተንፈስ አቃተኝ።

«እሜቴ ምስጢር መሆን ነበረበት፣ ግን ለማወቅ አጥብቀሽ መጓጓትሽ እንድነግርሽ አስገደደኝ። ይሁንና የምለው ነገር ቢኖር ኮከቦቹን የለቀምኳቸው ለቅርፊቶቻቸው ስል ነው፣ አንድ ነገር ሰርቼ በስጦታ ላበረከትልሽ። ለዚሁ ብቻ ነው።»

ውሸቴ ሰመረልኝና «ፓፒዮ፣ ለእኔ ብለህ እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ መግባት የለብህም። አንድ የማይረባ ነገር እሠራላታለሁ ብለህ ገንዘብህንና ጊዜህን አታጥፋ። ከልብ አመሰግናለሁ፤ ማድረግ የለብህም» አለች።

ያንን መወሰኑ የእኔ ጉዳይ ነው። ይገርማል እኮ! ከእሁን በፊት እድርጌው የማላውቀውን አንድ ፓስቲስ እንድትሰጠኝ ጠየቅኳት።

ከሰዓት በኋላና ማታ ሀይለኛ ዝናብ ወረደ። በስሱ ከለበሰው አፈር ውስጥ ውሃ ሰርስሮ በመውረድ ርብራቡን ይገልጠዋል ብዬ ሠግቼ ነበር። ማቴዎስ ዘወትር አፈረን እየመለሰ ያለብሰው ነበር። ከሥር በኩል ጎርፍ እንደሚገባ እርግጠኛ ስለሆንኩ፣ ርብራቡን ስንከፍተው ውሃው ከሬሳ ሣጥኑ ላይ ሊደርስ ምንም አልቀረውም። አሳሳቢ ነበር። ከዚያ በጣም ሳይርቅ ከብዙ ዓመታት በፊት የሞቱ ሁለት ሊጆች መቃብር ይገኛል። የመቃብሩን ድንጋይ አነሣንና ወደ ውስጥ ተሰቢ በመግባት ጀልባው ባለበት

t.me/OLDBOOKSPDF

የመቃበር ጉድጓድ በኩል ያለውን ሲሚንቶ በዶማ ሰነጣጠቅኩት። ወዲያውኑም አፈሩን በዶማ ገለል ሳደርግለት ከፍተኛ የውሃ ጥርቅም ወደ ልጅቱ መቃበር ውስጥ ፈሰሰ። ወደ ጉልበቴ አካባቢ ሲደርስ ተንጠላጥዬ ወጣሁ። ድንጋዮን በቦታው መለስንና ናሪክ ባገኘልን ነጭ ሰትኮ መረግነው። በዚህ ዓይነት ዘዴ ከነበረው ውሃ በከፊል ለማቃለል ቻልን።

በዚያም ምሽት ካርቡኔሪ፣ «በዚህ የማምለጥ ሙከራችን ችግር እንጂ ሌላ ምንም ያተረፍነው ነገር ያለ አልመሰለኝም» አለ።

«አይዞህ፣ እንግዲህ ተቃርበናል» አልኩ።

«እስኪ እስከዚያ በተሰሩ እንኑር። ሲበዛ መቅበጥበጥ ጀምረን ነበር።

በሚቀጥለው ጧት ወደ ወደቡ ወረድኩና ቻፓር አምስት ፓውንድ ዓሣ ለማስመሰያ ያህል እንዲገዛልኝ ጠየቅኩት። ቀትር ሲሆን እንደምወስደው ነገርኩት። ከዚያም ወደ ካርቡኔሪ አትክልት ቦታ ሔድኩ። ሦስት ዘበኞች ከዚያ ነበሩ። ምን እያደረጉ ይሆን? ይህ ብዙ ጊዜ ያልተለመደ ነበር። ፍተሻ እያካሔዱ ይሆን እንዴ? በአካባቢው ዘበኞች ፍጹም አይቼ አላውቅም። አንድ ሰዓት ያህል ጠበቅኩ። ከዚያም ምን እንደሚካሔድ ማወቅ አስፈለገኝ። የሆነው ይሁን ብዬ ወደ አትክልት ቦታ በምትወስደው የእግር መንገድ መራመድ ቀጠልኩ። ዘበኞቹ ስመጣ ይመለከቱኛል። ዐርባ ያርድ ርቀት ላይ እንደደረስኩ ማቴዎስ ነጩን መሐረብ በጭንቅላቱ ላይ አደረገ። ደጋግሜ ተነፈስኩና ወደ እነርሱ ከመቅረቤ በፊት ራሴን አስተካከልኩ።

«እንደምን አደራችሁ ወዳጆቼ፣ እንደምን አደርክ ማቴዎስ። እዚህ የመጣሁት ቃል የገባህልኝን ፓፓየ ፍለጋ ነው» አልኩ።

«አዝናለሁ ፓፒዮ፣ ለባቄላዎቼ ማስደገፊያ ባላዎች ለመፈለግ እንደሔድኩ አንድ ሰው ሰርቋቸዋል። በዐራት ወይም በአምስት ቀን ውስጥ ሌሎች ተጨማሪ የሚበሰሉ ይኖሩኛል፤ አሁንም ወደ ቢጫነት እየተቀየሩ ነው። ወዳጆቼ ትንሽ ሠላጣዎች ወይም ቲማቲሞች አትፈልጉም እንዴ? ምናልባት ለሚስቶቻችሁም ትንሽ ቀይ ሥሮች» አለ።

«የአትክልት ቦታህ በሚገባ ለምቷል ካርቡኔሪ። እንኳን ደስ አለህ አላለሁ» አለ ከእነርሱ አንደኛው።

ሠላጣዎቹን፣ ቲማቲሞችንና ቀይሥሮችን ተቀብለው ሔዱ። እኔም ሁለት ራስ ሠላጣዎች ያዝኩና ከእነርሱ በፊት መሔድ ጀመርኩ።

በመቃበር ቦታው በኩል አለፍኩ ውሃው መቃበሩን በከፊል ገልጦ አፈሩን አጥቦ ወሶዶታል። ርብራቡን ከዐሥር እርምጃ ርቀት ላይ ማየት ቻልኩ። ካለ መጋለጥ አጥቦ ወሶዶታል። ርብራቡን ከዐሥር እርምጃ ርቀት ላይ ማየት ቻልኩ። ካለ መጋለጥ ያዳነን ቸሩ እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ነፋሱ ዘወትር ለሊት ያፏጫል፤ አንዳንድ ጊዜም

t.me/OLDBOOKSPDF

የዝናም ውሽንፍር ይመጣል። ለማምለጥ ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ ነበር።

በጣም ተፈላጊና በአንጻሩ ደግሞ ችግር ፈጣሪ የነበረው ባለስድስቱ ጫማ እንጨት ከሌሎቹ ጋር ተደባለቀ። በቦታው ውስጥ ሳስቀምጠው ልክክ ብሎ ተሰካ። ደርሶኝ እንደሆነ ለማረጋገጥ ቦርሴ ወደ ካምፕ ሲሮጥ መጣ። ሁሉም ነገር መስተካከሉን ሲያውቅ በጣም እፎይታ ተሰማው።

«ችግር ተፈጥሯል እንዴ?» ስል ጠየቅኩት። «አንድ ሰው ይከታተለናል ብለህ ታስባለህ መሰለኝ? ስለዚህ ጉዳይ ለሰው ነግረሃል እንዴ?»

«አልነገርኩም። በጭራሽ አልነገርኩም።»

«ግን አንድ ነገር እያብሰለሰልህ ነው። ምንድን ነው?»

«ቤቨርት ሴሊየር የተባለ አንድ ሰው ዐይኑን የጣለብን ይመስላል። እንደሚመስለኝ፣ ናሪከ ቁራጭ እንጨት ከስራ ቦታው ተሸክሞ ሲወጣ አይቶታል። እስከ ወርክሾፑ በር ድረስ ተከትሎ ነበር። ይህ ነው ያሰጋኝ።» አሉ።

ለግራንዴ እንደዚህ አልኩት። «ቤቨርት ሴሊየር የሚኖረው እኛ ሣጥን ውስጥ ነው። አዋሻኪ ሊሆን በምንም አይችልም። ሊሆን ይችላል እንዴ?»

«በማህበራዊ ሥራ አገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ከተመደቡት አንዱ ነበር። በሞሮኮና በአልጀሪያ በማንኛውም ወታደራዊ ወህኒ ቤት ውስጥ በነበሩ የአፍሪካ ባታሊዎን ኮሚሳሪያት ከተባሉ ችኮ ወታደሮች አንደኛው ነው። ተደባዳቢ፣ በጨቤ ውግያም አደገኛ፣ ቁማርተኛ ነው። የቀኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ለእርሱ አለሙ ነው። እናም በእርግጥ የምትጠራጠረው ነገር ካለ 'ወይፈኑን ቀንዶቹን ጠምገዘህ ጣለው' እንደሚባለው ውለህ ሳታድር ዛሬ ማታ ግደለው። አስኪያቃጥር ድረስ ጊዜ አትስጠው። «አሣባቂ ለመሆኑ ማረጋገጫ የለንማ» አልኩ።

«ዕውነት ነው» አሉ ግራንዴ፣ «ግን ላለመሆኑ ማረጋገጫ የለንምኮ! የእርሱ ዓይነት ከባድ ኢሥረኞች ማምለጥ ሲባል አይወዱም። በሚገባ የተደላደለ ኑሯቸውን የሚያናጋባቸውን ማንኛውንም ነገር ይጠላሉ። ስለሌላ ነገር አሣባቂዎች ላይሆኑ ይችላሉ፣ ስለማምለጥ ግን ማን ያውቃል?»

ማቴዎስንም አዋየሁት። የእርሱም ምክር በዚያው ዕለት ማታ ቤቨርትን መግደል ነበር። እንዲያውም ራሱ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆነ። እምቢ በማለቴ ስህተት አደረግኩ። በይመስላል ብቻ አንድን ሰው ልግደል ብሎ ማሰብ ወይም እንዱ እንዲገድለው መፍቀድ አልዋጥልኝ አለኝ። ምናልባት ቦርሴ መስሎት ቢሆንስ? ፍርሃት አንድ ነገር ሊያስፈለስፈው ይችል ይሆናል፣ ማን ያውቃል።

ናሪከን ጠየቅኩት። «ስለ ቤቨርት ሴሊየር የተመለከትከው እንግዳ ነገር አለ እንዴ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አኔ? የለም። እንጨቱን ኖራ በርሜል ውስጥ ከትቼ በርሜሉን ቧትከሻዬ ቀሽኮሜ ስለወጣሁ ከበሩ ያለው ቁልፍ ያዥ በውስጡ ያለውን ለማየት አልቻለም። አማቼ አስኪመጣ ድረስ ልከ ከእርሱ ፊት ለፊት ቆምሁ። አረቡ አለመቸኮሌን ሲመለከት ያለጥርጥር ስለሚያምነኝ፣ በበርሜል ውስጥ ያለውን ለማየት እንደማይፈልግ ገምቻለሁ። ግን በኋላ አማቼ እንደነገረኝ ቤቨርት ሴልየር በጣም አተኩሮ ይመለከተኝ ነበር።»

«ታድያ ምን ይመስልሃል?»

«ትልቅነቱ በጣም ስለሚያሳጣ፣ በተለይ አማቼ ከፉኛ ደንግጦ ነበር። ዘወትር ከሚያየው የበለጠ ሆኖ ነው የታየው።»

«እኔም ያሰብኩት ይህንኑ ነው። እንግዲህ እንርሳው። ወደ መጨረሻው ቁራጭ ስንደርስ፣ በምትወጡበት ወቅት ቤቨርት ሴሊየር በአካባቢው አለመኖሩን እርግጠኞች ሁኑ። ለአንድ ዘበኛ የምታደርጉትን ሁሉ ለእርሱም ተመሳሳይ ጥንቃቄ ውሰዱ።»

በዚያ ሌሊት በጣም ከፍተኛ መደብ አያስያዝኩ ስቆምር አደርኩና ሰባት ሺ ፍራንክ በላሁ። ለጨዋታው ስሜቴ ቢቀዘቅዝም፣ የማሸንፈው ገንዘብ እየጨመረ ሔደ። ከሌሊቱ ፀሥር ሰዓት ተኩል ላይ ለሥራ ተነሣሁ። ይሁንና ሥራውን ለማርቲኒካዊው ጥቁር አስተላለፍኩ። ዝናሙ አባርቶ ስለነበር፣ በጨለማ ውስጥ ወደ መቃበር ቦታው እየዳከሁ ሔድኩ። አካፋውን ማግኘት ስላልቻልኩ፣ አፈሩን በእግሮቼ እየገፋሁ መመለስ ነበረብኝ። ዓላ ለማጥመድ ወደ ታች ስወርድ ፀሐይዋ ወጥታ ነበር። ጀልባዋን አንሳፍፍበታለሁ ብዬ ከአቀድኩበት ከሮያሌ ደቡባዊ የመጨረሻ ዳርቻ ሔድኩ። ማዕበሉ ከፍተኛና ባሕሩም ቁጡ ስለነበር ወደ ኋላ ተመልሰው ከቋጥኞች ጋር ሳይላተሙ ከደሴቷ መራቅ አስቸጋሪ መሆኑ ግልጽ ነበር። ማጥመድ ጀመርኩና ወዲያውኑ ብዛት ያላቸው ዓሣዎች ያዝኩ። በአንድ አፍታ ከፀሥራ ሁለት ፓውንድ በላይ አጥምጄ ነበር። ማጥመዴን አቆምኩና ዓሣዎቹን ባሕሩ ውስጥ አጸዳሁ። በጣም ውጥረት ይዞኛል፣ ከረጅም ሌሊት የቁማር ጨዋታ የተነሳም ተጫጭኖኛል። በጥላ ሥር ተቀመጥኩና ሐሳቤን ለማሰባሰብ ሞከርኩ። ሦስት ወር ሙሉ ታምቆ የነበረው ጭንቀቴ በቅርቡ ፍጻሜ ሊያገኝ ነው ብዬ ራሴን አጽናናለሁ። ከዚያም ስለ ቤቨርት ሴሊያር አሰብኩና እሱን ለመግደል መብት እንደሌለኝ ወሰንኩ።

በመጨረሻም ማቴዎስን ለመታበኘት ሔድኩ። ከእርሱ አትከልት ቦታ ሆኖ መቃበሩን በቀላሉ ማየት ይቻላል። በገፍልየት በኩል አለፍኩና ግማሾቹን ዓሣዎቼን ሰጠኋት።

«ፓፒዮ ባለፈው ሌሊት ስለአንተ መጥፎ ህልም አየሁ። በሰንሰለት ታስረህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰውነትህን በደም ተበክሎ ነበር። እባክህ የሞኝ ነገር እንዳትሰራ፣ በአንተ ላይ እንድ ነገር ቢደርስ በጣም ሲበዛ የምሰቃየው እኔ ነኝ። አየህ ህልሜ ከፉኛ ስላስደነገጠኝ ነና አልታጠብኩም፤ ጸጉሬን እንኳ አላበጠርኩም። የት እንደምታጠምድ ለማወቅ በሩቅ መነጽሬ ብመለከትም ላገኝህ አልቻልኩም። እነዚህን ከወዴት ነው የያዝካቸው?»

«ከደሴቷ በስተጀርባ። ያላየሽኝም ለዚህ ነው።»

"ማንም ሰው ሊያይህ ከማይችልበት ቦታ ለምን በጣም ርቀህ ትሔዳለህ? ማዕበል ቢወስድህ ምን ትሆናለህ? ከዓሣ ነባሪዎች የሚያተርፍህ ማንም ሰው አይኖርም» አለች።

«አ፡ አታጋኚው እንጂ!»

«አያጋነንኩት ነው ብለህ አሰብክ? መልካም! ግን ከዚያ እንዳታጠምድ ከልከዬሃለሁ። የማትታዘዘኝ ከሆነ ፈቃድህን ለማስወሰድ አስብበታለሁ።»

«ተይ እንጂ ማመዛዘን ይኖርብሻል። ደስ የሚያሰኝሽ ከሆነ ለማጥመድ የምሔድበት ቦታ የቤት ልጅሽ እንዲያውቀው አደርጋለሁ።»

«መልካም! ለምንድን ነው በጣም የደከመህ።»

«ስለደከመኝ ነዋ። ስለዚህ ለመተኛት ወደ ካምፕ እየተመለስኩ ነው።»

«እሺ ግን በዐሥር ሰአት ቡና አፍልቼ እጠብቅሃለሁ። ትመጣለህ?»

«አዎ እመቤቴ! በኋላ አይሻለሁ።»

የገፍልየት ሕልም! ልሰማው የጓጓሁለት! ራሱን የቻለ ሌላ ችግር እንደሌለኝ ሁሉ...

እንደሚከታተሉት አርግጠኛ መሆኑን ቦርሴ ነገረኝ። አምስት ጫማ ርዝመት ለነበረው የመጨረሻ ቁራጭ ዐሥራ አምስት ቀን ጠበቅን። ናሪከና ኬኔር ቢወተውቱትም ቦርሴ ግን ለመሥራት ፈርቶ ነበር። ናሪከና ኬኔር ጸሎት ቤቱን ስለሚያድሱ፣ ማንኛውም ዓይነት ዕቃ ይዘው ከወርከሾፑ መግባትና መውጣት ይችሉ ነበር። አንዳንድ ጊዜም በአንድ ጎሽ በሚሳብ አንደ ትንሽ ጋሪ ሳይቀር ይጠቀማሉ። በዚህ አጋጣሚ መጠቀም ነበረብን።

ከራሱ ጋር እየተማከተ ቦርሴ ቁራጩን መስራት ጀመረ። ከዚያም አንድ ቀን እርሱ በሌለበት ወቅት አንድ ሰው እንዳንቀሳቀሰው አርግጠኛ መሆኑን ገለጸልኝ። ከማጋጠሚያዎቹ አንደኛውን ገና መስራት ስለነበረበት ያንን እንዲያደርግና ከዚያም በኋላ ቁራጩን ከሥራ ጠረጴዛው ሥር እንዲያስቀምጠው ወሰንን። ሰው የነካካው ከሆነ ምልከት እንዲሰጥ አንዲት የጸጉር ዘለላ ያስቀምጥበት ነበር። ሥራውን ጨረሰና ከዘበኞቹ በስተቀር ማንም ሰው አለመቅረቱን ካረጋገጠ በኋላ፣ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ከወርከሾፑ ወጣ። ጣውላውና ጸጉሩ በቦታቸው ተቀምጠዋል። ቁትር ሲሆን ከወርከሾፑ

t.me/OLDBOOKSPDF

የሚመጡትን ሰማንያ ሰዎች በመጠባበቅ እኔ በካምፑ ውስጥ ነበርኩ። ናሪከና ኬኔር ሊወጡ ይታዩኛል። ቦርሴ ግን የለም። አንድ ጀርመናዊ ወደ እኔ ቀረብ ብሎ በጥንቃቄ የታሸገ አንድ ደብዳቤ ሰጠኝ። ተከፍቶ እንዳልነበር ላረጋግጥ ችያለሁ።

«ጣውላውን አንድ ሰው ነክቶ ነበር፣ ጸጉሩ ለምልክትነት ከተቀመጠበት ተነስቷል። በዕረፍት ሰዓት ቆይቼ እንድሰራ ዘበኛው ፈቅዶልኛል። ጀምሬያት የነበረችውን አንዲት ሣጥን እንድጨርስ ነግሬው ነው። ጣውላውን ወስጄ ከናሪከ የሥራ መሣሪያዎች ጋር አስቀምጠዋለሁ። ስለሁኔታው እንድትነግረው። ከጣውላው ጋር ልከ በዘጠኝ ሰዓት መውጣት አለበት። በምስጢር የሚከታተለኝን ያንን ሰው፣ በሆነ ዘዴ ልናምታታው ይገባል።» የሚል አነበብኩ።

ናሪከና ኬኔር ተስማሙ። ማንኛውም ሰው ወደ ወርከሾፑ ከመመለሱ በፊት፣ ሁለት ሰዎች አበሩ ውጭ እንድ አምባጓሮ ይጀምራሉ። ይህን ሥራ እንዲያቀናብሩ የተመደቡ ማሲኒና ሳንቲኒ የተባሉ ከማርሴ የመጡ ሁለት ኮርሲካውያን የካርቡኔሪ ጓደኞች ነበሩ። ደግነቱ ለምን ብለው አልጠየቁም። ናሪከና ኬኔር ከሠልፉ በመጀመሪያው መስመር ሆነው ይጠባበቃሉ። እንባጓሮው እንደተፈጠረም በግርግሩ ሰበብ ወደ ውስጥ ለመሮጥ አጋጣሚውን ይጠቀሙበታል። በሥራ ላይ ለመገኘት የተጣደፈ በመምሰልና አምባጓሮውን እንደማይመለከታቸው ችላ በማለት የተዘበራረቁ ዕቃዎቹን ተሸክመው ሊወጡ ነበር ዕቅዳችን። ይህ የመጨረሻ እድላችን መሆኑን ሁላችንም ተስማምተንበታል። ይህ ከተሳካ ለአንድ ወይም ለሁለት ወራት ምንም ሳንቀሳቀስ እናደፍጣለን፣ ሰዎች ጀልባ በመስራት ላይ መሆናችንን እንዳይደርሱብን።

ሰምንት ሰአት ተኩል ሲሆን ሰዎቹ ተዘጋጅተው ነበር። ለስም ጥሪና ወደ ሥራ ለመሔድ የሚሰለፉበት ሠላሳ ደቂቃ አላቸው። እያንዳንዳቸው ዐራት ሰዎች ካሉባቸው ሐያ ረድፎች ውስጥ በአንደኛው ቤቨርስ ሴሊየር ነበረበት።

ናሪከና ኬኔር በመጀመሪያው ረድፍ፣ ማሲኒና ሣንቲኒ በዐሥራ ሁለተኛው፣ ቤቨርት ሴሊየር በዐሥረኛው ነበሩ። ሁኔታው ልከ በገዛ ራሱ የተስተካከለ ይመስላል። ምክንያቱም ከረጃጅሞቹ ግንዲላዎች አደባልቀው የእኛን ጣውላ በማንሳት ላይ እንዳሉ ሌሎቹ ገና ከበራቸው ደረሱ። እንባጓሮው ሲፈነዳ ሁሉም፣ ቤቨርትንም ጨምሮ ወደኋላቸው በመዞር በጥሉ ላይ አተኮሩ። ብዙ ጫጫታና ትርምስም ተፈጠረ። በትክክልም እንደተባለው ተሳካ። በዐሥር ሰአት ሁሉም ተከናውኖ ጣውላው በጸሎት ቤት ውስጥ ከተቀለሉ እቃዎች ስር ተደበቀ። ከዚያ መውጣት እንዴት እንደሚችሉ ግን ገና ዘዴ አየፈለጉ ናቸው። ግን በጥንቃቄ ተቀምጦ ነበር። ዝርዝራችን ለማየት ስሔድ እቤት አልነበረችም። ስመለስ እግረ መንገዴን በአስተዳደሩ ሕንፃ በኩል ላልፍ ስል ማሲኒና ሳንቲኒ ከጥላ ስር ቆመው ወደ ጨለማው ግንብ ለመግባት ሲጠባበቁ

t.me/OLDBOOKSPDF

እየኋቸው። ይህ እንደሚደርስ ገምተን ነበር።

ወደ እነሱ ቀረብ አልኩና፣ «ምን ያህል ፈረዱባችሁ?» አልኳቸው።

«ስምንት ቀን።»

አንድ ኮርሲካዊ ዘበኛ «እንዴት ይህ ሊሆን ይችላል! ሁለት ኮርሲካውያን እርስ በርሳቸው ቢደባደቡ . . .!» አለ።

ወደ ካምፕ ተመልሼ ሔድኩ። ካርቡነሪና ጓደኞቹ በደስታ ተንሳፍፈው ድርጊቱን ለማቀነባበር ባደረግኩት ስልት «እንኳን ደስ አለህ» አሉኝ። ናሪክና ኬነርም እንደዚሁ ደስ አላቸው። ማንኛውም ነገር በከፍተኛ ደረጃ እየተቀላጠፉ ነበር። ምንም እንኳ ካርታ እንድጫወት ብጠየቅም ቅሉ ሌሊቱን ሙሉ ተኛሁ። ራስ ምታት አሞኛል በማለት አሳበብኩ። ሰውነቴ ፍጹም ዝሎ የተዳከምኩ ብሆንም፤ አላማዬ ሲሳካ በመሆኑ ከመጠን በላይ ፈንጥዣለሁ። በእመዛኙ ከባዱ ከፍል ተጠናቋል።

በማግስቱ ጧት ማቴዎስ ጣውላውን ጉድጓድ ውስጥ አስቀመጠው። የመቃብር ቦታው ዘበኛው ከመቃብሩ አጠገብ ያለውን መንገድ እየጠረገ ነበር። አሁን ወደዚያ በጣም መጠጋት አደገኛ ይሆናል። በየጊዜው ጧት አንድ የአንጨት ባልዲ አይዝና የመቃብሩ ጉድጓድ አፈር እመልሳለሁ። መንገዱን በአንድ መጥረጊያ አጸዳውና ከዚያም ባልዲውንና መጥረጊያውን ወደ አንድ ጥግ ሸጉጬ ወደ ሥራዬ እመለሳለሁ።

ይህን የማምለጥ እቅድ ከጀመርን ልክ አራት ወር ሲሆነን የጀልባውን የመጨረሻው ቁራጭ ካገኘን ደግሞ ዘጠኝ ቀኖች ሆነዋል። ሌሊት ሌሊት ትንሽ ከመጣሉ በስተቀር ዝናሙ አቁሟል። አስተሳሰቤ በሙሉ ያዘነበለው ወደ ሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች ነበር። በመጀመሪያ ያንን መመዘኛ ጣውላ ከማቴዎስ አትከልት ቦታ ማውጣትና ከዚያም በጀልባዋ ላይ መግጠም። ይህንንም ማድረግ የሚቻለው በቀን ብቻ ነበር። ከዚያም ማምለጥ! ግን ይህ እንኳ ኮከነቶቹንና ስንቃችን ተጭኖ ጀልባዋ እስከትንቀሳቀስ ድረስ መቆየት ይኖርበታል።

ለዮሐንስ ካስቴሊ የሚገኙበትን ደረጃ ገለጽኩለት። ይህን ያህል ወደ መጨረሻው በመቃረቤ ደስ አለው። «ጨረቃዋ ገና አዲስ መውጣቷ ነው» ሲል አስተያየቱን ሰነዘረ።

«ወውቃለሁ። ግማሽ ሌሊት ላይ ምንም ችግር አይኖርም። ማዕበሉ ወደ ውጭ የሚሔደው ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ነው፤ ስለዚህ ጀልባዋን ውሃው ላይ ለማስቀመጥ ተስማሚው ወቅት ከሌሊቱ በሰባትና በስምንት መካከል ይሆናል።»

ካርቡነሪና እኔ ነገሮችን ማቀላጠፍ እንደሚኖርብን ወሰንን። በሚቀጥለው ጧት የመጨረሻውን ከፍል እንገጥማለን። በዚያው ሌሊት እናመልጣለን።

በማግሥቱ ጧት ከአትክልቱ ቦታ ወደ መቃብሩ ሔድኩና አንድ ባልዲ በእጄ

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደያዝኩ በግንቡ አጥር ላይ ዘለልኩ። ከርብራቡ በላይ ያለውን አፈር እኔ ስገፍለት፣ ማቴዎስ ደግሞ ወደ ጣውላዎቹ ለመድረስ ድንጋዮቹን ከግንቡ እየፈነቀለ ያወጣ ነበር። ከዚያም ርብራቡን አብረን አነሣንና ከአንድ በኩል አስቀመጥነው። ጀልባዋ በጥሩ ሁኔታ ላይ ያለች ትመስላለች። ትንሽ ቆሸሸ ብትልም ምንም አልነበረም። የመጨረሻውን ቁራጭ ለመግጠም በቂ ቦታ እንዲኖረን ወደ ውጭ አወጣንና ከዚያም የተላጉትን የኑን ጣውላዎች በአንድ ድንጋይ እየመታን በየስኩቻቸው አስገባናቸው። ጨርሰንና ጀልባዋን ልክ ወደ ቦታዋ መልሰን ልናስቀምጥ ስንል ካርባይን በእጁ የወደረ አንድ ዘበኛ ከተፍ አለ።

«እንዳትንቀሳቀሱ፤ አለበዚያ እተኩሳለሁ!»

ጀልባዋን ጣልንና እጆቻችንን ወደ ላይ አነሣን። ዘበኛው ማን እንደሆነ አስታወስኩ። ወርከቦቹ ከሚጠብቁት አንዱ ነበር።

«ምንም ነገር ማድረግ እንዳትሞክሩ። አግኝቻችኋለሁ። ጥፋታችሁን እመኑና ቢያንስ ሕይወታችሁን እንኳ አድኑ። ነፍሳችሁ በከር መንጠልጠሏን አትርሱ። በእርግጥ አሁኑኑ አንድ ካርታ ሙሉ ጥይት ብነሰንስባችሁ ደስ ባለኝ ነበር። መልካም፤ መንገድ ቀጥሉ። እጆቻችሁን ወደ ላይ» አለ።

የመቃብሩን ቦታ መግቢያ እንዳለፍን አንድ ቁልፍ ያዥ አረብ አገኘን። «ስለ እርዳታህ አመሰግናለሁ ሞሐመድ። ቃል የገባሁልህን እንድሰጥህ ነገ ጧት እንድትመጣ» አለው ዘበኛው።

«አመሰግናለሁ» ሲል ያ ልከስከስ ውሻ መለሰ። «አያስቡ ጌታዬ፤ እንዳሉኝ ወደዚያው እመጣለሁ። ግን ቤቨርት ሲሊየርም አንድ ነገር ሊለኝ ይገባል እኮ!»

«ያንን ከእርሱ ጋር ተወያዩበት» አለ ዘበኛው።

እኔም ቀጠል አድርጌ «በእኛ ላይ ያቃጠረው ቤቨርት ሲሊየር ኖሯል ጌታዬ?»

«እንደዚያ አላልኩም። ወጣኝ?» አለ።

«ምንም አይደል፣ ብቻ ማወቁ ጥሩ ነው።»

ዘበኛው አሁንም ካርባይኑን እኛ ላይ እንደ ወደረ፣ «ሞሐመድ ፈትሻቸው» አለው።

ዐረቡ ጩቤዬን ከቀበቶየ ውስጥ አገኛት፣ ቀጥሎም የማቴዎስን ወሰደ።

«ሞሐመድ» አልኩት፤ «በጣም ፈጣን ነህ። እንዴት እኛን መያዝ ሆነልህ?»

«ጀልባዋን ምን እንደምታደርጉ ለማየት በየቀኑ አንድ ዘምባባ ዛፍ ላይ እንጠላጠል ነበር።»

«ይህን እንድታደርግ ማነው የነገረህ?»

«በመጀመሪያ ቤቨርት ሲሊየር፣ ከዚያም ዘበኛው ብሩየት ናቸው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አንሒድ» አለ ዘበኛው። «እንግዲህ መነጋገሩ ይብቃ። አሁን እጆቻችሁን ማውረድ ትችላላችሁ። ተንቀሳቀሱ።»

አዛዡ ድረስ ያሉት አራት መቶ ያርዶች፣ መቸውንም ተራምጃቸው የማላውቅ ረጅም ጉዞ ሆነብኝ። ለመሞት ፈለግኩ። ያ ሁሉ ትግል በሁለት ድንፈፍ አህዮች ለመያዝ! ወይ አምላኬ፣ ግን አንተ ጨካኝ ነህኮ! የእኛ ወደ ወህኒ አዛዡ ዘንድ መድረስ ታላቅ ሽብ ረብ አስከትሎ ነበር። ወደ አስተዳደሩ ሕንፃ ስንቃረብ ዘበኞች እየመጡ ከእኛ አጃቢ ጋር ይደባለቁ ጀመር። በምንደርስበት ወቅት ሰባት ወይም ስምንት ያህል መሆን አለባቸው።

ወሬውን ለአዛዡ ለማቀበል አረቡ ቀድሞ ሮጧል። ዴጋ ከአምስት ዘበኞች ጋር ሆኖ ከበሩ ላይ ቆሟል።

«ምንድን ነው ሙሴ ብሩየት?» አለ።

«እነዚህን ሁለቱን እጅ ከፍንጅ ያዝኳቸው። ልታልቅ የተቃረበች አንዲት ጀልባ ደብቀው ነበር።

«አንተ ራስህ የምትሰጠው ምን መልስ አለህ ፓፒዮ?»

«ምንም ነገር የለም። በምርመራው ወቅት እናገራለሁ።»

«ጨለማ ግንብ ውስጥ አስገቧቸው።»

ከሕንፃው መግቢያ አጠገብ የምትገኝ መስኮቷ የተደፈነ አንዲት ከፍል ውስጥ ገባሁ። ከፍሉ ጨለማ ነበረ፣ ግን ሰዎች ከውጭ በኩል ሲነጋገሩ ይሰማኛል።

ነገሮች እየተፋጠኑ ሔዱ። በዘጠኝ ሰዓት ወደ ውጭ ወጣንና እጆቻችን በካቴና ታሠሩ። የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ፣ ረዳት አዛዡና የዘበኞቹ ኃላፊ የሚገኙበት ልዩ ፍርድ ቤት የሚመስል አንድ ችሎት ተሠየመ። ሌላ አንድ ዘበኛ እንደ ጸሐፊ ሆነ። ዴጋ እርሳስ በእጁ እንደያዘ የእኛን ቃል ለመመዝገብ ተዘጋጅቶ አንዲት ትንሽ ጠረጴዛ አጠገብ ተቀመጠ።

«ሻሪየና ካርቡኔሪ፣ ሙሴ ብሩየት የሚያቀርቡባችሁን ክስ አዳምጡ። ሕጌ አውጉስቴ ብሩየት የዘበኞች ኃላፊና ዱላሊዩ ደሴቶች የሚገኘው ወርከሾፕ ዲሬክተር፣ ሻሪየና ካርቡኔሪ በተባሉት ሁለት ከባድ እሥረኞች ላይ በስርቆትና የመንግሥት ሀብት በማባከን ክስ አቀርባለሁ። አናጢው ቦርሴንንም በተባባሪነት እከሰሳለሁ። ናሪከና ኬነርንም እንደዚሁ በግብረ አበርነት ልከስ የምችል ይመስለኛል። ሻሪየንና ካርቡኔሪን እጅ ከፍንጅ የያዝኳቸው ለጀልባቸው መደበቂያ በድፍረት በቆፈሩት በማዳም ፕሪቫትን መቃብር ውስጥ ነው።» ይላል። «እና ለዚህ የምትሰጡት ምን መልስ አላችሁ?» ሲል አዛዡ ጠየቀ።

«በመጀመሪያ ደረጃ ካርቡኔሪን እዚህ ውስጥ ምንም የሚያገባው ነገር የለም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ያልባዋ የታቀደችው አንድ ሰው ብቻ ለመያዝ ነበር። ይኸውም እኔን። ርብራቡን ከመታበሩ ላይ ለማንሣት እንዲረዳኝ ብቻ እርሱን ጠይቄያለሁ። በስርቆትም ሆነ የመንግሥት ንብረት በማባከን ወይም የማምለጥ ተግባር እስካልተካሔደ ድረስ፣ በማምለጥ ግብረአበርነት ካርቡኔሪ ወንጀለኛ አይሆንም። ቦርሴም የሞት ዛቻ ተሰንዝሮበት እየተሠቃየ የሚሠራ አንድ ምስኪን ሰው ነው። ናርከና ኬነር ለተባሉት ግን፣ ማን መሆናቸውንም አላውቅም። እዚህ ውስጥ ምንም የሚያገባቸው ነገር አይኖርም።

«ጠቋሚየ የነገረኝ እንደዚያ አይደለም» አለ ዘበኛው።

«ጠቋሚህ ቤቨርት ሲሊየር ነው። በሐሰት በመወንጀል አንድ ሰው ላይ በቀሉን ለመወጣት ሲል ያደረገው ሊሆን ይችላል። እንዲያውም እንዴት አንድ አቃጣሪ ልታምን ቻልክ?»

«መልካም» አለ አዛዡ። «በስርቆትና የመንግሥት ንብረት በማባከን፣ መቃብር በመድፈርና በማምለጥ ሙከራ ተከሳችኋል። እዚህ ላይ ፈርሙ።»

«የምፈርመው ስለ ካርቡኔሪ፣ ቦርሴ፣ ናሪከና ኬነሪ የሰጠሁት ቃል ሲጨመርልኝ ብቻ ነው» አልኩ።

«ደህና፣ ጻፉለት።»

ፈረምኩ። ከዚያ ወዲያ የሆነውን በዕውነት ልነግራችሁ አልችልም። ከአእምሮየ ቁጥጥር ውጭ ነበርኩ። ፍጹም አልበላም፣ መንቀሳቀስ አልችልም፣ አንዱን ሲጋራ በአንዱ ላይ እያከታተልኩ ያለማቋረጥ አጨሳለሁ። ደግነቱ ዴጋ ትምባሆ በሚገባ ያስታቅፈኛል። በከፍተኛ ደረጃ በሚጠበቀው ቅጥር ግቢ ውስጥ ዘወትር ዟት አዘዋወራለሁ። የወህኒ አዛዡ ሊጠይቀኝ መጣ። የሚደንቀው ማምለጤ ቢሳካ ኖሮ ከባድ እርምጃ የሚወሰደው በእርሱ ላይ ሆኖ ሳለ፣ በእኔ ላይ ቁጣ አለማሳየቱ ነበር።

ማንም ሰው መቃብር ካልገባ በስተቀር ለማምለጥ ቢሞክር በትክክል ተገቢ ነው ብላ ሚስቱ መናገሯን ሲገልጽልኝ ፈገግ እያለ ነበር። በከፍተኛ ብልጠት የካርቡኔሪን ግብረ አበርነት ሊያሳምነኝ ሞከረ። እንደ መሰለኝ እኔ አሳምኜዋለሁ። ርብራቡን ለማንሣት ፈልጌ እርዳኝ ስለውም ካርቡኔሪ እምቢ ማለት እንደማይችል ለማንም ግልጽ መሆኑን አስረዳሁት።

ቦርሴም የማስገደጃ ደብዳቤውንና የሥራሁትን ጀልባ ዲዛይን አጋለጠ። አዛዡ በነገሩ ሙሉ በሙሉ እምኖበት ነበር። የመንግሥትን ንብረት መስረቅ ምን ቅጣት እንደሚያስከትልብኝ ጠየቅኩት። «ከዐሥራ ስምንት ወራት አይበልጥም» አለ።

ሰለሆነም ቀስ በቀስ ከገባሁበት የሐሳብ አዘቅት በመጠኑ ለመላቀቅ በቃሁ። ቤቨርት ሲሊየር የማያውቀው የጉበት መቁሰል በሽታ ያዘው ተብሎ ሆስፒታል ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ልዩ ክፍል መግባቱን የምትነግረኝ አንዲት ማስታወሻ ከጤና ረዳቱ ቻታል መጣችልኝ። እርሱን ከብቀላ ለመጠበቅ ሲባል በዶከተሩና በአስተዳደሩ የተቀነባ ዘዴ ለመሆኑ እርግጠኛ ነበርኩ።

ፍጹም ሳልፈተሽ በከፍሌ ውስጥ ብቻየን ስለ ተተውኩ አንድ ጩቤ ለማግኘት በአጋጣሚ ተሳካልኝ። የወርክሾፑ ዘበኛ፣ ቤቨርት ሲሊየር፣ አናጢውና እኔ አንድ ስብሰባ እንድናደርግ ናሪክና ኬነር እንዲያመለክቱ ነገርኳቸው። ከስብሰባው በኋላ እሥራት፣ ቅጣት፣ ወይም ነፃ መውጣት የሚገባቸውን የወህኒ አዛዡ ይወስናል።

ጧት በመዘዋወር ላይ እንዳለሁ አዛዡ በስብሰባው መስማማቱን ናሪክ ነገረኝ። በሚቀጥለው ቀን አራት ሰዓት ላይ ሊደረግ ነበር። ከዘበኞቹ ታላፊ እንዱ እንደ መርማሪ ዳኛ ሊሆን ነው። ቤቨርት ሲሊየርን ላለመግደል ከራሴ ጋር ስሟገት ሌሊቱን አሳለፍሁት። ግን ያን ዝንባሌ ለማገድ አልቻልኩም። ለአስተዳደሩ በሰጠው አገልግሎት የእኔን ማምለጥ በማጨናገፉ፣ ሽልማት እንዲሆነው ወደ ግራንዳቴሬ የመዛወር ዕድል ይገጥመዋል። ከዚያም በቀላሉ ለማምለጥ እንዲችል መታቀዱ ለእንደርሱ ዓይነት ሰው የሚገባ አልነበረም። ምናልባትም የሞት ቅጣት ይፈርዱብኝ ይሆናል። ፍጹም ደንታ አልሰጠውም። የአራት ወራት ተስፋ፣ ደስታና ዝግጅት፣ ከዚያም ሊሳካ አፋፍ ላይ ሲደርስ በአንድ ግማታም አይጥ ምክንያት ሁሉም ነገር መኮላሸት! የፈለገው ይምጣ ሲሊየርን እገድለዋለሁ።

ከሞት ቅጣት ለመዳን ያለው ብቸኛ መንገድ በቅድሚያ እርሱ ጩቤውን እንዲመዝ ማድረግ ይሆናል። የእኔን ካወጣሁ በእርግጥ የእርሱም ይመዘዛል። በቀጥታ ከስብሰባው በኋላ ወይም ትንሽ ቀደም ብዬ እንደዚያ አደርጋለሁ። በስብሰባው ወቅት ግን የማይቻል ይሆናል። ምክንያቱም አንድ ዘበኛ ተኩሶ አደጋ ሊያደርስበኝ ይችላል። የዘበኞቹን ግድየለሽነት ማጤን ይኖርበኛል።

ከዚህ ሐሳብ ጋር ስታገል ሌሊቱን ሙሉ አጠፋሁ። ተሸንፈያለሁ። ያም ሆኖ ሊታለፉ የማይችሉ እንዳንድ ነገሮች ነበሩ። ማንም ሰው ቢሆን የራሱን ሕጎች ለማውጣት መብት እንደሌለው ዐውቃለሁ፣ ያ ግን በሌላ ማኅበረሰብ መደብ ውስጥ ላሉ ሰዎች ነው። እንደርሱ የመሰለ አንድ ወራዳ ምናምንቴ እንዴት ይቀጣ ብላችሁ አታስቡም? ይህን ቀራፎ አፍ ፍጹም አልበደልኩትም፣ አያውቀኝ። እርሱ ግን ላልተወሰነ ዓመታት በግዞት እንድማቅቅ ሊያስፈርድብኝ ነው። በቁሜ ቀብሮኛል። ስለሆነም አንደገና መኖር አለብኝ። አይሆንም፣ አይሆንም፣ አይሆንም! በዚህ ዕድል እንዲጠቀም አልፈቅድለትም። መሸነፌ ተሰማኝ። ዐይን ላጠፋ ዐይኑን አጥፉ ነውና፣ እርሱም እንደዚሁ እንዲያውም ከእኔ የበለጠ ሽንፈት ይሰማው። ግን የሞት ቅጣት ከፈረዱብኝ ምን ልሆን ነው? እርሱን ለመሰለ አንድ ዝቃጭ ሲባል መሞት በጣም የሚያበሽቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደደብነት ይሆናል። በመጨረሻ ራሴን አንድ ቃል ኪዳን ማስገባት ቻልኩ። ጩቤውን በቅድሚያ እንዲመገ ማድረግ ካልቻልኩ አልገድለውም።

በጠቅላላው ያን ሌሊት አልተኛሁም። አንድ ፓኮ ሙሉ የወየበ ትምባሆ አጨስኩ። ጧት ይዐሥራ ሁለት ሰዓት ቡና ሲመጣ የተረፉኝ ሁለት ሲጃራዎች ነበሩ። ምንም እንኳ ከልክል ቢሆንም ናላየ በጣም ስለዞረ ቡና አሳላፊውን፣ «ትንሽ ሲጃራዎች ወይም ጥቂት ትምባሆ ለተስጠኝ ትችላለህ? የኡኔን ስለጨረስኩ ነው ሙሴ አንታርታሊያ» አልኩ።

«ግድየለም፣ በእውነት ለአንተ አዝኛለሁ ፓርዮ። ኮርሲካዊ ነኝ። ሰዎችን እወዳለሁ። በአንተ ላይ የተነሐደው ዐይነት ከሃዲነት ግን ያስጠላኛል» አለ።

ለአራት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ላይ ወደ አዳራሹ አስከጠራ ድረስ እየተጠባበቅሁ በግቢው ውስጥ ቆየሁ። ናሪክ፣ ኪነር፣ ቦርሴና ካርቡኔሪም እዚያው ነበሩ። ጠባቂው ዘበኛችን የቡናው አሳላፊ አንታርታሊያ ነበር። ካርቡኔሪን በኮርሲካውያን ቋንቋ እያዋራው የሦስት ዓመት ግዞት የሚጠበቀው መሆኑን ሲነግረው በጨረፍታ ተሰማኝ። በዚያ ነጥብ ላይ እንሰለን፣ ግቢው ተከፈተና አንድ አረብ፣ የወርክሾፑ በር ጠባቂ ሌላው አረብና ቢቨርት ሲሊየር ወደ ውስጥ ገቡ። ሲሊየር ሲመለከተኝ ወደ ኋላ አፈገፈገ፣ መርማሪው ዘበኛ ግን፣ «ና እንጂ፣ እዚያ በቀኝ በኩል ቁም፤ አንተ አንታርታሊያ በጣም እንዳይጠጋጉ ተመልከት»። ከሁለት ያርድ በማይበልጥ ርቀት ላይ ነበርን።

«መነጋገር የለም» አለ አንታርታሊያ። ሁለቱንም በድኖች ከሚጠብቀው ኮርሲካዊ የሀገሩ ልጅ ጋር ካርቡኔሪ ግን ማውራቱን ቀጠለ። ዘበኛው የጫማውን ከር ለማሠር ጎንበሰ ሲል፣ ማቴዎስ ወደፊት ትንሽ ራመድ እንዲልልኝ አንድ ምልክት አሳየሁት። ገባውና ሲሊየርን ተመልከቶ ወደ እርሱ አቅጣጫ ምራቁን ጢቅ አለበት። ዘበኛው ቁና ሲል፣ ሰሜቱ በሙሉ ወደ እርሱ እንዲያዘነብል ካርቡኔሪ በወሬ ሲያጠምደው፣ እርሱ ልብ ሳያደርግ እኔ አንድ እርምጃ ወደፊት መጨመር ቻልኩ። ጩቤዬን አንሸራትቼ በእጄ ውስጥ አስገብቻለሁ። ሲሊየር ብቻ ሲያያት ችሏል። እርሱ ቀደም ሲል ጩቤውን አዘጋጅቶ ቢኪሱ ይዞ ስለነበር፣ ከጠቡቅኩት በላይ ፈጥኖ በላየ ላይ ተምዘገዘገና በቀኝ ከንዱ ጡንቻዬ ላይ ወጋኝ። ግን እኔ ግራኝ ስለነበርኩ፣ ጩቤዬን ልክ አሰከ እጀታው ድረስ በደረቱ ውስጥ ለመቸከል ተመቸኝ። «አ-አ-አህ!» የሚል ጩኸት አሰማና ተዝለፍልፎ ወደቀ።

አንታርታሊያ ሽጉጡን መዘዘ። «ተመለስ አንተ፣ ተመለስ። ከወደቀ እንዳትመታው፣ አዕበለዚያ እንዳልተኩስብህ» አለ።

ካርቡኔሪ ወደ ሲሊነር ቀረብ አለና ጭንቅላቱን በእግሩ ነቅነቅ አደረገው። በኮርሲካዊ ቋንቋ ሁለት ቃላት ተናገረ። «ሞታል» ማለቱ እንደሆነ ገባኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ጩቤህን ስጠኝ» አለ ዘበኛው። ሰጠሁት። ሽጉጡን ወደ ፎደሮው መለሰና ወደ መክኒያው ሔዶ ቆረቆረ። ዘበኛው ሲከፍትለት፣ «አንድ የሞተ ሰው መጥተው እንዲያነሡ ሊቃሬዛ ተሸካሚዎቹ ንገር» አለው።

«ማነው የሞተው?» ብሎ ዘበኛው ጠየቀ።

«ቢቨርት ሲሊየር።»

«አ! ያስብኩት ፓፒዮ ነው ብየ ነበር።»

ወደ ከፍሎቻችን ተመልሰን ገባን። ስብሰባው ተቋረጠ። ወደ አዳራሹ ውስጥ ከመገለቻችን በፊት ካርቡኔሪ «ምስኪኑ ፓፒ፤ አሁንስ አለቀልህ» አለኝ።

«አዎ፣ ግን እኔ በሕይወት አለሁ፤ እርሱ ደግሞ የለም» አልኩት። ዘበኛው ብቻውን ተመልሶ መጣና መዘጊያውን ከፍቶ ፍርጥም ባለ ድምፅ፣ «ቆስያለሁ ብለህ ንገራቸው። መጀመሪያ የወጋህ እርሱ ነው። አይቸዋለሁ» ብሎኝ ሔደ።

እነዚህ ኮርሲካውያን ዘበኞች የሚያስደንቁ ናቸው፤ ሁሉም ጥሩዎች ወይም ሁሉም መጥፎዎች አልነበሩም።

መዘጊያውን እየቆረቆርኩ እጮኽ ጀመር። «ቆስያለሁ! ወደ ሆስፒታል መሔድ እፈልጋለሁ!»

ዘበኛው ከሌላ የሥነ ሥርዓት አስጠባቂ ጋር አብሮ ተመለሰ።

«ምን ሆንኩ ነው የምትለው? ይህ ሁሉ ኡኡታ ለምንድነው?

«ጌታዬ፣ እኔም ቆስያለሁ።»

«ምን? አንተም ቆስለሃል? ነክቶሃል ብዬም አላሰብኩም።»

«ከቀኝ ከንዴ ላይ ጡንቻዎን አግኝቶኛል።»

«መዝጊያውን ክፈት።»

መዝጊያው ተከፈተና ወደ ውጭ ወጣሁ። የከንዴ ጡንቻ ከፉኛ ተቆርጦ ነበር።

«አጁን በካቴና አስራችሁ ወደ ሆስፒታል ውሰዱት። ግን በምንም መንገድ እዚያ እንዳትተዉት። እንደታከመ በደቂቃ ውስጥ መልሳችሁ እንድታመጡት።»

ወደ ውጭ ስወጣ ከዐሥር የሚበልጡ ዘበኞች አዛዡን ከብበው ቆመው ነበር። የወርክሾፑ ዘበኛ «አንተ ነፍሰ ገዳይ!» አለኝ።

እኔ ምንም ነገር ከማለቴ በፊት የዘበኞቹ ኃላፊ በእኔ ፋንታ፣ «ዝም በል ብሩየት፣ ፓዮን በቅድሚያ የሰነዘረበት እርሱ ነው» አለው።

«እኔም እንደዚሁ አይቻለሁ። ምስክር ነኝ» አለና እንታርታሊያ በማከታተል፣ «ይህንንም እዚሁ በሚገባ መረዳት ይኖርብሃል ሙሴ ብሩየት ኮርሲካውያን አይዋሹም» አለው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ወዲያውኑ ሆስፒታል እንደ ደረስኩ ቻታል ዶክተሩን ጠራና የውስጥም ሆነ የውጪ ማደንዘዣ ሳያደርግልኝ በሰምምነት ማያያዣዎች ሰፋልኝ። በሚያበቃበት ወቅት፣ «ማደንዘዣ ልሰጥህ አልቻልኩም። በሙሉ አልቆብኛል» አለና ከዚያ በማያያዝ፣ «ያደረግከው ነገር ጥሩ አልነበረም» አለ።

«መቼም በዚያ የጉበት ቁስል በሽታው ለረጅም ጊዜ መኖር እንደማይችል ታውቃለህ።»

«ጅምሮታል፣ በዚያኛው ግን ሞትን አልጠበቀም ነበር።» ምርመራው ቀጠለ። በሴራው ውስጥ የቦርሴ መካፈል ተሠረዘለት። በማስፈራራት መሆኑን ተስማምተውለት ነበር። የናሪክና የኬነርም ማስረጃ ስለጠፋ እንደዚሁ ተሠረዘላቸው። የቀረነው እኔና ካርቡኔሪ ነበርን። ለካርቡኔሪም ስርቆትና ንበረት ማባከን ወዘተ... የሚለውን ክስ አነሡለት። የያዙበት የማምለጥ ሙከራ ግበረ አበርነቱን ነበር። ይህም ከስድስት ወር የበለጠ እያስፈርድበትም። እኔን በተመለከተ ግን ነገሮች ተወሳሰበዋል። ምስክርነቱ ለእኔ ያደላ ቢሆንም መርማሪው ሕጋዊ የመከላከያ ቃሌን አልቀበልም አለ። ዴጋ ዶሴየን አገላበጠና ምንም እንኳ መርማሪው ቢጨክንም ሰሞት ቅጣት እንደማልበቃ ነገረኝ። ችሎቱ ሊያገኘኝ የሚችለው ጠቤየን ለመምዘዝ እኔ ቀዳሚ መሆኔን ሁለቱ ዓረቦች ቢመሰክሩብኝ ነበር።

ምርመራው ተፈጸመ። ጦር ፍርድ ቤት ለመቅረብ ወደ ቅዱስ ላውረን እስከላከ ድረስ አዚያው ቆየሁ። ከወርከሾፑ ዘበኛና ከመርማሪው በስተቀር፣ የወህኒ አዛዡም ሆነ ዘበኞቹ በማንኛውም ጊዜ የሚያሳዩኝ የጥላቻ ሰሜት አልነበረም። በተጨማሪ የቻልኩትን ያህል ሲጃራ አንዳገኘ ተፈቀደልኝ። ዓርብ ልሐድ ነበር።

ረቡዕ ጧት በአራት ሰዓት በግቢው ውስጥ ሁለት ሰዓት ያህል እንደቆየሁ፣ የወህኒ አዛዡ ጠርቶ «ከእኔ ጋር ና» አለኝ። ወደ ቤቱ የምትወስደውን የአግር መንገድ ይዘን በመጓዝ ላይ እያለን እንደዚህ አለ። «ከመሐድህ በፊት ባለቤቱ ልታይህ ትፈልጋለች። መሣሪያ በታጠቀ ዘበኛ አንተን አሳጅቤ በማምጣት ላሸብራት አልፈለግኩም። ራስህን እንደምትቆጣጠር ተስፋ አደርጋለሁ።»

ወደ ቤቱ ደረስን። «ገቦልየት፣ ቃል አንደ ገባሁልሽ የአደራ ወዳጅሽን አምጥቻለሁ። አሰታውሺ፣ ከቀትር በፊት መልሺ አወስደዋለሁ። ያለሽ አንድ ሰዓት ቢሆን ነው» አላትና ተመልሶ መንገዱን ቀጠለ።

ገቦልየት ወደ እኔ ቀረብ ብላ አጂን ትከሻየ ላይ በማድረግ ትኩር ብላ ትመለከተኝ ጀመር። ጥቁቁር ዐይኖቿ አንባ አመነጩ ደግሉ ግን ፈገግ አላለቀሰችም።

«ወዳጂ፣ በእውነቱ አብድ ነህ። ለመሐድ አፈልጋለሁ ብለህ ብትነግረኝ ኖሮ ልረዳህ በቻልኩ ነበር ባለቤቴ ለአንተ የተቻለውን ማንኛውንም ነገር እንዲያደርግልህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠይቂው ያለኝ፣ «አርሱ መሄድ አይፈልግም» ነበር። እንድትመጣ የፈለግኩት እንዴት እንደ ሆንክ ማየት እንድችል ነው። ከገመትኩት በተሻለ አቋም ላይ ትገኛለህ። ከዚህም በቀር ለሰጠኸኝ ዓላዎች በሙሉ ልከፍልህ ማሰቤን ልነግርህ አፈልጋለሁ። አንድ ሺ ፍራንክ ያውልህ። ያለኝ ይኸው ብቻ ነው። ከዚህ የበለጠ ባለማድረጌ አዝናለሁ» አለች።

«ማዳም፣ ገንዘቡን አልፈልገውም። ልቀበል አልችልም። ወዳጅነታችንን ያበላሸዋል» አልኩና የሁለቱን ባለአምስት መቶ ፍራንክ ኖቶች ወደ ጎን አየገፋሁ፣ «አባከሽ አታስገድጅኝ» አልኳት።

«አሺ እንዳልክ፣ አትቀመጥምና ትንሽ ፓስቲስ አትወስድም?» አለች። ያኽ የምትደነቅ ሴት፣ ከአንድ ሰዓት በላይ ማራኪ በሆነ አቀራረብ አውራችኝ። የሚፈረድብኝ እጅግ ቢበዛ ከዐሥራ ስምንት ወር እስከ ሁለት ዓመት እንደሚሆን እርግጠኛ ነበረች።

ለመሐድ ስነሣ እጇን ሰረጅም ጊዜ ጭበጥ አደረገችና «ደህና ሁን። መልካም ዕድል» ብላ በእንባ ታጠበች። አዛገሁ ወደ መታሠሪያ ክፍሌ ግቢ ወሰደኝ።

በመንገድ ላይ እንዳለን፣ «ጌታዬ፤ ባለቤትህ ጨዋ ሴት ናት» አልኩት።

«ዐውቃለሁ ፓፒዮ። ቦታዋ እዚህ አልነበረም። ለእርሷ በጣም አስቸጋሪ ነው። ግን ምን ማድረግ እችላለሁ። ገና አራት ዓመት ይቀረናል» አለ።

«ጌታዬ፣ አሁን ብቻችንን ነን፤ ማምለጫ ቢሳካልኝ ኖሮ ላስከትልብህ የነበረውን ችግር ሁሉ ችላ ብለህ በመልካም ሁኔታ ስለተንከባከብከኝ ላመሰግንህ አፈልጋለሁ።»

«አዎ ፓፒዮ፣ በእርግጥም እንዳልከው ችግር ማስከተሉ አይቀርም ነበረ፣ ያም ሆኖ አንድ ነገር ልገልጽልህ፤ መጫራህ ሊሳካልህ በተገባ ነበር» አለ። በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠበቀው ከፍል በር ላይ ስንደርስ በተጨማሪ፣ «ደህና ሁን ፓፒዮ። እግዚአብሔር ይርዳህ። የሚያስፈልግህም ይኸው ነው» አለ።

«ደህና ሁን ጌታየ!»

በእርግጥም የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልገኝ ነበር! የጦር ፍርድ ቤቱን በበላይ ሰብሳቢነት የሚመራው አራት የማዕረግ ጥብጣቦች ያሉት አንድ አይበገሬ የፖሊስ ኮሚሽነር ነበር። ለስርቆት፣ የመንግሥትን ንብረት ለማባከን፣ መቃብር ለመድፈርና ለማምለጥ ሙከራ ሦስት ዓመት። በተጨማሪ ለሴሊየር ግድያ በተከታታይ የሚፈጸም አምስት ዓመት፣ በጠቅላላው ስምንት ዓመት በግዞት እንድቆይ ተፈረደብኝ። ባልቆሰል ኖሮ ያለ ጥርጥር የሞት ቅጣት ፍርድ ይበይንብኝ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ግዞት

ጳንጦስኪ ከተባለ አንድ ፖላንዳዊ ጋር በእጅ ካቴና ተቆራኝቼ ወደ ደሴቶቹ ተመለስኩ። እርሱ ለሁለት ጊዜ በቂም በቀል ግድያ አምስት ዓመት ሲፈረድበት፣ እኔ ስምንት ዓመት ተከናንቢያለሁ።

በጀልባዋ ላይ የተሳፈርነው ዐሥራ ስድስት ሰዎች ስንሆን፣ ዐሥራ ሁለታችን ግዞት የተፈረደብን ነበርን። ባሕሩ የጀልባውን ወለል በከባድ ማዕበል ይጠርገዋል። ተስፋ ከመቁረጤ የተነሣ፣ ምነው ጀልባው በሰመጠ እስከ ማለት ተመኘሁ። የዕድሌ ጉዳይ ስላስተከዘኝ ከማንም ጋር አልነጋገርም። ቀዝቃዛው ውሃ እየተረጨ ፊቴን ያርሰዋል። ነፋሱም ኮፍያዬን ወስዷታል። ምን ትሠራልኛለች! ለስምንት ዓመት ግዞት እስከዚህም አልፈልጋት። ይኼኔ በቭርት ሴሊየር በዓሣ ነባሪዎች ተበልቷል፤ እኔ ሠላሳ ዓመቴ ነው፤ «በሰው በላ» ግንቦች ውስጥ ስምንት ዓመታት መኖር እችላለሁ?

ካለፈው ልምዴ አንጻር ማለት ያለብኝ አይቻልም ነው። በዚያ የግዞት ሥፍራ የሰው ልጅ የመሣቂያም ደረጃው አራት ወይም አምስት ዓመት ቢሆን ነው። ሴሊየርን ባልገደል ኖሮ የሚፈረድብኝ ሦስት ዓመት ብቻ በሆነ ነበር። ግን ያ ግድያ ማንኛውንም ነገር አዘበራረቀው። ያን የሰው ዝቃጭ መግደል አይገባኝም ነበር። የእኔ ተግባር ብቀላን ላይሆን ለመኖር መጣር፣ መኖር ለማምለጥ መሆን ነበረበት። ምን ዐይነት ንክ ሆኜ ኖሯል? ቢሆንም እኮ ያ ብስብስ ምናምንቴ ሊገድለኝ ተቃርቦ ነበር። መኖር፣ መኖር፣ መኖር መሆን የነበረበት፣ መሆንም ያለበት ይኸው ነውና፣ ከእንግዲህ ወዲያ ብቸኛው እምነቴ ይኸው ይሆናል።

ኮንቮዩን ከሚያጅቡት ዘበኞች መካከል አንድ የማስታውሰው ሰው ነበር። ስሙን ማስታወስ አልችልም፣ ግን አንድ ጥያቄ ላቀርብለት በጣም ቸኩዬ ነበር።

«ጌታዬ አንድ ነገር ልጠይቅህ ፈልጌ ነበር።»

ደንገጥ አለና ወደ አጠገቤ መጥቶ «ምን ነበር?» አለ

«ከእኛ መሀል ስምንት ዓመት ያሳለፈ ከቶ የምታውቀው አለ?»

ለአንድ አፍታ አሰበና፣ «የለም፣ ግን አምስት ዓመት የቆዩ ብዙዎች ዐውቃለሁ፣ ጥሩ አድርጌ የማስታውሰው ከተሟላ ጤንነትና ከተስተካከለ አእምሮ ጋር ከስድስት ዓመት በኋላ የወጣ ሌላም አንድ ሰው ነበር። ነፃ ሲለቀቅ እኔ ወህኒ ቤት ነበርኩ» አለ።

«አመሰግናለሁ።»

«ምንም አይደለ፣ ሰምንት ዓመት እንደተፈረደብህ ሰማሁ።»

«አዎ፣ ጌታዬ!»

«ሌላ ቅጣት ካልተጨመረብህ ትጨርሰዋለህ።»

እነዚህ ከጥቂት ቁም ነገር ያዘሉ ቃላት ነበሩ። ተጨማሪ ቅጣት ካላገኘኝ ብቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሕይወት እወጣለሁ። ተጨማሪ ቅጣት ማለት በከፊል ወይም ሙሉ ምግብ ለተወሰነ ጊዜ ማጣት ነበር። ከዚያ በኋላ የተለመደውን ምግብ እንደገና ብታገኝ እንኳ ፍጹም ለማስተካከል አይሆንልህም። ያው መሞት ማለት ነበር።

ባጭሩ፣ ኮከነት ሆነ ሲኾራ አልቀበልም፣ ማስታወሻ እንኳ መጻፍ ወይም መቀበል አይኖርብኝም።

ቀሪውን ጉዞ ይህንኑ እየደጋገምኩ ሳሰላስል ቆየሁ። ከውጭውም ሆነ ከውስጡ ዓለም ጋር በጠቅላላው ምንም ነገር፣ አንድም ዓይነት ግንኙነት አይኖረኝም። ከዚያም አንድ ሐሳብ መጣልኝ። አደጋ ሳያስከትልብኝ የተሻለ ምግብ ለማግኘት ያለው ብቸኛ ዘዴ፣ አንድ ሰው ከውጭ በኩል ለሾርባ አዳዩ ገንዘብ የሚከፍልልኝ ፈልጌ፣ ቀትር ሲሆን ትልቁንና ምርጥ የሆነውን ሥጋ እንዲሰጠኝ ማስደረግ ነበር። ይህም ቀላል ነበር፣ ምክንያቱም ሾርባውን የሚጨልፈው አንድ ሰው ሲሆን፣ በአንድ ሣህን ደግሞ ሥጋ ተሸክሞ ቁራጩን እየመረጠ ወደ ሾርባው ሣህን የሚያስገባ ሌላ ሰው ነበር። የብረት ድስቱን ሥር እያሟጠጠ የቻለውን ያህል ብዙ አትክልት የሚሰጠኝ የመጀመሪያውን ሰው ማግኘት ነበረብኝ። ይህ አስተሳሰብ ራሱ እፎይታ ሰጠኝ። ይህን ለማመቻቸት ከቻልኩ ረኃቡን ለማስታገሥ አችላለሁ። ከዕብደት ለመዳን ማድረግ የሚኖርብኝ የቻልኩትን ያህል በሐሳቤ ርቂ እየበረርኩና በጣም ደስ የሚያሰኙ ትዝታዎችን እየመረጥኩ ማሰላሰል ነበር።

ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ደሴቶቹ ደረስን። ከጀልባው ሳልወርድ ነበር የደበዘዘ ቢጫ ቀሚስ እንደለበሰች ገፍልየትን ከባሏ ጎን ሆና ያየኋት። መሰለፍ እንኳ ገና አልጀመርንም ነበር። የወህኒ አዛዡ ወደ እኔ መጥቶ፣

«ምን ያህል?» ሲለኝ።

«ሰምንት» አልኩት።

ወደ ሚስቱ ተመለሰና ነገራት። ስሜቷን መቆጣጠር አቅቷት በአንድ ሹኝ ላይ ተቀመጠች። ባሏ ከንዲን ያዛት። ብድግ ብላ ቆመችና በትላልቅ ዐይኖቿ በትካዜ እየተመለከተችኝ መንገዷን ቀጠለች።

«ፓፒየ» አለ ዴጋ፣ «ምን ያህል?»

«የሰምንት ዓመት ግዞት።» ፀጥ አለ፣ ሊመለከተኝ እንኳ አቃተው። ጋልጋኒ ወደ እኔ ሲመጣ፣ ከመናገሩ በፊት፣ «አንድም ነገር እንዳትልከልኝ። መልዕክትም እንዳትጽፍልኝ። ከዚህ ረኾም ቅጣት ጋር ምንም አደጋ መቋቋም አልችልም» አልኩት።

«ይገባኛል» አለ።

«ምናልባት ከዕለታት አንድ ቀን እንደገና እንተያይ ይሆናል። ደህና ሁኑ» አልኩኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ቅዱስ ዮሴፍ መልሶ ወደሚወስደን ጀልባ አመራሁ። ሁሉም ሰው የሚመለከተኝ ወደመቃብር ጉድጓድ እንደሚወርድ አንድ የሬሣ ሣጥን ዐይነት ነበር። ማንም አይናገርም።

በአጭሩ ጉዞ ወቅት ሊጋልጋኒ ነግሬው የነበረውን ሰቻፓርም ደገምኩለት። «ቦርታ ፓፒ» ሲል መለሰልኝ። ከዚያም፣ «ካርቡኔሪስ እንዴት ሆነ?» አለና ጠየቀኝ።

«አዝናለሁ፣ ሳልነግርህ ረስቸው ነበር። ሰብሳቢው ዳኛ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ስለ እርሱ ከስ ተጨማሪ መረጃ ጠይቋል። ጥሩ ነው፣ ወይስ መጥፎ?» አልኩት።

«እንደሚመስለኝ ጥሩ ነው» አለ።

ወደ ወህኒ ቤት በዳገቱ ሽቅብ ከሚወጡት የዐሥራ ሁለት ሰዎች ሰልፈኛ ውስጥ እኔ በመጀመሪያው ረድፍ ነበርኩ። በችኮላ አራመዳለሁ። ሁኔታው እንግዳ ነገር ነበር። ይሁንና ግን የቸኮልኩት ቶሎ ወደ ከፍሌ ገብቼ ብቻዬን ለመሆን ነበር። በጣም ከመጣደፌ የተነሣ ዘበኛው፣ «ረጋ በል እንጂ ፓፒዮ። ወደ ቤትህ ለመድረስ የቸኮልክ ትመስለለህሳ» አለ። ብዙም ሳንቆይ ደረሰን።

ዘበኛው፣ «ሁላችሁም ልብሳችሁን አውልቁ። የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ አሁን ንግግር ሊያደርጉላችሁ ነው» አለ።

የተለመደ ዲሲኩሩን አደረገ - «ግዞተኞች፣ እዚህ እኛ - ወዘተ» አለና ከዚያም ወደ እኔ ዘወር ብሎ፣ «ፓፒዮ፣ እንደገና ተመልሰህ መምጣትህን በማየቴ አዝናለሁ። በሕንፃ ሀ - አንድ መቶ ሐያ ሰባት ክፍል ውስጥ ትገባለህ። በጣም ጥሩም ናት ፓፒዮ። ከአዳራሹ ትይዩ ስለሆንክ የተሻለ ብርሃንና ዘወትር ንጹሕ አየር ታገኛለህ። መልካም ጠባይ ለማሳየት እንደምትሞክር ተስፋ አደርጋለሁ። ስምንት ዓመት አንድ ረጅም ጉዞ ነው፣ ግን ማን ያውቃል? ጠባይህ ጥሩ ከሆነ የአንድ ወይም የሁለት ዓመት አመክሮ ታገኝ ይሆናል። እንደዚያው እንዲሆንልህ አመኛለሁ፣ ነበዝ ሰው ነህ» አለ።

በቁጥር 127 ውስጥ ገባሁ። ወደ መተላለፊያው የሚከፈት ቋሚ ፍርግርጎች ካሉት አንድ መዝጊያ ትይዩ ነበርኩ። ዐሥራ ሁለት ሰዓት ቢሆንም፣ በሚገባ ወለል ያለ ብርሃን ነበረው። እንደ መጀመሪያው ይህ ከፍል ሽታ አልነበረውም። ሁኔታው የሚያበረታታ ነበር። አንተ ሰው እነዚህ አራት ግድግዳዎች ለሚቀጥሉት ስምንት ዓመታት ሊያፈጡብህ ነው» አልኩት ራሴን። «እያንዳንዱን ወርና ሰዓት አትቁጠር፣ ጊዜ ማባከን ይሆናል። ቆይታህን በስድስት ወር ገደብ ለማለላት ሞክር። ዐሥራ ስድስት ሲባዛ በስድስት ወር ከዚያም ነፃ ትሆናለህ ማለት ነው። ይሁንና አንድ ጥቅም አለህ። እዚህ ብታሽልብ በብርሃን ውስጥ መሞትህ ራሱ አንድ ነገር ነው። ብትታመም ሌላው ቢቀር ዶክተሩ ፊትህን ማየት ይችላል። ለማምለጥ ሞክሬ አልተሳካልኝም ብለህ ራስህን እንዳትወቅስ፣ ሲሊየርንም በመግደልህ ጸጸት እንዳይሰማህ። አንተ ቀርተህ እርሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

አምልጦ ቢሔድ ኖሮ የቱን ያህል እንደምትበሽቅ አስኪ አስብ። ማን ያውቃል፣ ምናልባት ምሕረት ይመጣ ይሆናል። ጦርነት፣ መሬት መንቀጥቀጥ፣ ምናልባት አውሎ ነፋስ ይህን ቦታ ያወድመው ይሆናል። ለምን አይሆንም? ምናልባት ይህን የሰዎችን እንጉት ጭፍጨፋ ቅጣት አስተዳደሩ እንዲያቆም የፈረንሣይ ሐዝብ ሊያሳምን፣ ሊያሥሣ የሚችል አንድ ሰው ይወጣና እንተም ወደ ሀገርህ ነመመለስ ዕድል ይገጥምህ ይሆናል። ምናልባት ይህ ሁኔታ የዘገነነው አንድ ዶክተር ለአንድ ጋዜጠኛ ወይም ለአንድ ቂስ ግፍና ጭቆናውን ያሾልከ ይሆናል። ማን ያውቃል ለማንኛውም ጉዳይ ሲሊየር በዓሣ ነባሪዎች ተበልቷል፤ አንተ ግን አዚሁ እንደ ከራህ ትነኛለህ፤ ከዚህ መቃብር ጉድጓድም በሕይወት ትወጣለህ።›

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምሥት፣ ... አንድ ሁለት ሶስት አራት አምስት እንደገና አሥራለሁ። የራሴ አቅጣጫ፣ የክንዶቼ አወራወር የአያንዳንዱ አርምጃዬ ርዝመት መመጣጠን ልከ እንደ ግድግዳው ሰዓት ወገዋዚ መዛባት የለበትም። በተጨማሪም ምግብ መቀማመኔን ለማወቅ እስከምችል ድረስ ጧት ሉሁለት ሰዓት፣ ከሰዓት በኋላ ለሁለት ሰዓት ብቻ ለመራመድ ወሰንኩ። ኃይሌን ማባከን የለብኝም።

እም፣ ምንም እንኳ የአሁኑ የማምለጥ ሙከራዬ በአንዲት ተልካሻ ጀልባ ቢሆንም ወደፊት ዘጠና ማይል ቢጠበቀኝም፣ መጨረሻ ላይ መከሸፉ ልብ የሚሰብር ነበር። ግራንዴቱሬ ከደረስኩ ወዲያ አንደገና ሌላ የማምለጥ ዕቅድ ማውጣት ያስፈልግ ነበር። ጀልባዋን ማንቀሳቀስ ችየ ቢሆን ኖሮ፣ እንደ ነፉስ ሽራ የሚያገለግሉት ሦስቱ የዱቄት ከረጢቶች፣ ቢያንስ በሰዓት በስድስት ማይል ፍጥነት ወስደውኝ ምናልባትም በዐሥራ ሁለት ሰዓት ውስጥ የብስ ላይ በደረስኩ ነበር። የነፋስ ሽራውን የምሰቅለው በዝናም ወቅት ብቻ በመሆኑ ያው ያን ዕለትም ይዘንማል የሚል ግምት ነበረኝ። ወደ ጨለማ ግንብ ከገባሁ በኋላ የዘነመ መሰለኝ። ግን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ አልነበርኩም። ምን ስሕተቶች ሠርቼ እንደ ነበር ለማስታወስ ሞከርኩ። ሁለቱ ብቻ በሐሳቤ መጡልኝ፣ በመጀመሪያ ጀልባዋ ከሚገባት በላይ ተጠናክራ ተሠርታለች። ተደራርባ ሁለት ጀልባ መሆን ትችል ነበር። ሥራው ብዙ ቁርጥራጮች በማገናኘት ከመጠን በላይ ጊዜ ወስዷል።

ሁለተኛው ስሕተት ደግሞ ይበልጥ ከበድ ያለነበር፣ ሴሊየርን መጠርጠር በጀመርንበት በዚያኑ ዕለት ሌሊቱን መግደል ይገባኝ ነበር። ምን እንደሚሆን ቀደም ብዬ አስቤ ቢሆን ነበራ ግራንዴቱሬ ላይ ጀልባችን ብትሰባበር፣ ወይም ጀልባዋን በውሃ ላይ ሳሳርፍ ብታሰር ኖሮ በስምንት ፋንታ ሥስት ዓመት ብቻ በተፈረደብኝ ነበር፣ ሌላው ቢቀር ለማምለጥ መቃረቤ ራሱም ደስታ ነበር። በደሴቶቹና በግራንዴቱሬ ማንኛውም ነገር ቢሰተካከል ኖሮ ይሽኔ የት እሆን ነበር? ማን ያውቃል? ምናልባት ትሪኒዳድ ከቦውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋር መቀላለድ፣ ወይም ከአሬኒ ደብሩዮን ጋር ኩራሶ በሆንኩ ነበር። ከዚያም የምሄዳቸው ሊቀበልኝ ፈቃደኛ የሚሆነው የትኛው ሀገር እንደሚሆን በትክክል ሳውቅ ብቻ ነበር። ይህ የማይሠራ ከሆነ ደግሞ በቀላሉ እንዲት አስተኛ ጀልባ ይገዛ ከጓጅራ ነጣዎች ጋር እንደገና መቀላቀል በቻልኩ ነበር።

ወደ መኝታዬ በጣም ዘግይቼ ሔድኩ። እንቅልፌ አስከዚህም የሚጫጫን አልነበረም። መኖር፣ መኖር፣ መኖር። በየጊዜው የተስፋ መቁረጥ ፈተና ሲመጣብኝ እደጋግመዋለሁ። ሕይወት አስካለ ድረስ ምንጊዜም ተስፋ አለ።»

አንድ ሳምንት አለፈ። በምግቢ ላይ አንድ ለውጥ ማየት ጀመርኩ። በቀትር በጣም ምርጥ የሆነ የተቀቀለ መዳ ሥጋ፣ ግታ ደግሞ ውሃ አለበት ለማለት የማያስደፍር አንድ ዛሆን ሙሉ ምሥር ነበር። ልክ እንደ ሕፃን ልጅ «ምሥር በንጥረ ነገሮች የበለጸገ ነው። ምሥር በጣም ጥሩ ነው» እያልኩ አነበንባለሁ።

በዚሁ ከቀጠለ በቀን ከዐሥር እስከ ዐሥራ ሁለት ሰዓቶች መረመድ እችላለሁ፣ ግታ ግታ ወደ ፈለግኩበት ቦታ በሐሳቤ እንዳልበር ይደከመኛል ማለት ነው። ከአካባቢዬ ርቄ መሔድ አልቻልኩም። በደሴቶቹ ውስጥ ስለሚገኙት አሥረኞች ተራ በተራ እያሰብኩ ከመኝታዬ ላይ ተንልቻለሁ። በአካባቢው ስለሚናፈሱት ወሬዎች በምወጣበት ጊዜ አጣራለሁ ብየ አሰብኩ።

ቀደም ብዬ እንደ ገለጽኩት፣ አሥረኞች አይቀበሩም። በቅዱስ ዮሴፍና ሮያሉ መካከል ዓሣ ነባሪዎች በሚፍለከለኩበት አካባቢ ወደ ባሕር ይወረወራሉ። አስከሬኑ በዱቄት ከረጢት ይጠቀለልና እግሮቹ ላይ አንድ ቋጥኝ በጠንካራ ገመድ ይቆራኝበታል። ዘወትር የማይለወጥ ረኽምና ጠበብ የሆነ አንድ ሣጥን ከጀልባው ፊትለፊት ይቀመጣል። ጀልባው ወደተባለው አካባቢ ሲደርስ ስድስት ቀዛፊዎች መቅዘፊያዎቻቸውን ቀጥ ያደርጉና አንድ ሰው ሣጥኑን ወደዳር ያቀርባል፣ ሌላው ግጣሙን ከፍቶ አስከሬኑን ወደ ውሃው ውስጥ ያንሸራትታል። ዓሣነባሪዎቹ ወዲያው ገመዱን ይገዘግዛሉ። አስከሬኑ ለመስመጥ ጊዜ አይኖረውም። ከውሃው በላይ እንደተንሳፈፈ ምርጥ በሆነው የሥጋ ብልት ዓሣ ነባሪዎቹ መሻማት ይጀምራሉ። እንደሚሉት አንድ ሰው በዓሣ ነባሪዎች ሲበላ ወመመልከት እስከ መጨረሻው የማይረሳ አሰቃቂ ትዝታ ትቶ ያልፋል። በተለይ ዓሣነባሪዎቹ ብዛት ካሳቸው አንዳንድ ጊዜ ከነኮረኑ ከውሃው በላይ ይሸከሙና አንዱ በቀጥታ ከረጢቱን ዘነጣጥሎ ወዲያ በመጣል ከሬሳው ከፍል ትልቁን ብልት ገንጥሎ ይወስዳል።

ይህ መሆኑን ዐውቃለሁ። ግን ለማጣራት ያልቻልኩት አንድ ነገር ነበር። ዓሣ ነባሪዎቹን እዚህ የተወሰነ ቦታ ሰብስበ የሚያመጣቸው፣ አንድ አሥረኛ ሲሞት በጸሎት ቤቱ የሚደወለው ደወል መሆኑን አሥረኞቹ በሙሉ ያምናሉ። በሮያሉ ወደብ ከምሽቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ዐሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ብትቆም፣ አንዳንድ ጊዜ ጨርሶ ዓሣነባሪዎች አይገኙም። ግን የጸሎት ቤቱ ደወል በሚደወልበት ወቅት በአንድ አፍታ ቦታው በአነርሱ ይጨናነቃል። በዚያ ሰዓት ወደዚያ የተለየ ቦታ የሚሯሯጡበት ሌላ ምክንያት አልነበራቸውም፤ በምንም መንገድ የዓሣነባሪዎች «ልዩ ፍሪዳ» እንዳልሆን በእግዚአብሔር ተስፋ እደርጋለሁ። በማምለጥ ላይ እንዳለሁ ከበሉኝ አሰየው፣ ሌላው ቢተር በነፃነት ጎዳና ላይ ነበርኳ። ግን በከፍሌ ውስጥ በአንድ በሽታ እሞት እንዳይሆን። ይህ እንዲሆን አልፈልግም።

ለጓደኞቼ ምስጋና ይግባቸውና በሚገባ እየበላሁ፣ በተሟላ ጤንነት ላይ እገኛለሁ። ከጧቱ አንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ያለማቋረጥ አረመዳለሁ። ከዚያም የምሽቱ የምሥር፣ የአተር ክክ፣ የሩዝ ወይም የሆነው ዐይነት ሣህን ሙሉ ሾርባ ይመጣል። ደሰ አያለኝ ጥርግ አድርጌ እበላለዐ። ያ ሁሉ እርምጃም ጥሩ አስተዋጽኦ ስለነበረው፣ የጤንነት ድካም ያመጣልኝና በመራመድ ላይ እንዳለሁ እንኳ ወደ አለፈው ትዝታዬ መብረር የምችልበት ደረጃ ላይ እደርሳለሁ። ለምሳሌ እንድ ጊዜ በእርዴክ ውስጥ በምትገኝ ሩቨራስ ተብላ በምትጠራ አንዲት ትንሽ መንደር መስክ ላይ ሙሉ ቀን አሳልፌያለሁ። እናቴ ከሞተች በኋላ ዘወትር ወደዚያ በመሔድ የመንደሯ መምህርት ከሆነችው አክስቴ ማለት የእናቴ እህት ጋር ጥቂት ሳምንታት አሳልፍ ነበር። በጫካ ውስጥ እየተዘዋርኩም እንጉዳይ አለቅም ነበር። በግ አረኛው ጓደኛዬ እንዲት የባዘኑች በግ አንዲመልስለት ጠባቂ ውሻውን ሲያዛት ይሰማኛል። ቅዝቅዝ ብሎ በመጠኑ የብረት ጣዕም ያለውን የምንጭ ውሃ ስቀምሰው ትናንሾቹ ፍንጣቂዎች አፍንጫየን ሲረጩኝ ይታወሰኛል። ከዐሥራ አምስት ዓመት በፊት የተፈጸሙ እንደዚህ ዓይነት ገጠመኞችንና ድርጊቶችን ጥርት ባለ ሁኔታ ማስታወስ የሚቻለው፣ ፍጹም ረጭ ባለ ፀጥታ በአንድ ከፍል ውስጥ መሆን ስትችል ብቻ ነው።

የአክስቴ አውቲንስን ቢጫ ቀሚስ እንኳ ማየት እችላለሁ። በዛፎቹ ውስጥ የሚነፍሰውን ነፋስ፣ ፍሬያቸው በመሬት ላይ ሲወድቅ የሚያሰማውን ደረቅ ድምፅ ወይም በተከመሩ ቅጠሎች ላይ ሲያርፍ የሚያሰማውን ለስላሳ ኮሽታ መስማት እችላለሁ። በረጅም ጓሣ ከተሸፈነ አንድ ሜዳ ውስጥ አንድ ግዙፍ የዱር ዓሣማ ብቅ ሲልብኝ፣ ከፍርሃቱ የተነሣ ሰቅጫያቸው የነበሩትን እንጉዳዮች እያንጠባጠብኩ እግሬ አውጭኝ ሰል ...። አዎ፣ ከአክስቱና ከወጣቷ ጓደኛዬ ገቦልየን ጋር ሙሉውን ቀን በሩቨራስ አሳለፍኩት። በእነዚህ ትዝታዎች ውስጥ ከመንፈላሰስና ለቀሰለችው ነፍሴ መጽናኛ የሆነውን ሰላም ከመሻት ማንም የሚያግደኝ ኃይል አልነበረም።

በአካል ያለሁት ከ«ሰው በላ» ክፍሎች በአንዷ ውስጥ ነበር። ግን በሩቨራስ መስክና ዛፎች መካከል በመንፈሴ በርሬ አንድ ሙሉ ቀን አሳልፌያለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ስድስት ወር አለፈ። በስድስት ወር እየከፋፈልኩ ብቻ ላሰላ ራሴን ቃል ለገባቸው ነበር። ቃሌን አክበርኩ። ዛሬ ጧት ቁጥሩን ከዐሥራ ስድስት ወደ ዐሥራ አምስት ዝቅ አደረግኩ። አሁን የሚቀረኝ ዐሥራ አምስት ጊዜ ስድስት ወሮች ብቻ ነበሩ።

ሐተታዬን ለማሳጠር ያህል፣ በእነዚህ ስድስት ወሮች ውስጥ ምንም የጎላ ድርጊት አልተፈጸመም ነበር። ዘወትር የሚሰጠኝ ተመሳሳይ ምግብ ነው። ይሁንና ጤንነቴን ለመጠበቅ የተሟላ ነበር። ሕይወትን በገዘ እጅ ማጥፋት የተለመደ ነበር። ብዙም ዕቢዶች በዙሪያዬ ነበሩ፣ ደግነቱ እምብዛም ውለው አያድሩም። ጩኸታቸውን፣ ማላዘናቸውንና መነጫነጫቸውን ሳያቋርጡ ቀኑን ሙሉ መስማቱ አሰልቺ ነበር። እንድ ጥሩ መላ ባገኝም ለጤናዬ ግን ጎጂ ነበር። ሁለት ትናንሽ የሣሙና ቁራጮች ጨፈለቅኩና በጆሮዎቼ ውስጥ መረግኳቸው። ከጩኸት ቢገላግሉኝም ከሁለት ቀን በኋላ ጆሮዎቼ መምገል ጀመሩ።

ከመጣሁ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ ነገር እንዲደረግልኝ ጠየቅኩ። ሾርባ ከሚጨልፉት ዘበኞች አንዱ፣ እኔ ከመጣሁበት በጣም ከምትቃረብ ምንቴልማር ከመምጣቱም ሌላ በሮያሌም ፀውቀው ነበር። የአብዶቹን ጫጫታ የማፍንበት ፍሬ የሚያካክሉ ሁለት ድቡልቡል ሰሞች ሊያመጣልኝ ይችል እንደሆነ ጠየቅኩት። በሚቀጥለው ቀን አመጣልኝ። የነዚያን ምስኪን ዕብዶች ጩኸት ዳግመኛ አለመስማቴ ታላቅ ግልግል ነበር።

ከሙቶ አግር ትሎች ጋር መልካም የሆነ የተግባር ወዳጅነት መሠረትኩ። በስድስት ወር ውስጥ የተነደፍኩት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። ሰባንን አንደኛውን በሰውነቴ ላይ ሲርመሰመስ ባገኘውም ዝም ብዬ አጠብቃለሁ። ራስን የመቆጣጠር ጉዳይ እንጂ ከማንኛውም ነገር ጋር መለማመድ ትችላለህ። ግን የትሎቹ እግሮችና ጭራዎች ኮስኮስ በጣም ቀፋፊ ነበር። የሚሻለው ራሳቸው ለቅቀውህ እንዲሔዱ መተውና ከዚያም በኋላ አሰብት ቦታ ፈልጎ መጨፍለቁ ነበር። በተገቢው ሁኔታ ካልያዝካቸው መነደፍ ይደርስብሃል። በሲሚንቶ ዱካዬ ላይ ዘወትር ትንሽ ፍርፋሪዎች አይጠፉም ነበር። የዳቦ ሽታ እየሳባቸው ወደዚያው ይሔዳሉ። የምገሉቸውም ያንጊዜ ነበር።

አያብሰለሰለ ከሚያበሳጨኝ አንድ ሐሳብ መገላገል ነበረብኝ። መጠርጠር በጀመርንበት ቀን ቤቨርት ሲሊየርን ለምን አልገደልኩትም የሚል። ያለማቋረጥ ከራሴ ጋር አሟገታለሁ። ለመግደል መች ፅቡት ነበረህ? ውጤቴ ፍሬያማ እስከሆነ የወሰድኳቸው እርምጃዎች ሁሉ ትክክል ናቸው ወደሚለው ማጠቃለያ ሐሳብ እደርሳለሁ። የአእምሮ ዓላማ በተሳካ መንገድ ማምለጥ መቻል ነበር። እንዲት ጥሩ ጀልባ በመጨረስና አንድ ጥሩ ቦታ ለመደበቅ በቅቼ ነበር። የመነሻ ጊዜዬም ተቃርቦ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲሊየር አደገኛ እንደሆነ ዐውቂያለሁ። ወዲያውኑ ልጨርሰው በተገባኝ ነበር። ግን ስሕተት ቢሆንስ? በተሳሳተ አቅጣጫ ተመርቼ ከሆነስ? አንድ ንጹሕ ሰው ገደልኩ ማለት ነበር። ዕድሜ ልክ የተፈረደበት አንድ አሥረኛ እንደዚህ ከመሰለው የሕሊና ፍርድ ጥያቄ ውስጥ ይገባል ... ! የስምንት ዓመት ግዞተኛ ከመሆን በላይ ምን ይመጣል ... !

ለመሆኑ ማን ነኝ ብለህ ትገምታለህ፤ በሕብረተሰብ ዘንድ አንደ አንድ ቆሻሻ የምትታይ ብናኝ? ለመሆኑ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ሲበይኑብህ እነዚያ አሥራ ሁለት ደደብ ተቸዎች ከቶ ራሳቸውን ስለ ትከከለኛነታቸው ጠይቀው ይሆን? አልኩኝ ለራሴው። ምላሱን እንዴት ቆርጬ እንደማወጣው አሁንም ገና በትከከል ያልወሰንኩት ዓቃቤ ሕግ ከሱን ፈር አስለቅቆ በማቅረቡ ራሱን ታዝቦት ይሆን? የራሴው ጠበቃ እንኳ ምናልባት አሁን አያስታውሰኝም። «በ1932 በተሠየመው ችሎት ስሊፓፒዮ የተካሄደው ጠማማ ክርክር» በማለት በአጠቃላይ መልኩ ይናገርና፣ «ታውቃለህ፣ በተለይ የዚያን ዕለት በሚገባ እንዳልናገር አፈን የለጎመው ነገር ነበር፤ ከዚያም ቢላይ ዓቃቤ ፕራደል ጥሩ ቀን ገጥሞት ነበር። የተከራከረው እንኮን በማይመጣለት ዘዴና የበላይነት ስልት ነበር ...» እያለ ያወራ ይሆናል።

ይህንን ሁሉ ልክ ከጠበቃዬ ከሬይሞንድ ሂውበርት ጎን ቆሜ ከአንዳንድ ጠበቆች ጋር በፓርቲ ላይ ሲያወጉ ከፍርድ ቤቱ ሕንፃ ኮሪደሮች ውስጥ ተገናኝተው ሲያወሩ የምሰማ ይመስለኛል።

ከብሩን የጠበቀ አንድ ሰው ነበር፤ አንድ ብቻ፣ አርሱም ሰብሳቢው ዳኛ ቤቪን። በተቸዎች አማካይነት በአንድ ሰው ላይ ቅጣት መበየን ስለሚያስከትለው አደጋ ከአንዳንዶቹ ባልደረቦቹ ጋር በሚገባ ተወያይቶበት ይሆናል። እንደ ተለመደው ቃላት ለመምረጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ስለሚያውቅበት በትችቱ ላይ የተሠየሙትን ዐሥራ ሁለት ገጠሬዎች የፍርድ ኃላፊነትን ለመገምገም ያልተዘጋጁና በጠበቃ አፈጮሌነት ብቻ ወንጀለኛውን ነፃ አድርገው ንፁሑን ጥፋተኛ ነው ብለው ለመወሰን ጊዜ የማይፈጅባቸው፣ ሰባኪ የሆነ ጠበቃ በሚፈጥረው አፍራሽም ሆነ ገንቢ ሐሳብ ቶሎ ፈጥነው የሚመሩ ናቸው አያለ ያወራ ይሆናል።

እኔ በፈጠርኩባቸው ችግር፣ ምናልባት ቤተሰቦቼም ሐዘኔታ ተሰምታቸው ይሆናል። እኔ ልጁ ትከሻው ላይ በጫንኩበት ከባድ መስቀል የማያማርረው ምናልባት ምስኪኑ አባቴ ብቻ ይሆናል። ለዚያ ዕርግጠኛ ነኝ። መምህር እንደ መሆኑ ሕግን የሚያከብርና ተማሪዎቹንም እንዲያውቁ፣ እንዲቀበሉ የሚያስተምር ስለሆነ፣ ምናልባት እኔን ልጁን ምን ጊዜም ጨክኖ አይወቅሰኝም ይሆናል። በልቡም፣ «እናንተ ምናምንቴዎች ልጄን ገደላችሁት። በሐያ አምስት ዓመት ዕድሜው በአዝጋሚ ሞት አንዲሠቃይ ፈረዳችሁበት!» እንደሚል እርግጠኛ ነኝ። ልጁ የት እንዳለና አሁን ምን

t.me/OLDBOOKSPDF

አያደረጉት እንደሆነ ቢያውቅ፣ በቀጥታ ሥርዓተ አልበኛ መሆን በቻለ ነበር።

ዛሬ ማታ «ሰው በላ» ወህኒ ቤት በዕርግጥም ሰው በላነቱን አስመሰከረ። ሁለት ሰዎች ራሳቸውን ሰቀሉ፣ አንደኛው በአፉና በአፍንጫው ጨርቅ ጠቅጥቆ ታፈነ። ከጥል 127 የምትገኘው፣ ዘበኞች ከሚቀያየሩበት አቅራቢያ ስለነበር፣ አንዳንድ ጊዜ ዘበኞቹ የሚወያዩትን በጨረፍታ መስማት እችላለሁ። ጧት የሌሊቱን ድርጊት ሲወያዩ አዳመጥኳቸው። ስለዚህ ነበር ምን እንደ ተፈጸመ ያወቅኩት።

ሌላ ስድስት ወር አለፈና አንድ የሚያምር «14» የሚል ጽሑፍ በአንጨት ላይ ቀረፅኩ። በየስድስት ወሩ ለዚሁ ተግባር ብቻ የምጠቀምበት አንድ ምስማር ነበረኝ። ሐሳቤን ካሰተካከልኩ በኋላ፣ ጤንነቴም ሆነ ሞራሌ የተሟሉ መሆናቸውን ሰገነዘብ ደስ አለኝ።

በኮከቦች መካከል ስለምጓጓዝ መሰልቸት የሚፈታኮነኝ አልፎ አልፎ ነበር። ከዚህም በላይ የሲሊየር መሞት አንድ ትልቅ እርዳታ ሆነኝ። ራሴን በራሴ እንደዚህ አለዋለሁ፡- በሕይወት አለሁ፣ በሕይወት እኖራለሁ፣ መቀጠልም አለብኝ፣ አንድ ቀን እንደገና ነፃ ሆኜ ለመኖር። ግምለጤን የገታው ሰው ሞቷል። ከእንግዲህ ፈጽሞ ነፃ አይሆንም። በሠላሳ ስምንት ዓመቴ ብወጣ እንኳ አላረጅም። የሚቀጥለው የማምለጥ ሙከራዬ እንደሚሠምር ዐውቃለሁ።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ እንደገና እዘራለሁ። ከትንሽ ቀናት ወዲህ ባቶቼ እየጠቆሩ ነበር፣ ድዶቼም ዘወትር ይደማሉ። አሞኛል ብዬ ማመልከት ይኖርብኛል? ባቴን በእውራ ጣቴ ጥበቅ አድርጌ ስጫነው የጣቴ ማጎተም እንደ ተሰረጎደ ይቆያል። በውሃ የተሞላሁ ዓይነት ሆንኩኝ። ላለፉት ሳምንታት በቀን ዐሥር ወይም ዐሥራ ሁለት ሰዓቶች መሪመድ አቃተኝ፣ ለስድስት ሰዓትም ቢሆን የዕረፍት ጊዜ እያደረግኩ እንኳ ተዳከምኩ። ሣሙና በተነከረ ሸካራ ፎጣ ጥርሶቼን ዘወትር አጸዳቸው ነበር፣ ግን ድዴን ስለጎዳኝ ያደማው ጀመር። ዘዚያም ትላንት ከላይኛው ድዴ አንድ የከራንቻ ጥርሴ በገዛ ራሱ ረገፈ። የአሁኑ ስድስት ወር የተገባደደው ዕርግጠኛ የሆነ ሰውጥ አሳይቶኝ ነው። ትላንት ጭንቅላቶቻችንን ከከፍሎቻችን ውጭ ብቅ አድርጉ ተባልንና አንድ ዶከተር መጥቶ የኢያንዳንዱን ሰው የላይኛውን ከንፈር እየገለጠ ተመለከተ። ከዚያም በከፍሌ ዐሥራ ስምንት ወራት ብቻ እንደቆየሁ አንድ ቀን ጧት ማዘጊያው ተከፈተና «ወደ ውጭ ውጣ፣ በግድግዳው ትይዩ ቆመህ ጠብቅ» ተባልኩ።

ለመዝጊያው በጣም የቀረብኩት ሰው እኔ ነበርኩ። ሰባ የምንሆን በመስመር አንሸሸለን። ወደ ግራ አንድንዞር ሲነገረንና በሕንፃው የመጨረሻ አቅጣጫ እያመራን ወደ ትር ግቢው ስንወጣ የሰልፉ የመጨረሻው ጅራት ሆንኩኝ።

ሦስት ሰዓት ነበር። ጉርድ ካኪ ሸሚዝ የለበሰ አንድ ወጣት ዶከተር ከግቢው

t.me/OLDBOOKSPDF

መካከል ከአንዲት ትንሽ የአንጨት ጠረጴዛ ጎላ ተቀምጧል። አጠገቡ ሁለት የአሥረኛ ጤና ረዳቶችና አንድ የሕክምና ክፍል ዘበኛ ቆመዋል። አንዳቸውንም አላውቃቸውም። መጣሪያ በታጠቁ ዐሥር ዘበኞች ታጅበናል። የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥና የዘበኞቹ ኃላፊ ሁኔታውን በፀጥታ ይመለከታሉ።

«ሁላችሁም አውልቁ» ሲል የዘበኞች ኃላፊ አዘዘ። «ልብሶቻችሁን ብብቶቻችሁ ሥር ያዙ። የመጀመሪያው ሰው። ስምህ?» አለ።

«አከሌ... »

«አፍህን ከፈት፣ እግሮችህን አንፈራጥ። እነዚህን ሦስት ጥርሶቹን አውልቁ። ትንሽ አዮዲን ከዚያም ሜዝሊን ለቅልሉላትና ከምግብ በኋላ በቀን ሁለት ጊዜ አሰርቢከ አሲድ ስጡት።»

እኔ መጨረሻ ነበርኩ።

«ስምህ?»

«ሻሪየ»

«የሚገርም ነው። በጥሩ አቋም ላይ የምትገኘው እንተ ብቻ ነህ። አሁን ነው የደረስከው?»

«አይደለም።

«ዛሬ ዐሥራ ስምንት ወሬ መሆኑ ነው።»

«ታዲያ ለምን እንደ ሌሎቹ አልከሳህም?»

«ሕኔ እንጃ!»

«እንግዲያው እኔው እነግርሃለሁ። ወይ የተሻለ ምግብ ትበላለህ ወይም መለኮታዊ ኃይል ይጠብቅሃል ማለት ነው። አፍህን ከፈት፣ እግሮችህን አንፈራጥ። በቀን ሁለት ሎሚ፣ አንዱን ጪት አንዱን ማታ። ሎሚዎቹን ምጠጥና ጭማቂዎቹን በድድህ ላይ ፈግፍጋቸው። ስካርቪ ይዞሃል።»

ድዶቼን በአዮዲን አጸዱና ሜዚሊን ቀብተው አንድ ሎሚ ሰኩኝ። ፊቴን ወደ ግራ አዙሬ ከሰልፉ መጨረሻ በመሆን ወደ ከፍሌ ተመለስኩ።

ድውያን እሥረኞች ወደ ግቢው ወጥተው ፀሐይ እየሞቁ ከአንድ ዶክተር ጋር ፊትለፊት መተያየት፣ በእርግጥም አንድ ለውጥ ነበር። በዚያ ወህኒ ቤት ይህን ዐይነት ነገር ከቶውንም ቢሆን ተደርጎ አያውቅም። ምን ሊካሔድ ኖሯል? ያን ኢሰብአዊ ሕጋቸውን ምናልባት አንድ ዶክተር ለመጨረሻ ጊዜ ማጋለጥ ችሎ ይሆን? ጀርሚይን ጉበርት የተባለው ያ ዶክተር ከጊዜ በኋላ የራሴው ወዳጅ ሆነ። ኢንዶይቻይና ውስጥ ሞቷል። ከብዙ ዓመታት በኋላ በቬንዙዌላ፣ ማራካይቦ ውስጥ እንዳለሁ ባለቤቱ በደብዳቤ መሞቱን ገለጸችልኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

በየዐሥሩ ቀን ወደ ፀሐይ እንወጣለን። ዘወትር የሚታዘዘው አንድ ዓይነት መድኃኒት ነበር። አዮዲን፣ ሜዚሊንና ሁለት ሎሚዎች። አልተሻለኝም፣ ቢሆንም አልጠናብኝም። ዶክተሩን ሁለት ጊዜ ለአግሬ ሕመም መከላከያ ኮከሊያሪያ እንዲሰጠኝ ጠየቅኩት፣ ሁለት ጊዜም ከለከለኝ። ይህም በጣም አበሸቀኝ። በቀን ከስድስት ሰዓት በላይ መራመድ አሁንም አልቻልኩም፣ ባቶቼም ገና እንደ ጠፉሩና እንዳበጡ ናቸው።

አንድ ቀን ተራየን በመጠባበቅ ላይ እንዳለሁ ለጥላዋ ብዬ የተደገፍኳት እንዲት ወልጋዳ ዛፍ፣ ፍሬ የማትሰጥ መካን የሎሚ ተክል መሆኗን ተረዳሁ። ትንሽ ቅጠሎች ቀጠፍኩና አኘክሁ፣ ከዚያም ሳላስበው ቅጠሎች የያዘች እንዲት ቅርንጫፍ ዘነጠልኩ።

ዶክተሩ ሲጠራኝ ቅርንጫፉን ከኋላየ ሸንጥኩና ቀረብ በማለት፣ «ዶክተር፣ እንተ ከምትሰጠኝ መዓት ሎሚዎች የተነሣ መስሎኛል፣ ከኋላየ በኩል ምን እንደወጣብኝ ተመልከት» ብዬ ወደ ውጭ የተንጠለጠለችውን ትንሽ ቅርንጫፍ ማየት እንዲችል ዘወር አልኩ።

ዘበኞቹ አፋቸው እስኪሰነጠቅ ድረስ ሣቁ፣ የዘበኞቹ ኃላፊ ግን፣ «ፓፒዮ፣ ለዶክተሩ ተገቢውን ክብር ባለማሳየትህ ትቅጣለህ» አለ።

«በምንም ዐይነት» አለ ዶክተሩ። «እኔ ቅሬታ ካላቀረብኩ ይቀጣው አትችልም። ስለዚህ ከእንግዲህ ምንም ሎሚ አትፈልግማ? ልትነግረኝ የፈለከውም ይህንኑ ነበር?» አለ።

«አዎ ዶክተር። የሚበቃኝን ያህል ሎሚዎች አግኝቻለሁ። ምንም ፈውስ አላደረጉልኝም። ኮከሊያሪያውን ለመሞከር እፈልጋለሁ።»

«ለአንተ የማልሰጥበት ምክንያት፣ ያሉኝ በጣም የተወሰኑ በመሆናቸው፣ በጣም ሕመም ለጠናባቸው ሰዎች ቆጥቤ ነው። ይሁንና በቀን አንድ ማንኪያ አሰጥሃለሁ፣ ግን ሎሚዎቹን መውሰድ እንዳለብህ ነው።»

«ዶክተር፣ ሕንዳውያን አንድ የባሕር አራሙቻ ሲበሉ አይቻለሁ። የዚያ ዓይነት በሮያሌ ነበር። እዚህም እንደዚያው ጥቂት መኖር አለበት።»

«ይኸማ ጥሩ ሐሳብ ነው ፓፒዮ። አዎ፣ አንተ የምትለውን ዐይነት በውሃው ዳር አካባቢ እኔም አይቻለሁ። ለሰዎቹ በሙሉ በየቀኑ አንተ እንድታከፋፍላቸው እፈልጋሁ። ሕንዳውያኑ የሚበሉት ቀቅለው ነው ወይስ ጥሬውን?»

«ጥሬውን።»

«በጣም ጥሩ። አመሰግናለሁ። እንግዲህ አዛቹ፣ ይህ ሰው እንዳይቀጣ አረጋግጠልኝ በአንተ ላይ ጥየዋለሁ።»

«አሺ ካፕቴን።»

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ተለምር ነበር፡ በየዐሥሩ ቀን ወደ ፀሐይ መውጣትና ዶክተሩ እስኪመጣ ድረስ መጠባበቅ፣ ሌሎቹ በተራ ሲሰለፉ መመልከት፣ ሞኃልክ ለመልክ መተያየትና ትንሽ ቃላት መለዋወጥ ... ይሆን የመሰለ ጸጋ ይገኛል ብሎ ማን አሰበ? በጣም አስገራሚ የሆነ ለውጥ መጣ። የሞተው ተነሥቶ በፀሐይ ላይ ተራመደ፤ በሕይወታቸው የተቀበሩ ሰዎች ትንሽ ቃላት ተናገሩ። በጠርሙስ የተሞላ የአከስጂን አየር በሙትንፈስ እንደገና ነፍስ የተዘራብን ነበር የመሰለን።

ቋቋቂ...፣ አሉና አንድ ሐሙስ ጧት በሦስት ሰዓት ላይ የከፍሎቹ መዝጊያዎች በሙሉ ተከፈቱ።

«ግዙተኞች» የሚል አንድ ድምፅ አስተጋባ፣ «አገረ ገዢው እየጎበኙን ነው።»

ብርማ የሆነ ግራጫ ጸጉር ያለው፣ ግርማው የሚያስፈራ አንድ ግዙፍ ሰው ከአምስት የቅኝ ግዛት መኮንኖች /ምናልባት ሁሉም ዶክተሮች ሳይሆኑ አይቀሩም/ ጋር ሆኖ በእያንዳንዱ ከፍል እየቆመና በኮሪዶሩ ዝግ እያለ ይጓዛል። የእያንዳንዱን ሰው ቅጣትና ወንጀል አንድ ሰው ሲገልጽለት መስማት ችያለሁ። ወደ እኔ ከመድረሱ ቦፊት ራሱን ችሎ መቆም ያቃተው አንድ ሰው ደጋግፈው እያነሡ ነበር።

«ያ ሰው የሚራመድ ሬሣ ነው!» አለ አንድ መኮንን።

«ሁሉም በአሰቃቂ አቋም ላይ ነው ያሉት» ሲል አገረ ገዢው መለሰ። እሱን ቡድኑ ወደ እኔ ተዳርሷል። «በወህኒ ቤቱ ውስጥ በጣም ረጅም እሥራት የተፈረደበት ሰው ይኸ ነው» አለ የወህኒ ቤቱ አዛዥ።

«ስምህ ማነው?»

«ሻሪየ»

«የተፈረደብህ?»

«ስምንት ዓመት። ሦስቱ በመንግሥት ንብረት ስርቆትና ወዘተ ... አምስቱ በነፍስ ግድያ ሲሆን፣ ቅጣቱም የሚፈጸመው በተከታታይ እሥራት ነው።»

«ምን ያህሉን ጨርሰሃል?»

«ዐሥራ ስምንት ወር።»

«ጠባዩ እንዴት ነበር?»

«ጥሩ ነው» አለ የግዞት ቤቱ አዛዥ።

«ጤንነቱስ?»

«መካከለኛ ነው» አለ ዶክተሩ።

«አንተ ምን ሐሳብ አለህ?»

«እዚህ ኑሮው ከሰብአዊነት ውጭ የሆነና የፈረንሣይን ሕዝብ ክብር ዝቅ የሚያደርግ ነው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«እንዴት?»

«ፍጹም ዝምታ፣ ወደ ውጭ መውጣት የለም፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የሕክምና ከትትል አልነበረም።»

«መልካም ሥነ ምግባር አሳይ፣ እኔ በአገረ ገርነቴ ከቆየሁ ምናልባት ይቅርታ ይደረግልህ ይሆናል።»

ከዚያ ቀን በኋላ፣ ከማርቲኒክ በመጣው በአገረ ሻሾውና ከካየን መጥቶ በነበረው ዋና ዶክተር ማለት በሁለቱም ትእዛዝ፣ ለዓሣ ነባሪዎች መከላከያ በትልልቅ ቋጮች የተከበበ አንድ ኩሬ መሣይ ገንዳ ውስጥ እንድንዋኝና ዘወትር ጧት የአንድ ሰዓት ሽርሽር እንድናደርግ ተፈቀደልን።

ሁልጊዜ ጧት በሦስት ሰዓት በመቶ ቡድን እየተከፋፈልን ለመዋኘት እንወርዳለን። የዘበኞቹ ሚስቶችና ልጆች በቤታቸው ውስጥ እንዲቆዩ ተነግሯቸው ስለነበር፣ ራቁታችንን መሔድ እንችላለን።

በዚሁ ሁኔታ ለአንድ ወር እንደቀጠልን በሰዎች ገጽ ላይ አንድ አስደናቂ ለውጥ መጣ። በፀሐይ ላይ የምናሳልፋቸው ሰዓቶች፣ በጨው ውሃ ውስጥ መዋኘቱ፣ በየቀኑ ለአንድ ሰዓት ያህል ለማውራት መቻሉ፣ ያ ሁሉ ተጠራቅሞ ይሆን በሞራልም ሆነ በአካል የተሳሳቀለ የሰው መንጋ ለውጦት ነበር።

አንድ ቀን ዋኝተን ወደላይ ከምንመለሰው የመጨረሻዎቹ ሰዎች መካከል እንዳለሁ፣ ተስፋ የቆረጠ የአንዲት ሴት ዋይታና የሁለት ተከታታይ ሽጉጦች ተኩስ ሰማሁ።

«አርዱኝ! አርዱኝ! ሚስቴ እየሰጠመች ነው!»

ጩኸቱ የመጣው፣ ጀልባ ከሚታሰርበት በሲሚንቶ ከተሠራ አንድ የውሃ ግድብ ብዙም ሳይርቅ ነበር። ተጨማሪ ኡኡታዎች ቀጠሉ።

«ዓሣ ነባሪዎች!»

ከዚያም ሁለት ተጨማሪ ተኩሶች አስተጋቡ። ሁሉም ሰው ጫጫታው ወዳለበት አቅጣጫ ዞረ። ምን እንደማደርግ ሳላስብ አንድ ዘበኛ ወደ ጎን ገፈተርኩና ራቁቴን እንደሆንኩ ወደ ወደቡ ሮጥኩ። ፈዝዘው የቆሙትን ሦስት ዘበኞችና ጥቂት አረቦች እየጎተቱ ሁለት ሴቶች አዚያው እየጮሁ ቆመው ነበር።

«ወደ ውሃው ዝለል!» ብላ ከሴቶቹ አንዷ ጮኸችበትና፣ «ሩቅ አይደለችም። መዋኘት አልችልም እንጂ እኔ በሔድኩ ነበረ። አናንተ የፈሪ ጥርቃሚዎች!» አለች።

«ዓሣነባሪዎች!» ብሎ አንድ ዘበኛ ጮኸና እንደገና ተኮሰ።

ሰማያዊ ልብስ የለበሰች አንዲት ትንሽ ልጃገረድ፣ ዝግ ያለ ማዕበል እንሳፏት ይጓዛል። የምታመራው በቀጥታ ወደ ኢሥረኞቹ መታበር ነበር። ዘበኞቹ መተኮሳቸውን

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀጠሉ። በእርሷ አካባቢ ያለው ውሃ ተደበላለቀ። ጥቂት ዓሣነባሪዎች መትተው መሆን አለበት።

«ተኩሱን አቁሙ!» ብየ ጮህኩና ወደ ውሃው ውስጥ ተወረወርኩ። ዓሣነባሪዎቹን ለማራቅ ባለኝ ኃይል እየተወራጨሁና በማዕበሉም ዕርዳታ፣ ተንሳፋ ወዳለችው ልጅ ኂዜ ሳላባክን አመራሁ።

«አንድ ጀልባ ከሮያሌ ብቅ ሲል ከሠላሳና ዐርባ ያርድ የበለጠ አልራቅኩም ነበር። ከእኔ በፊት ወደ ትንሿ ልጃገረድ ደረሰና አወጣት፣ ከዚያም እኔን አወጡኝ። በንዴት አለቀስኩ። ፍሬቢስ በሆነ ነገር ሕይወቴን አደጋ ላይ ጥየው ነበር።

በአርግጥ እንደዚያ ስል አስቤ ነበረ። ግን ከአንድ ወር በኋላ ዶክተር ጉበርት ያንን ሙከራዬን እንደ ውለታ ቆጥሮልኝ፣ የተፈረደብኝ የብቸኝነት ቅጣት በሕክምና ሰበብ እንዲታገድልኝ ማድረግ ቻለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰምንተኛ ማስታወሻ

ወደ ሮያሌ መመለስ

ጎሾቹ

ወደ ሮያሌ መመለሴ አንድ ዐይነት ተአምር ነበር። ለስምንት ዓመታት በግዞተኝነት ትቸው ሔጄ ነበር። አንዲት ሀሣን ከአደጋ ለማትረፍ ባደረግኩት ሙከራ፣ ከወሥራ ዘጠኝ ወራት በኋላ ለመመለስ በቃሁ።

ጓደኞቹ ሁሉ እዚሁ ነበሩ። ዴጋ አሁንም ጸሐፊነቱን እንደያዘ፣ ጋልጋኒ አሁንም ፖስተኛ እንደሆነ፣ ግራንዴ፣ አናጢው ቦርሴ፣ «የጋሪ አምቻዎቹ» ናሪከና ኪነር፣ በመጀመሪያው የማምለጥ ሙከራ ተባባሪየ የነበረው ቻታል ሕከምና ሥራው ላይ እንዳለና የሕከምና ከፍል ረዳት የሆነው ማቹሬ።

እንደዚሁም የኮርሲካውያን ሽምቅ ቡድን አባል የነበሩት ወንበዴዎች በሙሉ እነ - ኢዛሪ፣ ቪዴዎሌ፣ ቹዛሪ፣ ራዞሪ፣ ፎስኮ፣ ማውሰርና ቻፓር ነበሩ፣ ከ1927 እስከ 1935 ድረስ በየጋዜጦቹ የወንጀል ዓምዶች ላይ ስማቸው የማይታጣው በሙሉ እዚያው ነበሩ።

ዱፍሬንን የገደለው ማርሲኖ የተባለው ሰው ከሳምንት በፊት በሕመም ምክንያት ሞቶ ነበር። በዚያ ቀን ለዓሣነባሪዎቹ ምርጥ የሆነ ከሽን ያለ ምግብ ገጥሟቸዋል። የተጣለላቸው፣ በከበሩ ድንጋዮች ጥበብ በመላው ፓሪስ ከታወቁት ከፍተኛ ኤክስፐርቶች አንዱ ነበር።

እንደዚሁም የራሱን ሹፌርና የሹፌሩን ጓደኛ፣ የራሱንም የቅርብ ጓደኛ ጭምር የገደለው፣ «ቀልደኛው» በሚል የቅፅል ስም የሚጠራው፣ ከሊሞጊስ ቀበሌ የመጣው ባራት የተባለው ከበርቴ ቴኒስ ተጫዋች ነበር። ባራት በሮያሌ ሆስፒታል ውስጥ የላቦራቶሪና የመድኃኒት ከፍል ኃላፊ ነበር። «ሰንተ ሆስፒታል ውስጥ ልትገባ የቻልከው በእግዚአብሔር ኃይል» ነው» አያለ አንድ ፈዘኛ ዶክተር ያሽሟጥጠው ነበር።

በእኔ ወደ ሮያሌ መመለስ ጭብጨባው እንደ ነጎድጓድ አስተጋባ። ወደ «ሕይወገሬዎቹ ወንጀለኞች» ሕንፃ የተመለስኩት አንድ ቅዳሜ ጧት ነበር። ከሞላ ጎደል ማንኛውም ሰው እዚያው ስላለ ሁሉም ከንዶቹን ዘርግቶ እንኳን ደህና መጣህ አለኝ። ሊላው ቀርቶ በስሕተት አንገቱ ሊቆረጥ ተቃርቦ ከነበረባት ከዚያች ታሪካዊ ማለዳ ጀምሮ ተናግሮ የማያውቀው ያ ሰዓት አዳሽ ሰው እንኳ ሰላምታ ሊሰጠኝ መጣ።

«ታዲያስ ልጆች፣ ሁሉም ሰው ደህና ነው?»

«ደህና ነን ፓፒ። እንኳን ደህና ተመለስከ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ቦታህ አሁንም እንደተጠበቀ ነው» አለ ግራንዴ። «ከሐድከበት ቀን ጀምሮ ከፍት ሆኖ ይገኛል።»

«አመሰግናለሁ። አዲስ ነገር አለ እንዴ?»

«አንድ መልካም ዜና።»

«ምንድን ነው?»

«ከዘንባባ ዛፍ አናት ላይ ሆኖ አንተን ሲሰልል የነበረው አቃጣሪ ባለፈው ሌሊት ተገድሏል። ከድርጊቱ አንተን ለማግለልና ሰይጣኑንም ማየት እንደማትፈልግ ያወቀ የአንተው አንድ ጓደኛ ሠርቶት መሆን አለበት።»

«ማመስገን እንድችል ማን መሆኑን ባወቅሁ።»

«ምናልባት አንድ ቀን ራሱ ይነግርህ ይሆናል። አቃጣሪውን ያገኙት ዛሬ ጧት በስም ጥሪ ወቅት አንድ ጩቤ ከልቡ ላይ ተተክሎበት ነው። ማንም ሰው የሰማው ወይም ያየው ምንም ነገር የለም።»

«በዚያው ዐይነት ቢሆን ይሻላል። ጨዋታውስ እንዴት ይካሔዳል?»

«መልካም ነው። ሥራህ አሁንም አለልህ።»

«ጣሩም። እንግዲህ የዕድሜ ልክ ጽኑ አሥራት ትሮ እንደገና ተጀመረ። ታሪኩ እንዴት ወይም መቼ እንደሚያበቃ ማን ያውቃል።»

«ፓፒ፣ ስምንት ዓመት ተፈረደብህ ማለትን ስንሰማ ልክ እንደ አንድ ነገር ከው ብለን ደንግጠን ነበር። አሁን እንግዲህ ታመልሰሃል፣ የፈለገውን አደጋ ያስከትል እንጂ እንድታመልጥ ለመርዳት የማይፈልግ ማንም ሰው አይገኝም።»

«የወህኒ አዛዡ ይፈልጉሻል» አለ አንድ ሽማግሌ።

ከእርሱ ጋር አብሬ ሔድኩ። በዘበኞቹ ቤት ሳልፍ አብዛኞቹ ዘበኞች መልካም ቃላት እየጣሉብን ሽማግሌውን እየተከተልኩ አዛዥ ፕሬሉ ዘንድ ቀረብኩ።

«እንደምን አለህ ፓፒዮ?»

«ደህና ጌታየ።»

«ምሕረት በማግኘትህ ተደስቻለሁ፣ የሥራ ባልደረባዬን ልጅ ለማዳን ያን የመሰለ የቆራጥነት እርምጃ በመውሰድህ ማመስገን አለብኝ።»

«አመሰግናለሁ።»

«የቀድሞው ሥራህ ከዓሣ ማጥመድ መብትህ ጋር እንደገና እስኪለቀቅልህ ድረስ ጎሾቹን እንድታግድ ልመድብህ ነው።»

«ማድረግ የምትችል ከሆነማ እኔም አፈልገዋለሁ።»

«ሥራዬ ነው አደርገዋለሁ። የወርክሾፑ ዘበኛ ዳግመኛ ወደዚህ ቦታ «አይመለስም፣ እኔም በሦስት ሳምንት ውስጥ ወደ ፈረንሣይ እሔዳለሁ። እሺ፣ እንግዲህ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገ እንድትጀምር።»

«እንዴት አድርጌ ላመስግንህ?»

«ሌላ የማምለጥ ዕቅድ ከመጀመርህ በፊት ለአንድ ወር ያህል በመቆየት» አለ ጥሩዬ እየሣቀ።

በከፍላችን ውስጥ እንደ ወትሮው ተመሳሳይ ኑሮ የሚገፉት ተመሳሳይ ሰዎች ናቸው። የሚኖሩትና የሚያስቡት ለካርታ ብቻ የሆነ አንድ ልዩ የቁማርተኞች መደብ አለ።

በኮንቮያችን ውስጥ የገንዘብ መደበቂያ የወርቅ ቱቦ የነበረውን ኢጣሊያዊ አየሁት። ሰላምታ ሊያቀርብልኝ መጣ።

«አሁንም ገና እዚሁ ነህ?» ሰል ጠየቅኩት።

«ማንኛውንም ነገር ሞክሬያለሁ። አናቴ ዐሥራ ሁለት ሺ ፍራንክ ልካልኝ ሰድስቱን ሺ ዘበኞቹ ኮሚሽን ወሰዱብኝ። ሆስፒታል ለመግባት እንድችል አራቱን ሺ አጠፋሁት። ወደ ካየን ሔጄ ራጅ ለመታየት ተሳከቶልኝ ነበር፣ ግን ምንም ሕመም አልተገኘብኝም። ከዚያም አንድ ጓደኛየን በማቁሰል ራሴው ተከሳሽ ሆኜ እንድቀርብ አደረግኩ። ሰውየው ማን እንደሆነ አንተም ታውቀዋለህ– ራዞሪ ኮርሲካዊው ነው።»

«ታዲያ ምን ሆነ?»

«በሀሳቤ ተስማማ። ሆዱን በገዛ ራሱ አቆሰለና እርሱ እንደ ከሳሽ እኔ እንደ ተከሳሽ ሆነን ወደ ጦር ፍርድ ቤት ተያይዘን ሔድን። አካባቢውን ለመቃኘት ፍጹም ጊዜ አልነበረንም። በዐሥራ አምስት ቀን ውስጥ የእኛ ጉዳይ አከተመለት። ስድስት ወር ተፈረደብኝና ያለፈውን ዓመት በግዞት አሳለፍኩት። እዚያ መሆኔን እንኳ አላወቅከም ፓፒ፣ ከእንግዲህስ ፍጹም መቋቋም አልችልም። ራሴን መግደል አፈልጋለሁ።»

«በማምለጥ ላይ እንዳለህ ባሕር ውስጥ መሞቱ ይሻላል። ስለሆነም ሌላው ቢቀር ነፃ ሆነህ እንኳ ትሞታለህ።»

«ልክ ነህ። ለማንኛውም ነገር ተባባሪ ለመሆን ዝግጁ ነኝ። አንድ ሀሳብ ከመጣልህ እንድታሰማኝ።»

«እሺ።»

ኑሮ በሮያሌ ቀጠለ። በአሁኑ ወቅት የጎሽ እረኛ ሆኛለሁ። ከማግዳቸው ውስጥ አንደኛው ሰሙ ብሩተስ ይባላል። ከብደቱ ከአራት ሺ ፓውንድ በላይ የሆነና ሌሊት ሌሎች ጎሾችን የጨረሰ ነፍሰ-ገዳይ ነበር። ቀደም ሲል ሁለት ተባዕቶችን ገድሏል። አንድ ዘበኛ፣ «ይህ የመጨረሻ ዕድሉ ነው። አንድ ተጨማሪ ጎሽ ከገደለ ወዲያውኑ አርምጃ ይወሰድበታል» ሲል ነገረኝ።

ከብሩተስ ጋር ተዋወቅኩ። ያግደው የነበረው ከማርቲኒክ የመጣው ጥቁር

t.me/OLDBOOKSPDF

ለአንድ ሳምንት ያህል ሲያለማምደኝ ሰነበተ። ከኮርማው ጋር ወዲያውኑ ጓደኝነት እበጀሁ። ረጅሙ ምላሱ ጨውነት ወዳለው ማንኛውም ነገር ይመዘዘል። ከሆስፒታሉ የአትክልት ቦታ የለቀምኳቸውን ጥቂት ጥሬ ማንነዎች አሰጠዋለሁ። ከአንድ ሠረገላ ብረት ጋር እንደ በሬ አጠምደውና ብሩተስን ቁልቁል እየሳብኩ አወስደዋለሁ። አንድ ሺ ጋሎን ያህለ ውሃ የሚይዝ አንድ በርሜል ይሸከማል። የብሩተስና የእኔ ተግባር ወደ ባሕር ወርደን በርሜሉን መሙላትና በወጣ ገባው ሸንተረር ወደ ደልዳላው አፋፍ ተመልሰን ማቅናት ነበር። አንድ ጊዜ እዚያ ከደረስኩ በኋላ ከማለዳው ቆሻሻ የተረፈውን ሣንኛውንም ጠራርጎ እንዲወስደው የበርሜሉን ከዳን ፈትቼ ውሃውን በቦዩ ቁልቁል መልቀቅ ነበር። በዐሥራ ሁለት ሰዓት እጀምርና ሦስት ሰዓት አካባቢ አጨርሳለሁ።

በአራተኛው ቀን መጨረሻ ላይ ሥራውን ራሴ ለማከናወን እንደተለማመድኩ ከማርቲኒክ የመጣው ሰው አመነበት። ከብሩተስ ጋር አንድ ችግር ብቻ አለ፣ መሥራት ካለመውደዱ የተነሣ ከሚደበቅበት አንድ ኩሬ ውስጥ ጧት በዐሥራ አንድ ሰዓት ሔጄ ማምጣት ነበረብኝ። አፈንፋኝ ከሆኑት አፍንጫዎቹ ቀዳዳዎች ላይ በአንድ የብረት ቀለበት ተሰንጎ በዚያ ላይ ደግሞ ርዝመቱ በግምት ሃያ ኢንች የሆነ አንድ ሰንሰለት ተንጠልጥሎበታል። ልክ ልደርስበት ስል ወደ ውስጥ ጠልቆ ይገባል፣ በሌላ አቅጣጫ ራቅ ብሎ ብቅ ይላል። ቅጠሎችና ትንኞች በሞሉበት የረጋ ኩሬ ውስጥ፣ እርሱን ለመያዝ እንዳንድ ጊዜ ከአንድ ሰዓት በላይ ይወስድብኛል። በንዴት አጨስና፣ «አንተ ምናምንቴ! አንተ እንደ በቅሎ ግትር የሆንክ! አትወጣም እንዴ? የማትወጣ ከሆነ ገሃነም ግባ።» ብዬ አጓራበታለሁ። በቁጥጥሬ ሥር ነው የምለው ሰንሰለቱን ለመያዝ ስችል ብቻ ነበር። ሲዖቦቼ እንዳይንቀሳቀስ ያደርጉታል። ግን ከኩሬው ካወጣሁት በኋላ እንደገና ጓደኛዬ ይሆናል።

ሁለት ባልዲ ንጹሕ ውሃ አቀዳለሁ። የሚገማውን የኩሬ ደለል ለማስለቀቅ በቅድሚያ ራሴ አታጠባለሁ። በሣሙና አየፈገፈግኩና አየተለቃለቅኩ ሙልጭ ብዬ ከጸዳሁ በኋላ፣ ዘወትር ግማሽ ባልዲ ውሃ ስለማስተርፍ በአንድ የኮከነት ቅርንጫፍ ብሩተስንም አሸዋለሁ። ደስ የሚያሰኘው የገላውን አካባቢዎች እየፈገፈግኩ በውሃ ሳለቃልቀው፣ ጭንቅላቱን ከእጆቼ ጋር እያፈጋፈገ ከጋሪው ቀንበር መካከል በገዛ ራሱ ሐዲ ይገባል። ጥቁሩ ያደርግ እንደነበረው ዓይነት እኔ ፍጹም አልኮረኩረውም። ምስጋና ለማቅረብ መሆን ያለበት ይመስላል፣ ብሩተስ ምንጊዜም ለእርሱ አድርጎ የማያውቀውን ለእኔ በጥጥነት ይሠግራል።

ከብሩተስ ጋር በጣም ኃይለኛ ፍቅር የያዛት አንዲት ትንሽ እንስት ጎሽ ነበረች። ዘወትር ከአጠገቡ አትለይም፣ እኔም ሌሎቹ እረኞች እንደሚያደርጉት ከእርሱ እንድትርቅ አላባርራትም። በተቃራኒው በየትኛውም ቦታ እንድትከተለንና ከብሩተስም ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

እንድትሰሽሽ ፈቀድኩላት። የፍቅር ጭውውት ሲያደርጉ ብቻቸውን አተዋቸዋለሁ፣ በዚህም የተነሣ ብሩተስ ለእኔ በጣም ቅን ታዛዥ ሆነ። አንድ ሺውን ጋሎን የሚጎትተው ቡተለየ ፍጥነት ነበር። ከማርጋሬት /የአንስቷ ጎሽ ስም ነበር/ ጋር በመመላለስ ያጠነጠንኝን ጊዜ ለማካካስ ይመስላል።

በቀን ሦስት ጊዜ እመላለሳለሁ። ረጅም ጊዜ የሚወስደው በርሜሉ ሲሞላ ነበር፣ ማን የሚተባበሩኝ ሁለት ሰዎች ስለነበሩ ሥራው በሚገባ ተቀላጥፎ ይካሔዳል። በሦስት ሰዓት አጨርስና ወደ ዓሣ ማጥመዱ ሰመውረድ ነፃ እሆናለሁ።

ብሩተስን ከኩሬው ሰማውጣት የምትረዳኝ ማርጋሬትን አጋጠመኝ። ጅሮዋ ሲታከክላት ልክ እንደ ሞቃት ባዝራ ፈረስ የምታሰማው አንድ ልዩ ድምፅ ነበራት። ከዚያም ብሩተስ በጣዛ ራሱ ይወጣል። ከእንግዲህ ወዲያ ራሴን ማጠብ አላስፈለገኝም፣ ብሩተስን ማን ከመቼውም የበለጠ አጥበዋለሁ። ከሚከረፋው የውሃ ሽታ ተላቅቆ ንፁሕ ሲሆን፣ ብሩተስ ለማርጋሬት እጥፍ ድርብ ማራኪ ሆነላት።

ተመልሰን እቀበቱን ተያይዘን ከኮረብታው ግማሽ መንገድ ስንደርስ አንድ ትልቅ ቋጥኝ ያለበት ደልዳላ ቦታ ላይ ለትንሽ ጊዜ እንቆማለን። ሰረገላውን ታኮ እደርግለትና ብሩተስም ትንፋሹ መለስ ይልለታል። በዛሬዋ የተለየች ማለዳ ግዙፍነቱ ብሩተስን የሚያክል ዳንተን በሚል ስም የሚጠራ አንድ ሌላ ጎሽ በኮከኑት ዘምባባ ቁጥቋጦዎች በስተጀርባ ተጋድሞ ይጠባበቀን ነበር። እንደ ደረስን ከተደበቀበት ቦታ ተንደርድሮ ወጣና ብሩተስን ውጊያ ገጠመው። ብሩተስ ወደ አንድ ጎን ሲዘል ነበረ ከዳንተን ቀንድኖ አንደኛው በቀጥታ ወደ በርሜሉ ውስጥ የተቸከለው። ዳንተን ቀንዱን ለማላቀቅ የሞት ሽረቱን በመታገል ላይ እንዳለ እኔ የብሩተስን ቀንበር ፈትቼ አላቀቅኩት። ቢያንስ የሦሳሳ ያርድ ርቀት ወደ ኋላ አፈገፈገና ኢጋሾ መሬት ላይ ከወጣ በኋላ ብሩተስ በሚያስፈራ ግልቢያ ወደ ዳንተን ተንደረደረ። ሳይደርስበት ቀደም ብሎ ቀንዱ ትንሽ ተሸርፎ ከመቅረቱ በስተቀር ዳንተን ራሱን ከበርሜሉ በመመንጨቅ አላቅቆ ነበር። ብሩተስም በወቅቱ ራሱን ተቆጣጥሮ መግታት ስላልቻለ፣ ከሰረገላው ጋር ተላተመና ገለበጠው።

ከዚያም በጣም የሚያስገርም ነገር ተፈጸመ። ብሩተስና ዳንተን ጭንቅላቶቻቸውን በማነካካት ምንም ሳይጋፉ ትላፊቅ ቀንዶቻቸውን ብቻ አንድ ላይ ያፈጋፍጉ ጀመር። ድምፅ ብቻ አያሰሙም እ.ጂ 'የሚያወሩ ይመስላሉ። በኋላም ማርጋሬት በቀጭኗ መንገድ በዝግታ ሽቅብ ስትወጣ፣ ሁለቱ ተባዕቶች አልፎ አልፎ አየቆሙ በመፈጋፈግና ቀንዶቻቸውን በማቆላለፍ ተከተሏት። በዚህ ሁኔታ ረጅም ጊዜ ሲወስዱባት ማርጋሬት አንድ ረጅም የፍቅር ድምፅ ታሰማና ጉዞዋን ትቀጥላለች። ሁለቱ ፍቅረኞች ይከተላሉ። ወደ ደልዳላው አፋፍ እስከንደርስ ለሦስት ተጨማሪ ጊዜ ቆመው

t.me/OLDBOOKSPDF

ተመሳሰይ ሥነ ሥርዓት ፈጸሙ። ስፋቱ በግምት ሦስት መቶ ያርድ ከሆነ ኢደጋ ማስጠንቀቂያ መብራት ያለበት ግንብ ፊት ለፊት ከሚገኝ አንድ ሰጥ ያለ ሜዳ ላይ ደረስን። ከዚያ ራቅ ብሎ የአሥረኞች ካምፕ ሲሆን፣ በግራና በቀኝ ደግሞ አንዱ የእኛ፣ ሌላው የዘበኞቹ ሆስፒታሎች ይገኛሉ።

ዳንተንና ብሩተስ አሁንም ሐያ እርምጃ ወደ ኋላ ናቸው። ማርጋሬት ወደ ሚጸው መካከል አመራችና በፀጥታ ሐዳ ቆመች። ሁለቱ ተፋላሚዎች ጎን ለጎን ሆነው ዘለቁ። ማርጋሬት አንድ ረጅም ድምፅ አሰተጋባች። ተባዕቶቹ እንደገና ቀንዶቻቸውን አነካኩ፣ በአሁኑ ወቅት በትከከል የሚነጋገሩ ይመስሉ ነበር።

ከውይይታቸው በኋላ አንደኛው በዝግታ ወደ ቀኝ ሲዞር፣ ሌላው ደግሞ ወደ ግራ ዞረ። ሰጥ ካለው ሜዳ የመጨረሻ ርቀት በሦስት መቶ ያርድ ላይ ቦታቸውን ያዙ። ማርጋሬታ አሁንም በመካከል ሆና ትጠብቃለች። በመጨረሻ ሁኔታው ገባኝ። ሥነ ሥርዓት ባለው ቱከከር አንድ ፍልሚያ ሊካሔድና ለአሸናፊው ሽልማቱ አንዲት ወጣት አንስት ልትሆን ነበር። ለማርጋሬት ግሩም ሆነላት - በእርሷ ላይ የሚፋለሙ እነዚህን መሳይ ሁለት አፍቃሪዎች በማግኘቷ ኩራት ተሰምቷት ነበር።

ከማርጋሬት የወጣ አንድ የተቆራረጠ ከፍተኛ ጩኸት የፍልሚያው መጀመሪያ ሆነ። ሁለቱ ኮርማዎች በኃይል ይንደረደሩ ጀመረ። በመካከላቸው ያለውን የሦስት መቶ ያርድ ልዩነት ለማቋረጥ ከራሳቸው አራት ሺህ ፓውንድ ከብደትና እየጨመረ ከሚሔደው ፍጥነታቸው ጋር ውጤቱ ምን እንደሚሆን መዘርዘሩ አያሻኝም። ሁለቱ ጭንቅላቶች አንድ ላይ በሚላተሙበት ወቅት ግጭቱ በጣም ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ሁለቱንም ለአምስት ደቂቃ ያህል ዘረራቸው። ለመነሣት የመጀመሪያ ብሩተስ ስለነበረ ተመልሶ ወደ ቦታው ጋለበ። ይህ የጦርነት መድረክ ሁለት ሰዓት ፈጀ። ከዚያ በኋላ አንዳንዶቹ ዘበኞች ብሩተስን ሊገድሉት ፈለጉ፣ እኔ ግን አይሆንም አልኩ። በሚቀጥለው ተከታታይ ፍልሚያ፣ በበርሜሉ ተጎድቶ የነበረው የዳንተን ቀንድ ተሰበረ። መሸሸ ሲጀምር ብሩተስ ከኋላ ተከተለው። ተከታዩ የመድረክ ጦርነት እስከሚቀጥለው ቀን ድረስ ቆይቶ ተፈጸመ። በእትከልቱ፣ በመቃብሩ፣ በየትኛውም ቦታ ከፍ ያለ ጥቃት አደረሱ። በመጨረሻ ዳንተንን ከወደቡ በታች ከሚገኘው የልኳንዳ ቤት ግንብ ጋር በማጣበቅ በቀንዶቹ ሆዱን የዘነጠለው ከጧቱ አንድ ሰዓት ላይ ነበር። ከዚያም ለመጨረሻ ጊዜ ከሚሰቃየው ጠላቱ ሆድ ውስጥ ብሩተስ ቀንዶቹን በጥልቀት እየከተተ በማጠማዘዝ ሁለት ጊዜ በላዩ ላይ ተንከባለለበት። የደም ጎርፍ ከሆድ ዕቃው ጋር ተዘረጋገፈና ዳንተን መሬት ላይ ተዘረጋ።

በሁለቱ ግዙፍ እንስሳዎች መካከል የተደረገው ጦርነት ብሩተስን በጣም ከማድከሙ የተነሣ ቀንዱን ከዳንተን ሆድ ውስጥ ማላቀቅ ነበረብኝ። ከዚያ በኋላ ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሕር ዳር የምትወስደውን መንገድ ተከትሎ እየተንዳገደ ቁልቁል ሲወርድ፣ ማርጋሬትም ጭንቅላቷን ቀና እያደረገች ከጎኑ ትራመድ ጀመር።

የጫጉላ ጊዜያቸውን አልተጋራኋቸውም። አንድ ዘበኛ የብሩተስን ቀንበር በመፍታቴ ከስ አቀረበብኝና የከብት አረኝነቴን ሥራ አጣሁ።

ስለ ብሩተስ ሁኔታ ለወህኒ አዛዡ እንዳሰረዳ ጠየቅኩ።

«ፓፒዮ፣ እስኪ ስለ እግዚአብሔር ብለህ የተደረገው ምን ነበር? ብሩተስ መገደል አለበት፣ ከመጠን በላይ አደገኛ ነው። በእርሱ ምክንያት ሦስት ጥሩ ጎሾች አጣን።»

«እኔ አንተ ዘንድ የመጣሁት ለዚሁ ጉዳይ ነበር። ብሩተስን እንድታተርፈው አፈልጋለሁ። ብሩተስ የሠራው በአልሞት ባይ ተጋዳይነት መሆኑ የመስኩ ዘበኛ አልገባውም። እንዳብራራልህ ትፈቅድልኛለህ?»

አዛዡ ፈገግ አለ። «አየሰማሁህ አኮ ነው።»

ታሪኩን ነገርኩት። «—እንግዲህ እንዴት ተጠንቅቆ እንደነበር አሁን ተረዳህልኝ ጌታየ። ከዚህም በተጨማሪ ብሩተስን ባልፈታው ኖሮ ዳንተን ይገድለው ነበር፣ ምክንያቱም ተጠምዶ ስለነበር መከላከል አይችልም።»

«እውነት ነው» አለ አዛዡ።

ከዚያም የመስኩ ዘበኛ ደረሰ። «እንደምን አደሩ ጌታዬ። ፓፒዮ፣ አንተን አየፈለግኩ ነበረ። ዛሬ ጧት ወደ ሥራ የምትሔድ መስለህ ወጣህ፣ ግን ምንም ሥራ አልነበረህም።»

«ሚስተር አንጎስቲ፣ የሔድኩት ጦርነቱን ለማቆም ፈልጌ ነበር። ግን ቆሞ ጠበቀኝ።»

«ያ ሊሆን ይችላል፣ ግን ዳግመኛ ጎሾቹን እንደማታግድ ነግሬሃለሁ። በተጨማሪ ብሩተስን እሔድ ጧት እናሳርደዋለን። አስፈላጊውን ሥጋ ያሟላል።»

«እንደዚያስ ማድረግ አትችልም።»

«አንተ ልትከለክለኝ አትችልም።»

«እንደማልችል ዐውቃለሁ፣ ግን እኔ ባልችልም፣ የወህኒ አዛዡ ግን ይችላል። ያም የማይሆን ከሆነ እንዳይታረድ ለዶክተር ጉበርት አመለክታለሁ።»

«አንተ እስከዚህ ምን አሳሰበህ?»

«የአንተ ጉዳይ አይደለም። ያ ጎሽ በእኔ ሃላፊነት ሥር ነው፤ ጓደኛዬም ነው።»

«የአንተ ጓደኛ ሆነ አንድ ጎሽ? ልታፈዝብኝ እየሞከርክ ነው?»

«ስማ ሚስተር አንጎስቲ፣ ለአንድ ደቂቃ መናገር ትፈቅድልኛለህ?»

«ለጎሹ ይከራከር» አለ አዛዡ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሺ፣ በል ቀጥል።»

«እንስሳዎች እርስ በርሳቸው እንደሚነጋገሩ ታምናለህ?

«ለምን አላምንም? ሙሉ በሙሉ ባይግባቡም።»

«መልካም እንግዲያው፣ ብሩተስና ዳንተን የገጠሙት ፍልሚያ ነበር።»

ታሪኩን በሙሉ እንደገና ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ተናገርኩ።

«የከርስቶስ ያለህ!» አለ ኮርሲካዊው። «ፓፒዮ፣ ጉደኛ ሰው ነህ። ከእንግዲህ ብሩተስ የግልህ ይሆናል። ግን ዳግመኛ ከገደለ፣ ማንም ሰው ቢሆን ወላ የወህኒ አዛዡ እንኳ አያድኑትም። ወደ ከብት አረኝነት ሥራህ ተመልሰህ ሒድ። ደግሞም ብሩተስ ሥራ መሥራቱንም ተከታትል።»

ከሁለት ቀን በኋላ በወርክሾፑ ሰዎች ሰረገላው ተጠግኖ ብሩተስ ሚስቱን ማርጋሬትን ከጎኑ እያደረገ ዕለታዊ ተግባሩን ቀጠለ። ወደ ማረፊያ ቦታችን ደርሰን ሰረገላውን ታኮ ካደረግኩለት በኋላ፣ «ብሩተስ፣ ዳንተን ወዴት አለ?» አለዋለሁ። ከዚያም ያ ግዙፍ እንስሳ በአንድ ስበት ሰረገላውን ይጎትትና በድል አድራጊነት እርምጃ አንድ አፍታ ገሥግሶ ጉዞውን ይጨርሳል።

በቅዱስ ዮሴፍ የተደረገ ሜመፅ

ዘላቂነት ያለው ሰላም ያገኘን መስሎን ለጊዜው እንደሰት እንጂ ደሴቶቹ ግን አደገኞች ነበሩ። ኑሯቸውን በምችት አደላድለው የሚዝናኑትን እነዚያን ሰዎች ባየሁ ቁጥር ሥቃይ ይሰማኛል። አንዳንዶቹ የእሥራት ዘመናቸውን እስኪፈጽሙ ይጠበቃሉ፣ ሌሎቹ ግን ምኞታቸውን ለማሟላት ይጥሩ ነበር። አንድ ሌሊት በተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋዬ ላይ ጋደም ብዬ ሳለሁ ከከፍሉ በስተጀርባ በካርቡኔሪና በግራንዴ በጣምራ የሚመራ በጣም የተጧጧፈ ቁማር በመካሔድ ላይ ነበረ። ውርርዱን ለመቆጣጠር አንድ ሰው በቂ አልነበረም። አንዳንድ ትዝታዎች ለማሰላሰል በመሞከር እኔ ከጨዋታው ውጭ ነበርኩ። በቁሜ በተቀበርኩባት ዕለት ጭጋግማ ሥዕሎች ላይ ሳነጣጠር በግልጽ ለማየት የቻልኩት ከሙሉው የጭካኔ ርቱዕ አንደበቱ ጋር ዓቃቤ ሕጉን ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ያጥፋህ፣ ትሪኒዳድ ውስጥ እነቦውን ዘንድ ስደርስ በእርግጥ አሸነፍኩህ ብየ አሰቤ ነበር። አንተ የውሻ ልጅ፣ ምን ዓይነት ሰላቢ ፍጥረት ብትሆን ነው ስድስቱም የማምለጥ መከራዎቼ የተከላሹብኝ?

ከከሳሼ ጋር በማውራት ላይ እንዳለሁ ሁለት ሰዎች ወደ ተንጠልጣዩ አልጋ መጡ።

«ተኝተሃል እንዴ?»

«አልተኛሁም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ልናነጋግርህ እንፈልጋለን፤»

«አሺ ንገሩኝ። ቀስ ካላችሁ ማንም የሚሰማችሁ ሰው የለም።»

«አንድ ዓመፅ እያዘጋጀን ነው።

«ዕቅዳችሁ ምንድን ነው?»

«አረቦቹን፣ ዘበኞቹን፣ የዘበኞቹን ሚስቶችና ልጆቻቸውን በሙሉ ልንገድል ነው። ሁሉም ግሞች ናቸው። እኔ፣ አርናውድ፣ ጓደኛየ ሐውቲንና ሌሎች አራት ሰዎች ሆነን የወህኒ አዛዡን የመሣሪያ ግምጃ ቤት ልንዘርፍ ነው። በአሁኑ ጊዜ የምሠራው በዚህ ግምጃ ቤት ውስጥ ተመድቤ ነው። ሃያ ሦስት አውቶማቲክ መትረየሶች፣ ከሰማንያ የበለጡ ሌሎች ጠመንጃዎችና ካርባይኖች አሉ። ይህንንም ተግባራዊ የምናደርገው ...»

«ተወው፣ ነገሩን እዚሁ ላይ አቁመው» እኔ አልስማማም። በእኔ ላይ እምነት ስለጣላችሁብኝ አመሰግናለሁ፣ ግን መደባለቅ አልፈልግም።»

«መሪነቱን አንተ ትይዝልናለህ ብለን አስበን ነበር። ዝርዝሩን በሚገባ ላብራራልህ፣ ማንኛውንም ነገር በጥንቃቄ ስላጠናን ሊከሽፍብን አይችልም። ይህን ስናዘጋጅ አምስት ወር ሆኖናል። ከእኛ ጋር የሚተባበሩ ከሃምሳ በላይ ሰዎች አሉ።»

«ስማቸውን እንዳትነግሩኝ። መሪ ለመሆን ቀርቶ ለመደብለቅ እንኳ እቃወማለሁ።»

«ለምን? አምነን ዕቅዳችንን ከገለጽንልህ በኋላ አምቢ የምትልበትን ምክንያት ልታስረዳን ይገባል።»

«ምንም ነገር እንድትነግሩኝ አኔ አልጠየቅኳችሁም እኮ። ከዚህም በቀር ማድረግ የምሻው እኔ የምፈልገውን እንጂ፣ ሌሎች እንዳደርግላቸው የሚፈልጉትን አይደለም። በጅምላ የምጨፈጭፍ ነፍሰ-ገዳይም አይደለሁም። እርግጥ መጥፎ በደል የፈጸመብኝን አንድ ሰው እገድል ይሆናል፣ ግን ምንም ነገር ያላደረጉኝን ሴቶችና ሕፃናት አይደለም። ባይታያችሁም እኔ ልጠቁማችሁና ዓመፃችሁ ቢሠምርላችሁ እንኳ በመጨረሻ ውድቀት ይከተላችኋል።»

«ለምን?»

«ምክንያቱም ዋናውን ዓላማችሁን ግብ ለማድረስ አትጉ.ም፣ ለማምለጥ አይሳካላችሁም። እንበል በሴራው ውስጥ የተካፈሉት አንድ መቶ ናቸው። ከሷሴቶቹ የሚወጡት እንዴት ሆነው ነው? እዚህ ያሉት ሁለት ጀልባዎች ብቻ ናቸው። አንድ ላይ አጠቃለው መያዝ የሚችሉት ቢበዛ ዐርባ አሥረኞችን ነው። ሌሎቹን ሲድሳ ሰዎች ምን ታደርጉዋቸዋላችሁ?»

«እኛ በጀልባዎች ከሚሔዱት ዐርባ ሰዎች መካከል እንሆናለን።»

«እናንተ የምታስቡት እንደዚህ ነው። ግን ሌሎቹ ደግሞ ሞኞች አይደሉም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁሉም እንደናንተው መሣሪያ ይታጠቃሉ፤ እናወድማቸዋለን ያላችኋቸውን በሙሉ እንድ ጊዜ ካወደማችሁ በኋላ ወደ ጀልባዎቹ ማን ቀድሞ ይመጣል ስትባባሉ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትታኮሳላችሁ። ከዚህም በተጨማሪ፣ አንዱንም ጀልባ በወደቡ ላይ ማሳረፍ የሚፈልግ ሀገር አይኖርም። እንሞክራለን በምትሉበት የትኛውም ሀገር ቴሌግራም ይሰራጫል። በተለይ እነዚያን ሁሉ ሰዎች ከጨፈጨፋችሁ በኋላ የትም ቦታ ብትሔዱ፣ ታሰራችሁ ለፈረንሣይ ባለሥልጣናት ትመለሳላችሁ። ከኮሶምቢያ ስለተመለስኩ የምናገረው ምን እንደሆነ ዐውቃለሁ። ያን የመሰለ አድራጎት ከፈጸማችሁ በኋላ ማንም ሰው እንደማያስጠጋችሁ በመሐላ ቃሌ እነግራችኋለሁ።»

«እሺ፣ ታዲያ እምቢ አልክ?»

«አዎ።»

«የመጨረሻው ቃልህ ይኸው ነው?»

«አዎ።»

«እንግዲህ ብንሔድ ይሻላል።»

«አንድ ደቂቃ። ይህን ለጓደኞቼ ለአንዳቸውም እንዳታማክሩ።»

«ለምን?»

«ምክንያቱን፣ አስቀድሜ እኔ ልንግራችሁ፣ ይቃወማሉ። እፋችሁን ሊታበላሹ።»

«መልካም።»

«ይህን ውጥናችሁን ማቆም አትችሉም?»

«በዕውነት ፓፒዮ፣ አንችልም።»

«ምን እንደ ገፋፋችሁ ሊገባኝ አልቻለም። በቁም ነገር፣ ቀደም ብየ እንዳልኳችሁ ምንም እንኳ ዓመፁ ቢሰምርላችሁም ነፃነታችሁን መቀዳጀት አትችሉም።»

«እንደ እውነቱ ከሆነ የእኛ ዋናው ፍላጎት መበቀላችን ነው። እንተም የሚቀበላችሁ ሀገር አይኖርም አስካልከን ድረስ ወደ አንድ ጫካ አምርተን ቡድን በመፍጠር በዱር ውስጥ እንኖራለን።»

«ለቅርብ ጓደኛየ እንኳ ስለዚህ ጉዳይ እንደማላነሳ ቃል እገባለሁ።»

«በእንተ መተማመን እንደምንችል እናውቃለን።»

«ጥሩ። አንድ የመጨረሻ ነገር የስምንት ቀን ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እንድትሰጡኝ አፈልጋለሁ፣ ወደ ቅዱስ ዮሴፍ ደሴት ለመሔድ እችላለሁና። ይህ በሚደረግበት ወቅት በሮያሌ መቆየት አልፈልግም።»

«ደሴቶችን ለመቀየር የሚበቃህን ያህል ጊዜ እንሰጥሃለን።»

«ሐሳባችሁን ላስለወጣችሁ እንዳልቻልኩ አርግጠኞች ሆናችሁ? ከእኔ ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

አንድ ሌላ ዕቅድ ብንሞክርስ? ለምሳሌ አራት ጠመንጃዎች መስረቅ ከቻልን ሌሊት ጀልባዎች የሚጠበቀውን ዘበኛ ማጥቃት እንችላለን። አንድም ሰው ሳንገድል ጀልባ ይዘን መሔድ እንችላለን።»

«ሕይወንም። በጉዳዩ በጣም በጥልቀት አስበንበታል። ሕይወታችንን እንኳ መሥዋዕት አድርገንም ቢሆን፣ ዋናው ዓላማችን ብቀላው ነው።»

«በጣም ጥሩ፣ ከእንግዲህ ስለዚህ ጉዳይ መናገር አልፈልግም።»

«መልካም ዕድል ልትመኝልንም አትፈልግም?»

«አልፈልግም። እደግመዋለሁ፣ ይቅርባችሁ። እንደዚህ ከመሰለ የተደናገረ ዕቅድ የተሻሉ ዘዴዎች ሞልተዋል።»

«በድራችንን ለመመለስ መብት እንዳለን አላመንክበትም?»

«በሚገባ አንጂ፣ ግን ንጹሕ ሰዎችን በመግደል አይደለም። ደህና እደሩ።»

«ደህና እደር። ያልተወያየንበት እናስመስል፣ እሺ ፓፒ?»

«እሺ ጓደኞቹ።»

ሐውቲንና አርናውድ ከዚያ ሔዱ። የክርስቶስ ያለህ! ይህ ደግሞ እንዴት ዐይነት ጉድ ነው። የምን ዕብዶች ናቸው! እስካሁን ድረስ ሃምሣ ወይም ስድሳ ሰዎች አለድመዋል። በማጥቂያው ሰዓት ጊዜ ደግሞ አንድ መቶ ይደርሳሉ። በሶ[illegible] ቁልጭ ያለ ዕብደት ነበር። ከጓደኞቹ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ ማንም ያናገረኝ የለም። ስለዚህ እነዚያ ሁለት ኢሥረኞች ያደመት ከብጤዎቻቸው ደደቦች ጋር ብቻ መሆን አለበት። በእንደዚህ ዐይነቱ ነገር ውስጥ፣ ከዕውቀቹ አራዳዎች ማንም ሰው አይደባለቅም። ከዚህ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ፣ አድመኞቹ በሙሉ የጅምላ ነፍሰ - ገዳዮች መሆናቸው ነበር። እንደ እኛ ያለ ነፍሰ-ገዳዮችም አለን፣ ግን የእነርሱ ፍጹም የማይቀራረብ ነው።

ስለአርናውድና ሐውቲን የቀድሞ ሕይወት ታሪክ፣ አንዳንድ ጥያቄዎችን በተዘዋዋሪ መንገድ አቀረብኩ። አርናውድ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ ተከሶ፣ ዐሥር ዐመት አንኳ ለማያስቀጣው ወንጀል የዕድሜ ይፍታህ ጽኑ ኢሥራት ተፈርዶበታል። ይህን የፈረዱበትም፣ ከዓመት በፊት ወንድሙ አንድ ፖሊስ በመግደሉ አንገቱ እንዲቆረጥ ስለተደረገ፣ ከሱን የያዘው ዐቃቤ ሕግ የጥላቻ አመለካከት እንዲሰፍን የፈጠረው ዘዴ በወንድሙ ሞት ቂም ይዟል የሚል መነሻ ብቻ ነበር።

ሐውቲን ነፃነትን ፈጽሞ አያውቃትም። ዕድሜው ዘጠኝ ዓመት ከሞላ ጀምሮ ወህኒ ቤት ውስጥ አለ። ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ሞልቶት ከወጣት ጠባይ ማረሚያ ሊፈታና በባሕር ኃይል ሊቀጠር በዋዜማው ደግሞ አንድ ሰው ገደለ። ከለአምሮ ቁጥጥር ውጭ ሆኖ ነበር። ወደ ቬኔዙዌላ በመሔድ በአንድ ወርቅ ማዕድን ውስጥ ተቀጥሮ ሳለ ጠቀም ያለ ካሣ ለማግኘት ሲል አግሩን በፈንጅ ለመቁረጥ ዕቅድ ያወጣ ሰው ነው። ያ አግሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀደም ሲል በቅዱስ ማርቲን ደሪ ጠባይ ማረሚያ በተወጋቸው መርፌዎች ሳቢያ ሽባ ሆኖ ነበረ።

በዛሬው ጧት በመጠኑ አንድ አስበርጋጊ ድርጊት ታየ። በስም ጥሪ ወቅት አርናውድን፣ ሐውቲንንና የጓደኛየ የማቴዎስ ካርቡኔሪን ወንድም ዮሐንስን ጠሯቸው። እርሱም የሚሠራው ከወደቡ በታች በዳቦ ጋጋሪነት ስለሆነ ለጀልባዎቹ ቅርበት ነበረው።

ያለምንም ማብራሪያ ወደ ቅዱስ ዮሴፍ ሰደዷቸው። ለምን እንደሆነ ለማወቅ ሞክርኩ፣ ግን ከአቅም በላይ ሆነ። አርናውድ መሣሪያ በመጠበቅ አራት ዓመት ቆይቶ ነበር፣ ዮሐንስ ካርቡኔሪም በዳቦ ጋጋሪነት አምስት ዓመት ሆኖታል። የዱብ ዕዳ ነገር ሊሆን አይችልም። አንድ የነፈሰ ወረ ሞኖር አለበት፣ ግን ምን ዐይነት ወሬ? ከብደቱስ የቱን ያህል ይሆን?

ሦስቱን የቅርብ ጓደኞቼን፣ ማቴዎስን፣ ግራንዴንና ጋልጋኒን ለመጠየቅ ወሰንኩ። ማንኛቸውም ቢሆኑ ምንም ያወቁት ነገር የለም። ልክ እኔ እንዳሰብኩት፣ ሐውቲንና አርናውድ ያስባሰቡት ከዕውቆቹ አራዳዎች ወጣ ያልሆኑ ተራ አሥረኞችን ብቻ ነበር።

«ታዲያ ለምን ለእኔ ነገሩኝ?»

«ምክንያቱም የፈለገውን መሥዋዕትነት ቢጠይቅም፣ አንተ ለማምለጥ ወደ ኋላ እንደማትል ማንኛውም ሰው ያውቃል።»

«ግን በዚያ ዓይነቱ መንገድ አይደለማ።»

«ልዩነቱን ማመዛዘን አልቻሉም።»

«ወንድምህ ዮሐንስ እንዴት ነው?»

«ይህን ከመሰለው አድማ ውስጥ ለመደባለቅ እንዴት እንደተጃጃለ እግዚአብሔር ይወቀው።»

«ምናልባት ወሬ አቀባዩ በጉዳዩ ሳይኖርበት አለህበት ብሎት ይሆናል።»

በዚያን ዕለት ምሽት ጅራሶሎ የተባለ ሰው ተገደለ። በማርቲኒካዊው ሽሚዝ ላይ የደም ነጠብጣብ አገኙበት። ከዐሥራ አምስት ቀን በኋላ፣ አጅግ በተቀላጠፈ ምርመራና በወህኒ ቤት በሚገኝ አንድ ሌላ ጥቁር ምስክርነት፣ የልዩ ፍርድ ቤት ማርቲኒካዊው የጎሽ እረኛ በሞት እንዲቀጣ ፈረደበት።

ግራቨል የተባለ አንድ ሽማግሌ ገላ መታጠቢያ ቤት ውስጥ እንዳለሁ ወደ እኔ መጣ። «ፓፒ፣ ጅራሶሎን የገደልኩት እኔ ነኝኮ። ጥቁሩን ለማትረፍ ደስ ባለኝ ነበር፣ ግን አንገት መቀንጠሻው አስፈራኝ። ሊከፈል የማይቻል እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ነው። ሦስት ወይም አምስት ዓመት ብቻ የሚያሳስረኝ አንድ ዓይነት ዘዴ ማግኘት ብችል እናዘዝ ነበር።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«የተፈረደብህ ነህ?»

«ሃያ ዓመት::»

«ምን ያህሉን ጨርሰሃል?»

«ወሥራ ሁለት::»

«የዕድሜ ልክ እሥረኛ የምትሆንበትን አንድ ዘዴ ፈልግ::»

«እንዴት ላደርገው እችላለሁ?»

«ስለ ሁኔታው ላስብበትና ዛሬ ማታ እነግርሃለሁ::»

በዚያው ማታ ለግራቨል እንደዚህ አልኩት:: «አይሆንም:: ራስህን ተከሳሽ አድርገህ፣ በኋላ መናዘዝ አትችልም::»

«ለምን አልችልም?»

«የሞት ቅጣት አደጋ ያስከትልብሃል:: በብቸኛ ግዞት ከመማቀቅ ያለው አማራጭ መንገድ የዕድሜ ይፍታህ እሥረኛ መሆን ነው:: ስለዚህ ኑዛዜህን አድርግ:: አንድ ንጹሕ ሰው አንገቱን ሲቆረጥ ማየቱ አእምሮየን ጤና ነሣኝ በል:: የሚከላከልልህ አንድ ኮርሲካዊ ጠበቃ ምረጥ:: ማን እንደሚሆን እኔ በኋላ እነግርሃለሁ:: ግን ሁኔታውን ማቀላጠፍ ይኖርብሃል:: የጥቁሩን አንገት በጣም ፈጥነው እንደማይዶሩት ተስፋ አደርጋለሁ:: ቢያንስ ሁለት ወይም ሦስት ቀን ያቆዩት ይሆናል::

ኮሎና ከተባለ አንድ ዘበኛ ጋር በጉዳዩ ተወያየሁበትና አንድ የሚደነቅ ሐሳብ አካፈለኝ:- ግራቨልን ይገዜ ወደ ዋናው የወህኒ አዛዡ ፊት በመቅረብ እንደ ጠበቃ ሆኜ እንድቆምለት የጠየቀኝ መሆኑንና እርሱም የሚናዘዝ ከሆነ ይህ የጨዋ አድራጎት ከሞት ቅጣት ሊያድነው እንደሚችል መተማመኛ ሰጥቼ ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን መግባቴን፣ ግን ያም ቢሆን ወንጀሉ በጣም ከባድ ስለሆነ ለነሰ ቢባል የዕድሜ ልክ እስራት እንደሚጠብቀው በተጨማሪ ማስጠንቀቄን እንዳስረዳ ነበር ዘበኛው የመከረኝ::

ዕቅዱ ሠራ:: ግራቨል ጥቁሩን ከሞት አተረፈውና ወዲያውኑ ነፃ ተለቀቀ:: በሐሰት ከሳሹም የአንድ ዓመት እሥራት ቀመሰ፣ ሮበርት ግራቨልም የዕድሜ ልኩ እሥራት ተበየነበት::

ሁለት ወር አለፈ:: አሁን ነገሩ እብቅቶ ስለተረሳሳ፣ የሆነውን ድርጊት በሙሉ ግራቨል አወራልኝ:: ጅራሶሎ በዐመፁ ውስጥ ለመካፈል ተስማምቶ ዝርዝር ሁኔታውን ከሰማ በኋላ፣ በአርናውድ፣ ሐውቲንና ዮሐንስ ካርቡኔሪ ላይ ያሳብቅባቸዋል:: ሆኖም ሊያውቅ የቻላቸው ስሞች እነዚሁ ብቻ ነበሩ::

ከሱ በጣም ከባድ ቢሆንም፣ መጀመሪያ ዘበኞቹ አላመኑበትም ነበር:: ግን ሰላም ለመፍጠር ያህል አንድም ቃል፣ ምንም ጥያቄ፣ ምንም ነገር ሳያደርጉ ሦስቱንም እሥረኞች ወደ ቅዱስ ዮሴፍ ላኳቸው::

t.me/OLDBOOKSPDF

«ግድያውን ለመፈጸም ስላነሣሣህ ምክንያት ምን ብለህ ነገርካቸው?»

«የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዬን ስለሰረቀብኝ ነው አልኳቸው። ከእርሱ ፊት ለፊት እንደምተኛ ገለጽኩላቸው፣ ይህም ዕውነቴን ነበር፣ ሌሊት የገንዘብ መደበቂያ ቱቦየን አውጥቼ እንደ ትራስ ከምጠቀምበት ብርድ ልብስ ሥር ደበቅኩ። በአንድ ወቅት ሌሊት ወደ መጸዳጃ ቤት ሔጄ ስመለስ፣ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዬ የለችም። በዚያ አካባቢ እንቅልፍ ያልወሰደው አንድ ሰው ብቻ አለ፣ እርሱም ጅራሶሎ ነበር። ዘበኞቹም እምነውኛል፣ በመሆኑም ስለዓመፁ ነገር ማሳበቁን ፈጽሞ አላነሡብኝም።»

«ፓፒዮ! ፓፒዮ!» ብሎ አንድ ሰው ተጣራ። «የስም ጥሪ ነው!» አለ።

«አለሁ።»

«በተቻለ ፍጥነት ተሰናዳ። ጋደ ቅዱስ ዮሴፍ ልትሔድ ነው።»

«አ፣ እነኝህ አዛባዎች!»

ፈረንሣይ ውስጥ ጦርነት ስለ ተቀሰቀሰ አዲስ የሥነ ሥርዓት ደንብ አስከትሏል። በወህኒ አስተዳደር አገልግሎት ላይ ተመድቦ የሚገኝ ማንኛውም ባለሥልጣን አሥረኛ አስካመለጠው ድረስ ከሥራው እንዲወገድ፣ የማምለጥ ሙከራ አድርጎ የተያዘ ማንኛውም አሥረኛ በሞት እንዲቀጣ አዲስ ደንብ ወጥቷል። ሁኔታው የሚታየው ‹ነፃዎቹ የፈረንሣይ ኃይሎች› ከተባሉትና እናት ሀገራቸውን ከከዱ ሰዎች ጋር ለመቀላቀል ካለ ፍላጎት እንደ መነጨ ተደርጎ ነው።

ይቅርታ የማይደረግለት ጥፋት የማምለጥ ሙከራ ብቻ ነበር።

አዛዡ ፕሩሌም ከሁለት ወር ቀደም ብሎ ሔዷል። አዲሱንም ሰው አላውቃውም፤ ስለሆነም እዚያ ምንም ማድረግ የምችለው ነገር የለም። ጓደኞቼን ደህና ሁኑ አልኩ። ሁለት ሰዓት ላይ ወደ ቅዱስ ዮሴፍ የሚሔደው ጀልባ ላይ ወጣሁ።

የሊሴቴም አባት የቅዱስ ዮሴፍን ካምፕ ሰቆ ነበር። እርሱና ቤተሰቦቹ ከሳምንት በፊት ወደ ካየን ሔደዋል። አሁን አዛዡ ስሙ ዱቴን የተባለ የለሐቩር ቀበሌ ተወላጅ ነበር። ጀልባው መቆሚያ ላይ ተገናኘኝ።

«ፓፒዮ እንተ ነህ?»

«አዎ ጌታዬ!»

«የምትገርም ሰው ነህ» አለ ፋይሌን እያገላበጠ።

«ለምን እንደዚያ ትላለህ?»

«ምክንያቱም ፋይልህ በአንድ በኩል በጣም ሲበዛ አደገኛ ነህ ይልና በተጨማሪ በቀይ ቀለም በተጻፈ ማስታወሻ፣ ‹ዘወትር ለማምለጥ የሚዘጋጅ› ይላል። በሌላው ጎን መጨረሻው ገጽ ላይ ደግሞ፤ ‹በዐሣነባሪዎች ተከብባ የነበረችውን የቅዱስ ዮሴፍ ወህኒ ቤት አዛዥ ልጅ ከአደጋ ለማትረፍ የሞከረ› የሚል አለ። እኔም ሁለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ትንንሽ ሴቶች ልጅች አሉኝ ፓፒዮ። ልታያቸው ትፈልጋለህ?»

ዕድሜያቸው በግምት ሦስትና አምስት የሚሆናቸው በጣም ለስላሳ ቡናማ ጸጉር ያላቸው ሁለት ሕፃናች ነጭ ሌበስ ከለበሰ እንድ ወረብና ጥቁር ጸጉር ካላት እንዲት በጣም ቆንጆ ሴት ጋር አብረዋቸው ወደ ቢሮው ገቡ።

«ጥቅርዬ፣ የከርስትና ልጅሽን ሊሰቱን ከአደጋ ሊያተርፋት የሞከረው ሰው ይኸው ነውኮ!»

«አ፣ ለጨበጥህ» አለች ወጣቷ ሴት።

የአንድን አሥረኛ አጅ መጨበጥ፣ ማንም ሰው የማያደርገው ታላቅ ክብር ነበር። ለአንድ አሥረኛ ፍጹም እጅ አይዘረጋም። ልባዊ አክብሮቷ ስሜቱን ነካው።

«ያሊሰቱ ከርስትና እናት ነኝ። ከወላጆቿ ጋር በጣም ወዳጆች ነን። ታዲያ ለእርሱ ምን ልታደርግለት ነው ጥቅርየ?»

«በመጀመሪያ ወደ ካምፕ መሐድ ይኖርበታል» አላትና ወደ እኔ ዘወር ብሎ፣ «ከዚያም የምትመርጠውን ሥራ ለእኔ ትነግረኛለህ» አለ።

«አመሰግናለሁ ጌታየ! አመሰግናለሁ እመቤቴ! ግን ወደ ቅዱስ ዮሴፍ ለምን እንደ መጣሁ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ? ለእኔ የመሰለኝ ልክ እንደ አንድ ዐይነት ቅጣት ነው።»

«እኔ እስከማውቀው ድረስ የተለየ ምክንያት የለውም። ሮያሌ ያለው አዲሱ የወህኒ አዛዥ ታመልጥ ይሆናል በማለት ፈርዶ ነው።»

«ለዚያስ ከሆነ ልክ ነው።»

«አሥረኛ በሚያመልጣቸው ላይ ሁሉ ቅጣቱን ጨምረውባቸዋል። ከጦርነቱ በፊት የሚደርስብህ ቅጣት በአንድ ማዕረግ ዝቅ ማለት ነበር። አሁን ወዲያው ትገፈፍና መጨረሻው ችግር ላይ መውደቅ ይሆናል። ስለዚህ ለእርሱ ከሮያሌ ይልቅ ኃላፊነት ከማይመለከተው ከቅዱስ ዮሴፍ ብታመልጥ ይሻለዋል።»

«እዚህ የምትቆየው ለምን ያህል ጊዜ ይሆናል አዛዥ?»

«ወሥራ ስምንት ወር።»

«እስከዚያስ መጠበቅ አልችልም። ግን ወደ ሮያሌ ለመመለስ አንዳ ዐይነት ዘዴ እፈልጋለሁ፣ ስለዚህ በአንተ አይመካኝብህም።»

«አመሰግናለሁ» አለች ባልተቤቱ። «ይህንንም ማሰብህ በጣም ጨዋ ሰው በመሆንህ ነው። ማንቸውንም ነገር በእኛ ላይ ጣለው። በሚፈልግበት ወቅት ፓፒዮ አየመጣ ሊጠይቀኝ እንዲችል ለዘበኞቹ ከፍል ትእዛዝ አስተላልፍ የኔ ፍቅር።»

«እሺ ፍቅርዬ። ሞሐመድ ወደ ካምፕ ይወስድህና ለመመደብ የምትፈልግበትን ክፍል መምረጥ ትችላለህ ፓፒዮ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ግድ የለም። ከአደገኞቹ ኢሥረኞች ጋር መሆን አፈልጋለሁ።»

«ይኸ ችግር አይደለም» አለ አዛገሙ እየሣቀ። አንድ ማስታወሻ ጻፈና ለሞሐመድ ሰጠው።

የሲሴቱ የቀድሞ መኖሪያ ቤት የነበረውንና አዛገሙ ለመኖሪያና ለቢሮ የሚጠቀምበትን ከወደቡ አጠገብ የሚገኝ ቤት አልፈን ከወጣቱ ዐረብ ጋር ወደ ካምፕ አመራን።

የዘበኞቹ ክፍል ተጠሪ የነበረው ሰው ሞገደኛና አረመኔነቱ የተመሰከረለት አንድ ሽማግሌ ኮርሲካዊ ነበር። ፊሊሳሪ ይባላል።

«ተመልሰህ መጣህ ፓፒዮ። በጥሩም ሆነ በመጥፎ፣ ማን እንደ ሆንኩ ታውቀኛለህ። አምልጠህ ከተያዝክ ልክ እንደ ጥንቸል እገድልሃለሁና ማምለጥ የሚባል ጉዳይ ፍጹም እንዳትሞክር። በሁለት ዓመት ውስጥ ጡረታ ስለምወጣ አሁን ምንም ዐይነት ችግር አልፈልግም።»

«ኮርሲካውያን በሙሉ ጓደኞቼ መሆናቸውን ታውቃለህ። ለማምለጥ አልሞክርም ልልህ አልፈልግም፤ ግን አንተ ተረኛ በማትሆንበት ወቅት እንደሚሆን አረጋግጥልሃለሁ።»

«እንደዚያ ከሆነ ጥሩ ነው ፓፒዮ። ጠላቶች አንሆንም። ታውቃለህ፤ ወጣቶቹ ዘበኞች ኢሥረኛ ቢያመልጣቸው የሚከተላቸውን የቅጣት ሜና ለመሸከም አይከብዳቸውም ይሆናል። ለእኔ ግን እንደ ሚገደል ነው የሚቆጠረው። በእኔ ዕድሜና ጡረታ ለወጣ በተቃረብኩበት ወቅት - እሺ። ገበቶሃል። አሁን ወደ ተመደብክበት ሕንፃ ሒድ።»

ከሙቶ እስከ ሙቶ ሐያ ኢሥረኞች የሚኖሩበት ልክ ሮያሌ እንዳለው ዓይነት ሕንፃ ውስጥ ገባሁ። ፒየሮ ለፋም አዚያው አለ፤ እንደዚሁም አርናውድ፣ ሐውቲንና ዮሐንስ ካርቡኔሪም ነበሩ። የማቴዎስ ወንድም እስከሆነ ድረስ ከዮሐንስ ጋር መዳበል ነበረብኝ። ግን ዮሐንስ ከማቴዎስ ጋር አልነበረም። ከዚህም በተጨማሪ ከአርናውድና ሐውቲን ጋር የጀመረውን ጓደኝነት አልወደድኩለትም። ስለዚህ በቂ ሥፍራ ተውኩለትና ከካሪየር ወይም በሚታወቅበት ስሙ ከፒየሮ ለፋ ጎን መሆኑን መረጥኩ።

የቅዱስ ዮሴፍ ደሴት ከሮያሌ ይበልጥ ምድረ በዳ ነች፤ በአርግጥ ትንሽ ብትሆንም ቅሉ፣ ከርዝመቷ የተነሣ ትልቅ ትመስላለች። ካምፑ የሚገኘው ከደሴቲቱ ወገብ ላይ ካለው አምባ ሲሆን በላይኛው አምባ ላይ ደግሞ ወህኒ ቤቱ ነበር።

በየቀኑ ቀትር ላይ ለአዛገሙ ቤተሰቦች የሚያገለግለው ዐረብ በአንድ ትሪ ሥስት ሣህኖች ያመጣልኝና ከዚያ ቀን በፊት አምጥቶባቸው የነበሩትን ሣህኖች ደግሞ መልሶ ይወስዳል። የሲሴቱ ከርስትና እናት፣ ለራሷ ቤተሰቦች ከምታዘጋጀው ምግብ ላይ ለእኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

በሃሞት ትልከልኛለች።

እኔም ምስጋናዬን ለማቅረብ አሉድ አሉድ እየሉኩ አጠይቃታለሁ። ነዘሰት በኋላ እርሷንበማወራትና ከትንሹዬ ልጅች ጋር ስጫወት አውላለሁ።

ቡናማ ጸጉራቸውን እየደባበስኩ፣ የሰውን ልጅ መሐኝ ለማወቅ የቱን ያህል ከባድ እንደሆነ አሰላስላለሁ። እነዚያ ዕብድ ሰዎች በዕቅዳቸው ከጸኑ ይህን ቤተሰብ ለእንድ አሰቃቂ መከራ ሊዳርጉት ነው ማለት ነው። የድራሉ ጥቅማ በዘበኞቹ ላይ አምብዘም ዕምነት ስላላሳደረባቸው፣ ሌላው ቀርቶ አርናውድን፣ ሐውቲንንና ካርቡኔሪን ለመከላከል እንኳ አልተጨነቁበትም። የሆነ ጥንጭ እንዳልሰጣቸው ደግሞ ስለ ዓመፀ-መጠንሰስ ቀደም ሲል የማውቀው ነገር እንዳለ ማረጋገጥ ሊሆንብኝ ነው። የዘበኞቹ አመለካከት በዚያን ጊዜ ምን ይሆናል? የሚሻለው አፈን ብዘጋ ነው።

አርናውድና ሐውቲን እንደ ማኩረፍ ብለውኛል። በዚህ ዓይነት መቀጠሉም ለእኔም ይሻላል። እንከባበራለን፣ ግን ጓደኝነት የለንም። ዮሐንስ ካርቡኔሪ ግን፣ ጭራሹንም አያናግረኝም። ከአርሱ ጋር ባለመደበሌ አኩርፌ ነበር። የምንቀራረበው አራት ሰዎች ብቻ ነበርን። እኔ፣ ፒየሮለሳ፣ በቫዮሊን የሚጫወተው «ፓሪዴሮም» ሽልማት ሁለት ጊዜ ያሸነፈውና በየጊዜው ለረጅም ሰዓቶች እየተጫወተ የሚያሰለቸኝ ማርኬቲ፣ ከሲት ቀበሌ የመጣው ኮርሲካዊው ማርሶሪ።

ስለሁኔታው አልተናገርኩም፣ ግን በሮያሌ ስለከሸፈው ዓመፅ እዚህ ማንም የሚያውቅ አንደሌለ ተሰምቶኛል። ዕቅዶቻቸውን ለውጠው ይሆን? በደሴቱ ውስጥ ከሥራዎቹ ሁሉ የከፋው እነርሱ ተመድበውበት የነበረው ነበር። በባሕሩ እንድ የመዋኛ ኩሬ ለመገንቢያ የሚያገለግሉ ግዙፍ ቋጥኞችን እየጎተቱ ወይም ይሸከሙ ነበር ማለቱ ይሻላል። በቋጥኞች ዙሪያ ሰንሰለቶች ይጠመጠሙባቸውና ርዝመቱ ከዐሥራ አምስት እስከ ሐያ ያርድ የሆነ እንድ ሌላ ሰንሰለት ደግሞ ይንጠለጠልበታል። ሁለት እሥረኞች በደረታቸውና በትከሻቸው ዙሪያ ቀንበሮች አጥልቀው ጎንና ጎን ሲቆሙ አንድ ረጅም ሚንጣ ከተንጠለጠለው ሰንሰለት ቀዳዳ ውስጥ ይገባል። ከዚያም ልከ እንደ ቤት እንስሳ ሚንጣ እየጎተቱ ወደ ሚያደርሱበት ቦታ ይወስዳሉ። በፀሐይ ሐሩር ከፉኛ አድካሚውና ከባዱ ሥራ ይኸ ነበር።

አንድ ቀን ዙሪያውን ተሰብስበን እንደ ተቀመጥን ድንገት የጠመንጃ ተኩስ ተገጣጣ። ካርባይኖች፣ ሽጉጦች፣ ሁሉም በአንድነት ከወደቡ በኩል አስተጋቡ። በከርስቶስ! እነዚያ ዕብድ ሰዎች ነገሩን ጀምረውታል! ምን እየተደረገ ይሆን? ማን አሸንፎ ይሆን? ምንም ሳልነታነቅ ከፍል ውስጥ ተቀመጥኩ። ማንኛውም ሰው «ዓመፅ ነው!» በማለት ተስማማ።

«ዓመፅ? ምን ማለታችሁ ነው?» አልኩና ምንም ነገር እንደማላውቅ በይሉ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠየቅኩ።

ያን ዕለት ሺት፣ ዮሐንስ ካርቡኔሪ ወደ ሥራ አልሔደም ነበር። ፊቱ በጣም ፀሐይ ያበለዘው ከመሆኑም ሌላ አሁን ልክ እንደ ሞተ ሰው አመድ መስሎ ወደ እኔ መጣ። በለሆሳስ ድምፅ፣ «ዓመፁ ነውኮ ፓፒ» አለ።

ረጋ በማለት፣ «የምን ዓመፅ? እኔ የተረዳሁት ምንም ነገር የለም» አልኩ።

የካርባይኑ ተኩስ ቆጠለ

ፒየሮ ለፉ እየገሠገሠ ወደ ከፍሉ ውስጥ ገባ። «ዓመፅ ነበር፣ ግን የከሸፈ መስሎኛል። ምን ዓይነቶች የሞኝ ጥርቃሚዎች ናቸው! ፓፒዮ፣ ጩቤሆን አዘጋጅ። ከሚጨርሱን በፊት የቻልነውን ያህል ዘበኞች መግደል አለብን!» አለ።

«ልክ ነው! የቻልነውን ያህል እንግደል» ሲል ዮሐንስ ካርቡኔሪም ተስማማ። ቼዚሊያም ስለቱን መዘዘ። ማንኛውም ሰው ራሱን ባገኘው ነገር አስታጠቀ።

«የቅዠታም ጥርቃሚዎች አትሁኑ!» አልኩ። «እዚህ ያለነው ምን ያህል እንሆናለን?»

«ዘጠኝ።»

«ሰባቶቻችሁ መሣሪያዎቻችሁን ወዲያ ጣሉ። ዘበኛ ለመግደል እነሣለሁ የሚለውን የመጀመሪያ ሰው ራሴ እንድለዋለሁ። ሰውን ልክ እንደ አንድ ጥንቸል መግደል አልፈልግም። እናንተ እዚህ ነገር ውስጥ አላችሁበት?»

«የለንበትም።»

«አንተስ?»

«እኔም እንደዚሁ የለሁበትም።»

«አንተስ?»

«ስለ ሁኔታው አንድም ነገር አላውቅም።»

«ኧሺ። እዚህ ያለነው በሙሉ በአራዳው ዓለም ውስጥ ነን። ስለዚህ ቅንብር የሌለው ዓመፅ ከእኛ መሐል ማንም ሰው አንድም ነገር አያውቅም። ገባችሁ?»

«አዎ።»

«ማንም ሰው አንድ ነገር ዐውቃለሁ ብሎ ቢተነፍስ በደቂቃ ውስጥ ሟች ነው። ስለዚህ እናገራለሁ የሚል ቋንም ሞኝ ሰው ካለ ምንም ነገር አያተርፍም። መሣሪያዎቻችሁን ወደ ባልዲ ውስጥ ወርውሩ። ዘበኞቹ እሁኑኑ ወደ እዚህ ይመጣሉ።»

«ያሸነፉት ኢሥረኞቹ ከሆኑስ ምን እናደርጋለን?»

«ኢሥረኞቹ ከሆኑ፣ ድል አድራጊነታቸውን ለማምለጥ ይጠቀሙበት እንደሆነ እስከናረጋግጥ ድረስ እንጠብቅ። እንደማየው ከሆነ የሚያስከፍለው የደም ዋጋ በጣም ከፍተኛ ነው። እናንተስ ምን ይመስላችኋል?»

t.me/OLDBOOKSPDF

ዮሐንስ ካርቡኔሪን ጨምሮ ሁሉም ተስማሙ።

ተኩሱ እስካቆመ ድረስ አሥረኞቹ መሸነፋቸውን ቀደም ሲል ብረዳውም፣ ስለ ሁኔታው አልገለጽኩም። እነርሱ አሸንፈው ቢሆን ኖሮ ጭፍጨፋው አሁንም እየቀጠለ በሐዲ ነበር።

ዘበኞቹ ልክ እንደ አበደ የአውሬ መንጋ ሆነው፣ በቋጥኝ ጉተታ ቡድን ተሰማርተው የነበሩትን ሰዎች፣ በጠመንጃ ሰደፍ፣ በዱላና በአርግጫ እያጣደፉ ነጂቸው። ከዚያም በሚቀጥለው ሕንፃ ውስጥ አጎሯቸውና ወዲያውኑ ጌታሮች፣ ማንዶሊኖች፣ ቼዝ መጫወቻዎች፣ ዳማዎች፣ ፋኖሶች፣ ወንበሮች፣ በጠርሙስ የተሞሉ ዘይቶች፣ ስኳር፣ ቡና፣ ነጫጭ ዩኒፎርሞች፣ የተገኘውን ማናቸውንም ነገር እየዘከዘኩ ከመዘጊያው ውጭ ወረወሯቸው። ሕጋዊ ያልሆነውን ማንኛውንም ነገር ዘበኞቹ ወደ ውጭ አወጡ።

ሁለት የሽጉጥ ተኩሶች አስተጋቡ።

በካምፑ ስምንት ሕንፃዎች ነበሩ። በእያንዳንዳቸው ውስጥ ያለው ታሪክ ተመሳሳይ ነበር። ዘበኞቹ በፊት ለፊታችን አቋረጡና በስተቀኞችን ከሚገኘው ሰባተኛው «ሳጥን» ውስጥ ገቡ። እኛ ከመጨረሻው ነበርን። ዘጠኞቻችንም እያንዳንዳችን የየራሳችንን ቦታ ያዝን። እውጭ ከሚሠሩት ሰዎች ውስጥ አንድም ገና ተመልሶ የመጣ የለም። እስከ መጨረሻው ደንዝዘን ቆመናል። ማንም አይናገርም። ጉሮሮዬ ደርቆ ነበር። ማሰላሰል የቻልኩት ይህን ኢጋጣሚ በመጠቀም እንድ ምናምንቴ አንዳይተኩስብኝ ብቻ ነበር።

«ወደዚህ እየመጡ ነው» አለ ዮሐንስ ካርቡኔሪ እየተርበተበተ።

ካርባይኖቻቸውንና ሽጉጦቻቸውን እንደ ወደሩ ከሐያ የበለጡ ዘበኞች ተሸነድጉደው ገቡ።

«ለምን አስካሁን ገና አላወለቃችሁም? ምን እየጠበቃችሁ ኖሯል እናንተ እበቶች? ሁላችሁንም ልንገድላችሁ ነው። ፈጠን በሉ! ሬሣ ከሆናችሁ በኋላ የእናንተን ልብስ ማውለቅ አንፈልግም» ሲል ፊሊሳሪ አጓራ።

«ሚስተር ፊሊሳሪ»

«ከፍት አፍህን ዝጋ ፓፒዮ! እዚህ ይቅርታ አታገኝም። እያውጠነጠንክ የጾላትካት ትንሽ ጉዳይ በአሁኑ ወቅት እጅግ አስከፊ ሆናለች። እዚህ ያላችሁትም በሙሉ እንደ ገባችሁበት የታወቀ ነው።»

ደም የለበሱት ዐይኖቹ ፈጠዋል።

ፔዩሮ መናገር ጀመረ።

አቋርጪው ልናገር ቆረጥኩ። «አንተን መሣይ ኮርሲካዊ ንፁሕ ሰዎችን

t.me/OLDBOOKSPDF

ይገድሳል ብየ ማመን አልችልም። መተኩስ ትፈልጋለህ? እሽ ቀጥል። ግን ንግግር አያሻም። እኛ ይህን እንፈልግም። ቱኩስ። ግን ስለ ከርስቶስ ብለህ ቶሎ ተኩስ! ወንድ ነህ ብየ እገምትህ ነበር ፊሊሳሪ፣ ያውም ዕውነተኛው ኮርሲካዊ፣ ግን ተሳስቻለሁ። ያውም ከባድ ስሕተት። ስትተኩስ አንተን መመልከት እንኳ አልፈልግም። ጀርባየን አዞራለሁ። ሁላችሁም ጀርባችሁን አዙሩላቸው፣ ሊገሉን ሲሉ ነው የተኮሰንባቸው እንዳይሉ።»

አንድ ሰው ሳይቀር ጀርባዎቻችንን ስናዞር፣ ዘበኞቹ ፈዝዘው ቀሩ፣ ምክንያቱም በኋላ እንደተረዳሁት፣ ቀደም ሲል በአንደኛው ከፍል ውስጥ ፊሊሳሪ ሁለት ምስኪን ሰዎች ገድሎ ነበር።

«ሊላ የምትለው ትርፍ ነገር አለ ፓፒዮ?»

አሁንም ጀርባየን እንዳዞርኩ፣ «ዓመፅ ስለምትሉት ታሪካችሁ አላምንበትም። ሰምን ዓመፅ ይደረጋል? ዘበኞችን ለመግደል? ከዚያም አምልጦ ለመሔድ? ወዴት መሔድ ይቻላል? እኔ ስለማምለጥ ልምድ ያለኝ ሰው ነኝ፣ ኮሎምቢያን ከመሰለ ሩቅ ቦታ ደርሼ ተመልሻለሁ። ለነፍሰ ገዳይ ጥርቅሞች ጥገኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ሀገር ነው? አስቂ ስሙን ንገሩኝ። ዝም ብላችሁ አትበሳበሱ። እንደዚህ ከመሰለው ነገር ውስጥ የሚደባለቅ ሰው ምን ስም ሊያተርፍ ነው?»

«አንተ ላትሆን ትችላለህ፣ ግን ካርቡኔሪስ እንዴት ነው?» አልጠራጠርም እርሱ ገብቶበታል። ወደ ሥራ ከመሔድ ፈንታ ዛሬ ጧት አሞኛል ብሎ ሲያመለክት አርናውድና ሐውቲንን ደንቋቸው ነበር።

«የግምት ንግግር ነው» ብየ ከዚያም ዘወር አልኩ። «ግን ነገሩን ትደርስበታለህ። ካርቡኔሪ ጓደኛየ ነው። ከእኔ ስለ ማምለጥ በሙሉ ስለ ተረዳ፣ ምን መዘዝ እንደሚያመጣ በሚገባ ጥርት አድርጎ ያውቃል።»

በዚህ ነጥብ ላይ እንዳለን የወህኒ አዛዡ ደረሰ። ከውጭ ቆሞ ጠበቀ። ፊሊሳሪ ወደ ውጭ ሲወጣ አዛዡ ተጣራ።

«ካርቡኔሪ!»

«አቤት።»

«ወደ ጨለማው ግንብ ውሰዱት፣ ግን አሁን ረጋ በሉ፣ ማንገላታት የሚባል ነገር የለም። ማንኛውም ሰው ወደ ውጭ። የዘበኞቹ ኃላፊ ብቻ እንዲቆይ እፈልጋለሁ። አንድም ሰው እንዳይገደል። ያለ አንድ ልዩነት ማንኛውም ሲሠራ የተሰማራ እሥረኛ ወደ ካምፕ እንዲመለስ እፈልጋለሁ።»

አዛዡ፣ የእርሱ ምክትልና ፊሊሳሪ ሆነው ከአራት ዘበኞች ጋር ወደ ከፍሉ ውስጥ ገቡ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ፓፒዮ፣ በጣም ከባድ የሆነ ጉዳይ ተፈጽሟል» አለ አዛቡ። «የጠባይ መረሚያው ዋና አዛዥ እንደመሆኔ ሁሉ፣ አንድ በጣም ከባድ ሃላፊነት መወጣት አለብኝ። ግን የሚቀጥለውን እርምጃ ከመውሰዴ በፊት ትንሽ መረጃ አፈልጋለሁ። እንደዚህ በመሰለው አሳሳቢ ወቅት ከእኔ ጋር በግል መወያየቱ ዐላዋቂነት ይሆናል ብለህ እንደምትገምት ስለ ተገነዘብኩ ወደዚህ መጣሁ። ዘበኛው ዳከሎስ ተገድሏል፣ ከመሣሪያ ማምጫ ቤት ጠመንጃ ለመውሰድ ተሞክሯል። በእኔ አመለካከት አንድ ዓመፅ ተካሒዷል ማለት ነው። ያሉን ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ናቸው። አምንሃለሁ። የአንተስ አስተያየት ምንድነው?»

«ስማ ዓመፅ ቢሆን ኖሮ፣ ለምን እኛ አልተደባለቅንበትም? ለምን አልተነሸረንም? የተካፈሉት ምን ያህል ናቸው? እንደሚመስለኝ እነዚህን ሦስት ጥያቄዎች ለመመለስ እችላለሁ፤ ግን ዳከሎስ ተገድሎ መሣሪያውን ከተገፈፈ በኋላ ምን ያህል ሰዎች በድርጊቱ ውስጥ እንደ ተካፈሉ በቅድሚያ ማወቅ አለብኝ።»

«ሦስት።»

«እነማን ነበሩ?»

«አርናውድ፣ ሐውንቲንና ማርሰው።»

«መልካም፣ እንግዲህ ወደድከም ጠላህም ዓመፅ የሚባል አልነበረም።»

ፊሊሳሪ አቋረጠና፣ «ይኸ ውሸት ነው ፓፒዮ» አለ። «ይህ ዓመፅ ሊደረግ የታቀደው በሮያሌ ነበር። ጅራሶሎም ጠቁሞን ነበር፣ ግን አላመንነውም። አሁን እርሱ ያለው ሁሉም ነገር ትክክል መሆኑን ተረዳን። እንደ አቫንጉሊት አትጫወትብን ፓፒዮ»

«ስማ፣ ዓመፅ ቢሆን ኖሮ ሃላፊነቱን የምንይዘው እኛ ነበርን እንጂ እነዚያ ጸርጻራዎች አይደሉም።»

«ማንም የተካፈለ ሰው የለም ብለህ ልትነግረኝ እየሞከርክ ነው? አላምንም።»

«መልካም፣ ታዲያ የቀሩት ሰዎች ምን አደረጉ? ከእነዚያ ከሦስቱ ተጨማሪ አንድ ዝረ ያለ ሰው አለ? ወደ ዘበኞቹ ከፍል አንድ ሰው? በቅዱስ ዮሴፍ ያሉት ጀልባዎች ስንት ናቸው? እንድ ባለሞተር ጀልባ። ታዲያ አንድ ጀልባ ለስድስት መቶ ሰዎች ሊጓጓ ይችላል? ይኸ ሞኝነት ነው፣ አይደለ? ያውም ሰዎችን በመግደል ለማምለጥ መሞከር? ሐያ ሰዎች እንኳ አምልጠው ይሔዳሉ ተብሎ ቢገመት፣ ታስረው እዚሁ ይመለሳሉ። አዛዥ፣ ጭፍራዎችህ ምን ያህል ሰዎች እንደገደሉ ባላውቅም፣ እርግጠኛ ነኝ የተገደሉት በሙሉ ንጹሆች ናቸው። አሁን ደግሞ እኛን የተረፍነውን ጥቂቶቻችንን ብታስቃዩን፣ እሞ ያን ጊዜ አንድ ዓመፅ ይቀሰቀስ ይሆናል። የተስፋ መቁረጥ ዓመፅ ደግሞ የጅምላ ግድያ ነው። ገደልን ወይም ተገደልን ዘበኞችም ሆን አሥረኞች ሁላችንም አንድ ላይ እናልቃለን። ሚስተር ዱቴን፣ ከአንጀቱ ምርር ብየ ነው የምነግርህ። ምን እንደምናስብ እናልቃለን። ሚስተር ዱቴን፣ ከአንጀቱ ምርር ብየ ነው የምነግርህ። ምን እንደምናስብ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማወቅ ወደዚህ መምጣትህ ተገቢ ይመስለኛል። ከእንግዲህ ግን እባካችሁ ተዉን።»

«በዓመፁ ተካፍለው የነበሩትስ?» አለ ፊሊሳሪ እንደገና።

«እነርሱን መፈለግ የአናንተ ጉዳይ ነው። ምንም የምናውቀው ነገር የለም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ለአናንተ ምንም የምንጠቁመው ነገር የለም። እደግመዋለሁ ይህ መላ የሌለው የልጆች ቀልድ እንጂ የእኛ ዓይነት ሰዎች ሥራ አይደለም።»

«ሚስተር ፊሊሳሪ፣ ተጨማሪ ማሳለቢያ እስኪሰጥ ድረስ ወደ ውስጥ አስገብታችሁ እንድታቆያቸው። ከበሩ ላይ ሁለት ዘበኞች እንዲቆሙ፣ ማንገላታት የለም፣ የሰዎቹ ንብረት የሆነውንም መንካት የለም። እንሒድ።» ከሌሎቹ ዘበኞች ጋር አዛቦ ወጥቶ ሒደ።

የኢየሱስ ያለህ! አልቆልን ነበር። ፊሊሳሪ በሩን በመዝጋት ላይ እንዳለ፣ «ኮርሲካዊ በመሆኔ በጣም ዕደለኛ ነህ» አለኝ።

አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እኛ ሕንፃ ካሉት ሰዎች ብዙዎቹ ተመለሱ። ዐሥራ ስድስቱ ጠፍተው ነበር። ዘበኞቹ ከመጣደፋቸው የተነሣ ወደ ተመሳሳይ ሕንፃዎች ወስደው ቆልፈውባቸው ኖሯል። ለመጨረሻ ጊዜ ሁሉም ሰው ወደየራሱ ምድብ ቦታ ከተመለሰ በኋላ እነዚህም ሰዎች ከመስክ ሠራተኞቹ ጋር አብረው ስለነበሩ የተደረገው ምን እንደሆነ ተረዳን።

ከቅዱስ ኢትየን የመጣ አንድ ሌባ በሹክሹክታ ታሪኩን በሙሉ ነገረኝ።

«ትዕይንቱ እንደዚህ ነው ፓፒዮ፣ በግምት አንድ ቶን የሚመዝን እንድ ቋጥኝ ከአራት ሙዮ ያርድ በላይ ከሆነ ርቀት እንትትት ነበር። የምንጠቀምበት መንገድ በሚገባ የተስተካከለ ሲሆን፣ ከአዛቦ ቤት በግምት በሃምሳ ያርድ ርቀት ላይ ከሚገኝ እንድ የውሃ ጉድጓድ ስንደርስ በኮከነት ዛፎች ጥላ ሥር ዘወትር እንደቆምን እናርፋለን። የጉዟችን ግማሽ ነበር። ስለሆነም፣ እንደ ተለመደው ቆምንና በአንድ ትልቅ ባልዲ የመጠጥ ውሃ ቀዳን። አንዳንዶቹ ሲጠጡ፣ ሌሎቹ በጭንቅላቶቻቸው ላይ የጠመጠሟቸውን መሐረቦች አራሱ። ዕረፍቱ እንደተለመደው ዐሥር ደቂቃ ገደማ ስለሚቆይ፣ ዘበኞችን ከጉድጓዱ ጫፍ ተቀምጠ ነበረ። አርናውድ ከጀርባው በኩል ሲመጣ፣ መለየውን አውልቆ ግንባሩንና ራሱን በአንድ ትልቅ መሐረብ ይጠርጋል። አርናውድ አንድ ዶማ ይዞ ነበር ግን ወደ ላይ ቀጥ ስላላደረገው ዘበኛውን ለማስጠንቀቅ ማንም ሰው አላሰበም። ከመቅጽበት ዶማውን በሹሉ ጫፍ በኩል በቀጥታ በዘበኛው መሐል አናት ቁልቁል ሰቀቀበት። የዘበኛው ጭንቅላት ለሁለት ተገመሰና ምንም ድምፅ ሳያሰማ ለጥ ብሎ ተዘረጋ። ወዲያው ቦታ አመቻችቶ የሚጠባበቀው ሐውቲን ካርባይኑን አነሣ፣ ማርሶው ዝናሩንና ሽጉጡን። ማርሶው ሽጉጡን በእጁ እንደጨበጠ ወደ ሠራተኞቹ አቅጣጫ ዘረና፣ «ይህ ዓመፅ ነው። ማንም ከእኛ ጋር የሚተባበር እጁን ያንሣ አለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዙፋኑ ያጮኸ በኩል አንድም ድምፅ አልነበረም፣ ከሠራተኞቹም ውስጥ አንድ ሰው ሊከተል አልተንቀሳቀሰም። አርናውድ ወደ እኛ እየተመለከተ፦ ‹‹እናንተ ፈሪዎች፣ ምን ዓይነት ቆራጥ ወንዶች መሆናችንን እናሳያችኋለን!›› አለ። ካርባይኑን ከሐውቲን እጅ እየነጠቀና ሁለቱም ወደ አዛዡ መኖሪያ ቤት አቅጣጫ ሮጡ። ማርሶው ወደ አንድ በኩል እየገፈገ። ትልቁን ሽጉጥ በእጁ ይዞ ስለነበር፣ ‹‹እንዳትንቀሳቀሱ! አንድ ቃል፣ አንድ ትንፋሽ የለም። እናንተ አረቦቹ ደግሞ ወደ መሬት ተንበርከኩ›› ሲል አዘዘ። አለሁበት ቦታ ሆኜ ማንኛውንም ነገር ማየት እችል ነበር።

‹‹አርናውድ የአዛዡን መኖሪያ ቤት ደረጃ በመውጣት ላይ እንዳለ ነበር አዚያ የሚያገለግለው አረብ ሁለቱን የአዛዡን ልጆች፣ አንደኛዋን በእጁ ይዞ፣ ሌላዋን በክንዱ ታቅፎ መዝጊያውን በመክፈት ላይ የነበረው። ሁለቱም ሰዎች በድንጋጤ ተዋጡ። አረቡ አርናውድን ለመምታት ታገለ። አርናውድ ሊገድለው ሲል አረቡ በፊት ለፊቱ ሕፃኗን እንደ ጋሻ መከተበት። ይህ ሁሉ ሲሆን አንድ ድምፅ አልነበረም። አርናውድ አምስት ወይም ስድስት ጊዜ በአረቡ ላይ በተለያዩ አቅጣጫዎች አነጣጠረበት። አረቡም በእርሱና በጠመንጃው መካከል ሕፃኗን እየከለለበት ነበር። ከዚያም አርናውድ የአረቡን ሱሪ የታችኛውን ጫፍ ያዘበት። አረቡ ለመውደቅ ሲንገዳገድ ሕፃኗን አርናውድ ወደ ያዘው ጠመንጃ ወረወራት። አርናውድ ሚዛኑን አጥቶ ሊወድቅ ሲል ደግሞ ሐውቲን የአረቡን ባት ጨመደደ። አርናውድ፣ አረቡና እንደኛዋ ሕፃን ሁሉም በአንድነት ተያይዘው ወደቁ። ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፅ አሰተጋባ። በቅድሚያ የሕፃኖቹ ጫጫታ፣ ከዚያም ዐረቡ፣ ከዚያም የአርናውድና ሐውቲን የስድብ መዓት ወረደ።

‹‹ጠመንጃው መሬት ላይ እንደወደቀ ነበር። በመጀመሪያ ያነሳው አረቡ ሲሆን፣ የያዘው ግን በአፈሙዙ በኩል በግራ እጁ ብቻ ነበር። ሐውቲን እንደኛ እግሩን ያዘው። አርናውድም የቀኝ ክንዱን ጨመደደና ጠመዘዘው፣ ይሁንና ካርባይኑን ከመገጠቃቸው በፊት አረቡ የዐሥር ያርድ ርቀት ያህል አሻግሮ ወርውሮት ነበር።

‹‹ሦስቱም ያን ተከትለው በመሮጥ ላይ እንዳሉ፣ ቅጠል በመጥረግ ላይ የነበረውን የእሥረኞች ቡድን ከሚቆጣጠር አ.ድ ዘበኛ የተተኮሰች የመጀመሪያዋ ጥይት ድምፅ አስተጋባች። አዛዡም በመስኮት በኩል ብቅ አለና መተኮስ ጀመረ፣ ግን አረቡን እመታለሁ ብሎ ስለፈራ የሚያነጣጥረው ካርባይኑ ከወደቀበት ቦታ ላይ ነበር። አርናውድና ሐውቲን፣ የባሕሩን ጠርዝ ተከትላ የምትገኝ አንዲት መንገድ ይዘው ወደ ካምፑ አቅጣጫ ፈረጠጡ። ሐውቲን በዛለው ባቱ ምክንያት እንደ ልብ መፍጠን ስላቃተው፣ ወደ ውሃው ከመድረሱ በፊት ተኩሰው ገደሉት። አርናውድ በዘበኞቹ የመቀኛ ኩሬና አሁን በመሠራት ላይ ባለው ግንዳ መካከል አፈተለከ። ቦታው ዘወትር ጭነባሪዎች የሚርመሰመሱበት ነበር። ሌላ አንድ ዘበኛ ከፊቱ ብቅ ሲልበት ከአንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉልቅ ቋጥኝ ኋላ ተደበቀ።

«አጅህን ሰጥተህ ሕይወትህን አትርፍ» ሲል ዘበኛው ጮኸ።

« ብፍጹም አለ አርናውድ። ብአሣነባሪዎች ብበላ ይሻለኛል። ስለዚህ ሊላው ቢቀር አስቀያሚ ፊቶቻችሁን ዳግመኛ አላይም።›

«ይህን ተናግሮ ወደ ባሕሩ ዘሎ ገባና በዓሣ ነባሪዎቹ መካከል ተመሰገ። ዘበኞቹ ወዲያው ተኩሣቸውን አከታተሉ፤ አርናውድም እየራቀ ሔደ። ዓሣነባሪዎቹ ሲጠልፉት ውሃው እደረቱ አልደረሰም ነበር። ከውሃው በላይ በከፈል የወጣ አንድ ዓሣ ነባሪ ከፊት ለፊቱ እየከነፈ ሲመጣ ለማስፈራራት ቡጢ ሲሰነዝር ዘበኞቹ አይተውታል። ሌሎቹም ዓሣነባሪዎች ዙሪያውን ከበው በየአቅጣጫው ጎተቱት። አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ደብዛው ጠፋ።

«ዘበኞቹ በጠቅላላው አነሰ ቢባል አንድ መቶ ጥይቶች ተኩሰዋል። አንድ ዓሣነባሪ ተገድሎ ስለነበር፤ ሆዱን ወደ ሰማይ እንደገለበጠ እስከ ባሕሩ ዳር ተንሣፈፈ። ዘበኞቹ ከሁሉም አቅጣጫ መሰባሰብ እንደጀመሩ፤ ማርሶው ሽጉጡን ወደ ውሃው ጉድጓድ ውስጥ በመወርወር ነፍሱን ለማትረፍ ሞከሮ ነበር። ግን አረቦቹ ወዲያው ደርሰውበት በቆመጥ እየደበደቡ፤ በጡጫና በእርግጫ እያካለቡ ወደ ዘበኞቹ ስመውሰድ፤ ዓመፁ ውስጥ እንደነበረበት አጋለጡት። ምንም እንኳ ዙሪያውን ተከብቦ እጆቹን ወደላይ እንዳደረገ ቢሆንም ዘበኞቹ ተኩሰው ገደሉት። ከዘበኞቹ አንዱ ለመጨረሻ ጊዜ ሊያሰናብተው፤ ልከ እንደ ዱላ ካርባይኑን በአፈሙዙ ጫፍ ያዘና በሰደቃ ጭንቅላቱን ፈጠፈጠው።

«የሐውቲንን አሟሟት በተመለከተ ደግሞ ዘበኞቹ የካርባይኖቻቸውን ጥይቶች ጨርሰው አራግፈውበታል፤ ሠላሳ ሰዎች እያንዳንዳቸው ስድስት ጊዜ ሲተኩሱ ክአንድ መቶ ሃምሳ ጥይት በላይ ተርከፍክፎበት ነበር። በፈሊሳሪ የተገደሉት ሁለቱ ያልታደሉ ሥሪኞች፤ አርናውድን ለመከተል ከጀመሩ በኋላ አቅማምተው የተመለሱ ናቸው ብለው አረቦቹ ስለ ነገሩባቸው ነበር። ይህም ሙሉ በሙሉ ዐይን ያወጣ ውሸት ነበር፤ ምክንያቱም ተባባሪ ከሆነውም ሆነ ካልሆነው ወገን ማንም ሰው ንቅንቅ አላለም ነበር።»

በተለያዩት ሕንፃዎቻችን ውስጥ ከታጎርን ዛሬ ሁለተኛ ቀናችን ነው። ወደ ሥራ የሔደ ማንም ሰው የለም። በበሩ ላይ ያሉት ዘበኞች የሚቀያየሩት በየሁለቱ ሰዓት ነበር። በሕንፃዎቹ መካከል ደግሞ ተጨማሪ ዘበኞች አሉ። ከአንዱ ሕንፃ ወደሚቀጥለው ለመነጋገር ካለመቻላችንም በላይ፤ በመስኮት እጠጉብ መቅረም ተከልክለናል። ግቢውን በፍርግርጉ በር በኩል ለማየት የምንችለው፤ በተርታ ያሉትን ሁለቱን የተንጠልጣይ አልጋዎች ረድፍ የሚያካፍለው መተላለፊያ አንድ ጎን በኩል

t.me/OLDBOOKSPDF

በመጫም ብቻ ነበር። ማጠናከሪያ ኃይል ከሮያሌ ተልኳል። እንድ ኢሥረኛም ሆነ ቁልፍ ያሸ አረብ ወደ ውጭ መውጣት አይፈቀድለትም። ሁላችንም ተቆልፎብን ነበር። አልፎ አልፎ ዕርቃኑን የቀረ አንድ ሰው በከፍተኛ ደረጃ ወደሚጠበቁት ክፍሎች ሲወሰድ ይታያል። ከጎን በኩል ባሉት መስኮቶች ዘበኞቹ ያለማሰለስ ወደ እኛ ይመለከታሉ። በመዘጊያው በኩል ቁመው የሚቆዩት ለአጭር ጊዜ ሲሆን፣ ፍጹም አይቀመጡም፣ ጠመንጃቸውንም ከእጃቸው አይለዩም።

አምስት አነስተኛ ቡድን ፈጠርንና ጨዋታ ልንሞክር አሰብን። ከፍተኛ ጨዋታ አልነበረም፡- ያ በጣም ብዙ ሚጫታ ያስከትላል። ማርኬቲ ከቪትሆቨን ሙዚቃ አንድ ስንኝ ለመጫወት ሲጀምር፣ አንድ ዘበኛ እንዲያቆም አዘዘው።

«ሙዚቃ የለም! ሐዘን ላይ ነን።»

በ«ሆፕኑ» ውስጥ ብቻ ሳይሆን ካምፑን በጠቅላላው አንድ ያልተለመደ ፀጥታ ሠፈነበት። ቡና የለም፤ ሾርባ የለም። ጧት አንድ ቁራጭ ዳቦ፤ በቀትር አንዲት ጣሳ የበሬ ሥጋ፣ ለራት እንደዚሁ አንዲት ጣሣ የበሬ ሥጋ፣ ለአራት ሰዎች ይሰጠን ነበር። ከእኛ ንብረት ውስጥ ምንም ነገር ስላልወደመብን ቡናና ትንሽ ምግብ ማለት ቅቤ፣ ዘይትና ዱቄት፣ ወዘተ... ነበረን። ሌሎቹ «ሣጥኖች» ምንም ነገር የቀረላቸው አልነበረም። ቡና ለማፍላት መፀዳጃ ቤት ውስጥ እሳት ማንደድ ጀመርን፤ ግን አንድ ዘበኛ እንዳያየን ጥንቃቄ አደረገን።

ኒስተን በሚል ስም የሚጠራ ከማርሴይ የመጣ አንድ ሽማግሌ ኢሥረኛ ቡና ሊሸጥ አፈላ። «እሳቱን ለማጥፋት ከፈለግህ ወደ ውስጥ ግባና ራስህ ሞክረው» ብሎ ዘበኛ ለመገለፍ ወኔ ያገኘው እርሱ ነበር። ዘበኛው በመስኮት በኩል ተኮሰ። ቡናና እሳት ወዲያው አልም አሉ።

ኒስተን ባቱ ላይ ተመታ። በጣም ከመፍራታችን የተነሣ ሁላችንም ሊተኮስብን ነው ብለን በመሥጋት በወለሉ ላይ እየዘለልን ተዘረጋን። ፊሊሳሪ አውንም በጥበቃ ላይ የተመደቡት ዘበኞች ታላፊ እንደመሆኑ እየሮጠ በአራት ዘበኞች ታጅቦ መጣ። የተኮሰው ሰው ፈረንሣዊ ነበር። ፊሊሳሪ በኮርሲካዊ ቋንቋ ሰደበው፤ እርሱ ግን አንድም ቃል አልገባውም ነበር። ማለት የቻለው፣ «አልገባኝም» ብቻ ነበር።

ወደ ተንጠልጣይ አልጋዎቻችን ተመለስን።

የኒስተን ባት እየደማ ነበር። «መቁሰሌን እንዳትነግሯቸው። ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ወዲያውኑ ሊጨርሱኝ ይችላሉ» አለ።

ፊሊሳሪ ለማርኬቲ በኮርሲካዊ ቋንቋ፣ «ሐኪሀ ቡናህን አፍላ። ምንም አትሆንም» ሲል ነገረው። ከዚያም ወጥቶ ሐደ።

ኒስተን ዕድለኛ ነበር። ጥይቷ ባቱ ውስጥ አልቀረችም። በታፋው ጡንቻ ሥር

t.me/OLDBOOKSPDF

ጉበታ ወደ ላይ ርቃ በመታፋት ቮልካ ሐዳለች። በጥጥና በጨርቅ ሲታፈን ደሙ ቆመለትና በሆምጣጤ በተነከረ ፋሻ ታሰረለት።

«ፓፒዮ፣ ወዲህ ና!» ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ስለነበር፣ ጨለማል። «አዛዡ ሊያዩህ ይፈልጋሉ።»

«ራሱ ወደዚህ እንዲመጣ ንገረው እንጂ እኔ አልሔድም።»

«እምቢ አልክ?»

«አዎ እምቢ ብያለሁ።»

ጓደኞቹ መጡና በዙሪያየ ልክ እንደ ቀለበት ከብበውኝ ቆሙ። ዘበኛው በተዘጋው በር በኩል ይናገራል። ማርኪቲ እርሱ አለበት ድረስ ሔደና፤ «የወህኒ አዛዡ ካልመጣ በስተቀር ፓፒዮን ወደ ውጭ እንዲወጣ አንፈቅድለትም» አለው።

«ግን እንድጠራው የላኸኝ የወህኒ አዛዡ ነውኮ።»

«ራሱ እንዲመጣ ንገረው።»

ከአንድ ሰዓት በኋላ ሁለት ወጣት ዘበኞች በበሩ ብቅ አሉ። የወህኒ ቤት አዛዡን የሚያገለግለውና ዕመፁን በመቅጨት ጌታውን ከውርደት ያዳነው አረብ ከእነርሱ ጋር አብሮ ነበር።

«ፓፒዮ፣ እኔ ሞሐመድ ነኝ። አዛዡ ሊያዩህ ይፈልጋሉ። ራሳቸው መምጣት ስላልቻሉ ነው እኔን የላኩኝ»

«ፓፒዮ፣ ሰውየው ጠመንጃ ይዟል» አለ ማርኪቲ። የከበቡኝን ሰዎች ሰነጣጠቅኩና ወደ በሩ ሔድኩ። በእርግጥም ነበር፤ ሞሐመድ አንድ ካርባይን ይዟል። ይህ በዕውነት የሚያስገርም ነገር ነበር። አንድ ኢሥረኛ በግልጽ ካርባይን መታጠቅ!

«ና» አለኝ አልጀሪያዊው። «አንተን ልጠብቅ ሰል ነው የመጣሁት።» እኔ አላመንኩትም።

«ና እንጂ።»

ወደ ውጭ ወጣሁ። ራሱ ሞሐመድ ከእኔ ጎን ቆመ፤ ሁለቱ ዘበኞች በስተጀርባ ቆሙ። በካምፑ መግቢያ ያለውን የዘበኞች ከፍል በማለፍ ላይ እንዳለን ፊሊሳሪ፣ «ፓፒዮ፣ በእኔ ምንም ቅሬታ እንደማትይዝብኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አለ።

«አዬ አልይዝም። ወይም በእኛ «ሳጥን» ያለ ማንም ሰው ቢሆን። ስለ ሌሎቹ ግን አላውቅም።»

ወደ አዛዡ ቤት ቁልቁል ወረድን። በወደቡና በቤቱ አካባቢ ድብዝዝ ያሉ የጋዝ ፋኖሶች ይበሩባቸዋል። በመንገዶቹን ላይ ሞሐመድ አንድ ፓኮ ትምባሆ ሰጠኝ። በሁለት የጋዝ ፋኖሶች ብርሃን ወለል ካለ አንድ ከፍል ውስጥ ስንገባ፣ የሮያሌ ዋና አዛዥና ምክትሉ፣ የቅዱስ ዮሴፍ ዋና አዛዥ፣ የማዞት ወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥና የቅዱስ ዮሴፍ

t.me/OLDBOOKSPDF

ምክትል አዛዥ ተቀምጠው ነበር።

አራት አረቦች በጥበቃ ሥር እንዳሉ ከውጭ በኩል ተመለከትኩ። ከእነርሱ ውስጥ ሁለቱ በምርመራ ላይ ከሚገኙት የቀን ሠራተኞች ቡድን ባልደረባ መሆናቸውን አስታወስኩ።

«ይቺው ፓፒዮ» አለ ሞሐመድ።

«እንደምን አመሸህ ፓፒዮ» አለ የቅዱስ ዮሴፍ ዋና አዛዥ።

«ደህና፣ እንደምን አመሸህ።»

«እባክህ ተቀመጥ።»

ከሁሉም ፊት ትይዩ በመሆን ተቀመጥኩ። የከፍሉ መዝገያ በወጥ ቤቱ በኩል ክፍት በመሆኑ የሊሴቱ ከርስትና እናት ሰላምታ ስትሰጠኝ ተመለከትኩ።

የሮያሌ ወህኒ አዛዥ ንግግሩን ከፈተ። «ፓፒዮ፣ አዛዥ ዱቴን ከሁሉም ሰው መሙን የሚችለው አንተን ብቻ እንደሆነ ገልጿል። እኔ የማውቅህ ደግሞ እደገኛ ሰው መሆንህን ከሚገልጹት በግል ማኅደርህ ውስጥ ካገኘኋቸው መረጃዎች ብቻ ነው። ግን እንዚያን ተወት አድርጌ የባልደረባዮን የዱቴንን ማምት መቀበል አመርጣለሁ። ድርጊቱን ለመመርመር አንድ ኮሚሽን አሁን ወደዚህ እንደሚላክና ኢሥረኞቹ ሙሉ የሚያውቁትን እንዲናገሩ እ[illegible]ሚጠይቅ እናውቃለን። በተጨማሪ፣ አንተና [illegible] ሴሎች ሰዎች በኢሥረኞቹ ላይ ከፍተኛ ተደማጭነት እንዳላችሁና የእናንተን ምክር እንደሚቀበሉም እናውቃለን። አሁን የምንፈልገው ስለ ዓመፁ ያለህን አመለካከትና ጠቃሚ ናቸው ስለምትላቸው አንዳንድ መረጃዎች እንድትነግረን፣ እንደዚሁም ጓደኞችህ ምን ያህል ሊተባበሩን እንደሚችሉ እንድትገልጽልን ነው።

«ጌታዬ፣ እኔ የማውቀው ምንም ነገር የለም። ሌሎቹም እንዲተባበሯችሁ ለማግባባት ችሎታ የለኝም። አሁን ባለው ሁኔታ ላይ አንድ ከባድ ምርመራ ቢደረግ፣ ሁላችሁም ችግር ላይ እንደምትወድቁ መገመት አችላለሁ።

«ምን ማለትህ ነው ፓፒዮ? በቅዱስ ዮሴፍ የተነሣውን ዓመፅ የገታኸው እኔና ባልደረቦቼ ነን እኮ?»

«ምናልባት አንተ በሐቅ ሠርተህ ይሆናል፣ የሮያሌ ባለሥልጣኖች ግን እንደዚያ አላደረጉም።»

«ራስህ አብራራው!» ሲሉ ሁለቱ የሮያሌ ወህኒ ቤት አዛዦች እንደመነሣት አሉና ተመልሰው ተቀመጡ።

«ሁኔታውን ዓመፅ ነው እያላችሁ በይፋ መናገር ከቀጠላችሁ ራሳችሁ ትጠየቁበታላችሁ። የእኔን ድርድሮች የምትቀበሉ ከሆነ ከፊሊፊሪ በስተቀር ሁላችሁንም አተርፋችኋለሁ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ድርድሮችህ ምንድን ናቸው?»

«በቅድሚያ፣ ከነገ ጧት ጀምሮ ሁኔታዎች እንደተለመደው ወደነበሩበት እንዲመለሱ ፍቀዱ። ለመርማሪው ኮሚሽን ምን እንደምንናገር የምንወስነውና ሌሎቹን ለማግባባት የምንችለው፣ መወያየት ሲደረግ ብቻ ነው። በዚህ ትስማማላችሁ?»

«አዎ» አለ ዱቴን፤ «ግን እኛን ማትረፍ ለምን አስፈለገ?»

«አናንተ ሮያሌ ያላችሁ ተጠሪነታችሁ ለሮያሌ ብቻ ሳይሆን፣ በጠቅላላው ለሦስቱም ደሴቶች ነው።»

«ልክ ነው።»

«አንድ ዓመፅ በመውጠንጠን ላይ መሆኑንና መሪዎቹም ሐውቲንና አርናውድ እንደነበሩ በጅራሶሎ አማካይነት ተነጋግራችሁ ነበር።»

«ካርቡኔሪም ጭምር።»

«አይደለም። ይህ ዕውነት አይደለም። ማርሴይ ከሚተዋወቁበት ጊዜ ጀምሮ፣ ካርቡኔሪ ምንጊዜም የጅራሶሎ ጠላት ነው። እዚህ ውስጥ የቀላቀለው በቂም በቀል ብቻ ነበር። ታዲያ፣ እናንተ በዚህ ዓመፅ አላመናችሁበትም። ለምን? የዓመፁ ዓላማ ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አረቦችንና ዘበኞችን ለመግደል ነው ብሎ ጅራሶሎ ሲነግራችሁ ቀልድ ነው ብላችሁ ገምታችኋል። በተጨማሪ ሆነ ብሎ ማምለጥም አይቻልም ብላችሁ ገምታችሁ ነበር። ለስምንት መቶ ሰዎች በሮያሌ ያሉት ጀልባዎች ሁለት ብቻ ሲሆኑ፤ በቅዱስ ዮሴፍ ደግሞ ለስድስት መቶ ሰዎች አንድ ጀልባ ነበር። በእንደዚህ ዓይነቱ ጋልጅ ጨዋታ ውስጥ ማንም አእምሮ ያለው ሰው አይደባለቅም።»

«እንዴት ዐወቅክ?»

«የግል ጉዳዬ ነው። ግን ስለ ዐመፅ ለማውራት እንዲያመቻችሁ እኔን ብታስወግዱ እንኳ ነገሩ አደባባይ ይወጣል። ስለዚህ አድመኞቹን ሳይነጣጠሉ ወደ ቅዱስ ዮሴፍ በላከው በሮያሌ ላይ ሃላፊነቱ ይወድቃል። መወሰድ ያለበት ተገቢ እርምጃ እንደኛውን ወደ ዲያብሎስ፣ ሌላውን ወደ ቅዱስ ዮሴፍ መላክ ነበር። ምንም እንኳ ይህን ዕቅድ በወቅቱ ለማስብ አስቸጋሪ ቢመስልም፤ መርማሪ ኮሚሽኑ ሐቁን በሚረዳበት ጊዜ ተጠያቂ የምትሆኑት እናንተው ናችሁ። ስለዚህ እደግመዋለሁ፤ ዐመፅ እያላችሁ ማውራት ከቀጠላችሁ የራሳችሁን መቃብር እየቆፈራችሁ ነው። እንግዲህ የእኔ ድርድሮች እነዚህ ናቸው። በመጀመሪያ፣ ቀደም ብየ እንዳልኩት ከነገ ጀምሮ ሁኔታዎች እንደተለመደው ይመለሱ፤ ሁለተኛ አሁን በጨለማ ግንብ ውስጥ ያሉት ሰዎች በሙሉ ባስቸኳይ ነፃ ይለቀቁ፤ ዐመፅ አስካልተካሔደ ድረስ በዐመፁ እንደ ግብረ አበር ናችሁ አየተቆጠሉ አይመርመሩ። ሦስተኛ፣ ፊሊሳሪ ለራሱ ደህንነት ሲባል ባስቸኳይ ወደ ሮያሌ ይላክ። ዐመፅ ስላልነበረ፣ የሦስቱን ሰዎች ግድያ እንዴት ማሳመን ትችላላችሁ? ፍሰ

t.me/OLDBOOKSPDF

ገጸይነት የሚባለው ይኸው ነው። ፊሊሳሪ ጨካኝ ነው። ግርግሩ በተካሔደበት ወቅት ከፉኛ ከመፍራቱ የተነሣ ሁላችንንም ተኩሶ ቢገድለን ደስተኛ በሆነ። እነዚህን ድርድሮች ከተቀበላችሁ አርናውድ፣ ሐውቲንና ማርሶው ከመገደላቸው በፊት የቻሉትን ያህል ብዙ ሰዎች ጨፍጭፈው ራሳቸውን በራሳቸው ለመግደል ወስነው እንደነበር ማንኛውም ሰው ታሱን እንዲሰጥ ለማድረግ እጥራለሁ። ተባባሪዎችም ሆኑ ጓደኞች የሏቸውም። እንግዲህ የምትፈልጉ ከሆነ፣ እኔ ወደ ወጥቤቱ ውስጥ እገባለሁ፣ በጉዳዩ እናንተ ልትነጋገሩበት ትችላላችሁ።»

ወደ ወጥ ቤቱ ሔድኩና መዝጊያውን ዘጋሁ። ማዳም ዱቴን እጇን ጭብጥ አደረገችና ትንሽ ቡና በብራንዲ ሰጠችኝ። «ስለ እኔ የገለጽከው ነገር አለ እንዴ?» አለ መሐመድ።

«ስለ አንተ አዛንፎ ያስብልሃል። ጠመንጃ እንድትይዝ ከፈቀደልህ ጊዜ ጀምሮ ምሕረት እንዲደረግልህ መፈለጉ የታወቀ ነው።»

ማዳም ዱቴን ለስለስ ብላ፣ «ይገርማል፤ ይገርማል! እንግዲህ ሮያሌም ከነገሩ ገለልተኛ ለመሆን አትችልም!» አለች።

«ከአንቺ ባለቤት በስተቀር ማንኛውም ሰው ያወቀው ዓመፅ በቅዱስ ሥፍራ ተካሒዷል ብለው ለመስማማት ለእነርሱ በጣም ቀላል ጉዳይ ነበር።»

«ፓፒዮ፣ ውይይታችሁን ስለሰማሁ አንድ ጥሩ ዘዴ እንዳገኘህ ወሬያውኑ ተገንዝቤያለሁ።»

መዝጊያው ተከፈተ። «ፓፒዮ ግባ» አለ አንድ ዘበኛ።

«አባከህ ተቀመጥ» አለ የሮያሌ ወህኒ አዛዥ፣ «ነገሩን ተወያይተንበት አንተ ትከከል መሆንህን ሁላችንም በአንድ ድምፅ ወስነናል። ዐመፅ አልነበረም። የቻሉትን ያህል ብዙ ሰዎች ገድለው ሦስቱ ሰዎች ራሳቸውን ለመግደል ወስነዋል። ስለዚህ፣ ከነገ ጀምሮ ሁኔታዎች እንደ ቀድሞው ይስተካከላሉ። ሙሴ ፊሊሳሪም በዛሬዋ ምሽት ወደ ሮያሌ ይሔዳል። የእርሱ ጉዳይ እኛን የሚመለከት ስለሆነ፣ አንተን እንድንተባበር አልጠይቅም። ቃልህን እንደምትጠብቅልን እንተመ፣ለን።

«ለእኔ ልትተዉት ትችላላችሁ።»

«መሐመድ፣ አንተና ሁለቱ ዘበኞች ሆናችሁ ፓፒዮን ወደ «ሣጥኑ» መልሳችሁ ሸኙት። ፊሊሳሪን እዚህ እንዲመጣ ንገሩት። ከእኛ ጋር ወደ ሮያሌ ይሔዳል።»

በጉዞ ላይ እንዳለን መሐመድ ነግሩቱን እንደሚያገኝ ተስፋ ያለው መሆኑን ነገርኩት። አመሰገነኝ።

ወደ «ሣጥኔ» ተመልሼ ድምፄን ከፍ በማድረግ ምን እንደ ተደረገ ቃል በቃል ሳስረዳ ረጭ ያለ ፀጥታ ሰፍኖ ስለነበር፣ ማንኛውም ሰው ለመስማት ቻለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሕጌ ያደረግኳቸውን ድርድሮች የሚተች ወይም የሚቃወም አንድ ሰው ካለ፣ አሁኑኑ ይናገር» አልኩ።

ማንም ሰው አልተቃወመም።

«ሌላ ግብረ አበር የላቸውም ብለው ስለ ማመናቸው እርግጠኛ ነህ፣»

«አይደለሁም፣ ግን ራሳቸውን ሊያድኑ ከፈለጉ ማመን አለባቸው። እኛም ችግር ካልፈለግን እንደዚሁ ብናምንበት ይሻላል።»

በሚቀጥለው ቀን ጧት አንድ ሰዓት ላይ በከፍተኛ ደረጃ ከሚጠበቀው ሰፈር ያሉትን ከፍሎች ባዶ አደረጉ። ከመቶ ሐያ ሰዎች በላይ ነበሩ በዚያ የታሠሩ። ወደ ሥራ የሐደ ማንም ሰው አልነበረም፣ ግን ኑንፃዎቹ በሙሉ ተከፈቱና በፀሐይ ወይም በጥላ ስር ተቀምጠው፣ ሲጋራ በሚያጨሩ በሚያወሩ እሥረኞች ግቢው በሙሉ ተጨናነቀ። ኒስተንም ወደ ሆስፒታል ሐደ። «በፀመፀ ተባባሪነት የተጠረጠሩ» የሚሉ ምልክቶች ቢያንስ በሰማንያ መዝጊያዎች ላይ ተንጠልጥለው እንደነበረ ካርቡኔሪ ነገረኝ።

አሁን ሁላችንም አብረን ስለነበርን ምን እንደ ተደረገ ተረዳን። ፊሊሳሪ የገደለው አንድ ሰው ብቻ ነበር። ሌሎቹ ሁለቱን የተኮሱባቸው ሁለት ወጣት ዘበኞች ነበሩ። ሁለቱ እሥረኞች ጀርባቸውን ወደ ግድግዳው አዙረው ስለነበረ፣ ልንገደል ነው ብለው በማሰት፣ መሞታችን ካልቀረ ቢያንስ አንድ ዘበኛ ጥለን እንወድቃለን በሚል ግምት ጩቤዎቻቸውን መዘዙ። በአንጻሩ ዘበኞቹ ደግሞ የሚጠቁ መስሎ ስለ ተሰማቸው ተኮሱባቸው። በዚህ ሰበብ ነበር ፀመፀ በአንጭጩ ሊጨናነፍ የቻለው አንጂ፣ ታይቶ ወደማይታወቅ አንድ ፀይነት የእርስ በርስ መፈጨፋጨፍ በተሸጋገረ ነበር። ይህ ሐሳብ በአስተዳደሩም ሆነ በእሥረኞቹ፣ በሁሉም ሰው ዘንድ በኦፊሺያል ተቀባይነት አግኝቶ ነበር።

በመሐሉም በካምፑ የተገደሉት የሦስቱ ሰዎችና እንደዚሁም የሐውቲንና የማርሶው የቅበር ሁኔታ በሚከተለው ሥነ ሥርዓት ተከናወነ። ያለው የአስከሬን ማንሸራተቻ ሣጥን አንድ ብቻ ስለነበር፣ ዘበኞቹ ሁሉንም አደራርበው አስቀመጧቸውና በአንድነት ለዓሣ ነባሪዎች ወረወሯቸው። እግሮቻቸው ላይ የታሰሩት ድንጋዮች ወደታች ስለሚስቧቸው ለመስመጥ ጊዜ ያገኛሉ ብለው ዘበኞቹ ገምተው ነበር። ግን ከአምስቱ ውስጥ አንዳቸውም እንዳልሰመጡና በዓሣነባሪዎች አፎችና ጅራቶች ከወዲያ ወዲህ እየተላጉ፣ ልክ የባሌ ዳንስ የሚያሳዩ አሻንጉሊቶች ይመስሉ ነበር። ያለማጋነን በናቡከደናፆር ዘመን፣ ሠለስቱ ደቂቅ በእቶነ እሳት ውስጥ ሲመላለሱ ከታየው ትርዒት ጋር ተመሳሳይ ነበር ለማለት ይቻላል። የሁኔታው አሰቃቂነት ዘበኞቹንና ጀልባ ቀዛፊዎቹን ከባሕሩ ዳር እንዲበረግጉ አስገድዷቸዋል።

አንድ መርማሪ ኮሚሽን መጥቶ በቅዱስ ዮሴፍ አምስት ቀን፣ በሮያሉ ሁለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ቀን ቆየ። ለልዩ ጥያቄ በተናጠል አልተጠራሁም፤ ግን እንደ ሌሎቹ ሁሉ እኔም ተመርምሬ ነበር። ማንኛውም ነገር በሰላም እንደተከናወነ ከአዛዡ ዱቴን ተረዳሁ። ፊሊሳሪ የጡረታ ጊዜውን አስኪጀምር ድረስ ፈቃድ ስለ ተሰጠው የሚመለስ አይሆንም። ሞሐመድ አመከሮ ተደረገለት። አዛዡ ዱቴንም የደረጃ ዕድገት አገኘ።

አንዳንድ ቅሬታም ነበር፣ ከቦርዶው ቀበሌ የመጣ አንድ አሥረኛ፣ «ለዘበኞች እንደዚህ ከፍተኛ አርዳታ ማድረጋችን ለእኛ ምን ጥቅም ያስገኝልናል?» ሲል ጠየቀኝ።

ትኩር ብየ ተመለከትኩና፣ «አምበዛም ነው። ግን ሃምሳ ወይም ስድሳ አሥረኞች በግብረ አበርነት ተወንጅለው የአምስት ዓመት ግዞት አያሳልፉም። ይህ አንድ ውለታ አይመስልህም? አልኩት።

ሊፈነዳ የነበረው አሳተግሞራ እዚሁ ላይ በረደ። በዘበኞችና በአሥረኞች መካከል የነበረው መግባባት የመርማሪ ኮሚሽኑን ጥረት አከሸፈው።

በራሴ በኩል ከጓዶቼ ምስጋና በስተቀር ምንም ያተረፍኩት ወይም ያጣሁት ነገር የለም። አንዳንድ ነገሮች ተስተካከሉ፣ ቋጥኝ ጉተታ ቀረ፣ አሁን ሥራው በጎሾች እንዲከናወን ተደረገ። አሥረኞቹ እያስተካከሉ ብቻ ይጭኗቸዋል። ዮሐንስ ካርቡኔሪም ወደ ዳቦ ቤቱ እንዲመለስ ተፈቀደለት።

ሮያሌ እንደገና ተመልሼ እንድላክ ምክርኩ። ቅዱስ የሲፍ ውስጥ ወርክሾፕ ስላልነበረ፣ ጀልባ ለመሥራት አመች መንገድ የለም። በፈረንሣይ የፔቲን ሥልጣን ላይ መውጣት በዘበኞችና በአሥረኞች መካከል ያለውን ግንኙነት አምታታው። የአስተዳደሩ ሰዎች በጠቅላላው ራሳቸውን፣ «የፔቲያን ደጋፊዎች» ነን ብለው ዓወጁ። አንድ የኖርማንዲ ዘበኛ እንኳ እንደዚህ ሲል አወራኝ። «አንድ ነገር ለመረዳት ትፈልጋለህ ፓፒዮ? እኔ ፍጹም ሪፑብሊካዊ ሆኜ አላውቅም።»

በደሴቶች ማንም ሰው ሬዲዮ ስለሌለው ወሬ አናገኝም። ከዚህም በላይ በጓዳሉፕና ማርቲኒክ ላሉት ጀርመን ባሕር ጠለቅ መርከቦች እየተባበርን ነው እየተባለ ወሬው ይነፍሳል። እርግጡ የሚታወቅበት ምንም መንገድ ስላልነበረ ዘወትር ከርከር እንደፈነዳ ነበር።

«በከርስቶስ! እኔ የማስበው ምን እንደሆነ ታውቃለህ ፓፒ? አሁን አንድ ዐመፅ ማካሔድ እንዳለብንና ከዚያም ደሴቶቹን ለደጎል ለነፃዋ ፈረንሣይ መልሰን መስጠት እንደምንችል ነው።»

«ታላቁ ቻርለስ ደጎል የቅኝ ግዛት አሰቃቂውን ወህኒ ቤት ይፈልገዋል ብለህ ታስባለህ? ምን ሊሠራለት?»

«ሁለት ወይም ሦስት ሺ ተጨማሪ ሰዎችን ያገኛል!»

«ቆማጡች፣ ወፈፌዎች፣ የሣምባ ነቀርሳ በሽተኞች፣ የደም ተቅማጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሕመምተኞች? ሳስበው ያስቀኛል። አሥረኛን ወታደር አጁ ማስገባት የሚፈልግ አስክዚህ ሞኝ ሰው አይደለም።»

«ሁለት ቪ ጤነኞች አሥረኞችስ እንዴት ናቸው?»

«ይህ ሌላ ጉዳይ ነው። ጎበዝ ሰዎች ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል፤ ግን ይህ ደግሞ ለጦር ግንባር ብቁ ይሆናሉ ማለት አይደለም። ጦርነት የጩቤ ግብግብ መስለህ? ይህ በወሥር ደቂቃ ያበቃል። አንድ ጦርነት ግን ዓመታት ይፈጃል። አንድ ጥሩ ወታደር ለመሆን የሀገር ፍቅር ስሜትም እንዲኖርህ ይሻል። ወደድክም ጠላህም ሕይወትን ለፈረንሣይ አሠዋለሁ የሚል አንድም አሥረኛ እዚህ ይኖራል ብየ አላስብም።»

«ምን በወጣን፣ ለዚህ ሁሉ ያደረሰን ማን ሆነና?»

«ስለዚህ ከእኔ ጋር ተስማማህ አይደለም? ወዳጆችን ቻርልስ ጦርነቱን የሚዋጉለት ከእኛ የተሻሉ ሰዎችን ማግኘቱ ጥሩ ነገር ነው። ጦርነቱ ባወጣ ያውጣው ብልም በእንጻሩ ግን፣ እነዚያ ምናምንቴ ጀርመኖች ሀገራችን ውስጥ ይቁዩ የሚለውን ሐሳብ ደግሞ አልደግፈውም! ከድሮው ከጀርመናውያን ጎን የተሰለፉ ፈረንሣውያን መኖራቸውን ታውቃለህ? እዚህ ያሉት ዘበኞች እንኳን የፔቲን ደጋፊዎች ናቸው ይባላል።»

«አንዱን ወገን መደገፍ ምሕረት ለማግኘ አንድ ዐይነት ዘዴ ሊሆን ይችላል» አለ የቤራኩ መኮንን። ምሕረት ሰምግኘት ያልሞከረ አንድም አሥረኛ አልነበረም። አሁን ማንኛውም ሰው - አራዳ ላጤዎቹም ሆኑ ገሪባዎቹ፣ አይበገሬዎቹ ወንጀለኞች እንኳ ሳይቀሩ - ከአድማስ ባሻገር ጭላንጭል ታይቷቸው ነበር።

«ከደጎል ጋር እንድንተባበር ..ምን አንድ ዐመፅ አናካሒድም ታጊ?»

«አገናለሁ፤ ግን እኔ ምሕረት የሚባል ነገር አልጠብቅም። የፈረንሣውያንን ፍትህና ጠባይ ማረሚያ የሚለውን አስተሳሰባቸውን ወደዚያ በለው። ጠባየን እንዳረምኩ ፍርድ የምሰጠው ራሴው እሆናለሁ። አሁን የእኔ ተግባር ማምለጥና ለመጨረሻ ጊዜ ነፃ ከሆንኩ ቢኋላ ለሕብረተሰብ ችግር ስለማልፈጥር አንድ የተስተካከልኩ ሰው መሆኔን ማረጋገጥ ነው። ማንነትህን ለማስመስከር ሌላ መንገድ የሚኖር አይመስለኝም። በማንኛውም ወቅት ከዚህ ለመሔድ ዝግጁ ነኝ፣ ማምለጥ እስከ ቻልኩ ድረስ። ደቤቶቹን ለታላቁ ቻርልስ መመለሱ ላይ አልተደሰትኩበትም፣ ያም ቢሆን እርሱም የሚፈልጋቸው አይመሰለኝም። በተጨማሪ እንደዚህ የመሰለውን ነገር ብናደርግ ቁንጮ ላይ ያሉት ባለሥልጣኖች ምን እንደሚሉ ታውቃለህ? ያደረግነው ለራሳችን ስንል እንጂ ለፈረንሣይ አይደለም። ለማንኛውም፣ የትኛው ትክክል መሆኑን አጣርተን እናውቃለን? ፔቲን ወይስ ደጎል? በዕውነት እኔ ምንም አላውቅም። ሀገሬ ተወርራለች ማለትን ስረዳ ከኃኔ እንዳለው ሰው አኔም አዝናለሁ። ስለ ሕዝቡ፣ ስለ አባቴ፣ ስለአሀቶቹ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለ እሠዎቹ ልጆችም አስባለሁ።

«ስለ እኛ ምንም ደንታ ሰሌለው አንድ ሕብረተሰብ ብለን አዚያ ችግር ውስጥ አንድንገባ እነዚህ ምናምንቴዎች ምን ጥልቅ አድርጓቸው ነው የሚገፋፉን?»

«በትክክል የሚያሰኝ ነው። እነኛ ዓሣሞች፣ ያ የፈረንሣይ የጭስ መዋቅር፣ ዘበኞቹ ሁሉ፣ ፈረንሣይን አይወክሉም። ከድጉን አእምሮ ጋር የተፈጠሩ እንድ የተለየ ያመደብ ክፍል ናቸው። በጀርመኖች ፊት ለማንብደድ ከእነርሱ ምኒ ያህሎቹ እንደተዘጋጁ አስኪ ገምት። የፈረንሣይ ፖሊሶች የገዛ ሀገራቸውን ሰዎች እያሰሩ ለጀርመን ባለሥልጣኖች እንደሚያስረከቧቸው መወራረድ ትፈልጋለህ፣ በድጋሚ እነግርሃለሁ፣ በምንም ምክንያት ከማንኛውም ዐመፅ ውስጥ አልካፈልም። ማምለጥ አስክልሆነ ድረስ።»

በተለያየነው አንጃዎች መካከል እጅግ ከረር ያሉ ውይይቶች ይነሣሉ እንዳንዶቹ ለደኅል ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ለፔቲን ነበሩ። ይሁንና ቀደም ብየ እንደገለጽኩት፣ እስረኞቹም ሆኑ ዘበኞቹ ሬዲዮኖች ስለሌሏቸው በትክክል ያወቅነው ምንም ነገር አልነበረም። ወሬዎች የሚደርሱን ስንታችንን ከሚያመጡልን ጀልባዎች ብቻ ነበር። ጦርነቱ ለእኛ በጣም ሩቅና ለመረዳትም አስቸጋሪ መሰለን።

«ለነዛዎቹ የፈረንሣይ ኃይሎች» መታደር የሚመለምል አንድ ጓድ ወደ ቅዱስ ላውረን መጥቶ እንደነበር ጭምጭምታ ይወራል። እኛ በደሴቶች ያለነው ግን - ጀርመኖች መላዋን ፈረንሣይን አጥለቅልቀዋታል የሚለውን ዜና ብቻ እንጂ ሌላ ምንም እናውቅም ነበር።

አንድ አሥቂኝ አጋጣሚ ግን ተፈጠረ። አንድ ቄስ ወደ ሮያሌ መጡና ከቅዳሴ ሥርዓት በኋላ ስብከት አደረጉ። «ደሴቶቹ ሲወረሩ፣ ለእናንተም መሣሪያ ይስጣችሁና የፈረንሣይን መሬት የሚከላከሉትን ትረዳላችሁ» አሉ። እርሳቸው የተናገሩት ከልባቸው ነበር። ስለእኛ -ስለእሥረኞች አንድ ለየት ያለ አስተያየት ኖሯቸዋል ማለት ነው። የወህኒ ቤት ክፍሎቻችንን እንድንከላከል እኛን መጠየቅ! ቀጥሎስ ምን ይመጣ ይሆን?

ለእኛ ግን፣ ጦርነቱ ያስከተለው የሚከተሉትን ነበር። የዘበኞች በእጥፍ መጨመር፣ የጀርመን ወይም አልሳቲን የእነጋገር ቅላጼ ያላቸው ብዙ ጎቆጣጣሪዎች ብቅ ማለት፣ በጣም ትንሽ ዳቦ ማግኘት፣ በቀን ከአንድ ፓውንድ በታች ተቀንሶብናል - ሥጋውም በጣም አነስተኛ ሆኗል። ማምለጥ የከሸፈበት አሥረኛ ቅጣቱ ሞት ሆነ፣ ምክንያቱም ከተሰመደው የማምለጥ መከራ ወንጀል ሌላ፣ «ወደ ፈረንሣይ ጠላቶች ለመከዳት በመሞከር» የሚል አንቀጽ ጨምሯል።

ከዶክተር ጀርሜይን ጉበርት ጋር መልካም ወዳጅነት ወደ አበጀሁበትም ወደ ሮያሌ ለመመለስ ተሳክልኝ። ለየ ዓይነት ሴት የሆነችው ባለቤቱ የተቀነሰውን ምግባችንን

t.me/OLDBOOKSPDF

ለማሚላት አንድ የአትክልት ቦታ አንዳለማ ጠየቀችኝ። ስላጣ፣ ራዲሽ፣ ባቄላ፣ ቲማቲምና ... ወዘተ ተከለከ። ደስ ስላላት የምትመለከተኝ ልክ አንደ ቅርብ ጓደኛ አድርጋ ነበረ። ከማንኛውም ሰው፣ ከፍተኛ ማዕረግ ይኑረው፣ ዶክተሩ እጅ አይጨባበጥም፤ ግን የሚያውቃቸውንና የሚያከብራቸውን አንዳንድ አሥረኞችን እኔን ጨምሮ ዘወትር ይጨብጠናል።

ከዓመታት በኋላ በመጨረሻ ነፃ አንደሆንኩ፣ በዶክተር ሮዘንበርግ አማካይነት ከዶክተር ጉበርት ጋር አንደገና ግንኙነት አድርጌ ነበር። ማርሴይ ውስጥ ራሱና ባለቤቱ በካነቢየ ማርሴይ የተነሡትን አንድ ፎቶግራፍ ልኮልኛል። ነፃ በመለቀቄም እንኳን ደስ አለህ ብሎኛል። አንድ ቁስለኛ ወታደር አተርፉለሁ ብሎ ሲታገል ኢንዶቻይና ውስጥ ተገደለ። የተለየ ሰው ነበር፤ ባለቤቱ ደግሞ ከርሱ የጣሰች ጥሩ ሴት ነበረች። በ1967 ወደ ፈረንሣይ ሰመለስ፣ ሳያት አሰብኩና ሳለማድረግ መሰንኩ። በቅድሚያ ፈቃደኛነቷን ጠይቄያት ተስማምታ ነበር። ከዚያ ወዲህ ግን ለመገናኘት አልቻልንም። ደብዳቤ ለምን መጻፍ አንዳቆመች ጉም አላወቅኩም፣ ግን በሮያሉ ቤታቸው ውስጥ ላደረጉልኝ መስተንግዶ ከልቤ አመሰግናቸዋለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዘጠነኛ ማስታወሻ

ቅዱስ ዮሴፍ

የካርቦኔሪ ምኅ

ጓደኛየ ካርቦኔሪ ትላንት በጩቤ ተወግቶ ሞተ። የአርሱ ሞት ራሱን የቻለ ብዙ ተከታታይ ማድያዎችን አስከተለ። የተወጋው በገላ መታጠቢያው ውስጥ ራቁቱን ሆኖ ፊቱን በሣሙና እንደ ተሸፈነ ነበር። በምንታጠብበት ወቅት ጩቤዎቻችንን በልብሶቻችን ሥር የመደበቅ ልማድ ነበረን። አንድ የምንጠረጥረው ጠላት ብቅ ሲልብን ቶሎ ለመሰንዘር እንችላለን። ካርቦኔሪ ይህን ማድረግ በመርሳቱ ሕይወቱን አጣ። የገደለው ሰው አንድ አርመናዊ አቃጣሪ ነበር።

በወህኒ አዛገቦ ፈቃድ ከአንድ ሴላ እሥረኛ ጋር በመረዳዳት የጓደኛየን አስከሬን ወደ ወደቡ ተሸከመን ወረድን። በጣም ከባድ ስለሆነ ለማሣረፍ ሦስት ጊዜ መቆም ነበረብን። በተለመደው ሃመድ ፈንታ የበረት ሰንሰለት በመጠቀም አንድ ትልቅ ቋጥኝ እግሮቹ ላይ አሰርኩለት። በዚህ ዐይነት ዓሣ ነባሪዎቹ ሰንሰለቱን መቁረጥ ስለማይቻላቸው ምንም ሳይበላ ወደታች ሊሰምጥ ይችላል።

ወደቡ እንደ ደረስን የደወሉ ድምፅ አሰተጋባ። ዐሥራ ሁለት ሰዓት ስለነበረ ፀሐይዋ በመጥለቅ ላይ ነበረች። ጀልባው ላይ ወጣን። ዘወትር በተለመደው የሬሣ ማንሸራተቻ ሣጥን ላይ ከተኪደነው ግጣም ሥር ማቴዎስ የመጨረሻ እንቅልፉን አሸልቧል። ከእንግዲህ ለአርሱ ማንኛውም ነገር አስትጭለት ነበር።

መረው ላይ ያለው ዘበኛ፣ «ሕንሒድ፣ መቅዘፍ ጀምሩ» አለ። ዐሥር ደቂቃ ሳይሞላ በሮያሌና ቅዱስ የሴፍ መካከል ከሚገኘው የባሕር ወሽመጥ ደረስን። ወዲያው ጉሮሮየ ድርቅ አለ። አንድ ደርዘን የሚሆኑ ዓሣ ነባሪዎች ውሃውን በከንፈሮቻቸው እየቀዱጡ በዙሪያችን በመወናጨፍ በጣም ተጨናንቀው ከብ ሠሩና አሰፈሰፉ። ቅጠሮቻቸውን አከብረው መዘጋጀታቸው ነበር።

ቸሩ ፈጣሪ፣ እንዲያገኙት ጊዜ አትስጣቸው፣ ለመሰነባበቻ ያህል መቅዘፊያዎቻችንን ወደ ላይ አነሳንለት። የሬሣ ሣጥኑን ከፈትን። የማቴዎስ አስከሬን በጻፉት ከረጢቶች እንደ ተጠቀለለ ወደ ውሃው ተንሸራተተ።

የከርሰቶስ ያለህ እንደፈራህት ግና ውኃው ውስጥ ከመግባቱ ነበር፣ ወዲያውኑ ሰባት፣ ዐሥር፣ ምናልባትም ሐያ ዓሣነባሪዎች ይሆናሉ አላወቅኩም፣ ተሸከመው ከውሃው በላይ ያነሡት። የጻፉት ከረጢቶቹ ተዘነጣጠሉና ምናልባትም ለሁለት ወይም ሶሥት ሲኮንዶች ይሆናል፤ ማቴዎስ ከነሕይወቱ ከውሃው በላይ ብቅ ብሎ የቆመ

t.me/OLDBOOKSPDF

መሰለ። የቀኝ ከንዱ ተንምዷል። ግማሽ አከላቱ ከውሃው በላይ ሆኖ ወደ እኛ ጀልባ በመንሳፈፍ ላይ እንዳለ ነበር አንድ የውሃ አዙሪት ጠልፎት ያጠፋው። ዓሣነባሪዎቹ ካሥር ሽው ብለው ሲያልፉ ጀልባዋን ከታች በኩል ስለመቷት፣ ከእኛ ሰዎች አንዱ ሚዘኑን ስቶ ወደ ውሃው ሊወድቅ ተቃርቦ ነበር።

ማንኛውም ሰው ዘበኞቹ ሳይቀሩ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ። በሕይወቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ሞትን ተመኘሁ። ራሴን ወደ ዓሣነባሪዎቹ ወርውሬ ይህን ገሃነመ እሳት ለዘለዓለም ለመገላገል ጊዜም ባልወሰደብኝ ነበር።

እያዘገምኩ በመራመድ ብቻዬን ወደ ካምፕ ተመለስኩ። የቃሬዛ ማጓጓዣውን በትከሻዬ እንደተሸከምኩ ዳንተንና ብሩተስ ተጋጥመው ከነበሩበት ቦታ ስደርስ ቆም አልኩና አረፍኩ። ጨለማው ለዓይን ይዞ ነበር። ገና አንድ ሰዓት ቢሆንም፣ የፀሐይ ጮራ ከአድማሱ ላይ በስተምዕራብ በኩል ምላስ መስላ ትታያለች። ከተለመደው የመርከብ አደጋ ማስጠንቀቂያ መብራት ወጋጋን በስተቀር፣ ማንኛውም ነገር ጥቁር ለብሷል። ልቤ በሐዘን ተሰብሮ ነበር።

እንግዲህ መቃበር ለማየት እንደተመኘኸው የጓደኛህን መቃብር አየህ። መልካም፣ ደወሉንም፣ ሁሉንም ነገር ምንም ሳይቀር አየህ። አሁን ማብቂያህን ተረዳኸው አይደል?

ግን ጓደኛየን ገድሎ የነበረውን ሰው ገና ማግኘት አለብኝ። መቼ? ዛሬ ማታ? አይደለም፣ በጣም መቸኮል ይሆናል፣ ራሱን ሊጠብቅ ይችል ይሆናል። በጣም ፈጥኖ መንቀሳቀሱ ፋይዳ የለውም። ከእርሱ ጋር የሚኖሩት ደባሎች ስድስት ሰዎች ነበሩ። አኔስ በስንት ሰዎች መመካት እችላለሁ? ከእኔ ሌላ አራት። እሺ፣ ማድረግ እንችላለን። እሞ፣ ከዚያም የሚቻል ከሆነ ወደ ዲያብሎስ ደሴት አሔዳለሁ። በዲያብሎስ ጀልባ የሚባል ነገር የለም፣ ምንም ነገር የለም፣ በሁለት ጆንያ ኮከነቶች ብቻ ወደ ባሕር ማፈትለክ ነው። ከዚያ እስከ ጠረፍ ድረስ ያለው፣ ቁራ ሊያቋርጠው የሚችል የሐያ አምስት ማይል አጭር ርቀት ነው። የመንፈስ ጥንካሬ ጉዳይ ብቻ ነው። ጠንካራ ስለ ነበርኩ በጆንያዎቹ ላይ እግሮቼን እንዳንፈራጠጥኩ ቆሜ ሁለቱን ቀኖች መጨረስ እንደምችል እርግጠኛ መሆን ይኖርብኛል።

ሽክሜን አነሣሁና መንገዴን ቀጠልኩ። ከበሩ ፊትለፊት ስደርስ ተበረበርኩ። በጣም ያልተለመደ ነገር። ካሁን በፊት ፍጹም እንደዚያ ተደርጎ አያውቅም። ዘበኛው ጩቤየን ገፈፈኝ።

«እንድገደል ትፈልጋለህ እንዴ? ለምን ጩቤዬን ትወስድብኛለህ? ወደ መቃብሬ እየላከኝ መሆንህን እንደተገነዘብክ እገምታለሁ» አልኩት ዘበኞቹም ሆኑ ቁልፍ ያዥ አረቦች፣ ማንም መልስ የሰጠኝ ሰው የለም። መዝጊያውን ከፈቱና ወደ «ሣጥናችን»

t.me/OLDBOOKSPDF

ገበሁ። «ምንም ነገር ማየት አልቻልም። ለምን አንድ ፋኖስ ብቻ ሆነ?»

«ፓፒ፣ ና ወደዚህ» አለና ግራንዴ ኮሌታዮን ይዞ ጎተተኝ። ልክ አንድ ከባድ ነገር እንደ ተፈጸመ ወይም ሊደረግ እንደታቀደ ዐይነት፣ ከፍሉ ያለወትሮው ረጭ ብሎ ነበር።

«ጩቤዬ የለም። አበሩ ላይ በር-በረው ወስደውብኛል።»

«ዛሬ ማታ አያስፈልግህም።»

«ለምን?»

«አርመናዊውና ጓደኛው ዕረፍት ላይ ናቸው።

«ተኝተዋል ማለትህ ነው?»

«ሞተዋል።»

«ማን አደረገው?»

«እኔ።»

በጣም ፈጣን አርምጃ ነው። ሌሎችስ እንዴት ናቸው?»

«አሁንም ገና አራት ቀርተዋል። ጳውሎስ ካንተ ጋር አስኪነጋገር ድረስ ምንም ነገር ላለማድረግ ቃል ገብቶልኛል።

«አንድ ጩቤ ስጠኝ።»

«የራሴን ውሰድ፤ እኔ እዚሁ እቆያለሁ።»

ወደ እነርሱ መኝታ አካባቢ ሔድኩ። ከፊል ጨለማውን አሁን ዐይኖቼ ተለማምደውታል። በመጨረሻ ወደ ቡድኑ ተቃረብኩ። እርስ በርሳቸው ጥብቅብቅ ብለው በተንጠልጣይ አልጋዎቻቸው ፊት ለፊት ቆመው ነበር።

«ጳውሎስ፣ ልታነጋግረኝ ፈልገሃል እንዴ?»

«አዎ።»

«ምን ትፈልጋለህ?»

ለጥንቃቄ ያህል በመካከላችን የአራት ጫማ ርቀት ትቻለሁ። ስለቱን በሸሚዜ እጅጌ ሥር አስገብቼ የጩቤውን እጀታ በመዳፌ ውስጥ ደህና አድርጌ ጨበጫለሁ።

«ለማለት የፈለግኩት፣ ጓደኛህ ብቀላውን ተወጥቶታል። አንተ በጣም ቅርብ የሆነ ጓደኛ እንዳጣህ ሁሉ፣ እኛም ሁለቱን አጥተናል። በእኔ ግምት ይህ በቂ ነው። አንተስ ምን ትላለህ?» አለ ጳወሎስ።

«ጳውሎስ፣ ድርድርህን አስብበታለሁ። ማድረግ የምንችለው፣ የምትስማማ ከሆነ፣ በሁለቱ ቡድኖቻችን መካከል ምንም ዐይነት አርምጃ ሳንወስድ ለአንድ ሳምንት በሰላም መቆየት ይኖርብናል። በዚህ ወቅት ቀጥሎ ስለምናደርገው ማሰብ እንችላለን። ትከክል አይመስልህም?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አዎ፣ ትክክል ነው።»

ተመለስኩ።

«ምን አሉ?»

«በአርመናዊውና ሳንሱቼ ሞት የማቴዎስን ደም ተበቅለናል ብለው ገምተዋል።»

«አይሆንም» አለ ጋልጋኒ።

ግራንዴ አልተናገረም። ዮሐንስ ካስቴሊና ሉዊ ግራሾን በሰላሙ ውል ተስማሙ።

«አንተስ ምን ታስባለህ ፓፒ?»

«በመጀመሪያ ነገር ማቴዎስን የገደለው ማነው? አርመናዊው ነው፣ ትክክል አይደለም? አንድ ድርድር አቅርቤላቸዋለሁ። አስከሚቀጥለው ሳምንት ማንም ሰው እንዳይንቀሳቀስ ቃሌን ሰጥቻለሁ፣ እነርሱም ሰጥተዋል።»

«ማቴዎስን ልትበቀልለት አትፈልግም?» ሲል ጋልጋኒ ጠየቀ።

«ስማ ጓደኛዬ፣ ማቴዎስን በሚገባ ተበቅለንለታል። ለርሱ ሲባል ሁለት ሰዎች ሞተዋል። ለምን እንደገና ተጨማሪ ይገደላል?

«የተቀሩትስ በነገሩ ውስጥ ነበሩበት፣ ወይስ አልነበሩበትም? ማጣራት ያለብን ይህን ነው።»

«ይቅርታ አድርጉልኝ፣ ሁላችሁም ደህና እደሩ። ትንሽ እንቅልፍ ማግኘት አፈልጋለሁ።»

ወይም ቢያንስ ብቻየን ለመሆን ፈልጌያለሁ። በተንጠልጣይ አልጋየ ላይ ጢ ብየ እንደ ተዘረጋሁ፣ አንድ እጅ ሲያርፍብኝና ጩቤዬ ሲወሰድ ተሰማኝ።

«ፓፒ፣ እትሥጋ ለመተኛት ሞከር፣ እንተን ልንጠብቅ ተራ እየተለዋወጥን ነው» የሚል አንድ ድምፅ ሹክ አለኝ።

ለጓደኛዬ በጭካኔ መገደል ተጨባጭ ምክንያት አልነበረውም። አርመናዊው ማቴዎስን የገደለው በካርታ ጨዋታ አንድ መቶ ሰባ ፍራንክ በግድ ስላስከፈለው ብቻ ነበር። በዚህም ያ የውሻ ልጅ የተዋረደ መስሎታል፣ ምክንያቱም አስገድዶ ያስከፈለው በሠላሳ ወይም አርባ ተጫዋቾች ፊት ነበረ። ማቴዎስና ግራንዴ አፋጠው ሲይዙት ያቺን ገንዘብ ተፍቷታል። ስለዚህ ያን ተስፋ የማይቆርጥና ለከባድ መከራ የማይበግረውን ማቴዎስን፣ ልከ እንደ አንድ ፈሪ ገደለው። ከባድ ሐዘን የወደቀብኝ ብሆንም፣ ብቸኛው ደስታየ ደግሞ ገዳዩም ከእርሱ በኋላ የኖረው ለጥቂት ሰዓታት ብቻ መሆኑ ነበረ። ያም ሆኖ ቅጣቱ ተመጣጣኝ ነው አልልም።

ራሳቸውን ለመጠበቅ ጊዜ ከማግኘታቸው በፊት ግራንዴ ጩቤውን

t.me/OLDBOOKSPDF

በጉሮሯቸው ላይ ሰክቶባቸዋል። የወደቁበት ቦታ ቢደም እንደ ተጥለቀለቀ ተሰማኝ። ከዚያም ወደ መጸዳጃ ቤት የንተታቸው ማን እንደሆነ ደነቀኝ። ማን መጠየቅ አልፈለግኩም። ፀሐይ ሐምራዊና ቀይ ጨረሯን በዚያ ትዕይንት ላይ በአሳዛኝ ሁኔታ ለመጨረሻ ጊዜ ስትፈነጥቅበትና ዐሣነባሪዎቹ ጓደኞየን ሲሻመጡት ታየኝ። እጅና እግር ኩልባ የሆነው አካላቱ ወደ ጀልባው አቅጣጫ ሲወዛወዝ፤ እንደሚወራው ደወሉ የዐሣ ነባሪዎች መጥሪያና እነሱም ምናምንቴዎች ደውሉን ሲሰሙ እራት ተዘጋጅቷል ማለት መሆኑን ማወቃቸው ለካስ እውነት ኖሯል። የደበዘዙ ብርማ ከንፎቻቸውን እያብለጨለጩ ልክ እንደ ባሕር ሰርጓጅ መርከብ ብቅ ጥልቅ እያሉ መላልሰው ሲዘዋወሩ በድጋሚ ታዩኝ፤ ከአንድ መቶ በላይ መሆን አለባቸው። የቁም ሥቃዩ ከእንግዲህ አከተመ።

በወርባ ዓመት ዕድሜው ከንቱ ሞት! ምስኪን ጓደኛየ። ከእንግዲህ እዚህ ሆኜ ትዝታውን መቋቋም አልችልም። ለነፃነቴ እሰከታገልሁ ድረስ ዓሣነባሪዎች ቢበሉኝም ደንታ የለኝ። የዱቄት ከረጢት የሚባል አይኖርም። ቋጥኝ ድንጋይ አይታሰርብኝም፣ ገመድ ፣የሚባል አያስፈልገኝም። ተመልካቾችም እንደዚሁ አይኖሩም፤ አሥረኞች፣ ዘበኞች የሚባሉ አያስፈልጉኝም። ደወልም የለም። የሚበሉኝ ከሆነ - ወደ ግራንዴቴሬ ለመድረስ በመታገል ላይ እንዳለሁ ከነሕይወቴ ይብሉኝ።

በዚሁ ቆረጥኩ። ማምለጥ። ከመጠን በላይ ማቀድ ከእንግዲህ የለም። ወደ ዲያብሎስ ደሴት ለመሔድ ይቅናኝ። ከዚያም በሁለት ጆንያ ኮከኑቶች ላይ እየተንሳፈፍኩ የዕድሌን እጠብቃለሁ። ለማንኛውም አስፈላጊው የአካል ጥንካሬ ጉዳይ ብቻ ነው። የሚፈጅብኝም ከአርባ ስምንት አሰከ ስድሳ ሰዓት ቢሆን ነው። በውሃ ውስጥ በኮከኑቶቹ ላይ ለዚያን ያህል ጊዜ መቆየቱ አግሮቼን ሽባ ያደርግብኝ ይሆን? ወደ ዲያብሎስ ለመሔድ ዕድል ላግኝ እንጂ ይህንንስ መሞከሬ አይቀርም። ማንኛውንም መሰዋዕት ከፍዬ ሮያሌን በመልቀቅ ወደ ዲያብሎስ መሔድ አሰብኝ። ከዚያ በኋላ እናያለን።

«እንቅልፍ ወሰዶሃል እንዴ ፓፒ?»

«አልወሰደኝም።»

«ትንሽ ቡና ትፈልጋለህ?»

«ብታደርገውማ» አልኩና በተንጠልጣይ አልጋየ ላይ በመቀመጥ የትኩሱን ቡና ኩባያ ስቀበል፣ ግራንዴ ደግሞ የተለኮሰ ሲጃራ አቀበለኝ።

«ሰዓቱ ስንት ይሆናል?»

«ሰባት. ሰዓት። ጥበቃየን የጀመርኩት ግማሽ ሌሊት ላይ ነበር፣ ግን ስትገላበጥ ሰምቼ እንቅልፍ እንዳልወሰደህ ገመትኩ።»

«ልክ ነበርክ። የማቴዎስ ሞት በዕርግጥ መንፈሴን አቁስሎታል፤ አቀባበሩና

t.me/OLDBOOKSPDF

ዓሣነባሪዎቹ ደግሞ ከዚያ የሰሱ ነበሩ። የሚዘገንን ነበር።»

«ስለሁኔታው መስማት አልፈልግም ፓፔ። እንዴት እንደነበር መገመት እችላለሁ። እንተም መሐድ አልነበረብህም።»

«የደውሉ ታሪክ በጣም የተጋነነ ውሸት መስሎኝ ነበር። በቋጥኙ ዙሪያ የተተበተበው ስንሰለት ዐሣነባሪዎቹ እንዳይደርሱበት ያደርጋቸዋል ብየ ገምቼ ነበር። ምስኪን ማቴዎስ። ያ የሚዘገንን ገጽታ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ሲታየኝ ይኖራል። እስኪ ንገረኝ ግራንዴ፣ እነዚያን ሁለቱን ሰዎች በዚያ ቅልጥፍና እንዴት ልትገድላቸው ቻልክ?»

«ማቴዎስን ገደሉት ማለትን የሰማሁት፣ በደሴቷ ዳር ያለውን የልኳንዳውን ቤት የብረት መዝጊያ እየገጠምኩ እንዳለሁ ነበር። ቀትር ሆኗል። ወደ ካምፕ ከመሐድ ፈንታ ለመዝጊያው አንድ ነገር የሚያስፈልገኝ በመምሰል ወደ ወርክሾፑ አመራሁ። አንድ ያርድ ርዝመት ባለው ቱቦ ውስጥ በሁለት በኩል ስለት ያለው አንድ ሳንጃ መደበቅ ቻልኩ። የሳንጃው እጀታ አንደ ቱቦው ከፍት ነበር። ቱቦውን በዐሥራ አንድ ሰዓት ወደ ካምፕ ይገቼ ተመለስኩ። ዘበኛው ለምን እንደሆነ ሲጠይቀኝ፣ የተንጠልጣይ አልጋየ አግዳሚ እንጨት ስለተሰበረ በብረቱ ቱቦ ልተካው መሆኑን ነገረኩት። ወደ ከፍላችን ስገባ ገና ቀን ስለነበረ ገላ መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ ተውኩት። መጨለም ሲጀማምር ከስም ጥሪ በፊት ሐይኩና አመጣሁት። አርመናዊውና ሳንሱቹ ከተንጠልጣይ አልጋዎቻቸው ፈትለፈት፣ ጳውሎስ ትንሽ ወደ ኋላ ፈቀቅ ብሎ ቆሟል። እንደሚታወቀው የሐንስ ካስቴሊና ሉዊ ግራቮን ጀግና ሰዎች ነበሩ፤ ግን በማርጀታቸው የተነሣ ለእንደዚያ ዐይነቱ የጨበጣ ግብግብ ፈጥነው መንቀሳቀስ አልሆነላቸውም። እንተ ከመመለስህ በፊት ያንን እርምጃ ለመውሰድ የፈለግኩበት ምክንያት እንተ በነሱ እንዳትገባበት በማሰብ ነው። ሁኔታዎች ወዲያው ተቀላጥፈው ካልተከናወኑ፣ ካለብህ ሪኮርድ ጋር የመጨረሻውን ከፍተኛ ቅጣት ያስከትልብሃል። ከከፍሉ በእንደኛው ዳር ያለውን መብራት ዮሐንስ ሲያጠፋ፣ በሌላ በኩል ያለውን ግራቮን አጠፋ። ከሞላ ጎደል ጨለማ ሆነ፤ ብርሃን የሚታየው በመካከል ከሚገኘው የጋዝ ፋኖስ ብቻ ነበር። ዴጋ የለጠኝ አንድ ትልቅ የእጅ ባትሪ ነበረኝ። እኔ እየተከተልኩት፣ የሐንስ ወደፊት ተራመደ። ሁለቱ ሰዎች ዘንድ ሲደርስ፣ ባትሪውን በቀጥታ ዐይኖቻቸው ላይ አበራባቸው። አርመናዊው ዐይኖቹን ሊከልል ከንዱን ሲያነሣ፣ ጩቤዎን ልከ በጉሮሮው ላይ ለመትከል በቂ ጊዜ ሰጠኝ። ለሳንሱቹም የዚህ ተመሳሳይ ጽዋ ደረሰው። ጩቤውን መዘዘ፣ ሆኖም ማለም አልቻለም። ከፉኛ በኃይል ወግቼው ስለነበር ጩቤው በሌላ አቅጣጫ ዘለቀ። ጳውሎስ ግን፣ ወለሉ ላይ በፍጥነት ተወረወረና ወደ አልጋው ሥር ተንከባለለ። በዚያ ጊዜ ዮሐንስ ባትሪውን አጥፍቶት ስለነበር፣ ጳውሎስን ለማየት አልቻልኩም። ከመሞት የዳነውም በዚህ የተነሣ ነው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ወደ መታጠቢያው ውስጥ ማን ጎተታቸው?»

«አላውቅም። የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዎቻቸውን ከሆድዕቃዎቻቸው ውስጥ ለማውጣት የፈለጉ ከአነርሱው ጋር ያሉ ሰዎች መሆናቸውን ጠርጥሬያለሁ።»

«መቼም ደማቸው እንደ ጎርፍ መፍሰስ አለበት።»

«አትቀልድ አንጂ፣ እንደ ዕንጨት ደርቀው ነበር። ደማቸው እስከ መጨረሻዋ ጠብታ አንጥፍጥፍ ማለት አለባት። በእጅ ባትሪ የመጠቀሙ ሐሳብ የመጣልኝ ጩቤዎን በማዘጋጅበት ወቅት ነበር። በወርክሾፑ ውስጥ አንድ ዘበኛ የራሱን ባትሪ ድንጋይ እየቀየረ ነበር። ከዴጋ ጋር ወዲያው ግንኙነት ፈጠርኩና በአስቸኳይ ለእኔም እንዲፈልግልኝ ጠየቅኩት። አሁን ፍተሻ ሊያካሒዱ ይችላሉ ግን ምንም አይደል። ሳንጃውንም ሆነ ባትሪውን ሁለቱንም፣ አንድ ቁልፍ ያዥ አረብ ለዴጋ መልሷቸዋል። ስለዚህ ጣጣው ቀላል ሆኗል። የምቆጭበት ምንም ነገር የለም። ጓደኞችን ዓይኖቹ በሣሙና እንደተሸፈኑ ገደሉት፤ የእነርሱም ዐይኖች በመብራት እንደ ተሸፈኑ ገደልኳቸው። መሣ ለመሣ ነን። አንተስ ምን ትላለህ ፓፒ?»

«ትከከል ሠርተሃል። በጉዳዩ በጣም ፈጥነህ እርምጃ ስለ ወሰድከበትና፣ በተለይም እኔን ከነገሩ ውጭ በማድረግህ ውለታ አለብኝ።»

«ውለታ አለብኝ በማለት አታስብ፣ ማድረግ የሚገባኝን ነው የፈጸምኩት። አንተ ከመጠን በላይ ተሰቃይተሃል፣ ነጻነትህንም ለማግኘት በጣም ስለምትፈልግ እኔ ማድረግ ነበረብኝ»

«አመሰግናለሁ ግራንዴ። ዕውነት ነው፣ አሁን ደግሞ ከመቼውም የበለጠ ለማምለጥ ፈልጌያለሁ። በቅድሚያ ግን፣ ይህ ጉዳይ በዚሁ አልባት ማግኘቱን ማረጋገጥ አለብን። ዕውነቱን ለመናገር፣ አርመናዊው ማቴዎስን ከመግደሉ በፊት ለደባሎቹ ዕቅዱን አለማካፈሉ እስከዚህ አይገርመኝም። እንደዚህ ከመሰለው የፈሪ ግድያ ውስጥ ጳውሎስ ፍጹም አይደባለቅም። የሚያስከትለውን መዘዝ በሚገባ ጥርት አድርጎ ያውቃል።»

«እኔም አምኜበታለሁ። እነርሱ ጥፋተኞች ናቸው ብሎ የሚያስበው ጋልጋኒ ብቻ ነው።

«ዐሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ምን እንደሚሆን እስኪ እናያለን። የመጸዳጃ ቤቱን አልጠርግም። የታመምኩ እመስልና እንቅስቃሴውን እመለከታለሁ።»

ዐሥራ አንድ ሰዓት ሆነ። ‹የሥራችን› ተጠሪ እኛ ዘንድ መጣና፣ «ጓደኞቼ ወደዘበኞች ክፍል መሔድ ይገባኝ ይመስላችኋል? መጸዳጃ ቤቱ ውስጥ አሁን ሁለት ሬሣዎች አገኘሁ» አለ። ያ የሰባ ዓመት ሽማግሌ እሥረኛ ከሰው ሁሉ እኛን የፈለገው፣ ሰዎቹ ከተወጉበት ከዐሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ ምንም ነገር እንዳላወቀ ለማስመሰል ነበረ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ግራንዴ ለሽማግሌው በመጠኑ ጀርባውን ሰጠና፤ «ምን? ሁለት የደረቱ አስከሬኖች መጸዳጃ ቤቱ ውስጥ. አሉ ብለህ ልትነግረኝ ነው? እዚያስ ስንት ጊዜ ቆይተዋል?»

«አኔ እንዴት ዐውቃለሁ?» አለ ሽማግሌው። «ተኝቼ ነበር። አሁን ግን ወደ ሽንት ቤት ስሔድ ጭቃ የሚመስል ነገር አንሸራትቶኝ በግንባሬ ተደፋሁ። የሲጃራ መለኮሻየን ሳቀጣጥል ደም ሆነና አገኘሁት። ከዚያም መጸዳጃ ቤቱ ውስጥ አስከሬኖቹን አገኘኋቸው። »

«ለምን አርዳታ አትጠራምና የሚሆነውን አታይም?»

«ዘብ! ዘብ!»

ዘበኞቹ እየተሯሯጡ መጡ። «ምን ሆነህ ነው የምትጓጉረው አንተ አሮጌ ፍየል? ሣጥንህ በአሳት ተያያዘ? አለ ከመሀላቸው አንዱ።

«አይደለም ጌታዬ፤ በመጸዳጃ ቤቱ ውስጥ ሁለት ሬሣዎች ስላገኘሁ ነው።»

«ታዲያ አኔ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ? እንደገና ነፍስ ዘርቼ ልመልሳቸው? አሁን ዐሥራ አንድ ከሩብ ነው፤ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ሲደርስ ስለ ሁኔታው አንድ ነገር እናደርጋለን። ማንም ሰው ወደ መጸዳጃ ቤት እንዲቀርብ አትፍቀድ።»

«ይኸስ የማይሆን ነው። እንዴት አችላለሁ? ሰዎቹ መሸናት አለባቸው እኮ።»

«ልክ ነህ። ቆይ። ለተረኛው ዘበኛ ሪፖርት አደርጋለሁ።»

አምስት ዘበኞች ብቅ አሉ። ወደ ከፍሉ ውስጥ ይገባሉ ብለን ስናስብ ከፍርግርጉ አጠገብ ቆመ።

«ሁለት የሞቱ ሰዎች መጸዳጃ ቤት ውስጥ አሉ ነው የምትለው?»

«አዎ ጌታዬ»

«ከመቼ ጀምሮ?»

«አላውቅም። እኔ ያገኘኋቸው አሁን ነው።»

«እነማን ናቸው?»

«አላወቅኩም። ለመሸናት ስሔድ ነው ያገኘኋቸው።»

«ደህና፤ እንግዲያውስ ቂሎ፤ እኔ እነግርሃለሁ። ከእነርሱ አንደኛው አርመናዊው ነው። ሔደህ ተመልከተው።»

«አዎ፤ ልክ ነህ። አርመናዊውና ሳንሱቹ ናቸው።»

«አሺ፤ ስም ጥሪ እስከሚደረግ ጠብቁ» አሉና ተመለሱ።

በዐሥራ ሁለት ሰዓት የመጀመሪያው ደወል ተደወለ። መዝጊያው ተከፈተና ሁለቱ ቡና አዳዮችና የዳቦውም ሰው ከኋላ ተከትሏቸው ከቦታ ቦታ ይዘዋወሩ ጀመር።

በዐሥራ ሁለት ተኩል ሁለተኛው ደወል ተደወለ። አሁን የቀን ብርሃን ስለታየ

t.me/OLDBOOKSPDF

መኮላለፊያው በደም በተበከሉ የእግር ኮቴዎች ተሞልቷል። ሁለቱ የወህኒ አዛዦች መጡ። በዶክተሩና በስምንት ዘበኞች ታጅበው ነበር።

«ሁላችሁም ልብሳችሁን አውልቁና በየተንጠልጣይ አልጋዎቻችሁ ፊትለፊት በተጠንቀቅ ቁሙ! የእግዚአብሔር ያለህ! ይኸስ ዕውነተኛው ቄራ ሆኗል። በየቦታው ይምቱ!»

ወደ መጸዳጃ ቤቱ ቀድሞ የሔደው ምክትል የወህኒ አዛዡ ነበር። ተመልሶ በሚወጣበት ወቅት ፊቱ ልክ እንደአንሶላ ነጭ ሆነ። ደማቸው እንጥፍጥፍ ብሎ ደርቀዋል። በዕርግጥ ማንም ያየ ወይም የሰማ ሰው የለም?» አለ።

ረጭ ያለ ጸጥታ።

«አንተ፣ እንተ ደደብ ሽማግሌ፣ ትጠብቃለህ ተብለህ የተገመትከው እንተ ብርክ። እነዚህ ሰዎች እንደ እንጨት ደርቀዋል። ዶክተር፣ ከሞቱ ምን ያህል ጊዜ ይሆናቸዋል ትላለህ?»

«ከስምንት እስከ ዐሥር ሰዓቶች።»

«እና እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት ድረስ አላገኘሃቸውም? ምንም ነገር አላየህም? ምንም ነገር አልሰማህም?»

«አልሰማሁም፤ መስማት ይቸግረኛል፤ የማየት ኃይሌም ተዳክሟል። ከዚህም በተጨማሪ ዕድሜዬ ሰባ ዓመት ሲሆን፣ ወርባዎቹን ያሳለፍኩት በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ነው። ስለዚህ ብዙ ጊዜ አተኛለሁ። ወደ አልጋየ የመሔደው በዐሥራ ሁለት ሰዓት ነው፤ የነቃሁት መቼናት ስለፈለግኩ ብቻ ነው። እኔ ዘወትር የምነቃው በደውሉ ነው።»

«አዎ ልክ ነህ! ዕውነትም በደወል የምትነቃ» አለ አዛዡ በከፍተኛ ብሽቀት። «ዘበኞችም ሆኑ አሥረኞች፣ ማንም ሳይቀር ሌሊቱን ሙሉ የሰላም እንቅልፍ ተኝቻሁ። አባክችሁ ቃሬዛ ተሸካሚዎቹን ጥሩና ሁለቱን ሬሣዎች ወደ ሆስፒታል አፐራሲዎን ከፍል ውሰዷቸው። ዶክተር፣ የአስከሬን ምርመራ እንድታደርግላቸው እፈልጋለሁ። የቀራችሁት ደግሞ እንደዚሁ እንደሆናችሁ ወደ ግቢው ሮ ሰልፍ ውጡ።»

በሰልፍ እንደሆን በአዛዡና በዶክተሩ ፊት የሰውነታችንን እያንዳንዷን ኢንች እየመረመሩን ተራ በተራ አለፍን። ብዙዎቹ ደም ቢፈናጠቅባቸውም ማንም ሰው አልነበረም። ወደ መጸዳጃ ቤት በሚሔዱበት ወቅት የነካቸው መሆኑን አረጋዱ። ግራንዴ፣ ጋልጋኒና እኔ ምንም ነገር ሳይቀር ተመረመርን።

«ጋኒዮ፣ ቦታህ የቱ ጋው?» ማንኛውንም ያለኝን ነገር በሙሉ በረበሩ። «ጫቤህ ወዴት አለ?»

«ጫቤዬ ባለፈው ምሽት አንድ ሰዓት ላይ ከበሩ ባለው ዘበኛ ተወስዶብኛል።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ዕውነቱን ነው» አለ ዘበኛው። «.....ሁ ምክንያት ትልቅ ንትርክ ተፈጥሮ ነበር፤ በተጨማሪም ሊገደሉኝ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ ሲል ነግሮኛል።

«ግራንዴ፣ ያ ጩቤ የአንተ ነው?»

«የተገኘው በእኔ መኝታ ላይ እስከሆነ የእኔ መሆን አለበት!»

አዛዡ በጥንቃቄ መረመረና ልከ እነደ አዲስ ሳንቲም ንጹሕ መሆኗን አየ።

ዶክተሩ ከመጸዳጃ ቤት ተመለሰ። «ሰዎቹ የተገደሉት በሁለት በኩል ስለት ባለው ሣንጃ ሲሆን፣ የተወጉት እንደ ቆሙ ነበር። ለማመን የሚያስቸግር ነው። ራሱን ለመከላከል ሳይሞክር ልከ እንደ ጥንቸል የሚገደል ማንም አሥረኛ የለም። አዚህ አንድ የቆሰለ ሰው መኖር አለበት።»

«ግን ራስህ አይተሃልኮ ዶክተር። አንዲት ጭረት ያለው ማንም ሰው የለም።»

«እነዚህ ሁለት ሰዎች አደገኞች ነበሩን?»

«በጣም እንጂ! አርመናዊው ያለጥርጥር የካርቡኔሪ ገዳይ ነው። የገደለውም ገላ መታጠቢያው ውስጥ ትላንት ጧት ሦስት ሰዓት ላይ ነበር።»

«ሁኔታው እንዲመዘገብ ይሁን» አለ አዛዡ። «የግራንዴን ጩቤ ለይታችሁ አስቀምጡ፣ ከታመማችሁት በስተቀር አሁን ማንኛውም ሰው ወደ ሥራው ይሒድ። ፓፒዮ፣ አንተም አሞኛል ብለህ አመልከተሃል እንዴ?»

«አዎ ጌታዬ።»

«ለጓደኛህ መበቀል ብዙም ጊዜ አላጠፋህ። ዕድለኛ ነህ፣ ማረጋገጫ አላገኘሁብህም፣ ምንም እንደማላገኝ ደግሞ ዐውቃለሁ። ለመጨረሻ ጊዜ፣ የምትናገሩት አላችሁ? በዚህ ድርብርብ ወንጀል ላይ ብርሃን ለመፈንጠቅ የሚችል ማንም ሰው ቢገኝ በነፃ ወደ ግራንዴቴሬ ይላካል። ታሴን እመኑ።»

ረጭ ያለ ጸጥታ።

የአርመናዊው ደባሎች በሙሉ አሞናል ብለው አመለከቱ። ያመለከቱትም ግራንዴ፣ ጋልጋኒ፣ የሐንስ ካስቴሊና ሉዊ ግራንቨን መታመማቸውን ከገለጹ በኋላ በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ ነበር። ክፍሉ ባዶ ሆነ። ያለነው ከእኔ ጋር እምስታችንና ከአርመናዊው ጋር ያሉት አራቱ፣ በተጨማሪ ሰዓት አዳሹ፣ ተከማችቶ በሚጠብቀው የጽዳት ሥራ የሚያጉመተምተው ሽማግሌና የአልላቲያኑን ተወላጅ - ታላቁን ሲለቪያንን ጨምሮ ሌሎች ሁለት ወይም ሦስት ቢሆኑ ነበር።

ሲልቪያኑ የሚኖረው በብቸኝነት ሲሆን፣ ጓደኞቹ በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ይገኙ የነበሩት ብቻ ናቸው። ለሐያ ዓመት ጽኑ እሥራት ያበቃውን እንድ ልዩ ድርጊት ያቀነባበረና ከፍተኛ አከብሮት የተሰጠው ተግባራዊ ሰው ነበር። ከፓሪስ - ብራሰልስ በሚመላለሰው ፈጣን ባቡር ላይ የሚገኝ አንድ ትንሽ የፖስታ ቍርጎ ራሱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብሯውን አጥቅቶ ሁለቱን ዘበኞች ከዘረረ በኋላ የፖስታ ክረጢቶቹን ግብረአበሮቹ አንዲያነሷቸው ወደ አንድ ወንዝ ዳርቻ የወረወረ ነበር። ከዚያ ድርጊት በጣም ጠቀም ያለ ገንዘብ አትርፏል።

ለአንድ ሳምንት ያህል ያለጠብ ለመቆየት መስማማታችንን ባለመረዳቱ ሁለቱ ጎረቤቶቻችን ሲንሾካሾኩ የተመለከተው ሲልቪያን፣ «የከረረ ጦርነት ለመክፈት ፍላጎት አንደሌላችሁ ተስፋ አለኝ» አለ።

«ዛሬ አንከፍትም» አለ ጋልጋኒ። «ያ ለወደፊት ነው።»

«ለምን ወደፊት?» አለ ጳውሎስ ። «ዛሬ ማድረግ የምትችለውን እስከ ነገ ፍጹም አታቁየው። በበኩሌ እርሰ በርሳችን የምንገዳደልበት ምክንያት አይታየኝም። አንተስ ምን ትላለህ ፓፒዮ?»

«አንድ ጥያቄ ብቻ አለኝ። አርመናዊው ምን ለማድረግ ፈልጎ እንደነበረ ዐውቀሃል?

«የመሐላ ቃሌ ነው ፓፒ፣ አንድ ነገር አላውቅም። እንዲያውም አንድ ነገር ማወቅ ትፈልጋለህ? አርመናዊው ቀደም ብሎ ባይሞት ኖሮ እኔ ራሴ አለቀውም ነበር።

«ታዲያ ሁኔታው እንዲህ ከሆነ፣ ቅራኔውን አሁኑኑ ለምን አንረሳውም?» አለ ግራንዴ።

«በእኔ በኩል እሺ። ማንኛውንም አሳዛኝ ድርጊት እንርሳና እንጨባበጥበት።»

«ተስማማን።»

«እኔም ምስክር ነኝ» አለ ሲልቪያን። «በማብቃቱም ተደስቻለሁ።»

በአሥራ ሁለት ሰዓት ደወሉ አስተጋባ። በምሰማበት ጊዜ ያለፈውን ዕለት ትዕይንት እንደገና ከማየት ልገታ አልቻልኩም። የጓደኛዬ አካላት ቀጥ እንዳለ ወደ ጀልባችን አቅጣጫ ሲያመራ ከሐያ አራት ሰዓት በኋላ እንኳ ሥሉ ቁልጭ ብሎ ይታየኝ ነበር፤ ለአርመናዊውና ለሰንሰቹ እንኳ ተመሳሳይ ዕድል ልመኝላቸው አልቃጣሁም።

ጋልጋኒ አያወራም ነበር። በተንጠልጣይ አልጋው ላይ እግሮቹን አንፈራጦ እንደ ተቀመጠ በቀጥታ ወደ ፊትለፊቱ አተኩሮ ይመለከታል። ግራንዴም ገና ወደ ውስጥ አልገባም። አሁንም ፊትለፊት አየተመለከተ ለሰስ ባለ ድምፅ፣ «ማቴዎስን ባገኙት በእነዚያው ተመሳሳይ ዓሣነባሪዎች ያም የውሻ ልጅ አርመናዊ እንዳይበላ እመኛለሁ። ሁለቱም በአንድ ዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ መግባታቸው ጸጸታችንን ሊበዛ የከፋ ያደርገዋል» አለ።

የዚያ ድንቅ ጓደኛ መታጣት በልቤ ውስጥ አንድ ትልቅ ባዶ ቦታ ፈጠረ። በተቻለ ፍጥነት ከሮያሌ መልቀቅ አለብኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሁን ጦርነት ስለሚካሔድ ቅጣቱ ከመቼውም የበለጠ ከባድ ነው፤ አምልጠው ላያመልጡ አጉል ሙከራ የማድረጊያው ወቅት አሁን አይደለም፤ አይመስልህ ሳልቪዲያን፣» የምነጋገረው ኮንቮዩ ውስጥ ዐመቀው ከነበረው ባለ ወርቅ የንዘባ መደበቂያ ቱቦ ካለው ኢጣሊያዊ ጋር ማምለጥን በሚመለከት ስለ ወጣው አዲስ መለሰሜ የሚያስረዳውን ማስታወቂያ አንብበን በገላ መታጠቢያው ውስጥ እንደ ተቀመጥን ነበር። «ግን ያም ሆኖ የሞት ቅጣት ቢጠበቅኝም ከመሞከር የሚያግደኝ አይኖርም። የአንተስ ሀሳብ እንዴት ነው?»

«ፓፒዮ፣ እኔም ከእንግዲህ በአሁኑ ኑሮዬ መግፋት አልችልም። የፈለገው ነገር ይሁን መሔድ አለብኝ። በዕብዶች ሆስፒታል ውስጥ በጤና ረዳትነት አንድ ሥራ ጠይቄያለሁ። እዚያ ካለው ግምጃ ቤት ውስጥ አንድ ጥሩ ጀልባ የሚወጣቸው ሁለት ባለ ሃምሳ አምስት ጋሎን በርሜሎች አሉ። እንደኛው ሙሉውን የወይራ ዘይት፤ ሌላው ሆምጣጤ ይዟል። አንድ ላይ በጥበቅ ከታሠረ እንደምገምተው ግራንዴቴሬ ለመድረስ ጥሩ ዕድል ይኖራል። ከሕንፃው በስተውጪ በኩል ያለው ግንብ ቁጥጥር የለበትም። በውስጥ በኩል ያለውም የሕክምና ክፍሉ አንድ ዘበኛና በሕመማኑ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ጥቂት ኦሥረኞች ብቻ ይገኙበታል። ከእኔ ጋር ለምን ወደዚያው አትሔድም?»

«እንደ ጤና ረዳት ሆኜ?»

«ይህንንስ ዕድል አይሰጠህም ፓፒዮ። በዕብዶች ሆስፒታል እንድም ሥራ ፍጹም እንደማይሰጠህ ራስህም በሚገባ ታውቃለህ። ከካምፑ በጣም የራቀ ስለሆነ፣ ቁጥጥሩ በጣም የላላ ነው፤ ፍጹም ወደ ቦታው እንድትቀርብ አየፈቅዱልህም። ግን እንደ አንድ እብድ ሆነህ መግባት ትችላለህ።»

«ሳልቪዲያ፣ በዕውነቱ ይህስ ከበድ ይላል። አንድ ዶክተር እብድ ሆነሃል ብሎ ከመስከረልህ የፈለግከውን ማንኛውንም ነገር እንድታደርግ መብት ሰጠህ ማለት ነው። ከዚያ ወዲያ ለምታደርገው ተጠያቂ አይደለህም። ይህን አምኖበት ስለ ሕመሙ ሲፈርም ዶክተሩ የሚወስደውን ኃላፊነት እሰኪ ንገሮት፣ ብትፈልግ አንድ ኦሥረኛ፤ ወይም አንድ ዘበኛ፣ አንዲት የዘበኛ ሚስት፣ አንድ የዘበኛ ልጅ፣ ማንኛውንም መግደል ትችላለህ። ካሻህም ማምለጥ ትችላለህ፤ ምን አለፋህ በጽሑፍ የተመዘገበን ማንኛውንም ዓይነት ወንጀል መፈጸም ትችላለህ፤ ሕግ አያግድህም። ማድረግ የሚችሉት አስከፊ ነገር ቢኖር በአንድ የቆረፈደ ሽራ ጠቅልለው ድርበርብ ግንብ ውስጥ ማስቀመጥ ብቻ ነው። ያንን እንኳ በጣም ለረጅም ጊዜ ማድረግ አይችሉም፤ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ያላሉታል። ምትሠራው ወንጀል የፈለገውን ያህል ከባድ ይሁን፣ ማምለጥ እንኳ ብትሞክ-

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተጠያቂነት ነፃ ነህ።»

«ፓፒዮ አምንሃለሁ፣ በዕርግጥም ከእንተ ጋር ለማምለጥ አፈልጋለሁ። እኔን ከአብዶቹ ጋር ለማገናኘት የመጨረሻውን ጥረት አድርግ። ለእንተ መሲይ ጤነኛ ሰው እነዚያ ሁሉ አብዶች መካከል አሸባሪነቱ የቱን ያህል እንደሚሆን አንነዘባለሁ። ግን እኔ ጤና ሪጳት እስከሆንኩ ድረስ፣ ጠበቅ ያሉ ጉዳዮችን ልረዳህና ከጎንህ ልቆም እችላለሁ።

«ሮሚዎ፣ እንተ ወደ አብዶቹ ሆስፒታል ሒድ። እኔ በሁኔታው ላይ አተኩርበትና ዶክተሩን ማሳመን እንድችል የዕብደት መነሻ ምልክቶችን አጠናለሁ። እንዳልከው ከተጠያቂነት ነፃ አድርጎ ቢመድበኝ እስከዚህ መጥፎ ነው አይባልም።»

በአንድ ከባድ ጥናት ተጠመድኩ። በወህኒ ቤቱ ቤተመጻሕፍት ውስጥ ይሆን በሚመለከት መጽሐፍ አልነበረም፤ ስለሆነም በማንኛውም አጋጣሚ ፉመው ከዳኑ ሰዎች ጋር እወያያለሁ። ስሜቱ እንዴት እንደሚያደርግ ቀስ በቀስ ግልጽ ሆነልኝ፣

1. ዕብዶች በሙሉ ከባድ የራስ ሕመም ይሰማቸዋል።

2. ጆሯቸው ውስጥ ሁልጊዜ ጭው ይልባቸዋል።

3. በጣም ብስጩ ከመሆናቸው የተነሣ በአንድ ጎናቸው ረግተው በምንም ዐይነት ለረጅም ጊዜ አይተኙም። ከአእምሯቸው መረበሽ የተነሣ ስለሚወራጩ፣ የሚደርስባቸው መዛል ይህ ነው አይባልም።

ዋናው ቁም ነገር እነዚህ ምልክቶች እንዲደርሱባቸው ማድረጉ ሲሆን እንዳይነቃብኝም ላለማጋነን አሰብኩ። የአብደቴ አደገኛነት ዶክተሩ ወደ ዕብዶች ሆስፒታል ለመላክ እስኪያበቃኝ ድረስ እንጂ እንደ ለየለት ወመኔ ሸሚዝ እስከ መቦጫጨቅ፣ እስከ መደባደብ በቀዝቃዛ ወይም በሞቀ ውኃ እስካለመታጠብ ወዘተ ... የሚያደርስ መሆን የለበትም። ዘዴውን በትክክል ከተጠቀምኩበት ዶክተሩን ለመሸወድ አችል ይሆናል።

የማይለየኝ አንድ ሐሳብ ነበር። በማታለል ዕብድ ለመሆን ለምን ፈለግኩ? ለዚህ ጥያቄ ቀጥተኛ የሆነ መልስ ዶክተሩ ማግኘት እስካልቻለ ድረስ ማምለጥ እችላለሁ። ለማንኛውም ብቸኛው ዕድሌ ይኸው ነበር። ወደ ዲያብሎስ መሔድ ከልክለውኝ ስለነበር፣ ከጓደኛዬ ሞት በኋላ ካምጮን መቋቋም አልቻልኩም። ማቅማማት የሚባለው ነገር ገሃነም ይግባ! ውሳኔየን አሳልፈያለሁ። ሰኞ ዶክተሩ ዘንድ አሔዳለሁ። አይሆንም፣ ራሴው ማመልከት የለብኝም፣ አንድ ሌላ ሰው በያደርገው ይሻላል። ሊታመን ለሚችል አንድ ሰው አንድ ሁለት ለወጥ ያሉ ትርዒቶችን በሳጥናችን ውስጥ አሳያለሁ። ከዚያም ዘበኞችን በሁኔታዬ በመገረም ለምርመራ ይመዘግበኛል።

ሶሥስት ቀን አልተኛሁም፣ አልታጠብኩም፣ ጺሜን አልተላጨሁም። ከሞላ ጎደል ምንም ነገር አልበላሁም። ጭራሽ ያልነበረውን ፎቶዬን ለምን አነሣሁኝ ብዬ

t.me/OLDBOOKSPDF

ትላንት ጎረቤቴን ጠየቅኩት። ከእኔ ንብረቶች አንድ ነገር ፍጹም እንዳልነካ ማለልኝ። ሁኔታው በጣም ስላበሳጨው ቦታውን ለወጠ። ሾርባችን ከአደላ በፊት ዘወትር ለትንሽ ጊዜ በብረት ድስቱ ውስጥ እንደሆነ ይቆያል። ወደ ብረት ድስቱ ራመድ አልኩና ሁሉም ሰው እያየኝ ሸናሁበት። ስለ ተገረሙ መሆን አለበት፤ ሁሉም ፊቴን ከመመልከት በስተቀር ትንፍሽ አላሉም።

ጓደኛዬ ግራንዴ፤ «ፓፒዮ፤ ለምን እንደዚህ አደረግክ?» አለ።

«ምክንያቱም ጨው ሳይጨምሩበት ስለቀሩ ነው» አልኩና፤ ለሴሎቹ ምግም የተለየ ስሜት ሳላሳይ ሣህኔን ይገር ዘበኛው እንዲጨልፍልኝ ወደፊት ዘረጋሁለት።

ሁሉም ሰው ሾርባዬን ስበላ በጸጥታ ይመለከተኝ ነበር። እነዚህ ሁለት አድራጎቶቼ ዕቅዴን አሳኩልኝ። እኔ አንድም ቃል ሳልናገር ወደ ዶክተሩ ተወሰድኩ።

«ደህና ነህ ዶክተርዬ?» ስል ጠየቅኩት። ከዚያም ያንኑ ጥያቄ ደጋገምኩ። ዶክትሩ ተደናግሮት ትክ ብሎ ተመለከተኝ። እኔም ዘወትር በተለመደው ሁኔታ ተመለከትኩት።

«አዎ፤ ደህና ነኝ» አለ ዶክተሩ። «ታመሃል እንዴ?»

«አልታመምኩም።»

«ታዲያ ለምን ወደ እኔ መጣህ?»

«ያለ አንድ ምክንያት። አንተው ታመሃል ብለው ነገሩኝ። እውነት አለመሆኑን በማወቄ ደስ ብሎኛል። ደህና ሁን።»

«አንድ ጊዜ ቆይ ፓፒዮ። ተቀመጥ። እስኪ ወደ እኔ ተመልከት።» ከዚያም ዶክተሩ ትንሽ የብርሃን ጨረር ባላት አንዲት ባትሪ ዐይኖቼን መረመረ።

«የጠበቅከውን ለማየት አልሆነልህም፤ ሆነልህ እንዴ ዶክተርዬ? ባትሪህ በቂ ኃይል የላትም። ግን ያው ነው፤ ሁሉንም እንደምትረዳው እገምታለሁ፤ ልከ ነው? ንገረኝ እስኪ፤ ለመሆኑ አየኻቸው?»

«ምኑን ነው የማየው?» ሲል ዶክተሩ ጠየቀ።

«ቂል አትሁን እንጂ። የሰው ዶክተር ነህ ወይም የከብት ሐኪም? ከመሰወራቸው በፊት አላየኋቸውም ብለህ ልትነግረኝ ነው እንዴ? ምናልባት ልትነግረኝ ስላልፈለግህ እንደሞኝ እየተጫወትክብኝ ይሆናል።»

ዐይኖቼ በድካም ይሰለመለማሉ። ጺሜን አለመላጨቴና አለመታጠቤ ረድቶኛል። ዘበኞቹ እንደ ተገተሩ ያዳምጣሉ፤ ግን እነርሱን ጣልቃ ሊያስገባ ከሚያስችል ከማንኛውም ድርጊት ተቆጥቤያለሁ።

ዶክተሩ እኔን ላለማስቆጣት ምርመራውን በዘዴ ተያያዘው። ብድግ አለና እጁን ትከሻየ ላይ አስቀመጠ። «አዎ ፓፒዮ፤ ልነግርህ አልፈለግኩም እንጂ በሚገባ

t.me/OLDBOOKSPDF

አይቻቸዋለሁ።»

«ዶክተርዬ፣ ራስን መቆጣጠር በሚለው የቅኝ ግዛት አርኩስ ፈሊጥ እየዋሸህ ነው። አንድም ቅንጣት ነገር አላየህም! በግራ ዐይኔ ውስጥ ያሉትን ሦስት ጥቁር ነጥቦች ለማየት ቂምጠህ ነበር። እኔ የማያቸው ወደ ሕዋ ስመመለከት ወይም ሳነብ ብቻ ነው። መስታወት ስመለከት ዐይኔን ጥርት ብሎ እየዋለሁ፤ ሦስቱ ነቁጦች አይኖሩም። መስታውቱን ሳነሣ ይደበታሉ።»

«ሆስፒታል አስገቡት» አለ ዶክተሩ፤ «ወደ ካምፕ ሳትመልሱ ቶሎ እዚያው እንድትወስዱት። ፓፒዮ፣ አንተ አልታመምክም ነው የምትለው፣ ምናልባት ይሆናል፤ ግን እንደ መሰለኝ በጣም ደክሞሃልና ለትንሽ ቀናት ሆስፒታል እንድትቆይ እፈልጋለሁ፤ ፈታይኛ ነህ?»

«ምንድን ነው ልዩነቱ? ሆስፒታልም ሆነ ካምፑ ሁሉም ያሉት ያው ደሴቶች ላይ ነው።»

የመጀመሪያውን ደረጃ ተወጠቼው ነበር። ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሆስፒታል ተወሰድኩና ነጭ አንሶላ የተነፈጠበት ንጹሕ አልጋና ወለል ያለ መብራት ያለበት ክፍል ውስጥ ገባሁ። መዝጊያው ላይ ያለው ጽሑፍ፤ «ቁጥጥር ሥር የሚገኝ» ይላል። ቀስ በቀስ በመላ ምት እየተረዳሁ የወጣልኝ ዕብድ ሆንኩ። አደገኛ ጨዋታ ነበር። አፌን የማጣመምና የታችኛውን የውስጥ ከንፈሬን የመንከስ እንቅስቃሴ ፈለሰፍኩ። እንዴት እንደሆነ በአንድ መስታወት አጠናሁና በጣም ስለ ተለማመድኩት፣ እንዲያውም ያለ ምንም ጥረት አቀላጥፈው ጀመር። ጨዋታውን ለረጅም ጊዜ መቀጠል የለብህም ፓፒ። ስንኩል ለመምሰል የምታደርገው ጥረት ከባድ ጠንቅ ያስከትልብህና እንዲያውም እስከ መጨረሻው ገጽታህን ያበላሸዋል። ዓላማየን መምታት ስለሚኖርብኝ፣ ሙሉ ስሜት አሁንም ገና ጨዋታውን መቀጠል ነበረብኝ። ራሴን ከተጠያቂነት ውጭ መድቤ ወደ ዕብዶች ሆስፒታል መግባትና ከጓደኛዬ ጋር አምልጬ መሔድ ይኖርብኛል። ማምለጥ የሚለው ምትሐታዊ ቃል ተሸከም ሲወስደኝና በሁለቱ በርሜሎች ላይ አንፈራጥጬ ከጣሊያናዊው ጤና ረዳት ጓደኛዬ ጋር ወደ ግራንዴቴሬ ስሄድ ከአሁኑ ታየኝ።

ዶክተሩ በየቀኑ በአጠገቤ ሲያልፍ ይቆማል። እኔን በመመርመር ረጅም ጊዜ ያሳልፋል፤ ዘወትር እርስ በርሳችን በትሕትናና በመልካም መግባባት እናወራለን። ተግትቶበታል። ሆኖም፣ ገና አላመነበትም። ስለዚህ ማጅራት የሚጨመድደው በሽታ የመጀመሪያ ምልክት እንደሚያሰቃየኝ ነገርኩት።

«እንደምን አለህ ፓፒዮ? ጥሩ እንቅልፍ ተኛህ?

«አዎ ዶክተር አመሰግናለሁ። በጣም ግሩም ነው። ማች የተሰኘውን መጽሔትህን ስላዋስከኝ አመሰግናለሁ። እንቅልፍ ስላልከው ግን ያ ሌላ ጉዳይ ነው።

t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ሲያጠጡ እንደሆነ አላውቅም፤ ከከፍሌ በስተጀርባ ቧንቧ ሌሊቱን ሙሉ ሲንሿሿ ይሰማኛል። ያ ድምፅ እንደ ገደል ማሚቶ ይጮህብኛል። ሌሊቱን ሙሉ በዚህ ዓይነት ይቀጣላል። ልቋቋመው አልቻልኩም። ከፍሌን ብታስቀይርልኝ በጣም ባለውለታዬ ትሆናለህ።»

ዶክተሩ ወደ ጤና ረዳቶቹ ተጠራ ዘበኛ ዘወር አለና በዝግታ፤ «የቧንቧ ውሃ አለ እንዴ?» አለው።

ዘበኛው ራሱን ነቀነቀ።

«ዘበኛ፤ ወደ ሌላ ከፍል አስገባው። ወደ ማንኛው መሔድ ትፈልጋለህ?»

«ከዚህ እርኩስ ቧንቧ በተቻለ መጠን ሩቅ ቦታ። ከአድራሹ የመጨረሻ ዳር። አመሰግናለሁ ዶክተርየ።»

መዝጊያው ተዘጋ፤ በከፍሌ ውስጥ ብቻየን ነበርኩ። ግን ከድምፅ ከትትል ብዙም አልተላቀቅኩም ነበር። በመሰለያዋ ቀዳዳ እጠበቃለሁ። የእርምጃዎቹን እንቅስቃሴ አልሰማሁም ዶክተሩ መሆን አለበት። ራሴው የፈጠርኩት ቧንቧ በስተጀርባ አለበት ብየ በምገምትበት ግድግዳ ላይ ቶሎ ቡጢየን አጣበቅኩበትና ጮኽኩ። ግን ድምጼን በጣም ከፍ ሳላደርግ ነበር። « አቁም! አቁም አንተ ግም! ያን ብስብስ ውሃ መቅዳትህን መቼ ነው የምትጨርሰው?» ብየ፤ ከዚያም አልጋየ ላይ ተወርውሬ ጭንቅላቴን ከትራሴ ሥር ደበቅኩ።

ትንሿ የነሐስ ከዳን በቀዳዳዋ ለይ ስትዘጋ አልሰማኋትም። ግን ወደ ኋላ የሚመለሱ የእርምጃዎች ድፅ መለየት ችያለሁ።

በዚያው ቀን ከሰዓት በኋላ ከፍል ቀየርኩ። ጥሩ ትርዒት ያሳየሁ መሆን አለበት፤ ምክንያቱም ወደ አዲሱ ከፍል ለምትወስደው አጭር ጉዞ፤ እኔን ለማጀብ ሁለት ዘበኞችና ሁለት ጤና ረዳቶች ተመድበው ነበር። አንድ ቃል አልተነፈሱም፤ ስለዚህ እኔም አላናገርኳቸውም። በፀጥታ ብቻ ተከተልኳቸው። ከሁለት ቀን በኋላ ሁለተኛውን የሕመም ምልክት ፈጠርኩ የጆሮ ውስጥ ጫጫታ።

«እንደምን አለህ ፓፒየ? የሰጠሁህ መጽሐት ጨረስከ?»

«አልጨረስኩም፤ ፈጽሞ አልቻልኩም። ቀኑን ሙሉና ሌሊቱን በከፊል ያሳለፍኩት፤ ቢምቢዎችን ወይ ትንኞችን አፍናለሁ እያልኩ ስታገል ነበር። ጎጇቸውን በጆሮየ ውስጥ ሠርተዋል። በአንድ ቁራጭ ጥጥ ጠቅጥቄው ነበር፤ ግን አልሠራም። ከንፎቻቸው የሚጥሩትን ዚን - ዚን - ዚን የሚል ድምፅ ማቆም የምችል አይመስለኝም። ፍጹም አያቆምም። ደም ነው የሚያፈሉት ዶክተርዬ ምን ይመስልሃል? ምናልባት ልናፍናቸው፤ ይህ ካልሠራ ደግሞ ልናሰምጣቸው እንችላለን? ምን ይመስልሃል?»

የአፈን መጣመም ዶክተሩ ተመለከተ። ከዚያም እጁን ወደ ራሱ እጅ ወስዶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሀይኖቼን ትከ ብሎ ተመለከተኝ። ተደናግሮት እንደነበረ ተሰማኝ።

«አዎ፣ የእኔ ወዳጅ፣ እናሰምጣቸዋለን። ቻታል፣ ጆሮዎቹ እጥበት ተደርጎላቸው እንደሆነ ተከታተል።»

እነዚህን ትርጓሮች ዘወትር ጧት በተለያየ ሁኔታ እየቀያየርኩ ደጋምኩ፣ ግን ዶከተሩ ስለ እኔ ወደ ዕብዶች ሆስፒታል መላክ ገና አልቆረጠም ነበር።

ቻታል አንድ የቭሮማይድ መርፌ ሲወጋኝ፣ «ለጊዜው ሁኔታው እየተመቻቸልህ ነው። ዶከተሩ ግራ ተጋብቷል፤ ግን ወደ ዕብዶች ሆስፒታል ከሚልክህ በፊት ገና ረጅም ጊዜ ሊወስድበት ይችላል። ነገሮችን ለማፋጠን ከፈለግክ፣ አደገኛ መሆን እንደምትችል አሳየው» ሲል አስጠነቀቀኝ።

በቻታልና በሁለት የሕክምና ከፍሉ ጤና ረዳቶች ታጅቦ፣ የከፍሌን መዝጊያ በመክፈት ላይ እንዳለ ነበር ዶከተሩ የተለመደውን የወዳጅነት ሰላምታ ያቀረበልኝ። «እንደምን አለህ ፓፒዮ?»

«ዶከተር፣ ይህን የማይረባ መደለያ አትስጠኝ! በጣም ቁጡ ሆኜ ነበር።

«እንዴት እንደሆንኩ የምታውቀው ቅንጣት ነገር የለም። ከእኔ አሰቃይ ጋር የተሻረካችሁት ማንኛችሁ ሆናችሁ ማወቅ አፈልጋለሁ!»

«ማን እያሰቃየህ ነው? መቼ? እንዴት?»

«ዶከተር፣ የዶከተር ደ አሶንቫል ምርምሮችን ታውቃለህ?»

«አዎ።»

«የአንጀት ቁስል በያዘው አንድ ሕመምተኛ ዙሪያ ያለውን ከባቢ አየር በከፍተኛ የአየር እንቅስቃሴ ግፊት ለመለወጥ የሚያስችል መሣሪያ መፈልሰፉን ታውቃለህ። ተንቀሳቃሹም አየር የኤሌክትሪክ ሞገዶችን ይሰጣል። ታዲያ የእኔ ጠላት የሆነ አንድ ሰው ከካየን ሆስፒታል ያንኑ ዐይነት አንድ መሣሪያ የሰረቀ ይመስለኛል። በየጊዜው ልተኛ ስል የአየሩን ሞገድ መከፈቻ ጫን ሲለው፣ የኤሌክትሪኩ ሙሌት በቀጥታ ሆዴን ይመታኛል። በአንድ ግፊት ከአልጋዬ በአምስት ኢንች ወደ ላይ ያነጥረኛል። ይህ ነገር እያለ እንዴት ይተኛል ብለህ ትጠብቃለህ? ሴሊቱን በሙሉ ካጠቢ ትኖኝ አይሔድም። ዐይኖቼን ለደቂቃ ስከድን፣ ድም ይልና ኤሌክትሪኩ ይነሣል። በጠቅላላው አካላቴ ልክ እንደ አረግራጊ ሽቦ ይንዘፈዘፋል። ከእንግዲህ ወዲያ ሰቋቋመው አልችልም ዶከተር። የምጠረጥረውን የመጀመሪያ ሰው እንደምገድል ሰሙም ንገር። አርግጥ መሣሪያ የለኝም፣ ግን ማንም ሰው ይሁን፣ ሲጥ አድርጌ የማንቅበት በቂ ጡንቻ አለኝ። ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷል! ስለዚህ እንደምን አለህ ፓፒዮ፣ የምትለውን መመጻደቂህን ይዘህ ገደል ግባ። እደግመዋለሁ፣ እንደዚያ የመሰለ መሸንገያ እንዳትሰጠኝ!»

t.me/OLDBOOKSPDF

ግጭቱ ፍሬ አፈራ። ዘበኞቹ በቅርብ እየተከታተሉ እንዲጠብቁኝ ዶክተሩ አስጠንቅቋቸው እንደነበረ ቻታል ነገረኝ። ሁለት ወይ ሦስት ካልሆኑ በስተቀር ምንጊዜም መዝጊያየን መከፈት እንደሌለባቸውና ሲያናግሩኝም ዘወትር በእርጋታ መሆን እንዳለበት መከሯቸዋል። የራሴው ድርጊት መንፈሴን ኢያሰቃየኝ ስለነበር ወደ አብዶቹ ሆስፒታል ባስቸኳይ መሔድ ይገባኛል።

«ጥሩ አድርገህ በላህ ፓፒ?»

«አዎ ቻታል፣ በጣም የሚጥም ነበር።»

«ከእኔና ከሚስተር ግንስ ጋር መሔድ ትፈልጋለህ?»

«ወዴት?»

«ወደ ዕብዶች ሆስፒታል፣ መድኃኒት ልናደርስ ነው። ለአንተም ጥሩ ሽርሽር ይሆንሃል።»

«እንግዲያማ እንሒድ።»

ሦስታችንም ወደ ዕብዶች ሆስፒታል ጉዞ ጀመርን። ወደዚያው ስንቃረብ ነበር ቻታል፣ «ፓፒ ካምቹ አልሰለቸህም እንዴ?» ሲል የጠየቀኝ።

«በእርሱ ጥላቻ ታምሚያለሁ፣ በተለይ ጓደኛዬ ካርቡኔሪ ከጠፋ ጀምሮ።»

«አብዶች ሆስፒታል ጥቂት ቀናት ለምን አታሳልፍም? በዚህ ዓይነት ምናልባት ባለኤሌክትሪኩ ሞገድ ሰውዬም ሊያገኝህ አይችል ይሆናል።»

«ሐሳቡ የሚከፋ አይደለም፣ ግን ምንም የተለየ ነገር ሳይታይብኝ ይቀበሉኛል ብለህ ትገምታለህ?»

በቻታል አስተያየት ወጥመድ የገባሁ ስለመሰለው ዘበኛው በጣም ደስ አለውና፣

«ለእኔ ተውልኝ። ራሴው እጨርስልሃለሁ» አለ።

ሰለዚህ አንድ መቶ አብዶች ከሚገኙበት ሆስፒታል ውስጥ ገባሁ። ከአብዶች ጋር ኑሮ በሚያረገርግ አልጋ ላይ መተኛት አይደለም። ጤና ረዳቶቹ ከፍሎቹን በሚጸዱበት ወቅት፣ በሠላሳ ወይም በአርባ ቡድን እየተሰበሰብን ግቢው ውስጥ እንናፈሳለን። ሴትና ቀን ማንኛውም ሰው ዕርቃኑ ሥጋውን እንደሆነ ነበር። ደግነቱ መቀት ነው። ካልሲ እንዳደርግ ለእኔ ፈቀዱልኝ።

እንድ ጤና ረዳት የተለኮሰ ሲጃራ አቀበለኝ። እዚህ አምስት ቀን ሆኖኝ ነበር። ሆኖም ከሳልቪዲያ ጋር ገና ግንኙነት ለማድረግ አለመቻሌን ያወቅሁት ፀሐይ ላይ እንዳለሁ ነበር።

አንድ አብድ እኔ ዘንድ መጣ። ታሪኩን ዐውቃለሁ። ፋውሺት ይባላል። አናቱ ቤቷን በዐሥራ አምስት ሺ ፍራንክ ሽጣ ማምለጥ እንዲችል በአንድ ዘበኛ

t.me/OLDBOOKSPDF

አማካይነት ገንዘብ ልካለት ነበር። ውላቸው አምስቱን ዘበኛው አስቀርቶ ዐሥሩን ለእርሱ እንዲሰጠው ሲሆን፤ ግን ዘበኛው ሁሉንም ወሰደና ወደ ካየን ሔደ። እናቱ መሥዋዕት ማድረጓን ፋውሺት ሲረዳ፣ ከቁጥጥር ውጭ ሆነና ዘበኞች ተቀናኩለ። አንድም ጉዳት ከማድረሱ አፈዘዙት። ይህ የሆነው ከሦስት ወይም ከአራት ዓመት በፊት ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮም በአብዶቹ ቤት ይገኛል።

«አንተ ደሞ ማነህ?» ሲል ጠየቀኝ።

ከፊት ለፊቴ የቆመውን ምስኪን ተመለከትኩና፤ «ማነኝ? አንተኑ የምመስል ወንድ፤ ምንም የሚጨመር፤ ምንም የሚቀነስ ነገር የለም» አልኩት።

«ያልኩህ የቂል መልስ ነው። ወንድ መሆንህንማ ማየት ችያለሁ፣ ይኸውም ሴት ባለመሆንህ ነው። እኔ ያልኩህ ማን ነህ ነው። ስምህ ማን ይባላል ማለቴ ነው።»

«ፓፒዮ።»

«ፓፒዮ? ቢራቢሮ ነህ እንዴ? እንግዲያ ሰነፍ ቢራቢሮ ነሃ። ቢራቢሮ ከንፎች አሏት። የአንተ ወዴት ናቸው?»

«ጠፉብኝ»

«ልትፈልጋቸው ይገባል። እንዲያ ካደረግህ ማምለጥ ትችላለህ። ዘበኞቹ ከንፎች የሏቸውም። ልክ እንዳሻንጉሊት ልትጫወትባቸው ትችላለህ። ሲጃራህ ስጠኝ።» ከመስጠቴ በፊት ቀድሞ ነጠቀኝ። ከዚያም ቁጭ አለና በደስታ እየተመለከታት አጨሳት።

«አፈዘዙኝ። አንድ ነገር ሊቀናኝ ሲል በየጊዜው ያፈዙኛል።»

«ለምን?»

«ምክንያቱም ብዙ ዘበኞች ገድየ ነበር። ባለፈው ሌሊት ሁለት ሰቀልኩ። ግን ለማንም ሰው እንዳትናገር።»

«ለምን ሰቀልካቸው?»

«የእናቴን ቤት ሰረቁኝ። ታውቃለህ፤ እናቴ ቤቷን ልካልኝ በጣም ውብ መሆኑን ሲያዩ ለራሳቸው አስቀርተው ገቡበት። እነርሱን በመሰቀሌ ትከከል ነኝ፤ እ?»

«ትከከል ነህ። የእናትህን ቤት ሊጠቀሙበት አይችሉም።»

«እዚያ ወዲያ ከፍርግርጉ በስተጀርባ ያን ወፍራም ዘበኛ ታየዋለህ? በቤቱ ውስጥ ይኖርበታል። እዚያ ወዲያ ያለውን ሌላ ዘበኛ ደግሞ ታየዋለህ? እርሱንም እንደዚሁ ላፈነዳው ነው፤ እመነኝ።» ከዚያም ብድግ ብሎ ሔደ።

በከርሰቶስ! ከአብዶች ጋር መኖር ቀልድ አይደለም፤ ሰላም የለውም። ሌሊቱን በሙሉ እየጮሁ ያለቅሳሉ። በሙሉ ጨረቃ ሰሞን ደግሞ እንዲያውም ይብስባቸዋል። ጨረቃዋ አብደት ለምን እንደምታባብስ አይገባኝም፤ ግን ሁኔታውን አዘውትሬ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተከታትያለሁ።

በተጥጥር ሥር በሚገኙት ሰዎች ላይ ዘበኞቹ ሪፖርት ያቀርባሉ። እኔን በተመለከተ ቁጥጥሩ እጥፍ ነበር። ለምሳሌ ወደ ግቢው እንዳልወጣ ዐውቀው ይረሱኝና ቅሬታ እንዳለኝ ለማየት ይጠብቃሉ። ወይም ምሳ ይረሱኛል።

ከር የተንጠለጠለበት አንድ በትር ይገቡ፣ ዓሣ የማጠምድ በመምሰል አወዛውዛለሁ።

የዘበኛ አለቃው፣ «ለየነከሱልህ ነው ፓፒዮ?» ይለኛል።

«አልቻሉም። ዙሪያዬን የሚከተለኝ አንድ ትንሽ ዓሣ አለ፣ ትልቁ ሊነክስ ሲመጣ ትንሹ፣ 'ተጠንቀቅ እንዳትነክስ፣ የሚያጠምደው ፓፒዮ ነው' እያለ ያስጠነቅቀዋል። ስለዚህ ምንም አልያዝኩም። ግን ያው ነው፤ ማጥመዴን እቀጥላለሁ። ምናልባት አንድ ቀን አንድ ዓሣ ይመጣ ይሆናል» አልኩት። ዘበኛው ለአንድ ረዳት፣ «በዕርግጥም ያ ሰው ተለከፏል!» ሲል ሰማሁት።

ከምድር አዳራሹ ገበታ ሲያስቀምጡኝ ለመብላት ፍጹም አልቻኩም። ባቶቹ፣ ከንዶቹና አካላቱ ልክ እንደ ዝንጀሮ በጸጉር የተሸፈኑና ቢያንስ ስድስት ጫማ ቁመት ያለው አንድ ግዙፍ ሰው ሥቃዬን ሊያስቆጥረኝ እኔን መርጦ ነበር። ዘወትር ከጎኔ ይቀመጣል። ምግቡ የሚቀርበው በጣም ትኩሱን ስለሆነ እስኪበርድ ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ። በእንጨት ማንኪያ ትንሽ ጨለፍ እያደረግኩ እፍ እላለሁ። በዚህ ሁኔታ ትንሽ ማንኪያዎችም አወራርጃለሁ። በዚያ ወቅት ኢይቫንሆ፣ ኢይቫንሆ ነኝ ብሎ ገምቷል - የራሱን ሣህን ብድግ አደረገና እጆቹን እንደ አሸንዳ ለግቶ በአምስት ጉንጭ ሀሱንም ጠጣው። ከዚያ የእኔንም ሳብ አድርጎ እንደዚያው ካደረገ በኋላ፣ ከፊት ለፊቴ ሣህኑን በማጋጨት እንዴት እንደምበላ ታያለህ እንደማለት ደም የለበሱ አስፈሪ ዐይኖቹን አፈጠጠብኝ። ልሸናበት ቃጥቶኝ ነበር። አንድ ሌላ ምግብ ነበር። ኢይቫንሆም እዚያው አጠገብ ተቀምጦ ከራሱ በኋላ የእኔን ለማወራረድ በመቋመጥ ምኞት አብድ ፊቱ በደስታ ፈክቷል። አንድ የውሃ መያዣ ትልቅ ማንቆርቆሪያ ወዳጠገቤ ሳብኩ። ግዙፉ ሣህኔን ልክ ወደ እቃ ማንሣት ሲጀምር፣ ብድግ አልኩና ያለኝን ኃይል በሙሉ በመጠቀም ማንቆርቆሪያውን በጭንቅላቱ ላይ አፈጋሁበት። እንደ ቆሰለ ከብት ጓሬና ወለሉ ላይ ተኮራመተ። ወዲያውኑ አብዶቹ በሙሉ ሣህኖቻቸውን እንደጦር መሳሪያ በመጠቀም እንዱ በእንዱ ላይ ይረባረብ ጀመር። ጩኸትና ኡኡታ የተደባለቀበት አንድ የጦፈ ረብሻ ሆነ። አራት ወጠምሻ ጤና ረዳቶች የወሳንሳ ተሸከመውኝ ወደ ክፍሌ ስመለስ በድን ነበርኩ። ቦርሣዬን ከመታወቂያ ካርዴ ጋር ኢይቫንሆ ሰርቆኝ ስለነበር ኡኡታዮን አቀለጥኩት። ይህም ሠራ። ዶክተሩ ለድርጊቱ ሃላፊነት እንደሌለብኝ መሰከረልኝ። እልፎ አልፎ እንጂ ሰላማዊ ዕብድ መሆኔንም ዘበኞቹ ተስማሙበት። ኢይቫንሆ እንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ያሸበረቀ ፋሻ በጭንቅላቱ ላይ ታሠረለት። አናቱን ከአምስት ኢንች በበለጠ ሰፋት እንደ ፊነከትኩ ግልጽ ነበር። ደግነቱ የምንዘዋወረው በአንድ ወቅት አለመሆኑ ነበር።

በመጨረሻ ሳልቪዲያንን ማነጋገር ቻልኩ። በርሚሎቹ የተቀመጡበትን የመጋዘን ቁልፍ ተመሳሳይ መፍቻ ቀደም ሲል ይዘ፤ አንድ ላይ የሚያስርበትን በቂ ሽቦ ለማግኘት እየሞከረ ነበር። አንድ ላይ ባሕር ላይ ከተንሳፈፍን በኋላ በርሚሎቹ ሲሳቡ ሽቦውን ይበጥሱታል የሚል ጥርጣሬ እንዳደረብኝ ነገርኩት። ስለሚለጠጥም ምቹው ገመድ ነው። እኔም ትንሽ አፈልግና ሽቦውንና ገመዱን ሁለቱንም መጠቀም እንችላለን። በተጨማሪም ሦስት ቁልፎች ይፈልጋል። አንድ ለእኔ ከፍል፤ አንዱ ወደ ክፍሉ ለሚያስገባው ኮሪደርና አንዱ ለሆስፒታሉ ዋና መዝጊያ። በከባድ ሁኔታ እንጠበቅም። ሌሊት ከሦስት ሰዓት እስከ ሰባት ሰዓት፤ ከሰባት ሰዓት እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት፤ በየአራት ሰዓቱ ለጥበቃ የሚመደበው አንድ ዘበኛ ብቻ ነበር። የቀሩት ይተኛሉ። ተረኝነት የሚሸፍንላቸውና የሚተማመኑበት አንድ የአሥረኛ ጤና ረዳት ነበር። ስለዚህ ማንኛውም ነገር አመች ሆኗል፤ ያሉበን ረጋ ማለት ብቻ ነበር። ቢበዛ አንድ ወር፤ ከዚያም መሰስ እንላለን።

ወደ ግቢው በመውጣት ላይ እንዳለሁ፤ የዘበኛው ኃላፊ አንድ የሚጎረንን ሲጃራ ሰጠኝ። ግን እንደ መሳፍነኑ ሳይሆን አርኪ ነበር። የሚዘፍኑትን፤ የሚያለቅሱትን፤ ወረፍ እያደረገ የሚያወራጫቸውን፤ ከራሳቸው ጋር የሚያወሩትን፤ ዕርቃነ ሥጋቸውን የቀሩትን የሰዎች መንጋ አመለከታለሁ። ከመውጣታቸው በፊት ገላቸውን መታጠብ ስለ ነበረባቸው ገና አርጥብ ነበሩ። ከሚደርስባቸው ድብደባ ወይም ራሳቸውን በራሳቸው ከማሰቃየታቸው፤ አለበለዚም ከቆረፈደው ሽራ ጭረት የተነሣ በሚያሳዝን ሁኔታ የተጎሳቆሉት ገላዎቻቸው ተሸንታትረዋል። የገሃነም አሳት የመጨረሻ እምብርቱ በትክክል ይህ ነበር። ፈረንሣይ ውስጥ ያለ አግባብ ተጠያቂ ናችሁ ተብለው ከተያዙት ከእነዚህ ዕብዶች መሀል ምን ያህሎቹ ንፁህ እንደሆኑ ደንቆኛል።

ቲቲን በ1933 እኔ በወጣሁበት ኮንቨይ ውስጥ ነበር። ማርሴይ ከተማ አንድ ሰው ገድሎ ታክሲ ያቆምና የገደለውን ሰው ወደ ሆስፒታል ወስዶ «እንከብካቤ አድርጉለት፤ ያመመው መስሎኛል» ይላል። ወዲያው ታሠረና ፈረዱበት። ግን ያን የመሰለ ነገር ለማድረግ ቀደም ሲልም በግልጽ እብድ መሆን አለበት። አታሰራለሁን የማያውቅ እብድ ሰው ብቻ ነው። ስለሆነም ቲቲን እዚሁ አጠገቤ ተቀምጦ ይገኛል። ሥር ከሰደደው የደም ተቅማጡ የተነሣ፤ የሚራመድ ሬሣ ሆኗል። እንደ ብረት በገረጡት የሳደጎዱ ዐይኖቹ ተመለከተኝ። «ጓዴ፤ ሆዴ ውስጥ ትናንሽ ዝንጀሮዎች ይገፍሉሁ። ከፋዎቹ እንጀቴን ይነከሱኛል ከዚያም አደማለሁ። ይህም በሚቆጡበት ወቅት ነበር። ሊሎቹ ደግሞ ልክ እንደ ላባ የለሰለሱ እጆች አሏቸው። ከፉዎቹ እንዳይነክሱኝ ረጋ

t.me/OLDBOOKSPDF

ብለው እየዳሰሱ ይጠብቁኛል። ሲከላከሉልኝ ደም አይኖርም።»

«ማርሴይን ታስታውሳለህ ቲቲን?»

ምን ማለትህ ነው? ጥርት አድርጌ አስታውሳለሁ እንጂ። የአቃጣሪዎቹንና የሌቦቹን ሠፈር ፕላስ - ደ - ቦርሴን»

«ከስሞቻቸውስ አንዱን እንኳ ታስታውሳለህ? ለ - አንገርን? ለ ሊከርን? ለ - ግራቫትን? ከሎመንን?»

«አላስታውስም። ምንም ስሞች አላስታውስም። ከታመመው ጓደኛየ ጋር ወደ ሆስፒታል የወሰደኝንና የታመመውም በእኔ ምክንያት እንደነበረ የነገረኝን መናጢ ባለታክሲ ብቻ አስታውሳለሁ። ይህንኑ ብቻ ነው።

«ጓደኞችህንስ?»

አላስታውስም።»

ምስኪን ቲቲን። ልክ እንደ አንድ እንስሳ ለሆነው ለዚህ አሳዛኝ ሰው ከፍተኛ ሐዘን እየተሰማኝ የሲጃራ ቁሩየን ሰጠሁትና ተነሣሁ። አዎ፣ ከዕብዶች ጋር መኖር አደገኛ ነበር። ቢሆንም ምን ማድረግ እችላለሁ? ሌላ የቅጣት አደጋ ሳይከተለኝ ለማምለጥ የሚያስችለኝ ብቸኛው ዘዴ ይኸው ነበር።

ላልቪዲያ ከሞላ ጎደል ተዘጋጅቶ ነበር። ከመከፈቻዎቹ ሁለቱን ይዞ የቀረው የእኔ ክፍል ብቻ ነበር። በተጨማሪ አንድ ወፍራም ገመድ አግኝቷል፣ ከዚያም ሌላ ከተንጠልጣይ የሽራ አልጋ ትልታዮች በአምስት ፈርጅ አንድ ገመድ ጎንጉኖ አዘጋጅቷል። በዚያ በእርሱ ያለው ዝግጅት ደህና ይመስል ነበር።

ለማምለጥ ተጣድፈያለሁ። ዕብዶች ሆስፒታል ውስጥ በተሰጠኝ ክፍል መቆየት በጣም አስቸጋሪ ስለሆነብኝ አንድ ትርኢት አሳየሁ።

ሁለት የብሮማይድ መርፌ ጤና ረዳቶቹ ወግተው ወደ ፍልውሃ ገላ መታጠቢያ ውስጥ አስገቡኝ። ወደ ውጭ እንዳልወጣ ተብሎ የመታጠቢያ ገንዳው በጣም ጠንካራ በሆነ ሽራ ተሸፍኖ ነበር። ጭንቅላቴ ብቻ ቦእንድ ቀዳዳ በኩል ብቅ ብሏል። አይቫንሆ ከመግባቱ በፊት ለሁ..ት ሰዓት ያህል እዚያው ቆየሁ። አመለካከቱ የሚያስፈራ ነበር። ሊያሾፍኝ መሆኑን አርግጠኛ ሆንኩ፣ ከንዶቼም በሽራው ውስጥ ስለነበሩ ራሴን የምከላከልበት መንገድ የለኝም። ዐይኖቹን እንደተከለ እየተጠጋኝ መጣ። የትንፋሹ ግማት አፈነኝ። አርዱኝ ብየ ልጮህ ፈለግኩ፣ ግን ያስቆጣው እንደሆን ብየ ደግሞ ፈራሁ። በግዙፍ እጆቹ እንቅ ሊያደርገኝ መስሎኝ ዐይኖቹን ጭፍን አድርጌ ቆየሁ። ያን የጥቂት ሴኮንዶች ጭንቀት ለመርሳት ረጅም ጊዜ ወስዶብኛል። በመጨረሻም ትቶኝ ወደ ውሃው መዘውር ሔደ። ቀዝቀዛ ውሃውን ዘጋና ፍል ውሃውን እስከ መጨረሻ ከፍቶ ለቀቀው። ጓጎኩ። በውሃ ነፍሬ መሞቴ ነበር። አይቫንሆ ትቶኝ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሔደ። ከፍሉ በአንቱሎት አፍኖኝ ሳለ ሞቴን ከሚጋብዘው ሽራ ቀድጄ የምወጣበትን መንገድ ለማግኘት የሰው ልጅ ከሚያደርገው ጥረት በላይ ታገልኩ። በመጨረሻ ዘበኞቹ በነፍሱ ደረሱ። አንቱሎቱ ከመስኮቱ በላይ እየተትለገለገ ሲወጣ አይተው ሰለነበር ከጉዳው ውስጥ ጎትተው ሊያወጡኝ ደረሱልኝ። ከመጠን በላይ ተቃጥዬ ስለነበር፣ በተለይ ቆዳው ተቀቅሎ የተገሸለጠበት የፅፍረተ ሥጋዬ አካባቢ ልክ እንደ እሳት ቆጠቆጠኝ። ፒከሪክ ቅባት ለቀለቁኝና ሆስፒታሉ ውስጥ ከምትገኘው ትንሽ የሕክምና ክፍል አልጋ ላይ አስተኙኝ። ለሚቀጥሉት ሐያ አራት ሰዓቶች ያደነዘዘኝን የሞርፊን መርፌ ደከተሩ ወጋኝ። የሆነው ምን እንደነበር ሲጠይቀኝ፣ አንድ አሳተ ገሞራ በመታጠቢያ ገንዳው ውስጥ መፈንዳቱን ነገርኩት። በዕርግጥ ምን እንደተደረገ ማንም ሊረዳ አልቻለም ነበር። የውሃውን አወራረድ በሚገባ ባለማስተካከሉ፣ መታጠቢያ ገንዳ የሚያዘጋጀውን ሰው ዘበኛው ከሰሰው።

ሳልቪዲያ የፒከሪክ ቅባት ለቅልቆኝ ወዲያው ሔደ። ተዘጋጅቶ እንደ ነበርና የእኔ ወደ እዚሁ ከፍል መግባትም አንድ ዕድል መሆኑን አመነበት፣ ምክንያቱ ማምለጡ ውድቀት ቢያስከትል እንኳ ምንም ሳንታይ ወደዚህ ከፍል ልንመለስ እንችላለንና ነው። የሕክምና ከፍሉን ቁልፍ በአንድ ቁራጭ ሳሙና ላይ ወዲያው ቅርፁን ነድፎ ስለነበር፣ በበነጋው ይኖረዋል። በሚገባ ሰድን ለእርሱ ማስታወቂ የእኔ ጉዳይ ይሆናል። ከዚያም በጥበቃ ተረኝነቱ ወቅት በሚተኛው ከዘበኞቹ በአንዱ የጥበቃ ሰዓት እንጠቀምበታለን።

ዛሬ ማታ ከሰባት እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት ባለው የጥበቃ ጊዜ ሊደረግ ነው። ሳልቪዲያም በዕረፍት ላይ ይሆናል። ጊዜ ለመቆጠብ የሆምጣጤውን በርሜል ወደ አምስት ሰዓት አካባቢ ሊገለብጠው ነበር። የዘይቱን በርሜል እንደያዘ እንተወዋለን፣ ምክንያቱም ባሕሩ በጣም ቁጡ ስለነበር፣ ወደ ባሀሩ በምንዘልቅበት ወቅት ዘይቱ ሚዛን በመጠበቅ ሊጠቅመን ይችላል።

ከዱቄት ከረጢቶች የተሰፉ ሱሪዎች፣ አንድ የሱፍ ቩራብና አንዲት ጥሩ ጩቤ ይዣለሁ። በተጨማሪ ሲጃራዎችና የክብሪት መጫሪያ ውሃ በማያረጥባት አንዲት ከረጢት አንገቴ ላይ አንጠልጥያለሁ። ሳልቪዲያም በስኳርና በዘይት የተለወሰ ታፒዎካ ውሃ በማያረጥባት አንዲት ትንሽ የወታደሮች ሻንጣ ሞልቶ ነበር። በግምት ሲድስት ፓውንድ ይሆናል።

ወቅቱ መሸ። ልቤ ደረቴን እየደሰቀው የጓደኛየን መምጣት በመጠባበቅ አልጋየ ላይ ተቀምጫለሁ። በጥቂት ጊዜ ውስጥ ማምለጡ ይጀመራል። ዕድልና ቸሩ ፈጣሪ ከእኛ ጋር ከሆኑ እንግዲህ ይህን ገሃነመ እሳት ለመጨረሻ መገላገል እችላለሁ።

መዝጊያው በመከፈት ላይ እንዳለ ዓሣነባሪዎቹ ማቴዎስን ወደ ላይ ከፍ አድርገው እንደያዙት ከጨለማው አቅጣጫ በስሜት መጣብኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«ጋጢ እንሒድ!» ሲለኝ ተከተልኩ። ወዲያው መዝጊያውን ዘጋና መከረቻውን በኮሪደሩ ጥግ ደበቀው። «ቶሎ በል! ወደፊት ገሥግሥ» ከመጋዘኑ ስንደርስ መዝጊያው ተከፍቶ ነበር። ጉዳዩ ተቃሏል። እርሱ ገመዱን በትከሻው ዙሪያ ሲጠመጥም፣ እኔም ሽበውን እንደዚያው አደረግኩ። የዱቄት ከረጢቱን አነሣሁና ጥቁር ቀለም በመሰለው ሌሊት በርሜሉን ወደ ባሕሩ አቅጣጫ ማንከባለል ጀመርኩ። ሳልቪዲያም ከዘይቱ በርሜል ጋር ተከተለኝ። ከቦዱ በርሜል እንዳለ ወርዶ ሊከሰክስ ሲል፣ በጣም ጠንካራ በመሆኑ ሊገታው ቻለ።

«ተጠንቀቅ! ፍጥነት እንዳይጨምር ተቆጣጠር።» ድንገት በርሜሉ ካመለጠው እኔ መገደብ እንድችል ተጠባበቅኩት። ከቁልቁለቱ አቅጣጫ ወደ ላይ ዞርኩና እኔ ከፊት፣ ቀጥሎ በርሜሉ ሆነ። ያለ ምንም ችግር ወደ ረባዳው ደረሰን። ወደ ባሕሩ የምትወስደው እንዲት ጠባብ መሿለኪያ መንገድ ነበረች ሌላው ቋጥኞቹ ስለሞሉበት በዘይ ለማለፍ አይቻልም።

« በርሜሉን ባዶ አድርገው። እንደሞላ ከቋጥኞቹ በላይ ልታሳልፈው ፍጹም አትችልም።» ነፋሱ እየተንሿሿ ማዕበሎችም ከቋጥኞቹ ጋር ይፋጩ ነበር። እንደ ተባለው ሆነ። በርሜሉ ተገለበጠ። «ከዳኑን አጥብቀህ ዝጋው። ቆይ፣ በተጨማሪ ይሆንን የብረት ከዳን ጨምርበት።» ቀዳዳዎቹም ተበጅተውለት ነበር። «ምሰማሮቹን እርቀህ ምታቸው።» የነፋሱና የማዕበሎቹ ዋካታ የበርሜሉን ቁርቆራ ድምፅ አፍኖት ነበር።

ጥብቅ ብለው ሲቆራኙ ደግሞ ሁለቱን በርሜሎች ከቋጥኞቹ በላይ ማንሣት ችግር ሆነ። እያንዳንዳቸው ብቻ ከሃምሳ ጋሎን በላይ ይይዛል። ጓደኛዬ ለጀልባ ማንሣፈፊያ የመረጠው ቦታ ነጥሮችን የሚያቃልል አልነበረም። «ስለ ክርስቶስ ግፋ! ትንሽ ወደ ላይ ከፍ አድርገው። እዚያ ማዶ ማዕበሉ ይታይሃል!» ሁለታችንንም አንድ ላይ ከበርሜሎቹ ጭምር አነሆንና ወደ ኋላ እያምዘገዘገ ወሰዶ ከቋጥኞቹ ጋር ቢጋይል አላተመን። «ወደ ፊት ተመልከት! ወደ ፊት ተመልከት!» እያለ ሳልቪዲያ ጓጎረ።

« ረጋ በል ጓደኛዬ። ወይ ወደ ውሃው ግባ፤ አለበለዚያ ወደ ኋላ ተመልሰህ ና። እንደዚያ ነው፤ አሁን ጥሩ አቅጣጫ ይዘሃል። ሳገዝህ ወደ አጉተ አቅጣጫ ሳብ። በዚያ ወቅት አኔም እገፋና ከቋጥኞቹ እንገላገላለን። ግን ማዕበል ቢመታን እንኳ ለእንድ አፍታ ችለን መያዝ አለብን።» በነፋሱና በማዕበሎቹ ዋካታ መካከል ለሳልቪዲያ ትእዛዝ በማስተላለፍ ላይ እንዳለሁ፣ እንድ ግዙፍ ማዕበል መጥቶ በርሜሎቹን፣ እርሱንና እኔን አለበሰን። ከዚያም ባለው ኃይል ጀልባዋን ወደ ባሕሩ አቅጣጫ ሲስባት በእንድ እመርታ ነጻ ወጣን። ከእኔ ቀድሞ በርሜሉ ላይ የወጣው እርሱ ሲሆን እኔም ለመውጣት ወደ ላይ በምላብበት ወቅት እንድ የማዕበል ቁልል ከሥር እየተንከባለለ መጥቶ ልክ እንደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደሮ ላባ አኳኋን ከጭጮቹ ጋር አላተመን። ከራሳቸ ከመጋጨታቸን የተነሣ በርሚሎቹ ተፈረከሰው ተከሳፊቱና በየቦታው ብትንትናቸው ወጣ። ማዕበሉ እየተንከባለለ ሲመለስ አኔንም ከሠላሳ ያርድ ይበልጥ ወደ ባሕሩ ተሸከመኝ። ከዚያ ደግሞ መዋኘት እንደጀመርኩ አንድ ሌላ ማዕበል እያንከባለለ ወደ ባሕሩ ዳርቻ አወጣኝና ከሁለት ቋጥኞች መካከል ሰዘረፈጥ፣ እንደገና ተመልሸ ከመወሰዴ በፊት አነርሱን ጨምድጄ ለመያዝ ጊዜ አገኘሁ። መላው አካሉ እንደ ቆሳሰለ እየዳሁ ለመውጣት ቻልኩ፣ ግን ደረቅ መሬት ላይ ከደረስኩ በኋላ ልብ ሳደርግ፣ ጀልባዋን ልናንሳፍፍበት ከነበረው ቦታ ከመቶ ያርድ በላይ ርቂ ነበር።

ስለምንም ነገር ሳላስብ «ሮሚዎ ሳልቫዶይ! ወዴት ነው ያለኸው?» ብየ ተጣራሁ። መልስ የለም። ካልሲዎቹ ሲቀሩ ሱሪየንና ሹራቢን አወላለቅኩና ዕርቃነ ሥጋየን ኩርምት አልኩ። «ሰለ ከርስዮስ ብለህ ጓደኛየ ወዴት ነው ያለኸው? ወዴት ነው ያለኸው?» ነፋሱ ማዕበሎቹና ባሕሩ ብቻ መላሱልኝ። በአካልም ሆነ በስሜት በጠቅላላው እንደ ደከምኩና እንደ ፈዘዝኩ ለሰንት ጊዜ መቆየቴን አላስታውስም፣ ከዚያም ተጋደምኩ። በንዴት ሲታ አያለቀስኩ፣ ለማያጠሰው ጓደኛየ የወንድማዊ አክብሮት መግለጫ ትሁን በማለት አንገቴ ላይ አንጠልጥያት የነበረችውን ትንሣሆና ማቀጣጠያ የያዘችውን ከረጢት ቦጫጭቄ ጣልኳት።

ፊቴን ወደ ነፋሱ አቅጣጫ በማድረግ ማንኛውንም ነገር ጠራርገው ወደ መጨረሻው ሥቃይ የከተቱኝን ግዙፍ ማዕበሎች እያየሁ ቡጢዮን ጨብጨ እግዚአብሔርን አማረርኩ።

ነፋሱ በርዶ እርጋታ ሲሰፍን እኔም ወደ ቀድሞው ሁኔታየ ተመለስኩ።

ተመልሼም ወደ ዕብዶቹ ሆስፒታል ለመግባት ሞከርኩ ከመነመነች ዕድል ጋር። ከሁሉም በላይ አንድ ሐሳብ ብቻ እያብሰለሰልኩ የባሕሩን ዳር ትቼ ወደ ላይ ተቃናሁ፡- ሳልታይና ሳልሰማ አልጋየ ውስጥ ተመልሼ ለመግባት። ወደ ዋናው በር የሚያስገባውን ቁልፍ መክፈቻ ሳልቪዲያ ወዴት አስቀምጦት እንደነበር ስላልተረዳሁ በሆስፒታሉ ግንብ ላይ ከዘለልኩ በኋላ፣ ያለ ችግር ወደ ሕክምና ክፍሉ ኮሪዶር ደረስኩ።

የሕክምና ክፍሉን ቁልፍ መክፈቻ ለማግኘት ረጅም ጊዜ አልወሰደብኝም። ገሁና መዝጊያው ደጋግሜ በመቆለፍ ከዚያም ወደ መስኮቱ ሔጄ የቁልፉን መክፈቻ የቻልኩትን ያህር አርቄ ወረወርኩ። ከአጥሩ ውጭ ወደቀ። ከዚያ በኋላ አልጋዬ ውስጥ ገሁ። ሊያጋልጡኝ የሚችሉት ካልሲዎቼ ብቻ ነበሩ። ተነሥቼ ወደ መጻዳጃ ቤት ሔድኩና ሰቀልኳቸው። ወደ አልጋየ እንደ ተመለስኩ አንሶላውን ፊቴ ድረስ ሳብኩና ቀስ በቀስ ትንሽ ተሟሟቅኩ። ነፋሱና ባሕሩ ደሜን አርግቶት ነበር። በእርግጥ ጓደኛየ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሰምጦ ይሆን? ትንሽ መጠበቅ ነበረብኝ? በጓደኛየ በሮሚዎ ላይ እንደዚህ በቀላሉ ተበሳ በመቁረጤ ራሴን ታዘብኩት።

ከመዲኖ መሳቢያዬ ውስጥ ሁለት የእንቅልፍ እንክብሎች ነበሩ። ያለውሃ ዋጥኳቸው። ለማወራረድ በቂ ምራቅ ነበረኝ። የተንነተልኩ መስሎኝ ነቅቼ እፊቴ አንድ ጤና ረዳት ቆሞ አስካይ ድረስ ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ላይ ነበርኩ። ከፍሉን የፀሐይ ጮራ ሞልቶታል። በተከፈተው መስኮት በኩል ሦስት ሕሙማን ይመለከቱ ነበር።

«ምነው ፓፒዮ? ልክ እንደሞትክ ሆነህ ተኝተሃልሳ። ከጧቱ አራት ሰዓት ሆኗል። ቡናህንም አልጠጣህ፣ ቀዝቅዟል። ተነሥተህ ጠጣው።»

ጉዳዩ ከተለመደው የተለየ ነገር እንዳልነበረ ግማሽ እንቅልፍ ላይ ሆኜ እንኳ ተገንዝቤዋለሁ።

«ለምን ቀሰቀሳችሁኝ?»

«ምክንያቱም አሁን ቁስልህ ስለዳነልህ አልጋህን እንፈልገዋለን። ወደ ከፍልህ ተመልሰህ መሔድ አለብህ»

«እሽ ጌታየ!»

ተከተልኩት። ግቢው ውስጥ ሲተወኝ ካልሲዎቼን ፀሐይ ላይ ለማድረቅ ዕድል አገኘሁ።

ማምለጤ ከከሸፈ ወዲህ ሦስት ቀን ሆኖ ነበር። ስለ ሁኔታው እስካሁን እንድም ቃል አልሰማሁም። ከክፍሌ ወደ ግቢው፣ ከግቢው ወደ ከፍሌ አመላለሳለሁ። የሳልቪዳ ደብዛውም የለ። ያልታደለው ከንቱ ከቋጥኞች ጋር ተላትሞ ሞቶ መሆን አለበት። እኔም ያመለጥኩት ለጥቂት ነበር የዳንኩት ከጀልባዋ ፊት ከመሆን ፋንታ ከኋላ በመሆኔ መሆን አለበት። ግን ዕርግጡ የሚታወቅበት ምንም መንገድ አልነበረም። እንግዲህ ከአብዶች ሆስፒታል መውጣት ይኖርብኛል። በሚገባ ድኛለሁ ወይም ሌላ ቢቀር ወደ ካምፑ ብሔድ ይሻለኛል ብየ አነርሱን ለማሳመን ደግሞ ፈተና ሊገጥመኝ ነው። አሁን የዶከተሩን ሐሳብ ማስለወጥ አለብኝ።

«ሚስተር ሩቨዋ» የሕክምና ከፍሉ ኃላፊ ነበር፣ «ሌሊት ይበርደኛል። እንደማላበላሻቸው ቃል ብገባ አንድ ሱሪና ሸሚዝ ትሰጠኛለህ?»

ሩቨዋ ግራ ተጋባ። ትኩር ብሎ ተመለከተኝና። «ፓፒዮ፣ እስኪ ተቀመጥ። ሁኔታው እንዴት እንደሆነ እስኪ ንገረኝ?»

«ለምን እዚህ እንዳልሁ አልገባኝም። ይህ የአብዶች ሆስፒታል አይደለም እንዴ? ለምን ከአብዶች ጋር ሆንኩኝ? የአእምሮ ቀውስ አሳየሁ እንዴ? ለምን ወደዚህ መጣሁ? እባክህ ንገረኝ ጌታዬ! መቸም እንዳስቸገርኩህ ይሰማኛል።»

«ወዳጄ፣ ታመህ ነበር፣ ግን አሁን የተሻለህ ትመስላለህ። መሥራት

t.me/OLDBOOKSPDF

ትፈልጋለህ?»

«አዎ»

«ምን ዐይነት ሥራ?»

«የሆነው ቢሆን ግድ የለኝም::»

ልብሶች ሰጡኝና በጽዳት ሥራ ላይ መድቡኝ:: የሌሊቱ ተረኛ ዘበኛ መጥቶ አስኪቆልፍ ድረስ፣ መዝጊያዬ ወለል ብሎ እንደተከፈተ ያመሻል::

ከአውቬኝ ቀበሌ የመጣ አንድ የኢሥረኛ ጤና ረዳት ትላንት ማታ ለመጀመሪያ ጊዜ አነጋገረኝ:: ዘበኛ ከፍል ውስጥ ብቻችንን ነበርን:: ዘበኛው ገና አልተመለሰም:: ለውየውን አላውቀውም፣ እርሱ ግን በሚገባ አውቅሃለሁ አለኝ::

«ከእንግዲህ ወዲያ መቀጠልህ ፍሬ የለውም ጓደኛ» አለ::

«ምን ማለትህ ነው?»

«አሱን ተወው! ድርጊትህን አልተከታተልኩም ማለህ ትገምታለህ? በዚህ የዕበዶች ሕክምና ከፍል ሰባት ዓመት ስለቆየሁ መጀመሪያ ካጭበርበርክባት ታል ጀምሮ ዐውቃለሁ:: ከሳልቪዲያ ጋር ያደረጋችሁት የማምለጥ ሙከራ ውጤት ባለማግኘቱ በዕርግጥ አዝኛለሁ:: ሕይወቱን ከፊለበት:: ስለሁኔታው ለእኔ ባይነግረኝም ትሉ፣ ጥሩ ጓደኛዬ ስለነበር በጣም ቆጭቶኛል:: ግን በእርሱ ላይ ይህን እንደ ቂም አሳይዝበትም:: እንተም ማንኛውም ዓይነት ዕርዳታ ቢያስፈልግህ ንገረኝ:: የምችለውን ሁሉ ለማድረግ ደስ ይለኛል::»

ሐቀኛ መሆን አንዳለበት ተሰማኝ:: ምስኪን ሳልቪዲያ! «አንድ ከፍተኛ ውሸንብር ተፈጥሮ ነበር:: ከዚያም መሔዱን ተረዳ» አለ ሰውየው:: «በባሕሩ ተተፍተው የተመለሱ የበርሜል ቁርጥራጮች አግኝተው ስለነበር፣ በዓሣነባሪዎች እንደ ተበላ እርግጠኛ ሆነዋል:: የወይራ ዘይቱ በመባከኑ ዶክተሩ ከመጠን በላይ በሽቋል:: በዚህ የጦርነት ወቅት ከእንግዲህ ወዲያ ተጨማሪ ዘይት ለማግኘት ረጅም ጊዜ ይወስዳል» አለ::

«ምን ትመክረኛለህ?»

«ምግባችንን ለማምጣት በየቀኑ ወደ ሆስፒታል ከሚሔዱት ቡድኖች ጋር እንዲመድብህ ሐሳብ ላቀርብልህ ነው:: ለእንተም ጥሩ ሽርሽር ይሆናል:: ጠባይህን አሻሽል:: አነጋገርህ አብዛኛው ስሜት የሚሰጥ መሆኑን አረጋግጥ:: በጣም ፈጥነህ የዳንክ መምሰል የለብህም::»

«አመሰግናለሁ:: ማን ነው ስምህ?»

«ዶፖን»

«አመሰግናለሁ ጓደኛዬ:: ምክርህን አልረሳህም::»

t.me/OLDBOOKSPDF

የተዝረከረከው የማምለጥ ሙከራ አንድ ወር አለፈው። የሮሚዎን አስከሬን ከስድስት ቀን በኋላ አግኝተውት ነበር። ባልታወቀ ምክንያት ዓሣነባሪዎቹ አልበሉትም። ግን ሆድታውንና አንደኛውን ባቱን በከፊል ሌሎች ዓሣዎች ቦትርፈውት ነበር። በተጨማሪ የራስ ቅሉ ተፈጥፍጧል። በመበስበስ ደረጃ ላይ ከመሆኑ የጎነሣ የአስከሬን ቀዶ ምርመራ አልተከናወነበትም።

አንድ ደብዳቤ ይልክልኝ እንደሆነ ዴቫንን ጠየቅኩት። ለጋልጋኒ ማድረስ ከቻለ የፖስታው ከረጢት ከመታሸጉ በፊት እርሱ ሊያስገባልኝ ይችላል።

ጣሊያን ለሚገኙት ለሳልቪዲያ እናት የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፍኩ።

እመቤቴ፣ ልጅዎ በእግሩ ሰንሰለት ሳይገባበት፣ ከወህኒ ቤት ርቆ ባህር ላይ በጀግንነት እንደ አንድ ነፃ ሰው ሞተ በቆራጥነት ለእርነቱ ሲታገል ሞቷል። ከሁለት አንዳችን ላይ አንድ ነገር ቢደርስ ለሌላው ቤተሰብ እንድጽፍ አርስበርሳችን ቃል ኪዳን ገብተን ነበር። ይህን የሚያስቅቅ ተግባር ስፈጽም እጆችዎን እየሳምኩ ነው።

የልጅዎ ጓደኛ ፓፒዮ

ይህችን አነስተኛ ተግባር ከጀርባዬ ላይ ካወረድኩ በኋላ ስለ አሳዛኙ ትዝታ ማሰቤን ለማቆም ወሰንኩ። ኑሮ ይኸው ነበራ። የቀረኝ ነገር ቢኖር ከዕብዶች ሆስፒታል መውጣትና በምንም መንገድ ወደ ዲያብሎስ ደሴት መሔድ፤ ከዚያም እንደገና ለማምለጥ መሞከር ነበር።

ከዘበኞቹ አንድ የአትክልት ቦታውን እንድንከባከብለት መደበኝ። አሁን ለሁለት ወር ያህል የተስተካከለ ጠባይ አያሳየሁ ስለሆነ ዘበኛው በእኔ ላይ በጣም ከፍተኛ ግምት ስላደረበት መልቀቄን አልፈለገም። ባሰፈው ጊዜ ዶክተሩ ሲያየኝ ከዕብዶቹ ሆስፒታል አውጥቶ በ «ሙከራ መልክ» ወደ ካምፑ መልሶ ሊያስቀምጠኝ እንደነበር ዶፖን ነገረኝ። ግን የአትክልት ቦታየ ከዚያ የተሻለ እንክብካቤ ፍጹም ተደርጎለት አያውቅም በማለት ዘበኛው እርምጃውን ተቃውሞ ነበር።

ስለዚህ አንድ ቀን ጧት የእንጆሪ አትክልቶቹን በሙሉ ነቃቀልኩና ወደ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ ወረወርኳቸው። በእያንዳንዱ አትክልት ምትክ አንዳንድ ትንሽ መስቀል ተከልኩ። ብዙ በተነቀሉ እንጆሪዎች ፋንታ፣ ብዙ የተተከሉ መስቀሎች። የንዴቱን ሁኔታ ለመግለጽ ያዳግት ነበር። ወፍራሙ ዘበኛ በጣም ናላው ከመበጥበጡ የተነሣ ተወጣጠረና ሊፈነዳ ተቃረበ። እናገራለሁ ብሎ ቢሞክር አረፋ እየደፈቀ መንተባተብ እንጂ የሚመጣ ቃል ጠፋው። ከዕቃ መግፊያ ጋሪ ላይ ተቀምጦ ዕውነተኛውን አንባ አነባ። ምናልባት ትንሽ ፈር ለቅቄ ይሆናል፣ ግን ደግሞ አንድ ነገር ማድረግ እንዳለብኝ ግዴታ ነበር።

ዶክተሩ ሁኔታውን በዕርጋታ ተመለከተው። ሕመምተኛው ወደ ካምፑ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተመልሶ በሙከራ ላይ ቢቀመጥ፣ ልማዳዊ አኗኗርን ራሱ መቅሰም ይችላል እያለ ይወተውታል።

«እስኪ ንገረኝ ፓፒዮ፣ ለምን እንጆሪዎቹን ነቅለህ በእነርሱ ቦታ መስቀሎች?»

«መዘርዘር አልችልም ዶክተርዬ፣ ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ዘበኛውን ጠይቄዋለሁ። እንጆሪዎቹን ከመጠን በላይ ስለሚወዳቸው በዕውነት አዝናለሁ። ተጨማሪ እንጆሪዎች እንዲልከለት እግዚአብሔርን አለምንለታለሁ።»

ስለሆነም ወደ ካምፑ ተመልሼ ከጓደኞቼ ጋር ተደባለቅሁ። የካሪቡኔሪ ቦታ አውንም ገና ባዶ ስለነበረ፣ ልክ እርሱ እዚያው እንዳለ ሁሉ ከባዶው ቦታ ቀጥዬ የእኔን ተንጠልጣይ አልጋ ዘረጋሁ።

ዶክተሩ፣ «ልዩ ምርመራ» የሚል ምልክት በሹራቤ ላይ ለጥፎልኛል። ትእዛዝ የሚሰጠኝ እርሱ ብቻ ነበር። በየቀኑ ጧት ከሁለት እስከ አራት ሰዓት ከሆስፒታሉ ፊትለፊት ቅጠሎች እጓፍፍ ነበር። ሲጃራ በማጤስና ቡና በመጠጣት ዘወትር ከዶክተሩና ከባለቤቱ ጋር እቀመጣለሁ። አንድ ላይ በመሆን ስላለፈው ታሪኬ ለማወቅ ይሞክራሉ። ስለ ሁኔታዬ እንድነግራቸው እኔን በመጎትጎት ሊፈውሱኝ እንደሚችሉ ተማምነዋል። ወደ ዲያብሎስ ደሴት እንዲልኩኝ ዶክተሩን ልጠይቀው ወሰንኩ።

ነገሩም ሆነ። በሚቀጥለው ቀን መሔዴ ነበር። ለምን መሔድ እንዳስፈለገኝ ዶክተሩና ባልተቤቱ ዐውቀዋል። ለእኔ በጣም ደጎች ሆነውልኝ ስለነበር ላታልላቸው አልቻልኩም። «ዶክተርዬ፣ እዚህ የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤቱን ኑሮ አየሁት። ወደ ዲያብሎስ እንድላክ እርዳኝ። ይህ አስከሚሆን ድረስ አምልጬ ሔድኩ ወይም ሞትኩ ደንታ የለኝም።

«ይገባኛል፣ ፓፒዮ። እዚህ ያለው የዕብዶች ሆስፒታል እኔንም እንደዚሁ ይዘገንነኛል። አስተዳደሩ የገማ ነው። ደህና ሁን፣ መልካም ዕድል!»

t.me/OLDBOOKSPDF

ዐሥረኛ ማስታወሻ

የድሬይፈስ ወንበር

ዲያብሎስ (የዲያብሎስ ደሴት) ከሦስቱ ዱሳሊዮ ደሴቶች አነስተኛዋ ነች። ከዚህም በላይ ይበልጡን ወደ ሰሜናዊ አቅጣጫ ሆና ለነፋስና ለማዕበሉ በጣም የተጋለጠች ነች። ለጥ ካለው የጠረፍዋ አካባቢ የዘበኞች ቤትና በቁጥር ዐሥር የሚሆኑ ከባድ ወንጀለኞች የሚገኙበት ምሽግ ወዳለበት ቁጥ ብሎ ወደ ቆመ አንድ ከፍተኛ አምባ ትነሣለች። ዲያብሎስ በፖለቲካ ምክንያቶች የተወነጀሉና ከሀገር የተባረሩትን ብቻ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውንም ወንጀለኛ በአፈሺያል አትቀበልም ነበር።

አያንዳንዱ የፖለቲካ እሥረኛ የቆርቆሮ ክዳን ያላት ትንሽ ቤት ነበረችው። ለሳምንት የሚበቃው ምግብ ሰኞ ይሰጠውና በየቀኑ ደግሞ አንድ ዳቦ አለው። በግምት ሠላሳ ያህል የእነዚህ ዓይነት ሰዎች ይገኛሉ። የእነርሱ ጤና ረዳት ዶክተር ሴጀር የተባለ በሊዮን አካባቢ ቢተሰቦቹን በመርዝ የጨረሰ አንድ ሰው ነበር። መደበኛዎቹ ከባድ ወንጀለኞች ከሌሎች ጋር ፍጹም ግንኙነት የላቸውም፣ አንድ እሥረኛ ቢበድላቸው ቅሬታቸውን የሚያመለክቱት ወደ ካፖን ነበር። ከዚያም ያ ሰው ወደ ሮያሌ እንዲመለስ ይደረጋል።

ባሕሩ ዘወትር በጣም ቁጡ ስለሆነ ከሮያሌ የሚመጣ የሞተር ጀልባ ከሰሚንቶው የወደብ ድልድይ ሊታሰር ስለማይችል ሮያሌን ከዲያብሎስ የሚያገናኝ አንድ በአየር ላይ የተዘረጋ የጓዝ ማመላለሻ ኬብል ነበር።

የዘበኞቹ ታላፊ በነበረው ሣንቲኒ በተባለና የስምንት ቀን ጺም ባሳደገ አንድ ከፍተኛ ጨካኝ ወደ ካምፑ ስደርስ አቀባበል ተደረገልኝ።

"ፓፒዮ በዲያብሎስ መልካም ሥነ ምግባር እንደምታሳይ ተስፋ አለኝ። ምንም ዐይነት ችግር አትፍጠርብኝ እኔም በሰላም አተውሃለሁ። ወደ ካምፑ ተቃና፤ በኋላ አገኝሃለሁ።" እኔ ከፍል ውስጥ ሰድስት እሥረኞች ማለት ሁለት ቻይናውያን ሁለት ጥቁሮች አንድ ከቦርዶው ሌላው ከሊል የመጡ ነበሩ። ከቻይናውያኑ አንደኛዉ ጥሩ አድርጎ ያውቀኛል። በነፍስ ግድያ ተጠርጥሮ በቅዱስ ላውረን ታስሮ ነበረ። ሐቁ ግን ዜግነቱ ኢንዶ ቻይናዊ የሆነና በፓውሎ ኮንደር አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ከተደረገው ዓመፅ ሕይወቱን ያተረፈ መሆኑ ነበር።

የወጣለት የባሕር ሽፍታ ነበር። ጀልባዎችን በማጥቃት አንዳንድ ጊዜ በውስጡ ያሉትን ሁሉ ወንድ ሴት ሕፃናት ሳይል ይገድላል። ምንም እንኳን በጣም አደገኛ ቢሆንም ቅሉ ጓደኛው አንድ ነገር ሲደርስበት ሐዘኑን የሚካፈልና የሚያበረታታ አብረውት ሊኖሩ የሚገባ ጥሩ ሰው ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት ይሆሃል ፓፒዮ?"

"አንተስ እንዴት ነህ ቻንግ?"

"እለሁ እዚህ ደህና ነው። ከእኔ ጋር ትበላለህ። ከእኔ ጎን ትተኛለህ። በቀን ሁለት ጊዜ ምግብ አበስላለሁ። አንተ ዓሣ ታጠምዳለህ። እዚህ ዓሣ ሞልቷል"።

ሳንቲኒ መጣ። "ታዲያስ ሁላችሁም እዚሁ ተጠራቀማችሁ። ነገ ጧት እሣማዎቹን ለመመገብ ከቻንግ ጋር ትሔዳለህ። ኮከኑቶቹን እርሱ ይሸከማል። አንተ በቀንጨራው እየፈለጥክ ትፈረካከሳቸዋለህ። ፊሳሹን ለዓሣማ ግልገሎቹ አስተርፍላቸው። ከሰዓት በስተቀር ማንኛውንም ደስ የሚላችሁት ነገር ለመሥራት ነፃ ናችሁ። ዓሣ የሚያጠምዱት ሰዎች ሁሉ ለእኔ ወጥ ቀያይ ሁለት ፓውንድ ዓሣ መስጠት አለባቸው። በዚህ ሁኔታ ማንኛውም ሰው ደስተኛ ነው። በእንቶስ በኩል ትስማማበታለህ?"

"እዎ ሚስተር ሳንቲኒ"

"ኃምላጭ ሰው መሆንህን አውቃለሁ፤ ግን ከዚህ ማምለጥ ስለማይቻል ሁኔታው የሚያሠጋኝ አይደለም። ሴሊት ይቆለፍብሃል፤ ግን አንዳንዶቹ እንደሚወጡ ባውቅም ግድ የለኝም። የፖለቲካ እሥረኞቹን ተጠንቀቅ። ሁሉም ቆንጨራ አላቸው ወደቤታቸው አጠገብ ስትሔድ የሚገምቱት እንቁላል ወይም ዶሮዎቻቸውን ልትሰርቅባቸው እንደመጣህ አድርገው ነው። ጉዳት ሊደርስብህና ልትገደል ትችላለህ። አስታውስ እነርሱ ሊያዩህ ይችላሉ። አንተ ግን ልታያቸው አትችልም።"

ሁለት መቶ ዓሣማዎችን ከመገብኩ በኋላ ማንኛዋንም ቦታ በስንዝር ከሚያውቃት ከቻንግ ጋር ሆኜ የቀረውን ቀን ደሴቷን ስዞር አሳልፋለሁ። በባሕሩ ጠርዝ የደሴቷን ዙሪያ ገጠም በማካበብ ላይ እንዳለን ረጅምና ነጭ ሪዝ ያለው አንድ ሸማሌ አቋረጠን። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀርመንን በመደገፍ አንድ ሐተታ የጻፈ ከኒው ካሌዶንያ የመጣ ጋዜጠኛ ነበር። እንደዚሁም ኤዲዝ ካቬል የተባለችውንና በ1917 የእንግሊዛውያንን አውሮፕላን አብራሪዎች ሕይወት ያተረፈችውን እንግሊዛዊት ትሁን ቤልጅጋዊት ነርስ አላስታውስም፤ የገደለውንም ምናምንቴ አገኘነው። በጣም የተዘረጋገፈ እጅግ ወፍራምና ርዝመቱም በግምት አምስት ጫማ የሚሆን ግዙፍ ሰው ነው። የእኔን ጭን የሚያክል አባብ የመሰለ አንድ ግዙፍ ዓሣ ሲቀጠቅጥ ነበር ያገኘነው።

ምንም እንኳ ትንንሾቹ ቤቶች የሚፈቀዱት ለፖለቲካ እሥረኞቹ ብቻ ቢሆንም ጤና ረዳቱም የሚኖረው ከእነርሱ በአንደኛው ውስጥ ነበር።

ዶክተር ሌጀር ጠንካራና ግዙፍ ሰው ነበር። ፊቱ ብቻ ሲቀር ዘወትር ቆሻሻ የሆነ በአንገቱና በጉንጮቹ የወረደ ጉብስማ በመሆን ላይ የሚገኝ ረጅም ጸጉር ነበረው። በባሕሩ ዳር በሚገኙት ሻካራ ቋጥኞች ምክንያት ሳይሆን አይቀርም፤ እጆቹ በጣም

t.me/OLDBOOKSPDF

በተቆራረጡና በተሸነታተሩ ጠባሳዎች ተሸፍነዋል።

"ማንኛውንም የሚያስፈልግህን ነገር ወደ እኔ ብትመጣ አሰጥሃለሁ። ግን የምትመጣው ስትታመም ብቻ ይሁን። እንድነበኝ አልፈልግም፤ ሌላው ቀርቶ ሊያወሩኝ አንኳ ቢሆን። እንቁላሎችና አንዳንድ ጊዜም ሲካካ ዶሮዎች እሸጣለሁ። ምንጊዜም እንዲት ጠቦት ዓሣማ በድብቅ ካረድክ አንድ ወርች እንድታመጣልኝ፤ እኔም አንድ ሲካካ ወይም ስድስት እንቁላሎች አሰጥሃለሁ። እዚህ አስካለህ ድረስ ይሆን ቢልቃጥ እንክብል ተጠቀም፤ በውስጡ እንድ መቶ ሃያ ኪኒኖች አሉ። ወደዚህ የመጣኸው ለማምለጥ መሆን አለበት፤ ስለሆነም በአንድ አይነት ተአምር ከቻልህ እነዚህ ያስፈልጉሃል።"

ጧትና ማታ ቁጥራቸው የበዛ ዓሣዎችን አይዛለሁ። በቀን ሰባት ወይ ስምንት ፓውንድ ለዘበኞቹ ምግብ ቤት አልካለሁ። ሳንቲሂ ገነት ውስጥ ገብቶ ነበር። ይሀን ያህል ብዙ ዓሣ ፍጹም አግኝቶ አያወቅም። በዝቅተኛ ማዕበል በሁለት ጊዜ ማጥመድ እስከ ሦስት መቶ የሚደርሱ ያዝኩ።

ትላንት ዶክተር ጀርሚይን ጉበርት ወደ ዲያብሎስ መጥቶ ነበር። ባሕሩ የረጋ ስለነበር የመጣው ከሮያሌ ወሀኒ አዛዥና ማዳም ጉበርት ጋር ነበር። ይህች ልዩ ሰው ዲያብሎስ ላይ ገና እግሯን ያሳረፈች የመጀመሪያዋ ሴት ነበረች። ከአንድ ሰዓት በላይ አወራኋትና ድሬይፈስ የተባለ ሰው አንቅራ ወደ ጣለችው ፈረንሣይ አትጣጫ በባሀሩ ትይዩ ተቀምጦ ይመለከት ወደ ነበረበት የድንጋይ ወንበር ከእኔ ጋር አብራ ሔደች።

የድሬይፈስ ወንበር ከደሴቷ ሰሜናዊ ጫፍ ከባሕር በላይ በአንድ መቶ ሐያ ጫማ ከፍታ ላይ ትገኛለች። ድንጋዩን በእጇ እየዳሰሰች "የድሬይፈስ አስተሳሰቡች ምን እንደነበሩ ይህ ለስላሳ አለት ሊነግረን ቢችል . . ." አለች። "ፓፒዮ በቅርቡ ለማምለጥ የምትሞክር ከሆነ ምናልባት ለመጨረሻ ጊዜ መታያያችን ይሆናል። እንዲሳካልህ ፈቃዱ እንዲሆን ወደ አማዚአብሔር እጸልያለሁ። ታዲያ ከመሔድህ በፊት መሰነባበቻ እንዲሆነኝ ወደዚህ ተመልሰህ ለእንዲት ደቂቃ በዚህ ወንበር ላይ እንድታርፍ አጠይቅሃለሁ" አለችኝ።

በማንኛውም ባስፈለገኝ ወቅት በአየር ማጓጓዣው ኪብል ዓሣዎች ለዶክተሩ እንድልክ የወሀኒ አዛዡ ፈቀደልኝ። ሳንቲኒም ተስማማ።

"ደህና ሁን ዶክተር፤ ደህና ሁኚ እመቤት።" ጀልባቸው ከመነሳቱ በፊት ደህና ሁኑ ያልኳቸው ከልብ በመነጨ ስሜት ነበር። ምንጊዜም አትርሳን ዘወትር እናስታውስሃለን ለማለት ያህል ማዳም ጉበርትም አፍጥጣ ተመለከተችኝ።

ዛሬ ዓሣ ለማጥመዱ አልሔድኩም። በተፈጥሮ ከተሠራ አንድ ኩሬ ውስጥ ከሁለት መቶ ፓውንድ በላይ ይገር አምስት መቶ ያህል ደግሞ በአንድ የብረት በርሜል ውስጥ አጠራቅሚያለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

1941 ነበር። ወሀኒ ቤት ውስጥ ዐሥራ አንድ ዓመት ሆነኝ። የሕይወቴን አፍላ ዘመኖች ያሳለፍኳቸው በእሥር ቤቶች ከፍል ወይም በጨለማ ማንብ ውስጥ ነበር። ብቸኛው ነጻነቴ ከሕንዳውያን ጎሣዎች ጋር የቆየሁባቸው ሰባት ወሮች ብቻ ነበሩ። ከሁለቱ ሕንዳውያን ሚስቶች የሚናኖሩኝ ሕፃናት ስምንት ዓመት ዕድሜ መድረስ አለባቸው። በከርስቶስ ጊዜው ምንኛ ሐዲል! ግን መለስ ብዬ ስመለከት እነዚያ ሰዓቶችና ደቂቃዎች እያንዳንዳቸው በትውስታ ይደቀኑብኛል።

ሠላሳ አምስት ዓመታት! የክሊሽ መናፈሻ፣ በፐቲ ጎርዶን የሚደረገው የዳንስ ምሽት፣ እና ፕላስ ብላንሽ፣ እነ ሞንትማርትር ወዴት ይሆኑ? በፍርዴ ቀን "አታስብ ፍቅርዬ፣ ከዚህ አወጣሃለሁ!" ብላ ጥቋቁሮቹ ዐይኖቿ ተስፋ በመቁረጥ ሀዘን እንደ ተሞሉ ያለቀሰችውን ዕንቁ የመሰሉችው ታላቋ ኒኔቱ ወዴት ትሆን? "እኛ ነጻ እንለቀቃለን" የሚለው ሬይሞንድ ሂውበረትስ ወዴት ይሆን? ከዚያም ዓቃቤ ሕጉስ? አባቴና የእህቴ ቤተሰቦች በጀርመን ሥር ወድቀው ምን እየሠሩ ይሆን? ብዙ ጊዜ ለማምለጥ ሞክሬያለሁ። የመጀመሪያው ዘበኞቹን ዘርፌ ከሆስፒታል ሳመልጥ ነበር። ሁለተኛው ኮሎምቢያ ውስጥ በሬዮ ሐቻ ነበር። ያ ደስ የሚል ማምለጥ ነበር። ስኬታማ። ለምን ጎሣዎቼን ተውኩ? የሚያንዘፈዝፍ የናፍቆት ትዝታ በመላው ሰውነቴ ተሰራጨ። ከሚስቶቹ ጋር እንደገና የፍቅር ጭውውት የማደርግ መስሎ ነበር የተሰማኝ።

ከዚያም ሦስተኛው፣ አራተኛው፣ አምስተኛውና ስድስተኛው በባራንኳላ የተደረጉት ነበሩ። በእነዚህ ሁሉ ያልቀናኝ ምን ዐይነት ሰንካላ ዕድል ቢኖረኝ ኖሯል!

የመጨረሻውና በጣም መጥፎ ውጤት ያስከተለው በቅዳሴው ሰዓት የጨነገፈው . . . የከሸፈው ፈንጅና በሚቀጥለው ወቅት ደግሞ የከሎሲዎ ሱሪ . . . አልሠራ ያለው የአንቅልፍ መድሐኒት . . . ነበር።

ሰባተኛው ያ ብስብስ ቢቨርት ሴሊየር ያቃጠረብኝ የሮያሌው ነበር። እርሱ ምክንያት ባይሆን ኖሮ በአርግጥም ያ ይሠራ ነበር። ከፍት አፋን ዘግቶ ቢይዝ ኖሮ ካልታደለው ጓደኛዬ ካርቡኔሪ ጋር ነፃ እሆን ነበር።

ከዚያም የመጨረሻውና ስምንተኛው፤ ከአብዶቹ ሆስፒታል ነበር። አንድ ስህተት ፤ የአንድ ደደብ ስሕተት ሠርቻለሁ። ጀልባ የማንሳፈፊያችንን ቦታ ኢጣልያዊው እንዲመርጥ ፍጹም መፍቀድ አልነበረብኝም። ወደ ልኳንዳ ቤቱ አጠገብ ሁለት መቶ ያርድ ራቅ ብለን ወርደን ቢሆን ኖሮ በጣም የተሻለ ቦታ በሆነ ነበር።

የሞት ቅጣት ተፈርዶበት እንደገና ኑሮን ለመቀጠል ብርታትን ያገኘው የዚያ ንጹሕ ሰው የድሬይፈስ ወንበር ለእኔም ወኔን ይሰጠኛል። ሽንፈትን አሜን ብዬ አልቀበልም። እንድ ሌላ ጊዜ ለማምለጥ እሞክራለሁ።

ልክ ነው። ማዕበሎች ያለ ዕረፍት ከሚጋጩበት ቋጥኛማ ባህር ዳር ላይ

t.me/OLDBOOKSPDF

የተንጠለጠለው ይህ እንደ ሐር የለሰለሰ አለት ወኔ ይሰጠኛል። ድሬይፈስ ፍጹም አልተረታም ፤ እስከ መጨረሻ ድረስ ከወንጀሉ ንጹሕ ለመሆን ታግሏል። ሐቅ ለመሆኑም ኤሚል ዞላ "ተከስሻለሁ" በሚለው ገዘኛ መጽሐፉ ይመሰክርለታል።

እንደ ብረት የጠበቀ ጠንካራ ዓላማ ባይኖረው ኖሮ በእርግጥም ከዚህ ወንበር ተምዘግዝጎ ወደ እንጦርጦስ በወረደ ነበር። ታግሏል። እኔም ከእርሱ የማንስ ሰው መሆን የለብኝም። ግን ከማምለጥ አኳያ "እሸንፍ አለበለዚያ ሙት" የሚለውን ሃሳብ አልቀበልም። "ሙት" የሚለውን ቸላ አልና "አሸንፍና ነፃ ሁን" ለሚለው ልዩ ትኩረት እሠጣለሁ።

ድሬይፈስ ወንበር ላይ ተቀምጬ ባስለፍኳቸው ረጅም ሰዓቶች ውስጥ አእምሮዬ ባለፈው የታሪክ ሕልሞችና ወደፊት ጽጌሬዳማ ተስፋ መካከል ሲመላለስ ቆየ። የሚያብለጨልጩትና እንደ ፕላቲኒየም የሚያንጸባርቁትን የማዕበል እንቅስቃሴዎች ከማየቴ የተነሣ ዐይኖቼ ፈዘዙ። ባህሩን በጣም ለረጅም ጊዜ ከመመልከቴ የተነሣ ልብ ብየ ሳላስተውል የማንኛውንም ነፋስና ማዕበል ንቅናቄ ማወቅ ቻልኩ። የተጋለጡትን የደሴቷን ቋጥኞቹ ባሕሩ ያለመሰልቸት በየሥር ሥራቸው እየገባ ሲቦረቡራቸው ዲያብሎስን ሒጂ ጥፊ! በመንገዴ ላይ ሆነሽ ወደ ግራንዴቴሬ መተላለፊያዬን ከልለሽኛል! ከዚህም የተነሣ በየቀኑ ያለርኅራኄ ትናንሽ ሽርፍራፊዎች አነሳልሻለሁ የሚላት ይመስላል። አንድ ሞገድ በሚነሣበት ወቅት ባህሩ ያለውን ቁጣና ሃይል በዲያብሎስ ላይ አውርዶ ከደሴቷ ቆርጦ እየሸራረፈ ከዚያም ጠራርጎ የሚያባርራት ይመስላል። ግዙፎቹ ቋጥኞች ደግሞ ማለፍ አትችልም ያሉት ይመስል ሞገዱ ውሃውን በየስንጣቂዎቹና በየተቦረቦሩት ቀዳዳዎ በማዝለቅ ቀስ በቀስ ሲጨርሳቸው ይታገላል።

አንድ በጣም ጠቃሚ ግኝት የተከሰተልኝ በዚሁ ሁኔታ ነበር። በቀጥታ ከድሬይፈስ ወንበር ትይዩ ከሚገኙ ሁለት ጥርብና ግዙፍ ቋጥኞች ጋር ልዩ በሆነ ሃይል የሚጋጩ ማዕበሎች ነበሩ። ውሃው መሐጃ አልነበረውም ምክንያቱም እነዚህ ሁለት ቋጥኞች የፈረስ ኮቴ የመሰለ ቅርፅ በመሥራት በግምት አምስት ወይም ስድስት ያርድ ስፋት ሲኖራቸው ማዕበሎቹን ወደ ባሕሩ ከመመለስ በስተቀር ማለፊያ የሚያሳጣ አንድ ገደል ደግሞ ከበላያቸው ቀጥ ብሎ ቆሟል።

የዚህም ጠቃሚነት ማዕበሉ እየተወረወረ ወደዚህ ጠባብ ሸለቆ ሲመጣ እኔ አንድ ጆንያ ኮክነት በመያዝ በቀጥታ ከቋጥኙ ወደ መካከል ብዘል ወደኋላ ሲመለስ አብሮ የሚወሰደኝ መሆኑ የሚያጠራጥር አልነበረም።

ለኮክነቶቹ መያዣ የሚሆን የታጠፈ ጆንያዎች ከየት ላገኝ እንደምችልም አውቄአለሁ ዐሣማዎቹ ጉሮኖ ውስጥ በብዛት ነበሩ።

የመጀመሪያው ጉዳይ ሐሳቤን በተግባር መሞከሩ ነበር። በሙሉ ጨረቃ ሰሞን

t.me/OLDBOOKSPDF

የባሕሩ ንቅናቄ እያደገ ሲሔድ በዚያው አካያ ማዕበሎቹም ከፍ ይላሉ። ሙሉዋን ጨረቃ አጠቢቃለሁ። በጥንቃቄ የተሰፋውን የኮከነት ጅንያ ከማውቀው አንድ ዋሻ ውስጥ ደበቅኩት። ላውቀው የቻልኩትም አንድ ቀን ዓሣዎች በምፈልግበት ወቅት ነበር። በዝቅተኛ የባህር ንቅናቄ ካልሆነ በስተቀር ጣሪያው በቀንድ ለበሰ ዓሣዎች አጥንት ተለብዶ ሙሉ በሙሉ ከውሃው ሥር ነበር። በግምት ከብደቱ ሰማኒያና ዘጠና ፓውንድ ቋጥኝ የተጠጠረበት አንድ ሴላ ከረጢት ከኮከነቱ ጅንያ ጋር አቆራኘሁ። በሁለት ጅንያዎች ለለምሔድና የእኔም ከብደት አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ፓውንድ በመሆኑ አመጣጤ ትከከለኛ ነበር።

በሙከራዬ በጣም ተደነቅኩ። በዚህ በኩል ያለው የደሴቷ ኣካባቢ አደገኛ ነበር። በደሴቷ ከሁሉም በላይ ነፋሻማ የሆነው ይህ ሥፍራ ለማምለጥ መጠቀሚያ ይሆናል ብሎ መቸውንም የሚጠረጥር ማንም ሰው የለም።

ከዚህም በላይ ከባሕሩ ጠረፍ መልቀቅ ከቻልኩ ሮያሌ ሳልደርስ አደጋ ላያጋጥመኝ ወደ ፊት የሚያዘልቀኝ ብቸኛው ቦታ ይኸው ነበር።

የጅንያው ኮከነትና ቋጥኙ ከባድ ስለነበሩ ለሽከም አስቸጋሪ ሆኑ። ብቻዬን ማድረግ አልቻልኩም፣ ስለዚህ ከቻንግ ጋር ተነጋገርኩና መጥቼ እረዳሃለሁ አለኝ። የዓሣ መንጠቆና ከባድ ሲባጎዎች ይዞ መጣ ከተያዝን ለዓሳነባሪዎች ወጥመድ ልናዘጋጅ ነው እንላለን።

"መግፋት ቀጥል ቻንግ። ትንሽ ፈቀቅ ካልን እዚያው እንደርሳለን።"

የሙሉዋ ጨረቃ ብርሃን ልክ እንደ ቀን ወለል ብሷል። የማዕበሎቹ ዋካታ ጆሮ ያደነቁር ነበር። "ተዘጋጀህ ፓፒዮ? ከዚህ ቀጥሎ ወደሚመጣው?" አለ ቻንግ ዐሥራ አምስት ጫማ ከፍታ ያለው አንድ ማዕበል የቻለውን ያህል ወደቋጥኙ ተቃንቶ ልክ ከሥራችን ሲከሰክስ። ንቅናቄው በጣም አስፈሪ ከመሆኑ የተነሣ ፍንጣቂው አልብሶን ከበላያችን አለፈ። ያም ሆኖ ማዕበሉ ወደ ኋላ በሚመለስበት ወቅት ጅንያውን መወርወር ችለን ነበር። ጅንያዋ ልክ እንደ ሣር ተንሳፍፋ ወደ ተንጣለለው ባሕር ገባች።

"ይኸ ነው ቻንግ! ሠራ!!"

"ትመለስ እንደሆነ ቆይና ጠብቅ"

ዕውነትም ነበር። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ጅንያዋ በአንድ ማዕበል ላይ በሐያ ጫማ ከፍታ ወደ ኋላ መጋለቢን ሳይ ልቤ በሐዘን ተሸማቀቀ። ከቋጥኞቹ ጋር ተላተመችና ኮከነቶቹን በየአቅጣጫው በታኑና ወደ ሽለቆው ቁልቁል ተምዘገዘገች።

አግሮቻችንን ነቅሎ ጠራርጎ ሊወስደን ምንም ያልቀረውንና ያን ሰይጣናም ቦታ ብዙም ወደ ኋላ መለስ ብለን ሳንመለከት ቻንግ እና እኔ አጥንታችን ድረስ በውሃ እንደ በሰበሰን ተመለስን።

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጥሩ አይደለም ፓፒዮ። ከዲያብሎስ ማምለጥ ጥሩ አይደለም። ሮያሌ ይሻላል። ከደቡብ ጠረፍ መነሣቱ በጣም ይመረጣል።"

"አዎ፤ ግን ከሮያሌ ማምለጥ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ያስይዛል። የኮከነቶቹ ከረጢት የሚንቀሳቀሰው በማዕበሎቹ ብቻ ስለሆነ ጊዜ ሳይወስዱ ይይዙኛል። እዚህ ጀልባ የለም መሐዴን ከማወቃቸውም በፊት ሙሉ ሌሊት አለኝ ያም ሆኖ እንኳ ዓሣ ሲያጠምድ ሰምጧል ብለው ይገምቱ ይሆናል። በተጨማሪ በዲያብሎስ ስልክ የለም። በከባድ የባህር እንቅስቃሴ ወቅት ብሔድ ከሮያሌ ጋር የሚገናኙበት ምንም ዘዴ የላቸውም። ስለዚህ መሐዴ ያለብኝ ከዚሁ ነው። ግን እንዴት?"

የቀትሯ ፀሐይ እስከ መጨረሻው ድረስ ትነድ ነበር። በራስ ቅልህ ውስጥ ያለውን አንጎል የምትቀቅል የምድር ወገብ ፀሐይ ያልጠነከሩ ዕፅዋትን ኩምትርትር የምታደርግ ፀሐይ በጣም ጥልቅ የሆኑ የጨው ውሃ ኮሬዎችን በትንሽ ሰዓት ውስጥ ከሸን ወዳለ የጨው ግግር የምትለወጥ ፀሐይ፤ አየሩን እየቀዘፈች ከፀይኖቹ ሥር የምታስደንስ፣ በውሃው ላይ የሚያርፈውም ነጸብራቋ ብሌኖቹን የሚያቃጥለኝ ፀሐይ ወደ ድሬይፈስ ወንበር ተመልሼ ስለ ባሕሩ መከታተሌን ልትገታኝ አልቻለችም። ከዚያ በኋላ ነበር ምን ፀይነት ሞኝ እንደነበርኩ ሊከሰትልኝ የቻለው።

ጆንያየን ወደ ኋላ መልሶ ከጭጥኞቹ ጋር ከሰከሳት፣ ከሰባቱ ማዕበሎች መካከል እንደ ደራሲን ግዙፍ የሆነው አንደኛው ብቻ ነበር። ሌሎቹ ከአርሱ ግማሽ መጠን ትንሽ ከፍ የሚሉ ነበሩ። ይህ ዘወትር ተመሳሳይ መሆኑን አልፎ አልፎም የመቀያየር ሁኔታ እንደሌለው ወይም ልማዱን ለመለወጥ ያሰኘው እንደሆነ ከቀትር ጀምሬ ጀምበር እስከትጠልቅ ድረስ ስመለከት አውላለሁ።

አልነበረም። የመሬቱ ዕብጠት ፍጹም ፈጥኖ አይመጣም፣ ፍጹም ዘግይቶ አይመጣም። በግምት ሃያ ጫማ ከፍታ ያለው ማዕበል ነበር፣ ከባሕሩ ዳር በግምት ሦስት መቶ ያርድ ርቀት ይጀምርና ያብጣል። ልክ እንደ መድፍ ጥይት ተወርውሮ በቁመትም ሆነ በመጠን እያደገ ይጠጋል። ከሌሎቹ ስድስቱ ጋር ሲነጻጸር በመጠኑ ይተልቃል። ጫፉ ላይ ብዙም ፍንጣቂ የለውም። ልክ በሩቅ የሚያጉረመርም ነጎድጓድ የመሰለ የራሱ ልዩ ድምፅ ነበረው። በሁለቱ ቋጥኞች ላይ ይከሰክሰና በመካከላቸው ባለው መሹለኪያ ውስጥ ተሽቀንጥሮ ለመውጣት ሲል ከገደሉ ጋር ተጋጭቶ፣ የተከመረው ውሃ እየተጨናነቀ በገዛ ራሱ ይመለሳል። ከዚያም ከዐሥር ወይም ዐሥራ አምስት ሴኮንድ በኋላ አነስተኞዎቹ ማዕበሎች ግዙፎቹን ድንጋዮች ወደ ኋላና ወደፊት እየናጡ በመፈረካከስ ከመቶ ሠረገላዎች እንደሚገለበጡ አሸዋድጉደዋቸው መንገዳቸውን ይቀጥላሉ።

አንድ ጆንያ ውስጥ አንድ ደርዘን ኮከነቶችና ሃምሳ ፓውንድ የሚመዝን አንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድጦኝ ጨመርኩበት። ማዕበሉ ሲያብጥ ጅንያውን ወረወርኩት። በሚረጨው ኮረፋት ምክንያት ዐይኖቼ ሊከተለው አልቻለም፤ ግን ውሃው ወደ ባሕሩ በመመለስ ላይ እንዳለ ለሁለተኛ ጊዜ አየሁት። አልተመለሰም። የሚቀጥሉት ስድስቱ ማዕበሎች መልሰውት ወደ ባሕሩ ዳር ለመወርወር ኃይል አነሳቸው፤ ሰባተኛው ማዕበል ከሶስት መቶ ያርድ ላይ መነሣት ሲጀምር ጅንያው ከዚያ ባሻገር አልፎ መሆን ይኖርበታል ዳግመኛ አላየሁትም።

ደንቆኝ በደስታ ልፈነዳ እንደ ተቃረብኩ ወደ ካምፕ ሔድኩ። ዐወቅኩት! ትከለኛውን ማንሳፈፊያ አግኝቼአለሁ። እንግዲህ ዕድል የሚባል ነገር የለም። እንደገና አንድ ሌላ ሙከራ አደርጋለሁ። በአሁኑ ጊዜ ዕውነተኛ የማምለጥ ግፊት ባለው ስሜት፣ ሁለት ጅንያ ኮከነቶች አንድ ላይ በመቀርቀብና በጠቅላላው አንድ መቶ ሃምሳ አምስት ፓውንድ የሚመዝኑ ሁለት ወይም ሦስት ቋጥኞች በላዩ ላይ በማድረግ ይሆናል። ስለ ሁኔታው ለቻንግ ስነግረው በጥሞና አዳመጠ።

"ጥሩ ነው ፓፒዮ። እንደ መሰለኝ ዐውቀኸዋል። ከፉኔ አረዳሃለሁ። ሃያ አምስት ጫማ ከፍታ የሚሆነውን የባሕር እንቅስቃሴ ወቅት ጠብቅ። ቀንና ሌሊቱ ዕኩል ሚሆንበት ወራት በቅርቡ ይደርሳል።"

ከዚያም በቀንና ሌሊት ተመጣጣኝ ወራት የሃያ አምስት ጫማ ከፍታ የባህር እንቅስቃሴና በቻንግ እርዳታ፤ ሁለቱን ጅንያዎችና ሦስቱን ቋጥኞች ወደ ታወቀችው ማዕበል ወረወርን።

"በቅዱስ ዮሴፍ ልታጥርቃት የምከርከው ትንሽ ሴት ልጅ ስም ማን ይባል ነበር?"

"ሊሴቴ"

"አንተን የምትወስድህን ማዕበል ስምም ሊሴቴ ብለን እንለይማት። እሺ?"

"እሺ"

ሊሴቴ ወደ ጣቢያዋ የምትገሠግሥ አንዲት ፈጣን ባቡር መስላ እያጓራች መጣች። ልክ እንደ ምሽግ ቀጥ ብላ እየቆመች በየሴኮንዱ ትጨምራለች። በጣም ግራቢ ትዕይንት ነበራት። ከኃይለኛነቷ የተነሣ ቻንግና እኔ ከቋጥኙ ላይ ተጠራርገን ከመውረድ አመለጥንና ጅንያዎቹ ወረዱ። በቋጥኙ ላይ ቆመን መቆየት አለመቻላችንን በሴኮንድ ውስጥ ተገነዘብንና ወደ ኋላ ተፈናጥረን ተመለስን፤ ግን ከመውደቅ ባለተርፍም፣ ከመበሰበስ አልዳንም። ይህ የሆነው ከጧቱ አራት ሰዓት ላይ ነበር። ለምንም አደጋ ጥንቃቄ አልወሰድንም፤ ምክንያቱም ሦስቱም ዘበኞች ከደሴቷ በሌላ ጣረፍ በኩል የንብረት ቆጠራ ሥራ በማከናወን ላይ ነበሩ። ጅንያዎቹ ከባሕሩ ዳር በጣም ርቀው እንደወጡ በግልጽ ልናያቸው ቻልን። ከማዕበሉ ዕጠጠት ባሻገር ይሆኑ? ጠበቅን። ሊሴቴን የሚከተሉት ስድስቱ ማዕበሎች ሊደርሱባት አልቻሉም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለሁለተኛው ጊዜ መጥታ ተመለሰች፤ ግን ጆንያዎቹ አሁንም የሉም። ከመድረሻዋ ባሻገር ሆነዋል።

እንደገና ልናያቸው እንችል እንደሆነ ለመመልከት ወደ ድሬይፈስ ወንበር በፍጥነት ተቃናን። ጆንያዎቹ በእራት የተለያዩ ጊዜያት ማዕበሎቹ አናት ላይ ሲጋልቡ እየናቸው። ማዕበሎቹ ወደ ዲያብሎስ አቅጣጫ ሳይመጡ የሚያመሩት ወደ ምዕራብ ነበር። ማመሳከሪያውን አግኝተናል። በሊሴቴ ጀርባ ሆኜ በታላቁ አስቸጋሪ ጉዞ አቅጣጫ ልቀዝፍ ነው።

"ተመልከት፤ እየመጣች ነው" አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት . . . ከዚያም ሊሴቴ።

ከድሬይፈስ ወንበር በታች ያለው ባሕር ዘወትር ከባድ ነበር፤ ግን በተለይ ዛሬ ደግሞ የባሰ ክፉ ሆኗል። ሊሴቴ ከተለመደው ጩኸቷ ጋር እየገሠገሠች ነበር። ከመቼውም ይበልጥ ያደገች ትመስላለች። ካሁን በፊት ከምታደርገው ከመቼውም በበለጠ ፍጥነትና ቀጥተኛነት አስፈሪ በሆነው ቁልቋ ሁለቱን ቋጥኞች አፋጨቻቸው። በምትከሰከስበት ወቅት ያስተጋባው ጩኸት ጨርሶ ጆሮ ያደነቁር ነበር። "እንድንዘል የምትፈልግበት ቦታ ይኸ ነው? መልካም፣ በዕርግጥም አንድ ከፍተኛ ቦታ ቀንቶሃል! ግን ለእኔ አይደለም። የምፈልገው የማምለጥ ሙከራ ለማካሔድ እንጂ ራሴን በራሴ ለመግደል አይደለም።

ስለ ሊሴቴ ባቀረብኩት ዘገባ ሲልቪያን ደንቆት ነበር። ,ዘ:ለት ቀኑ ገፊት ወደ ዲያብሎስ መጥቶ ሳለ እንደ ተለመደው እያንዳንዳችን በየራሳችን ጀልባ ሆነን አብረን እንድንሔድ አቅጃለሁ። የሚስማማ ከሆነ በግራንዴቴሬ ደግሞ ለሁለተኛው የማምለጥ ሙከራ የሚተባበረኝ አንድ ኢጋር ማግኘት ይኖርብኛል። ጫካ ውስጥ ለብቻ መገኘት ሽርሽር አይሆንም።

"ጊዜው ሳይደርስ ቀድሞ መፍራቱ ፍሬ የለውም። በመጀመ,ጋ አስተሳሰብ ማንኛውም ሰው ትንሽ ሊያቅማማ እንደሚችል እገነዘባለሁ። ግን እስከ መጨረሻው አርቆ የሚያዘልቀን ብቸኛ ማዕበል ይኸው ነው።"

"አትሸበር። ስማ፤ እኛ ሞከረነዋል" አለ ቻንግ። እርግጠኛ ነገር ነው። አንድ ጊዜ ከሔድክ በኋላ ወደ ዲያብሎስም ሆነ ወደ ሮያሌ ተገፍተህ አትመለስም። የፈረጠመ ጡንቻ፣ ስድስት ጫማ ቁመትና የስፖርተኛ አቋም ያለውን ሲልቪያንን ለማሳመን ፤ አንድ ሳምንት ያህል ወሰደብኝ።

"እሺ፣ እስኪ እስከ መጨረሻው ርቀት ስንሔድ አያለሁ። ግን ከዚያ በኋላ ግራንዴቴሬ ለመድረስ ምን ያህል ጊዜ ይወስድብናል?"

"ዕውነቱን ለመናገር ከሆነ አላውቀውም። የባሕሩን ግፊት የሚወስነው የአየሩ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠባይ ነው። ነፋሱም በመጠኑ ተጽዕኖ ይኖረዋል፤ ምክንያቱም በውሃው ላይ በጣም ዝቅ እንላለን። ግን ከባድ የአየር ጠባይ ብናገኝ ማዕበሎቹ ከፍ ይሉና በፍጥነት ይገፉናል። ቢበዛ ሰባት፣ ስምንት፣ ዐሥር የባሕር እንቅስቃሴዎች ካሳለፍን በኋላ ወደ ዋናው የብስ መድረስ ይኖርብናል። በአማካይ ግምት አርባ ሰምንትና ስድሳ ሰዓት መካከል ሊወስድ ይችላል።"

"እንዴት መገመት ቻልክ?"

"ከደሴቶቹ እስከ ዋናው የብስ ድረስ ከሃያ አራት ማይል አይበልጥም።"

የባሕሩ ግፊት መስመር ከሦስቱ ማዕዘኖች በረጅሙ በኩል ነው። የማዕበሎቹን አቅጣጫ ተመልከት። ቢበዛ ከሰባ አምስትና ከዘጠና ማይል መካከል መጓዝ አለብን። ወደ የብስ እንደ ተጠጋን በሐድን መጠን ማዕበሎቹም ይበልጥ ወደ ጠረፉ እንድናመራ ግፊታቸውን ይጨምራሉ። በዚህ ርቀት በውሃ የሚገፉ አንድ ቁራጭ የባሕር እንጨት ከጠረፍ ቢነሣ ቢያንስ በሰዓት ሦስት ማይል ይጓዛል ብለህ አትገምትም?"

ገላጻዎቼን በጣም ተጠንቅቆ አዳመጠ። ግድንግዱ ሰው የወጣለት ጮሌ ነበር።

"ትከከል መሆንህ ተሰምቶኛል። ወደ ኋላ የሚጎትቱን ዝቅተኛ የባሕር እንቅስቃሴዎች ካልሆኑ በስተቀር የብስ ለመድረስ ከሠላሳ ሰዓቶች የበለጠ አይወስድብንም። ሒሳቡን አስልቼ አንደ ደረስኩበት በአማካይ ግምት ከአርባ ስምንትና ከስድሳ ሰዓት መካከል ይወስዳል።"

"ተማመንከበት?"

"ወደዚያው ነኝ። ግን ግራንዴቴሬ ደርሰን ጫካ ከገባን ወዲያ ምን እንሆናለን?"

"ወደ ኩሩ ድንበር የሚያደርሰንን መንገድ መፈለግ ይኖርብናል፥ ሞቅ ያለች የዓሣ አጥማጆች ትልቅ መንደር ነች፣ ከዚህም በላይ ወርቅና የሙጫ ዛፎች የሚፈልጉ ሰዎች አሉባት። ግን መጠንቀቅ ይኖርብሃል ምክንያቱም የከባድ እሥረኞች ካምፕ ይገኝባታል። ወደ ካየንና ኢኒኒ ወደ ምትባል የቻይናውያን ካምፕ የሚወስዱ ተመሳሳይ የእግር መንገዶች ይኖራሉ። ኢኒኒ የሚያደርሰን አንድ እሥረኛ ወይም አንድ ሲቪል ማስገደድ አለብን። አምስት መቶ ፍራንክ እንሰጠውና እንዲሰማማ እናደርገዋለን። እሥረኛ ከሆነም ከእኛ ጋር እንዲያመልጥ እንጋበዘዋለን።"

"የቻይናውያን ካምፕ ከሆነችው ኢኒኒ ምን እናደርጋለን?"

"የቻንግ ወንድም የሚኖረው እዚያ ነው።"

"አዎ፤ የእኔ ወንድም እዚያ አለ። ከናንተ ጋር አምልጦ ይሔዳል። ጀልባና ምግብ ይፈልግላችኋል። ኪኪን ስትገናኙ ለማምለጥ የሚያስፈልጋችሁን ማንኛውንም

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር አገኛችሁ ማለት ነው። ቻይናውያን ፍጹም አይፈሩም። በጫካው ውስጥ የምታገኙትን ማንኛውንም መንደረኛ ለኪኪ እንዲነግርላችሁ ንገሩት።"

"ወንድምህ ኪኪ ተበሎ የተሠየመው ለምንድነው ነው?" ሲል ሲልቪያን ጠየቀው።

"አላውቅም። ፈረንሣውያን ኪኪ ብለው አጠመቁት" አለና ከዚያ አከታትሎ "ተጠንቀቁ! ግራንዬቴሬ ለመድረስ ስትቃረቡ የአሸዋ ማጥ አለ። በአሸዋው ማጥ ላይ ፍጹም እንዳትራመዱ መጥፎ ነው። ይውጣችኋል። ወደ ጫካው ውስጥ እንዲገፋችሁ የሚቀጥለውን የባሕር እንቅስቃሴ ጠብቁ፤ ስለዚህ ሐረግ ወይም ቅርንጫፎች ትጨመድዳላችሁ። ያ ካልሆነ አሰቀላችሁ" አለ።

"እሺ ፓፒዮ። ካንተ ጋር አሔዳለሁ" አለ ሲልቪያን።

"እንግዲያው መልካም ጀልባዎቻችን ተመሳሳይና ከብደታቸውም በእጣኪይ ተመጣጣኝ መሆን አለባቸው። በብዙ ልዩነት መራራቅም የለብንም። ግን የሚሆነው ፍጹም አይታወቅምና መለያየት ቢያጋጥመን እርስ በርሳችን የምንገናኝበትን ዘዴ መፈለግ ይኖርብናል። እዚህ ሆነህ ኩሩን ለማየት አትችልም፤ ግን ሮያሌ በነበርክበት ወቅት ከኩሩ በስተቀኝ በኩል በግምት ዐሥራ ሁለት ማይል ራቅ ብሎ ቀጥ ብለው የቆሙ ቋጥኞች እንዳሉ ታስታውሳለህ?"

"አዎ"

"በመላው የባሕሩ ጠረፍ ያሉት ቋጥኞች እነርሱ ብቻ ናቸው፤ በግራም ሆነ በቀኝ ለብዙ ማይሎች ከአሸዋ ማጥ በስተቀር ምንም ነገር የለም። በአሞራዎቹ ኩስ ምክንያት ቋጥኞቹ ነጫጮች ናቸው። በሺ የሚቆጠሩ አሞራዎች አሉባቸው፤ ወደዚያ አጠገብ ምንጊዜም የሚቀርብ ሰው እስከሌለ ድረስ የጫካውን ጉዞ ከመጀመራችን በፊት ትንሽ እፎይ ለማለት ጥሩ ቦታ ነው። እንቁላሎችና ኮከነታችንን መበላትም እንችላለን። እሳት ማንደድ የለብንም። በቅድሚያ እዚያ የደረሰ ሌላውን ይጠብቃል።"

"ለስንት ቀናት?"

"እምስት። ከአምስት ቀን በላይ አይወስድም። ሊሆንም አይችልም።"

ጀልባዎቹ ተዘጋጁ። ጆንያዎቹን ለማጠናከር ደራረብንና የሚቀጥሉትን ዐሥር ቀናት እነርሱን በመጋለብ ልንለማመድ ወሰን። ጆንያዎቹን ከመገልበጥ ለመጠበቅ የተለየ ጥረት እንደማያሻው ወዲያውኑ ተረድተናል። በሚቻልበት አጋጣሚ ሁሉ ለጥ ብሎን መጋደም እንዳለብንና ግን እንቅልፍ ላለመውደቅ መጠንቀቅ ነው። ከወደቅን፤ እንደገና ተመልሰን መንጠልጠል አንችል ይሆናል። እንጉቴ ላይ የማንጠለጥላት ሲጃራና ማቀጣጠያ የምትይዝ ውሃ የማያረጥባት አንዲት ትንሽ ከረጢት ቻንግ ሠራልኝ። እያንዳንዳችን አሥር ኮከነቶች ልንከሰከስ ነው። ውሃ ጥሙንም ሆነ ረኃቡን ይከላከላል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለጉቲኒ ወይን ጠጅ የሚይዝባት አንድ እርኩት ነበረችው። ዘበኛውን አልፎ አልፎ የሚሰበኘው ቻንግ ያችን አጭልጎት ነበር።

ጉዳዩ አሑድ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ ሊደረግ ታቀደ። ሙሉ ጨረቃ ስለምትወጣና የሃያ አምስት ሜማ ከፍታ የባሕር እንቅስቃሴ ስለሚኖር ሊሴቴ በመጨረሻው ኃይሏ ላይ ትሆናለች። በዚያ አሑድ ጧት ቻንግ ዐሣማዎቹን ብቻውን ሊመግብ ነበር። ቅዳሜና አሑድን በሙሉ እኔ ልተኛ ነው። ጉዞው አራት ሰዓት ላይ ሊሆን ታቀደ። የባሕሩ እንቅስቃሴ መመለስ የሚጀምረው ከሁለት ሰዓት ቀደም ሲል ነው።

ሁለቱ ጆንያዎቼ በምንም መንገድ መበታተን አይችሉም። ለጀልባ የነፋስ ሽራ መጠቀሚያ በሚሆኑ ጠንካራ ከሮች ተሰፍተው ከመዳብ ሽቦና ከቃጫ በተጎነጎኑ ገመዶች አንድ ላይ ተቀርቅበው ታስረዋል። ከተለመደው የበለጡ ትላልቅ ጆንያዎች አማኙተን እንዳታቸውን በማስተላለፍ ስለአቆራኝናናቸው ኮከነቶቹ አፈትልከው መውጣት አይችሉም።

ሲልቪያን ከመቼውም የበለጠ የሰውነት እንቅስቃሴ ያደርጋል፤ እኔም ትናንሾቹ ማዕበሎች ታፋየን ማሳጅ እንዲያደርጉልኝ እግሮቼን ለረጅም ሰዓት እባሕሩ ውስጥ አጋድማለሁ። የማያቋርጠው ግፊትና ያንንም ለመቋቋም የማደርገው መውተርተር የበረት ባቶችና ታፋዎች ሰጠኝ።

በአንድ የደረቀ የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ርዝመቱ በግምት ሦስት ያርድ የሆነ አንድ ሰንሰለት አገኘሁና ጆንያዎቼን አንድ ላይ ከቀረቀበው ገመድ ጋር በውስጥና በውጭ አጠላልፌ ተበተብትኩ። ከዚያም ከአንድ ጫፍ በኩል አንድ ብሎን አበጀሁለት። አስፈላጊ መስሎ በሚታየኝ ወቅት ራሴን ከጆንያዎቼ ጋር አስርበታለሁ። በዚህ መንገድ ወደ ውሃው ውስጥ ሳልወድቅና ጀልባየንም ሳላጣ ለሙተኛት እችላለሁ። ጆንያዎቹ ቢገለበጡም ውሃው ወዲያው ያባንነኝና ጀልባዋን ለማስተካከል እችላለሁ።

"ፓፒዮ፣ ልክ ሦስት ቀን ቀረን።" ሊሴቴን እየተመለከትን በደሬይፈስ ወንበር ላይ ተቀምጠን ነበር።

"አዎ፤ ልክ ሦስት ቀን ቀረን።" እንደሚሳካልን እምነቴ ነው። አይመስልህም አንዴ?"

"እርግጠኛ ነኝ ፓፒዮ። ማከሰኞ ሌሊት ወይም ረቡዕ ጧት ጫካ ውስጥ እንገባለን። ከዚያ በኋላ ተገላገልን!"

ቻንግ ለእያንዳንዳችን ዐሥር ኮከነቶች አቀረበልን። ከጩቤዎቻችን ሌላ ከብረታብረት ግምጃ ቤት ያነሣናቸው ሁለት ገጀራዎች ነበሩን።

የኢኒኒ ካምፕ ከኩሩ በስተምሥራቅ ነች። በእቅጣጫችን ለመተማመን ከጧት

t.me/OLDBOOKSPDF

ፀሐይ ጋር መጓዝ አለብን።

"ሰኞ ጧት ሳንቲኒን እናሞኝዋለን። እኔ ምንም አልናገር፣ ሰኞ ኪሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ዘበኞቹ ዕረፍት ላይ አንዳሉ ፓፒዮና ሲልቪያን ጠሩ ብቻ አላለሁ።" አለ ቻንግ።

"ግን ዓሣ በማጥመድ ላይ እንዳሉ አንድ ማዕበል ጠራርጎ ወሰዳቸው ለምን አትልም?

"አይሆንም። ጣጣ ውስጥ ለመግባት አልፈልግም። ጌታዬ፣ ፓፒዮና ሲልቪያን ዛሬ ወደ ሥራ አልመጡም። ዓሣማዎቹን የምመግበው ብቻየን ነው አላሰሁ። የሚጨመር የሚቀነስ የለም።"

ከዲያብሎስ ማምለጥ

አሑድ ከምሽቱ ልከ አንድ ሰዓት ከአንቅልፍ ነቃሁ። ከቅዳሜ ጧት አንሥቼ ተኝቼ ነበር። ጨረቃዋ በሦስት ሰዓት ትወጣለች። በጣም መጠነኛ ኮከቦችና ዝናም ያዘሉ ከባድ ደመናዎች ከበላያችን የሚነዱበት የጥቁር ጥቁር ሌሊት ነበር። አምባውን ያኔውኑ 'ቁቀቅን። ሌሊት ዓሣ ለማጥመድ ወይም በደሴቷ አካባቢ ለመዘዋወር አዘውትረን እየተሸለከን ስለምንወጣ ሌሎቹ ዛሬም እንደ ተለመደው ሊያደርጉ ነው ብለው ገምተዋል።

"እንሒድ!" በችኮላ ወደ ደሴቷ የመጨረሻ ሰሜናዊ ጫፍ ሸመጠጥን።

ሁለቱን ጀልባዎች ከዋሻው አወጣን። ምንም ሳንቆይ ሦስታችንም በውሃ ተዘፈቅን። ነፋሱ በእውሎ ነፋስ ደረጃ ያፏጭል። ጀልባየን ወደ ቋጥኙ ጫፍ ለማውጣት ሲልቪያንና ቻንግ ተባበሩኝ። ከጀልባዋ ዙሪያ በተተበተበው ገመድ የግራ እጇን አንጓ የማቆራኘት ሐሳብ በመጨረሻዋ ደቂቃ መጣልኝ። ብቻየን ብወሰድሳ የሚለው ሐሳብ ድንገት አስጨነቀኝ። ሲልቪያንም በቻንግ እርዳታ ፊት ለፊት ካለው ቋጥኝ ላይ ተንጠላጠለ። ጨረቃዋ ቀደም ሲል ከፍ ብላለች። ጥርት ብላ ለማየት ቻልን።

አንድ ፎጣ ጭንቅላቴ ላይ ጠመጠምኩ። ስድስት ማዕበሎች ማሳለፍ ነበረብን። ከሠላሳ ደቂቃ በለጠ።

ቻንግ ወደ እኔ ተመልሶ መጣና አንገቴን ጥምጥም እድርጎ ይዞኝ ጉንጩን ሳመኝ። ከዚያም የማዕበሉ ንቅናቄ ሲገፈትረኝ መቋቋም እንድችል ባቶቼን ከቋጥኙ መካከል እንደ ሽብልቅ አቆምኩ።

ሲልቪያን "እንድ ቀረን፤ ከዚያም የመጨረሻው ይሆናል!" ሲል ጮኸ። የሚመጣውን ፈረሰኛ ውሃ በሰውነቱ ተከላክሎ ሊከልል ከጀልባው ፊት ቆሞ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተጨማሪዎቹ የቻንግ አጅች ድጋፍ ጋር እኔም በተመሳሳይ አቅጣጫ ሆኛለሁ። ከመደነቁ የተነሣ የባቶቼን ጡንቻዎች በእግሮቹ ጥፍሮች ይወጋኛል።

በጉዞዋ ላይ ትገኛለች፤ ሊሴቴ ልክ እንደ ቤተክርስቲያን ጉልላት ቀጥ ብላ በቀጥታ ወደ እኛ ትገሠግሣለች። ከተሰመደው ኢደንቋሪ ጉርምርምታዋ ጋር ከእኛ ቋጥኞች በላይ ተከሰከሰችና ወደ ገደሉ አሻቀበች።

ሴኮንድ ባልሞላ ጊዜ ከጓደኛዬ ቀድሜ ስወረወር እርሱም እንደዚሁ ተከተለኝና አንድ ላይ አንደ ተጠጋጋን ሊሴቴ በሚያፈዝዘው ፍጥነቷ እየሳበች ወደ ሰፈው ባሕር አስገባችን። አምስት ደቂቃ ሳይሞላ ከጠረፉ ከሦስት መቶ ያርድ በላይ ራቅን። ሲልቪያን ገና ጀልባው ላይ አልተፈናጠጠም። እኔ ግን በሁለት ደቂቃ ውስጥ ወጥቼ እግሮቼን አንፈራጥጫለሁ። ቻንግ ወደ ደሬይፈስ ወንበር ተንደርድሮ ወጣና አንድ ነጭ ጨርቅ በእጁ ይዞ የመጨረሻ መሰነባበቻ ያውለበልብልን ጀመር። አሁን ማዕበሎቹ አቅጣጫቸውን ወደ ዳያብሎስ ሊማምራት ከሚጀምሩበት አደገኛ አካባቢ በአምስት ደቂቃ አምልጠናል። እንንሳፈፍባቸው የነበሩት ማዕበሎች በጣም ሰፊዎችና ከፍታ ስላልነበራቸው ያለምንም መንጠርና ጀልባዎቻችንም የመገልበጥ አደጋ ሳያጋጥማቸው ጉዞዋችንን መግፋት ቻልን።

ከረጅም ከፍታ ወደ ከባድ አዘቀት በየጊዜው ብቅ ጥልቅ እያልን ወደ ሰፈው ባሕር ከሚመለሱት ማዕበሎች ጋር በሳላም እናዘግማለን።

ከማዕበሎቹ በአንደኛው ጫፍ ላይ ብድግ እንዳልኩ ወደ ኋላ ስመለከት በቻንግ እጅ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ነጯን ጨርቅ አየሁ። ሲልቪያን ከእኔ በጣም ቅርብ ነበር፤ ምናልባት ወደፊት በዐርባ ያርድ ርቀት ላይ ቢሆን ነው። በድል አድራጊነት ደስታ ከንዱን ሲያውለበልብ ለተደጋጋሚ ጊዜ አየዋለሁ።

ሌሊቱ በሰላም አለፈ። ቆየት ብሎ አንድ ኃይለኛ ለውጥ ተሰማን። ማዕበሉ ወደ ኋላ ሲስበን የነበረውን እንቅስቃሴ አዞረና አሁን ወደ ግራንዴቴሬ አቅጣጫ ይገፋን ጀመር።

ፀሐይ ስትወጣ በግምት ዐሥራ ሁለት ሰዓት ነበር። ጠረፉን ለማየት በጣም ራቅ ብለናል። ምንም ማጣራት ስለማይቻል በግምት በሃያ ማይል ርቀናል ብዬ ገምቻለሁ።

ድል ማድረጋችንን አሰብኩና ፈገግ አልኩ።

ጀልባየ ላይ ቁጭ ብል ከጀርባየ ያለው ነፋስ ፈጠን ብየ ለመጓዝ ይረዳኝ ይሆን?

ሰንሰለቴን ፈታሁና በወገቤ ዙሪያ ጠመጠምኩት። ቡሎኑ በሚገባ ግራሶ ጣግቦ ስለነበር ማላላቱ ቀላል ነበር። እጅቼን ለማድረቅ በአየር ላይ ዘረጋኋቸው። አንድ

t.me/OLDBOOKSPDF

ሲጃራ አስፈልጎኛል። አቀጣጠልኩ። በረጅም ሳብኩና ቀስ በቀስ ጢሱን አወጣኩት። ጭንቀቴ ለቀቀኝ። በሆዴ ውስጥ የነበረውን የሞት ሽረት ጭንቀት ለመግለጽ ሥነሞከሩ አስፈላጊ አይሆንም። ቁም ነገሩ ግን ከአንግዲህ ወዲያ አለመሥጋቴ ነበር። ለማንኛውም ሲጃራዮን ከጨረስኩ በኋላ አንድ ጉንጭ የኮክነት ዱቄት ለመቃም ወሰንኩ። አንድ ደህና እፍኝ አንከሁና ከዚያም አንድ ሌላ ሲጃራ አጨስኩ። ሲልቪያን አልም ብሎ ርቆ ነበር። ከአንድ ማዕበል ከፍታ ላይ ሁለታችንም በአንድነት ከፍ ስንል አለፍ ቀረት እያልን በጨረፍታ እንተያያለን። ፀሐይዋ ልክ በራሱ በገሃነም አሳት የመቀት ደረጃ መሐል አናቴን ታንጫርረኝ ስለነበር የራስ ቅሌ ተጠበሰ። ፎጣዬን አራስኩና ጭንቅላቴ ላይ ጠመጠምኩት። ከዚያም ሱፍ ሹራቤን አወለቅኩ። ከነፋሱ ጋር አንኳ ሆኖ ወበቁ ያፍን ነበር።

በክርስቶስ! ጀልባየ ወዲያው ተገለበጠችና ወደ መስመጡ ደረጃ ተቃረብኩ። ሁለት ትላልቅ ጉንጭ የጨው ውሃ ገሰምኩ። የቻልኩትን ያህል ብታገልም፣ ጆንያዎቹን በትከሻ አታንቼ በላያቸው ተመልሼ መንጠላጠል አልቻልኩም። እንቅስቃሴዮን የከለከለኝ ሰንሰለቱ ነበር። በመጨረሻ ከአንድ በኩል እንዲንጠለጠል በማድረግ፣ ልላቀቅ ሞከርኩ፣ ግን ጣቶቼ ብሎኑን ሊፈቱልኝ አልቻሉም። እነርሱን የማላላበትም ኃይል ስለከዳኝ ንዴትም ብስጭትም ሰውነቴን ወረረው።

መጨረሻ ላይ ተሳካልኝ። ያ ወቅት አንድ ቀውጢ ሰዓት ነበር። ከዚያ መናጢ ሰንሰለት መላቀቅ አልቻልኩም ብየ ከአአምሮየ ቁጥጥር ውጭ ልሆን ተቃርቤ ነበር።

ጀልባዋን ለማስተካከል አልተቸገርኩም። ከመጠን በላይ ደክሞኝ ስለነበር ዝም ብዬ ተቀመጥኩባት። ከሰንሰለቱም ይሆን ከምንም ነገር ዳግመኛ ራሴን ፍጹም አላቆራኝም። ጀልባዋን ከእጄ አንጓ ጋር በማቆራኘት ራሴን ያሰርኩት ምን ዐይነት ቂል ብሆን ኖሯል! ይህ ልምድ ትምህርት ሊሆነኝ ይገባል።

ባቶቼንና ከንዶቼን ፀሐይዋ ለበለበችኝ። ፊቴም በእሳት ላይ ተጣደ። ሳረጥበው ደግሞ የባስ መሰለኝ፤ ምክንያቱም ውሃው ከመቅፅበት ተንኖ ሲነሣ እንዲያውም ይበልጥ ያቃጥላል።

ነፋሱም ፀጥ አለና ምኞት ሰጠን፤ ሆኖም በጣም አዘገየን። ከዚህ ዝግታ ይልቅ ነፋሰና ኃይለኛው ሞገድ በተሻሉን። ቀኝ ባቴን በጣም ደነዘዘኝና ጮህኩ። ድንዘዙ እንዴት እንደሚጠፋ ሴት አያቴ ይሉት የነበረውን በማስታወስ፣ በጣቴ መስቀለኛ ምልክት አጋደምኩበት። አልሠራም። አውን ፀሐይዋ በስተምዕራብ ዝቅ እያለች ነበር። በግምት ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት መሆን አለበት፤ ከተነሣን ጀምሮ አራት ማዕበሎች አልፈዋል።

ሲልቪያንና እኔ በየጊዜው እንተያያለን። ሸሚዙን አወልቆ ወደ እኔ ምልክት

t.me/OLDBOOKSPDF

እያሳየ ነበር ። በባሕሩ ፊት ለፊቴ ሦስት መቶ ያርድ ርቀት ላይ። በእጅቹ የሚቀገፍ መስሎ ይታየኛል፣ ምክንያቱም በጀልባው ዙሪያ ትናንሽ የውሃ አረፋዎች አይቻለሁ። ወደ አርሱ መቅረብ እንድችል ጀልባዋን ዝግ ለማድረግ አየሞከረ ይሆን? በሆዴ ተጋደምኩና ከንዶቼን ወደ ውሃው ሥር አስገብቼ ቀዘፍኩ። አርሱ አየገታ እኔ ከቀዘፍኩ፣ ምናልባት በመካከላችን ያለውን ልዩነት ማቀራረብ እንችላለን።

አንድ ጥሩ ጓደኛ መርጫለሁ። ሲሊቪያን መከራን ለመጋፈጥ ያለጥርጥር ቆርጦ ተነሥቷል።

መቅዘፌን አቆምኩ፤ አድካሚ ሥራ ሆነ። ጉልበቴን መቆጠብ አለብኝ። ረኃብና ውሃ ጥም ያዙኝ። ጀልባዋን ለማስተካከል ያለው ጥሩ ዘዴ በማዕበሎቹ ትይዩ ሆኜ መጠባበቅና ከዚያም ከፍ በማለት ሲቃረቡ በአንድ ኃይለኛ አርግጫ በአግሬ ወደፊት መግፋት ነበር። ከአምስት ሙከራዎች በኋላ በመጨረሻው ማድረግ ቻልኩ። ትግሉ አድከሞኝ ስለነበር ጀልባዋ እንደተገለበጠች ተመልሼ ወጣሁ።

ፀሐይዋ ከአድማሱ ላይ በፍጥነት እየጠለቀች ነበር። ዐሥራ ሁለት ሰዓት። ያለማቋረጥ የሚከለበስብኝ ውኃ ኃይሌን እንዳዳከመው በመገንዘቤ ሌሊቱም በጣም እንዳይከብድብኝ ተመኘሁ።

ከሳጉቲኔ አርኮት ውሃ በረጅሙ ጠጣሁና በሁለት እፍኝ የኮከነት ዱቄት አወራረድኩት። በሚገባ ስጠጣ፤ እጅቼን በነፋስ አደረቅኩና አንድ ሲጃራ አውጥቼ በማቀጣጠል በደስታ ተመስጬ አጨስኩ። በሌሊት ጨለማ ከመዋጣችን በፊት ደህና እደር ለመባባል ሲሊቪያን ፎጣውን ሲያውለበልብ አኔም አጸፋውን መለስኩለት። አሁንም በመካከላችን ያለው ርቀት ገና ያው ነበር። እግሮቼን ወደፊት ጧ አድርጌ እንደ ዘረጋሁ ተቀምጫለሁ። ሹራቤን የቻልኩትን ያህል በኃይል ጠመዘዝኩና ለበስኩ። እርጥብም ቢሆን እነዚህ ሹራቦች ሙቀት ይይዛሉ፤ ፀሐይ ስትጠፋ ደግሞ ወዲያው ይቀዘቅዛሉ።

ነፋሱ ተነሣ። በስተምዕራብ በኩል ያሉት ዝቅተኛ ደመናዎች ብቻ ገና ፍም ይመስላሉ እንጂ፣ የትኛውም ቦታ ጨለማ እየሆነና ጨለማውም በየደቂቃው እየባሰበት ሔደ። ነፋሱ ከሚመጣበት በስተምሥራቅ በኩል ደመናዎች ስለሌሉ፣ ለጊዜው የዝናም አደጋ አይኖርም። ዋናው ሃሳቤ ከሚፈለገው በላይ እንዳልበሰብስና በምንም መንገድ ጠንከር ብየ ለመቋቋም ነበር። በአጋጣሚ ድካም ቢያጠቃኝ ራሴን ከጀንያዎቹ ጋር ማሰሩ ጥሩ ሐሳብ መሆኑን ገመትኩ። በቅርቡ ካጋጠመኝ ልምድ አንጻር ደግሞ በጣም ለአደጋ መጋለጥ ይሆን? ለመንቀሳቀስ ችግር የሆነብኝ የሰንሰለቱ በጣም አጭርነት መሆኑን ያኒውኑ ተገነዘብኩ። እንዱ ጫፍ ከሸቦውና ከገመዱ ጋር በመተብተቡ ብዙ ባከኖ ነበር። ወዲያው አፍታታሁና በማርገብ ከቀበቶየ ጋር አቆራኘሁት። ብዙ ግራሶ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለነበረው በሚገባ ሠራ። ዕንቅልፍ ይጥለኝና ጀልባዋን አጣለሁ የሚለው እንባ ፍርሃት አሁን ቀለል አያለ ተሰማኝ።

እዎ፣ ነፋሱ እንደ ጉድ እየጨመረ ሲመጣ ማዕበሎቹም የዚያኑ ያህል ሆኑ። ዕውነተኛው የባሕር ላይ ግልቢያ ሆነ።

ሲልቪያንን ለማየት አልቻልኩም። ነፋሱ ኃይሉን ከቀጠለ ይህ ሌሊት በጣም ጠቃሚ ይሆናል፤ ምክንያቱም አስከዊት ድረስ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እናደርጋለን።

ሌሊቱ እየገፋ ሲሔድ ነፋሱም እያየለ መጣ። የቀይ ቡናማ ጨረቃ ከባሕሩ ሥር ዝግ እያለች ተነሣች። ከበና ግዙፍ ሆና ስትንሳፈፍ፤ በገጿ ላይ ያሉትን መስመሮች በግልጽ መለየት ቻልኩ።

በግምት አራት ሰዓት ይሆን ነበር። ሌሊቱ ወግማ ማለቱን እያደር ሲጨምር የጨረቃዋ ብርሃንም ድምቀት ይበልጥ ከፍተኛ ሆነ። ቀደም ሲል በምታንገበግበው ፀሐይና በጨው ውሃ የነደዱትን ዐይኖቼን፣ ማዕበሎቹ ደግሞ በብርማ ቀለም ስለተነከሩ፣ ያልተለመደ ነጸብራቅ አንጸባባቸው። ይሁንና ከመመልከት መቆጠብ አልችልም። ሞኝነት እንደሆነ ዐውቃለሁ፤ ግን መቋቋሙ ደግሞ አልሆነልኝም። እያከታተልኩ ሦስት ሲጃራዎች አጨስኩ።

ጀልባዋ በሚያብጠው ባሕር ላይ በከፍተኛ ግርማ ብቅ ጥልቅ እያለች እንከን የሌለበት ሥነ ምግባር ታሳያለች።

ግን ስለ አካላዊ ሁኔታዬ ምን ላድርግ? በእንድ በኩል እግሮቼን በጣም ለረጅም ጊዜ እንደዘረጋኋቸው ከቆየሁ መከረኛው ድንዛዜ ይመለሳል። ከዚህም በላይ ያለማቋረጥ እስከ ጭኔ መጋጠሚያ ድረስ በውሃ እየራስኩ ነበር። ግን ነፋስ ሹራቤን ስለሚያደርቀውና ማዕበሉም ከወገቤ በላይ ስለማያልፍ ቢያንስ ከሞላ ጎደል ደረቴ ደረቅ ነበር። ዐይኖቼም ያለማቋረጥ ያቃጥሉኛል ምን ልሁን! ጨፍኛቸው አቆያለሁ። አለፍ አለፍ እያልኩ እተኛለሁ። "እትተኛ!" ማለቱ ቀላል ነው፤ ግን ከቁጥጥር ባሻገር ሆነ። አ ከርስቶስ! ምን ልሁን! ብንን ባልኩ ቁጥር ኃይለኛ ራስ ምታት ይሰማኛል። ከዚያም የሲጃራ መለኮሻዬን አወጣና ከንዴን ወይም አንጉቴን በዝ ራሴ አቃጥላለሁ። ልገላገለው በማልችለው አንድ አስፈሪ ጭንቀት ተወጥሬ ነበር። እንቅልፍ ቢወስደኝ እንዴት ልሆን ነው? ወደ ባሕሩ ብገነበር ቀዝቃዛው ውሃ ያበንነኝ ይሆን? ራሴን እንደገና በሰንሰለቱ ማሰሬ ጥሩ ነገር ነበር። ለሕልውናየ ዋስትና ስለሆኑ አነዚህን ሁለት ጀንያዎች ማጣት የለብኝም። ወደ ባህሩ ስገነበር ካልነቃሁማ የጉድ ያሰኛል!

ከመጠን በላይ ርሺ ነበር። መስመራቸውን የያዙትን ሌሎቹን አሳብሮ እንድ የተደናበረ ማዕበል ልክ በስተኮኔ በኩል ገጨኝ። ማራሰ ብቻ ሳይሆን ገፍትሮ ስለ ወረወረኝ ተከታዮቹ ሁለት ማዕበሎች ከእግር እስከ ራሴ አጠቡኝ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሁለተኛው ሌሊት ሊነጋ ተቃርቦ ነበር። ስንት ሰዓት እንደሚሆን ገርሞኛል። በስተምዕራብ ካለችው ጨረቃ አንጻር ስምንት ወይም ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ መሆን ነበረበት። በውሃ ውስጥ ሠላሳ ሰዓቶች ሆኖን ነበር። በውሃ መራሱ አንድ ጥሩ ነገር ሆኖልኝ ቅዝቃዜው አነቃኝ። ያንቀጠቀጠኛል ግን ዐይኖቼን ገልጬ መቆየት የምችለው ያለ ድካም አልነበረም። እግሮቼ በድን ሊሆኑ ተቃረቡ፤ ስለሆነም ልኮረትማቸው ወሰንኩ። አንዱን በሁለት እጄ ከዚያም ሌላውን ሳብኩ። በመጨረሻም አጠላልፌ ለመኮርተም ቻልኩ። የእግር ጣቶቼ እንደ በረዶ ቀዝቅዘው ስለነበር በዚህ ሁኔታ መቀመጤ ምናልባት ያሞቃቸው ይሆናል።

በዚህ የዐረቦች ዐይነት አቀማመጥ ለረጅም ጊዜ ቆየሁ፤ ለውጡም ጠቀመኝ። በደማቁ ጨረቃ ወለል ባለው ባሕር ላይ አሻግሬ ሲልቪያንን ፈለግኩት ግን ጨረቃዋ በጣም ዝቅ በማለቷ ዐይኖቼን ስለ ወጋችኝ ለማየት ችግር ፈጠረብኝ። ላገኘው አልቻልኩም። ራሱን ከጀንያዎቹ ጋር የሚያቆራኝበት ምንም ነገር አልነበረም። ደህ ዳር ወድቆ ይሆን እንዴ? አሳሰበኝና በደፈናው መመልከቴን ብቻ ቀጠልኩ። ነፋሱ ኃይለኛ ቢሆንም ውሽንፍር የሌለበትና ለስለስ ያለ ነበር። ይህም በጣም ጠቃሚ ሆነ። አሁን ቅኝቱን ስለ ተከታተልኩ የሰውነቴ እንቅስቃሴ ከጀንያዎቹ ጋር አንድ ሆኖ ነበር።

በጨለማው ውስጥ ትኩር ብየ እየተመለከትኩ ጓደኛየን መፈለጌን ቀጠልኩ። ጣቶቼን በነፋስ አደረቅኩና ባለኝ ኃይል አፏጨሁ። ከዚያም ሳዳምጥ መልስ የለም። ሲልቪያን በጣቶቹ ማፏጨት ይችላል? ምንም የማውቀው አልነበረም። ከመነሣታችን በፊት መጠየቅ ይገባኝ ነበር። አፈን በእጆቼ ከበብኩና አ - ሆይይ!" ብየ ተጣራሁ። ብቸኛው መልስ የነፋሱና የማዕበሎቹ ዋካታ ነበር።

ሰንሰለቱን በግራ እጄ እንደ ጨመደድኩ ሚዛኔን አስተካከልኩና እምስት ማዕበሎችን አሳለፍኩ። በአንድ ማዕበል ቁንጮ ላይ ስደርስ ቀጥ እልና እቆማለሁ፤ ወደ ላይ ስወጣ ወይም ስወርድ ቁጢጥ አላለሁ። በስተቀኝ ምንም ነገር የለ፤ በስተግራም ምንም ነገር የለ። ከኋላ ሊሆን ይችላል እንዴ? በምቆምበት ጊዜ ወደ ኋላ ለመዞር አልደፈርኩም። እርግጠኛ የሆንኩበት ነገር ቢኖር በጨረቃዋ አማካይነት በስተግራየ በኩል ያየሁት አንድ ጥቁር መስመር ብቻ ነበር። ጫካ መሆን አለበት።

ሲነጋ ዛፎች ላይ ይሆናል! የእግሮቼን ጣቶች አሻሸሁና እግሮቼን እንደገና ዘረጋኋቸው። ከዚያም ሲጀራ ማጨስ እንድችል እጆቼን አደረቅሁ። ሁለቱን አጨስኩ። ስንት ሰዓት ይሆን? ጨረቃዋ በጣም ዝቅ ብላ ነበር። ባለፈው ሌሊት ጨረቃ በምትገባበትና ፀሐይ በምትወጣበት መካከል ሰዓቱ ስንት እንደነበረ ማስታወስ አልቻልኩም። ዐይኖቼን ጨፈንኩና የመጀመሪያው ሌሊታችንን ትዝታ እንደገና ለማስታወስ ሞከርኩ። ድንገት በስተምሥራቅ በኩል የምትወጣውን ፀሐይ ስመለከት

t.me/OLDBOOKSPDF

በዚያው ወቅት ደግሞ ብር የመሰለች አንዲት ጨረቃ በሰተምዕራብ በኩል ትታይ ነበር። ስለሆነም በግምት ዐሥራ አንድ ሰዓት መሆን አለበት። ጨረቃዋ ግን ለመጥለቅ ጊዜዋ ተቃርቧል። ኮከቦቹ በሙሉ ደብዝዘዋል። የደቡብ መስቀልም ሆነ ትልቁና ትንሹ ድቡቅ ከረጅም ጊዜ በፊት ቀደም ብለው ጠፍተዋል። ሁሉንም በልጣ አሁንም ገና እዘያው ያሉችው ፓላሪስ ብቻ ነበረች። የደቡብ መስቀል ስለሔደላት የሰማዩ ንግሥት አሁን ፓላሪስ ሆናለች።

ነፋሱ በመነሣት ላይ ይመስላል ወይም ቢያንስ ከበድ ያለ ይመስላል ማዕበሎቹም ሃይለኛና ከባድ ሆነው አረፋዎቻቸው ከሌሊቱ ይበልጥ ትላልቅ ነበሩ።

ለጊዜው ነገሮች የከፉ ናቸው ከማለት ይልቅ ቢያንስ የተሻሉ መሆናቸውን ማመን ነበረብኝ። ግን በመቀጠል ላይ ያለው ቀን ዕውነተኛው መከራ ይሆናል።

ትላንት ከጧቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት አስከ ምሽቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ድረስ በፀሐይ ላይ ተሰጥቼ ነበር። ዛሬ ደግሞ ፀሐይዋ መጥታ ማቃጠል ስትጀምረኝ እንዲህ በቀልድ የሚታይ ጉዳይ አልሆነም። ከንፈሮቼ ተቃጠሉ፣ ዐይኖቼ፣ ከንዶቼና እጆቼም እንደዚያው ሆኑ። ከንዶቼን ላለማጋለጥም ሹራቤን መልበስ ግድ ሆነብኝ። ከዚህም በላይ ከጆንያዎቹ ጋር በመፈጋፈጌ መቀመጫየ ተገሸልጦ ነበር።

ተቃጠልኩም አልተቃጠልኩም በማምለጥ ላይ ስለሆንኩ ለጥቃቅን ችግሮች ዋጋ አልሰጠኋቸውም። በሕይወት ወደ ግራንዴቴሬ ለመድረስ ያለኝ ዓላማ ከመጉ ዘጠናው ስለ ተገባደደልኝ ይህ ራሱ አንድ ነገር ነው። አይደለም እንዴ? በግልጽ ቆዳዬ ተገፍፎ ግማሽ አካላቴ የተቀቀለ ሥጋ መስሎ ብደርስ እንኳ የከፈልኩትን መስዋዕትነት እንደ ዋጋ አልቆጥረውም። ከዚህም ሌላ አንድ ዓሣነባሪ አላየሁም። ሁሉም ዕረፍት ላይ ይሆኑ እንዴ? በአሁኑ ጊዜ በዕውነት ዕድል ከአንተ ጋር ነች፤ ግን አንተ አላመንክባትም፤ የተለየህ ጉደኛ ሰው ነህ አልኩኝ በልቤ። በአሁኑ ወቅትስ ሊሠራ ነው። ሌሎቹ በሙሉ በጥንቃቄ የታሰበባቸውና በከፍተኛ ዝግጅት የታቀዱ ሆነው የከሸፉ፡ ይህኛው ሊሳካ ነው እንዴ? ሁለት ጆንያ ኮከነቶች ነፋስና ባሕሩ ወደ ግራንዴቴሬ ሊወስዱኝ ማለት ነው! ማንኛውም በባሕር የተጣለ ነገር ስበርባሪ መጨረሻ ላይ ጠረፍ ዳር መተፋቱን ለማወቅ የቅዱስ ሲር ዩኒቨርስቲ ምሩቅ መሆንን አይጠይቅም።

ነፋሱና ማዕበሎቹ ቀኑን ሙሉ በዚህ ሁኔታ ከቀጠሉ እርግጠኛ ነኝ ከስዓት በኋላ ከሞላ ጎደል ወደ የብስ መድረስ እችላለሁ።

የምድር ወገብ ፀሐይ በስተጀርባዬ ነበረች። ዛሬ ማንኛውንም ነገር ከሸለል ሊታደርገው የቆረጠች ትመስላለች። ራሷን አለቃና ማንም የማይቋቋማት የምድር ወገብ ንግሥት ነኝ ብላ በማወጇ ጨረቃዋ ጊዜ ሳትፈጅ ነጉዳለች። ነፋሱም ጊዜ ሳያባክን ከፋገቷነት ወደ ሞታትነት አየተለወጠ ነበር። በአንድ ሌላ ሰዓት ውስጥ ደግሞ

t.me/OLDBOOKSPDF

ይፋጃል። በመሳው አካላቴ ውስጥ አንድ ግሩም የሆነ የሚያጽኃኑ ስሜት ተሰራጨብኝ። የመጀመሪያው የፀሐይ ጨረር ቆዳዮን ከመንካቱ ነበር አንድ ለሰስ ያለ መቀት ከወገቤ አንሥቶ እስከ መሐል አናቴ ድረስ የወረረኝ። በሚንቅላቴ ላይ የጠመጠምኩትን ፎጣ አነሣሁና ጉንጮቼን በፀሐይ አንቃቃሁ። ፀሐይዋ ሕይወት መሆኗንም እንዳውቅላት እያሳመነቸኝ ነበር። በፍጥነትም ሞት ትሆናለች።

ደሜ በደም ሥሮቼ ውስጥ ሲዘዋወር፤ የቆሰለው ጀርባየ አንኳ ሳይቀር በታደሰው የደም ዝውውር ሕይወት መዝራት ጀመረ።

ጫካውን በግልጽ በማየት የዛፎቹን ቁንጮዎች ልለይ ቻልኩ። ቅርብ ይመስላሉ። ሲልቪያንን ለመፈለግ ጅንያየ ላይ ቆሜ ፀሐይዋ ትንሽ ከፍ እስከትል ጠበቅሁ።

አንድ ሰዓት ሳይሞላ ፀሐይዋ ከፍ አለች። መፋጀታን መጀመሯ ነበር! የግራ ዐይኔ ከሞላ ጎደል ተደፍኗል። ትንሽ ውሃ አስነከቼ ሳረጥበው ቆጠቆጠኝ። ሹራቤን አወለቅኩ። ፀሐይዋ በጣም ከመፋጀቷ በፊት ደረቴን ለትንሽ ጊዜ አራቶትሁ።

አንድ ያልተለመደ ኃይለኛ ማዕበል ወደላይ እጓነኝ። በሴኮንድ ቅንጣት ጊዜ ውስጥ ሲልቪያን ውልብ ሲል ታየኝ። በጀልባዋ ላይ ደረቱን እንደ ገለጠ ተቀምጦ ነበር። እርሱ አላየኝም። በስተግራየ ትንሽ ቀደም ብሎ ከሁለት ሙዮ ያርድ በማይበልጥ ርቀት ላይ ነበር። ነፋሱ አሁንም ኃይለኛ ስለነበር ሹራቤን አውልቄ እጅጌውን ብቻ ከንዶቼ ውስጥ በማጥለቅና ከሥሩ በኩል በአፌ በመያዝ ልክ እንደ ነፋስ ሸራ በአየር ላይ ዘርግቼ ወደ እርሱ ለመቅረብ ልሞክር ወሰንኩ።

በዚህ ሀኔታ ጥርሶቼን ማመም እስኪጀምረኝ ድረስ አንድ ሰዓት ሙሉ ቆየሁና ነፋሱን እቋቋማለሁ ብለ ደከመኝ። ግን በመካከላችን ያለውን ርቀት ያጠበብኩ መስሎኛል።

ሃሌ ሉያ! አንድ መቶ ያርድ በማይሞላ ርቀት ዳግመኛ አየሁት። የት እንዳለሁ ለማወቅም የተጨነቀ አይመስልም። አንድ ሌላ ማዕበል መጥቶ ሲያጉነኝ አንድ ሁለት ሦስት ጊዜ አየሁት። አካባቢውን የሚቃኝ መስሎ እጁን ከዐይኖቹ በላይ እንዳስቀመጠ ጥርት አድርጌ አየሁት። ወደ እኔ አቅጣጫ ይመለከታል። ግን ምንም ነገር የሚያይ አይመስልም።

ቆምኩና አቃጨሁ። ጀልባዋ ማዕበሉ ላይ እንደ ወጣች ሲልቪያንን በእኔ ትይዩ ቆሞ አየሁት። ሹራቡን ወደ አየር አነሣ። ተመልሰን ከመቀመጣችን በፊት ቢያንስ ለሃያ ጊዜ እያውለበለብን ሰላምታ ተለዋወጥን። በየወቅቱ አንድ ማዕበል ባነሣን ቁጥር ሰላምታ እንለዋወጣለን። በአጋጣሚ የምንወጣውና የምንወርደውም በተመሳሳይ ቅኝት ነበር። በመጨረሻዎቹ ሁለት ማዕበሎች ላይ አሁን በጣም ግልጽ ወደሆነው ጫካ

t.me/OLDBOOKSPDF

አቅጣጫ ከንዱን ዘረጋ። ከስድስት ወይም ሰባት ማይል መራቅ አይችልም። ሚዛኔን ሳትክና በቂጤ ጀልባዋ ላይ ተዘረፈጥኩ። ጓደኛየና ጫካው እንደዚህ ቀርበውኝ በማየቴ ደስታ ውጦኝ ስለነበር ልከ እንደ ሕፃን ልጅ አለቀስኩ። በመግል በተሞሉት ዐይኖቼ ውስጥ ያሉት የአንባ እንክብሎች በሺ የሚቆጠሩ ፊርጦች ሆኑ። ፓፒ፤ ዛሬ አግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው! አግዚአብሔርን ያገኘኸውና በጣቶችህ የዳሰስከው፤ ምናልባትም እዚህ ነው። ያለ ፀሐይ ጮራ በአሸቀያሚው ጨለማ ግንብ ውስጥ በቱሜ ተቀብሬ ባሳለፍኳቸው በሺህ የሚቆጠሩት ሰዓቶች አርሱን አስታውስ ነበር፤ ዛሬ ደግሞ ምንም ዓይነት ኃይል በማይበግራት፤ ማንኛውንም ነገር በምትከሽልለው ፀሐይ ዳሰስኩት። አግዚአብሔርን ዳሰስኩት፤ ዙሪያየን ተሰማኝ፣ በውስጤም ሠረፀብኝ። "ተስቃየህ፤ ይበልጥም ልትሠቃይ ነው፤ ግን በአሁኑ ርቀት ከጎንህ ነኝ። ነጻ ትወጣለህ። ቃል አገባልሃለሁ ትወጣለህ" ብሎ በጆሮየ ሳይቀር ሹክ ብሎኛል።

ምንም ዓይነት ሃይማኖታዊ መመሪያ ፈጽሞ አልነበረኝም። የክርስትናን ሃይማኖት ምኑንም አላውቅም፤ ያም ሆኖ እነርሱ ከልብ በምፈልግበት ወቅት በነፋሱ፣ በባሕሩ፣ በፀሐይዋ፣ በጫካው፣ በኮከቦቹ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሰውን ልጅ ለመመገብ ሲል ራሱ በፈጠራቸው ዓሣዎች አምሳያ ሳይቀር አግዚአብሔርን ከማግኘቴ አላገደኝም። ፀሐይዋ ፈጠን ብላ ወጥታለች። አራት ሰዓት መሆን አለበት። ከወገቤ በላይ ከውኃ ብየ ስለ ደረቅኩ ፎጣየን አራስኩና በጭንቅላቴ ዙሪያ አጣጥፌ ጠመጠምኩ። ከዚያም የሚቃጠለውን ጀርባየንና ከንዶቼን ለመከላከል ሹራቤን ለበስኩ። እግሮቼ ያለማቋረጥ በውሃ ቢዘፈቁም፤ እነርሱም በሚገባ ቀልተው ነበር።

የጠረፉ ዳር ቅርብ በመሆኑ ምክንያት አውን ማዕበሎቹ በረጅምና በቀጥታ መስመሮች ወደ አዚያው አቅጣጫ እየተሽቀዳደሙ ነበር። ጫካውን በሚገባ መለየት ስለቻልኩ ርቀቱን እንዴት ፈጥነን እንዳጣበብነው ተገነዘብኩት። ርቀት እንዴት እንደሚገመት በመጀመሪያው ማምለጫ ወቅት ዐውቄ ነበር። የአንድ አይታ ገመገም ብቅ ካለ፤ ከሦስት ማይል በማይበልጥ ርቀት ላይ ነህ ማለት ነው። በአብዛኞቹ ዛፎች መካከል ያለውን የውፍረት መጠን ለማወቅ ችያለሁ ከዚያም በላይ በተለይ በአንድ የማዕበል ቁንጮ ላይ እንደ ወጣሁ፤ አንድ የወደቀ ግዙፍ ዛፍ ቅርንጫፎቹ በባሕሩ ሲታጠቡ ለመለየት ቻልኩ።

በድንገት ዶልፊኖችና አሞራዎች ብቅ አሉ። ብቻ ዶልፊኖቹ ከጀልባዋ ጋር እንጫወታለን ባላሉ! ባሕር ያመጣውን እንጨትና ሰው የመግፋት ልማድ አላቸው ሲባል እሰማለሁ። እናም ሰዎቹ ከራሳቸው መርበትበት የተነሣ ብዙውን ጊዜ ይሰምጣሉ። ሦስት ወይም አራት የሚሆኑት መጡና ትንሽ ጊዜ ዙሪያየን ከተሽከረከሩ በኋላ ጀልባየን እንኳ ሳይታከኳት ጥለው ሔዱ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፀሐይዋ በቀጥታ ከራስ በላይ ስለነበረች ቀትር ሆኗል። ያለማወላወል በጨው ውሃ ልትቀቅለኝ ቆርጣለች። ዐይኖቼ መግል ያጎርፉ፤ ከአፍንጫየና ከከንፈሬም ቆዳዬ ተገልፍፎ ሐዲል። አሁን ማዕበሎች አጫጭር ሆነው በሚያደነቁር ጩኸት ያስገመግማሉ።

ሲልቪያንን በተደጋጋሚ ለማየት ቻልኩ። አንዳንድ ጊዜ እያረፈ ወደ እኔ ይዞርና ከንዱን ያነሣል። ፎጣውን በራሱ ላይ ጠምጥሞ ከወገቡ በላይ ራቁቱን ነበር።

ከዚያም ማዕበሎቹ ወደ ከባድ ደረጃ ተቀየሩ። በሚያስፈራ ጉርምርምታ የሚመቱት አንድ የአሸዋ ከልል አለ፤ ከዚያም ያን ካለፉ በኋላ ኮረፋታቸውን እያፈነዱ ወደ ጫካው ውስጥ ያመራሉ። ባሕሩ በሚያስጠላ ዝቃጭ የተሸፈነ ነበር።

በውሃው ውስጥ የሚንበጫረቁትን በሺ የሚቆጠሩ አሞራዎች ጫጫታ የማዕበሉ ዋካታ እንኳ መዋጥ አልቻለም። ሁለት ወይም ሦስት ያርድ ሲቀረኝ ወደመሬት ዘልዬ ወረድኩ። ግን መልመድ አቃተኝ። በአሸዋ ማጥ ውስጥ መዋጤ ነበር። ወደፊት የሚወስደኝ በቂ ውሃ የለም። በፀሐይዋ አቅጣጫ ከቀኑ ስምንት ሰዓት ገደማ ይመስላል፤ወይም ጉዞ ከጀመርኩ አርባ ሰአቶች ሆነዋል። ማዕበሉ ሦስት ሠዓት ገደማ ቢመለስ ሲመሽ ወደ ጫካው ውስጥ እገባለሁ። ማዕበሎቹ በላየ ላይ ሲንከባለሉብኝ ከጀልባየ ላይ ጠራርገው እንዳይወስዱኝ ለመከላከል ሰንሰለቱን እንዳቆራኘሁ መቆየት አለብኝ። ለመንሳፈፍ የሚያስችል በቂ የውሃ ማፊት ለማግኘት የሁለት ወይም የሦስት ሰዓት ቆይታ ይፈልጋል።

ሲልቪያን በስተቀኝ በኩል በግምት አንድ መቶ ያርድ ራቅ ብሎ ወደ እኔ አቅጣጫ እንቅስቃሴ ያደርግ ነበር። አንድ ነገር ሊነግረኝ የፈለገ ይመስላል፤ ግን ድምፁ ሊሰማለት አልቻለም። በስተጀርባችን ካሉት ማዕበሎች ጋር የሚሰማው ብቸኛ ጩኸት የአሞራዎች ጫጫታ ነበር። እኔ ከጫካው አምስት መቶ ያርድ ላይ ስሆን ሲልቪያን ደግሞ አሁንም ከእኔ ፊት በአንድ መቶ ያርድ ላይ ይገኛል። ከጅንያው ተለይቶ ቀጥ ብሎ ቆሞ ነበር። አስምሮውን ጣተ እንዴ? መራመድ ከጀመረ ወደ ጀልባው መመለስ አስከማይችልበት ደረጃ በእያንዳንዱ እርምጃ ቀስ በቀስ ይሰምጣል። ለማቋጨት ሞከርኩ ግን አልሆነልኝም። እርኮት ውስጥ የቀረች ትንሽ ውሃ ስለነበረች ያችን ጠጣሁና እንዲቆም ለመጥራት ታገልኩ። ድምፅ ሊወጣልኝ አልቻለም። ከአሸዋው ማጥ ውስጥ ደጋግ ኮረፋት እየተፍለቀለቀ ይወጣ ስለነበር ጥልቅ መሆኑና ከሥር በኩል ጭቃ እንዳለው የታወቀ ነበር። እዚህ ውስጥ የተዘፈቀው ምስኪኑ ዕድለቢስ የተፈጠረው ለዚሁ ሲዳረግ ነበር እንዴ።

ልረዳው ያልቻልኩት ሲልቪያን አንድ ምልክት እያሳየኝ ወደ እኔ አቅጣጫ ይዞራል። "እይሆንም፤ ጀልባህን እንዳትተው፤ ፈጽሞ ወደ ጫካው አትደርስም" ብዬ

t.me/OLDBOOKSPDF

ልነግረው ለመሞከር እጆቼን አርገበገብኩ። በጀልባውና በእኔ መካከል ሰለሆነ ከጀልባው ምን ያህል እንደ ተራራቀ ለመገመት አልቻልኩም። በጣም ቅርብ ስለሚሆን መሰመጥ ሊጀምር ጭምድድ አድርጎ ሊይዝ ይችላል ብየ መጀመሪያ ፈሞቼ ነበር።

ብዙ ርቀ ስለሔደ በመዋጥ ላይ መሆኑንና ራሱን ማላቀቅ እሊመቻሉን ተገነዘብኩ። አንድ የኡኡታ ድምፅ እኔ ዘንድ ደረሰ። ጆንያየ ላይ ሊጥ ሥበየ በመጋደም እጆቼን ወደ ማጡ ከትቼ ባለኝ ኃይል ተሳብኩ። ጀልባዋ መንቀሳቀስ ጀመረችና ሐያ ያርድ ያህል ወደፊት ተንሷቀቅኩ። አሁን ባለሁበት ቦታ እንደቆምኩ ጓደኛየ ሲልቪያን ከጀልባው ቢያንስ በሐያ ያርድ ርቀት ላይ እስከ ወገቡ ድረስ ተቊበሮ ላየው ቻልኩ። ድንጋጤ ድምፄን መለሰልኝና "ሲልቪያን! ሲልቪያን! እንዳትንቀሳቀስ! በአሸዋማው ማጥ ላይ ለጥ ብለህ ተጋደም፤ ባቶችህን ለማላቀቅ ሞክር!" ብየ ጮህኩ። ሰማና የተስማማበት መሆኑን ለመግለጽ ራሱን ነቀነቀ። እንደገና በሆዴ ተጋደምኩና አሸዋውን መቧጠጥ ያዝኩ። አልሀ የደመ ነፍስ ኃይል ሰጠኝና ሌላ ሠላሳ ያርድ ተንቀሳቀስኩ። ይህ ሁሉ አንድ ሰዓት ያህል መውሰድ አለበት፣ ሆኖም ወደ እርሱ በጣም እየተቃረብኩ ነው፤ ምናልባት ሃምሳ ወይም ሰድሳ ያርድ ብርቅ ነበር። እርሱን ለማየት ችግር ሆነብኝ፤ ምክንያቱም እጆቼ ከንዶቼና ፊቴ በጭቃ ተሸፍነው ነበር። አብሳለሁ ብየ ስሞክር ጨዋማው ከርፋታም ጭቃ የግራ ዐይኔን ቆጠቆጠኝና ከማየት ጋረደኝ፤ ዐይኔም ያለቅስ ጀመር። በመጨረሻ ላየው ቻልኩ። አልተጋደመም፤ አሁንም ከአሸዋው ማጥ ውስጥ ግማሽ አካላቱ ብቻ እየታየ ቀጥ ብሎ ቆሟል።

የመጀመሪያው ማዕበል ጀልባየን ልክ ከነበረችበት ቦታ እንዳለች ትቶ በላየ ላይ አለፈና የአሸዋ ማጡንና ኮረፋቱን በማልበስ ከፊት ለፊቴ አዘቀጠ። በሲልቪያን ላይ ሲያልፍ ደግሞ አሁን ደረቱ ብቻ በአሸዋው ማጥ ትከከል ሆነ። ማዕበሎቹ በተንከባለሉ ቁጥር አሸዋው እየለሰለሰ መሐዱን ተገነዘብኩ። ወደ እርሱ መድረስ አለብኝ።

ልጄን ከአደጋ ለማትረፍ እንደምትፍጨረጨር እናት፤ ባለኝ በሌለኝ ኃይል ወደ ሲልቪያን ለመድረስ አሸዋውን እየደጋገምኩ ቧጠጥኩ፣ቧጠጥኩ ምንም ሳይነቃነቅ ፣ምንም ሳይናገር ዐይኖቹ ፍጥጥ ብለው ከኔ ዐይኖች ጋር ግጥምጥም እንዳሉ ወደ እኔ ይመለከታል። እጆቼ ወዴት ቦታ እንደሚንቀሳቀሱ ሳልመለከት ትንሽ ወደፊት እንደ ተንሷቀቅኩ፤ ሁለት ማዕበሎች በላየ ላይ ተንከባልለው ሲያልፍ አሸዋው በጣም ለስላሳ ከመሆኑ የተነሣ እንቅስቃሴየን ለመቀጠል አስቸጋሪ አልሆነብኝም። ትንፋሼን በመዋጥ ከጀልባዋ አፈናጥሮ ሊወስደኝ ምንም ያልቀረው አንድ ግዙፍ ማዕበል ሲመታኝ ተነሣሁና ቁጭ አልኩ። ማጡ ወደ ብብቱ ደርሶ ነበር። አሁን ከዐርባ ያርድ በማይበልጥ ርቀት ላይ ሆንኩ። ሲልቪያንም ትኩር ብሎ እየተመለከተኝ ነበር። ልናርፍበት ተስፋ ካደረግንበት መሬት በሦስት መቶ ያርድ ርቀት እዚህ የጣማ ገዘፍ ውስጥ መሞቱን

t.me/OLDBOOKSPDF

እንደተገነዘበ ተረዳሁ።።

እንደገና ተጋደምኩና አሁን ፍጹም ወደ ፈላሽነት የተለወጠውን አሸዋ ወደ ኋላ መቧጠጥ ያዝኩ።። ዐይኖቻችን አንዱ ከሌላው ላይ እንደ ተተከሉ ቀርተዋል።። "አይሆንም፤ ተስፋ ቁረጥ፤ ማድረግ አትችልም" ለማለት አንድ ምልክት አሳየኝ።። ግን ለመድረስ ሠላሳ ያርድ ያህል እስኪቀረኝ ድረስ እንደቀጠልኩ፤ አንድ ከባድ ማዕበል ከተከመረ ውሃ ጋር አለበሰኝና ተጨማሪ አምስት ወይም ስድስት ያርድ ወደፊት ተንሳፈፍኩ።።

ማዕበሎቹ እንዳለፉ ቀና አልኩና ተመለከትኩ።። ሲልቪያን ሔዷል።። የአሸዋ ግጡ ስስ በሆነ ኮረፋታማ ውሃ ተሸፍኖ ነበር።። ለመሰነባበቻ ያህል አንድ እጁ እንኳ አልተነሳም ነበር።። ወዲያውኑ የሆነ የአውሬነት ስሜት ያዘኝ።። ገና በሕይወት አለሁ ትል ይሆናል።። ግን ብቻህን ያለ አንድ ጓደኛ ስትቀር መከራ ላይ መውደቅህ ነው አልኩት ራሴን በራሴ።።

አንድ ማዕበል እየተንከባለለ በጀርባየ ላይ ሲያልፍ፤ እኔነቴን ወደማወቅ ተመለስኩ።። ማዕበሉ በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ ለብዙ ደቂቃዎች ትንፋሼን መመለስ አልቻልኩም ነበር።። ሌላ መጠነኛ ያርድ ጀልባዋ ወደፊት ሸርተት ስትልና ከዚያም ማዕበሉ ወደ ጫካው ሥር ሔዶ መብረዱን ካየሁ በኋላ ብቻ ነበር ለጓደኛየ ያለቀስኩለት።። በጣም ተቀራርበን ነበር።። ምን ነው ባልሞተ ኖሮ! ከሦስት መቶ ያርድ ለማይበልጥ ርቀት! ወደ ጠረፉ መራመድ ትችላለህ ብሎ የገፋህ ምን ነበር? ይህን ገሃነም አሳት ለመሻገር ፈጽሞ ኃይል አጣህ? አንተን መሣይ ወንድ ያቀፉትን የጥቂት ሰዓቶች መከራ እንዴት መቋቋም አቃተው?

ማዕበሎቹ በነጎድጓዳዊ ጉርምርምታ መንከባለላቸውን ቀጠሉ።። እያደጉና እየተቀራረቡ ይመጡ ጀመር።። ከላይ አስከታች በውሃ እዘፈቃለሁ ያም ሆኖ በየወቅቱ ትንሽ ያርድ ወደፊት ሸርተት እላለሁ።። ካለፉ በኋላ ደግሞ ወርጄ እወዘፋለሁ፤ ግን አንድ ቅርንጫፍ ወይም ሐረግ በእጄ እስከይዝ ከጀልባየ ንቅንቅ ላለማለት ቆርጬ ነበር።። ለመጨረስ ሐያ ያርድ ይቀረኛል።። የመጨረሻው ማዕበል ወደ ዛፎቹ ውስጥ ከሚያደርሰኝ በፊት ሌላ አንድ ሰዓት እንደሚፈጅ ነበር።። ፈታሁና ከሰንሰለቱ ራሴን አላቀቅኩ።። ግን እንደ ያዝኩት ነበር።። እንደገና ሊያስፈልገኝ ይችል ይሆናል።።

በጫካ ውስጥ

ዙሪያውን በአሸዋ ግጥ የተከበበ ስለሆነ በከፊል አርምጃና ከፊል ዋና ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት በጥድፊያ ወደ ጫካው ውስጥ ተሳብኩ።። ውሃው ከመጠን በላይ ወደ ጫካው ውስጥ ስለሰረገ ሲመሽ እንኳ ከደረቅ መሬት ገና ሩቅ ነበርኩ።። የበሰበሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

ዝቃጭ ሽታው አፍንጫየን ሲተነፍየኝ፤ ጋዙም በጣም ኃይለኛ ከመሆኑ የተነሣ ዐይኖቼን ለበለበኝ። እግሮቼ በሣርና በቅጠሎች ተሸፍነው ነበር። አንድ እርምጃ በተራመድኩ ቁጥር ከውሃው በታች ያለውን መሬት በቅድሚያ አፈትሻለሁ። የሚቋቋመኝ ነገር ሳገኝ ብቻ ወደፊት እንቀሳቀሳለሁ።

የመጀመሪያውን ሌሊት ያሳለፍኩት በአንድ የወደቀ ዛፍ ግንድ ላይ ነበር። ጅንያየን ከአንድ ቅርንጫፍ ላይ ከፍ አድርጌ ሰቀልኩና ጥብቅ አድርጌ ቋጠርኩት። ሕልውናየ ያች ጅንያ ነበረች፤ በእርሷ ውስጥ የተቋጠሩት ኮከነቶች ከሌሉ ፈጽሞ መኖር አልችልም። ገጀራየን በቀኝ እጄ እንጓ ላይ አሰርኩ። ከዚያም ሰውነቴ ተቃጥሎና ቆስሎ ዛል ብየ ደከሜ ስለነበር፤ ያላንዳች ሐሳብ ከነበጠው ግንድ ላይ ጧ ብየ ተጋደምኩ። ምናልባት አንድ ሁለት ጊዜ፤ "ምስኪን ሲልቪያን!" በማለት አጎመትምቼ ይሆናል፤ ግን እርግጠኛ መሆኔንም እንጃ!

የእሞራዎቹ ጩኸት ከእንቅልፌ አባነነኝ። ፀሐይዋ ሜካውን ሰንጥቃ ከገባችበት አቅጣጫ እንደ ገመትኩት ከጧቱ አንድ ወይም ሁለት ሰዓት መሆን አለበት። በየቦታው ውሃ ሞላ፤ የባሕሩ እንቅስቃሴ መነሣቱ ነበር። ዲያብሎስን ከለቀቅኩ ምናልባት በግምት ስድሳ ሰዓቶች ይሆናሉ። ከባሕሩ ምን ያህል እንደምርቅ ለማወቅ አልቻልኩም። ለማንኛውም ውሃው ዝቅ እስከሚል ድረስ መጠበቅ ነበረብኝ። የመጠጥ ውሃ ጨርሻለሁ። የመጨረሻዎቹን ሦስት እፍኝ የኮከነት ዱቄት በላሁና በቁስሎቼ ላይ ትንሽ ርጋፊዎች ነሰነስኩ። በዱቄቱ ውስጥ ያለው ቅባት ያበርዳል። ከዚያም ሁለት ሲጃራዎች አጨስኩና ስለ ሲልቪያን አሰብኩ፤ ልቤ በሐዘን ተሞላ። ሃዘኔን የሚቀንስልኝ ይመስል ዐይኖቼን ለመጨፈን ታገልኩ። ግን የእርሱ ነገር አከትሞለታል።

ጅንያየ ከተንጠለጠለችበት ቦታ በሰላም አድራልኝ ስለነበር፤ ኮከነቱን ዘረገፍኩ። እግሮቼን ወደፊት እንፈራጥጬ ተቀመጥኩና ቅርፊቱን እስከ መጨረሻው ለመፈረካከስ እስከ ቻልኩ ድረስ ባለኝ ኃይል ከዛፉ ጋር እከሰከሰው ጀመር። በገጀራም መቁረጥ ትችላለህ፤ ግን ደጋግሞ ከአንድ ነገር ጋር ማጋጨቱ ይሻላል። አንድ ሙሉ ኮከነት በላሁና በውስጡ ያለውን ጣፋጭ ፋሳሽ ጠጣሁ። አሁን ባሕሩ ወደ ኋላ እያፈገፈገ ስለሆነ ወደ ደረቅ መሬት ለመዝለቅ በጭቃው ላይ መራመድ እችላለሁ።

ቀትር ሆነ። ባሕሩ እንደዚህ በጣም ውብ ሲሆን ፈጽሞ አይቸው አላውቅም። ሲልቪያን ሰምጦባታል ብየ ከገመትኳት ኑጥብ ላይ ለረሻም ጊዜ ትኩር ብየ ተመለከትኩ። በጨው ውሃ ታጠብኩና፤ ልብሶቼንም እንጨፈጨፍኩ። ወዲያው ፀሐይዋ ከሸለለ አደረጉችልኝ። ከአንድ ሲጃራ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ የጓደኛዬን መቃብር ተመለከትኩና ወደ ጫካው ጉዞ ጀመርኩ። ለእርምጃ በጣም ቀላል ሆነ። ጅንያየን በትከሻየ ላይ አንግቢ ከሁለት ሰዓት በኋላ ወደ መጨረሻው ደረቅ መሬት እስከደረስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ድረስ ጥቅጥቅ ባለው ጫካ ውስጥ ዝግ እያልኩ ተጓዝኩ። በዛፎቹ ግንዶች ላይ የማዕበል አሻራ አይታይም። እዚህ ሃያ አራት ሰዓት ለማረፍ ወሰንኩ። ኮከነቶችን አንድ በአንድ በመፈርከስ ፍሬዎቹን አወጣና ከረጢቴ ውስጥ ከትቼ በሚርበኝ በማንኛውም ወቅት ለመብላት አዘጋጀሁ። እሳት ለማንደድ እችል ነበር። ግን አልፈለግሁም።

ቀሪውን ቀንና ሌሊቱም ጭምር ምንም አዲስ ትዕይንት አልነበራቸውም። ከፀሐይዋ መውጣት ጋር አዕዋፍ ከእንቅልፌ ቀሰቀሱኝ። የኮከነት ዱቄቴን ለይቼ ጨረስኩና በጣም የቀለለች ጆንያየን ትከሻየ ላይ እንዳነጥበኩ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አመራሁ።

ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ገደማ ወደ አንዲት የአግር መንገድ ደረስኩ። የመጫ ዛፍ ወይም ግንድ ለሚፈልጉ አለበለዚያም ወርቅ ለሚያስሱ ጓዝ ማመላለሻ መሆን አለባት። ጠባብ ብትሆንም በጣም ለስላሳ ስለነበረች የዘውትር መጠቀሚያ መሆኗ ግልጽ ነበር። በደረቀው ጭቃ ላይ ግልጽ ሆኖ የሚታይ የሰው ወይም የእህያና የበቅሎ ኮቴ በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ ያጋጥመኝ ነበር። እስኪመሽ ድረስ ተጓዝኩ። ለረሃቤም ሆነ ለውሃ ጥሙ ማስታገሻ የሚሆነኝ ትንሽ ኮከነት አልፎ አልፎ እኝከና ከዚያም ቅባትና ምራቅ በመቀላቀል አፍንጫየን፣ ከንፈሮቼንና ጉንጮቼን አለቀልቃለሁ። በመግል የተሞሉት ዐይኖቼ ዘወትር እንደ ተጣበቁ ናቸው። እጋጣሚ ባገኘሁ ጊዜ በንጹሕ ውሃ አርሳቸው ነበር። ጆንያየ ውስጥ ከያዝኳቸው ኮከነቶች ጋር አንድ ቁራጭ የማርሴይ ሳሙና፣ አንድ የጀሌት ጺም መላጫ፣ ዐሥራ ሁለት ምላጮችና አንድ የጺም ብሩሽ ውሃ በማያረጥባት አንዲት ከረጢት ውስጥ ነበሩኝ።

የአግር መንገዱ ገላጣ ስለሆነች ባያስፈልገኝም የምራመደው ገጀራየን ከእጄ ሳልነጥል ነበር። ከሳንና ጎኔ በቅርቡ የተቆረጡ የሚመስሉ ቅርንጫፎች አያለሁ። በዚህች የአግር መንገድ ላይ ብዙ አንቅስቃሴ መኖር አለበት። ብጠነቀቅ ይሻለኛል።

ከቅዱስ ላውረን ዱ-ማሮኒ በመጀመሪያ ላመልጥ ዐውቀው ከነበረው ጫካ ልዩነት ነከረው። እንደዚህኛው ጥቅጥቅ ያለ አልነበረም። ይህኛው ከስድሳ ጫማ በላይ ከፍታ ያለው ጥቅጥቅ ያለ አረንጓዴ አጎበር አለው። የቀን ብርሃን የሚገባው ከአግር መንገዱ በስተቀኝ በኩል ሲሆን የግራው ግን ሙሉ በሙሉ ጨለማ ነበር።

የምራመደው በቸኮላ ሲሆን ገላጣ ቦታ አልፎ አልፎ አደርሳለሁ። የፀሐይዋ ጨረር ማጋደል ሊመሽ መቃረቡን ያመለክታል። ጀርባየን ለፀሐይዋ አዞርኩና ወደ ጥቁሮቹ መንደር ኩሩም ሆነ በዚያው ስም የሚጠራው ጠባይ ማረሚያ ወደሚገኝበት ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ አመራሁ።

ምሽት ላይም የምተኛበት ቦታ ፍለጋ ገባሁ። ከመንገዱ ሠላሳ ያርድ ሳይርቅ የመገዛ ኮባ በሚመስሉ ለስላሳ ቅጠሎች ጥቅጥቅ ብሎ የተከለለ ቦታ አገኘሁ። ቆራርጬ

t.me/OLDBOOKSPDF

አልጋ ቢጤ አዘጋጀሁ። ያለጥርጥር ከርጥበት እምልጫለሁ ዝናም እንደማይጥል አስተማማኝ ነው። ሁለት ሲጃራዎች አጨስኩ።

ዛሬ ማታ ብዙም አልደከመኝ፤ የኮከነት ዱቄቱም ረሃቤን አስታግሶልኛል። አፈ ብቻ በጣም ከው ብሏል - ምራቅ አልነበረኝም።

የማምሰጡ ሁለተኛ ከፍል በመካሄድ ላይ ይገኛል። ያለ አንድ መጥፎ አጋጣሚ ሦስተኛውን ሴሊት በግራንዴቴሬ ላይ ጀምሬያለሁ። ሲልቪያን ምነው አብሮኝ በሆነ ኖር! ከእንግዲህ እርሱ የለም ስለሁኔታው ማድረግ የምችለውም የለ። ሞኝ አትሁን ፓፒዮ። ለጓደኛህ ማዘኑ መልካም ነው ግን በጫካ ውስጥ ብቸኛ መሆንህ ሊያርበደብድህ አይገባም። ከጠፋህ አምስት ቀን መሆኑ ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ወደዚህ መልዕከት መተላለፍ አለበት። በመጀመሪያው በጫካው ካምፕ ለሚገኙት ዘበኞች ከዚያም በመንደሯ ውስጥ ላሉ ጥቁሮች። እዚህም አንድ ፖሊስ ጣቢያ ይኖር ይሆናል። ስለዚህ ወደዚህች መንደር መጓዙ ትክክል ነው?

በመንደሯና በወንዙ መካከል ካምፑ መገኘቱን እንጂ ስለአካባቢው ምንም የማውቀው ነገር የለም። በመንገዴ ላይ ያጋጠመኝን የመጀመሪያ ሰው ይገር በማስገደድ የቻንግን ወንድም ኪኪን ወደምፈልግበት ኢኒኒ ድረስ እንዲመራኝ ለማድረግ ዴያብሎስ በነበርኩበት ወቅት አቅጄ ነበር። ታዲያ አሁን ዕቅዴን ለምን አለውጣለሁ? መስመጤን ቢተማመኑበትማ ችግር አልነበረም። ግን ጠርጥረው ከሆነ ወደዚያ ማምራቱ አደገኛ ይሆናል። የጫካ ካምፕ እስከሆነች ድረስ ብዙ ዐረቦችም ይኖሩ ይሆናል ስለሆነም እኔን ለማደን በቂ የሰው ኃይል ማግኘት ይችላሉ። እነርሱን ተጠንቀቅ ፓፒዮ! አሁንስ መሳሳት የለብህም። ካልሆነ ቦታ ተሰንቅረህ እንዳትያዝ። ከሚያዩህ በፊት አንተ እነርሱን ማየትህን አረጋግጥ። ስለዚህ የእግር መንገዴን ለቅቄ በጫካው ውስጥ ብቀጥል ይሻላል ወደሚለው መደምደሚያ ደረስኩ። አንድ ገጀራ ብቻ ጨብጦ በዚያ መሰናክል ማለፍ አጉል ሞኝነት ነበር፤ ከሞኝነትም የባሰ ዕብደት።

ንጋቱን ኧንኳን ደህና መጣህ በሚሉት የአዕዋፍና የአውሬዎች ጩኸት ከእንቅልፌ ማለድ ብየ ነቃሁ። ለእኔም እንደዚሁ እንድ ሌላ ቀን እየጀመረልኝ ነበራ። አንድ እፍኝ ኮከነት አኘከሁና ፊቴ ላይ ትንሽ ለቅልቁ መንገዴን ቀጠልኩ።

መንገዴን አልራቅሁም ሆኖም በሚገባ ተከለየ ነበር። ከባድ ጉዞ ሆነ ምክንያቱም ምንም እንኳ ሐረጎቹና ቅርንጫፎቹ ጥቅጥቅ ያሉ ባይሆኑም መተላለፊያ ለመክፈት ያህል መመንጠር ነበረባቸው። ይህ ችግር ቢኖርም መንገዴን መልቀቄ ጥሩ አድርጌያለሁ፤ ለምን ቢባል ድንገት አንድ ሰው ሲያፏጭ ሰማሁ። ወደ ውጭ ብቅ አልኩና ተመለከትኩ። ሃምሳ ያርድ ስፋት ያለው መንገድ ከፊት ለፊቴ ለጥ ብሏል። ምንም ሰው የለም። ጸሃ አዎ ያውና መጣ። በትከሻው ጓዝ የተሸከመና በቀኝ እጁ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጠመንጃ የያዘ እንደ ከሰል የጠቆረ ሰው ነበር። በባዶ እግሩ ሆኖ ካኪ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ ለብሷል። ዐይኖቹን ከመንገዱ ላይ አይነቅልም ከጭነቱ ከብደት የተነሣ ጀርባው ጎብጦ ነበር።

ከመንገዱ ዳር አንድ ወፍራም ዛፍ ጎላ ተደበቅኩና ጩቤዮን አውጥቼ እንደ ጨበጥኩ ጠበቅኩት። በዛፉ አጠገብ ሲያልፍ እላዩ ላይ ዘለልኩበት። በቀኝ እጄ ጠመንጃውን ጨመደድኩና ወደ መሬት አስኪጥል ድረስ ከንዱን ጠመዘዝኩት። "እትግደለኝ! ስለ እግዚአብሔር ብለህ ራራልኝ!" አለ። የጩቤዮን ሜፍ አንገቱ ላይ እንደ ያዝኩ ወደ መሬት ጎንበስ አልኩና ጠመንጃውን አነሣሁ። ቀለሀና ባሩዱን በአፈሙዙ በኩል የሚጎርስ ጊዜው ያለፈበት ባለ አንድ ባንቧ ጠመንጃ ነበር።

የጠመንጃውን ሰደፍ ይገፍ ሁለት ያርድ ወደኋላ ተራመድኩ። "ጓዝህን ጣል። ለመሮጥ ብትቃጣ እገድልሃለሁ" ብየ ዛትኩበት።

ምስኪኑ ጥቁር እየተርበተበተ የታዘዘውን አደረገ። ከዚያም ወደ እኔ እየተመለከተ "ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ያመለጥከው ነህ እንዴ?" አለ።

"አዎ"

"ምን ትፈልጋለህ? ያለኝን ማንኛውም ነገር ልትወስድ ትችላለህ። ግን ይቅር እንዳትገድለኝ። አምስት ልጆች አሉኝ። እንዳሳድጋቸው ፍቀድልኝ።"

"እ ይህን ውሸትህን አቁም። ማን ነው ስምህ?"

"የሐንስ"

"ወዴት ነው የምትሔደው?"

"ለሁለቱ ወንድሞቼ ምግብና መድኃኒት ተሸክሜ ነው። በጫካው ውስጥ እንጨት ይቆርጣሉ።"

"የመጣኸውስ ከወዴት ነው?"

"ከኩሩ"

"መንደሯ ውስጥ ትኖራለህ?"

"የተወለድኩትም እዚያው ነው።"

"ኢኒኒን ታውቃታለህ?"

"አዎ አንዳንድ ጊዜ በወህኒ ቤቱ ውስጥ ካሉት ቻይናውያን ጋር እነግዳለሁ።"

"ይህን ታየዋለህ?"

"ምንድነው?"

"አንድ ባለ አምስት መቶ ፍራንክ ኖት ነው። ሁለት ምርጫዎች አሉህ። እኔ የምነግርህን ካደረግህ አምስት መቶው ፍራንክ የአንተው ይሆናል። ጠመንጃህንም መልሰህ ታገኛለህ። ይህን ባታደርግ ወይም በእኔ ላይ አሻጥራለሁ ብትል ግን

t.me/OLDBOOKSPDF

እገድልሀለሁ። የትኛውን ትመርጣለህ?»

«ምን እንዳደርግልህ ትፈልጋለህ? የጠየከኝን ማንኛውንም ነገር በነጻ እንኳ ቢሆን አደርጋለሁ።»

«ወደ ኢኒኒ ካምፕ እንድትወስደኝ እፈልጋለሁ። ከአንድ የሆነ ፅይናዊ ጋር ስገናኝ አንተ መንገድህን ልትቀጥል ትችላለህ። እሺ?»

«እሺ።»

«ግን በእኔ ላይ ካቃጠርከ ሟች ነህ።»

«አላደርገውም። እምልልሃለሁ አላደርገውም።»

የቆርቆሮ ወተቶች ይዘ ነበር። ስድስት ጣሳዎች ሀሊት ፓውንድ የሚመዝን ዳቦና ጥቂት የዓሣማ ሥጋ ጨምሮ ሰጠኝ።

«ጓዝህን ጫካው ውስጥ ደብቅ በኋላ ልታነሣው ትችላለህ። ይሀን ዛፍ በገጀራዬ ምልክት አደርግበታለሁ ስለዚህ ቦታው የት እንደሆነ ታውቀዋለህ።»

አንድ ቆርቆሮ ወተት ጠጣሁ። እንደዚሁም አንድ አዲስ ሰማያዊ ሉሥራ የሚያገለግል ሱሪ ሰጠኝ። ጠመንጃየን ከእጄ ሳልነጥል ሱሪውን አጠለቅኩት።

"እሺ ዮሐንስ እንግዲህ እንሂድ። ማንም ሰው እንዳያየን ተጠንቀቅ። ከተያዝን ጥፋቱ የአንተ ነውና ሞት ዕድልህ ይሆናል።"

ከእኔ የበለጠ ዮሐንስ በጫካው ውስጥ ይራመዳል። መከተሉ ችግር ሆነብኝ። እርሱ ግን በመዝናናት መንገዱን ቀጠለ።

«ከደሴቶቹ ሁለት እሥረኞች አምልጠዋል ብለው ለኩሩ እንዳስጠነቀቁት ዐውቀሃል? ለአንተ ግልጽ መሆን አለብኝ በዚያ አጠገብ ማለፍ በጣም አደገኛ ይሆናል።»

«ዮሐንስ ጨዋ ሰው ትመስላለህ። ከእኔ ጋር እንደምንግባባም ተስፋ አለኝ። ወደ ኢኒኒ እንዴት እንደምንደርስ የአንተ ምክር ምንድን ነው? ልብ አድርግ፤ የአንተ ህልውና የሚረጋገጠው በእኔ ሰላም ማግኘት ነው። ከተያዝኩ አንተን መግደል አለብኝ።»

«ማን ብየ ልጥራህ?»

«ፓፒዮ»

«እሺ ሚስተር ፓፒዮ። ወደ ጫካው ውስጥ በጣም ሰርገን በመግባት የኩሩን አካባቢ በሩቁ መማተር እንዳለብን ነው። በጫካው ውስጥ አስከሔድን ድረስ ኢኒኒ እንደማደርስህ ላረጋግጥልህ እችላለሁ።»

«በመዳፍህ ውስጥ ነው ያለሁት። ሰላም አለው ብለህ የምትገምተውን መንገድ ራስህ ምረጥ።»

የጫካው ጉዟችን ዝግ ያለ ነበር፤ መንገዱን እየራቅን ስንሄድ ዮሐንስ ይበልጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

እየተረጋጋ ሔደ። አስከዚህ በጣም አያልበውም ነበር። ድንጋጤውም ከፊቱ በረደለት። አንድ ማረጋጊያ መድኃኒት የወሰደ ይመስላል።

«ዮሐንስ አሁን ብዙም የፈራህ አትመስልምላ?»

«አልፈራም ሚስተር ፓፒዮ፤ የእግር መንገዴን ብዙ መጠጋት ለአንተ በጣም አደገኛ ነው፤ ለእኔም እንደዚያው ነው።»

ወደፊት ደህና አድርገን ገሠገሥን። ጥቁሩ ሰው ጮሌ ነበር፤ በመካከላችን ከዐሥራ ሁለት ጫማ ከፍታ ርቀት ይበልጥ ፈጽሞ አይጨምርም።

«አንድ ጊዜ ቆይ ሲጃራ መጠቅለል እፈልጋለሁ።»

«እንካ፤ እንድ ፓኬት ሲጃራ ይገባለሁ።»

«አመሰግናለሁ ዮሐንስ። ደግ ሰው ነህ።»

«ካቶሊካዊ ነኝ። ዘበኞች አሥረኞቹን እንዴት እንደሚያንገላቷቸው ማየቱ ያሳዝነኛል።»

«ብዙዎች አይተሃል እንዴ? የት ቦታ?»

«በኩሩ ከሚገኘው ካምፕ። በደም ተቅማጥ ወይም በቢጫ ወባ አለበለዚያም በእንጨት ቆረጣ በአዝጋሚ ሞት ሲያልቁ አነርሱን ማየት ልብን ይሰብራል። ቦ[illegible]ሴዎቹ የታሰራችሁት እጥፍ ድርብ ትሻላላችሁ። ምንጊዜም ካየኋቸው ውስጥ የ[illegible]ሪያው ጤነኛ አሥረኛ ያለጥርጥር አንተ ነህ።»

«ዕውነት ነው በደሴቶቹ መታሠሩ ይሻላል።»

አንድ ትልቅ የዛፍ ቅርንጫፍ ላይ ለአንድ አፍታ ተቀመጥን። ከራሱ የጣሳ ወተቶች አንዱን አበረከትኩለት። ግን ኮከነት ማላመጡን ስለመረጠ እምቢ አለ።

«የሚስትህ ዕድሜ ስንት ይሆናል?»

«ሠላሳ ሁለት ዓመቷ ነው። እኔ ዐርባ ነኝ። አምስት ልጆች አሉን ሦስት ሴቶችና ሁለት ወንዶች።»

«የተደላደለ ኑሮ ትኖራላችሁ?»

«ከአንጨት ሽያጭ መጠነኛ ገቢ ስለምናገኝ እስከዚህ ብዙም አይከፋንም። ለዘበኞቹ ሚስቶች ልብስ የማጠብና የመተኮሱን ሥራ የያዘችውም ባልተቤቴ ናት። ይህም በመጠኑ ይረዳናል። በጣም ድሆች ነን ግን ለምንበላውና ልጆቹን በሙሉ ትምህርት ቤት ለመላክ የሚበቃንን ያህል የዕለት ገቢ አለን። ከዚያም ሌላ ሁሉም የሚያደርጉት ጫማ አላቸው።»

አይ የድሀ ነገር! ልጆቹ ጫማ በማድረጋቸው ሁሉም ነገር ተሟልቷል ብሎ አብቅቷል። የቁመቱ መጠን ልክ እንደ እኔ ሆኖ፣ ፊቱም ተንኮል ያለበት አይመስልም። ጥሩ ከርስቲያን፣ መልካም አባወራ፣ ብርቱ ሠራተኛና በቅን አስተሳሰብ የተሞላ ሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

መሆኑን ዐይኖቹ በግልጽ ይናገራሉ።»

«አንተስ እንዴት ነህ ፓፒዮ?»

«ዮሐንስ፣ እኔ አዲስ ሕይወት ለመጀመር በመንገድ ላይ ነኝ። ለወሮር ዓመታት በሕይወት ተቀብሬበት ከነበረው ቦታ ለማምለጥ ከመታገል አልቦዘንኩም፣ ስለሆነም በሐሳቤም እንኳ ቢሆን ማንንም ሰው ሳልጎዳ ልክ እንደ እንተው ሚስትና ልጆች ያሉት ነጻ ሰው አንድ ቀን መሆን እችላለሁ። አንተ ራስህም ተናግሮኝዋል፣ የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤቱ ኑሮ የተግማማ ነው። የራሱን ከብር ለመጠበቅ ቅንጣት ታህል ስሜት ያለው ማንም ሰው ለማምለጥ መሞከር ይኖርበታል።»

«አንተን ለመርዳት የቻልኩትን ጥረት አደርጋለሁ። መንገዶችንን እንቀጥል።»

ፍጹም የአንድ ሴኮንድ ዳተኝነት ሳያሳይ ዮሐንስ ልዩ በሆነ የአቅጣጫ አመራረጥ፣ በቀጥታ ወደ ቻይናዎቹ ሠፈር መራኝ። ከመሸ በኃላ ሁለት ሰዓት ገደማ ደረስን። አንዳንድ ቅጭልጭልታዎች በሩቁ እንሰማለን፣ ግን መብራ የለም። ወደ ካምፑ አጠገብ ለመድረስ ሁለት የዘብ ጣቢያዎችን ከልል መዞር እንዳለብን ዮሐንስ ገለጸልኝ። አለንበት ቦታ በመቆየት ሌሊቱን ለማሳለፍ ወሰን።

በጣም ዝልፍልፍ ብዬ ደክሜ ነበር፤ ግን መተኛት ፈራሁ። ስለ ሰውዬው ግምቴ የተሳሳተ ቢሆንስ? እንደተኛሁ ጠመንጃውን ነጥቆ ቢገድለኝስ ምን ይታወቃል? ለእርሱ ድርብ ድል ይሆንለታል፣ እኔ ካመጣሁበት አደጋ ይተርፋል፣ አንድ ያመለጠ እሥረኛ በመግደሉም ጉርሻ ይሸለም ይሆናል።

አዎ! ልክ ነኝ፣ ጨዋ ነበር። ያለ ምንም ቃል ወርዶ ተዘረጋና እንቅልፍ ወሰደው። ሰንሰለቴን አሁንም እንደ ያዝኩ ነበር። በእርሱ ላቆራኘው አሰብኩ፣ ግን በቀላሉ ሊፈታው ስለሚችል ፋይዳ የለውም። ስለዚህ እንደ ነቃሁ ለመቆየት መታገል አለብኝ። ዮሐንስ የሰጠኝ ፓኮ ሲጃራ ነበረኝ። በእንቅልፍ ላለመውደቅ አጥራለሁ። ዮሐንስን ለማመን አልችልም፣ ምንም ጨዋ ሰው ቢሆን እኔን ያው እንደ አንድ ወንጀለኛ ማየት አለበት።

ሌሊቱ በጣም ጨለማ ነበር። ዮሐንስ የተኛው ከእኔ በስድስት ጫማ ብቻ ራቅ ብሎ ቢሆንም፣ ልለየው የቻልኩት በውስጥ እግሮቹ ንጣት ብቻ ነበር። ከብዙ ማይል ርቀት የሚያስተጋባው የትላልቅ ዝንጀሮዎች የማያቋርጥ ጎርናና ጩኸታቸው የጫካውን የሌሊት ጸጥታ ያደፈርሰዋል። ጩኸቱ ልምድ እስከሆነ ድረስ ዘበኞቹም ስለሚያንቀላፉ በጣም ጠቃሚ ይሆናል።

አልፎ አልፎ በሲጃራ ጢስ አማካይነት የቢንቢ መንጋዎችን እየተከላከልሁ ጧ ብየ እንደ ተጋደምኩ የዕንቅልፌን መፈታተን ተቋቋምኩት። ግን እነርሱ ዙሪያየን ካልጮሁብኝ ደግሞ እንቅልፍ እንደሚጥለኝ አርግጠኛ ነበርኩ። ምኞቴ ቢጫ ወባ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስተላላፊዎች እንዳይሆኑ ነበር። ሰዓቱን በትዝታ አሰለፍኩት። ሌላው ቢቀር ለጊዜው እንኳ ከቅጣት ጎዳና ውጭ ሆኜ አያለሁ። ወደ ቅጣት ጎዳና መውረድ ስጀምር በ1931 ዕድሜየ ሃያ አምስት ዓመት ነበር። አሁን 1941 ሆኗል። ዐሥር ዓመታት አልፈው ነበር። ፫፡፫፭ ያ ፕራደል የተባለ ጨካኝ ዓቃቤ ሕግ፣ ቆሻሻ ጉድጓድ ውስጥ አስገብቶ ሙሉ በሙሉ እስከጠፋ ድረስ ቀስ በቀስ ከዝቃጭ አንድዋሐድለት ወርውሮኝ ነበር። የመጀመሪያውን የማምለጥ ከፍል ተወጥቸዋለሁ። ከጉድጓዱ ውጭ ተንጠላጥየ ጫፉን ጨምድጃለሁ። አሁን ሁለተኛውንም ከፍል ለማሳካት ሙሉ ኃይሌንና ዕውቀቴን መጠቀም አለብኝ። ሌሊቱ ረጅም ነበር፤ ሆኖም ወደመጣበደዱ ተቃርቧል። እንደነቃሁ በመቆየት ነፃነቴን በተሣካ ሁኔታ ራሴው በመጠበቄ ተደሰትኩ። አንድ የመንፈስ ድል ስለሆነ፣ የንጋቱን መምጣት የሚያበስሩትን የመጀመሪያዎቹን የአዕዋፍ ጫጫታ ስሰማ፣ በሙሉ ስሜት ራሴን እንኳን ደስ አለህ አልኩት። የእነርሱ መንቃት ወዲያው የሌላውንም አስከተለና ጥቁሩ ሰው ተንጠራርቶ ቁጭ በማለት እግሮቹን አሻሸ።

«እንደምን አደርክ። አልተኛህም እንዴ?»

«አልተኛሁም።»

«ይኸ ሞኝነት ነው። እኔን የምትፈራበት ምክንያት የለህም። ልረዳህ እፈልጋለሁ ብየ አንዴውኑ ወስኛለሁ።»

«አመሰግናለሁ ዮሐንስ። የቀን ብርሃን እዚህ እኛ ዘንድ እስኪደርስ ምን ያህል ጊዜ ያስጠብቀናል?»

«የቀን ብርሃን መምጣቱን የሚያውቁት አራዊቱ ብቻ ናቸው። ምናልባት ከእንግዲህ ወዲያ አንድ ሰዓት ብንቆይ ማየት እንችላለን። ጩቤውን አውሰኝ ፓፒዮ።?»

ያለምንም ማመንታት ሰጠሁት።

የአንድ ወፍራም ተክል ቅርንጫፍ ዘንጥሎ ቆረጠና አንዱን ጉማጅ ለእኔ አቀበለኝ፣ ሌላውን ለራሱ አስቀረ። «ከውስጡ ያለውን ፈሳሽ ጠጣና ከዚያም ፊትህን አብስበት።»,አለኝ።

ጠጣሁና ከዚያም ታጠብኩበት። ዮሐንስ ጩቤዬን መልሶ ሰጠኝ። ቀኑም ወጣ። እያንዳንዳችን አንድ ሲጃራ አጨስንና ጉዞ ቀጠልን። ከባድ የጭቃ ማጥ ከማላቆጥ በስተቀር ምንም ሳናይ ቀትር ገደማ ወደ ኢኒኒ ተጠጋን።

ከአንድ ሰፊና ጥርጊያ መንገድ ጎን ለጎን አንድ ቀጭን የብረት ሐዲድ ተዘርግቷል። ከሩቁ የሚሰማው ቅጭልጭልታ የሚመነጨው በቻይናዎች ነው ሲል ዮሐንስ ነገረኝ። አንዱን ሲያልፍ ተመለከትነው። ሁለት ዘበኞች ተቀምጠው ከእነርሱ ኋላ ሁለት ቻይናውያን ሰረገላውን በአንድ ስታንጋ ደግፈዋል። ሽከርካሪዎቹ የእሳት ብልጭታ ያፈናጥሩ ነበር። ስታንጋዎቹ የብረት ጫፎች ስለ ነበሯቸው ለሁለቱም ማለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ለመግፋትም ሆነ ለመግታት እንደሚጠቀሙባቸው ዮሐንስ ገለጸለኝ።

ለብዙ ተግባር የሚጠቀሙበት አውራ ጎዳና ነበር። የሐረግ ጥቅሎች በትከሻቸው የተሸከሙ ቻይናዎች ያልፋሉ- አንዱ የዱር ዓሣማ ተሸክሟል፤ ሌሎቹ የዘንባባ ቅጠሎች ሰብስበው ቀርቅበዋል። ማንኛውም ሰው የሚያመራው ወደ ካምፑ ነበር። ሰዎቹ ጫካው ውስጥ የሚያከናውኑዋቸውን የተለያዩ ነገሮች ዮሐንስ ተነተነልኝ - የዱር አውሬዎች በማደን፤ ለቅርጫት ሥራ የሚያገለግሉ ሐረጎችን በመምዘዝ፤ የእትክልት መደቦችን ከፀሐይ ሙቀት የሚከላከሉ ሰሌኖች መሥሪያ የሚሆኑ የዘንባባ ቅጠሎችን በመቁረጥ ነበር። አንዳንዶቹ ቢራቢሮዎች ሲያድኑ፤ ሌሎቹ ደግሞ የተለያዩ በራሪ ነፍሳት ወይም አበቦችን ይቃርሙ ነበር። አሰተዳደሩ የመደበላቸውን ሥራ ከጨረሱ በኋላ ወደ ጫካው ለመሐድ ይፈቅድላቸዋል። ማታ ዐሥራ አንድ ሰዓት ሲሆን ማንኛውም ሰው ወደ ካምፕ መመለስ ነበረበት።

«አምስት መቶው ፍራንክና ጠመንጃህ ያውልህ ዮሐንስ።» ቀደም ብየ ጥይቱን አውጥቸው ነበር። «አኔ ጩቤና ገጀራው አለኝ። አሁን መሐድ ትችላለህ። አመሰግናለሁ። ወደ ሕይወት የሚመለስ አንድ ሰው ስለረዳህ አኔ ከማደርገው በላይ እግዚአብሔር ውለታህን እንደሚከፍልህ ተስፋ አለኝ፤ ለልጆችህ፤ ዶ አሥረኛ ደግ ሰው ነበር። ስለረዳሁት አይቆጨኝም፣ እንድትላቸው።»

«ሚስተር ፓፒዮ፤ ጊዜው መሽቷል። ከመጨለሙ በፊት ብዙም ርቄ መሐድ አልችልም። ጠመንጃውን ያዝና አስኪነጋ ድረስ ካንተ ጋር እቆያለሁ። የምትፈልግ ከሆነም ከቻይናውያኖቹ አንዱን አቱሚ፤ ለኪኪ መልዕክቱን እንዲያስተላልፍ ልንገረው። ከወህኒ ቤት ካመለጠ ነጭ ሰው ይልቅ ከእኔ ጋር ለመገናኘት ብዙም አይፈራም፤ ወደ መንገዱ ልውጣ። አንድ ዘበኛ ቢመጣ እንኳ እኔን ካየ አካባቢውን አይጠረጥርም። ካየን ለሚገኘው ጣውላ መሰንጠቂያ እንጨት እየፈለግሁ ነው ብየ እነግረዋለሁ። አመነኝ።»

«አሺ ግን ጠመንጃህን ውሰድ። አንድ ሰው ጠመንጃ ሳይዝ ጫካ መግባቱ ሊቀልድ ነው ብለው ይገምቱ ይሆናል።»

«ልክ ነህ»

ዮሐንስ መንገዱ መካከል ሔዶ ተጥተረ። ሁኔታው ደስ ያለኝን አንድ ቻይናዊ ሰመለከት እንድ ለስላሳ ፉጨት ላሰማው ነበር።

አንድ የሙዝ ግንድ በትከሻው እንደ ተሸከመ አንድ አጭር ሽማግሌ ቻይናዊ፤ «ሰላም ወዳጄ» አለው። ይህ ሰላምተኛ ሽማግሌ ደህና መስሎ ስለታየኝ አቁጨሁ።

«ሰላም፤ አንድ ጊዜ ቆይ አስኪ። አንድ ነገር ልጠይቅህ አፈልጋለሁ።»

«ምን ትፈልጋለህ ወዳጄ?!

አምስት ደቂቃ ያህል አወሩ። አንድም ነገር መስማት አልቻልኩም። ትልቅ

t.me/OLDBOOKSPDF

አጋዘን በወጋግራ የተሸከሙ ሁለት ቻይናውያን በአጠገባቸው አለፉ። በእግሩ ተንጠልጥሎ ጭንቅላቱ ቆሻሻውን እየጓፈፈው ይሔድ ነበር። ጥቁሩን አላናገሩትም፤ ግን ከቻይናዊው ጋር ትንሽ ቃላት ተለዋወጡ።

የሐንስ ሽማግሌውን እኔ ወዳለሁበት ጫካ እየመራ አመጣው። እኔ ዘንድ ሲደርስ እጁን ዘረጋልኝ።

«ኮብላይ ነህ?» አለኝ።

«አዎ»

«ከወዴት ቦታ?»

«ከዲያብሎስ»

«ደህና» በማለት ሳቅ አለና በተጨነቆሩት ዐይኖቹ ፍርጥምጥም ብሎ ተመለከተኝ። መልካም ነው፣ ስምህ?»

«ፓፒ።»

«ስለ አንተ አስካሁን ፍጹም አልሰማሁም።»

«የቻንግ ጓደኛ ነኝ፤ ቻንግ ሻውኬን፣ የኪኪ ወንድም።»

«አሃ! ጥሩ» ብሎ እንደገና እጄን ጨበጠኝ። «ምን ትፈልጋለህ?»

«ኪ-ህ መጥቶልኝ እንዳየው መፈለጌን ለኪኪ እንድትነግርልኝ ነበር።»

«አይቻልም»

«ለምን?»

«ኪኪ የካምፑን አዛዥ ስድሳ ዳከየዎች ሰርቆ አዛዡ ለመግደል ሲፈልገው፤ ኮበለለ» አለ።

«መቼ?»

«ሁለት ወር ሆኖታል።»

«ወደ ባሕር ወጥቷል እንዴ?»

«አላውቅም። ወ ? ካምፕ አሔድና የኪኪ የቅርብ ጓደኛ የሆነ ቻይናዊ ጋር አነጋገራለሁ። እርሱ ይነግረኛል። አንተ አንዳትንቀሳቀስ። ዛሬ ማታ እመለሳለሁ።»

«በስንት ሰዓት?»

«አላውቅም። ግን ምግብና ሲጃራም አመጣልሃለሁ። አሳት ማንደድ የለም። አቋጫለሁ። እጓደ ሰማህ ወደ መንገዱ ዳር ውጣ። ገባህ?»

«ገባኝ» ከዚያ በኋላ ሔደ። «ዮሐንስ፣ ምን ይመስልሃል?»

«ችግር የለም። ከፈለግከ አውንም እንደገና ወደ ኩሩ መመለስ እንችላለን። እዚያ አንዲት የግንድ ጀልባ፣ ምግብና አንድ የነፋስ ሽራ ላዘጋጅልህ እችላለሁ።»

«ዮሐንስ፣ በጣም ራቅ ብየ ነው የምሔደው። ብቻየን አልችልም። ግን ስለ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስተላስብህ አመሰግናለሁ። ችግሩ እየባሰ ከመጣ እንደ ሁኔታው የእጮን ትብብር አፈልግ ይሆናል።»

ቻይናዊው ሰጥቶን የነበረውን ምግብ በላን። ዮሐንስ ጥበቃውን ልቀጥል አለ። እኔም አመንኩት። የቢምቢዎቹ ደም መጠጣ ቀደም ሲል ተጀምሮ ስለነበር በፊቴና እጆቼ ላይ የትምባሆ ጭማቂ ለቀለቅኩ።

ዮሐንስ ቀሰቀሰኝ። «ፓፒዮ፣ አንድ ሰው በማቷጨት ላይ ነው።»

«ጊዜው ስንት ሰዓት ይሆን?»

«በጣም አልመሸም። ምናልባት ሦስት ሰዓት ይሆናል።» ወደ መንገዱ ዳር ወጣሁ። ሌሊቱ አሁንም በጣም ጨለማ ነበር። አንድ የሚያቷጭ ሰው እየቀረበ ይመጣ ጀመር። እኔም አጸፋውን መለስኩ። ቀስ በቀስ በመቅረብ ላይ ቢሆንም፣ ገና ላየው አልቻልኩም። በየተራ ቍጩት በመለዋወጥ መጨረሻ ላይ ተገናኘን። ሦስት ነበሩ። በየተራ ጨበጡኝ።

«አዚሁ አመንገዱ ዳር እንቀመጥ» አለ ከእነርሱ አንዱ በተስተካከለ ፈረንሣይኛ። «ማንም ሰው ሊያየን አይችልም።» ዮሐንስም መጣና ተቀላቀለን።

«መጀመሪያ ብላና በኋላ እንነጋገራለን።» ዮሐንስና እኔ እንፋሎቱ የሚትሎገሎግ የአትክልት ሾርባ ጠጣን። የተረፈንንም ለኋላችን ለማቆየት ወሰን። የሜንታ ቃና ያለው አርኪ የሆነ ትኩስ ጣፋጭ ሻይም ጠጣን።

«የቻንግ ጓደኛ ነህ እንዴ?»

«አዎ፤ ከኪኪ ጋር አብረን ማምለጥ እንደምንችል ነግሮኛል። ቀደም ሲል ኮሎምቢያ ድረስ ረጅም ጉዞ አድርጌያለሁ። በዚህ ምክንያት ነው ቻንግ ወንድሙ ከእኔ ጋር እንዲሔድ የፈለገው። ይተማመንብኛል።»

«ይሆናል። የቻንግን ውቅራቶች አስኪ ግለጽልን?»

«ደረቱ ላይ አንድ ደራጎንና በግራ እጁ ላይ ሦስት ነጥቦች አሉበት። ነጥቦቹም ኢንዶቻይና ወስጥ ፓውሎ ኮንደር በተደረገው ዓመፅ ከመሪዎቹ አንዱ መሆኑን እንደሚያመለክቱ ነግሮኛል። ሌላው የዓመጹ መሪ ደግሞ የቅርብ ጓደኛው ቫን ሁዊ የተባለው ሲሆን፣ አሱም ባለአንድ እጅ ነው።»

«አዬ ነኝ» አለ አንደኛቸው። «የቻንግ ጓደኛ መሆንህን አስመስከረሃል፤ ስለዚህ የእኛም ጓደኛ ነህ። አሁን በጥንቃቄ አዳምጥ። ኪኪ ገና ወደ ባሕር አልወጣም፤ ምክንያቱም ጀልባ እንዴት እንደሚቀዘፍ አያውቅም። ከዚህ በግምት ስባት ማይል የሚርቅ ጫካ ውስጥ ብቻውን አለ። ከሰል ያከሰላል፤ ጓደኞቹ እየሸጡ ገንዘቡን ይሰጡታል። የሚበቃውን ያህል ሲያጠራቅም አንድ ጀልባ ገዝቶ ከእርሱ ጋር የሚያመልጥ አንድ ሰው ይፈልጋል። አሁን ያለበት ቦታ አያሠጋውም። ማንም ሰው ወደ

t.me/OLDBOOKSPDF

ደሴቷ መድረስ አይችልም። ምክንያቱም በሚዋልል የአሸዋማ ማጥ ተከብባለች። ለመሻገር የሚሞክር ማንም ሰው ሰምጦ ይቀራል። ፀሐይ እንደወጣች ወደ አርሱ ሄጋስድሃለሁ። አሁን ከእኛ ጋራ ና።»

ጨረቃዋ ከፍ ብላ ስለወጣችና ከፊት ለፊት በሃምሳ ያርድ ርቀት ለማየት በቂ ብርሃን ስላላት የመንገዱን ዳር ያዝን። ወደ አንድ የአንጨት ድልድይ ደረስንና ቫን ሁዊ «ወደ ድልድዩ ሥር ውረድና እዚያው ተኛ፣ እኔ ጧት ወደ አንተ እመጣለሁ» አለ።

ተጨባበጥንና ተለያየን። ወደ መሐል መንገድ ገቡ። ከተያዙ፣ በጫካ ውስጥ ያስቀመጥናቸውን ወጥመዶች ልንፈትሽ ሔደን ነው ሊሉ ነበር።

«ጋሚዮ እዚህ አትተኛ። ጫካ ግባ፤ እኔ እዚህ አተኛለሁ» አለ ዮሐንስ።

«መልካም» ወደ ጫካው ሔድኩና ሾርባው ሆዴን አሙቆት ስለነበር በደስታ ለጥ አልኩ።

ቫን ሁዊ ወጋገን ከመድመቅ በፊት ብቅ አለ። ጊዜ ለመቆጠብ ፀሐይዋ እስክትወጣ ድረስ በመንገዱ ተጓዝን። ለዐርባ ደቂቃ በችኮላ ተራመድን። ወዲያው ነጋና በሐዲዶቹ ላይ የሚመጣ የአንድ ሰረገላ ድምፅ በሩቁ ሰማንና ጫካው ወስጥ ተሸሸግን።

«ደህና ሁን ዮሐንስ። አመሰግናለሁ፣ መልካም ዕድል። አንተንና ቤተሰቦችህን እግዚአብሔር ይባርካችሁ።» አምስት መቶውን ፍራንክ እንዲወስድ ገፋፋሁት። በምንለያይበት ጊዜ፣ ከኪኪ ጋር የማከናውነው ሥራ ካልሰመረ መንደሩን እንዴት ማግኘት እንደምችልና ከእርሱ ጋር ተገናኝተን ከነበረችበት መንገድ እንዴት እንደምደርስ ገለጸልኝ። በሳምንት ሁለት ጊዜ ስለሚጠቀምባት መኖኘታችን እንደማይቀር ነበር። ከጥቁሩ ጓደኛዬ ጋር ተጨባበጥንና መንገዱን ይዞ በችኮላ አፈተለከ።

«አንሒድ» አለ ቫን ሁዊ፣ ወደ ጫካው ውስጥ ሸመጠጥን። ወዲያውኑ አቅጣጫውን መረጠና በግሩም ፍጥነት ተንቀሳቀስን። ጫካው በጣም ጥቅጥቅ ያለ ስላልነበረ፣ በገጀራ መቆራረጥ ሳያስፈልግ ቅርንጫፎቹንና ሐረጎቹን በመለያየት ብቻ ገሠገሥን።

ኪኪ

ሦስት ሰዓት በማይሞላ ጊዜ ውስጥ ከእንዲት የጭቃ ኩሬ ፊትለፊት ደረስን። አበቦችና ትላልቅ አረንጓዴ ቅጠሎች ከጭቃው ውስጥ ብቅ ብቅ ብለዋል። የኩሬዋን ጠርዝ አግድም በመከተል ቀጠልን።

ስርበተበት ተመለከተችና፣ «ተጠንቀቅ፣ እንዳያዳልጥህ። ወደ ላይ ተንጠላጥለህ መውጣት ፍጹም አትችልም» ሲል ቫን ሁዊ አስጠነቀቀኝ።

«አንተ ወደፊት ቅደም። እኔ በጣም እየተጠነቀቅኩ እከተልሃለሁ።» ከጠረፉ ዳር በማምት አንድ መቶ ሃምሳ ያርድ ዙሪያ ከብ ያላት አንዲት ትንሽ ደሴት ከጭቃው

t.me/OLDBOOKSPDF

ባሕር መካከል ትገኛለች። ከመካከሏ ጢስ እየተነነ ይወጣ ነበር። የከሰሉ ጉድጓድ መሆን አለበት። ከወይኗ በስተቀር ሁለመናዋ የሰመጠ፣ አንዲት እዞ ከአሸዋው ማጥ ውስጥ ድንጉት አየሁ። እዚያ አረንቋ ወስጥ በምን ተአምር የሚበላ ነገር ማግኘት ትችላለች?

በኩሬዋ ጠርዝ በግምት የአንድ ማይል ሦስት አራተኛ የዙሪያ መንገድ ከተጓዝን በኋላ ነበር ቫን ሁዊ ቆም ብሎ ቻይናውያን ቋንቋ ሳንባው እስኪሰነጠቅ ድረስ ማቀንቀን የጀመረው። አንድ ሰው ወደ ደሴቷ ጠርዝ መጣ። የለበሰውም ቁምጣ ሱሪ ነበር። ሁለቱ ቻይናውያን በጣም ለረጅም ጊዜ ስላወሩ ትዕግሥቴ ሊሟጠጥ ትንሽ ሲቀረው ነበር ቫን ሁዊ፣ «በዚህ መንገድ ና» ያለኝ።

ተከተልኩትና እርምጃዎቻችንን አስተካከልን።

«መልካም። ይሽ የኪኪ ጓደኛ ነው። ኪኪ ወደ አደን ሔዷል፣ ግን ቶሎ ይመለሳል። እዚሁ እንጠብቀዋለን።

ተቀመጥን። አንድ ሰዓት ሳይሞላ ኪኪ ደረሰ። የሩቅ ምሥራቅ ላህይ ያለው ድርቅ ያለ ደቃቅና ፈገግታ የማይለየው፣ ከሞላ ጎደል የሻገቱ ጥርሶችና ተመራማሪ ዐይኖች ያሉት ሰው ነበር።

«አንተ ነህ የወንድሜ የቻንግ ጓደኛ?» አለ።

«አዎ።»

«ጥሩ። ቫን ሁዊ መሔድ ትችላለህ።»

«አመሰግናለሁ» አለ ቫን ሁዊ።

«ያውልህ፤ ይህን ተባዕት ቆቅ ውሰድ።»

«አልፈልግም አመሰግናለሁ» ብሎ እጁን ጨበጠና ሔደ።

አንዲት ዓሣማ ወደ ነበረችበት ቦታ ኪኪ መራኝ። በትክክል የእርሷኑ ኮቴ እየረገጥን ተከተልን።

«በጣም ተጠንቀቅ ፓፒዮ። አንድ አርምጃ ከተሳሳትክ ሰመጥክ ማለት ነው። መረዳዳት አንችልም፤ ሁላችንም እንሞታለን። መንገዱ ቀጥተኛ አይደለም። ምክንያቱም የአሸዋው ማጥ ይዋልላል። ዓሣማዋ ግን ታገኘዋለች። አንድ ጊዜ መሻገር ከመቻላችን በፊት ሁለት ሙሉ ቀኖች ጠብቀናል።»

ጥቁሯ ዓሣማ አካባቢውን አነፈነፈችና ወዲያው የአሸዋ ማጡን ተሻግራ ሔደች። ኪኪ በቻይናውያን ቋንቋ አነጋገራት። ልክ እንደ ውሻ በምትታዘዘው በዚች ትንሽ እንስሳ ፈዝዤ ነበር። ምንጊዜም ከአንድ ወይም ከሁለት ኢንች የበለጠ ሳትሰምጥ ዓሣማዋ ወደ ሌላው ዳር ስትሻገር ዐይኖቼ እንደ ፈጠጡ ቀሩ።

«አግሮችህን በእኔ አርምጃዎች ላይ አሳርፍ። መፍጠን ይኖርብናል። ምክንያቱም የዓሣማዋ ኮቴ ድንጉት ይሰወራል» አለና ኪኪ ከአርሷ ኋላ ተከተል።

t.me/OLDBOOKSPDF

ያለምንም ችግር ተሻገርን። የአሸዋ ማጡ ከቁርጭምጭሚቴ በላይ አልደረሰም ቢሆን ወደ መጨረሻው ላይ ብቻ ነበር።

ዓሣማዋ ሁለት መቶ ያርድ የሚያስኪድ ዙሪያ መንገድ አባዘነችን። ተና ይንጠፈጠፍ ነበር። መፍራት ብቻ ሳይሆን ድንጋጤም ያዘኝ።

በመጀመሪያው የሽግግር ከፍለ ጊዜ ልክ እንደ ሲልቪያ ለመሞት እኔም ጽዋ ደረሰኝ ብየ ደንግጬ ነበር። በዚያች የመጨረሻዋ ሰዓት ላይ እንደነበርኩ ምስኪኑን ዕድለቢስ እንደገና እየሁት፤ ግን ምንም እንኳ ሰውነቱ የእርሱ ቢሆንም ፊቱ የእኔን ምሥል የያዘ መስለኝ። ያ እርምጃ ገሃነመ እሳት ነበር የሆነብኝ። ቶሎ መርሳት አልሆነልኝም።

«ሕጅህን አቅበለኝ» አለና ሁለመናው አጥንትና ቆዳ ብቻ የሆነው ደቃቃ ሰው ከኩሬው ወደ ላይ እንድወጣ ረዳኝ።

«ወዳጄ፤ ይህችን መንገድ እኔን እይከነሁ የሚል ማንም ሰው ሊጠቀምባት የሚችል አይመስለኝም።»

«የለም፤ ስለዚህ እያሠጋንም።»

ወደ ትንሿ ደሴት መሐል መራመድ ቀጠልን። ጢስ ጉሮሮየን ከርከሮ አፈነኝ። ሳልኩ። በመቃጠል ላይ ካሉት ሁለት የከሰል ጉድጓዶች የሚመጣው ጢስ ነበር። እዚህ በቢንቢዎች መሠቃየት የለም። ከቅጠላ ቅጠል የተሠራች አንዲት ትንሽ ጎጆ፣ ከነፋሱና ጢሱ ፈቀቅ ብላ ቆማለች። ከኪኪ ጋር ከመገናኘታችን በፊት አይተነው የነበረው ደቃቃ ኢንዶ ቻይናዊ፣ በመዘጊያዋ ፊት ለፊት ቆሞ ነበር።

«ሰላም ወዳጄ» አለ።

«በፈረንሣይኛ አነጋግረው። የወንድሜ ጓደኛ ነው።»

ከሳሳው ቻይናዊ ከእግር እስከራሴ ደጋግሞ ተመልከቶኝ ሲረካ እጁን ዘረጋና አሳየኝ።

«ግባ። ተቀመጥ።»

ጎጆዋ ንጹሕ ሆና ሁለመናዋ ኩሽና ቤት ነበረች። ምድጃ ላይ ከተጣደ አንድ ትልቅ ሰፌ ብረት ድስት ወስጥ አንድ ነገር እየተቀቀለ ነበር። ከአንጨት ባላ የተሰራ ለአንድ ሰው መተኛ የሚሆን አልጋ ከመሬት በላይ ሦስት ጫማ ከፍ ብሎ ተንጠልጥሏል።

«ለዛሬ ማታ የእርሱ መተኛ የሚሆን አንድ ነገር እንድንሠራለት ተባበረኝ።»

«መልካም ኪኪ።»

ግማሽ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አልጋ ተሠራልኝ። የምግብ ገበታ አዘጋጁና እጅ የሚያስቆረጥም ሾርባ ጠጣን፣ ከዚያም ሥጋና ነጭ ሩዝ በሽንኩርት ተከተለ።

t.me/OLDBOOKSPDF

የኪኪ ጓደኛ ከሰሉን የሚሸጥለት ነበር። በደሴቷ አይኖርም፣ ስለዚህም ምሽት ሲመጣ ኪኪና እኔ ብቻችንን ቀረን።

«ዕውነት ነው። የካምቱን አዛዥ ዳከየዎች ሰርቄያለሁ። ስለዚህም ነበር በማምለጥ ላይ ያለሁት።»

የተቀመጥነው ፊት ለፊት ሆነን ስለነበር፣ ከትንሿ ምድጃ የሚነደው እሳት አልፎ አልፎ ፊታችንን ያበራዋል። አንዱ ሌላውን ለማወቅና ለመግባባት በሰሜት እየተጠናናን ነበር።

የኪኪ ፊት ሙሉ በሙሉ ቢጫ ሳይሆን፣ አብዛኛውን ፀሐይ ያበለዘው ነበር። በምንነጋገርበት ወቅት የሚንቀለቀሉት ጥቋቁር ዐይኖቹ አጥንቴን ሰርስረው ይመለከቱኛል። ከጥቁር ትምባሆ ቅጠል ራሱ የሠራውን ረጅም ሲጃራ ያጨሳል። እኔም እርሱ በሰጠኝ የሩዝ ወረቀት የጠቀለልኳቸውን ሲጃራዎች አጨሳለሁ።

«የዳከየዎቹ ባለቤት ሊገድለኝ ስለፈለገ አምልጬ መጣሁ። ይህም ከሦስት ወር በፊት ይሆናል። በጣም መጥፎው ደግሞ ዳከየዎቹን ሸፍጬም ሆነ በተጨማሪ ከከሰሉ የማተርፈውን ገንዘብ ለቁማር ማሰበላቴ ነበር።»

«የት ትጫወታለህ?»

«ጫካው ውስጥ። ከኢኒኒ የሚመጡ ቻይናዎችና ከካስኬድ ከሚመጡ ነፃ የወጡ ኢሥረኞች ጋር በየሌሊቱ ጨዋታ አለ።»

«በባሕር ለመሔድ መፈለግህን ቆርጠህበታል?»

«የማሰበው ይህንኑ ብቻ ነው። የማጠራቅመውን ከሰል ስሸጥ፣ አንድ ጀልባ ገዝቼ እርሷን የሚቀዝፍና ከእኔ ጋር መሔድ የሚሻ አንድ ሰው አፈልጋለሁ። በሦስት ሰምንት ውስጥ የምሸጠው በቂ ከሰል ይኖረኛል። ጀልባ እንዴት እንደሚቀዘፍ ዐውቃለሁ ካልከ፣ ምናልባት አንተና እኔ አብረን እንሔዳለን።»

«እኔ ገንዘብ አለኝ ኪኪ። አንተ ከሰል አስከትሸጥ ድረስ መጠበቅ አያስፈልግም።»

«ይኸማ ጥሩ ነው። አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ የምትሸጥ እንዲት ግሩም ጀልባ አለች። ሊሸጣት የሚፈልገው እዚሁ ጫካው ውስጥ አንጨት የሚቆርጥ አንድ ጥቁር ነው።»

«ጥሩ። አይተሃታል?»

«አዎ።»

«እኔም ለማየት እችላለሁ?»

«ቸኮላትን፣ እኔው የሰጠሁት ስም ነው - ነገ ሔጄ አፈልገዋለሁ። ፓፒዮ፣ ስለ ማምለጥህ ሁኔታ እስኪ ተርከልኝ። ከዲያብሎስ ማንም ያመልጣል ብየ አልገምትም።

t.me/OLDBOOKSPDF

ለምን ወንድሜ ቻንግ ከአንተ ጋር አልመጣም?»

ስለ ሲልቪያን ሞትና ስለሊሴቱ ማዕበል የማምለጥ ታሪክ ዘረዘርኩለት።

«ከአንተ ጋር ቻንግ ለምን እንዳልሔደ መገንዘብ ቻልኩ። አንድ ትልቅ ፈተና ተጋፍጠሃል። አዚህ በሕይወት በመድረስህም በጣም ዕድለኛ ነህ። ስለ ተሳካልህ ተደስቻለሁ።

ረዘም ላለ ጊዜ አወራን፣ ኪኪ በማለዳ ችኮላትን ማየት ስለፈለገ ሌሊቱን ሙሉ እንደ ነደደ እንዲቆይ አንድ ተልቅ ቅርንጫፍ በእሳቱ ላይ ተውንና ቀደም ብለን ወደ መኝታ ሔድን። ጢሱ ቢያስነጥሰኝና ቢያስለኝም አንድ ጥቅም ነበረው አንዲት ቢንቢ የለችም።

በቆጥ አልጋዬ ላይ ከሞቀው ብርድ ልብስ ሥር ተጋደምኩና ዐይኖቼን ጨፈንኩ። ግን መተኛት አልቻልኩም፣ ስሜቴ ከመጠን በላይ ተቀስቀሰ። ማምለጤ በመሳካት ላይ ነበር። ጀልባዋ ጥሩ ከሆነች በማንኛውም መንገድ በስምንት ቀን ውስጥ ባሕር ላይ እንሆናለን። ኪኪ ኮሳሳ ሰው ቢሆንም፣ ጠንካራና የማይበገር ነበር። ምናልባት በጠላቶቹ ዘንድ ጨካኝ ሆኖ ቢገመትም በጓደኞቹ ዘንድ ግልጽና ቁምነገረኛ ይመስላል። የአስያውያንን ፊት ለማንበብ ከባድ ነው - ምንም ነገር አይገልጽልህም፣ ግን ዐይኖቹ ስለ እርሱ ጥሩ አድርገው ይናገራሉ።

በመጨረሻም እንቅልፍ ወሰደኝና ፀሐይ ባጥለቀለቀው ባሕር ላይ በጀልባየ ተንጋልዬ በደስታ ወደ ነፃነት አቅጣጫ ሰመራ ሕልም አየሁ።

«የምትፈልገው ቡና ነው ወይስ ሻይ?»

«አንተ ምን ትጠጣለህ?»

«ሻይ።»

«አንግዲያ ለእኔም ሻይ ይሁንልኝ።»

ቀኑ ገና አልነጋም፣ እሳቱ አሁንም ይነድዳል፣ በብረት ድስቱ ውስጥ ውሃ እየፈላ ነበር። ከአንድ አካባቢ አውራ ዶሮ ጮኸ። እዚህ አዕዋፍ የሉም። ያራቃቸውም ጢሱ መሆን አለበት። ጥቁሯ ዐሣማ ከኪኪ አልጋ ላይ ተጋድማለች። በዕንቅልፍ ላይ ነበረች። ከሩዝ ዱቄት የተዘጋጁ ቂጣዎች በከሰሉ ላይ እየበሰሉ ነበር። አዲሱ ጓደኛዬ የሚጣፍጥ ሻይ ሰጠኝ፣ ከዚያም አንድ የሩዝ ቂጣ ለሁለት አጠፈና ማርጋሪን ለቅልቆ አቀበለኝ። እስከንጠግብ በላን። ሦስት የሩዝ ቂጣዎች አጣጥሜ ጨርሼ ነበር።

ሐንግዲህ መሔዴ ነው። ኩሬዋ ድረስ ከእኔ ጋር ና። ማንም ሰው ሲጣራ ወይም ሲያፏጭ ብትሰማ መልስ እንዳትሰጥ። ምንም አደጋ አያገኝህም። ማንም ሰው ወደዚህ መሻገር አይችልም። ግን ከታየህ ሊተኮስብህ ይችላል።»

ዓሣማዋ የጌታዋን ትእዛዝ አከበረችና ብድግ አለች። የምትበላውና

t.me/OLDBOOKSPDF

የምትጠጣውን ከጨረሰች በኋላ ሁላችንም ወደ ውጭ ወጣን። ዓሣማዋ በቀጥታ ወደ እሸዋው ማጥ አመራች። ትላንት ከተሻገርንበት ራቅ ብላ በማጡ ዳር ዳር በግምት ዐሥር ያርድ ያህል ወረደችና ከዚያም ወደ ኋላ ተመልሳ መጣች። ያንን ቦታ ብዙም አልፈለጉትውም። የሚሰማማት እስከታገኝ ድረስ ሦስት ጊዜ ደጋግማ ፈተሸች፤ ከዚያም ኪኪ ቶሎ ተከተላት።

አስኪመሽ ድረስ ኪኪ መመለስ አይችልም። ምድጃው ላይ ጥዶት ከነበረው ሾርባ ጠጣሁና ከዚያም ከዶሮዎቹ ቤት ስምንት እንቁላሎች ሰብስቤ ሦስቱን አንቁላሎች በትንሽ ማርጋሪን ጠበስኩ። ከሁለቱ ጉድጓዶች የሚወጣው ጢስ የነፋሱን አቅጣጫ ተከትሎ ይግፈጠፈጥ ነበር። ከሰዓት በኋላ ዝናም ስለጣለ አልጋዬ ላይ ጥቅልል ብየ ተጋደምኩ።

ጧት ደሴቷን አንድ ጊዜ ዞሬያት ነበር። ወደ መካከሏ አካባቢ አንድ ለጥ ያለ ሰፊ ሜዳ ነበር። ከወደቁት ዛፎችና ከተቆለሉት እንጨቶች አኳያ፣ ኪኪ ለከሰሉ እንጨት የሚያገኘው ከዚህ ቦታ መሆኑን ግንዛቤ አገኘሁ። እንደዚሁም አንድ ትልቅ ቀዳዳ ያለው ነጭ ሽክላ ነበር፤ ይህም እንጨቱ አሳት ሳይፈጥር እንዲከስል ለመሸፈኛ የሚጠቀምበት መሆን አለበት። ዶሮዎቹ በሜዳው አካባቢ ይለቃቅማሉ። አንድ ወደል አይጥ በእግሬ ሥር ሹልክ አለ፤ ከዚያም ትንሽ ያርድ ራቅ ብሎ ርዝመቱ ቢያንስ ስድስት ጫማ የሆነ አንድ የሞተ እባብ በመንገዴ ላይ አጋጠመኝ። በአይጡ ተገድሎ መሆን አለበት።

በትንሿ ደሴት ላይ በብቸኝነት ያሳለፍኩት ቀን ብዙ ግኝቶችን አሳየኝ። አንድ የምስጡ በላ (አቦልድጌሳ) ቤተሰብም አጋጠመኝ። አንዲት እናትና ሦስት ግልገሎቿ ነበሩ። አንዱን የምስጥ ኩይላ አንዳልነበር በመነቃቀር ሽበር ለቀውበታል። አሥራ ሁለት የሚሆኑ ትናንሽ ዝንጀሮዎች ደግሞ በገላጣው ሜዳ ላይ ከዛፍ ወደ ዛፍ ይዘላሉ። አንድ የጠጣ መንጋ ከእኔ ትይዩ በመሆን የሞተ ሊቀሰቅስ በሚችል ከፍተኛ ጩኸት ይጓጉራል።

ኪኪ ተመለሰ። «ቸኮላትንም ሆነ ጀልባዋን ማግኘት አልቻልኩም። ስንቁን ሊያመጣ ወደ ካስኬድ ሐዶ መሆን አለበት። ቤቱ እዚያ ነው። እስከትጠግብ በላህ?»

«አዎ።»

«አሁንስ ርቦሃል?»

«አልራበኝም።»

«ሁለት ፓኬት መናኛ ትምባሆ አምጥቸልሃለሁ። እዚያ የሚገኘው ይኸው ብቻ ነው። »

«አመሰግናለሁ። ለእኔ ሁሉም ያው ነው። ቸኮላት ወደ መንደሩ ሐዶ ምን ያህል ጊዜ ይቆያል?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ሁለት ወይም ሦስት ቀን። ግን ነገም እሞክራለሁ። ከዚያም በኋላ በየቀኑ እንደዚያው እቀጥላለሁ። የሒደው መቸ እንደሆነ አላውቅም።»

በሚቀጥለው ቀን ዝናም ጣለ፤ ግን ኪኪን ተሰሩ አላስቆረጠውም። ልብሱን በቁራጭ ላስቲክ ጠቅልሎ ከብብቱ ሥር አደረገና ዕርቃነ ሥጋውን እንደሆነ ሒደ። አበሬው አልሔድኩም። «የአንተ መበስበስ ዋጋ የለውም» አለ።

በመጨረሻ ዝናሙ አባራ። ፀሐይዋም ወጣችና አቅጣጫዋን በማየት ጊዜው በአራትና በአምስት ሰዓት መካከል መሆን እንዳለበት ገመትኩ። ከሁለቱ የከሰል ጉድጓዶች ውስጥ አንደኛው ከዝናሙ ከብደት የተነሣ ተደርምሶ ነበር። ብልሽቱን ለማየት ወደዚያው ሔድኩ። አሳቱ ሙሉ በሙሉ አልጠፋም ነበር። ከረጠበው ቁልል በላይ አሁንም ጪስ ይወጣል። ፊት ለፊቴ ባየሁት ያልታሰበ ትዕይንት ወዲያው ዐይኖቼን አሸሁ፤ አምስት ጫማዎች ወደ ላይ አፍጥጠዋል። ቀሰ በቀስ የሚጠበሱ ሦስት ሰዎች ነበሩ። ከፉኛ ተንቀጠቀጥሁ። ጎንበስ አልኩና አንድ ጉማጅ ከሰል ወደ ጎን ገፉ ሳደርግ፣ ስድስተኛውን አግር አገኘሁት።

ለካ ኪኪ ጥብቅ ሰው ኖሯል፤ መደዳውን አጋድሞ ከቀበራቸው በኋላ ወደ አመድነት ለውጧቸዋል። ወዲያው ከዚያ ተመለስኩና ወደ ገላጣውና ወደ ፀሐያማ ሥፍራ አመራሁ። ሙቀት አስፈለገኝ። በወበቁ ውስጥ እንኳ በጣም እያንቀጠቀጠኝ ነበር፤ የምታነደው የምድር ወገብ ፀሐይም አልጠቀመኝም።

አንደዚህ ከመሰለው ግኝት በኋላ አልቦታል ብላችሁ ትገምቱ ይሆናል፤ ግን መንኳለል የጀመረው ከአንድ ሰዓት በኋላ ነበር። ስለ ሁኔታው አያደር ባሰብኩ መጠን አኔም በሕይወት መቆየቴ ተአምር መሆኑን እየተገነዘብኩ ሔድኩ። እንዲያውም በጎንዘብ መደበቂያ ቱቦዬ ውስጥ ጠቅም ያለ ገንዘብ እንዳለኝ ነግሬው ነበር። አንድ ሌላ ሦስተኛ ጉድጓድ ወስጥ ሊከተኝ አየጠበቀ ይሆን?

ኪኪ አንድ ጀልባ ላይ በዘረፋና በነፍስ ግድያ ተወንጅሎ እንደነበረ ቻንግ የነገረኝን አስታወስኩ። የአርሱ ቡድኖች ጀልባ ሲመዘብሩ፣ «የፖሊቲካ» ጉዳይ ነው በማለት ያገኙትን ሰው ይገድላሉ። ስለዚህ እነዚህም ሰዎች የተገደሉት በዚያው ሳቢያ ይሆናል። ከገቡ የማይወጡበት አስቸጋሪ ጣጣ።

ኪኪን መግደል እችላለሁ፤ ከዚያ በኋላ እርሱን በተራው ወደ ጉድጓድ ወስጥ መማገድ ነው፤ ማንም ሰው መቸውንም አያውቅም። ግን ዓላማዋ ደግሞ እትታዘዘኝ፤ ስለዚህ ከደሴቱ የምወጣበት ምንም መፍትሔ አይኖረኝም። ጠመንጃ ባነሳበት ቻይናዊው ሊታዘዘኝ ይችል ይሆናል። ከዚያም አንድ ጊዜ ከደሴቷ ካወጣኝ በኋላ እርሱን መግደል አለብኝ። ወደ አሸዋው ማጥ ልወረውረው እችላለሁ፤ ይሰምጣል ሰል አስባለሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ኪኪ በአፈ ሙዙ ብቻ የሚጎርስ ባለ አንድ ቧንቧ ጠመንጃ ነበረው። ምግብ ሲያበስል እንኳ ዘወትር ከእጁ አይለየውም። የሚተኛውም ከአርሱው ጋር ነው፣ ወደ ዕዳሪ ሲወጣም ተሸክሞ ነበር። እኔም ዘወትር ጩቤዬን አዘጋጅቼ መቆየት አለብኝ፣ ሆኖም እንቅልፍ ደግሞ ሊያስፈልገኝ ነው። ከርስቶስ! ለማምለጥ ኢጋር ይሆነኛል ብየ መርጨው የነበረ ሰው! ሙሉውን ቀን መብላት አልቻልኩም። እንጉርጉሮ የሰማሁት ምን እንደማደርግ ገና ሳልወሰን ነበር። ኪኪ ወደ ቤቱ በመጓዝ ላይ ነበር። ከአንድ ዛፍ በስተጀርባ ሆንኩና ጠበቅኩት። በጭንቅላቱ ላይ የተሸከመውን አንድ ጥቅል እያደላደለ ነበር፣ ወደ ኩሬዋ ዳር ሲደርስ ታየሁት። ኩሬዋን በእኔ ትይዩ በኩል ተሻገረና በዱቄት ከረጢት የተጠቀለለውን ጓዝ ፈገግታ እያሳየ አቀብሎኝ ወደ ጎጆዋ አመራ። እኔም ተከተልኩት።

«መልካም ዜና ፓፒዮ። ቸኮላት ተመልሷል። ጀልባዋን አሁንም አልሸጣትም። ከአንድ ሺ ፓውንድ የበለጠ መሸከም ትችላለች። የሰጠሁህ ለነፋስ ሽራውና ለአቅጣጫ ማስተካከያው የሚሰፉት የዱቄት ከረጢቶች ናቸው። ይህም የመጀመሪያው ዝግጅታችን ይሆናል። አይተህ በጀልባዋ ከተማመንክባት የተረፈውን ደግሞ ነገ እናመጣለን» አለ።

ኪኪ ሲያወራ ፍጹም ዘወር ብሎ አልተመለከተኝም። የምንራመደው በነጠላ ረድፍ - ዓሣግዋ ከፊት፣ ከእርሷ ቀጥሎ እርሱ፤ ከዚያም እኔ ሆነን ነበር። ጀልባዋን ሔጄ እንድመለከታት ካማከረኝና ለማምለጡ አስፈላጊ ነገሮችን ሊያጠራቅም ማዘጋጀት ከጀመረ፣ ወደ ከሰል ጉድጓዱ ሊማግደኝ አልተሰናዳም የሚለው ሐሳብ መጣብኝ። የዱቄት ከረጢቶቹንም ሳይቀር ገዝቷል።

«ያንን ተመልከት፤ ይታይሃል! ጉድጓዱ ተሰርጉዷልሳ! በዝናሙ መሆን አለበት። በዚያ ዶፍ እንደዚህ ቢሆን አይገርመኝም።»

ወደ ጉድጓዱ አቫቅቦ ሳይሔድ፣ በቀጥታ ወደ ጎጆዋ አመራ። ምን እንደምናገር ወይም እንደማደርግ ማሰብ አልቻልኩም። ምንም ነገር አላየሁም ብየ ለማስመሰል ደግሞ አልሆነልኝም። በደሴቷ ላይ ሙሉ ቀን ስውል አንድ ጊዜ እንኳ ጉድጓዱን ለማየት አልሔድኩም ብል ቅጥ ያጣ ቀልድ ይሆናል። ከጎጆዋ ከሐያ አምስት ያርድ የበለጠ አትርቅም ነበር።

«አሳቱ ሲጠፉ ችላ አልከ እንዴ?»

«አስከዚህ ልብ ብየ አላስተዋልኩትም ነበር።»

«ምንም ነገር አልበላህም?»

«አልበላሁም። አልራበኝም።»

«ሕመም ይሰማሃል እንዴ?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አይሰማኝም::»

«ታዲያ ለምን ከሾርባው ምንም አልጠጣህም?»

«ኪኪ እሰኪ ተቀመጥ፤ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ::»

«መጀመሪያ እሳቱን ላቀጣጥል::»

«አይሆንም፣ አሁኑኑ ላናግርህ እፈልጋለሁ::»

«ምንድን ነው ነገሩ?»

«ስለ ከሰሉ ጉድጓድ ነው:: በሚሰረጎድበት ወቅት ከውስጡ ትጠበሳቸው የነበሩትን ሦስት ሰዎች አየሁ:: አንድ ማብራሪያ እፈልጋለሁ::»

«ታዲያ በዚህ ምክንያት ኖሯል እንዴ በጣም የተቀያየርከው» አለኝ ያለ አንዳች መደናገጥ በቀጥታ ወይኔን ትኩር ብሎ እየተመለከተ፣ «ሕሰደነገጠህ እንዴ? ይገባኛል:: ብትደነግጥም አያስገርምም:: ብቻ በጀርባየ ጩቢ ሳትሸጥብኝ መቅረትህም ዕድለኛ ነኝ ብየ እገምታለሁ:: ፓፒዮ፣ እነዚያ ሦስት ሰዎች ስላዮች ነበሩ:: በማምት ከወሥር ቀናት በፊት ይሆናል:: ለቸኮላት አንድ ሽከም ከሰል ሸጥኩ:: በመጀመሪያ ቀን ያየኸው ቻይናዊ ጀንያዎቹን ከደሴቷ ለማሻገር ይተባበረኛል፤ ርዝመቱ ከሁለት መቶ ያርድ በላይ የሆነ አንድ ገመድ በመያዝ በአሸዋ ማጡ ላይ መደዳውን የተቀመጡ ጀንያዎችን ሥ ጎትታለን:: ታዲያ ቸኮላት ጀልባውን ከሚያስቀምጥባት ትንሽ ወንዝና በዚህ መካከል ብዛት ያላቸው የእግር ኮቴዎች ትተን ኖሯል:: እንደዚሁም እንዳንዶቹ ጀንያዎች ተቀድደው ሰለነበር በመንገዳችን ላይ ቁርጥራጭ ከሰሎች ተንጠባጥበዋል:: ይህንንም የመጀመሪያው ሰላይ ይደርስበታል:: አንድ ሰው ጫካ ውስጥ መኖሩን በአውሬዎች ጩኸት ማወቅ አችላለሁ:: እርሱ ፍጹም ሳያየኝ እኔ አየሁት:: በአንድ ሌላ አቅጣጫ ተሻገርኩና ከኋላው መጣሁበት:: ከዚያ በኋላ በጣም ቀላል ነበር:: ማን እንደገደለው ሳያውቅ ሞተ:: ከትንሽ ቀን በኋላ ሬሣ ከአሸዋ ማጡ በላይ እንደሚንሳፈፍ ቀደም ሲል ተመልክቼ ስለነበር፣ ተሸክምኩና ወደ ከሰል ጉድጓድ ውስጥ ማገድኩት:: »

«የሌሎቹስ?»

«ያ ደግሞ የሆነው እንተ ከመምጣትህ ከሦስት ቀን በፊት ነበር:: ጫካው ውስጥ ካሁን በፊት የልተለመደ በጣም ጨለማና ፀጥታ የሰፈነበት ሌሊት ነበር:: እነዚህ ሁለቱ ከመሸ ጀምሮ ከኩሬዋ ዳር አልተለዩም:: ነፋስ ጢሱን እነርሱ ወዳሉበት አቅጣጫ ሲመልሰው ከሁለቱ በአንዱ ላይ የመሳል ዱብ ዕዳ አመጣበት:: በዚህ ምክንያት ነበር እዚያ መኖራቸውን ያወቅኩት:: ከመንጋቱ በፊት ሣሉን ከሰማሁበት ቦታ በሌላ አቅጣጫ በአሸዋው ማጥ ላይ ተሻገርኩና የመጀመሪያውን ሰው ጉረሮ ቆረጥኩት:: ኮቴ ለመስማት እንኳ ጊዜ አላገኘም:: ሌላው ደግሞ አንድ የእይን ጠመንጃ ይዞ ነበር፣ ግን ቀድሜው በአንድ ተኩስ መታሁት፤ ሆኖም አልሞተም:: ስለዚህ በጩቤዬ መጨረስ ነበረብኝ::

t.me/OLDBOOKSPDF

ፓፒዮ፣ እንግዲህ ጉድጓዱ ውስጥ ያየሃቸው ሦስቱ ሰዎች እነዚህ ናቸው። ከእነርሱ ውስጥ ሁለቱ ዐረቦች ሲሆኑ፣ ሌላው ፈረንሣዊ ነው። ይገርምሃል እነርሱን በአሸዋ ማጡ ላይ መሸከም እንደዚህ የዋዛ አልነበረም። መመላለስም ነበረብኝ።»

«በእርግጥ የሆነው ይኸው ነው?»

«ፓፒዮ፣ እምልልሃለሁ።»

«ለምን አሸዋ ማጡ ውስጥ አትቀበራቸውም ነበር?»

«ነገርኩህ እኮ፣ የአሸዋ ማጡ ሬሣ ይተፋል። አንድ ጊዜ አንዲት ወደል ኡጋዘን ሰመጠችበትና ከሳምንት በኋላ ተንሳፈፈች። በስብሶ እሰኪያበቃ ድረስ የሚያስጠላ ግማት ያመጣል። ይህ ደግሞ ረጅም ጊዜ ስለሚወስድ፣ የአሞራዎቹ ጩኸትና ማንጣበብ ተመልካችን ያስበረግጋል። ፓፒዮ፣ አምላለሁ እኔን የምትፈራበት ምንም ነገር የለም። ልብ አድርግ፣ ጠመንጃዬን ብሰጥህ ይሻልሃል?» አለኝ።

አዎ አንድል አንድ ኃይለኛ ግፊት አደፋፍሮኝ ነበር፣ ግን ተቆጣጠርኩና ቡቲቻለ መጠን በተለመደው አነጋገር፣ «አልፈልግም ኪኪ። እዚህ ያለሁት አንተ ጓደኛየ ነህ የሚል ስሜት ስላደረብኝ ነው። ግን አሳቱን አጋግለህ ሰዎቹን ነጣ አታጥለህ መጨረስ አለብህ። እኛ ከሐድን በኋላ ምን እንደሚመጣ ማን ያውቃል። ከሐድኩ በኋላም እንኳ፣ በሦስት ሰዎች ግድያ እንድከሰስ አልፈልግም» አልኩት።

«እሺ፤ ነጣ ዐመድ አደርጋቸዋለሁ። ግን አትሥጋ፣ በዚህች ደሴት ላይ ምንጊዜም ቢሆን ማንም ሰው እግሩን አያሳርፍም። በአሸዋው ማጥ ላይ ምን ቢሆን መሻገር አይችሉም።»

«የቡሽ ጀልባ ቢኖራቸውስ?»

«ስለዚያስ ፍጹም አላሰብኩበትም።»

«የደሴቷን አካባቢ ለመሰለል ፖሊሶች ከፈለጉ በቀላሉ በአንዲት ጀልባ መሻገር ይችላሉ። ለዚህም ነው በተቻለ መጠን ባስቸኳይ መንቀሳቀስ ያለብን።»

«ልክ ነህ። ጉድጓዱን ነጣ ማቀጣጠል እንጀምራለን። ከባድ አይሆንም። ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ አልጠፉም። የሚፈለገው ሁለት ማናፈሻ ቀዳዳዎች መከፈት ብቻ ነው። »

«ደህና አደር ኪኪ።»

«ደህና አደር ፓፒዮ። በደንብ ተኛ፣ ልታምነኝ ይገባሃል፣ ዕውነቴን ነው።»

ብርድ ልብሴን አገጨ ድረስ ሳብከና አንድ ሲጃራ አጨስኩ። በዐሥር ደቂቃ ውስጥ ኪኪ ዓሣማውን ከጎኑ አድርጎ በረጅሙ ያንኮራፋል። ምድጃው ጠፍቶ ነበር፤ ነፋሱ በጎጆዋ ውስጥ ሲነፍስ የሰላምና የዕርጋታ ስሜት ሰጠኝ። አሸለብኩ። ግን አንድ ሃሳብ በአእምሮየ ይጉላላል፣ ነጣ ከእንቅልፌ ስነቃ በቻይናዊውና በእኔ መካከል ሁሉም

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገር እንዳማረ ይሆናል ወይም አንድ መዓተኛ አስገራሚ ድርጊት ይፈጸማል። በጣም ብዙ ነገሮችን ስለአወቅሁበትና ይህም ጤና ስለሚነሣው ከአንግዲህ ፀሐይን ዳግመኛ አላያት ይሆናል።

በጅምላ ነፍስ ግድያ የሠለጠነው ባለሙያ ከአንቅልፌ ቀሰቀሰኝና ምንም ነገር አንዳልሰራ ሁሉ ከሞቀ ልባዊ ፈገግታ ጋር አንድ ኩባያ ቡና አቀበለኝ። ፀሐይዋም ቀደም ሲል ወጥታ ነበር።

«ና፣ ትንሽ ቡናና የሩዝ ቂጣ ውሰድ።» ማርጋሪን በላዩ ላይ ተደርጎበታል።

ቁርሴን አደረግሁና ከዚያም ዘወትር እንደሞላ ከሚቀመጥ አንድ በርሜል ውሃ ቀድቼ ታጠብኩ።

«አንድ ጊዜ ትተባበረኝ ፓፒዮ?»

ምን እንደሆነ ሳልጠይቅ «በደስታ» አልኩት።

በከፊል የተጠበሱትን አስከሬኖች አግሮቻቸውን እየያዝን ጎተትናቸው። ሆድ ዕቃቸው ተዘረጋግፏል። ርኅሩኑ ቻይናዊው ምናልባት የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ አላቸው ብሎ በረቃቅኗቸው መሆን አለበት። በእውነት ኪኪን እያደኑት ኖሯል? ኢጋዘኖች ማደኑ አይቀላቸውም ነበር? የገደላቸው ከመከላከል ውጭ ሆነውበት ይሆን፣ ወይስ ሊመዘብራቸው? ስለዚህ ጉዳይ ይብቃን። በተረበረቡ አንጨቶችና በሸክላ ዘሚገባ ተሸፍነው ወደ ጉድጓዱ ተመለሱ። ኪኪ ሁለት የነፋስ መከፈቻ ቀዳዳዎች ገላለጠና ጉድጓዱ እንደገና ሁለት ተግባሮችን፣ ማለት ከሰል የማከሰልና ሦስት አስከሬኖችን ወደ ዐመድነት የመለወጥ ሥራ ሊያከናውን ተቀጣጠለ።

«አንብሒድ ፓፒዮ።»

አሣማዋ ጊዜ ሳትፈጅ መሻገሪያ አገኘችልን። የአሸዋ ማጡን በነጠላ ረድፍ ተጠጋግተን በመከታተል ተሻገርን። በመጀመሪያው እርምጃ የሚዘገንነው ያ ፍርሃት ተመልሶ መጣብኝ። የሲልቪያን ጽዋ በእኔም ይደርስ ይሆን እንዴ? በቀዝቃዛ ላብ እንደ ተዘፈቅኩ የእግሮቼን ኮቴ በማስተካከል ከኪኪ ኋላ ተከተልኩ። ለማንኛውም እርሱ ወደ ታች ከወረደ ለእኔም እንደዚያው ነው።

ከሁለት ሰዓት ጉዞ በኋላ ቸኮላት አንጨት ይቆርጥበት ወደነበረው ቦታ ደረስን።

«ሰላም ወዳጄ።»

«ሰላም ኪኪ።»

«እንዴት ነህ?»

«ደህና።»

«ጀልባዋን ለጓደኛየ አሳየው።»

t.me/OLDBOOKSPDF

የጭነት የምትመስል በጣም ጠንካራ ጀልባ ነበረች። ከባድ ነች። አትበገርም። ጩቤየን በየቦታው ተከልኩባት። ከሩብ ሊንች የበለጠ ፍዱም ጠልቆ አልገባም። ወለሏም እንደዚሁ እንከን የማይወጣለት ነበር። ጀልባዋ የተሠራችው ከአንደኛ ደረጃ እንጨት ነበር።

«ስንት ነው የምትሸጣት?»

«ሁለት ሺ አምስት መቶ ፍራንክ።»

«ሁለት ሺ ልክፈልህ።»

«ውሰዳት።»

«አንድ ወለል ያስፈልጋታል። አንድ ወለል፣ መሪና የነፋስ ሸራ መስቀያ ምሰሶ ከጨመርክልኝ ሌላ አምስት መቶ እከፍላለሁ። ወለሉ ከጠንካራ እንጨት መሆን አለበት፤ መሪውም እንደዚያው ነው። የነፋስ ሸራ መስቀያ ምሰሶው ከፍታ ዐሥር ጫማ ሆኖ ከቀላልና አረግራጊ እንጨት እንዲሆን እፈልጋለሁ። እስከ መቼ ድረስ ልታዘጋጅ ትችላለህ?»

«በስምንት ቀን ውስጥ።»

«የሁለት ሺ ፍራንክ ኖትና አንድ ባለ አምስት መቶ ይኸው ይግባለሁ። ሁለት ሺውን አሁኑኑ እንካ። ቀሪውን ጀልባዋን ስታስረክበኝ እሰጥሃለሁ እሺ?»

«እሺ።»

«አንድ በርሜል ውሃ፣ ጥቂት ፐርማንጋኒት፣ ሲጃራና ከብሪት፣ ለአንድ ወር ለእራት ሰዎች የሚበቃ ምግብ ማለት፣ ዱቄት፣ ዘይት፣ ቡናና ስኳር እፈልጋለሁ። ለእነዚህ በተሰይ እከፍላለሁ። ማንኛውም ጉዳይ ተጠናቅቆ በኩሩ ወንዝ መረከብ እፈልጋለሁ። »

«ጓደኛዬ፣ እኔ ወንዟ አፍ ድረስ ከአንተ ጋር ልሔድ አልችልም እኮ?» አለ ኪኪ።

«አንተን ትሔዳለህ ብየ አልጠየቅኩም። እርሱ ጀልባዋን ከወንዙ ድረስ ወስዶ ያስረክበኝ ነው ያልኩት።»

«አኘሁልህ፤ እነዚህን የዱቄት ከረጢቶች ከገመዶቹ፣ ከመርፌና ከሩ ጋር ውሰድ።»

ከመምሸቱ በፊት በጣም ቀደም አልንና ወደ መሸሸጊያ ቤታችን ተመለስን፤ ግን ዐሣማዋ በጣም ስለ ደከመች ኪኪ መሸከም ግዴታ ሆነበት።

በሚቀጥለው ቀን ብቻየን ሆኜ የነፋስ ሸራውን በመስፋት ላይ እንዳለሁ ነበር ድንገት አንድ ድምፅ የሰማሁት። ወደ አሸዋ ማጡ አቅጣጫ አመራሁና ተደብቄ በስተግዶ ምን እንደሚደረግ መመልከት ያዝኩ። እጆቻቸውን በአየር ላይ እያወራጩ

t.me/OLDBOOKSPDF

.የጋለ ከርከር የሚያደርጉት ኪኪና ቫን ሁዊ ነበሩ። ቫን ሁዊ ወደ ደሴቷ ለመምጣት እየፈለገ ኪኪ ግን፣ እንዳይመጣ እየከለከለው መሆኑ ገባኝ። ሁለቱም ገጀራዎቻቸውን ተማዝዘው ነበር፤ ኪኪን ብቻ እንዳይገድልብኝ እንጂ!። ብቅ ብዬ አንድ ቱጩት ሳለማ ወደ እኔ አቅጣጫ ዞሩ።

«ምንድነው ጉዳዩ ኪኪ?»

ቫን ሁዊ ተናገረ። «ከአንተ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ ፓፒዩ፤ ኪኪ ግን አልፈቅድልህም አለኝ።»

ከአንድ ሌላ የዐሥር ደቂቃ ውይይት በኋላ፣ ዓሣማዋ ስትንቀሳቀስ አነርሱም ተነሡ። ሻይ በኩባያ አንደ ጨበጥን ጎጆዋ ውስጥ ቀመጥንና መነጋገር አስኪጀምሩ ጠበቅኳቸው።

«ችግሩ እንደዚህ ነው» አለ ኪኪ። «ከእኛ ጋር አብሮ ሊሔድ ይፈልጋል። የከፈልከባት አንተ አስከሆንክ ድረስ ሙሉ ኃላፊነት ስላለህ እኔን አያገባኝም ብየ ገለጽኩለት፤ ግን ማመን አልቻለም።»

«ፓፒዮ» አለ ሌላው ሰው ደግሞ፣ «ሊወስደኝ ይገባዋል።»

«ለምን?»

«ከሁለት ዓመት በፊት በአንድ የካርታ ጨዋታ ላይ አለመግባባት ተፈጥሮ ከንዴን ቆረጠኝ። እንዳልገድለውም አስምሎኛል። በአንድ ድርድር ተስማማሁ፤ ይኸውም እኔ እስከ ፈለግኩበት ጊዜ ወይም በሕይወት እስካለሁ ድረስ ሊመግበኝ ነበር። አሁን አሔዳለሁ ካለ ዳግመኛ አላገኘውም። ስለዚህ ወይ አንተ ብቻህን እንድትሔድ ይፍቀድልህ፤ አለበለዚያ ከእርሱ ጋር ይውሰደኝ።»

«ይኸ ደግሞ የጉድ ነው! ሰማ፤ አብረኸን መሔድ ትችላለህ። ይህች ጀልባ ትልቅና በጣም ጠንካራ ስለሆነች ተጨማሪ ሰዎችን እንኳ መያዝ እንችላለን። ኪኪ እሺ ካለህ በእኔ በኩል እሺ።»

«አመሰግናለሁ» አለ ቫን ሁዊ።

«አንተ የምትፈልግ ከሆነ፤ እሺ።»

«አንድ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ አለ። ጠፍቷል ተብሎ ሪፖርት ሳይቀርብብህ ካምፑን መልቀቅና ከመምሸቱ በፊት ወደ ወንዙ ልትደርስ ትችላለህ?»

«ምንም ችግር አይኖርም። ከዘጠኝ ሰዓት በኋላ በማንኛውም ጊዜ ብነሣ ሁለት ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ወደ ወንዙ መድረስ እችላለሁ።»

«ኪኪ፣ ቦታውን በጨለማ ልታውቀው ትችላለህ? ብዙ ጊዜ ሳናባክን ጓደኛህን ወደ ጀልባዋ ልናሳፍረው እንድንችል?»

«በሚገባ፤ ለዚህ ችግር የለም።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከአሁን ወዲያ አንድ ሳምንት ቆይተህ እዚሁና፤ መቸ እንደምንሔድ እንነግርሃለን።»

ቫን ሁዊ ሞቅ አድርጎ እጇን ጨበጠና በፍንደቃ ስሜት ተውጦ ሔደ። ኩሬው ዳር ደህና ሁን ሲባባሉ ተመለከትኳቸው። ከመለያታቸውም በፊት እጅ ለእጅ ተነካኩ። ስለዚህ ሰላም ነበር።

ኪኪ ወደ ጎጆዋ ተመልሶ ሲመጣ፣ «ከጓደኛህ ጋር ያደረግከው ውል ታይቶ፣ ተሰምቶ የማይታወቅ ነው፤ ዕድሜውን በሙሉ ልትመግበው መስማማት። እንተስ ለምን ከንዱን ቆረጥከው?» አልኩት።

«በካርታ አከፋፋይነት ምክንያት በተነሣ ጠብ ነበር።»

«ብትገድለው አይሻልም ነበር እንዴ?»

«አልፈለግሁም። በጣም የቅርብ ጓደኛየ ነው። ወደ ልዩ ፍርድ ቤት በቀረብክበት ወቅት እንኳ በማንኛውም መንገድ ተከላከሎልኛል። እርሱ መጀመሪያ አጥቅቶኝ እኔ ራሴን ለመከላከል ስል የፈጸምኩት ድርጊት እንደሆነ ቃሉን ሰጠ። ውሉን የተስማማሁት በራሴው ነፃ ፍላጎት ስለሆነ በዚሁ እንደጸናሁ አገፋበታለሁ። ስለዚህ ጉዳይ ልነግርህ አልደፈርኩም።

«ነፃ ስትወጣ ምን ለመሥራት ዕቅድ አለህ?»

«አንድ ሆቴል ቤት ለመክፈት እፈልጋለሁ። ጥሩ ወጥ ቀቃይ ነኝ፤ ቫን ሁዊም በቾው ሜይን (የቻይናውያን የባህል ምግብ) ሙያ የተካነ ነው።»

ቸኮላት ቃሉን የሚያከብር ጥሩ ሰው ነበር። ከአምስት ቀን በኋላ ሁሉም ነገር ተሰናዳ። በዶፍ ወስጥ ጀልባዋን ለመመልከት ሔድን። የነፋስ ሽራ መስቀያው ምሰሶ፣ መሪውና ወለሉ በአንደኛ ደረጃ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ተገጣጥመዋል። በርሜል ውሃና በጠቅላላው የስንቅ ከምችቱን እንደያዘች ጀልባዋ በአንድ የወንዝ ጠመዝማዛ ዳርቻ ላይ ታብታለች። የቀረ ነገር ቢኖር ወደ ቫን ሁዊ መልዕክት ማስተላለፍ ብቻ ነበር። ቸኮላት ራሱ ወደ ካምፕ ሔዶ ሊቀሰቅሰው ፈቃደኝነቱን ገለጸ። ከወንዙ ዳር ቢሣፈር የሚያመጣውን አደጋ ለመከላከል ሲባል፣ በቀጥታ ወደ እኛ መሸሸጊያ ቦታ ሊያመጣው ነው።

የኩሩ ወንዝ አፍ በሁለት የመብራት ምልክቶች ተለይቶ ነበር። ዝናም ከዘነመ የነፋስ ሽራ በመሰቀል አደጋ ላይ ሳንወድቅ ወደ ወንዙ መካከል በሰላም መውረድ እንችላለን። ቸኮላት አንድ ብሩሽና ትንሽ ጥቁር ቀለም ሰጠን። በነፋስ ሽራው ላይ ቁጥር 21 በትልቁ ልንጽፍ ነበር። አንዳንድ ጊዜ በሌሊት በዚያ የምትመላለስ የዚህ ዓይነት ምልክት ያላት አንዲት የዓሣ አጥማጅች ጀልባ ነበረች። የነፋስ ሽራችንን እንደ ሰቀልን ወደ ባሕር ስንገባ ማንም ሰው ቢያየን የሚመስለው የዓሣ አጥማጅች ጀልባ ነች ብሎ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነው።።

ለመነሳት የተወሰነው፤ ከመሸ በኋላ አንድ ሰዓት ላይ ነበር። ወደ መሸሸጊያው ቦታ የምትወስደንን መንገድ ማግኘት እንደሚቻል ኪኪ አረጋገጠልኝ። ለጉዞ የሚሆነን የአንድ ሰዓት የቀን ብርሃን አንድናገኝ ደሴቷን ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ እንለቃለን።

በከፍተኛ ሞራል ተሞልተን ወደ ጎጇችን ተመለስን። ኪኪ ዓሣማዋን በትከሻው እንደ ተሸከመ ከፊት ለፊቴ ይጠሠሣል። ወሬ ከማነብነብ በቀጹም አላባራም።

«አንግዲህ አሰቃቂውን የቅኝ ግዛት ወሀኒ ቤት መልቀቂ ነው። ለአንተና ለወንድሜ ምስጋና ይግባችሁና መጨረሻ ላይ መውጣቴ ነው። ምናልባት ፈረንሣይ ጋግሞ ኢንዶቻይናን ብትለቅ፣ ወደ ራሴው ሀገር ለመመለስም እችል ይሆናል።»

እምነቱን በእኔ የጣለ ይመስላል፤ ጀልባዋን ከልብ ስለ ወደድኳት ፈንድቄል። እኔም እንደዚሁ የደስታ ሲቃ ያዘኝ። በዚያች ደሴት ላይ የመጨረሻየን ሌሊት እያሳለፍኩ ነበር፤ በጊያናም የመጨረሻዬ ሌሊት እንደሚሆን ተሰፋ አለኝ።

ወደ ሰፊው ባሕር መድረስ ከቻልኩ፣ ነፃ እሆናለሁ። አጠያያቂነት የለውም። ከዚያ በኋላ ያለው ብቸኛ አደጋ የጀልባ መሰባበር ቢሆን ነው። ጦርነቱም በጅቶ ስለነበር ካመለጠ በኋላ የተመለሰ አንድም ወንጀለኛ የለም። ይሁንና ከተያዝን ደግሞ የሞት ቅጣት እንደሚፈረድብን ነው። ሲልቪያንን አስታወስኩ። ያ ዝቃጭ ባይውጠው ኖሮ አዚሁ ከእኔ ጋር በሆነ ነበር። አንድ የቴሌግራም መልዕክት አቀነባበርኩና አሸለብኩ። « ለዐቃቤ ሕግ ፕራደል- አንተ ከላከኝ ገሃነም አሳት ውስጥ ለመጨረሻ ጊዜ በአስተማማኝ ሪ·ኔታ አምልጫለሁ። ለዚህም ዘጠኝ ዓመታት ወስዶብኛል።»

ኪኪ ሲቀሰቅሰኝ ፀሐይዋ ከፍ ብላ ነበር። ሻይና የሩዝ ቂጣ ቁርስ አደረግን። በየበታው ጣሳዎች ወዳድቀው ነበር። ሁለት የቅርጫት ዘምቢሎች ተመለከትኩ።

«ምን ልታስቀምጥባቸው ነው?»

«ዶሮዎቹን። በማምለጥ ላይ እንዳለን ልንበላቸው አንችላለን።»

«አብደሃል እንዴ ኪኪ! አንድም አንወስድም።»

«እኔ ግን መውሰድ እፈልጋለሁ።»

«አምሃል ልበል? ጠራራ ሲሆን ምን እንደሚደርስባቸው ገምግመሃል?» «ያለ ዶሮቼ መሔድ አልፈልግም።»

እንግዲያው ደህና። አሁኑኑ ቀቅልና በዘይት አሽጋቸው። እንደዚያ ከሆኑ እንዳይበላሹ ይረዳል። ከወጣን በኋላ ባሉት ሦስት ቀናት ውስጥ እንበላቸዋለን።»

በዚሁ ተስማማና ዶሮዎቹን ሊፈልግ ወጥቶ ሐደ። ግን በቅድሚያ የያዛቸው የአራቱ ጫጫታ ለሌሎቹ ማስጠንቀቂያ ሳይሆን አልቀረም። በጫካው ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

ተሰማው። ተጨማሪ መያዝ አልቻለም። እንስሳዎች የአደጋን ጠረን
እንዲት ሀሳቡ ለእኔ ምስጢር እንደ ሆነብኝ ነው።
ኢላህ ተጭነን ከዓሣማዋ ኋላ በመከተል የአሸዋ ማጡን ተሻገርን።
ዓሣማዋ እንድትሔድ እንድፈቅድለት ኪኪ ለመነኝ።
እንደሚ ድምፅ አታሰማም?»
ነበር። አደርጊ ብየ ከነገርኳት ጭጭ ትላለች። ሁለት ጊዜ ነብር
ሲያባርረ የተነሣ ጸጉሯ ቁጥ ብሎ ቆመ እንጂ ምንም ድምፅ
አላሰማች
ስለዚህ የሚንሰፈሰፍላትን ጓደኛውን ለመውሰድ ተስማማሁ።
ጀልባዋ ሥፍራ በምንደርስበት ወቅት መሸቷል። ቸኮላትም
ከሻን ነበር። ማንኛውም ነገር ተስተካከለ እንደሆነ ለማረጋገጥ
በሁለት ነቅቷል። ምንም የጎደለ ነገር የለም። የነፋስ ሽራ ቀለበቶቹ
በምሰሶ ላለ ሦስት ማዕዘን ሸራውም ለመዘርጋት ተዘጋጅቶ
በቦታው ሦስት ሰዓታም ሦስት ጊዜ አያገለባበጠ እንዲሞከር አድርጌው
ነበር። ቋሚ ከፈለክ፤ አመርቂ ተግባር አከናውኗል። ሰውን
አማኝ የመሣሪ ማጠቢያና ኖቶች አምጥቶ እንዳጣብቅለት
ጠየቀኝ ኃይሌ ሊሔድ ይችል ይሆናል የሚል ሐሳብ ፍጹም
አልመሰ የሚያምኑ ራሳቸውም ታማኞች ናቸውና፣ ቸኮላት መልካም
ሰው ነበ እንደሚንላቱ ተመልክቶ ስለነበረ፣ ያን ገሃነመ እሳት
እንደ ፈሰኖት አልተሰማውም። «ደህና ሁን ቸኮላት። ለአንተና
ለቤተሰ ሳት።»
ሁላችም አሰላናፍስሁ።»

t.me/OLDBOOKSPDF

ዐሥራ አንደኛ ማስታወሻ

ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መሰናበት
ከቻይናውያኑ ጋር ማምለጥ

ወደ ጀልባዋ ውስጥ ለመግባት የመጨረሻው ነበርኩ። ኃይለኛ ግፊት ሰጣትና ወደ ወንዙ ገብታ ወዲያው ተንቀሳቀሰች። ያለው ከፊት ኪኪ፣ በኋላ በኩል ያለነው ደግሞ እኔና ቫን ሁዊ ነበርን።

እየዘነበ ነበር። ለዝናም መከላያ የሚሆን የዳቄት ማዕበሉ ፈጣንና አዙሪት የሞላበት ነበር፤ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ደረስን። የወንዙን አፍ መለያ መብራቶች ከሦስት ሰዓት በኋላ አለፍን። አፍ ላይ በመሆናቸው ባሕሩ ቅርብ መሆን እንዳለበት ሸራውን ዘረጋንና ከመቅዕበት ኩሩን ወጣን። ነፋሱ ባለው ኃይል ወደ ስለሆነ ሸራውን ማውረድ ነበረብኝ። እንደ ቀስት ተስፈንጥረን ከባሕሩ ወዲያው ከጠረፉ ዳር ርቀን ወጣን። ሐያ አምስት ማይል ከዘለቅን በኋላ የአደጋ ማስጠንቀቂያ መብራት አቅጣጫችንን ለማስተካከል ረዳን።

ከዐሥራ ሦስት ቀናት በፊት ከዚያ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ባሻገር በዲያብሎስ ላይ ቆሜ ነበር።

በማንኛውም መንገድ ወደ ባሕር መውጣታችን ቱሬም ፈጥኖ ወደ ኋላችን ርቆ በመቅረቱ ቻይናውያኑ ጓደኞቼ ደስታ ሰማሳል። እነዚህ ከሌላ ዓለም የወረዱ የሚመስሉ ሰዎች እንደኔ ፋንታ ስሜቶቻቸውን ይደብቃሉ። ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ሰፈው ባለሥ ኪኪ ለዘብ ባለ ድምፅ፣ «ጥሩ አጀማመር ነው» ሲል፤ «አዎ፤ በአሳሳቅ መጣነው፤» በማለት ቫን ሁዊ ጨመረበት።

«ኪኪ፣ ጠምቶኛል። እስኪ አንድ ጉንጭ ሩም ጠብ እያ ቀዱልኝና፣ ለእነርሱም አንዳንድ ደህና ጉንጭ ከለበሱ። ግን በመጀመሪያው ማምለጫ ወቅት በፀሐይዋ፣ በጨረቃዋ በነፋሱ አቅጣጫ፣ የባሕርን መስመር መቀየስ ለምጄ ነበር። የፖላሪስን መስመር ያዝኩና በቀጥታ አመራሁ። ጀልባዋ፣ ሁኔታ ያለአንድ ችግር ታልፋለች። ነፋሱ ኃይለኛ ስለሆነ ሱሳሊዩ ደሴቶች ረጅም መንገድ ርቀን ነበር። ወደ ዲያብሎስ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነበር፤ ግን ለአደጋ መጋለጥ ይሆናል ብዬ ተውኩት።

ለስድስት ቀናት መጥፎ አየር ገጥሞን ነበር፤ ይሁንና ዝናብም ሆነ ውሽንፍር የለም። አንድ ኃይለኛ ነፋስ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እንድናመራ ሳያቋርጥ ገፋን። ኪኪና ቫን ሁዊ ነበዝ አጋሮች ነበሩ፤ ስለ አየሩ ጠባይ ቀርቶ፣ ስለ ፀሐይዋ ወይም ስለሌሊቱ ቅዝቃዜ ፍጹም ቅሬታ አያሰሙም። ብቸኛው ድክመታቸው የትንሽ ሰዓት ዕረፍት እንዳገኘ ከሁለቱ አንዳቸውም መሪውን አለመያዛቸው ነበር። በቀን ሦስት ወይም አራት ጊዜ ምግብ ይቀቅላሉ። ዶሮዎቹን በሙሉ በላናቸው። አንድ ቀን ለቀልድ ያህል፣ «ዓሣማዋን የምንበላት መቼ ነው?» አልኩት ኪኪን። አእምሮውን ሊስት ነበር።

«ይህች እንስሳ ጓደኛየ ነች። አስቀድመህ እኔን መግደል አለብህ» አለ።

በማንኛውም ወቅት ጓደኞቼ ሥራ ይበዛባቸው ነበር። ዘወትር የተዘጋጀ ትኩስ ሻይ አለ። ማንኛውንም ነገር የሚሠሩት ሳላዛቸው ነበር። ትምባሆው በሙሉ ለእኔ እንዲሆን በማለት ማጨስ እንኳ ትተዋል።

አሁን ለሰባት ቀናት ተጉዘናል። ሕሊናየን ለመሰት ምንም አልቀረኝ። ፀሐይዋ በጣም ከመጋሏ የተነሣ ቻይናውያኑም ተጠበሱ። ለእንድ አፍታም ቢሆን እንቅልፍ ማግኘት ነበረብኝ። ፍጥነት ጨመርኩና የነፋስ ሽራውን በመጠኑ ከፍ አድርጌ ተውኩት። ጀልባዋ ነፋሱ በሚገፋን በየትኛውም አቅጣጫ ትሔዳለች። ልክ የሞትኩ መስየ አራት ሰዓት ያህል ተኛሁ። ከእንቅልፌ ያባነነኝ፣ ከተለመደው ጠንከር ያለና በድንጋጤ እንድነሣ ፊቴን ጥብ ያደረገኝ ድንገተኛ ጥሬ ነበረ። እንቅልፍ እንደ ወሰደኝ ጂሜን ተላጭቻለሁ። የላጨኝ ኪኪ ሲሆን፤ ምንም አልተሰማኝም። ለዚሁ ብሎ ፊቴን በቅባት ለቅልቆኝ ነበር።

ወደ ሰሜን አቅጣጫ በጣም ርቄ መሔዴን ስለ ገመትኩ፤ ካሰፈው ሌሊት ጀምሮ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫስ አመራሁ። ሆኖም መላ ምት ሒሳብ በምቀምርበት ወቅት እንደተገነዘብኩት ለካስ መስመራችንን ስተን ወዳልታወቀ አካባቢ ሔደናል።

ድንገት ወደ ሰማይ ቀና ስል፤ አንድ አውሮፕላን ተመለከትኩ። ወደ እኛ አቅጣጫ የሚመጣ አይመስልም፤ መጠኑንም ለመገመት በጣም ሩቅ ነበር። በአሉሚኒየሙ ላይ የሚያርፈው የፀሐይ ነጸብራቅ በጣም ስለሚያበለጨልጭ ያንን መመልከት ያሳምማል። ጥቂት ቆይቶ ደግሞ በቀጥታ ወደ እኛ ለመምጣት መስመሩን የቀየረ መሰለ። እየቆየ ይጠጋን ጀመር ፤ ሐያ ደቂቃ በማይሞላ ጊዜ ውስጥ በቀጥታ ከበላያችን ሆነ። ኪኪና ጓደኛው በጣም ተጨንቀው በድንጋጭቸው ያለማቋረጥ መቅባጠራቸውን ቀጠሉ።

«ስለ ከርስቶስ ብላችሁ በፈረንሣይኛ ተናገሩ፤ የምትሉትን መረዳት እንድችል»

«የመንገደኞች አውሮፕላን ነው» አለ ኪኪ።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አይደለም። የስለላ አውሮፕላን መሆን አለበት።»

አከሮባት በመሥራት ከበላያችን እየደጋገመ በመዞር ዝቅ ይል ጀመር። ለምልከት የሚሆኑ ባንዲራዎች ታይተውን ነበር። ግን ስለ ባንዲራ ፍች ምንም የምናውቀው ነገር ስለሌለን አፀፋውን መመለስ አልቻልንም። አውሮፕላኑ የሚተወን አልሆነም፣ ከመቸውም ይበልጥ እየቀረበን መጣ። በጣም ከመቅረቡም የተነሣ በውስጡ የተቀመጡትን ሰዎች ማየት ቻልን። አንድ ሌላ አውሮፕላንም መጥቶ እየደጋገመ በላያችን ላይ አንዣበበ።

በድንጉት ነፋሱም ተነሣና ባሕሩ ይናወጥ ጀመር። ግን አድማሱ በሁሉም አቅጣጫ የጠራ ስለሆነ የገዘናም አደጋ አልነበረም።

«ተመልከት!» አለ ቫን ሁዊ።

«ወዴት?»

«አዚያ ወዲያ። በእኛና መሬት በሚመስለው ቦታ መካከል ያለው ያ ነጥብ። ያ ጥቁር ነጥብ ጀልባ ነው።»

«አርግጠኛ ነህ?»

«ያወቅኩት ጀልባነቱን ብቻ ሳይሆን ፈጣን የጦር ጀልባ መሆኑንም ልነግርህ እችላለሁ።»

«እንዴት ዐወቅክ?»

«ምክንያቱም የሚወጣ ጢስ የለውም።»

አንድ የጦር መርከብ በቀጥታ ወደ እኛ በማምራት ላይ እንደሚገኝ ያለጥርጥር ግልጽ የሆነልን ከአንድ ሰዓት በኋላ ብቻ ነበረ። በተለየ ፍጥነት እየተንቀሳቀሰ በየደቂቃው አድጎ ይታያል። በጣም ከቀረበን በዚህ ከባደ ባሕር ውስጥ አደገኛ ይሆናል። ማዕበሎቹን እየሰነጠቀ ሲያልፍ በቀላሉ ሊያስምጠን ይችላል።

አነስተኛ የጦር ጀልባ ነበር። እየቀረበ ሲመጣ በጎኑ በኩል «ታርጋን» የሚል ጽሑፍ ማንበብ ከመቻላችንም ሌላ ከፊት በኩል የእንግሊዝ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሏል። በግማሽ ከብ ከዞረን በኋላ፣ ዝግ አያለ ከኋላ በኩል መጥቶ በጥንቃቄ በጎናችን ቆመ። የእንግሊዝ የባሕር ኃይል አባላት ሰማያዊ ዩኒፎርማቸውን እንደለበሱ በወለሉ ላይ ቆመዋል።

አንድ መኮንን በአንድ ድምፅ ማጉሊያ በእንግሊዝኛ ቋንቋ፣ «ቁሙ! እናንተ፣ ቁሙ!» ብሎ ጮኸ።

«ኪኪ፣ የነፋስ ሸራዎቹን አውርድ!»

ሁለት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዋናውን የነፋስ ሸራ፣ ባለ ሦስት ማዕዘኑን ሸራና የአቅጣጫ ማስተካከያውን ሸራ አወረድን። አሁን የሚያንቀሳቅሱን ማዕበሎቹ ብቻ

t.me/OLDBOOKSPDF

ስለሆኑ ወደ ጎን ለመንሸራተት ይቃጣን ጀመር፣ በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ቆየን።

እጆቼን በአፌ ዙሪያ ከበብኩና፣ «ካፕቴን ፈረንሣይኛ ትናገራለህ?» ብየ ጮህኩ።

ድምፅ ማጉሊያውን አንድ ሌላ መኮንን ተቀብሎ፣ «አዎ ካፕቴን፣ ፈረንሣይኛ ይገባኛል» አለ።

«ምን አድርጉ ነው የምትሉን?»

«ጀልባችሁን አስጠጉ።»

«አናስጠጋም፤ በጣም አደገኛ ነው። እንጋጫለን።»

«ለጥበቃ የምነዘዋወር የጦር መርከብ ተቆጣጣሪዎች ነን። መታዘዝ አለባችሁ።»

«ምንም ብትሆኑ ጉዳዬ አይደለም። እኛ ከማንም ሰው ጋር ጦርነት አልገጠምንም።»

«ከአንድ የተደበደበ መርከብ የተረፋችሁ አይደላችሁም እንዴ?»

«አይደለንም፤ እኛ ከፈረንሣይ የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ያመለጥን እሥረኞች ነን።»

«የምን ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት? የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ምን ማለት ነው?»

«አስር ቤት፤ ጠባይ ማረሚያ። ወንጀለኞች ነን። ዕድሜ ይፍታህ የተፈረደብን።»

«አሃ! አዎ፤ አሁን ገባኝ። ከካየን ነዋ?»

«አዎ፤ ከካየን።»

«ወዴት ነው የምታመሩት?»

«እንግሊዝ ሆንዱራስ።»

«አይቻልም። ወደ ደቡብ ምዕራብ አምርታችሁ የጆርጅ ታውንን አቅጣጫ መያዝ አለባችሁ። ትእዛዝ ነው። ማክበር አለባችሁ።»

«አሺ።»

ኪኪ የነፋስ ሽራ እንዲሰቅል ነገርኩና ወደ ተመለከትነው አቅጣጫ አመራሁ።

ከኋላችን አንድ ሞተር ሰማን። ከትልቁ የጦር ጀልባ የወጣች አንዲት ባለሞተር ጀልባ ወደ እኛ ለመድረስ እየገሠገሠች ነበር። ጠመንጃ በትከሻው ያነገተ አንድ መርከበኛ ከፊት በኩል ቆሟል። ጀልባዋ በስተቀኞችን በኩል መጣችና ሳትቆም ወይም እኛ አንድንቆም ሳትጠይቅ ታከከችን። መርከበኛው በአንድ እመርታ ዘልሎ ወደ እኛ ጀልባ ወጣ። ከዚያም የሞተር ጀልባዋ ወደ ኋላ ተመለሰችና ከጦር ጀልባዋ ጋር

t.me/OLDBOOKSPDF

ተቀራኘች።

«እንደምን ዋላችሁ?» አለ መርከበኛው በእንግሊዝኛ ቋንቋ።

ከጎኔ መጥቶ ተቀመጠና ጀልባዋን ወደ ደቡብ ትንሽ ጨመር አድርጎ ለማስተካከል እጁን በመሪው ላይ አሰቀመጠ። በጥንቃቄ ተመለከትኩት። ጠጋ ብዬው ተቀመጥኩ። የሚሆነው ፍጹም አይታወቅምና፤

«ሲጃራ?» አለና ሦስት ፓኬት የእንግሊዝ ሲጃራዎች አውጥቶ ለእያንዳንዳችን አንዳንድ ሰጠን።

«ዕውነት አላችኋለሁ» አለ ኪኪ፣ «ዘልሎ ሲወርድ ሦስቱንም ፓኬቶች ሰጥተውት መሆን አለበት እንጂ ይኸ ሁሉ በኪስ ተይዞ አይዞር።»

ሳቅኩና ከእኔ የተሻለ መርከበኛ ወደሆነው እንግሊዛዊ ትኩረቴን መለስኩ። እስምሮዬ ነፃ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ማምለጡ በትከከል ተሳክቷል። ነፃ ወጣሁ። በመሳው አከላቴ አንድ የሙቀት ስሜት ሲሰራጭ ተገነዘብኩ። ወይኖቼም በእንባ ራሱ።

ጦርነቱ ከማብቃቱ በፊት በመጨረሻ ከምደርስበት ቦታ ራሴን ለማቋቋምና በሰዎች ዘንድ ከብርን ለማትረፍ ጊዜ ይኖረኛል። ዋናው ችግሬ ግን ጦርነቱ በመካሔድ ላይ እያለ በየትኛው ቦታ እንደምኖር መምረጥ አለመቻሌ ነበር። ቁምነገሩ የትም ቦታ ቢሆን፤ ከሕዝቡና ከባለሥልጣኖቹ አከብሮትንና ዕምነትን ማትረፍ አለብኝ። የኑሮ መመሪያየ ከተወቃሽነት ባቫገር መሆነ ይኖርበታል።

ድል አድራጊነቴ እንደዚህ የመሰለውን ልዩ የሰላም ስሜት ሰላጎናጸፈኝ የማስበው ስለዚሁ ብቻ ነበር። ፓፒዮ፣ በመጨረሻ አሸንፈሃል። ዘጠኙን ዓመታት ወደኋላህ ትተሃቸዋል። አመሰግንሃለሁ አምላኬ። ትንሽ ፈጠን ብለህ ልታደርገው በቻልክ ነበር፤ ግን የአንተ መንገዶች ምስጢራዊ ናቸው። በዕርግጥ ቅሬታ ማሰማቴ አይደለም፣ ምክንያቱም ምስጋና ይግባህና አሁንም ገና ወጣት፣ ጤነኛና ነፃ ነኝ አልኩኝ በልቤ።

በሁለቱ ዓመታት የፈረንሣይ ወህኒ ቤቶችና በዘጠኙ ዓመታት የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤቶች ውስጥ አእምሮዬ በመናወዝ ላይ እያለ ነበር አንድ ጉንተላ ከንዴ ላይ የተሰማኝ። «መሬት» አለ መርከበኛው።

ዐሥር ሰዓት ላይ አንድ የጨለመ የመርከብ አደጋ ማስጠንቀቂያ መብራት አለፍንና፣ ዴሜራራ ወደተባለው ትልቅ ወንዝ ገባን። የሞተር ጀልባዋ እንደገና ብቅ አለች። መርከበኛው መሪውን ለእኔ መለሰልኝና ወደፊት ሔዶ ቦታ ያዘ። አንድ ትልቅ ገመድ ከሞተር ጀልባዋ ወደ እርሱ ተወረወረለትና ፊትለፊት ካለው መቀመጫ ላይ አሰረው። የነፋስ ሽራዎቹን ራሱ አወረደና የሞተር ጀልባዋ በጣም ረጋ ብላ እየንተተችን፣ የጦር ጀልባዋ በሁለት መቶ ያርድ ርቀት ከኋችን ሆና በድፍርሱ ወንዝ ላይ ዐሥራ ሁለት

t.me/OLDBOOKSPDF

ማይል ሽቅብ ተጓዝን። ወንዙ ጠመዝማዛ ነበር። ብቅ እንዳልን አንድ ትልቅ ከተማ ፊትለፊታችን ተንጣለለ። «ጀርጅታውን» አለ እንግሊዛዊው መርከበኛ።

የጭነት መርከቦች፣ የጦር መርከቦችና ባለሞተር ጀልባዎች በየቦታው ተሠትረዋል። በውሃው ዳርና ዳር የመሣሪያ መደበኛ ሰንሰቶች ቆመዋል። በመሬትም ሆነ በጦር መርከቦቹ ላይ ሀልቆ መሣፍርት የጦር መሣሪያ ዓይነቶች ተቀምጠዋል።

ጦርነት በመካሔድ ላይ እንደሆነ ዐውቀናል፤ ይሁንና እኛን፣ በቅኙ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ያለነውን፣ አልነካንም ነበር። ጀርጅታውን ግን መቶ በመቶ በጦርነት ወላፈን ውስጥ ነበረች። በጦር መሣሪያ የተከበበች ከተማ ውስጥ መግኘቴ የሚያስገርም ስሜት አሳደረብኝ። ወደ አንድ ወታደራዊ የመርከብ ማገቻ ድልድይ ሰንጠጋ የጦር ጀልባዎም ከጎናችን መጣች። ኪኪ ከዓሣማው ጋር፣ ቫን ሁዊ አንዲት ትንሽ ቋጠሮ እንደ ተሸከመ፣ እኔ ባዶ እጄን ሆኜ ወደ ወደቡ አመራን።

t.me/OLDBOOKSPDF

ፀሥራ ሁለተኛ ማስታወሻ

ከጀርጅታውን ማምለጥ

አስፈላጊ የሆኑ አነስተኛ ፎርማሊቲዎችን አጠናቀቅንና ከስምንት ቀን በኋላ ነፃ ተለቀቅን። ኑሯቸውን በጀርጅታውን መሥርተው በወደብ ለሚገኙ አሜሪካውያን መርከበኞች ትኩስ አትክልት በመሸጥ ከሚተዳደሩና ካመለጡ ፈረንሣውያን አሥረኞች ጋ ከተቀራረቡ ሕንዶች ዘንድ ሔድን። እኔም በሳን በኩል አንዳንድ የውቅራት ሥራዎችን ጀምሬያለሁ። በሆቴል ሥራ፣ ቢራቢሮዎችን በመሸጥና አንዲት የቦከሳይት ማዕድን ያላት ኮተማ ውስጥ የዳንስ ምሽት አዘጋጅ በመሆን፣ የተለያዩ ጊዜያዊ ሥራዎች ከቀያየርኩ በኋላ፣ ሁሉም አኔንና ቻይናውያን አጋሮቼን ከፖሊስ ትኩረት ውስጥ ስላስገቡን፣ ከእንግዲህ የአንግሊዝ ጊያና ይብቃኝ ብየ ወሰንኩ። ኪኪና ቫን ሁዊ እዚያው ቀሩ።

ያለ ሕጋዊ ፈቃድ መንቀሳቀስ ጦርነቱ እንደ ከባድ ወንጀል ቢገመተውም፣ ያለ ፓስፖርት፣ ያመለጥነውም ሆን ነፃ የወጡት አስረኞች በሙሉ በአንዲት ጠንካራ ጀልባ ሆነን ወደ ባህር በመውጣት የሰሜንን አቅጣጫ ያዝን። አንድ አሰቃቂ አውሎ ነፋስ በመካከል ገባብንና የነፋስ ሽራችንን የሊይኛውን ምሰሶ፣ የነፋሱን ሸራ፣ መሪውንና ስንቃችንን በሙሉ አጣን። የተረፉን አንዲት አጭር መቅዘፊያና በጀርባዎቻችን ላይ የቀሩት ልብሶች ብቻ ነበሩ። መቅዘፊያውን እንደ መሪ ተጠቀምንበት። ከዚያም ካናቴራዎች ብቻ ሲቀሩን ሁሉንም አውልቀን ከሞገዱ ባመለጠች አንዲት ጥቅል ሸበ አርዳታ እንድ የነፋስ ሸራ ሠርተን ከተረፈው ምሰሶ ላይ አያያዝነው።

የመርከቦች መመኪያ ነፋስ ተነሣና ወደ ደቡብ አቅጣጫ ለማምራት ረዳን። የትም ቦታ ብናርፍ፣ ሊላው ቀርቶ ወደ እንግሊዝ ጊያና ተመልሰን ብንሔድ እንኳ ደንታ አልነበረኝም። ካሳለፍነው መከራ እንባር እዚያ የሚጠብቀንን ቅጣት በጸጋ እንቀበለዋለን። በሞገዱ ወቅት ወይም የጥፋት ውሃ፣ የነርፍ መጥለቅለቅ፣ የነፋስ ነውጥ ቢባል ይሻላል፣ በፊትም ሆነ በኋላ፣ ጓደኞቼ የሚያከራ ተግባር ፈጽመዋል።

ከወጣን ስድስት ቀን ሲሆነን፣ በመጨረሻዎቹ ሁለቱ ቀናት አየሩ ፀጥ ብሎ ነበር። ያንጊዜም መሬት በሩቁ ያየሁ መሰለኝ። ወዲያውኑም ወደ እዚያው አመራሁ፣ ግን አርግጠኛ አስከሆን ድረስ ምንም ነገር ላለማለት ወሰንኩ። ድንገት አሞራዎች ከበላያችን ሰላንጎበቡ ልከ መሆን አለብኝ ብዬ አሰብኩ። በእነርሱ ዋካታ ጓደኞቼ ባነኩ። ከፀሐይ ጨረር ለመከለል ከንዶቻቸውን ፊቶቻቸው ላይ አጋድመው በድካምና በፀሐይ እንደ ዛሉ ከጀልባዋ ሥር ተረፍርፈው ነበር።

«ያለነው የት ቦታ ነው ብለህ ትገምታለህ ፓፒ?» አለ ቻፓር።

t.me/OLDBOOKSPDF

«በዕውኑ አላውቅም። ያ ቁራጭ መሬት ደሴት ሳይሆን፤ አንድ የባሕር ወሽመጥ ከሆነ ወደ ኦሪኖኮ ወንዝ የሚያገባና ከቬኔዙዌላ የሚከፍለው የእንግሊዝ ጊያና ጫፍ ሊሆን ይችላል። ግን በግራና በቀኝ ካለው መሬት መካከል አንድ ትልቅ ክፍት ቦታ ካለ፣ ልላነ ምድር ሳይሆን፣ ትሪኒዳድ ነው። በስተግራ በኩል ያለው ቬኔዙዌላ ይሆናል፣ ይህም ማለት ያለነው በፓሪያ የባሕር ሰላጤ ወስጥ መሆኑ ነው።»

ይህንንም ያስታወስኩት ከዓመታት በፊት አጥንቻቸው ከነበሩ የባሕር ጉዞ ካርታዎች ይመስለኛል። በስተቀኝ በኩል ትሪኒዳድ፣ በስተግራ በኩል ቬኔዙዌላ ቢሆኑ፤ የትኛውን መምረጥ አለብን? ዕድላችን የተንጠለጠለው በዚህ ውሳኔ ላይ ነበር። የነፋስ ሽራችንን ከሞላው ጥሩ ነፋስ ጋር ወደ ጠረፉ ለመድረስ አስከዚህ በጣም ከባድ አይሆንም።

ትሪኒዳድም ያው «የእንግሊዞቹ» ማለት ነበረ። ልክ እንደ እንግሊዝ ጊያና ተመሳሳይ መንግሥት ነበር ያለው።

«መልካም ከብካቤ ሊያደርጉልን ሙሉ ፈቃደኞች ይሆኑ ይሆን?» አለ ጊቱ

«ምናልባት፤ ያደርጉልን ይሆናል፣ ግን በጦርነት ወቅት ያለ ሕጋዊ ፈቃድ የእንግሊዝን ግዛት ስለ ለቀቅን ምን ያደርጉልናል ብለህ ትገምታለህ?»

«ቬኔዙዌላስ እንዴት ነው?»

«ምንም የሚታወቅበት መንገድ የለም» አለ ደፐላንከ። «ፐሬዚዳንት ጎሚዝ ሥልጣን ላይ በነበረበት ወቅት፤ ኢሥረኞችን በመንገድ ሥራ ብርጌደ ውስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ ከአሠሩ በኋላ ለፈረንሣይ አሳልፈው ሰጧቸው።»

«ጦርነቱ ያንን ሁሉ ለውጦት ይሆናል»

«ግን ስለጀርጅታውን እንደተረዳሁት ከሆነ እነርሱ ገለልተኞች ናቸው።»

«ዕርግጠኛ ነህ?»

«ጥርጥር የለውም።»

«እንግዲያ ለእኛ አደገኛ ይሆናል»

በሁለቱም አቅጣጫ መብራቶች ማየት ችለናል። ከዚያም የመርከብ ጡሩምባዎች ሰማን፣ ሦስት ጊዜ አከታትለው አምባረቁ። ጨረቃዋ በስተጀርባችን ብቅ አለች። ወዲያው ሁለት የሾሉ ግዙፍ ቋጥኞች ከፊት ለፊታችን ባሕሩ ውስጥ በጣም ጥቁር ሆነው ብቅ አሉ። የጡሩምባው ምክንያት እነርሱ መሆን አለባቸው።

«ተመልከት፣ ተንሳፋፊ የጉዞ አመልካቾች፣ በመስመር ያሉት በሙሉ እነርሱ ናቸው። ለምን በእንደኛው ላይ ጀልባችንን ኢሥረን እስኪነጋ ድረስ እዚሁ አንቆይም? ቻፓር፣ የነፋስ ሽራውን አውርድ።»

በ«ነፋስ ሽራ» ስም ከብር የሰጠኋቸውን የሱሪዎችና የሸሚዞች ቅጥልጣዮች

t.me/OLDBOOKSPDF

ከአወሪደ በታላ በአጭሩ መቅዘፊያ አማካይነት ወደ አንደኛው የባሕር ላይ ተንሳፋፊ አመልካች አቅጣጫ አዞርኩ። እንደ ዕድል ሆኖ ከአውሎ ነፋሱ ቁጣ ያመለጠና ከጀልባዋ ፊትለፊት የተንጠለጠለ አንድ ረጅም ገመድ ነበር። ተንሳፋፊው ላይ የሚታሰርበት ምንም ነገር ስላልነበረ፣ በቀጥታ ከሚቆራኙበት ሰንሰለት ላይ ነበር ያሰርነው። ጠባቡን የውሃ ወሽመጥ ማመልከቻ እንዲሆን የተቀመጠ መስመር ይመስላል። ያለማቋረጥ የሚያናፋውን የመርከብ ጡሩምባ ጆሮ ዳባ ልበስ ብለን ከጀልባዋ ወለል ላይ ለጥ አልን። ለስላሳ ሙቀት በሰውነቴ ውስጥ ሲሰራጭብኝ ተሰማኝና ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ይዞኝ ሔደ። ፍንትው ያለ ቀን ሲወጣ ነቃሁ። ፀሐይዋ ወዲያውኑ ወጣች። ባሕሩም በአረንጓዴ ሰማያዊ ቀለሙ ከሥሩ ኮራል እንዳለው ያስታውቃል።

«ምን እናድርግ? ከመሬት ልናርፍ ነው? አርቦኛል። ውሃ ጥሙም ሊገድለኝ ነው።» በእነዚህ ሁሉ የግዳጅ ጾም ቀናት ውስጥ ዛሬ ሰባተኛው ቀናችን ሲሆን፤ የመጀመሪያው አሮሮ መሰማቱ ነበር።

«በጣም ቅርብ ስለሆነ ከመሬት ልናርፍ እንችላለን» በማለት የተናገረው ቻፓር ነበር።

ከሁለቱ ትላልቅ ቋጥኞች በስተጀርባ ያሉትን ወጣ ገባ የሆኑ የጠረፍ መስመሮች በግልጽ ለማየት ቻልኩ። በስተቀኝ ያለው ትሪኒዳድ፣ በስተግራ ቬኔዙዌላ መሆን አለበት። በፓሪያ የባሕር ሰላጤ ውስጥ መሆናችን አጠራጣሪነት የለውም። ከአሪኖኮ በሚመጣው ደለል ውሃው ያልደፈረሰበት ብቸኛው ምክንያት ገና ከባሕሩ ወሽመጥ በመሆናችን ነበር።

«አሮ፣ ታዲያ ምን እናድርግ? መወሰን የሚገባችሁ እናንተ ናችሁ እኮ። ለአንድ ሰው በጣም ከባድ ነው። በስተቀኝ በኩል የእንግሊዝ ደሴት የሆነችው ትሪኒዳድ፣ በስተግራ ቬኔዙዌላ አሉላችሁ። አንድ የማይታበል ሐቅ ቢኖር፣ ከጀልባችን ሁኔታና ከሰውነታችን አቋም አንጻር በተቻለ ፍጥነት ወደ የብስ መድረስ እንዳለብን ነው። ጊቱና ኩርቢየ ነፃ የወጣችሁ ኢሥረኞች ናችሁ። የቀረነው፣ ቻፓር፣ ደፐላንከና እኔ በዕርግጥ አደጋ ላይ ነን። ስለዚህ እኛ ሦስታችን መወሰን ይገባናል። ምን ትላላችሁ?»

«ወደ ትሪኒዳድ መሔዱ የተሻለ ይሆናል። ቬኔዙዌላ ምኑም የማይታወቅ ሠፊ ምድር ነው።»

«አንድም ውሳኔ እናሳልፋለን ብየ አልገምትም። ያች ባለሞተር ጀልባ ልትቀርጥልን ይመስለኛል» አለ ደፐላንከ።

እውነትም ነበር፤ አንዲት ባሞተር ጀልባ በቀጥታ ወደ እኛ አመራች። ሃምሳ ያርድ ራቅ ብላ እንደቆመች፤ አንድ ሰው አንድ የድምፅ ማጉሊያ አነሣ። የጀልባዋ ሰንደቅ ዓላማ ብዙ ከከቦች ያሉት ስለነበረ የእንግሊዝ አለመሆኑን ለማጣራት ችያለሁ። ካሁን

t.me/OLDBOOKSPDF

በፊት በሕይወቴ ፈጽሞ አላየሁትም ነበር። የቬኔዙዌላ መሆን አለበት። ከጊዜ በኋላ ያ ሰንደቅ ዓላማ «የራሴው ሰንደቅ ዓላማ» የአዲሷ ሀገሬ ሰንደቅ ዓላማ፤ ለእኔ በጣም ልብ የሚነካ አርማየ ነው፤ ምክንያቱም በዚያች አንዲት ቁራጭ ጨርቅ ጠለላ ሥር የሚኖሩት የጨዋ ጨዋና ምርጥ የሆኑ ታላቅ ሕዝቦች፣ የራሴው ሕዝቦች ሆነዋላ።

የድምፅ ማጉሊያ የያዘው ሰው በስፓኝኛ ቋንቋ «እነማን ናችሁ?» ሲል ጮኸ።

«ፈረንሣውያን ነን።»

«ዕብዶች ናችሁ?»

«ለምን እንደዚህ ትላለህ?»

«ምክንያቱም የተቆራኛችሁት ከፈንጅ ጋር ነዋ!»

«ለዚህ ነው ቀረብ ብላችሁ ያልመጣችሁት?»

«አዎ፤ ፈጠን በሉና ከዚያ ውጡ።»

ቻፓር ገመዱን ለመፍታት የወሰደበት ጊዜ ሦስት ሴኮንድ ብቻ ነበር። የማይታመን ነው! ራሳችንን ያሰርነው በተንሳፋፊ ፈንጅዎች ሰንሰለት ላይ ኖሯል! አለመፈንዳቱም ተአምር ነበር። ባለሞተሯ ጀልባ አየኑተች ከአወጣችን በኋላ መርከበኞቹ ትንሽ ቡና፣ ትኩስና ጣፋጭ ወተት ከሲጃራ ጋር አቀበሉን።

«ወደ ቬኔዙዌላ ሒዱ። ደህና ከብካቤ ይደረግላችኋል። መንገዱን በሙሉ ልንነትታችሁ አልቻልንም፤ ምክንያቱም ከባሪማስ በከባድ ሁኔታ የተጎዱ ሰዎችን ለማንሣት አንድ ‹የነፍስ አድን› ጥሪ ደርሶናል። ወደ ትሪኒዳድ እንዳትሔዱ። አለበለዚያ ከአንድ ፈንጅ ጋር ተጋጭታችሁ ከዚያም . . .»

«ደህና ሁኑ፤ መልካም ዕድል» ከተባባልን በኋላ ሁለት ሊትር ወተት ትተውልን ጀልባቸው ተፈተለከች። እኛም የነፋስ ሸራ ሰቀልን። አንድ ሲጃራ በከንፈሮቼ መካከል ይዤ፤ ከማንኛውም አደጋ ሳልጠነቀቅ አራት ሰዓት ላይ ጀልባዋን ወደ አንድ ለጥ ያለ ለስላሳ አሸዋ አድርሼ መሰግኳት። በተሰባበረ ምሰሶ ላይ ከሸሚዞችና ሱሪዎች የተሠራ የነፋስ ሸራ ከተንጠለጠለባት ልዩ የሆነች ጀልባ ምን ዐይነት የምድር ጉድ እንደሚወጣ ለማየት ወደ ሃምሳ የሚጠጉ ሰዎች ቆመው ይጠባበቁ ነበር።

t.me/OLDBOOKSPDF

ዐሥር ሦስተኛ ማስታወሻ

ቬኔዙዌላ

የኢራፓ ዓሣ አጥማጆች

በአጠቃላይ አይቼው የማላውቀው ሥልጣኔ፣ ሕዝብና ልዩ ዓለም አየሁ። በቬኔዙዌላ አፈር ላይ የቆምኩባቸው አነዚያ የመጀመሪያ ደቂቃዎች በጣም ስሜት የሚነኩ ስለነበሩ፣ ከእነዚህ ለጋስ ሕዝቦች የተቀበልነውን የጋለ መስተንግዶ ለመተንተን በጣም የመጠቀ ታላቅ ችሎታ ይጠይቃል። ሰዎቹ፣ ማለትም ጥቁርና ነጭ ቢሆኑም፣ አብዛኞቹ ጠያይሞች ናቸው። ከሞላ ጎደል ሁሉም ሱሪዎቻቸውን እስከ ጉልበታቸው ድረስ ጠቅልለዋል።

«እናንተ ምስኪኖች! በጣም ታሳዝናላችሁ!» አለ ከሰዎቹ መካከል አንዱ።

ወርፈንባት የነበረችው የዓሣ አጥማጆች መንደር ስም ኢራፓ ይባላል፣ የምትገኘውም በሱከር ከፍለ ሀገር ውስጥ ነበር። ሴቶቻቸው በሙሉ የተዋቡ ሲሆኑ፣ ከዚያ የሚበልጠው ግን ርኅሩኅነታቸውና እንግዳ ተቀባይነታቸው ነበር። መካከለኛ ዕድሜ ያላቸውና ባልቴቶቹ ደግሞ ወዲያው ነርሶችና የእናት ምትክ ሆኑልን።

አምስት የሰፍ ብርድ ልብሶች አንድ ጥላ ሥር አንጠልጥለው ዘረጉና በጠረጴዛና ወንበሮች አሟሏቸው፣ ከዚያም ከእግር እስከ ራሳችን በኮኮስ ቅባት ለቀለቁን። እንቅልፍ መፈለጋችንና መመገብ ያለብንም በጣም በአነስተኛ መጠን እንደሆነ ወውቀዋል።

ምቾት ባላቸው ተንጠልጣይ አልጋዎቻችን ላይ በዕንቅልፍ ሰመመን ላይ እንዳለን፣ ፈቃደኛ በሆኑት ነርሶቻችን አማካይነት እጅ የሚያስቆረጥሙ ምግቦችን ተመገብን፤ ልክ እናቶቻቸው እንደሚመግቧቸው የወፍ ጫጩት ዓይነት ነበር። በጣም ከመድከሜ የተነሣ በተረፈችኝ ትንሽ ኃይል ሙሉ በሙሉ በተንጠልጣይ የብርድ ልብሱ አልጋ ላይ ወደቅኩበት። በተላጠው ቁስሌ ላይ በተመረገው የኮኮስ ቅባት ምክንያት ፍስስ አልኩና ዕንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወሰደኝ። በአጠቃላይ ምን እንደሚመጣብን ሳልጨነቅ አበላለሁ። አጠጣለሁ፣ አተኛለሁ።

የመጀመሪያዎቹን ማንኪያዎች ባዶው ሆዴ አልተቀበላቸውም። እኔ ብቻ አልነበርኩም። ሴቶቹ በማንኪያ ወደ አፋችን ሊያስገቡልን የሞከሩት አብዛኛው ምግብ ሁላችንንም አስታወከን።

የኢራፓ ሰዎች በጣም ድሆች ነበሩ፤ ግን ለመርዳት ያልሞከረ ማንም

t.me/OLDBOOKSPDF

አልነበረም። ምስጋና ይግባቸውና በሦስት ቀን ውስጥ ከሞላ ጎደል ወደ ቀድሞ ቅርፃችን ተመለስን። በዘንባባ ከተከለለው አስደሳች ጥላ ሥር ተቀምጠን ከሰዎቹ ጋር ስናወራ ረጅም ጊዜ እናሳልፋለን። ሁላችንንም በአንድ ጊዜ ለማልበስ አቅም ሰለሚያንሳቸው አንድ ትንሽ ማኅበር መሠረቱ፤ አንደኛው ጊቱን ሲንከባከብ ሲረከብ፤ ሌላው ደጥላንከን፤ እንደዚሁ እያለ ቀጠለ። እኔን ለመንከባከብ ዐሥር ያህል ሰዎች ተረከቡኝ።

ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ቀኖች የተገኘውን ማንኛውንም ጨርቃጨርቅ ለበስን። ግን ምንም ይሁን ዘወትር ንጹህ ነበር። ከዚያም ለመግዛት አቅም በፈቀደላቸው ወቅት እንዳንድ አዲስ ሸሚዝ፤ ሱሪ፤ ቀበቶና ጥንድ ነጠላ ጫማ ገዙልን። እኔን ከሚንከባከቡት ሴቶች መካከል በጣም ውብ የሆኑ ሁለት ወጣት ኮረዳዎች ነበሩ። ከስፖኝ ወይም ከፖርቱጊዝ ደም ጋር የተቀየጡ የሕንዳውያን ከለቦች ነበሩ። አንዷ ቲቢሴይ ፣ ሌላዋ ደግሞ ኔኒታ ይባላሉ።

«ከወዴት ቦታ መጣችሁ ብለን መጠየቅ አንፈልግም። ከፈረንሣይ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ያመለጣችሁ አሥረኞች መሆናችሁን ዐውቀናል።»

የሚገርም ነበር። ወንጀለኞች መሆናችንንም ዐውቀዋል። ስለነበርንበት ወህኒ ቤት ከጋዜጦችና ከመፅሐፍት ተረድተዋል፤ ስለሆነም፤ እነዚህ ሰዎች እኛን ከአደጋ ማትረፍና መርዳት በትክክል ተገቢ ነው ብለው አምነውበታል። ሲደላህ ሌላውን ሰው ማልበስ፤ ወይም አንተም ሆንክ ቤተሰብህ ችግር ውስጥ እስካልገባችሁ ድረስ አንድ የተራበ አንግዳ መመገብ ምንጊዜም ተገቢ ነገር ነው። ግን ለራስህ ቤተሰቦች ምሳ እንኳ የማትበቃ አንዲት የበቆሎ ቂጣ ለሁለት ቆርሰህ ከአንድ አንግዳ ጋር፤ ያውም ካመለጠ አሥረኛ ጋር መካፈል፤ በዕውነት የሚያስገርም ነው።

አንድ ቀን ጧት መንደርተኞቹ በሙሉ ፀጥ አሉ። ግራ የተጋቡና የተጨነቁ ይመስላሉ። ምን እየተካሔደ ይሆን? ለመጀመሪያ ጊዜ ጺሜን ስላጭ፤ ኔኒታና ተቢሴይ አተኩረው እየተመለከቱኝ ነበር። ከእነዚህ በጎ መንፈስ ካላቸው ሰዎች ጋር በቆየንባቸው ስምንት ቀኖች ውስጥ ከተለበለበው ሰውነቴ ላይ ቆዳዬ መነሣት ጀምሮ ስለነበር ልጎዳው እችላለሁ ብዬ አሰብኩ። በጺሜ ምክንያት ኮረዳዎቹ ዕድሜዬ ስንት እንደነበረ ምንም የተረዱት ሐሳብ አልነበረም። ሙልጭ አድርጌ ጺሜን ተላጭቼ ሲያዩ፤ በጣም ስለ ደነቃቸው ባገር ቤት ፈሊጥ ወጣት ሆኜ እንዳገኙኝ ገለጹልኝ። ምንም እንኳ ሠላሳ አምስት ዓመቴ ቢሆንም፤ ገና የሃያ ስምንት ወይም የሠላሳ እመስላለሁ። ግን የሚያብሰለስላቸው አንድ ነገር ነበር። አጥንቴን ሰርስሮ ሊሰማኝ ችሏል።

«ምንድን ነው የሚካሔደው? እስኪ ንገሪኝ ቲቢሴይ፤ ነገሩ ምንድነው?»

«ባልተወሰነ ደቂቃ ውስጥ ከጎሪያ የሚመጡ ባለሥልጣኖችን እየተጠባበቅን ነው። እዚህ ምንም ፖሊስ የለንም፤ ግን ያም ሆኖ የእነርሱ ፖሊሶች ስለእናንተ እዚህ

t.me/OLDBOOKSPDF

መኖር ዐውቀዋል። በጉዞ ላይ ናቸው።»

የተመጣጠነ የስፖርተኛ አካል ካለው ከአንድ ጎረምሳ ጋር አንዲት ረጅም፣ ውብ ጥቁር ሴት እኔ ዘንድ መጣች። ሴትየዋ የምትጠራው ላ አግሪታ በተባለው፣ በዘርም ሆነ በሃይማኖት ፍጹም መድልዎ በሌለበት፣ በመላው ቬኔዙዌላ ለጠያይም ሴቶች መጠሪያ በሚጠቀመብት ተወዳጅ ስም ነበር።

«ሚስተር ሔንሪ፣ ፖሊሶቹ በመንገድ ላይ ናቸው። መጥፎም ይሁን ደግ የሚሉትን አላውቅም። ለምን ለጥቂት ጊዜ አትደበቅም? ማንም ሊያገኝህ ወደማይችልበት አንዲት ትንሽ ቤት የሚወስደውን መንገድ ወንድሜ ሊያሳይህ ይችላል። በቲቪሴይ፣ በኔኒታና በእኔ አማካይነት ወሬውንም ሆነ የምትበላውን አንዳንድ ነገር ልናመጣልህ እንችላለን» አለች።

ስሜቴ ከመነካቱ የተነሣ እጇን ሊመሳም ቀረብ ስል፣ ወደ ኋላ ሸሸት አለችና በንፁሕ ስሜት ጉንጩ ላይ ሳመችኝ።

ከዚያም ልክ እንደ ፈጣን ባቡር የሚያስገመግም አንድ የፈረሰኛ ቡድን ደረሰ። አያንዳንዱ ሰው በግራው በኩል አንድ ጎራዴ የታጠቀው አንድ ገጀራ፣ በጥይት የተሞላ ዝናርና በቀኝ ዳሌው በኩል ያገነደረው አንድ ትልቅ ሽጉጥ ነበረው። ወደ መሬት ዘለው ወረዱና አንደ ሕንዳዊ የሚቋለጨለጩ ዐይኖችና የሞንጎላውያን ፊት ያለው ፣ ቆዳው መዳብ የመሰለ አንድ ግዙፍ ሰው ወደ እኛ መጣ።

«ደህና ዋላችሁ። የፖሊስ አዛዥ ነኝ።»

«እንደምን ዋሉ ጌታዬ።»

«ከፈረንሣይ ጊያና ያመለጡ አምስት እሥረኞች መኖራቸውን ለምን አልነገራችሁንም? ስምንት ቀን እዚህ መቆየታቸውን ሰምቻለሁ።»

«በሚገባ መራመድ እስኪችሉ ድረስ እየጠበቅን ነበር።»

«ደህና፣ ወደ ጎሪያ መልሰን እንወስዳቸዋለን። አንድ ካሚዎን እየመጣላቸው ነው።»

«ቡና ይምጣላችሁ?»

«አዎ እናመሰግናለን።»

ዙሪያ ከበን ተቀመጥንና ሁሉም ሰው ቡና ታደለ። የፖሊሱን አዛዥና ሌሎቹንም ባለደረቦቹን ተመለከትኳቸው። ከፉዎች አይመስሉም። ትእዛዝ ለማከበር ያህል አንጂ ነገሩ አስፈላጊ ሆኖ እንዳልታያቸው ስሜታቸው ይናገራል።

«ከዲያብሎስ ነው ያመለጣችሁት?»

«አይደለም፣ ከእንግሊዝ ጊያና፣ ጆርጅ ታውን ነው የመጣነው።»

«ለምን እዚያው አልቆያችሁም?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«እዚያ ኑሮ አስቸጋሪ ነው።»

«እዚህ ይሻላል ብለህ አሰብክ?» አለ ከፈገግታ ጋር።

«አዎ፣ ከዚህም በላይ እኛም እንደ እናንተው ላቲኖች ነን።» ሰባት ወይም ስምንት ሰዎች ያሉበት አንድ ቡድን እኛ ወደ ነበርንበት አካባቢ መጣ። ፈካ ያለ የቸኮላት ቀለም ቆዳ፣ ቁመቱ ሰድስት ጫማ የሚደርስና ነጭ ጸጉር ያለው ዕድሜው በግምት ሃምሳ ዓመት የሚደርስ አንድ ሰው ከፊት ለፊት ነበር። ትላልቅ የሆኑት ጥቋቁር ዐይኖቹ አምብዛም ብልህነትና ተግባቢነት እንደማያንሰው ያመለክታሉ። ቀኝ እጁን በገጀራው እጀታ ላይ ጣል አድርጎት ነበር። «ጌታዬ፣ እነዚህን ሰዎች ምን ልታደርጓቸው ነው?» አለ።

«ጎሪያ ወደሚገኘው ወህኒ ቤት እወስዳቸዋለሁ።»

«ከእኛ ጋር እንዲኖሩ ለምን አትፈቅዱላቸውም? እያንዳንዱ ቤተሰብ አንዱን ይቀበላል።»

«አይቻልም። ከአገረገሸው ታዝዤ ነው።»

«ግን በቬኔዙዌላ ምንም ጥፋት አልሰሩም እኮ!»

«ዐውቃለሁ። ሆኖም አደገኞች ሰዎች ናቸው፤ ያ ባይሆ በፈረንሣይ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ አይቀጡም ነበር። አንድ ከበድ ያለ ወንጀል ፈጽመው መሆን አለበት። ከዚህም ሌላ ያለ መታወቂያ ወረቀት አምልጠዋል፤ ስለዚህ ቬኔዙዌላ ወስጥ መሆናቸውን ሲያውቁ የእነርሱ ፖሊሶችም እንዲመለሱላቸው መጠየቃቸው የታወቀ ነው።»

«ከእኛ ጋር ቢኖሩ እንወዳለን።»

«አይቻልም። የአገረ ገዢው ትእዛዝ ነው።»

«ይቻላል። ስለነዚህ ሰዎች አገረ ገዢው ምን ያውቃሉ? እድሜ ልኩን ጥፋተኛ ሆኖ የሚኖር ማንም ሰው የለም። የፈጸመው ምንም ነገር ይሁን ሊጸዳ የሚችልበት አንድ ወቅት ሲያጋጥመው ማንም ሰው ደግና ለሕብረተሰቡም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። እናንተ የቀራችሁትስ ምን ትላላችሁ?»

ልክ እንደ ዘማሪዎች በአንድ ድምፅ፣ «አዎ፣ ለእኛ ተውዋቸው። አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ እኛ እንረዳቸዋለን። ጥሩ ሰዎች መሆናቸውን ለማወቅ ለእኛ ስምንት ቀን በቅቶናል» አሉ።

«በሥልጣኔ ከእኛ የበለጡ ሰዎች ጨለማ ግንብ ውስጥ የቆለፉባቸው ስለሆነ ወንጀል ከመሥራት ሊመለሱ አይችሉም» ሲል የፖሊሱ አዛዥ መለሰ።

"ምኑን ሠለጠኑት ጌታዬ?" ስል ጠየቅሁ፤ "ፈረንሣውያን አሳንሰሮች አውሮፕላኖችና በመሬት ውስጥ የሚሽከረከሩ ባቡሮች ስላሏቸው እኛን ተቀብለው

t.me/OLDBOOKSPDF

ከተንከባከበን ከእነዚህ ሰዎች ይበልጥ ሥልጡን መሆናቸውን ይመሰክርላቸዋል ብለህ ትገምታለህ? በእኔ አስተያየት እነዚህ እዚህ ያሉት ሰዎች ይበልጥ ሰብአዊ ሥልጣኔ ይበልጥ በጎ መንፈስና ከፍተኛ ግንዛቤ አላቸው፤ ምክንያቱም ከተፈጥሮ ጋር ተጠጋግተው ይኖራሉ። በዕድገት አቅጣጫ የሚጎድላቸውን በከርሰ-ሲያናዊ በጎ ምግባር ስለሚያካክሱት ሠልጥነዋል ተብለው የሚጠሩትን ሀገሮች ኃፍረት ላይ ይጥላሉ። በማንኛውም ቀን ከዚህች መንደር አንድ መሃይም ወስጄ ፓሪስ ውስጥ ከሶርቦን ዩኒቨርስቲ ምሩቅ ከሆነ አንዱ ጋር ባወዳድረው በተለይ እኔን ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት እንድላክ ከፈረደብኝ ዓቃቤ ሕግ ዓይነት ጋር ባመሳስለው ይህ እውነተኛ ሰው ሲሆን ያ ግን ሰብዕናውን የረሳ ፍጡር መሆኑን በቀላሉ ማሳመን እችላለሁ" አልኩት።

«አባባልህን ተረድቸዋለሁ። እኔም መሣሪያ ብቻ ነኝ። እና ለማንኛውም ካሚዎኑ ይሸውና። አባካችሁ ተገቢው ሥነ ምግባር እንዲኖራችሁ ሞክሩ ነገሮች ይበልጥ እንዲቃለሉ ያደርጋል።»

እያንዳንዷ ሴት በተለይ እንድትንከባከበው ከተሰጣት ጋር አንገት ለአንገት ተቃቀፈች። ቲቢሲይ ኔኒታና ላ ኔግሪታ ደህና ሁን ለማለት ሲሰሙኝ እያለቀሱ ነበር። የእኛን ወደ ወህኒ ቤት መሔድ በማየቱ የቱን ያህል እንዳዘነ ለመግለጽ እያንዳንዱ ሰው በየተራ ከኛ ጋር እጅ ለእጅ ተጨባበጠ።

«እናንተ የኢራፓ መልካም ሰዎች ደህና ሁኑ። እንደገና ነፃ ከወጣሁ እናንተ እንደረዳችሁኝ ሁሉ እኔም ምንጊዜም ሊሎችን ለመርዳት እሞክራለሁ።» በኋለኛዎቹ ዓመታት እነርሱን ከመሰሰሉ ደጋግ ሰዎች ጋር በብዛት ለመገናኘት በቃሁ።

የሔልዶራዶ አሰቃቂ ወህኒ ቤት

ከሁለት ሰዓት በኋላ ከተማ ከምትመስልና ወደብ ካላት ጎሪያ ከተባሉች እንዲት ትልቅ መንደር ደረስን። የፖሊሱ አዛዥ ለአውራጃው ፖሊስ አዛዥ በግንባር አስረከበን። በፖሊስ ጣቢያው አልተንገላታንም ነበር ፤ ግን ከእንግሊዝ ጊያና መምጣታችንና ነፃ ሰዎች ሆነን እንደ ነበርን ሐቁን አልቀበልም ያለ አንድ ደንዝ ባለሥልጣን ፊት ለጥያቄ ቀረብን። ለምን ቪኔዙዌላ እንደ ደረስን እንድናስረዳው ጠየቁን። የአውሎ ነፋሱን ታሪክ ስነግረው ልናታልለው የሞከርን መስሎት ከስ መሠረተብን።

«በከሳይት የተጫነ አንድ መርከብ በላዩ ላይ ካሉት ሰዎችጋር ያሰመጠ ዐሥራ አምስት ጫማ ብቻ ስፋት ባላትና ለማንኛውም አደጋ በተጋለጠች እንዲት ጀልባ አለፍን ብላችሁ ልትነግሩኝ ነው? ማን ያምናችኋል? ማንም አይታለልላችሁም። ውሸታችሁን ነው።»

«ለምን ከጀርጅታውን ጠይቀህ አታጣራም?»

t.me/OLDBOOKSPDF

«ከእንግሊዞች ጋር ውዝግብ ውስጥ ልገባ አልፈልግም።» ያ ግትርና ጉረኛ ደደብ ሰው ለበላይ አለቃው ምን ዐይነት ሪፖርት እንደላከ አግዚአብሔር ይወቅ። ለማንኛውም አንድ ቀን ማለዳ በዐሥራ አንድ ሰዓት ከአንቅልፋችን ተቀሰቀስንና በሰንሰለት ታስረን አንድ ካሚዎች ላይ ተጫን። እኛን ከሚጠብቁ ዐሥር ፖሊሶች ጋር የቦሊቫር ከፍለ ሀገር ዋና ከተማ ወደሆነችው ወደ ሲዳድ ቦሊቫር አመራር። የአቧራው መንገድ የሥቃይ ጉዞ ነበር። አሥረኞችም ሆን ፖሊሶቹ በካሚዎኑ ወለል ላይ ልከ እንደ ጀንያ እየተነሣን መፍረጥ ሆነ። ጉዞው አምስት ቀን ወሰደ። በየምሽቱ በካሚዎኑ ላይ እንተኛና ሲነጋ ደግሞ መድረሻው ባልታወቀ የምድረ በዳ ጉዞ እንቀጥላለን። በመጨረሻ ኤልዶራዶ መንደር ስንደርስ ሁላችንም በጣም በተጎሳቆለ አቋም ላይ ነበርን። ኤልዶራዶ የጥንቶቹን የስፓኝ ወራሪዎች ሕልም ታንፀባርቃለች። በዚህ ቀበሌ ይኖሩ የነበሩ ሕንዳውያን ወርቅ በብዛት ይዘው ተመልከተዋቸው ስለነበር አንድ የወርቅ ተራራ መኖር አለበት ብለው ተማምነው ነበር። ይሁን እንጂ ኤልዶራዶ ፓራንሃስ ፒራና፣ የተባሉ ሥጋ - በል ዓሣዎችና በኤሌክትሪክ ኃይላቸው የሚያደነዝዙና ከዚያም ግድያዎቻቸው ሲበሰብሱላቸው የሚሰለቅጡ ቴምብላዶሬስ የተባሉ ባለ ኤሌክትሪክ ዓሣዎች ከሞላበት ወንዝ ላይ ያለች መንደር ናት። በወንዙ መካከል አንድ ደሴት አለች። ዕውነተኛው የአሥረኞች ማጎሪያ ካምፕ ከደሴቷ ላይ ይገኛል። ይህም የቬኑዜዌላ አስቃቂ ወህኒ ቤት መሆኑ ነበር።

ይህ የጽኑ አሥራት ካምፕ ምንጊዜም ሊይቸው የማላውቅ ከሁሉም በላይ ኢሰብአዊ ድርጊት የሚፈጸምበት ነበር። በአማካይ ግምት ስፋቱ አምስት መቶ ጫማ ካሬ ሆኖ ዙሪያውም በእሾሃማ ሽቦ የተከበበና ምንም ዐይነት መጠለያ የሌለው ግቢ ነበር። አራት መቶ የሚሆኑ ሰዎች ለሌሊት ቁርና ለቀን ሐሩር ተጋልጠው ተጋድመዋል። እዚህም እዚያም በቆርቆሮ ጣሪያ የተከለሉ ትናንሽ መጠለያዎች አሉ።

አንድም ጥያቄ ሳያቀርቡልን ምንም ምክንያት ሳይሰጡን ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ኤልዶራዶ አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ አኖሩን። በሰንሰለት እንደ ታሰርን ካደረግነው አሰልቺ ጉዞ የተነሣ ድካም ገድሎን ነበር። በዘጠኝ ሰዓት ተኩል ስማችንን እንኳ ሳይጠይቁን ነበር ለሁለታችን አካፋዎች ለቀሩት ሦስቱ ደግሞ ዶማዎች የተሰጠን። ጠመንጃና የበሬ ጅራፍ የያዙ እምስት ወታደሮች ከበቡንና በሰንሰለት ታሥረን እየተገረፍን ወደ ሥራ ቦታ እንድናመራ አንድ ዐሥር አለቃ አዘዘ። ነገሩ ገባን የተነሣሡት ሥልጣናቸውን ሰማሳወቅ ነበር። አሁን እነርሱን አንታዘዝም ማለት በጣም አደገኛ ነው። ምናልባት ወደ ኋላ ይሆናል።

ወደ ሥራ ቦታው አካባቢ ስንደርስ በድንግሉ ጫካ ውስጥ በመዘርጋት ላይ ከሚገኙ አንድ መንገድ ጠርዝ ቦይ እንድንቆፍር ተነገረን። አንድም ቃል ሳንመልስና

t.me/OLDBOOKSPDF

ፍጹም ቀና ብለን ሳንመለከት በሙሉ ታማቸኮነት ባለን ኃይል ሥራ ቀጠልን። ዘበኞቹ ሌሎቹን እሥረኞች እንዴት እንደሚገርፏቸውና እንደሚሰድቧቸው ከመስራት አልቦዘንም።

ከሥራ በኋላ በላብና በአቧሯ እንደተነከርን ካምፕ እንድንመለስ ተፈቀደልን። ፎርሞች ገና አልሞላንም ነበር።

«አምስቱ ፈረንሣዮች በዚህ በኩል» ያለው የእኛ ዐሥር አለቃ ነበር። ቁመቱ ስድስት ጫማ ከአራት ኢንች የሆነ ከልሰ ነበር። ካምፑ ውስጥ የሥነ ሥርዓት ተቆጣጣሪ ስለሆነ የበሬ ጅራፍ ከእጁ አይለይም።

ተንጠልጣይ አልጋዎቻችንን የምንዘረጋበትን ቦታ ከካምፑ መግቢያ አጠገብ አሳየን። ምንም እንኳ ከፀሐይና ከዝናም የምንጠለልበት አንድ የቆርቆሮ ጣራ ቢኖረንም ግልጥልጥ ያለ ቦታ ነበር።

ከእሥረኞቹ ብዛት ያላቸው ኮሎምቢያውያን ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ ቬኒዙዌላዊያን ነበሩ። ከፈረንሣይ ቅኝ ግዛት አለቃቸ ወህኒ ቤቶች የትኞቹም በሰቆቃ ከዚህ ጋር መወዳደር አይችሉም። በእስረኞች ላይ የሚፈጽሙት ማንገላታት የመሣይል ያህል ነበር፤ ይሁንና ማንኛውም ሰው በጥሩ ጤንነት ላይ ያለ ይመስላል። ለዚህም ምክንያቱ ምግቡ በገፍና ጥሩ በመሆኑ ነበር።

አንድ አድማ ለማካሔድ ተመካከርን። አንድ ወታደር ከእኛ ውስጥ አንዱን እመታለሁ ካለ ሥራ ማቆምና በመሬት ላይ ለመጋደም እንደሚሆን ወሰን። የፈለጉትን ያህል ይደብድቡን፤ ግን አንነሣም። ከእነዚህ ወቅቶች በአንደኛው እንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ይመጣና ወንጀል አስካልፈጸምን ድረስ ለምን እዚህ አለቃቸ ወህኒ ቤት እንደታሰርን ይጠይቅልናል። ሁለቱ ነገ የወጡ እሥረኞች ጊቱና ኩሪቢየ ወደ ፈረንሣይ እንዲመለሱ ሊጠይቁ አሰቡ። ከዚያም ዐሥር አለቃ ኔግሮ ብላንኮን ወደ እኛ ለመጥራት ወሰንን። ለመናገር የተመረጥኩት እኔ ነበርኩ። ጊቱ አርሱን ፍለጋ ሔደ። አረመኔው የበሬ ጅራፉን እንደያዘ ሲደርስ ዙሪያውን ከበብነው።

«ምን ትፈልጋላችሁ?»

«አንድ ነገር ልናስረዳህ እንፈልጋለን። የዚህን አለቃቸ ወህኒ ቤት ደንብ ቅንጣት ያህል ለመጣስ አስካላሰብን ድረስ አንተም እኛን ለመደብደብ ፍጹም ምክንያት የለህም። ግን ያለ አንድ ሰበብ ዘወትር ሰዎችን ስትማታ እንመለከታለን። ስለዚህ እዚህ የጠራንህ ከእኛ ውስጥ አንዳችንን ብትነካ የምትሞት መሆንህን ልንነግርህ ነው፤ ገባህ?" በማለት እኔ ተናገርኩ።

«አዎ» አለ ኔግሮ ብላንኮ።

«አንድ የመጨረሻ ትንሽ ምክር።»

t.me/OLDBOOKSPDF

«አሺ» አለ በለሆሳስ ድምፅ።

«የንገርከህን ለሌላ ለማስተላለፍ ከፈለግህ ለተራ ወታደር ሳይሆን ለአንድ መኮንን መናገሩ እንደሚሻል አስብበት።»

«እስቲ ይሁና» ብሎ መንገዱን ቀጠለ።

ይህ የተደረገው አሥረኞች ሥራ በሌላቸው አንድ የሰንበት ዕለት ነበር። አንድ መኮንን እኛን ለመጠየቅ ወዲያው መጣ።

«ማነው ስምህ?»

«ፓፒዮ።»

«የፈረንሣውያኑ መሪ አንተ ነህ?»

«ያለነው አምስት ነን ሁላችንም መሪዎች ነን።»

«ከዐሥር አለቃው ጋር የተነጋገርከው ለምን አንተ ሆንክ?»

«የተሻለ የስፓኝ ቋንቋ ስለምናገር ነው።»

የወህኒ ቤት አዛዥ ሳይሆን የብሔራዊ ጦር ሻምበል ነበር። ከእርሱ በላይ ሁለት መኮንኖች አሉ ሆኖም በወቅቱ አልነበሩም - ወጥተዋል። እኛ ከመጣን ጀምሮ ኃላፊው እርሱ ነበር። ሌሎቹ ሁለቱ ተመልሰው የሚመጡት ማክሰኞ ነው።

«ከእናንተ ውስጥ አንዳችሁን ቢደበድብ ዐሥር አለቃውን ለመግደል ዝተህበታል። ይኸ ልክ ነው?»

«አዎ፤ ብያለሁ። ለግርፊያ የሚያበቃን ጥፋት እንደማንፈጽምም በተጨማሪ ነግሬዋለሁ ሻምበል። በቬኒዙዌላ ውስጥ ወንጀል እንዳልፈጸምንና በማንኛውም ፍርድ ቤት እንዳልተቀጣን ታውቃለህ?»

«ስለዚህ ምንም የማውቀው ነገር የለም። ወደ ካምፕ የደረሳችሁት ያለ ምንም የይለፍ ፈቃድ ከመንደሯ ፖሊስ አዛዥ ሕገዚህ ሰዎች ወዲያው እንደ ደረሱ በሥራ ላይ መድቢቸው ከምትል አንዲት ማስታወሻ ጋር ብቻ ነበር።»

«መልካም ሻምበል እንግዲህ አስተያየት አድርግልን። የበላይ ኃላፊዎችህ አስኪመጡ ድረስ ከሌሎቹ አሥረኞች ጋር አኩል መታየት እንደሌለብን ለወታደሮችህ ንገር። እደግመዋለሁ፤ በቬኑዙዌላ ውስጥ ምንም ዐይነት ጥፋት አስካልፈጸምን ድረስ እንደ ወንጀለኞች መታየት አይኖርብንም።»

«መልካም ትእዛዙን አቀርባለሁ። መቸም በእኔ ላይ ምንም ዐይነት ቅሬታ እንደማይኖራችሁ ተስፋ አለኝ።»

ከሰዓት በኋላ ስለ አሥረኞቹ ሁኔታ ልከታተል ዕረፍት ወሰድኩ። አንደኛ፣ ሁሉም ጤነኞች መሆናቸውን በማየቴ ደንቆኝ ነበር። ሁለተኛ፣ ዱላን በጣም ከመለማመዳቸው የተነሳ አሰቃዮቻቸውን በማብሸቅ በራሳቸው መከራ ደስታን

t.me/OLDBOOKSPDF

መሻታቸው ነበር። የተከለከሉ ነገሮችን ለማድረግ ይገፋፋሉ። ከራሳቸው ጓደኞች ይሰርቃሉ፣ የመንደሯን ሴቶች የሠሯቸውን ዘንቢሎች ወይም አነስተኛ ቅርፃ ቅርፆች በሲጃራዎችና በሌሎች ነገሮች በመለዋወጥ የዕቃ በዕቃ ንግድ ያካሒዳሉ። በእሾሃማው የሸበ አጥር ላይ ሴቶቹ የሚሰቷቸውን ዕቃዎች እንዳንዶቹ ኢሥረኞች እየመነተፉ ሮጠው ይጠፉሉ። አግባብ ያልሆነውና ምክንያት አልባው የዐሥር አለቃው ቅጣት በመላው ካምፕ ውስጥ የሰቆቃን እዝዝ ማባባስ እንጂ ለሕግም ሆነ ለሥርዓቱ ወይም ለሕብረተሰቡ ፋይዳ ቢስ የሆነና ያልታደሉትንም ኢሥረኞች የሚያርምበት አንድም መፍትሔ አልነበረውም።

እዚህ ጭንቀቱ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም እንደ ሰንበት በመሳሰሉት በማይሠራባቸው ቀናት በምሽት ጊዜ ማውራት ይቻላል። የተሟላና በቂ ምግብም ነበር። ስለሆነም ከአምስት ዓመት የበለጠ ቅጣትን በቀላሉ ፈጽሞ መውጣት ይቻላል ማለት ነው።

ቡና በመጠጣትና በማጤስ እያወራን አሐድን አሳለፍን። አንዳንድ ኮሎምቢያውያን ወደ እኛ ለመቅረብ ሞከሩ፤ ግን ረጋ በማለት ኮስተር ብለን ከእኛ ገለል እንዲሉ ነገርናቸው። ከሌሎቹ ኢሥረኞች ልዩ ሆነን መታየት እንዳለብን ተመካከረናል። አለበለዚያ እኛም እንደነርሱው እንሆናለን።

በሚቀጥለው ቀን ቁርስ በላንና ወደ ሥራ ለመሠማራት ከሌሎቹ ጋር ተሰልፈን ወጣን። ኋላና ፊት እየሆን በሁለት ረድፍ መሰመር ያዝን፤ አንዱ ረድፍ ሀምሳ አስረኞች፣ ሌላው ረድፍ ደግሞ ሃምሳ ወታደሮች ይዟል። ለአንዳንዱ ኢሥረኛ አንድ ወታደር ማለት ነው። በሁለቱ ረድፎች መካከል ሃምሳ አካፋዎች፣ ዶማዎችና ቆንጨራዎች ተደርድረዋል። ኢሥረኞቹ በሰቀቀን ተሸማቅቀው፣ ወታደሮቹ ለቁጣና ለማሰቃት በመቋመጥ ሁለቱም ረድፎች እርስ በርስ ተፋጠዋል።

ሃምሳ አለቃው አንድ ሰምና አንድ መሣሪያ ይጠራል። ምስኪኑ ያነሣና በትከሻው ተሸክሞ ሥራውን ለመጀመር ወደፊት በመሮጥ ላይ እንዳለ ሃምሳ አለቃው «አገሌ አገሌ» ብሎ አንድ ወታደር ይጠራል። ወታደሩም ከምስኪኑ ሰው ኋላ ይከተልና በጅራፍ ያንሚርረዋል። ትዕይንቱ በቀን ሁለት ጊዜ ይደገማል። ሁኔታው ፈረሶቻቸውን አየገረፉ እንደሚያሰሩ ጋሪ ነጅዎች እንጂ ወደ ሥራ እንደሚሔዱ ሰዎች አልነበረም።

ተራችንን በመጠባበቅ ላይ እንዳለን በከፍተኛ ጭንቀት ተውጠን ነበር። ግን እኛን በሚመለከት ሁኔታው የተለየ ሆነ።

«አምስቱ ፈረንሣዮች፤ በዚህ በኩል! እናንተ ወጣት የሆናችሁት እነዚያን ዶማዎች አንሱ ሽምገል ያላችሁት ደግሞ እነዚህን ሁለት አካፋዎች ያዙ።»

ከሚጠበቁት አራት ወታደሮችና አንድ ዐሥር አለቃ ጋር በጣም ተጠጋግተን

t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ ሥራ ቦታው አካባቢ ጉዞ ቀጠልን። ከመጀመሪያው ይልቅ የዛሬው ቀን የባሰ ነበር። በልዩ ጥፋት ምክንያት ተለይተው የነበሩ ሰዎች በገመዶቻቸው እንደ ተጠፈሩ በጉልበታቸው ተንበርከከው ድብደባው እንዲቆምላቸው ይማፀናሉ።

ከሰዓት በኋላ ደግሞ ገና አሰታቸው በሚገባ ያልጠፋና በየቦታው የወዳደቁ ቁርጥራጭ እንጨቶችን ለመከመር አሥረኞቹ ታዘው ነበር። እንጨቱን አንሥቶ ወደ ማጠራቀሚያው በመሮጥ ላይ ያለን ይበልጥ እንዲሰግር ለማድረግ እያንዳንዱ ወታደር የራሱን እስረኛ ይገርፍ ነበር። ይህ ሩጫ እንዳንዶቹን ሰዎች ሕሊናቸውን እስከመሳት ደረጃ ስለ ገፋፋቸው ከችኮላቸው የተነሣ ገና በመንደድ ላይ ያለውን እንጨት እያነሡ እጆቻቸው ሲቃጠሉ ባዶው እግራቸውን በክብል ፍም ላይ ይራመዱ ነበር። ይህ እርኩስ ተግባር ሦስት ሰዓት ፈጀ። በእኛ በኩል አንዳችንም እንድንካፈል አልታዘዝንም ይሁንና በቁፈራ ላይ እንዳለን በአራቱ ዘበኞቻችንና በዐሥር አለቃው ላይ ዘልለን መሣሪያዎቻቸውን በመንጠቅ ሚዳው ላይ ባሉት የአረመኔ ቡድኖች ተኩስ ልንከፍት ተመካከረናል።

ማከሰኞ አልሠራንም። ግን ወደ ሁለቱ መኮንኖች ዘንድ ለመቅረብም ተጠርተን ነበር። ያለ ምንም ሰነድ ወደ ኤልዶራዶ ለምን እንደመጣንና ፍርድ ቤት ሳንላክ መታሰራችን ገርሟቸው ነበር። የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ እንዲያብራራላቸው ፣ሚቀጥለው ቀን የሚጠይቁት መሆናቸውን ታል ገቡልን።

ሁለቱ መኮንኖች ኮስታሮችና በቃላቸው የሚጸኑ ስለነበሩ የወህኒ ቤቱ ዋና አዛዥ በግንባር መጥቶ ሁኔታውን እንዲያብራራላቸው ጠየቁት።

አሥር አለቃው ከአማቹና ከሁለቱ መኮንኖች ጋር ከፈታችን ቆሟል። «የኤልዶራዶ የቅጣት ሠፈር ዋና አዛዥ ነኝ። ከእኔ ጋር ለመነጋገር ጠይቃችኋል። ምን ትፈልጋላችሁ?»

«በመጀመሪያ ወደዚህ ካምፕ እንድንገባ የፈረደብን የትኛው ችሎት እንደሆነ ማወቅ እንፈልጋለን? ወንጀላችን ምን ነበር? የተፈረደብንስ ለምን ያህል ጊዜ ነው? ኢራፓ የደረሰነው በባሕር ነው። የፈጸምነው ጥፋት የለም። ታድያ እዚህ ምን እናደርጋለን? እኛንስ በሥራ ለመቅጣት ምን ገፋፋችሁ?»

«በመጀመሪያ ደረጃ ቦርነት ላይ ነን። ምን እንደ ሆናችሁ ማወቅ አለብን።»

«ያ ሊሆን ይችላል፤ ግን አሰቃቂው ወህኒ ቤታችሁ ውስጥ ለመታሰር የሚያበቃ አይደለማ።»

«ያመለጣችሁት ከፈረንሣይ ወህኒ ቤት ነው። ፈረንሣይ መልሳ ትፈልጋችሁ እንደሆነ ማጣራት ይኖርብናል።»

«አሁንም ያም ሊሆን ይችላል። ግን እደግመዋለሁ፤ ተፈርዶብን የታሰርን

t.me/OLDBOOKSPDF

ይመስል ለምን ታንገላቱናላችሁ?»

«ጉዳያችሁን ማጣራት እስከችል ድረስ ተባራሪ ቦዘኔዎችን በሚመለከተው ሕግ መሠረት ለጊዜው እዘህ ናችሁ።»

ከመኮንኖቹ አንዱ በተቃውሞ ጣልቃ ገብቶ ባይቆርጠው ኖሮ ይህ ውይይት በቀጠለ ነበር።

«አዛዥ በሐቅ ከሆነ በሌሎቹ እስረኞች ላይ የምንፈጽመውን በእነዚህ ሰዎች ላይ ማድረግ አንችልም። ከካራካስ አንድ ቃል እስኪመጣልን ድረስ እነርሱን በሥራ ላይ ለማዋል ያህል አንድ ዐይነት ዘዴ መፈለግ እንዳለብን አሰተያየቴን አሰጣለሁ።»

«እነዚህ ሰዎች አደገኞች ናቸው እኮ! ቢመታቸው ዐሥር አለቃውን እንደሚገድሉት ዝተውበታል። ዕውነት አይደለም?»

«ጌታዬ በእርሱ ላይ ብቻ ሳይሆን ከእኛ ውስጥ አንዳችንን ለመደብደብ በራሳቸው ሃላፊነት እርምጃ የሚወስዱትን ሁሉ ለመግደል ዝተናል።»

«ወታደር ቢሆንም?»

«ለእርሱም ያው ነው። ለዚህ ሥቃይ የሚያበቃ የፈጸምነው ነገር የለም። ምናልባት የእኛ ሕጎችና የቅጣት መዋቅሮች ከእናንተ የከፉ ይሆናሉ። ግን ልክ እንደ እንስሳ መደብደብ ደግሞ የባሰ ነው።»

አዛገፎ በኩራት አመለካከት ወደ መኮንኖቹ ዘወር አለና «እነዚህ ሰዎች እንዴት አደገኞች እንደሆኑ አያችሁ!» አለ።

ከሁለቱ መኮንኖች ሽምገል ያለው ለትንሽ ሰኮንድ አሰበና ከዚያ ለሁሉም ሰው ይግረመው ብሎ «እነዚህ ፈረንሣውያን ሰደተኞች ልክ ናቸው። በዚህ ካምፕ ሕግ ለመጣሥ ወይም በአሥራት እንዲቀጡ የሚያበቃ ቬኒዙዌላ ውስጥ የፈጸሙት ምንም ነገር የለም። በዚህ በኩል ከእነርሱ ጋር አስማማለሁ። አዛዥ፣ ወይ ከሌሎቹ እሥረኞች ሰይተህ አንድ ዐይነት ሥራ ፈልግላቸው፤ አለበለዚያ ፈጽሞ ሥራ አይሥሩ። ከማንኛውም ሰው ጋር ከተቀላቀሉ፣ በቅርቡም ሆነ ወደፊት ከእንድ ወታደር ጋር ሲመታቸው እንደሚጋጩ ነው» አለ።

«ስለዚህ እናያለን። ለአሁኑ በካምፑ ውስጥ ተዋቸው። ምን እንደሚደረግ ጧት እነግራችኋለሁ» አለና አዛገፎና አማቹ ሔዱ።

መኮንኖቹን አመሰገንኩ። ሲጃራ ሰጡንና ወታደሮቹ እንዳይመቱን በምሽቱ ሪፖርታቸው መመሪያ የሚሰጧቸው መሆኑን ቃል ገቡልን።

እዘህ አሁን ስምንት ቀን ሆነን። መሥራት አቁመናል። በትላንቱ ሰንበት እንድ አሰቃቂ ነገር ተፈጽሞ ነበር። ኔግሮ ብላንኮን ለመግደል ኮሎምቢያውያኖቹ ዕጣ ተጣጣሉ። ዕድሚው በግምት ሠላሳ ዓመት የሚሆን አንድ ሰው ላይ ዕጣው ወደቀበት።

t.me/OLDBOOKSPDF

ጫፉ ሹል እንዲሆንና በሁለቱም ጠርዝ ስለት እንዲወጣለት እጀታው ሲሚንቶ ላይ የተሞረደ አንድ የበረት ማንኪያ ተሰጥቶት ነበር። በገባው ውል መሠረት በቆራጥነት ጸንቶ ኔግሮ ብላንኮን ከልቡ አጠንብ ሦስት ጊዜ ወጋው። ኔግሮ ብላንኮ ወደ ሆስፒታል ተወሰደ። ወኒውም በካምፑ መካከል የቆመ አንድ አንጨት ላይ ተጠፈረ። ወታደሮቹ ተናደዱ፤ መሣሪያ ለማግኘት ማንኛውንም ሰው እየበረበሩ፣ እሥረኞቹንም ያለርኅራኄ ይደበድቡ ጀመር። ሱሪየን ሳወልቅ ፈጠን ባለማለቴ ከሚቅበዘበዙት ወታደሮች አንዱ ከኋላየ ገረፈኝ። ኩርቢያ አንድ ወንበር አፈፍ አድርጎ ከሰውዬው ጭንቅላት በላይ ሲያነሣ፣ አንድ ሌላ ወታደር በያዘው ሳንጃ ከንዱ ላይ ሸነተረው፤ በዚያው ወቅት እኔ ደግሞ የገረፈኝን ሰው ሆዱ ላይ አንድ ቡጢ አቅምሼ ዘረርኩት። አንድ ሃይለኛ ድምፅ ወደ እኛ የደረሰው ጠመንጃውን ሳነሣ ነበር።

«ተው! ፈረንሣዮቹን አትንኳቸው! አንተም ያን ጠመንጃ አስቀምጥ!» በመጣንበት ቀን ተቀብለኝ የነበረው ሻምበል ፍሎሪስ የተባለው ሰው ነበር። በተጧጧፈው ግብግብ ውስጥ ተኩስ ልከፍት ስዘጋጅ ነበር አርሱ ጣልቃ የገባው። አርሱ ባይኖር ኖሮ፣ አንድ ሁለት ወታደሮች መግደል አንችል ይሆናል፤ ግን እኛም በገባንበት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ሕይወታችንን በየዋህነት ልናጣ ነበር።

ለሻምበሉ ምስጋና ይድረሰውና፣ ወታደሮቹ እኛን ትተው የድበደባ ሱሳቸውን ለመወጣት ወደ ሌላ ቦታ ተራወጡ። ይህም ምንጊዜም ያላየነውን የሚዘገንን ትርዒት ለመታዘብ የቻልንበት ወቅት ሆነ።

በካምፑ መካከል ከቆመው አንጨት ላይ የታሰረውን ምስኪን ዐሥር አለቆችና ባለ ሌላ ማዕረጎች በየተራ እየተፈራረቁ ይገርፉታል። ከሰዓት በኋላ በዐሥራ አንድ ሰዓት ተጀምሮ በሚቀጥለው ቀን ጧት በዐሥራ ሁለት ሰዓት አበቃ። አንድን ሰው በመግረፍ መግደል ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ግብረአበሮቹ እነማን እንደሆኑ፤ ማንኪያውን ማን እንደ ሰጠውና ማን እንደሳለለት ለመጠየቅ ለአንድ አፍታ ጋብ አድርገውለት ነበር። ከተናገረ ግርፋቱ እንደሚያቆሙለት ተስፋ ቢሰጡትም እንኳ ሰውየው ምንም ነገር አልወጣውም። ብዙ ጊዜ ሕሊናውን ይስታል። በላዩ ላይ የባልዲ ውሃ በመቸለስ ተመልሶ ነፍስ እንዲዘራ ያደርጉታል። ውጤቱ የታያቸው ከንጋቱ ዐሥር ሰዓት ላይ ነበር። ጡንቻዎቹ መኮመታተር አቁመው ስለነበር የሚገርፉት ሰዎች አለመንቀሳቀሱን ተመለከቱ።

«ሞቷል እንዴ?» ሲል አንድ መኮንን ጠየቀ።

«ማረጋገጥ አልቻልንም።»

«ደህና ጥቱትና እንዲንበረከክ አድርጉት።»

በአራት ሰዎች ተደግፎ ከሞላ ጎደል ተንበረከከ። ከዚያ በኋላ በሰውየው

t.me/OLDBOOKSPDF

መቃመጫ አልፎ አስክ ዕፍረተ ሥጋው አካባቢ የደረሰ አንድ ግርፋት አንዱ አሰመረበት። ለመጨረሻ ጊዜ አንድ የጣዕረሞት ጩኸት አሰማ።

«ቀጥሉ፤ ገና አልሞተም» አለ መኮንኑ።

ፀሐይ እስከምትወጣ ድረስ እየተገረፈ ነበር። በመጨረሻም ብርጭቆ በእጁ የያዘ አንድ ጤና ረዳት መጣ።

«ይህን ጠጣው፣ መልሶ ያበረታሃል» አለው አንድ መኮንን።

ሰውየው ትንሽ አቅማማና በአንድ ትንፋሽ ጨለጠው። ከአንድ ሰዓት በኋላም ለመጨረሻ ጊዜ አሸለበ። በጣዕር ላይ እንዳለ አንድ ወረፍተ ነገር ከከንፈሩ አመለጠች «ዋ እኔ! መርዝ አጠጡኝ።»

እኛም ጭምር ስሜቱ ያልተነካ አስረኛ አልነበረም። ሰው መሆናችን ዘነጋነን። በሕይወቴ ውስጥ ለሁለተኛ ጊዜ ሞትን ተመኘሁ። ከዚያም በአገጠቤ አንድ ወታደር በግዴለሽነት ይዞት ወደ ነበረው ጠመንጃ ዐይኔ ተተከለ። የገታኝ ብቸኛ ነገር ያን መናጢ ጠመንጃውን ነጥቄ ለመተኮስ ጊዜ ከማግኘቴ በፊት ቀድመው ይገድሉኝ ይሆናል የሚለው ሐሳብ ነበር። ኔግሮ ብላንኮ ከወር በኋላ ካምፑን መልሶ ማሸበሩን ተያያዘው። ግን በኤልዶራዶ እንደሚሞት ሳይታለም የተፈታ ነበር። አንድ ቀን ማታ በዘብ ጥበቃ ላይ የነበረ አንድ ወታደር ጠመንጃውን አነጣጠረበት።

«ተንበርከክ» ሲል ወታደሩ አዘዘው። ኔግሮ ብላንኮም ትእዛዙን ፈጸመ።

«ጸሎትህን አድርስ። ለመሞት እየተቃረብክ ነው።»

አጠር ያለች ጸሎት እንዲያደርግ ፈቀደለትና ሦስት ጊዜ ተኮሰበት። አሥረኞቹ እንደሚሉት ይህን ያደረገበት ምክንያት አረመኔው ሰው በአሥረኞች ላይ የሚፈጽመውን ጭካኔ መሟቋም ባለመቻሉ የተነሣ ነበር። ሌሎቹ ደግሞ የወታደርነት አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት ካራካስ ውስጥ ሌባ እንደነበርና በኔግሮ ብላንኮ ላይ ቂም ይዞ ነው ይላሉ። የእርሱም መቃበር መጀመሪያ ኔግሮ ብላንኮን ለመግደል ከሞከረው አሥረኛ መቃበር ጎን ይሆናል። እንደ ተባለው ሌባ ሊሆን ይችላል፤ ግን ወኔ ካላቸው ከሚባሉት በጣም መጠነኛ ሰዎች አንዱ ነበር።

እነዚህ ድርጊቶች የእኛ ጉዳይ አንድ አፋጣኝ አልባት እንዳያገኝ አጓተቱበን። ለሁለት ሳምንት ከአሥረኞቹ ማንም የሠራ አልነበረም። የኩርቢ የሣንጃ ሽንትር መንደሯ ውስጥ በሚገኝ አንድ ዶክተር ታክመለት። ለጊዜው በክብር ተይዘናል። ቻፓር የወህኒ አዛዡ ወጥ ቤት ለመሆን ትላንት ከእኛ ተለየ። ጊቱና ኩርቢየም በነፃ ተለቀቁ። እኔ የምጠቀመው በእንድ ኢጣልያዊ ስም ነበር። አሁን ዕርግጠኛው ስሜ የጣት አሻራዎቼና የዕድሜ ይፍታህ ሥራቴ መረጃ ወጣ። የደፐላንክም እንደ ቻፓር የሐያ ዓመት አስራት መረጃው ቀረበ። አዛገቡም ደረቱን በኩራት ወደፊት እንደነፋ ከፊረንሣይ የመጣውን ዜና

t.me/OLDBOOKSPDF

ከእኛ ጋር ተካፈለ። «ቬኔዙዌላ ውስጥ የሠራችሁት ምንም ጥፋት አይኖር ይሆናል ግን ነፃነታችሁን ከመስጠታችን በፊት ረዘም ላለ ጊዜ እዚሁ ልናቆያችሁ ነው። ጠባያችሁን ማሻሻልና መሥራት ይኖርባችኋል። ይህም የመታዘቢያ ወቅት ይሆናል።»

በመንደሯ ውስጥ አትክልት ለማግኘት የቱን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ መኮንኖቹ በተደጋጋሚ ያነሱብኝ ነበር። ወሀኒ ቤቱ ማሳ ቢኖረውም የአትክልት መደብ አልነበረውም። የሚያመርቱትም ሩዝ፣ በቆሎና ፎሶልያ ብቻ ነበር። ዘሮቹን ካቀረቡልኝ የጓሮ አትክልት ለማልማት ተስማማሁ። እነርሱም ተስማሙበት።

የዚህ ጉዳይ ጥሩነቱ ከካምፕ ውጭ እንድንወጣ ማድረጉ ነበር። ሁለት አዲስ አሥረኞች ከሲዳድ ቦሊቫር መጡና፣ ከደፕላክና ከእኔ ጋር ተቀናጁ። ቶቶ የመጣው ከፓሪስ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከኮርሲካ ነበር። ለእኛ ተብለው በእንጨትና ዘንባባ ቅጠሎች የተሠሩ ሁለት ትናንሽ ጠንካራ ቤቶች ነበሩ ደፕላንክና እኔ በአንደኛዋ ውስጥ ተዳበልን ሁለቱ ወደ ሌላዋ ገቡ።

ቶቶና እኔ ጊዜ ሳንወስድ ጤናማ የሆኑ የቲማቲም የኤግፕላንት የሜሎንና የባቄላ ፍሎችን አደረስን። በቂ ዕድገት እንዳገኙ ወደ ሌላ ቦታ በመበታተን መልሰን ተከልናቸው። ለቲማቲሞቹ ውሃ የሚሞላበት ቦይ በእያንዳንዱ እግር ዙሪያ ቆፈረን። ይህም አትክልቶቹን እንደ ለመለሙ ከማቆየቱም ሌላ በድንግሉ ጫካ ውስጥ የሚፈሉትን ተሐዋስያን እንዳይቀርቡ ያግዳቸዋል።

«አሆ ይህን ተመልከተው! እንዴት እንደሚያንጸባርቅ አየህ!» አለ ቶቶ።»

«አስኪ እጠበው።»

መጠኑ ሽምብራ የሚያክል ባልጩት ነበር። በድጋሚ ከታጠበ በኋላ እንዲያውም የበለጠ አንጸባረቀ የላይኛው ቅርፊት ተሰብሮለት እንኳ በጠንካራና ግራጫ ልባስ እንደ ተሸፈነ ነበር።

«አልማዝ መሆን ይችላል እንዴ?»

«አፍህን ዝጋ ቶቶ። አልማዝ ቢሆንም መለፈፍ አያስፈልግም። ምናልባት አንድ የአልማዝ ማዕድን ላይ ቆመን ይሆናል። እስከ ማታ እንጠብቅ እስከዚያ ደብቀህ ያዘው።»

እጩ መኮንን ለመሆን የሚዘጋጅ አንድ ዐሥር አለቃ በየምሽቱ የሒሳብ ትምህርት አያስጠናሁ ነበር። ያ ዐሥር አለቃ ዛሬ ኮሎኔል ፍራንቺስኮ ቦላኞ ኤትሬራ ሲሆን ከዚያም በኋላ በቀበሌው በሃያ አምስት ዓመት የጓደኝነታችን ዘመን ውስጥ ከፍተኛ ጨዋና ቁምነገረኛ ሰው መሆኑን አስመስክሯል።

«ፍራንቺስኮ ይኸ ምንድን ነው? ባልጩት ነው እንዴ?» ብየ ጠየቅኩት። በጥንቃቄ መረመረው።

t.me/OLDBOOKSPDF

«አይደለም፤ አልማዝ ነው። ደብተው ማንም ሰው እንዳያይበህ። ከየት ቦታ አገኘኸው?»

«ከቲማቲም እትክልቶቹ ሥር።»

«እንግዳ ነገር ነው። ለእትክልቶቹ ከምትጠቀምበት የወንዝ ውሃ ጋር አንድ ላይ እምጭተኸው መሆን አለበት። ባልዲህ ሥሩን ሲፍት ከጥቂት አሸዋ ጋር አብሮ መውጡ ይሆናል።

«ሊሆን ይችላል።»

«መሆን አለበት። የመጣው ከሪዮ ካሮኒ ወንዝ ነው። ሌሎች የአርሱ ዐይነት ጨምራችሁ አምጥታችሁ ከሆነ ለምን አታዩም? ግን ልብ አድርግ፤ ሌሎችም መኖር አለባቸው።»

ዶኑ ወደ ሥራው ሔደ። በሕይወቱ እንደዚህ ከባድ ሥራ በፍጹም ሠርቶ አያውቅም።

ምንም ነገር ያልገለጽንላቸው ሁለት ጓደኞቻችን «ለምን ብለህ ነው አቅልህን አስክትሰት እንደዚህ የምትሆነው ዶኑ? እነዚያን ሁሉ ባልዲዎች ከወንዝ በማመላለስ ራስህን መጣደልህ ነው አኮ! ያን ያህል አሸዋስ ለምን ወደ ላይ ታመጣለህ?" የሚል አስተያየት መሰንዘራቸውን ነው።

«ጓዶቼ አፈሩን ለማለስለስ ነው። ከአሸዋ ጋር ሲደባለቅ ውሃው ይበልጥ ወደ ውስጥ ተጣርቶ ይገባል።»

ዶኑ ተስፋ ሳይቆርጥ ከባልዲው ጋር መሯሯጡን ተያያዘው። ከጉዞቹ በእንደኛው ወቅት እኛ ተቀምጠንበት ከነበረው ጥላ ፊት ለፊት በማንባሩ ተደፋ። ባልዲው ሲከነበል ሽጉብራ የሚያክል አንድ አልማዝ ከአሸዋው ውስጥ ብቅ አለ። የላይኛው ቅርፊት ባይሰበር ኖሮ ልብ ብለን ባልተመለከትነው ነበር። ዶኑ በጣም ፈጥኖ በመያዙም ስሕተት አደረገ።

«ስማ» አለ ደፕላንክ። «አልማዝና ወርቅ በወንዙ ውስጥ መኖሩን ወታደሮቹ ነግረውኛል።»

«እነዚያን ሁሉ ባልዲዎች የምሸከመው ለዚህ ነውኮ! እንደምትገምተው ሞኝ አይደለሁም!» ዶኑን ያስደሰተው ድካሙን ለመግለጽ መቻሉ ነበር። ዶኑ በሰባትና በሰማንት ካራት መካከል የሚመዝን አልማዝ ነበረው። እኔም አንድ ደርዘንና በግዕድን ቋንቋ «በንግድ» ደረጃ የሚመደቡ ሠላሳ ያህል ትናንሽ አልማዞች ነበሩኝ። አንድ ቀን ከሰድሰት ካራት በላይ የሚመዝን አንድ አልማዝ አገኘሁ። ከጊዜ በኋላ ካራካስ ውስጥ አስቆረጥክትና ቀለበት አሠራሁት። አሁንም ከእኔው ጋር አለ። እንደዚሁ ደፕላንክም አስቆረጥክትና ቀለበት አሠራሁት። አሁንም ከእኔው ጋር አለ። እንደዚሁ ደፕላንክም በመጠኑ ሰብስቧል። የገንዘብ መደበቂያ ቱቦየ አሁንም ስላለች አርሷው ውስጥ

t.me/OLDBOOKSPDF

አስቀምጫቸዋለሁ።

ከዐሥር አለቃው ጓደኛዬ በስተቀር ስለዚህ ጉዳይ ከወታደሮቹ ማንም ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ቲማቲሞቹና የቀሩትም አትክልቶች በሙሉ እደጉና ለምግብ ደረሱ። ለምንወስድላቸው አትክልቶች መኮንኖቹ ወዲያው ይከፍሉን ነበር።

ነጻ ወደ መሆኑ ደረጃ ተቃረብን። የምንሠራው ያለ ዘበኛ የምንተኛው በትንሹቹ ቤቶቻችን ውስጥ ነበር። ወደ ካምፑ አቅራቢያ ፈጽሞ አንሔድም። በሚገባ እየተንከባከቡንና እየተከበርን ነበር። የወህኒ አዛዡን ባገኘነው በማንኛውም አጋጣሚ ሙሉ ነፃነታችንን እንዲሰጠን ከመጎትጎት አልተገታንም። እርሱም ዘወትር የሚመልሰው «በቅርቡ» እያለ ነበር። ከመጣን ስምንት ወር ሆኖናል ግን ምንም ነገር አልተደረገልንም። ስለዚህ ስለማምለጥ ጉዳይ መወያየት ጀመርኩ። ቶቶ መካፈል አልፈለገም። ሌሎቹም እንደዚያው ነበሩ። ወንዙን ለማጥናት ስለፈለግኩ የዓሣ ማጥመጃ መሣሪያዎች ገዛሁ። ከአትክልቶቹ ተጨማሪ ዓሣም እሸጣለሁ። ሁለት ፓውንድ ተኩል የሚመዝነውና ጥርሶቹ የዓሣ ነባሪ መስለው አስፈሪነቱም የዚያኑ ያህል የሆነው ዝነኛው ፒራናም ይገኝበት ነበር።

በካምፑ ውስጥ እንደ ጉድ የሚታይ አንድ ሰው ነበር። ሰውነቱ በሙሉ በውቅራቶች ተሸፍኗል። ፊቱ ተጣሞ ወፍራም ምላሱም ወደውጭ በመንጠልጠል ፈጋጭ ከአፉ ይዝረከረካል። ከአንድ አደጋ መትዳቱ ግልጽ ነበር። ከየት እንደመጣ ማንም ሰው አያውቅም። እኛ ከመምጣታችን ቀደም ብሎም እዚያው ነበር። ያመለጠ አሥረኛ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነበር። በደረቱ ላይ «የአፍሪካ ባታሊዮን» የሚል ጽሑፍ ተወቅሯል፤ ይህም በአፍሪካ ውስጥ ሳለው የፈረንሣይ የቅጣት ብርጌድ የተሰጠ የቅፅል ስም ነበር። ይህም አሥረኛ እንደነበር በግልጽ ያረጋግጣል።

ሁሉም ሰው የሚጠራው ፒኮሊኖ እያለ ነበር። በእንክብካቤ ተይዟል። ከሲጃራ ጋር ምግቡን ዘወትር በቀን ሦስት ጊዜ ያገኛል። ንቁ የሆኑት ሰማያዊ ዐይኖቹ ሕይወት የተሞላባቸው ሆነው አንዳንድ ጊዜም የደስተኝነት ስሜቱን ይገልጻሉ። አንድ የሚወደው ሰው ላይ ዐይኖቹ ሲያርፉ በደስታ ይቁለጨለጫሉ። ቋንቋ ይገባዋል ግን መናገር አይችልም። የቀኝ ክንዱ በድን በመሆኑና ከግራ እጁም እንደዚሁ አውራ ጣቱ ስለጎደለ መጻፍም አይችልም። አትክልት ይገፍ ወደ መኮንኖቹ የምግብ አዳራሽ በምመላለስበት መንገድ እኔን ለመጠበቅ ይህ አሳዛኝ ፍጡር በእሾሃማው አጥር ላይ ተንጠልጥሎ ብዙ ሰዓቶች ያሳልፋል። ዘወትር በየጧቱ ላዋራው እቆማለሁ። በእሾሃማው የሽቦ አጥር ላይ ሰገግ ይልና በድን ከሆነው ሰውነቱ ውስጥ ባሉት በእነዚያ ጥቁርና ሰማያዊ ዐይኖቹ ትኩር ብሎ ይመለከተኛል። ሳጫውተው ነገሩ የገባው መሆኑን ለማሳወቅ ጭንቅላቱን ይነቀንቃል ወይም ዐይኖቹን ያርገበግባል። በድን የሆነ ፊቱ

t.me/OLDBOOKSPDF

ለአንድ አፍታ ፈገግ ይልና ዐይኖቹም ቦግ ይላሉ።

እኔም ዘወትር ትናንሽ ቅምሻዎችን ማለት ቲማቲም ወይም የዱባ እምፖቲዶ፣ ትንሽ ሜሎን ወይም በከሰል የተጠበሰ ዓሣ አመጣለታለሁ። አይርበውም ግን ከተለመደው ምግቡ ለውጥ ይሆነው ብዬ ነበር። ገጸ በረከቶቼን አልፎ አልፎ በሲጃራዎች አቀይርለታለሁ። እነዚህ ወደ ፒኮሊኖ የማደርጋቸው አጫጭር ጉብኝቶች እንደ ልማድ ሆኑና ወታደሮችና አሥረኞች የሚጠሩት «የፓፒዮ ልጅ» እያሉ ነበር።

ነጻነት

አንድ አስገራሚ ሁኔታ መጣ። ቬኔዙዌላውያን በጣም የሚማርኩ ሆነው ስላገኘኋቸው ኑሮዬን ከእነርሱ ጋር ለማድረግ ወሰንኩ። አምልጬ መሔድ አልፈለግም። አንድ ቀን እኔም ከእነርሱ አንዱ እሆናለሁ የሚል ተስፋ አደረብኝ። አሥረኞቻቸውን ከሚያሰቃዩበት አረመኔያዊ መንገድ አንጻር እኔ ከእነርሱ ጋር ለመኖር መፈለጌን ማመን አስቸጋሪ ይመስላል፤ ይሁንና አሥረኞቹም ሆኑ ወታደሮቹ ቅጣቱ ተገቢ እንደሆነ ያመኑበት መሆናቸውን መገንዘብ ችያለሁ። አንድ ወታደር አንድ ጥፋት ከሠራ እርሱም እንደዚሁ ግርፋቱን ያገኛል።

ከዚያም ከትንሽ ቀናት በኋላ የገረፈው ሰው ማንም ይሁን ማን ምንም ነገር እንዳላደረገው ሁሉ ከእርሱው ጋር ያወራል።

ይህ የጭካኔ መዋቅር የአምባገነኑ የፐሬዚዳንት ጎሜዝ ውጤት ሲሆን የሥልጣን ዕድሜውንም አራዝሞለታል። በበሬ ጅራፍ እየሞሸለቀ ከሥሩ ያሉትን ሰዎች የሚቀጣ የሲቪል ባለሥልጣን ሞልቷል።

ነጻነቴ የመጣው አብየት ሲቀሰቀስ ነበር። በቬኔዙዌላ ታሪክ ውስጥ ከታላላቆቹ ሊበራሎች አንዱና የሪፑብሊካኑ ፐሬዚዳንት ጀኔራል አንጋሪታ ሜዲናን ከፊል ወታደርና ከፊል ሲቪል የሆነ አንድ መፈንቅለ መንግሥት ከሥልጣን አወረደው። ጀኔራሉ ዲሞክራት ከመሆኑ የተነሣ መፈንቅለ መንግሥቱን ለመግረር እንኳ አልቃጣም። እርሱን በሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲሉ ቬኔዙዌላዊያን እርስ በርሳቸው እንዳይጨፋጨፉ ተቃውሟል ይባላል። ሆኖም ያ ታላቅ ዲሞክራት በኤልዶራዶ የሚፈጸመውን ግፍ ያውቃል ብየ ማመን ያዳግተኛል።

መፈንቅለ መንግሥቱ ከተካሔደ ከአንድ ወር በኋላ መኮንኖቹ በሙሉ ተዛወሩ። ኔግሮ ብላንኮን በወጋው አሥረኛ ምርመራ ተካሄደ። የወህኒ አዛዡና አማቹም ደብዛቸው ጠፍቶ በአንድ የቀድሞ ዲፕሎማቲክ ጠበቃ ተተኩ።

«ፓፒዮ ነገ ነጻ ልለቅህ ነው። ግን ምስኪኑን የቅርብ ወዳጅህን ፒኮሊኖን እንደምትወስድልኝ ምኞቴ ነው። የመታወቂያ ካርድ የለውም ሆኖም እኔ

t.me/OLDBOOKSPDF

አዘጋጅልታለሁ። የአንተ ያውልህ። ትከከለኛው ስምህ አለበት። ግዴታዎችህም እነዚህ ናቸው ወደ ከተማ ከመግባትህ በፊት በገጠር ለአንድ ዓመት መኖር አለብህ። የ፩ን ያህል እንደምታሻሽልና ራስህንም እንዴት እንደምትቆጣጠር ለመከታተል ያመቸናል። በዓመቱ መጨረሻ የአውራጃው ተጠሪ አንድ መልካም ጠባይ ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ከሰጠህ እንደሚሰጥህም አተማመናለሁ ከዚያ በኋላ የግዞትህ ማከተሚያ ይሆናል። ካራክስ ለአንተ የምትስማማ ከተማ እንደምትሆን እገምታለሁ። አሁን እዚህ ሀገር ለመኖር ሕጋዊ መብት አለህ። ያለፈው ታሪክህ እኛን የሚያሳስበን አይሆንም። ጨዋ ሰው ልትሆን መቻልህን ባጋጠመህ ዕድል ሁሉ ማስመስከሩ የራስህ ፋንታ ነው። ከአምስት ዓመታት ወዲህ የእኔው ሀገር ዜጋ እንደምትሆን ተስፋ አለኝ። አግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን! ፒኮሊኖንም በማስጠጋትህ አመሰግናለሁ። እርሱን እቀበላለሁ ብሎ አንድ ሰው ብቻ በጽሑፍ ይግለጽልኝ። ነጻነቱን መስጠት እችላለሁ። ምናልባት ሆስፒታል የሚያደርግለት ነገር ይኖራል እስኪ ተስፋ እናድርግ።»

በሚቀጥለው ቀን ጧት አንድ ሰዓት ላይ ከፒኮሊኖ ጋር ነጻ ልለቀቅ ነው። በልቤ ውስጥ አንድ ከፍተኛ ሙቀት ተሰማኝ። በቅጣት ጎዳና ስማቅቅ እንዳልኖርሁ አሁን ግን ሥቃዬ ሁሉ አከተመ። ቀኑ ጥቅምት 18፣ 1945 ነበር። ይህችን ቀን ዐሥራ አራት ዓመታት ሙሉ ስጠብቃት ቆይቻለሁ።

ወደ ትንሿ ጎጆየ ተመለስኩ። ብቻዬን ለመሆን አፈልጋለሁ በማለት ጓደኞቼን ይቅርታ ጠየቅኩ። ስሜቴ ጥልቅና እጅግ የተዋበ ነበር። የመታወቂያ ካርዴን ደጋግሜ አገላበጥኳት፤ በስተግራ፣ ከጥግ በኩል ፎቶግራፌ፣ ከእርሱ በላይ ደግሞ ቁጥር 1728629 እና ቀኑ አለበት። መሀል ላይ የመጨረሻው ስሜ ከዚያ ሥር ደግሞ የመጀመሪያ ስሜ ነበር። በስተጀርባው የተወለድኩበት ቀን ሀዳር 16 ፣ 1906 የመታወቂያ ካርድ አገልግሎት ዲሬክተሩ ፈርሞበትና ማኅተም አድርጎበት ሁሉም ነገር ተሰተካክሏል። ምዝገባዬም «ነዋሪነት» ነበር። ይህ ነዋሪ የሚል ቃል በዕርግጥም ቬኔዙዌላ የመኖሪያ ቦታየ መሆኑን ያመለክታል። ልቤ ከበሮ መታ። አግዚአብሔርን ለማመስገን በጉልበቴ መንበርከክ ፈለግኩ። «ግን ፓፒዮ እንዴት እንደሚጸለይ አታውቅም እኮ፤ አልተጠመቅህም። የየትኛውም ሃይማኖት አባል ሳትሆን ለየትኛው አምላክ ልትጸልይ ነው? ለካቶሊካውያን አምላክ? ለፕሮቴስታንቶች? ለአይሁዶች? ለእስላሞች?" ማንኛውም ይሁን በደፈናው አንድ ጸሎት አደርጋለሁ። ለማንኛውም አምላክ ብጸልይ ምን አለበት? ባለፈው ጊዜ ዘወትር ድረስልኝ እያልኩ የምማፀነው ወይም የማማርረው በበረት ውስጥ የተወለደውን ሕፃኑን ኢየሱስን አልነበረም? ለምን አእምሮየን ከማንኛውም ነገር በማላል ወደ ተከበሩት የኮራሶ ጳጳስ ብፁዕ ኢሬኔ ደብሩየን ወይም ወደ ኋላ ራቅ በማለት ጥበቃ ጣቢያው አጋጥመውኝ ወደነበሩት መልካም ቄስ እንዲያዘነብል

t.me/OLDBOOKSPDF

አላደርግም?

ከነፍስ ግድያው ንጹሕ ሆኜ ሳለ አንድ ዓቃቤ ሕግ መጠነኛ ፖሊሶችና ዐሥራ ሁለት ደደቦች የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ፈርደውብኝ ነበር። ከርታታና ባተሌ በመሆኔም ነበር የሐሰት አሉባልታቸውን ለማራባት ያን ያህል ቀላል ሆኖ ያገኙት። በእርግጥ ሌብነት ተቀባይነት ያለው ሙያ አይደለም እንዲያ ከመሳሰሉት ራሱን ለመጠበቅ ሕብረተሰቡ ራሱ ሙበት አለው። ወደ ቅጣት ጎዳና አዘቅት በሐቅ ተወርውሬ ከሆነ ለቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መዳረጌን መቀበል ይኖርብኛል። የእኔ ቅጣት ለፈረንሣይ ሕዝብ ዋጋ አልነበረውም ሕብረተሰቡ ራሱን መጠበቅ ቢያስፈልገውም እንደዚህ መቀበሉ አግባብነት የለውም። ግን ይህ አንኳ ያለፈውን ታሪኬን ከመቅፅበት አልም አድርጎ ሊፍቀው አይችልም። መጀመሪያ በራሴው ራሴን ማረም ከዚያም በሌሎች ዐይን መግምገም አለብኝ።

አብዛኛዎቹ የፈረንሣይ ሕዝቦች ካለፈው ታሪኬ አንጻር እኔን የመሰለ ሰው አንድ ጥሩ ዜጋ መሆን ይችላል ብለው ለማመን ያዳግታቸዋል። በፈረንሣይና በቬኔዙዌላ ሕዝቦች መካከል ያለው ልዩነትም ይኸው ነበር። አስከ መጨረሻው ወንጀለኛ እንደሆነ የሚኖር ማንም ሰው የለም። ጨዋ ሰው እንዲሆን አንድ ዕድል ማግኘት አለበት ብሎ ለፖሊሱ አዛዥ ሊያስረዳ የሞከረውን ያንን በኢራፓ የነበረ ምስኪን ዓሣ አጥማጅ ታስታውሳላችሁ? እነዚያ በሰፈው የአሪኖኮ ወንዝና የባሕር መጋጠሚያ ላይ ብቻቸውን ተጥለው የሚገኙት አብዛኞቹ መሀይም ዓሣ አጥማጆች ብዙዎቹን የሀገሬን ሕዝቦች ሊያስቀና የሚችል ሰብአዊ ርኅራኄ አላቸው። በጣም የመጠቀ የቴክኖሎጂ እድገት ያለው የእኛ ህብተሰብ አላማው አንድ ብቻ ነው፣ አሁንም የቴክኖሎጂ ተአምሮችን በመፍጠር ኑሮን ይበልጥ የተመቻቸና የተሻለ ማድረግ። ለማንኛውም አዲስ ሳይንሣዊ ግኝት በጣም መሰገብገብ የተሻለ ምቾትን ለማግኘት የማያቋርጥ የትግል ሱሰን መጨመር። ይህ ሁኔታ ጨዋነትን መግባባትን ርኅሩኅነትንና መንፈሳዊነትን ይገድላል። ከሁሉም በላይ በወንጀለኞች ላይ ምን እንደሚፈጸምባቸው ለማጤን ጊዜም አይሰጣቸውም። ሰላምን በማሰብ በኩል በገጠሩ ቬኔዙዌላ ያሉ ባለሥልጣኖች እንኳ የተሻሉ ናቸው። ካልታሰበ ችግር ውስጥ ቢከታቸውም እንድን ሰው ወደ ሰላማዊነት መመለሳቸውን ለድካማቸው ዋጋ እንዳገኙበት ይቆጥሩታል። ይህም ድንቅ ተግባር ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

አዎ በእግዚአብሔር ፈቃድ ጨዋ ለመሆንና በዚያው ለመጽናት የተቻለኝን ማንኛውንም አደርጋለሁ። አንዱ ችግሬ በተለየ ሙያ አለመሠልጠኔ ነበር። ለመኖር ያህል የሆነውን ብሠራ ደንታ የለኝም። ቀላል ላይሆን ይችላል ግን እቋቋመዋለሁ። ለዚህም አርግጠኛ ነበርኩ። ነገ ልክ አንደ ማንኛውም ሰው ልሆን ነው።

ነጻ መውጣቴን አባቴ እንዲያውቅ መግለጽ ይገባኛል? ለዓመታት ከኔ የደረሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

ወሬ የለም። የት እንደሚሆንም አንጃ። መቸኮል የለብኝም። ዘመናት ያልፈወሱለትን ቁስሉን እንደገና መቀስቀስ አይኖርብኝም። በምደላደልበት ጊዜ አንድ ቋሚ ሥራ ሲኖረኝ ችግሮቼ ተቃልለው በሁለት እግሮቼ ሰቅም እንዲህ ስል አጽፍለታለሁ። «አባቴ ልጅህ ነጻና ጨዋ ሰው ሆኛለሁ። የምኖረው እዚህ ቦታ ነው፤ የምሠራው ይህን ሥራ ነው። አሁን ራስህን ቀና ማድረግ ትችላለህ። ለዚህም ነው ስለአንተ ዘወትር ጥልቅ በሆነ አክብሮት የማስበውና እወድሃለሁ እያልኩ የምጽፍልህ።»

ለዐሥራ አራት ዓመታት ስትጎትታቸው ከነበሩት ሰንሰለቶች በአንድ ጊዜ ተላቅቀህ መራመድ እንደዚህ ቀላል አይደለም። ከእንግዲህ ወዲያ ነጻ ወጥተሃል ብለው፣ ፔርባቸውን አዙረው ይሔዳሉ። ነገሩ ያን ያህል ቀላል ነው። ግን መገረምህ አይቀርም። ቁልፍ በልብስ ላይ እንደመትከል ኑሮን በአንድ ጊዜ ማሚላት አትችልም። ይሁንና ዛሬ ከሃያ ሦስት ዓመታት በኋላ ትዳር መሥርቼ የአንዲት ሴት ልጅ አባትና ቬኔዙዌላ ሆኜ ካራካስ ውስጥ በደስታ እኖራለሁ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ያጋጠሙኝንና አንዳንዶቹ የተሳኩ ወይም የከሸፉ በጣም ብዛት ያላቸው አስደናቂ ተግባሮቼን መናዘዝ ይኖርብኛል እንደ አንድ ነጻና ጨዋ ዜጋ ሆኜ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ለማስፈር ቦታ ካላገኘሁላቸው ከሌሎች አስደናቂ ታሪኮች ጋር በማጣመር ምናልባት አንድ ቀን እጽፋቸው ይሆናል።

---------- ተፈጸመ ----------

t.me/OLDBOOKSPDF

t.me/OLDBOOKSPDF